

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ - 25

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ውሳኔዎች





ቅፅ- 25

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

# ቅጽ-25

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ፍ/ቤት**

**ምርምርና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት**

**ጥር 2015 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-111-55-34-00/+251111733031
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992



## ክብርት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት መልዕክት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተመረጡ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ማሳተም ከጀመረ እነሆ 25ኛ ቅጽ ደርሷል፡፡ በዚህም የተለያዩ ወገኞች ማለትም ዳኞች፣ ጠበቆች፣ ዓቃብያነ ሕግ፣ የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራን እንደዚሁም በዘርፉ እውቀትን ለመገብየት የሚሹ ዜጎች ተጠቃሚ እንደሆኑ ተስፋ አለኝ፡፡ ፍርድ ቤቱም በተለይም በአዲሱ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/2013 አንቀጽ 10 (3) በተጣለበት ሕጋዊ ግዴታ እና ኃላፊነት መሰረት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕትመቶቹን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎችም ጭምር በማሰራጨት ተደራሽነታቸውን ለማረጋገጥ ከመቸውም ጊዜ በላይ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት ግን ሕትመቶች አይኖሩም ማለት አይሆንም፡፡ በተለይም ኤልክትሮኒክስ መሳሪያዎች እና መሰረተ ልማቶች ባልተዳረሱባቸው የሃገራችን አካባቢዎች ሕትመቶቹን ለማሰራጨት አሁንም ጥረቱ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ እንደሚታወቀው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በሁሉም ደረጃ ባሉት የፌደራል እና ክልል ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው በአዲሱ የፌደራል

ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁ. 1234/2013 አንቀጽ 10 (2) ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሰረታዊ ዓላማዎችም በሀገሪቱ ውስጥ የሚወጡ ሕግጋት ወጥነት ባለው መንገድ እየተተረጎሙ ሥራ ላይ እንዲውሉ እንዲሁም ተመሳሳይ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር ያለባቸው ጉዳዮች ተመሳሳይ የፍርድ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማስቻል እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህም ፍርድ ቤቶች የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች ጥራት፣ ተገማችነትና ቅቡልነት እንዲጨምር ከማድረጉም ባለፈ የፍርድ ቤቶችና የባለጉዳዮች ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ እንዳይባክን የማድረግ ሃገራዊ ፋይዳ እንዳለው እሙን ነው፡፡ ስለዚህም ፍርድ ቤታችን የሕትመቶቹን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚያደርገው ያልተቆጠበ ጥረትና እንቅስቃሴ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የተለመደ እገዛቸውን እና የዘውትር ትብብራቸውን እጠይቃለሁ፡፡

**መዓዛ አሸናፊ መንግስቱ**

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት**

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

## ምርምርና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት መልዕክት

ውድ አንባብያን !!!

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (2) እና (3) መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላለፉት በርካታ ዓመታት የተመረጡና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በማሳተም ሲያሰራጭ መቆየቱ ይታወሳል፡፡ በነዚህ ዓመታት በርካታ አስገዳጅ የሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቶች ውሳኔዎች ታትመው ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ተጠቅመውባቸዋል ብለን እናምናለን፡፡ ከተጠቃሚዎችም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ አስተያየቶች ስንቀበል ቆይተናል ወደፊትም ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን መቀበላችንን እንቀጥላለን፡፡

የተወደዳችሁ አንባብያን !!!

አስገዳጅ የሆኑ የሰበር ሰሚ ውሳኔዎች የማሳተም ስራ እንዲህ በቀላሉ ወይም በአጭር ጊዜ የሚሰራ ሳይሆን ከዝግጅት እና ህትመት ጀምሮ እስከ ስርጭት ድረስ ክቡራን ዳኞችን ጨምሮ ሌሎች የሚሳተፉበትና ውሳኔዎቹ ባሉበት ሁኔታ በጥንቃቄ የሚሰራ ስራ መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህትመትም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ውሳኔዎችን በማደራጀትና የተቋማችንን የሕትመት ቅርጽ በመጠቀም እያሳተሙ የሚያሰራጩ አካላት ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ ሆኖም ግን ከውሳኔዎቹ ጥራትና ተአማኒነት እንዲሁም እውነተኛነት አንጻር በዋነኛነት አንባብያን ይህንን ስራ እንዲሰራ በሕግ ግዴታና ኃላፊነት የተሰጠው ተቋማችን እንደመሆኑ መጠን በተቋማችን የሚታተመውንና የሚሰራጨውን ቅጽ ብቻ እንዲጠቀም በአክብሮት እያሳሰብን በቀጣዩ ማለትም በቅጽ 26 እስከምንገናኝ ድረስ መልካም ንባብ እየተመኘሁ በዚሁ እሰናበታለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ !!!**

**አሮን ደሳል ሃብቱ**

**የምርምርና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

# የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ /ቅፅ 25/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | **1** |
| 1. | ወራሽ የሆነ ወገን አውራሽ ተካፋይ በነበረበት ክርክር ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት መቃወም የማይችል ስለመሆኑ | 180551 | ሀዊ ሁንዴ<br>እና<br>እነ አምበሳ አዱና<br>(26 ሰዎች) | ህዳር 28/2013 ዓ.ም | 2 |
| 2. | በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት የቀረበ አቤቱታ የክርክር ውጤት ተጠብቆ የቀረበ ነው በሚል ውድቅ ለማድረግ አቤቱታ አቅራቢው የቀደመውን ክርክር ስለማወቁ በተገቢው ማስረጃ ሊጣራ የሚገባ ስለመሆኑ | 181236 | አቶ ሽለመ አበራ<br>እና<br>እነ አቶ መገርሳ ምትኩ<br>(2 ሰዎች) | ጥር 25/2013 ዓ.ም | 6 |
| 3. | በፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያ ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጥ ማስረጃ ላይ ሊቀርብ የማይችልና በማስረጃው ምክንያት መብቴ ተነክቷል የሚል አካል ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ተጓደለብኝ የሚለውን መብት ማረጋገጥ የሚችል መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 79871 ላይ የተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የውርስ ሀብት ተለይቶ በተሰጠ የወራሽነት ምስክር ወረቀት ክርክር ላይ በአስገዳጅነት ሊጠቀስ የማይችል ስለመሆኑ | 181999 | ወ/ሮ ተሰሜ ገዳ<br>እና<br>እነ አቶ ለማ ነጋሽ<br>(2 ሰዎች) | መስከረም 27/2013 ዓ.ም | 12 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 4. | በፍርድ የተረጋገጠ መብት ስነ ስርዓቱን ጠብቆ እስካልተሻረ ድረስ ሊፈፀም የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 392 | 182361 | አቶ ግርማ የሺጥላ<br>እና<br>ወ/ሮ አመለወርቅ እሸቴ | ጥር 28 2013 ዓ.ም | 16 |
| 5. | በፍትህ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 358 መሰረት ፍርድ ላይ መቃወሚያ ለማቅረብ ተነካብኝ የተባለው መብት ራሱን ችሎ ዳኝነት ሊጠየቅበት የማይችል መሆን ያለበት ስለመሆኑ | 181367 | ወ/ሮ ስንቅነሽ አስፋው<br>እና<br>እነ ፍቅርተ ይሂይስ<br>(9 ሰዎች) | ጥቅምት 25/2013 ዓ.ም | 22 |
| 6. | የውርስ ሀብት ተጣርቶ ወራሽነት እንዲረጋገጥ የቀረበ አቤቱታ ውድቅ ከተደረገ በኂላ በዳግም ዳኝነት እንዲታይ ቀርቦ ፍ/ቤት የቀደመውን ውሳኔ በመሻር በግማሽ የውርስ ሀብት ላይ ውርስ እንዲጣራና አቤቱታ አቅራቢዎች ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጦ ውሳኔ ከሰጠ በኂላ ወራሾች በቀደመው ክርክር ውሳኔ የተወሰነበትን ተከራካሪ ንብረት ከህግ አግባብ ውጭ ስለያዘብን ይለቀቅልን በሚል ለበላይ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡት አዲስ ክስ በዳግም ዳኝነት የቀረበ ነው በሚል ውድቅ የማይደረግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 | 172008 | እነ ወ/ሮ ፀሐይ ሐይሉ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ሰማ ሰይድ | ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም | 26 |
| 7. | በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ዳግም ክስ ክልከላ ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ፍርድ ቤት በዝምታ ባለፈው ጉዳይ ላይ ጭምር ሲሆን ሆኖም በግልፅ ዳኝነት በተጠየቀበት ላይ ፍርድ ቤት በዝምታ | 183339 | እነ አቶ ሀጎስ ገ/ሂይወት<br>(3 ሰዎች)<br>እና | የካቲት 26/2012 ዓ.ም | 31 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የከለከለው መሆን ያለመሆኑ ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ከቀረበው ክርክር እና ጥያቄ ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበትና ተከሳሽ ወገን በግልፅ ክዶ ሊከራከርበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5(3) | | እነ መ/ር ሀጎስ በርሀ<br>(2 ሰዎች) | | |
| 8. | ያለፈበት ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ/ ቀርቦ እንዲታይለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ከአቤቱታው ጋር ጊዜው ሊያልፍ የቻለበትን ምክንያት የሚገልፁ ማስረጃዎቹን ማቅረብና እነኚህ ማስረጃዎቹም ይግባኙ/የሰበር አቤቱታው/ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበበትን ምክንያት የሚገልፁ እና ውሳኔም እንዲሰጥበት በቂ ሆነው መገኘት ያለባቸው ስለመሆኑ<br><br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.352 እና የተሻሻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀፅ 27(2) | 184388 | አቶ በዳዳ ኤጀርሳ<br>እና<br>አቶ ቦክና ጉርሙ | መጋቢት 29 2013 ዓ.ም | 36 |
| 9. | የጣልቃ ገብነትን አቤቱታ ለመቀበል በቀደመው በሁለት ተከራካሪ ወገኖች መካከል በተጀመረው ሙግትና በኋላም በሚሰጠው ውሳኔ አፈፃፀም ጣልቃ ገብ ሆኖ መከራከር የሚፈልግ ሰው ጥቅሙ ይነካል ወይስ አይነካም የሚለው መሰረታዊ መስፈርት በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው መብት የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ፍፁም | 184509 | አቶ ዘውድነህ አባተ<br>እና<br>ወ/ሮ ከበቡሽ ጋሻው | መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ/ም | 39 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተለየና ቀደም ሲል ከተጀመረው ክርክር የማይጣጣም አዲስ ጭብጥና የግል የዳኝነት ጥያቄ ይዞ ያልቀረበ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 41 | | | | |
| 10. | እግድ እንዲነሳ አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅራቢው እግዱ እንዲነሳ ያቀረበው ምክንያት ግልፅ በማድረግ በቂ ምክንያት መኖሩን ባላሳየበት ሁኔታ የቀረበው ምክንያት በቂ ነው በማለት ተቀብሎ እግድን ማንሳት የማይገባ ስለመሆኑ<br>የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 158 | 196172 | የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት<br>እና<br>የድሬ ዳዋ ከተማ ስራ አስኪያጅ | የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ.ም | 44 |
| 11. | ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ ሳይቀርብ ቀርቶ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ ወይም ተከሳሹ ቀርቦ መቃወሚያውን ያላነሳው ቢሆንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን በክርክሩ ሒደት ባረጋገጡ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ድንጋጌ የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸው እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ አዲስ የቀረበውን ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት ውድቅ የማድረግ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ 36780 እና 124660 መዝገቦች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል።)** | 182044 | ወ/ሮ ጠጂቱ ጎረምሶ<br>እና<br>ወ/ሮ ወርቅነሽ በሻ | ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 48 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 12. | ➢ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 394/1፣ ቁጥር 404 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ንብረት ለማስከበር በተሰጠ ትእዛዝ የፍርድ ባለእዳን የታክስ ከፋይ ንብረት ያስከበሩ የፍርድ ባለመብቶች ከሌሎች የቀደምትነት መብት አለኝ ብለው ለመጠየቅ እንደሚችሉ የተደነገገ ባለመሆኑ ንብረቱ ከመከበሩ ወይም ከመያዙ በፊት በንብረቱ ላይ መብት የነበራቸዉና በክርክሩ ዉስጥ የሌሉ ሦስተኛ ወገኖች በሕግ፣በፍርድ ወይም በዉል ንብረቶቹ ላይ ያቋቋሙት የቀደምትነት መብት የማይነካ ስለመሆኑ<br><br>➢የፍርድ ባለእዳን ታክስ ከፋይ ንብረት ካስከበረ የፍርድ ባለመብት ይልቅ በሕግ የቀደምትነት ጥበቃ መብት የተሰጠዉ ታክስ ሰብሳቢ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በታክስ ህግ መሰረት በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ከፍርድ ባለመብቱ የቀደምትነት መብት ያለው በመሆኑ ከፍርድ ባለመብቱ ቀድሞ ንብረቶቹን ያስከበረ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ የሚችልበት የሕግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 | 184757 | የደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን<br>እና<br>እነ ፍራኦል ኢትዮጵያ የእርሻ ልማት ድርጅት<br>(2 ሰዎች) | መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ/ም | 54 |
| 13. | የፍትሐ ብሔር ክርክር ተከራካሪን የተከተለ (party doctrine) ሲሆን አቤቱታ የቀረበለት የዳኝነት ነክ አካልም ውሳኔው መመስረት ያለበት ተከራካሪውን አስመልክቶ የተጣሱ መብቶችን በማረም፣ አቤቱታውን | 192823 | አቶ ፀጋይ ተስፋይ<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ብረታ ብረት | ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ/ም | 63 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመመርመርና አመልካች በጠየቀው መብት ልክ/ዳኝነት ላይ ስለመሆኑ | | ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | | |
| 14. | ➢ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 151 መሠረት የሚሰጥ የንብረት ማስከበር ትዕዛዝ ሊነሳ ስለሚችልበት አግባብ የሚደነግገዉ የህጉ አንቀጽ 153(3) ድንጋጌ ከፍርድ በፊት በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሦስተኛ ወገን መብት ያለዉ መሆኑ የሚመረመረዉ በፍርድ አፈፃፀም ላይ ያለዉ ንብረት የሶስተኛ ወገን መብት ያለበት መሆኑ በሚመረመርበት ዓይነትና ሁኔታ ስለሆነ መብቱን የሚያስከብረዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 158 ሳይሆን በአንቀጽ 418 እና ተከታዮቹ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ስለመሆኑ | 201182 | ወ/ሮ ጦይባ እንድሪስ<br>እና<br>ወ/ሮ መሠረት አበበ | ሚያዝያ 29 ቀን 2013 ዓ.ም | 68 |
| 15. | የግራ ቀኙን ክርክር ለማጣራት ተከራካሪዎች የሰው ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ቢሰጥም ከሳሾች ምስክሮችን ማግኘት ባለመቻላቸው ምትክ ምስክሮች ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ፍ/ቤት ሳይቀበለው ቀርቶ ተከሳሾች ምስክሮቹን ማቅረብ እንደሚችሉ አስተያየት በመስጠታቸው በነሱ በኩል መጥሪያ እንዲደርሳቸው ሲታዘዝ የሥነ ሥርዓት ጉድለት አለበት በማለት ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታው ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ሆኖ ከሥረ ነገር ፍርድ በፊት ይግባኝ የማይቀርብበት ስለመሆኑ | 184447 | እነ አቶ መስፍን ጌታቸዉ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ መለሰ ግርማ<br>(3 ሰዎች) | ህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም | 74 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 (1) እና (3) | | | | |
| 16. | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74 (2) ድንጋጌ መሰረት "በቂ ሆኖ የሚገመት እክል" ምን እንደሆነ የተመለከተ ባይሆንም በቀጠሮ ለመቅረት ምን ምክንያት እንደሆነ አጠቃላይ ሁኔታዉን መመርመር የሚያስፈልግ ሆኖ፣ አመልካች በራሱ ጉድለት ወይም ቸልተኛነት ቀጠሮዉን ሳይከታተል ቀርቶ ካልሆነ በቀር፣ ፍትሕ የማግኘትና የመከራከር መብት ከግምት በማስገባት አመልካች የገጠመዉ እክል እንደ በቂ ምክንያት በመዉሰድ ለተጠሪ ተገቢ ኪሳራና ወጪ በማስከፈል፣ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲሰማ መድረጉ አግባብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.32 (2) እና 74 (1) | 182136 | አቶ ገ/ማርያም ገ/እግዚአብሔር<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለምፀሐይ ገብሩ | ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም | 78 |
| 17. | ➢ እግድ እንዲሰጥ የተጠየቀው ክስ ሳይቀርብ ከሆነ ተከሳሽ የሚሆነው ወገን ላይ ያልተገባ የመብት ገደብ እንዳይደረግበት፣ ጊዜያዊ እግድ የሚጠይቀው ወገን ክስ ለማቅረብ ዝግጅት ላይ እንዳለና የክስ ዝግጅቱ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈለገበትን ምክንያት፣ ክሱ እስኪቀርብ ድረስ የእግድ ትዕዛዙ ባይሰጥ የሚያስከትለው ጉዳት ማሳየት ያለበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክሱን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ምክንያታዊ ጊዜ ድረስ ብቻ በጊዜ ገደብ የተገደበ የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ | 191402 | የማነ ግርማይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ቻይና ሲ ኢ ኤም ሲ ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሊሚትድ | መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ/ም | 82 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154(ለ) ☞ የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጥ የተጠየቀው ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ክፍያ ላይ ከሆነ፣ የገንዘብ ግዴታ/ዋስትና ሠነድ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 2(20)ን ጨምሮ በተለያዩ ሕጎች የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሠነድ ሲሆን የግምጃ ቤት ሠነድን፣ የተስፋ ሠነድን እና ቦንድን ይጨምራል ተብሎ ትርጉም የተሰጠበትና፤ ዋስትናው የተሠጠው ያለ ቅድመ ሁኔታና የሚፈጸመውም ያለ ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ፤ በዚህ ላይ የሚቀርብ ክስ የሚታገድ ከሆነ የውሉን ባሕሪ የሚቀይረው፣ ህግንና ተዋዋዮች ያሰቡትን ዓላማ ማሳካት የማይቻል ስለመሆኑ<br>ያለ ቅድመ ሁኔታ ለመክፈል የተገባን የዋስትና ግዴታ እንዳይከፈል እግድ ማቅረብ ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ | | (2 ሰዎች) | | |
| 18. | አዲስ በቀረበ ክስ በጭብጥነት ተይዞ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ በሌላ መዝገብ ላይ በጭብጥነት ተይዞ እልባት የተሰጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ ምንም እንኳን በቀደመዉ ክስ ለተጠየቀዉ ዳኝነት ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ አዲስ ከቀረበዉ ክስ ጋር የተለያየ ቢሆንም አዲስ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት የሚገባዉ ጭብጥ በቀደመዉ ክርክር እልባት የተሰጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ አዲስ የቀረበዉ ክስ ድጋሚ የቀረበ | 193312 | እነ አቶ ጉዑሽ ካሳ (2 ሰዎች) እና አቶ ሲሳይ ታረቀኝ | የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ.ም | 89 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | (res judicata) ነዉ የሚባል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 5 | | | | |
| 19. | ☞ በፍትሀ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ከአንቀጽ 342-344 ያሉት ድንጋጌዎች በሥረ-ነገረ ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በተቻለ መጠን ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሳይመለስ ጭብጡን በይግባኝ ሰሚ ችሎት በኩል እንዲለወጥ ተደርጎ ክርክሩ እንዲቋጭ የሚያዝ፣ መጣራት የሚገባው ነገር ካለ ግን ግራ ቀኙና ማስረጃዎች በቅርብ በሚገኙበትና ጉዳዩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት እንዲታይ እድል የሚሰጥ፤ የተጣራው ውጤት ሲቀርብም አዲስ የይግባኝ መዝገብ ሳይከፈት ቀድሞ በተመለሰበት መዝገብ ተጠቃሎ ፍርድ የሚሰጥበት እንጂ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና እንዲጣራ በሠጠው ውሳኔም ሆነ የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ በደረሰበት ድምዳሜ ላይ የይግባኝም ሆነ የሠበር አቤቱታ የማይቀርብበትና ተጠቃሎ ሲመጣ በሠበር አቤቱታ የሚታይ ስለመሆኑ<br>☞ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩ በፍሬ ነገር የሚጣራና የሥር ፍርድ ቤት እንዲመለከተው የሚመለስ ከሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበት ሳይሆን ተጣርቶ እንዲቀርብለት ባዘዘው መሰረት የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ እስኪልክ ውጤቱን የሚጠብቅበትና መዝገቡን ለጊዜው በመዝጋት ውጤቱን መላክ | 186816 | ወ/ሮ ታንጉት ዲበኩሉ<br>እና<br>እነ አቶ ይታያል ዲበኩሉ<br>(2 ሰዎች) | መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ/ም | 94 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት እንደ አዲስ እንደገና በሕግ አግባብ የመሠለውን እንዲወስን መመለስ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከሚያዘው ውጪ ስለመሆኑ<br>✍በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሰረት የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ ማስረጃ በማጣራትና ተገቢ ያለውን እርምጃ በመውሰድ ለመለሰለት ፍርድ ቤት አባሪ በማድረግ የሚመለስበት ሥርዓት ማስረጃ ማጣራትና መመዘን የሚጠይቅ ተግባር ከሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን የማድረግ ሥልጣን ስለሌለው የሥር ፍርድ ቤት አዲስ ያጣራውን አባሪ አድርጎ ሳይልክ ቀድሞ ከተሰማው ማስረጃና ክርክር ጋር አጣምሮ እንደ አዲስ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ለሰበር ችሎት ሊመለስ የማይችል ስለመሆኑ | | | | |
| 20. | ✍ ከአንድ በላይ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የችሎቱ ዳኞች ተሟልተው በጉዳዩ ላይ ውይይት አድርገው በሙሉ ድምጽ ወይም በአብላጫ ድምጽ ለመወሰን አቋም ሳይዙ ከተሰየሙት ዳኞች ከፊሎቹ ብቻ ፈርመው የሚሰጡት ውሳኔ/ትዕዛዝ የስነ ስርዓት ጉደለት (irregular proceedings) ያለበት ስለመሆኑ<br>✍ በዳኝነት ታይቶ የተሰጠ የሥነ ሥርዓት ጉድለት (irregular proceedings) ያለበት ውሳኔ/ትዕዛዝ የማረም ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ቀርቦ በሚሰጥ ዳኝነት ይታረማል እንጂ በተከራካሪ ወገኖች | 185837 | ጀፎር ኮንስትራክሽን<br>እና<br>አስማማዉ<br>ኃላ/የተ/የግ/ማህበር | መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም | 101 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አመልካችነት ወይም በፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አነሳሽነት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ በሚደራጅ ችሎት በድጋሚ ታይቶ እንዲታረም ማድረግ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 209/1 እና 211/2፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 138/1991፣ በአዋጅ ቁጥር 254/1993 እንተሻሻለው እና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደገና እንደተሻሻለው) አንቀጽ 16(2/ሀ)፣ 18(ሀ/1)፣ 21፣ 22 እና 27(/1/ሐ) እንዲሁም የተሻሻለው የፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002 አንቀጽ 6(1/ሰ) | | | | |
| 21. | ይግባኝ የተባለበት ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ የተሻሻለዉ ወይም የተለወጠዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በነበረዉ የመጀመሪያ ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ መሰረት የተወሰደ ነገር እንዲመለስ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየዉ ፍርድ ቤት ተስማሚዉን ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 349 | 193215 | አቶ በቀለ ኢሳያስ<br>እና<br>እነ አቶ በረከት እንዳሻው<br>(9 ሰዎች) | 25/05/2013 ዓ/ም | 120 |
| 22. | ☞በሕግ የውክልና ስልጣን መስጫ ሰነድ አረጋግጦ እንዲመዘግብ ስልጣን በተሰጠው አካል ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ የውክልና ስልጣን ማስረጃ በመያዝ ሌላ ሰው ወክሎ ለመሟገት የቀረበን ሰው ለመወከል ብቁ የሚያደርግህን የውክልና ስልጣን ማስረጃ ይዘህ አልቀረብክም ብሎ ፍርድ | 185273 | አፍሪካ ጁስ ቲቢላ አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ታዱ ጫላ<br>(7 ሰዎች) | ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 130 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ቤቱ ሊያስናብተው የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 63/1፣ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 9(1/ለ) እና አዋጅ ቁጥር 110/1990 10/1<br>☞አስቀድሞ መከላከያ መልሱን ያላቀረበ ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀን የፍትሀ ብሄር ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 137ን ጠቅሶ ከማስረጃ መግለጫ ጋር የሚያቀርበው የሰነድ ማስረጃ ይያያዝልኝ ጥያቄ በስነ ስርዓት ህጉ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | | | | |
| 23. | በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ነፃ እና ገለልተኛ የዳኝነት አካል በየደረጃው ማቋቋም ያስፈለገው ሰዎች ነፃና ገለልተኛ በሆነ አካል ፊት ቀርበው መብታቸውን በማስከበር ዳኝነታዊ መፍትሄ ማግኘት እንዲችሉ፣ በህግ ፊት እኩል ጥበቃ እና ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ለማስከበር እንዲሁም ሌሎች የሰዎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር በመሆኑ የክልል ፍርድ ቤቶች በህግ በታወቀ ምክንያት በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸውን የውክልና ሥልጣን መጠቀምና ለዜጎች ፍትህ መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ሲሆኑ እና ጉዳዩም የፌደራል ጉዳይ ሲሆን የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት፣ እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት እና ሌሎች መብቶችን ለማስከበር የፌደራል ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ጉዳዩን ተቀብለው የመዳኘት ሥልጣን የሚኖራቸው | 219089 | ኦሮሚያ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>እነ ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ<br>(2 ሰዎች) | ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 138 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25፣ 37/1፣ እና አንቀጽ 78 እና ተከታዮቹ፤ የተባበሩት መንግስታት የሰበዓዊ መብቶች መግለጫ (Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 7፣8 እና 10 እንዲሁም የዓለም አቀፍ የሲቪልና ፓለቲካ መብቶች ቃልኪዳን (International Covenant on Civil and Political Rights/ICCPR) አንቀጽ 2(3/ሀ እና ለ)፣ 26 | | | | |
| **ውል** | | | | | **153** |
| 24. | በፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1179 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ በባለይዞታዉ እና ይዞታዉን ይዞ ቤት በሰራ ሰዉ መካከል የታወቀ ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ ብቻ በመሆኑ የባዶ ቦታ ሽያጭ ዉል መፍረሰን ተከትሎ በቦታዉ ላይ የተሰራ ቤት ህጋዊ ዉጤትን አስመልክቶ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1818 ስለመሆኑ | 189608 | እነ ወ/ሮ ትርንጎ ገመቹ (3 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብርሀኔ ገመቹ (2 ሰዎች) | የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም | 154 |
| 25. | ⮳ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የሽያጭ ዉል ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ መመዝገብ እንዳለበት ህጉ ሲደነግግ ገዥዉ ዉሉ እንዲመዘገብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ሲቀርብ ንብረቱ በሻጭ ስም መመዝገብ አለመመዝገቡን ወይም ሻጩ ዉሉን ለማድረግ ህጋዊ መብት ያለዉ መሆን አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን በንብረቱ ላይ ዕዳ እና እገዳ ያለበት | 186626 | አቶ ሶሪ ጉተማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሀረገወይን ተ/ጽዮን<br>(2 ሰዎች) | የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም | 162 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሆን ያለመሆኑንም ለማጣራት ዕድል ያገኛል በሚል በመሆኑ ማንኛዉም ጠንቃቃ ገዥ ዉል ሲዋዋል ተገቢዉን ጥንቃቄ እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ስለመሆኑ<br>☞ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነ ቤት ያለ አንደኛው ተጋቢ ፈቃድና ስምምነት ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት አስቀድሞ እግድ የተሰጠበት ስለመሆኑ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ ተረጋግጦ እያለ፣ የሽያጭ ዉሉም መመዝገቡም ሆነ የሚመለከተዉ አካል ዉሉን ሲመዘግብ ወይም ሲያረጋግጥ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርግ ቤት በሽያጭ በመተላለፉ የገዛ ሰው እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ማድረግ የሚገባዉን ጥንቃቄ አለማድረጉን የሚያሳይና አስቀድሞ የተቋቋመ የሌላ ሰዉ መብትና ጥቅም ያለበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በመግዛት የተደረገ ዉል ጸንቶ የማይቀጥል ስለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1543-1566 እና 1185 | | | | |
| 26. | የፍርድ ቤት እግድ የተሰጠበትን ቤት በሽያጭ በማስተላለፍ የሚደረግ የሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት የሌለውና ሊፈርስ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች፣ የፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 1808/2 | 177862 | ወ/ሮ አበበች ዘበርጋ<br>እና<br>እነ አቶ ሙላት ለጃ<br>(4 ሰዎች) | ጥር 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 170 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 27. | ያለፍርድ ቤት ፈቃድ የህፃን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሚደረግ ውል ህጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ | 194876 | ፍቅሩ መገርሳ<br>እና<br>እነ ሚሊዮን ተካ<br>(2 ሰዎች) | ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም | 183 |
| 28. | በፀና አኳኋን ባልተደረገ ውል በተገኘ ቦታ ላይ ቤት የሰራ ሰው ቤቱን ለመገንባት ያወጣው ወጪ (Book Value) እንዲከፈለው ክስ በማቅረብ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ | 188881 | አቶ ማስሬ ገድፍ<br>እና<br>አቶ ፈንታሁን ቸኮል | መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም | 197 |
| 29. | በጽሁፍ የተደረገ ውል በይዘቱ ውሉ ለጥቅሙ የተደረገለትን ሶስተኛ ወገን የማይገልጽ ከሆነ በውሉ ላይ በግልጽ ከተመለከቱት ከተዋዋዮች ሀሳብ ውጪ በመውጣት ተዋዋዩ ውሉን በስሙ የተዋዋለው ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ነው በማለት በውሉ በግልጽ ከተመለከተው ተዋዋይ ውጪ ሌላ ሰው ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ፍርድ ቤቶች ውልን እንዲተረጉሙ ህግ ስለማይፈቅድ በእኔ ገንዘብ የተገዛ ቤት ነው በሚል በሌላ ሰው ስም የተገዛና የተመዘገበ ቤት ለማስለቀቅ የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 207885 | አቶ መልካምአየሁ መንገሻ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አለም በርሄ<br>(2 ሰዎች) | ጥር 26 ቀን 2014 ዓ.ም | 204 |
| 30. | የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ለማስተላለፍ የተደረገ ውል በውል አዋዋይ ፊት ተረጋግጦ የተመዘገበ ከሆነ በስጦታ ውሉ ላይ ውሉ በስጦታ ሰጪና በምስክሮች ፊት የመነበብ ስርዓት የተፈፀመበት ነው ተብሎ ባይፃፍም | 193067 | እነ መሰረት ወ/አማኑኤል<br>(2 ሰዎች)<br>እና | ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 213 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የመነበብ ስርዓት በሰነድ አረጋጋጪ እንደተፈፀመ ተቆጥሮ የስጦታ ውሉ ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ **(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁጥር 32337፣70057፣147331፣17429 እና 22712 ላይ እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከኑዛዜ እና ከስጦታ ውል ፎርምና ከመነበብ ስርዓት ጋር በተያያዘ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ተለውጧል።)** | | እነ ጌታቸው ይልማ (3 ሰዎች) | | |
| 31. | ☞የቅድሚያ ክፍያ ማገቻ ሰነድ (Advance Payment Guarantee/Bond) በሰነድ ሰጪውና በተጠቃሚው (ቅድሚያ ክፍያ በከፈለው አሰሪ) መካከል የዋስትና ውል የሚያቋቁም ሰነድ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1902 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችና በአንቀጽ 3271 መሰረት የሚገዛ ስለመሆኑ<br><br>☞ዋናውን ውል ለማከራከር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ተቀፅላውን ውል የሚመለከት ክርክር ተቀብሎ የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ | 211616 | ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት | ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም | 226 |
| 32. | የይመስል ውል (simulated contract) እና ሽሽግ ውል (counter-deed or back-letter) ተቋቁመዋል የሚያሰኙ ሕጋዊ መሰረቶችና ሕጋዊ ውጤታቸው፡-<br>አንድ ባለእዳ ለባለገንዘቦች የገባውን ግዴታ ላለመወጣት ካለው ዓላማ | 207446 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ጋሜ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ኤልሳቤት ኪ/ማሪያም | መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ.ም | 239 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመነሳት ብቻ ሳይከስር በእጁ ያለው ሀብት ለባለገንዘቡ የመብት ጥያቄ ማስፈፀሚያ እንዳይውል በተለያዩ መንገዶች በተንኮል ንብረቱን በግዥ ወይም በስጦታ አገኘሁ ከሚል ሶስተኛ ወገን ጋር በመመሳጠር ባለገንዘቡን የሚጎዳ የአጭበርባሪነት ተግባር በመፈፀም ንብረቱን ቢያስተላልፍ ከሶስተኛ ወገን ጋር የተደረገው ውል ሕጋዊ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑ | | (2 ሰዎች) | | |
| **ንብረት** | | | | | **256** |
| 33. | ☞ በባለሀብትነት መብት አለመጠን መገልገል በተፈጠረ ጊዜ ይህንን አስመልክቶ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1149 እና 1225 መሰረት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br><br>☞የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በተጨባጭ በይዞታ መብት ላይ የተፈጠረን የሁከት ተግባር ለማስወገድ እንጂ ሊሰራ የታሰበ ስራ ሊያስከትል የሚችለውን ጫና በመገመት ባልተፈፀመና ወደፊት ሊፈጠር በሚችል ድርጊት ላይ የሁከት ክስ ሊቀርብ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149 | 181821 | አቶ መኮንን ስሜነህ<br>እና<br>አቶ ፀጋሁን ሁነኛው | ጥቅምት 26/ 2013 ዓ.ም | 257 |
| 34. | የአስተዳደር አካል በክርክር ሂደት በፍርድ አደባባይ ከተረታ በኋላ ተከራካሪው ወገን መብት ያገኘበትን ካርታ በማምከን አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ እንዲለወጥለት የሚያቀርበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ የሚገባው | 184069 | ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት | መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ.ም | 262 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) (2)፣ 12/1 እና 40/1 ድንጋጌዎች እና የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 እና 1196 | | እና<br>ጂብሪል ሚስባህ | | |
| 35. | በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195 (1) መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት ምስክር ወረቀት በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠው ሰው ባለሃብት እንደሆነ የተወሰደውን የህግ ግምት ማስተባበል የሚቻለው ማስረጃው የተገኘው ከህግ አግባብ ውጭ በሆነ ሁኔታ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1196 በተደነገገበት ሁኔታ የሰው ምስክር በመስማትና ቦታው ድረስ በመሄድ የችሎት ምልከታ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ የምስክር ወረቀት በተሰጠበት ንብረት ላይ ባለሃብትነትን የማይለውጥ ስለመሆኑ | 183001 | አቶ ነጋ ኃይሉ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀና ኃይሉ | ታህሳስ 22 2013 ዓ.ም | 267 |
| 36. | የሁከት ይወገድልኝ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሁከት የተፈጠረ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ በመወሰን ረገድ ሁከት ተፈጠረ በተባለበት ወቅት ንብረቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በከሳሽ ይዞታ ስር የነበረ መሆን አለመሆኑን እና ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰዉን ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል መብት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን እንጂ ከዚህ በላይ በመሄድ በዉርስ እና በይዞታ ባለቤትነት ላይ ተመስርቶ መወሰን ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1140፣ 1149 (1) እና 1149 (3) | 186348 | ወ/ሮ አሚና አደን<br>እና<br>አቶ አብዲ ሙሀመድ | መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 272 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 37. | ➢ ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ መብቶች እና ግዴታዎች የሚመሩት በንብረት ህግ አጠቃላይ መርሆዎች በመሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚወጡ ህጎች/አዋጆች በንብረት ህግ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚመደቡ በመሆኑ ከንብረት ጋር በተገናኘ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ህጎች እና መርሆዎች ከመሬት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክርክር እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት ያላቸው ስለመሆኑ<br><br>➢ አንድን ንብረት አስመልክቶ የሚቀርበዉን ክስ ተከትሎ ንብረትን የሚመለከት የህግ ክፍል ተፈፃሚ የሚሆነዉ ከሳሽ ክሱን ያቀረበዉ ንብረቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ካደረገ በኋላ በንብረቱ ላይ ያለዉ መብት እንዲከበርለት የተረጋገጠ ሲሆን በመሆኑ የተጠየቀዉ ዳኝነት ንብረትን የሚመለከት መሆኑ ብቻዉን ጉዳዩን የንብረት ክርክር የማያደርገው ስለመሆኑ | 186461 | ሰይድ ዑመር<br>እና<br>ወ/ሮ ሀዋ ሰይድ | መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም | 276 |
| 38. | በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179 ስር የተመለከተው በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የሚደረግ ግንባታን የመቃወም ጉዳይ አግባብ ባለው የአስተዳደር አካል በተሰጠ ይዞታ ላይ በሚደረግ ግንባታ ላይ ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ | 186946 | እነ ወ/ሮ አለሚቱ ተክሌ (2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እብስቴ ምስክር (2 ሰዎች) | 26/08/2013 ዓ.ም | 282 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ውርስ** | | | | **289** |
| 39. | ተወላጅ መሆን ለወራሽነት ብቁ ከሚያደርጉ ህጋዊ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 842 እና 830 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም ይህ ማለት ግን የሟችን ንብረት ለመውረስ ስለተወላጅነት በተመለከተው ሥርዓት መሰረት መወለድን ማረጋገጥ የግድ ማለት ሳይሆን በተለይ ውርሱ የሚመለከተው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን በሆነ ጊዜ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ መያዝ በቂ ስለመሆኑ | 180281 | ወ/ት ዮዲት ሰለሞን<br>እና<br>ወ/ሮ አይናለም ወርቁ | ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 290 |
| 40. | አስቀድሞ ከዉርስ ንብረት የተቀበለ ወራሽ የዉርስ ክፍፍል ፋይል ሲከፈት የዉርስ ሀብቱን ለመዉረስ ካልጠየቀ አስቀድሞ የወሰደዉን ንብረት ወደ ዉርስ ሀብት መልሶ ለመዉረስ የሚገደድበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1073 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች | 191963 | እነ አቶ ምንዳዬ አስታጥቄ<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ በላይነሽ አስታጥቄ<br>(5 ሰዎች) | ሚያዚያ 12 ቀን 2013 ዓ.ም | 295 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ቤተሰብ** | | | | | **300** |
| 41. | በባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር ወቅት ድብቅ የጦር መሳሪያ መኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ በሕግ አግባብ ስልጣን ባለዉ አካል አለመመዝገቡ መሳሪያዉ የለም የሚያስብል ሳይሆን የኢኮኖሚ ጥቅም ያለዉ እና ባልና ሚስት በትዳር እያሉ ያፈሩት እስከሆነ ድረስ ከሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ መሳሪያዉን ለመያዝ ፈቃድ አለመሰጠቱ፣ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት እንዳይሆን የማያደርገዉ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 73 (1) እና 101 | 179121 | አቶ ካሳ በለጠ<br>እና<br>ወ/ሮ ሥራይቱ ነጋሽ | ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 301 |
| 42. | ጋብቻ በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ በንብረት ክርክር ወቅት የግል ዕዳ ነዉ ተብሎ ውሳኔ ያገኘ ዕዳ ፍ/ቤት ቀርቦ ባልተለወጠበት ሁኔታ በባለዕዳው ተጋቢ በኩል ለመጣው እዳ ሌላኛው ተጋቢ ተጠያቂነት የሌለበት ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 (1)፣ የፌደራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57፣ 70፣ 71፣ 89 እና 93 | 190295 | ወ/ሮ ቱኒዝ ሙሉጌታ<br>እና<br>እነ አቶ አብርሃም ከለለዉ<br>(3 ሰዎች) | ሚያዚያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም | 305 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ግብር** | | | | | **315** |
| 43. | ➢ ማንኛውም አካል ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ባስገባቸው እቃዎች በአንዱም ሆነ በሌሎቹ ወይም በሌላ ምክንያት የሚፈለግበት መክፈያ ጊዜው የደረሰ የታክስ እዳ መኖሩን የኢትየጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያረጋገጠ እንደሆነ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀዳሚነት መብት ስላለው በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 41(4)(ለ) መሰረት በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትዕዛዝ የተሰጠበት ንብረትን ባለስልጣኑ የመያዝ ስልጣን የሌለው መሆኑ የተመላከተ ቢሆንም ድንጋጌው ንብረትን የመያዝ ሁኔታን ብቻ የሚከለክል እንጂ ባለስልጣኑ የግብር እዳውን ለማስከፈል የሚኖረውን የቀደምትነት መብት የሚያሳጣ ስላለመሆኑ<br>የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 73(3)፣ እና 130፣122(1)፣ 6 እና የታክስ አስተደዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 39(1 እና 2)<br><br>➢ ከቀረጥ ነጻ የገባ ንብረት ተመልሶ እስካልወጣ ድረስ ተገቢው የግብር እዳ ተከፍሎበት ሀገር ውስጥ የሚቀር በመሆኑ ለግብር እዳ በዋስትና ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ | 192732 | መሐመድ አብዱላሂ የማሽነሪ ኪራይ<br>እና<br>በጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት | ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ/ም | 316 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 44. | ፍ/ቤቶች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155 (3) እና በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 57 (4) መሰረት ከግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቀረበላቸዉን ጉዳይ የሕግ ስህተት ካልሆነ በቀር ፍሬ ነገር በማስረጃ አጣርቶ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ስልጣን የሌላቸዉ ስለመሆኑ | 187882 | ቲ.ኤም.ዜድ.ቢ. ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት | ሚያዚያ 25 ቀን 2013 ዓ.ም | 322 |
| 45. | ➢ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበትን እቃ ወይም አገልግሎት የሚሸጥ ማንኛውም የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ለተጠቃሚው የሚሸጠውን እቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ሲገልፅ በዋጋው ላይ 15 በመቶ ተ.እ.ታ አካቶ መግለፅ ወይም ዋጋው ተ.እ.ታ ያላካተተ ከሆነም ይህንኑ ለገዥ በማያሻማ አኳኋን ማሳወቅና ተ.እ.ታ በደረሰኝ የመሰብሰብ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br><br>➢ የእቃው ወይም የአገልግሎት ዋጋ ላይ ተ.እ.ታ መካተቱ ሳይገለጽ ወይም ዋጋው ላይ ተ.እ.ታ አልተካተተም ብሎ በግልጽ ለተጠቃሚው ሳይገለጽ ግብይት የተፈፀመ እንደሆነ የእቃው ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ ነው ተብሎ በውሉ የተጠቀሰው ገንዘብ ተ.እ.ታ እንዳካተተ የሚቆጠር ስለመሆኑ | 194135 | ዳይናሚክ ሎጅስቲክ አቅርቦት የድጋፍ አገልግሎት<br>እና<br>አቶ ፈሬሳ ኢዶ | የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ/ም | 330 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የዳኝነት ስልጣን** | | | | **335** |
| 46. | የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት ይሰረዝልን ጥያቄ ሰፊና ዉስብስብ ክርክሮች ተደርጎ፣ በሕጉ አግባብ ተገቢ ማጣራትና ምርመራ ተደርጎበት ዉሳኔ የሚሰጥበት እንጂ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት ከሚቀርብ አቤቱታ ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ባለመሆኑ የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታን መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ-ነገር ስልጣን የፌደራል ፍ/ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ስላለመሆኑ | 171061 | አቶ ጌታቸዉ ሙሉጌታ<br>እና<br>እነ አቶ መላኩ ሙሉጌታ<br>(3 ሰዎች) | መጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ.ም | 336 |
| 47. | ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን የማረጋገጥ ጉዳይ አስመልክቶ የዳኝነት ስልጣኑ ተለይቶ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተሰጠ በመሆኑ የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ<br>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1(ፕ)) እና 11(1)፣ (3) | 230167 | የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን<br>እና<br>እነ ሙሉጌታ መንግስት<br>(3 ሰዎች) | ሐምሌ 28/2014 ዓ.ም | 341 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ንግድና ኢንሹራንስ** | | | | | **346** |
| 48. | መድን ሰጪ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ ከመድን ገቢዉ ለማስመለስ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይርጋ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1676(1) መሠረት መቆጠር የሚችለዉ ከሳሹ በመብቱ መስራት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ነዉ የሚለው በፍትሀ ብሄር ህግ አንቀጽ 1846 ላይ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት ሲሆን በንግድ ህግ አንቀጽ 674/1/ ላይ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር የሚጀምረዉ መድን ሰጪዉ በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ካሳ ከከፈለበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ | 177907 | ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ<br>እና<br>ሚካኤል አባተ ሕንፃ ተቋራጭ | መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም | 347 |
| 49. | ➚ በሦስተኛ ወገኖች ላይ በተሽከርካሪ ለሚደርስ አደጋ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ ኢንሹራንስ ኩባንያ በአንሹራንስ ዉሉ ላይ ኢንሹራንስ ገቢዉ ይህንን ካደረገ ወይም ካላደረገ ተጠያቂነት አይኖርብኝም በማለት ያስቀመጠዉን ሁኔታ መሰረት በማድረግ በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ካሳ ላለመክፈል ጉዳት ለደረሰበት ሦስተኛ ወገን መከራከሪያ ለማድረግ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/1<br>➚ በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉ ላይ የተቀመጠዉን የማግለያ ወይም ሌላ | 196878 | ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ሃብቴ አንማዉ<br>(3 ሰዎች) | የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም | 353 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሁኔታ መሰረት በማድረግ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በኢንሹራንስ ገቢዉ ላይ መከራከሪያ ሊያደርግ የሚችለዉ በቅድሚያ ጉዳት ለደረሰበት ሦስተኛ ወገን በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16 እና በኢንሹራንስ ዉል ፖሊስዉ መሰረት ካሳ ከከፈለ በኋላ ስለመሆኑ<br>አዋጁ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 | | | | |
| 50. | የገንዘብ መጠኑ እና ቀን ሳይፃፍበት በቼክ አውጭው ተፈርሞ የተሰጠ ቼክ (Blank Cheque) ቀንና የገንዘብ መጠን ተሞልቶ ለከፋዩ ባንክ በቀረበ ጊዜ በንግድ ህጉ አንቀጽ 827 እና 828 ስር አንድን ሰነድ ቼክ የሚያሰኙ መገለጫዎችን ስለሚያሟሉ እንደ ቼክ የሚቆጠሩ እና ህጋዊ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ | 193270 | አቶ ሐበን ጉዕሽ<br>እና<br>ናይል ፔትሮሊየም ካምፓኒ ሊሚትድ ኢትዮጵያ | የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም | 358 |
| 51. | የኢንሹራንስ ሽፋን ወደፊት ለሚደርስ አደጋ የሚሰጥ የመድን ሽፋን በመሆኑ በልዩ ሁኔታ በግልጽ ስምምነት ካልተደረገ በቀር በዋናው ኢንሹራንስ ውል ላይ ሳይካተት የቀረውን የአደጋ ምክንያት ለማካተት የሚደረግ የመድን ሽፋን ማስፊያ (Extension) ውል ወደ ኋላ ተመልሶ ዋናው የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲሆን መወሰን መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 659/1 | 173380 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ሐበሻ ሲሚንቶ አክሲዮን ማህበር | ጥቅምት 28 ቀን 2012 ዓ.ም | 370 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 52. | አንድ እቃ በአየር መንገድ ተጭኖ ሲጓጓዝ ባለእቃው ሲያስረክብ በእቃው ያለውን ልዩ ጥቅም በመግለጽ ተገቢውን ተጨማሪ ዋጋ መክፈሉን ካላስረዳ በቀር እቃው ተጓጉዞ ርክክብ እስከሚፈፀም ድረስ ባለው ጊዜ ቢጠፋ ወይም ጉዳት ቢደርስበት ካሳ ሊከፈል የሚገባው በጠፋው እቃ ወይም ጉዳት ለደረሰበት እቃ በአንድ ኪሎ ግራም 17 ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት በመክፈል ስለመሆኑ<br>የሞንትሪያል ቃል ኪዳን (Montreal Convention of 1999) አንቀጽ 22 (3) እና አዋጅ ቁጥር 820/2006 | 171352 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ<br>እና<br>ብርሃን ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ | ጥር 25 ቀን 2012 ዓ.ም | 377 |
| 53. | ለሶስተኛ ወገኖች የካሳ ክፍያ የፈፀመ የኢንሹራንስ ኩባንያ በደንበኛው ላይ የሚያቀርበውን ክስ ማቅረብ ያለበት ለሶስተኛ ወገን የካሳ ክፍያ ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ባለው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንጂ በሶስተኛ ወገኖች ላይ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 674/1፣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 እና የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1846 | 179983 | ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጀኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ሀሪያ ታደሰ | መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም | 385 |
| 54. | ➢ አንድ የንግድ ምልክት በባለቤትነት ያስመዘገበ ሰው ላስመዘገበበት የዓለም አቀፍ ምድብ የንግድ ምልክቱን በብቸኝነት የመጠቀም መብት (Exclusive Right) ያለው ስለመሆኑ፤<br>➢ በንግድ ምልክትነት እና በንግድ ስምነት ተመዝግቦ ጥቅም ላይ እየዋለ | 192580 | እንደራስ ናሽናል ኃላ/የ/የግ/ማህበር<br>እና<br>እንደራስ የንብረት | ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም | 391 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ያለ በሌላ ሰው ባለቤትነት በንግድ ስምነት ሊመዘገብ አይገባም ወይም የተመዘገበው ሊሰረዝ ይገባል የሚል ክርክር ሲቀርብ ተቃውሞ የቀረበበት አንድ አይነት ስለመሆኑ ወይም የሚመሳሰልና ህዝብን የሚያሳስት እንዲሁም የአስመዘጋቢውን መብት የሚጎዳ ስለመሆን አለመሆኑ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባ እንጂ የህግ ማዕቀፍ የለም ተብሎ የሚታለፍ ስላለመሆኑ፤<br><br>ዓለም አቀፍ እቃዎች እና አገልግሎቶች ምድብ ለመወሰን የወጣ ናይስ ስምምነት (Nice Agreement Concerning the International Classification of Goods and Services for the purposes of the Registration of Marks)፣ አዋጅ ቁጥር 813/2006፣ ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008፣ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና የእነዚሁ አዋጆች ማስፈፀሚያ ደንቦች | | አስተዳደር<br>ኃላ/የተ/የግ/ማህበር | | |
| 55. | በኢንሹራንስ ውል ፓሊሲ ላይ የተመለከተው አደጋ ደርሶ ከሚከፈለው ካሳ ወይም ጉዳቱን በማስጠገን ከሚወጣው ወጪ ላይ ኢንሹራንስ ገቢው በውሉ በተወሰነው ልክ የራስ ኪሳራ/*Own Damage* (የአደጋ መነሻ ወይም Excess) ኢንሹራንስ ሰጪው ቀንሶ እንዲያስቀር የሚደረግ ስምምነት ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው የሚገባ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 663/2፣ 654/1 እና 658፣ 678 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 | 197994 | ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ ዳዊት ገ/ህና | ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ.ም | 401 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 56. | የደላላነት ስራ ለመስራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ሳይኖር የደላላነት ስራ ሰርቻለሁ ብሎ ክፍያ ለማስከፈል የሚቀርብ ክስ የህግ ጥበቃ በሌለው መብት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ስለሆነ ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀጽ 5/19፣ 56 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች | 204199 | አቶ ዳዊት በላይ<br>እና<br>አቶ ፀጋዬ ሰኚ | ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም | 409 |
| 57. | የብድር ውል የአራጣ ውል ነው ለማለት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች | 178414 | እነ ወ/ሮ ገነት በላቸው<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ዮሴፍ አከበረኝ | ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም | 415 |
| --- | ይህ ውሳኔ በቅጽ 24፤ ገጽ 252 ላይ የታተመ ሲሆን በዚህ ቅጽ ጭብጡ ብቻ ተስተካክሎ ወጥቷል፡፡<br>አንድ ባንክ ለደንበኛው ክፍያ የፈጸመዉ በዋናነት ተከፋዩ ሰዉ ብቻ ያዉቀዋል ተብሎ የሚገመተዉን ፍሬ ነገር ማለትም ገንዘቡን የላከዉ ሰዉ ማንነት፤የተላከዉ ገንዘብ መጠን፤የሚስጥር ቁጥር እና የተላከለት ሰዉ ስም እና ተከፋዩ ሰዉ የሰጠዉ መረጃ ተዛማጅና ትክክል መሆናቸዉ በተለመደዉ አሰራር መሰረት በማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ክፍያዉን የተቀበለዉ ሰው ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ ይዞ ስለቀረበ ክፍያው ለማይገባው ሰዉ ነዉ በሚል ምክንያት ባንኩ በድጋሚ ገንዘቡን እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ | 188419 | አባይ ባንክ አ.ማ<br>እና<br>አቶ ማርቆስ ጋትሮ | መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ.ም | ---- |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2/2/መ/፣ 53 | | | | |
| **አፈፃፀም** | | | | | **424** |
| 58. | ☞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 435 በጠባቡ መተርጎም ስላለበት በአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ የሚገባዉ ነገር ባለመገለጹ ወይም የሽያጩ ሥነ ሥርዓት በትክክል ባለመፈጸሙ ምክንያት በተፈጠረ ጉድለት ሐራጁ ሊፈርስ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ድንጋጌዉ ባለማመላከቱ ጉዳት የደረሰበት ማንኛዉም ሰዉ የሐራጅ ሽያጩ ሳይፈርስ ለጉዳቱ አላፊ በሆነዉ ሰዉ ላይ ክስ አቅርቦ ተገቢውን ካሳ የሚካስ ስለመሆኑ | 193115 | አቶ ቶፊቅ መለሰ<br>እና<br>እነ አቶ እንድሪስ ሳቢር<br>(2 ሰዎች) | ጥር 27 ቀን 2013 ዓ/ም | 425 |
| **የወንጀል ህግ** | | | | | **431** |
| 59. | የቅጣት ውሳኔ እንዳይገደብ በወንጀል ህግ አንቀፅ 194 ስር የተቀመጠው ክልከላ ባልተሟላበት ሁኔታ ተከሳሽ ክሱን ክዶ ከመከራከሩም በላይ ከተበዳይ ጋር ታርቆ ለመካስ እና የፍርድ ቤትን ወጪ ለመሸፈን የሰጠው ማረጋገጫ የለም በሚል በመልካም ጠባይ የሚመራ ለመሆኑ በፍርድ ቤት እንዲያቀርብ የሚጠየቅ የዋስትና ማረጋገጫ ትዕዛዝ ቅጣትን ለመገደብ ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ የሚወሰድ ስላለመሆኑ | 185700 | የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ ቢዝነስ ለማ | የካቲት 30 2013 ዓ.ም | 432 |
| 60. | በተደጋጋሚ ወንጀል ፈጽሞ የተቀጣ ተከሳሽ አዲስ ወንጀል ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤት ቅጣቱን ለማክበድ በወንጀል ሕግ ልዩ ክፍል ከተደነገገው | 186919 | አቶ ብርሃኑ ምላው<br>እና | ታሕሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም | 435 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጣራ ቅጣት በማለፍ የዚህን መጠን እጥፍ በመያዝ መወሰን የሚችል ቢሆንም ይህ የሚቻለው ወንጀሉ የተደጋገመ መሆኑን ብቻ በማየት ሳይሆን ጥፋተኛው የፈጸማቸው ወንጀሎች ዓይነት፣ ክብደት እና ብዛት እንዲሁም ወንጀል ለመፈጸም የነበረው የአደገኝነት መጠን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ<br>የወንጀል ሕግ አንቀጽ 188 (1) እና (2)፣ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22/2 | | የትግራይ ክልል ዓቃቤ ሕግ | | |
| 61. | በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶች እንደ ሙከራ ሊቆጠሩ ይችላሉ የሚል አስተያየት ቢኖርም አንድን የወንጀል ድርጊት ሙከራ ነው ለማለት ድርጊቱ በእውቀትና በፍላጎት የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ መሰረታዊ መስፈርት ስለሆነ በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶችን እንደ ሙከራ መቁጠር በአሁኑ ጊዜ ብዙም ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 27(1)፣ 23(2) እና 58(1) (ለ) | 181206 | አቶ ሐይሉ (አብይ) ሲሳይ<br>እና<br>የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ | መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ/ም | 440 |
| 62. | በወንጀል ህግ አንቀጽ 670፣ 672ና 240፣ የተደነገጉት ውንብድና፣ ዘረፋ እና ሽፍታነት የሚሉት ቃላት ቴክኒካዊ ልዩነት በመካከላቸው ያለና በተናጠል የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትሉ በመሆኑ የአንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት “ውንብድና ነው” ወይም “ዘረፋ ነው” ወይም “ሽፍታነት ነው” ለማለት ከመነሻው አጠቃላይ የተፈፀመው ድርጊት እና | 209051 | ዳኜ ደጀኔ<br>እና<br>በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሸካ | ጥር 27/2014 ዓ.ም | 445 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የተከሳሹ ተሳትፎ በተገቢው መንገድ ተለይቶ ሊታወቅ እና ሊረጋገጥ፤ በእምነት ቃል መሰረት ውሳኔ ለመስጠትም የተሰጠው ቃል ተከሳሹ ከተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር ጋር አንድ ሊሆን፤ ዝርዝር ቃሉም ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የማያጠራጥርና ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 20፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134 (1) እና 141 | | ዞን ዐቃቤ ህግ | | |
| 63. | በወንጀል ህግ አንቀጽ 693(1) መሰረት የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል የተከሰሰ ቼክ አውጪ ቼኩን ለመመንዘር ሳይሆን በግለሰቦች መካከል በነበረው የንግድ ግንኙነት መነሻነት ለመተማመኛ የሰጠ በመሆኑ ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊወጣ የሚችለው ቼኩን ለዋስትና ወይም ለመያዥ'ያነት የሰጠ ለመሆኑ እና የዋስትና ወይም የመያዥ'ያ ውሉም በንግድ ህግ እና በፍትሐ ብሔር ህግ በተመለከተው መመዘኛ መሰረት ስለመፈፀሙ በማስረዳት ከመሆኑ በቀር በሰው ምስክር የሚሰጥ ማረጋገጫ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ አንቀፅ 952 እና የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2864-2866<br>**(በፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ. 67947 ተሰጥቶ** | 161448 | የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ<br>እና<br>የሺመቤት ጥላሁን | ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም | 450 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የነበረው የህግ ትርጉም ተሻሽሏል)** | | | | |
| **አሠሪ እና ሰራተኛ** | | | | | **462** |
| 64. | ☞ የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ያስቀመጠው አስገዳጅ የክርክር መፍቻ መንገድ ሳይጣስ በሕጉ ከተጠቀሱት ዘዴዎች በተሻለ ሁኔታ የጊዜ፣ የሰው እና የገንዘብ ሀብት የሚቆጥብ እና በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የሚከሰት አለመግባባት ፍትሀዊ በሆነ አኳኋን የሚፈታበትን ዘዴ ወይም የስራ ክርክር እልባት የሚያገኝበትን ስርዓት በኅብረት ስምምነት መዘርጋትን ህጉ የማይከለክል ስለመሆኑ<br>አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 136፣142፣144 እና 145<br>☞ለስራ ክርክር ችሎት ክስ ማቅረብ የሚቻለው በኅብረት ስምምነት በተመለከተው መሰረት ቅሬታ ለቅሬታ ሰሚ አካል ከቀረበ በኋላ በሆነ ጊዜ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት ቅሬታ ሰሚ አካል ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 164/1 | 219611 | አቶ አስራኤል ሉሌ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ/ም | 463 |
| 65. | በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገው ይርጋ ክስ የማቅረብ መብትን ቀሪ የሚያደርግ ባለመሆኑ ሰራተኛው የተሰናበተበትን ምክንያት፣ ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን እና ምክንያቱ የተከሰሰበትን ቀን | 222297 | አቶ ተስፋልኡል ቱፋ<br>እና<br>የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ | ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም | 469 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አሰሪው መቼ እንዳወቀ በግልጽ በማሰናበቻ ጽሁፍ ላይ ሳይገልጽለት አሰናብቶት ከሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ለማወቅ ያልተቻለ እንደሆነና እነዚህን ፍሬ ነገሮች ያወቀው አሰሪው ተከሶ በሰጠው መከላከያ መልስ ላይ ከተገለፀው ፍሬ ነገርና ከቀረበው ማስረጃ መነሻ የሆነ እንደሆነ ክሱን ለማሻሻል የግድ ከሆነ የአዋጁን አንቀጽ 27/3 ይዘት ባገናዘበ መልኩ ክሱን በማሻሻል አሊያም ክስ በሚሰማበት ጊዜ በቃል አንስቶ መከራከር የሚችል ስለመሆኑ | | ግብዓቶች ልማት ድርጅት | | |
| **ከውል ውጪ ኃላፊነት** | | | | | **476** |
| 66. | ➢ የፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 2143/2 ዓላማ ለካሳ ጥያቄው መነሻ የሆነው ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣና የይርጋ ጊዜውም ረዘም ያለ ከሆነ ካሳ ጠያቂው ረዘም ያለውን የወንጀል ህግ የይርጋ ጊዜ በመጠቀም ክሱን ማቅረብ እንዲችል ለማስቻል በመሆኑ የወንጀል ሕግ ይርጋ ጊዜ ከ2 ዓመት ያነሰ በሆነ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ላይ የተደነገገው ስለመሆኑ<br><br>➢ ኢንሹራንስ ኩባንያዎች በደንበኛቸው በመዳረግ ጉዳት አድራሹ ላይ ለሚያቀርቡት ክስ የይርጋ ጊዜ መቆጠር ያለበት ካሳ ከከፈሉበት ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ | 194880 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ፈይሰል አህመድ | የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ/ም | 477 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 67. | ✍ ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት ለደረሰ ጉዳት እንዲከፈል የሚወሰን ካሳ በተቻለ መጠን ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090/1 እና 2091<br>✍ ኢንሹራንስ ሰጪዎች ቅሪት አካሉ እንዲሰጣቸው ወይም የቅሪት አካሉ ግምት ከካሳው ላይ እንዲቀነስ በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ካሳው ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል መሆን አለበት በሚል መከራከሪያ ማእቀፍ ውስጥ ሊታይ የሚገባ እንጂ ዳኝነት ተከፍሎ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መቅረብ አለበት የሚባል ክርክር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234 (1/ረ) | 204256 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>ሳምራዊት ጫኔ | ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም | 486 |
| | **የወንጀል ሥነ ስርዓት ህግ** | | | | **491** |
| 68. | ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ምስክር ሊሰማ አይገባም በሚል የተሰጠ ውሳኔ ራሱን ችሎ ይግባኝ የሚቀርብበት እንጂ ከዋናው ጉዳይ ጋር ተጠቃሎ በይግባኝ የማይታይ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ፣ የወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 6/1/ለ እና 4/1/ቀ | 200520 | የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>እነ እስክንድር ነጋ<br>/5 ሰዎች/ | የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ.ም | 492 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 69. | በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.184 መሠረት የትዕዛዝ ይግባኝ የሌለ ስለመሆኑ የተደነገገ ቢሆንም የተሰጠው ትዕዛዝ ወደፊት በዋናው ጉዳይ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ የማይችልና ውጤቱም የሚቀለበስ ካልሆነ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የተሰጠ ይግባኝ ነው በሚል ተቃውሞ የማይቀርብበትና በይግባኝ የሚታይ ስለመሆኑ<br><br>ለእስረኞች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በማረሚያ ቤት ውስጥ በተዘጋጀ የጤና ተቋም ቢሆንም በሕግ ጥላ ስር የሚገኝ ተጠርጣሪ በጤና ተቋሙ ለመታከም እምነት የሌለው በመሆኑ በመረጠው የግል የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኝ በጠየቀ ጊዜ ይህንን ለማከናወን የፀጥታ ስጋት ቢኖርም መንግስት ጸጥታ እና ደሕንነትን በማስጠበቅ ተጠርጣሪው ህክምናውን እንዲያገኝ ሊያመቻች የሚገባ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22/1፣ አዋጅ ቁጥር 1174/2012 ድንጋጌዎች | 203051 | እነ አቶ ጀዋር ሲራጅ መሐመድ<br>(4 ሰዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም | 498 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 70. | ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታን ጨምሮ ተከራካሪ ወገኖች ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች በነፃነት እና ያለ አድሎ የመዳኘት ግዴታቸውን አልተወጡም በማለት የሚያቀርቡት ማናቸውም አቤቱታ ሕጋዊ መሠረት ያለው እና በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ ሊቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ<br><br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 እና 79፣ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 106፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን እና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/1968 | 189472 | አቶ አሸብር አውዴ<br>እና<br>በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>የወላይታ ምድብ ዓቃቤ ሕግ | ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 504 |
| 71. | ብርብራ የሚደረግበት የህግ ስርዓት ዝርዝር ሁኔታዎች የተመላከቱ ቢሆንም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32(2) የተመለከቱት ቀሪ ሁኔታዎች (Exceptions) በሌሉበት ብርበራ ያለ ብርበራ ትዕዛዝ ቢከናወን ወይም በብርበራ ትዕዛዙ ከተመለከተው ጊዜና ቦታ ውጪ ብርበራ ቢደረግ አልያም በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በሆነ ሁኔታ ፖሊስ በብርበራ የመያዙ አግባብነት ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት በቂ እና ምክንያታዊ ጊዜ ነበር የሚለው የብርበራውን ህጋዊነት ለመመዘን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ ስለመሆኑ | 211525 | እነ መንሱር ጁሃር<br>(2 ሰዎች)<br>እና<br>የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ | መጋቢት 08 ቀን 2014 ዓ/ም | 512 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ☞ ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ከተሰጠው የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት አንፃር በፍርድ ቤት በብርበራ ትዕዛዝ ላይ ከተመለከተው ውጪ በሆነ ሁኔታ ፖሊስ የመያዙ አግባብነትን በተመለከተ ቅድሚያ ሊከበር የሚገባ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት ያለ መሆኑ የሚታይና የሚመዘን ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 26 (1)፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32(2)(ለ) እና 33 (1) | | | | |
| | **የምርጫ ጉዳዮች** | | | | **521** |
| 72. | ☞ ከህገ መንግስት ነክ ክርክሮች አወሳሰንና የህገ መንግስት ትርጉም አስፈላጊነትን መወሰንን በተመለከተ የህገ መንግስት ትርጉምን በማይጠይቁ ግልጽ የሆኑ የህገ መንግስት ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በህገ መንግስት ክርክሮች ላይ ውሳኔ መስጠት እንዲሁም ትርጉም የማያሻቸው መሆኑን በፍርድ መወሰን የፍርድ ቤቶች ስልጣን ስለመሆኑ<br>የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(2) እና የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 4(2)<br>☞ የክልል ህገ መንግስት ድንጋጌ ህገ መንግስታዊ መሆን አለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ተጣርቶ ውሳኔ እስካልተሰጠበት ድረስ ህገ መንግስታዊ ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ | 207036 | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ<br>እና<br>በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ | ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም | 522 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከር እና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 9<br>☞የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ በጉባኤው የተደረሰበት ውሳኔ እና የክልሎች ሕገ መንግስት እንዲሁም እነዚህን ሰነዶች መሰረት በማድረግ የሚከናወን የምርጫ ሂደት ሕገ መንግስታዊ አይደለም የሚል ከሆነ ይህንን ለማስለወጥ ጉዳዩን ወደ ፌደሬሽን ምክር ቤት አቅርቦ ከሚታይለት በቀር ቦርዱ በራሱ ውሳኔ የማይሰጥ ስለመሆኑ<br>የፌደሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከር እና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 4(1) እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1) | | | | |
| 73. | የምርጫ ውጤት ከድምጽ መስጫ ወረቀት ጋር በተያያዘ ግድፈት የተፈፀመበት ነው ተብሎ የምርጫ ውጤት ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እንደ ፍርዱ ድጋሚ ምርጫ ለማድረግ መሰረት የሆነው የውሳኔ ሁኔታ የተቀየረና ዳግም ምርጫውን ማከናወን የማይቻለው በመሆኑ የቀደመውን የምርጫ ውጤት ተግባራዊ ማድረጉን በመግለጽ | 228650 | የደ/ብ/ብ/ክ/መንግስት ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና ፓርቲ) እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ፣ | ሀምሌ 6 ቀን 2014 ዓ/ም | 538 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚሰጠው ውሳኔ የምርጫ ሂደትን የሚመለከት የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚቀርብበት እንጂ አስተዳደራዊ ውሳኔ ነው በሚል ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ስላለመሆኑ<br>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) እና የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) | | የቁጫ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቁህዴፓ) | | |
| 74. | የምርጫ ክልሎችን አከላለል በሚመለከት የሕዝብ እና ቤት ቆጠራን መሠረት በማድረግ እና ተገቢውን ጥናት በማካሄድ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ለፌደሬሽን ምክር ቤት በሚያቀርበው የምርጫ ክልል ረቂቅ መሠረት የፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ አዲስ የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልሎች አከላለልን በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 103(5) እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/6 መሠረት ለፌደሬሽን ምክር ቤት ረቂቅ አቅርቦ የተሰጠ ውሳኔ በሌለበት ሁኔታ ለምርጫ ማስፈጸሚያ ዓላማ በምርጫ አካባቢ በተደራጀ የአገሪቱ ግዛት ላይ ለውጥ የማይደረግ ስለመሆኑ<br>የኢትዮጲያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 13/1(ሀ) (ለ) | 208898 | የኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እና ሞቻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ | ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም | 545 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **557** |
| 75. | ከማስታወቂያ ስርጭት ጋር በተያያዘ የአሰራጩ ሃላፊነት፡፡<br>የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 | 193480 | ኢ.ቢ.ኤስ ቴሌቪዥን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አምሳሉ ሲሳይ<br>(73 ሰዎች) | ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም | 558 |
| 76. | ➢ ከገጠር መሬት ይዞታ ክርክር ጋር በተያያዘ ሁለት ዳኝነቶች በአንድ ላይ ተጣምረው ሲቀርቡ የፍርድ ቤት ስልጣንን በሚመለከት የስነ ስርዓት ህግ ይዘት ያላቸው ድንጋጌዎች በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፣ በሥነ-ሥርዓት ሕግና በክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የተመለከቱ ቢሆንም የክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ልዩ ሕግ ስለሆነ በሕግ አተረጓጎም መርሕ መሠረት ልዩ ሕጉ በቀዳሚነት የሚተገበር ስለመሆኑ<br>የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16(1)(ረ)፣ የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 30(3)<br><br>➢ የገጠር መሬት ውርስን መሠረት አድርጎ ለቀረበ ክስ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ ስለመኖሩ የክልል የገጠር | 191968 | አቶ ዋኬኔ ዲንቃ<br>እና<br>እነ አቶ ኤብሳ እጅጉ<br>(4 ሰዎች) | ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ/ም | 575 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ የተለየ ድንጋጌ በሌለው ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1677(1) እና 1845 የተመለከተው የ10 ዓመት ጊዜ ስለመሆኑ | | | | |
| 77. | የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ጋብቻ በፍቺ ወሳኔ እንዲፈርስ በወሰነበት ሁኔታ የፍቺ ዉጤቱንም ሰምቶ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ይኼዉ የሸሪዓ ፍ/ቤት እንጂ የፌደራል ፍ/ቤቶች የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 (5) እና አንቀጽ 78 (5)፣ የፌደራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 5 (4)፤የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 (2፣ሀ) እና 245 (2) | 175719 | አቶ ረዲ አህመድ<br>እና<br>ወ/ሮ መኪያ ሀሰን | ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም | 584 |
| 78. | የመንግስት መኖሪያ ቤት የሚከራየው በከተማ ውስጥ ነዋሪ ኢትዮጲያዊ ዜግነት ላለው እና/ወይም በከተማው ውስጥ ነዋሪ ለሆነ የጸና/የታደሰ የኢትዮጲያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ላለው የውጭ ዜጋ ብቻ ነው ተብሎ የተደነገገው ከከተማው አስተዳደር ቤትን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚከራዩ ሰዎችን የሚመለከትና ውል በሚታደስበት ጊዜም በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል የሚባል ከሆነ ተከራይ ይህን ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በቅድሚያ | 181359 | እነ አቶ ዲክሳ ኪዳኔ<br>(3 ሰዎች)<br>እና<br>የጉለሌ ክፍለ<br>ከተማ ወረዳ 9 ቤቶች<br>ልማት ጽ/ቤት | ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም | 589 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊረጋገጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 43/ሀ፤ 44/3፤ 44/13 እና 45/2 | | | | |
| 79. | የክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ከገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ጋር በተያያዘ መመዘኛዎችን ከማስቀመጥ ባለፈ ወራሽነትን ቀድሞ ያረጋገጠ ብቻውን የሚወርስ ስለመሆኑ ባልደነገገበት ሁኔታ በወራሾች መካከል በተነሳ የገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ይገባኛል ጥያቄ ወራሽነትን ቀድሞ አረጋግጦ የውርስ ሀብት በመያዝና ቀድሞ ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ ልዩ የመውረስ መብት የሚገኝ ስላለመሆኑ<br>የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 17 እና ተከታዮቹ | 181643 | ወ/ት እንኳአየሁሽ ነጋሽ<br>እና<br>አቶ ካሳሁን ነጋሽ | ህዳር 29/2013 ዓ.ም | 596 |
| 80. | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ህጋዊ ሰውነት የሚመነጨው ከ1952ቱ የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀፅ 398 በመሆኑ ቤተክርስቲያንዋ ተካፋይ የሆነችበት ክርክር እንደ ክርክሩ ዓይነት፣ መጠን እና ቦታ ጉዳዩ በቀረበበት ክልል የሚታይ ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግሰት አንቀፅ 78(2)፣ 80(2) ፣ (4) እና (5)፣ የፌደራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(6) እና 11(1) | 184533 | አስገዳጅ ደብረ መዊ ቅዱስ ጊወርጊስ ቤ/ክርስቲያን<br>እና<br>ቄስ ሞላ ሰማው | መጋቢት 30 2013 ዓ.ም | 600 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 81. | ለፍርድ ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን ህግን መሰረት ያደረገ የዳኝነት አገልግሎት መሰጠት በመሆኑ ይህ ማለት በፍርድ ቤት ለሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ፤ በተለይም መብትን የሚያሳጣ በሆነ ጊዜ ግልፅ የህግ መሰረት ሳይጠቀስ ውሳኔ ከተሰጠ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 78 እና 79 | 181278 | አቶ ሀፍቱ ኪሮስ<br>እና<br>የሀውልቲ ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | ጥቅምት 26 2013 ዓ.ም | 603 |
| 82. | የገጠር መሬት በዉርስ እንዲተላለፍ ዳኝነት የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ የተለየ የህግ ድንጋጌ በሌለ ጊዜ ክርክሩ በወራሾች መካከል ሲሆን በእርሻ መሬት የዉርስ ጥያቄ ላይ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ የይርጋ ደንብ ጠቅላላ የ10 አመት የይርጋ ጊዜ ሳይሆን በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) ላይ የተደነገገው የ 3 አመት የይርጋ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 | 187340 | እነ ወ/ሮ ዙፋን መንግስቱ (2 ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ በልስቲ አባተ (4 ሰዎች) | መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም | 608 |
| 83. | የክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም ለመወሰን በወጣ አዋጅ መሰረት የገጠር መሬትን በሽያጭ ውል ማስተላለፍ ክልከላ የተደረገበት ከሆነ መሬቱ ላይ ቤት ቢኖርበትም ባይኖርበትም የሽያጭ ውሉ ከመጀመሪያውኑ ህጉን ያልተከተለ ስለሆነ በህግ ፊት የማይፀና ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ፣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ | 186431 | ወ/ሮ አዝመራ መኮንን<br>እና<br>እነ አቶ ገ/ሂወት መኮንን (2 ሰዎች) | ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም | 613 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 239/2006 | | | | |
| 84. | የተሻሻለ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በነባር ህግ መሰረት በሕይወት ያለ ሰው የገጠር መሬት ይዞታውን በሚመለከት የመሬት ስጦታ ውል አድርጓል የሚባለዉ በሥራ ላይ በነበረዉ አዋጅ መሰረት እንጂ ከዛ ወዲህ የክልል መንግስት የፖሊሲ ለዉጥ በማድረግ ያወጣዉን ሕግ መሰረት ተደርጎ ስላለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና የተሻሻለው የአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 | 185848 | አቶ ጌታሰዉ አገሩ<br>እና<br>እነ አቶ አስማማዉ ለማ<br>(3 ሰዎች) | ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም | 618 |
| 85. | የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች በጡረታ ከተሰናበቱ በኋላ መብትና ጥቅማቸውን ለመወሰን በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ስለተሰጠ የአገልግሎት ዘመን በፌደራል መንግስት ታሳቢ የሚደረግ ስለመሆን አለመሆኑ አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 53/3 የደነገገው ባይኖርም ዳኞች በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት እና በፕሬዝዳንትነት ማገልገላቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በገንዘብ ተሰልተው የሚከፈሉ የመቋቋሚያ አበል፤ የመኖሪያ ቤት አበል እና የተሽከርካሪ አበል ክፍያዎችን ለማግኘት በፌደራል ፍርድ ቤት ያገለገሉበት ዘመን ሲቆጠር በክልል በዳኝነት እና በፕሬዝዳንትነት የሰጡት አገልግሎት ታሳቢ የሚደረግ ስለመሆኑ | 201181 | አቶ ጳውሎስ አርሺሶ<br>እና<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር | ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም | 623 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ አንቀጽ 50/2፣ አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1003/2009 | | | | |
| 86. | የግልግል ዳኝነት ስምምነት ላይ የሕጋዊነት ጉድለት በመኖሩ ምክንያት ለመፈጸም እምቢተኛ መሆንን በሚመለከት የሚቀርብ ክርክር የግልግል ሥምምነቱ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት እንዲፈርስ መወሰኑን ሳይጠብቅ የግልግል ጉባዔው ጉዳዩን ተመልክቶ ሊወስን የሚችል ቢሆንም የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ ስለማጣቱ እንዲሁም የግልግል ጉባኤው ጉዳዩን ለመመልከት ስልጣን የለውም በሚል የሚቀርብ ክርክርን ሰምቶ የመወሰን ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1809፣3330 | 180793 | አቶ ያሬድ ተስፋይ /ያሬድ ተስፋይ ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንጂነሪንግ/<br>እና<br>ዓዲግራት ዩንቨርስቲ | ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ/ም | 631 |
| 87. | ➢ በፍትሐ ብሔር ሕግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል መኖር ሳይረጋገጥ ክርክርን ከስጦታ ዉል ከማስመዝገብ አንጻር ብቻ በማየት የስጦታ ዉል እንዲመዘገብ የሚያስገድድ ሕግ ስለሌለ መሬትን ይዞ በመጠቀም ብቻ በስጦታ የተላለፈ ነዉ ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 ወይም 882<br>➢ የገጠር የእርሻ መሬት በስጦታ ማስተላለፍ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ልዩ ሕግ ሆነዉ ተፈጻሚ መሆን ያለባቸዉ ስለገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር የወጡ ሕጎች ቢሆኑም በእነዚህ ሕጎች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች እና | 188853 | አቶ ሻረው ወርቅዬ<br>እና<br>እነ ልክዬ ወርቅዬ<br>(2 ሰዎች) | መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም | 637 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሕጎቹ ስራ ላይ ባልዋሉበት ጊዜ የተፈጸሙ ሕጋዊያን ተግባራት ላይ እንደ ነገሩ ሁኔታ በፍትሐ ብሔር ሕግ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ስለሚተላለፍበት የተደነገገዉ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ | | | | |
| 88. | በመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5(2) የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር አመት ማገልገል እና በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 18 መሰረት የጡረታ እድሜ መድረስ ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ እና በራሱ ፈቃድ ወይም በአዋጁ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ለዘለቄታው የማያገኝ ስለመሆኑ<br>**(የፌ/ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው በአዋጅ ቁጥር 454/1997 መሰረት በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁጥር 132861 ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ተለውጧል።)** | 160792 | የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ተስፋዬ መብራቴ | መጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ/ም | 645 |
| 89. | አንድ ግለሰብ የያዘውን የገጠር እርሻ መሬት በሕግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል ካልሆነ በቀር ሌላ ግለሰብ መሬቱ የተያዘው በሕገ-ወጥ መንገድ ነው በማለት አስለቅቆ ሊይዝ የማይችል ስለመሆኑ | 187618 | አቶ የሸዋስ አስማረ<br>እና<br>አቶ ያሲን አሊ | መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ.ም | 652 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 90. | ✐ከገጠር የእርሻ መሬት ኪራይ ውል ጋር በተያያዘ በልዩ ሕግ የተደነገገ የይርጋ ጊዜ ከሌለ ተፈፃሚነት የሚኖረው የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1845 ስር የተደነገገው ስለመሆኑ<br>✐ ይርጋን በሚመለከት መቃወሚያ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው የክስ ምክንያትን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33 (2 እና 3)፣ 80፣ 222 (1/ረ እና ሽ) እና 234(1/ሐ) | 187484 | አቶ በየነ ከበደ<br>እና<br>እነ ገረመው አይናለም<br>(2 ሰዎች) | የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ.ም | 662 |
| 91. | ✐ በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ 699/2003 አንቀጽ 4/1 (ተ) እስከ (ሰ) እና (ዘ) ስር የተዘረዘሩት ጥበቃዎች በባሕርያቸው ከክርክር ሂደቱ ጋር የተያያዙ ሆነው በአስፈፃሚ አካል የሚወሰዱ ሳይሆን በአዋጁ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ድንጋጌ መሠረት በምክንያት ተደግፈው የሚቀርቡ የፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ስለመሆናቸው<br>✐በወንጀል ምስክሮችና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ 699/2003 አንቀጽ 4 ስር የተዘረዘሩ የጥበቃ ዓይነቶች ውስጥ የጥበቃ ዓይነቱ ሲወሰን የተከሳሾችን ሕገ መንግስታዊ መብት ሊጎዳ በማይችል መልኩ መሆን እንዳለበት የሚደነግገውን የአዋጁን አንቀጽ 5/3 ከግምት ያስገባ፣ በአንቀጽ 3/ሀ ስር የተገለፀውን ቅድመ ሁኔታ ሊያሟላና የሚቀርብ ምክንያትም በቂ፤ አሳማኝ እና በአዋጁ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ የተፈቀደበትን ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ስለመሆኑ | 210997 | የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>እነ እስክንድር ነጋ<br>(5 ሰዎች) | ነሐሴ 10 ቀን 2013 ዓ.ም | 669 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 | | | | |
| 92. | በጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 1177/2012 አንቀፅ 4(2) መሰረት ለቀረበ ክስ አዋጁን ለማስፈፀም የመቆጣጣር ስልጣን የተሰጠው አካል አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ የሌለውን የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች መሳሪያውን አስመዝግበው ፈቃድ ለመውሰድ የሚችሉበትን የጊዜ ሰሌዳ ወስኖ ወደ ስራ ያልገባ ስለሆነ መሳሪያ ይዞ መገኘት ወንጀል አይደለም በሚል ህግ ወጥ የጦር መሣሪያ ማዘዋወር ወንጀል ክስን ውድቅ ማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የአዋጁ አንቀፅ 4(2)፣ 6 እና 23(2) እንዲሁም የወንጀል ህግ አንቀፅ 808 | 205727 | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ<br>እና<br>ባህሩ ታዬ | ጥቅምት 29/2014 ዓ.ም | 683 |
| 93. | የቡና ጥራት ቁጥጥርን አስመልክቶ የህግ አውጪነት ስልጣኑ የፌደራል መንግስት አልያም የክልል መንግስታት ስለመሆኑ በግልፅ የተመለከተ ነገር በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት መሰረት ባይኖርም የክልል መንግስታት የወንጀል ጉዳይን አስመልክቶ በፌደራል መንግስት ከወጣው ህግ ጋር የሚቃረን ወይም የማይጣጣም ህግ የማውጣት ስልጣን ያልተሰጣቸው በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ቡናን ከማጓጓዝ የወንጀል ኃላፊነት እና የቅጣት ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ያለው በፌደራል መንግስት የወጣው አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 55(5) | 209763 | አቶ እምራን ታጁ<br>እና<br>የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ | ጥር 25/2014 ዓ.ም | 687 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 94. | ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለበት ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት በሀራጅ በሌላ ሰው እጅ የገባ ቢሆንም የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከንብረቱ ላይ የሚፈለገውን ቀረጥ እና ታክስ ለማስከፈል ንብረቱን ተከታትሎ የመያዝ ከህግ የመነጨ ስልጣን ያለው በመሆኑ ለዚህ አላማ ኮሚሽኑ ንብረቱን በቁጥጥር ስር የማዋል ድርጊት በህግ የተሰጠውን የመቆጣጠር ኃላፊነት ተግባራዊ አድርጓል ከሚባል በቀር የሁከት ተግባር ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1149(3)፣ የጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 130፣ 141፣ 2(22)፣ 2(38)፣ 143 እና 147 | 210238 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ጌታቸው ታደሰ | ህዳር 27/2014 ዓ.ም | 694 |

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ.መ.ቁ. 180551

ህዳር 28/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

አመልካች፡- ሀዊ ሁንዴ

ተጠሪዎች፡

1. አምበሳ አዱና
2. አዱና ኢዴሳ
3. ዱዴሳ አያኖ
4. ውሌሳ ለታ
5. ሻምቦ ውሌሳ
6. ታደሰ ውሌሳ
7. በንቲ ለታ
8. እናኑ ጉሬጃ
9. ዳባ ለታ
10. ጫልቺሳ እናኑ
11. ሂርጰ ሰርዳ
12. ገሸማ ጉሬጃ
13. በዳዳ በንቲ
14. ትርፌሳ ገሸማ
15. ኢጀራ ለታ
16. ፉፋ ጣፋ
17. ቶለሳ ጣፋ
18. ጃለኔ ለታ
19. ዱጋሳ ውሌሳ
20. ገደፋ አዱኛ
21. አዱና ሰቦቃ
22. ኢዴሳ አያኖ
23. ደበሎ ሙለታ
24. ሙለታ አዱና
25. ነገሳ ሙለታ
26. ተፈራ አያኖ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው በፍትሐ ብሔር ክስ ክርክር ተከሳሽ የነበረ ሰው በክርክር ላይ እያለ መሞቱን ተከትሎ የሚቹ ወራሾች ሚቹን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ሊቃወሙ አይችሉም በሚል የተወሰነበትን የህግ አግባብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን እናት ጨምሮ በሶስት ሰዎች ላይ የገጠር መሬት ይዞታን በተመለከተ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ያቀርባሉ፡፡ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ የአሁን አመልካች እናት ከዚህ ዓመት በሞት ይለያሉ፡፡ ክርክሩም በዚሁ ቀጥሎ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን አመልካች ከእናታቸው አኳያ የተሰጠው ውሳኔ መብታቸውን የሚነካ መሆኑን ጠቅሰው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የመቃወም አቤቱታ ውሳኔን ለሰጠው ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም በመቃወም አቤቱታው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ክርክር የቀረበበት ይዞታ የአሁን አመልካች እናት እና አባት መሆኑ እና በስማቸውም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት ቀድሞ የተሰጠውን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ውሳኔን አፅንቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በመ/ቁ/305233 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ሐምሌ 02/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች የመቃወም አቤቱታ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ የአመልካች እናት የክርክሩ ተካፋይ ሆነው በክርክር ላይ እያሉ ከሞቱ አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 50 በሚያዘው መሰረት በእናታቸው እግር ተተክተው ክርክሩን ከሚያስቀጥሉ በቀር በሚያውቁት ጉዳይ ላይ ውሳኔውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ሊቃወሙ አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 05/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የአሁን ተጠሪዎች ክርክር የተነሳበት ይዞታ ይገባናል የሚል መከራከሪያ ከማቅረብ ባለፈ አመልካች በመቃወም አመልካችነት ቀርባ ልትከራከር አይገባም የሚል ክርክር ባላቀረቡበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባልተነሳ ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አይደለም፤ ወላጅ እናት ከተጠሪዎች ጋር በክርክር ላይ የነበሩ ስለመሆኑ የማውቀው ነገር የለም፤ እናቴ በክርክር ላይ እያሉ ሞሞታቸውን ፍርድ ቤቱ

ከተረዳ ከእርሳቸው አንፃር ጉዳዩን ማቋረጥ ሲገባው ክርክሩን ቀጥሎ በተጠሪዎች ማስረጃ ብቻ ውሳኔ መስጠቱ ከሥነ ሥርዓት ውጭ በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ ስህተቱን አርመው የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የውርስ ሀብቱን ለመጠየቅ መብታቸው የሚቋቋመው እናታቸው ሲሞቱ ሆኖ እያለ የአሁን ተጠሪዎች ከአመልካች እናት ጋር ሲከራከሩ አመልካች ታውቅ ነበር በሚል ምክንያት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ያቀረቡትን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገበት አግባብ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ 24ኛ ተጠሪ መሞታቸው በመረጋገጡ ምክንያት ከእኚህ ተጠሪ ውጭ ያሉት ተጠሪዎች በጠበቃቸው አማካኝነት ጥር 14/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ባቀረቡበት ጉዳይ ላይ ወላጅ እናታቸው በተከራካሪነት ተካፋይ የነበሩ ስለመሆኑ እና ሌሎች ተከሳሾች የነበሩትም የአመልካች ወንድሞች በመሆናቸው አመልካች ክርክሩን ታውቅ ነበር፤ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚፈልጉ ከሆነ አንድም በክርክር ላይ እያሉ በሞቱት እናታቸው እግር ተተክተው ክርክሩን ማስቀጠል አልያም ከውሳኔው በኋላ ቅሬታ ካላቸው በይግባኝ ከሚያሳርሙ በቀር መብቱ በውርስ እንደተላለፈላቸው ወራሽ ሳይሆን መብቱ እንደተነካ 3ኛ ወገን ሆነው በፍርድ ተቃዋሚነት ሊቀርቡ አይችሉም፤ ወሳኔውም በአፈፃፀም ያለቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ የሚቀርብበት ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ውሳኔ መብቱ የሚነካ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡ አንድ ሰው ወይም አካል በፍርድ ቤት በተያዘ ክርክር የክርክሩ አካል ሊሆን የሚችለው በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ፣ በራሱ በጣልቃ ገብ አቤቱታ አቅራቢነት አልያም በተከሳሽ ወገን ጥያቄ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40፣ 41 እና 43 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ በሂደት ላይ በሚገኝ ሙግት መግቢያ መንገዶች ውስጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት በፍርድ ተቃዋሚነት ሊቀርብ የሚችለው

በዋናነት ቀድሞ በተደረገው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 በተመለከተው መሰረት በጣልቃ ገብነት ቀርቦ መብቱን እና ጥቅሙን ማስከበር ይችል የነበረ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ የግል ይዞታዬ ነው በሚል ሳይሆን ከወላጅ እናቴ በውርስ ሊተላለፍልኝ የሚገባ ሀብት ነው የሚል ነው፡፡ አውራሻቸው የሆኑት ወላጅ እናታቸው ደግሞ ይህንን ይዞታ በተመለከተ በአሁን ተጠሪዎች ክስ ቀርቦባቸው በክርክር ላይ እያሉ ስለመሞታቸው የተካደ አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ይዞታ በተመለከተ አመልካች የሚኖራቸው መብት ከአውራሻቸው የተላለፈላቸው እንጂ እራሱን የቻለ መብት ባለመሆኑ ወላጅ እናታቸው ተካፋይ ለነበሩበት ክርክር 3ኛ ወገን የሚባሉ አይደለም፡፡ ቀድሞ በተደረገ ክርክር እና በተሰጠ ውሳኔ 3ኛ ወገን ያልሆነ ሰው ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት በፍርድ ተቃዋሚነት የሚመጣበት የህግ አግባብ የለም፡፡ የአመልካች ጉዳይም በክርክር ላይ እያለ የሞተን ተከሳሽ መብት የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩ የሚመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 50 እና ተከታዮቹ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አመልካች በክርክር ላይ የነበሩት ወላጅ እናቴ ከሞቱ በኋላ ወደ ክርክሩ እንድገባ እና የክርክሩ አካል እንድሆን ለሟች ወራሾች ተገቢው መጥሪያ አልተደረገም የሚል መከራከሪያ በአመልካች በኩል አልቀረበም፡፡ ይህ ባልሆነበት አመልካች አውራሻቸው ተከራካሪ በነበሩበት ጉዳይ ላይ በፍርድ ተቃዋሚነት ቀርበው የሚከራከሩበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/305233 ሐምሌ 02/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.181236

ጥር 25/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-አቶ ሽለመ አበራ

ተጠሪዎች፡1. አቶ መገርሳ ምትኩ

2. ወ/ሮ ጠጂ በዳዳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/303165 ላይ ሚያዚያ 29/2011 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የክርክሩ ሥረ ነገር የጀመረው የአሁን አመልካች በወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከተው ይዞታ የወላጅ አባታቸው መሆኑን፤ አባታቸው በ1992 ዓ.ም ከሞቱ ወዲህ የአሁን 2ኛ ተጠሪ በውርስ ሊተላለፍላቸው የሚገባውን የአባታቸውን ድርሻ ይዘው የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ እንዲያካፍሏቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ የአሁን 2ኛ ተጠሪም "አመልካች የአባታቸውን ድርሻ ቢካፈሉ ተቃውሞ የለኝም" የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው ጭብጥም "ግራ ቀኙ ተከራክረዉበት ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም ይዞታነቱ

የራሴ በመሆኑ ውሳኔው በይዞታዬ ላይ የተሰጠ ነው” የሚል ነው፡፡ የመቃወም አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም በአቤቱታው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ግንቦት 22/2010 በዋለው ችሎት የመቃወም አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 29/2010 ዓ.ም በተፃፈ የመቃወም አቤቱታ በአመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የመቃወም አቤቱታው መነሻም “ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ ነባር ይዞታነቱ የአመልካች ወላጆች ቢሆንም ‘ግብር መገበር አልቻልንም’ በሚል ይዞታውን ለአስተዳደሩ በመመለሳቸው ምክንያት በ1989 ዓ.ም ተሰጥቶኝ እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ ሳርስ ቆይቼ ከ1992 በኋላ ደግሞ በቦታው ላይ ዛፍ እና ፅድ ተክዬበት ከ21 ዓመት በላይ በእጅ አድርጌ እየተጠቀምኩበት ያለ ይዞታዬ በመሆኑ በይዞታዬ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል” የሚል ነው፡፡

በዚሁ አቤቱታ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ መቃወሚያ እና የስረ ነገር ክርክር በማቅርብ ተከራክረዋል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም የመቃወም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በተመለከተ ቀደም ሲል የመቃወም አቤቱታ አቅራቢ ወላጅ አባት ይዞታው በ1ኛ ተጠሪ ስም የሚገኝ ቢሆንም የራሴ ነው፤ 1ኛ ተጠሪም የአእምሮ ታማሚ እና ከእኔ ጋር የሚኖር በመሆኑ ውሳኔው በይዞታዬ ላይ የተሰጠ ነው በሚል ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከወላጅ አባቱ ጋር የሚኖር በመሆኑ ይህ ሲሆን ያውቃል፤ አቤቱታውም የቀረበው የክርክሩን ውጤት በመጠበቅ ወላጅ አባቱ ሞክሮ ያልተሳካለትን በ1ኛ ተጠሪ በኩል ለማሳካት ተመሳጥረው ያቀረቡት ነው፤ ክርክር መደረጉን እያወቁ ውጤቱን በመጠበቅ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/56745 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርብበት አይችልም የሚል ነው፡፡ በሥረ ነገር ክርክሩ ደግሞ ውሳኔ ያረፈበት ይዞታ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ በእኩሌታ ሲያርሱ የቆዩ ከመሆኑ ውጭ ይዞታው የ1ኛ ተጠሪ አይደለም፤ 1ኛ ተጠሪ ይዞታው ከመንግስት ተሰጠኝ ባሉበት 1989 ዓ.ም ህፃን የነበረ በመሆኑ በራሱ ስም ይዞታ ለማግኘት በሚያስችለው እድሜ ላይ አልነበረም፤ አሁንም ቢሆን 1ኛ ተጠሪ የመንግስት ሰራተኛ እንጂ ገበሬ ባለመሆኑ ይዞታው የራሴ ነው በሚል ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመቃወም አቤቱታው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ስለይዞታው ከክፍሉ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክርክር የቀረበበት ይዞታ ነባር ይዞታነቱ የአሁን አመልካች ወላጅ አባት ነው፤ ይህንን ይዞታ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ይዞ እያረሰ የሚገኘው የመቃወም

አቤቱታ አቅራቢው ሳይሆን ወላጅ አባታቸው ነው፤ የመቃወም አቤቱታ አቅራቢ ወላጅ አባት ደግሞ ይዞታውን በተመለከተ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ግንቦት 22/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውድቅ ተደርጓል፤ የይዞታው ስም ሀብት በመቃወም አመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም ይዞታውን ያገኙበት መንገድ የማይታወቅ ስለመሆኑ ከክፍሉ አስተዳደር የተገለፀ በመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መያዛቸው ብቻ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1146(1-3) መሰረት የሚፈጥርላቸው የይዞታ መብት የለም፤ የይዞታ ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት በፍ/ብ/ህ/ቁ/1196 መሰረት ሊስተባበል የሚችል ማስረጃ በመሆኑ እና የመቃወም አመልካች ማስረጃውን ያገኙበት መንገድ የማይታወቅ እና ሥርዓቱን የጠበቀ ባለመሆኑ የሚያጎናፅፋቸው መብት የለም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 337 መሰረት ውድቅ ተደርጓል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ከላይ በመግቢያው ላይ በተመለከተው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በሰጠው ውሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ከ20 ዓመት በላይ በአሁን 1ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኝ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን፤ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 40(3 እና 7) መሰረት መሬት በርስት የማይተላለፍ የህዝብ እና የመንግስት የጋራ ሀብት በመሆኑ ከ20 ዓመት ቆይታ በኋላ አመልካች ያቀረበው ጥያቄ በክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀፅ 32 መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 16/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡበትን ውሳኔ አስመልክቶ ቀደም ሲል ወላጅ አባታቸው ተመሳሳይ የመቃወም አቤቱታ አቅርበው ውድቅ መደረጉ እና የአሁን 1ኛ ተጠሪም የዚህኑ ክርክር ውጤት ጠብቀው መቃወምያውን ያቀረቡ ለመሆኑ የቀረበው ክርክር እያሳየ አቤቱታው ተቀባይነት ማግኘቱ አግባብ አይደለም፤ ክርክር የቀረበበት ይዞታንም በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ በማይታወቅ መንገድ የይዞታ ማረጋገጫ ከመያዛቸው በቀር ይዞታውን ይዘውም ሆነ ተጠቅመውበት እንደማያውቁ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ አባቱ በይዞታው ተጠቅሟል በሚል ለልጁ የይርጋ መብት መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤ የ1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባትም ቢሆኑ በይዞታው መጠቀም የጀመሩት በ2001 ዓ.ም መሆኑን እና የአመልካች ወላጅ አባት በ1992 ዓ.ም ሲሞቱ አመልካች የ5 ዓመት ህፃን የነበረ ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን ጊዜ በመቁጠር ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ ተጠሪዎች መጋቢት 02/2012 ዓ.ም የተፃፈ የተናጠል መልስ አቅርበዋል፡፡ የ1ኛ ተጠሪ መልስ መሰረታዊ ይዘትም ክርክር በተነሳበት ይዞታ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ያወቅሁት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ እንጂ ከዚያን በፊት ወላጅ አባቴ አቅርበዋል ስለተባለው የመቃወም አቤቱታም ሆነ ስለክርክሩ የማውቀው ነገር የለም፤ ይዞታውን በተመለከተ የአመልካች እናትና አባት በ1988 ዓ.ም መሬት ለማስተዳደር ስልጣን ላለው አካል ቀርበው የመሬት ግብር መክፈል አለመቻላቸውን በመግለፃቸው ምክንያት ከነበራቸው ይዞታ ላይ ተቀንሶ አሁን ክርክር የቀረበበት ይዞታ ተሰጥቶኝ እስከ 1992 ዓ.ም ድረስ ካረስኩ በኋላ በ1992 ዓ.ም ዕድና ባህርዛፍ ተክዬበት እና ቤት ሰርቼበት እንዲሁም በ1996 ዓ.ም የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስጄበት እየተጠቀሙበት የምገኝ ህጋዊ ይዞታዬ እንጂ የውርስ ይዞታ አይደልም፤ በዚህ መልኩ ይዞታውን በእጄ አድርጌ ስጠቀምበት አመልካች የሚያውቅ ሲሆን ያቀረበው መቃወሚያ አለመኖሩን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አረጋግጦ ጥያቄን ውድቅ ያደረገ በመሆኑ ውሳኔው የሚነቀፍ አይደለም የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ጥያቄ መሰረት ቢወሰንለት ቅሬታ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በመስጠት ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታውን ያቀረቡት ክርክር መኖሩን እያወቁ የክርክሩን ውጤት በመጠበቅ በመሆኑ የመቃወም አቤቱታ ልታቀረቡ አይገባም በማለት በአሁን አመልካች የቀረበው መቃሚያ የታለፈበት አግባብ በቅድሚያ መጣራት ያለበት ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ባላወቀው እና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ውሳኔ መብቱ የሚነካ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ተግባራዊ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ አንድ ሰው መብቱን የሚነካ ክርክር መጀመሩን እያወቀ የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት ፍርዱን ሊቃወም የማይችል ስለመሆኑ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/56795 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ መቃወሚያ አቅራቢው ቀድሞ ሲደረግ የነበረውን ክርክር የሚያውቅ መሆኑን ያለመሆኑ ጉዳይ ደግሞ የህግ ነጥብ አልያም በችሎት ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል ክርክር ሳይሆን ተከራካሪ ወገኖች በሚያቀርቡት አግባብነት ያለው ማስረጃ ነጥሮ የሚወጣ የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ ከዚህ አኳያ ተከራካሪዎች የሚያቀርቡት ክርክር እና ማስረጃ በአግባቡ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ ከወላጅ አባቱ ጋር በአንድ ቤት የሚኖር በመሆኑ እና አባቱ የመቃወም አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ ሲደረግበት ክርክሩን ያውቅ የነበረ በመሆኑ የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መቃወሚያ ሊያቀርብ አይገባም በማለት ተቃውመዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በዚህ መልኩ የቀረበውን ክርክር ክደዋል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ "ቀድሞ ሲደርግ የነበረውን ክርክር ማወቅ" የሚለው ሀረግ ለፍርድ መቃወሚያ አቤቱታው መሰረት የሆነውን ክርክር ብቻ የሚመለከት ነው ወይስ ፍርዱን በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት ቀርቦ የተደረገውን ክርክርንም የሚጨምር ነው የሚለው በአግባቡ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረታዊ ዓላማ ባላወቀው እና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠ ፍርድ መብቱ የተነካበት አካል ከፍርዱ በኋላ መብቱን የሚያስከብርበትን ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ዓላማ አኳያ የመቃወም አቤቱታ አቅራቢው ክርክር እየተደረገ ስለመሆኑ የነበረው እውቀት በዋናው ጉዳይ ላይም ሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት በቀረበ አቤቱታ ላይ መሆኑ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ እናም መብቴን እና ጥቅሜን ነክቷል በተባለ ፍርድ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት ክርክር ሲደረግ የነበረ መሆኑን የሚያውቅ አካል ውጤቱን ጠብቆ ከፍርድ በኋላ በራሱ ፍርዱን በመቃወም የሚያቀርበው አቤቱታ ፍርድን መቃወም ከተፈቀደበት መሰረታዊ ዓላማ ውጭ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ባቀረቡበት ፍርድ ላይ ቀድሞ ሲደረግ የነበረውን ክርክር ከማወቃቸው ጋር ተያይዞ ግራ ቀኙ ተካክደዋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ 1ኛ ተጠሪ በእርግጥም እውቀቱ የነበራቸው መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ማስረጃ በአግባቡ አጣርቶ መወሰንን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንፃር የወረዳው ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት ቀደም ብለው የመቃወም አቤቱታ አቅርበው ውድቅ የተደረገባቸው ስለመሆኑ በፍርድ ሀተታው ውስጥ ከመግለፁ ውጭ 1ኛ ተጠሪ ያንን ክርክር ያውቁ የነበረ መሆኑ ስላለመሆኑን አስመልክቶ ያደረገው ማጣራትም ሆነ ከቀረበው መቃወሚያ አኳያ የወሰደው ግልፅ አቋም የለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ቀድሞ ሲደረግ የነበረውን ክርክር ማወቅ ያለማወቃቸው ጉዳይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ አኳያ 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ካለመሆኑ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የወረዳው ፍርድ ቤት ይህንን ነጥብ በግራ ቀኙ ማስረጃ በተገቢ አኳኋን አጣርቶ አቋም ሳይያዝ በሌላው የክርክር ዘንግ ላይ ውሳኔ መሰጠቱ እና በየደረጃው ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንን ሳያርሙ መቅረታቸው መሰረታዊ የሙግት አመራር ግድፈት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/303165 ላይ ሚያዝያ 29/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/47133 ላይ ታህሳስ 04/2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/18497 ላይ ህዳር 19/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአሁን 1ኛ ተጠሪ "ቀድሞ የተደረገውን ክርክር እያወቁ ውጤቱን ጠብቀው የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡ በመሆኑ ፍርዱን ሊቃወሙ አይችሉም" በማለት አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ በተገቢው ማስረጃ ተጣርቶ አቋም ሳይያዝበት በሌላው የክርክር ዘንግ ላይ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የሙግት አመራር ግድፈት የተፈፀመበት ነው በማለት ተወስኗል፡፡
3. የወንጪ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ፤
   - 3.1. የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ላይ ክርክር ሲደረግ ያውቁ የነበረ መሆን ስላለመሆኑ ግራ ቀኙ ቀድሞ በጠቀሷቸው ማስረጃዎች በማጣራት፤ ቀድሞ የተቆጠረ ማስረጃ ከሌለም ከዚህ አኳያ ግራ ቀኙ አለን የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ ፍሬ ነገሩን ካጣራ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ረገድ የሚኖረውን ውጤት በአግባቡ በመመርመር የመሰለውን እንዲወስን፤
   - 3.2. 1ኛ ተጠሪ የመቃወም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል የሚባል ከሆነ በሥረ ነገር ክርክሩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ቀድሞ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይዘት በመመርመር እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ተጨማሪ ምስክር በመስማት ወይም ማስረጃ በማስቀረብ ማስረጃዎቹን ከቀረበው ክርክር አኳያ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ መርምሮ እና መዝኖ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343(1) መሰረት መዝገቡ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.181999

መስከረም 27/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ ወ/ሮ ተሰሜ ገዳ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡ 1. አቶ ለማ ነጋሽ ቀርበዋል

2. አቶ መለሰ ዘውዴ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ በፍርድ ቤት በተሰጠ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቅት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 358 መሰረት የቀረበ መቃወሚያን የሚመለከት ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበውም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/310729፤ ሰኔ 10/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ወላጅ አባታቸው አቶ ገዳ ኡርጌሳ መስከረም 11/2010 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን እና ሟች በህይወት እያሉ በስማቸው ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠበት 1.61 ሄክታር የገጠር እርሻ መሬት ያላቸው መሆኑን በመግለፅ የወላጅ አባታቸው ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ የወራሽነት ምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ለዲክሰስ ወረዳ ፍርድ ቤት ባመለከቱት መሰረት ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ/15004 ላይ ህዳር 17/2011 ዓ.ም ይህንኑ አረጋግጦ የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን ተጠሪዎች ጥር 2/2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፍርድ ቤቱ የተሰጠው የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መብታችንን ነክቷል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት ውሳኔውን በመቃወም ይቀርባሉ፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም አመልካች የወራሽነት ምስክር ወረቀት በወሰዱበት ይዞታ ላይ ቀደም ሲል

የአመልካች ወንድሞች በዚያው ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/14008 ተመሳሳይ የውርስ ክስ በተጠሪዎች ላይ አቅርበው ጥያቄያቸው በይርጋ ይታገዳል ተብሎ ውድቅ ተደርጎ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና መሆኑን፤ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ በይዞታቸው ላይ ለአመልካች የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀት መብታችንን የሚጎዳ በመሆኑ የተሰጠው የወራሽነት ምስክር ወረቀት ሊሰረዝ ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ መቃወሚያ በሰጡት መልስ መኖሪያ ቦታቸው ሰሜን ሸዋ ዞን ደገም ወረዳ በመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 14008 ላይ ተደረገ የተባለውን ክርክር እንደማያውቁ፤ የወራሽነት ምስክር ወረቀት የወሰዱበት ይዞታ የወላጅ አባታቸው ሲሆን እስከ 2010 ዓ.ም ድርስ በወላጅ አባታቸው ስም ግብር ሲገበርበት የቆየ መሆኑን፤ የአሁን ተጠሪዎች ይዞታውን በኪራይ ለረዥም ጊዜ ሲያርሱ የነበረ በመሆኑ ከይዞታው ላይ የተወሰነውን በመጀመሪያ ዙር የይዞታ ምዝገባ በወላጅ አባታቸው ከተመዘገበ በኋላ ሁለተኛ ዙር አመልካች ባላወቁት መንገድ በስማቸው ከማስመዝገባቸው ውጭ ከይዞታው ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን በመግለፅ መቃወሚያቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ሞግተዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በአመልካች ወንድሞችና በተጠሪዎች መካከል ክርክር ተካሂዶበት ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ አመልካች የመውረስ መብት የላቸውም በማለት ቀድሞ የሰጠውን የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃውን ሰርዟል፡፡ ይኸው ውሳኔ በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 01/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/79871 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ተላልፈው በተጠሪዎች መቃወሚያ አቤቱታ መነሻነት የወራሽነት ማረጋጋጫ ማስረጃቸውን መሰረዛቸው አግባብ እንዳልሆነ፤ የወራሽነት ምስክር ወረቀት የተሰጠበት ይዞታም የሟች አባታቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪዎች በስማቸው ሳያስመዘግቡ በሀሰት ምስክርነት ውሳኔ መሰጠቱ የአመልካችን የመውረስ መብት የሚያሳጣ መሆኑን፤ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ በጉልበታቸው እያለሙ ከአመልካች አባት ጋር በእኩል ሲጠቀሙ የነበረ ከመሆኑ ውጭ ከይዞታው ላይ የሚጠይቁ መብት የሌላቸው መሆኑን፤ ተጠሪዎች የሀሰት ማስረጃ አያይዘው ከሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ተጨማሪ ማስረጃ በማቅረብ ጉዳዩን ማጣራት ሲገባቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲከራከሩ የተሰጠ ውሳኔን መሰረት አድርገው በህግ አግባብ የተሰጣቸውን የወራሽነት ማስረጃን መሰረዛቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን በመጥቀስ የተሰጠው ውሳኔ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካች የወራሽነት ማስረጃ የተሻረበት አግባብ ግራ ቀኙ በተገኙበት በዚህ ችሎት እንዲፈተሽ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪዎች የካቲት 03/2012 ዓ.ም በተፃፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች የአባቷ ወራሽ ብትሆንም መሬቱን ተጠሪዎች በህግ አግባብ ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ በስማቸው ተመዝግቦ ካርታ ተሰርቶላቸው ግብር እየገበሩበት ከ30 ዓመት በላይ ይዘው እየተጠቀሙ ያሉ መሆኑን፤ የአመልካች ወንድሞች በዚሁ መሬት ላይ ቀደም ሲል ክስ አቅርበዉባቸው እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የተወሰነላቸው መሆኑን፤ አመልካች የግል ይዞታቸውን ከተጠሪዎች ይዞታ ጋር ቀላቅለው የወራሽነት ማስረጃ የወሰዱበት በመሆኑ እና ውሳኔው መብታቸውን የሚነካ በመሆኑ መቃወማቸውም ሆነ የስር ፍርድ ቤቶችም በመቃወሚያ መሰረት ማስረጃውን መሰረዛቸው አግባብ መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር የመል መልስ በማከል ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው አካል ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ውሳኔ መብቱ የሚነካው ማናቸውም አካል ስለመሆኑ እና መቃወሚያውም ሊቀርብ የሚገባው ፍርድ ከመፈፀሙ በፊት ስለመሆኑ ከድንጋጌው ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያ ወራሽነትን ለማረጋገጥ በሚሰጥ ማስረጃ ላይ ሊቀርብ እንደማይችል፤ ይልቁንም በማስረጃውም ምክንያት መብቴ ተነክቷል የሚል አካል ካለ ተገቢውን ዳኝነት ከፍሎ ተጓደለብኝ የሚለውን መብት ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/79871 ላይ የካቲት 11/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎተ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በማናቸውም ደረጃ ባሉት የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች ላይ የአስገዳጅነት ኃይል ያለው ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀፅ 2/4/ ይደነግጋል፡፡

ሆኖም የሰበር ችሎቱ የህግ ትርጉም የአስገዳኝነት ባህሪ የሚኖረው በምን ዓይነት ጉዳይ ላይ ነው የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በሰበር ችሎቱ የሚሰጠው የህግ ትርጉም የአስገዳጅነት ኃይል ወይም ባህሪ የሚኖረው ቀድሞ በተሰጠው የህግ ትርጉም እና ዳኝነት ተጠይቆበት በክርክር ላይ ባለው ጉዳይ መካከል ተመሳሳይ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር ሲኖር ብቻ እንደሆነ (The

same fact and the same question of law) ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/67924፣ 68573፣ 37964፣ 52407፣ 84353፣ 58157 እና በሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ ትርጉም ተሰጥቶ አቋም ተይዟል፡፡ የሰበር ችሎቱ የሚሰጠው የህግ ትርጉም አስገዳጅ እንዲሆን የተፈለገው በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ህጎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተተርጉመው እንደ ሀገር ወጥ እና የተረጋጋ የህግ ሥርዓት እንዲሰፍን ለማስቻል እንጂ ችሎቱ በማናቸውም መልኩ የሚጠቅሳቸው ጉዳዮች በሙሉ እንደ ህግ እንዲወሰዱ አይደለም፡፡

ከዚህ አንፃር በሰ/መ/ቁ/79871 ላይ ቀርቦ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው ማስረጃውን መሰረት በማድረግ የውርስ ሃብት ነው በሚል የያዙትን ንብረት የሚመለከት ክርክር ሲሆን በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ክርክር ደግሞ የውርስ ሀብት ተለይቶ በሀብቱ ላይ የተሰጠ የወራሽነት ምስክር ወረቀትን የሚመለከት ነው፡፡ እናም በሁለቱ ጉዳዮች መካከል ተመሳሳይ የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክር ባለመኖሩ በሰ/መ/ቁ/79871 የተሰጠው ትርጉም በዚህ መዝገብ ላይ ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ያለው ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አስገዳጅ የህግ ትርጉምን ተላልፏል የሚባል አይደለም፡፡

ከዚህ በመለስ ለአሁን አመልካች የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ የአሁን ተጠሪዎች በፍርድ መብት ባገኙበት ይዞታ ላይ የተሰጠ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን ከቀረበው የስር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ግልባጭ መገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች የወራሽነት ማስረጃ የወሰዱበት ሀብት ሌላ ሰው በፍርድ መብቱን ባረጋገጠበት ሀብት ላይ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ ቀደም ሲል የተሰጠው ማስረጃ መሰረዝ ያለበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ መልኩ በመወሰናቸው የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/310729 ላይ ሰኔ 10/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/88043 ላይ የካቲት 29/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የዲክሰስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/15004 ላይ የካቲት 12/2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.182361

ጥር 28/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-አቶ ግርማ የሺጥላ

ተጠሪ፡-ወ/ሮ አመለወርቅ እሸቴ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በሁከት ይወገድልኝ ክስ መነሻነት ቀርቦ ውሳኔ ያገኘ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አፈፃፀም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 30140 በቀን ሐምሌ 18/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረበትን የመጨረሻ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ እና በከተማ አስተዳደሩ ሶስት የመንግስት ጽ/ቤቶች ላይ ክስ ያቀርባሉ፡፡ በቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ ቀርቦ የነበረው ክስ ጭብጥም የአሁን ተጠሪ ከመንግስት ተከራይተው የነበረውን የንግድ ቤት ለሁለት ከፍለው ግማሹን ለአሁን አመልካች ያከራይዋቸው መሆኑን፤ በዚሁ አግባብ አመልካች በተከራዩት ቤት የንግድ ፈቃድ አውጥተው በመስራት ላይ እንዳሉ መመሪያ ቁጥር 4/2004 በመውጣቱ እና በመመሪያው መሰረት የአሁን ተጠሪ ከመንግስት የተከራዩትን ንግድ ቤት ሸንሽነው ለ3ኛ ወገን እያከራዩ ስለመሆኑ በማስረጃ በመረጋገጡ ምክንያት አመልካች ከተጠሪ የተከራዩት ቤት በቤት ቁጥር 913(1) ተሰይሞ በስማቸው ከመንግስት ጋር የኪራይ ውል የተዋዋሉ መሆኑን፤ ይህ ከሆነ በኋላ በፍርድ ቤቱ 1ኛ ተከሳሽ የነበረው የአዲስ አበባ ከተማ ዲዛይንና ግንባታ ልማት አስተዳዳር ጽ/ቤት ያቋቋመው ግብረ ኃይል አመልካች የተከራዩት ቤት ለአሁን ተጠሪ ይገባል በሚል ባቀረበው የተሳሳተ ሪፖርት

መነሻነት "የንግድ ቤቱ አልተሸነሸነም፣ የአሁን ተጠሪም ገቢ የሌላቸው እና አቅመ ደካማ ናቸው" የሚሉ ነጥቦችን በመጥቀስ ተጠሪ በስማቸው የኪራይ ውል እንዲዋዋሉ ያደረገ መሆኑን፣ በዚሁ መነሻነት በቤቱ ላይ የተሰጣቸው የንግድ ፈቃድም የተሰረዘባቸው መሆኑን በመጥቀስ የተከሳሾቹ ድርጊት የሁከት ተግባር ነው ተብሎ ከአስተዳደሩ ጋር የገቡት የኪራይ ውል እንዲቀጥል እና የተሰረዘባቸው የንግድ ፈቃድ ወደነበረበት እንዲመለስ ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን ተጠሪ ክስ የቀረበበት ቤት የሚገባኝ መሆኑ ተጣርቶ የተወሰነልኝ በመሆኑ የፈጠርኩት ሁከት የለም የሚል የመከላከያ መልስ እና አመልካች ክስ ያቀረበበትን ቤት ከህግ አግባብ ውጭ የያዘ በመሆኑ የ4 ወር ውዝፍ ኪራይ ከፍሎ ሊለቅልኝ ይገባል የሚል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ሸንሽነው ማከራየታቸው ተረጋግጦ እያለ አስተዳደሩ ከአመልካች ጋር የገባውን የኪራይ ውል ማቋረጡ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊወገድ ይገባል፣ የንግድ ፈቃዱም መሰረዙ አግባብ ባለመሆኑ ወደነበረበት ሊመለስ ይገባል፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን የለኝም ሲል ወስኗል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን ተጠሪ ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ የቀረበለት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በመ/ቁ/19288 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የካቲት 18/2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቀደም ሲል ከአስተዳደሩ ጋር የገቡት የንግድ ቤት ኪራይ ውል ፀንቶ ባለበት አስተዳደሩ ከአሁን አመልካች ጋር የገባው የኪራው ውል ህገ ወጥ ነው፣ የአሁን አመልካችን የንግድ ፈቃድ በተመለከተ በአዋጅ ቁር 686/2002 አንቀፅ 39(1(ሀ-ሰ)) መሰረት ፈቃዱን የሚያሰርዝ ምክንያት በሌለበት መሰረዙ አግባብ ባለመሆኑ ወደነበረበት ይመለስ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ነው፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን በተመለከተ የከተማ አስተዳደሩ አከራክሮ የመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው በመሆኑ በዚሁ ነጥብ ላይ አከራክሮ ይወስን በሚል ጉዳዩን በነጥብ መልሷል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው በሰ/መ/ቁ/87917 ላይ በመታየት ላይ እያለ የአሁን ተጠሪ ደግሞ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔው መሰረት ጉዳዩን ለከተማ አስተዳደሩ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ ክርክሩን አስቀጥለዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጥቅምት 08/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ለአሁን ተጠሪ እንዲለቁ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለመባሉ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/87917 ላይ በመታየት ላይ የነበረው የግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ጥቅምት 22/2006 ዓ.ም ውሳኔ አግኝቷል፡፡ በውጤቱም የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት የመስተዳድሩ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን አለው ብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆኑን፤ ግራ ቀኙ ከአስተዳደሩ ጋር የገቡትን ውል በተመለከተ ከቀረበው ክርክር አኳያ የአሁን ተጠሪ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀፅ 6(1) መሰረት በልዩ ሁኔታ በመመሪያው ተጠቃሚ ስለመሆናቸው በአግባቡ ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የውሉን ህጋዊነት አስመልክቶ በየፊናቸው ውሳኔ መስጠታቸው አግባብ አለመሆኑን በመተቸት ከዚሁ አኳያ የግራ ቀኙ ክርክር በተጨማሪ ማስረጃ በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ለመስተዳድሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነጥብ ተመልሷል፡፡

በዚሁ አግባብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን በመስማት ላይ እንዳለ የአሁን ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ አስመልክቶ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀምላቸው ግንቦት 18/2006 ዓ.ም የተፃፈ የአፈፃፀም አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በዚሁ ነጥብ ላይ የአሁን አመልካችን መከራከሪያ ከሰማ በኋላ ሐምሌ 17/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የተሰጠው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/87917 ላይ በመታየት ላይ የነበረው የግራ ቀኙ ክርክር ውጤት ሳይታወቅ መሆኑን፤ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጥቅምት 22/2006 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንደገና እንዲጣራ በሚል ካዘዘው ነጥብ አኳያ ውሳኔው በውጤት ደረጃ የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሻረ በመሆኑ ውሳኔው ሊፈፀም የሚችል አይደለም ሲል የተጠሪን አቤቱታ በብይን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ ክርክሩ እንዲቀጥል አዟል፡፡ ይኸው ብይን እስከ ከተማ አስተዳዳሩ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ቀርቦበት ፀንቷል፡፡

ዋናውን ክርክር በተመለከተ ሐምሌ 01/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክር የተነሳበትን ቤት አስተዳደሩ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 መሰረት የአሁን ተጠሪን ተጠቃሚ ያደረገበት ሁኔታ አግባብ አለመሆኑን ማረጋገጡን ጠቅሶ በአሁን አመልካች ላይ የተፈጠረው ሁከት ሊወገድ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በመቀጠል ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበው በሰ/መ/ቁ/140055 ላይ ሲታይ ቆይቶ መጋቢት 24/2010 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ አስተዳደሩ በቅሬታ ሰሚ አካል ጉዳዩን በማጣራት የአሁን ተጠሪ በመመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀፅ 6(1) መሰረት ልዩ ተከራይነት ሊፈቀድላቸው እንደሚገባ ያሳለፈው ውሳኔ ለአስተዳደሩ በህግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ የተወሰነ ነው ወይም

በህግ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ወይም የተዘረጋውን ስርዓት ባለመከተል የተወሰነ ነው የሚያሰኝ ባለመሆኑ የአስተዳደሩ ውሳኔ ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡

ይህንን ተከትሎ የአሁን ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን አስመልክቶ ጥቅምት 08/2006 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲፈፀምላቸው ሚያዝያ 26/2010 ዓ.ም የተፃፈ የአፈፃፀም አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚሁ ጉዳይ ላይ የአመልካችን መልስ ከሰማ በኋላ ጥቅምት 16/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት አፈፃፀም የተጠየቀበት ውሳኔ ቀደም ሲል የአሁን ተጠሪ የአፈፃፀም አቤቱታ አቅርበዉበት ሐምሌ 17/2006 ዓ.ም በተሰጠ ብይን ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ የለም በሚል ውድቅ የተደረገ በመሆኑ እና ይህ ብይን ፀንቶ ባለበት የአፈፃፀም ጥያቄው በድጋሚ መቅረቡ አግባብ አይደለም በማለት የተጠሪን አቤቱታ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡

በአሁን ተጠሪ ይግባኝ ባይነት በዚሁ ውሳኔ ላይ ጉዳዩ የቀረበለት የከተማው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በመ/ቁ/30140 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሐምሌ 18/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቀደም ሲል አቅርበዉት የነበረው የአፈፃፀም አቤቱታ ሐምሌ 17/2006 ዓ.ም በተሰጠ ብይን ውድቅ የተደረገው ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ክርክሩ ሳይቋጭ የቀረበ ጥያቄ ነው በሚል መሆኑን፤ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን አስመልክቶ በመስተዳድሩ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት ያልተለወጠ በመሆኑ ፀንቶ ያለ ውሳኔ መሆኑን፤ በኋላም እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገ ክርክር የአሁን ተጠሪ ክርክር በቀረበበት ቤት ላይ በፍርድ የተረጋገጠ መብት ያገኙ በመሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ፍርዱ ሊፈፀም አይችልም ያለበት ምክንያት ቀሪ መሆኑን ተገንዝቦ አፈፃፀሙን ማስቀጠል ሲገባው በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ በህግ አግባብ የተሰጠ ፍርድንና በፍርድ የተረጋገጠውን የተጠሪን መብት ዋጋ የሚያሳጣ መሆኑን በመግለፅ የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን እና ትዕዛዝ ሽሮ በአፈፃፀም አቤቱታው መሰረት ጥያቄውን ተቀብሎ እንዲያስፈፅም ጉዳዩን ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ መልሷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 9/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የቀድሞ ውሳኔዎች እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሰው ሊፈጸም የሚችል ነገር የለም ተብሎ በተሻረበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት አፈፃፀም

ይቀጥል በማለት የወሰነበትን አግባብ ለዚ ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከላይ በፍርድ ሀተታው ላይ በዝርዝር ከተመለከተው የክርክሩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙን ለዚህ የሰበር ችሎት ክርክር ያበቃው የአሁን ተጠሪ ያቀረቡትን የፍርድ አፈፃፀም አቤቱታን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰደው አቋም ነው፡፡ የአፈፃፀም አቤቱታው የቀረበለት የከተማ አስተዳደሩ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው ቀደም ሲል ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ የለም በሚል ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በድጋሚ ሊቀርብ አይገባም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሰረቱ አፈፃፀም የሚቀርበው በፍርድ በተረጋገጠ መብት ላይ ነው፡፡ የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት መብት ፍርድ ያረፈበት ቢሆንም በተለያየ ምክንያት ፍርዱ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊፈፀም የማይችል ስለመሆኑ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ከተረዳ ስለፍርዱ አፈፃፀም ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደማይገባ፤ ይልቁንም ፍርዱ ሊፈፀም በሚችልበት በማናቸው ጊዜ እንደፍርዱ እንዲፈፀም ሊታዘዝ የሚቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 392(2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው መሰረታዊ ቁም ነገር በፍርድ የተረጋገጠ መብት እንደማናቸውም ክርክር ተቆጥሮ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ሙግት ሊቀርብበት የሚቻል ሳይሆን መብቱ እስከሚፈፀም ድረስ አመቺ በሆነ ጊዜ ሁሉ ስለአፈፃፀሙ ተገቢው ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ እናም የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት በዋናነት ማረጋገጥ ያለበት የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ ፍርድ ያረፈበት እና ጥያቄው በቀረበበት ወቅት ሊፈፀም የሚችል መሆኑን እንጂ የአፈፃፀም ጥያቄው ስንት ጊዜ ቀረበ የሚለው አይደለም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የሁከት ክስ ያቀረቡበትን ቤት አስመልክቶ የአሁን ተጠሪ አቅርበዉት በነበረው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መነሻነት አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲለቁ እና ውዝፍ የቤት ኪራይም እንዲከፍሉ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ይህ ውሳኔ ይግባኝ ተጠይቆበት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ስለመለወጡም በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡ እንዲያውም ውሳኔው ይግባኝ ያልተጠየቀበት ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በእርግጥ ይህንን ቤት በተመለከተ ከግራ ቀኙ መካከል ማን ህጋዊ የተከራይነት መብት እንዳለው አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ሲደረግበት ቆይቷል፡፡ የመጀመሪያው የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበውም ይኸው የመብት ማረጋገጥ ክርክር መቋጫ ባላገኘበት ወቅት

በመሆኑ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በዚያ ደረጃ ውሳኔው የሚፈፀም አለመሆኑን ጠቅሶ የአፈፃፀም አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የተከራይነት መብቱን አስመልክቶ በግራ ቀኙ የቀረበው ክርክር በየደረጃው ባሉት ፍርድ ቤቶች ሲታይ ቆይቶ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/140055 ላይ መጋቢት 24/2010 ዓ.ም በተሰጠ ፍርድ መብቱ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ በውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ የአሁን ተጠሪ ድጋሚ የአፈፃፀም አቤቱታ ያቀረቡትም ይህንኑ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ እናም የቤቱ የተከራይነት መብት የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ በፍርድ በተረጋገጠበት እና ከዚሁ ቤት ጋር በተያያዘ አመልካች ውዝፍ ኪራይ ከፍለው ቤቱን ለአሁን ተጠሪ እንዲያስረክቡ የተሰጠ እና የፀና ውሳኔ ባለበት የአፈፃፀም ጥያቄው ድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ በእርግጥም በፍርድ የተረጋጠ መብትን ዋጋ ያሳጣ መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተረጓጎም ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ተገንዝቦ በየደረጃው ያሉትን ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ማለቱ የጉዳዩን ባህሪ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁር 392 ድንጋጌን መንፈስ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት ነጥብ የለውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/30140 ላይ ሐምሌ 18/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.181367

ጥቅምት 25/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ ወ/ሮ ስንቅነሽ አስፋው- ወኪል ጥሩእናት ከልክሌ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡ 1. ፍቅርተ ይሂይስ } ቀርበዋል

2. ምህረት ይሂይስ

3. ትዕግስት ይሂይስ

4. አብስራ ይሂይስ } ሞግዚት መስዋዕት ይሂይስ ቀርበዋል

5. ሀብታሙ ይሂይስ

6. በላይ ይሂይስ

7. የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር ጽ/ቤት

8. የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ፍትሕ ጽ/ቤት } የቀረበ የለም

9. የጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የቀረበ መቃወሚያን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/235677 ላይ ሐምሌ 04/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት የሰጠውን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉት ተጠሪዎች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ከ7ኛ እስከ 9ኛ ባሉት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ውስጥ የቤት ቁጥር 789/3 የሆነውን የሻይ እና ምግብ መሸጫ ንግድ ቤት ለንግዱ ሥራ አስፈላጊ

የሆነውን ቅድም ሁኔታ አላሟላችሁም በሚል ከጥር 22/2005 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱ ውስጥ ካለው ንብረት ጋር ቤቱን ያሸገባቸው መሆኑን፤ የንግድ ስራው በመቋረጡ ምክንያት እሸጉን እንዲያነሱላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው እሸጉን አንስተው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው እና በቤቱ ውስጥ በነበሩት ንብረቶች ላይም ለደረሰው ጉዳት ተገቢውን ካሳ የመጠየቅ መብታቸው እንዲጠበቅላቸው ዳኝነት ይጠይቃሉ፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ የታዘዘ ቢሆንም ከ7ኛ እስከ 9ኛ ያሉ ተጠሪዎች የፅሁፍ መልስ ያልሰጡ እና ክስ በሚሰማበት እለትም ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ በዚሁ አግባብ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የከሳሽ ወገንን ምስክር ሰምቶ ታሽጓል ስለተባለው የንግድ ቤትም በአሁን 7ኛ ተጠሪ በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ አስተዳደር ክፍሉ ቤቱ ስለታሸገበት ምክንያት ምንም መረጃ ማግኘት አለመቻሉን እና በቤቱ ላይም እሽግ አለመኖሩን የገለፀ ቢሆንም ስለመታሸጉ በሰው ምስክር ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ተከሳሾቹ እሽጉን በማንሳት ቤቱን ለከሳሾች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት ውሳኔውን በመቃወም ይቀርባሉ፡፡ የመቃወም አቤቱታቸው መሰረትም ታሸገ ተብሎ ክስ የቀረበበት ቤት በውርስ የተላለፈላቸው እና በእጃቸው የሚገኝ መሆኑን፤ ቤቱም የንግድ ቤት ሳይሆን መኖሪያ ቤት ሲሆን በማናቸውም አካል ያልታሸገ እና በእጃቸው አድርገው እየኖሩበት ያሉ መሆኑን፤ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ባላወቁት መንገድ የአሁን ከ1ኛ እስከ 6ኛ ያሉት ተጠሪዎች አስተዳደር ክፍሉ ላይ ክስ አቅርበው ቤቱ የታሸገበት እሽግ ተነስቶ ቤቱን ለመረከብ ያስወሰኑት ውሳኔ መብታቸውን የሚነካ መሆኑን በመግለፅ በሌሉበት የተሰጠው ውሳኔ እንዲሰረዝ የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚህ መልኩ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ሰጥቶ ከ9ኛ ተጠሪ በስተቀር ሌሎቹ አለን ያሉትን ክርክር በፅሁፍ ማቅረባቸውን፤ መልስ ከሰጡት ተጠሪዎች ውስጥም 7ኛ እና 8ኛ ተጠሪዎች የፅሁፍ መልስ ብቻ ሰጥተው ከቀጠሮ በመቅረታቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ የተደረገ መሆኑን፤ በኋላም ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ሰምቶ ቀድሞ የተሰጠውም ውሳኔ የሚያስለውጥ ምክንያት አላገኘሁም በሚል የአመልካች አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 17/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ አድማስ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ የመሆኑ ጉዳይ በቅድሚያ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችለው ቀድሞ በተደረገው ክርክር የሙግቱ አካል ሊሆን ይችል የነበረ ሆኖ እርሱ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር በተሰጠው ውሳኔ መብቱ የሚነካ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡ አንድ ሰው ወይም አካል በፍርድ ቤት በተያዘ ክርክር የክርክሩ አካል ሊሆን የሚችለው በፍርድ ቤት በሚሰጥ ትዕዛዝ፣ በራሱ በጣልቃ ገብ አቤቱታ አቅራቢነት አልያም በተከሳሽ ወገን ጥያቄ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40፣ 41 እና 43 ድንጋጌዎች ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ በሂደት ላይ ባለ ሙግት መግቢያ መንገዶች ውስጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ጥር 358 መሰረት በፍርድ ተቃዋሚነት ሊቀርብ የሚችለው በዋናነት ቀድሞ በተደረገው ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 በተመለከተው መሰረት በጣልቃ ገብነት ቀርቦ መብቱን እና ጥቅሙን ማስከበር ይችል የነበረ ሶስተኛ ወገን ነው፡፡

በእርግጥ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 በሌሎች ተከራካሪ ወገኖች መካካል በመካሄድ ላይ ባለ በአንድ ክስ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ወገን የመብቱን ሁኔታ በመግለፅ የክርክሩ አካል መሆን የሚችል ስለመሆኑ ከመግለፁ ውጭ ለጣልቃ ገብነት የሚያበቁ ግልፅ እና ዝርዝር መመዘኛዎች አላስቀመጠም፡፡ ሆኖም የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2) ድንጋጌ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን የሚችለው ክርክር ከቀረበበት ጉዳይ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው ወገን እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

እናም ሶስተኛ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 41 መሰረት ወደ በሂደት ላይ ባለ ተካፋይ ለመሆን በመሰረታዊ ህግ የተረጋገጠ መብት ወይም ጥቅም ያለው እና በክርክር ላይ ያለው ጉዳይም በህግም ሆነ በፍሬ ነገር ረገድ ከዚሁ መብት እና ጥቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን፤ በጣልቃ ገብነት ቀርቦ ይህንን መብቱን ካላስከበረ በቀር ሌላ መብት እና ጥቅሙን የሚያስጠብቅበት ዘዴ ወይም እድል የሌለ መሆኑን እና በክርክሩ ውጤትም በቀጥታ የሚነካ አልያም የክርክሩ ውጤት በቀጥታ ሊፈፀምበት የሚችል አካል ሊሆን እንደሚገባ ከዚሁ ድንጋጌ መንፈስ እና በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች መቃወሚያ ባቀረቡበት ውሳኔ ላይ የቀረበው ክርክር ያላግባብ የታሸገው ቤት እሽጉ ሊነሳ ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ጥያቄ ደግሞ ታሽጓል የተባለው ቤት ባለቤት እኔ ነኝ የሚል ከባለቤትነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የቀደመውን ክርክር በተመለከተ በጭብጥነት ተይዞ እልባት ሊሰጥበት የሚችለው ነጥብ "እሽጉ ሊነሳ ይገባል? ወይስ አይገባም?" የሚል ሲሆን ከአመልካች ጥያቄ አኳያ ደግሞ በጭብጥነት ሊያዝ የሚችለው ከቤቱ ትክክለኛ ባለቤትነት ጋር የተያያዘ ይሆናል፡፡

እነዚህ ሁለት ዳኝነቶች ሊነሳ ከሚችለው የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር አኳያ የተለያዩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ ከተደረገው ክርክር ጋር በተያያዘ የእሽጉ መነሳት ወይም አለመነሳትን አስመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካች በንብረቱ ላይ የይገባኛል ጥያቄን ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይደለም፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች ጥያቄ እራሱን ችሎ ዳኝነት ተጠይቆበት መፍትሄ ማግኘት የሚችል በመሆኑ በቀደመው ክርክር በጣልቃ ገብነት ተካፋይ የሚሆኑበትም ሆነ ከፍርድ በኋላ በተቃዋሚነት ሊቀርቡ የሚችሉበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የአመልካች ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ሊስተናገድ የሚገባ አይደለም፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 ተቀብለው ማስተናገዳቸው የድንጋጌውን መንፈስ እና የተፈፃሚነት ወሰን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/235677 ላይ ሐምሌ 04/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/ 56417 ላይ ሚያዝያ 08/2011 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአመልካች ጥያቄ እራሱን ችሎ በተገቢ ሥነ ሥርዓት ዳኝነት ተጠይቆበት የሚስተናገድ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 358 መሰረት የሚስተናገድ አይደለም፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.172008

ጥቅምት 30/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ ፀሐይ ሐይሉ

2. ህፃን ስመኝ መምሬ ፈይሳ /አሳዳጊ ወ/ሮ ፀሐይ ሐይሉ/

ተጠሪ፡ -ወ/ሮ ሰማ ሰይድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/299397 ላይ በ03/04/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን አመልካቾች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ ሥረ ነገር አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች የእናታቸው የውርስ ሃብት ተጣርቶ ወራሽነታቸው እንዲረጋገጥላቸው ለበሌ ወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀርባሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁ/13772 ላይ ጉዳዩን በማየት ላይ እያለ የአሁን ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ቀርበው በውርስ ሀብትነት እንዲጣራ የተባለውን ቤት በ233 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ እንዳረፈ ከአመልካቾች ወላጅ እናት ላይ ግንቦት 19/2000 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የገዙ መሆኑን ገልፀው "ንብረቱ የውርስ ሃብት ሳይሆን የግል ንብረቴ በመሆኑ ሊጣራ አይገባም" በማለት ይቃወማሉ፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በውርስ ሀብትነት እንዲጣራ ተብሎ በአመልካቾች የተጠየቀው ቤት የአሁን ተጠሪ የገዙት መሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ሰኔ 23/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን አመልካቾች ተጠሪ የገዙት 122 ካሬ ሜትር ብቻ ሆኖ እያለ 233 ካሬ ሜትር እንደሆነ ተደርጎ የቀረበው ውል የሀሰት መሆኑን ገልፀው የቀደመው ውሳኔ በዳግም ዳኝነት እንዲታረምላቸው ለወረዳው ፍርድ ቤት ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡

በዚህ መልኩ ጥያቄው የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የካቲት 17/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካቾች አውራሽ በሽያጭ ያስተላለፉት 122 ካሬ ሜትር ብቻ ስለመሆኑ ማረጋገጡን ጠቅሶ በተቀረው የውርስ ሀብት ላይ ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ሚያዚያ 30/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት ደግሞ በሽያጭ ለአሁን ተጠሪ ከተላለፈው ውጪ ባለው ንብረት ላይ የአመልካቾችን ወራሽነት በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህንኑ መነሻ በማድረግ የአሁን ተጠሪ በ186 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ግምቱ 450,000(አራት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሆነ የውርስ ሀብት ያለአግባብ ይዘው በወር በብር 600(ስድስት መቶ) በማከራየት እየተገለገሉበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው ተጠሪ ንብረቱን ለቀው እንዲያስረክባቸው፤ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ ያለውን የኪራይ ዋጋ ብር 7,200(ሰባት ሺህ ሁለት መቶ) እንዲከፈሏቸው እና ቀሪውን የኪራይ ዋጋ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅላቸው ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዲስ ክስ አቅርበዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው፤ ጉዳዩም የውርስ ክርክር በመሆኑ ፍርድ ቤት ክርክሩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ቤቱን በግዥ ያገኘሁት በመሆኑ ልለቅ አይገባም የሚል የሥረ ነገር ክርክር በማቅረብ ሞግተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የመ/ቁ/70460 በሆነ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሚያዝያ 26/2008 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ “የአመልካቾች ጥያቄ የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው ሊባል አይችልም፤ የአመልካቾች ክስ የውርስ ጥያቄ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም፤ የዳግም ዳኝነት ይታይልኝ ጥያቄውም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል” በማለት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/244480 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ህዳር 15/2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ “አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በውርስ የተላለፈልን እና በፍርድ የተረጋገጠልን ንብረት ከህግ አግባብ ውጭ በተጠሪ ስለተያዘብን ይለቀቅልን የሚል በመሆኑ የውርስ ክርክር ሊባል አይገባም፤ የውርስ ክርክር ነው ቢባል እንኳን የንብረቱ ግምት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ውስጥ የሚወድቅ በመሆኑ የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም መባሉ ተገቢ አይደለም፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ካለ ሌላውን ጉዳይ መመልከቱ ተገቢ አይደለም” በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥረ ነገር ክርክሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን በነጥብ መልሶለታል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን የሥረ ነገር ክርክር ሰምቶ፤ ስለጉዳዩም ተገቢ ነው ካለው አካል ካጣራ በኋላ የካቲት 17/2009 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት ቤት በሽያጭ ለአሁን ተጠሪ የተላለፈ መሆኑን አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት አመልካቾች በቤቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም ሲል ክሱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2) መሰረት ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/258621 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ጥቅምት 08/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 መሰረት ክሱን ውድቅ ማድረግ ሲገባው አከራክሮ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን በመተቸት በውጤት ደረጃ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የአመልካቾችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት በበኩሉ በመግቢያው ላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር ላይ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር አያበቃም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች የካቲት 08/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀደም ሲል በክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/13772 ላይ የአሁን አመልካቾች በ2000 ዓ.ም ከገዛችው ውጭ ያለውን ንብረት እንዲወርሱ በሚል የተሰጠው ውሳኔ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ሳያገናዝቡ የወሰኑበት አግባብ ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተከናወነው ክርክር ይዘት እና አድማስ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ ውድቅ ያደረገው ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ ቀድሞ በፍርድ/ውሳኔ ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ዋና ዋና የድንጋጌው ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ቀድሞ የተሰጠ ፍርድ/ውሳኔ መኖር፣ ይኸው ውሳኔ በክርክሩ ዋናው ጭብጥ(On the merit of the case/ ላይ የተሰጠ መሆኑ፣ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን፣ ቀድሞ በፍርድ በተወሰነው ክርክር ስረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት መሆን፣ እንዲሁም በቀደመው ፍርድ/ውሳኔ ላይ የነበሩት እና አሁን በክርክር ላይ ያሉት የክርክር አካላት ተመሳሳይ ወይም ከእነርሱ መብት ያገኙ መሆን የሚሉት ናቸው፡፡ እናም አንድ

ጉዳይ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በድጋሚ የቀረበ ነው ለማለት እነዚህን መመዘኛዎች በአግባቡ የሚያሟላ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ቀደም ሲል በወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13772 ላይ ቀርቦ የካቲት 17/2007 እና ሚያዝያ 30/2007 ዓ.ም ውሳኔ ያገኘ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው በተጠቀሰው መዝገብ ላይ ቀርቦ በሁለቱ ቀናት ውሳኔ የተሰጠው አመልካቾች ባቀረቡት የዳግም ዳኝነት ጥያቄን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚሁ አግባብ የካቲት 17/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ተጠሪ ከአመልካቾች አውራሽ ላይ የገዙት 122 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈን ቤት ብቻ ነው በሚል ቀደሞ የተሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል በተቀረው ይዞታ ላይ ውርሱ ተጣርቶ እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚህ መልኩ ተጣርቶ የቀረበለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ ደግሞ የአሁን አመልካቾች ከ122 ካሬ ሜትር ውጭ ባለው ይዞታ እና ንብረት ላይ ወራሾች ናቸው በሚል ሚያዝያ 30/2007 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን የቀረበው የውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ደግሞ የዳግም ዳኝነት ውሳኔውን መሰረት በማድረግ ተጠሪ 186 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ያረፈ የውርስ ሃብት ያለአግባብ ይዘው የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ክሶች በይዘት ደረጃ ሲታዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ላይ የነበረው ክርክር ወራሽነትን ከማረጋገጥ ጋር የተያያዘ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ የቀረበው ክስ ደግሞ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የወራሽነት ማስረጃ መሰረት ተደርጎ ያለአግባብ የተያዘ የውርስ ሃብት ለማስለቀቅ የቀረበ ክስ ነው፡፡ እናም ቀድሞ ውሳኔ አግኝቷል በተባለው ጉዳይ እና አመልካቾች ኋላ ላይ ባቀረቡት ክስ መካከል ፍፁም የሆነ የስረ ነገር እና የክርክር ጭብጥ ልዩነት ያለ በመሆኑ ክሱ በድጋሚ ቀርቧል የሚባል አይደለም፡፡

ያም ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/244480 ላይ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ በነጥብ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲመልስ ቀድሞ ውሳኔ አግኝቷል የተባለው ጉዳይ እና አመልካቾች ኋላ ላይ ያቀረቡት ክስ የተለያየ ስለመሆኑ አቋም ይዞ በሥረ ነገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ እያለ ፍርድ ቤቱ መልሶ እራሱ ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በሚሽር አኳኋን የተለየ አቋም መያዙ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህንን ማረም ሲገባው ማለፉ በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/299397 ላይ ታህሳስ 03/2011 የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/256821 ላይ ጥቅምት 08/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን የመ/ቁ/256821 በማንቀሳቀስ በቀረበለት ይግባኝ የሥረ ነገር ክርክር ላይ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መዝገቡ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.183339

የካቲት 26/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡ 1. አቶ ሀጎስ ገ/ሂይወት

2. አቶ ገ/ሄር ወልደጊወርጊስ

3. አቶ ኃይሉ በላይ

ተጠሪዎች፡- 1. መ/ር ሀጎስ በርሀ

2. ወ/ሮ አብርሃት ወሊሄት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአድዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች በተጠሪዎች እና በሌሎች ሶስት ሰዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ጭብጥም ፣ አዋሳኙ እና መጠኑ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን ቤት እና ይዞታ የአውራሻቸው ሟች ወ/ሮ ብዙ ገብረሂዎት መሆኑን፣ ሟች ወደታች የሚቆጠር ተወላጅ የሌላቸው በመሆኑ የምትክ ወራሽነታቸውን በፍርድ ቤት አረጋግጠው የሟች የውርስ ሃብት መጣራት ሲጀመር ተጠሪዎች ንብረቱ የእኛ ነው በማለት የተቃወሙ መሆኑን በመግለፅ ንብረቱ የውርስ ሀብት መሆኑ ተረጋግጦ በፍርድ ኃይል እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ ተከሳሾች መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም ክስ የቀረበበት ጉዳይ ቀደም ሲል የአሁን አመልካቾች አውራሽ ተጠሪዎች በቤቱ የኖሩበትን ኪራይ ከፍለው እንዲለቁ በሚል በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዉባቸው አቤቱታቸው በመ/ቁ/83/95 ላይ ውድቅ የተደረገ በመሆኑ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም፣ ቦታ እና ቤቱንም ከ25 ዓመት በላይ ይዘን ስንጠቀምበት የቆየን በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል

ነው፡፡ አማራጭ የስረ ነገር ክርክሩ ይዘት ደግሞ ክርክር የተነሳበትን ቤት እና ይዞታ ከሟች በስጦታ የተላለፈልን በመሆኑ ልንለቅ አይገባም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው የተባለውን ክርክር አስመልክቶ ቀድሞ ውሳኔ አግኝቷል በተባለበት መዝገብ ላይ የቀረበው ክርክር የቤት ኪራይ ክርክር ስለመሆኑ መዝገቡን አስቀርቦ በመመርመር ማረጋገጡን ጠቅሶ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይም ተጠሪዎች ክስ የቀረበበት ቤት እና ይዞታ በስጦታ የተላለፈላቸው ለመሆኑ አግባብነት ያለው አስረጂ አልቀረበም በማለት ለቀው ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ በአሁን አመልካቾች አውራሽ እና በተጠሪዎች መካከል በመ/ቁ/83/95 ላይ በተደረገው ክርክር በአመልካቾች አውራሽ የተጠየቀው ዳኝነት የአሁን ተጠሪዎች በቤቱ የኖሩበትን ኪራይ ከፍለው ቤቱን ሊለቁልኝ ይገባል የሚል መሆኑን፣ ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል ግንኙነት ስለመኖሩ ያልተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች የተጠየቀውን የኪራይ ዋጋ ሊከፍሉ አይገባም በሚል ወስኖ የቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን በዝምታ ያለፈ መሆኑን፣ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ያላረፈበት ጉዳይ እንደተነፈገ የሚቆጠር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 5(3)የሚደነግግ መሆኑን፣ አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ላይ በአመልካቾች አውራሽ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥበት የታለፈ በመሆኑ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይችልም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመለወጥ የአመልካቾችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካቾች በዚሁ ውሳኔ ላይ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጳጉሜ 04/2011 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው ፍሬ ቃልም ቀደም ሲል በመ/ቁ/83/95 ላይ የነበረው ክርክር የቤት ኪራይ ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን አሁን ክስ የቀረበው ደግሞ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባ የሟች ንብረት ይለቀቅልን የሚል በመሆኑ ሁለቱ ጉዳዮች የተለያዩ ሆነው እያለ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል አቤቱታችን ውድቅ መደረጉ ከህግ አግባብ ውጭ በመሆኑ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ውድቅ ተደርጎ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ የተደረገበት የህግ አግባብ ቀደም ሲል በአድዋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/83/95 ላይ ቀርቦ

ከነበረው እና ውሳኔ ከተሰጠበት ክርክር ይዘት አኳያ በዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካቾች የክስ አቤቱታ ውድቅ የተደረገው ክስ የቀረበበት ንብረት በተመለከተ በመ/ቁ/83/95 ላይ ክርክር ሲደረግ አሁን ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በአመልካቾች አውራሽ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሳኔ ሳይሰጥበት በዝምታ የታለፈ በመሆኑ ክሱ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በእርግጥ ቀድሞ በፍርድ/ውሳኔ ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ የሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 ይከለክላል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ዋና ዋና የድንጋጌው ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ቀድሞ የተሰጠ ፍርድ/ውሳኔ መኖር፣ ይኸው ውሳኔ በክርክሩ ዋናው ጭብጥ(On the merit of the case/ ላይ የተሰጠ መሆኑ፣ ውሳኔውን የሰጠው ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን፣ ቀድሞ በፍርድ በተወሰነው ክርክር ላይ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩት ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስ ላይም ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው የቀረቡ መሆን፣ እንዲሁም በቀደመው ፍርድ/ውሳኔ ላይ የነበሩት እና አሁን በክርክር ላይ ያሉት የክርክር አካላት ተመሳሳይ ወይም ከእነርሱ መብት ያገኙ መሆን የሚሉት ናቸው፡፡

በዚህ ድንጋጌ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ውስጥ "ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ" የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው በቀደመው ክርክር ላይ ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሳኔ ያረፈበትን የክርክር ነጥብ ነው፡፡ በሌላ በኩል በቀደመው ክርክርና ሙግት ላይ በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ ከታለፈ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ የሚቆጠር በመሆኑ በዚያው ጉዳይ ላይ ድጋሚ ክስ ማቅረብ እንደማይቻል የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 3 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ በእርግጥ በዚህ ንዑስ ድንጋጌ ውስጥ "በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ከታለፈ" የሚለው አገላለፅ በተጠየቀው ዳኝነት ላይ ግልፅ ክልከላ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ሆኖም የድንጋጌው ይዘት ከስነ ስርዓት ህጉ የእንግሊዘኛ ትርጎም ጋር ተዳምሮ ሲታይ የንዑስ ድንጋጌው አንኳር መልዕክት በግልፅ የተጠየቀውን ዳኝነት በዝምታ ማለፍን የሚመለከት ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 ስር የተመለከተው በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ዳግም ክስ ክልከላ ተፈፃሚነት በተከራካሪ ወገኖች በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ፍርድ ቤት በዝምታ ባለፈው ጉዳይ ላይ ጭምር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም በግልፅ ዳኝነት በተጠየቀበት

ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቱ በዝምታ የከለከለው መሆኑን ያለመሆኑ ጉዳይ ዳኝነት የተጠየቀበትን ጉዳይ አስመልክቶ ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ከቀረበው ክርክር እና ጥያቄ ጋር ተገናዝቦ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ፍርድ ቤት በዝምታ ያለፈውን የዳኝነት ጥያቄ ተከሳሹ ወገን በግልፅ ክዶ የተከራከረበት ሊሆን ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካቾች አሁን ክስ ያቀረቡበትን ንብረት አስመልክቶ አውራሻቸው ቀደም ሲል ተጠሪዎች በቤቱ ውስጥ የኖሩበትን የ18 ወራት ውዝፍ የቤት ኪራይ ከፍለው ቤቱን ያስረክቡኝ በሚል ክስ አቅርበው የነበረ መሆኑን፣ ተጠሪዎች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ተከራይተው ሳይሆን ያለኪራይ እንዲኖሩበት የተሰጣቸው መሆኑን ገልፀው ኪራይ ልንጠየቅ አይገባም በማለት የተከራከሩ መሆኑን፣ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም "በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል ግንኙነት አለ? ወይስ የለም?" የሚል ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪዎች ያለኪራይ በቤቱ ውስጥ እንዲኖሩ በአመልካቾች አውራሽ ተፈቅዶላቸው ሲኖሩ የነበረ ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በሚል መነሻነት ተጠሪዎች የተጠየቀውን ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም የሚል ውሳኔ ሰጥቶ ቤቱን ለመረከብ የቀረበው ጥያቄ በዝምታ ያለፈ መሆኑን አጣሪው ችሎት አስቀርቦ ከመዝገብ ካያያዘው ሰነድ እና የስር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመ/ቁ/83/95 ላይ በቀረበው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች የቤት ኪራይ ልንጠየቅ አይገባም በሚል ከመከራከራቸው በስተቀር ቤቱን በተመለከተ ያቀረቡት የይገባኛል ክርክር የለም፡፡ ይህም ማለት የአመልካቾች አውራሽ ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ ተጠሪዎች በግልፅ ክደው ያቀረቡት ክርክር አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የተጠየቀው ዳኝነት በሌላኛው ወገን በግልፅ ባልተካደበት ሁኔታ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄን በዝምታ ማለፉ ዳኝነቱ እንደተከለከለ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በጉዳዩ ላይ አዲስ ክስ እንዳይቀርብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 የሚከለክል ባለመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ነው የሚያስብል አይደለም፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾች ጥያቄ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ድጋሚ የቀረበ ነው በሚል ውድቅ ማድረጉ እና ሰበር ችሎቱም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 5 ድንጋጌን መሰረታዊ አላማ እና የተፈፃሚነት ወሰን ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በ/መ/ቁ/116353 ላይ ሰኔ 11/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/112927 ላይ መጋቢት 27/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካቾች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ ቀደም ብሎ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በክሱ ሥረ ነገር ላይ የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 341(1) መሰረት ጉዳዩ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ.184388

መጋቢት 29/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ በዳዳ ኤጀርሳ

ተጠሪ፡ አቶ ቦከና ጉርሙ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ይቅረብልኝ አቤቱታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/318798 ላይ መስከረም 27/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበለትን "ጊዜው ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ላቅርብ" የማስፈቀጃ ጥያቄን አስመልክቶ በቂ ምክንያት አልቀረበበትም በማለት ውድቅ ያደረገበት ትዕዛዝ "መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው" በማለት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የማስፈቀጃ ጥያቄውን ያቀረቡት ቀደም ሲል ስራ ላይ በነበረው ህግ መሰረት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ሶስት ወር ሲሆን ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2011 መሰረት ጊዜው ወደ ሁለት ወር ዝቅ ስለመደረጉ አላውቅም ነበር የሚል ነው፡፡ ችሎቱም ምክንያቱ በቂ አይደለም ሲል ውድቅ አድርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 05/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎ ተፈፅሟል ያሉትም መሰረታዊ የህግ ስህተተ ጠቅሰው በዚሁ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በገጠር የምኖር አርሶ አደር በመሆኔ እና የክልል ህግጋት እንኳንስ በገጠር በከተማም ተደራሽ ባለመሆናቸው አዲሱ ህግ ስለመውጣቱ

አላውቅም፤ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜም ያለፈው በዚሁ ምክንያት ስለመሆኑ ገልጩ እያለ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል ምክንያት የማስፈቀጃ አቤቱታዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ትዕዛዙ ተሽሮ የሰበር አቤቱታዬ ቀርቦ እንዲታይ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተምርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት በተሻሻለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀፅ 27(2) መሰረት የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 60(ስድሳ) ቀናት ውስጥ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርቡ አቤቱታዎች ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ ከመደንገጉ ውጭ ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ቀርቦ ሊታይ ስለሚቻልበት ሁኔታ አዋጁ የደነገገው ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል እስከ አሁን ድርስ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ወጥቶ ተግባራዊ የተደረገ ልዩ የሰበር ሰሚ ችሎት የሥነ ሥርዓት ህግ ባለመኖሩ እየተሰራበት ያለው በመደበኛው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ነው፡፡

እስከ አሁን ስራ ላይ ባለው የ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ መሰረት ጊዜ ያለፈበት ይግባኝ/የሰበር አቤቱታ/ ቀርቦ እንዲታይለት አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ከአቤቱታው ጋር ጊዜው ሊያልፈ የቻለበትን ምክንያት የሚገልፁ ማስረጃዎችን ማቅረብ ያለበት መሆኑን እና ማስረጃዎቹም ይግባኙ/የሰበር አቤቱታው/ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልቀረበበትን ምክንያት የሚገልፁ እና ውሳኔም እንዲሰጥበት በቂ ሆነው መገኘት ያለባቸው ለመሆኑ በቁጥር 325(2) ደንግጓል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈባቸው አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜውን ያሻሻለው ህግ መውጣቱን ባለማወቃቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንግዲህ አንድ ህግ ተፈፃሚ የሚሆነው በሀገሪቱ ባለው የህግ ማውጫ/ማሳወቂያ ስርዓት መሰረት ከወጣበት ወይም በልዩ ሁኔታ ተፈፃሚ እንዲሆን ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እንጂ እያንዳንዱ ዜጋ ህጉ ስለመውጣቱ ካወቀበት ጊዜ አይደለም፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ምክንያታዊ ዜጋ በሀገሩ ውስጥ የሚወጡ ህጎችን ያውቃል ተብሎ ግምት የሚወሰድ በመሆኑ ህግን ያለማወቅ ይቅርታ የሚያሰጥ አይደለም፡፡ እናም ህግ መውጣቱን አላውቅም ነበር የሚለው ጉዳይ መከራከሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም ብሎ ውድቅ በማድረጉ የፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/318798 ላይ መስከረም 27/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን አመልካችን "ጊዜ ያለፈበት የሰበር አቤቱታ ላቅርብ" ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ/መ/ቁ.184509

መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ዘውድነህ አባተ መኮንን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ከበቡሽ ጋሻው ተገኝ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የሁከት ይወገድ ክርክርን የተመለከተ ሲሆን አመልካች በስር ፍ/ቤት ከሳሽ እና ተከሳሽ በሚያደርጉት ክርክር ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር ይፈቀድልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታም የስር ከሳሽ እና ተከሳሽ የሚከራከሩበት በቦሌ ክ/ከ/ወ/10 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነው ቤት አመልካች ጳጉሜ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁ/ቅ8/283/2ለ/2008 በ01/13/08 ዓ.ም የስር ተከሳሽ ቤቱን እና ቤቱን የተመለከቱ ሰነዶችን ሸጦልኝ እና አስረክቦኝ በቤቱ በመጠቀም ላይ ስለምገኝ ክርክር ለተነሰበት ቤት ባለቤት እና ባለመብት ስለሆንኩ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 41(2) መሰረት ጣልቃ ገብቼ መከራከር ይገባኛል በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ ጣልቃ ገብ ያያያዙት ማስረጃ ውል ከስር ተከሳሽ ጋር ውል እንደተዋዋሉ ያስረዳል እንጂ የይዞታ ማረጋገጫውና የግንባታ ፍቃዱ አሁንም በስር ተከሳሽ በአቶ ደረጀ ደፋሩ ስም መሆኑን ከቀረበው ማስረጃ መረዳት ይቻላል ክርክሩም አቶ ደረጀ ደፋሩ የተጠሪን አጥር

በማፍረስ እና በግቢዬ ላይ መንገድ በማውጣት የፈጠረውን ሁከት እንዲወገድልኝ በማለት አቤቱታ አቀረብኩ እንጂ የአመልካችን መብት አልነካሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ባቀረቡት የጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የተጠሪን አስተያየት በመቀበል በሰጠው ብይን ተጠሪ እና የስር ተከሳሽ የሚከራከሩበት ቤት አመልካች ከስር ተከሳሽ የገዛሁት ቤት ነው በማለት የባለቤትነትን አቤቱታ ማቅረባቸውን፤ ተጠሪ በስር ተከሳሽ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ እያለ እና ሁከቱም ተፈጠረብኝ ያለው በተጠሪ መኖሪያ ቤት ላይ ሆኖ እያለ አመልካች ደግሞ በስር ተከሳሽ የመኖሪያ ቤት ክርክር የባለቤትነት ክርክር እንዲያደርጉ ጣልቃ እንዲገቡ መጠያቃቸው አግባብነት የሌለው እና ተጠሪ ከቀረበው ክስ ጋር ተመሳሳይነት የሌለው እና የአመልካችንም መብትና ጥቅም የሚነካ ስላልሆነ አመልካች በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ የሚከራከርበት የህግ አግባብ የለም በማለት አቤቱታው በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካች ከስር ተከሳሽ ላይ የካርታ ቁጥር 10/55/4/12/36823/00 የሆነ ቤት ገዛሁ ቢሉም ክርክር ባስነሰው ይዞታ /መንገድ/ ላይ ያላቸውን መብትና ጥቅም አላስረዱም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሳሽ እና ተጠሪዋ አጎራባች መሆናቸውን፣ ተከሳሽ ሁከት ፈጠሩበት የተባለውን ቤት ለአመልካች ሸጠውልኝ የተከሳሽ መብትና ግዴታ ሁሉ ጳጉሜ 1 ቀን 2008 ዓም ቤቱን ገዝቼ ወደኔ እንዲዛወር ማድረጌ፤ የስር ተከሳሽም ሆነ አመልካች በሌለንበት ክርክሩ ተሰምቶ ውሳኔ ቢሰጥ በተለይ በአመልካች ላይ ሊመለስ የማይችል ጉዳት ሊደርስብኝ ስለሚችል ወደ ክርክሩ ጣልቃ በመግባት ተጠሪዋ በቤቱ ባለቤት በነበሩት አቶ ደረጀ ደፋሩ ላይ የመሰረቱት የሁከት ይወገድልኝ ክስ የተሳሳተና በአንፃሩ ሁከት ፈጥረው በመካከለችን 8 ሜትር መንገድ ዘግተው መውጫ መግቢያ ያሰጡኝና ሕገ ወጥ ግንባታ ያደረጉት ሁከትም የፈጠሩት ተጠሪዋ ራሳቸው መሆናቸውን አስረድቼ ክሱ እንዳላዘጋ ወደ ክርክሩ አትገቢም መባሌ አግባብ አይደለም፤

አመልካች ሁከት ተፈጠረብኝ የሚሉትን መንገድ ዘግተው ከተፈቀደላቸው ይዞታ አልፈው የፈጸሙት ግንባታ ሕገ ወጥ በመሆኑ ግንባታውን እንዲያቆሙ መስተዳድሩ በስልጣኑ መሰረት ሕጋዊ ትዕዛዝ መስጠቱ ሁከት እንደማያሰኘው ማስረዳት እንድችል ጣልቃ ሳያስገባኝ በክርክሩ መብትና ጥቅም የለውም በማለት የሰጠው ፍርድ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 37742 እና 77322 ክርክር ከተነሳበት ንብረት ጋር ግንኙነትና መብት ያለው አመልካች በማስረጃ የተደገፈ ጥያቄ ካቀረበ ወደ ክርክሩ ገብቶ ሙግቱን እንዲያቀርብ መፍቀድ ይገባዋል እንጂ ፍ/ቤቶች ሌላ ምክንያት በመስጠት ክርክሩን እንዳያቀርብ ሊያግዱ አይገባም በማለት የሰጠው

አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር ተከሳሽ የነበሩት ግለሰብ የነበራቸውን ቤት እና ይዞታ ለአሁን አመልካች በሽያጭ አስተላልፈዋል በተባለበት እና የስር ተከሳሽ በአሁኗ ተጠሪ ይዞታ ላይ ሁከት ፈጥረዋል የተባለው ከዚሁ ለአመልካቹ ካስተላለፉት ይዞታ ጋር በተያያዘ ሁኔታ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ እንዲሁም በክርክሩ መጨረሻ የሚሰጠው ውሳኔ የአመልካቹን መብትና ጥቅም ሊነካ እንደሚችል ግምት መውሰድ በሚቻልበት ሁኔታ አመልካች በጣልቃ ገብነት ገብተው ለመከራከር ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉ አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ከገዙት ቤት ካርታ ላይ ያልተመለከተ እና ተያያዥነት የሌለው ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ፕላን የሌለውና ገና ለወደፊት ምን አልባት አስፈቅዳለሁ ብለው የገመቱትን ቤት መንገድ እንጂ በአሁኑ ደረጃም ሆነ ከመግዛታቸውም በፊት ከገዙም በኋላ መንገድ ነው ተብሎ የተሰጠው ፕላን እውቅና የለውም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ያቀረቡበት ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሁከት ይወገድልኝ በማለት ካቀረብኩበት አቤቱታ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የሌለበት እና የአመልካችን መብትና ጥቅምን የማይነካ በመሆኑ መብትና ጥቅም ስለሌለው በክርክሩ ጣልቃ መግባት የለብህም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ አግባብ ያለውና የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ ከተገቢው ህግና፤ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በመሰረቱ ከክርክር አመራር መርህ አንፃር የክርክሩን አድማስ ቅጥ የለሽ የሚያደርጉትን እና መዘግየትን የሚያስከትሉ አዳዲስ ጭብጦችን በማስቀረት ለጉዳዩ መጨረሻ እንዲኖረው ማድረግ የአንድ ፍርድ ቤት መሰረታዊ ግዴታው ነው፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ያቀረበው ወገን በተጀመረው ክርክር መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑ መረጋገጡ ግዴታ ቢሆንም ጣልቃ ገብ እንዲሆን የተፈቀደለት ወገን ፍፁም የተለየና ቀደም ሲል ከተጀመረው ክርክር የማይጣጣም አዲስ ጭብጥና ጥያቄ ይዞ እንዲቀርብ ግን ሊፈቀድለት አይገባም፡፡የግሉን የዳኝነት ጥያቄ ይዞ የሚቀርብ አቤቱታ አቅራቢ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.41 መሰረት ጣልቃ ገብ ሆኖ እንዲከራከር ሊፈቀድለት የሚችልበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

የጣልቃ ገብነትን አቤቱታ ለመቀበል በሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች መካከል በተጀመረው ሙግትና በኋላም በሚሰጠው ውሳኔ አፈፃፀም ጣልቃ ገብ ሆኖ መከራከር የሚፈልገው ጥቅሙ ይነካል?ወይስ አይነካም ?የሚለው መሰረታዊ መስፈርት በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በክርክሩና ክርክሩን ተከትሎ በተሰጠው ውሳኔ አፈፃፀም ወቅት መብቱ የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ እደተመለከተው ተጠሪ በስር ተከሳሽ ላይ በስር ፍርድ ቤት ክሱን ያቀረቡት በጊቢዬ ውስጥ የማከናውነውን ግንባታ ግቢዬ ውስጥ በመግባት እንዳልገባና እንዳልጠቀም አድርጎኛል በዚህም የሁከት ተገባር ፈፅሟል በማለት የስር ተከሳሽ የግል የሆነው የሁከት ተግባር እንዲወገድላቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱ የቀረበው ክስ በተገቢው ማስረጃ ቢረጋገጥ እንኳ ለጉዳዩ የሚሰጠው የስር ተከሳሽ ፈፀሙት የተባለውን ድርጊት ብቻ መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ መሰረት ያደረገው ክርክር መብትና ጥቅሜን የሚነካ ነው በማለት ጣልቃ ለመግባት መጠየቃቸው የሚያሳምን ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ የስር ተከሳሽ ፈፀመ ያሉትን የሁከት ተግባር መሰረት ያደረገ በመሆኑ አመልካች ደግሞ ወደ ክርክር ጣልቃ ለመግባት መነሻ ያደረጉት በግዢ አገኘሁ የሚሉትን ቤትና ይዞታ አስመልክቶ የመፋለም ክስን መሰረት በማድረግ ውሳኔው በቤቱ ላይ ያለኝን መብት ያጣብባል በማለት በመሆኑ አመልካች በቤትና በቦታው ላይ አለኝ የሚሉት መብት የስር ተከሳሽን የግል ተግባር መሰረት አድርጎ የቀረበን ክስ መርምሮ ለሁከት ይወገድልኝ ክስ ተገቢውን እልባት በሚሰጠው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጣበብ የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንኑ መሰረት በማድረግ የአመልካችን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፤ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካች የጣልቃ ገብነት አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩ እልባት ባላገኘበት ወደ ፍሬ ጉዳዩ ክርክር በመግባት የስር ተከሳሽ የሌላቸውን መብት ለአመልካች ሊያተላለፉ አይችሉም በማለት የስር ተከሳሽን የግል ተግባር መነሻ በማድረግ በቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ላይ አመልካች ክርክር ባስነሳው ይዞታ ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም በማለት መወሰኑ አግባብ ባይሆንም ከውጤት አንፃር የስር ፍርድ ቤትን ብይን ማፅናቱ  አግባብ በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1.የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 84139 በቀን 16/07/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 231614 በቀን 03/02/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከውጤት አንፃር በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡

2.በዚህ መዝገብ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 332 መሰረት በቀን 14/2/2012 ዓ.ም የተሰጠው ዕግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 196172

የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት

ተጠሪ፡- የድሬ ዳዋ ከተማ ስራ አስኪያጅ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረው እግድ እንዲነሳ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰጠቱና ይህ ትዕዛዝ በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መፅናቱ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመን መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሳይ በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም ይገባል በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ መሰረት በማድረግ ሲሆን አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስም ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 2362 የሆነውን ቤት አከራይተን ተከራዩ በቤቱ ላይ እድሳት በማድረግ ላይ እያለ ተጠሪ በቤቱ ላይ አንዳችም መብት ሳይኖረው ተከራዩ በቤቱ ላይ እድሳት እንዳያደርግና እንዳይገለገል በማድረግ ሁከት የፈጠረ በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ይህንን ተከትሎም ተጠሪ ቤቱን ለቃችሁ እንድታስረክቡ በማለት አስገድዶኛል በማለት አመልካች የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጠይቆ በ29/11/2012 ዓም ፍርድ ቤቱ የእግድ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በማስከተልም ተጠሪ ጳጉሜ 03 ቀን 2012 ዓም በተፃፈ አቤቱታ ክርክር የተነሳበት ቤት ለጅቡቲ ፕሬዝዳንት መኖሪያ ቤት ለማስፋፊያነት እንዲጠቀምበት የተሰጠ መሆኑን በመግለፅ እግዱ እንዲነሳለት ያመለከተ ሲሆን አመልካች መስከረም 04 ቀን 2013 ዓም በተሰጠ ምላሽ

የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ የድርጅቱን ንብረት አስመልክቶ ውሳኔ ማሳረፍ የማይችል መሆኑን፤የከተማ አስተዳደር ከሌላ ሀገር ጋር የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ በቀጥታ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለማድረግ የማይችል መሆኑን በመጥቀስ ቢከራከርም ፍርድ ቤቱ መስከረም 04 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ የከተማውን ይዞታ በአግባቡ የማልማትና የማስተዳደር ስልጣኑ የአስተዳደሩ መሆኑን ፤ ለንብረቱ ተገቢው ካሳ የተወሰነ በመሆኑ ካሳው በቂ ካልሆነ በመጠኑ ላይ ቅሬታ ከማቅረብ ባለፈ ይዞታውን አላስረክብም ለማለት ስለማይችል እግዱ ሊነሳ ይገባል በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.154 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ጉድለት የለበትም በማለት አቤቱታውን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት መስከረም 20 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ባቀረበው የሰበር አቤቱታም አመልካች ድርጅት የተቋቋመው በሁለቱ ሀገሮች ስምምነት ሆኖ የድርጅቱን ንብረትና ይዞታ ለመጠበቅ በ1973 ዓም እና 1989 ዓም ግዴታ ገብተው ግዴታው ሊጠናቀቅ 14 አመት የሚቀረው ሆኖ እያለ ይህ ስምምነት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9(4) መሰረት የሀገሪቱ የህግ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ሆኖ እያለ ተጠሪ በቤቱ ላይ ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት ሳይኖረው እግድ በማንሳት በንብረቱ ላይ ጉዳት እንዲያደርስ በመፈቀድ ለካቢኔ ውሳኔ ከአለም አቀፍ ስምምነት እና ከህገ መንግስቱ ቅድሚያ በመስጠት የተሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

የከተማ አስተዳደሩ በአለም አቀፍ ግንኙነት ላይ በቀጥታ ተሳታፊ ለመሆን ስምምነቶችንም ለማድረግ የሚያስችል ህገ መንግስታዊ ስልጣን የሌለው ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ተጠሪ የፈፀመው ቤቱን ለጅቡቲ ፕሬዝዳንት ማስፋፊያነት በማለት በማፍረስ መስጠት ለህዝብ ጥቅም ሊባል የማይችል አዋጅ ቁጥር 455/1997ን የሚጣረስ ሆኖ እያለ የእግዱም መነሳት የክርክሩን መቋጨት የሚያስከትል ሆኖ እያለ እግዱ እንዲነሳ መታዘዙ መሰረታዊ የህግ ስህተት በስር ፍርድ ቤቶች መፈፀሙን ስለሚሳይ መዝገቡ ገና በቀጠሮ ላይ እያለ የመጨረሻ ውሳኔ አይነት ትእዛዝ መሰጠቱ አግባብ ስላልሆነ ትእዛዙ ተሽሮ ሁከት እንዲወገድ ትዕዛዝ ይሰጥልን፤ተጠሪ የድርጅቱን ንብረት በመስበር እየፈፀመ ያለው ተግባር ህገ ወጥ ስለሆነ በግቢው ውስጥ ያሰማራቸውን ግለሰቦች እንዲያወጣ ለቀበሌ 03 አስተዳደር ፅ/ቤትና ለከዚራ ፖሊስ ጣቢያ ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት አመልክቷል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ አላስረክብም ማለት አትችልም በማለት እግዱ እንዲነሳ ትዕዛዝ የተሰጠበትን አግባብ ለማጣራት

የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በዚህ መልሱም ክልሎች በክልላቸው የሚገኝን በማንኛውም አካል የተያዘን ይዞታ ፌደራል መንግስት በሚያወጣው ህግ መሰረት ሀገራዊ ፋይዳ ላላቸው ጉዳዮች፤ለኤምባሲዎች፤ለህዝብ ጥቅም ወይም ለተሻለ ልማት ወይም መንግስት ለሚያካሂደው የልማት ስራ አስፈላጊ ሆኖ ካመነበት ይዞታውን በማስለቀቅ ለታሰበው አላማ የማዋል ስልጣን እና ሃላፊነት የተሰጣቸው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 52(2)(መ) እና በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀፅ 12 እና 26(3) እንዲሁም በካሳ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀፅ 5 የተመለከተ ሲሆን 1973 እና 1989 በተደረገው ስምምነት አንቀፅ 3 ሁለቱ መንግስታት በየግዛታቸው በሚገኙ የምድር ባቡር ድርጅት መኖሪያ ቤቶች ሀዲዶችና ጣቢያዎች ወዘተ መጠቀም እንደሚችሉ የሚደነግግ በመሆኑ የአዲስ አበባ መስተዳደርም በዚሁ አግባብ የድርጅቱን ንብረቶች ለልማት እያዋለው በመሆኑ አመልካች የካሳ ግምቱ በቂ አይደለም የሚሉ ከሆነ ለተገቢው አካል ከማመልከት ውጪ ካቢኔው የወሰነውን ይዞታ አላስረክብም ለማለት አይችሉም፤ተጠሪ ይዞታን ለማስለቀቅ የሚችለው ለህዝብ ጥቅም ብቻ ነው በማለት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሊዝ አዋጁን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ለይዞታው ካሳ እንዲከፈል የተወሰነ በመሆኑ፤የእግዱ መነሳት የክርክሩን መቋጨት የሚያስከትል ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካች የመልስ መልሱን በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ ከተገቢው ህግና፤ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡አመልካች በተጠሪ ላይ ክሱን ያቀረበው ክርክር የተነሳበትን ቤት አከራይቶ የመጠቀም መብቱን በመተላለፍ ቤቱን የተከራየው ሰው ቤቱን እንዳያድስና እንዳይገለገል በአካልና ደብዳቤ በመፃፍ ሁከት የፈጠረ መሆኑን በመግለፅ ሁከቱ እንዲወገድ በመጠየቅ ሲሆን በዚህ አግባብ ክርክሩ እየተመራ ባለበት ተጠሪ በ28/11/2012 ዓም በተፃፈ ደብዳቤ ቤቱን በ7 ቀናት ውስጥ ለቀው እንዲያስረክቡ መጠየቁን መነሻ በማድረግ እግድ እንዲሰጥለት ጠይቆ በዚሁ አግባብም የእግድ ትዕዛዝ መሰጠቱን የግራ ቀኙ የስር ፍርድ ቤት ክርክር ያሳያል፡፡

በመሰረቱ ይህ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.154(ሀ) አግባብ በመሆኑ የእግድ ትዕዛዙ መነሻ ተጠሪ ንብረቱን ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ እያደረገ ያለው ጥረት እግድ ትዕዛዝ ሳይሰጥበት እንዲቀጥል ቢደረግ በዋናው ጉዳይ የተያዘው የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ዋጋ የሚያጣ መሆኑን መነሻ በማድረግ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክርና ፍርድ ቤቱ ይህንን ተከትሎ ከተሰጠው ትዕዛዝ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ፍርድ ቤቱ ለአመልካች በአቤቱታው መሰረት የእግድ ትዕዛዙን የሰጠው

እግዱን ለመስጠት የሚያስችል በቂ ምክንያት ቀርቦለት በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.158 እግዱን ሊያነሳ የሚችለው በህጉ በግልፅ እንደተመለከተው እግዱ እንዲነሳ የቀረበው "...አቤቱታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን ..."ያረጋገጠ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሊሆን እንደሚገባ ከድንጋጌው ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

እግዱ በስር ፍርድ ቤት የተነሳው የተሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ለማስነሳት የሚያስችል በቂ ምክንያት ቀርቦ መሆን አለመሆኑን ስንመረምረውም ተጠሪ እግዱ እንዲነሳለት የጠየቀው ክርክር የተነሳበት ቦታ ለጅቡቲ ፕሬዝደንት መኖሪያ ቤት ማስፋፊያ በካቢኔ ውሳኔ መሰጠቱን መነሻ በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስም የእግዱ መቀጠል "...በኢትዮጲያና በጅቡቲ መንግስታት መካከል የነበረውን የረዥም አመታት የጉርብትና ታሪክና መልካም ግንኙነት 3000 ካሜ በማይሞላ ቦታ ምክንያት..."ሊያበላሸው ስለሚችል እግዱ ሊነሳ ይገባል በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ይህ ምክንያት በምን አግባብ ክርክሩ ሳይጠናቀቅ እግዱን ለማንሳት በቂ ምክንያት እንደሆነ ግልፅ ያላደረገ ሲሆን ክርክሩ በህጉ አግባብ ተመርቶ በተገቢው ጊዜ እልባት እስኪሰጠው ጊዜ ድረስ የእግዱ መቀጠል በምን አግባብ የሀገራቱን የጉርብትና ታሪክና መልካም ግንኙነት እንደሚያበላሽ ተጠሪ ግልፅ በማድረግ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂ ምክንያት መሆኑን ባላሳየበት ፍርድ ቤቱ በተጠሪ የቀረበውን ምክንያት በቂ ነው በማለት ተቀብሎ እግዱን ማንሳቱ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.158ን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ አግባብ ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ/ቁ.78425 በ04/01/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በ15/11/2012 ዓም የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ በማንሳት የሰጠው ትዕዛዝና ይህንን ትዕዛዝ በማፅናት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ.17124 በ15/01/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.78425 በ15/11/2012 ዓም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በግራ ቀኙ መሃል የተያዘው ክርክር በስር ፍርድ ቤት ተገቢውን እልባት እስኪያገኝ ድረስ ወይም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.158 እግዱን ለማንሳት የሚያስችል በቂ ምክንያት ቀርቦ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት አግኝቶ እግዱ እንዲነሳ ተገቢው ትዕዛዝ እስኪሰጥበት ድረስ ፀንቶ ሊቆይ ይገባል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ተገቢውን እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ 182044

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ጠጂቱ ጎረምሶ ማገር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ወርቅነሽ በሻ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አመልካች በስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይዞታና ቤቱ ይለቀቅልኝ፤ በተጠሪ ስም የተሰራው ካርታም እንዲመክን ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 5 መሠረት ውድቅ መደረጉ እና ይህም ውሳኔ በይግባኝ መጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው መነሻነት ነው፡፡

አመልካች ለስር ፍርድ ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ቤ.ቁ 147 የይዞታ መለያ ቁጥሩ 559 የሆነ እና በ500 ካ.ሜ. ላይ ያረፈውን ቤት ተጠሪዋ በስጦታ ወይም በግዢ ሳይተላለፍላቸው 250 ካ.ሜ. የሆነውን ይዞታ በስማቸው ካርታ አሰርተው የያዙባቸው መሆኑን በመግለጽ ይዞታውን እንዲለቁ እና አላግባብ ያሰሩት ካርታ እንዲመክን ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው ስላልቀረቡ ጉዳያቸው በሌሉበት የታየ መሆኑን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክሱን ሲሰማ ተጠሪ በአሁን አመልካችና በባለቤታቸው ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበውባቸው ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ ሁከት እንዲወገድ ተወስኖ ቤቱንም በአፈፃፀም ተገደው በመልቀቃቸው የመፋለም ክስ ያቀረቡ መሆኑን ለፍ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በተጠሪ ክስ አቅራቢነት ውሳኔ እና የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሰጥቶባቸዋል የተባሉትን የመዝገብ ቁጥራቸው 14278 እና 95883 የሆኑትን መዛግብት ካስቀረበ እና ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካልም ተጠሪ ቤቱን በምን አግባብ እንደያዙ አጣርቶ እንዲልክለት ካደረገ በኋላ አመልካች ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው ሲል አጽንቶታል፡፡

አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ በአመልካች እና በባለቤቱ ላይ በመ.ቁ 14278 ያቀረበችው ክስ ሁከት ይወገድልኝ በሚል የቀረበ እንጂ ይዞታ እንዲመለስ ወይም ካርታ እንዲመክን በሚል የቀረበ ክስ አይደለም፣ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የተሰጠውም የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ በሚል እንጂ ይዞታው የተጠሪ መሆኑ ተገልጾ የተሰጠ ውሳኔ የለም፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀርባ ባልተከራከረችበት እና ካርታውም ባልመከነበት ሁኔታ ጉዳዩን ከሁከት ክስ ጋር አገናኝቶ አመልካች ያቀረቡት ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎቱ ተመርመሮ ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 14278 በቀን 30/11/1999 ዓ.ም. ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሆኖ አሁን የቀረበው ክስ ግን ባለቤትነትን የሚመለከት ሆኖ ሳለ፤ ተጠሪዋም በዚህ ረገድ ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሳይኖር ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ስለሆነ በድጋሚ የክርክር ምክንያት ሊሆን አይችልም በሚል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተልኮላቸው መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አመልካች ካቀረቡት ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. ፍርድ ቤቶች ከሳሽ ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል መቃወሚያ ከሌላው ተከራካሪ

ወገን ባልቀረበበት ሁኔታ ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም?

2. ፍርድ ቤቶች በሌላው ተከራካሪ ወገን የቀረበ መቃወሚያ ባይኖርም ከሳሽ ያቀረበው ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ መሆኑን በማናቸውም ምክንያት ባረጋገጡ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ክሱን ውድቅ ማድረግ ይችላሉ ከተባለ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ በተጠቃሹ ድንጋጌ መሠረት ውድቅ ያደረገው በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን አረጋግጦ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች የሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 በንዑስ ቁጥር (1) ላይ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይችሉም በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ የሚቀርበው መቃወሚያም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚቀርብበትን ሥርዓት አስመልክቶ በተደነገገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 ድንጋጌ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የሚቀርቡ ናቸው ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (3) የቀረቡት መቃወሚያዎች ከአንድ በላይ ሲሆኑ በተቻለ መጠን በቶሎ ተጠቃለው ሁሉም መቅረብ እንዳለባቸው፤ መቅረብ ከሚገባቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ሳይቀርቡ የቀሩት ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት የማያሰናክሉ ከሆኑ ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተዋቸው ይቆጠራል በማለት ይደነግጋል፡፡

ከላይ በዝርዝር የተመለከቱት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች አንድ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው በሚል የሚቀርበው መቃወሚያ የሚቀርብበትን ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ሳይቀርብ ቀርቶ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ በሆነ ጊዜ ወይም ተከሳሹ ቀርቦ መቃወሚያውን ባላነሳው ጊዜ ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን በአንድም ወይም በሌላ ምክንያት ባወቁ ጊዜ ሊኖራቸው የሚገባው ሚና በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት ያለበት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡ ስለሆነም በጉዳዩ ላይ ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 36780 እና 124660 አንጻር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 36780 በሰጠው ውሳኔ በአብዛኛው ትኩረት ያደረገው አስቀድሞ በተሰጠው ፍርድ ላይ የነበረው የፍሬ ነገር ጭብጥ እና አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ተመሳሳይ ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ሲሆን የፍሬ ነገር

ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሳ ተቀባይነት አለው በሚል በውሳኔ ላይ በግልጽ አመልክቷል፡፡ ችሎቱ ይህንኑ ውሳኔ በመጥቀስ በሰ.መ.ቁ 124660 የሰጠው ውሳኔ ደግሞ የስር ፍርድ ቤቱ ከተጠሪ ጋር የነበረውን ጋብቻ የፈረሰ መሆኑን በመግለጽ የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ይህ ክርክር አስቀድሞ ታይቶ አብቅቷል በማለት ቢሆንም በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ለተጠሪ ደርሶ ተጠሪ መቃወሚያ አላቀረቡበትም፤ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡበት በማድረግ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ በድጋሚ ሊቀርብ አይገባም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ካለ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ መሆን ያለመሆኑን በማስረጃ አጣርቶ ከሚወስን በቀር ተከራካሪዎች ባላነሱት መቃወሚያ በራሱ ጊዜ ማንሳት አይችልም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች መልስ ያልሰጡበትን እና ያላነሱትን መቃወሚያ በማንሳት ጉዳዩ በድጋሚ ሊቀርብ አይገባም በማለት አቤቱታውን ውድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም ካለ በኋላ ግራ ቀኙ በስምምነት ፍቺ ፈጽመው የንብረት ክፍፍላቸው በፍርድ ቤት የጸደቀ በመሆኑ ምንም እንኳን ፍርድ ቤቱ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡት ሳያደርግ መቃወሚያው በተጠሪ ሳይነሳ በራሱ ጊዜ በማንሳት ጉዳዩ አስቀድሞ ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል በማለት መዝጋቱ ተገቢ ባይሆንም የንብረት ክፍፍላቸው በፍርድ ቤት ጸድቆ ባለበት እና ይህ ስምምነት እንዲፈርስ ጠይቀው ባላስፈረሱበት እንደ አዲስ ንብረት እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብሎ ያጸናው መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡

ከላይ ከተመለከቱት ውሳኔዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ሰበር ሰሚ ችሎቱ በአንድ በኩል ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል መቃወሚያ በተከራካሪ ወገኖች እስካልቀረበ ድረስ ፍርድ ቤቱ ራሱ ማንሳት አይችልም የሚል አቋም ያለው መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጠ የጸና ፍርድ ባለበት ሁኔታ አዲስ በቀረበው ክስ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት አግባብ አይኖርም የሚል አቋም ያለው መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ይህም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ሳይቀርብ ቀርቶ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ በሆነ ጊዜ ወይም ተከሳሹ ቀርቦ መቃወሚያውን ባላነሳው ጊዜ ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን ባወቁ ጊዜ አዲስ የቀረበው ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ውድቅ ማድረግ የሚኖርባቸው ስለመሆን አለመሆኑ ግልጽ የሆነ አቋም ያልያዘበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የተደነገገበት ዋና ዓላማ አንድ ተከራካሪ ወገን በተመሳሳይ

ጉዳይ ላይ በተለያየ ጊዜ ክስ እየቀረበበት ጊዜውን እንዳያባክን፤ ተጨማሪ ወጪ እንዳያወጣ እና እንዳይሸማቀቅ ለማድረግ፤ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተሻረ ድረስ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ፤ ክርክሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ መቋጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ፤ ሕጉ ላልተፈለገበት ዓላማ እንዳይውል በመከላከል የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ ተገማች እና ፍትሐዊ እንዲሆን ለማድረግ ስለመሆኑ በዘርፉ ከዳበረው ሥነ ሕግ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አንድ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑ ከተረጋጠ አዲስ የቀረበውን ክስ በድጋሚ አይቶ ውሳኔ መስጠት ከላይ የተመለከተውን የሥነ ሥርዓት ሕጉን አይነተኛ ዓላማ የማያሳካ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተጣረሰ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበትን ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ሳይቀርብ ቀርቶ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ በሆነ ጊዜ ወይም ተከሳሹ ቀርቦ መቃወሚያውን ባላነሳው ጊዜ ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን በአንድም ወይም በሌላ ምክንያት ባወቁ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸው እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ አዲስ የቀረበውን ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሰረት ውድቅ ሊያደርጉት ይገባል በማለት ቀደም ሲል የተሰጠውን የሕግ ትርጉም አሻሽለን በያዝነው ጉዳይ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ገዢ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡ ፍርድ ቤቶች በፊታቸው የቀረበላቸው ጉዳይ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን በክርክሩ ሂደት ባረጋገጡ ጊዜ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት አዲስ የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ ከተባለ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ድጋሚ የቀረበ ክስ ነው በማለት ውድቅ ያደረገው በእርግጥም በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1) ላይ በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ ሊደረግ የሚችለው ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት ከሆነ እና አዲስ በቀረበው ክስ ላይ ተከራካሪ በመሆን የቀረቡት ወገኖች ቀድሞ በነበረው ክርክር ላይ የነበሩ ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በሆኑ ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች እና በባለቤታቸው ላይ በመ.ቁ 14278 አቅርበውት የነበረው ክስ ይዞት ሁከት ይወገድልኝ በሚል የቀረበ ሲሆን አሁን በእጃችን ባለው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት ክስ ደግሞ ተጠሪ አከራከሪ የሆነው ቤት በስጦታም ሆነ በሽያጭ ሳይተላለፍላት ካርታ በስሟ ያወጣችበት ስለሆነ ያለአግባብ የተሰጣት ካርታ እንዲሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡ ይህም ቀድሞ በነበረው ክስ

ሊያዝ የሚችለው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል? ወይስ አልተፈጠረም? የሚል መሆኑን አመልካች ባቀረቡት አዲስ ክስ ላይ ደግሞ ሊያዝ የሚችለው ጭብጥ የንብረቱ ባለቤት ማነው? የሚል እና ከዚሁ ጭብጥ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ጭብጥ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት ባልሆነበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ በድጋሚ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ አለመሆኑን ተገንዝቦ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን አጣርቶ እንዲወስን ማድረግ ስነ- ስርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1) ከላይ በፍርድ ሐተታው በተገለጸው ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 36780 እና 124660 የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ሳይቀርብ ቀርቶ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ ወይም ተከሳሹ ቀርቦ መቃወሚያውን ያላነሳው ቢሆንም ከሳሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን ያቀረበው ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ ላይ የቀረበ መሆኑን በክርክሩ ሒደት ባረጋገጡ ጊዜ በድንጋጌው የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላታቸው እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ አዲስ የቀረበውን ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሰረት ውድቅ ሊያደርጉት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
2) የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 61458 በቀን 02/05/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 222445 ሐምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3) የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡት ክስ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በማለት የተወሰነ መሆኑን ተረድቶ በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

- የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡
- ይህ ውሳኔ ይታተም ዘንድ ለሕግ እና ጥናት ክፍል ግልባጩ ይድረሰው፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 184757

መስከረም 25 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ደረጀ አያና

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- የደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ገቢዎች ባለስልጣን፡- አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1.ፍራኦል ኢትዮጵያ የእርሻ ልማት ድርጅት፡- አልቀረቡም

2. የፌዴራል መንግስት ልማት ድርጅት ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ፡- ነ/ፈጅ ምህረቱ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሕግ የተሰጠ የቀደምትነት መብት አፈጻጸም የሚመለከት ሆኖ የፍርድ አፈጻጸም ክርክር በዉክልና በሚታይበት በደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ሆነዉ በሚከራከሩበት መዝገብ ላይ አመልካች የመቃወም አመልካች በመሆን የተከራከረ ነዉ፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፍርዱን እያስፈጸመ የሚገኘዉ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረደዉን ፍርድ እንዲያስፈጽም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን መነሻ ነዉ፡፡ ይህ የተወከለዉ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለእዳዉ ንብረት የሆኑትን የዕርሻ መሳሪያዎች ፣የዕርሻና ኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፣ ተቀጽላ መሳሪያዎች፣ ሞተሮች፣ የዉሃ ፓምፖችና ጀኔሬተሮች፣ የወርክ ሾፕ መገልገያ መሣሪያዎች እና የተለያዩ አይነት መገልገያ መሳሪያዎች ተከብረዉ እንዲቆዩ ካደረገ በኋላ የመነሻ ዋጋቸዉ እንዲታወቅ አድርጎ በብር 25,284,862.69 መነሻ ዋጋ በሐራጅ እንዲሸጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከላይ የተመለከተዉ ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት የአሁን አመልካች ለፍርድ ቤቱ ባቀረበዉ አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ ብር 10,393,364.75 የግብር እዳ ስላለበት እንዲከበሩ(እንዲታገዱ) በተደረጉት በተጠቃሾቹ

ንብረቶች ላይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እና በደቡብ ክልል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 166/2009 አንቀጽ 39፣41፣እና 43 መሰረት 1ኛ ተጠሪ ባልከፈለዉ ዉዝፍ የግብር እዳ ልክ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ የቀደመ መብት ስላለኝ በሕጉ መሰረት የቀደምትነት መብት ይጠበቅልኝ በማለት ጠይቋል።

ፍርዱን እያስፈጸመ ያለዉ የደቡብ አሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በመ/ቁጥር 11785 ላይ በቀን 07/09/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ የአሁን 2ኛ ተጠሪ(የፍርድ ባለመብት) የንብረት ዝርዝርና ግምታቸዉን አቅርቦ ንብረቶቹ በሐራጅ ተሸጠዉ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ በጠየቀበት ሁኔታ የአሁን አመልካች 1ኛ ተጠሪ(የፍርድ ባለዕዳዉ) ላለበት የግብር እዳ እነዚህን ንብረቶች በመያዣያነት ማስከበሩን የሚያስረዳ ማስረጃ ከአቤቱታዉ ጋር አያዞ አላቀረበም።ስለሆነም መብቱን አስከብሮ ባልቀረበበት በ2ኛ ተጠሪ በኩል የቀረቡት ንብረቶች በጨረታ ሲሸጥ የቀደምትነት መብት ይሰጠኝ በማለት መጠየቁ ተገቢነት የለዉም። ነገር ግን ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ ከሚቀረዉ ቀሪ ገንዘብ ላይ ገንዘቡን ከፍርድ ባለእዳዉ ላይ መቀበል ይችላል በሚል 2ኛ ተጠሪ በጠየቀዉ መሰረት ንብረቶቹ በሐራጅ ተሸጠዉ በፍርዱ መሰረት ለ2ኛ ተጠሪ እንዲከፈለዉ አዟል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቦ ችሎቱ በመ/ቁጥር 178407 ላይ በቀን 18/11/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል።

አመልካች በቀን 10/02/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ አግባብ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ።የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 ስር ያልተከፈለዉን የግብር እዳ አመልካች የግብር ባለእዳዉን ንብረት በማሸጥ ለማስከፈል የቀዳምነት መብት እንዳለዉ የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ። የአዋጁን ድንጋጌ አለአግባብ በመተርጎም የቀደምትነት መብት ተጠቃሚ ለመሆን የግብር ባለእዳዉ ንብረት በዋስትና መያዝና መያዣዉ መመዝገብ አለበት በማለት አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ።በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 እንደተደነገገዉ እና በሰ/መ/ቁጥር 48997 እና 86133 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በፍርድ አፈጻጸም በታገደዉ ንብረት ላይ አመልካች ተቀዳሚ መብት አለኝ በሚል ያቀረበዉን አቤቱታ ተቀብሎ በመደበኛ የሙግት አመራር መሰረት ግራ ቀኙን ሳያከራክር ፣የአመልካችን የሠነድ ማስረጃዎች ሳይመረምር የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አድርጎ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል ማዘዙ ከስነ ስርዓት ሕጉ ዉጪ ነዉ።2ኛ ተጠሪ ያለዉ መብት በንብረቱ ወይም በሽያጭ ገንዘቡ ላይ የቀዳሚነት መብት ያለዉ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈልገዉን የግብር እዳ በቀዳሚነት ካስከፈለ በኋላ የሚተርፈዉን ገንዘብ መዉሰድ በመሆኑ አመልካች በተጠየቀዉ መሰረት በንብረቱ ላይ 2ኛ ተጠሪ ያሰጠዉ እግድ እንዲነሳ ማዘዝ ሲገባዉ የሥር ፍርድ ቤት ከአመልካች ዳኝነት ጥያቄ ዉጭ ንብረቱ በሐራጅ ከተሸጠ በኋላ ከ2ኛ ተጠሪ የሚተርፈዉን ገንዘብ መጠየቅ ይችላል

በማለት መወሰኑ በሰ/መ/ቁጥር 48042 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 ላይ የተደነገገዉን ያልተከተለ በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡አመልካች ዳኝነት ባልጠየቀበት ንብረቱ በሐራጅ ሲሸጥ ንብረቱን አመልካች በቀደምነት የመግዛት መብት እንዲጠበቅለት እንደጠየቀ አድርጎ የሥር ፍርድ ቤት በትእዛዙ ላይ መግለጹም ስህተት ነዉ፡፡1ኛ ተጠሪ የግብር እዳ ዉሳኔ ማስታወቂያ ደርሶት በተጠየቀ ጊዜ ካልከፈለ  አመልካች የግብር እዳዉን ለማስከፈል በሕግ የሚጠበቅበት ተግባር የባለእዳዉን ንብረት አግዶ በመሸጥ ግብር ያስከፍላል እንጂ ለፍርድ ቤት ጥያቄዉን አቅርቦ ንብረቱን እንዲያስከብር አይገደድም፡፡ በተጨማሪም ንብረቱን ይዞ መሸጥ የሚችለዉ ንብረቱ ላይ በፍርድ ቤት የተሰጠ እግድ ካለ እግዱን ካስነሳ በኋላ በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ የግብር እዳ የሚፈለግበት መሆኑን የሚያሳይ የግብር ማስታወቂያ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ ከመሆኑ በፊት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መስጠቱን ለስር ፍርድ ቤት ያቀረብነዉ ማስረጃ የሚያሳይ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ከሕግና ካቀረብነዉ ማስረጃ እንጻር ሳይመረምር የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ እያለ ስህተቱን ይግባኝ ሰሚዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አለማረሙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ ሲል አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ እንዲከፈለዉ ለሚጠይቀዉ የግብር እዳ ንብረቱን በመያዣነት ስላላስከበረም የቀዳሚነት መብት የለዉም የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39/1 ከደቡብ ክልል አዋጅ ቁጥር 166/2009 ጋር ተገናዝቦ እንዲመረመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን ተከትሎ ተጠሪዎች እንደቅደም ተከተላቸዉ በቀን 01/05/2012 ዓ/ም እና በቀን 30/04/2012 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ 1ኛ ተጠሪ በዉጭ ባለሀብቶች የተቋቋመ፣የኢንቨስትመንት እና የንግድ ፈቃድ የተሰጠዉ ከፌዴራል መንግስት በመሆኑ አመልካች 1ኛ ተጠሪን ግብርና ታክስ የማስከፈል ሥልጣን የለዉም፡፡አመልካች እየጠየቀ ያለዉ የመሬት መጠቀሚያ ግብርና የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለኝ አለ በሚል ቢሆንም መከፈል ያለበትን የቴምብር ቀረጥ የከፈልን ሲሆን የሊዝ ክፍያ የለም እንጂ የሊዝ ክፍያ አለ ቢባል እንኳን አመልካች በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ከመጠየቅ በስተቀር የቀደምትነት መብት አለኝ በሚል መጠየቅ የሚችልበት የሕግ መሰረት የለም፡፡የመሬት የሊዝ ክፍያ ማስከፈል እንዲችል በሕግ ከሌሎች ባለመብቶች የቀደመ መብት ለአመልካች አልተሰጠዉም፡፡ የቀደምትነት መብት የሚኖረዉ የሊዝና የቴምብር ቀረጥ ለማስከፈል ሳይሆን ያልተከፈለ የንግድ ግብርና የግብርና ግብር ክፍያ ሲኖር ብቻ ሲሆን ከዚህ አንጻር እዳ እንደሌለብን የፌዴራል ግብር አስከፋይ መስሪያ ቤት በጽሁፍ ስላሳወቀ አመልካች አለአግባብ የቀደምትነት መብት አለኝ በሚል ያቀረበዉን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤት ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ ስለሆነ የሠበር አቤቱታዉ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካች የግብር ሰብሳቢ በመሆኑ ብቻ ያለምንም ገደብ የግብር ከፋይ ንብረት ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ በማለት የሐራጅ ማስታወቂያዉ እንዲታገድና እግዱ እንዲነሳ መጠየቅ አይችልም፡፡በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 41(4/ለ) መሰረት በማንኛዉም የፍርድ ሂደት እገዳ በተደረገበት ወይም የአፈጻጸም ትእዛዝ በተሰጠበት ንብረት ላይ የመያዣ ዋስትና መስጠት እንደማይቻል ስለተደነገገ አመልካች በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት አለኝ በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 እና በደቡብ ክልል አዋጅ ቁጥር 166/2009 አንቀጽ 41 በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት ለግብር እዳዉ ንብረቱን በመያዣያነት መያዙን የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ ሳያስረዳ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418/3 መሰረት በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለዉ የሚያሳይ የጽሁፍ ማስረጃ ሳያቀርብ በማንኛዉም ግብር ከፋይ ንብረት ላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የቀደምትነት (absolute preemption right) አለኝ ሲል አቤቱታ ማቅረቡ የሕግ መሰረት ስለሌለዉ የሥር ፍርድ ቤት አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት ሙግት ከተደረገ በኋላ ዉድቅ የተደረገ በመሆኑ ተገቢዉ ሙግት ሳይደረግ ዉድቅ እንደተደረገ በመቁጠር የሰ/መ/ቁጥር 48997 እና 86133ን በመጥቀስ ያቀረበዉ መከራከሪያም አግባብ አይደለም፡፡በእዳ ምክንያት በፍርድ ቤት የተከበረ ንብረት እንዲሸጥ በተደረገ ጊዜ ንብረቱን ያስከበረዉ ወገን የሚኖረዉ መብት ከሽያጭ ገንዘብ ላይ የቀደምትነት መብት ካላቸዉ ባለገንዘቦች የሚተርፍ ካለ የመዉሰድ መብት ብቻ እንዳለዉ በሰ/መ/ቁጥር 48042 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ስለተሰጠና አመልካች በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለዉ በማስረጃ ስላላስረዳ አመልካች ያለዉ መብት እንደማንኛዉም መብት ጠያቂ ለ2ኛ ተጠሪ ተከፍሎ በሚቀረዉ ገንዘብ ላይ ብቻ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ማንኛዉም ታክስ ከፋይ ታክስ የመክፈል ግዴታዉን ያልተወጣ እንደሆነ ባለስልጣኑ እዳዉን በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ማስፈጸም የሚፈልግ ከሆነ በዋስትናነት ማስመዝገብና ንብረቱን በማሸጥ ታክሱን እንደሚያስከፍል የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ ይሰጣል ተብሎ ተደንግጓል እንጂ የግብር ዉሳኔ ማስታወቂያ እንደደረሰዉ የግብር ከፋይ ንብረት ይይዛል የሚል ሕግም ሆነ አሰራር ባለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከላይ በአጭሩ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በዚህ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች የቀደምትነት መብት አለኝ በሚል የፍርድ አፈጻጸሙን በመቃወም አቤቱታ ያቀረበዉ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረደዉን የገንዘብ ፍርድ ለማስፈጸም 2ኛ ተጠሪ ባስከበረዉ የ1ኛ ተጠሪ ንብረቶች ላይ በ1ኛ ተጠሪ የግብር እዳ ልክ የቀደምትነት መብት አለኝ በሚል

እንደሆነ ክርክራቸዉ ያሳያል። 1ኛ ተጠሪ ደግሞ የግብር እዳ ስለሌለብኝ የጠቀሳቸዉን ሕጎች መሰረት በማድረግ በንብረቶቹ ላይ የቀደምትነት መብት አለኝ ብሎ መጠየቅ አይችልም ብሎ ተከራክሯል። እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ የሚፈልገዉን እዳ ለማስከበር ንብረቱን ከ2ኛ ተጠሪ አስቀድሞ ያስከበረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ ይህንን ሳያደርግ ሕግ የቀደምትነት መብት አይሰጠዉም በሚል ተከራክሯል።

በመሰረቱ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 እና በደቡብ ክልል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 166/2009 ስር በተመሳሳይ እንደተደነገገዉ መሰረት ታክስ ሰብሳቢ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባዉ የመክፈያ ጊዜዉ የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት አለዉ።በዚህ ድንጋጌ የታክስ ሕግ ተብሎ የተገለጸዉ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(36) ላይ በተመለከተዉ ትርጓሜ መሰረት የታክስ አስተዳደር አዋጁን ጨምሮ የገቢ ግብር አዋጅ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣የሴክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣የቴምብር ቀረጥ አዋጅ፣የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣የጉምሩክ ሕግ ሳይጨምር ማንኛዉም ታክስ፣ ቀረጥ ወይም ክፍያ የሚጥል ሕግና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም የሚወጣ ደንብና መመሪያ እንደሆኑ በግልጽ ተመልክቷል።በመሆኑም ታክስ የመጣልና የመሰብሰብ የሥልጣን ክፍፍሉን ተከትሎ የፌዴራል እና የክልል ታክስ ሰብሳቢ ባለሥልጣን የሚሰበስቡት የታክስና የቀረጥ ዓይነት እንዲሁም የእነዚሁ ምንጭ የሆኑ ሕጎች ሊለያዩ የሚችሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራሉ ታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 39(በክልሉ አዋጅም በተመሳሳይ እንደተደነገገዉ) መሰረት በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት የሚኖረዉ በእነዚህ ሕጎች መሰረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባዉን የመክፈያ ጊዜዉ የደረሰዉን ታክስ ቀረጥና ተያያዥ ክፍያ ለማስከፈል መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።ይህም ቅቡልነት ያለዉ ዋና ግዴታ መኖሩን(valid principal obligation) መሠረት ያደረገ ነዉ።

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣን በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የሚኖረዉን የቀደምትነት መብት አፈጻጸምና አድማስ ሌሎች ከታክስ ከፋዩ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከሚኖራቸዉ መብት ጋር በማነጻጸር መመርመር እና ያላቸዉን ልዩነት በግልጽ ማወቅ ያስፈልጋል።በዚህ መልኩ በታክስ ከፋይ ሀብት ላይ ታክስ ሰብሳቢዉ ባለስልጣን ያለዉ የቀደምትነት መብት በሕግ ጽንሰ ሐሳብ በእንግሊዝኛዉ Preferential/Preferred Creditor ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን ጥቅል ሀሳቡም በአገራችን የታክስ አስተዳደርና በሌሎች የታክስ ሕጎች ላይ ጭምር እንደተንጸባረቀዉ በመርህ ደረጃ ገንዘብ ጠያቂ (በታክስ ጉዳይ ታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣን) በባለእዳዉ(በታክስ ከፋዩ) ሀብት ላይ ከሌሎች ከባለዕዳዉ ገንዘብ ከሚጠይቁ ተራ ባለገንዘቦች(unsecured/ordinary creditor) ቅድሚያ እንዲከፈለዉ መብት የሚሰጠዉ ነዉ።እንዲህ አይነት የገንዘብ ጠያቂዎች የቀደምትነት መብት( Preferential/Preferred Creditor) ከባለእዳዉ ሀብት ላይ በቅድሚያ እዳ የማስከፈል መብት እንደመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1386ና ተከታዮቹ ፣በቁጥር 1410ና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ እንዲሁም በሌሎች የሕግ ድንጋጌዎች ላይ

ተደንግጎ ከሚታወቀዉ ከሕግ ወይም ከዉል ከሚመነጨዉ አንድን ንብረት በቀደምትነት መግዛትን (Pre-emption) ከሚመለከተዉ የተለየ ነዉ፡፡

እንዲሁም ከፍርድ በኂላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 394/1 እና ከቁጥር 404 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የፍርድ ባለእዳዉ የሆነዉን ታክስ ከፋይ ንብረት ያስከበሩ የፍርድ ባለመብቶች በሕግ የቀደምትነት መብት ከተሰጠዉ ታክስ ሰብሳቢ ባለሥልጣን ጋር የሚኖራቸዉ የመብት ቅደም ተከተል ምን እንደሆነ መመርመር ይገባል፡፡በዚህ መልኩ የሚሰጠዉ ንብረት የማስከበር ትእዛዝ ዓላማዉ የፍርድ ባለዕዳዉ ዕዳዉን ከመክፈሉ በፊት ይህንን ንብረት ለሌላ ሰዉ እንዳይሰጥ፣እንዳይሸጥ፣እንዳይለዉጥ ወይም በማናቸዉም ሌላ ሁኔታ መብቱን ለማንም እንዳያዛዉር ለማገድና የፍርድ ባለእዳዉ እዳዉን መክፈል ካልቻለ ንብረቱን በሐራጅ በማሸጥ በፍርዱ መሰረት ለፍርድ ባለገንዘቡ ለመክፈል ቢሆንም በዚህ መልኩ የሚደረገዉ ንብረት ማስከበር በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 3044 መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በፍርድ ከሚቋቋመዉ የመያዣያ መብትን (Judicial mortgage right) የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ምክንያቱም በፍርድ የሚቋቋም መያዣ አስቀድሞ በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ዳኝነት አካል አንዱ ተከራካሪ ወገን ለሌላዉ ተከራካሪ ወገን እንዲከፍል የተወሰነን የገንዘብ እዳ ለማስፈጸም ዳኝነት ተጠይቆ ተለይቶ በሚታወቅ ንብረት ላይ እዳ ለማስከፈል የሚቋቋም በመሆኑ በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ንብረት ለማስከበር ከሚሰጥ ትእዛዝ የተለየ በመሆኑ ነዉ፡፡ስለሆነም በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት የፍርድ ባለእዳዉን ንብረት ያስከበረ ሰዉ የቀደምትነት መብት አለኝ ብሎ ለመጠየቅ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 404 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ አልተደነገገም፡፡

በሌላ በኩል በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 39(2 እና 7) ላይ እንደተመለከተዉ በታክስ ሰብሳቢዉ ባለስልጣን ታክስ ከፋዩ እንዲከፍል የጠየቀዉ ታክስ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የሚከፈል ታክስ፣የተጨማሪ እሴት ታክስ፣የተርን ኦቨር ታክስ ወይም የኤክሳይስ ታክስ ካልሆነ በስተቀር ባንኮች በንብረቱ ላይ የዋስትና(የመያዣያ) መብት ያቋቋሙት ብድሩን ከመስጠታቸዉ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ እዳ የሌለበት መሆኑን ከታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣን አረጋግጠዉ ከሆነ በታክስ ከፋዩ ንብረት ላይ የዋስትና(የመያዣያ) መብት ያቋቋሙ ገንዘብ ጠያቂ ባንኮች (secured creditor) እና ከታክስ ከፋዩ ደመወዝ የሚጠይቁ የታክስ ከፋዩ ተቀጣሪዎች ከታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ከታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣን የቀደመ መብት አላቸዉ፡፡

እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ታክስ የመክፈል ግዴታዉን ያልተወጣ እንደሆነ ታክስ ሰብሳቢ ባለስልጣን በሕግ የተሰጠዉን የቀደምትነት መብት በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የሚጠቀም መሆኑን፣ ያልተከፈለዉን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚወስደዉ እርምጃ የሚያስከትለዉን ወጪ እንደሚያስከፍለዉና በንብረቱ ላይም የዋስትና መብት እንደሚያስመዘግብ የሚገልጽ ማስታወቂያ ለታክስ ከፋዩ መስጠት እንዳለበት በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 39/3 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡በተጨማሪም ታክስ ከፋዩ የታክስ

ማስጠንቀቂያ በደረሰዉ በ30 ቀናት ዉስጥ ታክሱን አለመክፈሉን ምክንያት በማድረግ ታክስ ሰብሳቢዉ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩ ንብረት በማናቸዉም የፍርድ ሂደት እገዳ ተደርጎበት ከሆነ ወይም በንብረቱ ላይ የፍርድ አፈጻጸም ትእዛዝ ተሰጥቶበት ከሆነ ንብረቱ ላይ የተሰጠዉን እግድ ወይም የአፈጻጸም ትእዛዝ ካላስነሳ በስተቀር የታክስ ከፋዩን ንብረት መያዝ (Seizure of Property) እንደማይችል በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 41(4/ለ) ስለተደነገገ የቀደምትነት መብቱን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የታክስ ከፋዩን ንብረት ለመያዝ በንብረቱ ላይ የተሰጠዉን የፍርድ ቤት እግድ ወይም የፍርድ አፈጻጸም ትእዛዝ አሰቀድሞ ማስነሳት ይጠበቅበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረደዉን ፍርድ ለማስፈጸም የ1ኛ ተጠሪን ንብረት ያስከበረ ተከራካሪ ወገን እንደመሆኑ ያለዉ መብት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 394/1፣ቁጥር 404 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት እግዱን የሠጠዉ ፍርድ ቤት እግዱን እስካላነሳ ድረስ ያስከበረዉን ንብረት 1ኛ ተጠሪ ዕዳዉን ከመክፈሉ በፊት ለሌላ ሰዉ እንዳይሰጥ፣ እንዳይሸጥ፣ እንዳይለዉጥ ወይም በማናቸዉም ሌላ ሁኔታ መብቱን ለማንም እንዳያዛዉር አስከብሮ ማቆየትና የፍርድ ባለእዳዉ እዳዉን መክፈል ካልቻለ ንብረቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ መጠየቅ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ የፍርድ ባለእዳውን በዚህ አግባብ ማስከበሩ ንብረቱ ከመከበሩ ወይም ከመያዙ በፊት በንብረቱ ላይ መብት የነበራቸዉና በክርክሩ ዉስጥ የሌሉ የሦስተኛ ወገኖች *በሕግ፣በፍርድ ወይም በዉል በንብረቶቹ ላይ ያቋቋሙትን የቀደምትነት መብት የሚነካ አይደለም፡፡* ከያዝነዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አመልካች በፌዴራልም ሆነ በክልል የታክስ አስተዳደር አዋጆች ላይ በተመሳሳይ በተደነገገዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ አልከፈለም ብሎ ንብረቱን ይዞ በመሸጥ ለማስከፈል የፈለገዉ የክልሉን ታክስ የታክስ አስተዳደር አዋጅን ጨምሮ ከገቢ ግብር አዋጅ፣ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ከሲክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ከቴምብር ቀረጥ አዋጅ፣ከተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣የጉምሩክ ሕግ ሳይጨምር ማንኛዉም ታክስ፣ ቀረጥ ወይም ክፍያ የሚጥል ሕግና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም ከወጣ ደንብና መመሪያ የመነጨ መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ቀድሞ ንብረቱን በመሸጥ ያልተከፈለዉን ታክስና ቀረጥ የማስከፈል በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መብት አለዉ፡፡ ነገር ግን አመልካች 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍለዉ የጠየቀዉ ታክስና ቀረጥ እንዲሁም ተያያዥ ክፍያ በዝርዝር ከተጠቀሱ ሕጋጋት የመነጩ መሆናቸዉን እና በሥልጣኑ ክልል ዉስጥ የሚገኝ ታክስና ቀረጥ መሆኑን በሌላ አገላለጽ ቅቡልነት ያለዉ ዋና ግዴታ መኖሩን(valid principal obligation) ማስረዳት እና ፍርድ ቤቶችም ማስረዳቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ሆኖም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 በሚጠይቀዉ የክርክር አመራር መሰረት ከዚህ አኳያ የግራ ቀኙን ክርክር ካለመመርመራቸዉም በተጨማሪ ፍሬ ነገሮቹን ከሕግና ከማስረጃ አንጻር አለማጣራታቸዉን ተገንዝበናል፡፡

እንዲሁም በሕግ የተሰጠዉን የቀደምትነት መብት በ1ኛ ተጠሪ ሀብት ላይ የሚጠቀም መሆኑን፣ ያልተከፈለዉን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚወስደዉ እርምጃ የሚያስከትለዉን ወጪ

እንደሚያስከፍለዉና በንብረቱ ላይም የዋስትና መብት እንደሚያስመዘግብ የሚገልጽ ማስታወቂያ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ(ለታክስ ከፋዩ) የሰጠ መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ፍርድ ቤቶችም አመልካች ባቀረበዉ ማስረጃ ማስረዳቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ ማስረዳት እስከቻለ ድረስ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በተከበሩት በ1ኛ ተጠሪ ንብረቶች ላይ የቀደምትነት መብት መጠቀም ይችላል፡፡ አመልካች በዚህ በቀደምትነት መብቱ መጠቀም ይችል ዘንድ ንብረቶቹን ለማስከበር የተሰጠዉ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳለት መጠየቁ በፌዴራልና በክልሉ ታክስ አስተዳደር አዋጆችም ሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከ2ኛ ተጠሪ ቀድሞ ንብረቶቹን ያስከበረ ስለመሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም የቀደምትነት መብት ያገኘዉ በሕግ በመሆኑና ንብረቶቹን መያዝና ሸጦ ታክስና ቀረጥ እንዲሁም ከላይ ከተጠቀሱ ሕጎች የመነጩ ሌሎች ክፍያዎችን ማስከፈል የሚችለዉ አስቀድሞ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ንብረቶቹን ለማስከበር የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ሲነሳለት ብቻ በመሆኑና ለዚህ የፍርድ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉን አቤቱታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 መሰረት ያቀረበዉንም ለዚሁ ዓላማ በመሆኑ ነዉ፡፡ከዚህም ረገድ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 418 በሚጠይቀዉ የክርክር አመራር መሰረት የግራ ቀኙን ክርክር ሳይመረምሩና ፍሬ ነገሮቹን ከሕግና ከማስረጃ አንጻር ማስረዳት ያለበት ተከራካሪ ወገን እንዲያስረዳ በማድረግ ሳያጣሩ በሕግ ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን የቀደምትነት መብት ዉድቅ ማድረጋቸዉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

**<u>ዉ ሳ ኔ</u>**

1. የደቡብ አሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11785 ላይ በቀን 07/09/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 178407 ላይ በቀን 18/11/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥ 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. 2ኛ ተጠሪ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ባስከበራቸዉ የ1ኛ ተጠሪ ንብረቶች ላይ አመልካች የቀደምትነት መብት አለዉ ብለናል፡፡ሆኖም አመልካች በዚህ የቀደምትነት መብት መጠቀም የሚችለዉ የክልሉን የታክስ አስተዳደር አዋጅን ጨምሮ ከገቢ ግብር አዋጅ፣ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ከቴምብር ቀረጥ አዋጅ፣ከተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ፣የጉምሩክ ሕግ ሳይጨምር ማንኛዉም ታክስ፣ ቀረጥ ወይም ክፍያ የሚጥል ሕግና እነዚህን አዋጆች ለማስፈጸም ከወጣ ደንብና መመሪያ የመነጨ እና ይህም በአመልካች እንዲሰበሰብ በሕግ ለአመልካች ሥልጣን የተሰጠዉ መሆኑን እንዲሁም አመልካች በሕግ የተሰጠዉን የቀደምትነት መብት በ1ኛ ተጠሪ ሀብት ላይ የሚጠቀም መሆኑን፣ ያልተከፈለዉን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚወስደዉ እርምጃ የሚያስከትለዉን ወጪ እንደሚያስከፍለዉና

በንብረቱ ላይም የዋስትና መብት እንደሚያስመዘግብ የሚገልጽ ማስታወቂያ ለ1ኛ ተጠሪ(ለታክስ ከፋዩ) መስጠቱ ሲረጋገጥ በመሆኑ የደቡብ አሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከዚህ አኳያ ግራ ቀኙን አከራክሮና በማስረጃ ሊረጋገጡ የሚገባቸዉን ፍሬ ነገሮች በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ በማስረጃ እንዲረጋገጡ በማድረግ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

**ት እ ዛ ዝ**

1. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 192823

ቀን፡- ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ፀጋይ ተስፋይ፡- ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት-ነ/ፊጅ አድማስ ደምሳቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የደረጃ ዕድገት ውድድርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ሲሆኑ በመሥሪያ ቤቱ በወጣው የገበያ ልማት ቡድን መሪ የደረጃ ዕድገት ውድድር ላይ ያላቸው የሥራ ልምድ በቂ አይደለም ተብሎ ከውድድሩ ውጭ በመሆናቸው ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያመለከቱ ሲሆን ኮሚቴው ለሥራ መደቡ ከሚያስፈልገው ስምንት ዓመት የሥራ ልምድ አመልካች ያላቸው ሰባት ዓመት ከአስራ ስድስት ቀን የሥራ ልምድ በመሆኑ ለሥራ መደቡ በቂ አይደለም በማለት ቅሬታቸውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የደረጃ እድገት ውድድሩ ለነባሩ የሥራ መደብ የተዘጋጀውን ፎርም ቁጥር 14 መከተል ሲገባው በነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ፎርም-14 ሥራ መዘርዝር መሠረት የደረጃ ዕድገት ውድደሩ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ በነባሩ የሥራ መደብ የተዘጋጀው ፎርም ቁጥር 14 መሠረት ለገበያ ልማት ቡድን መሪ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት አመልካች ስለማያሟሉት በደረጃ ዕድገት ውድድሩ እንዳይሳተፉ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በሥር ከተከራከርንበት ጭብጥ እና ከቀረበው ማስረጃ ውጭ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ለሁሉም የደረጃ ዕድገት ውድድር በነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ፎርም-14 ሥራ መዘርዝር መሠረት ተደርጎ እያለ ለምንከራከርበት የሥራ መደብ ብቻ በነባሩ የሥራ መደብ የተዘጋጀው ፎርም ቁጥር 14 ተግባራዊ ይደረግ መባሉ ስህተት ነው፡፡ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ፎርም-14 ሥራ መዘርዝር መሠረት የተደረጉ የደረጃ ዕድገት ውድድሮችን ውጤት አጽድቋል፡፡ ለሥራ መደቡም ከስምንት ዓመት በላይ የሥራ ልምድ ስላለኝ ልወዳደር ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የነበረው የአመልካች ቀጥታ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ለደረጃ ዕድገቱ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚል ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ ባልተከራከሩበትና ዳኝነት ባልተጠየቀበት የትምህርት ዝግጅት ላይ መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ሕጋዊነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪ የሠጠው መልስ የአመልካች የሥራ ልምድ ሰባት ዓመት ከአስራ ስድስት ቀን ብቻ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔም ከጭብጡ ውጭ ሳይሆን የውድድሩን መሠረት ያደረገ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ክርክሩ የተደረገው የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ሲሆኑ በመሥሪያ ቤቱ በወጣው የገበያ ልማት ቡድን መሪ የደረጃ ዕድገት ውድድር ላይ ያላቸው የሥራ ልምድ በቂ አይደለም ተብሎ ከውድድሩ ውጭ በመሆናቸው ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የደረጃ እድገት ውድድሩ ለነባሩ የሥራ መደብ የተዘጋጀውን ፎርም ቁጥር 14 መከተል ሲገባው በነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን አፈጻጸም መመሪያ ለማስፈጸም በተዘጋጀው ፎርም-14 ሥራ መዘርዝር መሠረት የደረጃ ዕድገት ውድደሩ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ በነባሩ የሥራ መደብ የተዘጋጀው ፎርም ቁጥር 14 መሠረት ለገበያ ልማት ቡድን መሪ የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅት አመልካች ስለማያሟሉት በደረጃ ዕድገት ውድድሩ እንዳይሳተፉ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/2002 ተጠሪነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ የተቋቋመ የፌደራል መሥሪያ ቤት ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ሠራተኞችንም በፌደራል የመንግሥት ሠራተኞች ሕጎች መሠረት የሚያስተዳድር ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 11(2)(ለ)

ላይ ተደንግጓል፡፡ እንደ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ከሚፈጽመው የሥራ ተግባር እና ከሚያስተዳድራቸው ሠራተኞች ጋር በተያያዘ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት የራሱ ብቸኛ ሥልጣኑ ስለመሆኑ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50(2) ላይ የተመለከተው የመንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍል መርህ (principle of separation of powers) ያሥገነዝባል፡፡ በሦስቱ የመንግሥት አካላት በሆኑት ሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈጻሚው እና የሕግ ተርጓሚው መካከል የሥልጣን ክፍፍል ያለ ቢሆንም በመካከላቸው የእርስ በእርስ ቁጥጥር (check and balance) ከሌለ ተቋማቱ በሕግ የተጣለባቸውን የዜጎችን ሠብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ማክበርና ማስከበር አይችሉም፡፡ የእርስ በእርስ ቁጥጥሩ ጣልቃ መግባትን ካስከተለ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝንና የተጣለባቸውን ግዴታ እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው ስለሚችል ቁጥጥሩ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ መፈጸም አለበት፡፡

አስተዳደራዊ አካላት የሚሠጧቸው ውሳኔዎች በፍ/ሕ/ቁ. 401(1) እንደተመለከተው ከተሠጣቸው ሥልጣን በማለፍ ከወሰኑ (ultra vires) ወይም በተሠጣቸው ሥልጣን ስር ሆኖ ነገር ግን በሕጉ የተመለከቱትን አስገዳጅ ሁኔታዎችና ፎርም ሳይከተሉ የሚፈጽሙት ተግባር ወይም ውሳኔ ፈራሽ ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ላይ ሠዎች ፍትሕ የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የሰዎችን መብቶች ሲነኩ በዳኝነት አካል ጉዳዩ ቀርቦ ውሳኔያቸው ሕግን የተከተለ መሆን አለመሆኑ ይመረምራል፡፡ የመዳኘት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ቢሆንም የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(4) እና 37 ላይ አንድ ላይ ሲነበቡ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓትን የሚከተል የዳኝነት ነክ አካላት በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ የእነዚህ አካላት የዳኝነት ሥልጣን በተፈጥሮ የሚገኝ ሳይሆን በግልጽ ሕግ ለመዳኘት ሥልጣን ሲሰጣቸውና የሚሰሩበት የተደነገገ የዳኝነት ሥርዓት ሲኖራቸውና ይህን ተከትለው ሲሰሩ የሚኖራቸው ሥልጣን ነው፡፡ ይህም በዘመናዊው የመንግሥት ሥርዓት መንግሥት ብዙ ጉዳዮች ላይ ሠፊ ሥልጣን ያለው በመሆኑ ለመንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል የዳኝነት ነክ ሥልጣን አስፈላጊ በመሆኑ፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ደግሞ ፍሬ ነገሮችን ለመመልከት ልዩ ዕውቀት የሚጠይቁ (specialization) በመሆኑ እና ፍርድ ቤቶች ላይ ያለውን የሥራ ጫና ለማቃለል ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤትም በዚህ አግባብ የተቋቋመ የዳኝነት ነክ አካል ነው፡፡ ተጠሪ የሠጠው አመልካችን ከደረጃ ዕድገት ውድድር ውጭ የማድረግ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርብበት ስለመሆኑ የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 81 የተመለከተ በመሆኑ ጉዳዩ በአስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ ተጀምሮ መመራቱ ሕጉን የተከተለ ነው፡፡ ነገር ግን ጠንካራና አስተማማኝ የዜጎች ሰብዓዊ መብት የሚከበርበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሕግ የበላይነትን ማስፈን ወሳኝ ነው፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መግቢያ ክፍል ላይ እንደተመለከተው የሕግ የበላይነት የሕገ-መንግሥቱ ዋነኛ መገለጫ ሲሆን አንዱ መስፈርት ደግሞ የዳኝነት ሥልጣን በነፃና ገለልተኛ ፍርድ ቤት መታየቱ ነው፡፡ ሥለሆነም ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ በሕግ የመዳኘት

ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚወስኑት ውሳኔ በዳኝነት ክለሳ (judicial review) ሂደት በማለፍ በፍርድ ቤት መታየት ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሠጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዳኝነት ክለሳ ሂደት ታይቶ ለዚህ ችሎት የቀረበ የሠበር አቤቱታ ነው፡፡

የሠበር አቤቱታው የተመሠረተው የሥር ክርክሩ አመልካች ያላቸው የሥራ ልምድ ለሥራ መደቡ በቂ ነው ወይስ አይደለም የሚል ሆኖ እያለ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የትምህርት ዝግጅት ላይ ተመስርቶ መወሰኑ ተገቢ የሆነ የዳኝነት አመራር ሂደት አይደለም በሚል ነው፡፡ የዳኝነት ነክ አካል ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጭ በአስፈጻሚው አካል ሥር የሚቋቋም በሕግ በግልጽ የተለዩ ውስን ጉዳዮችን የሚመለከት ዳኝነት ሰጭ አካል እንደመሆኑ መጠን መደበኛው ፍርድ ቤት የሚመራበት ሥርዓትን መከተል ሳይገባው በሚወጣለት ልዩ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ማንኛውም የዳኝነት አካል ሊከተለው የሚገባ የዳበረ የዳኝነት አሰጣጥ ዝቅተኛ መስፈርቶች አሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹም የቀረበለትን ጉዳይ ለመመልከት ሥልጣን ያለው መሆኑ፣ ጉዳዩን ያቀረበው ሠው አቤቱታውን ለማቅረብ መብት ያለው መሆኑ (standing right)፣ መብቱ የበሰለ ስለመሆኑ (ripeness)፣ የግራ ቀኙን ወገን የመደመጥ መብት (basic due process) ያከበረ መሆንና ውሳኔው የተመሠረተው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ መሆን ናቸው፡፡

የፍትሐ ብሔር ክርክር ተከራካሪን የተከተለ (party doctrine) ሲሆን አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የተመለከተውም አቤቱታ የቀረበለት በአመልካች በመሆኑ ውሳኔው መመስረት ያለበት አመልካችን አስመልክቶ የተጣሱ መብቶችን በመመርመርና አመልካች በጠየቀው ዳኝነት ላይ ነው፡፡ የአስተዳደር መሥሪያ ቤት በራሱ አነሳሽነት ሆነ አቤቱታ ሲቀርብለት በደረጃ ዕድገት ውድደሩ ላይ ጥሰት ካገኘ ማንኛውንም አስተዳደራዊ ጥሰት የማረም ሙሉ ሥልጣን ያለው በመሆኑ ግድፈቱን ማረም ይችላል፡፡ ጉዳዩ ለዳኝነት አካል ከቀረበ ግን የዳኝነት አካል የሚመራበት ሥርዓት ያለው በመሆኑ ማንኛውንም ስህተት የማረም ሥልጣን የለውም፡፡ ማረም የሚችለው አቤቱታውን ባቀረበው ሰው መብት ልክና በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ ነው፡፡ የአመልካች ክርክር ለደረጃ ዕድገት ውድድሩ በቂ የሥራ ልምድ አለኝ የሚል ሆኖ እያለ ባልተጠየቀ ዳኝነት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውድድሩ መሠረት ያደረገበትን ፎርምና የአመልካች የትምህርት ዝግጅትን መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ስህተቱን ሳያርም ውሳኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የዳኝነት አሰጣጥ ሂደት ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 182944 ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 697/2011 ነሀሴ 16 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት አመልካች በይግባኝ ማመልከቻቸው በጠየቁት ዳኝነት አግባብ ለሥራ መደቡ የደረጃ ዕድገት ውድድር ያላቸው የሥራ ልምድ በቂ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ በውሳኔው መሠረት የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት እንዲፈፅም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 201182

ሚያዝያ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ወ/ሮ ጦይባ እንድሪስ

ተጠሪ- ወ/ሮ መሠረት አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርዱ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ አንድ የፍትሐብሔር ጉዳይ በክርክር ሂደት ላይ እያለ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ተሽከርካሪ ከተከሳሽ በግዥ ይገቼ ባለሀብት የሆንኩበት ነዉ በሚል ምክንያት የሚቀርብ የእግድ ይነሳልኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑት ወ/ሮ ዳግማዊት ጌታቸዉ ላይ ያቀረቡት ክስ በሂደት ላይ እያለ የሰሌዳ ቁጥሩ ኢት 03-91811 የሆነ ጣሊያን አይቬኮ ተሽከርካሪ ታግዶ እንዲቆይ በፍርድ ቤቱ ታዟል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ በቀን 07/03/2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ሰኔ 03 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ የውል ስምምነት እግድ የተሰጠበት ተሽከርካሪ የጋራ ባለሀብት ከሆኑት ከስር ተከሳሽ እና አቶ ሰለሞን ሰመረ ከተባሉት ግለሰብ በብር 700,000.00 ገዝቼ ውሉ በተደረገበት ቀን ብር 400,000.00 ከፍዬ ቀሪውንም ክፍያ በኋላ ላይ ከፍዬ ንብረቱን በእጄ አድርጌ እየተጠቀምኩበት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 158 መሠረት እንዲነሳ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው በቀን 11/03/2013 ዓ.ም ጽፈው ለፍርድ ቤቱ በሰጡት አስተያየት ተሽከርካሪው የታገደው በአፈፃፀም ተይዞ እንጂ የክርክሩ መነሻ ባለመሆኑ አቤቱታው መቅረብ ያለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 418 መሠረት እንጂ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 158 መሠረት መሆን አልነበረበትም፤ የቀረበው የሽያጭ ውልም በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ያልተመዘገበ ሲሆን ንብረቱን በእጅ ማድረግ ብቻውን በቂ አይደለም፤ የንብረት ባለቤትነት የሚረጋገጠው በተመዘገበ የሽያጭ ውል እና ስመ ንብረቱ ተሠርዞ በገዢ

ስም ሲተላለፍ ብቻ በመሆኑ የቀረበው የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አቤቱታዉ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በተጠሪ እና የተሽከርካሪው ባለንብረት በነበሩት ግለሰቦች መካከል የሽያጭ ውል ስለመኖሩ ባልተካደበት በአዋጅ ቁጥር 681/2002 መሠረት የስም ምዝገባ ባለመደረጉ ብቻ በሽያጭ ውል የተገኘውን የባለቤትነት መብት የሚያሳጣበት የህግ መሠረት የለም በማለት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ አንስቶታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት አመልካች ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተሠርዞባቸዋል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 13/05/2013 ዓ.ም በተፃፈ ስድስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ተሽከርካሪው የእሳቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ ሳይኖር እግዱ እንዲነሳ የሰጡት ውሳኔ የህግ እና የማስረጃ መሠረት የሌለው በመሆኑ፤ በተጠሪ እና በተሽከርካሪው ባለንብረቶች መካከል የተደረገ የሽያጭ ውል የሌለ እና በማስረጃነት የቀረበውም ሀሰተኛ በመሆኑ፤ ተጠሪ ታግዶብኛል በማለት የሰሌዳ ቁጥሩን የጠቀሱት ተሽከርካሪ እና እኔ ያሳገድኩት ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥር የተለያየ በመሆኑ ባላሳገድኩት ተሽከርካሪ ላይ የእግድ አቤቱታ ይነሳልኝ በማለት አቤቱታ ሊቀርብ አይገባም ሲል ያቀረብኩት ክርክር ያለበቂ ምክንያት መታለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የሽያጭ ውል ስለመኖሩ በሻጮች እና በተጠሪ አልተካደም በሚል ምክያት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ የመወሰኑ አግባብነት ይህ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24693 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንፃር መጣራት አለበት ተብሎ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ጥሪ ተደርጎላቸው በቀን 10/06/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ተሽከርካሪውን መግዛቴን የሚያሳይ የሽያጭ ውል ሰነድ ካቀረብኩ፣ ሻጮችም የሸጡ መሆናቸውን ካረጋገጡ፣ እንዲሁም የሽያጭ ገንዘቡን ለሻጮች ስለመክፈሌ ያቀረብኩት ማስረጃ የተሽከርካሪው ባለቤት መሆኔን ለማረጋገጥ በቂ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ብይን ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለዉ የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በሆኑት ወ/ሮ ዳግማዊት ጌታቸዉ በተባሉት ግለሰብ ላይ ያቀረቡት ክስ ከቼክ ጋር የተያያዘ ዕዳን የሚመለከት እንጂ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ተሽከርካሪ የሚመለከት አለመሆኑን እና ጉዳዩ በሂደት ላይ እያለ ተሽከርካሪዉ እንዲከበር የተደረገዉ ለፍርድ ማስፈጸሚያ እንዲዉል ታስቦ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም እግዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 151 መሠረት የሚሰጥ ዓይነት ይዘት ያለዉ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ የሚሰጥ የንብረት ማስከበር ትዕዛዝ ሊነሳ ስለሚችልበት አግባብ የሚደነግገዉ የህጉ አንቀጽ 153(3) ድንጋጌ ከፍርድ በፊት በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚለዉ ሦስተኛ ወገን መብት ያለዉ መሆኑ የሚመረመረዉ በፍርድ አፈፃፀም ላይ ያለዉ ንብረት የሦስተኛ ወገን መብት ያለበት መሆኑ በሚመረመርበት ዓይነትና ሁኔታ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ይህም ማለት ክርክሩ ስለሚመለከተዉ ሳይሆን በሌላ ክርክር ምክንያት ከፍርድ በፊት በሚሰጥ ትዕዛዝ በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሦስተኛ ወገን መብቱን የሚያስከብረዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 እና ተከታዮቹ ላይ በተመለከተዉ አግባብ መሆን አለበት ማለት ነዉ፡፡ የህጉ አንቀጽ 158 ድንጋጌ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ንብረት ወይም ለክርክሩ መነሻ ከሆነዉ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ንብረት ከፍርድ በፊት በአንቀጽ 154 እና 155 መሠረት የታገደ ሲሆን ተፈፃሚ የሚሆን ድንጋጌ እንጂ ለተያዘዉ ጉዳይ ዓይነት ማለትም በሌላ ክርክር ምክንያት ከፍርድ በፊት ስለተከበረ ንብረት የሚመለከት ባለመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለዉም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንብረቱ የተከበረዉ ከፍርድ በፊት እንጂ በአፈፃጸም ምክንያት አይደለም በሚል ምክንያት አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በህጉ አንቀጽ 158 መሠረት መቅረቡ በአግባቡ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መታረም ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ወደ ዋናዉ የክርክር ነጥብ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ ተጠሪ ላቀረቡት የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ መሠረት ያደረጉት ተሽከርካሪዉን ገዝተዉ ተረክበዉ እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ሲሆን፣ ይህም የተጠሪ አቤቱታ ተሽከርካሪዉ የግሌ እንጂ የስር ተከሳሽ አይደለም የሚል ይዘት ያለዉ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ አመልካች ማሳገዳቸዉን ሳይክዱ እግዱ ተጠሪ በአቤቱታዉ ላይ የጠቀሱትን ተሽከርካሪ አይመለከትም በማለት ነገር ግን የትኛዉን ተሽከርካሪ እንዳሳገዱ ለይተዉ ሳይገልጹ በደፈናዉ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ ይልቁንም እግድ የተሰጠበት ተሽከርካሪ ተጠሪ በአቤቱታቸዉ የጠቀሱት ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ እልባት ለመስጠት መያዝ የሚገባዉ ጭብጥ ተጠሪ በተሽከርካሪዉ ላይ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ በህግ አግባብነት ያለዉን ማስረጃ ያቀረቡ መሆን አለመሆኑ ነዉ፡፡

በዚህም መሠረት ተጠሪ ለመቃወም አቤቱታቸዉ ምክንያት የሆነዉን ተሽከርካሪ ከስር ተከሳሽ እና ከባለቤታቸዉ መግዛታቸዉንና ተሽከርካሪዉን ተረክበዉ እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን እንጂ

የተሽከርካሪዉ ስመ ሀብት በስማቸዉ የተዛወረ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ አንድን ንብረት አስመልክቶ የሚደረግ የሽያጭ ዉል የንብረቱን ባለቤትነት ወደ ገዥዉ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል ነዉ (የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2266 ይመለከቷል)፡፡ ይሁንና ንብረትን በዉል የገዛ ሰዉ የንብረቱ ባለቤት ሊሆን የሚችለዉ እና የንብረት ባለቤትነት መብት በሚሰጠዉ መብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ ንብረቱ በዉሉ መሠረት የተፈጸመ ሲሆን ማለትም የንብረት ባለቤትነት መብቱ በህግ አግባብ የተላለፈለት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ዉል መፈጸም በሚል ርዕስ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2273 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ ይህም ማለት አንድን ንብረት መግዛት ብቻዉን በንብረቱ ላይ የባለቤትነት መብትን አያጎናጽፍም፤ የባለቤትነት መብት የሚተላለፈዉ ወይም ገዥዉ በገዛዉ ንብረት ላይ ባለመብት የሚሆነዉ ንብረቱን በዉሉ መሠረት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ሲያደርግ ነዉ፡፡ ስለሆነም በዉል የገዛሁት ንብረት የባለቤትነት መብቱ ከሻጭ ወደ እኔ ተላልፎልኛል የሚል ክርክር የሚያቀርብ ገዥ በእርግጥም በህግ አግባብ ይህ መብቱ የተላለፈለት መሆኑን የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ የሚከራከሩት በሽያጭ ዉሉ መሠረት ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ተሽከርካሪ ላይ የባለቤትነት መብት አግኝቻለሁ በማለት በመሆኑ ተሽከርካሪዉ በህግ አግባብ ከሻጮች የተላለፈላቸዉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለባቸዉ፡፡

በዚህ አግባብ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ተሽከርካሪ ከሻጮች ወደ ተጠሪ የተላለፈ መሆን አለመሆኑን ወይም ተጠሪ በእርግጥም የተሽከርካሪዉ ባለቤት መሆን አለመሆናቸዉን በመወሰን ረገድ አንድ ንብረት ከሻጩ ወደ ገዥዉ በህግ አግባብ ተላልፏል የሚባለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ የንብረት ባለቤትነት የሚተላለፍበትን ሁኔታ በአንቀጽ 1184 እና ተከታዮቹ ላይ ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ በአንቀጽ 1186 ላይ የተመለከተዉ ሲሆን፣ ይህ አንቀጽ የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት የሚተላለፍበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የሚመለከቱ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነዉ፣ አንድ ሰዉ የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ተላልፎለታል ማለት የሚቻለዉ ንብረቱን በእጁ ማድረጉ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት ባለቤትነት ከአንድ ወደ ሌላ ሰዉ ተላልፏል ሊባል የሚችልበት ሁኔታ በህግ በተለይ የተመለከተ እንደሆነ፣ ንብረቱ ተላልፏል ሊባል የሚችለዉ ስለጉዳዩ በሚደነግገዉ ህግ በተመለከተዉ መሠረት መሆኑ ሲረጋገጥ መሆኑን ነዉ፡፡

የተያዘዉ ጉዳይ ተሽከርካሪን የሚመለከት ነዉ፡፡ የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 4 የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለንብረት መታወቂያ (ሊብሬ) መያዝ ግዴታ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ተሽከርካሪን አስመልክቶ በተደረገ ዉል የተሽከርካሪዉ ባለንብረትነት ከሻጩ ወደ ገዥዉ ተላልፏል ወይም ገዥ በዉሉ መሠረት ተረክቧል ማለት የሚቻለዉ ከላይ በተጠቀሰዉ አዋጅ አንቀጽ 6 እና 7 ላይ በተዘረጋዉ ስርዓት መሠረት የመኪናዉ ባለቤት መሆኑ

ተረጋግጦ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በስሙ የተሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ አዋጁ ይህን ጥብቅ መስፈርት ሲያስቀምጥ የተለያዩ ምክንያቶችን ታሳቢ በማድረግ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ አንዱ አንድ ተሽከርካሪ ከአንዱ ወደ ሌላ የሚተላለፍበትን ጥብቅ የምዝገባ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ መስፈርት በማስቀመጥ የሦስተኛ ወገኖችን መብትና ጥቅም ለማስከበር እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ለተያዘዉ ክርክር መነሻ የሆነዉ ተሽከርካሪ በግዥ ዉል መሠረት ተላልፎልኛል በማለት ተጠሪ ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ባለሀብትነቱ ከላይ በተመለከተዉ አግባብ የተላለፈላቸዉ ስለመሆኑ ገልጸዉ አልተከራከሩም፤ ይልቁንም የተሽከርካሪዉ ስመ ሀብቱ በስር ተከሳሽ ወ/ሮ ዳግማዊት ጌታቸዉ ስም ያለ ስለመሆኑ ግራ ቀኝ የተማመኑበት ፍሬ ነገር መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ተጠሪ ላቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ምክንያት ያደረጉት የተሽከርካሪዉ ባለሀብት እኔ እንጂ የስር ተከሳሽ አይደለም የሚል ከመሆኑ አንፃር የአመልካች የመቃወም አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት ተቀባይነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ በመወሰን ረገድ መመርመር ያለበት ነጥብ፣ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ፣ በህግ አግባብ በተሽከርካሪዉ ላይ የባለቤትነት መብት ያገኙ መሆን አለመሆኑ እንጂ የግዥ ዉሉን ህጋዊነት አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ተሽከርካሪ ገዝቼ ባለሀብት ሆኛለሁ በማለት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ይህ የመቃወም አቤቱታቸዉ ተሽከርካሪዉን በዉሉ መሠረት ተረክበዉ እና ባለሀብትነትም በስማቸዉ መመዝገቡን በሚያሳይ ማስረጃ ባልተደገፈበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክርክር ከዉሉ ህጋዊነት አንፃር ብቻ በመመርመር የቀረበዉን የመቃወም አቤቱታ በመቀበል እግዱ ሊነሳ ይገባል በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የተሽከርካሪ ባለንብረትነት መብት ከአንዱ ወደ ሌላ ሊተላለፍ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከፍ ሲል በዝርዝር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 281065 በቀን 18/03/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 260954 በቀን 06/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል።

2. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ተሽከርካሪ ተከብሮ እንዲቆይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ የነበረዉ ትዕዛዝ ሊነሳ አይገባም ተብሏል።

3. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 14/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል።

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ.መ.ቁ.184447

ህዳር 21 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡- 1. አቶ መስፍን ጌታቸዉ
2. ወ/ሮ ሂሩት አድማስ } ጠበቃ - መሐመድ አወል አህመድ ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ መለሰ ግርማ
2. አቶ ሚኪያስ ግርማ } ጠበቃ - ስንታየሁ ባህሩ ቀርበዋል
3. አቶ ሐየሎም ግርማ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ይህ የዉርስ ሀብት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር ከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.239640 በ02/12/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ለማጣራት ግራ ቀኙ የሰው ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ታዞ በቀጠሮው ቀን አመልካቾች 1ኛና 2ኛ ምስክሮቻችን ስልካቸውን እየዘጉና እየተደበቁ ፤ማግኘትም ስላልቻልን ሌሎች ምትክ ምስክሮች እንዲቀርቡላቸው የጠየቁ ሲሆን፤ ተጠሪዎች በበኩላቸው የአመልካቾች ምስክሮች ያሉ በመሆኑ በሚኖሩበት ወረዳ በኩል ወይም እራሳቸው(ተጠሪዎች) ማቅረብ እንደሚችሉ አስተያየት በመስጠታቸው፣ ፍ/ቤቱም በአሁን ተጠሪዎች በኩል መጥሪያ እንዲደርሳቸው በማዘዙ መጥሪያውን ለአመልካች ምስክሮች እንዲያደረሱ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ይህን

ተከትሎ አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ የእኛን ምስክሮች የአሁን ተጠሪዎች እንዲያቀርቡ የታዘዘው ስነ ስርዓታዊ ባለመሆኑ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሻርላቸው ቢጠይቁም ፍ/ቤቱ አቤቱታዉን በመመርመር በሰጠዉ ብይን የስነ ስርዓት ግድፈት የለበትም በማለት በመወሰኑ እና ይህም ስህተት እንዲታረምላቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ብይንና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካቾች በ6/2/2012 ዓ.ም በተጻፈዉ የሰበር አቤቱታ፡ እነዚህ ምስክሮች በተጠሪዎች ተፅዕኖ ስር ያሉ በመሆኑና ትክክለኛ ፍትህም ማስጠት የማይችሉ በመሆኑ፤ በእኛ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ ትዕዛዙን በትዕዛዝ መበየን ሲችል፤የአመልካቾችን ምስክሮች መጥሪያ የሚያደርሰውና የሚያቀርበው አመልካቾች ሆነው ሳለ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.111 እንዲሁም ማስረጃችንን መለወጥ የሚከለከል አይደለም በማለት በሰበር መ/ቁ.45984 ተወስኖ እያለ ጥያቄያችን ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሻርልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ የአመልካቾች አቤቱታ ጊዜያዊ ትዕዛዝ እንጂ የመጨረሻ ፍርድ አይደለም፤የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.111 እና የሰበር ቅፅ.9 የመ/ቁ.45984 ምስክሮች ያለመጥሪያ ከቀረቡ እና ፍ/ቤትም ምስክር ለመቀየር በቂ ምክንያት እያለ ካለፈ እንጂ እንደ አመልካቾች ያለን ምስክር ያለበቂ ምክንያትና በስር ፍ/ቤት ባልተነሳ ምክንያት ምስክር ለመቀየር የሚቀርብ ጥያቄን አይደለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፤በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ የሚባልበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል። ከዚህ አንጻር የግራ ቀኙ ክርክር ሲታይ የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ ሁለት የሰዉ ምስክሮቻችን ስልካቸዉን እየዘጉና እየተደበቁን ልናገኛቸዉ ስላልቻልን፣ በእነርሱ ምትክ ሌሎች ምስክሮች እንድናቀርብ እንዲፈቀድልን የሚል አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን፤ የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጡት አስተያየት የአመልካቾች ምስክሮች እንዳሉ በመግለጽ፣ አመልካቾች ያለበቂ ምክንያት ምስክሮችን ለመቀየር ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም፤ ምስክሮቹ በወረዳዉ በኩል ወይም እኛ መጥሪያ እንያናደርስ እንዲታዘዝልን በማለት መጠየቃችንን ተከትሎ፤ የሥር ፍ/ቤት የተጠሪዎችን አስተያየት በመቀበል

ተጠሪዎች ለምስክሮቹ መጥሪያ እንዲያደርሱ ትዕዛዝ ሰጥቷል። የአሁን አመልካች ይህ ትዕዛዝ የሥነሥርዓት ጉድለት አለበት በማለት አቤቱታ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል።

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 [1] መሰረት ሕግ በሌላ አግባብ ካልደነገገ በስተቀር ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በፍትሐ ብሔር ፍ/ቤት በተወሰነበት የመጨረሻ ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማለት እንደሚችል ይደነግጋል። እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.320 [3] ሥር የተዘረዘሩት ጉዳዮች በተመለከተ ከሥረ ነገር ፍርድ በፊት ይግባኝ ማለት እንደማይቻልና ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ እነዚህን ነገሮች የቅሬታ ምክንያቶች በማድረግ ከሥረ ነገር ይግባኝ ጋር ማቅረብ እንደሚቻል ያስገነዝባል።

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የሥር ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ክሳቸዉ የጠቀሱአቸዉን ምስክሮች ቀይሮ በእነርሱ ፋንታ ሌሎች ምስክሮች ለማቅረብ በቂ ምክንያት የለም፣ ለምስክሮቹ በተጠሪዎች በኩል መጥሪያ ደርሷቸዉ እንዲቀርቡ በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ፣ እና የአሁን አመልካቾች ይህ ትዕዛዝ የስነሥርዓት ጉድለት አለበትና እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ መደረጉ፣ ይግባኝ የሚባልበት ጉዳይ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት አለበት። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል የተመለከተ ከመሆኑ አንጻር የሥር ፍ/ቤት አመልካቾች ምስክሮቻቸዉን ለመቀየርና በምትካቸዉ ሌሎች ምስክሮች ለማቅረብ ያቀረቡት ምክንያት በቂ አይደለም፣ ለምስክሮቹ የፍ/ቤቱ መጥሪያ በተጠሪዎች በኩል ይድረስ፣ ይህም ትዕዛዝ ደግሞ የሥነሥርዓት ጉድለት የለበትም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ፣ በዚህ ጉዳይ የመጨረሻ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም። ምክንያቱም የአመልካቾች ምስክሮች በተጠሪዎች ወይም በወረዳዉ አስተዳደር በኩል መጥሪያ ደርሷቸዉ፣ ምስክሮቹ ቀርበዉ በሕጉ አግባብ የሚያዉቁትን ጉዳይ መመስከር የሚችሉበት እድል ሊኖር ስለሚችል ነዉ። ከዚህም በላይ ምስክሮቹ ቀርበዉ ቃላቸዉን ከሰጡ በኋላ እና በሥረ ነገሩ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ፣ አመልካቾች የሥር ፍ/ቤት ምትክ ምስክሮች ለማቅረብ ያቀረብነዉን ጥያቄ በቂ ምክንያት የለዉም፣ ለምስክሮቹ የፍ/ቤቱ መጥሪያ በተጠሪዎች በኩል ይድረስ ማለቱ እና ይህም ትዕዛዝ የሥነሥርዓት ጉድለት የለዉም በማለት የሰጡት ብይን መብታችንን ጎድቶታል የሚሉ ከሆነ፣ በሥረ ነገሩ ላይ በሚሰጠዉ የመጨረሻ ፍርድ ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡ ከሆነ እነዚህን ምክንያቶችም ጨምሮ ቅሬታቸዉን ማቅረብ ይችላሉ። ስለሆነም የአሁን አመልካቾች በዚህ ጉዳይ ላይ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠዉ ብይን ላይ የይግባኝ ቅሬታ የሚቀርብበት የመጨረሻ ፍርድ ባልሆነበት የይግባኝ ማመልከቻ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረባቸዉ እና ፍ/ቤቱም ይህ ጉዳይ

በክርክሩ የመጨረሻ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ፣ የቀረበዉን ይግባኝ በማየት የሰጠዉ ትዕዛዝ የህግ መሰረት የለዉም።

ሲጠቃለል የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ብይን ላይ ይግባኝ የማይባልበት ሆኖ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ ይግባኝ የሚባልበት ጉዳይ አይደለም በማለት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.239640 በ02/12/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል።
2. አመልካቾች ያቀረቡት ቅሬታ ከመሰረቱም ከሥረ ነገር ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት ጉዳይ አይደለም ብለናል።
3. አመልካቾች በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ የሚሉ ከሆነ እነዚህን ምክንያቶች በሥረ ነገር ፍርድ ላይ ከሚያቀርቡት ቅሬታ ጋር ጨምሮ ከማቅረብ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል።
4. በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፤ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ.182136

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ገ/ማርያም ገ/እግዚአብሔር -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለምጸሐይ ገብሩ - ጠበቃ የሺዋስ ኢያሱ - ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የተጀመረዉ በትግራይ ክልል የሓየሎም ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.102019 በ21/9/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነዉ፡፡

የአሁን ተጠሪ በሥር ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ከአሁን አመልካች ጋር የነበራቸዉ ጋብቻ እንዲፈርስ፣ በጋራ ያፈራናቸዉ ንብረቶች እንድንካፈል በማለት ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ የአሁን ተጠሪ አሻሽለዉ ያቀረቡት ክስ የክስ ማሻሻል ዓላማን የሚቃረን ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልኝ፣ ከተጠሪ ጋር ጋብቻ የፈጸምን በ1992 ዓ.ም ሳይሆን በ1997 ዓ.ም ነዉ፣ የአሁን ተጠሪ ያልደከሙበትና ያልጣሩበት ሃብት ለመዉሰድ በማሰብ እዉነታ የሌለዉ ክስ ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሓየሎም ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት፣ የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ የሰነድ ማስረጃ በመመርመር የግራ ቀኙ ጋብቻ ከ11/6/2009 ዓ.ም ጀምሮ እንዲፈርስ፣ የጋራ ንብረቶች ናቸዉ ያላቸዉን እንዲካፈሉ እና የልጆች ቀለብ ወስኗል፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለትግራይ ክልል የሓወልቲ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች በበኩላቸዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ አመልካች በ27/7/2011 ዓ.ም በዋለዉ ቀጠሮ መቅረብ ባለመቻሉ

መዝገቡ የተዘጋ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ጠበቃ በቀጠሮዉ ቀን ያልቀረብኩት በሁለት ፍ/ቤቶች ቀጠሮ ስለነበረኝ ነዉ የሚል ምክንያት ያቀረቡ ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በበኩላቸዉ ባቀረቡት ክርክር የአመልካች ጠበቃ ያቀረቡት ምክንያት በቂ ስላልሆነ መዝገቡ ሊንቀሳቀስ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአመልካች ጠበቃ በቀጠሮ ቀርቶ መዝገቡ ሊዘጋ የቻለዉ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ ነበረኝ የሚል እንጂ ሌላ በቂ ምክንያት ስላላቀረቡ እና ይህ ምክንያት ደግሞ በቂ ሆኖ ስላላገኘነዉ የተዘጋዉ መዝገብ ሊከፈት አይገባዉም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በያዘዉ ቀጠሮ በችሎቱ ብቻ ሳይሆን አራት የተለያዩ መዝገቦች የነበሩ መሆኑ እየታወቀ መጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም የአመልካች ጠበቃ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ ነበረኝ እንጂ ሌላ በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ ምክንያቱም የሥር የሰበር ሰሚ ችሎት ሌላ ቀጠሮ መኖሩን ተቀብሎ እያለ ይህን ነባራዊ ሁኔታ፣ ከመከራከር መብትና የሕጉን ዓላማ አንጻር ከግንዛቤ ሳይገባ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል መዝገቡን በመዝጋት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩን ሰምቶ ዉሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አመልካች መዝገቡ በተዘጋበት ቀን ከሌላ ቦታ ሁለት መዝገብ ቀጠሮ ያለዉ መሆኑን ገለጾ እያለ ያከራከረዉ ምክንያት በቂ አይደለም የተባለበትን አግባብ ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ በ24/4/2012 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር በፍ/ቤት በ27/7/2011 ዓ.ም በነበረን ቀጠሮ አመልካች ራሳቸዉ የቀረቡ ሲሆኑ ጠበቃቸዉ ግን በቀኑ በነበረን ሶስት ቀጠሮዎች አልነበሩም፣ ስለዚህ የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረዉ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር አመልካች የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ ግራ ቀኙን ለመስማት በቀጠረዉ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ጠበቃ ከቀጠሮ በመቅረታቸዉ መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክርና የችሎቱ የትዕዛዝ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪ ካቀረቡት ክርክር መረዳት እንሚቻለዉ በተባለዉ ቀጠሮ አመልካች ራሳቸዉ እንደቀረቡና የአመልካች ጠበቃ በቀኑ በነበራቸዉ ሶስት ቀጠሮዎች ያልነበሩ መሆናቸዉን ገልጸዋል፡፡ የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ትዕዛዝ እንዳረጋገጠዉ አመልካች ጠበቃ በተያዘዉ ቀነ ቀጠሮ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ ነበረኝ በማለት የተጠቀሰዉን

ፍሬ ነገር ከተቀበለ በኋላ ይህ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፤ አመልካች በቀጠሮዉ የቀሩበትን ሌላ በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት ዉድቅ አድርጓል፡፡ ከክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ መረዳት እንደሚቻለዉ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ መኖሩ በቂ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.73 መሰረት በአንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰዉ ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነ ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነና ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፍል ያመነ እንደሆነ ከሳሹ በሌለበትም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነዉ ጉዳይ የፍርድ ዉሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡ ከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት ያሰናብተዋል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ደግሞ ለይግባኝ ጉዳይም ተፈጻሚነት እንዳለዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.32 [2] እና 74 [1] ድንጋጌ ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ለሰበር ጉዳይ የተለየ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ እስከሌለ ድረስ ይህ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ማለት ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የሕግ ድንጋጌ መሰረት ከሳሽ ክርክር በሚሰማበት ቀነ ቀጠሮ በመቅረቱ መዝገቡ የተዘጋ እንደሆነ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74 [1] መሰረት መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ እንደገና ተከፍቶ ነገሩ እንዲታይለት መጠየቅ እንደሚችል እና ከሳሹ በቀዳሚዉ ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረዉ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ የተረዳዉ እንደሆነ ስለ ኪሳራዉና ስለ ወጪዉ አከፋፈል ተስማሚ መስሎ የታየዉን ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ ነገሩ እንደገና እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠትና የሚሰማበትን ቀጠሮ መወሰን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን በዚህ ድንጋጌ "በቂ ሆኖ የሚገመት እክል" ምን እንደሆነ የሚጠቁም ነገር የለዉም፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ለመስማት በያዘዉ ቀነ ቀጠሮ ከችሎት ለመቅረት የቻለዉ የአመልካች ጠበቃ በቀጠሮዉ ቀን በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ ስለነበረዉ መሆኑን የችሎቱ የትዕዛዝ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች ጠበቃ በቀነ ቀጠሮዉ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ የነበረዉ መሆኑን አረጋግጦ ከተቀበለ በኋላ፣ ነገር ግን ይህ ምክንያት በቂ ሆኖ የሚገመት እክል አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የተዘጋዉ መዝገብ መከፈት የለበትም ማለቱን መረዳት ተችሏል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74 [2] ደንጋጌ መሰረት "በቂ ሆኖ የሚገመት እክል" ምን እንደሆነ የተመለከተ ባይሆንም አመልካች ቀጠሮ ለመቅረት የቻለዉ በምን ምክንያት እንደሆነ አጠቃላይ ሁኔታዉን መመርመር የሚያስፈልግ ሆኖ፣ አመልካች በራሱ ጉድለት ወይም ቸልተኛነት ቀጠሮዉን ሳይከታተል ቀርቶ ካልሆነ በስተቀር፣ ፍትሕ የማግኘትና የመከራከር መብት ከግምት በማስገባት አመልካችን የገጠመዉ እክል እንደ በቂ ምክንያት በመዉሰድ ለተጠሪ ተገቢ ኪሳራና ወጪ በማስከፈል፣ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲሰማ መድረጉ አግባብ ነዉ፡፡ በመሆኑም አመልካች ክርክሩን በጠበቃ ለማካሄድ ወስኖ በሕጉ አግባብ ተገቢዉን ዉክልና ሰጥቶ እያለ ጠበቃዉ ችሎት በሚሰጠዉ ቀነ ቀጠሮ ተገኝቶ አመልካችን ወክሎ ተገቢዉን ክርክር የማቅረብ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ጠበቃ የተለያዩ

ደንበኞች ሊኖሩት ስለሚችል ፍ/ቤት በሚሰጠዉ ቀነ ቀጠሮ በተቻለ መጠን ለደንበኞቹ ተገቢዉን የጥብቅና አገልግሎት መስጠት በሚያስችለዉ አግባብ አጀንዳዉን አስማምቶ ቀጠሮ እንዲያዝለት ለፍ/ቤቱ ማመልከት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም ሆኖ ቀጠሮ ተደራርቦበት በአንድ ጊዜ በተለያዩ ችሎቶች የሚቀርብበትን እድል በማዛባቱ ምክንያት የባለጉዳዩ መዝገብ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህጉ ድንጋጌ መሰረት ተዘግቶ እንደሆነ፣ አጠቃላይ የነገሩን ሁኔታ በመመርመር፣ የአመልካች የመከራከርና ፍትሕ የማግኘት መብት ታሳቢ በማድረግ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲሰማ ማድረጉ ተገቢ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የአሁን አመልካች ራሱ በችሎት መገኘት በተጠሪ የተነገረ ቢሆንም ጠበቃዉ በሌላ ፍ/ቤት ቀጠሮ ስለነበረዉና ባለመቅረቡ መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ የሥር የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተቀበለ እስከሆነ ድረስ፣ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.74 [2] መሰረት መዝገቡ የተዘጋዉ "በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን" የሚያስገነዝብ ሆኖ ሳለ፣ የሥር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህ እክል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት የተዘጋዉ መዝገብ ሊከፈት አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.102019 በ21/9/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የተዘጋዉ መዝገብ ሊከፍት አይገባም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ የአመልካች ጠበቃ ችሎቱ ክርክሩን ለመስማት በያዘዉ ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረዉ "በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት" ስለሆነ የተዘጋዉ መዝገብ ተከፍቶ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 [1] መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
4. የአሁን አመልካች በዚህ ምክንያት በተጠሪ ላይ ለደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ ብር 5000 [አምስት ሺህ] ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
5. ይህ ችሎት የካቲት 4 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 191402

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የማነ ግርማይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር ፡- ጠበቃ አውግቸው ክብረት ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. ቻይና ሲ ኢ ኤም ሲ ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ሊሚትድ ፡- ጠበቃ ሙሴጌታ በላይ ቀረቡ

2. ወጋገን ባንክ አ.ማ. ፡- ነ/ፈጅ በላይ ተህልቁ ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ 2ኛ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥሮች 220837 እና 228090 ያቀረባቸው ክሶች ተጣምረው የታዩ ሲሆን ይዘቱም 1ኛ ተጠሪ በወልቃይት ስኳር ፋብሪካ የሲቪል ወርክ ሥራዎች ለመገንባት ባወጣው ጨረታ አመልካች አሸናፊ በመሆን ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም የግንባታ ውል ተደርጓል፡፡ ለዚህም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ብር 20,800,000.00 እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ብር 28,801,383.62 ከ2ኛ ተጠሪ የተሠጠ በአመልካች ቀርቧል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ግንባታው ዘግይቷል በሚል ጥቅምት 17 ቀን 2011 ዓ/ም ውሉን በመሠረዝ 2ኛ ተጠሪ በዋስትናው መሠረት እንዲፈጽምለትም ጠይቋል፡፡ ግንባታው የዘገየው አመልካች ባለሀብት ላይ በደረሠ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያትና በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት በመሆኑ የሥምምነት ውል ማቋረጥ ተግባሩ ውድቅ እንዲደረግና የችሮታ ጊዜ እንዲሰጠኝ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የቅድመ ክፍያ ዋስትና እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፍል ትዕዛዝ እንዲሰጥ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ

የሠጠው መልስ ውሉ የተቋረጠው አመልካች በሥምምነቱ መሠረት ባለመፈጸሙ ነው፡፡ አመልካች ጥፋት ባይኖርበትም ውሉን የማቋረጥ በሕግ መብት አለን፡፡ ውሉ የችሮታ ጊዜን አይፈቅድም፡፡ ሁለቱም ዋስትናዎች ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈሉ በመሆናቸው በፍርድ ቤት ክርክር የሚቀርብባቸውና የሚታገዱ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች እግድ ካላሰጠ በስተቀር ክፍያውን ለ1ኛ ተጠሪ እንፈጽማለን ብሏል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሉ የግንባታ ውል በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 3035 መሠረት አሠሪው ተቋራጩ አንዳችም ጥፋት ባያደርግም እንኳን የፈረመውን ውል ማፍረስ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ለሥራ ተቋራጩ የሠጠው መብት ሌሎች የይገባኛል መብቶች/ጥቅሞች ካሉ ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ ውሉን በተናጠል ማፍረስ ስለሚፈቅድ ውሉ መፍረሱ ተገቢ ነው፡፡ በፈረሰ ውል የችሮታ ጊዜ ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ዋስትናዎቹም በፍ/ሕ/ቁ. 1925(1) መሠረት ያለ ቅድመ ሁኔታ የተደረጉ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ከመክፈል የሚያስቀር የሕግ ሆነ የውል ግዴታ የለም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ባደረግነው የግንባታ ውል መሠረት ዝቀተኛ አፈጻጸም ነው ያለን ወይስ አይደለም የሚለውን እና ውሉ ቢቋረጥ እንኳን የምንጠይቀውን የተለያዩ ክፍያዎች መጠየቅ የምንችለው በሥምምነታችን መሠረት በግልግል ጉባዔ ሆኖ እያለ የግንባታ ውሉን አስመልክቶ በፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ጉዳዩ ለግልግል ቀርቦ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስም በዋስትናው የተያዘው ብር 48,300,000.00 ገንዘብ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ ሊሠጥ ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ በውላቸው አለመግባባት የሚፈታው በግልግል ጉባዔ እንደሆነ ተመልክቶ እያለ ይህ ታልፎ ውሉ ተቋርጧል፤ በዋስትና የተያዘው ገንዘብም ለ1ኛ ተጠሪ ይከፈል መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ 1ኛ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የአመልካች የሠበር አቤቱታ በዋነኛነት መሠረት ያደረገው እግድ እንዲሰጥ ሲሆን የእግድ ጥያቄ የሚቀርበው ዋና ክርክር ወይም ክስ ኖሮ ክርክሩ በፍርድ ቤት እስኪወሰን ድረስ ለጊዜው የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፡፡ ዋና ክርክር በሌለበት ገና ለገና ጉዳዩ በግልግል እስኪታይ ድረስ እግድ ይሰጥልኝ ብሎ ዳኝነት መጠየቅ በሕግ ያልተፈቀደ ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤትም ያልተነሳ ክርክር ነው፡፡ ክሱን ለግልግል ጉባዔ ማቅረብ እየቻለና የእግድ ጥያቄውን በዚሁ ማቅረብ እየተቻለ ሆነ ብሎ ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ክስ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት የተከራከረን ሲሆን አመልካች ፍርድ ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህም በውሉ መሠረት ለግልግል ጉባዔ ማቅረብ የሚችለውን መብቱን እንደተወ ይቆጠራል፡፡ ማንም ሠው በጥፋቱ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ውሉን ማቋረጥ መብት አለን፡፡ ዋስትናውም ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈል በመሆኑ እግድ ሊቀርብበት አይገባም በማለት

ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ለሠበር አቤቱታው መልስ ባያቀርብም በዚህ ችሎት በነበረው የእግድ ክርክር ላይ ቀርቦ የዋስትናው ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፈል እግድ ስለተሠጠበት እንጂ አንከፍልም አላልንም በማለት ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ፍርድ ቤት የግንባታ ውሉን አስመልክቶ ክርክር ለማድረግ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የዋስትና ገንዘቡ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፈል እግድ እንዲሰጥ ዳኝነት መቅረቡ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከለተ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በወልቃይት ስኳር ፋብሪካ የሲቪል ወርክ ሥራዎች ለመገንባት ባወጣው ጨረታ አመልካች አሸናፊ በመሆን ሚያዚያ 26 ቀን 2008 ዓ/ም የግንባታ ውል ተደርጓል፡፡ ለዚህም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ብር 20,800,000.00 እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ብር 28,801,383.62 ከ2ኛ ተጠሪ የተሠጠ በአመልካች ቀርቧል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ግንባታው ዘግይቷል በሚል ጥቅምት 17 ቀን 2011 ዓ/ም ውሉን በመሠረዝ 2ኛ ተጠሪ በዋስትናው መሠረት እንዲፈጽምለትም ጠይቋል፡፡ ግንባታው የዘገየው አመልካች ባለሀብት ላይ በደረሠ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያትና በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት በመሆኑ የሥምምነት ውል ማቋረጥ ተግባሩ ውድቅ እንዲደረግና የችሮታ ጊዜ እንዲሰጠኝ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የቅድመ ክፍያ ዋስትና እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፍል ትዕዛዝ እንዲሰጥ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ ውሉ የተቋረጠው አመልካች በሥምምነቱ መሠረት ባለመፈጸሙ ነው፡፡ አመልካች ጥፋት ባይኖርበትም ውሉን የማቋረጥ በሕግ መብት አለን፡፡ ውሉ የችሮታ ጊዜን አይፈቅድም፡፡ ሁለቱም ዋስትናዎች ያለ ቅድመ ሁኔታ የሚከፈሉ በመሆናቸው በፍርድ ቤት ክርክር የሚቀርብባቸውና የሚታገዱ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪም አመልካች እግድ ካላሰጠ በስተቀር ክፍያውን ለ1ኛ ተጠሪ እንፈጽማለን ብሏል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ የግንባታ ውል በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 3035 መሠረት አሠሪው ተቋራጩ አንዳችም ጥፋት ባያደርግም እንኳን የፈረመውን ውል ማፍረስ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ለሥራ ተቋራጩ የሠጠው መብት ሌሎች የይገባኛል መብቶች/ጥቅሞች ካሉ ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ ውሉን በተናጠል ማፍረስ ስለሚፈቅድ ውሉ መፍረሱ ተገቢ ነው፡፡ በፈረሰ ውል የችሮታ ጊዜ ሊጠየቅ አይችልም፡፡ ዋስትናዎቹም በፍ/ሕ/ቁ. 1925(1) መሠረት ያለ ቅድመ ሁኔታ የተደረጉ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ከመክፈል የሚያስቀር የሕግ ሆነ የውል ግዴታ የለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርገዋል፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ የተመሠረተው በግንባታው ውል መሠረት የሚጠየቁ ክፍያዎችን ለመጠየቅ በውላችን መሠረት አለመግባባት የሚፈታው በግልግል ጉባዔ በመሆኑ ግንባታ ውሉን አስመልክቶ

የተሠጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም እንዲሁም ክሱን ለግልግል ጉባዔ እስክናቀርብ ድረስ 2ኛ ተጠሪ የቅድመ ክፍያ ዋስትና እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብ 48,300,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፍል ታግዶ ሊቆይ ይገባል የሚል ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ ክሱን ለግልግል ጉባዔ ማቅረብ እየቻለና የእግድ ጥያቄውን በዚሁ ማቅረብ እየተቻለ ሆነ ብሎ ሥልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ክስ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም በማለት የተከራከርን ሲሆን አመልካች ፍርድ ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት ክርክር አቅርቧል፡፡ ይህም በውሉ መሠረት ለግልግል ጉባዔ ማቅረብ የሚችለውን መብቱን እንደተወ ይቆጠራል፡፡ ማንም ሠው በጥፋቱ ተጠቃሚ ሲሆን አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ሆነ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ችሎት ባደረጉት ክርክር የግንባታ ውሉ አስመልክቶ ያለመግባባት ካለ የሚፈታው በግልግል ጉባዔ ስለመሆኑ መስማማታቸውን ግራ ቀኙ ተማምነዋል፡፡ የዳኝነት ሥልጣን በመርሕ ደረጃ የሚወሰነው በሕግ ቢሆንም ተዋዋዮች በሕግ በተፈቀደው አግባብ አለመግባባት የሚታይበትን የዳኝነት አካል የመምረጥ መብት አላቸው፡፡ ሰዎች በመካከላቸዉ ከፈጠሩት ሕጋዊ ተግባራት በመነጨ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለወደፊት በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን አለመግባባት ወይም ተፈጥሮ ያለዉን አለመግባባት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጭ በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም መስማማት እንደሚችሉ የፍ/ሕ/ቁ. 3328 እና የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(1) ያስረዳሉ፡፡ የግልግል ዳኝነት ሥምምነት በጽሁፍ በተዋዋሉት በዋናዉ ዉላቸዉ በሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ቃል (Arbitration Clause) ወይም አስቀድሞ በመካከላቸዉ ተከስቶ ያለዉን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ራሱን በቻለ የጽሁፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነት (Arbitral Submission) ሊመለከት ይቻላል፡፡

ተዋዋዮች በውል አለመግባባቱ የሚታይበትን ሥርዓት ከወሰኑ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ አስገዳጅ በመሆኑ በወሰኑት የዳኝነት አካል የመዳኘት ግዴታ ይጥልባቸዋል፡፡ በግልግል ዳኝነት ሊታይ የሚገባው ክስ ፍርድ ቤት ከቀረበ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለሌው ስለመሆኑ ውላቸውን መሠረት በማድረግ ተከራካሪዎች ወይም ፍርድ ቤቱም በግልግል እንዲታይ ሥምምነት መኖሩን ካወቀ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9(2) መሠረት በማናቸውም የክርክሩ ደረጃ ሊያነሳው ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የማይኖረው በሕግ መሠረት ይሁን በተዋዋዮች የግልግል ዳኝነት ጉባዔን መምረጥ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ተዋዋዮች በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ሊታይ የሚገባን ጉዳይ ፍርድ ቤት ካቀረቡ በኋላ መልሰው ጉዳዩን ለግልግል ጉባዔ ማቅረብ የማይችሉት በሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ሥምምነቶች (Bilateral Investment Treaties) ሁለት አማራጮች የያዙ ድንጋጌዎች (fork in the road provisions) ሲኖሩ ነው፡፡ መርሑ ተዋዋዮች አለመግባባትን በዓለም አቀፍ የግልግል ጉባዔ ሆነ በሀገሪቱ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሥምምነት ሲያደርጉ እና በመጀመሪያ በፍርድ ቤት ከታየ ሥምምነታቸውን መሠረት አድርገው ለሁለተኛ ጊዜ በዓለም አቀፍ

የግልግል ጉባዔ እንዲታይ ክስ ከማቅረብ የሚከለክል ነው። ይሕም በሥምምነቱ ጉዳዩ በሀገሪቱ ፍርድ ቤት ሆነ በግልግል ጉባዔ እንዲታይ አማራጭ የሚሰጥ መሆኑን መሠረት ያደረገ ነው። በዚህ አግባብ አማራጭ ሥምምነት ከሌለ ጉዳዮች ከፍርድ ቤት ውጭ እንዲታዩ ካስፈለገበት ዓላማ አንዱ የፍርድ ሂደት ቅልጥፍና (efficiency) ለመጨመር በመሆኑ ተዋዋዮች ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ እንዲታይ ከተስማሙ በኋላ ሊተው እንደሚችል መብት (waivable right) ተቆጥሮ ክሱን በፍርድ ቤት ካቀረቡት ለግልግል ጉባዔ የማቅረብ መብታቸውን እንደተውት የሚቆጠርና ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የሚሰጠው አይደለም። ሥለሆነም ጉዳያቸው በግልግል ዳኝነት ያደረጉትን የፅሑፍ ስምምነት በተመሣሣይ የፅሁፍ ምምነት አድርገው እስካላሻሻሉት ድረስ የዳኝነት ሥልጣን በተከራካሪዎች የክርክር አቀራረብ ሆነ ክርክሩ በደረሰበት ደረጃ ምክንያት የሚወሰን አይደለም። በግንባታ ውል አለመግባባት ላይ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያለው የግልግል ጉባዔ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የግንባታ ውል ማቋረጥ ተግባር ውድቅ ተደርጎ ውሉን የሚፈጽምበት የችሮታ ጊዜ እንዲሰጠው የጠየቀውን ዳኝነት በሥረ-ነገሩ አከራክረው መወሰናቸው ሥልጣን ሳይኖራቸው የተሠጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች በሠበር አቤቱታው ለግልግል ጉባዔ የሚገቡንን ክፍያዎች በተመለከተ ክስ እስከምናቀርብ ድረስ ዋስትናዎች እንዳይከፈሉ ታግዶ እንዲቆይ ሊደረግ ይገባል ያለ በመሆኑ ለክርክሩ አወሳሰን ዋናው ጭብጥ ክስ ባልቀረበበት ሁኔታ የእግድ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላልን? ዋስትናዎቹ ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈሉ መሆናቸው ሲታይ እግድ ሊሰጥባቸው ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ የሚከራከረው የእግድ ጥያቄ የሚቀርበው ዋና ክርክር ወይም ክስ ኖሮ ክርክሩ በፍርድ ቤት እስኪወሰን ድረስ ለጊዜው የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው። ዋና ክርክር በሌለበት ገና ለገና ጉዳዩ በግልግል እስኪታይ ድረስ እግድ ይሰጥልኝ ብሎ ዳኝነት መጠየቅ በሕግ ያልተፈቀደ ነው በማለት ነው።

እግድ በሠው የንብረት መብት አጠቃቀም ላይ ገደብ የሚፈጥር ነው። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 40(1) ላይ ጥበቃ የተደረገለት ንብረት መብት ላይ ገደብ ለማድረግ ደግሞ በሕግ በግልጽ በተመለከተ፣ ውስን ጉዳይና አፈጻጸሙም መብቱን መልሶ የመውሰድ ያህል ውጤት በማይፈጥር ሁኔታ ውስጥ ብቻ ሊሆን ይገባል የሚለው ስለሠብዓዊ መብት ጥበቃ የተደረጉ የሥምምነት ድንጋጌዎች ሆነ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀረጸ የሕግ መርሕ ነው። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 151 መሠረት ከፍርድ በፊት ንብረት ተከብሮ እንዲቆይ (attachment) የሚደረግበትን ሥርዓትና ሁኔታ የሚመለከተው ሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 መሠረት ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ወይም ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ንብረቱ እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን ወይም እንዳይበላሽ፣ ለሌላ ሰዉ ተላልፎ እንዳይሰጥ፣ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይዛወር ወይም እንዳይባክን የእግድ ትዕዛዝ የተጠየቀው ለጥያቄው መሠረት የሆነው ክስ

ቀርቦ ከሆነ እግድ መሰጠቱ የተከሳሹ ወገን የንብረት መብት አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በመረዳት በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነው፡፡

የእግድ ትዕዛዝ በመርሕ ደረጃ የቀረበ ክስን መሠረት ያደረገ እና በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ በተመለከቱት መስፈርቶች የሚሰጥ ነው፡፡ ዓላማው ደግሞ ክሱ ያለ ውጤት እንዳይቀርና ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜም የሚፈጸምበት ንብረት እንዲኖርና ዜጎች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉበትን ዕድል የሚፈጥርና በሂደቱም ፍርድ ቤቶች ላይ ያላቸውን እምነት የሚጨምር ነው፡፡ በመሆኑም ሠዎች ክስ ከማቅረባቸው በፊት ነገር ግን በክስ ዝግጅት ላይ እያሉ ተከሳሽ የሚሆነው ወገን ጉዳዩን በመረዳት ክስ ሲቀርብ ክሱ ውጤት እንዳይኖረው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154(ለ) እንደተመለከተው ተግባሮችን እየፈጸመ ከሆነ፤ ተግባሩን አለመከላከል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተቀረጸበትን ዓላማ እንዳይሳካ ያደርገዋል፡፡ ነገር ግን እግዱ እንዲሰጥ የተጠየቀው ክስ ሳይቀርብ ከሆነ ተከሳሽ የሚሆነው ወገን ላይ ያልተገባ የመብት ገደብ እንዳይደረግበት፤ ጊዜያዊ እግድ የሚጠይቀው ወገን ክስ ለማቅረብ ዝግጅት ላይ እንዳለ፣ የክስ ዝግጅቱ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈለገበትን ምክንያት፣ ክሱ እስኪቀርብ ድረስ የእግድ ትዕዛዙ ባይሰጥ የሚያስከትለው ጉዳት ማሳየት ያለበት ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክሱን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ምክንያታዊ ጊዜ ድረስ ብቻ በጊዜ ገደብ የተገደበ የእግድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

አመልካች እንዲሰጥ የጠየቀው የዋስትና ክፍያ የእግድ ትዕዛዝን እንደተመለከትነው በግልግል ጉባዔ ክፍያ እንዲከፈለው የሚያቀርበው ክስ ካለ ለምን እስካሁን እንዳላቀረበ፣ ክስ ለማቅረብ እያደረገ ያለው ዝግጅትና የክስ ዝግጅቱ በዚህ ጊዜ ሂደት ሁሉ ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት ላይ ክርክር ያላቀረበና ያላስረዳ በመሆኑ የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ያቀረበው ጥያቄ የሕጉን መስፈርት ያላሟላ ስለሆነ አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የእግድ ትእዛዝ እንዲሰጠው የሚጠይቀው ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈል የዋስትና ክፍያን (irrevocable and unconditional bank bond guarantee) ነው፡፡ የገንዘብ ግዴታ/ዋስትና ሠነድ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 2(20) ጨምሮ በተለያዩ ሕጎች የፋይናንስ ቃል ኪዳን ወይም የፋይናንስ ግዴታን ለመፈጸም የሚሰጥ ወይም የሚያዝ ማንኛውም ሠነድ ሲሆን የግምጃ ቤት ሠነድን፣ የተስፋ ሠነድን እና ቦንድን ይጨምራል ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ ዋስትናው የተሠጠው ያለቅድመ ሁኔታ በመሆኑ የሚፈጸመውም በውሉ አግባብ ያለ ማናቸውም ቅድመ ሁኔታ መሆን ይገባዋል፡፡ ያለቅድመ ሁኔታ የሚከፈለን ዋስትና ክስ ስለሚቀርብ የሚታገድ ከሆነ የውሉን ባሕሪ የሚቀይረው ስለሚሆን ሕጉ ሆነ ተዋዋዮች ያሰቡትን ዓላማ ማሳካት አይችልም፡፡ ሥለሆነም ያለቅድመ ሁኔታ ለመክፈል በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የተገባውን የዋስትና ግዴታ ውል 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይከፍል እንዲታገድለት ያቀረበው ጥያቄ ሕጋዊ ባለመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ጥያቄውን ውድቅ ማድረጋቸው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 186987 የካቲት 13 ቀን 2012 ዓ/ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 228090 ሕዳር 16 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች የግንባታ ውል ማቋረጥ ተግባር ውድቅ ተደርጎ ውሉን የሚፈጽምበት የችሮታ ጊዜ እንዲሰጠው የጠየቀውን ዳኝነት በሥረ-ነገሩ መወሰኑ ሥልጣን ሳይኖራቸው የተሠጠ በመሆኑ ተሽሯል፡፡

3. የዋስትና ክፍያ ሊታገድ አይገባም ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- የካቲት 20 እና ሚያዚያ 08 ቀን 2012 ዓ/ም የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

*ሠ/ኃ*

የሰ/መ/ቁ. 193312

የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ኑረዲን ከድር

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች- 1. አቶ ጉዑሽ ካሳ

2. አቶ ዳንኤል ጸጋዬ

ተጠሪ- አቶ ሲሳይ ታረቀኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ አንድ ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ሊባል የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክሯል፡፡

የተጠሪ ክስ ይዘትም ተከሳሾች ባለአክሲዮኖች የሆኑበት ጂድጂ የኮንስትራክሽን ስራዎች ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የሚባል ኩባኒያ በህዳሴ ግድብ ዉስጥ የምንጣሮ ስራ ለመስራት ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር ዉል የፈጸመ ሲሆን ከሳሽ እና ሌሎች ጓደኞቼ ደግሞ የምንጣሮ ስራዉን ለመስራት ከኩባኒያዉ የንዑስ ተቋራጭነት ዉል ፈጽመን ስራዉን የሰራን ቢሆንም ኩባኒያዉ የሰራንበትን ገንዘብ ሊከፍለን ፍቃደኛ ባለመሆኑ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበን ብር 21,362,40.00 ከታህሳስ 21 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ ይሁንና ኩባኒያዉ በዉሳኔዉ መሠረት ገንዘቡን ባለመክፈሉ የአፈፃፀም ክስ ያቀረብን ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ (1ኛ አመልካች) ኩባኒያዉ ምንም ዓይነት ገንዘብ የሌለዉ እና በምንጣሮ ስራዉ የተከፈለዉ ገንዘብ ያለመኖሩን ለፍርድ ቤቱ ገልጸዋል፡፡ ይሁንና ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ኩባኒያዉ ብር 22,408,085 የተከፈለዉ መሆኑንና ለተከሳሾችም ከ02/08/2006 ዓ.ም እስከ 19/10/2007 ዓ.ም ባለዉ ጊዜ ዉስጥ በአጠቃላይ ብር 16,420,383.00 ለተከሳሾች የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተከሳሾች የኩባኒያዉን ትርፍ የተከፋፈሉት በንግድ ህጉ አግባብ ኩባኒያዉ ትርፍ ማግኘቱ በኦዲተር ሳይረጋገጥ መሆኑ

ክፍፍሉን ህገ ወጥ የሚያደርገዉ ሲሆን ተከሳሾች ይህን በማድረግ ከሳሽ በፍርድ ባገኘሁት መብት እንዳልጠቀም ምክንያት በመሆናቸዉ ወለዱን ጨምሮ ከተወሰነዉ ብር 2,811,436.48 ዉስጥ የእኔን ድርሻ ብር 702,859.12 ክሱ ከቀረበበት ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካቾች ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማስቀደም የተለያዩ የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርበዉ የተከራከሩ ሲሆን፣ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በሚል ላቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ መሠረት ያደረጉትም ከሳሽ ከሌሎች ከሳሾች ጋር አብሮ በመሆን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 161772 በጂዲጂ የኮንስትራክሽን ስራዎች ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ላይ ያቀረቡት ክስ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠዉ በመሆኑ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ዳኝነት ማቅረብ አይችልም የሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ከሳሽ ከሌሎች ጋር በመሆን ክስ መስርተዉ ከኩባኒያዉ ጋር ባደረጉት የንዑስ ኮንትራት ዉል መሠረት ብር 2136240.00 እንዲከፈላቸዉ ተወስኗል፤ ፍርዱ ባለመፈጸሙ ምክንያት በአፈ/መ/ቁጥር 205193 አቅርበዉ ከሳሾች የአፈፃፀም ተከሳሽን ንብረት ወይም ገንዘብ አጣርተዉ ሲያቀርቡ አፈፃፀሙ የሚቀጥል መሆኑን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መዝጋቱ መረጋገጡን፤ ይህ ከሆነ በኋላ የኩባኒያዉ ወራሾች በሆኑት ተከሳሾች ላይ ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 5 መሠረት በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ተጠሪ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ቀደም ሲል በመ/ቁጥር 161772 በሆነዉ መዝገብ ጂዲጂ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ላቀረቡት ክስ ዉልን መሠረት ያደረገዉ ሲሆን በመ/ቁጥር 210891 በአሁን አመልካቾች ላይ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ደግሞ አመልካቾች የማህበሩን ገንዘብ ወደ እራሳቸዉ በማዛወራቸዉ የተወሰነላቸዉ ገንዘብ እንዳይፈጸምላቸዉ በማድረግ ጉዳት አድርሰዋል የሚል ያላግባብ መበልጸግን የሚመለከት በመሆኑ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ለማለት አይቻልም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች በጠበቃቸዉ አማካይነት ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም አዘጋጅተዉ ባቀረቡት አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ የአቤቱታቸዉ መሠረታዊ ይዘትም በአጭሩ የአሁን ተጠሪ አስቀድመዉ መርጠዉ እና ወስነዉ አመልካቾችን መክሰስ ሲችሉ ሆን ብለዉ ትተዉ ጂዲጂ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ላይ በመ/ቁጥር 161770 ላይ ዳኝነት ጠይቀዉ ተወስኖላቸዉ የኩባኒያዉን ንብረት ባገኙ ጊዜ መዝገቡን ማንቀሳቀስ እንዲችሉ መብት ተጠብቆላቸዉ

እያለ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በድጋሚ የቀረበ ሆኖ እያለ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በሚል የሰጠዉ ዉሳኔ ክስ በድጋሚ እንዳይቀርብ የሚከለክለዉን የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን ዓይነተኛ ዓላማ ያገናዘበ አይደለም የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም ተጠሪ ያቀረቡት የመጀመሪያ መቃወሚያ ተቀባይነት የማግኘቱን አግባብነት ከፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 5 አንፃር ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገላቸዉ ጥሪ መሠረት ህዳር 23 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረቡት ሁለቱ ክሶች የተለያዩ በመሆናቸዉ ክሱ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በማለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አለመሆኑን ጠቅሰዉ ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የመልስ መልስ አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ጂዲጂ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ላይ ባቀረቡት ክስ ከማህበሩ ጋር ባደረጉት የምንጣሮ ስራ ዉል መሠረት ለሰሩት ስራ ያልተከፈላቸዉ ገንዘብ መኖሩን ጠቅሰዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን ተከትሎ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 15ኛ ፍትሐብሔር ችሎት ጉዳዩን በመ/ቁጥር 161772 ላይ አስተናግዶ ከታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ብር 2136240.00 እንዲከፈላቸዉ መወሰኑንና ማህበሩ እንደ ፍርዱ ባለመፈጸሙ ምክንያትም የአፈፃፀም ክስ ቀርቦበት ማህበሩ ገንዘብ እንደሌለዉ በመረጋገጡ ምክንያት ተጠሪን ጨምሮ በፍርዱ መብት ያገኙት ሌሎች ሰዎች ማህበሩ ገንዘብ ሲያገኝ የማንቀሳቀስ መብታቸዉ ተጠብቆ የአፈፃፀም መዝገቡ ለጊዜዉ እንዲዘጋ ስለመደረጉ የግራ ቀኝ ክርክር እና የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ ተጠሪ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነዉ ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት አመልካቾች የጂዲጂ ኃላ/የተወ/የግል ማህበር ባለአክሲዮኖች በተለይም 1ኛ አመልካች የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በመሆን የማህበሩን ስራ ባልተገባ መንገድ በመምራት ማህበሩ ትርፍ ማግኘቱ ሳይረጋገጥ ለማህበሩ የተከፈለዉን ገንዘብ የንግድ ህጉ ከሚፈቅደዉ ዉጪ ያላግባብ ተከፋፍለዉ ማህበሩ ገንዘብ እንዳይኖረዉ በማድረግ ተጠሪ በማህበሩ ላይ ያስፈረደዉን ገንዘብ እንዳያገኝ ምክንያት መሆናቸዉን ስለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንግዲህ የተጠሪ ክስ ይዘት ይህ ከሆነ ቀደም ሲል በማህበሩ ላይ በቀረበዉ ክስ መነሻነት የተሰጠ ዉሳኔ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረበዉን ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ የሚያስብለዉ መሆን ያለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ መሠረታዊ ጭብጥ ይሆናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሃሳቦች ዉስጥ አንዱ የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች (Res judicata) የሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን አንቀጽ 5 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 5 ድንጋጌ መሠረት ማንኛዉም ፍርድ ቤት ወይም በህግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነዉ ክርክር ሥረ ነገርና የተያዘዉ ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪ መብት ያገኙት 3ኛ ወገኖች በዚያዉ ነገር ላይ ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸዉም ዓይነት ሌላ ክርክር ሊቀርብባቸዉ አይችልም፡፡ አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነዉ ለማለት መረጋገጥ ካለባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበዉ ክስም ላይ በቀጥታ የፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነዉ መቅረባቸዉ፣ ቀደም ሲል የነበረዉን ክርክር አሁን በክርክር ተሳታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸዉ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮችም ቀደም ሲል በተካሄደዉ ሙግት የመጨረሻ ዉሳኔ ያረፈባቸዉ መሆኑን ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 28522፣ 36780 እና በሌሎች መዛግብት ላይ የሰጣቸዉ የህግ ትርጉሞችም ይህንኑ የሚያስገነዝቡ ናቸዉ፡፡ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለዉ ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያዉ ክርክር ላይ በአንደኛዉ ወገን ተጠይቆ በሌላኛዉ ወገን የተካደ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተካደ እና በዚህ ጉዳይ ላይም ዉሳኔ የተሰጠበት ወይም ሊሰጥበት ይገባ የነበረ መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ አዲስ በቀረበዉ ክስ መሠረት በጭብጥነት ተይዞ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ በሌላ መዝገብ ላይ በጭብጥነት ተይዞ እልባት የተሰጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ ምንም እንኳ በቀደመዉ ክስ ለተጠየቀዉ ዳኝነት ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ አዲስ ከቀረበዉ ክስ ጋር የተለያየ ቢሆንም አዲስ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ በጭብጥነት ተይዞ መጣራት የሚገባዉ ጭብጥ በቀደመዉ ክርክር እልባት የተሰጠበት መሆኑ ከተረጋገጠ አዲስ የቀረበዉ ክስ ድጋሚ የቀረበ (resjudicata) ነዉ የማይባልበት ምክንያት የለም፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ተጠሪ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን ቀደም ሲል በማህበሩ ላቀረቡት ክስ መሠረት ያደረጉት በመካከላቸዉ የተደረገዉን የምንጣሮ ስራ ዉል ሲሆን በክሱ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ማህበሩ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ በመወሰን ረገድ በጭብጥነት የሚያዘዉ ወይም በጭብጥነት ተይዞ ሊሆን የሚችለዉ በመካከላቸዉ የምንጣሮ ስራ ዉል ግንኙነት መኖር ያለመኖሩ እና ዉሉ መኖሩ ካልተካደ ወይም መኖሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ ማህበሩ በዉሉ መሠረት ገንዘቡን የማይከፍልበት ህጋዊ ምክንያት መኖር ያለመኖሩ ነዉ፡፡ በአንፃሩ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነዉ ጉዳይ ላይ ግን ተከሳሾች የአሁን አመልካቾች እንጂ ማህበሩ (ማህበሩ ምንም እንኳን በአመልካቾች የተቋቋመ ቢሆንም ራሱን

የቻለ ህለረዉና ያለዉ መሆኑን ልብ ይሏል) አይደለም፤ አመልካቾች ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግም በፍርድ ቤቱ የሚያዘዉ ጭብጥ አመልካቾች ለማህበሩ መክፈል የነበረበትን ገንዘብ ከህግ አግባብ ዉጪ ተከፋፍለዉ በዚህም ምክንያት ማህበሩ ገቢ እንዲያጣ አድርገዋል? ወይስ አላደረጉም? ድርጊቱን መፈጸማቸዉ ከተረጋገጠ ይህ ድርጊታቸዉ ተጠሪ በማህበሩ ላይ ያስወሰነዉን ገንዘብ እንዳያገኝ ምክንያት ሆኗል ወይ? አልሆነም? የሚሉ እና ተያያዥ ጭብጦች እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረበዉ ክስ እና በቀደመዉ መዝገብ ላይ በሚያዙ የክርክር ጭብጦች መካከል ልዩነት መኖሩን ነዉ፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን ክስ መሠረት በማድረግ ከላይ በተመለከተዉ መልኩ የሚያዙ ከጭብጦች በቀደመዉ ክርክር በጭብጥነት አልተያዙም፤ መያዝ የሚገባቸዉ ጭብጦችም አይደሉም፡፡ በመዝገብ ቁጥር 161772 ላይ በቀረበዉ ክስ መነሻነት ለተሰጠ ዉሳኔ ምክንያት የሆነዉ ዉል ሲሆን፣ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ለተጠየቀዉ ዳኝነት ምክንያት የሆነዉ ከዉል ዉጪ ኃላፊነትን የሚመለከት መሆኑ ሲታይ በሁለቱ መዝገቦች ላይ የቀረቡት ክሶች የተለያዩ የክስ ምክንያቶችን መሠረት ያደረጉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

በአጠቃላይ በመ/ቁጥር 161772 ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ተጠሪ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን ክስ እንዳያቀርብ የሚከለክል ባለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የተጠሪ ክስ በድጋሚ የቀረበ አይደለም በሚል ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር፣ የሰጠዉ ዉሳኔ በሁለቱ መዝገቦች ላይ በቀረቡት ክሶች መካከል ያለዉን መሠረታዊ ልዩነት እና ባህሪ ክስ በድጋሚ ቀርቧል ለማለት የሚቻልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 5 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የተሰጠ ትክክለኛ ዉሳኔ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 178204 በቀን 28/07/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ/መ/ቁ.186816

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ታንጉት ዲበኩሉ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ይታያል ዲበኩሉ

2. ወ/ሮ የወጌ በልስቲ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር መዝገቡ የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ ዓለም ወረዳ በሚገኘው ይዞታዬ ላይ ያለን የባህር ዛፍ አትክልት ተጠሪዎች ቆርጠው ስለወሰዱ ግምቱን ብር 100,000.00 እንዲከፍሉኝ የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ የአመልካችን ባህር ዛፍ ቆርጠን ጉዳት ያላደረስን በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በአማራ ክልል የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00749 ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ላይ ለደረሠው የንብረት ጥቅም ጉዳት ተጠሪዎች ብር 15,000.00 እንዲከፍሉ ሠኔ 28 ቀን 2010 ዓ/ም ወስኗል፡፡ አመልካች በጉዳት መጠኑ ላይ ባለመስማማት ይግባኝ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በመዝገብ ቁጥር 73226 ሕዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ የደረሠው ጉዳት ግራ ቀኙ በመረጧቸው ገለልተኛ ሽማግሌዎች እንዲገመትና ቀድሞ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በመመዘን በጉዳዩ ላይ እንደገና ውሳኔ እንዲሰጥበት ለወረዳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሶታል፡፡ የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት የደረሠውን ጉዳት ካስገመተ በኋላ ለአመልካች ብር 8,000.00 ከወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው

ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዟል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር አጣሪ ችሎት የአመልካች የሠበር አቤቱታን በአብላጫ ድምጽ ለሠበር ሰሚ ችሎቱ አያስቀርብም በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪዎች የጉዳት ካሣ ብር 15,000.00 እንዲከፍሉ በተሠጠው ውሳኔ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ የለም፡፡ ካሣው አንሷል በማለት ይግባኝ ያቀረብኩት አመልካች ሆኜ እያለ የመጀመሪያ ቅሬታዬን ባላገናዘበ መልኩ ቀድሞ ከተወሰነው በታች ብር 8,000.00 እንዲከፈለኝ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ግምቱ እንደገና እንዲሰራ ጉዳዩ ሲመለስ ቀድሞ ከተወሰነው በታች መወሰኑ ሕጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ክርክሩ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ በአዲስ ዓለም ወረዳ በሚገኘው ይዞታዬ ላይ ያለን የባህር ዛፍ አትክልት ተጠሪዎች ቆርጠው ስለወሰዱ ግምቱን ብር 100,000.00 እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች የሚከራከሩት የአመልካችን ባህር ዛፍ ቆርጠን ጉዳት ያላደረስን በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ላይ ለደረሠው የንብረት ጥቅም ጉዳት ተጠሪዎች ብር 15,000.00 እንዲከፍሉ ሲወስን አመልካች በጉዳት መጠኑ ላይ ባለመስማማት ይግባኝ አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎት የደረሠው ጉዳት ግራቀኙ በመረጧቸው ገለልተኛ ሽማግሌዎች እንዲገመትና ቀድሞ ከተሰሙት ምስክሮች ቃል ጋር በመመዘን በጉዳዩ ላይ እንደገና ውሳኔ እንዲሰጥበት ለወረዳ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሶታል፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም የደረሠውን ጉዳት ካስገመተ በኋላ ለአመልካች አስቀድሞ ከተወሰነው ካሣ በመጠኑ የሚያንስ ብር 8,000.00 እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታም ተጠሪዎች ይግባኝ ባላቀረቡበት ሁኔታ አስቀድሞ ከተወሰነው ካሣ በታች መወሰኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ነው፡፡ መመርመር ያለበት ጭብጥም የሥር ፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር ሥርዓት ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከው ፍርድ ቤት ክሱን በሥረ-ነገሩ

አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ ለአመልካች ተገቢ ነው ያለውን ካሣ ወስኗል፡፡ አመልካች በካሣ መጠኑ ላይ ይግባኝ በማቅረባቸው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ለሥር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡

በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ወደሥር ፍርድ ቤት የሚመልስበት ሁኔታ የመጀመሪያው በአንቀጽ 341(1) የተመለከተ ሲሆን ይህም የሥር ፍርድ ቤት ወደ ሥረ-ነገሩ ሳይገባ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ውሳኔ ከሰጠና ውሳኔው በይግባኝ ሠሚ ችሎት ከተለወጠ ሊመረምራቸው የሚገቡ ነጥቦችን በመለየት ጉዳዩን የሚመለስበት ሥርዓት ነው፡፡ ሁለተኛው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 እና 344 ላይ የተደነገገው በዚህ ችሎትም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው ሲሆን ውሳኔው በሥረ-ነገሩ የሠጠው ፍርድ ቤት መያዝ የሚገባውን ጭብጥ ባለመያዙና ማጣራት የሚገባውን ፍሬ ነገር በተገቢው ሁኔታ ሳያጣራ ሲወሰን ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ እንደገና እንዲመረምርና ማስረጃ እንዲሰማ ጉዳዩ የሚመለስበት ሥርዓት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት መያዝ የሚገባውን ጭብጥ አለመያዙ ሁልጊዜ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለመመለስ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 እንደተመለከተው በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ በቂ ከሆነ የተያዘውን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሳይመለስ የመጨረሻ ፍርድ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህም የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሩ እንዲመራ ያለውን ዓላማ ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 መሠረት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ፍርድ የመጨረሻ መሆኑ መገለጹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት የሚሰጠው ፍርድ የመጨረሻ አለመሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩ ሲመለስ የሥር ፍርድ ቤት ያጣራውን ማስረጃ፣ የወሰደውን እርምጃና ለነገሩ አወሳሰን ምክንያት ያደረገውን በመግለጽ ለይግባኝ ሰሚ ችሎት እንደሚልክ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ የሚልከው ማስረጃ ሆነ ማናቸውም ዓይነት ውሳኔ የቀድሞው መዝገብ አባሪ ሆኖ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(2) ላይ ተገልጿል፡፡ ሥለሆነም ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጠው የመዝገቡ አባሪ ተሟልቶ ውጤቱ ከቀረበለት በኋላ ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 344(1) መሠረት የሥር ፍርድ ቤት በአዲስ አጣርቶ በላከው የመዝገቡ አባሪ ላይ መቃወሚያ ያለው ወገን ክርክሩን (አስተያየቱን) የሚያቀርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሚወስነው ጊዜ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሚልከው አባሪ እንደ አዲስ ውሳኔ የማይቆጠርና ራሱን ችሎ ይግባኝ የማይባልበት በመሆኑ አዲስ የይግባኝ መዝገብና ቅሬታ የሚቀርብበት አይደለም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዲስ በመጣው የመዝገብ አባሪ ላይ ግራ ቀኙ ክርክር እንዲያደርጉበት እድል ከሠጠ በኋላ አስቀድሞ ከተከፈተው የይግባኝ መዝገብና ክርክር ጋር መርምሮ በይግባኙ ላይ ውሳኔ ይሠጣል፡፡

የሥነ-ሥርዓቱ ሕጉ ከ342-344 ያሉት ድንጋጌዎች በሥረ-ነገሩ ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ ላይ በተቻለ መጠን ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሳይመለስ ጭብጡን በይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በኩል እንዲለወጥ ተደርጎ

ክርክሩ እንዲቋጭ የሚያዝና መጣራት የሚገባው ነገር ካለ ግን ግራ ቀኙ ሆኑ ማስረጃዎች በቅርብ በሚገኙበትና ጉዳዩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት እንዲታይ እድል የሚሰጥና የተጣራው ውጤት ሲቀርብም አዲስ የይግባኝ መዝገብ ሳይከፈት ቀድሞ በተመለሰበት መዝገብ ተጠቃሎ እንዲታይ መደረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጪና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ያለውን ሃሳብ ያሳያል፡፡ በፍርድ ቤቶች በተግባር የሚሰራበት የተሰማው ማስረጃ በቂ ሆኖ የተያዘው ጭብጥ ስህተት በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የሚመለስበት ሥርዓት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342ን ድንጋጌ ያልከተለና ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ጉዳዩ በፍሬ ነገሩ የሚጣራና የሥር ፍርድ ቤት እንዲመለከተው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት የሚመለስ ከሆነም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበት ሳይሆን የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ እስኪልክ ውጤቱን የሚጠብቅበትና የሥር ፍርድ ቤት ባጣራው ነጥብ ሆነ በወሰደው እርምጃ ላይ አዲስ ይግባኝ ሳይቀርብበበት ከቀድሞ ይግባኝ መዝገብ ጋር አባሪ በመሆን የሚቀርብ ነው፡፡ ተጣርቶ ከቀረበ በኋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቱ አንድ ላይ ፍርድ የሚሰጥበት ነው፡፡ በፍርድ ቤቶች ያለው አተገባበሩ ግን ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና እንዲጣራ በሠጠው ውሳኔ ሆነ የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ በደረሰበት ድምዳሜ ላይ በሀሉቱም ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ ሆነ የሠበር አቤቱታ በማቅረብ አንድ ጉዳይ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች ላይ እንዲታይ የሚያደርግ አላስፈላጊ የፍርድ ቤቱን ሆነ የተከራካሪዎችን ጊዜና ወጪ የሚወስድ እና ፍርድ ቤቶች ላይ የሥራ ጫና በመፍጠር ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ካሰበው ዓላማ ውጭ የሆነ መታረም ያለበት የክርክር አመራር ግድፈት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተወሰነው ካሣ አነሰኝ በማለት ይግባኝ ያቀረቡ በመሆኑ ጉዳዩ በሥረ-ነገሩ የተወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ እንደገና እንዲወሰን የመለሰበት ፍርድ ላይ በቀጥታ ይግባኝ ሆነ የሠበር አቤቱታ ባይቀርብበትም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 119851 ቅጽ 23 ላይ ተጠቃሎ ሲመጣ የሠበር አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችልና በሰበር ችሎት የሚመረመር ስለመሆኑ በተሠጠው ትርጉም መሠረት የውሳኔው ተገቢነትን ተመልክተናል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ለካሣ አወሳሰኑ የንብረቱ ግምት መገመት አስፈላጊ ነው ካለ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) እንደተመለከተው ግምቱ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማዘዝ መዝገቡን ለጊዜው በመዝጋት ውጤቱን መላክ ሲገባው ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት እንደ አዲስ እንደገና እንዲወስን መመለሱ ተገቢ አይደለም፡፡ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤት ካሣ መጠኑ ላይ መርምሮ ቀድሞ ከወሰነው ብር 15,000.00 በመቀነስ ብር 8,000.00 ለአመልካች እንዲከፈል ወስኗል፡፡ አመልካችም የሚከራከሩት ብር 15,000.00 ካሣ ሲወሰን አነሰኝ በማለት ይግባኝ ያቀረብኩት እኔ ሆኜ እያለ ተጠሪዎች ካሣ መጠኑ በዛ በማለት ያቀረቡት ይግባኝ ሳይኖር ቀድሞ ከተወሰነው በታች መወሰኑ ይግባኝ ያቀረብኩበትን ዓላማ ይጥሳል በማለት ነው፡፡ ይግባኝ የሚቀርበው በሥር ፍርድ ቤት የተሰራውን ስህተት ለማረምና በይግባኝ ባይ መብት የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ነው፡፡ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 እና 344 በሚያዘው አግባብ

የንብረቱ ግምት ተጣርቶ እስኪመጣ ጠብቆ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ቢወስን ኖሮ ቀድሞ ከተወሰነውና ይግባኝ ከቀረበበት ከብር 15,000.00 በታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ሊወሰን አይችልም ነበር፡፡ ምክንያቱም ብር 15,000.00 ካሣ መወሰኑን ተጠሪዎች ተቀብለውት ይግባኝ ያላቀረቡበት በመሆኑ ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከሚያዘው ውጭ ጉዳዩ ላይ የሥር ፍርድ ቤት በሥረ-ነገሩ እንደገና እንደ አዲስ እንዲወስን በመመለሱና ፍርድ ቤቱም በሕግ አግባብ የመሠለውን የመወሰን ነጻነት ያለው በመሆኑ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ቀድሞ የወሰነውን በመለወጥ ወስኗል፡፡ ውጤቱም አመልካች የካሣ መጠኑ በቂ አይደለም በማለት ይግባኝ ካቀረቡበት ብር 15,000.00 በታች የሆነ ብር 8,000.00 ካሣ እንዲወስን ሆኗል፡፡ በዚህም ይግባኝ የሚቀርበው በሥር ፍርድ ቤት የተሰራውን ስህተት ለማረምና በይግባኝ ባይ መብት የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ዓላማ ቢሆንም በሂደቱ የይግባኝ ሥርዓትን ዓላማ የለወጠና ይግባኝ ባለው ሠው ላይም የመብትና የጥቅም ጉዳት በሚያመጣ ሁኔታ ክርክሩ ተመርቷል፡፡ አመልካች ላይ የመብት ጥሰት ያስከተለው የሥር ፍርድ ቤቶች የክርክር አመራር ግድፈት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግምት ውጤት ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከተላከ በኋላ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገውበት አመልካች አስቀድሞ ባቀረቡት የይግባኝ መዝገብና ቅሬታ መሠረት በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊመረመር የሚገባው ጭብጥ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ. 343(1) አተገባበር በሰበር ችሎት ያለው ውጤት ነው፡፡ የሠበር ችሎት በዋነኛነት የሚመራበት ሥርዓት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት፣ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 454/1997 የተመለከቱ ልዩ ደንቦች ካልሆነ በቀር፤ ልዩ የሥነ-ሥርዓት ደንብ እስካልወጣለት ድረስ፤ በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ስለይግባኝ አቀራረብ የተመለከተው ለሰበር ችሎቱም ተፈጻሚ ነው፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ ይህም ማስረጃ ማጣራትና መመዘን ሥልጣን እንደሌለው ያስገነዝባል፡፡ ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን የለውም ማለት ግን ከማስረጃ ጋር የተያያዘ ጭብጥ ያለውን የሠበር አቤቱታ አይመለከትም ማለት አይደለም፡፡ ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ የተለየ የማስረዳት ደረጃ (standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና

ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት በሥር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ በቂ ከሆነ ነገር ግን የጭብጥ አመሠራረቱ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ ከሆነ የተያዘውን ጭብጥ በማሻሻል ወይም በመለወጥ ጉዳዩን ሳይመልስ የሰበር ችሎቱ ሊወስን ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ ማስረጃ ማጣራትና መመዘን የሚጠይቅ ተግባር ከሆነ እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) እንደተመለከተው ለሥር ፍርድ ቤት የሚመለስ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት አጣርቶ የሚልከው ውጤት ቀድሞ ከተሰማው ማስረጃ ጋር ምዘና የሚጠይቅ ከሆነ ሰበር ችሎት ማስረጃን በመመዘን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሊደርስ ስለማይችል ጉዳዩ የተመለሰለት የሥር ፍርድ ቤት አዲስ ያጣራውን አባሪ አድርጎ ሳይልክ ቀድሞ ከተሰማው ማስረጃና ክርክር ጋር አጣምሮ ተመልክቶ ጉዳዩ ላይ እንደገና እንደ አዲስ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡ ይህም የሥነ-ሥርዓት ሕጉ አቀራረጽና አተገባበር ላይ የተለየ ውጤት የሚያስከትል ነው፡፡

የሥነ-ሥርዓት ሕጉ የወጣው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመሆኑ የክርክር አመራር ሥርዓቱ በሕገ-መንግሥቱ ስለ ሰበር ችሎት የተሠጠውን ሥልጣን ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡ ሕገ-መንግሥቱ በአንቀጽ 9(1) ላይ እንደተመለከተው የሀገሪቱ የበላይ ሕግ በመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሕገ-መንግሥቱ ሰበር ችሎት ካለው ሥልጣን ጋር ተጣጥሞ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ ሥለሆነም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) የተመለከተው ጉዳዩ የሥር ፍርድ ቤት እንደገና ተመልክቶ ማስረጃ በማጣራትና ተገቢ ያለውን እርምጃ በመውሰድ ለመለሰለት ፍርድ ቤት አባሪ በማድረግ የሚመለስበት ሥርዓት ማስረጃ እንደገና እንዲመዘን የሚያደርግ ከሆነ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህን የማድረግ ሥልጣን ስለሌለው ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤት እንደ አዲስ ውሳኔ የሚሰጥበት እንጂ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊመለስ አይችልም በማለት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90436 ጥቅምት 21 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73226 ሕዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 75183 ሠኔ 12 ቀን 2011 ዓ/ም እንዲሁም የአዲስ ዓለም ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00749 ግንቦት 12 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 73226 የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ የሥር ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት ስለካሣ አወሳሰኑ በመዝገብ ቁጥር 00749 የቀረበውን የንብረት

ግምት ውጤት አመልካች አስቀድመው ካቀረቡት የይግባኝ መዝገብና ቅሬታ ጋር መርምሮ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሠ/መ/ቁጥር 185837

መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ኑረዲን ከዲር

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ጀፎር ኮንስትራክሽን

ተጠሪ ፡- አስማማዉ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግንባታ ሥራ ዉል አፈጻጸምን መሰረት ሳደረገዉ ክርክር የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ የቀረበ አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሆኖ ይህ ዉሳኔ የተሰጠዉ ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ተብሎ የሚወሰንበትን ሥርዓትና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አንድ ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት ለማድረግ በሕግ የተሰጣቸዉ ሥልጣን ተግባራዊ የሚሆነዉ መቼና በምን ሁኔታ ነዉ የሚሉትን ጭብጦች በተመለከተ ነዉ፡፡

አመልካች በግልግል ዳኝነት ጉባኤ በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ከተጠሪ ጋር በቀን 20/01/2006ዓ/ም በፈጸመዉ የሕንጻ ግንባታ ዉል ሁለት ምድር ቤቶች፣አንድ የመነሻ ፎቅና ዘጠኝ ፎቆች ያሉት የሆቴል ሕንጻ በጠቅላላ ዋጋ በብር 44,475,608.75 ለመገንባት ተስማምቶ የዋጋዉን 10% ቅድመ ክፍያ ተቀብሏል፡፡ተጠሪ አንድ ተጨማሪ ፎቅ እንዲጨመር በመጠየቁ የዲዛይን ክለሳ ከተደረገ በኋላ በአመልካች ለተሰራዉ ስራ ክፍያ ተጠይቆ አምስት ጊዜያዊ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች (Interim payment certificates) ተዘጋጅተዉ በተዋዋዮችና በአማካሪ መሐንዲሱ በጊጋር ኮንሰልት እየጸደቁ ቢቀርቡም ተጠሪ በመጀመሪያዉ የክፍያ ምስክር ወረቀት የተጠየቀዉን ቢከፍልም ከሁለተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀት ያልተከፈለዉን ቀሪ ክፍያ፣ ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ምስክር ወረቀቶች የተጠየቀዉን ክፍያ አልከፈለም፡፡በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 59.2.4 መሰረት ክፍያ አለመፈጸም ዉሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ መሰረታዊ የዉል ጥሰት ነዉ፡፡በተጨማሪም ተጠሪ የዉሉን አንቀጽ 59.2.2 በመተላለፍ

ሥራዉ ከ28 ቀናት በላይ እንዲቆም አድርጓል፡፡በእነዚህ ምክንያቶች አመልካች ዉሉን በማቋረጥ በዉሉ ላይ በመጀመሪያ ጉዳዩ ለአማካሪ መሐንዲስ ታይቶ መወሰን ስላለበት ለአማካሪ መሐንዲሱ አቅርቦ ማስወሰኑን ገልጾ ከሁለተኛ ክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይከፈል የቀረዉን፣ ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ምስክር ወረቀቶች ተጠይቆ ያልተከፈለዉን ብር 9,282,136.82፣ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ የታሰበ ወለድ ብር 1,022,707.50፣የቀረ የትርፍ ጥቅም ብር 1,695,261.09፣ሥራዉ በመዘግየቱ ያስከተለ ተጨማሪ ወጪ ብር 1,770,691.38፣ተቀንሶ የተያዘ ክፍያ ብር 874,183.94፣በግንባታ ስፍራ የሚገኙ ቁሳቁሶች ዋጋ ብር 31,344.16፣ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ብር 655,722.02 በድምሩ ብር 14,447,339.50 ተጠሪ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጠዉ የፍሬ ነገር መልስ ዉሉ ከተቋረጠ በኋላ ጊዜያዊ የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት በማድረግ (የመጨረሻ የክፍያ ምስክር ወረቀት ባለመሆኑ) ክፍያ አልተፈጸመም በሚል ምክንያት ክስ መመስረት አይችልም፡፡ አማካሪ መሀንዲሱ የክፍያ ምስክር ወረቀቶቹን ያጸደቀዉ በአመልካች ጋር በመመሳጠር ነዉ፡፡ይህ በመታወቁ አማካሪ መሐንዲሱ በሌላ ላይፍ ኮንሰልት በተባለ አማካሪ መተካቱ ለአመልካች ተገልጾለት እያለ ለዚህ አማካሪ አመልካች የክፍያ ጥያቄ አላቀረበለትም፡፡በዉሉ አንቀጽ 43.1 መሰረት የወለድ ጥያቄዉ በአማካሪ መሐንዲሱ ያልጸደቀ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡በኋለኛዉ አማካሪ መሐንዲስ በተዘጋጀዉ የማጠቃለያ ክፍያ ምስክር ወረቀት አመልካች የሠራዉ ሥራ ሙሉ በሙሉ ግድፈት ያለዉ(Defective)መሆኑ ስለተረጋገጠ በዉሉ ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 57 እና 60/2 መሰረት አመልካች ሊያነሳዉ የሚችል የክፍያ ጥያቄ አይኖርም፡፡አማካሪ መሀንዲሱ ባጸደቀዉ የመጨረሻ ክፍያ የምስክር ወረቀት አመልካች በዉሉና በዉሉ መሰረት በጸደቁት የሥራ ለዉጥ ትእዛዞች (Variation Orders)መሰረት የሰራዉ ሥራ ዋጋ ብር 11,563,316.00 ሲሆን የተከፈለዉ ከተ.እ.ታ በፊት ብር 11,311,995.00 ነዉ፡፡በአጠቃላይ አመልካች የሕንጻዉን የመዳረሻ ወለል(Lobby entrance floor)ከዋናዉ የቦሌ መንገድ ጋር በእኩል ከፍታ መስራት ሲገባዉ ከመንገዱ በላይ 1.34 ሜትር አስበልጦ በመስራቱ ሕንጻዉ ለታቀደለት ተግባር እንዳይዉል ስለሚያደርገዉ በዲዛይኑ መሰረት እንዲያስተካክል ተጠይቆ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡የመሰረቱ የኮንክሪት ንጣፍ፣የግድግዳ አፈር መጠበቂያ ስራዉ፣ እና የኮንክሪት ምሰሶዎች በሕግ የተቀመጠዉን ደረጃ በጠበቀ አኳኋን አልተሰሩም፡፡እንዲሁም የዉሃ መከላከያ ጥጋቱ በሸክላ መስራት ሲገባዉ ዉስጡ ክፍት በሆነ ብሎኬት የተሰራ በመሆኑ እነዚህ ግድፈቶች ሕንጻዉን በማይጠገንበት ደረጃ ያደረሱ ስለሆኑና ይህም በአመልካች ጥፋት የደረሰ በመሆኑ በዉሉ መሰረት ለአመልካች ክፍያ አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ የግንባታ ሥራዉ በአግባቡ አልተሰራም በማለት አስቀድሞ ለአመልካች የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስለት፣የካሳ ክፍያና የተሰራዉ ሥራን ለማስፈረስ የሚያስፈልግ ወጪ ጨምሮ በድምሩ ብር 17,126,759.00 እንዲከፈለዉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡አመልካች

ለተከሳሽ ከሳሽነቱ ክስ በሰጠዉ መልስ ለተከሳሽ ከሳሽነቱ ክስ መሰረት ያደረገዉ ላይፍ ኮንሰልት የተባለዉ አማካሪ መሐንዲስ የሰራዉን ሪፖርት ነዉ፡፡ተጠሪ አማካሪ መሐንዲሱን የቀጠረዉ ዉሉ ከተቋረጠ ከረጅም ጊዜ በኋላ በመሆኑና ግንባታዉን ሲቆጣጠርና ዉሉን ሲያስተዳድር የነበረዉ ጊጋር የተባለዉ አማካሪ መሐንዲስ የቁጥጥር ሥራዉን ሰርቶ ክፍያዉን ያጸደቀ በመሆኑ ግንባታዉን ተቆጣጥሮ ያልሰራዉን መሐንዲስ አማካሪ አድርጎ መቅጠሩም ሆነ ይህ አማካሪ ያቀረበዉን ሪፖርት መሰረት አድርጎ ያቀረበዉ ክስ የሕግም ሆነ የዉል ድጋፍ ስለሌለዉ ክሱ ዉደቅ ሊሆን ይገባል የሚሉትንና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማንሳት ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የግራ ቀኙን ክርክር፣ምስክሮች፣የሙያ ምስክርነት በመስማት እና የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር በቀን 18/01/2011ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ዉሉ ከተቋረጠ በኋላ ላይፍ ኮንሰልት የተባለዉን አማካሪ ስለቀጠረ ይህ አማካሪ በቀጣይ የሚኖረዉን የግንባታ ሂደት በተመለከተ የሙያ ድጋፍ ሊሰጥ ከሚችል በስተቀር በግራ ቀኙ መካከል በነበረዉ ዉል መነሻ የተሰራዉን ግንባታ በተመለከተ ወደ ኋላ ተመስርቶ አማካሪ መሐንዲስ መሆን ስለማይችል ይህ አማካሪ መሀንዲስ ያዘጋጃቸዉን ማስረጃዎች ተቀባይነት የለዉም በማለት እነዚህን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ አድርጓል፡፡አመልካች የግንባታ ሥራዉን በዉሉ እና በዲዛይኑ መሰረት ባለመስራቱ እና የተሰራዉ የሕንጻ ግንባታ ጉድለት ያለበት ሆኖ እያለ ዉሉን አለአግባብ አቋርጧል በማለት አመልካች በክፍያ ምስክር ወረቀቶቹ ሊከፈለኝ ይገባል ሲል የጠየቀዉን እና ለሌሎች በክሱ የጠየቃቸዉ ክፍያዎች እንዲሁም በግንባታ ሥፍራ ቀርተዋል የተባሉ እቃዎች ከነዋጋ ግምታቸዉ በማስረጃ የተደገፈ አይደሉም በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ተጠሪ ያቀረቡትን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ በአመልካች የተሰራዉ ግንባታ ሥራ ላይ ያለዉ ጉድለት በተጨማሪ ሥራ ሊስተካከል እንደሚችል በማስረጃ በመረጋገጡና ይህም በተጠሪ ላይ ተጨማሪ ኪሳራ ስለሚያስከትልበት አመልካች ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች እንዲከፈለዉ ጠይቆ ሳይከፈለዉ የቀረዉ ብር 7,461,146.02 ተጠሪ ጉድለቱን ለማስተካከል የሚደርስበትን ኪሳራ ለመካስ በቂ ነዉ በማለት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2102/1 የተደነገገዉን በመጥቀስ በርትእ በመወሰን ለተጠሪ የሚከፈል ክፍያ የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሁለቱም ወገኖች በተለያዩ መዝገቦች ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 165539 ላይ በቀን 30/01/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በላይፍ ኮንሰልት የቀረበዉን ሙያዊ አስተያየት ሳይቀበል ከግራ ቀኙ የቀረቡትንና ሌሎች ማስረጃዎችን መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡እንዲሁም የግልግል ዳኝነት አካሉ አመልካች የሰራዉ ግንባታ ጉድለት አለበት በማለት እንዲሁም አመልካች እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፈለዉ አይገባም ሲል የሠጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡በሌላ በኩል የተለያዩ ጭብጦችን

በመያዝ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ ግራ ቀኙ በሚመርጡት ወይም በሌላ ገለልተኛ ኮሚቴ ወይም በባለሙያ እንዲጣራ አድርጎ የመሰለዉን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ለግልግል ዳኝነት ጉባኤ መልሶለታል፡፡

አመልካች በቀን 09/03/2012 ዓ/ም በ20 ገጽ ላይ የተጻፈ የሰበር የአቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡-የግንባታ ሥራዉን የሚቆጣጠረዉና ዉሉን የሚያስተዳድረዉ አማካሪ መሐንዲስ በኩል አመልካች የሠራዉ ግንባታ ጉድለት አለበት በሚል አልተረጋገጠም፡፡በሁለቱም በኩል ያሉት የሕንጻዉ መግቢያዎች በየአቅጣጫዉ ካለዉ መንገድ ጋር ታሳቢ ተደረጎ ዲዛይን የተሰራዉ ዋናዉ የቦሌ መንገድ እንደገና ከመሰራቱ በፊት ሲሆን የቦሌ መንገድ ፈርሶ እንደ አዲስ በመሰራቱና መንገዱ ቀድሞ ከነበረበት ዝቅ በማለቱ ምክንያት የሕንጻዉ ሁለቱ መግቢያዎች በኩል ያለዉ የመንገድ ከፍታ ቢለያይም ይህንን ታሳቢ በማድረግ በአማካሪ መሐንዲሱ በተሰጠ ማስተካከያ መሰረት በአመልካች ግንባታ ተፈጸመ እንጂ በአመልካች ጥፋት ምክንያት የተፈጠረ ጉድለት አይደለም፡፡ተጠሪ በአማካሪ መሐንዲሱ በጸደቁት ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች የተጠየቁ ክፍያዎች ቅሬታ ካለዉ ለአማካሪ መሐንዲሱ በማቅረብ ከማሳረም በስተቀር ክፍያዉን አልፈጽምም ማለት ስለማይችልና አማካሪ መሀንዲሱ የተሰራዉ ስራ ትክክል መሆኑን አረጋግጦ እያለ ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ የክፍያ ምስክር ወረቀቶች የተጠየቀዉን ክፍያ ተጠሪ እንዲከፍል አለመወሰኑ በሰ/መ/ቁጥር 44604 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም እና የዉሉን አንቀጽ 24 የሚቃረን ነዉ፡፡ተጠሪ ግንባታዉ እንዲቆም የሰጠዉ ትእዛዝ በ28 ቀናት ዉስጥ አለማንሳቱና በአማካሪ መሃንዲሱ የተፈረሙ የክፍያ ምስክር ወረቀቶችን በ90 ቀናት ዉስጥ አለመክፈሉ መሰረታዊ የዉል ጥሰት በመሆኑ በአማካሪ መሃንዲስ የተረጋገጡ ክፍያዎች ከ13.75 ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፈል አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም በክሱ የተጠየቁ ሌሎች ክፍያዎች ለአመልካች ሊከፈል እንደሚገባ ዉልንና ሕግን መሰረት በማድረግ በማስረጃ ተድግፎ ተጠይቆ እያለ በግልግል ዳኝነት ጉባኤዉና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡የተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን ያቀረበዉ የግንባታ ሥራዉን ሲቆጣጠርና ዉሉን ሲያስተዳድር ባልነበረ እና የግንባታ ዉሉ ከተቋረጠ ከረጅም ጊዜ በኋላ የተቀጠረዉ አማካሪ ያቀረበዉን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በመሆኑ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ዉድቅ መደረግ ነበረበት፡፡ዉሳኔዎቹ ተሽረዉ በድምሩ ብር 14,447,339.40 ከነወለዱ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

አንደኛ ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም በሁለት ዳኞች ተፈርሞ በኮምፒዩተር በተዘጋጀ የትእዛዝ ፎርም ላይ ተፈርሞበት ትእዛዝ መስጠቱን መዝገቡ ያሳያል፡፡የትእዛዙ ይዘትም፡- "በቀረበዉ የሰበር አቤቱታ በግልግል ዳኝነት ጉባኤና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተሰርቷል ለማለት የሚያስችል እንዳልሆነ ገልጾ ጉዳዩ ለሰበር

ችሎት የሚያስቀርብ አይደለም ብለናል፡፡ መዝገቡ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ" የሚል ይዘት ያለዉ ሲሆን በተጨማሪም በዚሁ ትእዛዝ በእጅ በእስክርብቶ ተጽፎ "የሐሳብ ልዩነት ከመሰጠቱ በፊት ለመነጋገር" የሚል ጽሁፍ እንደተጨመረበትና በችሎቱ ከተሰየሙት ሶስት ዳኞች መካከል ሰብሳቢዉ ዳኛ በትእዛዙ ላይ ፊርማቸዉን እንዳላኖሩ መዝገቡ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በቀን 14/07/2012 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በጻፈዉ አቤቱታ "... የሰበር አቤቱታ አቅርቤ መዝገቡ ለተመራለት ለ1ኛ ሰበር አጣሪ ችሎት ቅሬታዬን ያሰማሁ ቢሆንም በዳኝነት ሥራ ፍጹም ባልተለመደ መልኩ ችሎቱ እስከ ዛሬ ድረስ በቅሬታዬ ላይ ምንም አይነት ትእዛዝ ሳይሰጥበት መዝገቡም ከቀጠሮ ዉጪ ሆኖ በመንከራተት ላይ እገኛለሁ...በግልግል ዳኝነት አካልና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ የፍትህ መጓደልን ያስከተለ ፍርድ ሆኖ እያለ ሳይታረምና መዝገቡ ከነጭራሹ ከቀጠሮ ዉጪ መሆኑ ተገቢነት የሌለዉ ስለሆነ ክብርነቶዎ ይህንኑ ተገንዝበዉልኝ ሕጉ በሚፈቅደዉ አግባብ ጉዳዩ ታይቶ ተገቢዉ ትእዛዝ እንዲሰጥ አመለክታለሁ፡፡"ሲል ጠይቋል፡፡ይህንን ተከትሎ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አቤቱታዉን በማጠፍ የሚከተለዉን በማስፈር፡-

> "በዚህ ጉዳይ ላይ በችሎቱ ዳኞች የሀሳብ ልዩነት ስለተከሰተ እና ጉዳዩም ወሰብሰብ ስለሚል ሁለት ዳኞች (ዳኞች በስም ተጠቅሰዋል) ተጨምረዉ በአምስት እንዲታይ ታዟል፡፡" በጊዜዉ ለነበሩት ለ1ኛ ሰበር አጣሪ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ አቤቱታዉን መርተዋል፡፡

በመቀጠልም በችሎቱ በነበሩት ሶስት ዳኞች ላይ ሁለት ዳኞች ተጨምረዉ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮ በግልግል ዳኝነት አካሉና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጡ ዉሳኔዎች ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያለዉን ነጥቦች በመለየት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በአብላጫ ድምጽ በቀን 29/07/2012ዓ/ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ከተሰየሙት አምስት ዳኞች ሁለቱ ዳኞች አስቀድሞ በሰጠነዉ ትእዛዝ በነበረን አቋማችን ጸንተናል በማለት በሀሳብ ተለይተዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ ተጠሪ በቀን 02/10/2012ዓ/ም የአመልካች አቤቱታ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገዉ ፍጹም ከሕግ እና ከሥነ ሥርዓት ዉጪ ነዉ ያለበትን ምክንያት እና ዋናዉን ጉዳይ የሚመለከት መከራከሪያ በ13 ገጽ ጽፎ ያቀረበ ሲሆን አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገበት አግባብ ከሕግ ዉጪ ነዉ ያለበትን ምክንያት በአጭሩ በሚከተለዉ መልኩ አቅርቧል፡-

አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ አቅርቦና ሶስት ዳኞች ለተሰየሙበት ችሎት ካስረዳ በኋላ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል በቀን 30/06/2012ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ ወስኖ መዝገቡ እንዲዘጋ አዟል፡፡ በአብላጫ ድምጽ የተሰጠዉ ዉሳኔ በፍርድ ቤቱ ድህረገጽ ላይ ከመለጠፉም በተጨማሪ

በፍርድ ቤቱ የመረጃ ቋት (data base) እና በፍርድ ቤቱ አጭር የስልክ ቁጥር 992 በአጭር መልእክት(SMS) ተገልጾልናል፡፡ የልዩነት ሀሳብ መጻፍ የነበረባቸዉ ዳኛ የልዩነት ሀሳብ ጽፈዉ መዝገቡን ሳይመልሱ አዘግይተዋል፡፡ከዚህ በኋላ አመልካች በቀን 14/07/2012ዓ/ም ፍትህ ተጓደለብኝ የሚል አቤቱታ አቅርበዉ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ "የሀሳብ ልዩነት ስለተከሰተ እና ጉዳዩም ዉስብስብ ነዉ በሚል ምክንያት ጉዳዩን አምስት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት በማለት በማዘዝ" ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይ ለማድረግ በሕግ ሥልጣን አልተሰጣቸዉም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አንድን ጉዳይ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ ማድረግ እንዲችሉ ሕጉ ሥልጣን የሚሰጣቸዉ ጉዳዩ ዉሳኔ ከማግኘቱ በፊት እንጂ ጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ አይደለም፡፡በተያዘዉ ጉዳይ በተሰጠ ዉሳኔ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም ተብሎ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ከዚህ በኋላ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ ጉዳዩን እንዲያዩ በማድረግ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገበት አግባብ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22 መሰረት የተሰጠ ዉሳኔ ዉጤት አልባ አድርጓል፡፡ ይህም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 79/3 እና በአለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነጻነት ያከናዉናሉ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም በማለት የደነገጉትን መርሆ እና የሕግ የበላይነት የጣሰ ነዉ፡፡በመሆኑም የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በቀን 22/07/2012ዓ/ም ጉዳዩ በአምስት ዳኞች እንዲታይ የሰጡት ትእዛዝም ሆነ በዚህ መነሻ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ በአብላጫ ድምጽ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የሰጡት ትእዛዝ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1 መሰረት ተፈጻሚነት የለዉም በማለት ከሥነ ሥርዓት ዉጪ በሆነ አግባብ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ መልሱን በመስጠት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በቀን 17/02/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ በአብላጫ ድምጽ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ተብሎ ተወስኖ አቤቱታዉን ላቀረበዉ አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ 180 እና 181 መሰረት ተነብቦ የተገለጸልን ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ የለም፡፡ ተጠሪ በሁለት ዳኞች ተሰጠ ባለዉ ትእዛዝ መዝገቡ ተዘግቶ እንደነበር ያወቅነዉ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ ጉዳዩን አይተዉ ያስቀርባል ብለዉ መጥሪያ ስናወጣ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 181 መሰረት ለተከራካሪ ወገኖች ያልተገለጸ ዉሳኔ እንደረቂቅ እንጂ እንደ ዉሳኔ ሊቆጠር አይችልም፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ካቀረብኩና ከተሰማሁ በኋላ መዝገቡ ላይ ትእዛዝ ባለመሰጠቱ ስመላለስ በዳኞች ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል በሚል ስላልተገለጸልኝ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አቤቱታ አቅርቤ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 21/1 ስር በተሰጣቸዉ ስልጣን መሰረት በጉዳዩ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ እንደሌለ አረጋግጠዉ ጉዳዩን አምስት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ ያደረጉት በሕግ በተሰጣቸዉ ስልጣን በመሆኑ ተጠሪ ያለአግባብ አቤቱታ ስላቀረበ ሥነ ሥርዓታዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ተጠሪ አያስቀርብም በሚል ተገልጿል

ብሎ የገለጸዉ በዳታ ቤዝ ሠራተኞች በተፈጠረ ስህተት መሆኑ ተረጋግጦ ስህተቱ ስለታረመ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ የተሰጠ ትእዛዝ ሕጉን የተከተለ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክር፣ በግልግል ዳኝነት አካል እና በይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት እና ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለበትን አግባብ የሚያሳይ ሲሆን እኛም ዋናዉ ጉዳይ ከመመርመሩ በፊት ተጠሪ የሰበር አቤቱታዉ ለዚህ ችሎት የቀረበዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥነ ሥርዓት አግባብ ዉጭ ነዉ በማለት ባቀረበዉ መከራከሪያ መነሻ ለተደረገዉ ክርክር አስቀድሞ ዉሳኔ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን በማመን 1) ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ እንዲወስን መዝገቡ የተመራለት አጣሪ ችሎት አስቀድሞ ሰጠ የተባለዉ ትእዛዝ የሚኖረዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ? 2) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አንድ ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ ለማድረግ በሕግ የተሰጣቸዉ ሥልጣን ተግባራዊ የሚሆነዉ መቼና በምን ሁኔታ ነዉ? እንዲሁም 3) ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገዉ በሕግ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት በመከተል ነዉ ወይ ? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ እንዲወስን መዝገቡ የተመራለት ሰበር አጣሪ ችሎት አስቀድሞ ሰጠ የተባለዉ ትእዛዝ የሚኖረዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ?በሚል የያዝነዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት አንድ ዉሳኔ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የሚሰማዉ አስቀድሞ ሦስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ዉሳኔዉ ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ የመጨረሻ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ መርምሮ ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰን የሚችለዉ ሦስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት(በተለምዶ ሰበር አጣሪ ችሎት የሚባለዉ) ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ ሶስት ዳኞች የተሰየሙበት የሚለዉ የሕጉ ይዘት የሚያሳየዉ ሶስቱም ዳኞች አመልካቹ ያቀረበዉን አቤቱታና ዉሳኔዉን መርምረዉና እንደነገሩ ሁኔታ አመልካቹን በመስማት ተወያይተዉ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንዳለባቸዉ ነዉ፡፡ በተጠቃሹ ድንጋጌ መሰረት ሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታዉንና ለአቤቱታዉ መሰረት የሆነዉን ዉሳኔ መርምሮ ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ወይም የለበትም ብሎ የሚሰጠዉ ትእዛዝ እንደ ዉሳኔ የሚቆጠር ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 25/1988 ላይ ሰበር አጣሪ ችሎት ዉሳኔ የሚሰጥበት ጊዜ፣ዉሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታና የዉሳኔዉ ይዘት(ፎርም) ምን ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ አልተደነገገም፡፡በመሆኑም አንድን የሕግ ድንጋጌ እንደነገሩ ሁኔታ አገናዝቦ ተግባራዊ ማድረግን የሚፈቅደዉን መርህ (Principle of mutatis mutandis) የሰበር ባህሪይን ባገናዘበ መልኩ በመጠቀም እንደ ጉዳዩ አይነት ስለ ፍርድ ዉሳኔ አሰጣጥ እና አጻጻፍ

እንዲሁም ዉሳኔዉ ስለሚነበብበት አግባብ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት እና በወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግጋት የተደነገገዉን እንደ አግባብነቱ ተግባራዊ እንዲያደርግ ይጠበቃል፡፡የተያዘዉ ጉዳይ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ በመሆኑ ስለፍርድ ዉሳኔ አሰጣጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 180 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተመለከተዉን እንደ አግባብነታቸዉ ተፈጻሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 12/1 ላይ እንደተደነገገዉ የመንግስት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡ፍርድ ቤት አንደኛዉ የመንግስት አካል እንደመሆኑ በሕግ በተደነገገ ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የሚሰጠዉን የዳኝነት አገልግሎት ለተከራካሪ ወገኖች ብቻ ሳይሆን ለሕዝብ ግልጽ በሆነ አኳኋን መተግበር ይኖርበታል፡፡ይህንን ግዴታዉን ለመወጣት ከሚከተልባቸዉ ሥነ ሥርዓቶች መካከል ክርክሮችን በግልጽ ችሎት መስማት እና ለክርክሮች የሚሰጠዉን እልባት ለተከራካሪ ወገኖች ግልጽ በሆነ አኳኋን መስጠትና መግለጽ(ማሳወቅ)አንዱ ነዉ፡፡በተለይ ከፍርድ ዉሳኔ አሰጣጥና ዉሳኔዉን ከማሳወቅ/ከመግለጽ ጋር በተያያዘ የሰበር አጣሪ ችሎት የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ከሰማና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የተባለዉን ዉሳኔ ከመረመረ በኂላ ወዲያዉኑ ወይም በሚወስነዉ አጭር ቀነ ቀጠሮ በግልጽ ችሎት ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 180 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡እንዲሁም የሚሰጠዉ ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ በአስቻሉት ዳኞች/ዳኛ ተፈርሞ ለተከራካሪ ወገኖች መነበብ እንዳለበት እና በአብላጫ ድምጽ የተሰጠ ዉሳኔ ከሆነም ገዥ የሚሆነዉ ዉሳኔ አብላጫ ቁጥር ባላቸዉ ዳኞች የተወሰነዉ ሆኖ በሀሳብ የተለየዉ ዳኛ የልዩነት ሀሳቡን በጽሁፍ ማስፈር እንዳለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 181(1 እና 2) ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ዉሳኔ ለተከራካሪዎች በንባብ ከማሰማት ጋር በተያያዘ ዉሳኔዉን የሰጡ ዳኞች በዉሳኔዉ ላይ ፊርማቸዉን እስካኖሩ ድረስ ሌላ ዳኛ ዉሳኔዉን በንባብ ሊያሰማ ይችላል(በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 181/3 ይመለከቷል)፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ መዝገቡ እንደሚያሳየዉ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት በሁለት ዳኞች ተፈርሞ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም በተጻፈ ትእዛዝ የሰበር አቤቱታ በቀረበበት ዉሳኔ ላይ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንዳልተፈጸም ተገልጾ መዝገቡ እንዲዘጋ መታዘዙን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በዚሁ ትእዛዝ ላይ በእጅ በእስክሪብቶ ተጽፎ <u>"የሐሳብ ልዩነት ከመሰጠቱ በፊት ለመነጋገር"</u> የሚል ጽሁፍ እንደተጨመረበትና በችሎቱ ከተሰየሙት ሶስት ዳኞች መካከል ሰብሳቢዉ ዳኛ በትእዛዙ ላይ ፊርማቸዉን እንዳላኖሩ አረጋግጠናል፡፡በሕግ ስለዳኞች አሰያየም ሲደነገግ ከግምት የሚገቡ መሰረታዊ ሁኔታዎች የጉዳዩን የክብደት ደረጃ፣ ዉስብስብነት፣ጉዳዩ በተከራካሪዎችና በአጠቃላዩ ሕብረተሰብ ላይ የሚኖረዉን አዉንታዊም ሆነ አሉታዊ ፋይዳ እና የመሳሰሉትን ምክንያቶች ሲሆኑ የሚሰየሙት ዳኞች ቁጥር ብዛት ሦስትና ከሦስት በላይ እየተደረገ በሕግ የሚደነገግበት ዓላማ ደግሞ የዳኞቹ ቁጥር ሲጨምር በዳኞች መካከል በሚደረግ ዉይይትና በጋራም ሆነ በተናጠል ዳኞቹ በጉዳዩ ላይ በሚያደርጉት ምርምር አከራካሪዉን ፍሬ ነገር በአግባቡ በመለየት ለሚያከራክረዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉን ሕግ

በአግባቡ በመለየትና በመተርጎም እና/ወይም ተፈጻሚ በማድረግ በአንጻራዊነት ትክክለኛ ዉሳኔ መስጠት ይቻላል በሚል እምነት ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር በቀን 30/06/2012 ዓ/ም ተጽፎና በሁለት ዳኞች ተፈርሞ በመዝገቡ ዉስጥ የተቀመጠዉን ትእዛዝ ስንመለከት ትእዛዙ በአንድ በኩል ከተሰየሙት ሶስት ዳኞች ሁለቱ በመፈረማቸዉ አብላጫ ቁጥር ባላቸዉ ዳኞች ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም ተብሎ ድምዳሜ ላይ መደረሱን አመላካች ሲሆን በሌላ በኩል ከሦስቱ ዳኞች አንደኛዉ ዳኛ "የሐሳብ ልዩነት ከመሰጠቱ በፊት ለመነጋገር" በሚል ያሰፈሩት ሀሳብ ዳኛዉ የልዩነት ሀሳባቸዉን እንዳሰፈሩ እንዲቆጠር የሚያደርግ መግለጫ ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በሶስቱም ዳኞች መደረግ የነበረበት ዉይይት አለመጠናቀቁን የሚያሳይ ሀሳብ ነዉ፡፡ከዚህ በመነሳት በቀን 30/06/2012 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ በተሰጠዉ ትእዛዝ ላይ ከዳኞች ቁጥር አኳያ ሦስት ዳኞች በስም ቢጠቀሱም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22/1 ስር ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙ መወሰን ያለበት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ነዉ የሚለዉን በሚቃረን መልኩ ከሶስቱ ዳኞች አንደኛዉ ዳኛ በተሟላ ሁኔታ ጉዳዩን ሳይመረምሩና በጉዳዩ ላይ መደረግ ያለበት ዉይይት ሳያልቅ የተሰጠ ትእዛዝ በመሆኑ ባልተሟሉ ዳኞች እንደተሰጠ ትእዛዝ የሚቆጠር በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ጉድለት (irregular proceedings) ያለበት ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰናል፡፡ስለሆነም በሕጉ ሶስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት ለሰበር አቤቱታዉ መሰረት የሆነዉ ዉሳኔ ተመርምሮ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ መወሰን አለበት ተብሎ በተደነገገዉ መሰረት የተሰየሙት ሦስቱም ዳኞች ተወያይተዉበት በጉዳዩ ላይ በማያሻማ አኳኋን በሙሉ ድምጽ ወይም በአብላጫ ድምጽ ለመወሰን በሚያስችል መልኩ በቂ ዉይይት አድርገዉ ድምዳሜ ላይ ባልደረሱበት የሚሰጥ ዉሳኔ ሕጉ ታሳቢ ያደረገዉን ዓላማ የማያሳካ እና ባልተሟሉ ዳኞች እንደተሰጠ ዉሳኔ/ትእዛዝ የሚቆጠር በመሆኑ ሕጋዊ ዉጤት ሊሰጠዉ የሚገባ አይደለም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 73696 ላይ (በቅጽ 13 ላይ እንደታተመዉ)"የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሰጠዉ ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ ሕጋዊ ዉጤት ሊኖረዉ እንደማይገባ የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ በመዝገቡ ላይ በቀን 30/06/2012ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ነዉ በሚል የደረስነዉ ድምዳሜ እንዳለ ሆኖ ይህ ትእዛዝ ለተከራካሪ ወገኖች ተነብቦላቸዋል ወይስ አልተነበበላቸዉም?ያለመነበብ ዉጤት ምንድን ነዉ?የሚሉ ነጥቦችም ክርክር የተነሳባቸዉ ስለሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ናቸዉ፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 181/3 ስር እንደተደነገገዉ በመርህ ደረጃ የተሰጠዉ ዉሳኔ/ትእዛዝ ለተካራከሪ ወገኖች መነበብ አለበት፡፡ ይሕም የዳኝነት ሥራ ግልጸኝነትን የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ዉሳኔዉን የሰጡት ዳኞች ወይም ሌላ ዳኛ ዉሳኔዉን በንባብ ባላሰሙበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ስልክና መሰል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በዘረጋዉ አሰራር መሰረት ዉሳኔዉን ለተከራካሪ ወገኖች በማድረስ ወይም በመግለጽ ያሳወቀ

ከሆነ ዉሳኔዉን በሰጡት ዳኞች ዉሳኔዉ ባለመነበቡ ብቻ ዉሳኔዉ ሕጋዊ ዉጤት እንዳይኖረዉ የሚያደርግ የሕግ መሰረት የለም፡፡በተጨማሪም ተከራካሪ ወገኖች ባለመቅረባቸዉ ምክንያት በንባብ ማሰማት የማይቻልበት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ዉሳኔ በንባብ አለማሰማት የአንድን ዉሳኔ ሕጋዊ ዉጤት ሊያስቀር የሚችል አይደለም፡፡ በጸና አኳኋን ያልተሰጠ ዉሳኔ ወይም የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ዉሳኔም ስለተነበበ ብቻ መታረም ባለበት ሥርዓት ሊታረም አይችልም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ አይችልም፡፡ በተያዘዉም ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ስልክና መሰል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን በመጠቀም በዘረጋዉ አሰራር መሰረት በቀን 30/06/2012 ዓ/ም የተሰጠዉን ትእዛዝ ለተከራካሪዎች ማሳወቁን ስለተገነዘብን ዉሳኔዉ አለመነበቡ ብቻዉን ትእዛዙ የለም የሚያስብል ወይም ትእዛዙን እንደረቂቅ የሚያስቆጥር አይደለም፡፡በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ በዳኝነት ታይቶ ሊታረም የሚችል የሥነ ሥርዓት ጉድለት እንዳለበት ትእዛዝ ከሚቆጠር በስተቀር ትእዛዙ ለተከራካሪ ወገኖች ባለመነበቡ ብቻ አብላጫ ቁጥር ባላቸዉ ዳኞች በተፈረመበት ሁኔታ እንደረቂቅ እንዲቆጠር የሚያደርግ የሥነ ሥርዓት ሕግ አግባብ ባለመኖሩ ከዚህ አኳያ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ ይህ ማለት ግን ከላይ በተጠቀሰዉ ምክንያት ባልተሟሉ ዳኞች ያተሰጠ ትእዛዝ ስልክና መሰል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተከራካሪዎች እንዲያዉቁት በመደረጉ ብቻ ትእዛዙ የስነ ሥርዓት ጉድለት የለዉም ወደሚል ድምዳሜ ተደርሷል ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በሰበር አጣሪ ችሎቱ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ ባልተሟሉ ዳኞች የተሰጠ በመሆኑ ሕጋዊ ዉጤት የለዉም ከተባለ ትእዛዙ ሕጋዊ ዉጤት የለዉም የሚል ዉሳኔ መቼ፣ በምን አግባብና በማን ሊሰጥ ይገባል የሚለዉ ጭብጥ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ሌላዉ ጭብጥ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የዳኝነት ነጻነት በዓለም አቀፍ ሕግጋት፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥትና በተለያዩ አገራዊ ሕግጋት እዉቅና የተሰጠዉና ጥበቃ የተደረገለት መርህ ነዉ፡፡በተለይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78/1 እና 79(2 እና 3) ስር ስለፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነጻነት እና የዳኞች ግላዊ ነጻነት በተመለከተ እንደተደነገገዉ ፍርድ ቤቶች ከማንኛዉም የመንግሥት አካል፣ከማንኛዉም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛዉም ሌላ ተጽእኖ ነጻ እንደሆኑና ዳኞችም ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነጻነት እንደሚያከናዉኑ ተደንግጓል፡፡በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 138/1991 እና በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 16(2/ሀ) ፣18(ሀ/1) እና 21/1 እንዲሁም በተሻሻለዉ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 684/2002 አንቀጽ 6(1/ሰ) ስር እንደተደነገገዉ ዳኞችን በየችሎቱ መድቦ የማሰራት ሥልጣንና ተግባር በፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነጻነት ማእቀፍ ዉስጥ የሚታይ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና/ወይም የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር ነዉ፡፡ የዳኝነት ነጻነት መርህ ዳኞች በተመደቡበት ችሎት የዳኝነት ተግባራቸዉን ከማናቸዉም ተጽእኖ ወይም ጣልቃ ገብነት

ነጻ ሆነዉ እንዲያከናዉኑ በዳኞች ላይ ግዴታ የሚጥል ነዉ፡፡ የፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችም አግባብ ባለዉ ሕግ በተደነገገዉ መሰረት በችሎት ተሰይመዉ ሊሰሩ የሚችሉ ቢሆንም ሌሎች ዳኞች ተሰይመዉ በዳኝነት በሚያዩት ጉዳይ የዳኝነት ተግባራቸዉን በነጻነት እንዳይተገብሩ ከሚያደርጉ ጣልቃ ገብነት ራሳቸዉን መቆጠብና ሌላ ማንኛዉም ሰዉ የዳኝነት ነጻነትን የሚነካ ተግባር እንዳይፈጽም መከላከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዳኞችን ከሚያስተዳድር አካልም ይሄዉ ይጠበቃል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በቀን 30/06/2012 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ የተሰጠዉ ትእዛዝ ከላይ ተደጋግሞ እንደተገለጸዉ ባልተሟሉ ዳኞች የተሰጠ ትእዛዝ በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ጉድለት (irregular proceedings) ያለበት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 209/1 እና 211/2 ስር ከተደነገገዉ መንፈስና ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ትእዛዝ ከእነጉድለቱም ቢሆን ጉዳዩ በዳኝነት ታይቶ የተሰጠ ትእዛዝ በመሆኑ የማረም ሥልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ቀርቦ በሚሰጥ ዳኝነት የሚታረም እንጂ በተከራካሪ ወገኖች አመልካችነት ወይም በፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አነሳሽነት ታይቶ በፕሬዚዳንት በሚሰጥ አስተዳደራዊ ዉሳኔ እንዲታረም የሚፈቅድ የሕግ አግባብ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ሥርዓቱን ጠብቆ ካልተሻረ ከእነጉድለቱም ቢሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 212 መሠረት የጸና ይሆናል፡፡ ይሕ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ በምን አግባብ ሊታረም ይችላል የሚለዉን የተመለከትን እንደሆነ ይህ ትእዛዝ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ተፈጽሞ የተሰጠና ትክክለኛ ፍርድ ከመስጠት የሚያግድ ሆኖ ከታየ ትእዛዙን በመሻር(ትእዛዙ እንዳልተሰጠ በመቁጠር) ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የሚያደርግ ትእዛዝ በመስጠት ማረም ይቻላል(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 211/2 ይመለከቷል)፡፡በግልጽ እንደሚታየዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 211/2 ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚጠቀመዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡ ሆኖም እስካሁን ሰበር ችሎት የሚመራበት ልዩ ሥነ ሥርዓት ስሌለ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 211/2 ስር የተደነገገዉን አንድን የሕግ ድንጋጌ  አገናዝቦ ተግባራዊ በማድረግ መርህ (mutatis mutandis) መሰረት ከሰበር ባህሪ አንጻር በማገናዘብ በሰበር በሚታይ ጉዳይ ላይም ተፈጻሚ ማድረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 30/06/2012ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ ባልተሟሉ ዳኞች የተሰጠ በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ስላለበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 211/2 መሰረት ሊሻር የሚገባዉ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደገና እንደተሻሻለዉ)አንቀጽ 21 ስር ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ ከማድረግ አንጻር ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የተሰጠዉ ስልጣን ተፈጻሚ የሚሆነዉ መቼና በምን ሁኔታ ነዉ የሚለዉን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 21 ስር በተለያዩ ምክንያቶች በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ትእዛዝ እና በሕጉ በተጠቀሱት ምክንያቶች ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ የሚያዩባቸዉ ጉዳዮች ተመልክቷል፡፡በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በራሳቸዉ አነሳሽነት ወይም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት አሳሳቢነት ወይም

ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ ጥያቄ ሲቀርብላቸዉ አንድን ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት ለማድረግ ይችላሉ፡፡በዚህ ድንጋጌ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አንድ ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ ሊያደርጉ የሚችሉት የትኞቹን ጉዳዮች እንደሆነ በግልጽ ባይደነገግም ከንኡስ አንቀጽ 2 ጋር አገናዝበን ካየን በንኡስ አንቀጽ 2 ስር ከተጠቀሱት ጉዳዮች ዉጭ በሌሎች ጉዳዮች ለማሳያነትም ጉዳዩ ዉስብስብ ነዉ ብለዉ ሲያምኑ ወይም ደግሞ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ ቢያዩ ትክክለኛ ፍርድና የሕግ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል ብለዉ ሲገምቱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት ማድረግ ይችላሉ፡፡ከዚህ አንጻር የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች በቀን 14/07/2012 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በጻፈዉ አቤቱታ ጉዳዩ በአምስት ዳኞች ይታይልኝ በማለት በግልጽ አልጠየቀም፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩን ሲመለከት የነበረዉ ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ እንዲደረግ ማሳሰቡን መዝገቡ አያሳይም፡፡ይልቁንም ከመዝገቡ የተገነዘብነዉ ጉዳዩን አምስት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ የተደረገዉ በፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት አነሳሽነት አመልካች በቀን 14/07/2012 ዓ/ም ጽፎ ላቀረበዉ አቤቱታ በተሰጠ ምላሽ ለሰበር አጣሪ ችሎት ሰብሳቢዉ ዳኛ በሰጡት ትእዛዝ ነዉ፡፡ይህም ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በአዋጁ አንቀጽ 21/1 የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ ከዚህ አንጻር የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡

ነገር ግን የአዋጁ አንቀጽ 21/1 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አንድን ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ ሊያደርጉ የሚችሉት መቼ ነዉ የሚለዉን በግልጽ አላመላከተም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት እየታየ ባለዉ አከራካሪ ጉዳይ ላይ ጉዳዩን ሲያዩ በነበሩት በችሎቱ ዳኞች በሙሉም ሆነ በአብላጫ ድምጽ የመጨረሻ ሊባል የሚችል ትእዛዝ ወይም ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛዉም ጊዜ ጉዳዩን ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ሰፊ ሥልጣን ለመስጠት ታስቦ እንደሆነ ይታመናል፡፡በመሆኑም የፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት በዚህ ረገድ የተሰጣቸዉን ሥልጣን ከመጠቀማቸዉ በፊት አስቀድሞ ጉዳዩ ተመርቶላቸዉ ጉዳዩን በዳኝነት ሲያዩ የነበሩት ዳኞች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ትእዛዝ/ዉሳኔ አለመኖሩን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡እንዲሁም አስቀድመዉ ጉዳዩን በዳኝነት ሲያዩ የነበሩ ዳኞች የሰጡትን ትእዛዝ/ዉሳኔ ዋጋ በሚያሳጣ አኳኋን ያንኑ ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲዳኙ ማድረግ እንዲችሉ ተጠቃሹ ደንጋጌ ሥልጣን አይሰጣቸዉም፡፡ከላይ እንደገለጽነዉ በቀን 30/06/2012ዓ/ም የተሰጠዉ ትእዛዝ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ትእዛዝ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም መታረም ያለበት በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሰረት በዳኝነት ታይቶ በመሆኑ ከዚህ ዉጭ በሆነ አኳኋን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበትን ትእዛዝ በአስተዳደራዊ ዉሳኔ ዉጤት እንዳይኖረዉ ማድረግ በሕግ ከተዘረጋዉ ስርዓት ዉጭ በዳኞች የተሰጠ ትእዛዝ/ዉሳኔ እንዳይፈጸም የሚያደርግ ዉጤት በማስከተል የዳኝነት ነጻነት መርህን ስለሚቃረን ተቀባይነት የሚሰጠዉ የዳኝነት ሥራ አመራር አይደለም፡፡በመሆኑም በቀን 30/06/2012ዓ/ም የተሰጠ ትእዛዝ ያለበት ጉድለት በዳኝነት ታይቶ ሳይታረም ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ ጉዳዩን

እንዲመረምሩ አስተዳደራዊ ዉሳኔ መስጠት በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 21/1 ስር የተሰጠዉን ሥልጣን በዳኝነት ሥራ ጣልቃ በሚያስገባ መልኩ በሰፊዉ በመተርጎም ተግባራዊ ማድረግ ስለሚሆን እና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 22/1 ስር የሰበር አቤቱታ ስለሚመረመርበትና ለሰበር የሚያስቀርብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የሚወሰንበትን ሥነ ሥርዓት አለመከተል ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ጉዳዩ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት እንዲታይ የሚደረግበት ዓላማ ጉዳዩን በአብላጫ ድምጽ መወሰን እንዲቻል ብቻ ሳይሆን ከጉዳዩ ባህርይ አንጻር ከአምስት ያላነሱ ዳኞች አከራካሪ የሆነዉን የሕግና የፍሬ ነገር ጉዳይ ቢመረምሩ አከራካሪዉን ነጥብ በአግባቡ በመለየት ሕግን መሰረት ያደረገ ፍትሀዊ ዉሳኔ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነ ነዉ፡፡ በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዳኞች የቀረበላቸዉን ጉዳይ በገለልተኛነት አይተዉ ዉሳኔ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡ገለልተኝነት ከሚረጋገጥበት መንገድ አንዱ አንድን ጉዳይ በዳኝነት የሚያዩ ዳኞች በዳኝነት የሚያዩትን ጉዳይ አስቀድመዉ በዳኝነት በማየትም ሆነ በሌላ ሁኔታ አቋም ያልያዙበትና ይሕንንም አቋማቸዉን ለሕዝብ ይፋ ያላደረጉ መሆን እንዳለባቸዉ በማድረግ ነዉ(አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 27(1/ሐ) ይመለከቷል)፡፡ ስለሆነም የሚሰየሙት አምስት ዳኞች ጉዳዩን አስቀድመዉ በዳኝነት አይተዉ አቋም የያዙ መሆን የለባቸዉም፡፡ ሆኖም በያዝነዉ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም ብለዉ አስቀድሞ በቀን 30/06/2012ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ አቋም የያዙ ዳኞች በድጋሚ በዚያዉ ጉዳይ ላይ ተሰይመዉ እንዲያዩ መደረጉ የገለልተኛነት መርህን ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ እነዚሁ ጉዳዩን የሚያዉቁ ዳኞች በተሰየሙበት ጉዳዩ መታየቱ ከዳኞች ቁጥር አንጻር ሲታይም በሕጉ አግባብ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዋል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በመዝገቡ ላይ አስቀድሞ ከተሰየሙት ሶስት ዳኞች አብላጫ ቁጥር ያላቸዉ የችሎቱ ዳኞች ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመበትም በማለት በቀን 30/06/2012 ዓ/ም በሰጡት ትእዛዝ መዝገቡ እንዲዘጋ ያዘዙ ቢሆንም በዚህ አግባብ በሁለቱ ዳኞች የተወሰነዉ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22/1 መሰረት ከችሎቱ ሶስተኛ ዳኛ ጋር ተገቢዉ ዉይይት ሳያደርግና የሶስተኛዉን ዳኛ የመወሰን ሥልጣን በሚያሳጣ መልኩ በመሆኑ ባልተሟሉ ዳኞች የተሰጠ ትእዛዝ ነዉ ብለናል፡፡ይህም የዉሳኔ አሰጣጥ ከትክክለኛ የዉሳኔ አሰጣጥ ተቃራኒ እና የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም ይህ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ትእዛዝ በዳኝነት ታይቶ ባልታረመበት ይህንን ትእዛዝ ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ጉዳዩን ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩ አስተዳደራዊ ዉሳኔ መሰጠቱና ጉዳዩን አምስት ዳኞች መርምረዉ በአብላጫ ድምጽ በተሰጠ ትእዛዝ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ተብሎ የታዘዘዉም በአዋጁ አንቀጽ 21/1 እና 22/1 ስር የሰበር አቤቱታ ስለሚመረመርበትና ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል? አልተፈጸመም ?የሚለዉን መርምሮ ለመወሰን የተዘረጋዉን ሥነ

ሥርዓት ካለመከተሉም በተጨማሪ ለዚህ ችሎት የቀረበበት አግባብ የዳኝነት ነጻነት መርህን የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡በሌላ በኩል በተፈጠረዉ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት የሰበር አቤቱታዉ በአግባቡ ባለመመርመሩና ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይም አልተፈጸመም የሚል ዉሳኔ በሕግ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ባለመሰጠቱ ምክንያት በተከራካሪ ወገኖች ላይ ፍትህ ሊዛባ ወይም ሊጓደል ስለማይገባ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ያለበት ትእዛዝ እና ይህንን ተከትሎ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ የሰጡት ትእዛዝ ተሽሮ አመልካች የሰበር አቤቱታዉን የዳኝነት ክፍያ መክፈል ሳይጠበቅበት አስቀድሞ በከፈለዉ ዳኝነት በአዲስ መዝገብ ላይ አቅርቦ ሊታይለት ይገባል ብለናል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ አቤቱታ ሲያቀርብ በሌላ የመዝገብ ቁጥር አዲስ መዝገብ ተከፍቶ አስቀድሞ ጉዳዩን ያላዩ ዳኞች በሕጉ በተመለከተዉ አግባብ በተሰየሙበት ችሎት አቤቱታዉ ተመርምሮ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም በሚለዉ ጭብጥ ላይ ተገቢዉ ዉሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡በመሆኑም በአብላጫ ድምጽ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 30/06/2012 ዓ/ም እና በቀን 29/07/2012 ዓ/ም የተሰጡ ትእዛዛት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 211/2 መሰረት ተሰርዘዋል፡፡

2. አመልካች የሰበር አቤቱታዉን አስቀድሞ በከፈለዉ ዳኝነት በድጋሚ ማቅርብ እንዲችል መብት ተጠብቆለታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ሲያቀርብ አቤቱታዉ በአዲስ መዝገብ ላይ በሌላ የመዝገብ ቁጥር እንዲከፈትና አስቀድሞ ጉዳዩን ያላዩ ዳኞች ለተሰየሙበት አጣሪ ችሎት እንዲመራና ችሎቱም አቤቱታዉንና ዉሳኔዉን መርምሮ ለሰበር የሚያበቃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም በሚል ነጥብ ላይ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ይስጥበት ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. ከላይ በዉሳኔ ተራ ቁጠር 2 ላይ በተመለከተዉ መሰረት ጉዳዩ በሚመራለት ችሎት ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የዉሳኔዉ ክፍል ብቻ ጉዳዩ ለሚመራለት ችሎት ሊቀርብ ይገባል፡፡ ሆኖም የፍርድ ዉሳኔዉ ግልባጭ ለግራ ቀኙ ሲጠይቁም ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

## የልዩነት ሀሳብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተሰየምን ዳኞች ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበበት አግባብ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት (procedural irregularity) የተፈፀመበት እና የዳኝነት ነፃነት የሚቃረን ነው በሚል ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ በአብላጫ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ላይ ባለመስማማት የልዩነት ሀሳባችንን እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

የክርክሩ መነሻ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገ የግንባታ ዉል አፈጻጸም የሚመለከት ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በሚል አመልካች ለሰበር ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ በመልስ እንዲሰጥ መደረጉን ተከትሎ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ ላይ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው ከሕግ እና ከሥነ-ሥርዓት ዉጪ ነው በሚል መቃወሚያ አቀርቧል፡፡

የተጠሪ መቃወሚያ መሰረት ያደረገዉ የአመልካች አቤቱታ ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር አጣሪ ችሎት ተሰምቶ የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም ተብሎ በአብላጫ ድምፅ ተወስኖ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት እንዲመለስ ከተባለ በኋላ የልዩነት ሀሳብ ያላቸው ዳኛ ልዩነት ሀሳብ አስፍረው መዝገቡን መመለስ ሲገባቸው አዘግይተዋል፡፡አመልካች በዚህ አጋጣሚ መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ለፌደራል ጠ/ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አቤቱታ አቅርቦ ፕሬዝዳንቷም ከህግ ውጪ አምስት ዳኞች እንዲያዩት አድርገዋል፡፡ይህም አካሄድ የዳኝነት ነፃነትና የሕግ የበላይነት የሚፃረር ነው፤ስለዚህም አምስት ዳኞች ተሰይመዉ በአብላጫ ድምፅ ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ የሰጡት ትዕዛዝ ተፈፃሚነት የለውም ተብሎ ውድቅ እንዲደረግ የሚል ነው፡፡ተጠሪ ያቀረበዉ መቃወሚያ ላይ በአመልካች በኩል የቀረበው መከራከሪያ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 21 መሠረት ስለመሆኑ በመግለፅ በአቀራረቡ ላይ የተፈፀመ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት የለም በሚል መቃወሚያው ውድቅ ተደርጎ በስረ ነገር ክርክር ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ አመልክቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ አምስት ዳኞች በተሰየሙበት አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለሰበር የቀረበበት ሂደት በመቃወም ተጠሪ ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት አለዉ ወይስ የለዉም (objection sustainable or not) የሚለውን ጭብጥ ችሎቱ መርምሯል፡፡ተጠሪ ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት አለው ሲል አብላጫው ድምፅ የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም የምንልበትን ምክንያት አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንመለከታለን፡፡

በመሰረቱ የሰበር ሥርዓት ዋነኛ ዓላማ ወጥነትና ተገማችነት ያለው የሕግ አተገባበር እና አተረጓጎም እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡በሌላ አነጋገር የሰበር ሥርዓት ተቀዳሚ ተግባር በአንድ ጉዳይ የቀረቡትን

ተከራካሪ ወገኖች መብትና ግዴታ ከማረጋገጥ ባሻገር በክርክር አመራር ስርዓት ወይም ሂደት እና በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ህጋዊነት እና የህግ የበላይነት መከበሩን እና ህጎች በሁሉም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ መደረጋቸዉን በማረጋገጥ ሰዎች በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዲኖራቸዉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነዉ፡፡ለዚህም ነዉ የሰበር ስርዓት ዓላማ ከተከራካሪ ወገኖች ፍላጎት ወይም በአንድ መዝገብ ከቀረበዉ ክርክር ባሻገር ተገማች የሆነ ፍርድ ማረጋገጥ ነዉ የሚባለዉ፡፡የሰበር ሥርዓት በፌደራልም ሆነ በክልል ፍርድ ቤቶች ተግባራዊ እንዲደረግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት መደንገጉ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ታስቦ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ይህንኑ ህገ መንግስት ድንጋጌ ተከትሎ የወጡት የፌደራል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የክልል ፍርድ ቤቶች አዋጆች የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘዉ እናገኛለን፡፡በእርግጥ ህጎቹ አስፈላጊና ዝርዝር ድንጋጌዎችን አሟልተዉ ባለመቀረጻቸዉ በክርክር አመራር ረገድ እንደአግባብነቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ወይም የወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚደረጉ ይታወቃል፡፡

የፌደራል ፍርድ ቤቶችን በተመለከተ የሰበር ሥልጣንና እና የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሰረታዊ ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 10 እና 22 ስር የተደነገገ ሲሆን ተጨማሪ መሰረተ ሀሳቦች በማሻሻያ አዋጆችም ተካተዉ እናገኛለን፡፡በዚህ ረገድ የሰበር ችሎቱ የህግ ትርጉም አስገዳጅነት (binding effect) እንዲኖረዉ አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(4) ላይ የተደነገገዉ ተጠቃሽ ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 25/88 እንደተደነገገው በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩ ለሰበር የሚቀርበው ሦስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን ስለመሆኑ በአንቀፅ 10 እና 22(1) ላይ ተመልክቷል፡፡ ችሎቱ አቤቱታዉን መርምሮ ዉሳኔዉ ለሰበር የሚያበቃ የሕግ ስህተት የለውም ብሎ ካመነ አቤቱታውን ዉድቅ ማድረግ እንደሚችል የዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አለው ወይም የለውም የሚል ውሳኔ የሚሰጠው ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት (በተለምዶ ሰበር አጣሪ ችሎት ተብሎ የሚታወቀዉ ማለት ነዉ) እንደመሆኑ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓትም በአዋጁ የተለየ ድንጋጌ ባለመኖሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ የሚመራ መሆኑ ልብ ይለዋል፡፡የሰበር አጣሪ ችሎት ውሳኔ እንደማናቸውም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚታይ እና የፍርድ አሰጣጥና አፃፃፍ ሥርዓት ተከትሎ መፈፀም እንዳለበት አከራካሪ አይደለም፡፡በዚህ ረገድ ዉሳኔዉ ስርዓቱን ያሟላ መሆን አለመሆኑ ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 180 እና 181 አንጻር መታየት አለበት ሲል አብላጫ ድምጽ የሰጠዉ ምክንያት እኛም የምንስማማበት ነዉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ አቤቱታዉ የተመራለት ሦስት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሰምተዉ በ30/06/2012 ዓ.ም አቤቱታዉ ለሰበር አያስቀርብም በማለት በአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ሰጥተዋል የሚል መከራከሪያ ነጥብ በተጠሪ በኩል ቀርቧል፡፡መዝገቡ ጋር የተያያዘዉ ትእዛዝ ይዘት ሲታይ በተጠቀሰው ዕለት በመዝገቡ ላይ ከተሰየሙት ሶስት ዳኞች ሁለቱ ዳኞች አቤቱታዉ

ለሰበር አያስቀርብም በሚል ትእዛዝ ሰጥተዉ ፊርማቸዉን ያኖሩ ቢሆንም አንደኛው ዳኛ **"<u>የሀሳብ ልዩነት ከመስጠቱ በፊት ለመነጋገር</u>"** (ሥርዝ የተጨመረበት) የሚል ጽሁፍ የሰፈረበት ስለመሆኑ እንጂ ዳኛዉ የልዩነት ሀሳባቸው አልገለፁም ወይም በአብላጫ ድምፅ ተስማምተው ፊርማቸውን አላስቀመጡም፡፡ ይህም፣ በአብላጫዉ ድምጽ ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉም በጉዳዩ ላይ በቂ ዉይይት ተደርጎ የሁሉም ዳኞች ሃሳብ በአግባቡ ተንሸራሽሮ አቋም ያልተያዘበት መሆኑን አመላካች ነዉ፡፡ በጉዳዩ ላይ ውይይት አለመጠናቀቁን ብቻ ሳይሆን በችሎቱ የተሰየሙት ሦስት ዳኞች በተመሳሳይ ድምፅ ወይም በአብላጫ ድምፅ ዉሳኔ ስለመስጠታቸው በፊርማቸው ያላረጋገጡ መሆኑንም የሚያሳይ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የሰበር አጣሪ ችሎት ውሳኔ ሰጥቶበታል ሊባል የሚችለው በችሎቱ የተሰየሙት ሦስቱም ዳኞች በአብላጫ ድምጽ ወይም በተመሳሳይ (ያለ ልዩነት) ድምጽ ውሳኔ መስጠታቸውን በፊርማቸው ማረጋገጥ ሲችሉ ነው፡፡የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 181(2 እና 3) ይመለከታል፡፡በመሆኑም የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጥቷል የተባለው ውሣኔ በሦስት ዳኞች ፊርማ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ ውሳኔ እንዳልተሰጠ ይቆጠራል ሲል ይህ ሰበር ችሎት የሰጠው የህግ ትርጉም ይህንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ ሰበር መ/ቁ 73696 ቅጽ 13 ይመለከታል፡፡ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ አብላጫው ድምፅ እንደሚለው የሥነ-ሥነዓት ጉድለት (procedural irregularity) ያለበት ነዉ ተብሎ በስነ ስርዓት ህጉ የሚታረም ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ ዉሳኔ ስለሆነ ዉሳኔው እንዳልተሰጠ ይቆጠራል የሚል  አቋም ወስደናል፡፡

ጉዳዩ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አመልካች መዝገቡ ባልታወቀ እና ባልተለመደ ሁኔታ ከቀጠሮ ውጪ ሆኖ በመቆየቱ ፍትህ ተጓድሎብኛል በሚል በ14/7/2012 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ማቅረባቸውን ተለትሎ በዚህ አቤቱታ መነሻ መዝገቡ ላይ ተጨማሪ ሁለት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት መደረጉን መዝገቡ ያሳያል፡፡ የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት አምስት ዳኞች እንዲያዩት ማድረጋቸው ከህግ ዉጪ ነው ሲል ተጠሪ ያቀረበው መከራከሪያ በአብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ላይ አልተስማማንም፡፡በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ጉዳይ ላይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት የሚደረገዉ በሁለት አግባብ ወይም መንገድ ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 21(1 እና 2) ድንጋጌዎች የምንገዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ አንደኛዉ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ በሰበር ችሎት የሚታይበትን አግባብ አስመልክቶ በህግ የተመለከቱ ሁኔታዎችን ተከትሎ ሲሆን ሁለተኛዉ ጉዳይ ደግሞ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በተሰጠዉ ስልጣን የሚወሰን ይሆናል፡፡ አንድ ጉዳይ በአምስት ዳኞች እንዲታይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ለወስንበት አግባብ የሚደነግገዉ የአዋጁ አንቀጽ 21/1/ **የፌዴራል ጠ/ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት በራሱ አነሳሽነት ወይም በፌደራል ጠ/ፍርድ ቤት ችሎት አሳሳቢነት ወይም ከተከራካሪ ወገኖች ባንዱ ጥያቄ ሲቀርብለት አንድን ጉዳይ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ማድረግ እንደሚችል** ተመላክቷል፡፡ ይህ

ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነዉ በየትኛዉ ችሎት እና ጉዳይ ላይ ነዉ የሚለዉን ድንጋጌዉ በግልጽ ለይቶ ያላስቀመጠ በመሆኑ ሊኖረዉ የሚችለዉ አንድምታ ከሶስቱ አንደኛዉ ምክንያት መኖሩ ሲረጋገጥ በየትኛዉም የፍርድ ቤቱ ችሎት እና በማናቸዉም ጉዳይ ላይ ተፈጻሚ ለማድረግ እንደሚቻል ለፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት የተተወ ፈቅደ ስልጣን መሆኑን ያሣያል፡፡ነገር ግን የዚህ ፈቅደ ስልጣን አተገባበር የዳኝነት ነጻነትን በማይነካ አኳኋን በጥንቃቄ እና በጠባቡ ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አቤቱታዉ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ በሰበር አጣሪ እንዲታይ የተደረገው በአመልካች አቤቱታ መነሻ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ሦስት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር አጣሪ ችሎት በአንድ በኩል ተጨማሪ ዉይይት እንዲደረግበት በተገለጸበት ትዕዛዝ ላይ ጉዳዩ ዉይይት ተደርጎበት አቋም እንደተያዘበት ተደርጎ በሁለቱ ዳኞች መፈረሙ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ ሳይመለስ በእንጥልጥል ላይ መቆየቱ አመልካች ሂደቱን እንዲጠራጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ በዉጤቱ ላይ አመኔታ እንዳይኖረዉም ምክንያት ይሆናል፡፡ አዋጁ ከላይ በተመለከተዉ ድንጋጌ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አንድ ጉዳይ በአምስት ዳኞች እንዲታይ መወሰን እንደሚችል ስልጣን ከተሰጠባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ በእንደዚህ መሰል ጉዳዮች ምክንያት ሊፈጠር የሚችለዉን የፍትሕ መጓደል ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ለማስቀረት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ተጨማሪ ውይይት ለማድረግ በሚል ጊዜ በመውሰዱ እና መዝገቡ በእንጥልጥል በመቆየቱ ፍትህ ተጓድሎብኛል በሚል አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ፕሬዝዳንቷ ተቀብለዉ ጉዳዩ በአምስት ዳኞች እንዲታይ ማድረጋቸው ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ጣልቃ እንደመግባት የሚያስቆጥር ሆኖ አላገኘንም፡፡ ይልቁንም የጉዳዩ ባህርይ እና የቀረበዉን አቤቱታ መሰረት በማድረግ አምስት ዳኞች እንዲያዩት ማድረጋቸዉ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 16/1/ እና 21/1/ መሠረት ያደረገ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

እንዲሁም ቀደም ሲል ሁለቱ ዳኞች የሰጡት ዉሳኔ ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ እንዳልተሰጠ ይቆጠራል የሚለዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞቹ የሰጡት ዉሳኔ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ (web site) እና መረጃ ቋት (data base) ተመዝግቧል የሚለዉ የተጠሪ ክርክር ስንመለከት በስነ ስርዓት ህጉ የተደነገገዉን የዉሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ተከትሎና ተሟልቶ የተሰጠ ዉሳኔ አለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ መለቀቁም ሆነ በመረጃ ቋት መመዝገቡ በራሱ ዉሳኔዉን የተሟላ እና አስገዳጅ ሊያደርገዉ አይችልም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መረጃዉ የተለቀቀበት አካሄድ ስህተት እንደነበር እና ስህተቱም የተፈጠረዉ በፍርድ ቤቱ የመረጃ ክፍል ሰራተኞች ስለመሆኑ በወቅቱ ከፍርድ ቤቱ የተሰጠዉ መግለጫ ያሣያል፡፡ የችሎቱ ዳኞች ቀደም ሲል በቂ ውይይት አድርገዉ አቋም የወሰዱበት መሆኑን ካመኑበት ከሌሎች ዳኞች ጋር በድጋሚ አንሰየምም ወይም ከችሎቱ እንነሳለን ማለት ይጠበቅባቸዉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ሁለቱ ዳኞች በጉዳዩ ላይ ከሌሎች ዳኞች ጋር ተሰይመው ማየታቸው አስቀድሞ የመጨረሻ ውሳኔ አለመስጠታቸው እንዲሁም በጉዳዩ ላይ በቂ ዉይይት ተደርጎበት በአግባቡ

ሃሳብ ተንሸራሽሮበት አቋም ያልተያዘበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ጉዳይ በ30/06/2012ዓ.ም የመጨረሻ ዉሳኔ ተሰጥቶበት እና መዝገቡ ተዘግቶ እያለ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ሌሎች ሁለት ዳኞች ተጨምረዉ አምስት ዳኞች ተሰይመዉ እንዲያዩት ማድርጋቸዉ እና በዚህ አግባብ አቤቱታዉ ለዚህ ሰበር ችሎት መቅረቡ ከህግ ዉጪ ነዉ በማለት ተጠሪ ያቀረበው መከራከሪያ መዝገቡ ዉስጥ ያለዉን እዉነታ ያገናዘበ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ብለናል፡፡

በአጠቃላይ የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ባልተሟላ ዳኛ የተሰጠ በመሆኑ ውሳኔዉ እንዳልተሰጠ የሚቆጠርና ተፈጻሚነት የሌለዉ መሆኑን እንዲሁም ጉዳዩ በአምስት ዳኞች እንዲታይ የተደረገዉ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 21(1) መሠረት መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ በሂደቱ ላይ የስነ ስርዓት ግድፈትም ሆነ ከህግ ዉጪ የተፈጸመ ተግባር ባለመኖሩ ተጠሪ ያቀረበው ተቋውሙሞ ውድቅ ተደርጎ በስረ ነገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት ይቻላል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰናል፡፡ ስለዚህም አብላጫዉ ድምጽ አቤቱታዉ ለሰበር ችሎት የቀረበዉ ከህግ አግባብ ውጪ ነው በማለት አቤቱታዉ እንደገና በሌላ ሰበር አጣሪ ችሎት እንዲታይ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የልዩነት ሀሳባችንን አጠቃለናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 193215

ቀን 25/05/2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-አቶ በቀለ ኢሳያስ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ በረከት እንዳሻው

2. አቶ አንዱአለም ስለሺ

3. ወ/ሪት ቤተልሔም ስለሺ

4. ተማሪ ናትናኤል ስለሺ

5. አቶ መሪሁን መኮንን

(1-5) አልቀረቡም

6. ወ/ሮ መረተች መኮንን ቀረቡ

7. ወ/ሮ እመቤት እንዳሻው

8. ወ/ሮ ታምሯ እንዳሻው

(7-8) አልቀረቡም

9. ወ/ሮ ንግስት እንዳሻው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ፍርዱን በሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት የተፈጸመ ሀራጅ እንዲፈርስ በማመልከት የተከራከሩ ሲሆን 5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብት በመሆን ፣ከተራ ቁጥር 7 እስከ 9 የተጠቀሱት የፍርድ ባለእዳ በመሆን እንዲሁም አመልካች በሐራጅ የተሸጠዉ ቤት ገዥ በመሆን በክርክሩ የተሳተፉ ናቸዉ፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ባቀረቡት አቤቱታ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20628 ላይ በሟች ወ/ሮ በየነች ንጉሴ ስም በአዲስ አበባ

ከተማ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ቀጠና 8 ውስጥ የሚገኝ ቤት የውርስ ሀብት እንደሆነ በመግለጽ በወራሾች መካከል በስምምነት ክፍፍል እንዲፈጸም ይህ ካልሆነ በሐራጅ ተሸጦ የፍርድ ባለመብትና ባለእዳ ሆነዉ የተሰየሙ ተከራካሪዎች እኩል እንዲካፈሉ በማለት በቀን 06/07/2010 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ዉሳኔ መሰረት በተሰጠ የፍርድ አፈጻጸም ትእዛዝ በወጣ የሐራጅ ማስታወቂያ መነሻ አመልካች በጨረታ ተሳትፈዉ በቀን 09/12/2010 ዓ/ም ቤቱን በብር 208,000.00 ገዝተዋል፡፡ አመልካች የሽያጨን ገንዘብ ገቢ አድረገዉ የቤቱ ስመ ሀብት በስማቸዉ ከመዞሩ በፊት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ፍርዱን በመቃወም አቤቱታ በማቅረባቸዉ አፈጻጸሙ ታግዶ መዝገቡ ተዘግቶ ቆይቷል፡፡

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ፍርዱን በመቃወም በመ/ቁጥር 20628 ላይ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ በተጠሪዎች መካከል ክርክር ተደርጎ በቀን 21/03/2011 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በዉርስ ሀብቱ ላይ ድርሻ እንዳላቸዉ በመግለጽ ከሐራጅ ሽያጩ ገንዘብ ላይ እንዲካፈሉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት ዉሳኔዉን አሻሽሎ ወስኗል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻ እነዚህ ተጠሪዎች ወራሾች በመሆናቸዉ ሁሉም ተጠሪዎች ተጠቃሹን የጋራቸዉ የሆነዉን የዉርስ ሀብት የሆነ ቤት በስምምነት እንዲካፈሉ፣ስምምነት ላይ ካልደረሱ በሕጉ መሰረት በሀራጅ ተሸጦ እንዲካፈሉ በማለት የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74413 ላይ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

ከላይ የተጠቀሰዉን ዉሳኔ ተከትሎ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች የውርስ ሀብት በሆነው ቤት ላይ ድርሻ እንዳለን በፍርድ ስለተረጋገጠ የአፈጻፀም ክርክሩ ተካፋይ ባልሆንበት የተካሄደው ሀራጅ የቀደምትነት መብታችንን የጎዳ፣ቤቱም በአነስተኛ ገንዘብ የተሸጠ በመሆኑ ሀራጁ እንዲፈርስ እንዲታዘዝልን እና ይህ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት የፍርድ አፈፃፀሙ እንዲጀመር ተደርጎ ሐራጁም በድጋሚ እንዲወጣ እንዲታዘዝልን በማለት የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 444 ጠቅሰዉ አቤቱታ ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ለዚህ አቤቱታ በተራ ቁጥር 6 እና 7 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ይህ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20628 ላይ በቀን 21/03/2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ከውርስ ሀብቱ ሽያጭ ድርሻቸውን እንዲያገኙ አለ እንጂ ሽያጩ እንደ አዲስ ተከናውኖ ክፍፍል ይፈፀም ሲል የሰጠው ውሳኔ የለም፡፡ በመሆኑም አቤቱታዉ ውድቅ ተደርጎ በቀድሞ ትዕዛዝ መሰረት በፍርድ ቤቱ እጅ ያለው ገንዘብ ለወራሾቹ ክፍፍል ሊደረግ ይገባል በማት ተከራክረዋል፡፡ ከተራ ቁጥር 7 እስከ 9 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ደግሞ ፍርድ ቤቱ በሕግ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ ቢሰጥ አንቃወምም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአሁን አመልካችም በአቤቱታዉ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጎ በሰጡት መልስ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሐራጅ እንዲፈርስ ያቀረቡት ጥያቄ ጊዜዉ ያለፈበትና የሥነ ሥርዓት

ሕጉን አንቀጽ 444/1 እና 447/1 የሚቃረን ከመሆኑም በተጨማሪ የሐራጅ ሽያጩን የሚያስፈርስ ምክንያት ስለሌለ አቤቱታዉ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርዱን እያስፈጸመ የሚገኘዉ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 24263 ላይ ግራ ቀኙን ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ሰምቶ በቀን 07/05/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ መጀመሪያ በመ/ቁጥር 20628 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ በቀን 21/03/2011ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ተሻሽሎ የተወሰነዉ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች የዉርስ ሀብት የሆነዉ ተጠቃሹ ቤት በሀራጅ ተሸጦ ከተገኘዉ ገንዘብ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ የሚል እንጂ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ የሚል ዉሳኔ እንዳልሆነ፤በሀራጅ ሽያጩ ተሳታፊ አለመሆን የሐራጅ ሽያጩን የሚያስፈርስ ምክንያት እንዳልሆነ፤በጨረታ ተወዳዳሪ ሆነዉ ሳይቀርቡ የቀደምትነት መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚሉ ምክንያቶችንና የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ አቤቱታ ያቀረቡት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥ 447/1 ስር የተደነገገዉ የሁለት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ የሚሉ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም በማለት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በይኗል፡፡

ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 74456 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም በሰጠው ዉሳኔ ፍርዱ መፈጸም ያለበት ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት ሊሆን እንደሚገባ፤በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 447/1 ስር የተደነገገው የ2 ወር የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነት በአፈፃፀም ክርክሩ ተሳታፊ በነበረ ሰዉ ላይ እንጂ በአፈጻጸም ክርክር ተሳታፊ ባልሆኑት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተጠቀሱ ተጠሪዎች ላይ አለመሆኑን፤ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ፍርዱን በመቃወም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ አፈጻጸሙ ታግዶ በመቆየቱና በጉዳዩ ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተሻሽሎ ከተወሰነ በኋላ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሐራጁ እንዲፈርስ አቤቱታ ያቀረቡት የሁለት ወር ጊዜ ሳይደርስ በመሆኑ፤በተቃውሞ መሰረት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከማረጋገጡ በፊት ሐራጁ እንዲፈርስ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች አቤቱታ ማቅረብ ስለማይችሉ፤ የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን በፊት ቀዳሚ ሆነው በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1261/1 እና ከቁጥር 1386-1409 የተደነገገ መሆኑን፤ እንዲሁም ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ቤት በስምምነት ለመከፋፈል ካልቻሉ ቤቱ እንዲሸጥ ትዕዛዝ ሲሰጥ በቀረበው የቤቱ መነሻ ግምት ላይ ክርክር የማቅረብ መብት ስላላቸዉ አከራካሪው የውርስ ቤት የተሸጠበት ዋጋ በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት ያነሱት ክርክር ተገቢነት ያለው ነዉ የሚሉ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሐራጁ እንዲፈርስ ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ዋናዉ ፍርድ ተሻሽሎ በተወሰነዉ መሰረት የተከናወነውን ሽያጭ በማፍረስ ፍርድ ያረፈበትን የውርስ ሀብት

የሆነዉን ቤት ባለመብቶች በስምምነት እንዲከፋፈሉ ፤ ስምምነት ላይ ካልደረሱ በሕጉ መሰረት ሐራጅ እንዲወጣ በማድረግ እንዲሁም የቀደምትነት እና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ከቀረቡ በሕጉ መሰረት በመመርመር አፈጻጸሙን እንዲመራ ጉዳዩን ለሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 186757 ላይ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት በቀን 21/11/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸው ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች በግልፅ በሐራጅ ጨረታ የተሸጠ ንብረት በዝቅተኛ ዋጋ የተሸጠ ነው በሚል ሽያጩን በማፍረስ የሰጡት ውሳኔ በሰ.መ.ቁጥር 37503(ቅጽ 8) ፣በሰ.መ.ቁጥር 39175(በቅፅ 16) እና በሰ.መ.ቁጥር 945571 ላይ የአንድ ንብረት ከፍተኛ ወቅታዊ ዋጋ እንዲሁም ትክክለኛ ዋጋ ንብረቱ በጊዜው በሐራጅ ለሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ነዉ ሲል የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በግልፅ የሚቃረን ነዉ፡፡አመልካች ቤቱን በጨረታ የገዛሁት ከስምንት ተጫራቾች ጋር በመወዳደር ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቤቱ ጉዳዩን ሳያጤን በዝቅተኛ ዋጋ ተሽጧል ተብሎ የቀረበዉን አቤቱታ መቀበሉ ስህተት ነዉ፡፡ ቀደም ሲል የውርስ ሀብቱ ሲጣራ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በወራሽነት ተለይተው የውርስ መብታቸው ተጠብቆ የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ በአፈጻጸም መዝገብ እየተደረገ የነበረዉን ጨረታ እያወቁ ሳይቃወሙ እንደቆዩ እየታወቀ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 444/1 ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሸጡ በፊት ነዉ የሚለዉን በተቃረነ መልኩ በተጠናቀቀ ጨረታ ላይ የቀረበዉን አቤቱታ በመቀበል የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ሽያጩ ከተካሄደ ከአራት ወራት በኋላ ሽያጩ እንዲፈርስ መደረጉ እና የ2 ወር የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ጨረታው ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ሲገባ በዋናው መዝገብ ቀድሞውኑ በተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችን እንደአዲስ የሚወሰን ነገር እንደነበር በማስመሰል ያቀረቡትን ያልተገባ ምክንያት መሰረት በማድረግ የአመልካች የይርጋ መከራከሪያ ታልፎ ጨረታው እንዲፈርስ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የቀደምትነት ጥያቄ በሌለበት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ቀደምትነትን በተመለከተ ምንም ውሳኔ ባልሰጠበት ተጠሪዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 447(1 እና 3) ስር የተደነገገዉን በመፃረር እና በሰ.መ.ቁጥር 31963 እና 97206 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሚቃረን መልኩ በጨረታ ሂደት የተፈጸመ የማጭበርበር ወይም በጨረታ ስነ ስርዓቱ ላይ የተፈፀመ ግዙፍ የሆነ ጉድለት እና ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር በሌለበት ጨረታዉ እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 443 እና 447 አንጻር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር የሰጠዉን ትእዛዝ ተከትሎ ተጠሪዎች በተናጠል እና በጋራ በቀን 24/02/2013 ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሱት መከራከሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የተወሰነዉ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም ሆኖ እያለ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረቡት የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ የተመለከተዉ የሶስት ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ አቤቱታዉ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንዲሁም በዋናዉ ጉዳይ ላይ ከ5ኛ እና 6ኛ ተጠሪዎች በስተቀር ሁሉም ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ትእዛዝ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ዋናዉን ፍርድ በመቃወም በፍ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡትን መቃወመሚያ በመቀበል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20628 ላይ በቀን 21/03/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል ከዉርስ ሀብቱ ሽያጭ ላይ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ በሚል ወስኗል፡፡ሆኖም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በመቅረቡ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 74413 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ባልተሳተፉበት በተደረገ ሐራጅ ከተሸጠ ቤት ገንዘብ ላይ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነዉ በማለት ዉሳኔዉን አሻሽሎ ቤቱ ለተጠሪዎች የጋራ የዉርስ ሀብት በመሆኑ ከተቻለ በስምምነት፤ስምምነት ከሌለ በሐራጅ እንዲሸጥ በተወሰነዉ መሰረት እንዲፈጸም የተደረገ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ሐራጁ የተከናወነው በቀድሞ ውሳኔ መሰረት በመሆኑ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ዉሳኔ ከማግኘቱ በፊት በመሆኑና በመቃወሚያዉ ላይ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ታግዶ በነበረዉ የፍርድ አፈጻጸም ላይ መቃወሚያ ወይም ሐራጁ እንዲፈርስና የቀደምትነት መብት እንዲከበር ለመጠየቅ የሚቻልበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ቤቱ ከመሸጡ በፊት ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ክርክር አቅርበዉ በፍርድ ያገኙት መብት ባለመኖሩ መቃወሚያቸዉን ተከትሎ ጉዳዩ ዉሳኔ ካገኘ በኋላ ሐራጅ እንዲፈርስ አቤቱታ ያቀረቡት በሕጉ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ ሳያልፍ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ሐራጁ እንዲፈርስ በመወሰናቸዉ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በሌላ በኩል በ5ኛ እና 6ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሱ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ በአግባቡ ስለሆነ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ተሽሮ የስር የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታ ሳያቀርቡ የሶስት ወር ጊዜ ያለፈባቸዉ በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ

ቤቶች ዝግ ሆነዉ በመቆየታቸዉ ምክንያት እንደሆነ በመግለጽና ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተም አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሎ ከያዘዉ ጭብጥ፣ ከግራ ቀኝ ክርክር እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል ፡፡

በመጀመሪያም አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሕጉ በተመለከተዉ 90 ቀናት ዉስጥ ስላላቀረቡ አቤቱታቸዉ ሊሰረዝ ይገባል በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ መርምረናል፡፡አመልካች ለዚህ መቃወሚያ በሰጡት መልስ አቤቱታቸዉን በ90 ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ያልቻሉት በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ ቤቶች ዝግ ሆነዉ በመቆየታቸዉ ምክንያት ስለሆነ አቤቱታዬ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ በአገራችን መከሰቱን ተከትሎ የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለዉን ጉዳት ለመቀነስ የወጣዉን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 466/2012 ወጥቶ ሥራ ላይ ዉሎ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በተጠቃሹ ደንብ አንቀጽ 2/2 እና 3/1 ስር እንደተደነገገዉ ከአራትና ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ቦታ በአካል መገኘት ለቫይረሱ ስለሚያጋልጥ ለመንግስታዊ ሥራም ሆነ በደንቡ ለተመለከቱ ተግባራት መሰብሰብ የተከለከለ ነዉ፡፡ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት አሰጣት ከአራት ሰዉ በላይ በአንድ ቦታ እንዲሰባሰብ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩን፣የወረቀት ቅብብሎሽ ለቫይረሱ አጋላጭ መሆኑንና ከየክልሉ ከከተማ አስተዳደሮች የሚመጡ ባለጉዳዮች ትራንስፖርት ተጠቅመዉ ሲመጡ ለቫይረሱ እንዲጋለጡ የሚያደርግ አጋጣሚ እንደሚፈጥር ታሳቢ በማድረግ የተጠቀሰዉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና ደንብ ከመጽናቱ በፊትና በኋላ በቀን 09/07/2012 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ በወጣዉ መግለጫ ፤በመቀጠል በቀን 23/07/2012 ዓ/ም፣በቁጥር W/1-38/8434 በቀን 30/08/2012 ዓ/ም፣በቁጥር ህ/ግ/0012 በቀን 28/09/2012 ዓ/ም ባወጣቸዉ መግለጫዎች የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በከፊል ዝግ አድርጎ አቆይቷል፡፡ ቀጥሎም በቀን 10/11/2012 ዓ/ም ባወጣዉ የሥራ መመሪያ እና ባወጣዉ መርሀ ግብር መሰረት ከታህሳስ 10 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ የመጨረሻ ዉሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ ከነሐሴ 01 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ መዝገብ የመክፈት ሥራ እንደሚጀምር ገልጿል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ የተሰጠዉ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታ ጽፈዉ ያቀረቡትና ፋይል ያስከፈቱት በቀን 21/11/2012 ዓ/ም ነዉ፡፡ ምንም እንኳን በመካከሉ ያለዉ ጊዜ ሲታይ አመልካች አቤቱታቸዉን ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22/4 ላይ የተመለከተዉ የ90 ቀናት ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢሆንም ይህ የ90 ቀን ጊዜ ያለፈዉ በአመልካች ጉድለት

ምክንያት ሳይሆን ከላይ በተገለጸዉ አግባብ ከዓቅም በላይ በሆነ ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ምክንያት ፍርድ ቤቶች መዝገብ የመክፈት አገልግሎት እንደማይሰጡ በይፋ ለሕዝብ በማሳወቅ በከፊል ዝግ ሆነዉ በመቆየታቸዉ ምክንያት ነዉ፡፡ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ያቋረጠዉን አገልግሎት አሰጣጥ ለመጀመር ባወጣዉ መመሪያና መዛግብት የሚከፈቱበት ጊዜ ነዉ ብሎ ባወጣዉ የሥራ መርሀ ግብር መሰረት አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በማቅረብ መዝገብ ስላስከፈቱ 1ኛ አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን መቃወሚያ አልተቀበልንም፡፡

ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ የያዝነዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ አመልካች የተጠሪዎች የዉርስ ሀብት የሆነዉን ቤት በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በተሰጠ ትእዛዝ ቤቱን በብር 208,000.00 የገዙት በቀን 09/12/2010 ዓ/ም በተከናወነ ሐራጅ ነዉ፡፡ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ደግሞ በዋናዉ መዝገብ ላይ የተሰጠዉን ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ተቃዉመዉ ያስወሰኑት በመጀመሪያ በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20628 ላይ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በቀን 21/03/2011 ዓ/ም ነዉ፡፡እንዲሁም ይሄዉ ዉሳኔ በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74413 ላይ በይግባኝ አሻሽለዉ ያስወሰኑት ደግሞ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም ነዉ፡፡ይህም የሚያሳየዉ ቤቱ በሐራጅ ለአመልካች የተሸጠዉ በተሸጠዉ ቤት ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች የዉርስ ድርሻ አላቸዉ ተብሎ ከመወሰኑ በፊት መሆኑን ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በዉርስ ሀብቱ ላይ ድርሻ አላቸዉ ተብሎ ከመወሰኑ በፊት ወራሾች ናቸዉ ተብሎ ስለተወሰነላቸዉ የዉርስ ሀብት ከፍፍል ለማስፈጸም ሲደረግ የነበረዉን የፍርድ አፈጻጸም እያወቁ ሳይቃወሙ እንደቀሩ በመግለጽ ያቀረቡትን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ስለማያሳዩ ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን ቅሬታ አልተቀበልንም፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች አከራካሪዉን ቤት በሐራጅ የገዙት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ፍርዱን በመቃወም የዉርስ ሀብቱ ላይ ድርሻ እንዳላቸዉ ከማስወሰናቸዉ በፊት መሆኑ ከተረጋገጠ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ማድረግ አስፈላጊ ነበር ወይ ለሚለዉ ነጥብ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ለተጠቀሱ ተጠሪዎች በፍርድ የተረጋገጠላቸዉ መብት ምንድን ነዉ የሚለዉን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የስር የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ባቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ መነሻ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በመ/ቁጥር 20628 ላይ በቀን 21/03/2011 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ የተወሰነላቸዉ ከዉርስ ሀብቱ ሽያጭ ላይ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ በመሆኑና ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች የሐራጅ ሽያጩ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ዉስጥ ሐራጁ እንዲፈርስ አቤቱታ ስላላቀረቡ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ ይህ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ ታይቶ በመ/ቁጥር 74413 ላይ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ተሻሽሎ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ

ተጠሪዎች ባልተሳተፉበት በተደረገ ሐራጅ ከተሸጠ ቤት ገንዘብ ላይ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነዉ ተብሎ ቤቱ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ለተጠቀሱ ተጠሪዎችና ለተቀሩት ተጠሪዎች የጋራ የዉርስ ሀብት በመሆኑ ከተቻለ በስምምነት፤ስምምነት ከሌለ በሐራጅ እንዲሸጥ በማለት ወስኗል፡፡ስለሆነም በዚህ መልኩ ከመወሰኑ በፊት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሐራጁ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት ስለማይኖራቸዉ ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ሐራጁ እንዲፈርስ በመጠየቅ ያቀረቡትን አቤቱታ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋናዉን ጉዳይ በይግባኝ አይቶ በመ/ቁጥር 74413 ላይ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም አሻሽሎ ከሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር መርምሮ መወሰን ሲገባዉ በዚህ ዉሳኔ መሰረት አይቶ አለመወሰኑን ነዉ፡፡

በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ስለ ፍርድ አፈጻጸም በሚደነግገዉ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር ካሉ ድንጋጌዎች እንደምንረዳዉ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ፍርዱን ማስፈጸም ያለበትና በፍርድ አፈጻጸም ሂደት የተከናወኑ ተግባራትን በመቃወም የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ መወሰን የሚገባዉ ፀንቶ ከሚገኘዉ የፍርድ ዉሳኔ አንጻር ሊሆን ይገባል፡፡እንደሚታወቀዉ አንድ የፍርድ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ይሄዉ የፍርድ ዉሳኔ ፍርዱን በሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም/እና በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ወይም/እና በሰበር ሰሚ ችሎት በሚሰጡ ዉሳኔዎች ተለዉጦ ሊወሰን ይችላል(የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 6፣360/2፣348/1 እና አዋጅ ቁጥር 25/1996 10 እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ)ይመለከቷል፡፡)፡፡ ዳግመኛ ዳኝነት የተጠየቀበት፣ተቃዉሞ፣ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የቀረበበት ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 6፣332፣ 359/4፣ 418/4 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ድንጋጌዎች መሰረት ሳይፈጸም ታግዶ እንዲቆይ ካልተደረገ በስተቀር ፍርዱን፣ዉሳኔዉን ወይም ትእዛዙን በተሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም/እና ጉዳዩን በይግባኝ ባየዉ ፍርድ ቤት ወይም/እና በሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ እስከሚለወጥ ድረስ ሊፈጸም የሚችልበት አግባብ መኖሩን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት ከዳኝነት ነጻነት ገጽታዎች መካከል አንዱ የዳኝነት አካሉ የሰጠዉን ዉሳኔ ማስፈጸም መቻሉ በመሆኑና የሥነ ሥርዓት ሕጋችንም ጸንቶ የሚገኝ ፍርድ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ እስካልታገደ ድረስ መፈጸም አለበት የሚል አቋም በመያዙ ምክንያት ነዉ፡፡ ይህ ማለት ግን ፍርዱ፣ዉሳኔዉ ወይም ትእዛዙ በተለይም በይግባኝ ታይቶ እስከሚሻሻል ወይም እስከሚለወጥ ድረስ በሚኖረዉ የክርክር ሂደት ፍርዱ፣ዉሳኔዉ ወይም ትእዛዙ ተፈጽሞ የተወሰደ ነገር ካለ ሥነ ሥርዓት ሕጉ መፍትሔ አላስቀመጠም ማለት አይደለም፡፡ለዚህ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ያስቀመጠዉ መፍትሔ በቁጥር 349 ስር የተደነገገዉ አንዱ ሲሆን ይኸዉም ይግባኝ የተባለበት ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ የተሻሻለዉ ወይም የተለወጠዉ ፍርድ ወይም ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በነበረዉ የመጀመሪያ

ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ትእዛዝ መሰረት የተወሰደ ነገር እንዲመለስ ነገሩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየዉ ፍርድ ቤት ተስማሚ ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት የሚደነግገዉ ነዉ፡፡

በያዝነዉም ጉዳይ የሐራጅ ሽያጭ የተፈጸመዉ ዋናዉን ፍርድ ለማስፈጸም ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ ከተፈጸመ በኂላ ሐራጁ ሲፈጸም የነበረዉ ዉሳኔ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ፍርዱን በመቃወም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡ ይሄዉ ዉሳኔ በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይቶ ለአመልካች ቤቱን በሐራጅ የተሸጠበትን ክንዉን (ሽያጭ) የሚንድ ዉጤት ባለዉ መልኩ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ባልተሳተፉበት በተደረገ ሐራጅ ከተሸጠ ቤት ገንዘብ ላይ ድርሻቸዉን እንዲያገኙ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ ስህተት ነዉ ተብሎ ቤቱ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ለተጠቀሱ ተጠሪዎችና ለተቀሩት ተጠሪዎች የጋራ የዉርስ ሀብት በመሆኑ ከተቻለ በስምምነት፤ስምምነት ከሌለ በሐራጅ እንዲሸጥ ተወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ታይቶ የቀድሞዉ ዉሳኔ ተለዉጦ የተወሰነበት ዉሳኔ ጸንቶ እስካለ ድረስ የፍርድ አፈጻጸሙ ሊተገበር እና ፍርዱን ለማስፈጸም የተፈጸመዉን የሐራጅ ሽያጭ በመቃወም ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ በዳኝነት ታይተዉ እልባት ሊያገኝ የሚገባዉ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋናዉን የፍርድ ዉሳኔ ለዉጦ በወሰነዉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተለወጠዉን ዉሳኔ መሰረት አድርጎ አከራክሮ አለመወሰኑ የፍርድ አፈጻጸም መመራት ያለበት ጸንቶ የሚገኘዉን የመጨረሻዉን የፍርድ ዉሳኔ መሰረት አድርጎ ሊሆን ይገባል ተብሎ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ የሰጠዉ ብይን መታረሙ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀረ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች በአቤቱታቸዉ በጠቀሷቸዉ የሰበር ዉሳኔዎች የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የተሰጡ ስላልሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የላቸዉም፡፡እንዲሁም በተለይም ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ለተጠቀሱ ተጠሪዎች በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዋናዉ ዉሳኔ ተለዉጦ በተወሰነዉ ዉሳኔ መሰረት የተረጋገጠላቸዉን መብት ለማስከበር ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የዉርስ ሀብት የሆነዉን ቤት ለአመልካች በሐራጅ ለመሸጥ የተደረገዉ ሐራጅ እንዲፈርስ መወሰኑም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 349 ማዕቀፍ ወስጥ ሊታይ የሚችል በመሆኑ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ በመሆኑ ከዚህም አኳያ ከዉጤት አንጻር በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 74456 ላይ በቀን 30/12/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 186757 ላይ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሠ/መ/ቁጥር 185273

ሀምሌ 28 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አፍሪካ ጁስ ቲቢላ አ.ማ

ተጠሪዎች፡- 1/ አቶ ታዱ ጫላ

2/ አቶ ቴዎድሮስ ስጣርጌ

3/ አቶ አለማየው ደጀን

4/ አቶ ቴዎድሮስ አስማማው

5/ አቶ ሰለሞን አባተ

6/ አቶ ፋኖስ አንዳሳ

7/ አቶ አብዱልናስር መሀመድ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአመልካች መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈበት አግባብና ከዚህ በኋላ ክሱ በተሰማበት እለት የሰነድ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት እንዳያገኝ የተደረገበት አግባብ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻ የተደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ በታየበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያየ የስራ መደብ ሲያገለግሉ ቆይተዉ ከሕግ ዉጭ እንዳሰናበታቸዉ በመግለጽ ከተራ ቁጥር 1-5 ለተጠቀሱ ተጠሪዎች የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ 6ኛ እና 7ኛ ተጠሪዎችን ደግሞ ወደ ሥራቸዉ እንዲመልሳቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ ያለዉን መልስ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲሰጥ ታዞ አመልካችን ወክሎ ወደ ፍርድ ቤት የቀረበዉ ሰዉ ዉክልና ይዞ ባለመገኘቱ እንዲሁም ከመልሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸዉ ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ተክፍሎበት ተሟልቶ አለመቅረቡን በመግለጽ መልሱን ሬጅስትራር ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡ከዚህ በኋላ አመልካች ለችሎቱ አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ በቀን 17/04/2011ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አመልካች መልሱን እንዲያቀርብ በታዘዘበት ቀነ ቀጠሮ የዉክልና ሰነድ የያዘ ተወካይ ያላቀረበበትንም ሆነ ከመልሱ ጋር ተያይዞ የሚቀርበዉን የሠነድ

ማስረጃዎች የቴምብር ቀረጥ ከፍሎ አሟልቶ ያላቀረበበትን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሳይገልጽና ይህንን አሟልቶ ማቅረብ የራሱ ግዴታ ሆኖ ሳለ በራሱ ጉድለት ምክንያት መልስ በጽሁፍ ሳያያይዝ በመቅረቱ ተጨማሪ ጊዜ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 196/3ን በመጥቀስ የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አድርጓል፡፡

በመቀጠል አመልካች ፍርድ ቤቱ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ክስ ለመስማት በቀጠረበት እለት የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 137ን በመጥቀስ የሰነድ ማስረጃዎች ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝለት ጠይቆ ፍርድ ቤቱ በቀን 20/06/2011ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አመልካች መልሱን በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ስለታለፈ መልስ የመስጠት መብቱ ከታለፈ በኂላ የሰነድ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበዉ ጥያቄ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ዉድቅ አድርጓል፡፡ ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተም በመ/ቁጥር 61569 ላይ በቀን 21/09/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ተጠሪዎችን ከሕግ ዉጭ አሰናብቷል በማለት ከተራ ቁጥር 1-5 ለተጠቀሱ ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ሕገወጥ ስንብትን ተከትሎ የሚከፈሉ ክፍያዎች እንዲከፈላቸዉ እንዲሁም 6ኛ እና 7ኛ ተጠሪዎችን ወደ ሥራ መደባቸዉ እንዲመልሳቸዉ ወስኗል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 233368 ላይ በቀን 20/02/2012 ዓ/ም በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት በሰጠዉ ብይን ይግባኙን ሰርዟል፡፡ አመልካች በቀን 28/02/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት የመከላከያ መልሳችንን በቀጠሮ ሰዓት ይዘን የቀረብን ሲሆን ፍ/ቤቱ ግን የውክልናው ደብዳቤ በሰነዶችና ማረጋገጫ አልተረጋገጠም የቀረበውም መልስ ቴምብር አልተለጠፈባቸውም ሲል በአመልካች ጉድለት ባልሆነ ምክንያት መልስ የማቅረብ መብታችንን አልፏል፡፡ ይህንን ተከትሎ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ መልሳችንን በአቤቱታ አስደግፈን አቅርበን ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት አመልካች መልሱን እንዲያቀርብ ማድረግ ሲገባው ጥያቄያችንን ውድቅ ማድረጉ የስር ፍርድ ቤት ያለበቂ እና ህጋዊ ምክንያት ባልሆነበት ስነ ስርዓታዊ የሆነውን እንደ ጉድለት በመውሰድ መሰረታዊ የሆነውን መልስ የማቅረብ መብታችንን እንድናጣ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137 በሚፈቅደው መሰረት ክስ በሚሰማበት ወቅት ከተራ ቁጥር 1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱ ተጠሪዎች የስራ መሪ መሆናቸውንና ስንብቱ ሕገ ወጥ ነዉ የሚባል ቢሆን እንኳን ለ2ኛ ፣3ኛ ፣6ኛ እና 7ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የስራ ውላቸው ከሕግ ውጪ ነው ቢባል እንኳን በሕግ አግባብ ሊፈጸምላቸው የሚገባው ማንኛውም ክፍያ የተፈፀመላቸው መሆኑን፤ እንዲሁም 1ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተጠሪዎች የፈፀሙትን ጉልህ የስራ ግድፈት ከሚያሳይ ዝርዝር አቤቱታ ጋር ያቀረብነዉን የሰነድ ማስረጃዎች የስር ፍርድ ቤት አይያያዝም በማለት ጥያቄያችንን ዉድቅ

ማድረጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137ን እና በሰ/መ/ቁጥር 37105 የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ ይታረምልን በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች መልስ እንዲያቀርብ በተቀጠረበት ቀን ሬጅስትራር ሳይቀበለው መቅረቱ ለችሎቱ አመልክቶ እያለ መልስ የመስጠት መብቶ ታልፎ የተወሰነበትን አግባብነት ከመደመጥ መብት አንፃር እንዲጣራ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 07/04/2012 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በተሰጠዉ ጊዜ መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ መብቱ እንደታለፈበት የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በግልፅ ያስረዳል፡፡ሰበር አጣሪ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉ ጭብጥ አመልካች መልሱን አቅርቦ ነበር ወይስ አይደለም የሚል ፍሬ ነገርን አጣርቶ መወሰንን የሚጠይቅ በመሆኑ በሰበር ችሎት የሚታይ ባለመሆኑ ዉድቅ ይደረግልን፡፡አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሬጅስትራር በሰዓቱ ሳያቀርብ በመቅረቱ እና መልስ ባለማቅረቡ ከጅምሩ መልስ የማቅረብ መብቱን በራሱ ጊዜ እንደተወዉ ያስቆጥረዋል እንጂ የመደመጥ መብቱን ፍርድ ቤቱ ሳያከብርለት እንደቀረ አያሳይም፡፡ ይህም ለቀጠሮው ምክንያት የሆነ መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መልኩ የማቅረብ መብቱን ሊያልፈው ችሏል፡፡አመልካች በከፍተኛ ቸልተኝነት ወይም መልስ ለማቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ በስር ፍርድ ቤት የተከናወኑት ቀጠሮ ቀናቶች በግልፅ የሚያስረዱት የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን የመደመጥ መብቱን ለማስከበር ጥረት ማድረጉን የሚያሳይ በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 01/05/2012ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ያያዘዉን ጭብጥ እና አመልካች ክሱ በተሰማበት እለት ከመዝገቡ ጋር የሰነድ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበዉ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ለቀረበበት ክስ መከላከያ መልሱን በፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ዘንድ ቀርቦ እንዲሰጥ በተያዘለት ቀነ ቀጠሮ መከላከያ መልሱን ይዞ የቀረበዉ ተወካይ የተሟላ የዉክልና ስልጣን ማስረጃ ይዞ እንዳልቀረበና ይህ የዉክልና ስልጣን ማስረጃ ሳይዝ የቀረበዉ ሰዉ ለሬጅስትራር ካቀረበዉ መልስ ጋር አያይዞ ያቀረበዉ የሰነድ ማስረጃ የቴምብር ቀረጥ የተከፈለበት መሆኑን ማረጋገጫ የሚሆን ቴምብር የተለጠፈበት ባለመሆኑ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር አልቀበልም ብሎ እንደመለሰለት ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ተመልክተናል ፡፡

በፍትሐብሔር ክርክር ባለጉዳዩ ራሱ ቀርቦ እንዲከራከር ፍርድ ቤት ካላዘዘ በስተቀር ወይም ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ከሌለ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት ወይም ለመከራከር ለሚጠየቀዉ ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰዉ በዋናዉ ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት ፣በወኪልነት እና በጠበቃነት መከራከር እንደሚችል በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 57 ስር ከተደነገገዉ መረዳት ይቻላል፡፡እንዲሁም ተሚጋች ስለማቆም በሚደነግገዉ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 63(1 እና 2) ስር እንደተመለከተዉ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ ስለራሱ ሆኖ እንዲከራከርለት ለሚፈልግ ሰዉ እንደራሴነት ካልሰጠዉ ወይም ነገረ ፈጅ ሆኖ እንዲሰራ ቀጥሮት ወኪል አድርጎ በመሾም የጽሁፍ ዉክልና ካልሰጠዉ በስተቀር ይህ ሰዉ ስለሌላ ሰዉ ጉዳይ (ማንኛዉንም ተከራካሪ ወገን ወክሎ) ፍርድ ቤት ቀርቦ ለመከራከር እንደማይችልና ይህም የዉክልና ስልጣን ማስረጃ ከክሱ ወይም ከመልሱ ጋር ቀርቦ ክርክሩ በሚደረግበት የፍርድ ቤቱ መዝገብ ዉስጥ መቀመጥ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ላይ ዉክልናዉ በጽሁፍ የተሰጠና በወካዩ የተፈረመ መሆን እንዳለበት የተደነገገ ቢሆንም የዉክልና ስልጣን ማስረጃዉ በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ አካል ተረጋግጦ መመዝገብ እንዳለበት አልተደነገገም፡፡አንድ ተከራካሪ በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ አካል ተረጋግጦ ያልተመዘገበ ነገር ግን በጽሁፍ በተደረገ የዉክልና ስልጣን ማስረጃ ላይ ፈርሞበት ለተወካዩ ዉክልና ቢሰጥና የተወከለዉ ሰዉ ይህንኑ ይዞ ለፍርድ ቤቱ ቢያቀርብ ፍርድ ቤቱ አልተሟላም ብሎ ተወካይ ነኝ ሲል የቀረበዉን ሰዉ እንደተወካይ ሳይመዘግብ ያሰናብተዋል ወይስ ሰነዱን ተቀብሎ ተከራካሪዉን ወክሎ እንዲከራከር ይፈቅድለታል የሚለዉን ከሌሎች ሕጎች አንጻር መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 ስር አንቀጽ 9(1/ለ) ስር በግልጽ እንደተመለከተዉ የዉክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ በዚህ አዋጅ ሰነዶችን እንዲያረጋግጥና እንዲመዘግብ ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል ቀርቦ ተረጋግጦ መመዝገብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ እንደተመለከተዉ የዉክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ በአዋጁ በተመለከተዉ መሰረት ካልተረጋገጠና ካልተመዘገበ ሕጋዊ ዉጤት እንደማይኖረዉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ስነ ስርዓት እንዲፈጸም ሕግ አዉጪዉ የደነገገበት ምክንያት ዉክልና ሰዎች በራሳቸዉ መፈጸም የማይችሉትን ሕጋዊ ተግባራት በሌላ ሰዉ ማስፈጸም የሚችሉበትን ሁኔታ የሚያመቻች የዉል አይነት ከመሆኑም በተጨማሪ መብትና ጥቅም የማስተዳደር፣ የማስተላለፍ እንዲሁም የወካዩ መብትና ጥቅም እንዳይጎዳ የመጠበቅና መሰል ተግባራት እንዲፈጸም ለተወካዩ ሥልጣን የሚሰጥ ሰነድ በመሆኑ ለወካዩ ፣ ለሦስተኛ ወገን መብትና ጥቅም እንዲሁም በዉክልና ሥልጣን የሚደረጉ ግብይቶች በማሳለጥ ለንግድ እንቅስቃሴዉና ተሳታፊዎቹ ጥበቃ ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዉክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ ሥልጣን ባለዉ አካል ተረጋግጦ እንዲመዘገብ የሚፈለግበት ሌላዉ ምክንያት በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990(በአዋጅ ቀጥር 612/2001

እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 3/11 መሰረት የቴምብር ቀረጥ ለማስከፈል ጭምር ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የቴምብር ቀረጥ ሳይከፈልበት የቀረበ የዉክልና መስጫ ሰነድ(ሌሎች ሰነዶችንም እንደሚጨምር ልብ ይሏል) ከ10 ብር ያላነሰ ሁለት እጥፍ የቴምብር ቀረጥ ከተከፈለበት በኋላ ሌላ ጊዜ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ ማስረጃ የመቀበል ሥልጣን ባለዉ ሰዉ ወይም የመንግስት መሥሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት እንደማይኖረዉ፣ ምልክት አደማይደረግበት ወይም ማረጋገጫ አንደማይሰጥበትም በዚሁ ሕግ አንቀጽ 10(1 እና 4) ስር ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም በሕግ የዉክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ አረጋግጦ እንዲመዘገብ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ በመያዝ ሌላ ሰዉ ወክሎ ለመሟገት የቀረብን ሰዉ ለመወከል ብቁ የሚያደርግህን የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ ይዘህ አልቀረብክም ብሎ ፍርድ ቤቱ ሊያሰናብተዉ ይገባል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ ሰዉ እንደመሆኑ የቀረበበትን ክስ መከላከል የሚችለዉ በተፈጥሮ ሰዉ በመወከል ስለሆነ ለቀረበበት ክስ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ቀርቦ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት መልሱን ማቅረብ የሚችለዉ ለሚሟገትለት ሰዉ በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል የተረጋገጠና የተመዘገበ የዉክልን ሥልጣን ማስረጃ በመስጠት ሊሆን ይገባዋል፡፡በዚህ አግባብ ለሚሟገትለት ሰዉ የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ ካልሰጠ መልሱን ይዞ የቀረበዉ ሰዉ በሱ የተወከለ ሰዉ መሆኑን ለማረጋገጥ ስለሚያዳግት ለራሱ መብት ጥበቃ ለማድረግ እና የዉክልና ሥልጣን መስጫ ሰነዱ ያልተረጋገጠና ያልተመዘገበ በመሆኑ የቴምብር ቀረጥ ስላልተከፈለበት ከላይ በተጠቀሱ ሕጎች ድንጋጌዎች መሰረት የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር በሰነዱ ላይ ምልክት አድርጎበት ከመዝገቡ ማያያዝ አይችልም፡፡

እንዲሁም አመልካች ከመልሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸዉ ሰነዶች በአዋጅ ቁጥር 110/1990 (ከአዋጁ ጋር የተያያዘዉን ሰንጠረዥ ጨምሮ) የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልባቸዉ የሚገቡ ሰነዶች አይደሉም ብሎ አመልካች ያሰማዉ ክርክር ባለመኖሩ ከመልሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸዉ ሰነዶች ከመዝገቡ ጋር ሊያያዙ የሚችሉት የቴምብር ቀረጥ ሊከፈልባቸዉ ለሚገቡ ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ የተከፈለባቸዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቴምብር ካልተመታበት ከላይ በተጠቀሰዉ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 10/1 መሰረት በመዝገቡ ሊያያዙ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር አመልካችን ወክሎ የቀረበዉን ሰዉ እንደ አመልካች ተወካይ ቆጥሮ ይዞ የቀረበዉን ያልተመዘገበዉን የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ እና የቴምብር ቀረጥ ያልተከፈለባቸዉን ከመከላከያ መልሱ ጋር ተያይዘዉ የቀረቡ ሰነዶችን በመዝገቡ አለማያያዙ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 63/1 ፣ አዋጅ ቁጥር 922/2008 ስር አንቀጽ 9(1/ለ) እና አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 10/1 ስር የተደነገገዉ ስለማይፈቅድለት ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በተጨማሪም ስለጊዜ እና ስለቀጠሮ አወሳሰን በሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ክፍል በሚገኘዉ አንቀጽ 196/3 ስር እንደተደነገገዉ ተጨማሪ ጊዜ ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠዉ የሚጠይቅ አመልካች ሊፈጽም የሚገባዉን ነገር በመጀመሪያ በተሰጠዉ የጊዜ ዉሳኔ ዉስጥ ሳይፈጽም የቀረዉ ከአቅሙ በላይ ባልሆነ ምክንያት ሳይሆን በሥራ ብዛት፤ በዝንጋታ፤ በቸልተኝነትና በራሱ ጉድለት መሆኑ የታወቀ አንደሆነ አዲስ የጊዜ መራዘም ዉሳኔ እንደማይሰጥ በግልጽ ተደንግጓል። አንደሚታወቀዉ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ክርክሮች ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ(በሂደቱ ተሳታፊ ለሚሆን የሰዉ ሀብትና ቁሳቁስ የሚወጣ ወጪና በክርክሩ ምክንያት የሚደርስ ኪሳራ አነስተኛ በሆነ ሁኔታ) ታይተዉ ፍትሐዊ ዉሳኔ በመስጠት ለክርክሮች እልባት ማስገኘት ነዉ።ይህ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ዓላማ ሊሳካ የሚችለዉ ክርክሮች የተቀመጠላቸዉን ሂደቶች ተከትለዉና ለሂደቶቹ ጥበቃ ለማድረግ የተዘረጋዉ ሥርዓትና ድንጋጌዎች በጥብቅ ዲስፕሊን ተጠብቀዉ ሲፈጸሙ ብቻ ነዉ። በሕጉ የተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብት በማስጠበቅ መሰረታዊ ሕጎች ላይ የተረጋገጡ መብቶችና ጥቅሞች ተግባራዊ ይሆናሉ ተብሎ ታምኖባቸዉ በመሆኑ የተከራካሪ ወገኖች የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብት የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ጠብቆ ዳኝነት በሚስጥበት ሂደት የሚረጋገጥ ነዉ።

አመልካች ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ወደ ፍርድ ቤቱ መልስ እንዲያቀርብለት የላከዉ ሰዉ ያቀረበዉ የዉክልና ሥልጣን ማስረጃና መልስ የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ሳይቀበለዉ በመቅረቱ መልሱን እንዲያቀርብ በተሰጠዉ ቀነ ቀጠሮ ሳያቀርብ ቀርቷል። ይህም ተገቢ መሆኑን ከላይ ተመልክቷል። በመቀጠል አመልካች ችሎቱ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ መልሱን እንዲቀበለዉ ለችሎቱ አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ አቤቱታዉን ለተጠሪዎች እንዲያደርስ ትእዛዝ ሰጥቶት በተሰጠዉ ጊዜ አመልካች ለተጠሪዎች ሳያደርስ ቢቀርም ፍርድ ቤቱ በድጋሚ እንዲያደርስ ትእዛዝ ሰጥቶና የተጠሪዎችን አስተያየት ሰምቶ በሰጠዉ ትእዛዝ አመልካች መልሱን እንዲያቀርብ በታዘዘበት የመጀመሪያዉ ቀነ ቀጠሮ የዉክልና ሰነድ የያዘ ተወካይ ያላቀረበበትንም ሆነ ከመልሱ ጋር ተያይዞ ላቀረበዉ የሠነድ ማስረጃዎች የቴምብር ቀረጥ ከፍሎ አሟልቶ ያላቀረበበትን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አለመግለጹን፤ አሟልቶ የማቅረብ ግዴታ የራሱ ሆኖ ሳለ በራሱ ጉድለት ምክንያት መልስ በጽሁፍ ሳያያይዝ በመቅረቱ ተጨማሪ ጊዜ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ አድርጓል። ይህም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 196/3 አንጻር ሲታይ አመልካች ማሟላት ያለበትን ነገር በማሟላት መልሱን በመጀመሪያ በተሰጠዉ ቀጠሮ ሳያቀርብ የቀረዉ ከአቅሙ በላይ የሆነ ምክንያት ገጥሞት እንደሆነ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር ተለዋጭ ቀጠሮ ሊሰጠዉ አይችልም። የገጠመዉን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማስረዳት ካልቻለ በመጀመሪያዉ ቀጠሮ አሟልቶ ያልቀረበዉ በሥራ ብዛት፤ በዝንጋታ፤ በቸልተኝነትና በራሱ ጉድለት እንደሆነ ስለሚያሳይ የሥር ፍርድ ቤት ተለዋጭ ቀጠሮ አልሰጥህም ማለቱ የሕጉን ዓላማ የሚያሳካ በመሆኑ የሕግ ድጋፍ ያለዉ ነዉ። ስለሆነም የአመልካች የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብት ሊጠበቅ

የሚገባዉ ክርክሮችን በዘፈቀደ በመምራት ሳይሆን የሥነ ሥርዓት ሕጉ በዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት ማእቀፍ ዉስጥ በመሆኑ ከዚህም አኳያ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡

በመቀጠል አመልካች ክሱ በተሰማበት እለት ክሱን ለመከላከል ያቀረብኳቸዉን የሰነድ ማስረጃዎች የስር ፍርድ ቤት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 137 ስር የተደነገገዉን የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በሚል ያቀረበዉን አቤቱታ በተመለከተ የያዝነዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረበዉን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ሳይቀበለዉ የቀረዉ አመልካች መልሱን በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ስለታለፈ መልስ የመስጠት መብቱ ከታለፈ በኋላ የሰነድ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበዉ ጥያቄ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት መሆኑን መዝገቡን አስቀርበን በመመልከት አረጋግጠናል፡፡

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 223/1፣ 234/1 እና 145 ጣምራ ንባብ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተከሳሽ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ ክርክሩን የሚያስረዱለት የሰነድ ማስረጃዎች ካሉት የሰነድ ማስረጃዎቹን ዘርዝሮና የሚያስረዱለትን ፍሬ ነገር ለዚህ በተዘጋጀ የማስረጃ መግለጫ ላይ አመላክቶ እንዲሁም ሰነዶቹ በእጁ የማይገኙና በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ የሚቀርቡ ከሆነም ይህንኑ በመግለጽ በእጁ የሚገኙት ሰነዶች ትክክለኛ ግልባጭ ከመከላከያ መልሱ ጋር አያይዞ ማቅረብ እንዳለበት በአስገዳጅነት ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137(1-3) ስር እንደተደነገገዉ ተከራካሪ ወገኖች በእጃቸዉ የሚገኘዉን ወይም ለማቅረብ የሚችሉትን ወይም ለክርክራችን ይጠቅመናል ብለዉ የሚያምኑበትን ወይም ፍርድ ቤቱ እንዲቀርብ የጠየቀዉንና አስቀድመዉ ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን የጽሁፍ ማስረጃ ሁሉ ዝርዝራቸዉንና ብዛታቸዉን ከሚገልጽ ጽሁፍ ጋር በመጀመሪያዉ ቀነ ቀጠሮ [ክሱን ለመስማት በተያዘዉ ቀነ ቀጠሮ] ወይም ከዚህ ቀነ ቀጠሮ በፊት ማቅረብ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የጽሁፍ ማስረጃ ለማቅረብ ሲፈልጉ የሚጠቀሙት እንደመሆኑ በዚህ አግባብ የተቀረጸበት ምክንያት ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 223/1 መሰረት አስቀድሞ እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የክስ አቤቱታ እና መከላከያ መልሳቸዉን ማቅረብ እንዳለባቸዉ ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ አንድ የፍትሐብሔር ክርክር የሚጀምረዉ የፍትሐብሔር ክስ አቤቱታ በሕጉ በተዘረጋዉ ስርዓት በጽሁፍ አስቀድሞ ከቀረበ በኋላ በመሆኑ ይህ መስፈርት ለከሳሽ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ተከሳሹ ግን በተለያየ ምክንያት መከላከያ መልሱን የማያቀርብበት ሁኔታ ስለሚኖር ተከሳሽ አስቀድሞ መከላከያ መልሱን በስነ ስርዓት ሕጉ መሰረት በጽሁፍ ያላቀረበ ከሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137ን በመጥቀስ ማስረጃ ይያያዝልኝ በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር በዚህ ድንጋጌ በስተጀርባ ታሳቢ የተደረገዉን ቅድመ ሁኔታ ስለማያሟላ ተቀባይነት ሊሰጠዉ አይገባም፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ምክንያቶች ተከሳሽ መከላከያ መልሱን በተሰጠዉ ጊዜ ማቅረብ ካልቻለ ወይም የመከላከያ መልሱን የማቅረብ መብቱ ከታለፈ የሠነድ ማስረጃ የሚቀርበዉ በመከላከያ መልሱ ላይ ክዶ መልስ የሰጠበትን

ፍሬ ነገር ለመከላከል እንደመሆኑ አንድን ፍሬ ነገር ክዶ መልስ ባልሰጠበት ሁኔታ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ የሰነድ ማስረጃዎች እንዲያያዝለት የሚያቀርበዉ ጥያቄ ምን ለመከላከል እንደሆነ በግልጽ የሚታወቅ ባለመሆኑ ከዚህ አኳያ ማስረጃ ይያያዝልኝ ብሎ የሚነሳዉ ክርክር አመክኖያዊ ካለመሆኑም በተጨማሪ ጥያቄዉን መቀበል በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን የክርክር አመራር ሂደቱን የሚያፋልስ በመሆኑ ነዉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አስቀድሞ በራሱ ጉድለት (ቸልተኝነት) መከላከያ መልሱን ያላቀረበ ተከሳሽ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137ን በመጥቀስ ማስረጃዎቹ ምን እንደሚያስረዱለት ከሚገልጽ ጽሁፍ ጋር የሰነድ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ መፍቀድ በሕጉ የተደነገገዉን ስርዓት ተከትለዉ የመከላከያ መልሳቸዉንና ከመከላከያ መልሳቸዉ ጋር ያላቸዉን የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ እየቻሉ በቀጣይ ባለዉ ሂደት እናቀርባለን የሚሉ ግደየለሽ ተከራካሪዎችን የማበራከት ዉጤት ስለሚኖረዉና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 223/1 እና 234/1 ድንጋጌዎችን ዉጤታማ ተፈጻሚነት ስለሚቀንስ አስቀድሞ መከላከያ መልሱን ያላቀረበ ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137ን ጠቅሶ ከማስረጃ መግለጫ ጋር የሚያቀርበዉ የሰነድ ማስረጃ ይያያዝልኝ ጥያቄ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ድጋፍ ያለዉ አይደለም፡፡ስለሆነም ከዚህም አኳያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች መልሱን በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ስለታለፈ መልስ የመስጠት መብቱ ከታለፈ በኋላ የሰነድ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበዉ ጥያቄ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም በማለት ዉድቅ በማድረጉና በዚህ ላይ የቀረበዉ ይግባኝ በመሰረዙ የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን መከላከያ መልስ እና የሰነድ ማስረጃዎች ይያያዝልኝ አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በመ/ቁጥር 61569 ላይ በቀን 21/09/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋለዉ ችሎት በመ/ቁጥር 233368 ላይ በቀን 20/02/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

1. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 10/03/2012 ዓ/ም የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 219089

ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኦሮሚያ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር

ተጠሪዎች ፡- 1/ ወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ

2/ አዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኅበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውል ውጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገ ሲሆን የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ከደንበኛው ከወ/ሪት ብርሃን ገ/ጻድቃን ግደይ ጋር በተዋዋለዉ የኢንሹራንስ ዉል የሰሌዳ ቁጥሩ 3-05135 ትግ ለሆነ ተሽከርካሪ ከቀን 19/11/2006ዓ/ም እስከ 18/11/2007ዓ/ም ድረስ ጸንቶ የሚቆይ እስከ ብር 1000,000.00 ካሳ ለመክፈል የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ ይህ ተሽከርካሪ በጉዞ ላይ እያለ በትግራይ ክልል ክልታ አዉላዕሎ ወረዳ ሐዉዛ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ በቀን 28/08/2007ዓ/ም ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነ በሰሌዳ ቁጥር 35-3337 የሆነ ተሽከርካሪ መስመሩን ለቆ ወደ አመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ መስመር 1.20 ሜትር በመግባት የአመልካችን ደንበኛ ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት አድርሶበታል፡፡ ተሽከርካሪዉ ከወደቀበት በክሬን ተንስቶ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ተደርጎ የደረሰበትን ጉዳት ለማስጠገን የሚያስፈልገዉ ወጪ ተጣርቶ የጥገና ወጪዉ ከገበያ ላይ ተሽከርካሪዉን ከሚገዛበት ዋጋ በላይ በመሆኑ የቅሪት አካሉ ዋጋ፣ የአደጋ ተቀናሽ(excess) እና ሌሎች ወጪዎች ተቀንሶ አመልካች ለደንበኛዉ ብር 505,363.00 መክፈሉን በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ ከ9% ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲተከለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች በደንበኛው ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ስለመድረሱ ተዓማኒነት ባለዉ ማስረጃ አስደግፎ ያላቀረበ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች የደንበኛው ተሽከርካሪ የእርጅና ዋጋ ሳይቀንስ የገበያ ዋጋ ግምት ብሎ ያቀረበው የገንዘብ መጠን በትክክል የገበያ ጥናት

ያልተደረገበት ነው፡፡ የተሽከርካሪውን ቅሪት በጣም በዝቅተኛ ዋጋ ሽጦ ይህንን ልዩነት ተቀናሽ አድርጎ ተጠሪ እንዲከፍል መጠየቁ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲሁም የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠዉ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ የሰጠዉን ትእዛዝ ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ በሰጠዉ መልስ ከኃላፊነት መጠን ጋር በተያያዘ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ በ3ኛ ወገኖች ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እስከ ብር 100,000.00 ለመክፈል ግዴታ ስለገባ ከዚህ በላይ ልጠየቅ አይገባም፡፡ ግጭቱ ሊፈጠር የቻለው በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት እንጂ በተጠሪ ተሽከርካሪ እንዳልሆነ እና አመልካች ያቀረበው የትራፊክ ፖሊስ አደጋ ሪፖርትም ትክክለኛ ያልሆነ እና እንዲታረም የተጠየቀበት ስለሆነ ይህንን ማስረጃ መሰረት በማድረግ አመልካች ያቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የተጠየቀው የጉዳት ካሳ ግምት የተጋነነ ነው፡፡ የአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ የ2010 ስሪት እንደሆነ ከአምስት ዓመታት በላይም አገልግሎት የሰጠ እና አመቺ ባልሆነ መንገድ እና መልከዓ ምድር ሲነዳ የቆየ ስለሆነ ቢያንስ የተሽከርካሪ አካል ላይ በአዲስ መለዋወጫ ሲተኩ ከ40-50 % የእርጅና ቅናሽ መደረግ ነበረበት፡፡ በተሽከርካሪው ዉስጣዊ ክፍሉ ሊደርስ የሚችለዉ ጉዳት ከብር 95,000.00 እስከ ብር 175,000.00 መሆኑ ተገምቶ እያለ አመልካች ተፈቶ ባልታየበት ሁኔታ አመልካች አጋኖ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ የቅሪት አካሉ በብር 275,000.00 በባለሙያ ተገምቶ እያለ አመልካች በብር 120,000.00 ቀንሶ መሸጡ የጉዳት ኪሳራ ካሳ መቀነስ ሲገባው አልቀነሰም የሚሉትንና ሌሎች የካሳ መጠን የሚመለከት መከራከሪያ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 190749 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና ማስረጃዎቻቸዉን መርምሮና መዝኖ በቀን 26/02/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በአመልካች ደንበኛ እና በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎች መካከል ግጭት ሊከሰት የቻለዉ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በተሻለ ሁኔታ ሚዛን በሚደፋ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት 1ኛ ተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 187653 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 12/02/2014 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት የለበትም ሲል በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 04/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉም ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 85(3/ሀ እና ለ) መሰረት በበላይ ትራፊክ ፖሊስ ፅ/ቤት ወይም በይግባኝ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ባለው

አካል ካልሆነ በስተቀር በትራፊክ ፖሊስ ልዩ እውቀት ላይ ተመስርቶ የቀረበውን የትራፊክ ፕላን ዉድቅ ማድረግ እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መካኒካል መሀንዲሶች የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኞች የሆኑት አደጋው ሲደርስ በቦታው ስላልነበሩ የአይን ምስክሮች አልነበሩም፡፡የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮችና የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መካኒካል መሐንዲሶች በትራፊክ መርማሪ ፖሊስ የተሰራዉን የትራፊክ ፕላን ለመሻር በሕግ የተሰጣቸዉ ሥልጣን የላቸዉም፡፡የስር ፍርድ ቤት የመቀሌ የኒቨርሲቲ መካኒካል መሐንዲሶች የሰጡትን ማስረጃና የ1ኛ ተጠሪን ምስክሮች ምስክርነት ቃል ተቀብሎ የትራፊክ ፖሊሲ ያነሳዉን የአደጋ ፕላን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ከላይ የተጠቀሰዉን ደንብ እና በሰ/መ/ቁጥር 43452 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መካኒካል መሀንዲሶች ግጭቱን በተመለከተ ሰሩ የተባለው ሶፍትዌር አደጋው ከደረሰና ተሽከርካሪዎቹ ከቦታው ከተነሱ ከ2 ዓመት ተኩል በኋላ የተሰራ በመሆኑ የትራፊክ ሪፖርቱን ለማስተባበል ብቃት የሌለዉና በንድፈ ሀሳብ ላይ ተመሰረተ ማስረጃ ነዉ፡፡መካኒካል ምህንድስና ስለማሽን ንድፈ ሃሳብ አሰራር ወይም አመራረት እና ጥገና የሚያጠና ትምህርት ዘርፍ እንጂ የትራፊክ ደንብ በመተላለፍ ቀኝ ዘርዝን ትቶ ወደ ግራ መግባትና ከፊት ለፊት የሚመጣን ተላላፊ ተሽከርካሪ አለመኖሩን ሳያረጋግጥ በማለፍ ገጭቷል የተባለዉን አከራካሪ ነጥብ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ባለመሆኑ ከዚህም አኳያ ሲታይ የስር ፍርድ ቤት በመካኒካል መሐንዲሶች የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት አድርጎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ከትራፊክ ፖሊስ የተሰጠውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ ጥፋት በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ለደንበኛዉ የከፈለዉ ካሳ ብር 505,363.00 እንዲተካለት ያቀረበዉን ክስ የስር ፍርድ ቤት የመቐለ ዩኒቨርሲቲ መካኒካል ምህንድስና ትምህርት ክፍል የቀረበዉን መረጃ መሰረት አድርጎ ዉድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ ከመሰረታዊ የክርክር አመራርና ማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱት ተጠሪዎች በቀን 22/07/2014 ዓ/ም በተናጠል የተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-

አመልካች ያቀረበው የትራፊክ ፕላን በተገቢው ሁኔታ ያልተሰራና በአደጋው ቦታ ከነበረው እውነታ ጋር በተጣረሰ እና አጠራጣሪ በሆነ መልኩ የተሰራ ሪፖርት በመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ተጽፎ ቅሬታ ለትግራይ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ቀርቧል፡፡ ይህ ቅሬታ ቀርቦ እያለ የአመልካች ደንበኛ ሹፌር ለደረሰበት ጉዳት ካሳ ይከፈለኝ ሲል በ1ኛ ተጠሪ ላይ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 86558 ላይ ባቀረበው ክስ መነሻ ፍርድ ቤቱ ይህ የትራፊክ ፕላን አጠራጣሪና ቅሬታ የቀረበበት መሆኑን ከግምት በማስገባት በጉዳዩ ላይ ወገንተኛ ያልሆነና ሚዛናዊ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጥበት ለማስቻል ከክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን በተወከሉ የትራፊክ ፖሊስ አባላት እንዲሁም ከመቐሌ ዩኒቨርሲቲ በተውጣጡ ባለሙያዎች

በጋራ በተዋቀረ ኮሚቴ የአደጋው መንስዔ ተጣርቶ ለፍርድ ቤቱ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የአደጋውን መንስኤ በቪዲዮ በተደገፈ ሲሙሌሽን በግልፅና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያስረዳ ሙያዊ ትንታኔ ቀርቦለታል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 43453 ላይ በተሰጠ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ የሙያ ምስክርነት የሚሰጠዉ በቀጥታ ድርጊቱን በአይን በማየት ሳይሆን በሙያ ተመርምሮ የሚሰጥ ቀጥተኛ ያልሆነ ማስረጃ ወይም የሙያተኛ አስተያየት በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል ማስረጃ አይደለም፡፡የትራፊክ ፖሊሲ የአደጋ ሪፖርትም አደጋዉ ከደረሰ ከሰዓታት በኂላ ከአደጋዉ ቦታ በደረሰ የትራፊክ ፖሊስ የተሰራ በመሆኑ አደጋዉ ከደረሰበበት ቦታ አቀማመጥ አንጻር የተሻለ የሙያ ሀሳብ ሊያቀርቡ የሚችሉ ባለሙያዎች ያሉበት ኮሚቴ ተዋቅሮ አደጋዉ የተከሰተበት ሁኔታ በሳይንሳዊ ሙያ ተመርምሮ አደጋዉ የደረሰዉ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ነዉ የሚል ማስረጃ በመቅረቡ የስር ፍርድ ቤት ይህንን ማስጃና የምስክሮች ቃል መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸዉም ሲል በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መካኒካል ምህንዲስና ትምህርት ክፍል ያቀረበዉ ሪፖርት የትራፊክ ፖሊስ ሪፖርትን የመሻር ሥልጣን የለዉም ሲል ያቀረበዉም ክርክር ሪፖርቱ የቀረበበትን አግባብ ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡እንዲሁም የመካኒካል መሀንዲስና ትምህርት ዘርፍ ልዩ ልዩ ዘርፍ ያለዉ በመሆኑና ካሉት ዘርፎች መካከል ኃይልን እና እንቅስቃሴን የሚያጠና ዳይናሚክስ (Dynamics) የሚባል ዘርፍ ስላለዉ በተያዘዉ ጉዳይ አደጋ የደረሰበት ቦታ ፣መንገድ ስፋት፣ተሽከርካሪዎቹ የወደቁበት ቦታ፣የአደጋዉ ስፍራ አቀማመጥ ከትራፊክ ፖሊስ ሪፖርት ላይ በመዉሰድ ለአደጋዉ መንስኤ የሆነዉ የትኛዉ ተሽከርካሪ ነዉ የሚለዉን ለይተዉ ሙያዎ አስተያየት ለማቅረብ ብቃት ስላላቸዉ አመልካች ከዚህም አኳያ ያቀረበዉ ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን መዝኖ ለደረሰዉ ጉዳት የ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ ጥፋት የለበትም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ በመወሰኑ ከማስረጃ ምዘና አኳያ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 08/07/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በጉዳዩ ላይ የተሰጡ ዉሳኔዎችን የሚመለከት ሲሆን እኛም 1) የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? 2) የስር ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ መዳኘቱ ተገቢ ነዉ የሚባል ከሆነ አመልካች የኢንሹራንስ ዉል መሰረት በማድረግ ለደንበኛ በካሳ መልክ የከፈለዉ ገንዘብ እንዲተካለት ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ አድርጎ በመወሰኑ ከማስጃ ምዘና መርህ አተገባበር አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግና ከሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን መርመረናል፡፡እንደመረመርነዉም አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በቀን 02/06/2009ዓ.ም ጽፎ

ክስ የመሰረተዉ የመድን ሽፋን የሰጠዉን የደንበኛዉ ንብረት የሆነ በሰሌዳ ቁጥሩ 3-05135 ትግ የሚታወቅ ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነ ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚንዝ ተሽከርካሪ በትግራይ ክልል ክልታ አዉላዕሎ ወረዳ ሐዉዛ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ከመስመሩ በመዉጣት ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ለደንበኛዉ በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት ካሳ መክፈሉን በመግለጽ በካሳ መልክ የከፈለዉ ገንዘብ እንዲተካለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ። የስር የፌዴራል ከፍተኛ ጉዳዩን ከስረ ነገሩ አንጻር መርምሮ በአመልካች ደንበኛ ተሽካሪ ላይ ጉዳቱ የደረሰዉ በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት አይደለም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78/2 መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምጽ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲደራጅ እስካልወሰነ ድረስ የፌዴራል ከፍተኛና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል። ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በውክልና በተሠጠ ሥልጣን ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጉዳይ ነው። ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ሲሆን በዚህ ሂደት ፍርድ ቤቶች በቀዳሚነት መመርመር ከሚጠበቅባቸዉ ጉዳዮች መካከል ጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ መርምሮ መወሰን ዋነኛው ነው። የፍርድ ቤት ሥልጣን ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction)፣ የሥረ-ነገር ሥልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ወይም አካባቢያዊ ሥልጣን (local or territorial jurisdiction) በሚል የተከፋፈለ ነው።

ኢትዮጵያ የፌዴራል የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓትን በ1987 ዓ/ም በወጣው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መከተሏን ተከትሎ ሥልጣን በክልሎችና በፌዴራል መንግሥት የተከፋፈለ ስለመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ከአንቀጽ 50-52 ላይ ተመልክቷል። በዚህም ክልሎች በሥልጣናቸው ሥር ባሉ ጉዳዮች ሉዓላዊ ሥልጣን አላቸው። ክልሎች እንደ ፌዴራል መንግሥት ሕግ-አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካል ያደራጃሉ። በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 መሠረት የዳኝነት አካሉ በፌዴራል እና በክልል መንግሥት ደረጃ መቋቋሙ እና በአንቀጽ 80(1)(2) ላይ በፌዴራል ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤት፤ በክልላዊ ጉዳዮች የክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መሆኑ መመልከቱ በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የፍርድ ቤት የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ያሳያል። የፌዴራል ወይም የክልል ጉዳዮች የሚለው በጉዳይ ዓይነት የተከፋፈለ ሥልጣን ስለሆነ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የተለየው የሥረ-ነገር ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ቢመስልም ጉዳዩ ከሉዓላዊ ሥልጣን እና ክልላዊ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤት ቢታይ ከጣልቃገብነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጉዳዩ የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣንን የሚያስነሳ ነው። በፌዴራል መዋቅር የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግ ሳይሆን ሕገ-መንግሥት ነው። ሕገ-መንግሥቱ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ያቋቋመና አንዱ የሌላዉን ሥልጣን አክብረው ለማስከበርም ግዴታ የጣለ ነው።ይህንን ጉዳይ ከአለም አቀፍ አጠቃላይ

መርሆዎች አንጻር ሳይሆን በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል ከሚኖረዉ ግንኙነት አንጻር አጥበን ያየን እንደሆነ በአንድ ሀገር ያሉና በሕገ-መንግሥቱ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕብረሰብ ለመፍጠር በሚሠሩ ተቋማትና ዜጎች ላይ፣ የተለያየ ሥልጣን ቢሆንም የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ ባላቸው ተቋማት መካከል የሚነሳ ስለሆነ የተለየ ያደርገዋል። ይኸዉም በፌዴራል መዋቅር የፌዴራል መንግሥት ሉዓላዊነቱ በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ነው። ነገር ግን በግዛቱ ሥር ሁሉንም በፈቃዱ መወሰንና መፈጸም የሚችል ሳይሆን በግልጽ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት ሥልጣኑን የሚጠቀም መሆኑን የሚመለከት ነው። ለክልል ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረቱ ግን በግዛት ክልል ሥር ያለ ሰውና ንብረት መሆን አለመሆኑን መሠረት ያደረገ (limited sovereignty) ነው።

በሕገ-መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍሉም የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን በውክልና ማየት የሚችሉ ሲሆን ክልላዊ ጉዳዮች በክልሎች ሉዓላዊ ሥልጣን ክልል ውስጥ (exclusive jurisdiction of state courts) ያለ በመሆኑ፤ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3/ሀ) ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማየት አይችሉም። ይሕም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction) የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ በውክልና እና በጣምራ ሥልጣናቸው ከሚመለከቱት በሥተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ጉዳዮችን ማየት አይችሉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ መመርመር ያለበት በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) እና የፌዴራል ጉዳዮች የሚወሰኑበት ሥርዓት ነው። የፌዴራል ጉዳዩች ምን እንደሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ያልተወሰነ ቢሆንም የተያዘዉ ጉዳይ ለስር ፍርድ ቤት በቀረበበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት የፌዴራል ጉዳዮች ሕገ-መንግሥቱን፣ የፌዴራል መንግሥት ሕጎችንና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች (based on laws)፤ በፌዴራል ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች (parties) እና በሕግ በተገለጹ ቦታዎች (places) ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው። በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት የተዘረዘሩት የፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸው ሕግንና ባለጉዳዮችን መሠረት አድርጎ የተለዩ የፌዴራል ጉዳዮች ሲሆን በሌሎች ሕጎች በግልፅ ለፌዴራል ፍርድ ቤት የተሠጡ ጉዳዮችን ይጨምራል። የአዋጁን አንቀጽ 11 እና ተከታዮችን ስንመለከት ደግሞ ቦታን መሠረት በማድረግ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የሚነሡ ጉዳዮች የፌዴራል ፍርድ ቤት የሚመለከታቸው የፌዴራል ጉዳዮች እንደሆኑ ተደንግጓል።

በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት ሕግን መሠረት አድርጎ የተለዩት የፌዴራል ጉዳዮች ውስጥ የፌዴራል መንግሥት ሕጎችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ያሉበት በመሆኑና

በአዋጁ የትርጉም ክፍል አንቀጽ 2/3 ላይ የፌዴራል መንግሥት ሕጎች ማለት በሕግ በተሠጠው ሥልጣኑ ክልል ሥር ያሉ ነባር ሕጎችን የሚጨመር መሆኑ ሲታይ በሕግ በግልጽ የፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ከተመለከቱት ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች እና በፌዴራል ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ከተወሰኑት ባለጉዳዮች ውጭ ያሉ የፌዴራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው የሚመለከቷቸው ናቸው፡፡ ሥለሆነም የፌዴራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ሌሎች ጉዳዮች እንደተነሱበት ቦታ የፌዴራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤት በክልላዊ ሥልጣኑ ሊመለከተው ይችላል፡፡

በሕገ መንግስቱ በአገራችን የተዘረጋዉን የፌዴራል ሥርዓት መሠረት ተደርጎ የተዋቀረው የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78/2 እና 80(4-6) የፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል፡፡ ይህም ሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶችን ማብቃትን (empowerment)፣ተደራሽነትን፣ የክልሎችን ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ዓላማ ያለውና ተቋሞቻቸው ላይ አመኔታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌዴራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረድ ያለ የትይዩ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌዴራልና የክልል ጉዳይን የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተልም ያሳያል፡፡

የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው በክልል ግዛታቸው የተነሱ ጉዳዮች የመመልከት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አይኖረውም፡፡ ጉዳዩ በክልል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳዩ የተነሳበትን ቦታና ተከራካሪውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የጣምራነት ሥልጣን መሠረቱ የፌዴራል መንግሥት ሕግን መሠረት ያደረገ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳይ ላይ ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን የለውም ሊባል አይችልም፡፡ ነገር ግን በፌዴራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አቀራረጽ መሠረት ከተለዩት ውስን የፌዴራል ፍርድ ቤት ሥልጣኖች ውጭ ያሉ በክልል ግዛት የሚነሱ ጉዳዮችን የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲመለከቷቸው የተተወ በመሆኑ ጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌዴራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት እንዲታዩ የተለዩ ጉዳዮችን (exclusive jurisdiction) በግዛታቸው በተከሠቱ ጉዳዮች፣ ባሉ ሰዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሱ ሲሆን በውክልና (delegation) እንዲመለከቱ በሕገ-መንግሥት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በክልል የሚነሱ የፌዴራል ጉዳዮች ላይ ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን አላቸው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 የተመለከቱት የፌዴራል ጉዳዮችን በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣናቸውን ያከፋፈለ በመሆኑ

ይሄዉ ሕግ መሠረት ተደርጎ ሲታይ የፌዴራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን እንዳለው ያሳያል። የአፋር፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሶማሌና የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በሕገ-መንግሥቱ የተሰጣቸዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ሥልጣን በውክልና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶቻቸዉ የማየት ሥልጣን በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 322/1995 ሲነሳ በእነዚህ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደራጀቱ ታወጀ እንጂ በአምስቱ ክልሎች ግዛቶች የሚነሱ ጉዳዮችን የመመልከት የሥረ-ሥልጣን እንደ አዲስ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለመሠጠቱ ቀድሞውንም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 መሠረት የሥረ-ነገር ሥልጣን ተወስኖ ያደረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ውጭ በእነዚህ ክልሎች ሲደራጅ የማስቻያ ቦታው የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዮችን ለማየት የግዛት ክልል ሥልጣን ያገኛል።በአዋጅ ቁጥር 322/1995 መሰረት ከተጠቃሾቹ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዉክልና ስልጣን ቢነሳም የእነዚህ ክልሎች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዉክልና ሥልጣንም ሆነ የሌሎቹ ክልሎች የዉክልና ሥልጣን በሕገ መንግስቱ በተደነገገዉ አግባብ እስካሁን አልተነሳም። ይሕም የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸው ባሉ ሰዎቸ ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሳ በውክልና የሚመለከቱትን የፌዴራል ጉዳይ ውክልናቸው ሳይነሳ ጉዳዩ ለፌዴራል ፍርድ ቤት ቀርቦ ከታየ በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተውን የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) አለመከተል ስለሚሆን ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ይሆናል።

በዚህ መልኩ በሕገ-መንግሥቱ ለክልሎች የተሰጠዉን ሥልጣን አተገባበር በተመለከተ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 182775 ላይ በቀን 22/04/2013 ዓ/ም እና የሠ/መ/ቁጥር 201652 እና በቀን 05/02/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንደተገለጸዉ በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከተመለከተው የግዛት ክልል ሥልጣን የተለየ አተገባበርና ውጤት ያለው እንደሆነ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል። በመሆኑም ጉዳዩ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንደተቀረጸው የግዛት ክልል ሥልጣን በዋነኛነት አመቺነትን ብቻ መሠረት ያደረገ ስለሆነ አመቺ እስከሆነ ድረስ በፌዴራል ፍርድ ቤት ሊታይ ይችላል ከተባለ በሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶች ውክልና ሊነሳ የሚችለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 2/3ኛ ድምጽ ብቻ ስለመሆኑ በአንቀጽ 78/2 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ፤ የክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ የተሠጣቸውን የውክልና ሥልጣን በሕጉ በተገለጸው አግባብ ሳይነሳ በፍርድ ቤቶች ውክልናውን የማንሳት ውጤት ያስከትላል። ሕገ- መንግሥቱ የፌዴራል ጉዳይን በውክልና በክልል ፍርድ ቤቶች እንዲታይ በማድረግ ሊያሳካው የፈለገው ዓላማም ከግብ እንዳይደርስ ያደርጋል።

በተጨማሪም ጉዳዩን የሚመለከተው ፍርድ ቤት ሥልጣን የሚወሰነው በሕግ ሆኖ እያለ በክልል ፍርድ ቤት በውክልና ሊታይ የሚችል ሥልጣን በፌዴራል ፍርድ ቤት የሚቀርብ ከሆነ ተከራካሪዎች ክሱን የሚያቀርቡበት ፍርድ ቤት የፌዴራል ወይስ የክልል ፍርድ ቤት መሆን አለበት የሚለዉን በራሳቸው ምርጫ እንዲወስኑ (forum shopping) ስለሚያደርግ ተገቢ ያልሆነ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓት እንዲፈጠር ዕድል ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ምክንያቶች የክልል ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግሥቱ የፌዴራል ጉዳዮችን በውክልና እንዲመለከቱ የተሠጣቸው ሥልጣን መሠረቱ የፌዴራል አወቃቀር በመሆኑ ውክልናቸው በሕግ እስካልተነሳ ድረስ ጉዳዮቹ ለፌዴራል ፍርድ ቤት ሊቀርቡ አይችሉም፡፡ ጉዳዮቹ ቀርበው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከታዩ ውጤቱም አስገዳጅነት ያለውን የፍርድ ቤት ሥልጣን ክፍፍል የሚጥስ ስለሆነ ጉዳዩ በየትኛውም ደረጃ ፍርድ ቤት ሲደርስ በተከራካሪዎች ሆነ በፍርድ ቤቱ የሥልጣን ጥያቄው ተነስቶ ክሱ ውድቅ ሊደረግ እና ከዚህ ሥርዓት ዉጭ የተሰጠ ዉሳኔ ካለም ሊሻር ይገባል፡፡

ይህ ከላይ የተመለከተዉ የሕግ ትርጉም ተግባራዊ መደረግ የሚችለዉ ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን ያለዉ ክልል መደበኛ የዳኝነት አገልግሎት በሚሰጥበት ሁኔታ ላይ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነዉ፡፡ አከራካሪ የሚሆነዉ አንድ ክልል በተለያየ ምክንያት በክልሉ ዉስጥ መደበኛ የዳኝነት ሥልጣን መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ ከሆነ በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) አተገባበር ምን መሆን አለበት የሚለዉ ከሰዎች ፍትህ ከማግኘት እና በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ ከማግኘት መብቶች ጋር ተገናዝቦ ታይቶ ምላሽ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ እንደሚታወቀዉ ፍትህ የማግኘት መብት (*Right to Access to Justice)* በራሱ ሰብዓዊ መብት ሆኖ በተሟላ መልኩ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር የሚያስችል መሰረታዊ መብት ነዉ፡፡ይህ መብት ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸዉና ባጸደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት ፣ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና  ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ላይ እዉቅና ያገኘ መብት ነዉ፡፡ለአብነት ለመጥቀስ ያህል በዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን(International Covenant on Civil and Political Rights/ICCPR) አንቀጽ 2(3/ሀ እና ለ) 26 ላይ ማንኛዉም ሰዉ ፍትሕ የማግኘት መብት እና በሕግ ፊት እኩል ሆኖ የመታየትና እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለዉ ደንግጓል፡፡እነዚህን ድንጋጌዎች አተገባበር በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚቴ እንዳብራራዉ አገራት ሰዎች መብቶቻቸዉ ሲጣስ አቤቱታ አቅርበዉ ዳኝነታዊ መፍትሔ እንዲሰጣቸዉ መጠየቅ የሚችሉበትንና ዉጤታማ ፍትህ የሚያገኙበትን ተደራሽና ሥልጣን ያለዉን አካል በሕግ ስርዓታቸዉ የማቋቋምና የማመቻቸት ግዴታ አለባቸዉ፡፡እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ(Universal Declaration of Human Rights) አንቀጽ 7፣8፣እና 10 ላይ እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ በአገራት ሕግ ወይም ሕገ መንግስት በተደነገገዉ አግባብ ነጻና

ገለልተኛ በሆነ አካል ፊት ቀርቦ መብቱን ለማስከበር የሚያስችል ዳኝነታዊ መፍትሄ የማግኘት እና በሕግ ፊት እኩል ጥበቃ የማግኘት መብት እንዳለዉ ተደንግጓል፡፡

በተመሳሳይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 25 ላይ ሁሉም ሰዎች… በመካከላቸዉም ማንኛዉም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል ሲል ደንግጓል፡፡እንዲሁም ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ የማግኘት መብት እንዳለዉ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37/1 ስር ተደንግጓል፡፡በተጨማሪም ሕገ መንግስቱ ማንኛዉም ሰዉ እነዚህንና ሌሎች መብቶቹን የሚያስከብርበትን ነጻና ገለልተኛ ፍርድ ቤቶችን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ አቋቁሟል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ ከዉል ዉጭ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገ የጉዳት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መሰረት ያደረገ ሆኖ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ጉዳት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉ በትግራይ ክልል ዉስጥ በሚገኝ ስፍራ በደረሰ የተሽከርካሪ ግጭት ምክንያት ነዉ፡፡አደጋዉ የደረሰዉ በቀን 28/08/2007ዓ/ም ሲሆን አመልካች ለደንበኛዉ የከፈለዉ ካሳ እንዲተካለት በደንበኛዉ በመዳረግ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ያቀረበዉ ደግሞ በቀን 02/06/2009ዓ/ም ነዉ፡፡በዚህ ጊዜ በትግራይ ክልል መንግስት እና በፌዴራል መንግስት መካከል ጤናማ ግንኙነት የነበረበት ጊዜ በመሆኑና የትግራይ ክልል ፍርድ ቤቶች መደበኛ የዳኝነት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙበት ጊዜ ነበር፡፡በሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ክሱ የሚቀርበው ጉዳቱ በደረሰበት ሥፍራ በሚገኝ ፍርድ ቤት መሆኑን ስለግዛት ክልል በሚደነግገው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 27/1 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሕም ክሱ በትግራይ ክልል ዉስጥ በሚገኝ ፍርድ ቤት እንደሚታይ ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል የተከራካሪዎችን ማንነት ስንመለከት አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በፌደራል መንግሥቱ የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች መሆናቸዉ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪም በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ በጎ አደራጊ ማኅበር መሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/6 መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ምክንያት ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ቢሆንም ጉዳዩ የተነሳው በትግራይ ክልል በመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ በተሠጠው ውክልና መሠረት ክስ ከቀረበበት ገንዘብ መጠን አንጻር ጉዳዩ መታየት ያለበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡በመሆኑም አመልካች ከላይ በተመለከተዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/2 መሰረት ክሱን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረቡም ሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በትግራይ ክልል ዉስጥ የተከሰተን ከዉል ዉጭ የሆነ ኃላፊነትን መሰረት ያደረገ የካሳ ጉዳይ የሚመለከት ክስ በዉክልና ሥልጣን በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚገባዉ ነዉ ብሎ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ጉዳዩን በስረ ነገሩ ተመልክቶ ዉሳኔ መስጠቱ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ሆኖም የትግራይ ክልል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በሚቃረን አኳኋን በክልሉ ምክር ቤት የምርጫ ሕግ በሚል አዋጅ ቁጥር 352/2012ን በማዉጣት፣ የምርጫ ኮሚሽን በማቋቋም እና ክልላዊ ምርጫ ማካሄዱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የሚቃረን ስለሆነ ይህ አዋጅም ሆነ ይህንን አዋጅ ተከትሎ የተደረገዉ ምርጫም ሆነ የተቋቋመ የክልል መንግስት ኢ-ሕገ መንገስታዊ ስለሆነ ማንኛዉም ሕጋዊ ዉጤት እንደሌለዉና ከፌዴራል መንግስት ጋር ኦፊሴላዊ ግንኙነት ማድረግ እንደማይችል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ፌዴሬሽን ምክር ቤት ነሐሴ 30 ቀን 2012ዓ/ም ባካሄደዉ አስቸኳይ ስብሰባ ዉሳኔ አስተላልፏል፡፡ከዚህ በኋላም በተፈጠረ ግጭትና ይህንን ተከትሎ በፌዴራል መንግስቱ በተወሰደ ሕግ የማስከበር እርምጃ በትግራይ ክልልና በፌዴራል መንግስት መካከል ኦፊሴሊያዊ ግንኙነት እየተደረገ አይደለም፡፡ በዚሁ መልኩ ግንኙነቱ የተቋረጠዉ በክልሉና በፌዴራል አስፈጻሚ አካላትና ከምክር ቤቶች ጋር ብቻ ሳይሆን በፌዴራል ፍርድ ቤቶችና በክልሉ ፍርድ ቤቶች መካከል ያለዉ ዳኝነታዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ግንኙነት ጭምር እስካሁን ተቋርጦ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በክልሉና በአካባቢዉ የሰላምና መረጋጋት እጦት ችግር ምክንያት ወደ ክልሉና ከክልሉ ወደ ሌሎች የአገራችን ክፍል የሰዎች ዝዉዉር የተገደበ ሆኗል፡፡ እነዚህም እዉነታዎች በገሀድ (በተግባር) የሚታይ በመሆኑ ችሎቱ የዳኝነት ግንዛቤ(judicial notice) የወሰደበት ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸዉን የዉክልና ሥልጣን ተግባራዊ ማድረግ በማይችሉበት ሁኔታ ላይ መሆናቸዉን ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ምንም እንኳን ክሱ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበበት ጊዜ ጉዳዩን በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80/2 መሰረት የመዳኘት የዉክልና ሥልጣን ያለዉ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ክሱን ተቀብሎ ጉዳዩን በስረ ነገሩ ተመልክቶ ዉሳኔ መስጠቱ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ቢሆንም በዚህ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 9 መሰረት በዚህ ችሎት ቢሻር አመልካች ክሱን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ስለማይችል ፍትህ የማግኘት መብቱን ያጣል፡፡ እንዲሁም ተመሳሳይ የፌዴራል ጉዳይ ያላቸዉ ሌሎች ሰዎች መሰል ችግር በሌለባቸዉና የዉክልና ሥልጣን ባላቸዉ ክልሎች በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ክስ አቅርበዉ እንዲሁም የክሱ ምክንያት የተከሰተዉ በአዲስ አበባ እና በድሬ ዳዋ ከተሞች ሲሆን ደግሞ በቀጥታ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ክስ በማቅረብ ዳኝነታዊ መፍትሄና የሕግ ጥበቃ ሲያገኙ አመልካች ደግሞ የክሱ ምክንያት የተከሰተዉ በትግራይ ክልል በመሆኑና ክልሉ ከፌዴራል መንግስት ጋር ያለዉ ግንኙነት በተቋረጠበት ሁኔታና በጸጥታ ችግር ምክንያት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80/2ን መሰረት በማድረግ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሮ መተዉ ደግሞ በዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ሰነዶችና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ጥበቃ የተሰጣቸዉን የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት ከማሳጣትም ባለፈ ሰዎች

ሁሉ በመካከላቸዉ ማንኛዉም ልዩነት ሳይደረግባቸዉ እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸዉ የሚለዉን በሚቃረን አኳኋን በዚህ ረገድ የአመልካችን መሰረታዊ መብት ማሳጣት ይሆናል፡፡

ስለሆነም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ነጻ እና ገለልተኛ የዳኝነት አካል በየደረጃዉ ማቋቋም ያስፈለገዉ እነዚህንና ሌሎች የሰዎችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር በመሆኑ የክልል ፍርድ ቤቶች በሕጋዊ ምክንያት በሕገ መንግስቱ የተሰጣቸዉን የዉክልና ሥልጣን መጠቀምና ለዜጎች ፍትህ መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ሲሆኑ እና ጉዳዩም የፌዴራል ጉዳይ ሲሆን የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት ፣ እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት እና ሌሎች መብቶችን ማስከበር እንዲችሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ጉዳዩን ተቀብለዉ የመዳኘት ሥልጣን አላቸዉ ብለናል፡፡ በተጨማሪም አመልካች የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአሁኑ ጊዜ መደበኛ የዳኝነት ሥራ እየሰራ ባለመሆኑ ቀጥሎ ክሱን ማቅረብ የሚችለዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ በሆነበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ በቀረበለት ጊዜ በቀጥታ ክሱን ተቀብሎ ለመዳኘት ሥልጣን አልነበረዉም በሚል መነሻ ብቻ ዉሳኔዉ የሚሻር ከሆነ በአንድ ክርክር ተመሳሳይ የሆነ የጊዜ፣ የገንዘብና የሰዉ ጉልበት(ሀብት) ብክነት እንዲከሰት በማድረግ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓላማ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ምክንያቶች ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሕገ መንግስታዊ የሆነዉን የፍርድ ቤቶች የዉክልና ሥልጣን የተከተለ አይደለም በሚል ምክንያት ሊሻር አይገባም ብለናል፡፡

ሁለተኛዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉም አመልካች በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰዉ በ1ኛ ተጠሪ አሽከርካሪ ጥፋት ንብረትነቱ የ1ኛ ተጠሪ በሆነ ተሽከርካሪ ተገጭቶ ስለሆነ ለደንበኛዬ የከፈልኩትን ካሳ 1ኛ ተጠሪ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ክስ የመሰረተ ሲሆን 1ኛ ተጠሪም ሆነ 2ኛ ተጠሪ ጉዳቱ በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት የደረሰ ባለመሆኑ አመልካች ለደንበኛዉ የከፈለዉን ካሳ የመተካት ኃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ሰዉ ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ተገቢነትና ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከቷል)፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች የደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ የመገጨት አደጋ የደረሰበትና በዚህ መነሻ ካሳ የተከፈለበት ጉዳት ሊደርስ የቻለዉ በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በቀዳሚነት ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪዎች እንደነገሩ ሁኔታ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰዉ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት እንዳልሆነ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ መልኩ የማስረዳት ሸክም ያለባቸዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማስረጃ የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ሥልጣን ያላቸዉ ፍርድ ቤቶችም በግራ ቀኙ በቀረቡ ማስረጃዎች

ሳይገደቡና የገለልተኛነት ሚናቸዉንም ሳይተላለፉ አንጻራዊ እዉነታን የማፈላለግ ኃላፊነታቸዉን መወጣት በሚያስችላቸዉ መልኩ በተከራካሪ ወገኖች ሆነ በራሳቸዉ አነሳሽነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 ፣ 145/1፣249 ፣264 (1 እና 2) እና 345 መሰረት ተጨማሪ ምስክሮችን፣የሰነድ ማስረጃዎችን፣ የሙያ ምስክሮችን አስቀርበዉ መስማትና መመርመር ይችላሉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ለደንበኛዉ ካሳ እንዲከፍል ያደረገዉ ጉዳት በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ የደረሰዉ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ በወቅቱ ስለአደጋዉ ክስተት በትራፊክ ፖሊስ የተነሳዉን የአደጋ ፕላን እና ሪፖርት ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ይህ አመልካች ያቀረበዉ ማስረጃ በአደጋዉ ምክንያት በሰዉ ላይ ለደረሰ አደጋ ካሳ ለማስከፈል በቀረበ ክስ መነሻ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተከፈተ መዝገብ ላይ በተሰጠ ትዕዛዝ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ባለሙያዎችና የትራፊክ ፖሊሶች ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እንዲጣራ ተድርጓል፡፡ ኮሚቴዉ የአደጋዉ መንስኤ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ነዉ ተብሎ አስቀድሞ የቀረበዉ የትራፊክ ፖሊሲ የአደጋ ፕላንና ሪፖርት ትክክል እንዳልሆነና ለአደጋዉ መንስኤ የሆነዉን ጥፋት የፈጸመዉ የአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ እንደሆነ አረጋግጠዉ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ሪፖርት በማስረጃነት በመመርመርና የምስክሮችን ቃል ጭምር በመመዘን ጉዳቱ የደረሰዉ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት በመሆኑ ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለባቸወም ሲል ክሱን ዉድቅ አድርጓል፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4 እና 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲያርም ነዉ፡፡ ሰበር ችሎት የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትንና ተቀባይነትን (Production, relevancy and admissibility of evidence)እንዲሁም የማስረዳት ሸክምንና የማስረጃ ምዘናን (burden of proof and weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በግልጽ ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ መኖሩን አረጋግጦ ስህተቱ እንዲታረም ሊወስን ከሚችል በስተቀር ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች አቅርበዉ ማስረጃዎቹ ተመርምረዉና ተመዝነዉ የተደረሰዉን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ወደ ጎን በመተዉ ማስረጃዎችን በድጋሚ የመመዘን ተግባር ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ ፍሬ ነገር መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤት በዋናነት መሰረት የደረገዉ ማስረጃ በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች እና የትራፊክ ፖሊሶች ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ተጣርቶ የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ ኮሚቴ ተዋቅሮ የአደጋዉ መነሻ

ምክንያት እንዲጣራ የተደረገዉ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ባለሙያዎች አነሳሽነት ሳይሆን በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠ ትእዛዝ ነዉ፡፡ከላይ እንደገለጽነዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ አንድ አከራካሪ ጭብጥ በባለሙያ ተጣርቶ ማስረጃ እንዲቀርብለት ለማዘዝ እንዲችል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ይፈቅድለታል፡፡በዚህ መልኩ የቀረበዉ ማስረጃ ደግሞ አመልካች በማስረጃነት ያቀረበዉንና አስቀድሞ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ጥፋተኛ እንደሆነ ተገልጾ የቀረበዉ የትራፊክ ፖሊስ የተዘጋጀ የአደጋ ፕላን/ሪፖርት  ትክክለኛ ድምዳሜ አይደለም የሚያስብል በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በሳይንሳዊ መንገድ ስለአደጋዉ መንስኤ የሚያስረዳዉን ኋለኛዉን ማስረጃ መሰረት አድርጎ መወሰኑ ከማስረጃ አቀባበልም ሆነ ምዘና መርሆዎች አተገባበር አንጻር ጉድለት ፈጽሟል የሚያስብል አይደለም፡፡

እንዲሁም አመልካች ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ባለሙያዎችና የትራፊክ ፖሊሶች ያሉበት ኮሚቴ ተዋቅሮ ተጣርቶ የቀረበዉን ማስረጃ መቀበል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 85(3/ሀ እና ለ) ስር የተደነገገዉን እና በሰ/መ/ቁጥር 43452 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ በማለት ያቀረበዉንም ክርክር መርምረናል፡፡የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 በደንብ ቁጥር 395/2009 የተሻሻለ ሲሆን በዚህ በተሻሻለዉ ድንብ አንቀጽ 85 ላይ የተደነገገዉ በጠቅላላዉ በደንብ ተላላፊዎች ላይ ስለሚጣል ቅጣት የተደነገገ ሲሆን በተለይ በንኡስ አንቀጽ 4( ሀ እና ለ) ላይ ደግሞ ደንብ ተላላፊ ነዉ ተብሎ ቅጣት የተጣለበት ሰዉ ቅሬታ ሲያድርበት መቼ ለማን ቅሬታዉን ማቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ዉጭ በዚህ ድንጋጌም ሆነ በደንቡ ሌሎች ክፍሎች ላይ ስለአንድ የትራፊክ አደጋ በትራፊክ ፖሊስ የተነሳ የአደጋ ፕላን ወይም የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ሁኔታ ማሳያ ሪፖርት አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ በፍርድ ቤት ትእዛዝ በሌላ ባለሙያ ወይም በሌላ የትራፊክ ፖሊስ ባለሙያ ተጣርቶ እንዲቀርብ የሚከለክል ድንጋጌ አልተደነገገም፡፡ በትራፊክ ፖሊስ የተዘጋጀ የአደጋ ሁኔታ የሚያሳይ ፕላን/ሪፖርት እንደማንኛዉም የሙያ ምስክርነት ከፍተኛ ዋጋ (high probative value) ተሰጥቶ እንደሚመዘን አጠቃላይ የማስረጃ መርህ የሚያስገድድ ቢሆንም እንዲህ አይነት የሙያ ምስክርነት አጠራጣሪ በሆነ ጊዜ በሌላ ባለሙያ የሙያ ምስክርነት ማጣራትን የሚከለክል ወይም አስቀድሞ የመጀመሪያዉ የሙያ ምስክርነት የማይስተባበል ማስረጃ (አሳሪ/conclusive evidence) ነዉ የሚል የሕግ ድንጋጌም ሆነ ከዚህ አንጻር የተሰጠ የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔዉ መሰረት ያደረገዉ ማስረጃ ተጠቃሹን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እና የሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስ ነዉ በሚል አመልካች ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ኋለኛዉ የሙያ ምስክርነት ማስረጃ እና የምስክሮች ቃል መሰረት አድርጎና የተሻለ ዋጋ ሰጥቶ በመመዘኑ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 190749 በቀን 26/02/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 187653 ላይ በቀን 12/02/2014 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎትና ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 189608

የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች- 1. ወ/ሮ ትርንጎ ገመቹ
2. አቶ ቱፋ ደስታ
3. ወ/ሮ ሙሉዬ ያለው
} አልቀረቡም

ተጠሪዎች - 1. ወ/ሮ ብርሀኔ ገመቹ
2. ወ/ሮ መገርቱ ገመቹ
} ጠበቃ እጼሣ አራርሶ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ከተደረገ ዉል ይዘት ጋር በተገናኘ ክርክር ሲኖር የዉሉን ይዘት ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉን ማስረጃ የሚመለከት ነዉ፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪዎች ከሳሽ በመሆን በአመልካቾች ባቀረቡት ክስ በሟች እናታችን ወ/ሮ ነዲ ሆርዶፋ ስም በሱሉልታ ከተማ ቀሶ ወሰርቢ ቀበሌ ልዩ ቦታው ሹፋኔ ተብሎ ከሚጠራው ስር የሚገኝ መጠኑ 1.260 ሄክታር የሆነውን መሬት 1ኛ አመልካች እና ከሌላዋ እህታችን ወርቂ ገመቹ ጋር በውርስ አግኝተን በቀን 01/06/2005 ዓ.ም ባደረግነው የውል ስምምነት እያንዳንዳችን 2565 ካ.ሜ ደርሶን የተከፋፈልን ቢሆንም በግንቦት ወር 2007 ዓ.ም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩ ግለሰብ በተጠሪዎች ድርሻ ላይ አጥር ሰርተው ይዘውብናል፤ ይዞታችንን ለምን እንደያዙ ብንጠይቃቸው ከ1ኛ አመልካች ላይ ገዝተው እንደሆነና የስር 5ኛ ተከሳሽ የነበረው የሱሉልታ ከተማ አስተዳደርም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደሰጣቸው ገልጸውልናል፡፡ ውሉን እንዲያሳዩን ስንጠይቃቸው እኛም በ9500 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያለውን ባለ 30 ቆርቆሮ ቤት እንደሸጥንላቸው የሚያሳይ በሀሰት የተዘጋጀ በቀን 02/08/2002 ዓ.ም የተፃፈ ውል ይዘው ቀርበዋል፡፡ በቀን 28/04/2007 ዓ.ም 1ኛ

አመልካች መሬቱን መንግስት ለልማት ስለሚፈልገው ካሳ ለመውሰድ ቅጽ መሙላት አለባችሁ በማለት ጠርታን የተለያዩ ወረቀቶች ላይ የፈረምን ሲሆን አመልካቾች ያቀረቡት ውል ላይ ያለው ፊርማ የእኛ ሆኖ እንኳን ቢገኝ ተጭበርብረን የፈረምነው እና ሽያጩም ባዶ መሬትን የሚመለከት በመሆኑ ህገ-ወጥ ስለሆነ ውሉ ተሠርዞ መሬታችንን እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ያደረግኩት ውል ስለሌለ በእኔ ላይ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት፣ 2ኛ አመልካች ዉሉ ከተደረገ ሰባት ዓመት ስለሞላው ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት፣ 3ኛ አመልካች ደግሞ ተጠሪዎች መሬቱ የእነሱ ስለመሆኑ ያቀረቡት ምንም ማስረጃ ስለሌለ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚሉ መቃወሚያዎችን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የሱሉልታ ወረዳ ፍርድ ቤትም የተከሳሾችን የመጀመሪያ መቃወሚያ ተቀብሎ ክሱን በብይን ውድቅ ያደረገዉ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው በፊንፍኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይኑን በመሻር በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሶ ለወረዳ ፍርድ ቤቱ ልኮለታል፡፡ በዚሁም መሠረት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ያከራከረውና እና ማስረጃ የሰማው የወረዳ ፍርድ ቤቱ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ ያለውን ቤት ከ1ኛ አመልካች እና ከእህታቸው ወርቂ ገመቹ ጋር በጋራ በመሆን ባደረጉት ውል በብር 390,000.00 የሸጡ መሆናቸው በቀረበው ውል እና በምስክሮች ቃል መረጋገጡን ጠቅሶ አመልካቾች ይዞታውን ሊለቁ አይገባም በማለት የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው እና በቀን 02/08/2002 ዓ.ም የተደረገው ውል በባዶ ቦታ ላይ የተደረገ እና ቀኑ በሀሰት ወደ ኋላ ተደርጎ የተፈረመ ስለሆነ እንዲሰረዝ እና አመልካቾችን ጨምሮ በስር ፍርድ ቤት 4ኛ ተከሳሽ የሆነው ግለሰብ በይዞታው ላይ የሰሩትን ግንባታ አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በይግባኙ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሉ በይዞታው ላይ የተሰራውን ቤት ተጠሪዎች ስለመሸጣቸው ገልጾ እያለ እና በምስክርም ተረጋግጦ እያለ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በባዶ መሬት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል ነው በማለት ውሉን መሠረዙ አግባብ አይደለም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች ግንባታውን አፍርሰው ይዞታውን ለተጠሪዎች እንዲመልሱ፤ ተጠሪዎች ደግሞ የተቀበሉትን ብር 390,000.00 እንዲመልሱ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነውን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች በቀን 20/05/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች ዘርዝረው በማቅረብ እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታቸዉ ይዘትም በአጭሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሉ በይዞታው ላይ የተሰራውን ባለ 30 ቆርቆሮ ቤት በግዢ ለአመልካቾች የተላለፈልን ስለመሆኑ ተገልጾና በምስክሮችም ጭምር ተረጋግጦ እያለ ሽያጩ የባዶ መሬት ሽያጭ ስለሆነ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት መወሰናቸው፣ ተጠሪዎች 1ኛ አመልካች አሳስታን ውሉ ላይ አስፈርማናለች ብለው ቢከራከሩም ስለመሳሳታቸው በማስረጃ ሳያስረዱ በብር 2,000,000.00 ወጪ የሰራነውን ቤት አፍርሳችሁ ይዞታውን መልሱ መባሉ፣ በ 9500 ካ.ሜ ላይ የተሰራን ቤት መግዛት መሬቱን ለመግዛት ያለን ሀሳብ ያመለክታል መባሉ ውሉን ያለገናዘበ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የቤት ሽያጭ ውል የተፈፀመ ለመሆኑ በቀን 02/08/2002 ዓ.ም የተደረገው ውል ቀርቦ እያለ ውሉ የተደረገው በጋራ መሬት ስለሆነ ፈራሽ ነው ተብሎ የተወሰነበት አግባብ መጣራት አለበት በሚል ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 18/02/2013 ዓ.ም ጽፈው በሰጡት መልስ አመልካቾች ተደርጓል የሚሉት ውል ላይ የሰፈረው ቀን ወደ ኋላ ተደርጎ የተፃፈ ሲሆን በጊዜውም መሬቱ ቤት የሌለበት የእርሻ መሬት ነበረ፤ እስከ 2005 ዓ.ም ድረስም ቤት አልነበረበትም፤ የቀረበው ውልም በሀሰት የተዘጋጀ እንጂ እኛ የፈረምንበት አይደለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ብር 390,000.00 ለአመልካቾች እንድንመልስ ከሰጠው ውሳኔ ውጪ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ በዉርስ ከተከፋፈሉ በኋላ ያደረጉት የሽያጭ ዉል ሳይኖር ወይም የተጭበረበረ የሽያጭ ዉል ሰነድ መሠረት በማድረግ ይዞታዉን የአሁን 1ኛ አመልካች ለ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ማስተላለፏን እና ሽያጩም በባዶ ቦታ ላይ የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፤ አመልካቾች በበኩላቸዉ ቤቱን የገዙት በተጠሪዎች ስምምነት መሆኑንና የተሸጠዉም ቤት እንጂ ባዶ ቦታ አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ዉድቅ ሆኖ እንዲወሰንላቸዉ መከራከራቸዉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ የሽያጭ ዉል በተጠሪዎች መደረጉን እንዲሁም ተደረገ የተባለዉ የሽያጭ ዉልም ቤትን ወይም ባዶ ቦታን የሚመለከት መሆን ያለመሆኑም ግራ ቀኝን ያከራከረ ነጥብ መሆኑን ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ቀደም ሲል የተጠሪዎች፣ የ1ኛ አመልካች እና

የሌላ አንድ እህታቸዉ የዉርስ ድርሻ የነበረ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ይዞታዉ በህጋዊ መንገድ ለ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ተላልፏል ማለት የሚቻለዉ የሽያጭ ዉሉ በተጠሪዎች ስምምነት ወይም ይሁንታ የተደረገ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ከዚህም አልፎ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) መሠረት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት በሽያጭ ማስተላለፍ የተከለከለ በመሆኑ እና በዚህም ምክንያት ባዶ ቦታን አስመልክቶ የሚደረግ የሽያጭ ዉል በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1716 መሠረት ህገ ወጥ ዉል ነዉ፡፡ ስለሆነም 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቤትና ቦታዉ ላይ መብት ኖሯቸዉ ይዘዉ መቀጠል የሚችሉት ዉሉ በተጠሪዎች ይሁንታ ወይም ስምምነት የተደረገ መሆኑ እንዲሁም የዉሉ ይዘት ቤትን እንጂ ባዶ ቦታን የማይመለከት መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ መሰረታዊ ጭብጥ ዉሉ ስለመደረጉ ብሎም ዉሉ ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን የሚመለከት መሆን አለመሆኑን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ምን ዓይነት ሊሆን ይገባዋል? የሚለዉ ነጥብ ነዉ፡፡ ይህንንም ጉዳዩ ዉሉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት መሆኑን ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የአገራችን የፍትሐብሔር ፍትሕ ሥርዓት የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ለዜጎች የንብረት መብት ጥበቃ ከማድረግ አንፃር ፋይዳዉ የጎላ ስለመሆኑ ግምት ዉስጥ በማስገባት በፍትሐብሔር ህጉ የተለያዩ አንቀፆቹ ስለ ምዝገባ ይደነግጋል (አንቀጽ 1553-1646 እንዲሁም 1723፣ 2878 እና 3052 ይመለከቷል)፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የየራሳቸዉ የሆኑ ዓላማዎች የሚኖሩት ቢሆንም፤ አጠቃላይ ዓላማቸዉ ግን ለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ጥበቃ በመስጠት እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ባለይዞታዉ መብቱን ሲያገኝ ወይም ንብረቱ በሆነ ምክንያት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን በሚያስተላልፍበት ወቅት የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ መንግስታዊ አካል ካልተመዘገበ ህግ ፊት የሚጸና መብት እንዳይኖረዉ በማድረግ ዜጎች በዚህ ግዙፍነት ያለዉ ንብረት ያላቸዉን መብት ከፍላጎታቸዉ ዉጪ በሆነ መንገድ እንዳያጡ ጥበቃ ለመስጠት፤ ብሎም ንብረቱ ወይም ንብረቱን የሚመለከቱ መብቶች በዉል ሊተላለፉ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑንም በማጣራት የዉሉን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ጭምር ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ከሚከናወኑት ህጋዉያን ተግባራት ጋር በተያያዘ ምዝገባ ወይም ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ እንዲረጋገጥ የግድ ከሚልባቸዉ ዉስጥም አንዱ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1723(1) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ሲሆን፣ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስተላለፍ የሚደረጉ ዉሎች በጽሑፍና ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መሆን አለበት፡፡ ህግ አዉጪዉ ይህ እንዲሆን የፈለገበት ምክንያትም ዉሉ በተዋዋዮች መካከል ስለመደረጉ ለማረጋገጥ (certainty in transactions) ስለመሆኑ በዙሪያዉ ከተፃፉት አንዳንድ ጽሑፎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፤ ይህ ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ዉል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ ወስኗል፡፡

በሌላ በኩል ተከራካሪ ወገኖች ዉሉ መደረጉን ተማምነዉ ነገር ግን የዉሉን ይዘት አስመልክቶ የተለያዩ መከራከሪያዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 2005 በጽሑፍ ሰነዱ ላይ ስለሚገኘዉ የስምምነት ቃል እንዲሁም ስለተፃፈዉ ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ይደነግጋል፡፡ ይሁንና ይህ ሊሆን የሚችለዉ እንደ ዉለታዉ ዓይነት የጽሑፍ ዉል አደራረግን ሥርዓት አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1678(ሐ) እና 1719(1) መሠረት አስፈላጊ የሆነዉን የዉል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ ስለመሆኑ ከግምት ዉስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ የዉል አደራረግ ሥርዓት በተለየ አኳኋን እንዲደረግ በህግ ከተመለከተዉ ዉስጥ አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ዉል በጽሑፍ ሆኖ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ መረጋገጥ እንዳለበት የሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1723(1) ድንጋጌ ነዉ፡፡ በመሆኑም የዉሉን ይዘት አስመልክቶ ማለትም ዉሉ የተደረገዉ መቼ ነዉ? የሽያጭ ዉል ከሆነ በምን ያህል ዋጋ ነዉ የተደረገዉ? ለዉሉ ምክንያት የሆነዉ ምን ዓይነት ንብረት ነዉ? የትስ የሚገኝ ነዉ? የሚሉት እና መሰል የይዘት ክርክሮች የተነሱ እንደሆነ ይህን ለማጣራት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዓይነትም በጽሑፍ ሆኖ ዉል ለማዋዋል ስልጣን ባለዉ አካል ፊት የተደረገ ዉል ሊሆን ይገባል፡፡ ይህን አስመልክቶም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 78398 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መደረጉን ብሎም የሽያጭ ዉሉን ይዘት አስመልክቶ የሚነሳን ክርክር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዉሉ ዉል ለማማዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ዘንድ ቀርቦ መመዝገቡን ወይም መረጋገጡን የሚያሳይ ሊሆን የሚገባዉ መሆኑን እና ለእንደዚህ ዓይነት ክርክር የሰዉ ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳት የማይቻል መሆኑን ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ዉሉ መደረጉንና የዉሉም ይዘት ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን የሚመለከት መሆኑን የሚያሳይ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1723(1) መሠረት ዉል ለማዋዋል ስልጣን ባለዉ አካል ዘንድ የተረጋገጠ ወይም የተመዘገበ ዉል ያቀረቡ ስለመሆኑ መዝገቡ አያሳይም፡፡ ስለሆነም በእርግጥም ተደረገ የተባለዉ ዉል የተጠሪዎችን ስምምነት መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ ጥያቄ ዉስጥ የሚያስገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዉሉ ቤትን የሚመለከት ስለመሆኑ አመልካቾች ከላይ በተመለከተዉ አግባብ ያቀረቡት ማስረጃ ከሌለ የዉሉ ይዘት ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን የሚመለከት ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ባዶ ቦታን የሚመለከት ዉል ደግሞ በህግ ፊት ተፈፃሚነት የሌለዉ በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በዉል መሠረት ይዘናል በሚሉት ይዞታ ላይ ባለይዞታ ሆኖ ሊቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ በመሆኑም የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባዉ ዉሉን ለማስረዳት የግራ ቀኙን ምስክሮች እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን መሠረት ማድረጉ የጉዳዩን ልዩ ባህሪ መሠረት ያላደረገ የማስረጃ አቀባበል በመሆኑ ስህተት ቢሆንም፣ ዉሉ

ሊጸና አይገባም በሚል ዉሉ ፈርሶ አመልካቾች የያዙትን መሬት ሊለቁ ይገባል በሚል የሰጡት ዉሳኔ ከዉጤት አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላዉ መታየት የሚገባዉ ነጥብ በቦታዉ ላይ ወጪ አወጥተን ቤት ሰርተናል በማለት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሚያቀርቡት ክርክር ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤትና ቦታ የሚገኘዉ በሱሉልታ ከተማ አስተዳደር ስር መሆኑ አላከራከረም፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ቤትና ቦታዉን ይዘን በቦታዉ ላይ ገንብተናል ለሚሉት ቤት ምክንያት የሆነዉ ዉል ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ህጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ ይዞታዉን ይዞ የመቀጠል መብት የላቸዉም፡፡ የዉል መፍረስ በዉል የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች እንዲቋረጡ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸዉ ማድረግን የሚያስከትል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1807(ሀ) እና 1815 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዉል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮች በተቻለ መጠን ዉሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ እና ዉሉን ለመፈጸም የተሠራ ሁሉ ቀሪ ሆኖ በማናቸዉም አኳኋን ዉጤት እንደሌለዉ የሚደነግገዉ የህጉ አንቀጽ 1815 ድንጋጌ በተለይ ሲታዩ በዉል መሠረት አንዱ ለሌላዉ የፈጸመዉ ተግባር ካለ ቀሪ ተደርጎ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ግዴታ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሉ አንድን ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ከሆነ እና ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ዉጤቱ የሚሆነዉ ንብረቱን ገዝቶ በዉሉ መሠረት የተረከበዉ ተዋዋይ ንብረቱን ለሻጩ መልሶ እንዲያስረክብ፣ ሻጩም ደግሞ በዉሉ መሠረት የተቀበለዉ ገንዘብ ካለ ገንዘቡን ለገዥዉ እንዲመልስ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ግራ ቀኝ የተቀባበሉትን ነገር ባሉበት ሁኔታ አንዱ ለሌላዉ እንዲመልስ ከማድረግ ዉጪ ሻጩ በዉሉ መሠረት ከተቀበለዉ ገንዘብ በላይ ገዥዉም ደግሞ ከተረከበዉ ንብረት በላይ አንዱ ለሌላዉ ለመመለስ የማይገደዱ መሆኑን ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ህጋዊ ዉጤት የማያስከትል መሆኑ ተረጋግጦ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲፈርስ በተወሰነዉ ዉል መነሻነት በእጃቸዉ ባስገቡት ይዞታ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ ተጨማሪ ቤቶችን የገነቡ መሆኑን ገልጸዉ ይከራከራሉ፡፡ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1815 መሠረት ዉሉ በመፍረሱ ምክንያት 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በዉሉ ምክንያት በእጃቸዉ የገባዉን ይዞታ ለተጠሪ የማስረከብ ግዴታ እንዲሁም በዉሉ ምክንያት የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸዉ የመጠየቅ መብት ያላቸዉ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በእጃቸዉ ያስገቡትን ይዞታ መልሰዉ እንዲያስረክቧቸዉ የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል፤ ይህ ዉሉ በመፍረሱ ምክንያት ግራ ቀኝ የሚኖራቸዉ መብትና ግዴታ ሲሆን፣ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቦታዉ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ የገነቡት ቤት በዚህ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይሆንም፡፡ በዚህ ረገድ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በእጃቸዉ በገባዉ ቤትና ይዞታ ላይ የሰሩትን ተጨማሪ ግንባታ አስመልክቶ ሁለቱ አማራጮች ይኖራቸዋል፡፡ አንደኛዉ አማራጭ በይዞታዉ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ የሰሩትን ቤት አፍርሰዉ ባዶ ቦታዉን ብቻ ለተጠሪዎች

ማስረከብ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ በተጨማሪነት በቦታዉ ላይ የተሰራዉን ቤት እዚያዉ በመተዉ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ መጠየቅ ነዉ፡፡ አመልካቾች ሁለተኛዉን አማራጭ ከመረጡ ይህ ጥያቄአቸዉ የሚስተናገደዉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1818 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ነዉ፡፡

በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1818 ድንጋጌ መሠረት ዉሉ ከመፍረሱ የተነሳ ንብረትን የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰዉ ንብረቱን ለዉጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አድርጎ እንደሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጪ የተነሳ ያሉትን መብቶች በከዉል ዉጪ ኃላፊነት ድንጋጌዎች መሠረት መጠየቅ ይችላል፡፡ እንደሚታወቀዉ በዉል አንድ ሰዉ አንድን ንብረት በእጁ ካስገባ በኋላ በእራሱ ወጪ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ያደረገ እንደሆነ በእራሱ ወጪ ተጨማሪ ነገር የሰራዉ ተዋዋይ ንብረቱን መልሶ ሲያስረክብ ከነማሻሻያዎቹ ለሌላኛዉ ተዋዋይ ሊያስረክብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህ መሆኑ በአንድ በኩል ንብረቱ የተመለሰለት ሰዉ ያላግባብ እንዲበለጽግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱን የማስረከብ ግዴታ ያለበት ወገን ያላግባብ ተጎጂ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1818 ድንጋጌም ለእነደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች መፍትሔ የመስጠት ዓላማ ያደረገ በመሆኑ የድንጋጌዉ አፈፃፀምም ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለዉን ተወዳዳሪ ጥቅም (computing interests) ማስታረቅ በሚያስችል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ዉሉን ተከትሎ በእጃቸዉ በገባዉ ይዞታ ላይ ቤት ገንብተዉ ከሆነ ቤቱን ለመገንባት ያወጡትን ወጪ ተጠሪዎች እንዲከፍሏቸዉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ይህ የዳኝነት ጥያቄም የገንዘብ መጠኑ (ግምቱ) ተገልጾ ዳኝነት ተከፍሎበት የሚጠየቅ ነዉ፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቦታዉ ላይ የሰሩት ቤት ግምት ጠቅሶ ከማቅረብ ዉጪ ተጠሪዎች ቤቱን ለመስራት ያወጡትን ወጪ እንዲከፍሏቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ስለመኖሩ መዝገቡ አያሳይም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1179 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ በባለይዞታዉ እና ይዞታዉን ይዞ ቤት በሰራ ሰዉ መካከል የታወቀ ግንኙነት በሌለበት ሁኔታ ብቻ በመሆኑ ዉሉ መፍረሱን ተከትሎ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቦታዉ ላይ የሰሩት ቤት ህጋዊ ዉጤትን አስመልክቶ ተፈፃሚነት ያለዉ ድንጋጌ አይደለም፤ ይልቁንም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ ከላይ የተመለከተዉ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1818 ድንጋጌ ነዉ፡፡ ከዚህም አልፎ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቦታ በከተማ ዉስጥ የሚገኝ መሆኑ በመረጋገጡ የገጠር መሬትን አስመልክቶ አሁን በስራ ላይ ያለዉ አዋጅ ቁጥር 130/99 በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 1179 እንዲሁም የገጠር መሬት የገዛ ሰዉ ቤቱን አፍርሶ መሄድ እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 130/99 ላይ የተመለከተዉን በዋቢነት በመጥቀስ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የሰሩትን ቤት አፍርሰዉ ሊሄዱ ይገባል በሚል የደረሰበት ድምዳሜ የጉዳዩን መሠረታዊ ባህሪ ከግምት ዉስጥ ያላስገባ ድንጋጌ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ የያዙት በህግ ፊት ተቀባይነት በሌለዉ ዉል መሠረት በመሆኑ ዉሉ ፈርሶ ይዞታዉ ለተጠሪዎች ሊመለስ ይገባል በሚል በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ሆኖ ነገር ግን 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቤቱ ላይ የሰሩትን ቤት ሊያፈርሱ ይገባል በሚል የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 311491 በቀን 16/03/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ዉሉ ፈራሽ ነዉ በሚል 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ ለተጠሪዎች ሊመለስ ይገባል በሚል የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፤ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቦታዉ ላይ ለሰሩት ቤት ያወጡትን ወጪ ሊጠይቁ አይችሉም በሚል ምክንያት ቤቱን አፍርሰዉ ሊሄዱ ይገባል በማለት የተሰጠ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በቦታዉ ላይ የሰሩት ቤት ካለ ቤቱን ለመስራት ያወጡትን ወጪ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1818 መሠረት ተጠሪዎች እንዲከፍሏቸዉ ዳኝነት የመጠየቅ መብት አላቸዉ ተብሏል፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 186626

የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ ሶሪ ጉተማ

ተጠሪዎች- 1. ወ/ሮ ሀረገወይን ተ/ጽዮን

2. አቶ ያሲን ኑሩ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ዉል በህግ ተቀባይነት ባለዉ ምክንያት ሊፈርስ ወይም ዉሉ ዉጤት እንዳይኖረዉ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም የሦስተኛ ወገንን መብትና ጥቅም ለመጠበቅ ሲባል ጸንቶ ሊቀር የሚችልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ለፍርድ ቤቱ ያቀረበዉን የመቃወም አቤቱታ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረበዉ የመቃወም አቤቱታ ይዘትም በተጠሪዎች መካከል የነበረዉ ጋብቻ በፍርድ ቤት መፍረሱን ተከትሎ በተደረገ የንብረት ክርክር የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ናቸዉ ተብለዉ ዉሳኔ ከሰጠባቸዉ ዉስጥ በሻሸመኔ ከተማ አሌሉ ቀበሌ 10 ውስጥ በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ቤት 20/07/2009 ዓ.ም በተፃፈ ውል በብር 410,000.00 ከ2ኛ ተጠሪ ወኪል ገዝቼ ዉሉም በከተማው አስተዳደር ውል ምዝገባ ክፍል ቀርቦ ከተረጋገጠ በኋላ ስመ ንብረቱ በስሜ ዞሮ ማስረጃ ተሰጥቶኝ እና ተጨማሪ ገንዘብ አውጥቼ ቤት ሰርቼበት እየተጠቀምኩበት እያለ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ ይካፈሉት ተብሎ መወሰኑ መብቴን ስለሚነካ ውሳኔው ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ ለመቃወም አቤቱታዉ በሰጡት መልስ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት እንጂ የአመልካች አይደለም፤ ቤቱ ስለመሸጡም አላውቅም፡፡ ቤቱ ለአመልካች በሽያጭ ተላልፏል የተባለው በቀን 29/09/2009 ዓ.ም ሲሆን ቤቱ በፍርድ ቤት የታገደው ደግሞ በቀን 22/07/2007 ዓ.ም ነው፡፡ 2ኛ

ተጠሪ ንብረቱ መታገዱን እያወቀ በጋራ ያፈራነውን ሀብት ሊያሳጣኝ ሲል ሆን ብሎ እንዲሸጥ ያደረገ እና ውሉን ያዋዋለው አካልም ቤቱ የታገደ መሆኑን እያወቀ እንዲሸጥ ማድረጉ ተገቢ ስላልሆነ የአመልካች ተቃውሞ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ እኔና 1ኛ ተጠሪ በ 2005 ዓ.ም ቤቱን ወ/ሮ ቤሩት ቀነዓ ለምትባል ግለሰብ በብር 80,000.00 በመሸጥ ገንዘቡንም ለቤተሰብ ጥቅም ያዋልነው ሲሆን 1ኛ ተጠሪ በውሉ ላይ ባትፈርምም መሸጡን ታውቃለች፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ የእኔና የ1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በቀን 29/02/2006 ዓ.ም በፍርድ ቤት ውሳኔ የፈረሰ ሲሆን የቤቱ ስመ ንብረት ሳይዘዋወር 1ኛ ተጠሪ ቤቱ እንዲታገድ ያደረገች ሲሆን ቤቱ መሸጡን 1ኛ ተጠሪ ታውቃለች፡፡ ፍርድ ቤቱ እግዱን በቀን 26/06/2007 ዓ.ም ሲያነሳ ስመ ንብረቱን ለማዞር እንዲቻል ቤቱን በመጀመሪያ ለገዛችን ግለሰብ ሙሉ ውክልና ሰጥቻት፣ እሷም ለሌላ ግለሰብ ውክልና ሰጥታ ቤቱን ለአመልካች ተሸጠ እንጂ እኔ ከአመልካች ጋር ግንኙነት የለኝም፡፡ ስምምነቱ ሊፈርስ የሚገባበት ምክንያት የለም፡፡ በአቤቱታው መሰረት ለአመልካች ቢወሰንለት ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

የመቃወም አቤቱታዉ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ እንዲሁም ከሚመለከታቸዉ አካላት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ስለመሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ ቤቱ ተሸጦ ለቤተሰቡ የጋራ ጥቅም ስለመዋሉ አለማስረዳቱ ተረጋግጦ ተወስኖ እያለ እና ቤቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥም ታግዶ እያለ 2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ወገን ውክልና ሰጥቶ ቤቱ በወኪሎቹ አማካኝነት እንዲሸጥ ማድረጉ ያላግባብ ነው፤ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘው አመልካች የይግባኝ አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በመቀጠል የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ውድቅ ተደርጎበታል ፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 26/03/2012 ዓ.ም በተፃፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ሰበር ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ጅምር ቤት በምገዛበት ወቅት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን የማላውቅ ሲሆን እግድ መኖሩን ማረጋገጥ ህጋዊ ግዴታ ያለበት ሰነድ አረጋጋጩ ሲሆን ለሚደርሰው ጉዳትም ሃላፊነቱን የሚወስደው ይኸው አካል መሆን ሲገባው በቅን ልቦና እና በህጋዊ መንገድ ቤቱን የገዛሁትን አመልካችን የሚጎዳ ውሳኔ በስር ፍርድ ቤቶች መሰጠቱ፤ ተጠሪዎች የውሉን አደራረግ ፎርማሊቲ በሚመለከት ክርክር ሳያቀርቡ የስር ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ተነሳሽነት በማንሳት መወሰናቸው፤ እንዲሁም ውሉ አመልካች እና ተጠሪ በመመሳጠር የፈፀሙት የሽያጭ ዉል ነው የሚል ክርክር በተጠሪዎች ሳይቀርብ የስር ፍርድ ቤቶች ውሉ በክፉ ልቦና የተፈፀመ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር በህግ እና በማስረጃ

የማጣራት ሃላፊነት አለባቸዉ የሚለዉን መርህ ያልተከተለ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታዉም በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ አከራካሪዉን ቤት አመልካች ውክልና ካለው ግለሰብ ላይ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት በተደረገ ውል የገዛ መሆኑን ገልፆ እየተከራከረ የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል የመባሉን አግባብነት ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ ባቀረበችው መልስ አመልካች ቤቱ እግድ እያለበት በህገ-ወጥ መንገድ ገዝቶ እያለ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ በመሆኑ ሊጸና ይገባል ቢልም ይህ ብቻውን ውሉን ህጋዊ አያደርገውም፤ ውሉ የተፈፀመውም ከቅን ልቦና ዉጪ 1ኛ ተጠሪን ለመጉዳት ታስቦ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክራለች፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በስር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ላይ የሰጠውን መልስ በማጠናከር ቤቱ ሲሸጥ እግድ እንደሌለበት፤ 1ኛ ተጠሪ በውሉ ላይ ባትፈርምም በጋራ የሸጥነው በመሆኑ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መሠረት ቢወሰንለት ተቃውሞ የለኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት የነበረ መሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች በመቃወም አቤቱታዉ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ቤቱን መጋቢት 20 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል ከ2ኛ ተጠሪ ወኪል መግዛቱንና ዉሉንም በሚመለከተዉ አካል ዘንድ አስመዝግቦ የቤቱም ስመ ሀብት ወደ ስሙ ተዛዉሮ ማስረጃ የተሰጠዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በሌላ በኩል በተጠሪዎች መካከል ሲደረግ በነበረዉ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር መነሻነት ቀደም ሲል በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤቱን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትዕዛዝ ክርክሩ በዉሳኔ መቋጨቱን ተከትሎ መጋቢት 26 ቀን 2007 ዓ.ም የተነሳ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 24 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠዉ ትዕዛዝ ቤቱ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በድጋሚ እግድ የሰጠበት ስለመሆኑ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን፣ አመልካችም በዚህ ችሎት ባቀረበዉ አቤቱታ ይህን ክዶ አይከራከርም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ቤቱን የገዛዉ እግድ እያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ሳይክድ፣ በተለይም ለዚህ ችሎት ባቀረበዉ አቤቱታ፣ አጥብቆ የሚከራከረዉ ዉሉ ሲደረግ ቤቱ እግድ እንዳለበት እንደማያዉቅ፤ ዉሉንም በሚመለከተዉ አካል ዘንድ አስመዝግቦ ተጨማሪ ግንባታ ማካሄዱን፣ ይህ በሆነበት ሁኔታ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል መባሉ ያላግባብ መሆኑንና ቤቱ እግድ እያለበት መሸጡ ዉሉን ከመመዝገቡ በፊት እግድ ያለበት መሆን ያለመሆኑን የማጣራት በህግ ግዴታ ያለበት አካል ይህን ግዴታዉን ባለመወጣት ዉሉን ያረጋገጠዉ አካል ኃላፊነቱን

እንዲወስድ ምክንያት ከሚሆን በቀር ዉሉን ለማፍረስ ምክንያት ሊሆን አይገባም በማለት ነዉ፡፡ በዚህም መነሻነት የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ጭብጥ ቤቱ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ ተያይዞ እያለ ቤቱን ለአመልካች ለማስተላለፍ የተደረገዉ ዉል በሚመለከተዉ አካል ዘንድ በመመዝገቡ ብቻ ዉሉ ጸንቶ አመልካች የቤቱ ባለቤት ሆኖ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ መኖር ያለመኖሩ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት የነበረ ስለመሆኑ ያላከራከረ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 84(ሀ) መሠረት ያለ 1ኛ ተጠሪ ስምምነት እና ፍቃድ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ብቻዉን ለማስተላለፍ መብት የሌለዉ በመሆኑ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረገዉ ዉል መሠረት በገዛዉ ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ቤት ላይ ባለቤት ሆኖ መቀጠል የሚችል መሆን ያለመሆኑን የመወሰኑ ጉዳይ ለዉሉ ሦስተኛ ወገን የሆነችዉንና ከቤቱ ድርሻ ያላትን የ1ኛ ተጠሪን የባለቤትነት መብትና ጥቅም ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ የንብረት ባለቤትነት መብት ከሁሉ የሰፋ መብት ሲሆን፣ ይህም መብት ያላግባብ የተያዘን ወይም ለሌላ ሰዉ የተላለፈን ንብረት ለማስመለስ ክስ የማቅረብ መብትን እንደሚያጠቃልል በህጉ አንቀጽ 1204(1) እና 1206 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ምንም እንኳ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዲፈርስ የጠየቀችዉ ዳኝነት ባይኖርም አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለዉም፤ ቤቱ የእኔ እና የ2ኛ ተጠሪ ነዉ በማለት የምትከራከረዉ የጋራቸዉ በሆነዉ ቤት ላይ 2ኛ ተጠሪ ብቻዉን መወሰን የማይችል መሆኑንና በዚህም ምክንያት አመልካች የቤቱ ባለቤት እኔ ነኝ ሲል ያቀረበዉ ዉል ህጋዊ ዉጤት የማያስከትል መሆኑን በመግለጽ ነዉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከቤቱ ድርሻ ያላት መሆኑ እንዲሁም ያለ እርሷ ስምምነት ለአመልካች በዉል የተላለፈ መሆኑ ከተረጋገጠ በመርህ ደረጃ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት የሌለዉ ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ ዉሉ ህጋዊ ዉጤት ኖሮት አመልካች የንብረቱ ባለቤት ሆኖ ሊቀጥል የሚችለዉ የሽያጭ ዉሉን ያደረገዉ ሻጩ የቤቱን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስችለዉ ህጋዊ መብት ያለዉ መሆኑን እንዲሁም ንብረቱ የ3ኛ ወገን መብት ወይም ጥቅም የሌለበት መሆኑን እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሁሉ በማድረግ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ከዚህ ጀርባ ያለዉ የፖሊሲ ምክንያትም ንብረቱ የሻጭ መሆኑን በማመን መግዛቱ ከተረጋገጠ ዉሉ እንዳይፈርስ ወይም ንብረቱን የገዛዉ ሰዉ በዉሉ ባገኘዉ መብት መሠረት የንብረቱ ባለቤት ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ግብይቶች ዋስትና እንዲያገኙ ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ክርክር የቀረበለት ፍርድ ቤት በአንድ በኩል ባለ ሀብቱ በንብረቱ ላይ ያለዉን ከሁሉ የሰፋ መብት (widest right) ያላግባብ እንዳያጣ፣ በሌላ በኩል ገዥዉ ንብረቱን የገዛዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ በርግጥም ንብረቱ የሻጩ ነዉ በሚል ወይም የሌላ ሰዉ መብትና ጥቅም የለበትም በሚል እምነት መሆኑ ከተረጋገጠ በተቻለ መጠን ዉሉ እንዳይፈርስ በማድረግ ግብይቶች

ዋስትና (security of transactions) እንዲያገኙ በማድረግ ሁለቱንም ተወዳዳሪ ጥቅሞች (computing interests) አመዛዝኖ ዉሳኔ ላይ የመድረስ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ግዥዉ የተፈጸመዉ ተገቢዉ ጥንቃቄ ተደርጎ ነዉ በሚል ምክንያት ዉሉ ጸንቶ እንዲቀጥል የሚደረገዉ የገዥዉ መብት ከባለንብረቱ፣ ወይም አስቀድሞ በንብረቱ ላይ መብትና ጥቅም ካገኘዉ ሰዉ፣ በላይ በመሆኑ ሳይሆን የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረጉ ግብይቶች ጥያቄ ዉስጥ እንዳይገቡ ጥበቃ በማድረግ አጠቃላይ የማህበረሰቡን (general public interest) ጥቅም ለማረጋገጥ በመሆኑ የማጣራቱ ሂደት ይህን ሁሉ ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ በጥንቃቄ ሊከናወን ይገባል፡፡ ንብረቱን የገዛ ሰዉ እንዲያደርግ የሚጠበቅበት የጥንቃቄ ደረጃ እስከምን ድረስ ነዉ? የሚለዉን መለየቱ ቀላል ባይሆንም፣ በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚገዛ ሰዉ ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት ንብረቱ እርሱ የሚፈልገዉ ዓይነት መሆኑን ብሎም በርግጥም የሻጩ መሆኑን ወይም ሻጩ ንብረቱን ለመሸጥ በህግ ስልጣን ያለዉ መሆን ያለመሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢዉን ሁሉ ካደረገ በኋላ የገዛ ስለመሆኑ የተለያዩ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት መመዘን ያስፈልጋል፡፡ የተሸጠዉ ንብረት የሦስተኛ ወገን መብትና ጥቅም ያለበት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ቤቱን የገዛዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርጎ መግዛቱን የማስረዳቱ ሸክም የገዥዉ እንጂ የባለንብረቱ ወይም ከንብረቱ መብትና ጥቅም አለኝ የሚል ወገን አለመሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ጠንቃቃ ገዥ በሚል መስፈርት የሦስተኛ ወገንን ንብረት በሻጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል ጸንቶ እንዲቀጥል ወይም ገዥዉ የንብረቱ ባለቤት ሆኖ እንዲቀጥል የሚደረገዉ በልዩ ሁኔታ (exception) በመሆኑ በጠባቡ መተርጎም እንዳለበትም ይታመናል፡፡

ከስሙም መረዳት እንደሚቻለዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት በባህርዉ በሆነ ቦታ ላይ ተወስኖ የሚቆይ ንብረት (fixed asset) በመሆኑ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ ስለማይቻል ጥበቃ የሚያገኘዉ በምዝገባ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት የአገራችን የፍትሐብሔር ፍትሕ ሥርዓት የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ለዜጎች የንብረት መብት ጥበቃ ከማድረግ አንፃር ፋይዳዉ የጎላ ስለመሆኑ ግምት ዉስጥ በማስገባት በፍትሐብሔር ህጉ የተለያዩ አንቀፆቹ ስለ ምዝገባ ይደነግጋል (አንቀጽ 1553-1646 እንዲሁም 1723፣ 2878 እና 3052 ይመለከቷል)፡፡ የህጉ አንቀጽ 10 (Title 10) በተለይ ሲታይ በመሠረታዊነት ሁለት የምዝገባ ዓይነቶች እንዳሉ የሚያስገነዝብ ነዉ፤ አንደኛዉ የህጋዉያን ተግባራት ምዝገባ (registration of juridical acts) ሲሆን ሁለተኛዉ የባለቤትነት ምዝገባ (registration of ownership) ናቸዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ዓይነት ምዝገባ የሽያጭ ዉልን ጨምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚቋቋሙትን የተለያዩ መብቶችና ግዴታዎችን የሚመለከት ነዉ (በህጉ ከአንቀጽ 1567-1574 ይመለከቷል)፡፡ ይህ እንደ አጠቃላይ ሲሆን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል በሦስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ ይሆን ዘንድ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ መመዝገብ እንዳለበት የህጉ አንቀጽ 2878 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የየራሳቸዉ የሆኑ ዓላማዎች የሚኖሩት ቢሆንም፤ አጠቃላይ ዓላማቸዉ ግን ለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ጥበቃ በመስጠት እነዚህን

ንብረቶች በተመለከተ ባለይዞታዉ መብቱን ሲያገኝ ወይም ንብረቱ በሆነ ምክንያት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን በሚያስተላልፍበት ወቅት የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ መንግስታዊ አካል ካልተመዘገበ ህግ ፊት የሚጸና መብት እንዳይኖረዉ በማድረግ ዜጎች በዚህ ግዙፍነት ያለዉ ንብረት ያላቸዉን መብት ከፍላጎታቸዉ ዉጪ በሆነ መንገድ እንዳያጡ ጥበቃ ለመስጠት፤ ብሎም ንብረቱን የሚገዛ ወይም በንብረቱ ላይ ማናቸዉንም መብት ማቋቋም የሚፈልግ ሦስተኛ ወገን ንብረቱ ያለበትን ሁኔታ ወይም በንብረቱ ላይ አስቀድሞ የተቋቋመ መብትና ግዴታ መኖር አለመኖሩን እንዲያዉቅ ለማድረግ ነዉ፡፡ ስለሆነም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ እና የሚያስከትለዉን ዉጤት በተመለከተ የሚደረግ ክርክር ይህንኑ ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ እልባት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች ቤቱን ከመግዛቱ አስቀድሞ ቤቱ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት ታግዷል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባን አስመልክቶ ከላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ታሳቢ የሚያደርጉት የሚመለከታቸዉ አካላት ምዝገባዉን ሲያከናዉኑ በህግ አግባብ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸዉ ጥንቃቄ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከንብረቱ መብትና ጥቅም የተላለፈለት ሰዉም ለንብረቱ መተላለፍ ምክንያት የሆነዉን ህጋዊ ተግባር (juridical act) እንዲሁም የባለቤትነት መብቱን ሲያስመዘግብ (አንቀጽ 1543-1566 እና 1185 ማየት ይቻላል) በንብረቱ ላይ አስቀድሞ የተቋቋመ መብት ወይም ጥቅም ወይም ንብረቱ ለሌላ እንዳይተላለፍ የሚከለክል ወይም የንብረቱን መተላለፍ አጠራጣሪ የሚያደርገዉ ሰነድ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ዉስጥ የሚገኝ መሆን ያለመሆኑን በጥንቃቄ የማጣራት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ በአንቀጽ 1561 ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገቦች ለህዝብ ግልጽ መሆን እንዳለባቸዉ የደነገገዉም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የሽያጭ ዉል ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ መመዝገብ እንዳለበት ህጉ ሲደነግግ ገዥዉ ዉሉ እንዲመዘገብ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ ሲቀርብ ንብረቱ በሻጭ ስም መመዝገብ አለመመዝገቡን ወይም ሻጩ ዉሉን ለማድረግ ህጋዊ መብት ያለዉ መሆን አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን በንብረቱ ላይ ዕዳ እና እገዳ ያለበት መሆን ያለመሆኑንም ለማጣራት ዕድል ያገኛል በሚል መነሻ እንደሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ ይህ ማንኛዉም ጠንቃቃ ገዥ እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ንብረቱ አስቀድሞ ለሌላ ሰዉ የተላለፈ መሆኑን ወይም ሻጩ የንብረቱን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚያስችለዉ ሙሉ መብት እንደሌለዉ ወይም ንብረቱ እዳ እና እገዳ ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ እያለ ይህን ሳያረጋግጥ ዉሉን በንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ ያስመዘገበ ሰዉ ከአንድ ጠንቃቃ ገዥ የሚጠበቀዉን ጥንቃቄ ላለማድረጉ አመላካች ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት የህግ ጥበቃ የማይሰጠዉ በመሆኑ ዉሉ ጸንቶ የሚቀጥልበት ወይም በዉሉ መሠረት ባገኘዉ ንብረት ላይ ባለሀብት ሆኖ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ ጥያቄ ዉስጥ የሚገባ ነዉ፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሽያጭ ዉሉን ከማድረጉ በፊት ቤቱ ወደ ሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት የተሰጠ እግድ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ዉሉን ከማድረጉ በፊት ከቤቱ ጋር በተያያዘ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ የተመለከቱትን ሰነዶች ማየት ቢችል ኖሮ በቤቱ ላይ እግድ መኖሩን በቀላሉ ይደርስበት ነበር፡፡ ይህን ማድረግ ሲገባዉ የሽያጭ ዉሉን ማድረጉ አመልካች አንድ ጠንቃቃ ገዥ እንዲያደርግ የሚጠበቅበትን ግዴታ አለመወጣቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ዉሉ መመዝገቡ ብቻዉን አመልካች ዉሉን ሲያደርግ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረጉን የሚያሳይ ባለመሆኑ በዉሉ ምክንያት የቤቱ ባለቤት ሆኖ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ የለም፡፡ ዉሉ መመዝገቡም ሆነ የሚመለከተዉ አካል ዉሉን ሲመዘግብ ወይም ሲያረጋግጥ ተገቢዉን ጥንቃቄ አለማድረጉ ዉሉ እንዲጸና ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበዉ መከራከሪያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ አስፈላጊ የሆነበትን መሠረታዊ ዓላማ እንዲሁም አስቀድሞ የተቋቋመ የሌላ ሰዉ መብትና ጥቅም ያለበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት በመግዛት የተደረገ ዉል ጸንቶ ሊቀጥል የሚችልበትን ሁኔታ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ ክርክር ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ሆኖ ያለ 1ኛ ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ለአመልካች በሽያጭ የተላለፈ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ንብረቱ አስቀድሞ እግድ የተሰጠበት ስለመሆኑ ንብረቱ በተመዘገበበት መዝገብ ላይ እያለ አመልካች ቤቱን መግዛቱ እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ማድረግ የሚገባዉን ጥንቃቄ አለማድረጉን የሚያሳይ በመሆኑ ዉሉ ጸንቶ የማይቀጥል በመሆኑ እና በዚህም ምክንያት አመልካች የቤቱ ባለቤት ሆኖ ሊቀጥል የሚችልበት የህግ ምክንያት ባለመኖሩ የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20638 በቀን 10/08/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 308239 በቀን 13/10/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ችሎት እንዲሁም ሰበር ሰሚዉ ችሎት በቁጥር 318574 በቀን 02/03/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሠ/መ/ቁጥር 177862

ጥር 28 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበበች ዘበርጋ

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ሙላት ለጃ

2. አቶ ኃይሉ ቱሼ

3. እቴነሽ እስራኤል

4. በአዳማ ከተማ የጎሮ ቀበሌ መሬት ልማት ማኔጅመንት ኤጀንሲ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ ቤት እግድ የተሰጠበትን ቤት በሽያጭ ማስተላለፍ የሚኖረዉን ዉጤት በሚመለከት የተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል በቀረበ አቤቱታ መነሻ የተደረገ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ እንደተረዳነዉ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት ሲሆኑ በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር 5522/95 በ200 ካሬ ሜትር ስፋት ላይ የተገነባ የጋራ ሀብት የሆነ ቤት፤ይህ ቤት በአመልካች ስም ተመዝግቦ ይታወቅ የነበረና በ1ኛ ተጠሪ በዉክልና ይተዳደር የነበረ ሲሆን አመልካች በ2008 ዓ/ም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸዉ ጋብቻ እንዲፈርስ የፍቺ ክርክር ሲያደርጉ ይህ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ታግዶ እንዲቆይ ለአዳማ ከተማ ፍርድ ቤት አመልክተዉ ፍርድ ቤቱ በቀን 03/02/2008ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ቤቱ ታግዶ እንዲቆይ ለ4ኛ ተጠሪ ትእዛዝ ሰጥቶ 4ኛ ተጠሪም በቀን 09/02/2008ዓ/ም በጻፈዉ ደብዳቤ በትእዛዙ መሰረት ማገዱን ለፍርድ ቤቱ ማሳወቁን እና ዕግዱም

እስካሁን አለመነሳቱን በመግለጽ መከራከሯን የዉሳኔዎቹ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ እግድ መሰጠቱን እያወቀ የአመልካችን መብት ለማሳጣት በማሰብ ዘመዱ ለሆነዉ ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ስልጣን በመስጠት 2ኛ ተጠሪ የዉክልና ስልጣኑን በመጠቀም የቤቱን ዋጋ ዝቅ በማድረግ ባለቤቱ ለሆነችዉ ለ3ኛ ተጠሪ በብር 170,000.00 በቀን 22/05/2010 ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል በመፈጸም የቤቱ ስመ ሀብት ወደ 3ኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ አድርገዋል በማለት የቤት ሽያጭ ዉሉ የተፈጸመዉ በቤቱ ላይ የተሰጠዉን እግድ በመተላለፍ በመሆኑ ዉሉ እንዲፈርስ እንዲወሰንላት እና 4ኛ ተጠሪ ወደ 3ኛ ተጠሪ ያዛወረዉን ስመ ሀብት ወደ አመልካች ስም እንዲያዛዉር እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ ባሰማዉ ፍሬ ነገር በሚመለከተዉ ክርክሩ የሽያጭ ዉሉ የተፈጸመዉ አመልካች በሰጠችኝ የዉክልና ስልጣን በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ የተፈጸመዉ ከአመልካች ጋር ነዉ፡፡ቤቱን በቀን 20/01/2008ዓ/ም በተደረገ ዉል ለ2ኛ ተጠሪ በብር 130,000.00 ሽጫለሁ፡፡ ቤቱ ሲሸጥ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችለኝ በአመልካች የተሰጠኝ ዉክልና ጸንቶ ይገኛል፡፡ ቤቱ ከተሸጠ በኋላ ገዥዎች ተጨማሪ ግንባታ በማከናወን የቤቱን ስመ ሀብት ወደ ስማቸዉ እንዲዛወር አድርገዋል፡፡በቤቱ ላይ እግድ መሰጠቱን አላዉቅም፡፡የተሰጠ እግድም የለም፡፡የቤቱ ዋጋም ዝቅ አልተደረገም በሚል ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በጋራ ባቀረቡት ክርክር አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የባልና ሚስት ክርክር ሲያደረጉ በቤቱ ላይ እግድ አልተሰጠበትም፡፡በቤቱ ላይ እግድ አለመኖሩን አጣርተን የገዛነዉ ቤት ነዉ፡፡ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠችዉ ዉክልና ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል መሆኑን፣ እንዲሁም ይህ ዉክልና ተወካይ 3ኛ ወገን ለመወከል የሚያስችል ስልጣን የሚሰጥ መሆኑንና 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች በተሰጠዉ ዉክልና መነሻ 2ኛ ተጠሪን በቀን 23/05/2010 በቁጥር 02285/2010 ቤቱን ጭምር መሸጥ እንዲችል በሰጠዉ የዉክልና ስልጣን ዉክልናዉ ያልተሻረ መሆኑን አረጋግጠን የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ክፍለን በቅን ልቦን 3ኛ ተጠሪ የገዛሁት ቤት ከመሆኑም በተጨማሪ የቤቱ ስመ ሀብት እዳና እገዳ እንደሌለዉ ተጣርቶ በቀን 25/05/2010ዓ/ም ወደ 3ኛ ተጠሪ ስም ዞሮ እንዲመዘገብ ያደረግነዉ ቤት በመሆኑ አመልካች በቤቱ ላይ መብት አለኝ የምትል ከሆነ ድርሻዋን ከ1ኛ ተጠሪ መጠየቅ አሊያም እግድ እያለበት ተሸጧል የምትል ከሆነም ከ4ኛ ተጠሪ ከምትጠይቅ በስተቀር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪን ልትጠይቅ ስለማትችል ዉሉ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ ክሱ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

4ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ቀርቦ ባለመከራከሩ ክርከሩ 4ኛ ተጠሪ በሌለበት እንደታየ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29574 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በቀን 07/03/2011 ዓ/ም በዋለዉ

ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች የተሰጠዉን ዉክልና በመጠቀም ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና የሰጠዉ በቀን 23/05/2010 ዓ/ም ሆኖ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የዉክልና ስልጣን አለኝ በሚል ቤቱን ለ3ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈዉ በቀን 22/05/2010ዓ/ም የዉክልና ስልጣን ሳይሰጠዉ በመሆኑ የዉክልና ስልጣን ሳይኖር የተፈጸመ የቤት ሽያጭ ዉል ከሕግ ዉጭ የተፈጸመ ዉል እንደሆነ፤ እንዲሁም በቤቱ ላይ እግድ ተሰጥቶበታል የተባለበትን መዝገብ ቁጥር 91309 የሆነዉን መዝገብ ከአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አስቀርቦ እንደተመለከተና በመዝገቡ ላይ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ታግዶ እንዲቆይ በቀን 03/02/2008ዓ/ም ትእዛዝ ሰጥቶ ለ4ኛ ተጠሪ ማሳወቁንና እግዱ አለመነሳቱን ከመዝገቡ ማረጋገጡን፤ እግዱ ጸንቶ እያለ በቀን 22/05/2010ዓ/ም የቤት ሽያጭ ዉል ተፈጽሞ የቤቱ ስመ ሀብት በቀን 25/05/2010ዓ/ም ወደ 3ኛ ተጠሪ መዛወሩን ማረጋገጡን፤ እንዲሁም የቤቱን ማህደር አስቀርቦ በማህደሩ ዉስጥ የእግድ ትእዛዙ መኖሩን ማረጋገጡን በመግለጽ እግዱ እያለ 3ኛ ተጠሪ ቤቱን መግዛታቸዉ ቤቱን በቅን ልቦና ገዝተዋል አያስብልም በሚል በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መካከል የተፈጸመዉ የቤት ሽያጭ ዉል እና በ3ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበዉ የባለቤትነት መብት ፈርሷል በማለት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለቤቶች ናቸዉ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 301126 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 03/08/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ በቁጥር 5562/2005 በቀን 15/12/2005 የሰጠችዉ ዉክልና ቤቱን የመሸጥ ስልጣን የሚሰጠዉ ዉክልና በመሆኑና ዉክልናዉ እስካሁን ጸንቶ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ዉክልናዉ በሕግ አግባብ እንዲሻር ባላደረገችበት የዉክልና ዉሉ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያሰማችዉ ክርክር የሕግ መሰረት እንደሌለዉ፤ እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት 1ኛ ተጠሪ በቀን 23/05/2010 ዓ/ም 2ኛ ተጠሪ ይህንን ቤት መሸጥ መለወጥ የሚያስችለዉን የዉክልና ስልጣን እንደሰጠዉ፣ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉን ሙሉ ዉክልና በመጠቀም በቀን 23/05/2010ዓ/ም በተጻፈ የሽያጭ ዉል ለ3ኛ ተጠሪ በመሸጡ ዉሉ ጸድቆ ስመ ሀብቱ ወደ 3ኛ ተጠሪ መተላለፉን ማረጋገጡን ፤ በቤቱ ማህደር ዉስጥም ተሰጠ የተባለዉ እግድ እንዳልተገኘ በመጥቀስ እግዱ በማህደሩ ዉስጥ አልተገኘም እንጂ እግዱ ቢኖር እንኳን እግዱ በማህደሩ ዉስጥ መኖር አለመኖሩን መመርመር የከተማ አስተዳደሩ ስራ በመሆኑ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ማህደሩን ወስደዉ መመርመር ስለማይችሉ አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2183 እና 2184 መሰረት የዉክልና ስልጣኑን ባላሻረችበት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከላይ በተገለጸዉ መሰረት የገዙትንና በስማቸዉ ያስመዘገቡት ቤት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የዉክልና ስልጣኑ የሚያስከትለዉን ዉጤት ሳያገናዝብ እና በቤቱ ማህደር ዉስጥ እግዱ መኖሩን ሳያረጋግጥና ማህደሩን መመርመር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን የማይመለከት ጉዳይ ሆኖ እያለ ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን በሕጋዊ መንገድ በቅን ልቦና ስለገዙ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረበች ቢሆንም ችሎቱ በመ/ቁጥር 310074 ላይ በቀን 30/08/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትእዛዝ ለሰበር ችሎት አያስቀርብም በማለት አቤቱታዋን ሰርዟል፡፡አመልካች ከላይ በተጠቀሰዉ መሰረት በተሰጠ ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል በቀን 21/09/2011 ዓ/ም ጽፈዉ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት እንዳይሸጥ ላሳግድ የቻልኩት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከነበረን የጋብቻ ፍቺ ክርክር መነሻ 1ኛ ተጠሪ (ባለቤቴ) በነበረዉ የዉክልና ስልጣን ቤቱን ይሸጥብኛል በሚል ጥርጣሬ ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት መሸጥ እንዲችል በ1ኛ ተጠሪ ዉክልና የተሰጠዉ በቀን 23/05/2010ዓ/ም ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን የሽያጭ ዉሉን ባለቤቱ ከሆነችው 3ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገዉ በቀን 22/05/2010ዓ/ም ዉክልና ሳያገኝ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ የተወሰነዉን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91309 ላይ በቀን 03/02/2008ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማንኛዉም መንገድ ወደ 3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ ታግዶ እንዲቆይ ትእዛዝ ተሰጥቶበት 4ኛ ተጠሪ በቀን 09/02/2008ዓ/ም በጻፈዉ መልስ በትእዛዙ መሰረት ቤቱን ማገዱን ለፍርድ ቤቱ ማሳወቁን፤ እንዲሁም እግዱ አለመነሳቱን የአዳማ ልዩ ዞን መዝገቡን አስቀርቦ ተመልክቶ አረጋግጦ እግዱ ጸንቶ እያለ የተፈጸመ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ የሰጠዉ ተገቢ ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቤቱ ፋይል ዉስጥ እግዱ እያለና እግድ የተሰጠበትን ፋይል መርምሮ ያገደዉ አካል እግድ የለበትም የሚል ማረጋገጫ ሳይሰጥበት በቤቱ ማህደር ዉስጥ እግዱ የለም ቢኖር እንኳን መኖር አለመኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት የከተማ አስተዳደር ሥራ እንጂ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ኃላፊነት አይደለም በሚል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከራስ ጋር ያደረጉትን የጥቅም ግጭት ያለበት የሽያጭ ዉል መሆኑ ጭምር ተረጋግጦ እንዲፈርስ የተሠጠዉን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የሰጡት ዉሳኔዎች ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የንብረት ክርክር ላይ በነበሩበት ጊዜ ክርክር ያስነሳዉ ቤት በፍርድ ቤት ታግዶ እያለ ይህ እግድ ሳይነሳ በሽያጭ ለ3ኛ ወገን ተላልፏል ተብሎ መወሰኑ ከፍርድ በፊት ከሚሰጥ እግድ ዓላማ እና አፈጻጸም አንጻር አግባብ ስለመሆኑ እና በተሰጠዉ እግድ መሰረት የሚመለከተዉ አካል ቤቱን ስለማገዱ እግዱን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት መልስ ሰጥቶ እያለ እግዱ የቤቱ መዝገብ ዉስጥ የለም የተባለበት ሁኔታን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በሚከተለዉ መሰረት መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 29/11/2011ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ አመልካች ቤቱ ታግዶ እያለ እንደተሸጠ በመግለጽ የተከራከረች ቢሆንም ቤቱ የተሸጠዉ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ በሰጠችኝ ቤቱን መሸጥ መለወጥ በሚያስችል ዉክልና እግዱ ከመሰጠቱ በፊት ከአመልካች ጋር አብረን በቀን 20/01/2008ዓ/ም ሽጠን በጋብቻ ዉስጥ ገንዘቡን ከተጠቀምን በኋላ ዉክልና መስጠቷን ሳትክድ አመልካች በቀን 20/01/2008ዓ/ም የተደረገዉ ዉል ሳይፈርስ ከዚህ በኋላ የተደረገ ዉል እንዲፈርስ መጠየቋ ተገቢነት የለዉም፡፡ አመልካች የፍቺ ክርክር ባደረግንበት መዝገብ ላይ የነበረንን ክርክር በእርቅ ጨርሰን አብረን እየኖርን እያለ ከ2 ዓመት በኋላ ቤቱ ታግዶ ነበር በማለት የምታነሳዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡በቤቱ ማህደር ዉስጥ ምንም እግድ ባለመኖሩና ቤቱ ጅምር ቤት በመሆኑ በቅን ልቦና በብር 170,000.00 ከተሸጠ በኋላ ገዥ ጅምር ቤቱን አፍርሳ በአዲስ መልክ ከ1,500,000.00 ብር በላይ ወጪ አዉጥታ ገንብታ ወደ ስሟ አዛዉራ እየተጠቀመች እያለ አመልካች ጉዳት ሳይደርስባት አለአግባብ ለመበልጸግ ያቀረበችዉ ክስ መሆኑ ተረጋግጦ ክሱ ዉድቅ መደረጉ ተገቢ በመሆኑ ያቀረበችዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በጋራ በቀን 29/11/2011 ዓ/ም በተጻፈ መልሳቸዉ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ዉክልና የሰጠችዉ በቀን 15/2/2005ዓ/ም ሲሆን ይህንን የዉክልና ስልጣን በመጠቀም 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን የወከለዉ በቀን 23/05/2010 ዓ/ም ነዉ፡፡ ቤቱ ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን የቤቱ ፋይል ከሚገኝበት ከአሁን 4ኛ ተጠሪ አረጋግጠን ዉሉን ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ቀርበን በቀን 24/05/2010ዓ/ም ተዋዉለናል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሉ እንዲፈርስ ሲወስን በአከራካሪዉ ቤት ላይ እግድ መኖሩን ከ4ኛ ተጠሪ አስቀርቦ አላረጋገጠም፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቤቱን ፋይል ከ3ኛ ተጠሪ በትእዛዝ አስቀርቦ በማጣራት በቤቱ ፋይል ላይ እግድ እንደሌለና እግዱ አለ ቢባል እንኳን የቤቱን ፋይል መመርመር የገዥ ሳይሆን የከተማ አስተዳደሩ እንደሆነና ቤቱም የተሸጠዉ አመልካች በሰጠችዉ ልዩ ዉክልና እንደሆነና 3ኛ ተጠሪ ቤቱን በቅን ልቦና መግዛቴን በማረጋገጥ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በቤቱ ላይ አመልካች ያላትን መብት ያሳጣት ወገን ካለ መጠየቅ ትችላለች ብሎ የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻሩ የፈጸመዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ እግዱ መኖሩን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አናዉቅም ለማወቃችን በስር ፍርድ ቤት የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡እግድ በቤቱ ፋይል ላይ አለመኖሩን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባረጋገጠበት ሁኔታ ይህ ችሎት ተጠሪዎች እግዱ መኖሩን ያዉቁ ነበር ወይስ አይደለም የሚለዉን የማስረጃ ክርክር ተቀብሎ ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የለዉም፡፡3ኛ ተጠሪ በ4ኛ ተጠሪ ዘንድ ካለዉ የቤቱ ማህደር እግድ እንደሌለ አረጋግጠን ቤቱን በቅን ልቦና ከገዛሁ እና ስመ ሀብቱን በስሜ ካስመዘገብኩ በኋላ ብር 1,500,000.00 በላይ ወጪ አዉጥቼ ተጨማሪ ግንባታ በመፈጸም ቤቱን በመያዣነት በመስጠት ከብድርና ቁጠባ ተቋም ከፍተኛ ገንዘብ ተበድሬበታለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቤት ስለሆነ አመልካች ዉል እንዲፈርስላት መጠየቋ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 47800 ፣15551፣39336፣ 46527 እና

47378 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሉ አይፈርስም ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም እንዲባልልን፡፡ በሽያጭ ዉሉ አናት ላይ ዉሉ የተዘጋጀበት ቀን ጥር 22 ቀን 2010 ዓ/ም ተብሎ የተጻፈ ቢሆንም ዉሉን በዉል አዋዋይ ፊት የተፈራረምንበት ቀን 24/05/2010ዓ/ም በመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36740 እና 98583 ላይ በሰጠዉ ትርጉም እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2015/ሀ መሰረት ዉሉ የተደረገበት ቀን ጥር 24 ቀን 2010 ዓ/ም በመሆኑ አመልካች ከዚህ አንጻር ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡እንዲሁም ባል ከሚስት ፍቃድ ዉጭ ንብረቱን ሸጦ ቢገኝ የተሸጠዉ ቤት ወደ ገዥ ተዛዉሮ ከተገኘ ሚስት በተሸጠዉ ቤት ያጣችዉን ድርሻ ከባሏ መጠየቅ ከምትችል በስተቀር 3ኛ ወገን መጠየቅ እንደማትችል በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 114 እና 115 የተደነገገዉን በመጥቀስ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 28663 አስገዳጅ ትርጉም ስለሰጠ አመልካች ባሌ ቤቱን አላግባብ ሸጦብኛል የምትል ከሆነ ከባሏ መጠየቅ ከምትችል በስተቀር ዉል ይፍረስልኝ በማለት መጠየቅ አትችልም ተብሎ አቤቱታዋ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ከተራ ቁጥር 1-3 በተጠቀሱ ተጠሪዎች በቀረበ መልስ ላይ በቀን 30/01/2012ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ 4ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ባለመቅረቡ ክርክሩ በሌለበት ተሰምቷል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔና ትእዛዝ ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም 1ኛ ተጠሪ እና አመልካች ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በአዳማ ከተማ ጎሮ ቀበሌ ዉስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር 5522/95 በአመልካች ስም ተመዝግቦ የነበረዉና በ200 ካሬ ሜትር ስፋት ላይ የተገነባ ነዉ የተባለዉ ቤት ደግሞ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ወቅት ያፈሩት የጋራ ሀብት የሆነ ንብረት እንደነበር በስር ፍርድ ቤቶች በተደረገ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ይህንን ቤት መሸጥ እንዲችልና ይህንኑ ስልጣኑን ለ3ኛ ወገን በዉክልና ማስተላለፍ እንዲችል የሚፈቅድ በቁጥር 5562/2005 በቀን 15/12/2005 የተመዘገበ የዉክልና ስልጣን አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ መስጠቷን በግራ ቀኝ የታመነና በማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 91309 ላይ የጋብቻ ፍቺ ክርክር ሲያደርጉ በነበሩበት ጊዜ በአመልካች ጠያቂነት በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 03/02/2008 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪዉ ቤት እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በማናቸዉም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ እግድ መስጠቱንና እግዱም

እንዲነሳ ተለዋጭ ትእዛዝ አለመስጠቱን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እግድ ተሰጠ የተባለበትን መ/ቁጥር 91309 ከአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት አስቀርቦ ማረጋገጡን የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ያገኙትን ከላይ የተጠቀሰዉን የዉክልና ስልጣን በመጠቀም 2ኛ ተጠሪ አከራካሪወን ቤት መሸጥ መለወጥ እንዲችሉ በቀን 23/05/2010 በቁጥር 02285/2010 በተመዘገበ የዉክልና ስልጣን 2ኛ ተጠሪን መወከላቸዉም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ባገኙት ዉክልና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ለ3ኛ ተጠሪ መሸጣቸዉንና ሽያጩን ተከትሎ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የነበረዉ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ 3ኛ ተጠሪ ተላልፎ እንደሚገኝም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ሲሆን አመልካች እንዲፈርስ ዳኘነት የጠየቁበት የቤት ሽያጭ ዉልም ይኸዉ የቤት ሽያጭ ዉል ነዉ፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሰረት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መኖራቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቤት ሽያጭ ዉሉ የተፈጸመበት ቀን መቼ ነዉ የሚለዉ እና ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ዉሉን የፈጸሙት በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ መኖሩንና እግዱ አለመነሳቱን እያወቁ ነዉ ወይስ አይደለም ? በቤቱ ላይ የተሰጠ እግድ መኖሩን እያወቁ ወይም እግዱ መነሳቱን ሳያረጋግጡ የተፈጸመ ዉል ነዉ የሚባል ከሆነ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉ ጉዳዮች ግራ ቀኙን ያከራከሩ ጭብጦች ናቸዉ፡፡

ዉሉ የተፈጸመበትን ቀን በተመለከተ አመልካች ይፍረስልኝ እያለች ያለችዉ የቤት ሽያጭ ዉል 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ የተሰጠዉን የዉክልና ስልጣን በመጠቀም ፈጸመ የተባለዉን የቤት ሽያጭ ዉል በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በቀን 20/01/2008ዓ/ም ያደረኩት የቤት ሽያጭ ዉል እያለ ከዚህ በኋላ የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ መጠየቁ ተገቢ አይደለም በሚል የተከራከረ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በቀን 20/01/2008ዓ/ም በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ቤቱን ገዝቻለሁ በሚል ግልጽ ክርክር ያላነሳ በመሆኑ ከዚህ አኳያ 1ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን ክርክር አልፈነዋል፡፡ አመልካች እንዲፈርስ ዳኘነት የጠየቀችበት ዉል የተፈጸመዉ በቀን 22/05/2010 ዓ/ም ነዉ በማለት የተከራከረች ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ በዉሉ ሰነድ ላይ ቀን 22/05/2010 ዓ/ም ተብሎ የተጻፈዉ የዉል ሰነዱ የተዘጋጀበት ቀን እንጂ ዉሉ የተፈጸመበት ቀን አይደለም ፤ በቀን 22/05/2010 ዓ/ም የተዘጋጀዉ ዉል በዉል አዋዋይ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አካል ፊት ተዋዋዮች ፈርመንበት ተረጋግጦ የተመዘገበዉ በቀን 24/05/2010 ዓ/ም በመሆኑ ዉሉ እንደተደረገ የሚቆጠረዉ ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት ቀርቦ ተፈርሞ በተመዘገበበት ቀን ነዉ በሚል ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የቀረበዉን ክርክር መርምሮ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክርክር በመቀበል ዉሉ የተፈጸመዉ በቀን 22/05/2010 ዓ/ም በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ስልጣን የሰጠዉ በቀን 23/05/2010 ዓ/ም ነዉ በሚል 3ኛ ተጠሪ የዉክልና ስልጣን

ባልተሰጠዉ ጊዜ የቤት ሽያጭ ዉሉን መፈጸሙ ዉሉን የሚያፈርስ ምክንያት ነዉ ብሎ የወሰነ ቢሆንም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማስረጃ መርምሮ የቤት ሽያጭ ዉሉ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ባገኙት ዉክልና በቀን 23/05/2010 ዓ/ም ተፈጽሞ ወዲያዉ ዉሉ ስልጣን ባለዉ አካል መጽደቁ ተረጋግጧል በሚል የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡ አመልካችም ዉሉ በዉል አዋዋይ ተረጋግጦ በቀን 24/05/2010 ዓ/ም አልተመዘገበም (authenticate አልተደረገም) በሚል በግልጽ ክዳ አልተከራከረችም፡፡

እኛም ከዚህ አንጻር የቀረበዉን ክርክር እንደመረመርነዉ እንዲፈርስ ዳኝነት የተጠየቀበት የቤት ሽያጭ ዉል የተፈጸመዉ በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት መሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በዉል አዋዋይ ፊት ዉል ከሚደረግበት ዓላማዎች መካከል አንዱ ዉሉ የተደረገበትን እርግጠኛ ቀን ማረጋገጥ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2015/ሀ ስር በተደነገገዉ መሰረት የሽያጭ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ ከሆነ የሽያጭ ዉሉ ተፈጽመ የሚባልበት እርግጠኛ ቀን ዉሉ በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት ቀርቦ ተረጋግጦ የተመዘገበበት ቀን ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36740 ላይ በቀን 23/03/2001 ዓ/ም በተመሳሳይ ጉዳይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህ መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አዋጅ ለማሻሻል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1 መሰረት በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ዘንድ አስገዳጅነት ያለዉ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት ተረጋግጦ የተመዘገበበት ቀን 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ አከራካሪዉን ቤት የመሸጥ የመለወጥ የዉክልና ስልጣን ከሰጡ በኋላ እንደሆነ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማስረጃ መርምሮ ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር በመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ የሰነድ ማስረጃዎቹን ለመመርመር የሚያስችል ሥልጣን ስለሌለዉ ከዚህ አኳያ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉል የተደረገዉ ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና ከመስጠቱ በፊት ነዉ በሚል እንደ አንድ የዉል ማፍረሻ ምክንያት የተደረሰበትን ድምዳሜ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ ተገቢ በመሆኑ በዚህ ረገድ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንም፡፡

ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ዉሉን የፈጸሙት በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ መኖሩንና እግዱ አለመነሳቱን እያወቁ ነዉ ወይስ አይደለም ? በቤቱ ላይ የተሰጠ እግድ መኖሩን እያወቁ ወይም እግዱ መነሳቱን ሳያረጋግጡ የተፈጸመ ዉል ነዉ የሚባል ከሆነ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉት አከራካሪ ነጥቦች እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 154 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ የሚሰጠዉ ተከሳሹ የባለመብቶችን ጥቅም ለመጉዳት ሲል ንብረቱን ለሌላ

ሰዉ አሳልፎ ለመስጠት ወይም ለመሸጥ ወይም ለማሸሽ ወይም ለማባከን ወዘተ ማቀዱ በመሀላ ቃል በተረጋገጠ አቤቱታ በማስረዳት ሲጠየቅ በክርክሩ ሂደት ረቺ ለሚሆነዉ ወገን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ንብረቱ እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን፣ እንዳይበላሽ፣ ለሌላ ሰዉ ተላልፎ እንዳይሰጥ ገደብ ለመጣል ካለዉ ዓላማ የሚሰጥ ትእዛዝ ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ በሕግ አግባብ ለሌላ ሰዉ ሊያስተላልፍ የሚችለዉ መብት በሕግ ወይም በፍርድ ገደብ ያልተጣለበትና ያለዉ መብት መሆን አለበት፡፡ይህም ማለት ሕግ ጥበቃ የሚያደርገዉ አንድ ሰዉ ያለዉን መብት እና በሕግ ወይም በፍርድ ገደብ ያልተጣለበትን መብት የሚያስተላልፍ ሕጋዊ ተግባር ሲፈጽም ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 156/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ደግሞ በፍርድ ቤት የተሰጠዉን የማገጃ ትእዛዝ አለማክበር በወንጀል ሕጉ መሰረት ወንጀል ሆኖ የሚያስቀጣ ተግባር ጭምር ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አከራካሪዉ ቤት ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከመሸጡ በፊት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት የነበረ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በነበረዉ በመ/ቁጥር 91309 በሚታወቅ የጋብቻ ፍቺ ክርክር መዝገብ ላይ እንዳይሸጥ፣እንዳይለወጥ በማናቸዉም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ በቀን 03/02/2008 ዓ/ም በተሰጠ የእግድ ትእዛዝ በማሳገዷ ትእዛዙ ለ4ኛ ተጠሪ ደርሶት 4ኛ ተጠሪም እግዱን መመዝገቡን ገልጾ በቀን 09/02/2008ዓ/ም በጻፈዉ ምላሽ ለፍርድ ቤቱ አሳዉቋል በማለት ተከራክራለች፡፡ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱ ተጠሪዎች ደግሞ እግዱ በተጠቀሰዉ መዝገብ ላይ መሰጠቱንና 4ኛ ተጠሪም እግዱን መዝግቤያለሁ ማለቱን አናዉቅም፤ በቤቱ ማህደር ዉስጥ እግድ አለመያያዙን አጣርተን የፈጸምነዉ ዉል ነዉ በማለት ከመከራከራቸዉ በስተቀር በተጠቀሰዉ መዝገብ ላይ አከራካሪዉ ቤት ታግዶ እንዲቆይ እግድ አልተሰጠም በሚል በግልጽ ክደዉ ያሰሙት ክርክር የለም፡፡

እንዲሁም 4ኛ ተጠሪ እግዱን እንዲያዉቅ እግዱን የሰጠዉ ፍርድ ቤት ባዘዘዉ መሰረት 4ኛ ተጠሪ በቀን 09/02/2008 ዓ/ም ለፍርድ ቤቱ በጻፈዉ ምላሽ በትእዛዙ መሰረት በቤቱ ላይ የተሰጠዉን እግድ መመዝገቡን አሳዉቋል ተብሎ በአመልካች የቀረበዉን ክርክር ተጠሪዎች ከስር ጀምሮ በዚህ ችሎት ጭምር ክደዉ አልተከራከሩም፡፡ 4ኛ ተጠሪ በቀን 09/02/2008 ዓ/ም እግዱን ለሰጠዉ ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በጻፈዉ ምላሽ በትእዛዙ መሰረት በቤቱ ላይ የተሰጠዉን እግድ መመዝገቡን እንዳረጋገጠ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ ተወስኖ እያለ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ፍርድ ቤቱ አላረጋገጠም በሚል ይህንን የፍርድ ቤቱን ድምዳሜ ሊያፈርስ የሚችል ምንም አግባብነትና ተቀባይነት ያለዉ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት አቅርበዉ ባላስረዱበት ያሰሙት ክርክር የሕግ መሰረት ያለዉ አይደለም፡፡

በቤቱ ላይ ተሰጠ የተባለዉ እግድ መኖር አለመኖሩን እንዲሁም እግዱ ካለ መነሳት አለመነሳቱን ለማረጋገጥ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት ቁጥር 91309 የሆነ መዝገብ አስቀርቦ በመመልከት በመዝገቡ ላይ አከራካሪዉ ቤት እንዳይሸጥ በቀን 03/02/2008 ዓ/ም የእግድ ትእዛዝ መሰጠቱንና ይህም የእግድ ትእዛዝ በሌላ ተለዋጭ ትእዛዝ አለመነሳቱን አረጋግጧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ በዚህ መልኩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠዉ እዉነት እንዳልሆነ ወይም እግዱ መነሳቱን ማረጋገጡን በመግለጽ የሰጠዉ ዉሳኔ የለም፡፡

በሌላ በኩል እግድ በተሰጠበት መዝገብ ላይ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ተከራካሪ ወገኖች ባለመሆናቸዉ በመዝገቡ ላይ እግድ መሰጠቱን በቀጥታ ያዉቃሉ ተብሎ ባይገመትም 1ኛ ተጠሪ ግን በመዝገቡ ላይ ተከራካሪ ወገን በመሆናቸዉ 4ኛ ተጠሪ ደግሞ እግዱን በመመዝገብ በመሳተፉ (በቤቱ ማህደር እንዲያያዝ ማድረጉ በመረጋገጡ) በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ መኖሩን እንደሚያዉቁ ተረድተናል፡፡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ በዉክልና ስልጣን ቤቱን ለ3ኛ ተጠሪ ሲሸጡ የቤት ሽያጩን በወካይ ስም ስለተዋዋሉ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸዉ በዚህ ግኙኑነት በቤቱ ላይ ተሰጥቶ የነበረዉን እግድ ያዉቁ እንደነበር ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ዉል ሲፈጽሙ በቤቱ ላይ የተሰጠ እግድ እንደሌለ ከ4ኛ ተጠሪ አረጋግጠን በቅን ልቦና የፈጸምነዉ ዉል ነዉ በሚል ከመከራከራቸዉ በስተቀር በቤቱ ላይ እግድ አልተሰጠም ወይም ተሰጥቶ የነበረዉ እግድ ተነስቷል በሚል ይህንን ክርክራቸዉን የሚደግፍ ማስረጃ ከ4ኛ ተጠሪ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ ሌላ የአስተዳደር አካላት ተሰጥቶናል በሚል በማስረጃ አስደግፈዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን እና በይግባኝ ላዩት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ያሰሙት ክርክር ስለመኖሩ የስር ክርክር ግልባጭ አያሳይም፡፡

እንዲሁም የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአከራካሪዉ ቤት ላይ የተሰጠዉን እግድ በሚመለከት እግድ መሰጠቱን፣4ኛ ተጠሪ እግዱን መመዝገቡን በመግለጽ እግዱን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት አሳዉቆ የነበረ መሆኑንና እግዱም እንዳልተነሳ እግዱ ከተሰጠበት መዝገብና ከቤቱ ማህደር በማረጋገጥ የደረሰበትን ድምዳሜ ሊያስተባብል የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ ሳይቀርብለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እግዱ ቢኖር እንኳን የቤቱን ማህደር በመመርመር እግድ መኖር አለመኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት የከተማ አስተዳደሩ እንጂ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች አይደለም በሚል ቤቱን በዉክልና የሸጠዉም ሆነ የቤቱ ገዥ ቤቱ ከእዳና እገዳ ነጻ መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ ከሚመለከተዉ አስተዳደር አካል እንዲሰጣቸዉ የማድረግ ኃላፊነት እንደሌለባቸዉ አድርጎ በመዉሰድ አንድ ጠንቃቃ ገዥ ሊያደርገዉ የሚገባዉን ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሌለበትና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪም ከዚህ አኳያ ተገቢ ጥንቃቄ አለማድረጋቸዉን ካመላከተ በኂላ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር መወሰኑ የሕግ ድጋፍ ያለዉ አይደለም፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን አመልካች 1ኛ ተጠሪ ቤቱን መሸጥና ሌሎች ተግባራትን መፈጸም እንዲችል በቁጥር 5562/2005 በቀን 15/12/2005 ተመዝግቦ በአመልካች ዉክልና የተሰጠዉ ቢሆንም አመልካች በመ/ቁጥር 91309 ላይ ቤቱ እንዳይሸጥ በቀን 03/02/2008 ዓ/ም የእግድ ትእዛዝ ሲያሰጡ ከዚህ የዉክልና ስልጣን ላይ ቤቱን የመሸጥ ፣የመለወጥ እና በማናቸዉም ሁኔታ ወደ 3ኛ ወገን የማስተላለፍ እና እነዚህን ተግባራት ሌላ 3ኛ ወገን ወክሎ ለማስፈጸም የሚያስችል የ1ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣን መገደቡን ያሳያል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2208 ስር ተወካዩ ከወካዩ ጋር በሚያስተሳስረዉ ግንኙነት ዉስጥ ጥብቅ የሆነ የቅን ልቦና ሊኖረዉ እንደሚገባና የዉክልናዉ ሥልጣን የሚያስቀሩትን ምክንያቶች… ለወካዩ አሳብ ማቅረብና ማሳታወቅ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች በተሰጣቸዉ ዉክልና በራሱ በወካይነት ሲሰራም ሆነ 2ኛ ተጠሪ ወክሎ ሲያሰራ ጥብቅ በሆነ የቅን ልቦና ሊሰራና በተለይም ቤቱን መሸጥ ቢያስፈልግ በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ እንዲነሳ ለአመልካች ማሳወቅና እግዱ ከተነሳ በኋላ ቤቱ እንዲሸጥ ማድረግ ሲገባዉ በእግዱ ምክንያት ቤቱን በራሱ ወይም ሌላ ሰዉ ወክሎ እንዲሸጥ የተሰጠዉ የዉክልና ስልጣን ቀሪ ሆኖ (ተገድቦ) እያለ ለአመልካች ሳያሳዉቅ በ2ኛ ተጠሪ አማካኝነት ቤቱ እንዲሸጥ ማድረጉ ሕጉ የጣለበትን ጥብቅ የሆነ የቅን ልቦና መርህ መጣሱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪን የዉክልና ስልጣን ከዚህ አንጻር ሳይመረምር አመልካች ዉክልናዉን እስካላሻረች ድረስ 1ኛ ተጠሪ በዉክልና ስልጣን በራሱም ሆነ በ2ኛ ተጠሪ አማካኝነት ቤቱን በመሸጥ ያደረገዉ ዉል በጸና ዉክልና የተፈጸመ ዉል በመሆኑ ሊፈርስ አይገባም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የዉክልና ስልጣን አፈጻጸም ባህርይ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፡፡

እንዲሁም ምንም እንኳን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል በሕግ ስልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ቢሆንም በዚህ አግባብ በተደረገ ዉል የተሸጠዉ ቤት እንዳይሸጥ እግድ የተሰጠበት በመሆኑና የፍርድ ቤትን እግድ በመጣስ የሚፈጸም ተግባር በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ሕገ ወጥ ተግባር በመሆኑ ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት መደረጉ ከመነሻዉ ሕገ ወጥ የሆነን ተግባር ሕጋዊ ሊያደርግ የሚችል አይደለም፡፡ ሕግ ለግብይት ሥርዓት ጥበቃ የሚያደርገዉ ግብይቱ ሕግን ተከትሎ ሲፈጸም ብቻ ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የተላለፈዉ እግድ ጸንቶ እያለና በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ ተነስቷል ወይም በቤቱ ማህደር ዉስጥ ተመዝግቦ አይታወቅም የሚል ማረጋገጫ ሳይሰጣቸዉና ይህንን የሚያሳይ ማስረጃ ሳይዙ የቤት ሽያጭ ዉሉን በመፈጸማቸዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ለፈጸሙት ግብይት ሕግ ጥበቃ አያደርግላቸዉም፡፡ የፍርድ ቤቱን የእግድ ትእዛዝ በመጣስ ወንጀል ጠቀስ ተግባር ተፈጽሞ የተደረጉ ግብይቶች ወይም ዉሎች ጸንተዉ እንዲቀጥሉ ማድረግ ሕገ ወጥ ተግባራትን በማበረታታት የሕግ የበላይነት እንዲጠፋ የሚያደርግ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚንቀሳቀስ ንብረት ካልሆነ በስተቀር የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል በቅን ልቦና የተደረገ ነዉ ተብሎ በሕግ ጥበቃ የሚደረግበት የሕግ ስርዓት ስለሌለን ከዚህም

አንጻር ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱ ተጠሪዎች የሚያነሱት ክርክርና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቤቱን በቅን ልቦና ስለገዙ የቤት ሽያጭ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በሚል መወሰኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በዚህ የሰበር ችሎት ደረጃ የቤት ሽያጭ ዉል ከፈጸሙ በኋላ ከብር 1,500,000.00 በላይ የሆነ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ተጨማሪ ግንባታ መፈጸማቸዉን በመግለጽ የተከራከሩ ቢሆንም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይህንን ክርክራቸዉን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣንና በይግባኝ ባዩት በክልሉ ፍርድ ቤቶች አንስተዉ የተከራከሩ ስለመሆኑ የፍርድ ቤቶቹ ዉሳኔዎች ይዘት አያሳዩም፡፡ይህንን የሚመለከት በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር በዚህ ችሎት ደረጃ አንስተዉ እንዲከራከሩና ችሎቱም እንዲህ አይነት ክርክር ሰምቶ እንዲወስን የሚፈቅድ የሕግ ስርዓት የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ምንም እንኳን 1ኛ ተጠሪ ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ የቤቱ ገዥ ተጨማሪ ግንባታ ፈጽመዋል የሚል ክርክር ያነሳ ቢሆንም እንዲህ አይነት ክርክር 1ኛ ተጠሪ አንስቶ ለመከራከር የሚያስችል መብትና ጥቅም የሌለዉ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሆኖ እንዲህ አይነት ክርክር ለማንሳት በስነ ስርዓት ሕጉ የተዘረጋዉ የክርክር አቀራረብ ስርዓት አይፈቅድለትም፡፡በመሆኑም ምን እንኳን በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1817/1 ስር ዉል ሲፈርስ ወይም ሲሰረዝ ተዋዋዮች ወደነበሩበት የመመለስ መርህ ተግባራዊ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ወይም ለአንደኛዉ ተዋዋይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ዉሉን ለመፈጸም የተከናወኑ ተግባራት ጸንተዉ እንዲቆዩ ሊደረግ እንደሚገባ የተደነገገ ቢሆንም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የተጠቀሰዉን ገንዘብ ያህል ወጪ አድርገዉ ተጨማሪ ግንባታ በመፈጸማቸዉ ዉሉን አፍርሶ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያስከትልባቸዉ በመግለጽ በስር ፍርድ ቤቶች የሥነ ስርዓት ሕጉ በሚያዘዉ መሰረት ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩ ከዚህም አኳያ የቀረበዉ ክርክር በሰበር ችሎት ደረጃ ሊታይ የማይችል ፍሬ ነገርን የሚመለከት ክርክር በመሆኑ አልተቀበልንም፡፡ይህ ማለት ግን 3ኛ ተጠሪ የደረሰባቸዉ ጉዳት ካለ በሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ክስ በማቅረብ ከመጠየቅ ይህ ፍርድ ሊያግዳቸዉ አይችልም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በፍርድ ኃይል እንዲፈርስላቸዉ ዳኝነት የጠየቁበት የቤት ሽያጭ ዉል አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ዉስጥ ያፈሩት በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝና እንዳይሸጥ ፣እንዳይለወጥ እንዲሁም በማናቸዉም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት እግድ በተሰጠበት ቤት ላይ እግዱ ሳይነሳ እና እግዱ ስለመነሳቱ ሳይረጋገጥ የፍርድ ቤትን የእግድ ትእዛዝ በመተላለፍ ከሕግ ዉጭ የተፈጸመ ዉል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የቤት ሽያጭ ዉሉ በተፈጸመበት ቀን በቤቱ ማህደር ዉስጥ እግዱ እንዳልነበረ ወይም ደግሞ የነበረዉ እግድ ተነስቶ እንደነበር የሚያሳይ ከአስተዳደር አካል የተሰጣቸዉን ማስረጃ ተጠሪዎች ለክልሉ ፍርድ ቤቶች በማቅረብ ተገቢዉን ጥንቃቄ አድርገዉ የፈጸሙት ግብይት መሆኑን ማስረዳታቸዉን የፍርድ ቤቶቹ ዉሳኔዎች ግልባጭ አያሳይም፡፡4ኛ ተጠሪም መጥሪያ ቢደርሰዉም ከስር ጀምሮ ቀርቦ ባለመከራከሩ የቤት ሽያጭ

ዉሉ ሲፈጸም በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ በአስተዳደሩ አይታወቅም ወይም እግዱ ተነስቶ ነበር የሚል ክርክር ከ4ኛ ተጠሪ በኩል አልቀረበም፡፡ የሽያጭ ዉሉ ከተፈጸመ በኋላ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ያየዉ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በቤቱ ማህደር ዉስጥ እግድ መኖሩንና አለመነሳቱን ማህደሩን አስቀርቦ ተመልክቶ ባረጋገጠበት ሁኔታ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ባየበት ጊዜ የቤቱን ማህደር አስቀርቦ ተመልክቷል ቢባል እንኳን አስቀርቦ በተመለከተበት ጊዜ በማህደሩ ዉስጥ እግዱ አለመኖሩ ቤቱ በተሸጠበት ጊዜ በማህደሩ ዉስጥ እግዱ አልነበረም ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ባለሆነበት በዚህ ምክንያት ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት መወሰኑ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ስለሆነም በቤቱ ላይ የተፈጸመዉ የቤት ሽያጭ ዉል በቤቱ ላይ የተሰጠዉ እግድ ጸንቶ እያለ የተፈጸመ በመሆኑ በሕግና በፍርድ ጥበቃ የተደረገለትን አመልካች በቤቱ ላይ ያላቸዉን የባለቤትነት መብት የሚያሳጣ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር1808/2 መሰረት ሊፈርስ ይገባል ሲል የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሉ ሊፈርስ አይገባም ብሎ መሻሩና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተቱን ማረም ሲገባዉ የቀረበለትን የሠበር አቤቱታ በትእዛዝ መዝጋቱ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 301126 ላይ በቀን 03/08/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 310074 ላይ በቀን 30/08/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29574 ላይ በቀን 07/03/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር መነሻ ያወጡትን ወጪ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ወስነናል፡፡

## ትእዛዝ

- በዚህ መዝገብ ላይ በቀን 08/11/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ትእዛዝ በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10189 ላይ እየታየ ያለዉ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠዉ ትእዛዝ ተነስቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29574 ላይ በቀን 07/03/2011 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ታዟል፡፡

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 194876

ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ፍቅሩ መገርሳ

ተጠሪዎች ፡-1. ሚሊዮን ተካ

2. ዓለምነሽ አሼቱ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ዉል ለማስፈረስ የተጠየቀ ዳኝነት የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪዎች ላይ በመሰረተዉ ክስ በቡራዩ ገፈርሳ ቀበሌ በቀድሞ የቤት ቁጥር 665 በኢዲሱ የቤት ቁጥር 4765 የሚታወቅ በ100.8ካሬ ሜትር ስፋት ቦታ ላይ የተሰራ አራት ክፍል ያለዉን አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰዉን መኖሪያ ቤት ከአባቴ በዉርስ ተላልፎልኛል፡፡ይህንን ቤት ተጠሪዎች አታለዉኝ በቀን 24/10/2007ዓ/ም እድሜዬ 14 ዓመት ሆኖ እያለ በዉክልና ሥልጣን ቁጥር ቅ2/6107/13/07 ለ2ኛ ተጠሪ እንዲሰጣት በማድረግ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) ሸጣለታለች፡፡ በዉሉ ላይ ደግሞ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ ተደርጎ ተጽፏል፡፡በወቅቱ እድሜዬ 14 ዓመት ስለነበር ዉል ለማድረግ በምችለበት እድሜ ላይ ስላልነበርኩ በኦሮሚያ ክልል ቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 83/1996 አንቀጽ 233/3 እና 316 ዉሉ ፈራሽ ነዉ፡፡ቤቱ ተሽጦ የተገኘዉ ገንዘብም ለእኔ ጥቅም የዋለ አይደለም፡፡ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤት ፈቃድ ሳታገኝ ንብረቴን መሸጧ መብቴን የጎዳ በመሆኑ ዉሉ ፈርሶ ቤቴን እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በሰጠዉ መልስ ዉሉ የተፈጸመዉ በቀን 24/10/2007ዓ/ም ነዉ፡፡የቤቱ ሽያጭ ዉል ሲፈጸም ቤቱ አንድ ክፍል የነበረ ነዉ፡፡በአሁኑ ወቅት ብር 250,000.00 ወጪ አዉጥቼ አራት ክፍሎችን ሰርቻለሁ፡፡አመልካች በ1989ዓ/ም ስለተወለደ በ2007 ዓ/ም የቤቱ ሽያጭ ዉል ሲፈጸም የአመልካች እድሜ 18 ዓመት ነበር፡፡ይህንንም የቀበሌ መታወቂያ እንዲሰጠዉ ከጠየቀበት፣ ቁጥር 4630/07 ከሆነዉ መታወቂያዉና ከመዝገቡ ዉስጥ ከሚገኘዉ ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ይህንን መታወቂያዉን ይዞ የዉክልና ሥልጣን በፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት ቀርቦ ለ2ኛዋ ተጠሪ ሰጥቷታል፡፡2ኛ ተጠሪም በዚህ ዉክልና በመጠቀም ቤቱን ሸጣልኛለች፡፡ስለዚህ አመልካች እድሜዬ 18 ዓመት ሳይሞላኝ ነዉ የሸጥኩት በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካች ይህንን ክርክሩን በ2ኛ ተጠሪ ላይ እንጂ በ1ኛ ተጠሪ ላይ መከራከሪያ ሊያደርግ አይችልም፡፡አመልካች ሆነ ብሎ ቤቱን መልሶ ለመዉሰድ እድሜዉ 18 ዓመት ሳይሞላ የተደረገ ለማስመሰል ሥልጣን በሌለዉ አካል የተሰጠ ማስረጃ ስላቀረበ ተቀባይነት ሊሰጠዉ አይገባም፡፡አመልካች ቤቱ የተሸጠዉ በብር 40,000.00 እንጂ በብር 300,000.00 አይደለም በማለት ያቀረበዉ ክርክር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት ተቀባይነት የለዉም፡፡ቤቱን ከገዛሁ በኋላም ብር 250,000.00 ወጪ አዉጥቼ ተጨማሪ ግንባታ ስለፈጸምኩ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጠችዉ መልስ እኔ የአመልካች እናቱ ሆኜ አመልካች በዉርስ ያገኘዉን ቤት በማስተዳደር ላይ እያለሁ በገጠመኝ ችግር ምክንያት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተማክሬ አመልካች በሰጠኝ የዉክልና ሥልጣን ቤቱን በብር 40,000.00 ለ1ኛ ተጠሪ ሸጬለታለሁ፡፡1ኛ ተጠሪ የአመልካች እድሜ 14 ዓመት እንደሆነ እያወቀ ያጋጠመኝን ማህበራዊ ችግር ተገን አድርጎ አመልካች ለእኔ ዉክልና እንዲሰጠኝ በማድረግ ዉሉ እንዲፈጸም አድርጓል፡፡1ኛ ተጠሪ የማይገባዉን ብልጽግና ለማግኘትና የአመልካችንና የ2ኛ ተጠሪን መብት ለመጣስ ብሎ ቤቱ በብር 40,000.00 ተሽጦ እያለ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ አድርጎ አሳስቶ ጽፎ አስፈርሞኛል፡፡ ስለሆነም አመልካችን ለመጉዳት ብዬ የፈጸምኩት ዉል ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 36019 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች በመስማት እንዲሁም የአመልካች እድሜ ተመርምሮ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ የቀረቡለትን ማስረጃዎች በመመርመር በቀን 18/02/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የዉክልና ሥልጣን በሰጠበትና የቤት ሽያጭ ዉል በተደረገበት ጊዜ የአመልካች እድሜ 16 ዓመት እንደነበር በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በኦሮሚያ ክልል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 233/3 መሰረት እድሜዉ 18 ዓመት ያልሞላዉ ሰዉ የሚፈጽመዉ ማንኛዉም ዉል በሕግ ፊት የማይጸና ነዉ ሲል በመደንገጉ አመልካች እድሜዉ 16 ዓመት ላይ ሆኖ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን የሕግ ድጋፍ ያለዉ አይደለም፡፡ነገር ግን 2ኛ ተጠሪ አመልካች በዉርስ ያገኘዉን ይህንን ቤት ስታስተዳድር እንደነበር ስለተረጋገጠ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 237/1 መሰረት አባት በህይወት በሌለበት ሁኔታ እድሜያቸዉ ለአቅመ አዳም/ሄይዋን ላልደረሱ ልጆች አሳዳጊ ሞግዚት/አስተዳዳሪ እንደምትሆን

በመደንገጉ 2ኛ ተጠሪ ለምታሳድገዉ አመልካች ጥቅም ለማዋል ማንኛዉንም ድርጊት መፈጸም ትችላለች፡፡ቤቱ የተሸጠዉ የአመልካች እድሜ 18 ዓመት ሳይሆን 18 እንደሞላዉ በማድረግ መታወቂያ በማዉጣትና ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና እንዲሰጥ የተደረገዉ ሆን ተብሎ አመልካችን ለመጉዳት ተብሎ ሳይሆን ቤቱ ተሸጦ በተገኘዉ ገንዘብ ላይ ሌላ ገንዘብ በመጨመር ለአመልካች ቤት የገዛችለት መሆኑ በምስክሮች ቃል ተረጋግጧል፡፡የ1ኛ ተጠሪ ምስክሮችም 1ኛ ተጠሪ ዉሉን አመልካችን ለመጉዳት ብሎ እንዳልፈጸመ መስክረዋል፡፡እንዲሁም በ2ኛ ተጠሪ የቀረቡ ምስክሮች ያስረዱት ቤቱ ሊሸጥ የቻለዉ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የአካባቢዉ ሰዎች ስላስቸገሯት ቤቱ ወዳለበት አካባቢ ሄዳ በመቆጣጠር ለማስተዳደር ባለመቻሏ ምክንያት ነዉ፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የተቻለዉ ቤቱ የተሸጠዉ ለአመልካች ጥቅም ተብሎ እንደሆነ ነዉ፡፡የኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 294 ላይ ሞግዚት የሚንቀሳቀስ ንብረት ሲሸጥ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት የደነገገ ቢሆንም ቋሚ ንብረት ሽያጭ በተመለከተ የደነገገዉ ነገር የለም፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46490 ላይ ለሕጻኑ ጥቅም የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ እንደሚቻል ትርጉም ሰጥቷል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 103151 ላይ በኦሮሚያ ሕግ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ባይደነገገም በፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 306 እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2207/1 ስር የተደነገገዉን የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ እንደሚቻል ትርጉም ሰጥቷል፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሊሸጡ የቻሉት ለአመልካች ጥቅም በማለት በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 321147 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎችን መዝኖ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን የሸጠችዉ ባላት አመልካችን የማሳደግ ሥልጣን ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ጥቅም የዋለችዉ ነገር የለም፡፡ዉሉ ሲደረግ የአመልካች እድሜ 18 ዓመት ስላልሞላዉ በፍርድ ቤት ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ከልጁ ጋር ማንኛዉንም ዉል መፈጸም እንደማይቻል በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 306/1 ስር በመደንገጉ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና በሰጠበት ጊዜ እድሜዉ ለአቅመ አዳም እንዳልደረሰ 1ኛ ተጠሪ እያወቀ አመልካችን በማታለል ቤቱን መግዛቱ ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች የአመልካች እድሜ ለአቅመ አዳም አለመድረሱን እያወቁ በክፉ ልቦና አታለዉ ዉክልና እንዲሰጥ በማድረግ የፈጸሙት ዉል በመሆኑና ከሽያጩ የተገኘዉም ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም ስላልዋለ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1704/1 እና 1808/1 መሰረት እንዲፈርስ በመወሰን የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1815/1 መሰረት አስቀድሞ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

በመቀጠል 1ኛ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠበር አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 320926 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 15/07/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ሲመዘን 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛዉ ዉክልና ከወሰደችዉ 2ኛ ተጠሪ ላይ ነዉ እንጂ እድሜዉ ለአቅመ

አዳም ያደረሰዉ ልጅ አሳዳጊና የንብረት አስተዳዳሪ ላይ ነዉ የሚል አይደለም፡፡የተረጋገጠዉ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዙት ዉክልና ካላት 2ኛ ተጠሪ ላይ ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች እድሜዉ ለአቅመ አዳም ደርሷል ወይስ አልደረሰም እንዲሁም ዉክልና መስጠት ይችል ነበር ወይ በሚል የሚጣራበት ምክንያት የለም፡፡ይህ ቢሆን እንኳን የተሸጠዉ ቤት ለአመልካች ጥቅም እንደዋለ ከግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል መረዳት ስለተቻለና ቤቱ ከተሸጠ በኋላ በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለዉጥ መደረጉን መገንዘብ ተችሏል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቤቱ የተሸጠበት ዋጋ መረጋገጥ ያለበት በጽሁፍ ከተደረገዉ ዉል ላይ በመሆኑ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ ተረጋግጧል፡፡በአጠቃላይ ዉልን የሚያስፈርስ ምክንያት ሳይኖር ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካች በቀን 26/12/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች በዉርስ ያገኘሁት ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በተሸጠበት ጊዜ እና አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣን በሰጠሁበት በቀን 24/01/2007ዓ/ም እድሜዬ ለአቅመ አዳም እንዳልደረሰ ባቀረብኩት ማስረጃና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፎሬንሲክ እንዲመረመር አስደርጎ አረጋግጧል፡፡ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ህጻን ምንም አይነት ዉል ማድረግ እንደማይችልና ዉል አድርጎ ከሆነም ዉሉ ፍርስ እንደሆነ በኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 233/1፣316 እና 321/1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛዉ ልዩ ዉክልና ካላት 2ኛ ተጠሪ ላይ ስለሆነ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡1ኛ ተጠሪ ዉልን በቅን ልቦን የፈጸምኩት ነዉ የሚል ክርክር በግልጽ አላነሳም፡፡ይልቁንም አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረብኩት ማስረጃ ዉሉ በቅን ልቦና እንዳልተፈጸመ አስረድቻለሁ፡፡አመልካች ይህንን ቤት ለማግኘት በአቶ አየለ ባሻ ተወክዬ በምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስከራከር 1ኛ ተጠሪ እህቴን ቅድስት መገርሳን ወክሎ ሲከራከር ስለነበር ቤተሰብ ስለሆነ እድሜዬ ለአቅመ አዳም እንዳልደረሰ እንደሚያዉቅ ለስር ፍርድ ቤት በቀን 30/09/2000ዓ/ም የተጻፈ ቃለ ጉባኤ አቅርቤ አስረድቻለሁ፡፡2ኛ ተጠሪ ቤቱን አከራይተሽ እንዳትጠቀሚ የአካባቢዉ ዱርዬዎች ያስቸግሩሻልና ሽጭልኝ በማለት 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪን እንደጠየቃት እና አመልካች ለአቅመ አዳም ሳልደርስ እንደ ደረስኩ ተደርጎ መታወቂያ እንዲወጣልኝና ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና እንዲሰጥ 1ኛ ተጠሪ በራሱ መኪና አዲስ አበባ ኳስ ሜዳ አካባቢ ወደሚገኘዉ ዉልና ማስረጃ ወስደዉኝ እድሜዉ ለአቅመ አዳም አልደረሰም በሚል እንዳባረሯቸዉና መሳለሚያ አካባቢ ወደአለዉ ሌላ ዉልና ማስረጃ መስሪያ ቤት ሄደን ትልቅ ጃኬት አልብሰዉኝ እንዲሁም ወደ ዉስጥ ገብቶ አነጋግሮ ወጥቶ እንዳስፈረመኝ በመግለጽ በመመስከራቸዉ 1ኛ ተጠሪ ቅን ልቦና እንዳልነበረዉ ተረጋግጧል፡፡ዉሉ ሲደረግ የአመልካች እድሜ ለአቅመ አዳም ደርሶ ቢሆን ኖሮ በቀጥታ ከእኔ ጋር በመዋዋል ዉሉን መፈጸም ስለሚቻል እኔ ዉክልና እንዲሰጥ ማድረግ አይጠበቅበትም ነበር፡፡ቤቱም የተሸጠዉ በብር

40,000.00 እንጂ በብር 300,000.00 እንዳልሆነ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከሽያጩ የተገኘዉን ገንዘብ 2ኛ ተጠሪ ከማባከኗ በስተቀር ለእኔ ጥቅም አላዋለችም፡፡ለእኔ ጥቅም ያዋለች ስለመሆኑም የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡በመሆኑም የአመልካች ፈቃድ የተገኘዉ እድሜዬ ለአቅመ አዳም ባልደረሰበት በመሆኑ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1710 መሰረት ሊፈርስ ይገባል ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የተሸጠዉ አመልካች አቅመ አዳም ሳይደርስ ለ2ኛ ተጠሪ በሰጠዉ ዉክልና ሥልጣን ሆኖ እያለ የቤት ሽያጭ ዉሉ ሕጋዊ ነዉ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከኦሮሚያ ክልልና ከፌዴራል ቤተሰብ ሕግጋት ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በተናጠል የተጻፈ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 21/05/2012ዓ/ም በተጻፈ መልሱ በቀን 24/10/2007ዓ/ም በተደረገ ዉል ንብረትነቱ የአሁን አመልካች የሆነን ቤት ሞግዚቱና አሳዳጊ እናቱ 2ኛ ተጠሪ በነበራት የዉክልና ሥልጣን ሶስት ምስክሮች ይዛ ቀርባ በብር 300,000.00 ሸጣልኛለች፡፡ ከሽያጩ በተገኘዉም ገንዘብ 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በስሙ ወዲያዉኑ በሆለታ ከተማ ዉስጥ ሳዳሞ በሚባል ቀበሌ ዉስጥ መኖሪያ ቤት ገዝታለት አመልካች እስካሁን በዚህ ቤት እየተጠቀመ ሲለሚገኝ በሰ/መ/ቁጥር 103151 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ገንዘቡ ለአመልካች ጥቅም ስለዋለ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ ለአመልካች ቤቱን በዉርስ ተከራክሮ ያገኘለት አቶ አየለ ባሳ ምስክር ሆኖ ቀርቦ ሽያጩ ያለምንም ማታለል እንደተፈጸመና ለአመልካች ቤት እንደተገዛለት መስክሯል፡፡እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ ብር 250,000.00 የሚጠጋ ወጪ አዉጥቼ አስፋፍቼ ስርቼ እየተጠቀምኩ እንደሚገኝ አስረድቻለሁ፡፡አመልካች በሽያጩ ገንዘብ ቤት ተገዝቶለታል በሚል በ1ኛ ተጠሪ የቀረበዉን ክርክር ክዶ አልተከራከረም፡፡አመልካች ክሱን ያቀረበዉ ቤቱን ከገዛሁ በኋላ አስፋፍቼ ስለሰራሁ ትልቅ ዋጋ ያወጣል በሚል በቁጭት በመነሳሳት እንጂ በቅን ልቦና ዉጭ የፈጸምኩት ነገር ስላለ አይደለም፡፡ብር 250,000.00 ወጪ አዉጥቼ ተጨማሪ ሶስት ክፍል ስለሰራሁ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1815/1 መሰረት ወደነበርንበት ቦታ መመለስ የማይቻል ሆኗል፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሉ ሊፈርስ አይገባም ብሎ የወሰነዉ ሕግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 21/05/2013ዓ/ም በተጻፈ መልሷ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ጠያይቆ መጥቶ ዱርዬዎች ስለሚያስቸግሩሽ ሽጭልኝ በማለት በማባበል እንዲሸጥለት አድርጓል፡፡ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ ቤት መሸጥ እንደማይችልና እኔም በእናትነቴ ብቻ ቤቱን መሸጥ እንደማልችል ስላወቀ 1ኛ ተጠሪ እኔን በማታለል ልጄ ምንም በማያወቅበት እድሜ ላይ እያለ ዉክልና እንዲሰጠኝ አድርጎ በሕጋዊ መንገድ

እንደገዛ በማስመሰል ያደረገዉ ዉል ነዉ፡፡ቤቱን በብር 300,000.00 እንደገዛ አስመስሎ አስፈረመኝ እንጂ ቤቱን የገዛዉ በብር 40,000.00 ነዉ፡፡ቋሚ ንብረት ለመሸጥ እናት መሆን ብቻ በቂ አይደለም፡፡ስለሆነም በአመልካች አቤቱታ ላይ የተገለጸዉ ሁሉ እዉነት ስለሆነ በጠየቀዉ መሰረት ቢወሰንለት አልቃወመም በማለት መልሷን ሰጥታለች፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከኦሮሚያ ክልል ቤተሰብ ሕግ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ሕግጋት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረተዉ በዉርስ ያገኘዉን በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት 2ኛ ተጠሪ ሞግዚቱ ሆና ስታስተዳድር በነበረችበት ጊዜ ተጠሪዎች እድሜዬ ለአካለመጠን እንዳልደረስኩ እያወቁ የዉክልና ሥልጣን ለ2ኛ ተጠሪ እንድሰጥ በማድረግ ተጠሪዎች በፈጸሙት የሽያጭ ዉል 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን ከሕግ ዉጭ በሆነ አኳኋን ለ1ኛ ተጠሪ ስላስተላለፈችና ከሽያጩም የተገኘዉ ገንዘብ ለእኔ ጥቅም ስላልዋለ ዉሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና ሲሰጥና የቤት ሽያጭ ዉል በተደረገበት ጊዜ በ2007ዓ/ም የአመልካች እድሜ 18 አመት ሆኖታል፤2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ባገኘችዉ የዉክልና ሥልጣን በመጠቀም በብር 300,000.00 ሸጣልኝ ከብር 250,000.00 ብር በላይ ወጪ አዉጥቼ ተጨማሪ ክፍል ቤቶችን ስለገነባሁ ዉሉ ወደማይፈርስበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ እና የቤቱ ዋጋ ጨምሯል በሚል ፍላጎት የቀረበ ክስ ስለሆነ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ዉክልና በሰጣት ጊዜ የአመልካች እድሜ 14 ዓመት እንደነበርና በነበራት ማኅበራዊ ችግር ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንድትሸጥለት ጠይቆ ቤቱን በብር 40,000.00 ብቻ ገዝቶ እያለ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስቦ ቤቱ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ አድርጎ የተፈጸመ የቤት ሽያጭ ዉል እንደሆነ በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ አመልካችም ቤቱ የተሸጠዉ በብር 40,000.00 ሆኖ እያለ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ ተደርጎ በዉሉ ተጠቅሷል በማለት ተከራክራል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለሞግዚቱ ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣን በሰጠበት ጊዜም ሆነ ይህንን የዉክልና ሥልጣን በመጠቀም አመልካች በዉርስ ያገኘዉን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በሸጠችበት በ2007 ዓ/ም አመልካች እድሜዉ ለአካለመጠን እንዳልደረሰ ወይም እድሜዉ 16 ዓመት እንደነበር በሳይንሳዊ ዘዴ በምርመራ ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ከግራ ቀኙ ክርክር እና በማስረጃ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር በመነሳት የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ ጭብጥ አመልካች እድሜዉ ለአካለመጠን ሳይደርስ ሞግዚቱ ለሆነችዉ 2ኛ ተጠሪ እንዲሰጥ በተደረገዉ የዉክልና ሥልጣን በዉርስ ያገኘዉን ቤት ለ1ኛ ተጠሪ

በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገዉ ዉል ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡

ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል የተላለፈዉ ቤት የሚገኘዉ እና ተዋዋዮች በተለይም አመልካች ዉሉ በተደረገበት ጊዜ ሲኖር የነበረዉ በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በዋናነት ተፈጻሚነት ያለዉ የኦሮሚያ ክልል የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 83/1999 ሲሆን፣እንደአግባብነታቸዉ በፍትሐ ብሔር ሕግ ስለዉልና ስለዉክልና የተደነገጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 316 ስር አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽማቸዉ ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ለሞግዚቱ የዉክልና ሥልጣን በሰጠበት ጊዜ በ2007ዓ/ም እድሜዉ ለአካለመጠን እንዳልደረሰ ወይም እድሜዉ 16 ዓመት እንደነበር በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡እንደሚታወቀዉ ዉክልና ዉል በመሆኑና አመልካች የሰጠዉም የዉክልና ሥልጣን ግዙፍ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነዉን መኖሪያ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ማስተላለፍ ትችል ዘንድ ሥልጣን የሚሰጣት በመሆኑ ዉክልና የተሰጠበት ጉዳይ ለአመልካች እንደእለት ጉዳይ(Acts of everyday life) ሊቆጠር የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም በተሻሻለዉ የኦሮሚያ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 316 እና 310 ጣምራ ንባብ መሰረት አመልካች የመኖሪያ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የዉክልና ሥልጣን ለ2ኛ ተጠሪ በሰጠበት ጊዜ እድሜዉ ለአካለመጠን ያልደረሰ በመሆኑ ያለፍርድ ቤት ፈቃድ የዉክልና ሥልጣን መስጠት ስለማይችል ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን ፈራሽ ወይም ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ (shall be of no effect) ነዉ፡፡

በሌላ በኩል ከክርክሩ እንደተረዳነዉ የአመልካች አባት መሞቱን ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ በእናትነቷ የአመልካች አሳዳሪና ሞግዚት ሆና ለክሱ መነሻ በሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል የተሸጠዉን ቤት ስታስተዳድር ቆይታለች፡፡2ኛ ተጠሪ በዚህ አግባብ የአመልካች አሳዳሪና ሞግዚት በመሆን የአመልካችን ንብረት የማስተዳደር መብት እና ሥልጣን እንዳላት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 237፣286 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡2ኛ ተጠሪ የአመልካችን መኖሪያ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈችዉ በዉክልና ሥልጣን ነዉ ወይስ በሞግዚትነት ሥልጣን ነዉ የሚለዉን ቀጥለን የምንመለከተዉ ሆኖ 2ኛ ተጠሪ የሞግዚትነት ሥልጣኗን ተግባራዊ ማድረግ ያለባት የሕጻኑን(የአመልካችን) ሀብትና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን ሊያስከብር በሚችል መልኩ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ በክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 286/2 ስር ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሞግዚት የሞግዚትነት ሥልጣኑን በሕጉ አግባብ ተግባራዊ አድርጓል ወይስ አላደረገም የሚለዉን ጉዳይ በተመለከተ መርምረዉ ዉሳኔ የሚሰጡ አካላት ፍርድ ቤትን ጨምሮ የሚሰጡት ዉሳኔ የሕጻኑን ደህንነትና መልካም አስተዳደግ ወይም ጥቅሙን(best interest of child) የሚያስቀድም መሆኑን ማረጋገጥ

ይጠበቅባቸዋል፡፡(የኢፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት እና የኦሮሚያ ክልል የተሻሻለዉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 36/2 እና የኦሮሚያ ክልል የተሻሻለዉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 286/2 እና 235 ይመለከቷል፡፡)

2ኛ ተጠሪ የአመልካችን መኖሪያ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈችዉ በዉክልና ሥልጣን ነዉ ወይስ በሞግዚትነት ሥልጣን የሚለዉን በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ከተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር አንጻር መርምረናል፡፡በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 322 ስር እንደተደነገገዉ 2ኛ ተጠሪ በኃላፊነት ከማይጠየቁበት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ለአመልካች ጥቅም ለፈጸመችዉ ሕጋዊ ተግባራት ነዉ፡፡ሕጋዊ ተግባራት የሚባሉት ደግሞ በሕግ የተጣሉ ግዴታዎችንና ስርዓቶችን በመጠበቅ የተፈጸሙ ተግባራት እና ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ናቸዉ የተባሉትን ተግባራት አለመፈጸም ነዉ፡፡ 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ሞግዚትና አሳዳሪ በመሆኗ ለአመልካች መልካም አስተዳደግ ይረዳ ዘንድ የአመልካችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የአመልካችን ሀብት እና ንብረት የምትጠቀምበትን መንገድ መወሰን ትችላለች፡፡ ይህም ማለት ለአመልካች እድገት ንብረት መሸጥ የግድ ሲል በሕግ የተጣሉ ግዴታዎችን በመወጣት በሕግ የተዘረጋዉን ሥርዓት በመከተል ንብረቱን በመሸጥ ለአመልካች ጥቅም ማዋል ትችላለች ማለት ነዉ፡፡ከእዚህ ጋር ተያይዞ 2ኛ ተጠሪ እንደሞግዚት በፍርድ ቤት ፈቃድና የፍርድ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልጋት በሽያጭ ልታስተላለፍ የምትችለዉ ንብረት አይነቶች ምንድንናቸዉ የሚለዉን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡በክልሉ ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 294 ላይ በድንጋጌዉ ርእስና በይዘቱ እንደተመለከተዉ ሞግዚት መሸጥ የሚችለዉ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ የሕጻኑን ንብረቶች ፣አክሲዮኖችንና የገንዘብ ሰነዶች ተብለዉ የተጠቀሱትን ንብረቶችን እንደሆነ በግልጽ ተዘርዝሮ ተመልክቷል፡፡ከዚህ ድንጋጌ መንፈስና ይዘት መረዳት እንደሚቻለዉ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ለመሸጥ ሞግዚት የፍርድ ቤትን ፈቃድ አስቀድሞ ማግኘት እንዳበት ሕጉ አያስገድደዉም፡፡

በሌላ በኩል ከተዘረዘሩት ንብረቶች መካከል የማይንቀሳቀስ ንብረት አለመካተቱ ሲታይ በሕጉ በግልጽ ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሲሸጥ አስቀድሞ የሚመለከተዉን ፍርድ ቤት ማስፈቀድ እንዳለበት ባይደነገግም የማይንቀሳቀስ ንብረት በአገራችን ካለዉ ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፋይዳ አንጻር ሞግዚት ፍርድ ቤትን ማስፈቀድ ሳያስፈልገዉ በፈለገዉ ጊዜ የሕጻኑን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ይችላል የሚል አቋም በሕግ አዉጪዉ ተይዟል ብሎ ለመደምደም የሚቻል አይደለም፡፡በመሆኑም ሞግዚት ለሕጻኑ አስተዳደግ የሕጻኑን የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥ የግድ እንደሚል ካመነ በሽያጭ ከማስተላለፉ በፊት የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል ማለት ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁ.46490 መጋቢት 21 ቀን 2002 ዓ/ም እና በሰ/መ/ቁጥር 103151 እና መስከረም 24 ቀን 2008ዓ/ም በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሞግዚት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለልጆች መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሸጠ መሆኑ ከተረጋገጠ የሽያጭ ውል ለማፍረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ማለት የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በተመለከተ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለዉ ሽያጩ

የተከናወነዉና ከሽያጩ የተገኘዉ ገንዘብ ያለበት ለልጆች ቅጥም የዋለ መሆን ተጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ መሆኑን ለማሳየት እንጂ በማንኛዉም ጊዜ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ሞግዚት የህጻኑን የማይንቀሳቀስ ንብረት የመሸጥ ሥልጣን አለዉ የሚል ትርጉም መስጠቱን የሚያስገነዝብ አይደለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነዉ መኖሪያ ቤት በ2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ የተላለፈዉ 2ኛ ተጠሪ በነበራት የሞግዚትነት ሥልጣን ሳይሆን አመልካች እድሜዉ 16 አመት ሆኖ እያለ በሰጣት ቤቱን የመሸጥ የዉክልና ሥልጣን መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ እንደተረጋገጠዉ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በሞግዚትነት ሥልጣን ሸጣ ቢሆን ኖሮ የአመልካች እድሜ 18 ዓመት ሳይሞላዉ 18 ዓመት እንደሆነዉ በማስመሰል ለ2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያስችል የዉክልና ሥልጣን እንዲሰጣት ማድረግ ባላስፈለገ ነበር፡፡ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን ተረጋገጦ የተመዘገበዉ በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከሰነዱ በመረጋገጡ አመልካች የዉክልና ሥልጣን ለመስጠት የሚያስችል ችሎታ እንዳለዉ(እድሜዉ ለአካለመጠን መድረሱን) የማረጋገጥ ኃላፊነት በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 3፣9(1/ለ) እና 14 መሰረት የዉክልና ሥልጣኑን አረጋግጦ የመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠዉ የፌዴራል የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ነዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በመርህ ደረጃ 1ኛ ተጠሪ ከማያዉቀዉ ሰዉ ጋር ያደረገዉ ዉል ቢሆን ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጣት የዉክልና ሥልጣን በሚመለከተዉ አካል የተመዘገበና ቤት ለመሸጥ የሚያስችል ልዩ የዉክልና ሥልጣን እንዳላት ከማረጋገጥ ባለፈ የወካዩን እድሜ የማረጋገጥ ኃላፊነት እንደማይኖርበት ነዉ፡፡ሆኖም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሮና መዝኖ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና ሲሰጥ አመልካች አካለመጠን ያልደረሰ መሆኑን 1ኛ ተጠሪ እያወቀ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና መስጠት እንዲችል መታወቂያ እንዲያወጣና የዉክልና ሥልጣን ማስረጃ ወደተመዘገበበት መስሪያ ቤት በመዉሰድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተሳትፎ ማድረጉን ከምስክሮች ቃል አረጋግጧል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በማስረጃ ከተረጋገጠዉ መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ ዉክልና እንዲሰጥ ሲደረግም ሆነ 2ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣኑን ተጠቅማ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የቤት ሽያጭ ዉሉ ስትፈጸም አመልካች ለአካለመጠን እንዳልደረሰ 1ኛ ተጠሪ ያዉቅ እንደነበር ነዉ፡፡በዚህ መሰረት 1ኛ ተጠሪ አመልካች ለአካለመጠን አለመድረሱን ያዉቅ ከነበረ በክልሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 318/2 ስር እንደተደነገገዉ የአመልካችን አላዋቂነት መጠቀሙን ስለሚያሳይ የቤት ሽያጭ ዉሉን ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የፈጸመዉ በቅን ልቦና ነዉ ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ እንዲሁም አመልካች እድሜዉ ለአካለመጠን ሳይደርስ እንደደረሰ ተደርጎ መታወቂያ በማዉጣት የዉክልና ሥልጣን እንዲሰጥ መደረጉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስረጃ ተመዝኖ የተረጋገጠ ቢሆንም ባይረጋገጥ እንኳን በክልሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 321/1 መሰረት አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ሳይደርስ

ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳን ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት በሕግ የሚደረግለትን ጥበቃ ሊያጣ አይችልም፡፡በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ አመልካች ለአካለመጠን ያልደረሰ መሆኑን እያወቀ እድሜዉ 18 ዓመት ያልሞላዉ አመልካች ዉክልና ለ2ኛ ተጠሪ እንዲሰጥ በማድረግ በመቀጠልም 2ኛ ተጠሪ ቤቱን እንድትሸጥለት ያደረገዉ የቅን ልቦና ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡በዚህ አኳያ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ዉሉን ያደረገዉ በቅን ልቦና እንዳልሆነ አመላክቶ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ ድጋፍ ያለዉ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በተጨማሪም 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላፈችዉ አካለመጠን ያልደረሰዉ አመልካች በሰጣት የዉክልና ሥልጣን እንጂ በሞግዚትነት ሥልጣኗ አለመሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ዉሉን በሞግዚትነት ሥልጣኗ ፈጽማለች ተብሎ ቢታሰብ እንኳን በተሻሻለዉ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 323 መሰረት የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች፤ ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡በዚህ መሰረት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2207/1 ስር ተወካዩ ከስልጣኑ ውጭ የሠራው ስራ በቅን ልቡና ሆኖ ሲገኝ ሥራውን ወካዩ እንዲያጸድቅለት እንደሚደረግ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አግባብ የአመልካች ሞግዚት የሆነችዉ 2ኛ ተጠሪ "ቅን ልቡና" መታየት ያለበት የቤት ሽያጭ የፈጸመችዉ ለአመልካች ጥቅም ጥቅም ነዉ ወይስ አይደለም? ከሚል አንጻር መሆን አለበት፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘም በሰ/መ/ቁጥር 103151 አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንጻር 2ኛ ተጠሪ ከቤት ሽያጭ ዉሉ የተገኘዉን ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም አዉያለሁ በማለት አልተከራከረችም፤ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ በማንኛዉም ተከራካሪ በስር ፍርድ ቤት ስለመቅረቡ ግራ ቀኝ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር አያሳይም፡፡እንዲሁም ከቤቱ ሽያጭ የተገኘ ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም መዋሉን የሚያመለክት ማስረጃ መቅረቡን የሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ያረጋገጡት ነገር እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ስለሆነም ከዚህም አንጻር ከሽያጩ የተገኘዉ ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም አልዋለም በሚል ዉሉ እንዲፈርስ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ማስረጃን መርምሮ የመመዘን ሥልጣኑን በመጠቀም በመሆኑና የማስረጃ ምዘና መርህን ተግባራዊ ከማድረግም አንጻርም የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ የቤት ሽያጭ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የቤት ሽያጭ ዉሉ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ ጉዳዩን በይግባኝ ባየዉ የከልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ የሚባል ከሆነ የዉሉ መፍረስ ዉጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉ ቀጥሎ ዉሳኔ የሚሻ ነጥብ፡፡አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ቤቱ ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ የተላለፈዉ በብር 40,000.00 እንጂ በብር 300,000.00 አይደለም ብለዉ ሲከራከሩ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ቤቱን በብር 300,000.00 መግዛቱን በመግለጽ ተካራክሯል፡፡እንዲሁም ከስር ጀምሮ

1ኛ ተጠሪ ቤቱን ከገዛ በኋላ ብር 250,000.00 ተጨማሪ ወጪ አዉጥቶ ተጨማሪ ክፍሎችን መገንባቱን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የዉል መፍረስ በዉል የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች እንዲቋረጡ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸዉ ማድረግን የሚያስከትል ስለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1807/ሀ እና 1815 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዉል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮች በተቻለ መጠን ዉሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ እና ዉሉን ለመፈጸም የተሠራ ሁሉ ቀሪ ሆኖ በማናቸዉም አኳኋን ዉጤት እንደሌለዉ የሚደነግገዉ የሕጉ አንቀጽ 1815 ድንጋጌ በተለይ ሲታዩ በዉል መሠረት አንዱ ለሌላዉ የፈጸመዉ ተግባር ካለ ቀሪ ተደርጎ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ የግድ የሚል መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሉ አንድን ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ከሆነ እና ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ዉጤቱ የሚሆነዉ ንብረቱን ገዝቶ በዉሉ መሠረት የተረከበዉ ተዋዋይ ንብረቱን ለሻጩ መልሶ እንዲያስረክብ፣ ሻጩም ደግሞ በዉሉ መሠረት የተቀበለዉ ገንዘብ ካለ ገንዘቡን ለገዥዉ እንዲመልስ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ግራ ቀኝ የተቀባበሉትን ነገር ባሉበት ሁኔታ አንዱ ለሌላዉ እንዲመልስ ከማድረግ ዉጪ ሻጩ በዉሉ መሠረት ከተቀበለዉ ገንዘብ በላይ ገዥዉም ደግሞ ከተረከበዉ ንብረት በላይ አንዱ ለሌላዉ ለመመለስ የማይገደዱ መሆኑን ነዉ፡፡ በተሻሻለዉ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 319 ስር አካለመጠን ካልደረሰ ልጅ ጋር የሚደረግ ዉል ሲፈርስ የሚኖረዉን ዉጤት በተመለከተ የተደነገገዉም ይህንን በፍ/ብ/ሕጉ የተደነገገዉን የሚደግፍ ነዉ፡፡በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የነበረዉን ቤት ለአመልካች ሊያስረክብ ይገባል ብሎ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ብለናል፡፡

ሌላዉ ከላይ እንደተመለከተዉ በፍ/ብ/ ሕጉ ቁጥር 1815 ስር የተደነገገዉ ዉሉ በመፍረሱ ምክንያት ግራ ቀኝ የሚኖራቸዉ መብትና ግዴታ ሲሆን ተጠሪ በቦታዉ ላይ በእራሱ ወጪ የገነባዉ ቤት በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይሆንም፡፡ በፍ/ብ/ ሕግ ቁጥር 1818 ድንጋጌ መሠረት ዉሉ ከመፍረሱ የተነሳ ንብረትን የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰዉ ንብረቱን ለዉጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አድርጎ እንደሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጪ የተነሳ ያሉትን መብቶች በከዉል ዉጪ ኃላፊነት ድንጋጌዎች መሠረት መጠየቅ ይችላል፡፡ እንደሚታወቀዉ በዉል አንድ ሰዉ አንድን ንብረት በእጁ ካስገባ በኋላ በእራሱ ወጪ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ያደረገ እንደሆነ በእራሱ ወጪ ተጨማሪ ነገር የሰራዉ ተዋዋይ ንብረቱን መልሶ ሲያስረክብ ከነማሻሻያዎቹ ለሌላኛዉ ተዋዋይ ሊያስረክብ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህ መሆኑ በአንድ በኩል ንብረቱ የተመለሰለት ሰዉ ያላግባብ እንዲበለጽግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱን የማስረከብ ግዴታ ያለበት ወገን ያለአግባብ ተጎጂ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ የፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1818 ድንጋጌም ለእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች መፍትሔ የመስጠት ዓላማ ያደረገ በመሆኑ የድንጋጌዉ አፈፃፀምም ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለዉን

ተወዳዳሪ ጥቅም (computing interests) ማስታረቅ በሚያስችል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት በያዝነዉ ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በእጁ በገባዉ ይዞታ ላይ የሰራዉ ተጨማሪ ክፍል ቤቶች ካሉ ሁለት አማራጮች ይኖረዋል፡፡ አንደኛዉ አማራጭ በይዞታዉ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ የሰሩትን ቤት አፍርሶ ባዶ ቦታዉን ብቻ ለአመልካች ማስረከብ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ በተጨማሪነት በቦታዉ ላይ የተሰራዉን ቤት እዚያዉ በመተዉ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ አመልካች እንዲከፍል መጠየቅ ነዉ፡፡ ተጠሪ ሁለተኛዉን አማራጭ ከመረጠ ይህ ጥያቄዉ የሚስተናገደዉ በፍ/ብ/ ሕጉ ቁጥር 1818 ላይ በተመለከተዉ ይሆናል፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1704/1 እና 1808/1 መሰረት የቤት ሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ እና 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1815/1 መሰረት አስቀድሞ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ብሎ ሲወስን የሚመለሰዉ የሽያጩ ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ግራ ቀኙ በመካካዳቸዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ባለመሆኑ ይዘቱ ባከራከረ ጊዜ በዉሉ ላይ የተመለከቱ ምስክሮችን በመስማትና በሌላ ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2009 ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ትክክለኛዉን ቤቱ የተሸጠበትን ገንዘብ መጠን በማስረጃ ማረጋገጡ የሕግ ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት በቤት ሽያጭ ዉሉ ላይ ቤቱ በብር 300,000.00 እንደተሸጠ ቢገለጽም ቤቱ በእርግጥ በብር 40,000.00 ብቻ እንደተሸጠና 1ኛ ተጠሪም ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠዉ ብር 40,000.00 ብቻ እንደሆነ በምስክሮች ቃል አረጋግጦ 2ኛ ተጠሪ ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር)ለ1ኛ ተጠሪ እንድትከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍበትን ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች እድሜዉ ለአካለመጠን ሳይደርስ በዉርስ ያገኘዉን መኖሪያ ቤት 2ኛ ተጠሪ በሽያጭ እንድታስተላልፍ የሰጠዉ የዉክልና ሥልጣን ሕጋዊ ዉጤት የለዉም፡፡ይህንን ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉን የዉክልና ሥልጣን በመጠቀም 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ማስተላለፏ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 1ኛ ተጠሪ ቤቱን የገዛዉ ዉክልና ካላት 2ኛ ተጠሪ በመሆኑ አመልካች እድሜዉ ለአቅመ አዳም ደርሷል ወይስ አልደረሰም እንዲሁም ዉክልና መስጠት ይችል ነበር የሚሉ ጭብጦች ተይዘዉ ሊጣሩ አይገባም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠዉን ዉሳኔ በመሻር የከፍተኛዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራሉም ሆኖ በክልል ሕገ መንግስት እንዲሁም በተሻሻለዉ የክልሉ ቤተሰብ ሕግ በወቅቱ ሕጻን ለነበረዉ አመልካች የተደረገለትን ሕጋዊ ጥበቃ ያላገናዘበ እና ለሕጻን ጥቅም አጽንኦት ሰጥቶ እንዲወስን በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ የአመልካችን መኖሪያ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፈችዉ በአመልካች ስም ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 2ኛ ተጠሪ ዉሉን ለመፈጸም ያስቻላትን የሥልጣን ምንጭ ሕጋዊነት መመርመር አያስፈልግም ብሎ የደረሰበት ድምዳሜ የወካይና የተወካይ ግንኙነት ጽንሰ ሀሳብና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተሻሻለዉ የክልሉ ቤተሰብ ሕግ እና

በፍ/ብ/ሕጉ የተደነገገዉን ያገናዘበ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ አተገባበር ስህተት ነዉ፡፡በተጨማሪም አመልካች የዉክልና ሥልጣን ለ2ኛ ተጠሪ ሲሰጥም ሆነ የቤት ሽያጭ ዉሉ ሲደረግ ለአካለመጠን እንዳልደረሰ 1ኛ ተጠሪ እያወቀ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ስልጣን እንዲሰጥ በማድረግ ሂደት ተሳትፎ ማድረጉ ስለተረጋገጠ አመልካች በቅን ልቦና የፈጸመዉ ዉል ካለመሆኑም በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪም የአመልካች ንብረት የሆነዉን ቤት በሽያጭ ያስተላለፈችዉ ለአመልካች ጥቅም ስለመሆኑም ሆነ ከቤቱ ሽያጭ የተገኘዉን ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም ያዋለች ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግንና ማስረጃን መሰረት ያደረገ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያለዉ ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት ካለ መርምሮ ማረም ብቻ ሆኖ እያለ በራሱ ማስረጃ ወደመመርመር ዉስጥ ገብቶ ከቤቱ ሽያጭ የተገኘዉ ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም መዋሉ ተረጋግጧል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ቢሆንም ግራ ቀኙ ወሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት የሚመለሱበትን አግባብ ሲወስን 1ኛ ተጠሪ ተጨማሪ ክፍል ቤቶችን ሰርቻለሁ ብሎ ካሰማዉ ክርክር አንጻር በመግለጽ ዉሳኔ አለመስጠቱ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 320926 ላይ በቀን 15/07/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 36019 ላይ በቀን 18/02/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 321147 ላይ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

3. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ በፍርዱ መግቢያ ላይ የተጠቀሰዉን መኖሪያ ቤት ለመሸጥ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ያገኘችዉን የዉክልና ስልጣን የማይጸና ነዉ በማለት በዚህ የዉክልና ሥልጣን 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በቀን 24/10/2007ዓ/ም የፈጸመችዉ የቤት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክብ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) እንድትከፍል የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡

4. 1ኛ ተጠሪ በተሸጠዉ ቤት ተጨማሪ ክፍሎችን ገንብቶ ከሆነ ክፍሎቹን ለመስራት ያወጣዉን ወጪ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1818 መሠረት አመልካች እንዲከፍለዉ ክስ በማቅረብ ዳኝነት የመጠየቅ መብት አለዉ ብለናል፡፡

5. በዚህ ችሎት የወጣ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡ለግራ ቀኙም የዉሳኔዉ ግልባጭ እንዲሰጣቸዉ ሲያመለክቱ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 188881

መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ማስሬ ገድፍ

ተጠሪ፡- አቶ ፈንታሁን ቸኮል

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ ባልተመዘገበ(ባልተረጋገጠ) ዉል የተሸጠዉ ባዶ ቦታ እንጂ ቤት አይደለም የሚል ክርክር ለማስረዳት መቅረብ ያለበትን ማስረጃ የሚመለከት ነዉ፡፡ጉዳዩ በተጀመረበት በአማራ ክልል ጣቁሳ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በምስራቅ አለባቸዉ ጌቴ፣በምዕራብ መንገድ፣በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ ሲሳይ ወልዴ የሚዋሰነዉንና በካርኒ ቁጥር 12116 ከተሰጣቸዉ 400 ካሬ ሜትር ቦታቸዉ ላይ ተጠሪ መብትና ጥቅም ሳይኖራቸዉ ገንዘብ ወስዶብኛል በሚል ምክንያት በ180 ካሬ ሜትር ቦታዬ ላይ ግንባታ እየገነባ ስለሆነ ቦታዬን እንዲለቅልኝ እና ግንባታዉን እንዲያቆምልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ በእማኝ ፊት በቀን 03/11/2006 ዓ.ም በተደረገ ዉል 9 x 20ሜትር ወይም 180 ካሬ ሜትር ቦታ 10 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት ያለበትን በብር 9,000.00(ዘጠኝ ሺህ ብር) አመልካች ሸጠዉልኝ እኔም በዚህ አግባብ በያዝኩት ላይ 54 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት በ2006 ዓ/ም ሰርቼ ልጆቼ ሥራ እየሰሩበት የሚገኝ ቦታ እንጂ በጉልበት የያዝኩት ባለመሆኑ አመልካች በሀሰት ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 94754 ላይ ግራ ቀኙ ያሰሙትን ክርክርና ምስክሮች እንዲሁም የቀረቡለትን የሰነድ ማስረጃዎች መርምሮ አመልካች ክሱ ሲሰማ ለተጠሪ ብር ቸግሮኝ ባዶ ቦታ ሸጬለታለሁ የሚል ክርክር ማሰማታቸዉን መሰረት በማድረግ ግራ ቀኝ የተሻሻጡበት ባዶ ቦታ ነዉ ወይስ ከቤት ጋር ? የሚል ጭብጥ በመያዝ በቀን 09/08/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የዉሉ ይዘት የሚያሳየዉ ከ10 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት ጋር የሚል ነዉ፡፡አመልካች በቃል ክርክር ጊዜ የሽያጭ ዉሉ መኖሩን አምነዉ ነገር ግን

የዉሉን ይዘት ክደዉ ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ያቀረቧቸዉ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች የዉሉ ይዘት ቤትና ቦታ እንደሆነ በበቂ ሁኔታ አስረድተዋል፡፡በአንጻሩ አመልካች ያቀረቧቸዉ ምስክሮችና ያያዙት ደረሰኝ በቦታዉ ላይ የምርት ባለቤት የነበሩ መሆኑን ነዉ፡፡የቦታዉ የምርት ባለቤት አመልካች የነበሩ ለመሆኑ ደግሞ ያልተካደ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አመልካች የዉሉ ይዘት ቤት ሳይሆን ቦታ ብቻ እንደሆነ በማስረጃ አላረጋገጡም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ የነበረ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 01-39775 ላይ በቀን 06/10/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-78624 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 02/04/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ግራ ቀኝ የሽያጭ ዉል የተዋዋሉ ለመሆኑ አልተካካዱም፡፡ግራ ቀኙ የተለያዩት በተሸጠዉ ነገር ምንነት ላይ ነዉ፡፡አመልካች ባዶ ቦታ ነዉ በማለት ሲከራከሩ ተጠሪ ደግሞ ቤትና ቦታ ነዉ በማለት በመከራከራቸዉ ነዉ፡፡ግራ ቀኙ በቀን 03/11/2006ዓ ዓ.ም ባደረጉት የሽያጭ ዉል ላይ ደግሞ አመልካች ቦታዉን 10 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት እንደያዙ ለተጠሪ በብር 9,000.00 የሸጡ ለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡የዚህን ዉል መደረግ አመልካች እየካዱ ያሉት የተሸጠዉ መሬት ብቻ ነዉ በሚል ይዘቱን ብቻ በመሆኑ ይህ ክርክራቸዉ ሙሉ ለሙሉ ከተጠሪ ጋር የሽያጭ ዉሉን ክደዉታል ተብሎ የተደረገዉ የሽያጭ ዉል ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 አኳያ መመዝገብ አለመመዝገቡ በጭብጥነት ተይዞ ሊጣራ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 29/04/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት፡- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 ላይ መሬት መሸጥ መለወጥ እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ ለተጠሪ የተሸጠዉ በምሪት ያገኘሁትን ባዶ መሬት መሆኑን በምስክሮች ተመስክሮ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሉ ፈራሽ ነዉ በማለት ተጠሪ የያዙብኝን 180 ካሬ ሜትር ቦታ እንዲለቁልኝ አለመወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ የሥር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮ ተጠሪ ይዞታዬን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት በመጠየቅ ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች አንጻር ተሸጠ የተባለዉ መሬት ቤት ያለበት ነዉ በሚል የአመልካች ክስ ዉድቅ የተደረገበት አግባብ እንዲመረመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ መጥሪያ ለተጠሪ ቢደርሳቸዉም ተጠሪ መጥሪያ ስለመቀበላቸዉ ማረጋገጫ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸዉን አመልካች በመሐላ ቃል በማረጋገጣቸዉና ተጠሪ ቀርበዉም ባለመከራከራቸዉ ተጠሪ መልስ በማቅረብ ለመከራከር እንዳልፈለጉ ተቆጥሮ በሌሉበት ተመርምሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የሽያጭ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበ(የተረጋገጠ) ባልሆነበት የሽያጭ ዉል መደረጉን አመልካች አምነዉ ይዘቱን ብቻ ስለካዱ እንደተካደ አይቆጠርም በሚል ባዶ ቦታ ለመሸጥ የተደረገ ሳይሆን ቤት ለመሸጥ የተደረገ ዉል ነዉ በሚል ክሱ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ለተጠሪ የሸጥኩት በምሪት ያገኘሁትን ባዶ ቦታ እንጂ ቤት ስላልሆነ እየፈጸሙ ያሉት ግንባታ ቆሞ የያዙብኝን 180 ካሬ ሜትር እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ በቀን 03/11/2006 ዓ.ም በተደረገ ዉል 180 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተሰራ 10 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት ያለበትን በብር 9,000.00(ዘጠኝ ሺህ ብር) አመልካች በምስክሮች ፊት ሸጠዉልኝ እኔም በዚህ አግባብ በያዝኩት ላይ 54 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት በ2006ዓ/ም ሰርቼ እየተጠቀምኩ እገኛለሁ፤ የገዛሁት ባዶ ቦታ አለመሆኑን የዉሉ ይዘት ያሳያል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንደሚታወቀዉ በአገራችን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሕዝቡ ዘንድ ካለዉ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የተነሳ የፍትሐ ብሔር ሕጋችንና የፍትሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደሩ በአጠቃላይ ለዜጎች የማይንቀሳቀስ የንብረት መብት ልዩ ጥበቃ ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ከዘረጋዉ የጥበቃ ሥርዓት ዉስጥ አንዱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ የተለያዩ አናቅጽ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረጉ ዉሎች መከተል ያለባቸዉ ፎርማሊቲዎች እና ስለ ምዝገባ የተደነገገዉ ነዉ፡፡ (አንቀጽ 1553-1646 እንዲሁም 1723፣ 2878 እና 3052 ይመለከቷል)፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የየራሳቸዉ የሆኑ ዓላማዎች ያላቸዉ ቢሆንም፤ አጠቃላይ ዓላማቸዉ ግን ለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ጥበቃ በመስጠት እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ባለይዞታዉ መብቱን ሲያገኝ ወይም ንብረቱ በሆነ ምክንያት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን በሚያስተላልፍበት ወቅት የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ መንግስታዊ አካል ካልተመዘገበ ሕግ ፊት የሚጸና መብት እንዳይኖረዉ በማድረግ ዜጎች በዚህ ግዙፍነት ባለዉ ንብረት ላይ ያላቸዉን መብት ከፍላጎታቸዉ ዉጪ በሆነ መንገድ እንዳያጡ ጥበቃ ለመስጠት፤ ብሎም ንብረቱ ወይም ንብረቱን የሚመለከቱ መብቶች በዉል ሊተላለፉ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑንም በማጣራት የዉሉን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ ጭምር ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ከሚከናወኑት ሕጋዉያን ተግባራት ጋር በተያያዘ ምዝገባ ወይም ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ እንዲረጋገጥ የግድ ከሚልባቸዉ ዉስጥም አንዱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1723(1) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ሲሆን፣ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስተላለፍ የሚደረጉ ዉሎች በጽሑፍና ዉል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መሆን አለበት፡፡ ሕግ አዉጪዉ ይህ እንዲሆን የፈለገበት ምክንያትም ዉሉ በተዋዋዮች መካከል ስለመደረጉ

ለማረጋገጥ (certainty in transactions) ስለመሆኑ በዙሪያዉ ከተፃፉት አንዳንድ ጽሑፎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፤ ይህ ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ዉል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ ወስኗል።

በሌላ በኩል ተከራካሪ ወገኖች ዉሉ መደረጉን ተማምነዉ ነገር ግን የዉሉን ይዘት አስመልክቶ የተለያዩ መከራከሪያዎችን ሊያቀርቡ ይችላሉ። በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 2005 በጽሑፍ ሰነዱ ላይ ስለሚገኘዉ የስምምነት ቃል እንዲሁም ስለተፃፈዉ ቀን በተፈራራሚዎቹ መካከል ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ እንደሆነ ይደነግጋል። ይሁንና ይህ ሊሆን የሚችለዉ እንደ ዉለታዉ ዓይነት ዉሉ የጽሑፍ ዉል አደራረግ ሥርዓትን(ፎርማሊቲን) አስመልክቶ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1678/ሐ እና 1719/1 መሠረት አስፈላጊ የሆነዉን የዉል አደራረግ ሥርዓት አሟልቶ የያዘ ስለመሆኑ ከግምት ዉስጥ ሊገባ ይገባል። ከላይ እንደተመለከተዉ የዉል አደራረግ ሥርዓት በተለየ አኳኋን እንዲደረግ በሕግ ከተመለከተዉ ዉስጥ አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግ ዉል በጽሑፍ ሆኖ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ መረጋገጥ እንዳለበት የሚደነግገዉ የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1723/1 ድንጋጌ ነዉ። በመሆኑም የዉሉን ይዘት አስመልክቶ ማለትም ዉሉ የተደረገዉ መቼ ነዉ? የሽያጭ ዉል ከሆነ በምን ያህል ዋጋ ነዉ የተደረገዉ? ለዉሉ ምክንያት የሆነዉ ምን ዓይነት ንብረት ነዉ? የትስ የሚገኝ ነዉ? የሚሉት እና መሰል የይዘት ክርክሮች የተነሱ እንደሆነ ይህን ለማጣራት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዓይነትም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ በጽሑፍ ሆኖ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት የተደረገ ዉል ሊሆን ይገባል። ይህን አስመልክቶም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 78398 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መደረጉን እና የሽያጭ ዉሉን ይዘት አስመልክቶ ተክዶ ክርክር በቀረበ ጊዜ እንዲህ አይነት ክርክር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዉሉ ዉል ለማማዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተደርጎ መመዝገቡን ወይም መረጋገጡን (Authentication) የሚያሳይ ሊሆን የሚገባዉ መሆኑን እና እንደዚህ ዓይነት ክርክር ምስክር ወይም ሌላ ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳት እንደማይቻል መገንዘብ ይገባል።

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች የሸጥኩት ቤት ሳይሆን ባዶ ቦታ ነዉ በሚል እስከተከራከሩ ድረስ ተጠሪ ዉሉ መደረጉንና የዉሉም ይዘት ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን የሚመለከት መሆኑን የሚያሳይ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1723/1 መሠረት ዉል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት የተረጋገጠ ወይም የተመዘገበ ዉል በማስረጃነት በማቅረብ አለማስረዳታቸዉን የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ያሳያሉ። ዉሉ ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ስለመሆኑ ተጠሪ ከላይ በተመለከተዉ አግባብ ያቀረቡት ማስረጃ ከሌለ የዉሉ ይዘት ባዶ ቦታን ሳይሆን ቤትን የሚመለከት

ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አይቻልም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባቸዉ ዉሉን ለማስረዳት የግራ ቀኙን ምስክሮች እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ የተሸጠዉ ባዶ ቦታ ሳይሆን ቤት ስለሆነ ዉሉ የጸና ነዉ በማለት መወሰናቸዉ የጉዳዩን ልዩ ባህሪ መሠረት ያላደረገና አከራካሪንዉን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉን ማስረጃ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ሌላዉ መታየት የሚገባዉ ነጥብ ተጠሪ በቦታዉ ላይ ቤት ገንብቻለሁ በማለት በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቦታ ለመኖሪያ ቤት መስሪያት የተሰጠ ቦታ መሆኑን ወይም ደግሞ ቦታ የገጠር የእርሻ መሬት አለመሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ቤትና ቦታዉን ይዘን በቦታዉ ላይ ገንብተናል ለሚሉት ቤት ምክንያት የሆነዉ ዉል ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ ይዞታዉን ይዞ የመቀጠል መብት የላቸዉም፡፡ የዉል መፍረስ በዉል የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች እንዲቋረጡ ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸዉ ማድረግን የሚያስከትል ስለመሆኑ በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1807/ሀ እና 1815 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ዉል ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ተዋዋዮች በተቻለ መጠን ዉሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ እና ዉሉን ለመፈጸም የተሠራ ሁሉ ቀሪ ሆኖ በማናቸዉም አኳኋን ዉጤት እንደሌለዉ የሚደነግገዉ የሕጉ አንቀጽ 1815 ድንጋጌ በተለይ ሲታዩ በዉል መሠረት አንዱ ለሌላዉ የፈጸመዉ ተግባር ካለ ቀሪ ተደርጎ ግራ ቀኝ ከዉሉ በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ግዴታ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሉ አንድን ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ከሆነ እና ዉሉ የማይረጋበት ምክንያት መኖሩ ከተረጋገጠ ዉጤቱ የሚሆነዉ ንብረቱን ገዝቶ በዉሉ መሠረት የተረከበዉ ተዋዋይ ንብረቱን ለሻጩ መልሶ እንዲያስረክብ፣ ሻጩም ደግሞ በዉሉ መሠረት የተቀበለዉ ገንዘብ ካለ ገንዘቡን ለገዥዉ እንዲመልስ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህም ማለት ግራ ቀኝ የተቀባበሉትን ነገር ባሉበት ሁኔታ አንዱ ለሌላዉ እንዲመልስ ከማድረግ ዉጪ ሻጩ በዉሉ መሠረት ከተቀበለዉ ገንዘብ በላይ ገዥዉም ደግሞ ከተረከበዉ ንብረት በላይ አንዱ ለሌላዉ ለመመለስ የማይገደዱ መሆኑን ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1815 ስር የተደነገገዉ ዉሉ በመፍረሱ ምክንያት ግራ ቀኝ የሚኖራቸዉ መብትና ግዴታ ሲሆን፣ ተጠሪ በቦታዉ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ የገነቡት ቤት በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ አይሆንም፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1818 ድንጋጌ መሠረት ዉሉ ከመፍረሱ የተነሳ ንብረትን የመመለስ ግዴታ ያለበት ሰዉ ንብረቱን ለዉጦ ወይም በዚሁ ላይ ወጪ አድርጎ እንደሆነ ከዚህ መለዋወጥ ወይም ወጪ የተነሳ ያሉትን መብቶች በከዉል ዉጪ ኃላፊነት ድንጋጌዎች መሠረት መጠየቅ ይችላል፡፡ እንደሚታወቀዉ በዉል አንድ ሰዉ አንድን ንብረት በእጁ ካስገባ በኋላ በእራሱ ወጪ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ያደረገ እንደሆነ በእራሱ ወጪ ተጨማሪ ነገር የሰራዉ ተዋዋይ ንብረቱን መልሶ ሲያስረክብ ከነማሻሻያዎቹ ለሌላኛዉ ተዋዋይ ሊያስረክብ የሚችልበት

ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህ መሆኑ በአንድ በኩል ንብረቱ የተመለሰለት ሰዉ ያላግባብ እንዲበለጽግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ንብረቱን የማስረከብ ግዴታ ያለበት ወገን ያላግባብ ተጎጂ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1818 ድንጋጌም ለእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች መፍትሔ የመስጠት ዓላማ ያደረገ በመሆኑ የድንጋጌዉ አፈፃፀምም ከላይ በተመለከተዉ ምክንያት ሊፈጠር የሚችለዉን ተወዳዳሪ ጥቅም (computing interests) ማስታረቅ በሚያስችል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ በእጃቸዉ በገባዉ ይዞታ ላይ የሰሩትን ተጨማሪ ግንባታ አስመልክቶ ሁለት አማራጮች ይኖራቸዋል፡፡ አንደኛዉ አማራጭ በይዞታዉ ላይ በእራሳቸዉ ወጪ የሰሩትን ቤት አፍርሰዉ ባዶ ቦታዉን ብቻ ለአመልካች ማስረከብ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ በተጨማሪነት በቦታዉ ላይ የተሰራዉን ቤት እዚያዉ በመተዉ ቤቱ የተሰራበትን ወጪ አመልካች እንዲከፍሉ መጠየቅ ነዉ፡፡ ተጠሪ ሁለተኛዉን አማራጭ ከመረጡ ይህ ጥያቄአቸዉ የሚስተናገደዉ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1818 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ይዞታ የያዙት በሕግ ፊት በሚፀና አኳኋን በተደረገ ዉል መሆኑን ባላስረዱበት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሉ የጸና ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሉ ፈርሶ ተጠሪ አከራካሪዉን ይዞታ ለአመልካች ሊመለስ ይገባል ብለናል፡፡እንዲሁም ተጠሪ በቦታዉ ላይ የሰሩት ቤት ካለ ቤቱን ለመገንባት ያወጡትን ወጪ (Book Value) አመልካች እንዲከፍሏቸዉ የገንዘብ መጠኑን (ግምቱን) ጠቅሰዉ ክስ በማቅረብ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የጣቁሳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 94754 ላይ በቀን 09/08/2010ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ፣የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-39775 ላይ በቀን 06/10/2010 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-78624 ላይ በቀን 02/04/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል በቀን 03/11/2006ዓ/ም የተደረገ ዉል ፈርሷል፡፡ ተጠሪ ከላይ አዋሳኙ የተጠቀሰዉን 9 x 20ሜትር የሆነ ወይም 180 ካሬ ሜትር ቦታ ለአመልካች እንዲያስረክቡ ተወሰኗል፡፡

3. ተጠሪ በቦታዉ ላይ የሰሩት ቤት ካለ ቤቱን ለመስራት ያወጡትን ወጪ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1818 መሠረት አመልካች እንዲከፍሏቸዉ ክስ በማቅረብ ዳኝነት የመጠየቅ መብት አላቸዉ ብለናል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 207885

ጥር 26 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ መልካምአየሁ መንገሻ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አለም በርሄ

2. ወጣት አቤል ታደለ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች በእኔ ገንዘብ ለእኔ ጥቅም የተገዛ ቤት ነዉ በማለት በተጠሪዎች ስም የተመዘገበ ቤት አስለቅቀዉ ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት እና የ2ኛ ተጠሪ አባት እንዲሁም የአመልካች ወንድም በሆኑት አቶ ታደለ መስፍን ስም ቤት ለመግዛት ፈልጌ በቀድሞ ወረዳ 22 በአሁኑ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02 ወይም ወረዳ 02 የካርታ ቁጥር 02/35/8608/1237/01 የተመዘገበ የቦታዉ ስፋት 263 ካሬ ሜትር የወ/ሮ ቀነኔ ዳርጌ ንብረት የሆነዉን ቤት ቅድመ ክፍያ ብር 385,000.00 በባንክ ሂሳባቸዉ በወንድሜ ስም ገቢ አድርጌያለሁ፡፡ብር 578,600.00 ለሻጭ ወኪል በመክፈል በተለምዶ የመንደር ዉል በሚባለዉ በሟች ወንድሜ ታደለ መስፍን ስም የቤት ግዥ ፈጽሜያለሁ፡፡ለስም ማዛወሪያና ለተያያዥ ወጪዎች ብር 100,000.00 ከፍያለሁ፡፡አመልካች በዜግነት ካናዳዊ ስለሆንኩ የመቆያ ጊዜዬ ስለተጠናቀቀ ቀሪዉን ሟች ወንድሜ እንዲጨርሱ ዉክልና በመስጠት ተከራይቶ የሚኖርበትን ቤት ለቆ በዚህ ቤት ዉስጥ በጠባቂነት እንዲቀመጥበትም አድርጌያለሁ፡፡ከዚህ በኋላ ሟች ቤቱን በብር 200,000.00 እንደተገዛ በማስመሰል በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እንዲመዘገብ በማድረግ ህይወታቸዉ እስካለፈበት መስከረም 2003 ዓ/ም ድረስ በመኖሪያነት ቀሪዎቹን ክፍሎች ጨምረዉ ሲገለገሉበት ነበር፡፡ ተጠሪዎች ቤቱን በአደራ መልክ የተቀመጡበት መሆኑን እያወቁ የቤቱን ስመ ሀብት በስማቸዉ አዛዉረዉ አስመዝግበዋል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች ምንም ገንዘብ ያላወጡበትንና ያላፈሩትን

ከሕግ ዉጪ አለአግባብ ለመበልጸግ ይዘዉ አለቅም ስላሉ ቤቱን ለቀዉ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የ2ኛ ተጠሪ አባት ሟች አቶ ታደለ መስፍን ከቤቱ ሕጋዊ ባለቤት በቀን 13/04/2003 ዓ/ም በሕጋዊ መንገድ ግዥ ፈጽመዉ ያገኙትና ስመ ሀብቱም በስማቸዉ ተዛዉሮ ይገኝ የነበረ ነዉ፡፡አቶ ታደለ መስፍን ከሞቱ በኋላም ዉርሱ ተጣርቶ ስመ ሀብቱ ወደ ተጠሪዎች ስም ዞሯል፡፡አመልካች ሟች በአደራ የቤቱ ጠባቂ ነበሩ በማለት የገለጹት የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ሟች የወሰዱት ገንዘብ ካለ የብድር ግንኙነት መኖሩን መሰረት በማድረግ ከሚጠይቁ በስተቀር ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ስለሌለዉ ክሱ ዉደቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 210270 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 23/07/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች በክሳቸዉ ላይ ቤቱን በአደራ በጠባቂነት እንዲይዙ ሰጥቻቸዋለሁ በማለት የገለጹ ቢሆንም ይህ ሊሆን የሚችለዉ በቤቱ ላይ ተጠሪዎች መብት እንደሌላቸዉ ሲያረጋግጡ ነዉ፡፡ቤቱን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቀን 13/04/2003ዓ/ም በተደረገ ዉል ገዥ በመሆን ከሻጮች ጋር የተዋዋሉት ሟች አቶ ታደለ መስፍን ናቸዉ፡፡ አመልካች ለቤቱ መግዣ የተከፈለዉ ገንዘብ የእኔ ነዉ ቢሉም ይህንን የሚገልጽ ፍሬ ነገር በዉሉ ዉስጥ አልተመለከተም፡፡አቶ ታደለ መስፍን ዉሉን ያደረጉት በራሳቸዉ መብት እንጂ በዉክልና አይደለም፡፡በዚሁ እለት አቶ ታደለ መስፍን ከሻጩ ጋር የመንደር ዉል ያደረጉት በራሳቸዉ ስም ነዉ፡፡ይህ ባይሆን እንኳ የመንደር ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1720/1 መሰረት እንደረቂቅ የሚቆጠር ነዉ፡፡በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገዉ ዉል መሰረት ሆኖ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አቶ ታደለ ስም ዞሮ ተመዝግቧል፡፡አቶ ታደለ ከሞቱ በኋላ ወደ ተጠሪዎች ስም ተላልፎአል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት በቤቱ ላይ የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ያላቸዉ ተጠሪዎች ሲሆኑ አመጣጡም በሕጋዊ ዉል ላይ የተመሰረተና ዉሉም እስካሁን ስላልፈረሰ ባለቤት ስለመሆናቸዉ የሚወሰደዉ ግምት አልተስተባበለም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 እና 1952/1 መሰረት የሽያጭ ዉሉ መብትና ግዴታ የሚፈጥረዉ በተዋዋዮች መካከል ስለሆነ ተዋዋይ ያልሆኑት አመልካች በዉሉ ላይ ለእሳቸዉ ጥቅም የተደረገ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር ባለመኖሩ ዉሉ የሚሰጣቸዉ መብት የለም፡፡አመልካች ይህንን ዉል አላስፈረሱም፡፡አመልካች ለቤቱ መግዣ ወይም ለእኔ ግዛልኝ ብለዉ ገንዘብ ሰጥተዉ ከሆነ ገንዘቡን ከሚጠይቁ በስተቀር በዉሉ ሕጋዊነት ላይ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡ተጠሪዎችም ቤቱን በሕጋዊ መንገድ መያዛቸዉን አያስቀረዉም፡፡ተጠሪዎች ቤቱ በሕጋዊ መንገድ በቤተሰብ እና በዉርስ ሕግጋት መሰረት ተላልፎላቸዉ ስለያዙት በአደራ ይዘዋል ወይም አለአግባብ በልጽገዋል ለማለት እንደማይቻል ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1162 እና 2779 ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ቤት የያዙት የባለሀብትነት መብት በሕጋዊ መንገድ ተላልፎላቸዉ ስለሆነ ለአመልካች ለቀዉ ሊያስረክቡ እና በስማቸዉ የተመዘገበዉ ሊሰረዝ አይገባም

በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡እንዲሁም አመልካች ለሚች አቶ ታደለ መስፍን የሰጡት ገንዘብ ካለ የሚመለከተዉን ሰዉ ከሰዉ የመጠየቅ መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 200412 ላይ በቀን 18/06/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 18/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-በስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ጭብጥ ተይዟል በሚል በዉሳኔዉ የገለጸዉ ፍጹም ሀሰት እና የአመልካችን ፍትህ የማግኘት እና በእኩል የመደመጥ መብት ያላከበረ ስለሆነ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25 እና 37 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት ክርክሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት አልመራም፡፡አመልካች ያቀረብኩትን 20 ገጽ የሰነድ ማስረጃዎች እና የኤሌክትሮኒክስ ዲጂታል ማስረጃዎችን በአንድነት ሳይመረምርና ምስክሮች ቃላቸዉን ሳይሰጡ እንዲሁም ተገቢዉን ጭብጥ ሳይመረምር የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡አመልካች ያቀረብኩት ክስ በቅን ልቦና ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከሕግ አግባብ ዉጭ ያቀረብኩት ክስ ዉድቅ መደረጉ ሳያንስ ለተጠሪዎች ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ጠብቆ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕጉን መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበ ነዉ፡፡ስለሆነም የተፈጸመዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ታርሞና የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ተሽሮ ተገቢዉ ጭብጥ ተመስርቶ የአመልካች የመሰማት መብት ተጠብቆ፣ በአመልካች ማስረጃዎች ተጣርቶና ተመርምሮ እንዲወሰን ጉዳዩ ለስር ፍርድ ቤት ሊመለስ ይገባል በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሳይሰማ የወሰነበትን አግባብ ከመሠረታዊ የክርክር አመራር መርሆዎች አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 25/02/2014 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ያቀረቡት ክስ የቤት ባለቤትነትን የመፋለም ነዉ፡፡አመልካች በክሳቸዉ መሰረት እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1206 መሰረት ቤቱን በእጃቸዉ ይዘዉ ሲያዙበት እንደነበር እና በቤቱ ላይ ከተጠሪዎች የበለጠ መብትና ጥቅም እንዳላቸዉ የሚያሳይ ማስረጃ በማቅረብ አላስዱም፡፡ አመልካች ቤቱን በስሜ ግዛልኝ በማለት ከሚች ጋር ያደረጉት ዉል የለም፤ማስረጃ ሆኖም አልቀረበም፡፡ቤቱን በሚች አቶ ታደለ መስፍን ስም የገዙ ስለመሆኑ የሚያሳይ አንድም የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ተጠሪዎች ቤቱ በስማችን ተመዝግቦ የሚገኝ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አቅርበን አስረድተናል፡፡ የአመልካች ጠበቃ የኤሌክትሮኒክስ እና የሰነድ ማስረጃ ስላለኝ አቀርባለሁ እያሉ በችሎት ሁልጊዜ በቃል ከመናገር ባለፈ ዉሳኔ እስከተሰጠበት እለት ድረስ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ማስረጃ አቅርበዉ ባላስረዱበት ሁኔታ የስር ፍርድ ማስረጃ ካለ ለወደፊት ይቅረብ ብሎ ትእዛዝ ለመስጠት የሚችልበት የሕግ አግባብ ሳይኖር

እንደተከለከሉ አስመስለዉ ያቀረቡት ክርክር በሕግ ተቀባይነት የለዉም፡፡የስር ፍርድ ቤት የክርክር አመራርም ሆነ የተሰጠዉ ዉሳኔ ከጭብጥ አመሰራረት አኳያም ሆነ ከማስረጃ ምዘና አንጻር የአመልካችን ፍትህ የማግኘት መብት ታልፎ የተሰጠ ነዉ ሊባል የሚችል ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሁም ምስክሮች ያልተሰማዉ የቀረበዉ ማስረጃ የመፋለም ክስ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት በቂ ሆኖ ስለተገኘ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ተጠሪዎች እንዲለቁላቸዉ ለማስወሰን ያቀረቡትን ክስ ዉድቅ በማድረግ በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የአመልካች ክስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት በሰጧቸዉ ገንዘብ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና የ2ኛ ተጠሪ ወላጅ አባት ሟች አቶ ታደለ መስፍን በስሜ ለእኔ ጥቅም የገዙልኝ ሆኖ ሳለ በመጀመሪያ በሟች ስም በኋላም በተጠሪዎች ስም ያለአግባብ ስመ ሀብቱ ሊመዘገብ ችሏል በማለት የቤት ባለሃብት ስለሆንኩ ተጠሪዎች በአደራ በጠባቂነት የያዙትን ቤት ለቀዉ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁበት ነዉ፡፡ተጠሪዎች ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ሟች በስማቸዉ የገዙትና በስማቸዉ ተመዝግቦ የነበረና በኋላም ሲሞቱ በሕግ አግባብ ወደ ተጠሪዎች ስም ዞሮ የተመዘገበ እንጂ አመልካች በክሳቸዉ እንደገለጹት በአመልካች ገንዘብ የተገዛና በአደራ የያዝነዉ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የወሰነዉ ቤቱ በአመልካች ገንዘብ ለአመልካች ጥቅም በሟች አቶ ታደለ መስፍን ስም የተገዛ ስለመሆኑ እና አመልካች ከተጠሪዎች የተሻለ በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያላቸዉ ስለመሆኑ ከተጠሪዎች የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራትና እና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት ተከትሎ ሊሆን ይገባል፡፡ይህም ያስፈለገበት ምክንያት ክርክሮች ፍትሐዊ በሆነ አግባብ እንዲታዩ ያደርጋል ተብሎ ታምኖበት በተዘረጋዉ ሥነ-ሥርዓት አግባብ ታይተዉ የጊዜ የገንዘብና የሰዉ ሀብት ብክነት በሚቀንስ አግባብ በቅልጥፍና ታይተዉ ፍትሐዊ እልባት እንዲያገኙ ሕጉ ያቀደዉ ዓላማ እንዲሳካ ለማድረግና የሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረታዊ ግብ የሆነዉን ከሥረ ነገር ሕጎች (Substantuve Laws) ወይም ከዉል የተገኙ መብትና ግዴታዎችን ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ነዉ፡፡በሥነ ሥርዓት ሕጉ ከተዘረጉ ሥነ ሥርዓቶች መካከል አንዱ ስለ ጭብጥ አመሰራርት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246-248 እና 251-252

የተደነገገዉ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ጭብጥ መመስረት የሚያስፈልግበት ምክንያት ግራ ቀኙ በተከራከሩበት ነጥብ ላይ ብቻ ተመስርቶ አከራካሪዉን ጭብጥ ከተገቢዉ ማስረጃ ወይም ሕግ አንጻር መርምሮ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ እና ግብ በሚያሳካ መልኩ ፍትሐዊ ዉሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ጭብጥ የሚመሰረተዉ ደግሞ ክሱን የሚሰማዉ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ከሆነ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ ክሱንና ቀርቦም ከሆነ መከላከያ መልሱን መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ተከራካሪዎችን ከመረመረ በኋላ የክሱን ይዘት፣መከላከያ መልሱን፣ በተከራካሪ ወገኖች የቀረበዉን የጽሁፍ ማስረጃ፣ ግራ ቀኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 ተመርምረዉ የሰጡትን መልስ እና ሕግን መሰረት በማድረግ እንደሆነ በሕጉ በቁጥር 248 ላይ የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡እንዲሁም ጭብጥ የሚመሰረተዉ በተከራካሪ ወገን የተካደዉን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ክርክር መሰረት በማድረግ ሲሆን ዋነኛ ዓላማዉም ለጉዳዩ ትክክለኛ ዉሳኔ መስጠት ይቻል ዘንድ ነዉ፡፡(የሕጉ ቁጥር 246/1 እና 247 ይመለከቷል፡፡)

እንዲሁም አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ሰዉ ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በማስረጃ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከቷል)፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር ማስረጃ የሚቀርበዉ ተከራካሪ ወገን በተመቸዉ ጊዜ ሁሉ ሳይሆን በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥነ ሥርዓት አግባብ ነዉ፡፡ይኸዉም ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ የሆነ ወገን አለኝ የሚለዉንና በእጁ የሚገኘዉን ማስረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 223/1 እና 234 መሰረት ዘርዝረዉና ምን እንደሚያስረዳላቸዉ ገልጸዉ እንዲሁም በእጃቸዉ የማይገኘዉንና በራሳቸዉ ማቅረብ የማይችሉትን ማስረጃዎች የሚገኝበትን ቦታ ገለጸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 145 መሰረት በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ እንዲቀርብላቸዉ መጠየቅና ከክሱ እና ከመከላከያ መልሳቸዉ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡እንዲሁም በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 137 መሰረት አስቀድሞ ያልቀረበ ማስረጃ ክሱ ከመሰማቱ በፊት ክስ እስከሚሰማበት ቀን ድረስ ማቅረብ እንደሚቻል፤ እንዲሁም በከባድና በበቂ ምክንያት አስቀድሞ ማቅረብ ያልተቻለዉን ማስረጃ በፍርድ ቤቱ ፈቃደኝነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ ማቅረብ እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ከዚህ ዉጭ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136፣249፣ 264(1 እና 2) እና 345 በደነገገዉ አግባብ ፍርድ ቤቱ አንጻራዊ እዉነታ የመፈለግ ኃላፊነቱን ለመወጣት ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ያስችለዉ ዘንድ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማንኛዉም ጊዜ ማስረጃ አስቀርቦ ወይም ምስክሮች ጠርቶ መስማት ከሚችል በስተቀር በተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ በዘፈቀደ በማንኛዉም ጊዜ የሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት የለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች የስር ፍርድ ቤት ጭብጥ ሳይመሰርት ጭብጥ እንደመሰረተ አድርጎ የመሰማትና ፍትሕ የማግኘት መብቴን በሚጎዳ አኳኋን ዉሳኔ ሰጥቷል በማለት አጥብቀዉ

ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ በፍትሐ ብሔር ፍትሕ አስተዳደር የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት የሚከበረዉ ክስ የቀረበበት ተከሳሽ መጥሪያ በአግባቡ ደርሶት አለኝ የሚለዉን መልስ በጽሁፍ በማስረጃ አስደግፎ እንዲያቀርብ በቂ ጊዜ በመስጠት ቀጥሎም በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት አግባብ ክርክሩን በዳኛዉ መሪነት እንዲያሰማና ማስረጃዉ እንዲመረመርለት ወይም እንደየክርክሩ አይነት ምስክሮቹን አቅርቦ በማሰማት ክርክሩን የሚያስረዳበትን አግባብ በማመቻቸት ነዉ፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ክሱን የመሰረቱት የቤቱ ባለቤት መሆናቸዉን ገልጸዉ ተጠሪዎች በቤቱ እየኖሩበት የሚገኙት በጠባቂነት በአደራ በመያዝ እንደሆነና በመጀመሪያ ሟች አቶ ታደለ መስፍን ለለአግባብ በስማቸዉ እንዳስመዘገቡት በኋላም አቶ ታደለ መስፍን ሲሞቱ የሟቹ ባለቤት በሆኑት በ1ኛ ተጠሪና በሟቹ ልጅ 2ኛ ተጠሪ ስም አለአግባብ አዛዉረዉ አስመዝግበዋልና ይልቀቁልኝ በማለት በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1206 ስር የተደነገገዉን የመፋለም ክስ (petitory action) የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪዎች ደግሞ ቤቱን በዉል ገዝተዉ በስማቸዉ ያስመዘገቡት ሟች አቶ ታደለ መስፍን እንደሆኑና የእሳቸዉን ሞት ተከትሎ በሕግ አግባብ ተላልፎላቸዉ የቤቱ ስመ ሀብት በስማቸዉ ተመዝግቦ እንደሚገኝ እና በክሱ ላይ እንደተገለጸዉ በአደራ የያዙት እንዳልሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በተጠሪዎች ላይ የመሰረቱት ክስ ባለቤትነትን መፋለምን የሚመለከት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንን የክሱን ሥረ ነገር እና የተጠሪዎችን ክርክር መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 በሚያዘዉ መሰረት ተከራካሪዎችን መመርመሩን ወይም የመጀመሪያዉን የክስ አሰማም ሥነ ሥርዓት ማከናወኑን እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ግራ ቀኙን መርምሮ የሰማዉንና የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክርና ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ያስችሉኛል ያላቸዉን ጭብጦች መመሰርቱን ከዉሳኔዉ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ የያዛቸዉ ጭብጦችም "ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ቤት ለቀዉ ለአመልካች ለማስረከብ ይገደዳሉ ወይስ አይገደዱም? ይገደዳሉ ከተባለ ስመ ሃብቱ በአመልካች ስም ዞሮ ሊመዘገብ ይገባል ወይስ አይገባም?" የሚሉ ናቸዉ፡፡ እነዚህ ጭብጦች የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ አመልካች ላቀረቡት የመፋለም ክስ እና በተጠሪዎች በቀረበ ክርክር ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ስለሆኑ ጉድለት ያለባቸዉ እንዳልሆኑ ተገንዝበናል፡፡ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ክስ በመስማት ለጉዳዩ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉትን ተገቢ ጭብጦች የመሰረተ በመሆኑ ከክስ አሰማምና ከጭብጥ አመሰራረት ጋር በተያያዘ የአመልካችን የእኩልነት ፣የመሰማትና ፍትህ የማግኘት መብት በሚነካ አኳኋን የተፈጸመ የክርክር አመራር ጉድለት ስለሌለ አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነዉም፡፡

በተጨማሪም አመልካች ክሳቸዉን በሕግ ተቀባይነት ያለዉንና ተገቢዉን ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በሚል በስር ፍርድ ቤት በተደረሰበት ድምዳሜ የተፈጸመ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ አመልካች ንብረት የሚገኝበትን ሕጋዊ መንገድ ተከትለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ባለሀብት

መሆናቸዉን ተገቢዉንና ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1184 እና 1185 ስር እንደተመለከተዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆን የሚቻለዉ በሕግ ወይም በዉል ወይም በኑዛዜ (በሕጋዉያን ተግባሮች/Juridical acts) መሰረት ነዉ፡፡ በዉል ወይም በኑዛዜ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነትን ለማስተላለፍ ወይም በዉል ወይም በኑዛዜ መሰረት ባለሀብት መሆን የሚቻለዉ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ማስመዝገብ ሲቻል መሆኑን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1185 እና ከቁጥር 1553 እስከ 1646 ድረስ ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡እንዲሁም የአንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለሃብትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በስሙ በአስተዳደር አካል የተሰጠዉ ሰዉ የዛ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት ነዉ ተብሎ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195/1 ስር ተደንግጓል፡፡ይህ የሕግ ግምት ሊስተባበል የሚችል ግምት እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195/2 ላይ ተመልክቷል፡፡

ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ስናይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት አስቀድሞ በሕግ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አዋዋይ ፊት ባልተደረገ(በተለምዶ የመንደር ዉል በሚባለዉ) ሟች አቶ ታደለ መስፍን ስም የተገዛ በኋላም በቀን 13/04/2003ዓ/ም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ዘንድ በተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል ሟች አቶ ታደለ መስፍን በስማቸዉ የገዙት ቤት እንደሆነ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት ከቀረቡ የዉል ሰነዶች ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አመልካች ቤቱን በራሴ ገንዘብ የተገዛና በሟች ወንድሜ ስም መግዛት ስለፈለግሁ የሟቹ ስም በገዥነት በዉሉ ላይ ሊጠቀስ ችሏል በማለት ተከራክረዋል፡፡በመርህ ደረጃ ዉል መብት እና ግዴታ የሚፈጥረዉ ዉሉን ባቋቋሙ ሰዎች መካከል ነዉ፡፡ በልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1953 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ በተመለከተዉ አግባብ አንድ ሰዉ በዉሉ ላይ የተመለከተዉን መብት ሌላ ሰዉ እንዲጠቀምበትና ከዉሉ የሚመነጨዉንም ግዴታ እንዲወጣ ለሌላ ሰዉ ጥቅም በሚል ዉል ሊዋዋል ይችላል፡፡በዚህ አግባብ አንድን ዉል የተዋዋለ ሰዉ በዉሉ የመጠቀሱ ጉዳይ የእንደራሴነት አይነት ይሆናል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች መንፈስና ዓላማ መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ ዉል ከተዋዋዮች ዉጭ ለሆነ ሌላ ሰዉ ጥቅም የተደረገ ነዉ እንዲባል ዉሉ ለጥቅሙ የተደረገለት ሰዉ ማን እንደሆነ በዉሉ ላይ በግልጽ መገለጽ ይኖርበታል፡፡ምክንያቱም በጽሁፍ የተደረገ ዉል በይዘቱ ዉሉ ለጥቅሙ የተደረገለትን ሦስተኛ ወገን የማይገልጽ ከሆነ በዉሉ ላይ በግልጽ ከተመለከቱት ከተዋዋዮች ሀሳብ ዉጭ በመዉጣት ተዋዋዩ ዉሉን በስሙ የተዋዋለዉ ለራሱ ጥቅም ሳይሆን ለሌላ ሦስተኛ ወገን ጥቅም ነዉ በማለት በዉሉ በግልጽ ከተመለከተዉ ተዋዋይ ዉጭ ሌላ ሰዉ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ፍርድ ቤቶች ዉሉን እንዲተረጉሙ ሕግ ስለማይፈቅድላቸዉ ነዉ፡፡(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733 ይመለከቷል፡፡)ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ሟች አቶ ታደለ መስፍን አከራካሪዉን ቤት በገዙበት ዉል ይዘት ላይ ቤቱ የተገዛዉ ለአመልካች ጥቅም መሆኑ የሚያመላክት ነገር እንደሌለ አረጋግጧል፡፡ የዉሉ ይዘት አከራካሪዉ ቤት የተገዛዉ ለአመልካች ጥቅም መሆኑን

የማያሳይ ከሆነ ዉሉ የተደረገዉ ለአመልካች ጥቅም ነዉ የሚለዉን በምስክሮች የሚረጋገጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ሟችም ሆኑ ተጠሪዎች በጠባቂነት እየኖሩ እንደያዙ በክሳቸዉ ላይ በገለጹበት አግባብ በቤቱ ላይ ከሟች አቶ ታደለ መስፍን ወይም ከተጠሪዎች በተሻለ ሁኔታ ባለቤት ናቸዉ ተብሎ እንዲገመት የሚያያደርግ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይኖርባቸዋል፡፡አመልካች ይህንን ማድረግ የሚችሉት ደግሞ ከላይ በተመለከተዉና በክሳቸዉ ላይ በገለጹት አግባብ ቤቱ የተገዛዉ ለእሳቸዉ ጥቅም መሆኑን በዉሉ ማስረጃነት ማስረዳት ቢችሉ ነበር፡፡ሆኖም በዚህ አግባብ አላስረዱም፡፡ይልቁንም ዉሉ የአመልካችን ክርክር የሚደግፍ ይዘት የሌለዉ ከመሆኑም በተጨማሪ ሟች አቶ ታደለ መስፍን ቤቱን በዉል በስማቸዉ ገዝተዉ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 1553 እስከ 1646 ድረስ ስመ ሀብቱን በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ አስመዝግበዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በስማቸዉ ወስደዉ የያዙት እንደሆነና አቶ ታደለ መስፍን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኂላም በቤተሰብ እና በዉርስ ሕጋግት መሰረት የቤቱ ስመ ሀብት ወደ ተጠሪዎች ስም ዞሮ እንደተመዘገበ የስር ፍርድ ቤት የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ አረጋግጧል፡፡ይህም ቤቱ በሟች አቶ ታደለ መስፍን ተይዞ የነበረዉም ሆነ ተጠሪዎች ቤቱን የያዙት በአመልካች ክስ ላይ እንደተገለጸዉ በጠባቂነት ሳይሆን የቤቱ ባለሀብት በመሆናቸዉ ምክንያት እንደሆነ የሚያስቆጥር ነዉ፡፡በዚህ አግባብ ከክሱና ከመልሱ ጋር በግራ ቀኙ በቀረቡ ማስረጃዎች እነዚህ ፍሬ ነገሮች እስከተረጋገጡ ድረስ የሥር ፍርድ ቤት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በያዛቸዉ ጭብጦች ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉ በመሆኑና ከዚህ ዉጭ ምስክሮችን በመስማት ሊረጋገጥ የሚገባ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ምስክሮችን ሳይሰማ በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ መስጠቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 255 ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ የዉሳኔ አሰጣጥ ነዉ ከሚባል በስተቀር የክርክር አመራር ጉድለት ፈጽሟል የሚያስብል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤት በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ጭብጦች በመመስረት ክርክሩን እንደመራ አረጋግጠናል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከሩትን ጭብጦች ከማስረጃ እና ከሕግ አንጻር አገናዝቦ ዉሳኔ ከመስጠት አንጻርም አመልካች ባቀረቡት ክስ መሰረት አከራካሪዉ ቤት ለእሳቸዉ ጥቅም የተገዛ እና የቤቱ ባለሃብት መሆናቸዉን እንዲሁም ተጠሪዎች ቤቱን የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸዉ በጠባቂነት ይዘዉ አንለቅም ማለታቸዉን በማስረጃ አለማስረዳታቸዉን የቀረቡለትን ማስረጃዎች የመመርመርና የመመዘን ሥልጣኑን በአግባቡ ተጠቅሞና ተገቢዉን ሕግ መሰረት በማድረግ የሥር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡እንዲሁም የአከራካሪዉ ቤት ባለሀብቶች ተጠሪዎች እንደሆኑ የሥር ፍርድ ቤት የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ አረጋግጧል፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ተጠሪዎች ባለሀብት የሆኑበት እንደሆነ በማረጋገጥ ተጠሪዎች ቤቱን ሊለቁ አይገባም በማለት የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ

በሰጠዉ ዉሳኔና በዚህ ዉሳኔ ላይ የቀረበዉን ይግባኝ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመሰረዙ ከክርክር አመራር ረገድም ሆነ ከሕግ አተገባበር አኳያ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 210270 ላይ በቀን 23/02/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር በመ/ቁጥር 200412 ላይ በቀን 18/06/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 193067

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- መአዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካቾች ፡- 1. መሠረት ወ/አማኑኤል

2. ፍቅሩ ደበበ

ተጠሪዎች፡- 1. ጌታቸዉ ይልማ

2. አልማዝ ይልማ

3. ፀደቀ ኃይሌ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል መከተል የሚገባዉን ፎርማሊቲና ሕጋዊ ዉጤቱን የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ በመሰረቱት ክስ አመልካቾች ከሟች እናታችን ወ/ሮ ስንቅነሽ ወልደአማኑኤል በዉርስ የሚተላለፍልንን ቤት ይዘዉ በቀን 06/07/2009ዓ/ም በተደረገ የስጦታ ዉል ሟች አስተላልፈዉልናል በማለት የዉርስ ሀብት አካል ሆኖ ሊጣራና ክፍፍል ሊፈጸምበት አይገባም በማለት ተቃዉመዋል፡፡ሆኖም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881/2 በተደነገገዉ መሰረት በስጦታ ዉሉ ላይ ለስጦታ አድራጊዋ መነበብ እንዳለበት የተመለከተዉ ሥርዓት የተፈጸመ ስለመሆኑ ዉሉ አያሳይም፡፡የስጦታ ዉሉ ተጠሪዎችን ከዉርስ የሚነቅል ነዉ፡፡ እንዲሁም የስጦታ ዉሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜ የሟች እድሜ ከ90 አመት በላይ ስለሆነ በስጦታ ዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ እና ስም በሟች እናታችን የተጻፈ አይደለም፡፡ስለሆነም የስጦታ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ተብሎ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስ የስጦታ ዉሉን ሟች በምስክሮች ፊት ተነቦላቸዉ ፈርመዋል፡፡የስጦታ ዉሉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ በመሆኑ የዉሉን ይዘትና ፊርማዉን ማስተባበል አይቻልም፡፡ሟች ከመሞታቸዉ በፊት ባላቸዉ በንብረታቸዉ ላይ የመወሰን መብት ተጠቅመዉ በስጦታ ባስተላለፉልን መሰረት የቤቱ ስመ ሀብት በቀን 17/09/2009 ዓ/ም በአመልካቾች ስም ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶናል፡፡ሟች የስጦታ ዉሉን ሲያደርጉ እድሜያቸዉ ከ80 ዓመት በላይ የማይሆን ቢሆንም እድሜያቸዉ 80 ወይም 90 ዓመት በመሆኑ የስጦታ ዉሉን ተገንዝበዉ ሊፈርሙ አይችሉም ሊባል አይችልም፡፡ሰነዶችን ለማፈራረምና ለመመዝገብ ሥልጣን የተሰጠዉ የመንግስት አካል ሟች በስጦታ ዉሉ ቤቱን ለማስተላለፍ ሙሉ ፍላጎት እንዳላቸዉ አረጋግጦ ዉሉን ስለመዘገበ ከዚህ አኳያ የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ሟች በህይወት እያሉ ለአመልካቾች በስጦታ ስላስተላለፉና ሟች ኑዛዜ ትተዋል የሚያሰኝ ነገር ባለመኖሩ ሟች በስጦታ ባስተላለፉት ንብረት ላይ የዉርስ ጥያቄ ሊነሳ ስለማይችል ተጠሪዎች ከዉርስ ተነቅለናል በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም የሚሉ መከራከሪያዎችን በማንሳት ክሱ ዉድቅ እንዲሆን በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 72640 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እና የስጦታ ዉሉን ከሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀን 19/02/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስጦታ ዉሉ የመጨረሻዉ ክፍል "ስጦታ አድራጊ ለስጦታ ተቀባይ ወደዉና ፈቅደዉ ተስማምተዉ በዉሉ የተጠቀሰዉን መኖሪያ ቤት በስጦታ ሊያስተላልፉና በዉሉም ላይ ሲፈራረሙ ማየታችንን በፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡" በማለት ምስክሮች ማረጋገጣቸዉንና መፈረማቸዉን የሚያሳይ ቢሆንም በዉሉ ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881/2 ስር በአስገዳጅነት በተደነገገዉ መሰረት የስጦታ ዉሉ ስለመነበቡ በግልጽ የሰፈረ ነገር የለም፡፡ሕጉ ኑዛዜዉ መነበብ አለበት የሚል ብቻ ሳይሆን የተነበበ ስለመሆኑም ተገልጸ መጻፍ አለበት የሚል በመሆኑ በሕጉ አግባብ በዉሉ ላይ የመነበብ ስርዓት መፈጸሙን በሚያመላክት መልኩ አልተገለጸም፡፡ዉሉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ ቢሆንም ይህ አካል በሕጉ በጥብቅ የተደነገገዉን መስፈርት ማስቀረት አይችልም፡፡ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት መደረጉ ዉሉ በሕጉ የተመለከተዉን መስፈርት ማሟላት አለማሟላቱን ከመመርመር የሚያግድ አይደለም፡፡በመሆኑም ሟች ወ/ሮ ስንቅነሽ ወ/አማኑኤል በቀን 06/07/2009 ዓ/ም በተደረገ የስጦታ ዉል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 338 የሆነ መኖሪያ ቤት ለአመልካቾች በስጦታ ለማስተላለፍ ያደረጉት ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 እና 881/2 ስር በተደነገገዉ እና በሰ/መ/ቁጥር 700057 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የመነበብ ሥርዓት የተፈጸመበት ስለመሆኑ የተገለጸበት ስላልሆነ ፈርሷል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከፍ ሲል በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 222201 አከራክሮ በቀን 28/09/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 መሰረት ዋጋ እንዲኖረዉ በ2

ምስክሮች ፊት መደረጉ ብቻ በቂ ነዉ፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ኑዛዜዉ ለምስክሮች መነበብ እንዳለበት እንደቅድመ ሁኔታ አልተደነገገም፡፡ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 17(1/ሀ እና ሐ) ስር ተረጋግጦ የሚመዘገብ የስጦታ ዉል በምስክሮች ፊት መነበብ እንዳለበት አላስቀመጠም፡፡ይህም የሆነዉ ገለልተኛ የሆነዉ አካል በግልጽ የተደረገ ኑዛዜን ሲያረጋግጥ የኑዛዜዉን ፍሬ ነገር ለምስክሮችም ሆነ ለተናዛዡ በመግለጽ(በማንበብ) ያረጋግጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ ሕግ አዉጪዉ በዚህ አግባብ የሚረጋገጠዉን ሰነድ ለምስክሮች ማንበብ ይገባዋል ብሎ መደንገግ አላስፈለገዉም፡፡ስለዚህ ኑዛዜዉ በምስክሮች ፊት አልተነበበም ተብሎ ክርክር ሊቀርብበት የሚገባ አይደለም፡፡ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 922/2008 ላይ የተደነገገዉ ግልጽ ነዉ፡፡ ይህ አዋጅ ከፍትሐ ብሔር ሕግ በኋላ የወጣ ሕግ በመሆኑ በሁለቱ ሕጎች መካከል ተቃርኖ ካለ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡ስለሆነም የስጦታ ዉሉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገ ስለሆነና ስለኑዛዜ ከተደነገገዉ አንጻር የሚታይበት ምክንያት ስለሌለ የስር ፍርድ ቤት ዉሉ የፍትሐ ብሔር ሕግ ያስቀመጠዉን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ሲል የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

በመቀጠል ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱም በመ/ቁጥር 179562 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 29/07/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በአከራካሪዉ ዉል ላይ ስጦታ አድራጊዋ ተነቦላቸዉ የፈረሙ ስለመሆኑ በግልጽ የሚያሳይ ሀረግ የለም፡፡ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር ኑዛዜዉ በተናዛዡ ፊት መነበብ አለበት ተብሎ የተደነገገዉ ሥርዓት የተፈጸመበት አይደለም፡፡ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት መደረጉ በሕግ በአስገዳጅነት የተደነገገዉን ይህንን ሥርዓት የሚያስቀር ካለመሆኑም በተጨማሪ ለስጦታ ሰጭዋ የተነበበ ስለመሆኑ በሰነዱ ላይ አልተገለጸም የሚል ክርክር ከማቅረብ የሚከለክል አይደለም፡፡እንዲሁም የስጦታ ዉሉ ስጦታ ሰጭ በህይወት እያሉ የሚፈጸም መሆኑም የሕጉን መስፈርት እንዳያሟላ የሚያደርግ አይደለም፡፡ስለሆነም የስጦታ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር በተደነገገዉና በሰ/መ/ቁጥር 107020፣147331 እና 70057 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በስጦታ ሰጪዋ ፊት ስለመነበቡ ስለማያሳይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉሉ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ነዉ በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡አመልካቾች ለዚህ ችሎት በቀን 15/11/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ስጦታ ሰጭዋ በህይወት እያሉ ስመ ሀብቱ ወደ አመልካቾች ስም ዞሮ ተመዝግቧል፡፡ ስጦታ ሰጭዋ በሞቱበት ጊዜ ቤቱ በእጃቸዉ ስላልነበረ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 እና 2443 ተፈጻሚነት የለዉም፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸዉ ስጦታ ሰጭዋ የስጦታ ዉሉ የሚፈጸመዉ እኔ ከሞትኩ በኋላ ነዉ በሚል ያደረጉት ስጦታ ቢሆን ነበር፡፡ስጦታ አድራጊ በህይወት እያለ የሚፈጸም የስጦታ ዉል

ከሆነና የንብረቱ ስመ ሀብት ወደ ስጦታ ተቀባይ የዞረ ከሆነ ስለኑዛዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገዉ ተፈጻሚነት የለዉም በማለት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 61421(ቅጽ 10) የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በዚህ መሰረት አከራካሪዉ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 መሰረት በሁለት ምስክሮች ፊት የተደረገ ዉል ከሆነ በቂ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር የተደነገገዉ ተፈጻሚነቱ በዉል አዋዋይ ፊት ላልተደረገ(በተለምዶ የመንደር ዉል በሚባለዉ አኳኋን ለተደረገ የስጦታ(ኑዛዜ)) ብቻ ነዉ፡፡የስጦታ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ ስጦታ ሰጭ በንብረታቸዉ ላይ የመወሰን መብታቸዉን ተጠቅመዉ ለአመልካቾች ሲያስተላልፉ በምስክሮች ፊት ፈቃዳቸዉ ተጠይቆና ተረጋግጦ የተመዘገበ ዉል ሆኖ እያለ ስለመነበቡ የሚገልጽ ሀረግ በዉሉ ላይ ባለመገለጹ ብቻ ኑዛዜዉ ፈራሽ ሊሆን እንደማይችል በሰ/መ/ቁጥር 17429(ቅጽ 2) ላይ አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡በአዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 17/ሀ መሰረት የተደረገ የስጦታ ዉል ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የተመዘገበ ስለሆነ ወይም ይዘቱና ፊርማዉ እምነት የሚጣልበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 መሰረት የመነበብ ስርዓት አያሟላም ተብሎ ይዘቱ ሊስተባበልና ሊፈርስ የሚገባ አይደለም ተብሎ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ታርሞ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ይፅናልን በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ሟች ለአሁን አመልካቾች ያደረጉት የስጦታ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ ሟች በህይወት እያሉ ስመ ሀብቱ የተዛወረን ቤት የስር ፍርድ ቤት ፎርማሊቲ አያሟላም በማለት ዉሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲል የወሰነበት የሕግ አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 17/02/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ሟች በህይወት እያሉ በስጦታ ንብረታቸዉን አስተላልፈዉልናል በማለት ያነሱት ክርክር ተጠሪዎች የማናዉቀዉና አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 329 ላይ የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡ተጠሪዎች የስጦታ ዉል መኖሩን ያወቅነዉ ዉርስ በተጣራበት ጊዜ ነዉ፡፡የስጦታ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443፣881/2 እና 882 ስር የተደነገገዉን ፎርማሊቲ የማያሟላ በመሆኑ ፈራሽ ነዉ ተብሎ መወሰኑ ሕግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡እናታችን በህይወት እያሉ የቤቱ ስመ ሀብት ወደ አመልካቾች ስም ዞሮ የተመዘገበዉ የስጦታ ዉሉ ሕጉ ያስቀመጠዉን ፎርማሊቲ ባላሟላበት ሁኔታ በመሆኑና ተጠሪዎችም የዉርስ ሀብቱን እንዳንካፈል በማሰብ ከቅን ልቦና ዉጭ ያደረጉት በመሆኑ ስመ ሀብቱ በአመልካቾች ስም ዞሮ መመዝገቡ የሕጉን ፎርማሊቲ የማያሟላ ዉል እንዳይፈርስ የሚከለክል አይደለም፡፡ስለሆነም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 መሰረት የስጦታ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881-883 ስር የተደነገገዉን ፎርማሊቲዎች ማሟላት እንዳለበት በአስገዳጅነት የተደነገገዉን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የስጦታ ዉል እንደማያሟላ ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልን

በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም በቀን 14/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከግራ ቀኝ ክርክር፣ከዚህ ቀደም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ሟች ወ/ሮ ስንቅነሽ ወ/አማኑኤል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን የቤት ቁጥር 338 የሆነ መኖሪያ ቤታቸዉን በቀን 06/07/2009ዓ/ም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ፊት ተረጋግጦ በተመዘገበ የስጦታ ዉል ለአመልካቾች በስጦታ ለማስተላለፍ ዉል መዋዋላቸዉን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ከግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡እንዲሁም ሟች ወ/ሮ ስንቅነሽ ወ/አማኑኤል ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በቀን 05/06/2010ዓ/ም መሆኑን፣ተጠሪዎች የሟች ወራሾች መሆናቸዉን ያረጋገጡት በቀን 17/07/2010ዓ/ም እንደሆነና የስጦታ ዉሉን ተከትሎ በሟች ስም የነበረዉ ቤት ወደ አመልካቾች ስም ዞሮ ተመዝግቦ ለአመልካቾች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጣቸዉ በቀን 17/09/2009ዓ/ም እንደሆነ ከስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ተመልክተናል፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት የሕግ ትርጉም የሚሻዉ ጭብጥ ሟች ወ/ሮ ስንቅነሽ ወ/አማኑኤል መኖሪያ ቤታቸዉን ለማስተላለፍ ያደረጉት የስጦታ ዉል በስጦታ ሠጭዋና በምስክሮች ፊት ካልተነበበና በዉሉ ላይ የማንበብ ሥርዓት ስለመፈጸሙ ያልተመለከተ ከሆነ ሕጋዊ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? ከዚህ ጋር በተያያዘ ተፈጻሚነት ያላቸዉ ሕጎች ትክክለኛ ትርጉም ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉ ናቸዉ፡፡

ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ የስጦታ ዉል ላይ የዉሉ ጉዳይ የሆነዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ማስተላለፍ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2443 ስር በተደነገገዉ የስጦታ ዉል ፎርም ሥርዓት መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡በዚህ ድንጋጌ ላይ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ ዉል የሚፈጸምበት ፎርም በሚከተለዉ መሰረት ተደንግጓል፡፡

ቁ.፪ሺ፬፻፵፫ የስጦታ ሥርዓት ፎርም(፩) የማይንቀሳቀስ ንብረቶች

> *"በማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ መብትን የሚሰጥ ስጦታ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አሠራር ዐይነት ካልተደረገ ፈራሽ ነዉ፡፡"*

የሕጉ የእንግሊዝኛዉ ቅጅ Art. 2443 - Form — 1. Immovabes

*"A donation relating to an immovable or a right on an immovable shall be of no effect unless it is made in the form governing the making of a public will (Art. 881-883)."*

ከላይ ይዘቱ የተመለከተዉን ድንጋጌ አፈጻጸምና ትርጓሜ ከመመልከታችን በፊት ስለስጦታ ምንነት መመርመሩ ተጠቃሹ ድንጋጌ ሊኖረዉ የሚገባዉን ትክክለኛ አፈጻጸምና ትርጉም(Application and interpretation) ላይ ለመድረስ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ከስጦታ ዉል ሕግ(Law of Contracts of Donation) ጽንሰ ሀሳብና በዘርፉ ከተጻፉ ድርሳናት እንደምንገነዘበዉ ስጦታ ሁለት ገጽታዎች አለቱ፡፡ይሄዉም ስጦታ ሰጪዉ በህይወት እያለ ስጦታ ተቀባዩ የተሰጠዉን ንብረት የግል አድርጎ እንዲጠቀም መብት የሚሰጥ ስጦታ ዐይነት በላቲን donation inter vivos (የቁም ኑዛዜ) ተብሎ የሚታወቀዉ አንደኛዉ ነዉ፡፡ ይህም ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ በንብረቱ ላይ ያለዉን የመወሰን ወይም ከሁሉ የሰፋ የባለቤትነት መብት በመጠቀም ለፈለገዉ ሰዉ ንብረቱን የሚያስተላልፍብትን ሥርዓት የሚመለከት ነዉ፡፡ሁለተኛዉ ዐይነት ደግሞ ስጦታ ሰጪዉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ተፈጻሚ የሚሆን [የ]ስጦታ [ዉል] በላቲን donation mortis causa በሚል የሚታወቀዉ ነዉ፡፡ ይህም አንድ ሰዉ ሲሞት ንብረቱን የሚወስደዉን ወይም የሚወርሰዉን ሰዉ ከወዲሁ በስጦታ ዉል የሚወስንበት ሥርዓት ሲሆን ስጦታ ተቀባዩ ስጦታ በተደረገለት ንብረት ተጠቃሚ መሆን የሚጀምረዉ ስጦታ ሰጪዉ መሞቱን ተከትሎ በመሆኑ እንደ ኑዛዜ ስጦታ የሚቆጠር ነዉ፡፡እንዲሁም ይህ ሁለተኛዉ ዐይነት የስጦታ ዉል የሟቹን ሀሳብ በአግባቡ ተግባራዊ ከማድረግ (executing the will of the deceased) አንጻር እና ስጦታ ያልተደረገላቸዉ የሟቹ ወራሾች ሊኖራቸዉ የሚችለዉ የዉርስ መብት ከግምት እየገባ በዉርስ ሕጉ መሰረት ሟቹ ያደረገዉ የስጦታ ዉል አፈጻጸም ሊመረመር ስለሚችል በእንዲህ አይነት ስጦታ የስጦታ ሰጭዉ መብት በአንጻራዊነት በሕግ በተመለከተዉ ምክንያት ሊገደብ የሚችል ነዉ፡፡

ይህንን አጠቃላይ የስጦታ ጽንሰ ሀሳብ ይዘን ከላይ ይዘቱ የተመለከተዉን ድንጋጌ እንመልከት፡፡በአገራችን ስጦታንና ኑዛዜን የሚገዙ ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ በሁለት የተለያዩ ዘርፎች ተደንግገዋል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ከቁጥር 2427 እስከ 2470 ስለ ስጦታ በጠቅላላዉ የተደነገገ ሲሆን በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ (Title) አምስት ስር ስለወርስ በጠቅላላዉ እና በተለይ ደግሞ በክፍል 3 ከቁጥር 857 ጀምሮ ባሉ ድንጋጌዎች ስለኑዛዜ ተደንግጓል፡፡ከላይ ይዘቱ የተመዘገበዉ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 ከርዕሱ ጀምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ሲተላለፍ ዉሉ መደረግ ስላለበት ፎርም በጠቅላላዉ የሚመለከት መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነዉ፡፡በድንጋጌዉ ላይ የተመለከተዉን ፎርም መከተል ያለበት የትኛዉ ዐይነት የስጦታ ዉል ነዉ የሚለዉን ድንጋጌዉ ልዩነት አለማስቀመጡንም የድንጋጌዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህም ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ ተፈጻሚ የሚሆነዉን የስጦታ አይነት (donation inter vivos) በተመለከተ የሚደረግ ዉልም ሆነ ስጦታ ሰጭ ከሞተ በኋላ

ተፈጻሚ የሚሆነዉን ስጦታ (donation mortis causa) በተመለከተ የሚደረግ ዉል በድንጋጌዉ ላይ በተመለከተዉ መሰረት በግልጽ ለሚደረግ ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881 እስከ 883 የተደነገገዉን ተከትሎ መደረግ እንዳለበት በአስገዳጅነት መደንገጉን የሚያሳይ ነዉ። በዚህ መልኩ ጥብቅ የሆነ የዉል አደራረግ ሥርዓት የተደነገገበት ምክንያት ስጦታ ሰጭ ያለዋጋ ስጦታ ወይም ችሮታ በማድረግ ሀሳብ(without consideration) ንብረቶቹን (ከንብረቶቹ አንዱን) ለመስጠት ግዴታ የሚገባበት በመሆኑ ዉሉ የስጦታ ሰጭዉን ፈቃድ (ፍላጎት) በማያሻማ መልኩ የሚገልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲያስችል ለማድረግ ካለዉ ዓላማ ነዉ።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 የተደነገገዉ ሁለቱም ዐይነት የስጦታ ዉል መከተል ስላለበት ፎርም የተደነገገ መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ለሁለቱም ዐይነት ስጦታ ዉል በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆኑት በፍትሐ ብሔር ሕግ ስለኑዛዜ በሚመለከተዉ ክፍል ዉስጥ ካሉ ድንጋጌዎች መካከል በግልጽ ስለሚደረግ ኑዛዜ ፎርም ከቁጥር 881 እስከ 883 ድረስ የተመለከቱት ሲሆኑ ከእነዚህ ድንጋጌዎች በስተቀር ኑዛዜን የሚገዙ ሌሎች ድንጋጌዎች ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ ተፈጻሚ የሚሆነዉን የስጦታ ዐይነት (donation inter vivos) በተመለከተ ተግባራዊ የሚሆኑ አይደሉም።ይህንን ድምዳሜ የሚያጠናክረዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2428 ላይ በሞት ምክንያት የሚደረጉ ስጦታዎች (donation mortis causa) በሚል ርዕስ ስር "ሰጪዉ ሲሞት ይፈጸማሉ ተብለዉ በተወሰኑት ስጦታዎች ላይ ስለኑዛዜ የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈጻሚዎች ይሆናሉ።"በሚል መደንገጉ ነዉ።በመሆኑም ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ ተፈጻሚ የሚሆነዉን የስጦታ ዉል ፎርም (forms of donation inter vivos) በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881-883 ድረስ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሲሆኑ በሌሎች ይሄኛዉን የስጦታ ዉል በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕግ በቁጥር 2427 እና ተከታዮቹ ስለስጦታ የተደነገጉት ናቸዉ።

ቀጥለን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር ከቁጥር 881 እስከ 883 ስር በግልጽ ለሚደረግ ኑዛዜ (ከዚህ በኋላ ኑዛዜ ተብሎ የተገለጸዉ እንደነገሩ ሁኔታ የስጦታ ዉልንም የሚመለከት ነዉ) ከተቀመጡ የፎርም ሥርዓቶች መካከል ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትርጉም ለሚሹ ድንጋጌዎች አጽንኦት ሰጥተን እንመረምራለን። በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881 እስከ 883 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ማሟላት ያለባቸዉ ናቸዉ ተብለዉ የተጠቀሱ መስፈርቶች፡- 1)ኑዛዜዉ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/1 ይመለከተዋል)፣2) ስለምስክሮች ብዛት፣ችሎታ እና ስለተናዛዡና ስለምስክሮች ፊርማ(የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881(1 እና 3)፣882 እና 883 ይመለከቷል)፣ 3) ኑዛዜዉ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸዉ ሥርዓት መፈጸሙንና የተፈጸመበትን የሚያመላክት መሆን ያለበት ስለመሆኑ(በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ይመለከቷል) እንዲሁም 4) እነዚህን መስፈርቶች አለማሟላት ስለሚያስከትለዉ ዉጤት ተደንግጓል።ምንም እንኳን በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ በዉል አዋዋይ ፊት

እንዲደረግና እንዲመዘገብ (Authentication) ሕግ ባያስገድድም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር እንደተመለከተዉ በግልጽ የተደረገዉ ኑዛዜ በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ እንደሆነ ኑዛዜዉ በሁለት ምስክሮች ፊት የተደረገና የተፈረመ ከሆነ በቂ ሲሆን ከዚህ ዉጭ በሆነ አኳኋን በተለምዶ የመንደር ዉል በሚል በሚገለጸዉ አኳኋን የተደረገ ከሆነ ግን ኑዛዜዉ(የስጦታ ዉሉ) በአራት ምስክሮች ፊት ተደረጎ በአራቱም ምስክሮች የተፈረመ መሆን አለበት፡፡

ሌላዉ ትርጉም የሚሻዉ ነጥብ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር ኑዛዜዉ በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ይኸዉ ሥርዓት መፈጸሙንና የተፈጸመበትን የሚያመላክት መሆን አለበት የሚለዉ መስፈርት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 መሰረት በዉል አዋዋይ ፊት ለተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ጭምር ሊፈጸም የሚገባ ሥርዓት ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡ አንድን ሕግ ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለመተርጎም ጥቅም ላይ የሚዉሉ የተለያዩ መርሆዎች፣ዶክትሪኖችና ቴክኒኮች ያሉ ሲሆን የሕጉን ቃላት በቀጥታ ተግባራዊ ማድረግ (Texutualism ) ተብሎ የሚታወቀዉን የአተረጓገም አካሄድ የሚከተሉ ዳኞች (ፍርድ ቤቶች) ሕግ አዉጪዉ አካል ያወጣቸዉን ሕግጋት ሕጎቹ በወጡበት ጊዜ ያላቸዉን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸዉ እንጂ ሕግ አዉጪዉ በቃላቶቹ ለማስተላለፍ የፈለገዉን ዓላማ መፈለግ የለባቸዉም የሚል አስተሳሰብ የሚከተሉ ናቸዉ፡፡ ሌላዉ የሕግ አተረጓጎም አካሄድ ዓላማዊነት (Purposeivism) ተብሎ የሚታወቀዉ ሲሆን ይህንን ዘዴ ተከትለዉ ሕግ የሚተረጉሙ ዳኞች(ፍርድ ቤቶች) ትርጉም የሚያስፈልጋቸዉን ሕግጋት ሲተርጉሙ ሕግ አዉጪዉ ሕጉን ሲያወጣ የነበረዉ ሀሳብና ሊያሳካ የፈለገዉ ዓላማ ምን እንደሆነ አዉቀዉ መተርጎም አለባቸዉ የሚለዉን ኃላፊነት መወጣት አለባቸዉ የሚለዉን ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ይህንንም ኃላፊነት ለመወጣት ማንኛዉም ሕግ የራሱ የሆነ ዓላማ ይዞ የሚወጣ በመሆኑ ዳኞች የሚተረጎመዉን ሕግ ቃላቶች፣አዉድ፣የጉዳዩን ምንነት፣ዉጤት እና የሕጉን መንፈስ ተከትለዉ ወደ ሕግ አዉጪዉ ዓላማ የሚያደርስ ትርጉም መስጠት አለባቸዉ ይላሉ፡፡በዋናነት የሚጠቀሱ የሕግ አተረጓጎም እነዚህ ቢሆኑም ከዓላማዊነት አተረጓጎም ጋር ተቀራራቢ ዉጤት ያለዉ ቴሊ'ሎጅካል የሕግ አተረጓጎም(teleological interpretation of law) እና ሌሎች የሕግ አተረጓጎም ሥርዓቶች መኖራቸዉም የሚታወቅ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 79/1 ስር እንደተደነገገዉ በአገራችን የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች በመሆኑ ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ አግባብነት ያለዉን ተፈጻሚ ሕግ ለይቶ በቀጥታ ተግባራዊ ማድረግም ሆነ ለሕጉ ትርጉም መስጠት ባስፈለገ ጊዜ ሕጎችን በመተርጎም ዳኝነት መስጠት የፍርድ ቤቶች ሥራ ነዉ፡፡ ሕግ መተርጎም ማለት ለአንድ ሕግ ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ፍቺ መስጠት ማለት ነው፡፡በአገራችን ዳኞች ሕግን ሲተረጉሙ መከተል ስላለባቸዉ መርሆዎችና ዘዴዎች ወጥ በሆነ መልኩ የወጣ ሕግ ባይኖርም በተለያዩ ሕጎች ላይ በተበታተነ መልኩ የተደነገገዉንና(ለአብነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1733-1737) በዳኝነት ሥራ በተግባር የዳበረዉን (Judicial jurisprudence) መሰረት በማድረግ ትርጉም የማያሻቸዉ ሕጎች ሲሆኑ በቀጥታ ተግባራዊ በማድረግ

ትርጉም የሚፈልጉትን ደግሞ ሕግ ፊደል ብቻ ሳይሆን ፊደልና መንፈስ (letter and sprit) መሆኑን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ፊደሉን ብቻ ሳይሆን መንፈሱንም የተከተለ እንዲሆን በማድረግ የሕግ አተረጓጎም ዘዴዎችን በየሚዛናቸዉ በማየት ሲተረጎም ይስተዋላል፡፡ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት እስከአሁን በሰጠዉ የሕግ ትርጉሞች ላይ በአብዛኛዉ በዚህ መልኩ ትርጉም ለሚፈልጉ ሕግጋት ትርጉም ሲሰጥ ቆይቷል፤እየተሰጠም ይገኛል፡፡የተያዘዉም ጉዳይ በዚሁ አግባብ ተመርምሯል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ላይ ትርጉም ከሚሹ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ አስቀድሞ በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ትርጉሞችን የተመለከትን እንደሆነ በሰ/መ/ቁጥር 70057(ቅጽ 13 ላይ እንደታተመዉ) ላይ በተሰጠ የሕግ ትርጉም የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/1 ተከታይ ሆኖ የተደነገገ በመሆኑና በዉል አዋዋይ ፊት ለሚደረግ ግልጽ ኑዛዜ ስለመነበብ ሥርዓት የተደነገገዉ በኋለኛዉ ድንጋጌ አስፈላጊ አይሆንም ተብሎ ስላልተደነገገ በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ኑዛዜ ቢሆን እንኳን በተናዛዡና በምስክሮች ፊት ኑዛዜዉ *ስለመነበቡ በሰነዱ ላይ ካልተመለከተ* ኑዛዜዉ ፈራሽ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 147331 ላይም ተመሳሳይ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በሌሎች በሰ/መ/ቁጥር 17429(ቅጽ 2 ላይ እንደታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 22712(ቅጽ 4 ላይ እንደታተመዉ) ሕጉ ኑዛዜ መነበብ አለበት ብሎ ያስቀመጠበት ዓላማ ኑዛዜዉ በሚነበብበት ወቅት የተናዥዡ ፈቃድ መሟላቱን ማረጋገጥ እንዲቻል በመሆኑ በኑዛዜዉ ላይ ስለመነበቡ ባይገለጽም በኑዛዜዉ ላይ *"ሲናዘዙ ሰምተናል፤አይተናል"* በሚል የተገለጸዉ አገላለጽ ምስክሮች ያዩትና የሰሙት ኑዛዜዉ ሲደረግና የተጻፈዉ ሲነበብ ነዉ ተብሎ ሊገመትና ለኑዛዜዉ ዉጤት ሊሰጠዉ ይገባል የሚል ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

እንዲሁም ከቁም ኑዛዜ (ከስጦታ ዉል )ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 32337(ቅጽ 5 ላይ እንደታተመዉ) ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቁም ኑዛዜ (donation inter vivos) በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 መሰረት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር የተደነገገዉን ፎርማሊቲ የሚያሟላ ነዉ በሚል ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ስለአንድ ጉዳይ ለተደነገገ ድንጋጌ ትርጉም ሲሰጥ የሚሰጠው ትርጉም የተለያየ ሳይሆን ካሉት የተለያዩ ትርጉሞች ውስጥ ለድንጋጌዉ ህይወት ለሰጡት ቃላትም ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት ሕጋዊ ተቀባይነት ያለውንና ወደ ግቡ የሚያደርስ ትርጉም መስጠት ይገባል፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 መስፈርት የተደነገገዉ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ወይም ደግሞ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 ላይ በተደነገገዉ መሰረት ሁለቱም ዐይነት ስጦታ ሲደረግ የስጦታ ዉሉ ሊከተል የሚገባዉ ፎርም አካል ሆኖ የተደነገገ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ ስለፎርም ለተደነገገዉ ድንጋጌ ትርጉም ሲሰጥ ቃላቱን ብቻ ሳይሆን በድንጋጌዉ በተካተቱ ቃላት ለማሳካት የተፈለገዉን ዓላማ ከግብ በሚያደርስ መልኩ ወጥ የሆነና በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችል ትርጉም ሊሰጥ ይገባል፡፡በተጨማሪም ከዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ

በተለይም ኑዛዜ ወይም የስጦታ ዉል በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ወይም ዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ በሆነ ጊዜ ከዚህ ድንጋጌ ጋር ግንኙነት ያለዉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 እና ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ሲያደርግ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የሚከተለዉ አሰራር ከግምት ገብቶ ሊመረመር ይገባል፡፡

እንደሚታወቀዉ ኑዛዜ እና የስጦታ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት የግድ በዉል አዋዋይ ፊት እንዲደረጉ የማይጠበቅባቸዉ የዉል አይነቶች ናቸዉ፡፡ ስለኑዛዜና ስለስጦታ ዉል ሕጉ ባስቀመጠዉ ፎርም ላይ በተለይም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር "ኑዛዜዉ መነበብ እንዳለበትና ይኸዉ ስለመፈጸሙ በኑዛዜዉ ሰነድ ላይ መመልከት አለበት" የሚለዉ መስፈርት የተቀመጠበት ዓላማ በኑዛዜዉ ወይም በስጦታ ዉሉ ላይ የሰፈረዉ ቃል የተናዛዡ ወይም የስጦታ ሰጭዉ መሆኑን በመቆጣጠር ፈቃዱን ያለእንከን መስጠቱን ማረጋገጥ ይቻላል በሚል ዓላማ ነዉ፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የተቀመጠዉ መስፈርት በዉል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ኑዛዜ ወይም የስጦታ ዉል ሲሆን ኑዛዜዉ ወይም የስጦታ ዉሉ በተናዛዡ (በስጦታ ሰጭ) እና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸዉ ሥርዓት መፈጸሙ በኑዛዜ ሰነዱ ወይም በስጦታ ዉሉ ላይ ካልተመለከተ በሰነዱ ላይ የሰፈረዉ ቃል የተናዛዡ(የስጦታ ሰጪዉ)መሆኑ ሊረጋገጥ የሚችልበት መንገድ ስለማይኖር በጥብቅ ተግባራዊ ሊደረግና ይኸዉ ሥርዓት ካልተፈጸመም ኑዛዜዉ ወይም የስጦታ ዉሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ኑዛዜ ወይም የስጦታ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር የተደነገገዉ የፎርም አካል የሆነዉ መስፈርት ሲሆን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008*(በቀድሞዉ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 334/1995/በአዋጅ ቁጥር 467/1997 እንደተሻሻለዉ በተመሳሳይ እንደተመለከተዉ)* ዓላማና በአዋጁ ዝርዝር ድንጋጌዎች አንድን ሰነድ ለማረጋገጥ ከተዘረጋዉ ሥርዓት ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡በዚህ አዋጅ መግቢያ ላይ እንደተመለከተዉ....በሰዎች መካከል የሚደረጉ ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ሌሎች መስተጋብሮችን በሚመለከት የሚፈጸሙ የዉል እና ሌሎች ግንኙነቶችን በሕግ አግባብ በማረጋገጥ እምነት የሚጣልበት ሰነድ ማመንጨት በአዋጁ በተዘረጋዉ ሥርዓት ለማሳካት የታለመ ዓላማ ነዉ፡፡

በተጨማሪም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7/3 ስር እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰነድ የማረጋገጥና የመመዝገብ ተግባር እንዲፈጽም በአዋጁ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል የዜጎችን የግል ንብረት የማፍራት፣የመጠቀም እና በሕጋዊ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን በማስከበር የፍትሕ ሥርዓቱን በማገዝ የሕግ የበላይነትን የማስጠበቅ ዓላማ ከግብ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(2 እና 5) ፣8/5 እና 10/2 ስር ሰነድ አረጋጋጩ አዲስ ሰነድ በአዘጋጁ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሲፈረም ማየትና ይኸዉ መፈጸሙን ማረጋገጥ ወይም በትክክል መስፈሩን በማረጋገጥ እንዲፈረም ማድረግ ፣ለመረጋገጥ የሚቀርቡ ሰነዶችን ሕጋዊነት ማረጋገጥ እንዲሁም በአዋጁ አንቀጽ 17 ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ

ሆኖ አግባብ ባላቸዉ ሕጎች የተደነገገዉን ሥርዓት መከተል የሰነድ አረጋጋጩ ተግባርና ኃላፊነት እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ ከማረጋገጡና ከመመዝገቡ በፊት የሰነዱን ይዘት የመለወጥ ወይም የማስለወጥ ሥልጣን ባይኖረዉም የሰነዱን ይዘት ትክክለኛነት የማረጋገጥና የሰነዱ ይዘት ሕግንና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 13 ላይ የተደነገገዉ ያሳያል፡፡

ሰነድ አረጋጋጩ ከላይ በተጠቀሰዉ መሰረት የማረጋገጥ ኃላፊነቱን በአግባቡ ይወጣል በሚል እምነት ሕግ አዉጪዉ በአዋጁ አንቀጽ 17 ስር የስጦታ ዉል ወይም ኑዛዜ የማረጋገጥና የመመዝገብ ተግባር በሚፈጸምበት ጊዜ ሁለት ምስክሮች እንዲፈርሙ ማድረግ እንደሚገባ ከመደንገጉ በስተቀር በዚህ በአዋጁ አንቀጽ 17 ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 በተደነገገዉ መሰረት ሰነድ አረጋጋጭ "ኑዛዜ መነበብ እንዳለበትና ይኸዉ ስለመፈጸሙ በኑዛዜዉ ሰነድ ላይ መመልከት አለበት" የሚለዉ በኑዛዜ ሰነዱ ወይም በስጦታ ዉሉ ላይ መመልከቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል በሚል አልደነገገም፡፡ሕግ አዉጭዉ ይህንን መስፈርት በዝምታ ያለፈበት ምክንያት የስርዓቱ መፈጸም አስፈላጊ አይደለም በሚል ሳይሆን ሰነድ አረጋጋጭ ኑዛዜ ወይም የስጦታ ዉል ከማረጋገጡና ከመመዝገቡ በፊት(before authenticating and registering) የሰነዱን ይዘት ትክክለኛነት የማረጋገጥና ይዘቱ ሕግንና ሞራልን የማይቃረን መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት በአግባቡ ይወጣል በሚል እምነት ሰነዱ ላይ በቃላት ባይገለጽም አረጋጋጩ የማረጋገጥ ተግባሩን ሲወጣ የታለመዉ ዓላማ ከግብ ይደርሳል በሚል ነዉ፡፡

በመሆኑም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ(ሥልጣን በተሰጠዉ ዉል አዋዋይ ፊት) ተረጋግጦ በተመዘገበ የኑዛዜ ሰነድ ወይም የስጦታ ዉል ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 በተደነገገዉ መሰረት "ኑዛዜ መነበብ እንዳለበትና ይኸዉ ስለመፈጸሙ በኑዛዜዉ ሰነድ ላይ መመልከት አለበት" የሚለዉ ሥርዓት ስለመፈጸሙ በግልጽ ያልተገለጸ ቢሆንም እንኳን ይህ ተግባር ኑዛዜ ወይም የስጦታ ዉል ከመረጋገጡና ከመመዝገቡ በፊት በሰነድ አረጋጋጩ እንደተፈጸመ ሊቆጠር ይገባል እንጂ ይህ ሥርዓት ስለመፈጸሙ የሚያመላክቱ ቃላት ወይም ሐረጋት በኑዛዜ ሰነዱ ወይም በስጦታ ዉሉ ላይ አልተመለከተም በሚል ኑዛዜዉ ወይም የስጦታ ዉሉ ፈራሽ ሊሆን አይገባም፡፡

ከላይ ከተመለከተዉ የሕጎቹ አቋምና ትርጉም አንጻር የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት ሟች ወ/ሮ ስንቅነሽ ወ/አማኑኤል በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ክልል ዉስጥ በካርታ ቁጥር 018352/1 የተመዘገበ በቤት ቁጥር 338 የሚታወቀዉን መኖሪያ ቤታቸዉን በቀን 06/07/2009ዓ/ም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ በተመዘገበ ዉል ለአመልካቾች በስጦታ ማስተላለፋቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡በዉሉ ላይ ስጦታ ሰጭና ሁለት ምስክሮች መፈረማቸዉ ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የስጦታ ዉሉ ላይ አመልካቾች ሟች በህይወት እያሉ መኖሪያ ቤቱን በስማቸዉ እንዲጠቀሙበት ሟች መስማማታቸዉ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ሟች በህይወት እያሉ የመኖሪያ ቤቱ ስመ ሀብት ከሟች

ስም ወደ አመልካቾች ስም ዞሮ መመዝገቡ ስለተረጋገጠ ስጦታዉ ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ ተፈጻሚ የሚሆን የስጦታ ዐይነት (donation inter vivos) ነዉ፡፡ ለእንዲህ ዐይነት ስጦታ ከዉሉ ፎርም ዉጭ ላሉ ጉዳዮች ተፈጻሚ የሚሆኑ ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ስለስጦታ የተደነገጉ ድንጋጌዎች በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2463 መሰረት ስጦታ ተቀባዮች ስጦታዉን መቀበላቸዉን ዉሉ ያሳያል፡፡በስጦታ ዉሉ ላይ ከፎርም አንጻር ስለመፈጸሙ በቃላት ወይም በሐረጋት ያልተመለከተዉ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2 ስር የተደነገገዉ "ኑዛዜ(የስጦታ ዉሉ) መነበብ እንዳለበትና ይኸዉ ስለመፈጸሙ በኑዛዜዉ ሰነድ(በስጦታ ዉሉ) ላይ መመልከት አለበት" የሚለዉ ነዉ፡፡ይህ በስጦታ ዉሉ ላይ ስለመፈጸሙ ያልተመላከተዉ የፎርም መስፈርት ከላይ እንደተገለጸዉ የስጦታ ዉሉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ተረጋግጦ የተመዘገበ በመሆኑ በሰነድ አረጋጋጩ ዉሉ ተረጋግጦ በተመዘገበበት ጊዜ እንደተፈጸመ የሚቆጠር በመሆኑ ሥርዓቱ ስለመፈጸሙ በዉሉ ላይ በቃላትና በሐረጋት ባለመገለጹ ብቻ እንዳልተፈጸመ ተቆጥሮ ዉሉ ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የስጦታ ዉል ስጦታ ሰጪዉ በህይወት እያለ የሚፈጸምም ሆነ ስጦታ ሰጭዉ ከሞተ በኋላ የሚፈጸም ቢሆንም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 ስር በተደነገገዉ መሰረት በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 881 እስከ 883 ድረስ በግልጽ ለሚደረግ ኑዛዜ የተደነገገዉን ፎርም ተከትሎ መፈጸም አለበት፡፡ሆኖም የስጦታ ዉል በዉል አዋዋይ ፊት ተረጋግጦ የተመዘገበ ከሆነ ግን በስጦታ ዉሉ ላይ ዉሉ በስጦታ ሰጭና በምስክሮች ፊት የመነበብ ሥርዓት የተፈጸመበት እንደሆነ የሚያመላክት አገላለጽ ያልተመለከተ ቢሆንም የመነበብ ሥርዓት በሰነድ አረጋጋጩ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ ዉሉ ዉጤት ሊኖረዉ ይገባል፡፡በዚህ መሰረት በሰ/መ/ቁጥር 70057(ቅጽ 13 ላይ እንደታተመዉ)፣በሰ/መ/ቁጥር 147331፣በሰ/መ/ቁጥር 17429(ቅጽ 2 ላይ እንደታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 22712(ቅጽ 4 ላይ እንደታተመዉ) እና በሌሎች መዝገቦች ላይ ከኑዛዜና ከስጦታ ዉል ፎርም ጋር በተያያዘ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነታቸዉ በዉል አዋዋይ ፊት ተረጋግጠዉ ባልተመዘገቡ ኑዛዜዎችና የስጦታ ዉሎች ላይ ብቻ ነዉ በሚል በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 32337(ቅጽ 5 ላይ እንደታተመዉ) በተሰጠ የሕግ ትርጉም ላይ የቁም ኑዛዜ(ስጦታ ሰጭ በህይወት እያለ የሚፈጸም የስጦታ ዉል/donation inter vivos) በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ ከሆነ በፍ/ብ//ሕግ ቁጥር 2443 መሰረት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር የተደነገገዉን ፎርማሊቲ ካሟላ በቂ እንደሆነ በሚያመላክት መልኩ መተርጎሙ- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 ላይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 እስከ 883 ድረስ የተደነገጉ የፎርም አካል የሆኑ ሌሎች መስፈርቶችን ያላገናዘበና ሰነድ አራጋጋጭ የሰነዱን ይዘት ትክክለኛነትና የስጦታ ሰጭዉን ፈቃድ ከማረጋገጥ ጋር ያለበትን ኃላፊነት ቀሪ እንደሆነ በሚያመላክት መልኩ የተሰጠ ትርጉም በመሆኑ በመዝገቡ ላይ ከፎርም ጋር በተያያዘ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ትርጉም እንዲተካ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26 መሰረት ተለዉጧል፡፡ስለሆነም የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከላይ እንደተመለከተዉ

የስጦታ ዉሉ ፈራሽ ነዉ ብሎ መወሰኑ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከላይ በዝርዝር በተመለከተዉ መሰረት በማየት የስጦታ ዉሉ ዉጤት እንዲኖረዉ በማድረግ መወሰን ሲገባዉ አዋጅ ቁጥር 922/2008ን መሰረት በማድረግ የስጦታ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም ሲል የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነዉን በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881/2ን ዓላማ እና የአዋጅ ቁጥር 922/2008ን ዓላማና በአዋጁ የተዘረጋዉን ሰነድ የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 72640 ላይ በቀን 19/02/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 179562 ላይ በቀን 29/07/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 222201 ላይ በቀን 28/09/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ከላይ በፍርዱ ሀተታ ላይ በተመለከተዉ አግባብ በተወሰነ ደረጃ ምክንያቱ ተሻሽሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

3. በሰ/መ/ቁጥር 70057፣ በሰ/መ/ቁጥር 147331፣በሰ/መ/ቁጥር 17429 እና በሰ/መ/ቁጥር 22712 ላይ እና በሌሎች መዝገቦች ላይ በተመሳሳይ ከኑዛዜ እና ከስጦታ ዉል ፎርም ጋር በተያያዘ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ከፍ ሲል በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ልክ ተሻሽለዋል፡፡እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 32337 ላይ እና በተመሳሳይ በሌሎች መዝገቦች ላይ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ከቁም ኑዛዜ(ከስጦታ ዉል) ፎርም ጋር በተያያዘ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም በዚህ ፍርድ ማጠቃለያ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ተለዉጧል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
2. ግራ ቀኙ ሲጠይቁ ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
3. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ ዕግድ ካለ ተነስቷል ፤ይጻፍ፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 211616

ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

ተጠሪ፡- አዲስ አበባ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቅድመ ክፍያ ዋስትና አፈጻጸም መነሻ ያደረገ እና ከዚህ ጋር የተያያዘ ክርክር የመዳኘት ስልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በየደረጃዉ በይግባኝና በሰበር ታይቶ በትእዛዝ በጸናዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ነዉ፡፡ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ ከበደ ካሳዬ የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ላይ እና በስር 3ኛ ተከሳሽ ቡና ኢንሹራንስ አ.ማ ላይ በመሰረተዉ ክስ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በቀን 23/11/2007 ዓ/ም ባደረግነው በቦሌ አራብሳ ሳይት የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ውል በጠቅላላ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ጨምሮ በብር 26,801,738.00 ለመስራት ውል ተዋዉሎ ለግንባታው የዋናውን ውል 20% ቅድመ ክፍያ እንዲከፈለው ከአሁን አመልካች ለብር 5,360,347.60 ተ.እ.ታ ጨምሮ የቅድመ ክፍያ ጋራንቲ አቅርቧል፡፡እንዲሁም ከስር 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቦንድ አቅርቧል፡፡ተጠሪ የቅደመ ክፍያ ዋስትና በመቀበል ብር 5,360,347.60 ለስር 1ኛ ተከሳሽ ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ ነገር ግን የስር 1ኛ ተከሳሽ በገባው ውል መሰረት ግንባታውን ባለመፈፀሙና በማጓተቱ በተለያዩ ጊዜያት ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ግንባታውን ሊያጠናቅቅ ባለመቻሉ በቀን 04/13/2008 ዓ/ም ውሉን አቋርጠናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በሰጠው የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ የስር 1ኛ ተከሳሽ ወስዶ ሥራ ላይ ያላዋለውን ብር 422,500.66 (አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺ.ህ አምስት መቶ ብር ከስልሳ ስድስት ሳንቲም) ለባንኩ ካሳወቅንበት ከቀን 27/01/2009 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለን ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቅ ክስ መስርቷል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ የግንባታ ዉል የአስተዳደር ዉል ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በአማራጭ በሰጠዉ መልስ አመልካች ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የገባው የዋስትና ውል ግዴታ ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጠሪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ባለው ውል 1ኛ ተከሳሽ በውሉ ውስጥ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት እንዳልቻለ ገልፆ ብቻ የክፍያ ጥያቄ ሲያቀርብ ለመክፈል ነው፡፡ ተጠሪ በቀን 27/01/2009ዓ/ም በጻፈዉ ደብዳቤ ዋስትናዉ ታግዶ እንዲቆይ የጠየቀዉ ከዋስትና ዉሉ መንፈስ ዉጭ ነዉ፡፡ ክፍያዉን ማገድ ከአመልካች ሥልጣን ዉጭ እና ከዋስትና ውሉ መንፈስ ውጪ በመሆኑ ትርጉም የማይሰጥና የክፍያ ጥያቄም እንዳልቀረበ የሚያሳይ ስለሆነ አመልካች ክፍያዉን ለመፈጸም አይገደድም፡፡ተጠሪ በቀን 01/07/2010ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የዋስትና ገንዘቡን አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ እንዲደረግልን በማለት የጻፈዉ ደብዳቤ ለአመልካች አልደረሰዉም፡፡ስለመድረሱም ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በዋስትና ሰነዱ መሰረት የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለዉ ከቀን 04/02/2008ዓ/ም እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ በመሆኑና ተጠሪ በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ የክፍያ ጥያቄ ያልቀረበ ስለሆነ የመክፈል ግዴታ የለብንም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 18052 ላይ በሰጠዉ ብይን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ካለፈ በኋላ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ በቀን 20/01/2013 ዓ/ም ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አመልካችን በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የቅድመ ክፍያ ዋስትና መስጠቱ የተረጋገጠ ነዉ፡፡ እንዲሁም የስር 1ኛ ተከሳሽ ከተቀበለዉ ቅድመ ክፍያ ላይ ብር 422,500.06 ሥራ ላይ አለማዋሉም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በቁጥር ቢአይቢ/ኬ5ቢ/052/2015 እ.ኤ.አ በቀን 15/10/2015 ቅድመ ክፍያ ዋስትና መሰረት ተጠሪ ክፍያ ለመጠየቅ 1ኛ ተከሳሽ የዉል ግዴታዉን ለመወጣት ሳይችል ሲቀር ዉሉ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ዉስጥ በደብዳቤ ገልጾ ሲያቀርብ የካሳ ክፍያ ይከፍላል የሚል ነዉ፡፡ተጠሪ በቀን 27/01/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ 1ኛ ተከሳሽ በዉሉ መሰረት እየሰራ ባለመሆኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ዉሉ ስለመቋረጡ ጠቅሶ ብሩ ይታገድልኝ የሚል በመሆኑ የክፍያ ጥያቄ አልደረሰንም የሚያስብል አይደለም፡፡ በተጠሪ በቀን 27/01/2009 ዓ/ም የተጻፈዉ ይህ ደብዳቤ በቀን 06/07/2010 ዓ/ም ለአመልካች እንደደረሰዉ ተረጋግጧል፡፡የዚህ ደብዳቤ ይዘት ዉሉ ጸንቶ በነበረበት ጊዜ የክፍያ ጥያቄ መቅረቡን አያሳይም በሚል አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ በሰጠዉ የቅድመ ክፍያ ዋስትና መሰረት ብር 422,500.06 መመለስ ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ለተጠሪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 32651 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 18/09/2013 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በመቀጠል አመልካች አቤቱታዉን ለከተማዉ ሰበር ሰሚ

ችሎት ቢቀርቡም ችሎቱ በመ/ቁ 33981 ላይ በቀን 12/11/2013 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አቤቱታውን ሰርዞበታል፡፡

አመልካች በቀን 19/11/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል የግንባታ ዉል እንጂ የአስተዳደር ዉል አለመሆኑንና አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ የንግድ ድርጅት መሆኑን ምክንያት በማድረግ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም ሲል አመልካች ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን ጉዳዩን በስረ ነገሩ ተመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41 እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1/ተ) ስር የተደነገገዉንና በሰ/መ/ቁጥር 149221 እና 145053 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ በቅድመ ክፍያ ዋስትና ዉሉ መሰረት አመልካች የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ ያለበት ዉሉ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ሲሆን ተጠሪ በቀን 27/01/2009ዓ/ም የጻፈዉ የዋስትና ገንዘብ ይታገድልኝ የሚል እንጂ የክፍያ ጥያቄ አይደለም፡፡የክፍያ ጥያቄ አይደለም እንጂ ነዉ ቢባል እንኳን ተጠሪ ክፍያዉ የሚፈጸምበትን አሰራር አለመግለጹም የሚያሳየዉ ጥያቄዉ የክፍያ ጥያቄ አለመሆኑን ነዉ፡፡በአጠቃላይ ተጠሪ ለአመልካች የጻፈዉ ደብዳቤ የዋስትና ገንዘቡ ታግዶ እንዲቆይለት ብቻ በመጠየቅ በሆነበት እንደ ክፍያ ጥያቄ ሊቆጠር የሚችል ነዉ ማለቱ ስህተት ነዉ፡፡የቅድመ ክፍያ ዋስትና ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄ አቅቦ እያለ አመልካች ክፍያ እንዲፈጽም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት የግንባታና ዋስትና ውሎችን መነሻ ያደረገና ያልተከፈለ ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበውን ክስ ተቀብሎ ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለዉ መሆን ስላለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1/መ) እና በሰበር መ/ቁጥር 149221 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች ከተሰጠዉ ትርጉም አንፃር እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 23/05/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ይዘቱም በአጭሩ፡- ተጠሪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ባደረገዉ የግንባታ ዉል መሰረት የግንባታ ሥራዉን እና ሂደቱን ለማሳለጥ ለግንባታ የሚያስፈልጉ ማናቸዉንም ግብአቶች የማቅረብ ኃላፊነት እንዲሁም የግንባታ ሥራ አፈጻጸሙን ያለማቋረጥ ተከታትሎ የማሰራት እና ጉድለት ሲኖርም እርምጃ የመዉሰድ የአሠሪዉ መስሪያ ቤት እንደሆነ በዉሉ የተመለከተ በመሆኑ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3132/ለ እና በሰ/መ/ቁጥር 80464 እና 178806 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት የአስተዳደር ዉል በመሆኑ ይህንን ዉል መነሻ ያደረገ ክስ የመዳኘት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/መ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥላለዉ በዚህ ረገድ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ የዋስትና ውል እራሱን ችሎ የሚቆም የውል ግንኙነት ሳይሆን ሌላ ውልን መሰረት አድርጎ የሚፈፀም የውል አይነት ሲሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1923/1 መሰረት ዋናው የውል ግዴታ ከሌለ የዋስትናው ውል ግዴታም

እንደማይኖር ይደነግጋል። በግራ ቀኞችን ያለው ክርክር ዋናው ውል ጉድለት የሌለበት ከመሆኑም በላይ አመልካች ውሉ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውል መሆኑን እያወቀ ዋስትና የሰጠና ዋስትና ውሉም የግንባታ ውሉን የሚከተል በመሆኑ የስረ ነገር ስልጣንም በዚሁ መልክ የሚታይ ስለሆነ አመልካች ያነሳው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም።የዋስትና ሰነዱ ያለቅደመ ሁኔታ የተደረገ ስለሆነ ተቋራጩ እንደዉሉ አለመፈጸሙን ተከትሎ ተጠሪ በጠየቀዉ በማንኛዉም ሰዓት ለመክፈል ግዴታ አለበት። ተቋራጩ እንደ ዉሉ አለመፈጸሙን ተከትሎ ተጠሪ ጥያቄ ያቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም።ተጠሪ ዋስትናዉ ታግዶ እንዲቆይ የጠየቀዉ አመልካች ለቅድመ ክፍያ የሰጠዉን የዋሰትና ገንዘብ ብር 5,360,347.60 በሙሉ ከመጠየቅ የተሰራዉን ስራ አጣርቶ እና ከክፍያዉ ላይ ቀናንሶ ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ተቋራጩ ሥራ ላይ ያላዋለዉን ለመጠየቅ በሚል በመሆኑ አመልካች ከሥራ ተቋራጩ ጋር በፍ/ብ/ሕጉ ስለዋስትና በተደነገገዉ መሰረት የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ስላለበት የዋስትና ገንዘቡ እንዲታገድ መጠየቁ እንደ ክፍያ ጥያቄ ማስጠንቀቂያ ሊቆጠር ይገባል ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም።የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36935 እና 40186 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ የቅድመ ክፍያ ዋስትና እንደብድር ዋስትና (financial guaranty bond) ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለባለገንዘቡ መክፈል እንዳለበት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል።በዚህ መሰረት የስራ ተቋራጩ ያልመለሰዉ የቅድመ ክፍያ መኖሩ ከታወቀ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር የተደነገገዉ የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ዉስጥ መጠየቅ ይቻላል።የዋስትና ዉሉ ላይ ያሉ ኃይለ ቃላት መተርጎም ያለባቸዉ የግንባታ ዉሉንና በግንባታ ዉል ተፈጻሚነት ያላቸዉን አጠቃላይ ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ሊተረጎም ይገባል።እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 96697 እና 47004 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በዋስትና ዉሉ ላይ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎች የተጠሪን መብት በሚገድብና የአመልካችን የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት በሚያስቀር መልኩ ሊተረጎም ስለማይገባ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት መልሱን በመስጠት ተከራክሯል። አመልካችም በቀን 15/06/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል።

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ በተጨማሪ አመልካች በቅደመ ክፍያ ዋስትና ዉሉ መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ይክፈል ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

በመጀመሪያም የስር የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የሚያስችል የዳኝነት ሥልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ መርምረናል።ተጠሪ በአመልካች እና አሁን በዚህ መዝገብ ተከራካሪ ባልሆኑት በስር 1ኛ ተከሳሽ (በሥራ ተቋራጭ) እና በስር 3ኛ ተከሳሽ(የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ስጭ) ላይ ክስ የመሰረተ ሲሆን የክሱም ይዘት የስር 1ኛ ተከሳሽ በግንባታ ዉሉ ላይ በተመለከተዉ አግባብና ጊዜ ዉስጥ ባለመፈጸሙ በቀን 04/13/2008ዓ/ም ዉሉ እንዲቋረጥ

መደረጉን ገልጾ ቅድመ ክፍያ ተከፍሎት ተመላሽ ያላደረገዉን ገንዘብ ብር 422,500.06፣ ከተጠሪ የግንባታ ግብአቶችን ተረክቦ በሥራ ላይ ያላዋለዉን ብር 11,890,574.81፣ የዉሃ ፍጆታ ክፍያ ብር 11,604.06፣ ሥራ በመንተቱ ምክንያት በዉሉ መሰረት የመዘግየት ክፍያ ብር 26,801.73፣ በመንተቱ ምክንያት ኪሳራ ብር 750,448.66 1ኛ ተከሳሽ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል፤ የሥር 3ኛ ተከሳሽ ደግሞ በመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና መሰረት ብር 2,330,585.91 እንዲከፍል እና የአሁን አመልካች ደግሞ በቅድመ ክፍያ ዋስትና መሰረት የሥር 1ኛ ተከሳሽ ተመላሽ ያላደረገዉን ብር 422,500.66 ከቀን 27/01/2009 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ዳኝነት የጠየቀበት ነዉ፡፡ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በፌዴራል መንግስት አካል የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በመሆኑና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የግንባታ ዉል የአስተዳደር ዉል ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም ሲል ተቃዉሞዉን ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የግንባታ ዉል የአስተዳደር ዉል ነዉ በሚል የዳኝነት ሥልጣን እንዳለዉ በመግለጽ የአመልካችን መከራከሪያ ዉድቅ አድርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3131 እና 3132 ስር በተደነገገዉ መሰረት አንድ ዉል የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ዉል ለመባል ከተዋዋዮቹ አንደኛዉ ወገን መንግስት ወይም ሌላ የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ሆኖ፡- (ሀ) ሕግ ወይም ተዋዋዮች ግልጽ በሆነ ቃል የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ዉል ነዉ ብለዉ ለዉሉ ስያሜ ሲሰጡት፤ (ለ) ዉሉ ከሕዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዘና ለሥራዉም አፈጻጸም የተዋዋዩን የአስተዳደር መሥሪያ ቤቱን ሥራ ተካፋይነት ሳይቋረጥ የሚጠይቅ ሲሆን፤ (ሐ) በዉሉ ዉስጥ በአስቸኳይ ለጠቅላላ ጥቅም (urgent considerations of general interest) ብቻ የሚያስፈልጉና የግል ሰዎች በሚያደርጓቸዉ ዉሎች ዉስጥ የማይገኙ አንድ ወይም ብዙ ዉለታዎች ያሉበት ሲሆን ነዉ ከሚሉ መመዘኛዎች አንዱን አሟልቶ ሲገኝ ነዉ፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/መ) የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች (administrative contracts) በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን በከተማው ፍርድ ቤት ሥር የሚወድቅ የዳኝነት ሥልጣን ነው፡፡እንዲሁም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ውል የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት ያደረጉት የአስተዳደር ውል እስከሆነ ድረስ በየትኛውም ገንዘብ መጠን ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

ለክርክሩ መሰረት የሆነዉ ተጠሪ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር በቦሌ አራብሳ ሳይትአራት ባለ ሰባት ፎቅ ወጪ ቆጣቢ የጋራ መኖሪያ ሕንጻዎች ለማስገንባት የተፈጸመዉ ዉል በግልጽ የአስተዳደር ውል የተባለ አለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ለማቋቋም ባወጣዉ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 5/5 እና 24 ላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ ለከተማዋ ነዋሪዎች ግልጋሎት የሚዉል ምቹና

ተደራሽ መኖሪያ ቤቶች ለመገንባትና ለማስገንባት የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካል ሆኖ የተቋቋመ በመሆኑ ለግራ ቀኙ ክርክር መሰረት የሆነዉ ዉል የአስተዳደር አካል ከሆነዉ ተጠሪ ጋር የተፈጸመ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ሕንጻዎቹን ለመገንባት የሚያገለግሉ የግንባታ እቃዎችን ለስር 1ኛ ተከሳሽ እያቀረበ 1ኛ ተከሳሽ እነዚህን የሚቀርቡለትን ግብዓቶች እየተጠቀመ ግንባታዉን የሚፈጽም መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡ ግብዓቶቹን የሚያቀርበዉ ተጠሪ ከሆነ ግብዓቶቹ ለሚገነቡት ሕንጻዎች ጥቅም ላይ መዋላቸዉን ለማረጋገጥ የተጠሪን ክትትል የሚጠይቅ ዉል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካችም በደፈናዉ የግንባታ ዉሉ የአስተዳደር ዉል አይደለም ብሎ ከመግለጽ ባለፈ በዉሉ አፈጻጸም ላይ ተጠሪ ስላለዉ ተሳትፎ ክዶ አልተከራከረም፡፡ ተጠሪ የመኖሪያ ቤቶቹን የሚያስገነባዉ ለከተማዉ ነዋሪዎች መሆኑ፣የመሬትና የመሰረተ ልማት አቅርቦት መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ፣ ለቤቶች ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችና የግንባታ እቃዎችን ገዝቶ የማቅረብ እና ከዲዛይን እስከ ኮንስትራክሽን ያሉት የሥራ ሂደቶች ደረጃቸዉን እንዲጠብቁ በማድረግ የቤት ልማት ፕሮግራሙ በቅልጥፍና እንዲከናወን የማድረግ ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠዉ የአስተዳደር መሥሪያ ቤት እንደሆነ በከተማ አስተዳደሩ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 24 ላይ የተመለከተዉ ያሳያል፡፡ ተጠሪ የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካል (የአስተዳደር መሥሪያ ቤት) ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ፣ በተጠሪና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተፈጸመዉ የግንባታ ዉልና ሕግ ተጠሪ ላይ ከጣለበት ተግባርና ኃላፊነት መገንዘብ የሚቻለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዋናዉ የግንባታ ዉል ከሕዝብ አገልግሎት ሥራ ጋር በቀጥታ የተያያዘና የተጠሪን የግንባታ ግብዓት ከማቅረብ ጀምሮ በግንባታ ሥራዉ አፈጻጸም ላይ ያልተቋረጠ ተካፋይነት እንደነበረዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡

ስለሆነም ለክሱ መሰረት የሆነዉ ዋናዉ የግንባታ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3132/ለ ስር በተመለከተዉ መመዘኛ መሰረት የአስተዳደር ዉል መሆኑን በግልጽ የሚያሣይ ነዉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/መ) ስር የከተማዉ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ወይም በከተማዉ አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸዉን አስተዳደራዊ ዉሎች በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑና ተጠሪና የስር 1ኛ ተከሳሽ ያደረጉት የግንባታ ዉል የአስተዳደር ውል በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ያለው ሆኖ አግንኝተነዋል፡፡

ሌላው ከከተማው አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚገባው የፌደራል መንግስት አካል ተመዝጋቢ የሆነዉ የአሁን አመልካችና የስር 3ኛ ተከሳሽ የክርክሩ ተሳታፊ መሆናቸዉ በዳኝነት ስልጣን ላይ ለውጥ ያመጣል አያመጣም የሚለው ነው፡፡ ተጠሪ ከግንባታ ውል አንጻር አመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ በአመልካች ላይ ደግሞ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ውል አኳያ ክሱን አጣምሮ አቅርቧል፡፡ክሱ በቀረበበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረዉ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/6 ላይ በፌደራል መንግሥቱ አካል የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶችን በሚመለከት የሚነሱ

ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን የፌደራል ፍርድ ቤቶች እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ አመልካች የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናዎች የሰጠው በተጠሪ እና በስር 1ኛ ተከሳሽ መካከል የተደረገውን የግንባታ ውል ውጤታማ ለማድረግ እንደመሆኑ ከአመልካች ጋር የተደረገው የዋስትና ውል የዋናው ውል ማለትም የግንባታ ውሉ ተቀጽላ ተደርጎ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነት በአንድነት ተጣምረው መታየት የሚችሉ ጉዳዮች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ተነጥሎ ከታየ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሊያሳካው የፈለገውን ጉልበት፣ወጭና ጊዜ(ሀብት) ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክርን የመምራት ዓላማ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 17/2 ላይ በአንድ ክስ ውስጥ የተለያዩ ዳኝነቶች ሲቀርቡ ዋናውን ወይም ከፍተኛውን ዳኝነት የሚመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን እንዳለው ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ዋናው የክስ መሠረት ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር የተደረገው የአስተዳደር ውል የሆነው የግንባታ ውል ሲሆን በዚህ ውል ላይ ማን ግዴታውን አልተወጣም የሚለውን ተከትሎ የአመልካች ኃላፊነትም የሚወሰን በመሆኑ አመልካች ላይ የተጠየቀው ዳኝነትም ተከታይና ተጨማሪ ዳኝነት በመሆኑ ዋናውን ዳኝነት ለመወሰን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት አብሮ መወሰን ይኖርበታል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 96216 ቅጽ 16 ላይም ተመሳሳይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 149221 ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ የግንባታ ግብአቶች የማቅረብና ግብአቶቹ ለግንባታ ሥራዉ መዋላቸዉን የመከታተል ኃላፊነት የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ባልተሰጠ ዉል ላይ የተመሰረተ ክርክር መነሻ ተደርጎ የተሰጠ የሕግ ትርጉም በመሆኑ እና በሰ/መ/ቁጥር 145053 ላይ የተሰጠዉም የሕግ ትርጉምም ከዳኝነት ሥልጣን ጋር የተያያዘ ቢሆንም የክሱ ስረ ነገር የነበረዉ የዉሃ ፍጆታ ዉል በመሆኑ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር የጭብጥ ልዩነት ያለበት በመሆኑ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያላቸዉ አይደሉም፡፡ይልቁንም ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 178806 በቀን 28/11/2012 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ(ያልታተመ) ላይ የተጠቀሰዉ አይነት የአስተዳደር አካል ተሳትፎ ያለባቸዉ የግንባታ ዉሎች የአስተዳደር ዉል የሚያሰኝ መስፈርት እንደሚያሟሉ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 193208 በቀን 30/06/2013 ዓ/ም (ያልታተመ) በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሥልጣን ከሚመለከተዉ የአስተዳደር ዉል ጋር ተያይዞ የቅድመ ክፍያ እና የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ዉሎች በተመለከተም የከተማ አስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን እንዳለቸዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ከላይ እንደተመለከተው ከዋናው የግንባታ ውል ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የመዳኘት ስልጣን የከተማው ፍርድ ቤቶች በመሆኑ ከአመልካች አንጻር የተጠየቀውን ዳኝነትም የከተማው ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ስልጣን አላቸው ብለናል፡፡ ስለሆነም የስር የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንዳለዉ ገልጾ የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ሌላዉ የዚህን ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ ጭብጥ አመልካች በቅደመ ክፍያ ዋስትና ዉሉ መሰረት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን?የሚመለከት ነዉ፡፡እንደመረመርነዉም አመልካች በስር 1ኛ ተከሳሽ ጠያቂነት ለተጠሪ የሰጠዉ በሰነዱ ላይ Advance payment Guarantee ተብሎ የተገለጸ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡አመልካች በዚህ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ መሰረት የስር 1ኛ ተከሳሽ ከተጠሪ ላይ በቅድመ ክፍያ መልክ የወሰደዉን ገንዘብ ከቀን 04/02/2008ዓ/ም እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ ባይመልስ በዚህ ጊዜ ዉስጥ በተጠሪ ጥያቄ ሲቀርብለት አመልካች እስከ ብር 5,360,347.60 ድረስ ለተጠሪ ለመክፈል ግዴታ መግባቱን የሥር ፍርድ ቤት ከሰነዱ ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ ተጠሪ በሰነዱ ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ የስር 1ኛ ተከሳሽ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የወሰደዉን ገንዘብ ሥራ ላይ አለመዋሉን ገልጾ አመልካች በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ መሰረት የክፍያ ጥያቄ አቅርቧል ወይስ አላቀረበም? በሰነዱ ላይ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄዉን ያላቀረበ ከሆነ ሕጋዊ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚሉ ጭብጦች ናቸዉ፡፡ከዚህ አኳያ ተጠሪ ያነሳዉ ክርክር በቀን 27/01/2009 ዓ/ም ለአመልካች በጻፈዉ ደብዳቤ የስር 1ኛ ተከሳሽ በዉሉ መሰረት እየሰራ ስላልሆነ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ዉሉ ስለተቋረጠ ብሩ ይታገድልኝ በሚል ስለጠየቅሁ የክፍያ ጥያቄ እንደቀረበ ይቆጠራል በሚል ሲሆን አመልካች ደግሞ ተጠሪ ከቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ ዉጭ ዋስትናዉ ታግዶ እንዲቆይ መጠየቁ በቅድሚያ ዋስትና ዉሉ መሰረት የክፍያ ጥያቄ እንዳቀረበ አያስቆጥርም በሚል ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል የወሰነዉ ተጠሪ በቀን 27/01/2009 ዓ/ም የጻፈዉ ደብዳቤ የዋስትና ዉሉ ጸንቶ ባለበት ጊዜ የተጻፈ በመሆኑና ይህ ደብዳቤ ተጠሪ በቀን 05/07/2010 ዓ/ም ክፍያ ይፈጸምልን ሲል ከጻፈዉ ጋር ተያይዞ ሲታይ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄዉን ዉሉ ጸንቶ ባለበት ጊዜ አልጠየቀም የሚያስብል አይደለም በማለት ነዉ፡፡

ከላይ በተመለከተዉ አግባብ ለቀረበዉ የግራ ቀኙ ክርክር ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ (Advance Payment Guarantee/Bond) ምነትና ከሌሎች የዋስትና አይነቶች ያለዉ አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡በዚህ ረገድ መታየት ያለበት ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36935፣ 40186 እና 47004 (ቅጽ 13 ላይ የታተሙ)የሕግ ትርጉም ነዉ፡፡በእነዚህ መዛግብት ላይ በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ የዋስትና ዉሎች ናቸዉ የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶባቸዋል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 47004 ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) ማለት አንድ ሰዉ አንድን የተለየና የተወሰነ ሥራ ለሌላ ሰዉ ለመስራት ግዴታ ከገባ ይኸዉ ሰዉ በዉሉ መሰረት የገባዉን ግዴታ መፈጸም የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ ሌላዉ

ሰዉ የሚያቀርበዉ ዉል ነዉ፡፡ እንዲሁም ከኮንስትራክሽን ሥራ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ለኮንስትራክሽን ሥራዉ በዉሉ መሰረት መከናወን ዋስትና የሚሰጥ ሰነድ እንደሆነ ትርጉም ሰጥቷል፡፡በሌላ በኩል በሰ/መ/ቁጥር 36935 እና 40186 ላይ በተሰጠ የሕግ ትርጉም ላይ እንደተመለከተዉ የገንዘብ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ሌላ ሰዉ ያለበትን የገንዘብ እዳ በገባዉ ዉል መሰረት ባይከፍል ሌላ ሰዉ ራሱ ለአበዳሪዉ እንደሚከፍል ገልጾ ራሱን ግዴታ ዉስጥ የሚያስገባበት የማገቻ ሰነድ እንደሆነ የተለያዩ ሕግጋትን በማጣቀስ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጓሜዎች ላይ ስለ ቅድሚያ ክፍያ ዋስትና (Advance Payment Guarantee/Bond) ምንነትና ከመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና እና ከገንዘብ ዋስትና ሰነድ ጋር ያለዉ አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆነ የተመለከተ ነገር ባለመኖሩ ምንነቱን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 2/1 ስር በተሰጠዉ ትርጓሜ መሰረት "የቅድሚያ ክፍያ" ማለት የዋጋ ልዉዉጥ ያልተደረገበት እና ተቀባዩ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚያወራርደዉ ክፍያ ሲሆን ዉልን መሰረት በማድረግ በዉሉ የተመለከተዉ ግዴታ ከመጠናቀቁ በፊት በየደረጃዉ የሚደረግን ክፍያ አይጨምርም የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡በሌላ በኩል ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በወጣ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 2/2 ላይ "ማገቻ(Bond) ማለት የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰዉ ለሌላዉ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸዉንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ፣ ነገር ግን በትእዛዝም ሆነ ለአምጪዉ የማይከፈልበት አንድ ሰዉ ለሌላዉ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸዉንም ሰነድ ይጨምራል፡፡"የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡በተጨማሪም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3271 ስር ሥራ ተቋራጩ ከመስሪያ ቤቱ ጋራ ስለ ተዋዋለዉ ሥራ አስቀድሞ ገንዘብ ለመቀበል የሚችለዉ ለዚሁ አስቀድሞ ለሚከፈለዉ ገንዘብ እጅግ ቢያንስ ግማሹን መልሶ ለመክፈል የሚችል አንድ ዋስ ወይም ሌላ ዋስትና ከሰጠ በኋላ ሆኖ በዚህ መልኩ አስቀድሞ የሚከፈለዉ ገንዘብ በሥራዉ ዉል ጊዜ በተወሰነዉ መሰረት ወደፊት ሥራ ተቋራጩ ከሚፈልጋቸዉ ቀሪ ገንዘቦች ላይ ተቀናሽ የሚሆን ገንዘብ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ከተጠቃሾቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ በተለይ ከግንባታ(ከኮንስትራክሽን) ዉል ጋር በተያያዘ ሥራ ተቋራጩ ከአሠሪዉ ጋር በገባዉ ዉል መሰረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ለወደፊት ሥራ ሰርቶ በየጊዜዉ ከሚከፈለዉ ክፍያ ላይ እየተቀነሰ ለአሰሪዉ ተመላሽ እንደሚያደርግ ወይም እንደሚከፍል በመስማማት አስቀድሞ የሚቀበለዉ ገንዘብ ቅድሚያ ክፍያ የሚባል ሲሆን፣ በዚህ መልኩ ሥራ ተቋራጩ ከአሠሪዉ በቅድሚያ የሚቀበለዉን ገንዘብ በዉሉ በተወሰነዉ ጊዜ የግንባታ ሥራ ሰርቶ ከሚከፈለዉ ገንዘብ ላይ በየጊዜዉ እየቀነሰ ለአሰሪዉ(ለከፋዩ) ካልመለሰ ወይም መመለስ ካልቻለ ሌላ ሶስተኛ ወገን በዚህ መልኩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ ለሥራ ተቋራጩ የተሰጠዉን ገንዘብ ወይም ሥራ ተቋራጩ ሳይመለስ የቀረዉን ገንዘብ እከፍላለዉ ብሎ ራሱን ግዴታ ዉስጥ የሚያስገባበት ዉል ደግሞ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉል (Advance Payment Guarantee/Bond) እንደሚባል ነዉ፡፡

ስለሆነም የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉል (Advance Payment Guarantee/Bond) የሚሰጥበት ምክንያት ከመለየቱ በስተቀር ዓላማዉ ቅድሚያ ክፍያ ለሥራ ተቋራጩ የከፈለዉ አሠሪ ሥራ ተቋራጩ በዉሉ መሰረት የተቀበለዉን ገንዘብ በየጊዜዉ ከአሠሪ ከሚከፈለዉ ገንዘብ ላይ እየተቀነሰ ተመላሽ እንዲደረግ ማድረግ ባልቻለ ጊዜ ሦስተኛ ወገን ወይም በተግባር እንደሚሰራዉ ደግሞ ባንኮች ለሥራ ተቋራጩ ዋስ በመሆን የሚሰጡት የዋስትና ሰነድ በመሆኑ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ሰነድ (Financial Guarantee Bond) ከሚሰጥበት ዓላማ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ያለዉ ነዉ፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 36935፣ 40186 እና 47004 (ቅጽ 13 ላይ የታተሙ) በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እስከ 1951 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዙ የዋስትና ዉሎች ናቸዉ ተብሎ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንደተሰጠዉ ሁሉ በሥራ ተቋራጩ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የተወሰደዉ ገንዘብ ለአሠሪዉ የሚመለስ ስለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን የሚሰጥ የቅድሚያ ክፍያ ማገቻ ሰነድም (Advance Payment Guarantee/Bond) በሰነድ ሰጪዉና በተጠቃሚዉ(ቅድሚያ ክፍያ በከፈለዉ አሠሪ) መካከል የዋስትና ዉል የሚያቋቁም ሰነድ በመሆኑ በእነዚሁ የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚገዛ ነዉ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በያዝነዉ ጉዳይ ላይ እንደሆነዉ የግንባታ ዉሉ የአስተዳደር ዉል በሆነ ጊዜ የአስተዳደር ዉል በሆነዉ የግንባታ ዉል መነሻ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ተመላሽ የሚደረግ ስለመሆኑ ዋስትና እንዲሆን በሌላ ሰዉ የሚሰጥ ሰነድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3271 ስር እንደተደነገገዉ የዋስትና ዉል ተደርጎ የሚቆጠር ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ እንደዋስትና ዉል የሚቆጠር ስላልሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የላቸዉም ሲል ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል ከላይ በተጠቀሱት በሰ/መ/ቁጥር 36935፣ 40186 እና 47004 ላይ በተሰጡ ዉሳኔዎች ላይ መልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ሰነድ (Performance Guarantee Bond) እና የገንዘብ ዋስትና ግዴታ ሰነድ (Financial Guarantee Bond) መሰረት ያደረገ የክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ጊዜ ዉስጥ ክሱ ካልቀረበ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡በዚህ መልኩ የሕግ ትርጉም የተሰጠዉ ዉሎቹ የዋስትና ዉል በመሆናቸዉ በዋሱ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የይርጋ ጊዜ በዋናዉ ባለዕዳ ላይ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ጊዜ ስለሆነ እና ግንኙነቱም የኢንሹራንስ ዉል ግንኙነት ስላልሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 674/1 ስር የተደነገገዉ የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነት የለዉም በሚል መነሻ ነዉ፡፡የሕግ ትርጉሙ ሊሰጥ የቻለዉም በግልጽ በመዝገቦቹ ላይ የይርጋ መቃወሚያ ተነስቶ ክርክር ተደርጎበት በበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ

መቃወሚያ እና ተፈጻሚነት ስላለዉ ሕግ በተመለከተ ግልጽ ዉሳኔ ተሰጥቶ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ስለነበር ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች በግልጽ ቅድሚያ ክፍያ መነሻ በማድረግ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ታግዷል ሲል በግልጽ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ላይ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ያቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የለም፡፡ የቀረበዉ ክርክር ተጠሪ በዋስትና ሰነዱ መሰረት የክፍያ ጥያቄዉን ከቀን 04/02/2008ዓ/ም እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ አላቀረበም የሚል ነዉ፡፡ ከላይ እንደተመለከትነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነድ የዋስትና ዉል በመሆኑ ይህንን ዉል መነሻ ያደረገ ክስ ማቅረብ የሚቻለዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር በተደነገገዉ መሰረት በ10 ዓመት ጊዜ ዉስጥ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1855 ስር በተደነገገዉ መሰረት ክስ የማቅረብ መብት ቀሪ የሚሆንበት ጊዜ ገደብ ወይም ይርጋ የሚደነገገዉ በሕግ ሲሆን ሕግ የወሰነዉ የይርጋ ጊዜ እንዲቀር ወይም እንዲለወጥ አስቀድሞ ለመስማማት ወይም ለመዋዋል አይቻልም፡፡በመሆኑም በግራ ቀኙ መካከል በተፈጸመዉ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉል ላይ "ከቀን 04/02/2008ዓ/ም እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ" ተብሎ የተመለከተዉ ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች የክፍያ ጥያቄ የሚያቀርብበት ጊዜ እንጂ ክስ የማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡

ሆኖም ተጠሪ በ10 ዓመት ጊዜ ዉስጥ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉል መሰረት ያደረገ ክስ ማቅረብ የሚችለዉ በዋስትና ዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ማለትም ከቀን 04/02/2008 ዓ/ም እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ" ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ይከፈለኝ የሚል ጥያቄ ለአመልካች አቅርቦ አመልካች የክፍያ ጥያቄዉን ሳይቀበል ከቀረበት ቀን ጀምሮ ነዉ፡፡ ዉሉ የዋስትና ዉል ቢሆንም ከሌላዉ ዋስትና ልዩ የሚያደርገዉ ባህርይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1920 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ዋስ የዋስትና ግዴታ ዉስጥ የሚገባዉ ለራሱ ጥቅም በማግኘት ባለመሆኑ፤በባንኮች ወይም በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የሚሰጥ ቅድመ ክፍያ ዋስትና፣የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና …ወዘተ ግን ባንኮች ወይም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች የንግድ ድርጅቶች በመሆናቸዉ ዋስትናዎቹን ሲሰጡ ዋስትና እንዲሰጠዉ ከሚያመለክተዉ ሰዉ ላይ ባላቸዉ አሰራር መሰረት ክፍያ ወይም መያዣ በመቀበል በመሆኑ እና በዚህ መልኩ የሚቀበሉት ክፍያ ወይም መያዣ በጊዜ የተገደበ ስለሚሆን በዋስትና ሰነዱ ላይ ከተመለከተዉ ጊዜ ዉጭ የዋስትና ሰነዱ ተጠቃሚ የክፍያ ጥያቄ ባቀረበበት በማንኛዉም ጊዜ ክፍያ መፈጸም አለባቸዉ የሚባል ከሆነ በባንኮች፣ በስተጀርባቸዉ ባሉት ባለአክሲዮን፣ ገንዘብ አስቀማጮች ላይ ብሎም በአገር ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት ስለሚደርስ የዋስትና ሰነዱ ተጠቃሚ የክፍያ ጥያቄዉን በዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

እንዲሁም በቅድሚያ ዋስትና ሰነዱ ላይ "…በዚህ ዋስትና ስር የሚቀርብ ማንኛዉም የክፍያ ጥያቄ እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ መቅረብ የሚኖርበት ሲሆን በእኛ በኩል ጥያቄዎች ተቀባይነት

የሚኖርባቸዉ ከመቀበያዉ ቀን በፊት ወይም በእለቱ ነዉ፡፡…" በሚል የተገለጸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1865 ስር በስምምነቱ ወይም በልዩ ሁኔታዉ ለባለገንዘቡም እንዲጠቅም ተብሎ ካልተደረገ በቀር የጊዜዉ መሰጠት ሁልጊዜ ለባለዕዳዉ ጥቅም እንደተደረገ ይቆጠራል በሚል ከተደነገገዉ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከተዉ ተጠቃሹ ጊዜ በዋናነት ለአመልካች ጥቅም የተቀመጠ እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡በመሆኑም የተጠሪ ክስ ተቀባይነት አግኝቶ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንዲከፍል ሊወሰን የሚችለዉ ተጠሪ የክፍያ ጥያቄዉን እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ ማቅረቡ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ፡፡

ነገር ግን የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የክፍያ ጥያቄዉን በቅድሚያ ክፍያ ዉሉ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ አቅርቧል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የማስረጃ ምዘና ከሚመለከተዉ መሰረታዊ መርህ አተገባበር አኳያ መመርመር ያለበት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡የስር ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰዉ ተጠሪ በቀን 27/01/2009ዓ/ም በቁጥር ቢ/ግ/ቅ/13/24/246/09 ለአመልካች የጻፈዉን ደብዳቤ ይዘት ጠቅሶ የደብዳቤዉ ይዘት *"የስር 1ኛ ተከሳሽ በዉሉ መሰረት እየሰራ ባለመሆኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ዉሉ ስለመቋረጡ ጠቅሶ ብሩ ይታገድልን ፡፡"* የሚል በመሆኑ የዚህ የደብዳቤ ይዘት ተጠሪ በቀን 05/07/2010ዓ/ም ክፍያ ይፈጸምልኝ ብሎ ለአመልካች ከጻፈዉ ደብዳቤ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተጠሪ በቀን 27/01/2009 ዓ/ም በጻፈዉ ደብዳቤ የክፍያ ጥያቄ አላቀረበም የሚያስብል አይደለም በሚል ነዉ፡፡ሆኖም ተጠሪ ተገቢዉን ማስረጃ አቅርቦ ማስረዳት የሚገባዉና የስር ፍርድ ቤትም ተጠሪ ማስረዳቱን ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ተጠሪ የክፍያ ጥያቄዉን እስከ ቀን 28/01/2009ዓ/ም ድረስ ለአመልካች ማቅረቡን ቢሆንም ተጠሪ በቀን 27/01/2009ዓ/ም ለአመልካች የጻፈዉ ደብዳቤ ይዘት በግልጽ የሚያሳየዉ በዚህ ደብዳቤ የጠየቀዉ የዋስትና ገንዘብ እንዲታገድ እንጂ በዋስትና ሰነዱ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ እንዲከፈለዉ መጠየቁን የሚያሳይ አይደለም፡፡እንዲሁም በዋስትና ዉሉ ላይ የተመለከተዉ ጊዜ ካለፈ በኋላ 1 ዓመት ከ6 ወር በላይ ቆይቶ ክፍያ ይፈጸምልኝ በማለት ተጠሪ በቀን 05/07/2010 ዓ/ም ለአመልካች የጻፈዉ ደብዳቤም በቀን 27/01/2009ዓ/ም ከተጻፈዉ ደብዳቤ ጋር ተጣምሮ መታየቱም የሕግ መሰረት የሌለዉና በዉሉ የተመለከተዉ ጊዜ ለአመልካች ጥቅም መቀመጡን ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ዉሉ ላይ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ የክፍያ ጥያቄ አቅርቧል በማለት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ ይክፈል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ተጠሪ በማስረጃነት ባቀረበዉና በቀን 27/01/2009ዓ/ም ከተጻፈዉ የሰነድ ማስረጃ ግልጽ ይዘት ዉጭ ከመሆኑም በተጨማሪ የዉሉን የጊዜ ሁኔታና ዓላማ ያላገናዘበ ነዉ ብለናል፡፡ አንድን ክርክር ለማስረዳት የቀረበ ማስረጃ ይዘትን ያላገናዘበ ዉሳኔ መስጠት የማስረጃ ምዘና የሚመለከት መሰረታዊ መርህ የጣሰ ሰለሚሆን መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 44804 ላይ(በቅጽ 11 እንደታተመዉ) እና በሰ/መ/ቁጥር 121094 ላይ እና በሌሎች

መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡በመሆኑም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለአመልካች እንዲከፍል በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወሰኖ በየደረጃዉ በከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እና በሰበር ሰሚ ችሎት የጸናዉ ዉሳኔ የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርህና የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18052 ላይ በቀን 20/01/2013 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32651 ላይ በቀን 18/09/2013 ዓ/ም የሰጠው ዉሳኔ እና የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 33981 ላይ በቀን 12/11/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ቅድሚያ ክፍያ ዋስት ዉል መሰረት ተደርጎ የተጠየቀዉን ብር 422,500.00(አራት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡ይህንን ገንዘብ የስር 1ኛ ተከሳሽ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የተባለዉ የዉሳኔ ክፍል እና ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 207446

መጋቢት 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ፍሬህይወት ጋሜ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ኤልሳቤት ኪ/ማሪያም

2ኛ. ኤስኤን ቢ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ቤት ገንብቶ የማስረከብ ዉል አፈጻጸም መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረዉ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት በመቃወም የተከራከሩ ናቸዉ፡፡ የክሱም ይዘት በአጭሩ፡- ከተጠሪ ጋር በቀን 19/11/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል ስምምነት 2ኛ ተጠሪ G+1 የሆነ የቤተሰብ መኖሪያ ቤት በ9 ወራት ውስጥ ገንብቶ ስመ-ንብረቱን በ1ኛ ተጠሪ ስም ለማስረከብ ግዴታ የገባ ሲሆን፤ 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ብር 4,478,000.00 ለመክፈል ስምምነት አድርገናል፡፡በዚህ መሰረት 1ኛ ተጠሪ በውሉ አንቀፅ 3/6 ስር በተቀመጠው የአከፋፈል መንገድ በአጠቃላይ ብር 3,950,000 የከፈልኩ ቢሆንም ተከሳሽ በውሉ መሰረት በ9 ወራት ውስጥ ቤቱን ገንብቶ ስመ ንብረቱን በ1ኛ ተጠሪ ስም አስመዝግቦ የማጠቃለያ ሥራ አከናውኖ በውል በገባው ግዴታ መሰረት ሊያስረክበኝ አልቻለም፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በውሉ መሰረት በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 16 ከተሰሩት 28 ነጠላ የቤተሰብ ቤቶች ቪላ ውስጥ በስሜ ሲከፈልበት የነበረውን ብሎክ ሲ6 የካርታ ቁጥር 4/9/9/22/521/00 የሆነውን ቤት ገንብቶ አጠናቆ ስመ ንብረቱን በ1ኛ ተጠሪ ስም አስመዝግቦ ከሊዝ ክፍያ ነፃ የሆነ ቤት በውሉ ግዴታ መሰረት እንዲያስረክበኝ፤ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገንብቶ ሊያስረክበኝ ከሚገባው ጊዜ በእጅጉ የዘገየ በመሆኑ ማስረከብ

ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ በወር ብር 5,000.00 እና ለደረሰብኝ መጉላላት ኪሳራ በውሉ መሰረት ተሰልቶ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በሐምሌ 19 ቀን 2003 ዓ/ም ላይ ቤት ገንብቶ ለማስረከብ የውል ስምምነት እንዳደረገ አምኖ ነገር ግን ከመንግስት በተሰጠ ትዕዛዝ በተያዘው መሬት ላይ ማንኛውም የቤት ግንባታ እንዳይደረግ እገዳ ተጥሎበት ከቆየ በኋላ እግዱ የተነሳው በቀን 15/12/2006 ዓ/ም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለሁለት ዓመታት ያህል ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት 2ኛ ተጠሪ የቤት ግንባታውን ማከናወን አልቻለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ ለ2ኛ ተጠሪ የከፈሉት በክሱ ላይ እንደገለፁት ሳይሆን ብር 3,450.000 ብቻ ነው፡፡ በውሉ መሰረት ቀሪ ክፍያቸውን ብር 1,028,000.00 ከፍለው እንዲረከቡ 2ኛ ተጠሪ በተደጋጋሚ በቃልና በፅሁፍ የጠየቀ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ግን ብር የለኝም በማለት ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡ 2ኛ ተጠሪ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ከ9 ወራት በኋላ በቀን 09/09/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ 1ኛ ተጠሪ እንደ ውሉ ሊፈፅሙ ባለመቻላቸው በውል ስምምነታችን መሰረት ከከፈሉት ገንዘብ ላይ 3 ፐርሰንት ተቀንሶ የከፈሉት ገንዘብ ከሚመለስላቸዉ በቀር ቤት ለመረከብ ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ በውል ስምምነታችን መሰረት ክፍያ ባለመፈፀማቸው 2ኛ ተጠሪ 1ኛ ተጠሪ የጠየቁትን ክፍያ በርትዕ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ዉሉ የፈረሰዉ 1ኛ ተጠሪ ግዴታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ምክንያት በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ አይገደድም ተብሎ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 199597 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 03/05/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪዎች በቀን 19/11/2003 ዓ/ም ባደረጉት ውል መሰረት 1ኛ ተጠሪ ያለባቸዉን ቀሪ ክፍያ ባለመክፈላቸዉ የበኩላቸዉን ግዴታ ሳይወጡ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስረከብ አይገደድም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡1ኛ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 153192 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 06/09/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በጊዜዉ ገንብቼ ማስረከብ ያልቻልኩበት ምክንያት ግንባታ እንዳይካሄድ በመንግስት እግድ በመሰጠቱ ነዉ በማለት የተከራከረዉን በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ እግዱ ሳይሰጥ በፊት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገንብቶ ለማስረከብ የሚያስችል በቂ ጊዜ ነበረዉ፤2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገንብቶ አስረክቦ በዉሉ መሰረት መሰብሰብ ሲገባዉ ዉሉን በተናጠል ማቋረጡ ተገቢ አይደለም፡፡የስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ግዴታቸዉን ሳይወጡ 2ኛ ተጠሪ ግዴታቸዉን እንዲወጡ መጠየቅ አይችሉም ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ የግራ ቀኙን ዉል ይዘት ያገናዘበ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት ግንባታ አጠናቆ ስመ ሀብቱን ወደ 1ኛ ተጠሪ እንዲያዛዉሩ፤2ኛ ተጠሪም ቀሪ ክፍያ የመጠየቅ መብት አለዉ ሲል ወስኗል፡፡

በመቀጠል 2ኛ ተጠሪ በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በመ/ቁጥር 159065 ላይ አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 24/03/2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የይግባኝ ሰሚዉን ውሳኔ በማሻሻል 2ኛ

ተጠሪ ቤቱን አጠናቆ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ እና ስመ ሀብቱን እንዲያዛውር ሲል የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በማፅናት ቀሪ ክፍያውን በተመለከተ 2ኛ ተጠሪን ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብት በመጠበቅ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ክርክሩ በዚያው መዝገብ ቀጥሎ ክፍያውን በተመለከተ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ሲል ጉዳዩን በዚህ ረገድ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

ጉዳዩ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ከተወሰነ በኂላ እንደገና የተንቀሳቀስዉ አመልካች በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መብታቸዉ እንደተነካ በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ሲሆን የአቤቱታቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- የመቃወም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ በቀን 10/01/2010 ዓ/ም ድርድር ተደርጎ በቀን 27/01/2010 ዓ/ም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት በተደረገ ዉል 2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለአመልካች በብር 4,500,000.00 ሸጧል፡፡አመልካች ቤቱን የገዛሁት ቤቱ ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ አመልካች የቤቱ ባለሀብት ከሆንኩ በኂላ ቤቱን ተረክቤ ብር 873,120.00 ተጨማሪ ወጪ በማዉጣት ቤቱን በአመልካች ፍላጎት መሰረት ምቹ ለማድረግ ተጨማሪ ማስተካከያ/ግንባታ አድርጌያለሁ፡፡ 2ኛ ተጠሪም ከአመልካች ጋር ግብይት ባደረገ ጊዜ በቤቱ ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ክርክር እንዳለው አላሳወቀኝም፡፡ አመልካች ቤቱን ከ2ኛ ተጠሪ ስለተረከብኩ 1ኛ ተጠሪ ከግንባታ ዉሉ ጋር የተያያዘ ግንኙነት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ከሚኖረዉ በስተቀር በቤቱ ላይ መብት የላቸዉም ተብሎ ዉሳኔዉ እንዲሻርላቸዉ አቤታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ በቀን 15/06/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የ2ኛ ተጠሪ ማኀበር 50 ከመቶ ባለአክሲዮ/ባለድርሻ የሆኑት የአቶ ዳዊት ዘሪሁን ባለቤት በመሆናቸዉ ሽያጩ እዉነት አይደለም እንጂ እዉነት ነዉ ቢባል እንኳን ሽያጩ ከባለቤታቸዉ ጋር የተደረገ በመሆኑ አስቀድሞ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገዉ ፀንቶ ባለበትና ክርክርም በፍርድ ቤት መኖሩን ባለአክሲዮኖች እያወቁ አመልካች የትዳር አጋራቸዉ በመሆናቸዉ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ተይዞ ያለ በመሆኑ በድጋሚ መሸጥ ያልተገባ ድርጊት ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አደረጉት የተባለዉ ዉል በእዉነት ላይ የተመሰረተ ግብይት ሳይሆን ሆነ ተብሎ ቤቱ ለ1ኛ ተጠሪ እንዳይተላለፍና ፍርድ እንዳይፈጸም ለማድረግ የቀረበ አቤቱታ ነዉ በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ አስቀድሞ የሰጠዉን ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 360/2 በመሰረት በማጽናት ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች ለዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱም በመ/ቁጥር 172487 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 28/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በግልጽ የቀረበን ክርክር እና የተቆጠረን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ አለመስጠት መሰረታዊ የክርክር አመራር ጉድለት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹን መሰረት በማድረግ

በሰ/መ/ቁጥር 37105፣39144 እና በተለያዩ የሰበር መዝገቦች ላይ አስገዳጅነት ያለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡አመልካች አስቀድሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ወደ ክርክሩ መግባት ይችሉ ነበር የሚለዉ የ1ኛ ተጠሪ መከራከሪያ ተገቢነትና ዉጤቱ፣ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል የማስመሰል ዉል ነዉ በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መከራከሪያ እና ማስረጃዎች ተገቢነትና ዉጤቱ፣ዉሉ እዉነተኛ ዉል ነዉ ቢባል እንኳን ዉሉ የተደረገዉ በአመልካች እና የአመልካች የትዳር አጋር ባለአክሲዮን በሆኑበት 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገ ዉል መሆኑ ከሦስተኛ ወገን መብት አንጻር የሚኖረዉ ዉጤት ከሕግ አንጻር የሚያስከትለዉ ዉጤት፣ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ከ1ኛ ተጠሪ መብት አንጻር ተፈጻሚነት ሊኖረዉ አይገባም ቢባል አመልካች በቤቱ ላይ ተጨማሪ የማስተካከያ ግንባታ አድርገዋልን?አድርገዋል ከተባለ የወጪ መጠንና ዉጤቱስ ምን ሊሆን ይገባል? አመልካች ቤቱን ከገዙ በኋላ ቤቱ አሁን በሚገኝበት ሁኔታ የደረሰዉ በአመልካች ገንዘብ ነዉ ከተባለ እና በሌላ በኩል ሻጭ ለማስረከብ የሚገደደዉ በ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ የተገነባዉን ነዉ የሚለዉንና ቤቱ በሶስተኛ ወገን እጅ መኖሩ የሚፈጥረዉ ሕጋዊ ዉጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚሉትንና ተያያዥ ጭብጦች በማስረጃ አጣርቶ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ለይግባኝ ሰሚዉ ችሎት መልሶለታል፡፡

ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከፍ ሲል በተገለጸዉ መሰረት የተያዙትን ጭብጦች ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎች አንጻር መርምሮ በቀን 26/08/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አከራካሪዉን ቤት በተመለከተ ክስ መቅረቡንና ክርክር መኖሩን አስቀድሞ አመልካች ያዉቁ የነበረ መሆኑን ለማስረዳት 1ኛ ተጠሪ አቅርበዉ ያሰሟቸዉ ምስክሮች በክርክራቸዉ መሰረት አላስረዱም፡፡ የ2ኛ ተጠሪ ባለድርሻ የሆኑት አቶ ዳዊት ዘሪሁን የአመልካች የትዳር አጋር በመሆናቸዉና አቶ ዳዊት ዘሪሁን ደግሞ የክርክሩን መኖር ያዉቁ ስለነበር በተዘዋዋሪ መንገድ አመልካች የክርክሩን መኖር ያዉቁ እንደነበር ግምት ይወሰድልኝ ሲሉ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር በግምት ላይ የተመሰረተ ከሚሆን በስተቀር በማስረጃ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ አመልካች የክርክሩን መኖር አስቀድመዉ ያዉቁ ነበር በማለት ያቀረቡትን ክርክር በማስረጃ አላስረዱም በማለት ወስኗል፡፡

እንዲሁም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል እዉነተኛ ዉል ነዉ ወይስ የማስመሰል ዉል ነዉ የሚለዉን ጭብጥ በተመለከተም የ2ኛ ተጠሪ ባለድርሻዎች አቶ ቴዎድሮስ ዘሪሁን ላቀዉ እና አቶ ዳዊት ዘሪሁን ላቀዉ መሆናቸዉ እና አቶ ዳዊት ዘሪሁን ከአመልካች ጋር በጋብቻ ተሳስረዉ የሚኖሩ መሆናቸዉ ግራ ቀኙ የማይካካዱትና በማስረጃም የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸዉ፡፡አመልካች የቤት ሽያጭ ዉሉን ባለቤታቸዉ አባል ከሆኑበት ኃላፊነቱ ከተወሰነ የግል ማኅበር ጋር መዋዋላቸዉ በራሱ ዉሉን የማስመሰል ዉል የሚያደርገዉ አይደለም፡፡ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በቀን 24/02/2010ዓ/ም ሲሆን ክስ ከማቅረባቸዉ በፊት ከ2ኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር በቤቱ ጉዳይ አለመግባባት ዉስጥ ገብተዉ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ዉል

በአዋዋይ ፊት ያደረጉትም 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ስላደረጉት ዉል አፈጻጸም ጉዳይ አለመግባባት ላይ በነበሩበት ጊዜ በቀን 27/01/2010ዓ/ም ነዉ፡፡የአመልካች ባለቤት የ2ኛ ተጠሪ ማኀበር ሥራ አስኪያጅ መሆናቸዉ ባይረጋገጥ እንኳን ከሌላኛዉ የማኀበሩ ባለድርሻ ጋር ባላቸዉ ቤተሰባዊ ትስስር ምክንያት በማኀበሩና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በዉሉ አፈጻጸም ጉዳይ አለመግባባት መከሰቱን አያዉቁም ነበር ማለቱ የማኀበራዊ ኑሮን ገሀዳዊ እዉነታ መሰረት ያደረገ ሊሆን አይችልም፡፡ቤቱ የተገዛዉ ጋብቻዉ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ነዉ፡፡ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት እንጂ የባለቤታቸዉ ድርሻ ያለበት አይደለም በሚል በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፡፡በመሆኑም የማኀበሩ ባለድርሻ የአከራካሪዉም ቤት የጋራ ባለሀብት ይሆናሉ፡፡እንዲህ አይነት ግብይት በመሰረቱ የሦስተኛ ወገኖችን መብት የሚነካ እስካልሆነ ድረስ በንግድ ሕጉም ሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ባላቸዉ ሌሎች ሕጎች ክልከላ ያለበት አይደለም፡፡ይሁን እንጂ የማኀበሩ አንደኛ ባለድርሻ ባለቤት የሆኑት አመልካች ወደግዥዉ የገቡት በተለመደዉ የክንዉኖች ፍሰት ተመርተዉ ሳይሆን በማኀበሩ አንደኛዉ ባለድርሻ ባለቤት/አመልካች/ አማካኝነት የ1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም ለመጉዳት እና 1ኛ ተጠሪ ተከራክረዉ ሊያስጡ የሚችሉትን ፍርድ ከወዲሁ ለማጨናገፍ በማሰብ 2ኛ ተጠሪ በወሰደዉ እርምጃ መነሻ መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡በመሆኑም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የሽያጭ ዉል ከ1ኛ ተጠሪ መብት አንጻር የማስመሰል ዉል ነዉ ከሚባል በስተቀር አዉነተኛ ዉል ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ዉሉ በአዋዋይ ፊት መደረጉም የማስመሰል መሆኑን የሚያስቀር አይደለም፡፡ዉሉ ከአመልካች አንጻር እዉነተኛ ነዉ ቢባል እንኳን አመልካች የደረሰባቸዉን ጉዳት ከ2ኛ ተጠሪ መጠየቅ የሚችሉ ከሚሆን በቀር 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የገባዉን በፍርድ ጭምር የተረጋገጠዉን የዉል ግዴታ እንዳይፈጽም እንደመከላከያ ሊያገለግል የሚችል አይደለም፡፡ለእንዲህ አይነት የዉል ማሰናከያ መንገዶች መፍቀድ ዜጎች በዉሎች ላይ እምነት እንዲያጡ የሚያደርግ ነዉ፡፡ስለሆነም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 27/01/2010ዓ/ም የተደረገዉ የ1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም ለመጉዳት በማሰብ የተደረገ የማስመሰል ዉል ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡

በተጨማሪም አመልካች ባቀረቡት ማስረጃዎች ቤቱን ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ዉል ገዝተዉ ከያዙ በኋላ አንዳንድ የማጠናቀቂያ ሥራዎችን መስራታቸዉን ያስረዱትን 1ኛ ተጠሪ ሥራዉ አለመሰራቱን በማስረዳት አላስተባበሉም፡፡በሌላ በኩል በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገዉ ዉል መሰረት 2ኛ ተጠሪ የተጠናቀቀ ቤት ገንብቶ ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡አመልካች ብር 873,120.00 ለቤቱ ተጨማሪ ወጪ ያወጡት የዲዛይን ለዉጥ በማድረግ የተወሰኑ ግንባታዎችን በማፍረስ እንደሆነ አቤቱታቸዉ የሚያሳይ ሲሆን ያቋረቧቸዉ ምስክሮችም የግድግዳ ቁምሳጥን፣የኪችን ሥራ፣የደረጃ መወጣጫ፣የጂብሰም ሥራ እና ሌሎችንም ተመሳሳይ ሥራዎችን መስራታቸዉን መስክረዋል፡፡ከዚህ ዉጭ የዲዛይን ለዉጥ በማድረግ እና የተወሰኑ ግንባታዎችን በማፍረስ የለዉጥ ሥራዎችን የሠሩ ስለመሆኑ ግን ምስክሮቹ የሰጡት ምስክርነት አያሳይም፡፡በአመልካች በተሰሩ ሥራዎች መካከል

አንዳንዶቹ የቤቱ ግንባታ አካል ሆነዉ በ2ኛ ተጠሪ ሊሰሩ የሚችሉ ቢሆኑም ያወጡትን ወጪ ከ2ኛ ተጠሪ መጠየቅ ከሚችሉ በስተቀር የተሰሩ ሥራዎች የዋጋ ግምት ከአጠቃላይ ቤቱ እና ከቤቱ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ቤቱን ይዘዉ እንዲቀሩ ለመወሰን የሚያስችል ዉጤት የሚያስከትሉ አይደሉም፡፡ስለሆነም ይህ ችሎት አስቀድሞ በቀን 06/09/ 2010ዓ/ም እና በቀን 15/06/2011ዓ/ም የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚያስለዉጥ ምክንያት አልተገኘም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 11/09/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ያደረጉት ውል ሆነ ብለው 1ኛ ተጠሪን ለመጉዳት አስበው ነው ሲል በማስረጃ ያልተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችን በመውሰድ በሕግ ግምት እንዲወሰድባቸው ያልተደነገጉ ፍሬ ነገሮች ላይ ግምትን መሰረት በማድረግ የሰጠዉ ውሳኔ ነዉ፡፡አመልካች ቤቱን የገዙት 1ኛ ተጠሪ የዉል ግዴታቸዉን መወጣት ባለመቻላቸዉ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያለዉን ዉል ከሠረዘ በኋላ ነዉ፡፡ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የአመልካች ባለቤት አቶ ዳዊት ዘሪሁን የ2ኛ ተጠሪ ባለአክሲዮን ከሆኑት አቶ ቴዎድሮስ ዘሪሁን ጋር ባላቸው ቤተሰባዊ ትስስር ምክንያት በ2ኛ እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለውን አለመግባባት አቶ ዳዊት ዘሪሁን አያውቁም ብሎ መገመት አይቻልም ያለበት አግባብ እና ግብይቱ 1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም ለመጉዳት የተደረገ ነዉ ሲል በማስረጃ ባልተረጋገጠ ፍሬ ነገር ላይ ግምት በመዉሰድ የደረሰበት ድምዳሜ በሰ/መ/ቁጥር 38683፣37105 እና በሌሎችም ላይ የተሰጠ አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ አንድ ባለአክሲዮን ባለአክሲዮን የሆነበትን ኩባንያ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲያዉቅ አይጠበቅም ወይም ያዉቃል ተብሎ የሕግ ግምት አልተሰጠበትም፡፡2ኛ ተጠሪ ሲሰራ የነበረዉ 45 ቪላ ቤቶችን እና ሌሎች አፓርታማ ቤቶችን ስለሆነ ስለዚህ ቤቶች ሁሉ ሽያጭ ሥራ አስኪያጅ ያልሆኑትና በ2ኛ ተጠሪ የሥራ እንቅስቃሴ ዉስጥ ተሳትፎ የሌላቸዉ ባለአክሲዮን ያዉቃሉ ተብሎ ሊገመት አይችልም፡፡አመልካች ዉሉን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ከመፈራረማቸዉም በተጨማሪ የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ስለመክፈላቸዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ደረሰኝ በማቅረብ አረጋግጠዋል፡፡ተ.እ.ታ ለመንግስት ተከፍሎበት ክፍያ የተፈጸመበት ሽያጭ የማስመሰል ዉል አለመሆኑ አንዱ አመላካች ነገር ነዉ፡፡

በተጨማሪም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ግን በዚህ መከራከሪያ ነጥብ ላይ ምንም ሳይል አልፏል፡፡ዉሉ የማስመሰል ቢሆን ኖሮ አመልካች ብር 873,120.00 የሚያህል ከፍተኛ ወጪ በማዉጣት ቤቱ ላይ ከፍተኛ ግንባታ አያካሂዱም ነበር፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ከዚህም አንጻር ለቀረበዉ ክርክር ምንም ሳይል አልፎታል፡፡የማስመሰል ዉል የሚባለዉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል እዉነተኛ ዉል ሳይኖር፣ለሶስተኛ ወገን ግን ዉል ያለ እንዲመስል ተደርጎ የሚገባ ዉል ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ጉዳዩን ለይግባኝ

ሰሚ ችሎት ሲመልስ ከዚህ አንጻር እንዲጣራ ሆኖ እያለ ችሎቱ ግን የተዋዋይ ወገኖችን ሀሳብ በመመርመር ቅን ልቦናን መሰረት አድርጎ የተፈጸመ ዉል ነዉ ወይስ አይደለም ከሚል አንጻር አይቶ ግምትን መሰረት አድርጎ ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ ባለመሆኑ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እንደሆነ ያሳያል፡፡እንዲሁም አመልካች በገዙት ቤት ላይ ከፍተኛ ግንባታ በማከናወን እንደሰሩ ስለተረጋገጠ ዉሉን አፍርሶ ወደ ነበሩበት ለመመለስ የማይቻል ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1817 መሰረት የአመልካች የቤት ባለቤትነት እንደ ረጋ እንዲቀር በአንጻሩ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ተመሳሳይ ቤት የመተካትን እና መሰል አማራጭ የካሳ አከፋፈል መንገዶች በመከተል አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ አመልካች በቤቱ ላይ ሕጋዊ ባለቤት ስለሆኑ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለ1ኛ ተጠሪ ያስረክቡ ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ ይሻርልኝ በማለት በመጠየቅ አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ቤት ላይ እገዳና እዳ ያለመኖሩን አረጋግጦና ግዥ ፈጽመዉ ስመ ሀብቱ በስማቸዉ ዞሮ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ እና በአመልካች ተጨማሪ ግንባታ አካሂደዉ ባሉበት የስር ፍርድ ቤት በተጨባጭ ያልተረጋገጡ ግምቶችን በራሱ ጊዜ በመዉሰድ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ የወሰነበትን አግባብ ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1817፣ 2330፣ 2090፣2119 እና ከሰ/መ/ቁጥር 37105፣43845፣39336 እና ተያያዥ ትርጉሞች ጋር ተገናዝቦ እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በሚከተለዉ መሰረት መልሳቸዉን አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 22/11/2013 ዓ/ም ጽፈዉ ባቀረቡት መልስ፡- አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ስመ ሀብት በአመልካች ስም የዞረ ነው በሚል የተከራከሩ ቢሆንም የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠዉ የቀረቡለትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች መሰረት አድርጎ እንጂ በግምት ላይ ተመስርቶ አይደለም፡፡ የአመልካች ባለቤት እና የ2ኛ ተጠሪ ባለድርሻ መካከል ያለው ቤተሰባዊ ትስስር፣ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በመሆኑ ቤተሰባዊ ትስስር ባላቸዉ ሰዎች የተቋቋመ መሆኑ አመልካች እንዳሉት ትርጉም የማይሰጥ ተራ ነገር ተደርጎ የሚታለፍ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት እነዚህንና በአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ በባለአክሲዮኖቹ መካከል ያለዉ ግንኙነት ሆነ ተብሎ የ1ኛ ተጠሪን መብት ለመጉዳት የተደረገ ዉል እንደሆነ ያሳያል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በቀረቡት የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጡትንና በክርክሩ ሂደት ያልተካዱ ፍሬ ነገሮችን መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በተደረገ ዉል ላይ ገንዘቡ በዉሉ ደረሰኝነት እንደተከፈለ መገለጹ፣ነገር ግን አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡት ደረሰኝ ቁጥር 001 አዲስ ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የዱቤ ሽያጭ እንደተፈጸመ የሚያሳይ መሆኑ አመልካች ከተ.እ.ታ ጋር ክፍያ ፈጽመናል ያሉት እንደከፈሉና ሽያጩ እዉነት እንደሆነ ለማስመሰል ያቀረቡት እንደሆነ ያሳያል፡፡የሽያጭ ዉሉ ገንዘብ ሳይከፈል እንደተከፈለ ተደርጎ ዉል መፈጸሙ በእርግጥ ንብረቱን በሽያጭ ስም ከ1ኛ ተጠሪ በማዉጣት በባለቤታቸዉ አቶ ዳዊት ዘሪሁን በኩል የድርጅቱ ባለድርሻ ለሆኑት ንብረት የማሸሽ መንገድ እንጂ በቅን ልቦና የዉልን መሰረተ ሃሳቦች ባከበረ መልኩ የተደረገ ዉል አለመሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡

እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ሰርቶ እንዲያስረክበኝ 1ኛ ተጠሪ በ2003ዓ/ም ሲዋዋል የቤቱ ዋጋ ብር 4,478,000.00 የነበረ ሲሆን ከ7 ዓመት በኋላ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር አደረኩኝ ባሉት ዉል ላይ ቤቱ በብር 4,500,00.00 ለወደፊት ሰርቶ ሲያስረክቡ አንድ ቤት ያለዉ ዋጋ እና ምንም አይነት ክፍያ ሳይፈጽም ያለቀ ቤት የሚሸጥበት ዋጋ በማንኛዉም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት አንድ ወይም ተቀራራቢ ሊሆን ስለማይችል ማስረጃን እንደሚመዝን ፣ፍሬ ነገሮችን ትርጉም ባለዉ እና ምክንያታዊ በሆነ አግባብ ለሚተነትን ፍርድ ቤት በእርግጥ ሽያጩ የ1ኛ ተጠሪን መብት በመጉዳት ንብረቱን በቤተሰብ ደረጃ የማስቀረት ስልት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የአመልካች እና የ2ኛ ተጠሪ ባለድርሻ አቶ ዳዊት ዘሪሁን ሚስት መሆናቸዉ ሌላኛዉ ባለድርሻ አቶ ቴዎድሮስ ዘሪሁን ደግሞ የአቶ ዳዊት ወንድም መሆናቸዉ ያለዉ እንድምታ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑ ከሚኖረዉ ባህርይ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ሚስት በሚሊዮን ብር ቤት ሲገዙ ባል አያዉቅም ተብሎ ስለማይገመት፣በ2ኛ ተጠሪ ዉስጥ ያለዉ ግማሽ የአክሲዮን ዋጋ የአመልካች ባለቤት ብቻ ሳይሆን የአመልካች የጋራ ሀብት ጭምር መሆኑ፣ ሚስት ቤቱን እየገዙ ያሉት የጋራ ንብረታቸዉ ከሆነዉ 2ኛ ተጠሪ ላይ መሆኑ የሚያሳየዉ በቤተሰባዊ ትስስር የ1ኛ ተጠሪን መብት ለመጉዳትና አለአግባብ ለመበልጸግ እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡አመልካች በቤቱ ላይ ተጨማሪ ግንባታ ማካሄዳቸዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1817 እና 2330 መሰረት ቤቱን የእሳቸዉ የሚያደርግ አይደለም፡፡አመልካች በቤቱ ላይ የፊኒሽንግ ሥራ ከመስራት ባለፈ በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለዉጥ የሚያመጣ አፍርሶ የመስራት ሥራ አልሰሩም፡፡የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1817 ተፈጻሚነትም በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንጂ በ1ኛ ተጠሪ ላይ አይደለም፡፡የቤቱ ዋጋ በአሁኑ ጊዜ ከብር 15,000,000.00 በላይ ስለሚያወጣ አመልካች አወጣሁኝ ያሉት ወጪ እጅግ አነስተኛ ነዉ፡፡የቤቱን 20 በመቶ የማያክል ሥራ ወደነበርንበት ለመመለስ አስቸጋሪ ነዉ በማለት የቀረበዉም ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠዉ ፍሬ ነገሮችን በሚገባ አረጋግጦ በመሆኑ ጉድለት ስለሌለበት ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በቀን 30/10/2013ዓ/ም በሰጠዉ መልስ 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ቤቱን ሽጠዉ ዕዳና እገዳ ያለመኖሩ ተጣርቶ፣በሁለተኛ ተጠሪና በ1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረዉ ዉል ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ፣አመልካች ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና በመሆኑ፣ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍሬ ነገር ይልቅ በግምት ላይ የተመሰረተ በመሆኑና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተለያዩ ጊዜያት የሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ፣በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል የማስመሰል ዉል ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በተለያየ ጊዜ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ቤቱን ስለገዛሁና ተጨማሪ ግንባታም ስለፈጸምኩበት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች ሊያስረክብ ይገባል ተብሎ

የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን ስለሚነካ ይሻርልኝ በማለት ያቀረቡት የተቃዉሞ አቤቱታ ዉድቅ በመደረጉ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም በ1ኛ ተጠሪ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በቀን 19/11/2003 ዓ/ም በተደረገ ውል መሰረት 2ኛ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት ግንባታዉን አጠናቆና ስመ ሀብቱን በ1ኛ ተጠሪ ስም አድርጎ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ጉዳዩን በመ/ቁጥር 153192 ላይ በይግባኝ ተመልክቶ በቀን 06/09/2010 ዓ/ም ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ የዉሳኔ ክፍል በዚሁ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 159065 ላይ በቀን 24/03/2011ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ ፀንቷል፡፡አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ ዉሳኔ የተሰጠበትን ቤት በተጠሪዎች መካከል የተደረገዉ ዉል ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ ከዕዳና እገዳ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ በዉል አዋዋይ ፊት በቀን 27/01/2010 ዓ/ም በተደረገ ዉል ገዝቼ በመረከብ ተጨማሪ የማሻሻያ ግንባታ ያደረኩበት በመሆኑ ባለቤት የሆንኩበትን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብቴን የሚነካ ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት ነዉ፡፡1ኛ ተጠሪ በዚህ የተቃዉሞ አቤቱታ ላይ ያቀረቡት ክርክር ከላይ በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን በዋናነት ክርክራቸዉ አመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ግማሽ ባለድርሻ ባለትዳሮች በመሆናቸዉ የማኅበሩ 2ኛ ባለድርሻም የአመልካች ባል ወንድም በመሆናቸዉ፣ በማኅበሩ ዉስጥ የአመልካች ባል ባላቸዉ ድርሻ ላይ አመልካችም የጋራ ባለሀብት በመሆናቸዉ፣ቤቱም የተገዛዉ ከዚሁ የጋራ ባለሀብት ከሆኑበት 2ኛ ተጠሪ ላይ በመሆኑ እና አመልካች በሚሊዮኖች ብር ቤት ሲገዙ ባለቤታቸዉ አያዉቁም ተብሎ ስለማይገመት ከቤት ርክክብ ጋር በተያያዘ በተጠሪዎች መካከል የነበረዉን አለመግባባት እያወቁ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን እንዳይረከቡ በማድረግ የ1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም በመጉዳት ቤቱን 2ኛ ተጠሪ በሽያጭ እንዳስተላለፈ በማስመሰል ለማሸሽ የተደረገ ዉል ነዉ፡፡እንዲሁም የቤቱ ዋጋ ከ7 ዓመት ባላይ ቆይቶ በተቀራራቢ ዋጋ እንደተሸጠ መገለጹና አመልካች የቤቱን ዋጋ ሳይከፍሉ እንደከፈሉ ተድርጎ በዉሉ ላይ መጻፉ ዉሉ የይስሙላ መሆኑን ስለሚያሳይ የአመልካች አቤቱታ ዉደቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ለአመልካች ቤቱ የተሸጠዉ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የተደረገዉ ዉል ተቋርጦ ባለበት ጊዜ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተገቢ ነዉ ሲል ተከራክሯል፡፡

ከዚህ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት ከላይ ለያዝነዉ ዋና ጭብጥ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ለይምሰል የተደረገ ዉል (simulated contract) ነዉ ወይስ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዳይፈጸም ለማድረግ (2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ያለበትን ግዴታ ላለመወጣት) ብሎ በተንኮል የተፈጸመ ዉል ነዉ? ዉሉ ለይምሰል የተደረገ መሆኑ በምን አግባብ ሊረጋገጥ ይችላል? ለይምሰል የተደረገ ዉል በሦስተኛ ወገን መብት ላይ የሚያስከትለዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ? በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ

መካከል የቤት ሽያጭ ዉል የተደረገዉ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ያለበትን ግዴታ ላለመወጣት ብሎ በተንኮል የፈጸመዉ ዉል ነዉ የሚባል ከሆነ የተንኮል ተግባር መኖሩስ በምን አግባብ ሊረጋገጥ ይገባል? የሚሉ ተጓዳኝ ጭብጦች አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር ተገናዝቦ ዉሳኔ ማግኘት ያለባቸዉ ናቸዉ። በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ በሰጠዉ ዉሳኔ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል በእርግጥም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ሳይሆን ቤቱን 1ኛ ተጠሪ እንዳይረከቡ በማድረግ የ1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ የማስመሰል ዉል በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም የሚል የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

በቀዳሚነት በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ለይምሰል የተደረገ ዉል (simulated contract) ነዉ ወይ? በሚል የያዝነዉን ጭብጥ መርምረናል።የይምሰል ዉል (simulated contract) በታዋቂዉ ብላክስ ሎዉ መዝገበ ቃላት(በ9ኛ እትም ገጽ 373) ላይ የሚከተለዉ ትርጓሜ ተሰጥቶታል፦ *simulated contract* ... A contract that, by mutual agreement, does not express the true intent of the parties.- A simulated contract is absolute when the parties intend that the contract will impose no obligations; no obligations are enforceable on the parties by such a contract. A simulated contract is relative if the parties intend it to impose obligations different from those recited in the contract; the intended obligations are enforceable if all relevant conditions are met. A simulated contract may affect the rights of third parties.ይህም በግርድፉ የይምሰል ዉል ማለት የተዋዋዮችን እዉነተኛ ሀሳብ(ፍላጎት) የማያሳይ ስምምነት ነዉ።የይምሰል ዉል ፍጹማዊ እና አንጻራዊ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን የመጀመሪያዉ አይነት የይምሰል ዉል በተዋዋዮች ላይ ምንም ግዴታ የማይፈጥር እና የሚፈጸም ምንም ግዴታ የሌለበት ነዉ።ሁለተኛዉ አንጻራዊ የይስሙላ ዉል የሚባለዉ ደግሞ ተዋዋዮች በዉል ከተስማሙት በተለየ ሁኔታ ግዴታ ለማቋቋም አስበዉ ያደረጉት ከሆነ በዚህ መልኩ ያቋቋሙት ግዴታ ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንዲፈጸም የሚደረግ ነዉ።የይምሰል ዉል የሦስተኛ ወገኖችን መብት ሊነካ የሚችል ነዉ የሚል ሀሳብ የያዘ ነዉ።

የይስሙላ ዉል በተመለከተ የሕግ ትንታኔ የጻፈ አንድ አድሪያን ጋብሪኤል ዲነስኩ(Adrian-Gabriel Dinescu) የተባሉ የሕግ ምሁር "simulated contract is nothing else than to lie about something,to present a distorted truth and which is presented to the outsider world as true …whilest between the parties ,a secret agreement is drawn, the true expression of their will, and which is adversely different than the apparent contract." በሚል ይገልጸዋል።ይህም በግርድፉ የይምሰል ዉል ስለአንድ ተግባር ከመዋሸትና እዉነታዉን ከማዛባት የዘለለ ካለመሆኑም በተጨማሪ በምስጢር የተደረገዉ ሌላ እዉነተኛ ስምምነት እያለ

ከተዋዋዮቹ ዉጭ ለሆኑ ሰዎች እዉነተኛዉ ዉል ይህ ለይምሰል የተደረገዉ ዉል እንደሆነ አስመስሎ ለማቅረብ የሚፈጸም ተግባር ነዉ በሚል ሊገለጽ የሚችል ነዉ፡፡

ይህንን ትርጓሜ ይዘን ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በፍትሐ ብሔር ሕጋችን የተደነገገዉን የተመለከትን እንደሆነ በመርህ ደረጃ አንድ ሰዉ የሌላ ሰዉ ባለዕዳ በመሆኑ ብቻ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ዉል ከመዋዋል አይታገድም፡፡እንዲህ አይነት ክልከላ ማስቀመጥ የመዋዋል ነጻነቱን እና የንብረት ባለሀብትነት መብቱን ዋጋ ቢስ ማድረግ ይሆናል፡፡አንድ ሰዉ ሀብቱ ላይ በዚህ አግባብ ዉል የፈጸመ እንደሆነ ዉሉ ከእርሱ ላይ ገንዘብ ያላቸዉን ሰዎች መመለሻ እንደሚሆን እና ዉሉ ከተረጋገጠበት ቀን (the date of authentication) ጀምሮ ወይም እንዲህ አይነት ዉል ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ ሕግ የሚያዝ ከሆነ ይሄዉ ሥርዓት ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ሰዉ ንብረት ላይ ልዩ መብት በሚያገኙት ሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1989 ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡በዚህ መልኩ በተለይም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1989/1 ስር የተደነገገዉን ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ የኢትዮጵያ የዉል ሕግ መሠረተ ሀሳቦች በሚል ባሳተሙት መጽሐፋቸዉ ገጽ 333 ላይ “አንድ ሰዉ የሌላ ሰዉ ዕዳ እያለበት ንብረቱን ቢሸጠዉ፣ቢለዉጠዉ ወይም በስጦታ ቢያስተላልፈዉ የእርሱ ባለገንዘብ የሆነዉ ሰዉ ንብረቱ የተላለፈለትን ሰዉ ’የገዛኸዉ ንብረት፣ የለወጥከዉ ዕቃ፣ወይም የተቀበልከዉ ስጦታ የእኔ ባለእዳ የሆነ ሰዉ ሀብት ነዉ፤እርሱ የእኔን ዕዳ ሳይከፍል ሀብቱን ለአንተ ሊያስተላልፍ አይችልም’ ብሎ አዲሱን ተረካቢ ሊከለክለዉ መብት የለዉም፡፡” በማለት አብራርተዉ ጽፈዋል፡፡ ይህም የሚያስገነዝበዉ የባለዕዳዉ የመዋዋል ነጻነት እና ባለዕዳ ቢሆንም በንብረቱ ላይ ያለዉን የባለቤትነት መብቱን የመጠቀም መብት ሊረጋገጥለት እንደሚገባ ነዉ፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መልኩ በመርህ ደረጃ ለሌላ ሰዉ ባለዕዳ የሆነዉ ሰዉ ስላለዉ መብት የተደነገገዉ ሁለት ልዩ ሁኔታዎች አሉት፡፡አንደኛዉ ልዩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1990 ስር የተደነገገዉ ልዩ መብት ስላላቸዉ ገንዘብ ጠያቂዎች(*Preferred/Secured Creditors*) የተደነገገዉ ሲሆን ይሔዉም በሕግ አግባብ በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያቋቋሙ ሰዎች ወይም በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 168 ላይ ሥለሠራተኞች የቅድሚያ መብት የተደነገገዉን ዓይነት መብቶች በተመለከተ ሲሆን ሁለተኛዉ ልዩ ሁኔታ ደግሞ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1991/1 ስር እንደተደነገገዉ ባለዕዳዉ ንብረቱን በተመለከተ ያደረገዉ ዉል የይምሰል ዉል ሲሆን ነዉ፡፡በእነዚህ ልዩ ሁኔታዎች መሰረት አንድ ለሌላ ሰዉ ባለዕዳ የሆነ ሰዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1989 ስር በተደነገገዉ መሰረት ንብረቱን በተመለከተ ዉል የመዋዋል ነጻነት ስላለዉ ብቻ ወይም ንብረቱ ላይ የባለሀብትነት መብት ስላለዉ ብቻ ከሌላ ሰዉ ጋር በሚያደርገዉ እዉነተኛ ዉል ወይም በይምሰል ዉል ልዩ መብት ያላቸዉን ገንዘብ ጠያቂዎቹን መብት እና ከእሱ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎችን መብት መጉዳት አይችልም፡፡

የይምሰል ዉል (simulated contract)ም ሆነ ሌላ ሽሽግ ዉል (counter-deed or back-letter) በተመሳሳይ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚደረግ ነዉ፡፡ ለይምሰል የተደረገ ዉል ካለ ሌላ ይህንን የሚቃረን ሁለተኛ ዉል እንዳለ ያስገነዝባል፡፡ ሁለቱም ዉሎች እርስ በእርስ የሚጣረሱ ዉሎች ስለሚሆኑ ለሁለቱም ዉሎች ዉጤት መስጠት አዳጋች ይሆናል፡፡በዚህን ጊዜ ከሁለቱ ዉሎች አንዱን ማስፈጸም የግድ ይላል፡፡የይምሰል ዉሉን የሚዋዋሉት ዉሉ ዉጤት እንዲኖረዉ አስበዉ እንዳልሆነ (lack of the *intention obligandi*) ይቆጠራል፡፡ በዚህ መሰረት የይምሰል ዉል የተዋዋሉበት ዓላማ ይህ ለይምሰል የተደረገ ዉል ዉጤት እንዲኖረዉ በማሰብ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1991/2 ስር እንደተደነገገዉ ለመደበቅ የፈለጉት ዉል ወይም ድብቅ የሆነዉ ዉል (counter-deed or back-letter) በተዋዋዮች መካከል ብቻ ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም አንድ ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ወይም በሌላ ምክንያት ለሌላ ሰዉ ባለዕዳ የሆነ ሰዉ ንብረቱን በተመለከተ የይምሰል ዉል ተዋዉሎ የተገኘ እንደሆነ ከዚህ ሰዉ ገንዘብ የሚጠይቀዉ ሰዉ ለይምሰል ከተደረገዉ ዉል ዉጭ ሌላ ሽሽግ ዉል እንዳለ በማስረዳት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1991 እና በቁጥር 1994 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ባለዕዳዉ ያደረገዉ ዉል የማስመሰል እንጂ ተፈጻሚ እንዲሆን የተደረገ እዉነተኛ ዉል አለመሆኑን በመግለጽ በሽሽግ ዉሉ መሰረት መብቱ በፍርድ እንዲከበርለት ለመከራከር ወይም ዳኝነት ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ይህንንም ከያዝነዉ ጉዳይ ጋር አያይዘን ያየን እንደሆነ ሁለተኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በገባዉ ዉል መሰረት ያለበትን ግዴታ ላለመወጣት(ግንባታዉን አጠናቆ ለ1ኛ ተጠሪ ላለማስረከብ) ብሎ አመልካች ቤቱን እየጠበቁ ያለዋጋ እንዲገለገሉበት የሚፈቅድ እዉነተኛ ዉል ወይም ሽሽግ ዉል (counter-deed or back-letter) ካደረገ በኋላ 1ኛ ተጠሪና ሌላዉ ሰዉ ቤቱን ለአመልካች እንደሸጠ እንዲቆጥሩለት በማሰብ ብቻ ከአመልካች ጋር በዉል አዋዋይ ፊት በተደረገ ዉል ቤቱን እንደሸጠ በማስመሰል ቢዋዋል የሽያጭ ዉሉ ለይምሰል እንደተደረገ ዉል ይቆጠራል፡፡በዚህን ጊዜ 1ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1991/2 እና 1994 መሰረት የሽያጭ ዉሉ የይምሰል ዉል በመሆኑ እዉነተኛዉና ሊፈጸም የሚገባዉ አመልካች ቤቱን ያለ ዋጋ በጠባቂነት እንዲገለገሉበት የተደረገዉ ዉል ነዉ በማለት ይህ እዉነተኛ ዉል ቀሪ ሆኖ ቤቱን 2ኛ ተጠሪ አንዲያስረክባቸዉ የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል ፡፡

ሆኖም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በያዝነዉ ጉዳይ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በዉል አዋዋይ ፊት በቀን 27/01/2010 ዓ/ም ከተደረገዉ ከአከራካሪዉ የቤት ሽያጭ ዉል ዉጭ ይሄኛዉን ዉል የይምሰል ዉል እንዲሆን የሚያደርግ ሽሽግ ዉል (counter-deed or back-letter) ስለመኖሩ በተጨባጭ በማስረጃ ተረጋግጦ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበ ግልጽ ክርክር የለም፡፡በመሆኑም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል የይምሰል(የማስመሰል/simulated) ዉል ነዉ ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል የይምሰል ዉል አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ስለደረስን ከዚህ ጋር በተያያዘ ዉሉ ለይምሰል የተደረገ መሆኑ በምን

አግባብ ሊረጋገጥ ይችላል? ለይምሰል የተደረገ ዉል በሦስተኛ ወገን መብት ላይ የሚያስከትለዉ ሕጋዊ ዉጤት ምንድን ነዉ?በሚል የያዝናቸዉን ጭብጦች መመርመር አስፈላጊ ባለመሆኑ አልፈናቸዋል፡፡

በሌላ በኩል በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ዉል የተደረገዉ በ1ኛ ተጠሪና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዳይፈጸም ለማድረግ ወይም 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ ያለበትን ግዴታ ላለመወጣት ብሎ በተንኮል የተፈጸመ ነዉ ወይስ አይደለም? የተንኮል ተግባር መኖሩስ በምን አግባብ ሊረጋገጥ ይገባል? በሚል የያዝናቸዉን ጭብጦች ቀጥለን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም ተንኮለኛ ባለዕዳ ለቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ ተግባር ሀብቱ ለባለገንዘቡ የመብት ጥያቄ ማስፈጸሚያ እንዳይዉል በተለያዩ መንገዶች በሦስተኛ ሰዎች ስም የማዛወር ወይም የመሰወር ተግባር ሊፈጽም ይችላል፡፡ ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ ከላይ በተጠቀሰዉ መጽሐፋቸዉ ገጽ 341-342 እዉቁን ፈረንሳዊ የሕግ ሊቅ ፕላንዮልን ጠቅሰዉ እንዳስፈሩት "...ንብረቱ ለባለገንዘቦቹ የመብት ጥያቄ መመለሻ እንደሚዉል የተረዳዉ ባለዕዳ ሀብቱን ከእነዚህ ባለገንዘቦች ለመሸሸግ... ንብረቱን በግዥ ወይም በስጦታ አግኝቻለሁ ከሚል ሦስተኛ ወገን ጋር በመመሳጠር ባለገንዘቡን የሚጎዳ ሸር ሊያዉጠነጥን ይችላል፡፡...ለራሱ ምንም ባይጠቀም እንኳን ክፋት በማሰብ ብቻ ሀብቱን ለጓደኞቹና ለዘመዶቹ በማከፋፈል ባለገንዘቡን የሚጎዳ ተግባር ሊፈጽም ይችላል፡፡...እንዲህ በዋዛ ሊታወቁና ሊረጋገጡ በማይችሉ እጅግ በርካታ መንገዶች የባለገንዘቡን መብት ለመጉዳት የሚችሉ አጋጣሚዎችን ባለዕዳዉ ሊጠቀም ይችላል፡፡"ሕግ ደግሞ ምን ጊዜም ለቅን ልቦና አሠራር የማያወላዳ አቋም ስላለዉ የባለዕዳዉን የተንኮል ሥራ የሚገታበትን መንገድ ለባለገንዘቡ ይዘረጋል በሚል ስለተንኮለኛ ባለዕዳ ባህርይ ገልጸዋል፡፡ ይህንን አባባላቸዉን በሚደግፍ አኳኋን በፍትሐ ብሔር ሕጋችን ከቁጥር 1995 እስከ 2000 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች ባለገንዘቦች መብታቸዉን የሚያስከብሩበት አግባብ ተደንግጓል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ዓላማ ማንኛዉም ሰዉ በሌላዉ ኪሳራ ለመበልጸግ ብሎ የሠራዉ ሥራ ባለገንዘቡን በሚጎዳ አኳኋን በሕግ ፊት ዉጤት ሊሰጠዉ አይገባም የሚለዉን ርትዓዊ አተያይን መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት በተለይ ከባለዕዳዉ መክሰር ዉጭ ያሉ የባለዕዳዉን ድርጊቶች በተመለከተ ባለገንዘቡ እንዲያረጋግጥ የሚጠበቅበት ባለዕዳዉ ንብረቱን ወይም ያለዉን መብት ሆነ ብሎ እየለቀቀ ወይም እያስተላለፈ መሆኑንና ይህንንም እያደረገ ያለዉ ባለገንዘቡ የመብት ጥያቄዉን የሚያስፈጽምበትን ንብረት እንዲያጣ ለማድረግ ተንኮል አስቦ እንደሆነ፤ባለዕዳዉ ሆነ ብሎ እየለቀቀ ወይም እያስተላለፈ ያለዉ ይህ መብት(ንብረት) ለባለገንዘቡ መብት አፈጻጸም መድን በመሆኑ የዚህ ሀብት መጥፋት ወይም ሌላ ሰዉ መተላለፍ የባለገንዘቡ ጥያቄ መፍትሔ እንዳያገኝና ጉዳት እንዲደርስበት በማሰብ መሆኑን እና ይህ መብት(ንብረት) ባለገንዘቡ በራሱ ስም በሚጠይቀዉ ጥያቄ ልክ መሆኑን ማስረዳት እንደሚጠበቅባቸዉ በዘርፉ የተጻፉ ድርሳናትና በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 1995 - 1999 የተደነገጉ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የባለዕዳዉ የማጭበርበር ተግባር ከባለዕዳዉ መክሰር ጋር ሊያያዝና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2000 እና በንግድ ሕጉ ስለመክሰር በተደነገገዉ አግባብ ባለዕዳዉ ከስሯል ተብሎ ተወስኖ በንግድ ሕጉና በሌላ ሕግ በተደነገገዉ አግባብ የባለገንዘቦቹ መብት ጥበቃ እንዲያገኝ የሚደረገዉ መቼ ነዉ የሚለዉን ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ በእኛ እምነት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2000 ተፈጻሚ የሚሆነዉ ባለእዳዉ ለባለገንዘቦች የገባዉን ግዴታ ላለመወጣት ካለዉ ዓላማ በመነሳት ብቻ ሳይከስር በተንኮል በእጁ ያለዉ ሀብት ለባለገንዘቡ የመብት ጥያቄ ማስፈጸሚያ እንዳይዉል በተለያዩ መንገዶች ንብረቱን በግዥ ወይም በስጦታ አገኘሁኝ ከሚል ሦስተኛ ወገን ጋር በመመሳጠር ባለገንዘቡን የሚጎዳ የአጭበርባሪነት ተግባር በመፈጸም ንብረቱን ባስተላለፈበት በማንኛዉም ጊዜ ሁሉ ሳይሆን ባለዕዳዉ ተቃዉሞ የቀረበባቸዉን ሥራዎች የሠራዉ ራሱን ለማክሰር የፈጸመዉ ተግባር ሲሆንና መክሰሩም ሲረጋገጥ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተዉ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የነበረዉ ክርክር ተሰምቶ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገዉን ዉል በተናጠል መሰረዙ ተገቢ አይደለም ተብሎ 2ኛ ተጠሪ ለ1ኛ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉን ቤት ገንብቶ ለማስረከብ በገባዉ የዉል ግዴታ መሰረት የቤቱን ግንባታ አጠናቆ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ ተወስኗል፡፡በዚህ መልኩ ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት እና 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የፈጸመዉን ዉል በተናጠል ሠርዣለሁ ከማለቱ በፊት በተጠሪዎች መካከል ከቤት ርክክብና ከቀሪ ክፍያ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለረጅም ጊዜ የቆየ አለመግባባት እንደነበር የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡

ከንግድ ሕጋችን ከተለያዩ ድንጋጌዎች እና በአገራችን በልማድ ከዳበረዉ አሠራር መረዳት እንደሚቻለዉ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር ምንም እንኳን የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ የንግድ ማኀበር ቢሆንም ለሕዝብ ግልጽ በሆነ አኳኋን አክሲዮኑ ለማንኛዉም ሰዉ ለሽያጭ ቀርቦ በባለአክሲዮኖች የሚቋቋም ሳይሆን ዘመዳሞች የሆኑ ወይም በጓደኝነት ወይም በሙያ እርስ በእርሳቸዉ በደንብ የሚተዋወቁ ሰዎች ካፒታል በማዋጣት የሚቋቋሙት ነዉ፡፡እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር ሆኖ የተቋቋመ መሆኑ አከራካሪ ካለመሆኑም በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ የተቋቋመዉ ካለዉ ካፒታል ግማሹን የአመልካች ባለቤት ባለድርሻ በመሆንና ቀሪዉን ግማሽ ድርሻ ደግሞ የአመልካች ባል ወንድም ድርሻ በመሆን ያቋቋሙት እንደሆነ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በማስረጃ የተረጋገጠና በአመልካችም ያልተካደ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ በዚህ መልኩ ዘመዳሞች በሆኑ ሁለት ሰዎች የተቋቋመ በመሆኑ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ርክክብና ከቀሪ ክፍያ አከፋፈል ጋር በተያያዘ በተጠሪዎች መካከል የነበረዉን አለመግባባት ክርክሩ ወደ ፍርድ ቤት ከመምጣቱ በፊት 2ኛ ተጠሪን ያቋቋሙ ማኀበረተኞችም ሆኑ አመልካችም ማኀበረተኛ ከሆኑት ባለቤታቸዉ በኩል አያዉቁም ተብሎ አይገመትም፡፡

በተጨማሪም አመልካች አከራካሪዉን ቤት በቀን 27/01/2010 ዓ/ም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አጅንሲ በተደረገ ዉል ከ2ኛ ተጠሪ ላይ በብር 4,500,000.00 ገዝቻለሁ ያሉትን በሚሊዮኖች ብር የተደረገ ግብይት ባለቤታቸዉ (የ2ኛ ተጠሪ ግማሽ ባለድርሻ) አመልካች ቤቱን ከማንና በምን ያህል ገንዘብ ለመግዛት ዉል እንደተዋዋሉና በቤቱ ላይ አስቀድሞ መብት ያቋቋመ ሰዉ መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ከአመልካች ጋር መረጃ የመለዋወጥ እድል እንዳላቸዉ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መሰረት አድርጎ ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በየጊዜዉ ተከፍሎ በሚጠናቀቅ የአከፋፈል ሥርዓት ገንብቶ ለ1ኛ ተጠሪ ለማስረከብ በ2003ዓ/ም ስምምነት ያደረገዉ በብር 4,478,000.00 ሆኖ ግንባታዉ በመጠናቀቅ ደረጃ ያለዉን ይህንኑ ቤት ከ7 ዓመት በኋላ ለአመልካች በአንጻራዊነት ዝቅተኛ እንደሆነ በሚገመት ዋጋ በብር 4,500,000.00 በሽያጭ ማስተላለፉና *(በዉሉ ላይ ቤቱ የተሸጠበት ገንዘብ በዉሉ ደረሰኝነት እንደተከፈለ የሚገልጽ ቢሆንም የይግባኝ ሰሚዉ ችሎት መዝገብ እንደሚያሳየዉ የሽያጩ ዋጋ በዉሉ ደረሰኝነት የተከፈለ ሳይሆን በተ.እ.ታ. ደረሰኝ ቁጥር 001 በዱቤ ሽያጭ የተፈጸመ ግብይት እንደሆነ)* የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ከዚህ በላይ በተመለከተዉ አግባብ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መገንዘብ የተቻለዉ 2ኛ ተጠሪ የማኅበሩ አንደኛዉ ባለድርሻ ሚስት ለሆኑት አመልካች በአንጻራዊነት ዝቅተኛ እንደሆነ ግንዛቤ በሚወሰድ ዋጋ በሽያጭ ያስተላለፈዉ ቤት ለ1ኛ ተጠሪ በገባዉ የዉል ግዴታ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ያስገነባቱ ቤት መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ከቀረቡት ማስረጃዎችና ከአጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ የተረጋገጠ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፈዉ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረገዉ ዉል ላይ የተመለከተዉን ቤት በመሆኑ ይህንን ያደረገዉ 1ኛ ተጠሪ በክርክሩ የሚረቱና 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ያስረክብ የሚባል ከሆነ 2ኛ ተጠሪ የማስረክበዉ ቤት በይዞታዬ ስር አይገኝም ለማለት እና 1ኛ ተጠሪ የሚረከቡትን ቤት እንዲያጡና በዚህም ምክንያት በመብትና ጥቅማቸዉ ላይ ጉዳት እንዲደርስባቸዉ ለማድረግ በማሰብ የፈጸመዉ የተንኮል ተግባር እንደሆነ ያሳያል፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል በእርግጥም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ሳይሆን ቤቱን 1ኛ ተጠሪ እንዳይረከቡ በማድረግ የ1ኛ ተጠሪን መብትና ጥቅም ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ ዉል ነዉ በሚል ያረጋገጠዉ የፍሬ ነገር ድምዳሜም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡የተንኮል ተግባር ድርጊቱን ተመካክረዉ ከሚፈጽሙ ሰዎች ዉጭ ለማንኛዉም ሰዉ በግልጽ በሚታይና በሚሰማ አኳኋን የሚሰራ ባለመሆኑ የተንኮል ተግባር መኖሩን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ማስረጃም ይህንኑ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳት ግንዛቤ( factual inferences) ሊወሰድበት የሚችል ነዉ፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም በተጠቀሰዉ አግባብ አስቀድሞ ሰበር ሰሚ ችሎት ይዞ የመለሰለትን ጭብጦች በግራ ቀኙ

የታመኑትንና በማስረጃ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች መነሻ በማድረግ ድምዳሜ ላይ ደርሷል ከሚባል በስተቀር አከራካሪ ጭብጦችን በሙሉ በግምት ላይ ተመስርቶ ወስኗል የሚያስብል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካች የቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

እንዲሁም በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ ዉል እንዲፈርስ የተሰጠ ዉሳኔ ባይኖርም አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ የከፈሉት ገንዘብ ካለ እና 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በገባዉ የዉል ግዴታ ላይ ከተመለከተዉ የግንባታ ሥራ ዉጭ የፈጸሙት ግንባታ ካለ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ለተጨማሪ ግንባታ ያወጡት ወጪ እንዲተካላቸዉ መጠየቅ እንዲችሉ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ተወስኖላቸዋል፡፡እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ መስራት ይገባዉ ከነበረዉ ግንባታ በላይ በቤቱ ላይ አመልካች በራሳቸዉ ገንዘብ የሰሩት ተጨማሪ የማሻሻያ/የግንባታ ሥራ ካለ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ አመልካች ጋር በፈጸሙት ዉል ላይ ከተመለከተዉ በላይ የሆነ ወይም የተሻለ የግንባታ ማሻሻያ የተደረገለትን ቤት ተረክበዉ አለአግባብ እንዳይበለጽጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት አላግባብ ስለመበልጸግ በተመለከተው የሕግ ክፍል አግባብ አመልካች ክስ በማቅረብ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ዉጭ የሕጉ ድንጋጌዎች የ2ኛ ተጠሪን የተንኮል ተግባር የመቅጣትና የ1ኛ ተጠሪን(የገንዘብ ጠያቂን) መብት የማስከበር ዓላማ ያለዉ በመሆኑ አመልካች ተጨማሪ ግንባታ/ማሻሻያ በቤቱ ላይ አድርጌያለሁ በማለታቸዉ ብቻ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል ጸንቶ እንዲቀጥል የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡ይህ ይሆን የነበረዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1997 መሰረት ቤቱን የገዙት በቅን ልቦና መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ነገር ግን በዚህ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ መሰረት ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ቤቱን የገዙት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባላቸዉ ግንኙነት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር በተንኮል 1ኛ ተጠሪ እንዲጎዱ ለማድረግ መሆኑ ስለተረጋገጠ ከዚህ አንጻር ያነሱት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለዉ አይደለም፡፡በመሆኑም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አስቀድሞ በመዝገቡ ላይ የወሰነዉን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 360/2 መሰረት በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል በዝርዝር በተመለከተዉ አግባብ በተወሰነ ደረጃ ምክንያቱ ከመለወጡ በስተቀር ከዉጤት አንጻር ሲታይ ጉድለት ያለበት ባለመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 153192 ላይ በቀን 26/08/2013ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀድሞ በሰ/መ/ቁጥር 159065 ላይ በቀን 24/03/2011ዓ/ም በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት በቀሪዉ ጉዳይ ላይ ተገቢዉን እንዲወስን የዉሳኔዉ ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡

2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# ንብረት

የሰ.መ/ቁ.181821

ጥቅምት 26/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ መኮንን ስሜነህ

ተጠሪ፡ - አቶ ፀጋሁን ሁነኛው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው አመልካች በተጠሪ መኖሪያ ቤት አካባቢ የወፍጮ ቤት ስራ ለመስራት እንቅስቃሴ መጀመራቸው የሁከት ተግባር በመሆኑ ሊቆም ይገባል በማለት የተወሰነበትን የህግ አግባብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በደቡብ አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የቀረበው ክስ ይዘትም አመልካች ለሆቴል ስራ በሚገለገሉበት G+2 ህንፃቸው ጎን የወፍጮ ስራ ለመስራት ቤት ገንብተው እና የመብራት ቆጣሪ አስገብተው በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣ በቦታው ላይ ወፍጮ ከተተከለ ለጤናም ሆነ ለማህበራዊ ኑሮ ችግር የሚያደርስባቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ እንዲወገድላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ክሱ የቀረበው ወደፊት ሁከት ይፈጠርብኛል በሚል ሲሆን በተጠሪ እና በወፍጮ ቤቱ መካከል የ50 ሜትር ርቀት ያለ በመሆኑ እና የተጠቀሰው ህንፃም ለሆቴል ስራ ሳይሆን ለብረታ ብረት እና ሌሎች እቃዎች ንግድ እየዋለ ያለ በመሆኑ የሚፈጠር ሁከት የለም፣ ተጠሪ በራሳቸው በቦታው ላይ የወፍጮ ስራ ለመስራት በባለቤታቸው ስም ፈቃድ አውጥተው በሂደት ላይ ያሉ በመሆኑ ሁከት ይፈጠርብኛል በሚል ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ስለ ጉዳዩ አግባብነት አለው ካለው የአስተዳደር ክፍል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ

የወፍጮ ስራው በቦታው ላይ መቀጠል በተጠሪ አኗኗር ላይ ሁከት የሚያስከትል ስለመሆኑ አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት ግንባታው እንዲቆም ወስኗል፡፡

ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የከተማው መሪ ፕላን የትኛው ስራ በየትኛው ሳይት ላይ መሰራት እንዳለበት ለይቶ ባላስቀመጠበት አመልካች በህጋዊ መንገድ በቦታው ላይ የወፍጮ ስራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ንግድ ፈቃድ አውጥተው ስራ መጀመራቸው የሁከት ተግባር ነው የሚባል አይደለም በሚል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንኑ ወሳኔን አፅንቷል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በሰ/አ/መ/ቁጥር 03-76409 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ሰኔ 05/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ እና ትዕዛዝ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 25/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም የወፍጮ ስራው ባልተጀመረበት እና ሁከት ስለመፈፀሙም የተረጋገጠ ነገር በሌለበት ሁከት ተፈጥሯል መባሉ ከህግ አግባብ ውጪ ነው፤ ከተጠሪ ጋር የማንዋሰን እና በመካከላችንም የአራት ሰዎች ቤት እያለ እንዲሁም ተጠሪ በራሱ ተመሳሳይ ስራ ለመስራት በሂደት ላይ እያለ የወፍጮ ስራው መጀመር ሁከት ይፈጥራል በሚል መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በመግቢያው ላይ የተገለፀውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ በመታዘዙ ምክንያት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ህዳር 29/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሁከት ክስ በተፈጠረ ሁከት ላይ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠር በሚችል ድርጊት ላይም ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤቶችም በዚሁ መልኩ የወፍጮ መተከል በተጠሪ ኑሮ እና ጤና ላይ እርግጠኛ የሆነ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል አጣርተው የወሰኑ በመሆኑ ውሳኔው ሊነቀፍ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙ ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አጀማመር መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አመልካች በቤቱ አጎራባች ላይ ሊሰራ በሂደት ላይ ያለው የወፍጮ ስራ በኑሮ እና ጤናዬ ላይ ችግር የሚያስከትል በመሆኑ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ ሁከቱ ይቁምልኝ የሚል ነው፡፡

እንግዲህ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን በተመለከተ በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች ውስጥ አንዱ በሀብቱ ላይ የተፈጠረው ህገ ወጥ ሁከት እንዲወገድለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ በመሰረቱ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) የሁከት ተግባርን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮችን ከመጥቀስ ባለፈ በራሱ "ሁከት" ለሚለው ቃል የሰጠው ግልፅ ትርጉም የለም፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለውም የሁከት ተግባር የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ተብለው የተጠቀሱት ሁለት ድርጊቶች ናቸው፡፡ አንደኛው ባለይዞታው በሀብቱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመጠቀም መብቱ ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት አልያም የሚፈጠር እንቅፋት (Interferance) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በባለይዞታው እጅ የነበረን ንብረት/ይዞታ/ በሙሉ ወይም በከፊል በመውሰድ ባለይዞታውን በዚያው መጠን ይዞታ አልባ ማድረግን (Dispossession) የሚመለከት ነው፡፡

በሌላ በኩል የሁከት ተግባሩ በሁለት መንገድ ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንደኛው ይዞታውን ከባለይዞታው እጅ በመውሰድ ወይም በይዞታው ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም መብት ላይ በተጨባጭ/በተግባር/ የሚፈፀም ጣልቃ ገብነት/Disturbance in fact/ ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ በባለይዞታው የይዞታ መብት ላይ በህግ ረገድ የሚፈጠር ሁከት/Disturbance in law/ የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው የሁከት ዓይነት አብዛኛውን ጊዜ የሚፈፀመው አስተዳደር ክፍል ይዞታውን በተመለከተ በራሱ ተነሳሽነትም ሆነ በሌላ ወገን ጠያቂነት በተለያየ መንገድ የባለይዞታውን የይዞታ መብት በሚነካ መልኩ በሚወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፡፡ ይህ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደየሁኔታው ባለይዞታው ይዞታውን በተመለከተ አንድን ድርጊት እንዲፈፅም ወይም እንዳይፈፅም በማድረግ አልያም የባለሃብትነት መብቱን የሚያሳጣ ወይም የሚገድብ ተግባር በመፈፀም ሊሆን ይችላል፡፡

በእነዚህ ሁኔታዎች በይዞታው ላይ ሁከት የተፈጠረበት ባለይዞታ የተወሰደበት ነገር እንዲመለስለት ወይም የተነሳው ሁከት እንዲወገድለት እና በድርጊቱ ስለደረሰው ጉዳት ኪሳራ እንዲሰጠው በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ እና ዳኞችም ይኸው ስለመፈፀሙ ሲያረጋግጡ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድ እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝም ካሳ እንዲከፈል ሊወስኑ እንደሚችሉ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149 ድንጋጌ ጠቅላላ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሲሆንም ፍርድ ቤቶች በሁከት ክስ አርዕስት የቀረበው ጉዳይ በሌላ የህግ ማዕቀፍ ከሚስተናገድ ክርክር ጋር

እንዳይቀላቀል ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ እና ክርክሩንም ሆነ የቀረበውን ማስረጃ ከዚሁ አኳያ ብቻ ሊመለከቱ ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በተጨባጭ በይዞታ መብታቸው ላይ የተፈጠረን የሁከት ተግባር ለማስወገድ ሳይሆን ሊሰራ የታሰበው የወፍጮ ቤት ስራ ሊያስከትል የሚችለውን ጫና በመገመት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በተጨባጭ ባለተፈፀመ ድርጊት ላይ በይሆናል የሁከት ክስ የሚቀርብበት የህግ ማዕቀፍ የለም፡፡ ከተጠሪ ክስ ጭብጥ በግልፅ መረዳት የሚቻለውም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው በፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1225 ስር የተመለከተውን በባለሀብትነት መብት አለመጠን ስለመገልገል ጉዳይን እንጂ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1149 ስር የተመለከተውን በይዞታ ላይ የሚፈጠር የሁከት ተግባርን አይደለም፡፡

በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1225 መሰረት በባለሃብትነት መብት አለመጠን የመገልገል ተግባር መኖር አለመኖሩ የሚለየው የመብቱ አጠቃቃም በጉርብትና አኗኗር ሊታገሱት ከሚቻለው በላይ በአጎራባች ነዋሪዎች መብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ በዚህ መልኩ ክስ የቀረበበት ሰው በንብረት መብቱ ቢያንስ መጠቀም መጀመርን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የወፍጮ ስራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ሂደቶች ከመጀመር ባለፈ ስራው በተጨባጭ አልተጀመረም፡፡ ይህ ባልሆነበት የወፍጮ ስራው በተጠሪ አኗኗር እና ጤና ላይ ጉልህ የሆነ ጉዳት የሚያደርስ ስለመሆኑ በተጨባጭ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ እናም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ መልኩ ሊያስተናግዱ ሲገባ ለጉዳዩ አግባብነት የሌውን የህግ ድንጋጌን ጠቅሰው ግማሹ ሁከት አለ ሲል ሌላው ደግሞ ሁከት የለም በማለት መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተገባበር ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁጥር 03-76409 ላይ ሰኔ 05/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/0312523 ላይ ጥር 08/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/መ/ቁ/01.47520 ላይ ሚያዝያ 05/2010 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ ምክንያቱ ተለውጦ በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 184069

መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- ጂብሪል ሚስባህ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መስከረም 23 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 108602 በቀን 06/03/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 208039 በቀን 18/11/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች የመቃወም አመልካች፣ የአሁን ተጠሪ እና በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ ወ/ሮ አብረኸት አለማየሁ እና አቶ ንዲጋ ከማል ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የመቃወም አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- ፍርድ ያረፈበት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ቤ.ቁ 1223 የሆነው ቤት አካል የሆነው አንድ ክፍል ቤት ባለቤትነቱ የአመልካች መሆኑ እና የስር 2ኛ እና 3ኛ የመቃወም ተጠሪዎች ተከራይተው የሚኖሩበት ቤት መሆኑን፤ የተጠቀሰው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖረው የወሰነ መሆኑን ይህንኑ ቤት አስመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ይሻርለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ ፍርድ ያረፈበት ቤት የግል ቤት መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ቤት በሚመለከት አስቀድሞ የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር 2ኛ እና 3ኛ የመቃወም ተጠሪዎች እንደ አመልካች አቤቱታ አቀራረብ ፍርድ ያረፈበት የመንግስት ቤት ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሚመለከተው አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በአመልካች የቀረቡት ሰነዶች በሙሉ የቤት ቀጥር 1224 ን የሚመለከቱ ናቸው፤ ፍርድ ያረፈበት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ቁጥሩ 1223 የሆነው እና በካርታ ቁጥር 18/36/3523/00 የሚታወቀው ቤት የተጠሪ ቤት መሆኑ የክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሰጠው ማስረጃ ተረጋግጧል፤ ጽ/ቤት ከዚህ ቀደም በሰጠው ማስረጃም የስር 2ኛ እና 3ኛ የመቃወም ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤት ለተጠሪ በተሰጠው ካርታ ውስጥ የተካተተ መሆኑን አረጋግጧል፤ የአመልካች የመቃወም አቤቱታን መነሻ በማድረግ ፍርድ ቤቱ በድጋሚ በሰጠው ትዕዛዝም በተሰጠው  የቤት ቁጥር 1223 የተጠሪ ቤት መሆኑ እና የቤት ቁጥር 1223 እና 1224 የተለያዩ ቤቶች ወይም አንድ ቤት መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ እንደሌለው ገልጾአል፤ በተመሳሳይ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት በሰጠው ምላሽም ቁጥሩ 1223 የሆነው ቤት የግል ቤት መሆኑ እና ቁጥር 1224 ደግሞ የመንግስት ቤት መሆኑን ሁለቱም ቤቶች በአንድ ግቢ በአንድ ጣራ ተያይዘው የሚገኙ እና የያራሳቸው ክፍል ያላቸው ቤቶች መሆናቸውን አረጋግጧል፤ ለተጠሪ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለጊዜው የታገደ መሆኑን የተገለጸ ቢሆንም ካርታው መታገዱ ቤቱ የአመልካች መሆኑን አያረጋግጥም፤ ካርታው በሕጉ አግባብ አስካልመከነ ድረስ ተጠሪ ባለቤት እንደሚሆኑ ግምት ይወሰዳል፤ ስለሆነም ይህንኑ ቤት አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ የሰጠው ውሳኔ ሊሻር አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ መዝገቡን ለውሳኔ ከቀጠረ በኋላ አመልካች የአከራካሪው ቤት ካርታ ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ.ም የመከነ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃ እንዳለው ገልጾ ፍርድ ቤቱ ይህን ማስረጃ እንዲቀበለው አመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም አመልካች ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያያዝለት ያቀረበውን አቤቱታ ክርክሩ ተጠናቆ መዝገቡ ለፍርድ ከተቀጠረ በኋላ የቀረበ ስለሆነ ጥያቄው ስነ ስርዓታዊ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በመቀጠልም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ የጠየቀው ዳኝነት በሕጋዊ ካርታ ግብር እየከፈልኩ የምጠቀምበት ቤት ይለቀቅልኝ የሚል በመሆኑ አመልካች አዋጅ ቁጥር 47/67ን በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም በማለት ያቀረበው መከራከሪያ አግባብነት የለውም፤ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ የተሰጠው ካርታ ስለመምከኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ተጠሪ የቤቱ ሕጋዊ ባለቤት እንደሆነ ይገመታል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አከራካሪው ቤት ለረጅም ዓመታት በመንግስት እጅ የቆየ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለውም፤ አመልካች የተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በቀን 20/08/2009 ዓ.ም ታግዶ እንደነበረ እና በቀን 13/09/2010 ዓ.ም እንደ መከነ የሚያሳይ ተጨማሪ ማስረጃነት እንዲያያዝ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቧል፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማስረጃው ሊያያዝ አይገባም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገ ቢሆንም ይህንኑ በፍርዱ ላይ ሳያስቀምጥ ካርታው ስለመምከኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ለክርከሩ ምክንያት የሆነውን ቤት አካቶ ለተጠሪ ተሰጥቶ የነበረው ካርታ እንዲመክን የተደረገ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይለት ለስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 327(3) መሠረት አቤቱታ አቅርቦ በብይን ውድቅ በተደገረበት ሁኔታ ካርታው ስለመምከኑ የቀረበ ማስረጃ የለም በሚል የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የማጽናቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለተጠሪ የተሰጠው ካርታ እንዲመክን ደብዳቤ ከተጻፈ በኋላ ለተጠሪ እንዲፃፍ እና እንዲያውቀው ሳያደርጉ ስሙን በቀድሞ ሻጭ በማድረግ ጉዳዩ ለብይን ከተቀጠረ ከ10 ወራት በኋላ ተጨማሪ ማስረጃ ይያያዝልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት የለውም፤ አመልካች ተወርሷል ተብለው በመንግስታዊ እና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች በተያያዘ መርምሮ የመወሰን ስልጣን የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍርድ ቤቶች አይደለም በማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመጥቀስ ያቀረበው ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ እና በስር 2ኛ እና 3ኛ የመቃወም ተጠሪዎች መካከል ሲደረግ በነበረው ክርክር መርምሮ ውሳኔ የሰጠው በቀን 26/11/2008 ዓ.ም መሆኑን፤ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን እና ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለተጠሪ የተሰጠው

ካርታ እስካልመከነ ድረስ ተጠሪ የአከራካሪው ቤት ባለቤት እንደሆነ ይገመታል በማለት በቀን 06/03/2010 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ አስቀድሞ በመዝገቡ የሰጠውን ውሳኔ ያጸና መሆኑን፤ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን፤ በመቀጠልም በቀን 15/02/04 ዓ.ም በካርታ ቁጥር 18/36/3523/00 የተሰጠው ካርታ ከቀበሌ ቤት ጋር ተቀላቅሎ የወጣ መሆኑ ስለተገለጸ የክፍለ ከተማው መሬት ልማት ማኔጅመንት በቀን 03/09/2010 ዓ.ም ባጸደቀው መሠረት መክኗል በማለት ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ.ም የጻፈውን ደብዳቤ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀበለው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት ደግሞ አመልካች ያቀረበውን የተጨማሪ ማስረጃ ላያይዝ ጥያቄ መዝገቡ ለውሳኔ ከተቀጠረ በኋላ የቀረበ ነው በማለት ውድቅ አድርጎ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ያጸና መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ፍርድ ቤቱ የአሁን ተጠሪን እና የስር ተከሳሾችን አከራክሮ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ እንዲሁም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ካርታዉ መምከኑ ፍርዱን የሚያስለዉጥና ተጠሪ በፍርድ ያረጋገጠዉን መብት የሚያሳጣ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ መብት ያገኙበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲመክን የተደረገው ከፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ ሲሆን ካርታውን ለማምከን አስተዳደሩ የሰጠው ምክንያት ከቀበሌ ቤት ጋር ተቀላቅሎ የተሰጠ ነው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ መንግስት የሕዝብና የመንግስትን ንብረት የመጠበቅና የማስጠበቅ ሃላፊነት እና ግዴታ እንዳለበት ሁሉ የግለሰቦችን የንብረት መብት የማክበርና የማስከበር ሃላፊነት እንዳለበት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1)(2)፤ 12/1 እና 40/1 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ሁለት መሠረታዊ የመንግስት ሀላፊነቶች መነሻ በማድረግ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሣቀሰው ንብረት ባለሀብት ሆኖ ሊገመት እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህ የሕሊና ግምት ካርታው የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር ወይም ይህን ለመስጠት ስልጣን በሌለው የአስተዳደር ክፍል ወይም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሠረት ማስረጃ ተሰጥቶ ከሆነ ማፍረስ እንደሚቻል የዚሁ ሕግ ቁጥር 1196 ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡ ስለሆነም አንድ የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰረዝበት አካሄድ ሕጋዊ ስርዓት የተበጀለት ከሆነና በሕግ አግባብ የተገኘውን ማስረጃ መሠረት አድርጎ የመፋለም ክስ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አቅርቦ ዳኝነት ያገኘ ሰው በዚሁ ፍርድ መሠረት መብቱ ከሚከበርለት በቀር ከፍርድ በኋላ የባለቤትነት ማረጋገጫ

ደብተሩ ተከራካሪ ሁኖ በተረታው አካል በመሰረዙ ምክንያት በፍርድ የተረጋገጠለትን መብት ሊያጣ አይገባም፡፡

የአስተዳደር አካሉ በፍርድ ቤት ክርክር መረታቱን ከተረዳ በኃላ በሕጉ የተሰጠውን ስልጣን መነሻ በማድረግ ለፍርዱ መስጠት መሠረት የሆነውን ማስረጃ ዋጋ በማሣጣቱ ምክንያት ጉዳዩ እንደ አዲስ ሊታይ ይገባዋል ከተባለ ውጤቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37 ላይ ለዜጎች የተሰጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳይረጋገጥ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78/1 እና 79(1) እና (4) ስር የተረጋጠውንና የተከበረውን የነፃ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን ትርጉም አልባ የማድረግ እና ክርክሮች መቋጫ እንዳይኖራቸው የማድረግ ውጤት አለው፡፡

ስለሆነም አመልካች በክርክር ሂደት በፍርድ አደባባይ ከተረታ በኂላ ተጠሪ መብት ያገኘበትን ካርታ በማምከን አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ እንዲለወጥለት ያቀረበዉ አቤቱታ አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብለን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 208039 ሐምሌ 18 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ፡-183001

ቀን፡-ታህሳስ 22/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

አመልካች፡- አቶ ነጋ ኃይሉ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀና ኃይሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ጭብጥም ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን በ287.88 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈን ጠቅላላ ንብረት ጥር 09/2002 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ወንድማቸው በሆኑት በአሁን አመልካች ስም በብር 35,000(ሰላሳ አምስት ሺህ) ገዝተው አመልካች ቤቱን እንዲያስተዳድሩላቸው ሰጥተው ወደ ውጭ ሀገር የሄዱ መሆኑን፣ ውጭ ሀገር ሆነውም ለቤቱ ማስጨረሻ የሚሆን ብር በአመልካች ስም እየላኩ ቤቱን ያሰሩ መሆኑን፣ ከውጭ ሀገር ከተመለሱ በኋላ አመልካች በእማኞች ፊት ቤቱ የእርሳቸው መሆኑን አምነው ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን በሙሉ ያስረከባቸው ቢሆንም በቤቱ ውስጥ የነበሩትን ተከራዮች አስወጥተው እንዲያስረክቧቸው ሲጠይቁ ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ጠቅሰው በፍርድ ኃይል ተገደው ቤቱን እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት የሚጠይቁ ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ቤቱን ለራሳቸው እንጂ ለአሁን ተጠሪ እንዳልገዙ፣ በሽያጭ ውሉ ላይም ተጠሪ በ4ኛ ምስክርነት ከመፈረም በቀር በቤቱ ላይ መብት የሌለቸው መሆኑን፣ ውጭ ሀገር ሆኜ ገንዘብ ልኬ አሰርቻለሁ ያሉትም ሀሰት መሆኑን፣ ቤቱን ለማሰራት ከብር 200,000(ሁለት መቶ ሺህ) በላይ ወጪ ያደረጉ ሲሆን ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ለመላክ አቅም ያልነበራቸው መሆኑን፣ ተጠሪ ከውጭ ሀገር የላኩትም 320(ሶስት መቶ ሃያ) የኩዌት ገንዘብ ብቻ ሲሆን ይህም በእለቱ

የምንዛሪ ተመን 1,000(አንድ ሺህ) የኢትዮጵያ ብር ብቻ መሆኑን፤ ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን ለተጠሪ የሰጡት የነበረባቸውን እዳ እንዲከፍሏቸው ተጠሪ ይጨቀጭቋቸው የነበረ በመሆኑ ለእዳ መያዥ ያነት በሚል እንጂ ቤቱ የሚመለከታቸው ሆኖ እንዳልሆነ፤ የቤት ባለቤትነት የሚረጋገጠው ህጋዊ ሰነድ በማቅረብ እንጂ በሰው ምስክር ባለመሆኑ እና ከዚህ አኳያ ተጠሪ ቤቱ የራሳቸው ለመሆኑ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ሰምቶ እንዲሁም ቦታው ድረስ ሄዶ የችሎት ምልክታ ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ያቀረቧቸው ምስክሮች ክስ የቀረበበት ቤት የተጠሪ ለመሆኑ ሲያስረዱ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡት ደግሞ አመልካች ቤቱን ሲያስተዳድሩ የነበረ ከመሆኑ ውጭ ቤቱ የራሳቸው ለመሆኑ አላረጋገጡም በሚል ምክንያት አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ብሏል፡፡ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ፀድቋል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሓሴ 24/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት በመጥቀስ በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በስማቸው ሲገዙም ሆነ ውል ሲዋዋሉ የአሁን ተጠሪ በአካል ተገኝተው በ4ኛ ምስክርነት ስለመፈረማቸው እና የቀረቡት ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችም የንብረቱ ህጋዊ ባለቤት አመልካች መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ የሚያረጋግጡ ሆነው እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን በማድበስበስ አልፈው የሰጡት ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ ነው፤ ቤቱን የሸጡ ግለሰብ በምስክርነት ቀርበው ቤቱን የገዛሁትም ሆነ ገንዘብ የከፈልኩት አመልካች ሰለመሆኔ አስረድተው እያለ እንዲሁም ቤቱ ላይ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያቋቋምኩ ለመሆኔ ተገቢነት ባላቸው እና በማናቸውም መልኩ ሊስተባበሉ በማይችሉ እጅግ በርካታ የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎች አረጋግጬ ባለበት የስር ፍርድ ቤቶች እነዚህን ማስረጃዎች ወደ ጎን በማለት ውሳኔ መስጠታቸው ስህተት ነው፤ በአንፃሩ የአሁን ተጠሪ ክስ የቀረበበት ቤት ላይ መብት ያላቸው ለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም፤ ቤቱ ተሰርቶ ያለቀው ተጠሪ ውጭ ሀገር በነበሩበት ወቅት ሲሆን ለአመልካች የላኩት 320 የኩዌት ገንዘብ ብቻ ነው፤ ከዚህ በላይ ገንዘብ የተላከ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ የስር ፍርድ ቤቶች እነዚህን አልፈው ቤቱን ለተጠሪ እንድለቅ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክስ የቀረበበትን ይዞታና ቤት በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫው በአመልካች ስም የሚገኝ ለመሆኑ ከመረጋገጡ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት

ውሳኔ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195 ድንጋጌን ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ የካቲት 26/2012 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የቀረበው መልስ ፍሬ ቃልም ቤቱ በተገዛበት ወቅት አመልካች ምንም ገንዘብ ያልነበረ ሲሆን ተጠሪ ቤቱን የገዛሁት ከባለቤቱ ጋር ተፋትቼ በንብረት ክፍፍል ከደረሰኝ ብር 50,000(ሃምሳ ሺህ) ውስጥ ነው፤ ቤቱም ሲገዛ ይዞታው የገጠር ይዞታ የነበረ በመሆኑ እና በእንደዚህ ዓይነት ቦታ ላይ ውክልና መስጠት አይቻልም በመባሉ ምክንያት እና አመልካች ወንድሜ በመሆኑ በመተማመን በስሙ እንዲገዛ አድርጌ ወደ ውጪ ሀገር ሄጃለሁ፤ ውጭ ሀገር ሆኜም በአመልካች ስም ገንዘብ እየላኩ ቤቱን ማሰራቴን፤ ከውጭ ሀገር ከ6 ዓመት ቆይታ በኋላ ስመጣም አመልካች በሽማግሌዎች ፊት ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶችን አስረክቦኛል፤ አለመግባባቱም የመጣው በቤቱ መኖር ስለምፈልግ ውስጥ የነበሩ ተከራዮችን እንዲያስለቅቅልኝ በመጠየቄ ነው፤ የቤቱ ስመ ሀብት በአመልካች ስም መሆኑ ባለሀብት እንደሆነ ግምት የሚያስወስድ ቢሆንም ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች ቤቱ የራሴ መሆኑን በማስረዳት አስተባብያለሁ፤ የስር ፍርድ ቤቶችም ያቀረብኳቸውን ማስረጃዎች ብቻ ሳይሆን በቦየታው ድረስ ሄደው በችሎት ምልከታ የተገነዘቡትን መሰረት አድርገው የወሰኑ በመሆኑ ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ የለውም የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙ ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም ግራ ቀኙ የሚከራከሩት በቤት ይገባኛል ጉዳይ በመሆኑ ክርክሩ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ንብረት ላይ የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ለአሁን አመልካች ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተካካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት እንደሆነ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195(1) ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ በዚህ መልኩ የተሰጠ ምስክር ወረቀት በራሱ ፍፁም ሳይሆን ሊስተባበል የሚችል ማስረጃ ነው፡፡ ሊስተባበል የሚችልውም የባለሀብትነት ምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር ወይም ማስረጃውን ለመስጠት ሥልጣን በሌለው አስተዳዳር ክፍል መሆኑን፤ ወይም ማስረጃው የተሰጠው በማይረጋ ፅሁፍ መሰረት ወይም ለከሳሹ መቃወሚያ ሊሆን በማይችል ፅሁፍ መሰረት መሆኑን፤ ወይም ማስረጃው የተሰጠበት ንብረት የተገኘው የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠ በኋላ ስለመሆኑ በማስረዳት እንደሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ

መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አጠቃላይ መንፈስ የሚያስገነዝበው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195(1) የባለሃብትነት ማስረጃን በመያዝ ብቻ የተወሰደውን የህግ ግምት ማስተባባል የሚቻለው ማስረጃው የተገኘው ከህግ አግባብ ውጭ በሆነ ሁኔታ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው ለመሆኑ ተጠሪ በራሳቸው አልካዱም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ያቀረቡት መከራከሪያ የንብረቱ ስመ ሀብት በአመልካች ስም የሚገኝ ቢሆንም ንብረቱ የራሴ ለመሆኑ ባቀረብኳቸው ማስረጃዎች በማረጋገጥ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195 መሰረት የተወሰደውን የህግ ግምት አስተባብያለሁ የሚል ነው፡፡ እንግዲህ አስተዳደር ክፍል በአንድ ንብረት ላይ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን የሚሰጠው ማስረጃው የተጠየቀበት ንብረት በእርግጥም የጠያቂው ስለመሆኑ በራሱ በኩል ተገቢን ማጣራት አድርጎ ነው የሚል ግምት ይወሰዳል፡፡ እናም በዚህ መልኩ የተሰጠ ማስረጃን ማስተባበል የሚቻለው ንብረቱ የእኔ ነው የሚለውን ፍሬ ነገር በማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ማስረጃውም ከህግ እና የአሰራር ደንብ ውጭ የተሰጠ መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ተጠሪ ቤቱ የራሴ ነው በማለት ይህንኑ የሚያረጋግጡላቸውን የሰው ምስክር ከማቅረብ ባለፈ ቤቱ ላይ ለአመልካች የተሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1196 ስር በተመለከተው አግባብ ከህግ እና አሰራር ደንብ ውጭ የተሰጠ ስለመሆኑ ያቀረቡት መከራከሪያም ሆነ ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ ይህ ባልተረጋገጠበት ተጠሪ ማስረጃውን አስተባብለዋል የሚያስብል ነገር ባለመኖሩ ተጠሪ አረጋግጫለሁ የሚሉት ፍሬ ነገር ለአመልካች የተሰጠውን ማስረጃ ዋጋ የሚያሳጣው አይሆንም፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በህግ አግባብ የተሰጠ እና ባለው የህግ ስርዓት ያልተስተባበለ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ማስረጃን ወደ ጎን በማለት አመልካች ቤቱን እንዲለቁ መወሰናቸው ግልፅ የህግ ድንጋጌን የተላለፈ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ በእርግጥም የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/75008 ላይ ግንቦት 30/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26077 ላይ መጋቢት 18/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የሀዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/03140 ላይ ታህሳስ 28/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ አመልካች በአስተዳደር ክፍል የተሰጣቸው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የፍ/ብ/ህ/ ቁጥር 1196 በሚያዘው አግባብ ያልተስተባበለ በመሆኑ አመልካች የምስክር ወረቀቱ በተሰጠበት ንብረት ላይ ባለሃብት ናቸው ተብሏል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ/መ/ቁ. 186348

መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና አደን ኡመር

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ ሙሀመድ ኡመር

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር መሬትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሱማሌ ክልል አውበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አደን ኡመር ከተባሉ ግለሰብ ላይ ገዝቼው ይዞታነቱ የእኔ የሆነውና በቦድለይ ቀበሌ የሚገኘው ስፋቱ 192 ሜትር፣ ርዝመቱ ደግሞ 226 ሜትር የሆነውና ለ24 ዓመታት ያክል ያለማንም ተቃውሞ ስጠቀምበት የቆየሁበት የእርሻ መሬት ላይ አመልካች ሁከት የፈጠረች በመሆኑ ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሏ በሰጠችው መልስ አከራካሪውን መሬት ከአባቴ በውርስ ያገኘሁት ሲሆን ተጠሪ መሬቱን ከማንም ላይ የመግዛት መብት የለውም፤ ከተጠሪ ጋር የሚያገናኘን ምንም ነገር የሌለ ሲሆን አመልካች በአካባቢው መሬት የለውም፤ በዚሁ መሬት ላይ በቀበሌው አስተዳደር እና በወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሰጥቶኛል በማለት የተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲደረግላት ተከራክራለች፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ የሰማው የወረዳዉ ፍርድ ቤት አከራካሪውን መሬት አመልካች በውርስ ከአባቷ ያገኘችው ነው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኝ ክርክር ጭብጥ የነበረው ሁከት ይወገድልኝ ሆኖ እያለ መሬቱ ለአመልካች ከዉርስ ጋር የተያያዘ ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ መሠጠቱ ስህተት

ነው፤መሬቱንም ተጠሪ ለ24 ዓመታት ያህል በእጁ ይዞ የቆየና አመልካችም በሀገር ውስጥ እንዳልነበረች በመረጋገጡ መሬቱ የተጠሪ ነው በማለት የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 22/03/2012 ዓ.ም በተፃፈ ሶስት ገጽ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈጽመዋል ያለቻቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምላት ጠይቃለች፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክሩ የሁከት ይወገድልኝ ሆኖ ሳለ ይዞታው የማነው የሚለው ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ አይደለም በማለት የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሲሽር ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጭብጥ መስርቶ የስር ፍርድ ቤት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን መመለስ እየተገባው በህግ ከተሰጠው ስልጣን በመውጣት ማስረጃን መዝኖ መሬቱ የተጠሪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ሁከት ይወገድልኝ ሆኖ እያለ ይዞታው የማነው የሚል ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ መሰጠቱን ስህተት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ እራሱ መልሶ ይዞታው የአመልካች ነው ሲል የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል፡፡ ተጠሪም በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ በቀን 02/07/2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አከራካሪውን መሬት ከአቶ አደን ኡመር ላይ ገዝቼ አጥር አጥሬበት፣ ቤት ሰርቼ እና እያረስኩት ለ25 ዓመታት ያህል የተጠቀምኩበት ሲሆን ለ15 ዓመታት ያህል ደግሞ በስሜ ግብር ስከፍልበት ቆይቻለሁ፡፡ አመልካች ይህንን ይዞታዬን ልቀቅ በማለት አጥር ማፍረስ ስትጀምር ሁከት እንዲወገድልኝ የከሰስኳት ሲሆን የወረዳ ፍርድ ቤቱ ካቀረብኩት ዳኝነት ውጪ ይዞታው የማነው የሚል ጭብጥ በመያዝ ይዞታውን አመልካች በውርስ ያገኘችው ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመሻር መሬቱ የተጠሪ ይዞታ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥታለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘው ጭብጥ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ለ24 ዓመታት በእጁ በነበረዉ ይዞታ ላይ አመልካች ሁከት የፈጠረችበት መሆኑን ሲሆን የጠየቀዉ ዳኝነትም ሁከት ይወገድልኝ የሚል ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ ማንኛውም ዜጋ በንብረት መብቱ ላይ ከሚፈጸም የመብት ጥሰት በህግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡ ለዚህም መሠረታዊ ምክንያት ማንኛዉም ሰዉ ንብረቱን

በሠላም እንዲጠቀምበት ወይም እንዲገለገልበት ለማስቻል ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት የንብረት ባለመብት ወይም ባለይዞታ መሆን ከሚሰጣቸዉ መብቶች ዉስጥ አንዱ የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቦ የባለይዞታነት መብትን ማስከበር ነው፡፡ በመሆኑም በህጋዊ ይዞታዉ ላይ ሁከት የተፈጠረበት ወይም ከህግ ዉጪ ንብረቱ የተወሰደበት ሰዉ ለፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ በይዞታዉ ላይ የተፈጠረዉ ሁከት እንዲወገድ ወይም የተነጠቀዉ ንብረቱ እንዲመለስ እንዲሁም እንደ ሁኔታዉ በሁከቱ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ ካሳ እንዲከፈለዉ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል (የፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1149/1/ ይመለከቷል)፡፡ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ሁከት የተፈጠረ መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ በመወሰን ረገድ ግምት ዉስጥ እንዲያስገባ የሚጠበቅበት ሁከት ተፈጠረ በተባለበት ወቅት ንብረቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በከሳሽ ይዞታ ስር የነበረ መሆን አለመሆኑን እና ድርጊቱን የፈጸመዉ ሰዉ ወይም ተከሳሽ በክሱ የተጠቀሰዉን ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል መብት ያለዉ መሆን ያለመሆኑን ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1140፣ 1149(1) እና 1149(3) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ሁከት መኖር አለመኖሩን በመወሰን ረገድ ከግራ ቀኝ የንብረቱ ህጋዊ ባለቤት ማን ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ ይዞ መመርመር አግባብነት የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ የፍትሐብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኝን ክርክር መሠረታዊ ባህርይ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ትክክለኛ የህግ እና የፍሬ ነገር ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን የመምራት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 246(1)፣ 247 እና 248 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህን አለማድረግ ክርክሩ ከጊዜ እና ከወጪ አንፃር ዉጤታማ እንዳይሆን የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ የሚችል መሆኑንም ልብ ይሏል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ለብዙ ዓመታት በተጠሪ እጅ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ በክሱ ላይ ያመለከተዉን ተግባር የፈጸመች ስለመሆኑ ክዳ አትከራከርም፡፡ የአመልካች ክርክር ይዞታዉ ከአባቱ በዉርስ የሚተላለፍልኝ ነዉ፤ እንዲሁም ተጠሪ ይዞታዉን ከማንም ለመግዛት መብት የለዉም፣ ሽያጩ ከመነሻዉም ዉጤት የሌለዉ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ በእርግጥ የሽያጭ ዉሉ ህገ-ወጥ ሊሆን ይችላል፤ ይዞታዉም እንዲሁ በዉርስ የሚተላለፍላት ሊሆን ይቸላል፡፡ ይሁንና አመልካች ይዞታዉ የሚች አዉራሼ ነዉ የምትል ከሆነ ይህንኑ በማረጋገጥ እና የሽያጭ ዉሉም በህግ አግባብ እንዲፈርስ በማድረግ ተጠሪ በህግ አግባብ ይዞታዉን ለቆ እንዲያስረክባት መጠየቅ ከምትችል በስተቀር በተጠሪ እጅ የሚገኘዉን ይዞታ በኃይል ለመያዝ መብት የላትም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ የፈጸመችዉ ድርጊት የሁከት ተግባር ነዉ የማይባልበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤት እንዲሁም ይግባኙ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ መሠረታዊ ባህርይ ባላገናዘበ መልኩ ይዞታዉ ለአመልካች በዉርስ የሚተላለፍላት ነዉ በማለት የተጠሪን ክስ ዉድቅ

ማድረጉ ስህተት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለቱ ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ የሰጡት ዉሳኔ ከክርክሩ ጭብጥ ዉጪ ነዉ በማለት መተቸቱ በአግባቡ ነዉ፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በአመልካች እጅ ያለዉን ይዞታ በኃይል መያዟን ብቻ መሰረት በማድረግ ሁከት እንዲወገድ መወሰን ሲገባዉ ከዚያ በላይ ሄዶ ይዞታዉ የተጠሪ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔም ከክርክሩ ጭብጥ ዉጪ በመሆኑ መታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ለረጅም ጊዜ በተጠሪ ይዞታ ስር የሚገኝ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ከይዞታዉ መብት አለኝ የምትል ከሆነ በህግ አግባብ መብቷን ማስከበር እየቻለች ይዞታዉን በኃይል መያዟ በእርግጥም የሁከት ተግባር መፈጸሟን የሚያሳይ ሲሆን፣ በክልሉ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሁከት ተግባር ተፈጽሟል ለማለት የሚቻልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከላይ የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሰረት አጣርቶ የተፈጸመ የሁከት ድርጊት መኖር አለመኖሩን መወሰን ሲገባቸዉ ከዚህ በላይ በመሄድ በዉርስ እና በይዞታ ባለቤትነት ላይ የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1. የአዉበሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 106/09 በቀን 08/10/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08/10/2011 በቀን 09/05/2011 ዓ.ም እንዲሁም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 05-01-90/011 በቀን 26/02/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ የተጠሪ ነዉ በሚል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተሽሮ በአንፃሩ ይዞታዉን አስመልክቶ የፈጸመችዉን ሁከት እንድታቆም ተወስኗል፡፡
3. አመልካች በይዞታዉ ላይ መብት አለኝ የምትል ከሆነ መብቷን ለማስከበር ልታቀርብ የምትችለዉን ክስ ይህ ዉሳኔ አይከለክልም፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 186461

መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ሰይድ ዑመር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀዋ ሰይድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻ በአንደኛዉ ተጋቢ ሞት ምክንያት መፍረሱን ተከትሎ የሟች ወራሽ የሆነ ሰዉ የገጠር መሬትን አስመልክቶ በሚያቀርበዉ የድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉን የይርጋ ደንብ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በደቡብ ወሎ ዞን ወረ ባቦ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ በመሆን በተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ ተጠሪና ወላጅ አባቴ በ1976 ዓ.ም በድልድል መሬት ያገኙ ሲሆን ተጠሪ የአባቴን ድርሻ መሬት እንድታካፍለኝ ብጠይቃትም ፍቃደኛ ስላልሆነች የአባቴን ድርሻ መሬት እንድትሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሏ በሰጠችዉ መልስ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፣ አመልካች መብትና ጥቅም የለውም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያቀረበች ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም አመልካች አባቱ ሲሞት መሬቱን እኩል ተካፍለን በየግላችን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰርተን አመልካች የአባቱን ድርሻ የያዘ በመሆኑ ሊጠይቀኝ አይገባም በማለት ተከራክራለች፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የወረዳዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ተጠሪ የአመልካች አባት ድርሻ የሆነውን መሬት የያዘች በመሆኑ ለአመልካች ታስረክብ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኘችዉ ተጠሪ ይግባኟን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ያለፈው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ከመረመረ በኂላ የአመልካች አባት ከሞቱበት

ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ይዞታውን በስሟ በደብተር ላይ አስመዝግባ ይዛ የምትጠቀምበት በመሆኑ፤ አመልካችም አባቱ በህይወት እያለ የጎጆ መውጫ መሬት ተሰጥቶት ሲጠቀም እንደቆየ በሰውና ማስረጃ በመረጋገጡ፤ የአመልካች አባት ከሞተ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታይ 20 ዓመት ያለፈው መሆኑን ጠቅሶ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ውድቅ ተደርጎበታል፡፡ በመቀጠል የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይህም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 22/03/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ይዞታውን በህጋዊ መንገድ ይዛ ስትጠቀምበት ነበር በማለት በደፈናው ገልጾ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ቢወስንም በምን ዓይነት ህጋዊ መንገድ እንደተያዘ አልገለጸም፤ በይዞታው ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማውጣቷም ይዞታውን ህጋዊ አያደርገውም፤ በህገ-ወጥ መንገድ መሬትን የያዘ ማንኛውም ሰው የይርጋ መቃወሚያን ሊያነሳ እንደማይችል እየታወቀ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም የገጠር መሬት ውርስን በሚመለከት ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ደንብ የትኛው እንደሆነ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባቀረበዉ መልስ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ደንብ በውርስ ህጉ ላይ ያለው የይርጋ ደንብ ሲሆን ይህንኑ መሠረት አድርጎ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ ትክክለኛ እና ተገቢ በመሆኑ ሊፀና ይገባዋል በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሰረት ያደረገዉ የአባቱ የነበረ እና በዉርስ የሚተላለፍለትን ይዞታ ተጠሪ ድርሻዉን ልታካፍለዉ ፍቃደኛ አለመሆኗን በመጥቀስ ሲሆን፣ተጠሪ በበኩሏ አባቱ መሞቱን ተከትሎ አመልካች ድርሻዉ የተሰጠዉ ከመሆኑም በላይ የአመልካች አባት በ1990 ዓ.ም በዚህ ዓመት በሞት የተለየ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል በማለት መከራከሯን ነዉ፡፡አባቱ በ1990 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለመሆኑ አመልካች ክዶ አይከራከርም፡፡ የዉርስ ድርሻ ይገባኛል ጥያቄ ሳያቀርብ

የቆየበት የተለየ ምክንያት ያለዉ ስለመሆኑም አመልካች የገለጸዉ ነገር የለም። ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉም ክሱ የቀረበዉ አዉራሽ ከሞተበት ከ 20 ዓመት በኂላ መሆኑን በመጥቀስ ቢሆንም ለዚህ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ (ድንጋጌ) ግን አልጠቀሰም። አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበዉ ክርክር ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት አጥብቆ የሚከራከረዉ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 መሠረት በህገ ወጥ መንገድ የተያዘን መሬት ለማስለቀቅ የሚቀርብ ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት ነዉ። ስለሆነም ይርጋን አስመልክቶ ከገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጁ ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ድንጋጌ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ መሆን ያለመሆኑ አመልካች ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ካደረገዉ የክስ ምክንያት ጋር በማገናዘብ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቀዳሚነት እንዲያከናዉን ከሚጠበቁበት ተግባራት ዉስጥ አንድ እና መሠረታዊዉ ለቀረበለት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ የህግ ክፍል የመለየት ተግባር (identification of applicable law) ነዉ። አስቀድሞ ይህን ማድረግ የቀረበዉ ክስ የክስ ምክንያት ያለዉ መሆን አለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን እና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ካሉ አስቀድሞ በመለየት መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት የሚያችለዉ ሲሆን፣ ጉዳዩ ወደ ሙሉ የክርክር ሂደት (full scale trial) የሚገባ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ጭብጥ ይዞ ክርክሩን በመምራት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን ድንጋጌ በአግባቡ ለይቶ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት ያስችላል። በአጠቃላይ አስቀድሞ በጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል መለየት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከክርክር አመራር ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና ድንጋጌዎች መሠረት ባደረገ መልኩ ክርክሩን ይመራ ዘንድ ያስችለዋል። የክርክር አመራርን አስመልክቶ በህጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ጉዳዩን መምራት፣ የክርክር አመራሩ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ እንዲሆን በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ እንዲረጋገጥ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ፣ ተቀባይነት እና አግባብነት ያለዉን ማስረጃ ለይቶ በማስቀረብ እና በመመርመር ወሳኝ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ነጥሮ እንዲወጡ በማድረግ ብሎም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ድንጋጌ ለይቶ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ያስችላል። በክስ አቤቱታ ላይ የሚገለጹ ነገሮችን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 222 ላይ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች እንዲሁም ተከሳሽ ለክሱ ምክንያት በሆነዉ ነገር ላይ በኃላፊነት የሚጠየቅበትን ሁኔታ ከሳሽ በግልጽ በክሱ ማካተት እንዳለበት፤ እንዲሁም የሚጠየቀዉ ዳኝነት በግልጽ መመልከት እንዳለበት በአንቀጽ 224 በአስገዳጅ መልክ ከደነገገባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል አስቀድሞ እንዲለይ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ አመልካች ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ተጠሪ በእጇ የሚገኘዉን የአባቱ ድርሻ የሆነዉን መሬት እንድታካፍለዉ ነዉ፡፡ ይህም ዳኝነቱ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ አሁን በአገራችን በስራ ላይ ባለዉ የመሬት ስሪት መሠረት መሬት የህዝብ እና የመንግስት በመሆኑ እንዲሁም መሬት የእራሱ የሆነ የተለየ ባህርይ ያለዉ ቢሆንም፤ ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ መብቶች እና ግዴታዎች፣ አጠቃላይ ግንኙነቶች የሚመሩት በንብረት ህግ አጠቃላይ መርሆዎች በመሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚወጡ ህጎች/አዋጆች በንብረት ህግ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚመደቡ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከንብረት ጋር በተገናኘ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ህጎች እና መርሆዎች ከመሬት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክርክር እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የንብረት ህግ ማለት ለአንድ ንብረት ባለመብት ወይም ባለይዞታ የሆነ ሰዉ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት የሚገዛ ነዉ፡፡ የንብረት ህግ አንድ ሰዉ በአንድ ንብረት ላይ ባለቤትነት ወይም ባለይዞታ ሊሆን የሚቻልበትን መንገድ፤ የመብቱ ዓይነት፣ ስፋት እና ማዕቀፍ፤ መብቱ ከአንዱ ወደ ሌላ ሊተላለፍ የሚችልበትን ሥርዓት የሚደነግግ የህግ ክፍል ነዉ፡፡ ንብረትን የመከታተል መብት፣ በመብቱ ማዕቀፍ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የመጠቀም መብት እንዲሁም ክስ አቅርቦ መብትን የማስከበር መብት የንብረት ባለ ሀብት ወይም ባለይዞታ መሆን ከሚሰጣቸዉ መብቶች ዉስጥ ዋነኞቹ ስለመሆናቸዉ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

አንድ ሰዉ የአንድ ንብረት ባለመብት ወይም ባለይዞታ መሆኑ የሚታወቀዉ እና የንብረት ባለ ሀብት ወይም ባለይዞታ መሆን በሚሰጣቸዉ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ ንብረቱን በህግ አግባብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑም ከአጠቃላይ የንብረት ህግ ጽንሰ ሃሳብ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም አንድን ንብረት አስመልክቶ የሚቀርበዉን ክስ ተከትሎ ንብረትን የሚመለከት የህግ ክፍል ተፈፃሚ የሚሆነዉ ከሳሽ ክሱን ያቀረበዉ ንብረቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ካደረገ በኋላ በንብረቱ ላይ ያለዉ መብት እንዲከበርለት የቀረበ ክስ መሆኑ በክሱ የተረጋገጠ ሲሆን ነዉ፡፡ ይህም ማለት አንድ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ንብረትን የሚመለከት መሆኑ ብቻዉን ጉዳዩን የንብረት ክርክር አያደርገዉም ማለት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ንብረትን የሚመለከት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ዳኝነት ሁለት ገጽታዎች ያሉት ሲሆን አንደኛዉ የንብረት ባለሀብትነት ወይም ባለይዞታነትን ወይም ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ያለዉን ማንኛዉንም መብት ለማስከበር የሚቀርብ ዳኝነት ሲሆን፤ ሁለተኛዉ የንብረት ባለቤትነት ወይም ባለይዞታነት መብት በፍርድ ኃይል እንዲተላለፍለት በዚህም የንብረቱ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ለመሆን የሚቀርብ ዳኝነት ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ በንብረት ህግ ማዕቀፍ የሚመራ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ዓይነት ለቀረበዉ የመብት ይተላለፍልኝ ጥያቄ መሠረት የሆነዉን ምክንያት መሠረት በማድረግ የሚወሰን ሲሆን እንደየጉዳዩ ባህርይ በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች መሠረት የሚዳኝ ነዉ፤ ይህም ማለት ለቀረበዉ የመብት ይተላለፍልኝ

ዳኝነት መሠረቱ ዉል ከሆነ የዉል ህግ ድንጋጌዎች፣ ዉርስ ከሆነ የዉርስ ህግ ድንጋጌዎች፣ ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የቀረበ ከሆነ የቤተሰብ ህግን መሠረት በማድረግ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነዉ። ይህ፣ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት፣ ከመሬት ጋር የተያያዘ ለሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችም እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ የሟች አባቱ ባለቤት የነበሩት ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ይዛ ስለምትገኝ የአባቱን ድርሻ እንድታካፍለዉ ነዉ። ይህም የሚያሳየዉ አመልካች የወራሽነት መብቱን ተጠቅሞ የአባቱን የባልነት ድርሻ መሬት ተጠሪ እንድታካፍለዉ መጠየቁን የሚያሳይ ነዉ። በአመልካች አባት እና በተጠሪ መካከል የነበረ ጋብቻ በሞት ምክንያት መፍረሱን ተከትሎ የቀረበ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት በመሆኑም ጉዳዩ የሚመራዉ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተመለከተ በቤተሰብ ህጉ ላይ በተመለከቱት ደንቦች እና መርሆዎች መሠረት ነዉ። ይሁንና ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ የተለየ ድንጋጌ የለዉም። የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009ም ሆነ ከዚህ በፊት የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/98 ይህን ጉዳይ የሚገዛ ድንጋጌ የላቸዉም። በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ደንብም ቢሆን ያላግባብ የተያዘን የገጠር መሬት ለማስለቀቅ ለሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ እንጂ (ይህ የይርጋ ደንብ ይዞታዬ ያላግባብ ተይዟል በሚል ለሚቀርቡ ለሁሉም ጉዳዮች ተፈፃሚነት አለዉ ወይ? የሚለዉ ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ) የባለ ይዞታነት መብት ይተላለፍልኝ በሚል ለሚቀርብ ክስ ተፈፃሚነት ያለዉ አይደለም። በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 17937 ላይ (በቅጽ 4 ላይ እንደታተመዉ) ጋብቻ በአንደኛዉ ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በአስር ዓመት ጊዜ ዉስጥ ካልቀረበ ጥያቄዉ በይርጋ እንደሚታገድ የህግ ትርጉም ሰጥቷል። ይህ ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 መሠረት በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ ነዉ። በመሆኑም አመልካች አባቱ ከሞቱበት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ጥያቄ ሳያቀርብ ቆይቶ ከ20 ዓመት በኋላ ያቀረበዉ የድርሻ ይገባኛል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ነዉ። ስለሆነም፣ ምንም እንኳን ለቀረበዉ ክስ ምክንያት የሆነዉን ጉዳይ በአግባቡ በመመርመር ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የይርጋ ድንጋጌ መለየት ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ በደፈናዉ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ ስህተት ቢሆንም፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በሚል ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንፃር ሲታይ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም። በዚህም ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል።

## ዉሳኔ

1. የደቡብ ወሎ ዞን መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39263 በቀን 02/05/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 01-07795 በቀን 09/07/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 0325868 በቀን 02/03/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የሰ/መ/ቁ.186946

ቀን፦26/08/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡ 1. ወ/ሮ አለሚቱ ተክሌ

2. ሻለቃ ዮሐንስ አበበ

ተጠሪዎች፡ 1. ወ/ሮ እብስቴ ምስክር

2. የእንጅባራ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አቤ/መ/ቁ/03-76609 ላይ ህዳር 02/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አንደኛ ተጠሪ የካቲት 10/2001 ዓ.ም ፅፈው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አዊ ዞን ብሔረሰብ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ሁለተኛ ተጠሪ እና አመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ አንደኛ ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት ክስ ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን 1100 ካሬ ሜትር የከተማ ይዞታ አቶ ግርማ ጓልየ የተባለው ሟች ልጃቸው በ1989 ዓ.ም በህጋዊ መንግድ ለዳቦ ቤት ስራ በሚል ከመንግስት ተመርቶ ይህንኑ ይዞታ እላዩ ካለው ጅምር ግንባታ ጋር በመያዥያነት አስይዞ ከልማት ባንክ ብር ተበድሮ እዳውን ሳይከፍል የሞተ መሆኑን፣ እርሱ ከሞተ በኋላ በወራሽነት ሟች የተበደረውን እዳ ከፍለው በመጨረሳቸው ንብረቱ እንዲተላለፍላቸው ከልማት ባንክ ማረጋገጫ አፅፈው ወደ ሁለተኛ ተጠሪ ጽ/ቤት ሲሄዱ ጽ/ቤቱ ከይዞታው ላይ በስሜን አቅጣጫ 20X8 ሜትር በአጠቃላይ 160 ካሬ ሜትር ይዞታ ለአሁን አመልካቾች አስተላልፎ አመልካቾቹም በይዞታው ላይ ቤት ሰርተው መያዛቸውን ያረጋገጡ መሆኑን፣ ይኸው ይዞታ እንዲለቀቅላቸው ቢጠይቁም ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልፀው

ተከሳሾቹ በፍርድ ኃይል ተገደው በይዞታው ላይ ያለውን ቤት በራሳቸው ወጪ አፍርሰው እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ሁለተኛ ተጠሪ እና አመልካቾች አለን ያሉትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስረ ነገር ክርክር በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ በዚሁ አግባብ ጉዳዩ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ከታየ በኋላ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ የአሁን አመልካቾች ቤቱን ሲሰሩ ከአሁን አንደኛ ተጠሪ የቀረበ ተቃውሞ መኖር ያለመኖሩ በግራ ቀኙ ምስክር እንዲጣራ እንዲሁም ክርክር የተነሳበት ይዞታ መጠን እና የአሁን አንደኛ ተጠሪ ተቀነሰብኝ የሚሉት የይዞታ መጠን በባለሙያ ተጣርቶ እንዲወሰን በነጥብ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተመለሰ መሆኑን፤ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም እንዲያጣራ በተባለው ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ምስክር በመስማት እና ስለይዞታው ከክፍሉ አስተዳደር ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ቤቱን ሲሰሩ የአሁን አንደኛ ተጠሪ ተቃውመው የነበረ ለመሆኑ አረጋግጫለሁ፤ አስተዳደር ክፍሉም የሌላውን ሰው ይዞታ ቀንሶ ለሌላው መስጠት አይችልም፤ አመልካቾች በቦታው ላይ ስላወጡት ወጪ ከፈለጉ አስተዳደሩን ከሚጠይቁ በቀር የአሁን አንደኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ ያላቸውን መብት የሚያጡበት ምክንያት ባለመኖሩ በይዞታው ላይ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ሊያስረክቧቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ከዚህ በኋላ በነበረው ክርክር የከተማ አስተዳደሩ የክርክሩ አካል ያልነበረ በመሆኑ ጉዳዩ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ታይቶ በሰ/መ/ቁ/119930 ላይ ሚያዝያ 24/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ የክርክሩ አካል ተደርጎ እና የሚያቀርበው መከራከሪያ ተሰምቶ እንዲወሰን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነጥብ ተመልሷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም በታዘዘው መሰረት ለሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ ልኮለት ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ አዟል፡፡ ዋናውን የክርክር ጭብጥ በተመለከተ የአሁን አመልካቾች ቤት የሰሩበትን ይዞታ በህጋዊ መንገድ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል የወሰዱ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ቤቱን አፍርሰው ይዞታውን ሊለቁ አይገባም፤ የአሁን ተጠሪ ይዞታቸው ለሌላ አካል በመጠሰቱ ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳት ከፈለጉ አስተዳደሩን ይችላሉ በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሳኔ በማጠናከር ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ በመሻር የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ታህሳስ 01/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም

ይዞታው ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል በህጋዊ መንገድ የተሰጠን ሲሆን ግንባታውን ያከናወነውም ተገቢውን የግንባታ ፈቃድ በማውጣት ነው፤ በይዞታው ላይ ግንባታ ስናከናውንም የአሁን አንደኛ ተጠሪ በራሳቸው የግንባታ እቃ ሲሸጡልን የነበረ እና ግንባታውን የሚያውቁ ቢሆንም ቤቱ እንዳይሰራ ያቀረቡት ተቃውሞ አልነበረም፤ በዚህ መልኩ ቤቱ ከተሰራ ከአምስት ዓመት በኋላ አፍርሰው ይዞታውን ይልቀቁልኝ ተብሎ ክስ መቅረቡም ሆኖ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ተቀበሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት የሰሩት በህግ አግባብ ከሁለተኛ ተጠሪ ባገኙት 160 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ እና አንደኛ ተጠሪ በወቅቱ አንስቼ ነበር የሚሉትን መቃወሚያ እንዳልገፉበት በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾች ቤቱን አፍርሰው ይዞታውን ያስረክቡ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ምክንያት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት አንደኛ ተጠሪ ጥር 18/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች ቤቱን ሲሰሩ መቃወሜን በከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርበው በተሰሙት ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑ ግንባታውን አልተቃወምሽም ልባል አይገባም፤ በባንክ እዳ ምክንያት ይዞታው ታግዶ ባለበት እና ስለመታገዱም ማዘጋጃ ቤት በራሱ እያወቀ ለመኪና ማቆሚያ ተብሎ በተተው ቦታ ላይ ቅን ልቦና በጎደለው መልኩ በካርታ ላይ ካርታ ከመሰጠቱም በላይ ግንባታው በህገ ወጥ መንገድ የተገነባ በመሆኑ እንዲፈርስ መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ ጥር 08/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ቦታው ለአሁን አመልካቾች ሲሰጥ ክፍት እና የሚቆጣጠር ሰው ያልነበረው ነው፤ በቦታው ላይ ግንባታ ሲከናወንም የአሁን አንደኛ ተጠሪ አሸዋ እና ጠጠር ለአመልካቾች ሲሸጡ የነበረ እና ስለግንባታውም የሚያውቁ ቢሆንም ያቀረቡት ተቃውሞ አልነበረም፤ አመልካቾች በቦታው ላይ የሰሩት ግንባታ ከሚፈርስ ይልቅ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ ሌላ ተመጣጣኝ ይዞታ ቢሰጣቸው የተሻለ ይሆናል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆኑት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎች፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ይዞታ ቀደም ብሎ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ አውራሽ ልጅ የነበረ ሲሆን ከዚሁ ይዞታ ላይ 160 ካሬ ሜትር ተቀንሶ ለአሁን አመልካቾች የተሰጠ መሆኑ እና አመልካቾችም በዚሁ ይዞታ ላይ ቤት የሰሩ ስለመሆኑ

አላከራከረም፡፡ የአንደኛ ተጠሪ ዋነኛ መከራከሪያ ይዞታው ከህግ አግባብ ውጭ ተቀነሶ ለአመልካቾች የተሰጠ በመሆኑ በይዞታው ላይ የተሰራው ቤት ፈርሶ ይዞታውን ልረከብ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ቤቱን የሰራነው በህጋዊ መንገድ በተሰጠን ቦታ ላይ በተገቢ የግንባታ ፈቃድ በመሆኑ እና ግንባታውንም ስናከናውን የቀረበብን ተቃውሞ ባለመኖሩ አፍርሰን ልንለቅ አይገባም በማለት አጥብቀው ይሞግታሉ፡፡

እንግዲህ ከዚህ የክርክር አድማስ በዋናነት ሁለት አብይት ነጥቦች ምላሽ ማግኘት የሚጠበቅባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179 ስር የተመለከተው በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የሚደረግን ግንባታ የመቃወም ጉዳይ ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል በተሰጠ ይዞታ ላይ የሚደረግ ግንባታን ያጠቃልላል? ወይስ አያጠቃልልም? የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አግባብ ካለው የአስተዳደር ክፍል በህጋዊ መንገድ በተሰጠ ይዞታ ላይ ይዞታ ተቀባዩ ሀብትና ንብረቱን አፍስሶ ግንባታ ካከናወነ በኋላ ይዞታው የሌላ ሰው መሆኑን ቢረጋገጥ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ነጥቦች በሚከተለው መልኩ በተናጠል ታይተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ባለመሬቱ ሳይቃወም በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንፃ የሰራ ሰው የዚሁ ህንፃ ባለሃብት እንደሆነ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179(1) ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ሀሳቡ የሚመነጨው ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1178 ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1178 ይዘት ጋር ተዳምሮ ሲታይ መገንዘብ የሚቻለው አንዱ ቁምነገር ህንፃ የሚገነባው ሰው ህንፃውን የሚገነባው የራሱ ሳይሆን በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ስለመሆኑ የሚያውቅ እና የሚቀበል መሆኑን፣ ህንፃውን የሰራው ሰውም በገነባው ህንፃ ላይ የሚኖረው መብት ትክክለኛ ባለይዞታው ግንባታውን አስመልክቶ በሚኖረው እውቀት እንዲሁም ግንባታውን በመቃወም ወይም አለመቃወሙ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የፍ/ብ/ህ ቁጥር 1179 ድንጋጌ የሚመለከተው በአንድ መሬት ትክክለኛ ባለይዞታ እና በዚሁ ይዞታ ላይ መብት ሳይኖረው ህንፃ በሰራ ሰው መካከል የሚኖረውን የመብት አድማስ ነው፡፡

በአንፃሩ ስልጣን ባለው አስተዳደር አካል በተሰጠው ይዞታ ላይ ህንፃ የሚሰራ ሰው በይዞታው ላይ ግንባታ የሚያከናውነው በይዞታው ላይ ትክክለኛ ባለመብት ነኝ በሚል ስሜት እንጂ ይዞታው የሌላ ሰው ቢሆንም ባለው የህግ አግባብ ወደፊት የህንፃው ባለሃብት እሆናለው በሚል እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል ጉዳይ በመሆኑ ግንኙነቱ በሁለት ግለሰቦች መካከል ሳይሆን በመንግስት እና በባለይዞታው መካከል ነው፡፡ እናም አግባብ ካለው አስተዳደር አካል በተሰጠ ይዞታ ላይ በባለይዞታው የሚከናወን ግንባታን አስመልክቶ ይዞታው ይገባናል የሚሉ ሌሎች ሰዎች ግንባታውን መቃወም አለመቃወማቸው ህንፃውን በሰራው ሰው የባለሀብትነት መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179 ስር የተመለከተው በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የሚደረግ

ግንባታን የመቃወም ጉዳይ አግባብ ባለው አስተዳደር አካል በተሰጠ ይዞታ ላይ በሚደረግ ግንባታ ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ውጤቱ ሀገሪቱ ከምትከተለው የመሬት ስሪት ባህሪ፣ ከዜጎች ህገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብት እና ኋላ ላይ ትክክለኛ ባለይዞታ መሆኑ የተረጋገጠው ሰው በሌላ መንገድ ከመካስ አኳያ ከሚኖረው ተነፃፃሪ መብት ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ መሆኑን እና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት በመሆኑ ዜጎች በባዶ መሬት ላይ የሚኖራቸው የይዞታ መብት ብቻ ስለመሆኑ የህገ መንግስት አንቀፅ 40(3) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

በሌላ በኩል በመሬት ላይ ጉልበት እና ገንዘባቸውን አፍስሰው ሀብት ያፈሩ ዜጎች የዚያው ንብረት የባለሀብትነት መብታቸው በህገ መንግስት ጥበቃ የተደረገለት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(7) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህም የተነሳ በባዶ መሬት ላይ መብት አለን ከሚሉት ሰዎች ይልቅ ይዞታውን በእጁ አድርጎ እና ንብረት አፍርቶበት የያዘ ሰው የተሻለ መብት ያለው ስለመሆኑ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/105125 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ መሰረቱ የአሁን አንደኛ ተጠሪ አውራሽ የነበረ ቢሆንም አመልካቾች ይህንኑ ይዞታ ስልጣን ካለው አስተዳደር አካል አግኝተው ንብረት ያፈሩበት በመሆኑ ባዶ ይዞታው ይገባኛል ከሚሉት አንደኛ ተጠሪ ይልቅ የተሻለ መብት አቋቁመዉበታል፡፡ እናም ባዶ ይዞታው የእኔ ነው በሚል መነሻ ምክንያት ብቻ አመልካቾች በይዞታው ላይ ያፈሩትን ንብረት አፍርሰው እንዲለቁ የሚገደዱበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአንፃሩ የአሁን አንደኛ ተጠሪ ጥያቄ ባዶ ይዞታን የሚመለከት በመሆኑ እና በተወሰደባቸው ይዞታ ምትክ ተመጣጣኝ ይዞታ ለማግኘት እድሉ ያላቸው እና ሁለተኛ ተጠሪም በዚሁ መልኩ ለመፈፀም ፈቃደኛ ስለመሆኑ ካቀረበው መከራከሪያ መረዳት የሚቻል በመሆኑ በዚሁ መልኩ እንዲካሱ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ከዚህ አኳያ ማየት ሲገባው አመልካቾች ቤት የሰሩበት ይዞታ የሌላ ሰው ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት በመያዝ አመልካቾች ግንባታውን አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ መወሰኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1179 ድንጋጌ የተፈፃሚነት ወሰን፣ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት የተመለከተውን የመሬት ስሪት ባህሪና የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት እንዲሁም አንደኛ ተጠሪ በሌላ መንገድ ከመካስ አኳያ የሚኖራቸውን ተነፃፃሪ መብት ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አቤ/መ/ቁ/03-76609 ላይ ህዳር 02/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/36997 ላይ መጋቢት 07/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ሁለተኛ ተጠሪ ከአሁን አንደኛ ተጠሪ ይዞታ ላይ ቀንሶ ለአመልካቾች በሰጠው 160 ካሬ ሜትር ይዞታ ምትክ ተመጣጣኝ መጠን እና ደረጃ ያለውን ይዞታ እንዲተካላቸው ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

## የሀሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ በባልደረቦቼ ሃሳብ የማልስማማ በመሆኑ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡

በዚህ መዝገብ እያከራከረ ያለው ይዞታ ለአመልካች ልጅ በህጋዊ መንገድ ተሰጥቶ እና በባንክ እዳ ተይዞ የነበረ መሆኑ ግራ ቀኙን እና አመልካችም የልጃቸው ወራሽ መሆናቸው አላከራከረም፡፡

የሚያከራክረው ይዞታ ለልጃቸው ባንክ ላበደረው ብድር በመያዣ ተይዞ የነበረ መሆኑም እንዲሁ የሚታወቅ ነው፡፡ አመልካች ልጃቸው ከሞተ በኋላ ዕዳውን ከፍለው ይዞታውንና ቤቱን መረከብ የሚገባቸው በመሆኑ እዳ ከፍለው ይዞታውን ሊረከቡ ሲሉ ግን ከላዩ ላይ 160 ካ.ሜ. ይዞታ አስተዳደሩ ቀንሶ የሰጠ በመሆኑ አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ ያላቸውን የወራሽነት መብት የሚጥስ ከመሆኑም በላይ በባንክ በዕዳ የተያዘን ቦታ ቤት ሲሰራበት አልታቀወምሽም ሊባል የሚገባው ባለመሆኑ እንዲሁም አስተዳደሩ አንድን ይዞታ ከመሬት ባንክ አውጥቶ ለግለሰቦች የሚሰጥ እስካልሆነ ድረስ ይዞታው ላይ

ተገቢ ጥናት ማድረግና ከይገባኛል ክርክር ነፃ የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ እየተገባው በአንድ በኩል ለአመልካች ልጅ ሰጥቶ እና በባንክ ለዕዳ መያዣ ሆኖ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ ልክ ባለቤት እንደሌለው ይዞታ ለግለሰቦች የሸነሸነ መሆኑ ፍትሀዊነት የሌለውና የአስተዳደሩን አሰራር ብልሹነት የሚያሳይ በመሆኑ ይህ ይዞታና ቤት በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለአመልካች እንዲለቀቅ መወሰኑ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍና መሰረታዊ የህግ ስህተትም ያልተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊፀና እንጂ ሊሻር የሚገባው አልነበረም የሚል ሀሳብ ስላለኝ ከአብላጫው ድምጽ በዚህ ምክንያት ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

# ውርስ

የሰ.መ.ቁ 180281

ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ት ዮዲት ሰለሞን

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይናለም ወርቁ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው የምትክ ወራሾች የአውራሾቻቸውን ተወላጅነት ስላላረጋገጡ ሊወርሱ አይችሉም በሚል የተሰጠን የመጨረሻ ውሳኔ ህጋዊ አግባብነት መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

የክርክሩ ሥረ ነገር አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች የሴት አያታቸው የኑዛዜ ወራሽነት ባረጋገጡበት የወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ የአሁን ተጠሪ በመቃወም አመልካችነት ቀርበው በመከራከራቸው ኑዛዜው በህግ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አያሟላም በሚል ውድቅ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካች የወላጅ አባታቸው ምትክ ወራሽነት በፍርድ ቤት በማረጋገጥ የአሁን ተጠሪ ይዘው የሚገኙትን የአያታቸውን የውርስ ሃብት እንዲያካፍሏቸው አዲስ ክስ ያቀርባሉ፡፡ ይኸው ጉዳይ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የአሁን አመልካች የኑዛዜ ወራሽነት ውድቅ መደረጉ ምትክ ወራሽነቷን የሚከለክል መሆኑ አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲወሰን ለወረዳው ፍርድ ቤት በነጥብ ይመልሳል፡፡

በዚህ መልኩ ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ ግራ ቀኙ የአያታቸው ወ/ሮ ማሰሬ ወልደዓብ የምትክ ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጫለሁ በሚል ክርክር የተነሳበትን የሟች የውርስ ሃብት ተጠሪ ለአመልካች እንዲያካፍሉ ይወስናል፡፡

በአሁን ተጠሪ ይግባኝ ባይነት ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በነጥብ ከተመለሰ በኋላ የተሰሙት የግራ ቀኙ የሰው ምስክሮች ለየቀረቡላቸው ተከራካሪ ወገኖች እንደ ክሱ እና መከላከያ መልሱ ያረጋገጡ መሆኑን፤ የኑዛዜ ወራሽነት ክርክር በተደረገበት መዝገብ ላይ

የተሰሙት ምስክሮች ደግሞ የሟች ብቸኛ ልጅ የተጠሪ ወላጅ እናት መሆናቸውን ያረጋገጡ መሆኑን፤ የተጠሪ እናት በሞቱ ጊዜም ሟች ወ/ሮ ማሰሬ ወልደዓብ የሞተችው ልጇ ነች በሚል ለቅሶ ተቀምጠው እድርም የበሉ ስለመሆኑ መረጋጡን በምክንያትነት በመጥቀስ አመልካች ልትወርስ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማሻሻል ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

በዚሁ ጉዳይ ላይ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/291900 ላይ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከሰማ በኋላ ሚያዝያ 08/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙ የአያታችን ምትክ ወራሾች ነን ከማለት ባለፈ ወላጆቻቸው በእርግጥም የአያታቸው ተወላጅ ስለመሆናቸው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 769 እና 770(1 እና 2) ወይም በክልሉ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 171፣ 172፣ እና 174 በተመለከተው አግባብ ባልተረጋገጠበት ምትክ ወራሽ ናቸው ተብሎ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ ግራ ቀኙ ሊወርሱ አይችሉም ብሏል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሀምሌ 02/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተከናወነው ክርክር ይዘት እና አድማስ አንፃር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ መወለድ እና ወራሽነት ሁለቱም በቤተሰብ ህግ የሚገዙ ፅንሰ ሀሳቦች ቢሆኑም አንድ ዓይነት ዓላማ እና ግብ ያላቸው አይድሉም፡፡ የመወለድ መሰረተ ሀሳብ ዋናው ዓላማ ወላጅን እና ቤተዘመድን ለይቶ ከማወቅ ጋር የተያያዘ የማንነት ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን የወራሽነት ፅንሰ ሀሳብ መሰረታዊ ዓላማ ደግሞ ከሞት በኋላ የሟቹ ንብረት የመውረስ መብት ላላቸው ሰዎች የሚተላለፍበትን ሥርዓት የሚመለከት ነው፡፡ በቤተሰብ ህግ ውስጥ ሁለቱ መሰረተ ሀሳቦች የሚረጋገጡበት መንገድም የተለያየ ነው፡፡ መወለድ የሚረጋገጠው በቀዳሚነት የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ መሆኑን፤ በዚህ መልኩ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ከሌለ ደግሞ ተወላጅነት በሁኔታ የማረጋገጥ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 769 እና 770(1) ድንጋጌዎች እንዲሁም ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 አንቀፅ 171-174 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአንፃሩ የወራሽነት መብት ከኑዛዜ አልያም ያለ ኑዛዜ የሚመነጭ መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ ማረጋገጫ መንገድ የለም፡፡ በእርግጥ የሟች ተወላጅ መሆን ለሟች ወራሽነት ብቁ ከሚያደርጉ ህጋዊ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 842 እና 830 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን የሟችን ንብረት ለመውረስ ስለተወላጅነት በተመለከተው ሥርዓት መሰረት መወለድን ማረጋገጥ የግድ ይላል ማለት እንዳልሆነ ሊጤን ይገባል፡፡ በተለይ ውርሱ የሚመለከተው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን በሆነ ጊዜ (የማስረጃውን ህጋዊነት የመቃወሙ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ መያዝ በቂ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 996-998 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ወላጅ አባትዋ የሟች ወ/ሮ ማሰሬ ወልደዓብ ልጅ መሆናቸውን እና አባትዋ ሟችን ቀድመው የሞቱ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የምትክ ወራሽነት ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የዚህን ማስረጃ ህጋዊነት አስመልክቶ የቀረበ ተቃራኒ ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ አመልካች በወላጅ አባትዋ እግር ተተክተው የውርስ ሀብት የተባለውን ንብረት ለመጠየቅ በህግ የተቋቋመ መብት አላቸው ማለት ነው፡፡ እናም በዚህ መልኩ የተረጋገጠ መብት እያለ አመልካች የአባታቸውን ተወላጅነት እንዲያረጋግጡ የሚገደዱበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በህግ ያልተቀመጠን መመዘኛ ጠቅሶ አመልካች የወላጅ አባታቸውን ተወላጅነት ስላላረጋገጡ ሊወርሱ አይችሉም በሚል ከአመልካች አኳያ የሰጠው ውሳኔ የተወላጅነት እና የወራሽነት ፅንሰ ሃሳቦችን ባህሪ እና መሰረታዊ ልዩነት ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተረጓጎም ስህተት ሆኖ በመገኘቱ በእርግጥም የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1.የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/291900 ላይ ሚያዝያ 08/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/286137 ላይ ሰኔ 21/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ሄ/መ

## የሃሣብ ልዩነት

እኔ በሶስተኛ ተራ ቁጥር ስሜ የተጠቀሰው ዳኛ አመልካችና ተጠሪ በዚህ መዝገብ የተከራከሩበትን ጉዳይ /ጭብጥ/ በመመርመር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት አብላጫው ድምፅ በሰጠው የህግ ትርጉምና ውሣኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ ለልዩነት ምክንያት የሆኑኝን ነጥቦች ከዚህ ቀጥሎ እገልፃለሁ፡፡

በመሰረቱ የሟችን ንብረት ለመውረስ ስለተወላጅነት በተመለከተው ስርአት መወለድን ማረጋገጥ ሁሌም ግዴታ ነው ብዬ አላምንም፡፡ተከራካሪ ወገኖች ተወላጅነት ላይ ክርክር ከሌላቸው የሟችን ንብረት ለመውረስ ተወላጅነትን አረጋግጣችሁ ቅረቡ ሊባሉ የሚችሉበት አግባብ አይኖርም፡፡ነገር ግን ተወላጅነት ያለኑዛዜ ለመውረስ መነሻ ነውና ተወላጅነት ላይ ክርክር ከቀረበ ግን ይኸው ነጥብ በአግባቡ ተጣርቶና ተረጋግጦ እልባት ሊያገኝ ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ የአመልካች ወላጅ አባት የሟች ወ/ሮ ማስሬ ወልደዓብ ልጅ አለመሆናቸውን ገልፀው ተጠሪ መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የሚያሳይ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍድ ቤትም ይህንኑ መነሻ በማድረግ የኑዛዜ ወራሽነት ክርክር በተደረገበት መዝገብ ላይ የተሰሙትን ምስክሮች የምስክርነት ቃል በመጥቀስ የአመልካችን የወራሽነት ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ከዚህ በማለፍ የግራ ቀኙ አውራሾች የወ/ሮ ማስሬ ተወላጅ መሆናቸው ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቅሶ የግራ ቀኙን የተተኪ ወራሽነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የአመልካች አውራሽ ተወላጅነት ላይ ክርክር መቅረቡን ያሳያል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ተሠጠኝ የሚሉት የምትክ ወራሽነት ማስረጃ እንደ ፍፁም የማይስተባበል ማስረጃ የሚቆጠር ሳይሆን በማስረጃነት በቀረበበት መዝገብ ላይ አግባብነቱ ላይ እንደ አንድ ማስረጃ አይነት ክርክር ሊቀርብበት የሚችል ሊተችና ሊስተባበል የሚችል ከመሆኑ አንፃር የአመልካች አውራሽ ተወላጅነት በቅድሚያ ተረጋግጦ ከቀረበ በኋላ ወራሽነትን አስመልክቶ የቀረበው ክርክር ሊታይ ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶት በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የፀናው ውሳኔ ይህንን የአመልካችን አውራሽ ተወላጅነት መረጋገጥ አለመረጋገጥ አስመልክቶ በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ከግምት ውስጥ ያስገባ ባለመሆኑ፣ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የአመልካች አውራሽ ተወላጅነታቸው ላይ በሌላ መዝገብ ላይ የተሰጠን የምስክርነት ቃል በመውሰድ ከዚህ የምስክርነት ቃል አንፃር አመልካች ያላቸውን ክርክርና ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔውን መስጠቱ አግባብ ባለመሆኑ፣  ሰበር ሰሚ ችሎቱም አመልካችን አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ ከላይ የከፍተኛ

ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለመተቸት በተመለከተው ምክንያት አግባብ ባለመሆኑ ተጠሪን አስመልክቶም ተጠሪ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ሳይኖር ወራሽ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ እነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ተሽረው የአመልካች የተተኪ ወራሽነት የዳኝነት ጥያቄ በቅድሚያ የአውራሻቸው ተወላጅነት በህጉ አግባብ ተረጋግጦ ሢቀርብ የሚታይ ነው ተብሎ ሊዘጋ ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቼ በሃሳብ ተለይቼያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

የሰ.መ.ቁ.191963

ሚያዚያ 12 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካቾች፡........1. አቶ ምንዳዬ አስታጥቄ
2. አለሚቱ አስታጥቄ } ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡..........1. ወ/ሮ በላይነሽ አስታጥቄ
2. ብርቱካን አስታጥቄ
3. ጌጤ አስታጥቄ
4. ደነቀ አስታጠቄ
5. ናትናኤል አስታጥቄ } ተወካይ ወ/ሮ አለሜ ነገሰ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የዉርስ መሬት ክርክር የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን በሄጦሳ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካቾች የሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር ከሳሾች፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑ ባሻዉ አስታጥቄ እና ዳምጦ አስታጥቄ የሥር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካቾች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.3095 በ19/5/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሾች (የአሁን ተጠሪዎች) በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታችን አቶ አስታጥቄ ረታ በ2008 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን የሟች የዉርስ ይዞታ የሆነዉን 8 ገመድ የእርሻ መሬት የተለያየ መጠን ተከሳሾች ይዘዉ ስለሚገኙ አንድ ላይ ተመልሶ ለወራሾች ክፍፍል እንዲደረግልን እንዲወሰን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች (የአሁን አመልካቾች) በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ አባትና እናታችን በ1987 ዓ.ም አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ሰጥተዉን እስካሁን እየተጠቀምንበት

ያለን ስለሆነ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾችም በሰጡት መልስ አባትና እናታችን በ1998 ዓ.ም አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ሰጥተዉን ለአስራ ሶስት አመታት በየግላችን ስንጠቀምበት የነበረ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ዉድቅ ነዉ፣ 3ኛ ተከሳሽ ከአባቴ 3 ገመድ መሬት በኪራይ የተቀበልኩኝ ስለሆነ የኪራይ ጊዜዉ ሲያልቅ መከፋፈል ይችላሉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮች በመስማት በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከ1ኛ-3ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች አባታቸዉ በሕይወት እያለ አንድ አንድ ገመድ መሬት ሰጥቷቸዉ ሲጠቀሙበት የቆዩ ስለሆነ ይህ መሬት የዉርስ ይዞታ ስላልሆነ የከሳሾች ጥያቄ ዉድቅ ነዉ፤ 3ኛ ተከሳሽ 3 ገመድ መሬት በኪራይ ይዣለሁ እና 4ኛ ተከሳሽ አንድ ገመድ መሬት በስጦታ ተሰጥቶኛል የሚሉትን በተመለከተ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ የዉርስ መሬት በመሆኑ የሟች ልጆችና ወራሾች እንዲከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሾች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የሥር ከሳሾች አሁንም በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ተከሳሾች ለክርክር መነሻ የሆነዉን መሬት በስጦታ አግኝተናል የሚሉበት የስጦታ ዉል በሚመለከተዉ አካል ያልተመዘገበ ስለሆነ መሬቱ የዉርስ ሀብት ነዉ፤ መሬቱም ሟች ከሞተ በኋላ የተያዘ መሆኑ በሰዉ ማስረጃ እና ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ ያረጋገጠ ስለሆነ ሟች ከሞተ በኋላ ሶስት አመት ስላልሞላ የቀረበዉ ክስ በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ፣ ለክርክር መነሻ የሆነዉ 8 ገመድ የእርሻ መሬት የዉርስ ሀብት በመሆኑ፣ የሟች ወራሾች 8 ቦታ እኩል እንዲከፋፈሉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በ30/6/2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በአመልካቾች እጅ የሚገኘዉን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት አባትና እናታችን በ1987 ዓ.ም ሰጥተዉን ለ23 ዓመታት ያህል እየተጠቀምንበት ያለን መሆናችን በማስረጃ አረጋግጠን እያለ እና ይህ ደግሞ በተጠሪዎች ማስረጃ ባልተስተባበለበት፣ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ ሳለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች በአመልካቾች እጅ የሚገኘዉን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ ሀብት ተቀላቅሎ እኩል እንካፈል የሚል ዳኝነት ባልተጠየቀበት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን፤ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸናልን፣ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ16/3/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አከራካሪዉ መሬት ከአመልካቾች ተሰጥቶ የግላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ የለም፤ መሬቱ የዉርስ ሀብት መሆኑ ስለተረጋገጠ የገቢ ምንጭ የሌለን እኛ ተጠሪዎች በመሆናችን በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ቅድሚያ የማግኘት መብት አለን፣ አመልካቾች የዉርስ ሀብት እንካፈል የሚሉ ከሆነ በእጃቸዉ ላይ ያለዉን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ ቀላቅለዉ እንዲካፈሉ፣ ይህ ካልሆነ በእጃቸዉ ላይ ያለዉን ይዞታ ይዘዉ እንዲቀሩ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካቾች ባቀረቡት የመልስ መልስ ለክርክር መነሻ የሆነዉና በእጃችን ላይ ያለዉ መሬት በስማችን ተመዝግቦና የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠን ሆኖ ሳለ፣ እኛ በእጃችን ያለዉ ሀብት ይበቃናል እንጂ የቀረዉን የዉርስ ሀብት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንድንካፈል ያቀረብነዉ ጥያቄ ስለሌለ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ተቀባይነት የለዉም በማለት የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት የአሁን አመልካች የዉርስ ሀብት እንድካፈል የሚል ጥያቄ ባቀረቡበት ቀደም ሲል በወላጆቻቸዉ ተሰጥቷቸዉ ለረጅም አመታት ሲጠቀሙበት የቆዩትን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ ሀብት መልሰዉ ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ መባሉ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መሰረት የአሁን አመልካቾች ከሥር ጀምሮ ባቀረቡት ክርክር ወላጆቻችን በሕይወት እያሉ የሰጡትን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት የግላችን ስለሆነ ልንጠየቅ አይገባም ብሎ ከመከራከር ባለፈ የወላጆቻችን ቀሪ የዉርስ ሀብት ከሌሎች ወራሾች ጋር እንድንካፈል በማለት የጠየቁት ዳኝነት ያለመኖሩን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ተጠሪዎችም ባቀረቡት ክርክር አመልካቾች የዉርስ ሀብት እንካፈል የሚሉ ከሆነ የእርሻ መሬቱን ወደ ዉርስ እንዲቀላቅሉ፤ ይህ ካልሆነ የያዙትን መሬት ይዘዉ እንዲቀሩ፣ ቀሪ የዉርስ ሀብት እንዳይጠየቁ በማለት መከራከራቸዉ ሲታይ አመልካቾች በእጃቸዉ ያለዉ የእርሻ መሬት እንዳይጠየቁ እንጂ ቀሪ የዉርስት ሀብት መጠየቃቸዉን አስረግጠዉ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ የአመልካቾች ወላጆች በሕይወት እያሉ በ1987 ዓ.ም አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ለአመልካቾች ሰጥቷቸዉ አመልካቾች ከዛን ጊዜ ጀምሮ በመሬቱ ሲጠቀሙበት መቆየታቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካቾች ቀደም ሲል በወላጆቻቸዉ ተሰጥቷቸዉ ለረጅም አመታት ሲጠቀሙበት የነበረዉ የእርሻ መሬት እንዳይጠይቁ እንጂ ቀሪ የዉርስ ሀብት ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ከሆነ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ አመልካቾች ቀሪ የዉርስ ሀብት

ለመካፈል ጥያቄ ባላቀረቡት አስቀድመዉ በወላጆቻቸዉ ተሰጥቷቸዉ ሲጠቀሙበት የነበሩትን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መመለስ አለባቸዉ ወይ? የሚለዉ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1073 መሰረት ዉርሱን አልቀበልም ያለ ወራሽ ከሟቹ አስቀድሞ የወሰደዉን ነገር በዉርስ ዉስጥ መልሶ መግባት እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡ ይህ ማለት ወራሽ አስቀድሞ ከዉርስ የተቀበለዉ ንብረት/ነገር ካለ እና ዉርስ ሲከፈት የዉርስ ሀብቱን ለመዉረስ ካልጠየቀ ይህን አስቀድሞ የወሰደዉን ንብረት/ነገር ወደ ዉርስ መልሶ የዉርስ ሀብቱን ለመዉረስ የሚገደድበት አግባብ የለም፤ ወራሹ የዉርስ ሀብት ለመዉረስ ከፈለገ ግን አስቀድሞ የወሰደዉን ነገር ሳይመልስ የዉርስ ሀብት የሚዉርስበት አግባብ ስለሌለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1074 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈጸም ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካቾች ወላጆቻቸዉ አስቀድሞ የሰጧቸዉን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ልንጠየቅ አይገባም ብለው ከመከራከራቸዉ በስተቀር የዉርስ ሀብት ልንካፈል ይገባል ብሎ ያቀረቡት ጥያቄ አለመኖሩን ካቀረቡት ክርክርም ሆነ ከሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቾች አስቀድሞ የተሰጣቸዉ የእርሻ መሬት ይዘዉ እንዲቀሩ ከመጠየቅ ባለፈ የሟች አባታቸዉን የዉርስ ሀብት ለመካፈል የጠየቁት ዳኘነት እስከሌለ ድረስ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ ሀብት ለመመለስና ዉርሱን ከሌሎች ወራሾች ጋር ለመካፈል የሚገደዱበት የህግ አግባብ የለም ማለት ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ልንጠየቅ አይገባም ከማለት ባለፈ የዉርስ ሀብት ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ በሌለበት አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መልሰዉ ከሌሎች ወራሾች ጋር ሊከፋፈሉት ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉን የህግ ድንጋጌ ዓላማና የግራ ቀኙን ክርክር ያላገናዘበ ስለሆነ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መልሰዉ የዉርስ ሀብቱን ከሌሎች ወራሾች ጋር ሊከፋፈሉት ይገባል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ አግባብ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉሳኔ

1. የሂጦሳ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.26761 በ9/4/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.83480 በ27/5/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ክልል

ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.309550 በ19/5/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት እና የሥር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መመለስ የለባቸዉም በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ፍ/ቤቶች የሥር 3ኛ ተከሳሽ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መመለስ የለበትም በማለት የሰጡት ዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ መልሰው የዉርስ ሀብቱን ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲከፋፈሉ በማለት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡ ነገር ግን የሥር 3ኛ ተከሳሽ በተመለከተ እና ቀሪዉ የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የአሁን አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን አንድ አንድ ገመድ የእርሻ መሬት ልንጠየቅ አይገባም ከማለት ባለፈ የዉርስ ሀብት ለመካፈል ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ስለሌለ፤ አመልካቾች ይህን አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ወደ ዉርስ ለመመለስ አይገደዱም ብለናል፡፡ አመልካቾች አስቀድሞ የወሰዱትን የእርሻ መሬት ይዘዉ ከሚቀሩ በስተቀር ቀሪ የዉርስ የእርሻ መሬትን ከሌሎች ወራሾች ጋር ለመካፈል አይችሉም ብለናል፡፡ በአመልካቾች እጅ ካለዉ የእርሻ መሬት በስተቀር የሚች አባታቸዉ የዉርስ መሬት (ስድስት ገመድ የእርሻ መሬት) አመልካቾችን ሳይጨምር በሌሎች ወራሾች /ተጠሪዎች/ መካከል እኩል ሊከፋፈሉት ይገባል ብለናል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
7. ይህ ችሎት በ2/7/2012 ዓ.ም በሂጦሳ ወረዳ ፍ/ቤት በአፈጻጸም መ.ቁ.30585 ላይ የተጀመረዉ የአፈጻጸም ክርክር ታግዶ እንዲቆይ የሰጠዉ እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

# ቤተሰብ

የሰ.መ.ቁ.179121

ሐምሌ 28 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1.ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2.ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ካሳ በለጠ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ሥራይቱ ነጋሽ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር የተጀመረዉ በባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት በመ.ቁ.83938 ግንቦት 8 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የአሁን ተጠሪ ከአሁን አመልካች ጋር በነበረን ጋብቻ ዉስጥ ያፈረናቸዉ ንብረቶች እንዲያካፍለኝ በማለት ዘርዝራ ካቀረበቻቸዉ መካከል አጭር ሚኒሽር መሳሪያ የጋራ ሀብታችን ስለሆነ የአሁን አመልካች እንዲያካፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቃለች።

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ ከአሁን ተጠሪ ጋር ያፈራነዉ አጭር ሚኒሽር መሳሪያ የለም ሐሰት ነዉ፣ ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተ ክርክሩን አቅርበዋል።

ከዚህ በኋላ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር የሚኒሻ ጽ/ቤት ስለመሳሪያዉ አጣርቶ እንዲልክ በታዘዘዉ መሰረት አጭር ሚኒሽር መሳሪያ በአሁን አመልካች ስም ተመዝግቦ እንደሌለ የገለጸዉን እና የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ መኖሩ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ የአሁን ተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፣ በሌሎች ንብረቶች እና

በልጆች ቀለብ ጋር በተያያዘ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል። የአሁን ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባህርዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ዉሳኔ እና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ችሎቱ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን መሬት እና ባህርዛፍ በተመለከተ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት፤ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ በተመለከተ ግን የአሁን ተጠሪዎች የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል የአሁን አመልካች ድብቅ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ ያለዉ መሆኑን ያስረዱ ስለሆነ፣ ይህ መሳሪያ ድብቅ በመሆኑ አለመመዝገቡ መሳሪያዉ የለም የሚያሳኝ ስላልሆነ፣ የአሁን አመልካች ይህን መሳሪያ ለአሁን ተጠሪ ሊያካፍላት ይገባል፣ የሚኒሽር የጦር መሳሪያ ግምት ብር 10,000 ስለሆነ ይህን መሳሪያ እጣ በማጣጣል በእጣዉ አጭር ሚኒሽር መሳሪያዉ የደረሰዉ ለሌለዉ ብር 5,000 እንዲከፍልና አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ እንዲወስድ በማለት በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻሻል ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለመሻር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ22/9/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ ለክርክር መነሻ የሆነዉ አጭር ሚኒሽር መሳሪያ በስሜ ተመዝግቦ እንደማይገኝ የሚኒሻ ጽ/ቤት ገልጾ እያለ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን ተጠሪ የሰዉ ምስክሮች ዘመድ አዝማድ ሆኖ በሀሰት በሰጡት የምስክርነት ቃል ድብቅ መሳሪያ አለ በሚል ተጠሪ እንድትካፈል በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ ግድፈት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል።

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንደትሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ15/6/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ፍ/ቤት አከራካሪዉን የጦር መሳሪያ እኩል እንካፈል የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክራለች። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ ስላላቀረበ ታልፏል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፣የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክር ምክንያት የሆነዉ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ የጋራ ሀብት ስለሆነ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል። የአሁን ተጠሪ ባቀረበችዉ ክስ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ የጋራ ሀብታችን ስለሆነ እንዲያካፍለኝ በማለት የጠየቀች ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ይህ የጦር መሳሪያ የለም

በማለት ተከራክሯል። የሚኒሻ ጽ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ በአሁን አመልካች ስም ተመዝግቦ እንደሌለ ገልጾዋል። በሌላ በኩል የአሁን ተጠሪ የሰዉ ምስክሮች በሰጡት የምስክርነት ቃል የአሁን አመልካች ድብቅ አጭር ሚነሽር የጦር መሳሪያ እንዳለዉ መመስከራቸዉን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል። በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ድብቅ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ ያለዉ በመሆኑ ባይመዘገብም መሳሪያዉ መኖሩን የሰዉ ምስክሮች የመሰከሩ ሲሆን፣ በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰዉ ምስክሮች ስለዚህ መሳሪያ ያሉት ነገር አለመኖሩን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል። ይህ ማለት የአሁን አመልካች ድብቅ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ ያለዉ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ መሳሪያዉ በሕጉ አግባብ ስልጣን ባለዉ የሚኒሻ ጽ/ቤት ዘንድ አለመመዝገቡ መሳሪያዉ የለም የሚያስብል አይደለም። ይህ ሚኒሽር የጦር መሳሪያ መኖሩ እስከተረጋገጠ ድረስ በሕጋዊ መንገድ ስለመያዙ ከሚመለከተዉ አካል ዘንድ ተመዝግቦ ፈቃድ አለመሰጠቱ መሳሪያዉ የለም እና የኢኮኖሚ ዋጋ የለዉም የሚያስብል ነገር አይሆንም። ይህ የጦር መሳሪያ የኢኮኖሚ ጥቅም ያለዉ መሆኑን በመገንዘብ የአማራ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በ2007 ዓ.ም ባወጣዉ የጦር መሳሪያ ዋጋ ተመን ማሻሻያ መሰረት የሚኒሽር የጦር መሳሪያ ግምቱ ብር 10,000 መሆኑን አመልክቷል። ይህ የጦር መሳሪያ የኢኮኖሚ ጥቅም ያለዉ ንብረት እና ባልና ሚስት ይህን መሳሪያ በትዳር እያሉ ያፈሩ እስከሆነ ድረስ፣ ከሚመለከተዉ አካል ዘንድ መሳሪያዉ ተመዝግቦና መሳሪያዉን ለመያዝ ፈቃድ አለመሰጠቱ፣ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት እንዳይሆን የሚያደርገዉ እና ጋብቻቸዉ በፍቺ ሲፈርስ የሚካፈሉት ንብረት አይሆንም የሚያስብል አይደለም። ይህም ከአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 73 [1] እና 101 አንጻር ማየት ይቻላል። ስለሆነም ለክርክር መነሻ የሆነዉ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ መኖሩ በማስረጃ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ ግራ ቀኙ ይህን ንብረት እንዲካፈሉ መባሉ ተገቢ ነዉ። ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 [3፣ ሀ] እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክር መነሻ የሆነዉ አጭር ሚኒሽር የጦር መሳሪያ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ስለሆነ እኩል እንዲካፈሉ በማለት የክፍፍል ሥርዓቱን በማመልከት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ የተሰጠ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

## ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍ/ቤት በመ.ቁ.83938 ግንቦት 8 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ጸንቷል።

2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።

3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

**መዝገቡ ተዘግቷል።**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ.190295

ሚያዚያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፊይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡........ወ/ሮ ቱኒዝ ሙሉጌታ- ጠበቃ ብርሃኑ ተሻገር ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡.........1. አቶ አብርሃም ከለለዉ- ቀርበዋል

2. አቶ ዳንኤል ይስፉልኝ } ጠበቃ ይልማ አቻሜ ቀርበዋል

3. ወ/ሮ እመቤት አድማሱ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍርድ**

ይህ የባልና ሚስት የጋራ ሀብትና የግል ዕዳን የሚመለከት ክርክር የተጀመረዉ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር አመልካች፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሥር ተጠሪ፣ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የሥር የመቃወም አመልካቾች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.247544 በ20/5/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ የአሁን አመልካች እና የአሁን 1ኛ ተጠሪ በመካከላቸዉ የነበረዉ ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ መፍረሱን ተከትሎ አመልካች ባቀረበችዉ የንብረት ዝርዝር በአዲስ አበባ ከተማ አዲስ ከ/ክ/ማ ወረዳ 8 የሱቅ ቁጥር 380 ሽራ ተራ አካባቢ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉ ለተጠሪ የግል እዳ በሐራጅ የተሸጠ ስለሆነ ንብረቱ የጋራ ሀብታችን በመሆኑ የሽያጭ ገንዘቡ ግማሽ ድርሻዬ እንዲወሰንልኝ በማለት ያመለከተች ሲሆን፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር በፍርድ የተረጋገጠዉ ዕዳ የባልና ሚስት እዳ ስለሆነ እዳዉ ተከፍሎ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ እኩል ልንካፈል ይገባል እንጂ እዳዉ ሳይከፈል ግማሽ ድርሻ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረበችዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የተባለዉ እዳ መጠንና ባለገንዘቦቹ እነማን እንደሆኑ፣ ከአመልካች ጋር የጋራ ዕዳቸዉ መሆኑን በማስረጃ ያስረዳዉ ነገር ስለሌለ ከተያዘዉ ገንዘብ ላይ ግማሹ የአሁን አመልካች ድርሻ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የመቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረቡ ሲሆን፣ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት አቤቱታ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለንግድ ሥራቸዉ ምክንያት ህዳር 15 ቀን 2005 ዓ.ም የሚመነዘር ቼክ ብር 350,000 ጽፈዉ ሰጥተኝ በቂ ስንቅ ስለሌለዉ ክስ አቅርቤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246856 በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ከተለያየ ወጪና ወለድ ጋር እንዲከፍሉ የተወሰነባቸዉ ስለሆነ ከአመልካች ጋር የጋራ ዕዳቸዉ በመሆኑ የጋራ ንብረታቸዉ ተሽጦ ከተቀመጠዉ ገንዘብ ዉስጥ እዳዉ አስቀድሞ እንዲከፈልኝ፣ ዉሳኔዉ እንዲነሳልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ አቤቱታ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለንግድ ሥራቸዉ ምክንያት ብር 300,000 መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ.ም የሚመነዘር ቼክ ጽፈዉ ሰጥተዉኝ በቂ ስንቅ ስለሌለዉ ክስ አቅርቤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246809 በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ይህን ገንዘብ ከወለድና ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍለኝ ስለወሰነበት፣ እዳዉ ከአመልካች ጋር የጋራ እዳዉ ስለሆነ ይህን ገንዘብ እንዲከፍሉኝ እንዲወሰንልኝ፣ ዉሳኔዉ እንዲሻሻልን በማለት አመልክቷል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ የመቃወም ማመልከቻ ላይ በሰጠችዉ መልስ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የጠቀሱት እዳ የተወሰነዉ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ነዉ፣ እዳዉ ከጋብቻዉ በፊት 1ኛ ተጠሪ የገባዉ ነዉ፣ እዳዉ እኔን የሚመለከት አይደለም በማለት ተከራክራለች፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ የተጠቀሰዉ እዳ በትዳር ዉስጥ የተፈጠረ ስለሆነ የጋራ እዳ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በዚህ ላይ በሰጡት መልስ ይህ እዳ የተፈጠረዉ የአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ዉስጥ እያሉ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉም ሆነ በንግድ ሕጉ የጋራ እዳቸዉ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እዳን በተመለከተ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ዉሳኔ ያሰጡበትን መዛግብት በማየት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለአሁን 2ኛና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲከፍል የተወሰነበት እዳ የግል እዳ ነዉ ወይስ ከአሁን አመልካች ጋር የጋራ እዳቸዉ ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246856 እና 246809 በሆኑት መዝገቦች ለዉሳኔ መሰረት የሆኑት ሁለቱም ቼኮች የተጻፈባቸዉ ቀን የአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ይህን የሚያስተባብል ማስረጃ በማቅረብ ያስረዳችዉ ነገር የለም፤ በፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 (1) መሰረት ከአሁን 1ኛ ተጠሪ የግል

ሀብት የሚጠየቅ ቢሆንም ይህን ዕዳዉን ለመሸፈን በቂ ካልሆነ ከአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የጋራ ሀብት ላይ ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲከፈል፤ ይህም ዕዳዉን የማይሸፍን ከሆነ ከአሁን አመልካች ድርሻ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍ/ቤቱም ቅሬታዉን አያስቀርብም በማለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሻር ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ28/5/2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የመቃወሚያ ማመልከቻ ያቀረቡበት ፍርድ መብታቸዉን የማይነካ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች አቤቱታቸዉን በመቀበል የሰጡት ዉሳኔ ሊታረም ይገባል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በፍርዱ እንዳረጋገጠዉ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱት እዳ የ1ኛ ተጠሪ የግል እዳ እንጂ አመልካችን የሚመለከት አይደለም፡፡ ዕዳዉ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ ነዉ ተብሎ በፍርድ ተረጋግጦ እያለና እዳዉ ለትዳር ጥቅም መዋሉ ፍርድ ባልተሰጠበት እዳዉ ከአመልካች የግል ሀብት እንዲከፈል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246856 እና 246809 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ በሰጠዉ ቼኮች ስለሆነ አመልካችን አይመለከትም፤ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ ክርክር 1ኛ ተጠሪ እዳ መኖሩን ጠቅሶ የተከራከረ ቢሆንም በማስረጃ ማስረዳት ባለመቻሉ ዉድቅ ተደርጎበታል፡፡ እነዚህ ቼኮች ለክፍያ ያቀረቡት ጋብቻችን ከፈረሰ እና ቼኮቹ ለክፍያ መቅረብ ከሚገባቸዉ ጊዜ የ2ኛ ተጠሪ 3 ዓመት ከ11 ወር በኋላ እና የ3ኛ ተጠሪ 4 ዓመት ከ7 ወር ካለፈ በኋላ የቀረቡና የክፍያ ጊዜያቸዉ ያለፈባቸዉ ሆኖ ሳለ፣ 1ኛ ተጠሪ በእነዚህ ቼኮች የቀረበዉን ክስ በተመለከተ በቂ መከላከያ እያለዉ ማስፈቀጃ ሳያቀርብና ሳይከራከር ዉሳኔ እንዲሰጥበት ሆኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በእነዚህ ቼኮች በወንጀል ተከሶ የተቀጣ ሆኖ ሳለ፣ አሁን የቀረበዉ ክርክርና የተሰጠዉም ፍርድ የአመልካችን ጥቅም ለመጉዳት ሆን ተብሎ የተጻፈ ቼክ መሰረት ተደርጎ የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ አመልካች እዳዉን ልትከፍል አይገባትም ተብሎ እንዲወሰንልኝ ወጪና ኪሳራም እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያስነሳዉ እዳ የግሉ ነዉ ተብሎ ከተወሰነ በኋላ የባለእዳዉ ሀብት እዳዉን የማይሸፍን ከሆነ አመልካች ትክፈል የተባለበት እና ከጋብቻ ፍቺ በኋላ የቀረበ እዳም የግል ነዉ ተብሎ ከተወሰነ የጋራ የሚሆንበት አግባብነት፣ ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዟል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ሱቅ ከአመልካች ጋር ጋብቻ ዉስጥ ያፈራነዉ ንብረት በመሆኑ፣ ቼኩም ከአመልካች ጋር በጋብቻ ዉስጥ ለእያንዳንዱ እቃዎች መግዣ በዱቤ ስንጠቀምበት የነበረዉ ስለሆነ እዳዉ የአመልካችም ጭምር ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪ ህዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ላይ በቼክ ጉዳይ ክስ አቅርበን በመ.ቁ.246856 እና 246809 ላይ አስወስነንበታል፡፡ ይህ እዳ የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ እዳቸዉ ስለሆነ የጋራ ሀብታቸዉ ከመከፋፈላቸዉ በፊት እዳዉ መከፈል አለበት፡፡ ይህ እዳ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ በትዳር ዉስጥ እያሉ የተፈጠረ እዳ በመሆኑ ከ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት፣ ይህ ካልሆነ ከጋራ ንብረታቸዉ ለ1ኛ ተጠሪ የሚደርሰዉ ድርሻ፣ ይህም እዳዉን ለመክፈል በቂ ካልሆነ ከአመልካች ድርሻ እንዲከፈል ተወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ነጋዴ የነበሩ በመሆናቸዉ እና አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ዉስጥ እያሉ የተገባ እዳ በመሆኑ፣ በቼክ ክርክር የተሰጠዉ ዉሳኔ አለመሻሩን በመገንዘብ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ ስለሌለ፣ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም ተብሎ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ተቀባይነት የለዉም የምትልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር፣ የሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔ እና ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ በዚህ መሰረት እንደመረመርነዉ፡

1. የአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በ5/5/2004 ዓ.ም ጋብቻ ፈጽመዉ ባልና ሚስት ሆነው አብረዉ ሲኖሩ ቆይተዉ፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.53007 በ26/4/2008 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ መወሰኑን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸዉ ጋብቻ በዉሳኔ ከፈረሰ በኋላ የፍቺ ዉጤትን በተመለከተ የጋራ ንብረት እንዲያካፍላት የጠየቀች ሲሆን፤ በዚህ መሰረት በአዲስ አበባ አዲስ ከ/ክ/ከተማ ወረዳ 8 ዉስጥ የሚገኘዉ የሱቅ ቁጥር 380 የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ሀብታቸዉ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ሱቅ የሽያጭ ገንዘብ በፌደራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 213/1992 አንቀጽ 62 (1) መሰረት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ሀብታቸዉ እስከሆነ ድረስ፣ ንብረቱ በዚህ ሕግ አንቀጽ 90 መሰረት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል፡፡ ይህ መብት ሕግ ከዘረጋዉ አግባብ ዉጭ ሊሸራረፍ እና የአንደኛዉን ተጋቢ የጋራ ሀብት የመካፈል መብት የሚነፍግ ሁኔታ መኖር እንደሌለበት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

2. አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ የንብረት ክፍፍል ክርክር፣ የአሁን አመልካች የጋራ ንብረታችን እንድንካፈል በማለት ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን፤ 1ኛ ተጠሪ በበኩሉ የጋራ ንብረት መኖሩን በማመን ተከራክሮ፣ ባልና ሚስት በትዳር ዉስጥ በአንዱ በፍርድ ዕዳ መኖሩ ከተረጋገጠ የባልና ሚስት ንብረት ከመከፋፈሉ በፊት እዳዉ መከፈል አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.53007 በ23/5/2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ የጋራ እዳ ስላለብን ቅድሚያ መከፈል አለበት ከማለት ዉጭ እዳዉ ምን ያህል እንደሆነ መጠኑን ጠቅሰዉ ባለገንዘቦቹ እነማን እንደሆኑ በጽሁፍም ሆነ በቃል ተብራርቶና ግልጽ ተደርጎ በማስረጃ ተደግፎ የቀረበ ነገር የሌለ በመሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ የጋራ እዳ አለብን ስለሆነም እዳዉ በቅድሚያ እንዲከፈል ዉሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የትኛዉ እዳ እንደሆነ ስለማይታወቅ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ ዉሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ዉስጥ በነበረን ጊዜ የጋራ እዳ አለብን በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረበዉ ክርክር በፍ/ቤት ተጣርቶ በተሰጠዉ ፍርድ ተቀባይነቱ የቀረ በመሆኑ፣ አመልካች በተጠሪዉ በኩል ለሚመጣዉ እዳ ተጠያቂ የምትሆንበት አግባብ አይኖርም፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ዉስጥ በነበረን ጊዜ የጋራ እዳ አለብን በማለት ይህን ዉሳኔ የሚቃወም ከሆነ በሕግ ስልጣን ለተሰጣቸዉ በየደረጃዉ ላሉት ፍ/ቤቶች ቅሬታዉን አቅርቦ ዉሳኔዉን ማስለወጡን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በዚህ አግባብ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ቅሬታዉን አቅርቦ ያስለወጠዉ ነገር በሌለበት አሁን ለተነሳዉ ክርክር ከአመልካች ጋር በጋብቻ በነበርን ጊዜ የጋራ እዳ ስላለብን የጋራ ንብረታችን ከመከፋፈሉ በፊት እዳዉ መከፈል ይገባዋል በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት ሊኖረዉ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡

3. በሌላ በኩል የአሁን 2ኛ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246856 ላይ በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ከቼክ ጋር በተያያዘ ጥቅምት 24 ቀን 2009 ዓ.ም በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ባቀረበዉ ክስ 1ኛ ተጠሪ ህዳር 15 ቀን 2005 ዓ.ም የሚመነዘር ቁጥሩ BT 1873998 በሆነዉ ቼክ ብር 350,000 ጽፈዉ ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠ ስለሆን ባንክ ሲጠየቅ በቂ ገንዘብ የሌለዉ መሆኑ ስለተረጋገጠ ገንዘቡን ከነወለድና ወጪ ጋር እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብሎ ለመከላከል ስላልጠየቀ መልስ የማቅረብ መብቱን በማለፍ በ29/3/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ ብር 350,000 ቼኩ ለባንክ ለክፍያ ከቀረበበት ከ28/2/2009 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለ2ኛ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.246809 ላይ

በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ ከቼክ ጋር በተያያዘ ጥቅምት 22 ቀን 2009 ዓ.ም በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ባቀረበችዉ ክስ 1ኛ ተጠሪ መጋቢት 20 ቀን 2004 ዓ.ም የሚመነዘር ቁጥሩ BT 1575795 በሆነዉ ቼክ ብር 300,000 ጽፌዉ ለ3ኛ ተጠሪ የሰጠ ስለሆነ ባንክ ሲጠየቅ በቂ ገንዘብ የሌለዉ መሆኑ ስለተረጋገጠ ገንዘቡን ከነወለድና ወጪ ጋር እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀች ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም 1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብሎ ለመከላከል ስላልጠየቀ መልስ የማቅረብ መብቱን በማለፍ የካቲት 24 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ ብር 300,000 ቼኩ ለባንክ ለክፍያ ከቀረበበት ከ3/13/2008 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ እና ከወጪዎች ጋር ለ3ኛ ተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ እንደሚታወቀዉ ከንግድ ሕግ አንቀጽ 854 ድንጋጌ ማየት እንደሚቻለዉ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈልበት ሲሆን በዚህ ሕግ አንቀጽ 855 መሰረት ቼክ የወጣበት ቀን ከግምት ዉስጥ ሳይገባ በቼኩ ላይ የተጻፈዉ ቀን አንስቶ በሚከተሉት ስድስት ወራት ዉስጥ እንዲከፈልበት መቅረብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከፍ ሲል በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት ሲታይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ራሱ ቼኩን ፈርሞ ለተጠሪዎች የሰጠ ሲሆን ቼኩን መሰረት አድርጎ ለቀረበዉ ክስ ደግሞ በሕግ አግባብ ለመከላከል ማስፈቀጃ በማቅረብ የመከላከያ መልሱን አቅርቦ ሳይከላከልና ሳይከራከር ዉሳኔ የተሰጠ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንዲሁም አሁን በግራ ቀኙ መካከል በተያዘዉ ክርክር የአሁን 1ኛ ተጠሪ ቼኩን ለምን ዓላማ ፈርሞ ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች ሊሰጣቸዉ እንደቻለ በሕግና በማስረጃ አስደግፎ ያረጋገጠዉ ነገር እንደሌለ የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ይልቁንም ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች ፈርሞ በሰጣቸዉ ቼኮች ምክንያት የመጣዉ እዳ የግል እዳዉ መሆኑን በማረጋገጥ ዉሳኔ ማሳለፋቸዉን ነዉ፡፡

4. እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 34 (1) ሥር እንደተደነገገዉ ጋብቻ ፈጽመዉ ቤተሰብ የሚመሰርቱ ወንዶችና ሴቶች በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻዉ ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት እንዳላቸዉ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤትም ሆነ ማንኛዉም አካል ከተጋቢዎች ጋብቻ ጋር በተያያዘ ለሚወስዱት እርምጃም ሆነ ለሚሰጡት ዉሳኔ ይህን የሕገ መንግስታዊ መርህን ባከበረና ባስጠበቀ መልኩ መፈጸም የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ባልና ሚስት በትዳራቸዉ ዘመን የጋራ ሀብታቸዉን በተመለከተ እና ከፍቺ ዉጤት ጋር በተያያዘ የጋራ ንብረት ክፍፍል አስመልክቶ መወሰን የሚገባዉ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን የእኩልነት መርህ በጠበቀና ባከበረ አግባብ መሆን አለበት፡፡ በፌዴራል መንግስት ደረጃ ጋብቻ በንብረት በኩል የሚያስከትለዉ ዉጤት በፌደራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አግባብ የሚመራ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ በፌደራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70፣ 71፣

89 እና 93 ድንጋጌዎች ሥር ደግሞ የባልና ሚስት እዳን የሚመለከቱ ጉዳዮች ተመልክቷል፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች የባልና ሚስት የግል እዳ እና የጋራ እዳ በምን አግባብ መታየት እንደሚገባዉ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ 70 (1) መሰረት ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ፣ ከባለዕዳዉ ተጋቢ የግል ሀብት፣ የግል ሀብቱ ዕዳዉን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸዉ ይከፈላል በማለት ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 89 ሥር እንደተመለከተዉ ከባልና ሚስት አንደኛዉ ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸዉ ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ፣ ይኸዉ ዕዳ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በዚህ ሕግ አንቀጽ 93 ሥር ደግሞ ጋብቻዉ ከፈረሰ በኋላ ከባልና ሚስት ስለሚጠየቅ ዕዳ ያመለክታል፡፡

5. በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ የባልና ሚስት የንብረት ክርክር ወቅት 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የጋራ ዕዳ ስላለብን የጋራ ንብረታችን ከመካፈላችን በፊት ዕዳዉ ተቀንሶ እንዲከፈል በማለት የተከራከረ ቢሆንም ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ዕዳ አለብን ጥያቄ ተቀባይነት አጥቶ የተወሰነ ሲሆን፣ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቼክ ፈርሞ የሰጠ ቢሆንም ለምን ዓላማ እንደሰጣቸዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ቼክን መሰረት በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት የተጋቢዎቹ ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ ከፈረሰ በኋላና የቼኩ የመክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ ቀርቦ ተገቢዉን የመከላከያና መከራከሪያ ነጥቦች አንስቶ ሳይከራከር የግል ዕዳዉ መሆኑ ተረጋግጦ ዉሳኔ መሰጠቱን መገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪዎች የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ ቼኩን መሰረት በማድረግ ክስ ያቀረቡት በ1ኛ ተጠሪ ብቻ ላይ ሲሆን አመልካችን ጨምሮ ዉሳኔ የተሰጠበት ሁኔታ የለም፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በፍርድ የተረጋገጠበት ዕዳ ያለ ቢሆንም ከአመልካች ጋር በነበረዉ ክርክር የጋራ ዕዳ አለብን በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ተብሎ የተወሰነ ሲሆን፣ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አብረዉ ተከሰው በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸዉ ዕዳ መኖሩን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ ለምን ዓላማ ፈርሞ ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንደሰጠ በማይታወቅ ቼክ፣ ጋብቻቸዉ ከፈረሰ በኋላና የክፍያቸዉ ጊዜ ባለፈ ቼክ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የቀረበዉን ክስ ተከትሎ 1ኛ ተጠሪ በሕግ አግባብ ቀርቦ መከራከሪያና መከላከያ ሳያቀርብ የግል ዕዳዉ ነዉ ተብሎ ለተወሰነ ዕዳ፣ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበራቸዉ ክርክር የጋራ ዕዳ አለን በማለት 1ኛ ተጠሪ ያቀረበዉ ክርክር ዉድቅ ሆኖ ሳለ፣ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተከሳ እዳዉ የጋራቸዉ መሆኑን ዉሳኔ ባልተሰጠበት፣ ይህ ዕዳ የ1ኛ ተጠሪ እና የአመልካች ጋር የጋራ ዕዳቸዉ ስለሆነ አመልካች ከጋራ ሀብታቸዉ ድርሻዋን ሳትወስድ

በፊት ዕዳዉ መከፈል አለበት መባሉ አመልካች የጋራ ንብረት ላይ ያላትን መብት የሚያሳጣትና በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉን የእኩልነት መርህ የሚጋፋ ጉዳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የግል ዕዳዉ የሆነዉ ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች ከአመልካች ጋር የጋራ ዕዳቸዉ የሚሆንበት አግባብ ባለመኖሩ በፌደራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 70 (1) መሰረት ከጋራ ሀብታቸዉ ከአመልካች ድርሻ ላይ የሚከፈልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የተወሰነዉ የግል ዕዳዉ ሆኖ እያለ እና አመልካች ለዕዳዉ ተጠያቂ የምትሆንበት አግባብ ሳይኖር፣ ከጋራ ንብረታቸዉ ከሆነ የሱቅ ቁጥር 380 የሽያጭ ገንዘብ የአመልካች ግማሽ ድርሻ የሚከፈልበት አግባብ ሳይኖር፣ ለዕዳዉ ክፍያ የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብትና ከጋራ ሀብቱ የእሱ ድርሻ ያልበቃ እንደሆነ፣ ከአመልካች ድርሻ መከፈል አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ ከፍ ሲል የተጠቀሱት የሕግ ድንጋጌዎች የሚቃረን ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የግል ዕዳ ከጋራ ንብረት ከግማሽ ድርሻዋ ለመክፈል ኃላፊነት ሳይኖርባት፣ ከጋራ ንብረት ከሆነዉ የሱቅ ቁጥር 380 የሽያጭ ገንዘብ ግማሹን ተካፍላ የመዉሰድ መብት እያለት፣ አመልካች ግማሽ ድርሻዋን ከመዉሰዷ በፊት አስቀድሞ ዕዳዉ መቀነስ አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.53007 በ2/4/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.247544 በ20/5/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሻሽሏል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበዉ ያስወሰኑት ዕዳ የ1ኛ ተጠሪ የግል ዕዳ ሆኖ ሳለ ከአመልካች ጋር የጋራ ዕዳቸዉ ነዉ ተብሎ አመልካች ከሚደርሳት የንብረት ግማሽ ድርሻ ላይ አስቀድሞ ዕዳዉ መከፈል አለበት በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ የሰጡት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡
4. የአሁን አመልካች የ1ኛ ተጠሪን የግል ዕዳ ከጋራ ንብረት ግማሽ ድርሻዋ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም፣ ዕዳዉ አመልካች አይመለከታትም ብለናል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

6. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
7. ይህ ችሎት በ9/7/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.53007 የተጀመረዉ የአፈጻጸም ክርክር እንዲታገድ የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
8. የመ.ቁ.246856 እና 246809 ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ይመለሱ፡፡ የመ.ቁ.53007 ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኮ/ቀራንዮ ምድብ ችሎት ይመለስ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የ/ሰ/መ/ቁ 190295

ቀን 16/8/2013 ዓ.ም

**ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሃሳቤን እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ**

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የቀረበው፡- በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል ባለው የባልና ሚስት ንብረት ክርክር የአሁን ተጠሪ ለተበደረው ብድር የግል እዳው ነው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን ይህ የግል እዳው ከግል ንብረቱ ላይ እንዲከፈል ከግል ንብረቱ የማይሸፍን ከሆነ ከጋራ የባልና ሚስት ንብረታቸው ከሱ ከአሁን 1ኛ ተጠሪ /ከባል/ ድርሻ ይከፈል፣ ከሱ ድርሻ የማይሸፈን ከሆነ /ከሚስት/ የአሁን አመልካች ድርሻ ይከፈል ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ እዳ ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሀብት፣ የግል ሀብቱ እዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው እንዲከፈል ይደነግጋል፡፡ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ የጋራ ሀብታቸው ሲል የባልንም የሚስትንም ድርሻ ጨምሮ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንዲሁም ይሄው አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የግል እዳው የመጣው ለትዳር ጥቅማቸው ከሆነ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሃብት መከፈል እንዳለበት ጭምር ይገልፃል፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የባል የአሁን 1ኛ ተጠሪ የግል እዳ መሆኑ የተወሰነ ሲሆን በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔም የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ ድንጋጌ መሰረት መጀመሪያ ከሱ /ከባል/ የግል ሀብቱ እንዲከፈል፣ እዳው ከግል ሀብቱ የማይሸፈን ከሆነ ከባልና ሚስት የጋራ ሃብት ይከፈል ተብሉ

የተሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ እዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ ትርጉም አንፃር ስህተት የተፈፀመበት አይደለም፡፡

የባል የግል እዳ ከባልና ሚስት የጋራ ሀብት ከሚስት ድርሻ መከፈሉ ፍትሐዊ አይደለም የሚባል ከሆነ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ ድንጋጌ ለሁለቱም ወገን ለወንዱም ለሴቷም የሚሰራ ድንጋጌ እንጂ በሴቷ ላይ ብቻ የሚፈፅም አይደለም፡፡ የሚስት የግል እዳም ሲሆን እንዲሁ በተመሳሳይ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ በባል ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው ነው፡፡ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ የሴቶችን መብት የሚጎዳ ነው የሚባል ከሆነም የቤተሰብ ህጉ ይህ አንቀፅ መሻሻል ያለበት እንጂ ፍ/ቤቶች ህጉን የማሻሻል ስልጣኑ የላቸውም፡፡ በመሆኑም ህግ የማሻሻል ስልጣን የፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን ሲሆን የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ የሴቶችን የእኩል መብት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 34/1/ የሚፃረር ነው በሚል ምክንያት የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 70/1/ በመጣስ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ነው ብዬ አላምንም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ሊፀና የሚገባው ነው እላለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ማ/አ

# ግብር

የሰ/መ/ቁጥር 192732

ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- መሐመድ አብዱላሂ የማሽነሪ ኪራይ፡- ጠበቃ በፍቃዱ ስዩም ቀረቡ

ተጠሪ፡- በጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት፡- ነ/ፈጅ፡- አሸናፊ ማሞ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ አፈፃፀምን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የፍ/ባለመብት ዩኢቲ አልሳሜክስ ኢኮ አስፋልት ኢትዮጵያ 35 የፍርድ ባለእዳ የአሁን ተጠሪም ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤቶች ከተደረገው ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካች የስር የፍ/ባለእዳው ብር 1,778,477.29 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስምንት ሺ አራት መቶ ሰባ ሰባት ከ29/100) እንዲከፍለው ባቀረበው የአፈፃፀም ክስ መነሻነት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ንብረትነቱ የፍ/ባለእዳው የሆነ የአስፋልት ፓቼንግ ፕላንት ማሽን በሐራጅ ተሽጦ ለፍ/ባለመብቱ ክፍያ እንዲፈፀምለት ለፌደራል ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ዳይሬክቶሬቱም ሐራጁን እያከናወነ ባለበት የክፍሉ ፖሊስ ንብረቱ በጉምሩክ ፅ/ቤት ታግዷል በማለቱ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አለመቻሉን ገልፆ ሰኔ 12 ቀን 2011 ዓ.ም ፍ/ቤቱ መመሪያ እንዲሰጥበት ጠይቋል፡፡ የአፈፃፀም ችሎቱም ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ በሰጠው ምላሽ በፍ/ባለእዳው ስም ያልተከፈለ የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ብር 98,474,858.17 (ዘጠና ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ሀምሳ ስምንት ከ17/100) የሚፈለግበት በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ማገዱን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከፍ/ባለእዳው የሚፈልገው ገንዘብ የፍ/ባለእዳው ያለ ቀረጥና ታክስ ወደ ሀገር ውስጥ ላስገባቸው የተለያዩ እቃዎች(ማሽኖች) ለእያንዳንዱ ሊከፍል የሚገባውን ጠቅላላ ገንዘብ የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ባለእዳው ንብረት በሆነው የአስፋልት ፓንቺንግ ፕላንት ማሽን ላይ የፍርድ አፈጻፀም ዳይሬክቶሬቱ ሐራጁን እንዲቀጥል እና በዚህ ንብረት ላይ በተጠሪ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ ከሽያጭ ገንዘቡ ላይ ተቀናሽ ሆኖ ተራፊው ለአመልካች እንዲከፈል ብይን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህን ብይን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ የይግባኝ አቤቱታው ይዘት ባጭሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ/ባለእዳው የሚፈለገው ጠቅላላ የቀረጥ እና ታክስ እዳ ብር 98,474,858.17 መሆኑን እና ማሽኑን ቀድመን ለአጠቃላይ እዳው መያዣ የያዝን መሆኑን በመግለፅ ማስረጃዎችንም ጭምር በማቅረብ ተከራክረናል፡፡ ተጠሪ ባለው የቀደምትነት መብት መሰረት ማሽኑን እና ሌሎች ንብረቶችን ይዞ በግልፅ ጨረታ በመሸጥ ለእዳው ማካካሻነት ማዋል እንደሚችል በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 41/8 እና አንቀፅ 41/9 ላይ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በማሽኑ ላይ ብቻ የሚፈለግ እዳ ተቀናሽ ሁኖ ተራፊው ለአመልካች እንዲከፈል መወሰኑ የታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀፅ 41(8)(9)፣ 122(6)፣ የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀፅ 122(6) እና 148(2)ን ስለሚቃረን ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካች ለይግባኝ አቤቱታው በሰጠው መልስ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አቤቱታውን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ወይም 418 አግባብ አላቀረበም፡፡ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ 41(4)(ሀ) መሰረት በክርክር ታግዶ በአፈፃፀም ተይዞ ትዕዛዝ የወጣበትን ንብረት መያዝ ስለማይቻል እና ተጠሪው የፍ/ባለእዳው ያለበትን የግብር እዳ እንዲከፍል ጠይቆት እንቢተኛ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ማሽኑ ለጠቅላላ እዳ ክፍያው ሊውል ይገባል በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይግባኙን የተመለከተው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በሕግ አግባብ የተቋቋመ የመያዣ መብት በሕግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣ 2857(1) እና 3059 ተመላክቷል፡፡ ይህ መብት ያለው ሰው ከሌላው ሰው የቅድሚያ መብት አለው፡፡ ተጠሪ የግብር ሰብሳቢ ተቋም በመሆኑ በአዋጁ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 39(1) መሰረት የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በባለእዳው ማንኛውም ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት ያለው በመሆኑ በዚህ አግባብ እዳው ተከፍሎ ሳያልቅ የአስፋልት ፓንቺንግ ፕላንት ማሽኑ ላይ ብቻ የሚፈለገው እዳ ተቀናሽ ተደርጎ ቀሪው ለአመልካች እንዲመለስ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ችሎት ግንቦት 6 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔውን በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 73 መሰረት ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ለግንባታ ስራ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማሽነሮች ስራቸውን ከጨረሱ በኋላ ተመልሰው ከሀገር ውስጥ የሚወጡ በመሆኑ ለተጠሪ የቅድሚያ መብት አይፈጥሩም፡፡

ተጠሪ የስነ ስርዓት ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ አቤቱታ አቅርቦ አልተከራከረም፡፡ የፍ/ባለእዳውንም ጠይቆ እዳውን አልከፍልም ባላለበት ሁኔታ የከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሠጠው ውሳኔ መሻሩ አግባብ አይደለም፡፡ በተጠሪ እና በፍ/ባለእዳው መካከል በውል የተቋቋመ የመያዣ መብት መኖሩ ሳይረጋገጥ እንዲሁም ማሽኑ ልዩ ተንቀሳቃሽ እንጂ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስላልሆነ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857(1) እና 3059ን ጠቅሶ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ጨረታ የወጣበት ንብረት ለግንባታ ስራ ከቀረጥ ነፃ የገባ ሁኖ የቀረጥ እዳ አለብህ ክፈል ተብሎ ማስታወቂያ ባልወጣበት አመልካች በስር ፍ/ቤት የጠቅላላ እዳ ተጠያቂ የሆነበት አግባብነት ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 እና ከፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 41(8)(9) እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ጠ/ፍ/ቤት ንብረቱ በመያዣ ውል እንደተያዘ እና እንደማይንቀሳቀስ ንብረት በመውሰድ በፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣ 2857(1) እና 3059 አንፃር ጉዳዩን ያየበትን አግባብ ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 10 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ አመልካች የጉምሩክ አዋጅ 859/06 አንቀፅ 73ን መሰረት አድርጎ ያቀረበው አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ያልተነሳ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329 መሰረት ተቀባይነት የለውም፡፡ ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳ ተጠሪ ባለእዳው መክፈል የነበረበትን የቀረጥ እና ታክስ እዳ ብር 98,474,858.17 በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲት አረጋግጦ በቁጥር 4.3/አ52/1025 መጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ለድርጅቱ ወጪ ተደርጓል፡፡ ድርጅቱም በ15 ቀናት ውስጥ ባለመክፈሉ በአዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 122(6) እና 983/08 አንቀፅ 41(8) እና 41(9) መሰረት የድርጅቱ ንብረት ለቀረጥ እና ታክስ እዳው ዋስትና በመሆናቸው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው በማለት መወሰኑ አግባብ ነው፡፡ ተጠሪ በክርክሩ ተሳታፊ የሆነው ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ገብቶ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘው መሰረት ነው፡፡ የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857(1)ን የጠቀሰው ተጠሪ ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች የተሰጠውን የቀደምትነት መብት ለማጠናከር ሲሆን በፍ/ሕ/ቁ 1127 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ማሽን ልዩ ተንቀሳቃሽ በመሆኑ እንደማይንቀሳቀስ ንብረት የሚቆጠር በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 3059 መጠቀሱም ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው በፍርድ አፈፃጸም የተያዘው ንብረት ከቀረጥ ነፃ የገባ እና ተመልሶ ከሀገር ውስጥ የሚወጣ ስለሆነ ለተጠሪ የቅድሚያ መብት የሚሰጥ አይደለም፡፡ ተጠሪም የፍርድ ባለእዳው የግብር እዳውን እንዲከፍለው ሳይጠይቅ እና የስነ ስርዓት ሕጉን ተከትሎ አቤቱታውን ሳያቀርብ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለጉዳዩ ተገቢነት የሌላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ በፍርድ አፈጻጸም የተያዘውን ንብረት ለጠቅላላ የግብር እዳ ክፍያው ሊውል ይገባል በማለት የሠጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የሚከራከረው የፍርድ ባለእዳው ጠቅላላ የሚፈለግበትን የግብር እዳ ብር 98,474,858.17 ባለመክፈሉ በማንኛውም የፍርድ ባለእዳው ንብረት ላይ ተጠሪ የቀደምትነት መብት ስላለው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ተገቢ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በመጀመሪያ አመልካች የአፈፃፀም ትዕዛዝ የተሰጠበት ማሽን ከቀረጥ ነፃ የገባ እና ተመልሶ ከሀገር የሚወጣ ስለሆነ ለተጠሪ የቅድሚያ መብት አይፈጥርም በማለት የሚያቀርበውን መከራከሪያ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በአመልካች እና በፍ/ባለእዳው መካከል በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በነበረው የአፈፃፀም ክርክር መነሻነት ችሎቱ ንብረትነቱ የፍ/ባለእዳው የሆነ የአስፋልት ፓቺንግ ፕላንት ማሽን ተሸጦ ለአመልካች እንዲከፈል ለፌደራል ፍ/ቤቶች የአፈፃፀም ዳይሬክቶሬት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት ዳይሬክቶሬቱ ንብረቱን በሐራጅ ለመሸጥ እንቅስቃሴ ላይ ባለበት ተጠሪ አፈፃፀሙ እንዳይቀጥል አድርጓል በማለት ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ጠይቋል፡፡ በዚህ መነሻነት ችሎቱ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጥ እና በክርክሩ ተሳታፊ እንዲሆን አድርጎ ግራ ቀኙን ሲያከራክር አመልካች ማሽኑ ከቀረጥ ነፃ የገባ በመሆኑ ተጠሪው የቀደምትነት መብት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ በመሆኑም በስር ፍ/ቤቶች ያላነሳውን አዲስ መከራከሪያ በዚህ ችሎት ሊያነሳ የሚችልበት አግባብ ስለሌለ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 329 መሰረት ተቀባይት የለውም፡፡ በተጨማሪም ከቀረጥ ነጻ የገባ ንብረት ተመልሶ እስካልወጣ ድረስ ተገቢው የግብር እዳ ተከፍሎበት ሀገር ውስጥ የሚቀር በመሆኑ ለግብር እዳ በዋስትና የማይያዝበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በቀጣይ መታየት ያለበት ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 እና 418 መሰረት ተጠሪ አቤቱታ አቅርቦ አልተከራከረም በማለት አመልካች የሚያነሳው ክርክር ነው፡፡ በመሰረቱ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 በክርክሩ ተሳታፊ ያልሆነ አካል በሌሎች ተከራካሪዎች መካከል በተደረገ ክርክር መብቱን የሚነካ ፍርድ የተሰጠ እደሆነ በድንጋጌው የተጠቀሱ መመዘኛዎችን በማሟላት ፍርዱን በመቃወም ለማስለወጥ አቤቱታ የሚያቀርብበትን አግባብ የሚመለከት ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ዋናውን ፍርድ በመቃወም የሚያቀርበው መከራከሪያ በሌለበት በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታውን ማቅረብ ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡ በተጨማሪም የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 በፍርድ አፈጻፀም ምክንያት የተከበረ ወይም የተያዘ ንብረት ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚል አካል የሚያነሳው መከራከሪያ የሚስተናገድበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ድንጋጌ መብት ወይም ጥቅም አለኝ የሚለው

ተከራካሪ በክርክሩ ተሳታፊ የሚሆነው የግድ ግለሰቡ ወይም ተከራካሪው በቅድሚያ በራሱ አነሳሽነት በፍርድ ቤት በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ብቻ ስለመሆኑ በአስገዳጅነት የሚያስቀምጠው መመዘኛ የለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪው በጨረታ እንዲሸጥ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የወጣበት የፍ/ባለእዳው የሆነውን ንብረት በግብር እዳ ዋስትናነት ይዤዋለው በሚል እንዳይሸጥ በማድረጉ ፍ/ቤቱ ጥሪ አድርጎ በጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ እና ክርክር ሰምቶ ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በዚህ ረገድ የሚያነሳው መከራከሪያ የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ምላሽ ማግኘት ያለበት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2828፣2857 እና 3059 ድንጋጌን የመጥቀሱ አግባብነት ነው፡፡ በመሰረቱ ማንኛውም ፍ/ቤት በተከራካሪዎች የሚቀርቡ ክርክሮችን መርምሮ እና የክርክሩን ጉዳይ በመለየት አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነገር በአፈፃፀም በተያዘው የአስፋልት ፓቺንግ ፐላንት ማሽን ላይ ግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን የሆነው ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡ ተጠሪም በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት አለኝ በማለት የሚያነሳው ክርክር የግብር እዳን መነሻ ያደረገ ስለሆነ ለጉዳዩ በቀጥታ ተፈፃሚነት ያለው የጉምሩክ አዋጁ እና ሌሎች ግብርን የሚመለከቱ ልዩ ሕጎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን ከሚገዙ ልዩ ሕጎች በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ ተገቢነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በማመሳሰል እንዳይጠቀም የሚከለክለው ነገር የለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአስፋልት ፓንቺንግ ፐላንት ማሽኑ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ እና የቀደምትነት መብት የሚኖረውን ውጤት ለማሳየት የፍ/ሕ/ቁጥር 2828 እና 2857ን መጥቀሱ የሚያስነቅፍ ባይሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት የፍ/ሕ/ቁጥር 3059 ድንጋጌን በውሳኔው ላይ መጠቀሱ አግባብነት የለውም፡፡

በመጨረሻ አከራካሪ በሆነው የአስፋልት ፓቺንግ ፐላንት ማሽን ላይ ተጠሪ የቀደምትነት መብት አለው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የግንባታ ስራን ለማከናወን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ተደርገው በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ስራው በተጠናቀቀ የ3 ወር ጊዜ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ተመልሰው መውጣት ያለባቸው ስለመሆኑ እና ከሀገር ውስጥ በሕግ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተመልሰው ካልወጡ ወይም በሌላ መንገድ ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ አስመጪው አካል ተገቢውን ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 አንቀፅ 73(3) እና 130 መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍርድ ባለእዳው የተጠቀሰውን ማሽን ለግንባታ ስራ ከቀረጥ ነፃ ያስገባው እና ከሀገር ውስጥ ተመልሶ ያልወጣ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ በተጨማሪም ታክስ በማንኛውም ሁኔታ ያልተከፈለ ወይም ሊከፈል ከሚገባው በታች የተከፈለ መሆኑ በድህረ ኦዲት ምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለስልጣኑ ዲክላራሲዮን አቅራቢውን ሊያስከፍለው የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 122(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ በድንጋጌው ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረትም ባለእዳው የቀረጥ እና ታክስ እዳውን ያልከፈለ እንደሆነ ባለስልጣኑ በገቢ ግብር አዋጁ የተመለከተውን ንብረት ይዞ የማስፈፀም

ስርዓት ተፈፃሚ የሚያደርግ ስለመሆኑ ተመላክቷል፡፡ ከዚህም ሌላ የታክስ አስተደዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀፅ 39(1 እና 2) በሚመለከተው አካል የተመዘገበ ማንኛውም ቀዳሚ ዋስትና የተሰጠበት መብት (ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው የገንዘብ ጥያቄዎች እና የተቀጣሪዎች የደመወዝ ቅድሚያ መብት) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ ከፋዩ መክፈል የሚገባው የመክፈያ ጊዜው የደረሰ ታክስ በሙሉ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀደምትነት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ ተመላክቷል፡፡ ይህም ማንኛውም አካል ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ባስገባቸው እቃዎች በአንዱም ሆነ በሌሎቹ ወይም በሌላ ምክንያት የሚፈለግበት መክፈያ ጊዜው የደረሰ የታክስ እዳ መኖሩን ባለስልጣኑ ያረጋገጠ እንደሆነ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ በታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች የፍርድ ባለእዳው በጠቅላላው ብር 98,474,858.17 ያልተከፈለ (የበሰለ) የግብር እዳ ያለበት ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካችም የገንዘብ መጠኑን ወይም የመክፈያ ጊዜው የደረሰ አለመሆኑን አስመልክቶ በመቃወም ክርክር ቢያቀርብም ክርክሩን የሚደግፍ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በታክስ አስተዳደደር አዋጁ አንቀፅ 41(4) (ለ) መሰረት በማናቸውም የፍርድ ሂደት ዕገዳ በተደረገበት ወይም የአፈፃፀም ትዕዛዝ በተሰጠበት ንብረትን ባለስልጣኑ የመያዝ ስልጣን የሌለው መሆኑ የተመላከተ ቢሆንም ድንጋጌው ንብረቱን የመያዝ ሁኔታን ብቻ የሚከለክል እንጂ ባለስልጣኑ የግብር እዳውን ለማስከፈል የሚኖረውን የቀደምትነት መብት የሚያሳጣ አይደለም፡፡

በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፍርድ ባለእዳው ላለበት ጠቅላላ የግብር እዳ ተጠሪ በባለእዳው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 183044 መጋቢት 29 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁጥር 230663 ነሐሴ 3 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠውን ብይን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.187882

ሚያዚያ 25 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. መዓዛ አሸናፊ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ፈይሳ ወርቁ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- ቲ.ኤም.ዜድ.ቢ. ኃ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ይህ በዲክላራሲዮን ከተገለጸ ዕቃ ዉጭ ማስመጣትና በዚህ ላይ የሚወሰን ቀረጥ የሚመለከት ክርክር የተጠሪ ጽ/ቤት የወሰነዉን የመዉረስ ዉሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ክርክሩ የተጀመረ ሲሆን አመልካች ይግባኝ እና ተጠሪ ደግሞ መልስ ሰጭ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162466 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የተጠሪ ጽ/ቤት አመልካች ከዉጭ ያስመጣዉ ጥሬ ዕቃ እንዲወረስ የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ፣ ለፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረበ ሲሆን፤ የይግባኙ አጭር ይዘት፡ ይግባኝ ባይ በጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪ የተሰማረ ሲሆን በከፊል ያለቁ (semi-finished) ጥሬ እቃዎችን ከውጪ በማስመጣት በግብአትነት የሚጠቀም በመሆኑ በመልስ ሰጭ በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር.C.23969/15 ዲክሌር አድርገን ለልጆች ልብስ መስሪያ ጥሬ እቃ (track suit) የሚሆን በከፊል ያለቀለት (finished material recycled closed polyster fabric) ያስመጣንና መልስ ሰጭም ይህን ስያሜ መስጠት ሲገባው፣ ካስመጣነው ጥሬ እቃ ጋር በማይመሳሰል 100 % polyster knitted fabric ነው ሲል ስያሜ ሰጥቶት ያልጠበቅነውን ዋጋ በመስጠቱ ለመልስ ሰጪ በየደረጃው ቅሬታችንን ብናቀርብም ውድቅ በመደረጉ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልክተን ክርክር ላይ ባለንበት ወቅት የእቃውን መወረስ የሰማን በመሆኑ ህጉ ለዚህ

ዘርፍ የሰጠውን ማበረታቻን ከግምት ዉስጥ ያላስገባ ስለሆነ የመልስ ሰጭ የዉርስ ዉሳኔ ዉድቅ ሆኖ ለመንግስት ቀረጥና ታክስ ተፈላጊዉን ዋስትና አስይዘን ያስመጠናዉን ጥሬ ዕቃ ወደ ምርት እንድንለዉጥ እንዲወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህ ይግባኝ ላይ መልስ ሰጭ ባቀረበዉ መልስ ይግባኝ ባይ በዲክላራሲዮን ቁጥር C.23969/15 ለማስመጣት ዲክሌር ያደረገው blanket material (semi-finished) ሲሆን፣ ግን ያስገባዉ በባለሙያ በተደረገዉ አካላዊ ፍተሻ እንደተረጋገጠዉ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth ሆኖ በመገኘቱ በአስመጪዉ የቀረበው የግብይት ዋጋ ተቀባይነት እንደማያገኝና የእቃዉ ታሪፍ ምደባም የሚቀየር ሲሆን ፣ይግባኝ ባይ ያስገባዉ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ 2.8 USD/Kg በመሆኑ፣ በዲክላራሲዮኑ ላይ ከተጠቀሰው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ 1.8 USD/Kg ስለሆነ፣ ከተጠየቀዉ ከ50% በላይ የዋጋ ልዩነት ስላለው መወረሱ ህጋዊ እንደሆነ በአዋጅ ቁ.859/2006 አንቀጽ 8፣ 13፣ 102 እና መመሪያ ቁ.111/2008 አንቀጽ 5 (2) (ሀ) ላይ ተደንግጓል፤ ይግባኝ ባይ ያስገባው እቃ በዲክላራሲዮን ቁጥር 32078/14 ከዚህ ቀደም ከገባዉ እቃ ጋር ተመሳሳይና ከአንድ ላኪ ድርጅት ከመጡና ከጉምሩክ ዳታ ቤዝ በተገኘ መረጃ ነው፤ በዚህ ምክንያት ይግባኝ ባይ ያቀረበውን ስያሜ ውድቅ በማድረግ ጥሬ ዕቃዉን መውረሱ በህግ አግባብ ስለሆነ የጽ/ቤቱ ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ ከዉጭ ያስመጠዉ ጥሬ እቃ ላይ ከኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የቀረበዉ የባለሙያ አስተያየት ዕቃዉ ብርድ ልብሶችን ለማምረት የሚያገለግል መሆኑን አረጋግጠናል የሚል ሲሆን፤ ይግባኝ ባይ መንግስት የሀገር ውስጥ አምራችን ማበረታቻ እንዲያገኙ ለማድረግ እና ጉምሩክ ታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚ ስለሆኑ ይህን እድል ለመጠቀምና በዲክላራሲዮኑ ላይ ያለው ትክክል አለመሆኑን በመረዳት semi-finished recycled polyster fabric for truck suit የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫዉ መክፈል ያለበት ሲሆን መልስ ሰጭ በግብአቱ ላይ ያስተላለፈው የመውረስ ውሳኔ ከህግ ውጪ ነው በማለት በመሻር ወስኗል፡፡

የሥር መልስ ሰጪ ጽ/ቤት (ይግባኝ ባይ) በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ይግባኝ ባይ (መልስ ሰጭ ማህበር) ወደ ሀገር ውስጥ የገባዉ ጥሬ ዕቃ ላይ ለውጥ መደረጉ በግልጽ ተረጋግጦ ሲሆን በዚህ ለውጥ የዋጋ ልዩነት ከ50% በላይ ያሳያ መሆኑ እየታወቀና ይህም ባልተስተባበለበት ሁኔታ የመንግስትን ማበረታቻ እንዲያገኙ የሚል ምክንያት በመጥቀስ ይግባኝ ባይ እቃዉ እንዲወረስ የተላለፈውን ውሳኔ መሻሩ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (1) (ለ) እና መመሪያ ቁጥር

112/2006 አንቀጽ 15 (2) (ለ) ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው በማለት የጉባኤዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

የሥር መልስ ሰጭ ማህበር በዚህ ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ20/4/2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች ወደ ሀገር ዉስጥ ያገባዉ ዕቃ ስያሜ ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉን ጭብጥ በመያዝ በማጣራት ተጠሪ semi-finished recycled polyster fabric for truck suit በመመደብ የሰጠዉ የዉርስ ዉሳኔ ተገቢ አለመሆኑን በመወሰን በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በግብር ይግባኝ ጉባኤ በሚደረጉ ክርክሮች ላይ በይግባኝ ለመዳኘት የተሰጣቸዉ የዳኝነት ስልጣን ከሕግ ጭብጥ ጋር የተያያዘ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155 (2) (4) እና የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 112 (1) ላይ በግልጽ ተመልክቶ እያለ ፍ/ቤቶች ከዚህ ዉጭ የማስረጃ ምዘና ስልጣን ሳይኖራቸዉ፣ የጥሬ ዕቃዉ ስያሜና ዋጋዉን ተጠሪ ሳያስረዳ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የጉባኤዉ ስያሜና ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣ያከራከረው የአሁን አመልካች ወደ አገር ውስጥ ያስገባው እቃ ለመወረስ እንደምክንያት የቀረበው ለማስመጣት የተጠየቀውና ያስመጣው ዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ ሆኗል በሚል በመሆኑ አስመጣለው ያለው እቃና በኢንስቲትዩቱ የተረጋገጠው እቃ ዋጋ ከ50% በላይ መሆኑ ስለመረጋገጡ ለማጣራት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዟል፡፡

የአሁን ተጠሪ በ25/6/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካች በዲክላራሲዮን ቁጥር C.23969/15 ለማስገባት መግለጫ blanket material (semi-finished) ሆኖ ሳለ የተጠሪ መ/ቤት ባደረገዉ አካላዊ ፍተሻ ዕቃዉ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በዚህ የአገላለጽ ልዩነት የቀረጥና ታክስ ልዩነት ከ50% በላይ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ይህን ያስተባበለበት ሁኔታ የለም፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንስትቲዩት የላከዉ መግለጫ ዕቃዉ ባህር ከሚገልጽ በስተቀር የዕቃዉን ምንነት ያስቀመጠ ነገር የለም፣ ይህ መግለጫ የተጠሪ መ/ቤት በፍተሻ አገኘሁ የሚለዉን ዕቃ ይባልጥ የሚገልጽ አስተያየት ነዉ፡፡ ተጠሪ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ ለማስገባት ከገለጸዉ ዕቃ ልዩነት ስያሜ ምክንያት የዕቃዉ ዋጋ ልዩነት ከ50% በላይ መሆኑ በማስረጃ ነጥሮ ተረጋግጦ የዉርስ ዉሳኔ የተላለፈ ስለሆነ በዚህ ረገድ

የቀረበ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ከተባለዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ወደ አገር ለማስገባት በዲክላራሲዮን ቁጥር C.23969/15 መግለጫ በሰጠዉ እና በተጨባጭ ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ መካከል የስያሜ ልዩነት እንዳለ ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሥር በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና የሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነዉ፡፡ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም ሆነ በሥር ፍ/ቤቶች እንደተመለከተዉ አመልካች ወደ አገር ለማስገባት መግለጫ የሰጠዉ ጥሬ ዕቃ blanket material (semi-finished) ሆኖ ሳለ፣ በተጨባጭ ወደ አገር ያስመጣዉ ግን ከዚህ ስያሜ ዉጭ መሆኑን እና የተጠሪ መ/ቤት በባለሙያዎቹ አድርጌአለሁ ባለዉ አካላዊ ፍተሻ ዕቃዉ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth መሆኑን በመግለጽ፣ የዚህን ጥሬ ዕቃ ስያሜ መነሻ በማድረግ መከፈል ይገባል ያለዉ የቀረጥና ታክስ ዋጋ መተመኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ የሥር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በበኩሉ ወደ አገር የገባዉ ጥሬ ዕቃ እና ለማስገባት የተሰጠዉ መግለጫ ላይ የተጠቀሰዉ ጥሬ ዕቃ ልዩነት ያለዉ መሆኑን በመቀበል፣ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስለጉዳዩ ሙያዊ አስተያየት እንዲሰጥ በጠየቀዉ መሰረት ግንቦት 3 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አስተያየቱን መስጠቱን ከጉባኤዉ የዉሳኔ ግልባጭ የምንረዳዉ ነዉ፡፡ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ ባህርና የዕቃዉ አገልግሎት ከሚያብራራ በስተቀር የዕቃዉን ስያሜ እንደማይገልጽ እና የተጻፈዉን ደብዳቤ ይዘት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዉሳኔዉ በዝርዝር ማስቀመጡን ማየት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በዲክላራሲዮን ላይ ከገለጸዉ ጥሬ ዕቃ ዉጭ ወደ አገር ያስመጣ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ኢንስቲትዩት የጻፈዉ ሙያዊ አስተያየት የዕቃዉን ባህርና አገልግሎት የሚገልጽ እንጂ ስያሜዉን የማያመለክት በሆነበት፣ የሥር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የዕቃዉ ስያሜ semi-finished recycled polyster fabric for truck suit ተብሎ እንደተጻፈ በመዉሰድ፣ በዚህ አግባብ አመልካች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫዉ በመክፈል የተጠሪ መ/ቤት በግብዓቱ ላይ ያስተላለፈው የመውረስ ዉሳኔ መሻሩን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ጉዳይ በይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ ጉባኤዉ ለዕቃዉ የሰጠዉ ስያሜ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ዉሳውኔን መሻራቸዉን ማየት ይቻላል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በዉሳኔዉ እንዳመለከተዉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለጥሬ ዕቃዉ ስያሜ ለመስጠት መነሻ ያደረገዉ ኢንስቲትዩቱ የጻፈዉ ደብዳቤ ቢሆንም የደብዳቤዉ ይዘት ሲታይ

ጉባኤዉ ለዉሳኔዉ መሰረት ያደረገዉን ስያሜ እንዳማያመለከትና የተላከዉ ደብዳቤ ይዘት በዝርዝር በማስቀመጥ፤ የተጠሪ መ/ቤት ለዕቃዉ የሰጠዉ ስያሜ ተገቢ መሆኑን በማረጋገጥ መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ ከኢንስቲትዩቱ ግንቦት 3 ቀን 2008 ዓ.ም ተጽፎ የተላከዉን ደብዳቤ ይዘት ያላስቀመጠ በመሆኑ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በሰጠዉ ዉሳኔ የደብዳቤዉን ይዘት በግልጽ ያመለከተ በመሆኑ፣ ፍ/ቤቱ በዉሳኔዉ የገለጸዉ የደብዳቤዉ ይዘት ትክክለኛ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተላከዉ ደብዳቤ የዕቃዉን ስያሜ በማይገልጽበት ሁኔታና የደብዳቤዉ ይዘት የማይለዉን ትርጉም በመስጠት፣ ማስረጃዉ የማይለዉን መሰረት በማድረግ፣ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉን ዕቃ ስያሜ በማስጠት፣ ይህን መሰረት አድርጎ የተጠሪ መ/ቤት ያስተላለፈዉ የዉርስ ዉሳኔ በመሻር አመልካች የዕቃዉን ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫዉ በመክፈል እንዲወስደዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት ያደረገ ዉሳኔ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ ፍ/ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል የቀረበዉን ማስረጃ ይዘቱን በትክክል ካስቀመጠ በኋላ ማስረጃዉን መዝኖ ተገቢ ነዉ ያለዉ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማስረጃ ምዘና መርህ የሚደግፌዉ አግባብ ቢሆንም ማስረጃዉ የማይለዉን እንደሚል በመግለጽና ይዘቱን በመለወጥና የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ይህን መሰረት በማድረግ ዉሳኔ መስጠት የማስረጃ ምዘና መርህን የሚቃረን ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የሚሰጥም ዉሳኔ የቀረበዉን ማስረጃ መሰረት ያደረገ ወይም በማስረጃ የተደገፈ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠዉ የጥሬ ዕቃዉን ስያሜ የሚደግፍ ሌላ ማስረጃ ማቅረቡን የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሥር ፍ/ቤቶች የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ በተመለከተ የሰጠዉ ዉሳኔ በማስረጃዉ የተደገፌ አይደለም በማለት ዉድቅ በማድረግ፣ የተጠሪ መ/ቤት የሰጠዉን ስያሜ ማለትም knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth ነዉ በማለት ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሰጡት ዉሳኔ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155 (3) እና የፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 57 (4) ሥር ከግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቀረበዉን ዉሳኔ የህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ዳኝነት አይቶ እንዲወስኑ ከተሰጣቸዉ ስልጣን ዉጭ ወጥቶ ፍሬ ነገር አይተዋል የሚያስብል አይሆንም፡፡ ስለሆነም አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth ነዉ ብለዉ የሥር ፍ/ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ ይህ ችሎት ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን በሕግ የተሰጠዉ ስልጣን ስለሌለዉ ይህን የዕቃዉን ስያሜዉ የሚቀበለዉ ይሆናል፡ በዚህ ረገድ የአሁን አመልካች የሥር ፍ/ቤቶች ከስልጣናቸዉ ዉጭ ወጥተዉ ፍሬ ነገር አጣርቶ ዉሳኔ አሳልፏል በማለት ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት የአሁን ተጠሪ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉን ጥሬ ዕቃ ለመዉረስ የሚያስችለዉ ሁኔታ ተሟልቷል ወይስ አልተሟላም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ ከ50% በላይ መሆኑን ተጠሪ የማስረዳት ግዴታዉን ባልተወጣበት፣ የዋጋዉ ልዩነቱ ተጣርቶ ዕቃዉን የዉርስ ዉሳኔ ለማስተላለፍ የሚያበቃ መሆኑ ሳይረጋገጥ የተሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም የሚል ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ ጠቅላላ ዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ ማለትም 55.5% መሆኑን በተጠሪ መ/ቤት በተሰጡት ዉሳኔዎች ጋር ተያይዞ በተሰሩት ቀመር አስረድተናል፣ ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (1) (ለ) እና በመመሪያ ቁጥር 112/2008 አንቀጽ 15 (2) መሰረት የዉርስ ዉሳኔ መሰጠቱ ተገቢ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የሥር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና ፍ/ቤቶች አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ ከ50% በላይ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ነጥብ ያዩበት አግባብ መታየት አለበት፡፡ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዉ ተጠሪ የዉርስ ዉሳኔ ያስተላለፈበትን የዕቃዉን ስያሜ ስለቀየረዉ፣ በዚህ ምክንያት የዋጋዉ ልዩነቱ ከ50% በላይ አለመሆኑን ስለተገነዘበ፣ ተጠሪ የዉርስ ዉሳኔ በሰጠበት የዕቃዉ ስያሜ መሰረት የዋጋዉ ልዩነት ከ50% በላይ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ፍሬ ነገር ለማጣራት የሄደበት መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ለዕቃዉ ተጠሪ የሰጠዉን ስያሜ በመቀበል በዚህ ምክንያት የተፈጠረዉ ለዉጥ የዋጋ ልዩነት ከ50% በላይ ያሳዩ መሆኑ የሚታወቅና ያልተስተባበለ ነዉ ብሎ ዉሳኔ ከመስጠት በስተቀር የሥር ጉባኤዉ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት የዋጋዉን ልዩነት በማስረጃ አንጥሮ ስለማዉጣቱ የገለጸዉ ነገር የለም፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የደረሰበት ድምዳሜ ሲታይ በዕቃዉ ስያሜ ልዩነት ምክንያት የተፈጠረዉ የዋጋ ልዩነት ከ50% በላይ እንደሆነ በጉባኤዉ እና በዚህ ፍ/ቤት ዘንድ ከተደረገዉ ክርክር የምንገነዘበዉ ነዉ በማለት ማለፉን እንጂ የዋጋዉን ልዩነት በተመለከተ በምን አግባብ እንደተጣራ የሚገልጽ ሆኖ አልተገኘም፡፡

እንደሚታወቀዉ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (1) (ለ) መሰረት ተደብቆ የተገኘዉ ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ ከ50% በላይ ሆኖ ሲገኝ ተደብቀዉ የተገኙት ዕቃዎች ዉርስ ሆነዉ ለመንግስት ገቢ እንደሚደረጉ ይደነገጋል፡፡ እንግዲህ አመልካች ያስገባዉ ዕቃ ዋጋ በዲክላራሲዮን ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ አንጻር ሲታይ የዋጋዉ ልዩነት ከ50% በላይ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 147 (1) (ለ) መሰረት ዕቃዉን የሚያስወርስ ሲሆን፣ የዋጋዉ ልዩነቱ ግን ከዚህ በታች ከሆነ ዕቃዉ ላይ የዉርስ ዉሳኔ ለማሳለፍ የሚያበቃ አይሆንም ማለት ነዉ፡፡ ስለዚህ አመልካች ባስገባዉ ዕቃ እና በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ መካከል ያለዉ የዋጋ ልዩነት ከ50% በላይ መሆን አለመሆኑ ፍሬ ነገር የማጣራት

ስልጣን ባለዉ የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተጣርቶ መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155 (1) ማየት ይቻላል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 155 (3) እና በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 57 (4) መሰረት ከግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የቀረበላቸዉን ጉዳይ የሕግ ስህተት ያለበት ከሆነ ብቻ ስለሚያዩ ፍሬ ነገር በማስረጃ አጣርቶ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ስልጣን የላቸዉም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ መካከል የዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ መሆን አለመሆኑን በማጣራት፣ አመልካች ያስገባዉን ዕቃ ለዉርስ የሚያበቃዉ ሁኔታ መሟላት አለመሟላቱ ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን አለዉ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በዚህ አግባብ በማጣራት አመልካች ያስመጣዉ ዕቃ ላይ የዉርስ ዉሳኔ ለማስተላለፍ የሚያበቃ ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሚለዉን ነጥብ በማጣራት ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ይህን ሳያደርግ የሰጠዉን ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤቶች ደግሞ በጉባኤዉ ዘንድ በግልጽ ተጣርቶ ዉሳኔ እንደተሰጠበት በማመልከት መወሰናቸዉ የህግ ድጋፍ የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል ግብር ይግባኝ ጉባኤ አመልካች ያስመጣዉን ጥሬ ዕቃ ለማስወረስ የሚያበቃ ነገር ከዋጋ ልዩነት አንጻር መኖር አለመኖሩን በአግባቡ ሳያጣራ የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ ጉባኤዉ ሳያጣራ የሰጠዉን ዉሳኔ በማረም አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.205263 ሐምሌ 13 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.162466 መስከረም 22 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ መስከረም 30 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ጥሬ ዕቃ ስያሜ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth ነዉ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል አልተነካም ጸንቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ያስገባዉ ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ ልዩነት ምን ያህል እንደሆነ በጉባኤዉ ዘንድ መጣራቱን ሳያረጋግጡ

የዋጋዉ ልዩነት ከ50% በላይ ነዉ በማለት በዕቃዉ ላይ ዉርስ ዉሳኔ በተጠሪ መሰጠቱ ተገቢ ነዉ በማለት የሰጡት የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. የፌዴራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ መሰረት አመልካች ወደ አገር ያስገባዉ ዕቃ knitted/crouched fabric for the manufacturing of baby cloth መሆኑን በመገንዘብ፤ ይህ የገባዉ ዕቃ በዲክላራሲዮን ላይ ከተመዘገበዉ አጠቃላይ ዋጋ ልዩነቱ ከ50% በላይ ነዉ ወይስ አይደለም? የዋጋ ልዩነት አለ ከተባለ ዕቃዉ ዉርስ ሆኖ ለመንግስት ገቢ የሚያስደርግ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
5. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሠ/መ/ቁጥር 194135

የካቲት 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ዳይናሚክ ሎጅስቲክ አቅርቦት የድጋፍ አገልግሎት

ተጠሪ፡- አቶ ፈሬሳ ኢዶ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከሽያጭ ዋጋ ጋር ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) በግልጽ ተለይቶ መገለጽ አለመገለጹ የሚያስከትለዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 03-853387 ኢት የሆነ አውቶብስ መኪና በቀን 15/11/2009 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 310,000.00 ለተጠሪ ሸጦለት ተጠሪ ብር 250,000.00 በመክፈል መኪናውንና ሊብሬውን ተረክበዋል፡፡ ቀሪውን ብር 60,000.00 እና የተ.እ.ታ ብር 45,000.00 በድምሩ ብር 106,500.00 የሚከፍሉት እስከ ቀን 25/11/2009 ዓ/ም ድረስ ተጠሪ ያላገባ የሚል ማስረጃ አሟልተዉ አቅርበዉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት ቀርበው የመኪናው ስመ ሀብት በተጠሪ ስም ሲዞር ነው በሚል ስምምነት የተደረገ ቢሆንም ተጠሪ የበኩላቸዉን ግዴታ አልተወጡም፡፡ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም እንደውሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የከፈሉትን ቃብድ ለቀውና ተ.እ.ታ ከፍለው መኪናውንና ሊብሬውን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ በውላችን መሰረት የመኪናውን ባለቤትነት እንዲያዛውርልኝ፤ ከግብር ነፃ ነው የሚል ማስረጃ እንዲያቀርብ ወይም ውክልና ሰጥቶኝ ቀሪውን ክፍያ እንድሰጠው በተደጋጋሚ ብጠይቅም ፍቃደኛ አልሆነም ፡፡ በውሉ ላይ ተጠሪ ተ.እ.ታ ለመክፈል አልተስማማሁም፡፡ ብር 250,000.00 ስከፍል ተ.እ.ታ አልጠየቀኝም፡፡ የውሉ አብዛኛው ክፍል የተፈፀመ ስለሆነና ዉሉን የሚያስፈርስ ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንዲሁም ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ አመልካች በውሉ መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ በውሉ መሰረት ከግብር እዳ ነፃ ማስረጃ እና ያላገባ የሚል ማስረጃ ይዞ በመቅረብ የሸጠዉን መኪና በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ስመ ሀብቱን በተጠሪ ስም እንዲያዛወር ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ በሰጠዉ መልስ ከውሉ ቀነ ገደብ በፊት መንገድና ትራንስፖርት ቀርበን የውል ፎርም ሞልተን እኔ ፈርሜ ተጠሪ በፎርሙ ላይ ሳይፈርሙ ስለቀረ ውሉ ሳይፈፀም ቀርቷል፡፡ አመልካች እንደ ውሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ ጭምር ሰጥቶ ተጠሪ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ክሳቸው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 73223 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶ በቀን 25/08/2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኝ በመካከላቸው በቀን 15/11/2009 ዓ/ም የመኪና ሽያጭ ውል ማድረጋቸው አልተካካዱም፡፡ በአመልካች ክስ ላይ እንደተመለከተው በውሉ ላይ ተጠሪ ተ.እ.ታ.ብር 46,500.00 ለአመልካች ለመክፈል አልተስማሙም፡፡ በውሉ ላይ ተጠሪ የተስማሙት ቀሪ ብር 60,000.00 የመኪናው ስመ ሀብት ሲዞርላቸው ለመክፈል ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ተ.እ.ታ ጨምሮ ብር 106,500.00 ሊከፍሉ ይገባል በማለት የገለፀው መከራከሪያ ከውሉ ውጪ ነው፡፡ ስለሆነም በውሉ ያልተመለከተዉን ተ.እ.ታ ተጠሪ እንዲከፍሉ በመጠየቁ ምክንያት ውሉ ሊፈርስ አይገባም፡፡ እንዲሁም በወሉ ላይ አመልካች ተሸከርካሪው ከእዳና እገዳ ነፃ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ እንዳለበት ስላልተመለከተና የመኪናውም ስመ ሀብት ወደ ተጠሪ ያልተዛወረው በዚህ ምክንያት መሆኑ ስላልተረጋገጠ አመልካች ከግብር እዳ ነፃ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የተጠየቀው ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም በሽያጭ ውሉ መሰረት አመልካች ያላገባ ማስረጃ አቅርቦ ተጠሪም ቀሪውን ብር 60,000.00 ከፍለው ግራ ቀኝ ውሉን ያስመዝግቡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 240838 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡ አመልካች በቀን 16/11/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በቀን 15/12/2009 ዓ/ም በተደረገ የመኪና ሽያጭ ውል ላይ ዋጋዉ ብር 310,000.00 ተብሎ የተጠቀሰዉ የመኪና መሸጫ ዋጋ (Selling value) ነዉ፡፡ተጠሪ ተ.እ.ታ የመከፈል ግዴታ እንዳለባቸዉ ቀድሞ ተነግሯቸዋል፤እንዲሁም ተጠሪ የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ስለሆኑና ባላቸዉ ስራ የንግድ ልምድ ተ.እ.ታ እንደሚከፍሉ ያዉቃሉ፡፡እንዲሁም ተ.እ.ታ በባህሪው ሸማች ላይ የተጣለ ኃላፊነት በመሆኑ ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ግብይት ሲፈፅም ይህንኑ ታሳቢ ማድረግና

ተ.እ.ታ የመክፈል ሕጋዊ ግዴታቸዉን ሊወጡ ይገባል፡፡ ዋናው ውል የሚደረገው በመንገድና ትራንስፖርት ባለሥልጣን ፊት በመሆኑ የመኪና ሽያጭ ውል ሲደረግ በመንደር ውል የመኪናው ዋጋ ብቻ ተጠቅሶ ቅድሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡በዚህ መሰረት የሽጭ ዋጋው ታይቶ የተ.እ.ታ ክፍያ መጠኑ ለተጠሪ ሲገለፅ በመንገድ ትራንስፖርት ባለሙያ የተዘጋጀውን ውል ግዴታዬ አይደለም ብለዉ ትተዉ መሄዳቸዉ በስር ፍርድ ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ተ.እ.ታ ሊከፍሉ አይገባም በማለት መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በተደረገው የመኪና ሽያጭ ዉል ላይ ተ.እ.ታ የመክፈል ኃላፊነት የሻጭ ነው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንጻር እንዲመረመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 18/03/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-

አመልካች በውል ስምምነት ላይ የሌለን የተ.እ.ታ ክፍያ በተጨማሪነት ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ያቀረበዉ ጥያቄ ከስምምነታችን ውጪ አለአግባብ ለመበልጸግ ነዉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 23 መሰረት ተ.እ.ታ ተመዝጋቢ የሆነ ነጋዴ ሽያጭ ፈፅሞ ገንዘብ ከተቀበለ ለተቀበለው ገንዘብ የተ.እ.ታ ደረሰኝ ሊቆርጥ እንደሚገባ ፤ የተቀበለውን ገንዘብ ሰብስቦ ለሚመለከተው የታክስ ባለስልጣን ታክሱን በወቅቱ ገቢ ማድረግና ሪፖርት ማድረግ እንደሚገባዉ የደነገገ ቢሆንም አመልካች በቼክ ቅድመ ክፍያ ብር 250,000.00 ሲቀበል የተ.እ.ታ ደረሰኝ ለተጠሪ አልሰጠም፡፡ አመልካች ሽያጭ መፈጸሙንም ለገቢዎች መስሪያ ቤት አለማሳወቁን አረጋግጫለሁ፡፡በዚህ ምክንያት ጉዳዩ በወንጀል እየታየ ይገኛል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የመኪናው ስመ ሀብት ዝውውር የተፈፀመ በመሆኑ አመልካች የተ.እ.ታ ክፍያ ጥያቄ ለማንሳት ከውልም ከሕግም የመነጨ መብት ስለሌለዉ በስር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 21/05/2013 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል በቀን 15/11/2009 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል አመልካች የሰሌዳ ቁጥር 03-853387 ኢት የሆነ አውቶብስ መኪና በብር 310,000.00 ለተጠሪ ሸጦለት ተጠሪ ብር 250,000.00 በመክፈል መኪናውንና ሊብሬውን እንደተረከቡና ለአመልካች ሊከፍሉ የሚገባ ቀሪ ብር 60,000.00 እንደሆነ በዉሉ ላይ ከተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ግራ

ቀኙም በዉሉ ላይ የተገለጸዉ ይሄዉ እንደሆነ ይተማመናሉ። በዉሉ ላይ ስለተ.እ.ታ በግልጽ የተባለ ነገር አለመኖሩንም ግራ ቀኙ የሚካካዱት አይደለም። ግራ ቀኙን ያከራከረዉና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ በዉሉ ላይ የመኪናዉ ሽያጭ ዋጋ ነዉ ተብሎ የተገለጸዉ ብር 310,000.00 ተ.እ.ታ ያካተተ ነዉ ወይስ አይደለም?ዋጋዉ ተ.እ.ታ አላካተተም የሚባል ከሆነ ዉጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉ ናቸዉ።ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች በዋጋዉ ላይ ተ.እ.ታ ስላልተካተተ ተጠሪ በዋጋዉ ላይ የተ.እ.ታ ብር 46,500.00 ተ.እ.ታ ጨምረዉ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ሲከራከሩ ተጠሪ ደግሞ አመልካች የመጀመሪያዉን ክፍያ ሲቀበሉ የተ.እ.ታ ደረሰኝ ሳይሰጡኝ ክፍያዉን ከመቀበላቸዉም በተጨማሪ አመልካች በተ.እ.ታ ስም ሊከፈለኝ ይገባል ብለዉ የጠየቁትን ገንዘብ መክፈል እንደሚገባኝ ግልጽ ስምምነት ባለማድረግና በዉሉም ላይ ስላልተመለከተ ልከፍል አይገባም በማለት ተከራክረዋል።የስር ፍርድ ቤቶችም የተጠሪን ክርክር በመቀበል ወስነዋል።

እንደሚታወቀዉ የተ.እ.ታ በፍጆታ ዕቃ ወይም በተጠቃሚው ወጪ ላይ የተመሠረተ ታክስ ሲሆን የሚሰበሰበውም ምርት ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ወይም ማንኛውም ታክስ የሚከፈልበት የዕቃና የአገልግሎት ግብይት ሲካሄድ ከተጠቃሚዉ ላይ በመሆኑ ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ አይነት ነው። ይህንን ታክስ ልዩ ከሚያደርጉት ባህሪያት አንዱ በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ መከናወን መቻሉና በዚህ ምክንያት በቀላሉ ሳይከፈል ሊታለፍ ወይም ሊጭበረበር አለመቻሉ ነዉ። በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 7(1 እና 3) ላይ በተመለከተዉ መሰረት የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ከተ.እ.ታ ነጻ ከተደረጉ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች በስተቀር እቃዎች ፣ አገልግሎቶች ፣ የግብአት አቅርቦቶች ሽያጭ ሲያከናዉን 15 በመቶ ተ.እ.ታ በእቃዉ ዋጋ ላይ ጨምሮ ከገዥ ወይም ከተጠቃሚዉ ላይ መሰብሰብ ይጠበቅበታል። ከላይ እንደተመለከተዉ የእቃዉ ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ የሚባለዉ በእቃዉ/በአገልግሎቱ ላይ በተጨመረዉ እሴት ላይ ተ.እ.ታ ተጨምሮ በተጠቃሚዉ የሚከፈል ገንዘብ ነዉ።ስለሆነም ተ.እ.ታ የሚከፈልበትን እቃ ወይም አገልግሎት የሚሸጥ ማንኛዉም የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ለተጠቃሚዉ የሚሸጠዉን እቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ሲገልጽ በዋጋዉ ላይ 15 በመቶ ተ.እ.ታ አካቶ መግለጽ ወይም ዋጋዉ ተ.እ.ታ ያላካተተ ከሆነም ይህንኑ ለገዥ በማያሻማ አኳኋን ማሳወቅና በደረሰኝ መሰብሰብ ይኖርበታል።(አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 7 እና የንግድ ዉድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 15/2 ይመለከቷል።) በመሆኑም ተ.እ.ታ መክፈል የተጠቃሚዉ ግዴታ ቢሆንም የተ.እ.ታ ተመዝጋቢ የሆነ ሰዉ ተ.እ.ታ የሚከፈልበትን እቃ/አገልግሎት ሽያጭ ሲያከናዉን ተ.እ.ታ የመሰብሰብ ግዴታ ስላለበት በእቃዉ ወይም በአገልግሎት ዋጋ ላይ ተ.እ.ታ ማካተቱን ሳይገለጽ ወይም ዋጋዉ ላይ ተ.እ.ታ አልተካተተም ብሎ በግልጽ ለተጠቃሚዉ ሳይገለጽ ግብይት የፈጸመ እንደሆነ የእቃዉ ወይም የአገልግሎቱ ዋጋ ነዉ ተብሎ በዉሉ የተጠቀሰዉ ገንዘብ ተ.እ.ታ ያካተተ እንደሆነ ይቆጠራል።ይህም ሻጭ ግብይቱን የፈጸመዉ ተ.እ.ታ በመሰብሰብ እንደሆነ ይቆጠራል እንደማለት ነዉ።

እንዲሁም በአንድ የሽያጭ ዉል ስለዋጋ የሚደረገዉ ስምምነት ከዉሉ ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ ስለሚሸጠዉ እቃ ዋጋ በተዋዋዮች ግልጽ ስምምነት ተደርጎ በማያሻማ አኳኋን በዉሉ ላይ መገለጽ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1680/1፣1711፣ 1714 እና 2266 ስር ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ለሽያጭ ዉል ዋጋ የዉሉ አይነተኛ ጉዳይ እንደመሆኑ በዉሉ ከተመለከተዉ በላይ የእቃዉን ዋጋ መጨመር የገዥን ግዴታ ማክበድ ስለሚሆን ገዥ በዚህ አግባብ ዋጋዉ ከፍ እንደሚል ቢያዉቅ ኖሮ ዉሉን ላይዋዋል ይችል ስለነበር በዉሉ ላይ ተቃራኒ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ዉሉ መፈጸም ያለበት ገዥ በዉሉ በግልጽ የተመለከተዉን ዋጋ ብቻ እንዲከፍል በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ በመኪና ሽያጭ ዉሉ ላይ በግልጽ የመኪናዉ ዋጋ ነዉ ተብሎ የተገለጸዉ ብር 310,000.00 ስለሆነና በዉሉ ከተመለከተዉ ዋጋ ወጪ ብር 46,500.00 ተ.እ.ታ ተጠሪ እንደሚከፍሉ በዉሉ ያልተመለከተ በመሆኑ ተጠሪ ለመክፈል የሚገደዱት ይህንን ያህል ገንዘብ ብቻ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የመኪናዉ ዋጋ ነዉ ተብሎ በዉሉ አንቀጽ 310,000.00 ተ.እ.ታ ያካተተ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች እንደዉሉ እንዲፈጸም ሲወስኑ አመልካች በዉሉ ላይ ያልተመለከተዉን የተ.እ.ታ ብር 46,500.00 ተጠሪ በመኪናዉ ዋጋ ላይ ጨምረዉ እንዲከፍሉ ያቀረበዉን ዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ መወሰናቸዉ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 73223 ላይ በቀን 25/08/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 240838 ላይ በቀን 14/05/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# የዳኝነት ስልጣን

የሰ.መ.ቁ.171061

መጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡....1.ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ደጀኔ አያንሳ

4. ኑረዲን ከድር

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡............አቶ ጌታቸዉ ሙሉጌታ

ተጠሪዎች፡......... ..1. አቶ መላኩ ሙሉጌታ

2. አቶ ምንተስኖት ሙሉጌታ

3. ወ/ሮ ልኬለሽ ወልዴ የሟች አቶ ፋሲል ሙሉጌታ ተተኪ ወራሽ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ይህ የዉርስ ሀብት ክርክር የተጀመረዉ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣የአሁን አመልካች የሥር የመቃወም ተጠሪ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር የመቃወም አመልካቾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር።ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.28837 ጥር 21 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበዉ አቤቱታ ሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ በሕይወት እያሉ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም የተጻፈ ኑዛዜ ስላተረፉልኝ የዉርስ ሀብቱ እንዲጣራልኝ በማለት ያቀረበዉን ተከትሎ፣ ፍ/ቤቱ የዉርስ አጣሪ ያቀረበዉን ሪፖርት መሰረት በማድረግ የአሁን አመልካች የሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ የኑዛዜ ወራሽ ነዉ በማለት የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠዉ ወስኗል።

ይህን ዉሳኔ ተከትሎ የአሁን ተጠሪዎች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት በማድረግ ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም አድርገዋል በተባለዉ ኑዛዜ እኛ ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆች እና የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ሆነን እያለ ከዉርስ የነቀለን ስለሆነ እኛ ባልተከራከርንበት ኑዛዜዉን መሰረት አድርጎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መብታችን የሚጎዳ ስለሆነ ለአሁን አመልካች የተሰጠዉ የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝልኝ እና ዉሳኔዉ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክቷል። የአሁን አመልካች በዚህ አቤቱታ ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍ/ቤቱ ይህን አቤቱታ ለማየት የዳኝነት ስልጣን የለዉም፤ የቀረበዉ

አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ነዉ፤ የአሁን ተጠሪዎች በኑዛዜዉ ከዉርስ አልተነቀሉም፣ የተሰጠኝ የወራሽነት ማስረጃ በአግባቡ ስለሆነ አቤቱታዉ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም አድርገዋል የተባለዉ ኑዛዜ ሲታይ የአሁን ተጠሪዎች ከዉርስ ስላልተነቀሉ ለአሁን አመልካች የተሰጠዉ የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ልጆቻቸዉ የሆኑትን የአሁን ተጠሪዎች ከዉርስ የነቀላቸዉ ስለሆነ የአሁን ተጠሪዎች የኑዛዜዉ ተጠቃሚ ከሆነዉ ከአሁን አመልካች ጋር የዉርስ ሀብቱን እኩል እንዲካፈሉ በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል። ይህ ጉዳይ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር የሥር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ በዚህ ጉዳይ የከተማዉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በሰጠዉ ዉሳኔ ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት ሲመለስ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም የተሰጠዉ የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል በማለት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ ላይ አከራክሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ የሚል ሆኖ የሥር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከዚህ ዉጭ በመዉጣት ተጠሪዎች ከኑዛዜ ተጠቃሚዎች ጋር እኩል እንዲካፈሉ በማለት የሰጠዉ ወሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት፣በዚህ ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ኑዛዜዉ ተጠሪዎችን ከዉርስ ነቅሏል እና ንብረቱን እኩል እንዲካፈሉ በማለት የመወሰን ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ22/9/2011 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ በዚህ ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ሟች ያደረጉት ኑዛዜ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች የሆኑትን ተጠሪዎች ከዉርስ የነቀለ መሆኑን በማየት ከኑዛዜ ተጠቃሚ ጋር እኩል እንዲካፈሉ በማለት ለመወሰን ስልጣን ያላቸዉ ስለሆነ ዉሳኔዉ እንዲጸናልን አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

እንደሚታወቀዉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት የፌዴራል ጉዳዮች፣ ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል እስካልተሰጠ ድረስ፣ በዳኝነት የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆኑን ይደነግጋል። ይህን የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ ተከትሎ ደግሞ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር

25/1988 መሰረት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍትሐ ብሔርም ሆነ የወንጀል ጉዳዮችን የዳኝነት ስልጣን በዝርዝር ተመልክቶ እናገኛለን።

በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት የአዲስ አበባ ከተማ በተመለከተ የተደነገገዉን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የፍትሐብሔርም ሆነ የወንጀል/የደንብ መተላለፍ ዳኝነት ስልጣን በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ላይ ተመልክቶ እናገኛለን።የተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በአንቀጽ 10 [1፣ መ] መሰረት ካደራጃቸዉ አካላት መካከል የከተማዉ የዳኝነት አካላት እንደሆነ ያመለክታል። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 መሰረት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ተደንግጓል። እንዲሁም የተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁ.408/1996 አንቀጽ 2 [1] መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የወራሽነት፣ የባልና ሚስትነት፣ የሞግዚትነት እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ለማየት ስልጣን እንዳላቸዉ ይደነግጋል። የዚህ ድንጋጌ እንግሊዚኛ ቅጂ ደግሞ “The Addis Ababa City Courts shall have jurisdiction over application for certificates of succession, marriage and guardianship” በማለት ይደነግጋል። ይህ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የወራሽነት የምስክር ወረቀት፣ የባልና ሚስትነት የምስክር ወረቀት፣ የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ለማየት የሥረ-ነገር ስልጣን እንዳላቸዉ ያስገነዝባል። የወራሽነት የምስክር ወረቀት ደግሞ በሕግ ወራሽ የሆነዉን እና የኑዛዜ ወራሽ የሚያካትት መሆኑ ግልጽ ነዉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች በአዋጁ አንቀጽ 2 [1] ሥር የተመለከተዉን የምስክር ወረቀት ለመስጠት ስልጣን ያላቸዉ ከሆነ፣ እነዚህ የምስክር ወረቀቶች እንዲሰረዝ የሚቀርበዉን አቤቱታ ተቀብሎ ተከራካሪ ወገኖችን አከራክሮ ሰምቶ ዉሳኔ ለመስጠት የስረ-ነገር ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ ነዉ።

በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.105211 ጥቅምት 1 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የሰጠዉን የወራሽነት የምስክር ወረቀት በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የሚቀርበዉን የመቃወሚያ አቤቱታ በማየት የማስረጃዉን ትክክለኛ እና ህጋዊነት በማረጋገጥ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያላቸዉ አዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች መሆናቸዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል። በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.75560 ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ በተመለከተ የቀረበዉን ጥያቄ ትክክለኛነቱን እና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ በማስረጃነቱ ዉሳኔ [Declaratory Judgment] ከመስጠት ዉጪ ማስረጃዉ የተሰጠበትን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሰረት የተቃዉሞ አቤቱታ በመቀበልና የጋብቻ መኖር አለመኖርንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን ክርክሮችን ለማስተናገድ የሥረ-ነገር ስልጣን የላቸዉም፣ የጋብቻ መኖር ያለመኖር ዉስብስብ

ያልሆነ ክርክር የሚቀርብበት ሳይሆን ክርክር ተደርጎበት ዉስብስብ የህግ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበት በመሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የላቸዉም በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል።

እንዲሁም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.172282 የካቲት 27 ቀን 2012 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት መሰጡቱን በመቃወም፣ ማስረጃዉ እንዲሰረዝ የሚቀርብ አቤቱታ ሲታይ አስቀድሞ ማስረጃዉን የወሰደዉ እና ማስረጃዉ እንዲሰረዝልኝ በማለት አቤቱታ ባቀረበዉ ሰዉ መካከል ከልጆች አስተዳደግ ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ እና አግባብነት ካላቸዉ ከአለም አቀፍ ሰነዶችና ኢትዮጵያ ተቀብላ ካጸደቀቻቸዉ እነዚህ የቃልኪዳን ሰነዶች እና የሀገራችን ሕጎች መሰረት ሙሉ ክርክርን ማድረግንና አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ጉዳዩን አጣርቶ መወሰንን የሚጠይቅ ጉዳይ ነዉ። የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት ይሻርልኝን ጥያቄ በዚህ አግባብ ክርክሩን በመምራትና አግባብነት ካላቸዉ ሕጎች አንጻር ሰፊና ዉስብስብ ክርክር ተደርጎ እና ተገቢ የሆነ የማጣራት ሂደት ተካሂዶ መወሰንን የሚጠይቅ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ። በመሆኑም የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት እንዲሻርልኝ በማለት የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ተከራካሪ ወገኖችን ሰምቶ አከራክሮ አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር አጣርቶ መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አይደሉም በማለት መወሰኑን መገንዘብ ተችሏል።

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሟች አቶ ሙሉጌታ ጉዲሳ ጥቅምት 11 ቀን 1977 ዓ.ም አድርገዋል የተባለዉ ኑዛዜ መሰረት በማድረግ የአሁን አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽነት በማረጋገጥ የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠቱን በመቃወም የምስክር ወረቀቱ እና ዉሳኔዉ እንዲሰረዝላቸዉ ማመልከታቸዉን ከግራ ቀኛቸዉ ክርክር መረዳት ተችሏል። ይህ ጥያቄ ደግሞ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ኑዛዜ የህጉን ፎርማሊቲዎችን አሟልቶ የተደረገ ነዉ ወይስ አይደለም? ኑዛዜዉ በሕጉ የተመለከተዉን መስፈርቶችን አሟልቶ የተደረገ እንደሆነ የሟች ወደ ታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ከዉርስ ነቅሏል ወይስ አልነቀለም? ዉጤቱስ ምን ይሆናል? የሚሉትን የክርክር ጭብጦችን የሚያስነሳ መሆኑን ማየት ይቻላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ከግራ ቀኛቸዉ የሚቀርበዉን ሰፊና ዉስብስብ ክርክሮችን መሰረት በማድረግ፣ የፍትሐብሔር ሕጉን ኑዛዜን የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የሚቀርበዉን ክርክር ሰምቶ አጣርቶ መርምሮ ዉሳኔ መስጠትን የሚመለከት ጉዳይ ነዉ። በመሆኑም የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት ይሰረዝልን ጥያቄ ሰፊና ዉስብስብ ክርክሮች ተደርጎ፣ በሕጉ አግባብ ተገቢ ማጣራትና ምርመራ ተደርጎበት ዉሳኔ የሚሰጥበት ነዉ እንጂ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት ከሚቀርብ አቤቱታ ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ሆኖ አይገኝም። በመሆኑም የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝልኝ በማለት

የሚቀርበዉን አቤቱታ መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸዉ እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አይደሉም ብለናል።

ሲጠቃለል የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝልን በማለት የሚቀርበዉን አቤቱታ ተቀብሎ የግራ ቀኛቸዉን ሙሉ ክርክር ሰምቶ አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር አጣርቶ መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አይደሉም በማለት የአሁን ተጠሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ መወሰን ሲገባቸዉ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.2586/01 በ26/8/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ.28443 በ20/11/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.28837 ጥር 21 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል።
2. የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝልኝ በማለት የሚቀርበዉን አቤቱታ ተቀብሎ ግራ ቀኛቸዉን አከራክሮ ሰምቶ እና በሕጉ አግባብ ተገቢዉን ማጣራትና ምርመራ በማድረግ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ-ነገር ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች አይደሉም። የአሁን ተጠሪዎች ለአሁን አመልካች የተሰጠዉ የኑዛዜ ወራሽነት የምስክር ወረቀት ሊሰረዝልን ይገባል የሚሉበት ሕጋዊ ምክንያት ያላቸዉ እንደሆነ አቤቱታቸዉን ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ ይህ ዉሳኔ አያግዳቸዉም ብለናል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

የሰ.መ.ቁ.230167

ሐምሌ 28/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡-የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን

ተጠሪዎች፡- 1. ሙሉጌታ መንግስት

2. ካሳሁን መኳንንት

3. ዮሓንስ ጌታቸው

አመልካች 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ በዚህ መዝገብ ላይ፤ እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችን አስመልክቶ እንደቅደም ተከተላቸው በሰ/መ/ቁ/230168 እና 230169 ላይ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም በሶስቱም መዝገቦች ላይ የቀረበው የሰበር ቅሬታ ነጥብ ተመሳሳይ በመሆኑ ሶስቱም መዝገቦች ቀድሞ በተከፈተው በዚህ መዝገብ ላይ ተጣምረው ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በሶስቱም መዝገቦች ላይ የቀረበው ጉዳይ ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለውም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑን መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪዎች በተናጠል ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አካልን ነፃ ማውጣት አቤቱታ ነው፡፡ የአቤቱታቸው ፍሬ ቃልም በአሁን አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ለወንጀል ምርመራ በሚል የጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቶባቸው የተጠረጠሩበት ወንጀል ሲጣራ ከቆየ በኋላ አመልካች በድጋሚ ያቀረበው የተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ይሰጠኝ አቤቱታ

ውድቅ የተደረገ ቢሆንም አመልካች ከህግ አግባብ ውጭ አስሮ ያቆያቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ከእስር እንዲለቀቁ የሚጠይቅ ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ ለማየት የዳኝነት የሥረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ እና ተጠሪዎች በእስር የቆዩት በህግ አግባብ ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ጠቅሶ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ተገድዶ የመያዝን ህጋዊነት ማጣራት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ሲሆን ስልጣኑም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀፅ 11 ስር በዝርዝር በተሰጠ የፍትሓ ብሔር ስልጣን ውስጥ አልተጠቀሰም፤ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባልተሰጠ የፌዴራል ጉዳይ ላይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 14 ስር ተመልክቷል የሚል እና ሌሎች ምክንያቶችን ጠቅሶ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለኝ በሚል መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ የተጠሪዎችን በእስር የመቆየት ህጋዊነትንም አስመልክቶ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ እስሩ ህገ ወጥ ነው በሚል ተጠሪዎች በዋስትና ከእስር እንዲለቀቁ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ አመልካች በሶስቱም መዝገቦች ላይ በተለያየ ቀን በፃፋቸው የሰበር አቤቱታዎች በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያላቸውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ በሶስቱም መዝገቦች ላይ አመልካች ያቀረባቸው የሰበር አቤቱታዎች ተመርምረው ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተመለከተውን ነጥብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መገንዘብ እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር ከፍርድ ቤት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣንን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የዳኝነት የሥረ ነገር ስልጣን አንድን በፍርድ ቤት የቀረበ ክርክርን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ችሎታን የሚመለከት ነው፡፡ የዳኝነት የሥረ ነገር ስልጣን የሚመነጨው በዋናነት ከጉዳዩ ዓይነት እና ለክርክር ምክንያት ከሆነው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ከጉዳዩ ዓይነት

የሚመነጭ የዳኝነት ሥረ ነገር ስልጣን ማለት ተለይተው የታወቁ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን በህግ ተለይቶ ለአንድ ፍርድ ቤት ሲሰጥ ማለት ነው፡፡ ለክርክር ምክንያት ከሆነው የገንዘብ መጠን የሚመነጨው የዳኝነት ስልጣን ደግሞ በገንዘብ ሊተመን የሚችልን ጉዳይ መሰረት አድርጎ የሚኖር ስልጣን ማለት ነው፡፡

በዚሁ አግባብ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌዴራል መንግስቱን ፍርድ ቤቶች በሶስት ደረጃ ካዋቀረ በኋላ ፍርድ ቤቶቹ በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሔር በወል እና በተናጠል ስለሚኖራቸው የዳኝነት የሥረ ነገር ሥልጣን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍትሓ ብሔር የዳኝነት ስልጣን በአዋጁ አንቀፅ 5 ስር ዘርዝሯል፡፡ በእነዚህ በፌዴራል መንግስቱ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር ከሚሸፈኑ የፍትሓ ብሔር ጉዳዮች ውስጥ በሶስቱም ደረጃ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሚኖራቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ስልጣን በአንቀፅ 10፣ 11 እና 14 ስር በተናጠል ተመልክተዋል፡፡

በአዋጁ መሰረት የፍትሓ ብሔር ጉዳይን አስመልክቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያ በክርክሩ የገንዘብ መጠን ተለይቶ የተሰጠ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በጉዳይ ዓይነት ተለይቶ የተሰጠ የዳኝነት ስልጣን ነው፡፡ ከክርክሩ የገንዘብ መጠን አንፃር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን ሥር በሚሸፈኑ እና ግምታቸው ከብር 10,000,000(አስር ሚሊዮን ብር) በላይ በሆኑ ማናቸውም የፍትሓ ብሔር ጉዳይ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 11(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ከጉዳዩ ዓይነት አኳያ ደግሞ ለፍርድ ቤቱ የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በአዋጁ አንቀፅ 11(2) እና (3) ስር ተመልክቷል፡፡ በጉዳይ ዓይነት ለፍርድ ቤቱ ተለይተው የተሰጡት የዳኝነት ስልጣናት በአዋጁ አንቀፅ 5(1(ሀ) እስከ (ሠ)) ስር የተመለከቱት ጉዳዮች፣ በህግ በሚወሰን መሰረት የሚቀርብ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለን የክስ ይዛወርልኝ ጉዳይ፤ እንዲሁም በፍርድ ታይተው ሊወሰኑ በሚችሉ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱት መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች ለማስከበር የሚቀርብን አቤቱታ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግልፅ ያልተሰጠ የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀፅ 11፣ እና 14 ድንጋጌዎች አቀራረፅ እና የቃላት አጠቃቀም መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የቀረበው ክርክር ተገድዶ የመያዝን ህጋዊነት ለማረጋጥ የሚቀርብን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚቀርብ አቤቱታ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት የሥረ ነገር ሥልጣን ስር የሚሸፈን ሰለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 5(1(ኘ)) ደንግጓል፡፡ ይህ ዓይነት ጉዳይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳይ ዓይነት ተለይተው በተሰጡት የመጀመሪያ ደረጃ

የዳኝነት የሥረ ነገር ሥልጣን ስር በግልፅ አልተመለከተም፡፡ በእርግጥ ከህግ አግባብ ውጭ ያለመታሰር መብት በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ውስጥ ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ከተደረገላቸው መሰረታዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ የህገ መንግሰቱ አንቀፅ 17 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 11(3) መሰረት በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱትን መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶችን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ አቤቱታ መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ህግ አውጪ አካልን ነፃ የማውጣት ጉዳይ በአዋጁ አንቀፅ 11(3) ማዕቀፍ ውስጥ እንዲታይ ሀሳብ ቢኖረው ኖሮ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር ጥበቃ ከተደረገላቸው በርካታ መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች ውስጥ ነጥሎ እራሱን በቻለ አንቀፅ መደንገግ አያስፈልገውም ነበር፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 11(3) ስር የተመለከለተው ሀሳብ ቀደሞ በነበሩት ህጎች ውስጥ ያልነበረ እና አዋጁ ካስተዋወቃቸው አዳዲስ ሀሳቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሀሳቡ አዲስ እንደመሆኑ መጠን በአተገባበር ረገድ በርካታ ውስብስብ እና እንግዳ የሆኑ ነገሮች ሊፈጠሩ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጉዳይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የተፈለገበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡ በአንፃሩ ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ አቤቱታ በህገ መንግስቱ ጥበቃ ከተደረገላቸው መሰራዊ መብቶች እና ነፃነቶች ውስጥ አንዱ ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከመውጣቱ በፊትም ቢሆንም በፍርድ ቤት በዳኝነት ሲታይ የነበረ እና የተለመደ ጉዳይ በመሆኑ ያን ያክል ውስብስብነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር በአዋጁ አንቀፅ 11(3) ስር የተመለከተው አዲስ ሀሳብ በአዋጁ አንቀፅ 5(1(ኘ)) ውጭ ያሉትን በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱትን እና በፍርድ ሊያልቁ የሚችሉ መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶችን ለማመልከት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን የማረጋገጥ ጉዳይ አስመልክቶ የዳኝነት ስልጣኑ ተለይቶ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልተሰጠ በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 11(1) እና 14 መሰረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ነው፡፡

በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተገድዶ የመያዝ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ አቤቱታን የማየት የዳኝነት ስልጣኑ የእኔ ነው ማለቱ በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም፡፡ የአቤቱታውን ጭብጥ አስመልክቶም የተጠሪዎች እስር ህገ ወጥ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/208998፣ 208670 እና 208669 እንደቅደም ተከተላቸው ሰኔ 27/2014 እና ሰኔ 23/2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና ውሳኔ፣ ይህንኑ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/293599፣ 293581 እና 293561 ላይ ሰኔ 28/2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ተገድዶ የመያዝን ህጋዊነት ለማረጋገጥ የሚቀርብን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህ ፍርድ ግልባጭ ከሰ/መ/ቁ/230168 እና 230169 ጋር ይያያዝ፡፡
2. በሶስቱም መዝገቦች ላይ ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

# ንግድና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁ.177907

መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ

ተጠሪ- ሚካኤል አባተ ሕንፃ ተቋራጭ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ መድን ሰጪ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ ከመድን ገቢዉ ለማስመለስ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረዉን ይርጋ እና አቆጣጠሩን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የጀመረው በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-35810 ኢት የሆነ ተሽከርካሪ ተገቢ ባልሆነ የመንጃ ፍቃድ ሲሽከረከር በፈፀመው ጥፋት በሌላ ሶስተኛ ወገን በሆነው የሰሌዳ ቁ. ኮድ 2-A24910 በሆነ አሽከርካሪና ግለሰብ ላይ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ በገባው የሶስተኛ ወገን የመድን ሽፋን ግዴታ መሠረት ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ያስጠገነና ለደረሰው የአካል ጉዳትም ካሳ በድምሩ ብር 92,987.4 መክፈሉን ጠቅሶ ይህንኑ ገንዘብ ተከሳሽ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ክሱ የቀረበው ጉዳቱ ከደረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማቅረቡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት በመቃወሚያዉ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ከሳሽ ክሱን ያቀረበው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ ከተፈጠረ ከሁለት ዓመት በኋላ በመሆኑ በንግድ ህጉ አንቀፅ 674 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም መዝገቡን አስቀርቦ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተጠቀሱትን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች በቀን 22/09/2011 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ተፈፅመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ በስር ፍ/ቤት ባቀረብነው ክስ ድርጊቱ በሰው አካልና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ስለሆነ በወንጀል የሚያስቀጣ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ህጉ መሠረት የይርጋው ዘመን አምስት ዓመት ቢሆንም በተፈፀመው ድርጊት ምክንያት የመጨረሻውን የካሳ ክፍያ ከተፈፀመበት 12/11/2009 ዓ.ም ጀምሮ የተሻሻለው ክስ እስከቀረበት ጊዜ ድረስ አንድ አመት እንኳ አልሞላውም፡፡ የይርጋ ጊዜው ሊቆጠር የሚገባውም አደጋው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ካሳውን ከከፈልንበት ጊዜ አንስቶ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ላለው ክርክር ተፈፃሚነት ያለው የንግድ ህጉ አንቀፅ 674 ነው? ወይስ የፍ/ህ/ቁ 2143 ነው? የሚለው መጣራት አለበት በሚል ታምኖበት ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ በጠበቃው አማካኝነት በቀን 23/03/2012 የተፃፈ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የመልሱ ይዘትም አመልካች ለፈፀመው የካሳ ክፍያ ተጠሪ ወጪውን እንዲተካለት የጠየቀው ግንቦት 27 ቀን 2007 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪ ወጪውን እንደማይተካ በግንቦት 29 ቀን 2007 ዓ.ም አሳውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክሱን ያቀረበው ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው የኢንሹራንስ ውል ስምምነት ሲሆን ይህንን መሰረት አድርጎ ለሚቀርብ ክስ ተፈፃሚነት የሚኖረው የንግድ ህጉ እንጂ የፍትሐ ብሔር ህጉ አይደለም የሚል ነው፡፡ አመልካችም በሰጠው የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች የሰሌዳ ቁጥሩ 3-35810 ኢት ሆኖ ንብረትነቱ የአሁኑ ተጠሪ በሆነዉ ተሽከርካሪ በፈጸመዉ ጥፋት በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ አደጋ የመድን ሽፋን መስጠቱ አላከራከረም፡፡ አመልካች በዚህ ተሽከርካሪ ምንክያት በ3ኛ ወገን ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ ከከፈለ በኋላ በተጠሪ ላይ ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ጉዳቱ የደረሰዉ ተገቢ ባልሆነ መንጃ ፍቃድ በያዘ አሽከርካሪ ምክንያት መሆኑን እና ይህም ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 799/2005 መሠረት ከተጠሪ የማስመለስ መብት ያለዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ለጉዳቱ መንስኤ የሆነዉ አደጋ የደረሰዉ በ17/05/2007 ዓ.ም መሆኑ፣ አመልካች ክፍያዉን ለሦስተኛ ወገን የፈጸመዉ ሐምሌ 12 ቀን 2008 ዓ.ም መሆኑ እንዲሁም ክሱ የቀረበዉ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም ስለመሆኑ በግራ ቀኝ የታመነ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ የስር ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የመጀመሪያ መቃወሚያ በመቀበል የአመልካችን ክስ በይርጋ ዉድቅ በማድረግ ለሰጡት ዉሳኔ

መሠረት ያደረጉት አደጋዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለዉ ጊዜ ሲቆጠር ከሁለት ዓመት በላይ መሆኑን በንግድ ህጉ አንቀጽ 674 (1) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ ስለመሆኑ ከዉሳኔዎቹ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሚሰጥ የመድን ሽፋን የሚመነጨዉ በመድን ሰጭዉና በመድን ገቢዉ መካከል በሚደረግ የመድን ዉል ፖሊሲ መነሻ ቢሆንም በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ አደጋ የመድን ሽፋን ለመስጠት በወጣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት በመድን ዉሉ ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ አደጋ የደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች በሽፋኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ግንኙነት መፈጠሩን መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ ምንም እንኳን ግራ ቀኝ የመድን ዉሉ ተዋዋዮች ቢሆኑም ከዉሉ ተጠቃሚዎች ሦስተኛ ወገኖች ጭምር በመሆናቸዉ የመድን ዉል ፖሊሲዉ እና አዋጅ ቁጥር 799/2005 የሦስትዮሽ ግንኙነትን እንዳቋቋመ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ክሱን የመሰረተዉ የመድን ዉሉን እና በአዋጅ ቁጥር 799/2005 መሰረት በማድረግ በመሆኑ ግንኙነታቸዉ በመድን ዉል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረዉ የይርጋ ድንጋጌ ይህንን በዉል ላይ የተመሰረተዉን ግንኙነት መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ ግንኙነቱም የመድን ዉልን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ በንግድ ህጉ አንቀጽ 674 ላይ የተመለከተዉ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በዉሳኔያቸዉ ይህን ድንጋጌ መጥቀሳቸዉ በመሠረቱ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከዉል ዉጭ የሆነ ኃላፊነት መነሻ በማድረግ ካሳ ለማስከፈል ለሚቀርብ ክስ ተፈጻሚነት እንዲኖረዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር የተደነገገዉ የይርጋ ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ስለሌለዉ አመልካች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር የተደነገገዉ ነዉ በሚል ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልነዉም፡፡

ይልቁንም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ጭብጥ የሁለት ዓመቱ የይርጋ ጊዜ የሚቆጠረዉ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነዉ አደጋ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ የሚል የስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የግራ ቀኙን ክርክር መሠረታዊ ባህርይ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑ ነዉ፡፡ ስለ ሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የሚደነግገዉ አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 መድን ሰጪዉ በአደጋ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ካሳ ለሦስተኛ ወገን ከከፈለ በኋላ መድን ገቢዉ እንዲተካለት መጠየቅ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ይሁንና እንዲህ ዓይነት ክስ መቅረብ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በተመለከተ አዋጁ በተለይ አይደነግግም፡፡ ከኢንሹራንስ ዉል ጋር የተያያዙ ክሶችን ይርጋ በተመለከተ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር በኢንሹራንስ ዉል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛዉም ክስ የሚታገደዉ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያላቸዉ ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ (በእንግሊዘኛዉ ቅጅ፡ …from the occurrence giving rise to the claim or from the day when the parties knew of the occurrence) ከሁለት ዓመት በኋላ ነዉ በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜዉ መቁጠር የሚጀምረዉ ጉዳቱ ከደረሰበት ወይም መብት ያላቸዉ ወገኖች ጉዳት ስለመድረሱ ካወቁበት ጊዜ

ጀምሮ እንደሆነ ያሳያል። መድን ሰጪዉ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ መድን ገቢዉ እንዲተካለት፣ በመካከላቸዉ ያለዉን የመድን ዉል ወይም ህግ መሠረት በማድረግ፣ መጠየቅ የሚችለዉ በቅድሚያ ካሳዉን ለሦስተኛ ወገን መክፈሉ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ እሙን ነዉ። ይህ ደግሞ ሦስተኛ ወገኑ ካሳዉ እንዲከፈለዉ የሚያቀርበዉን ጥያቄ መሠረት በማድረግ በመሆኑ የመድን ሰጪዉ የይተካልኝ ዳኝነት ጥያቄ የሚያቀርበዉ ሦስተኛ ወገኑ ካሳ እንዲከፈለዉ በሚያቀርበዉ ሁኔታ እና ጊዜ ላይ የሚወሰን መሆኑን የሚያሳይ ነዉ። ስለሆነም መድን ሰጪዉ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉ ካሳ በመድን ገቢዉ እንዲተካለት ለመጠየቅ ባለዉ መብቱ መስራት የሚችለዉ በሦስተኛ ወገን ጥያቄ መሠረት ካሳዉን ከከፈለዉ በኋላ በመሆኑ ጉዳቱ ከደረሰበት ወይም ስለጉዳቱ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ የይተካልኝ ክስ ያቀርባል ተብሎ አይጠበቅም። ይህ እየታወቀ የሁለት ዓመት ጊዜዉ መቆጠር የሚጀምረዉ ጉዳቱ ከደረሰበት ወይም ጉዳቱ መድረሱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ በሚል መወሰን "መብታቸዉን በተገቢዉ ጊዜ ለማስከበር የሚተጉ ሰዎችን ለማበረታት (to encourage diligence and to discourage negligence) ነዉ" የሚለዉን የይርጋን መሠረታዊ ዓላማ የሚያፋልስ ከመሆኑም በላይ እንደ አመልካች ያሉ ሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት የመገደብ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘቡም ተገቢ ነዉ። ይህ በመሆኑም ለያዝነዉ ዓይነት ጉዳይ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረዉ መቼ ነዉ? ለሚለዉ ነጥብ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የመድን ዉል በባህሪዉ የሦስትዮሽ ግንኙነትን የሚመለከት ከመሆኑ አንፃር በማገናዘብ ትርጉም መስጠቱ ተገቢ ይሆናል።

ከላይ እንደተመለከተዉ ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የዉል ግንኙነትን መሠረት ያደረገ ነዉ። ከዉል የሚመነጩ ግንኙነቶች የሚገዙበት የይርጋ ደንቦች ስለ ዉሎች በጠቅላላዉ በሚደነግገዉ የፍትሐብሔር ህጉ ክፍል ከአንቀጽ 1845-1856 የተመለከቱ ሲሆን፣ ከእነዚህም ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል በአንቀጽ 1846 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ነዉ። ይህ ድንጋጌ "የይርጋ ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታዉን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነዉ፤ ወይም ዉሉ የሚሰጠዉ መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነዉ" በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ እንግሊዝኛዉ "The period of limitation shall run from the day when the obligation is due or the rights under the contract could be exercised" በማለት ይደነግጋል። በሌላ በኩል የመድን ዉልን መሠረታዊ ባህርይ ከግምት ዉስጥ በማስገባት የንግድ ህጉ አንቀጽ 674/1 ከመድን ዉል የሚመነጩ ክሶች የሚቀርቡበትን የይርጋ ጊዜ በተለይ የሚደነግግ ቢሆንም፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ "በመብት መስራት መጀመር" የይርጋ መቁጠሪያ መነሻ ጊዜ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ በግልጽ አላመላከተም። በመሆኑም የይርጋ መቁጠሪያ መነሻ ጊዜን በተመለከተ በፍትሐብሔር ህጉ እና በንግድ ህጉ መካከል ቅራኔ (contradiction) አለ ለማለት አይቻልም። በተለያዩ የህግ ክፍሎች በሚገኙ ድንጋጌዎች መካከል ቅራኔን ከማፈላለግ ይልቅ ተደጋጋፊ ሆነዉ የጋራ ዓላማ የሚያሳኩበትን የህግ ትርጉም መሻት የህግ ባለሙያዎች ሊመርጡት የሚገባ የህግ አተረጓጎም ዘይቤ በመሆኑ ልዩ ህግ ጠቅላላ ዓላማ ካለዉ ህግ ቅድሚያ ይሰጠዋል (the

special prevails over the general) የሚለዉን የህግ አተረጓጓም ተከትሎ ዉሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት በሁለቱ የህግ ክፍሎች መካከል የማይታረቅ፣ ምክንያታዊ የሆነ፣ በላቀ የህግ አዉጪዉ ፍላጎት የተደገፈ ግጭት መኖሩን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ይህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም ላይ ካሰፈረዉ ሃሳብ መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ከይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ጋር በተያያዘ በንግድ ህጉ እና በፍትሐብሔር ህጉ ላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መካከል የሚታይ ቅራኔ (apparent contradiction) የሌለ በመሆኑ የይርጋ ጊዜ አቆጣጠርን አስመልክቶ በንግድ ህጉ ላይ የተመለከተዉን ብቻ በመቀበል አንድ ሰዉ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ የሚችለዉ በመብቱ መስራት ከሚችልበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ከአጠቃላይ የይርጋ መሠረታዊ ዓላማ ጋር በማገናዘብ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1846 ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ወደ ጎን በመተዉ ከዉሳኔ ላይ መድረስ ትክክለኛ የህግ አተረጓጎም ዘይቤ አይደለም። በዚህ ችሎት እምነት በዚህ ጉዳይ ላይ ተመራጭ የሚሆነዉ የአተረጓጓም ዘይቤ በንግድ ህጉ ላይ የተመለከተዉን የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ በመዉሰድ፣ የይርጋዉ ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ አስመልክቶ ግን የያዝነዉን ጉዳይ መሠረታዊ ባህርይ ግምት ዉስጥ በማስገባት በፍትሐብሔር ህጉ ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ ተፈፃሚ በማድረግ ሁለቱ የህግ ክፍሎች ተደጋጋፊ ሆነዉ ተፈፃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የይርጋን መሠረታዊ ዓላማ ሊያሳካ የሚችል ዘዴን መከተል ነዉ።

በዚህም መሠረት፣ በንግድ ህጉ አንቀጽ 674/1/ ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ ቢሆንም ጉዳዩ የሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ዉል ያለዉን ልዩ ባህርይ ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ከሳሹ በመብቱ መስራት የቻለበት ቀን የይርጋዉ መቁጠሪያ መነሻ ቀን እንደሚሆን በግልጽ አላመለከተም። ይህ የህጉ ክፍተት በመሆኑም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1676(1) ላይ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚችለዉ ከሳሹ በመብቱ መስራት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ነዉ በሚል በህጉ አንቀጽ 1846 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ጉዳት ለደረሰበት ሦስተኛ ወገን የሚገባዉን ክፍያ ከፈጸመ በኋላ መድን ሰጭዉ በመድን ገቢዉ ላይ የሚያቀርበዉ የካሳ ይተካልኝ ክስ ሲሆን፣ በንግድ ህጉ ላይ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር የሚጀምረዉ ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን መድን ሰጪዉ በአደጋዉ ምክንያት በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ካሳ ከከፈለበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ አንፃር ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለጉዳቱ መንስኤ የሆነዉ አደጋ የደረሰዉ በ17/05/2007 ዓ.ም ቢሆንም፣ አመልካች ክፍያዉን ለሦስተኛ ወገን የፈጸመዉ ሐምሌ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ሆኖ ክሱ የቀረበዉ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም አመልካች ክሱን ያቀረበዉ ለሦስተኛ ወገን ካሳ ከፍሎ የሁለት ዓመት ጊዜ ከማለቁ በፊት በመሆኑ ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ አይደለም። ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉን አደጋዉ የደረሰበትን ቀን ለይርጋ

አቆጣጠር መነሻ በማድረግ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ታግዷል በማለት መዝገቡን መዝጋቱና ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህን ስህተቱን ሳያርም ማለፉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45499 ላይ በቀን 19/11/2010 ዓ/ም የሰጠዉ ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 223537 ላይ በቀን 27/06/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮና እንደአስፈኒነቱ ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

## ትዕዛዝ

- ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ግልባጩ ለጥናትና ህግ ስራ ክፍል ይድረስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሠ/መ/ቁጥር 196878

የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ

ተጠሪዎች ፡- 1. አቶ ሃብቴ አንማዉ

2. ወ/ሮ መሬም አሰፋ

3. አቶ አደራው እንቻለዉ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን የተገባለት ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ካሳ ለማስከፈል ዳኝነት ተጠይቆ በቀረበ ክርክር መድን ሰጪዉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳቱ የደረሰዉ በመድን ገቢዉ ጥፋት ነዉ በሚል የሚያነሳዉን ክርክር ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ 1ኛ ተጠሪ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ፣በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ እና በስር 3ኛ ተከሳሽ ላይ በመሰረቱት ክስ ንብረትነቱ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሆነ በሰሌዳ ቁጥር አማ03-12248 በሚታወቅ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ተሳፍረዉ ሲጓዙ በግምት 40 ሜትር ዝቀታማ ቦታ ላይ በመግባቱ ምክንያት በደረሰዉ አደጋ የግራ እግራቸዉ የጭን አጥንት የመሰበር ጉዳት እና የሕሊና ጉዳት እንደደረሰባቸዉ በመግለጽ ለህክምና የወጣ ወጪ፣ከጉዳቱ ለማገገም ለአልሚ ምግብ የወጣ ወጪ፣ለህክምና ለመመላለስ ለትራንስፖርትና ለአልጋ የወጣ ወጪና የሞራል ጉዳት ካሳ ጨምሮ በድምሩ ብር 74,358.00 አመልካች፣የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም የስር 3ኛ ተጠሪ አሽከርካሪዉ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰባቸዉ በተሽከርካሪዉ ተሳፍረዉ ሲሄዱ በመሆኑ ሊከፈላቸዉ የሚገባዉ የካሳ መጠን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 579 መሰረት ከብር 40,000.00 ሊበልጥ አይገባም፡፡ የህሊና ጉዳት ካሳም ከብር 1000.00 በላይ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ ለምግብ፣ ለአልጋና ለትራንስፖርት አወጣሁኝ ብለዉ የጠየቁት የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉና የተጋነነ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ በፖሊስ ሪፖርት መሰረት አደጋዉ የደረሰዉ ተሽከርካሪ መጫን ከሚገባዉ በላይ ከ40 እስከ 48 ሰዉ ጭኖ ሲሄድ በመሆኑ በአመልካችና የተሽከራከሪዉ ባለሀብቶች በሆኑት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል በተደረገዉ የኢንሹራንስ ዉል የማግለያ አንቀጽ 2 መሰረት ጉዳቱ ተሽከርካሪዉ በሕጋዊ መንገድ እየተሽከረከረ ባለበት ሂደት የደረሰ ባለመሆኑ አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም ሲል ተከራክሯል፡፡ኃላፊነት አለብህ ከተባለም 1ኛ ተጠሪ እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት ካሳ የተጋነነ በመሆኑና በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት የአመልካች ኃላፊነት ከብር 40,000.00 በላይ ሊሆን አይገባም፡፡የሞራል ካሳ ለመክፈል የመድን ሽፋን አልሰጠሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 0141524 ላይ ግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች በመስማት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከስር 3ኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በደረሰዉ ጉዳቱ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ያወጡትን ልዩ ልዩ ወጪዎች በተመለከተ እና ለህሊና ጉዳት ካሳ ብር 63,858.00 እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡እንዲሁም አመልካች በክርክሩ ላይ እንደገለጸዉ መኪናዉ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ብዙ ሰዎች በትርፍነት ጭኖ ሲያንጉዝ የነበረ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር የፈጸመዉ የመድን ዉል የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ተሽከሪካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርስ ጉዳት ካሳ ለመክፈል የተደረገ በመሆኑና አመልካች በክርክሩ በገለጸዉ መሰረት በኢንሹራንስ ዉሉ ላይ በማግለያነትም እንዳልተመለከተ ገልጾ አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም ብሎ መከራከር አይችልም በማለት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችና የስር 3ኛ ተከሳሽ ይክፈሉ ከተባለዉ ገንዘብ ላይ አመልካች ብር 40,000.00(አርባ ሺህ ብር) ለአሁን 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ እንዲሁም በክሱ ምክንያት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ያወጡትን ወጪዎች በተመለከተም አመልካች፣ የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችና የስር 3ኛ ተከሳሽ ብር 4,585.00 ለአሁን 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 53800 ላይ በቀን 26/09/2012 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞበታል፡፡አመልካች በቀን 10/02/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ መልኩ በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በተሽከርካሪዉ ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ ተሽከርካሪዉ መጫን ከሚገባዉ 24 ሰዉ በላይ ከ40-48 ሰዉ ጭኖ እንደነበር በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡የኢንሹራንስ ዉል እንደማንኛዉም ዉል ሕጋዊ ተግባራት ሲከናወኑ ለሚደርስ አደጋ የካሳ ክፍያ የሚፈጸምበት ዉል እንጂ በሕገ-ወጥ ድርጊት ምክንያት ለመጣ ጉዳት ጭምር የመካስ ኃላፊነት የሚያስከትል አይደለም፡፡የኢንሹራንስ ዉሉ ተሽከርካሪዉ ከአቅሙ በላይ ጭኖ ሲሽከረከር ለሚደርስ አደጋ አመልካች የመድን ሽፋን እንደማይሰጥ ወይም በዉል እንደተገለለ

የተገለጸዉን ባለማገናዘብ ካሳዉን ሙሉ በሙሉ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እንዲከፍሉ መወሰን ሲገባዉ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ብር 40,000.00 ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ ከመድን ዉሉና ከሕጉ ዉጭ ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ከተባለም የአመልካች ኃላፊነት እስከ ብር 40,000.00 ሆኖ እያለ አመልካች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በክሱ ምክንያት የወጣዉን ወጪ ብር 4,585.00 ለ1ኛ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ ከኢንሹራንስ ዉሉ ዉጭ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ከተፈቀደለት ተሳፋሪ በላይ በመጫኑ የተነሳ አደጋዉ የደረሰ መሆኑ በተገለጸበት አመልካች በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት ካሳ ሊከፍል ይገባል በሚል የተወሰነበትን አግባብ ከሕጉና ከኢንሹራንስ ዉሉ አንጻር እንዲጣራ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀን 06/04/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

ተሽከርካሪዉ መጫን ከሚገባዉ ሰዉ በላይ ጭኖ አልተገኘም፡፡ከአቅም በላይ ጭኖ ሲጓዝ የነበረ ተሽከርካሪ በሰዉም ሆነ በንብረት ላይ በሚያደርሰዉ ጉዳት የመድን ሽፋን እንደማይሰጥ የመድን ዋስትና ዉሉ ላይ በግልጽ የደነገገዉ ነገር የለም፡፡ስለሆነም አመልካች ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት ያቀረበዉ የዉልና የሕግ ድጋፍ ያለዉ ባለመሆኑ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 06/05/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

1ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸዉ መልሳቸዉን ባለማቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ባለቤትነት በሰሌዳ ቁጥሩ አማ03-12248 በሚታወቅ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ሊሚያደርሰዉ አደጋ አመልካች የኢንሹራንስ ሽፋን መስጠቱና በዚህ ተሽከርካሪ ተሳፍረዉ ሲጓዙ ተሽከርካሪዉ ገደል ዉስጥ በመግባት በ1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት መድረሱ ተረጋግጧል፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ 1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰዉ ተሽከርካሪዉ እንዲጭን ከተፈቀደለት በላይ ብዙ ሰዉ ትርፍ ጭኖ በማጓጓዝ ላይ እያለ በመሆኑ በኢንሹራንስ ዉሉ የማግለያ (Exception) አንቀጽ 2 መሰረት በእንዲህ አይነት ምክንያት ጉዳት ሲደርስ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም ሲል አመልካች ያቀረበዉ መከራከሪያ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን የሚመነጨዉ በኢንሹራንስ ሰጪዉና በኢንሹራንስ ገቢዉ መካከል በሚደረግ

የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ መነሻ ነዉ፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ አደጋ የኢንሹራንስ ሽፋን ለመስጠት በወጣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት በኢንሹራንስ ዉሉ ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ አደጋ የደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች በሽፋኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ግንኙነት በሕግ ተፈጥሯል፡፡ በዚህ አግባብ ምንም እንኳን አመልካችና የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የኢንሹራንስ ዉሉ ተዋዋዮች ቢሆኑም ከዉሉ ተጠቃሚዎች ሦስተኛ ወገኖች ጭምር በመሆናቸዉ የኢንሹራንስ ዉል ፖለሲዉ እና አዋጅ ቁጥር 799/2005 የሦስትዮሽ ግንኙነትን እንዳቋቋመ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

አመልካች ክርክሩን ያቀረበዉ በኢንሹራንስ ዉሉ ማግለያ አንቀጽ 2 ስር የተደነገገዉን ኢንሹራንስ ሠጪዉ ኃላፊ የማይሆንበትን የማግለያ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡ ሆኖም የኢንሹራንስ ዉሉ በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገኖች ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ለመካስ የተደረገ እንደመሆኑ ይህ የአመልካች መከራከሪያ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6 ስር ከተደነገገዉ አንጻር ተገናዝቦ መታየት ይኖርበታል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 6/1 ስር በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉ ዉስጥ ተጠያቂነትን አያስከትልም የሚል ወይም በፖሊሲዉ መሰረት ለካሳ ጥያቄ መነሻ የሚሆነዉ ክስተት ከደረሰ በኋላ የተወሰነ ድርጊት ከተፈጸመ ወይም ሳይፈጸም ከቀረ ኃላፊነት ቀሪ ይሆናል የሚል ሁኔታ ቢቀመጥ ሕጋዊ ዉጤት እንደማይኖረዉ ተድንግጓል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ በተሽከርካሪ ለሚደርስ አደጋ የኢንሹራንስ ሽፋን የሰጠ ኢንሹራንስ ኩባንያ በአንሹራንስ ዉሉ ላይ ኢንሹራንስ ገቢዉ ይህንን ካደረገ ወይም ካላደረገ ተጠያቂነት አይኖርብኝም በማለት ያስቀመጠዉን ሁኔታ መሰረት በማድረግ በሦስተኛ ወገን ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ካሳ ላለመክፈል ጉዳት ለደረሰበት ሦስተኛ ወገን መከራከሪያ ሊያደርግ እንደማይችል ነዉ፡፡በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉ ላይ የተቀመጠዉን የማግለያ ወይም ሌላ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በኢንሹራንስ ገቢዉ ላይ መከራከሪያ ሊያደርግ የሚችለዉ በመጀመሪያ ጉዳት ለደረሰበት ሦስተኛ ወገን በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16 እና በኢንሹራንስ ዉል ፖሊስዉ በተመለከተዉ መሰረት ካሳ ከከፈለ በኋላ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 6/2 ስር የተደነገገዉ ያስገንዝባል፡፡

በመሆኑም አመልካች ከ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋር በፈጸመዉ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የተመለከተዉን ኃላፊነት የሚያስቀር ማግለያ በመጥቀስ በ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ላይ መከራከሪያ ሊያደርግ የሚችለዉ አስቀድሞ በተሽከርካሪዉ በ1ኛ ተጠሪ ላይ የደረሰዉን ጉዳት ከካሰ በኋላ ነዉ ብለናል፡፡ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም ሲል ያቀረበዉን መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ይክፈሉ ተብሎ ከተወሰነዉ ላይ ብር 40,000.00 አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰናቸዉ ሕግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

እንዲሁም በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ እና በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 16(1/ለ) መሰረት አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰዉ የአካል ጉዳት ለመክፈል የሚገደደዉ የካሳ መጠን እስከ ብር 40,000.00 ድረስ ብቻ እንደሆነ የተመለከተ ቢሆንም ይህ ኃላፊነት በቀጥታ ኢንሹራንስ በተገባለት ተሸከርካሪ ሦስተኛ ወገን በሆኑት 1ኛ ተጠሪ አካል ላይ የደረሰዉን ጉዳት ከመካስ ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡በክሱ ምክንያት የወጣ ወጪ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፈላቸዉ የተወሰነዉ ደግሞ በኢንሹራንስ ዉሉና በሕግ በተደነገገዉ መሰረት ካሳ ባለመክፈሉ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ለክስ በመዳረጋቸዉና በክርክሩ በመርታታቸዉ በክሱ ምክንያት ያወጡት ወጪ ሊተካላቸዉ እንደሚገባ በመታመኑ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 462 ስር በተደነገገዉ መሰረት በክርክሩ የረታዉ ሰዉ በክሱ ምክንያት ያወጣዉን ወጪ ተረቺዉ እንዲተካለት ፍርድ ቤቱ ትክክል ነዉ ብሎ በሚገምተዉ መሰረት መወሰን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በክሱ ምክንያት ያወጡትን ወጪ አመልካች ከሌሎች ተከራካሪዎች ጋር በመሆን መጠኑ ከላይ የተጠቀሰዉን ገንዘብ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ በመሆኑ በዚህም ረገድ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1.በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0141524 ላይ በቀን 03/06/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 53800 ላይ በቀን 26/09/2012 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሠ/መ/ቁጥር 193270

የካቲት 24 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ሐበን ጉዕሽ

ተጠሪ፡- ናይል ፔትሮሊየም ካምፓኒ ሊሚትድ ኢትዮጵያ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገንዘብ መጠኑ እና ቀን ሳይጻፍበት በቼክ አዉጭዉ ተፈርሞ የተሰጠ ቼክ (Blank Cheque) የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአጭር ሥነ ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንለት በመሰረተዉ ክስ አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 10000002172 ካለዉ ገንዘብ ላይ በቼክ ቁጥር ID3905680 ብር 6,988,527.14 እንዲሁም በቼክ ቁጥር ID 3905681 ብር 5,136,773.70 በድምሩ ብር 12,125,300.84(አሥራ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም) በያዙ ቼኮች ባንኩ ክፍያ እንዲፈጽም አመልካች ቼኮቹን ፈርሞ ለተጠሪ ሰጥቷል፡፡ሆኖም ተጠሪ ቼኮቹን ለባንኩ ሲያቀርብ ባንኩ በአመልካች ሂሳብ ዉስጥ በቂ ገንዘብ የሌለ በመሆኑ መክፈል እንደማይችል በመግለጽ በቀን 10/09/2008ዓ/ም የተጻፈ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ስለሆነም አመልካች በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ብር 12,125,300.84(አሥራ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም) ቼኮቹን ከሰጡበት ከቀን 03/09/2008ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድና ክሱ ከሚያስከትለዉ ወጪ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ መከላከያ እንዳላቸዉ ገልጸዉ ያቀረቡትን ማስፈቀጃ ፍርድ ቤቱ መቀበሉን ተከትሎ ባቀረቡት መልስ ለክሱ መነሻ የሆኑ ቼኮች ተጠሪ እጅ ሊገቡ የቻሉት አመልካች ነዳጅ ለመግዛት ከተጠሪ ጋር ባደረገዉ የቃል ንግግር መሰረት ዉል ለመዋዋል በሂደት ላይ ስለነበርን ለቅድመ ክፍያ ለዋስትና ተብሎ የገንዘብ መጠንና ቼኩ የሚከፈልበትን ቀን ሳይጻፍ ፊርማ ብቻ በመፈረም ለተጠሪ የተሰጠ ነዉ፡፡በቼኮቹ ላይ የገንዘብ መጠኑ እና ቼኩ የሚከፈልበት ቀን የሚጻፈዉ ግን ዉል ከተፈራረምንና

የነዳጅ ዋጋ ታዉቆ በዉሉ መሰረት ነዳጅ ከወሰድኩ በኋላ ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ ክፍያ እንዲፈጸምለት ለባንኩ ከማቅረቡ በፊት የተደረገ ዉልና የተሠራ ሥራ ካለ በዚሁ መሰረት አመልካች ያልተወጣሁት ግዴታ መኖሩን አረጋግጦ መሆን እያለበት ተጠሪ ያለምንም ምክንያት ቼኮቹ ላይ የገንዘብ መጠኑንና ቀኑን ሞልቶ ክፍያ መጠየቁ የቅን ልቦና አሠራርን የሚቃረንና ቼኮቹ ከተሰጠበት ዓላማ ዉጭ ነዉ፡፡ ተጠሪ ዉል ስለመኖሩ ወይም የተወሰደ ነዳጅ ስለመኖሩ በክሱ ካለመግለጹም በተጨማሪ ይህንን የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 179745 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ምስክሮች በመስማት በቀን 20/02/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ቼክ እንደቀረበ ሊከፈል የሚገባ ሰነድ መሆኑን በንግድ ሕግ አንቀጽ 732፣827/ሀ እና 854 ላይ መደንገጉን፤አመልካች በድምሩ ብር 12,125,300.84 ዋጋ ያላቸዉን ቼኮች መስጠታቸዉን፤ቼክ አዉጪዉ በባንክ ሂሳቡ በቂ ስንቅ እንዳለዉ እርግጠኛ መሆን እንዳለበት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 830/2 ላይ መደንገጉን ፤አመልካች ለተጠሪ በሰጡት ቼኮች ለመክፈል የማይገደዱት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 ስር የተመለከቱትን መቃወሚያዎች በማስረዳት እንደሆነ፤አመልካች ያቀረቡት መከራከሪያ ለክርክሩ መነሻ በሆኑት ቼኮች ላይ የተጻፈዉን ገንዘብ ተጠሪ ራሱ በሚያመቸዉ መንገድ የሞላዉ ስለሆነ ለመክፈል አልገደድም የሚል ቢሆንም ቼኮቹን መስጠታቸዉን በቼኮቹ ላይ ያለዉ ፊርማ የራሳቸዉ እንደሆነ ስላልካዱ ቼኮቹ የሚከፈሉበት ቀንና የገንዘብ መጠኑ በተጠሪ መሞላቱ ቼኩን ዋጋ እንደማያሳጣዉ፤ተጠሪ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 137 መሰረት ባቀረበዉ ማስረጃ ከዚህ ቀደም በነበራቸዉ ግንኙነት መነሻ አመልካች ለተጠሪ በቼክ ቁጥር ID 3905671 የሚታወቅ ቼክ ፈርመዉ ሰጥተዉ ተጠሪ በቼኩ ላይ ብር 1,544,941.38 ጽፎ ቼኩን በመመንዘር ክፍያዉን በቀን 24/06/2008 ዓ/ም መቀበሉን ተጠሪ ማስረዳቱን፤ይህም ክሱ ከመመስረቱ በፊት በግራ ቀኙ መካከል ግንኙነት እንደነበረና በቼኩ ላይ የገንዘብ መጠን እየሞላ ተጠሪ ገንዘቡን ሲቀበል የነበረ መሆኑን፤አመልካች በቼኮቹ ላይ የተጻፈዉን ቀን ገንዘብ እንዳልጻፉ በመግለጽ በፎሬንሲክ እንዲመረመር ቢጠይቁም ይሕንን መከራከሪያ ያነሱት ከተጠሪ ጋር የቀደመ ግንኙነት እንደሌላቸዉ አስመስለዉ ቢሆንም በመካከላቸዉ የቀደመ ግንኙነት እንደነበራቸዉ በመረጋገጡ ከዚህ አኳያ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተአማኒነት የሌለዉ ከመሆኑም በተጨማሪ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 ስር ከተዘረዘሩት መቃወሚያዎች ስር የሚካተት አለመሆኑን፤እንዲሁም መከላከያ እንዳላቸዉ በመግለጽ መልስ እንዲሰጡ እንዲፈቀድላቸዉ ባቀረቡት ማስፈቀጃ ላይ ቼኮቹን ለተጠሪ የሠጡት ወንድማቸዉ ከአቶ ቢነጋ ጉዕሽ ጋር የፔትሮሊየም ምርቶች ለማከፋፈል ከተጠሪ ጋር በተዋዋሉት ዉል መነሻነት ላልተከፈለ ክፍያ የተጠየቀ ክፍያ እንደሆነ በመግለጽ መልሳቸዉን እንዲያቀርቡ ካስፈቀዱ በኋላ ባቀረቡት መከላከያ መልስ ላይ ደግሞ ለክሱ መነሻ የሆኑትን ቼኮች ለተጠሪ የሰጡት ራሳቸዉ ከተጠሪ ጋር በቃል ባደረጉት ንግግር የፔትሮሊየም ምርቶች የማከፋፈል ስምምነት እስከሚፈጸም ለቅድሚያ ክፍያ ዋስትናነት ነዉ በማለት መልስ መስጠታቸዉ ክርክራቸዉ እርስ በእርሱ የሚቃረን መከራከሪያ መሆኑን ያሳያል እንዲሁም የተጠሪ ምስክሮች በግራ

ቀኝ መካከል ዉል መኖር አለመኖሩን እንደማያዉቁ መመስከራቸዉ በሁለቱም መካከል ዉል የለም ብሎ ለመደምደም አያስችልም የሚሉትን ምክንያቶች በመዘርዘር አመልካች ክስ የቀረበበትን ብር 12,125,300.84(አሥራ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ ሦስት መቶ ብር ከሰማንያ አራት ሳንቲም) ከቀን 03/09/2008 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 187796 ላይ በቀን 13/06/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡አመልካች በቀን 22/11/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በዉሳኔዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አመልካች ለክሱ መነሻ የሆኑትን ቀንና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈባቸዉን ቼኮች ለተጠሪ የሰጠሁት ከተጠሪ ለምረከበዉ ነዳጅና ቅባት አከፋፈል ለዋስትና እንዲሆን በቃል በተነጋገርነዉ መነሻ ቢሆንም ዉል ባለመፈጸማችን የተረከብኩት ምንም አይነት ምርት አልነበረም፡፡ በሁለቱም ባዶ ቼኮች ላይ ቀንና የገንዘብ መጠኑን አመልካች አለመጻፌንና የሞላዉ ተጠሪ መሆኑን ተጠሪ አምኖ እያለ ቼኮቹን አመልካች ሰጥቷል በማለት ከተጠሪ እኔም ሆንኩ ወንድሜ የተረከብነዉ ምርት መኖሩ ሳይረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መስጠቱ ስህተት ነዉ፡፡በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 መሰረት በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብና የመክፈያዉ ቀን ከአመልካች እዉቅና እና ፈቃድ ዉጭ የተጻፈ በመሆኑ ለክሱ መነሻ የሆኑት እንደቼክ የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡የሥር ፍርድ ቤት ቀንና የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ቼክ አመልካችን ያስገድደዋል ወይ?ተጠሪስ በቼኩ ላይ እነዚህን ነጥቦች ከአመልካች እዉቅና ዉጭ ራሱ ሞልቶ ክፍያ መጠየቅ ይችላልን?እንዲሁም ከዚህ ቀደም አመልካች ለተጠሪ የሠጠዉ አንድ ባዶ ቼክ ለክሱ መነሻ ከሆኑ ቼኮች ጋር ምን ግንኙነት አላቸዉ?በባዶ ቼኮች ላይ ተጠሪ የፈለገዉን የገንዘብ መጠን ጽፎ ቢጠይቅ ተጠሪ የጻፈዉን ሁሉ አመልካች ለመክፈል ይገደዳልን?የሚሉ ጭብጦችን ይዞ መርምሮ መወሰን ሲገባዉ ተገቢ ጭብጦች ሳይዝና ክርክሩን በአግባቡ ሳይመራ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች በአግባቡ ሳይመረምር ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ተጠሪ በነዳጅ ኩባንያዎችና በነዳጅ ገዥዎች መካከል በቼክ ላይ የገንዘብ መጠን ሳይጻፍ (Blank Cheque) የሚሰጥበት አሰራር በዓለም አቀፍም ሆነ በኢትዮጵያ የተለመደ አሰራር ነዉ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ አመልካች የነዳጅ ምርት መዉሰዴን ካለማስረዳቱም በላይ በቀን 29/06/2011 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታዉ ተጠሪ ክስ የመሰረተበትን ገንዘብ የጠየቀዉ የአመልካች ወንድም አቶ ቢነጋ ጉዑሽ ለወሰደዉ ምርት ክፍያ እንደሆነ ያረጋገጠዉን ታልፎ አመልካችን በማይመለከተኝ ጉዳይ ባለእዳ የሚያደርገኝ ዉሳኔ መስጠቱ ስህተት ነዉ፡፡በቼኮቹ ላይ የፈለገዉን ገንዘብ መጠን በፈለገዉ ቀን እንዲከፈለዉ የጻፈዉ ራሱ ተጠሪ በመሆኑ አመልካች ለራሴም ሆንኩ ለወንድሜ እዳ ለመክፈል የምገደድበትን የዉል ወይም የሕግ ምክንያት ተጠሪ በክርክሩና በማስረጃ እንዲያስረዳ ሳያደረግ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 መሰረት መቃወሚያ በማቅረብ መከራከር የሚቻለዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና

828 መስፈርት መሰረት የተሟላ ቼክ በተሰጠ ጊዜ ሆኖ እያለ ቼኮቹ ላይ የተጻፈዉን ገንዘብና ቀን እኔ አልጻፍኩም ብዬ ያነሳሁትን ክርክር ባላገናዘበ መልኩ ለድንጋጌዎቹ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት የደረሰበት ድምዳሜ ነዉ፡፡በተጨማሪም አመልካች በቼክ ክፍያ ለመፈጸም ትእዛዝ ሰጥተሃል ሊባል የሚገባዉ በቼኮቹ ላይ የገንዘብ መጠን እና ቀን በመጻፍ ትእዛዝ ስሰጥ እንጂ የቼኩ አምጪ ሲጽፍባቸዉ አይደለም፡፡በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827(ሀ እና መ) እና 828 መሰረት ለክፍያዉ ተጠያቂ የሆነዉ ቼክ አዉጪ በቼኩ ላይ የገንዘብ መጠንና ቀን ጽፎ ፈርሞ ካልሰጠ እንደቼክ ስለማይቆጠር የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተጠሪ በክሱ በተጠቀሱት ቼኮች መነሻ አመልካችን ክፍያ መጠየቅ አይችልም ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 መሰረት አስገዳጅ የሆነ ክፍያ ሊፈጸምበት የሚችል ቼክ ለተጠሪ መስጠት አለመስጠታቸዉ ተጣርቶ መወሰን አለመወሰኑ? በአከራካሪዎቹ ቼኮች መሟላት ያለባቸዉ ፎርማሊቲዎች በአመልካች ተሟልተዋል ወይስ አልተሟሉም ?አመልካች ሰጡ በተባሉት ባዶ ቼኮቾ በተጠሪ የገንዘብ መጠን እንዴት እንደተሞላ ከመሰረታዊ የማስረጃ ሕግ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች አጣርተዉ መወሰን አለመወሰናቸዉን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 25/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ መልስ የሰጠ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 ላይ ቼክ እንደ ቼክ ለመቆጠር በቼኩ ላይ የተጠቀሰዉን ገንዘብና የመክፈያዉ ቀን በቼክ አዉጪ መጻፍ አለበት በሚል አልተደነገገም፡፡በቼኩ ላይ ቀንና የገንዘቡ መጠን በቼክ አዉጪ አለመሞላቱ ወይም በቼኩ ተካፋይ በሆነ ሰዉ መሞላቱ በአመልካች ለተጠሪ የተሰጠዉ ሰነድ ቼክ መሆኑን ቀሪ አያደርገዉም፡፡የገንዘብ መጠንና ቀን በቼክ ላይ መጻፍ ያለበት በቼኩ አዉጪ ብቻ ነዉ ብሎ የሚያስገድድ ሕግ የለም፡፡እንዲህ አይነት የሕግ ግዴታ ባለመኖሩም ባንኮች ለሚቀርብላቸዉ የቼክ ክፍያ ጥቄያ ቼኩ ላይ የተጠቀሰዉ ገንዘብ እና ቀን በቼክ አዉጪዉ በእርግጥም መጻፉን የማረጋገጥ ልማድም ሆነ አሰራር የለም፡፡ ነዳጅና የነዳጅ ዉጤቶችን በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማሩ እንደ አመልካች ያሉ ነጋዴዎች በሙሉ በሚባል ደረጃ ተጠሪን ከመሰሉ ነዳጅና የነዳጅ ዉጤቶችን ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ምርቶቹን በዱቤ ስለሚወስዱ ተጠሪን የመሰሉ ነጋዴዎች በዱቤ ለሚሰጡት ምርት ክፍያቸዉን በቀላሉ መሰብሰብ ይችሉ ዘንድ ቀን እና የገንዘብ መጠን ያለተጻፈባቸዉን ቼኮች (Blank Cheque) በመቀበል ሥራዉ እንደሚሰራ በስፋት የተለመደና የታወቀ አሰራር ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ይህንን የተለመደ የንግድ ሥራ ተግባር እና ሕጉን በሚጠብቅና በማያፈርስ መልኩ የሰጡት ዉሳኔ ስለሆነ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረዉ ግንኙነት አመልካች የሰጠዉ ቀን እና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈበት ቼክ- ቼክን መሆኑ የሚያረጋግጠዉ ሌላኛዉ ጉዳይ የገንዘብ መጠንና ቼኩ የተጻፈበትን ቀን ሳይጠቅስ ቁጥሩ ID3905671 የሆነ ቼክ አመልካች ለተጠሪ በመስጠቱ ብር 1,544,941.38 የሆነ ገንዘብ እና ቀን ተጠሪ ቼኩ ላይ ጽፎ ይህንኑ

ቼክ በመመነዘር ክፍያዉን ቼኩን መንዝሮ መቀበሉ ተረጋግጧል፡፡ይህም በቼክ ላይ የገንዘብ መጠንና ቀን በተጠሪ እየተጻፈ በቼክ ክፍያ መፈጸሙ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የቆየ የንግድ ሥራ ግንኙነት በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካች በዱቤ ለወሰዱት የነዳጅና የነዳጅ ዉጤቶች ምርት በተጠቀሰዉ መልክ ክፍያ ሲፈጽሙ ቆይተዉ አሁን ለተጠሪ የሰጡትን ቀን እና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈበት ስለሆነ እንደ ቼክ ሊቆጠር አይገባም በማለት ከቅን ልቦና ዉጪ በሆነ መንገድ ያቀረቡት ክርክር ነዉ፡፡በስር ፍርድ ቤት የተያዘዉ ጭብጥ አመልካች ለክሱ ከሰጡት መልስ አንጻር ተገቢ በመሆኑና አመልካች መያዝ ነበረበት ያሉት ጭብጦች ተይዘዉ እንኳን ቢሆን በክርክሩ ዉጤት ላይ የሚያመጣዉ ለዉጥ ባለመኖሩ በዚህም ረገድ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የቀረቡ ማስረጃዎችን ሰምቶና መርምሮ የመመዘን ሥልጣኑን ተጠቅሞ የሰጠዉ ዉሳኔ ሆኖ እያለ የትኛዉ ማስረጃ ሳይመረመር እንደቀረ እንኳን ሳይገልጹ ያቀረቡት መከራከሪያ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠዉ አይገባም በማለት መልሱን በመስጠት ተከራክሯል፡፡አመልካችም በቀን 09/04/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ማስቀረቢያ ነጥብ ከግምት በማስገባት የገንዘብ መጠኑ እና ቀን ሳይጻፍበት በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ የተሰጠ ቼክ (Blank Cheque) የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት እና ከዚህ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞበት ነገር ግን የሚከፈለዉ ገንዘብ መጠን እና ቀን ሳይጻፍበት ለአምጪዉ የተሰጠ ቼክ በአገራችን ሕግ ያለዉን ቦታና የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት ከማየታችን በፊት እንዲህ አይነት ቼክ ምንነት መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል ፡፡ እንዲህ አይነት ቼክ በዘርፉ በእንግሊዝኛ መጠሪያዉ "Blank Cheque" ተብሎ የሚታወቅ ነዉ፡፡ በታዋቂዉ ብላክስ ሎዉ መዝገበ ቃላት ይህ አይነት ቼክ(Blank Check):- is a check signed by the drawer but left blank as to the payee or the amount, or both.( Black's Law Dictionary (8th ed. 2004) P. 711) የሚል ፍቺ  የተሰጠዉ ሲሆን በሌላ መዝገበ ቃላት ላይም በተመሳሳይ Blank Cheque is a cheque that has been signed but does not yet have the amount of money written on it.(Cambridge Dictionary) የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ይህም አዉጪዉ በቼኩ ላይ ፈርሞበት ነገር ግን በቼኩ ላይ በተለይም የሚከፈለዉን ገንዘብ መጠን ሳይጽፍበት ለቼክ አምጪዉ የሚሰጠዉ ቼክ አይነት እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በንግድ ሥራ ዘርፍ ቀን እና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈበት ቼክ (Blank Cheque) በቼክ አዉጪዉ (drawer) ተፈርሞበት ለቼክ አምጪ (bearer) የሚሰጥበት አሰራር በተለይም በሚተማመኑ የንግድ ዘርፍ ሰዎች መካከል የተለመደ አሰራር እንደሆነ በዘርፉ የተጻፉ የሕግ ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ በእኛም አገር እንዲህ አይነት ቼክ (Blank Cheque) የመጠቀሙ

ልማድ በሚተማመኑ ነጋዴዎች መካከል የሚሰተዋል ወይም በቼክ አዉጪዉና አምጪ መካከል ባለ መተማመን ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም የክፍያ አፈጻጸም ልማድ እንዳለ የንግዱ ዘርፍ ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞበት ነገር ግን የሚከፈለዉ ገንዘብ መጠን እና ቀን ሳይጻፍበት ለአምጪዉ የተሰጠ ቼክ በአገራችን ሕግ ያለዉን ቦታና የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት መርምረናል፡፡ በ1952 ዓ/ም በወጣዉ የንግድ ሕግ አራተኛ መጽሐፍ ስለሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና የባንክ ሥራ ሕግ በሚል አብይ ርእስ ስር ባሉ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና በተለይ ደግሞ ስለቼክ በተደነገጉት የሕጉ አንቀጽ 827 እና ተከታዮች ስር ቼክ በሁለት ሰዎች መካከል የክፍያ ስምምነት መኖሩን የሚያሳይ የሚተላለፍ የንግድ ወረቀት (Commercial Negotiable Instrument) እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ድንጋጌዎች ያሉ ቢሆንም በሕጉ ቀን እና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈበት ነገር ግን በአዉጪዉ ስለተፈረመበት ቼክ (Blank Cheque) በግልጽ ተዘርዝሮ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ይህ ማለት ግን እንዲህ አይነት ቼክ በሕጉ ምንም ቦታ የለዉም ወይም ሕጉ በእንዲህ አይነት ቼክ ለሚፈጸም ክፍያ ሕጋዊ ዉጤት አይሰጠዉም ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለትና ሕጉንና በንግድ ሥራ ዘርፉ የክፍያ አፈጻጸም ለማሳለጥ የካበተዉን ልማድ ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በቼክ ላይ የሚጻፉ አስፈላጊ መግለጫዎች ናቸዉ ተብለዉ በንግድ ሕግ አንቀጽ 827 ከፊደል ሀ እስከ ሠ ባሉት ንኡሳን አናቅጽ የተጠቀሱ መግለጫዎች(Contents)፡- ሀ) የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትእዛዝ፤ ለ) መክፈል የሚገባዉ ከፋይ ስም፤ ሐ) የሚከፈልበት ቦታ፤ መ) ቼኩ የወጣበት ቦታና ጊዜ እና ሠ) ቼኩን ያወጣዉ ሰዉ ፊርማ የሚሉ ናቸዉ፡፡በዚሁ ሕግ አንቀጽ 828 ስር ባለዉ የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ እንደተመለከተዉ ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ እንደማይቆጠር ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ ላይ "ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ አይቆጠርም" የሚለዉ አገላለጽ ላይ ላዩን ሲታይ ግልጽ ቢመስልም አገላለጹ የሚያገለግለዉ መግለጫዎቹ ያልተሟላ ቼክ በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ በሚሰጥበት ጊዜ ነዉ ወይስ ቼኩ ለክፍያ ሲቀርብ ነዉ የሚል ጥያቄ በማንሳት ሲታይ ግን ግልጽነት የሚጎድለዉ (አሻሚ) ስለሚሆን ትርጉም የሚያሻ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

በመርህ ደረጃ እነዚህ በሕጉ አንቀጽ 827 ስር በቼክ ላይ መጻፍ ያለባቸዉ ናቸዉ ተብለዉ የተዘረዘሩ መግለጫዎች በቼክ አዉጪዉ መጻፍ እንዳለባቸዉ የሚጠበቅ ቢሆንም መግለጫዎቹ አንድ በአንድ ሲታዩ ግን የቼክ አዉጪዉን ፊርማ ከሚመለከተዉ መስፈርት በስተቀር ቀሪዎቹ መግለጫዎች በቼክ አዉጪዉ ስምምነት ወይም ፈቃድ በቼክ አምጪዉ ወይም በሌላ ሰዉ ሊጻፉ(ሊሞሉ) የሚችሉ ናቸዉ፡፡ ይህም በአንቀጽ 827 ስር በዝርዝር ከተጠቀሱ መግለጫዎች (Contents) መካከል አንዱ ወይም የተወሰኑት በአንድ ቼክ ላይ ሳይሞላ ቼኩ ለባንክ ለክፍያ ቢቀርብ ሰነዱ እንደ ቼክ ተቆጥሮ በባንክ

አይመነዘርም ወይም ክፍያ አይፈጸምም ከሚል መንፈስና አላማ የተደነገገ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሌላ አገላለጽ በድንጋጌዉ ከተጠቀሱት መግለጫዎች(ይዘቶች) በተለይም በቼኩ ላይ መጻፍ ያለበት ቀን እና የገንዘብ መጠን ቼኩ ከቼክ አዉጪዉ ሲወጣ ባይሞላም(በቼክ አዉጪዉ ባይጻፍም) በቼኩ ላይ ሌሎች መግለጫዎች በቼክ አዉጪዉ ተሞልተዉና ተፈርሞ ሰነዱ ለቼክ አምጪዉ ከተሰጠ በኋላ በአምጪዉ የቼኩን መክፈያ ቀን እና የሚከፈለዉን ገንዘብ መጠን ሞልቶ ሰነዱን ለባንክ ባቀረበ ጊዜ ሰነዱ እንደ ቼክ አይቆጠርም የሚል እንድምታ ያለዉ አይደለም፡፡ይልቁንም በአንድ የቼክ ሰነድ ላይ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 ስር የተደነገጉ መግለጫዎች ተሞልቶበትና በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞበት ለባንክ ከቀረበ ባንኩ ቀኑንና የገንዘብ መጠኑን ማን ጻፈዉ የሚለዉን ማረጋገጥ ሳይጠበቅበት በቼኩ ላይ ያለዉ ፊርማ በቼክ አዉጪዉ መፈረሙን ባለዉ አሰራር መሰረት አመሳክሮ አረጋግጦ በቼኩ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ መጠን ከቼክ አዉጪዉ ተንቀሳቃሽ(የቼክ) ሂሳብ ላይ ቀንሶ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 829፣ 830 እና 840 ላይ በተደነገገዉ እና በድንጋጌዎቹ በስተጀርባ ባለዉ አስተሳሰብ መሰረት ከአምጪዉ የቼክ ሰነድ ተቀብሎ ክፍያ የሚፈጽመዉ ባንክ ወይም በሕግ እንደ ባንክ የሚቆጠር የፋይናንስ ተቋም በመሆኑ ቼኩ ለባንክ ሲቀርብ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 ስር የተጠቀሱትን መግለጫዎች የሚያሟላ እስከሆነ ድረስ ባንኩ/ተቋሙ ቼኩን ተቀብሎ ከቼክ አዉጪዉ ሂሳብ ላይ ቀንሶ በቼኩ የተመለከተዉን ገንዘብ ለአምጪዉ ለመክፈል የሕግ ግዴታ ስላለበት ነዉ፡፡ ስለሆነም አንድ ቼክ እንደሚተላለፍ የንግድ ወረቀት (Commercial Negotiable Instrument) ወይም እንደሚተላለፍ የክፍያ ሰነድ የሚቆጠረዉም ይህንኑ በመተማመን በመሆኑ በአንቀጽ 827 እና 828 ስር "ከእነዚህ መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ አይቆጠርም" የሚለዉ አገላለጽ የቼክን ልዩ ባህርይና በዚህ ሰነድ የሚፈጸመዉን የክፍያ ሥርዓት በሚያሳልጥ መልኩ በቼኩ ክፍያ እንዲፈጸም በመጠየቅ ለባንክ ሲቀርብ ተፈጻሚ የሚሆን እንደሆነ ተቆጥሮ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ነዉ፡፡ይህም የቼክ ሰነድ በአዉጪዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ በተሰጠ ጊዜ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 አንጻር የተሟላ ባይሆንም ለከፋዩ ባንክ በቀረበ ጊዜ ተሟልቶ ከቀረበ ሕጉ ለእንዲህ አይነት ቼክ (Blank Cheque) ሕጋዊ ዉጤት ይሰጠዋል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ነዉ፡፡

በተጨማሪም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 732 ስር እንደተመለከተዉ ቼክ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ዉስጥ ጥሬ ገንዘብን ተክቶ ግብይትን እንዲያሳልጥ የተፈጠረ የሚተለለፍ የንግድ ወረቀት (Commercial Negotiable Instrument) እንደመሆኑ ቼክ አዉጪ የተፈረመበትን የቼክ ጥራዝ/ወረቀት በጥንቃቄ መያዝ ፣ገንዘቡን በቼክ ሊያዝበት መብት እንዳለዉ እና ቼኩን ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ቼኩ ለክፍያ እስከሚቀርብበት ቀን ድረስ ከከፋዩ ባንክ ዘንድ የገንዘብ ሥንቅ እንዳለዉ ማረጋገጥና ሰነዱን ከታለመለት ዓላማ አንጻር መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ይህንን ባለማድረግ ለሚመጣበት ኃላፊነት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 840 በመጀመሪያዉ ኃይለ ቃል ላይ እንደተመለከተዉ ቼክ አዉጪዉ በቼኩ ላይ ስለተጻፈዉ ገንዘብ አከፋፈል ዋስ እንደሆን ሕግ ግዴታ ይጥልበታል፡፡ ስለሆነም አንድ የቼክ ሰነድ በቼክ አዉጪዉ ተፈርሞበት ነገር

ግን የሚከፈልበት ቀን እና የገንዘብ መጠን በቼክ አዉጪዉ ሳይጻፍ ለቼክ አምጪ ከተሰጠና በዚህ የቼክ ሰነድ (Blank Cheque) ላይ አምጪዉ የገንዘብ መጠን እና የሚከፈልበትን ቀን ጽፎበት ለባንክ ካቀረበ ቼኩ በቼክ አዉጪዉ ተሞልቶ እንደተሰጠ ቼክ ተቆጥሮ ሊመነዘር የሚገባ እንጂ በቼኩ ላይ ያለዉ ቀን እና የገንዘብ መጠን በአምጪዉ በመጻፉ ብቻ ሰነዱ የቼክነት ባህርይዉንና ሕጋዊ ዉጤቱን ሊያጣ አይችልም፡፡

እንዲሁም ቼክ አዉጪ በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ለአምጪዉ እንዲከፈል ስለመስማማቱ/ስለማዘዙ ማረጋገጫ የሚሆነዉ ቼክ አዉጪዉ ቼኩ ላይ ፊርማዉን አኑሮ ቼኩን ለአምጪዉ መስጠቱ ነዉ፡፡ በመሆኑም ቼክ አዉጪዉ በቼኩ ላይ ፊርማዉን ብቻ ጽፎ በቼኩ የሚከፈለዉን የገንዘብ መጠን እና ቀን ሳይጽፍ ለአምጭዉ መስጠቱ ከተረጋገጠ ሌላ በሕጉ የተፈቀደ ተቃራኒ መከራከሪያ በማስረጃ ተደግፎ እስካልቀረበ ድረስ ይህንን ያደረገዉ ከቼክ አምጪዉ ጋር ያለዉን መተማመን መሰረት አድርጎ በቼኩ ላይ የሚጻፈዉን ገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ቀን አምጪዉ ጽፎ ለባንክ አቅርቦ ክፍያ እንዲጠይቅ ቼክ አዉጪዉ የመዋዋል ነፃነቱን (Freedom of Contract) ተጠቅሞ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡

በሌላ በኩል ቼክ አዉጪዉ መከራከሪያ አድርጎ ማንሳት የሚችላቸዉ በሕግ የተፈቀዱ መቃወሚያዎች ምንድን ናቸዉ የሚለዉን መመርመር ለያዝነዉ ጉዳይ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ተደጋግሞ እንደተገለጸዉ ቼክ እንደ ገንዘብ ወደተለያዩ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ የሚችል ባህርይ ስላለዉ የቼክ አከፋፈል ላይ በሕጉ በግልጽ ተለይተዉ ከተመለከቱት በስተቀር ማንኛዉንም መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡በዚህ አግባብ በመከራከሪያነት ሊነሱ የሚችሉ መቃወሚያዎች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 ፣841 እና 850 ስር የተደነገጉት ናቸዉ፡፡ በጥቅሉ በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት መቃወሚያ ሆነዉ ሊነሱ የሚችሉ መከራከሪያዎች ሁለት ገጽታዎች ያላቸዉ ሆነዉ አንደኛዉ ሰነዱ ከሚመለከተቻዉ ሰዎች መካከል(ጋር) ያለዉን የግል ግንኙነትን መነሻ ያደረገ (Defense in Personal Relation) ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ማንኛዉም በቼክ የተከሰሰ ሰዉ ሊያነሳቸዉ የሚችልና የቼኩን ሰነድ መሰረት ያደረገና በዚህ የሕግ ዘርፍ Real Defense ተብሎ የሚታወቅ ነዉ፡፡ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 717 ፣841 እና 850 ስር በመቃወሚያነት ሊነሱ የሚችሉ መከራከሪያዎች፡- በቼክ አዉጪዉ(እዳ ከፋዩ) እና ከአምጪዉ (ሰነዱን በያዘዉ ሰዉ) መካከል ያለዉን የግል ግንኙነት መሰረት ያደረገ፣በሰነዱ አጻጻፍ ፎርም፣በሰነዱ ላይ በተጻፉ ቃሎች ላይ በተደረገ ለዉጥ (Alteration)፣ፊርማዉ ተመሳስሎ የተፈረመ መሆኑን የሚመለከት፣ ቼኩ ሲወጣ ቼክ አዉጪዉ ችሎታ ወይም የዉክልና ሥልጣን የሌለዉ መሆን፣ ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች አለመሟላት፣በቼክ አምጪዉ ቼኩ የተገኘዉ በክፉ ልቦና እዳ ከፋዩን ለመጉዳት በማሰብ ወይም ከባድ ጥፋት በመፈጸም መሆኑን የሚመለከቱ ናቸዉ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 841 ስር የተደነገገዉን ለይተን ያየን እንደሆነ ቼኩ በሚወጣበት ጊዜ ጉድለት ቢኖርበት እንኳን (incomplete when issued) ቼክ አዉጪዉ ቼኩ በቼክ አምጪዉ የተገኘዉ በክፉ ልቦና መሆኑን ወይም አምጪዉ ቼኩን ከባድ ጥፋት በመፈጸም ያገኘዉ መሆኑን በማስረዳት ካላረጋገጠ በስተቀር ስለቼኩ አሞላል የተደረጉ ስምምነቶችን በሚቃረን መልኩ የተሞላ ቼክ ቢሆንም እንኳን ቼክ አዉጪዉ በስምምነቶቹ መሰረት አለመፈጸሙን በአምጪዉ ላይ መቃወሚያ ሊያደርግ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአንድ በኩል የንግድ ሕጉ በአንቀጽ 827 ላይ የተመለከቱ መግለጫዎች ተሟልቶ ያልተገለጸ ቼክ ተፈርሞ ለአምጪዉ የሚስጥበትን አግባብ በመደንገግ ለእንዲህ አይነት ቼክ (Blank Cheque) እዉቅና መስጠቱን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ አግባብ ደግሞ በቼክ ላይ የሚጻፉ መግለጫዎች ካለመሟላት ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ መቃወሚያዎች በድንጋጌዉ ተለይተዉ የተገለጹት እንጂ ማናቸዉም መቃወሚያዎች እንዳልሆኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

እንዲሁም ቼክ በዋስትናነት አይሰጥም በሚል በሕግ የተደነገገ ክልከላ ባለመኖሩ በመርህ ደረጃ ቼክ ለዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡ሆኖም በሰ/መ/ቁጥር 166392 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ቼኩ የተሰጠዉ ለዋስትና አላማ እንደሆነ ተገልጾ በጽሁፍ የዋስትና ዉል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ቼክ ለዋስትና አላማ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ ዕዳ ከፋዩ ወይም ቼክ አዉጪዉ በሕጉ የተፈቀዱትን መቃወሚያዎች በማንሳትና ተገቢዉን ማስረጃዎች በማቅረብ ማስረዳት የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አምጪዉ ቼኩን ለባንክ አቅርቦ ባንኩ በቼክ አዉጪዉ ሂሳብ ዉስጥ በቂ ስንቅ አለመኖሩን ምክንያት በማድረግ ወይም በሌላ መሰል ምክንያት በቼኩ የተመለከተዉን ገንዘብ ለአምጪዉ መክፈል እንደማይችል የሚገልጽ የእንቢታ ማስታወቂያ ለመስጠት ይገደዳል፡፡አምጭዉም የእንቢታ ማስታወቂያዉን በማያያዝ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆነዉን ሁኔታ በማሟላት በቼኩ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ከወለድና አግባብነት ካላቸዉ ወጪዎች ጋር እንዲከፈለዉ ዳኝነት በመጠየቅ በአዉጪዉ ላይ ክስ መመስረት እንደሚችልና ጉዳዩን የሚዳኘዉ ፍርድ ቤትም በዚሁ አግባብ ሊወስን እንደሚችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 716/1 እና 873 ስር ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር የተመለከተዉን መሰረት በማድረግ የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች በቼኮቹ የሚከፈለዉን ገንዘብ መጠን እና ቀን በቼኮቹ ላይ ራሳቸዉ ባይጽፉም ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቼኮች ፈርመዉ ለተጠሪ መስጠታቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በቼኮቹ ላይ የተጻፈዉን ቀን እና የገንዘብ መጠን የሞላዉ ተጠሪ መሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ አከራካሪዉና በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዳኝነት የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ያስፈለገዉ ነጥብ የገንዘብ መጠኑ እና ቀን ሳይጻፍበት በቼክ አዉጭዉ ተፈርሞ ለአምጪዉ የተሰጠ ቼክ (Blank Cheque)

የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ከላይ በዝርዝር እንደተዳሰሰዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 ስር ከተዘረዘሩት መግለጫዎች አንዱ እንኳን የሌለበት ሰነድ እንደ ቼክ አይቆጠርም በሚል በአንቀጽ 828 የተደነገገዉ ተፈጻሚ መሆን ያለበት የቼክን ልዩ ባህርይና በቼክ የሚፈጸመዉን የክፍያ ሥርዓት በሚያሳልጥ መልኩ በቼኩ ክፍያ እንዲፈጸም በመጠየቅ የቼኩን ሰነድ ተቀብሎ ክፍያ ለሚፈጽመዉ ባንክ ቼኩ በሚቀርብበት ጊዜ ነዉ፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሁለቱም ቼኮች በአመልካች ተፈርመዉ ለተጠሪ በተሰጡ ጊዜ ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 አንጻር ቀንና የገንዘብ መጠናቸዉ ባለመጻፉ የተሟሉ ባለመሆናቸዉ እንደ Blank Cheque የሚቆጠሩ ቢሆኑም ተጠሪ ቀንና የገንዘብ መጠን ሞልቶ ለከፋዩ ባንክ ባቀረበ ጊዜ ተሟልተዉ ቀርበዋል፡፡ክፍያ ያልተፈጸመባቸዉም በአመልካች ተንቀሳቃሽ ሂሳብ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ ምክንያት እንደሆነ ስለተረጋገጠ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827 እና 828 ያስቀመጣቸዉን አንድን ሰነድ ቼክ የሚያሰኙ መገለጫዎችን የሚያሟሉ ወይም እንደ ቼክ የሚቆጠሩ እና ሕጋዊ ዉጤት ያላቸዉ ናቸዉ፡፡

እንዲሁም የንግድ ሕጉ አንቀጽ 827ም ሆነ 828 በቼኩ ላይ የሚጻፈዉን ቀን እና በቼኩ የሚከፈለዉን የገንዘብ መጠን የግድ ቼክ አዉጪዉ ወይም ወኪሉ ብቻ መጻፍ አለበት የሚል አቋም የለዉም፡፡ በተጨማሪም የስር ፍርድ ቤት በማስረጃ እንዳረጋገጠዉ ለዚህ ክስ መነሻ የሆኑ ቼኮችን ለተጠሪ ከመስጠታቸዉ በፊት ግራ ቀኝ በመካከላቸዉ አስቀድመዉ የመሰረቱትን መተማመን መሰረት በማድረግ አመልካች ቀንና የገንዘብ መጠን ያልተጻፈበትን ቼክ ፊርማቸዉን ብቻ አኑረዉ ለተጠሪ ሰጥተዉ ተጠሪም ቀንና የገንዘብ መጠን ሞልቶ ቼኩን ለባንክ አቅርቦ ከአመልካች ሂሳብ ላይ በቼኩ ላይ የተጻፈዉን ገንዘብ እንዲከፈልዉ አድርጎ መቀበሉ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ይህም በግራ ቀኙ መካከል በመተማመን ላይ የተመሰረተ የቀደመ ግንኙነት መኖሩን እና በዚህም መነሻ አመልካች ለተጠሪ ክፍያ ለመፈጸም ተመሳሳይ ቼክ ፈርመዉ ለመስጠት ያስቻለ የሥራ ግንኙነት እንደነበራቸዉ የሚያሳይ ነዉ፡፡ እንዲሁም አመልካች የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቼኮች ፈርመዉ ነገር ግን ቀንና የሚከፈለዉን የገንዘብ መጠን ሳይጽፉ ለተጠሪ መስጠታቸዉን ፈቅደዉ ያደረጉት መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በሁለቱም ቼኮች ላይ ያለዉ ፊርማ የራሳቸዉ ፊርማ እንዳልሆነ በመግለጽ አመልካች አልካዱም፡፡በቼኮቹ ላይ የተጻፈዉ ቀንና የገንዘብ መጠን በተጠሪ መጻፉ ያልተካደ በመሆኑ በፎረንሲክ ማስመርመሩ ፋይዳ ስለማይኖረዉ ከዚህ አኳያ አመልካች ይህ የቼኮቹ ይዘት በፎሬንሲክ እንዲመረመር ያቀረቡትን ጥያቄ ፍርድ ቤቱ ባለመቀበሉ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

በተጨማሪም አመልካች በአንድ በኩል ቼኮቹን ለተጠሪ የሰጡት ወንድማቸዉ ከተጠሪ ለወሰዱት የፔትሮሊየም ምርቶች ለዋስትና አላማ እንደሆነ ገልጸዉ ክሱን እንዲከላከሉ እንዲፈቀድላቸዉ ባቀረቡት ማመልከቻ አስፈቅደዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመከላከያ መልሳቸዉ ላይ ይህንን ምክንያት ቀይረዉ ራሳቸዉ ከተጠሪ የፔትሮሊየም ምርቶችን ወስደዉ ለማከፋፈል ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የቃል ንግግር

መነሻ ለቅድመ ክፍያ ዋስትና እንዲሆኑ ቼኮቹን ቢሰጡም ባደረጉት ንግግር መሰረት ዉል ባለመፈጸሙ የነዳጅ ምርቶችን ከተጠሪ ባለመረከባቸዉ ተጠሪ ከቅን ልቦና ዉጭ ቼኮቹ ላይ ቀንና የገንዘብ መጠን በመሙላት ክፍያ እንዲፈጽምለት በመጠየቅ ለባንክ እንዳቀረበ በመግለጽ ክርክር ማቅረባቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ግልባጭ ስለሚያሳይ ከዚህ አኳያ ያቀረቡት ክርክር እርስ በእርሱ የሚጣረስ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ክርክር ተአማኒነት የለዉም ማለቱም የሚነቀፍ አይደለም፡፡ይህ መከራከሪያቸዉም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 841 ስር በመቃወሚያነት ሊነሱ የሚችሉ መከራከሪያዎች ናቸዉ ተብለዉ ከተመለከቱት አንጻር ሲታይ ቼኮቹን ፈርመዉ ለተጠሪ ሲሰጡ ተጠሪ ቼኮቹን ያገኘዉ በክፉ ልቦና አመልካችን ለመጉዳት አስቦ ከባድ ጥፋት በመፈጸም እንደሆነ በመግለጽ ካለመከራከራቸዉም በተጨማሪ ይህንን የሚያሳይ ተገቢዉን ማስረጃ በማቅረብ ባለማስረዳታቸዉ ተጠሪ የገንዘብ መጠኑን የሞላዉ ስለቼኩ ቀን እና የገንዘብ መጠን አሞላል ያደረጉትን ስምምነት በሚቃረን አኳኋን ነዉ በሚል የሚያነሱት በሕጉ ተቀባይነት ያለዉ መከራከሪያ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቼኮች ለተጠሪ ፈርመዉ የሰጡት በመካከላቸዉ ባለዉ ስምምነት መነሻ የፔትሮሊየም ምርት ሲቀበሉ ለቅድሚያ ክፍያ ዋስትና እንዲሆን በሚል ነዉ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆኑ ቼኮችን ለተጠሪ ፈርመዉ የሰጡት ለቅድመ ክፍያ ዋስትና አላማ እንደሆነ የሚያሳይ በጽሁፍ የተደረገ የዋስትና ዉል በማስረጃነት አላቀረቡም፡፡በመሆኑም አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረቡትንም ክርክር በሰ/መ/ቁጥር 166392 ላይ በቀን 26/08/2012 ዓ/ም በተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ለክሱ መነሻ የሆኑ ቼኮችን ለዋስትና መስጠታቸዉን በማስረጃ ያላስረዱ በመሆኑ በዚህም ረገድ በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡የሥር ፍርድ ቤት ተገቢዉን ጭብጥ ሳይዝና ማስረጃ በአግባቡ ሳይመዝን እንደወሰነ በመግለጽ የቀረበ መከራከሪያም ቢሆን የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ የሰጠዉ ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸዉን የግራ ቀኙን ማስረጃዎች በመመዘን እንደሆነ የዉሳኔዉ ይዘት ስለሚያሳይ በዚህም ረገድ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 179745 ላይ በቀን 20/02/2012 ዓ/ም እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 187796 ላይ በቀን 13/06/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 173380

ጥቅምት 28 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ተጠሪ፡- ሐበሻ ሲሚንቶ አክሲዮን ማኀበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሽራንስ ዉል መጽናት ከሚጀምርበት ጊዜ እና ኢንሹራንስ ሰጪዉ መድን ከሚሆንበት አደጋ ጋር በተያያዘ የተደረገዉን ክርክር አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38532 ላይ በቀን 26/04/2010 ዓ/ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እና ይህንን ዉሳኔ በመቃወም የቀረበዉን ይግባኝ በመሰረዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 214193 ላይ በቀን 19/06/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ የቀረበ ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተደረገዉ ክርክርና በቀን 08/07/2011 ዓ/ም ተጽፎ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት ከዚህ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረዉ ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ ሲሆን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ ተጠሪ በስር በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 14/03/2009 ዓ/ም ጽፎ ባቀረበዉ ክስ ከአመልካች የመድን ሽፋን ለሁለት የአለት መቆፈሪያ ማሽኖች(Rock Drilling Ring) ላይ በጦርነት፣በብጥብጥ፣ በሕዝባዊ አመጽን ጨምሮ በሌሎች በመደበኛነት የሚሰጡ ሽፋን ለመስጠት የአሁን አመልካች በቀን 21/08/2007 ዓ/ም የዋጋ ማቅረቢያ ልኮ በቀን 22/11/2007 ዓ/ም የኢንሹራንስ ዉል ቢዋዋሉም በዋጋ ማቅረቢያዉ ላይ የተዘረዘረዉ የአደጋ አይነት በኢንሹራንስ ዉሉ ላይ ባለመካተቱ በቀን 05/04/2008ዓ/ም በተፈጸመ የማሻሻያ (የሽፋን ማስፊያ/Extension) ዉል በጦርነት፣ በአድማ፣ በአመጽ እና ሆን ተብሎ (በተንኮል) ሳቢያ ለሚደርስ ጉዳት የአሁን አመልካች የመድን ሽፋን ለመስጠት

እንደተስማማ እና የማራዘሚያ ዉሉ ስምምነት ተፈጻሚነት የሚጀምረዉ ከግንቦት 19 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ እንዲሆን መስማማታቸዉን በመግለጽ በፊንፊኔ ዙሪያ በነበረዉ ሕዝባዊ አመጽ ምክንያት የመድን ሽፋን ከተገባላቸዉ 2 መቆፈሪያ ማሽኖች በአንዱ ላይ በቀን 04/04/2008ዓ/ም ጉዳት ደርሶበት ጉዳቱ መድረሱን በማሳወቅ ጉዳት ለደረሰበት ማሽን መለዋወጫ ለመግዣት ብር 399,424.50 እንዲሁም ለእጅ ዋጋ ብር 31,289.00 በድምሩ ብር 430,713.70 እንዲከፈለዉ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ መስርቷል። የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጠዉ መልስ የመድን ሽፋን የሚሰጠዉ ያልታወቀ አደጋ የሚደርስ ከሆነ ካሳ ለመክፈል በመሆኑ የማራዘሚያ ዉል ከመደረጉ በፊት በቀን 04/04/2008 ዓ/ም ጉዳት ስለደረሰ ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ በተደረገ የመድን ዉል ካሳ ለመክፈል እንደማይገደድ፤ ዉል ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑና ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ በመሆኑ የዉል ማራዘሚያ የተደረገዉ ማራዘሚያ ከተደረገ በኋላ ጉዳት ቢደርስ ካሳ ለመስጠት መሆኑን፤ የአሁን ተጠሪ የማስፊያ ዉል ተፈርሞ እንዲሰጠዉ የጠየቀዉ በዋናዉ ዉል ማግለያዎች ፊደል "ቀ" ስር የተገለሉትን ስጋቶች ሆኖ አመልካች በስህተት በዋና ዉል ማግለያዎች ፊደል "ቸ" ስር ለተገለሉ ስጋቶች ሽፋን ስለሰጠና በሁለቱ መካከል ልዩነት ስላለ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሃሳብ ስምምነት የሌለበትና በስህተት የተቋቋመ ዉል በመሆኑ አመልካች ይህንን ቢያዉቅ ኖሮ ዉል ዉስጥ ሊገባ ስለማይችል ዉሉ ፈራሽ ስለሆነ ተከሳሽ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት፤በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ ከታህሳስ 4-6/2008 ዓ/ም ድረስ ተነስቶ የነበረዉና ጉዳት ያደረሰዉ ድርጊት የፖሊቲካ ተቃዉሞ አካል ስለሆነና ሽፋን የተሰጠዉ በመድን ገቢዉ ሠራተኞች የሚፈጠርን ብጥብጥ እንዲሁም በፋብሪካዉ አካባቢ ያለ ማህበረሰብ ክፍሎች ከፋብሪካዉ ጋር ተያይዞ የጥቅም ጥያቄ/ተቃዉሞ/ ለማቅረብና ጫና ለመፍጠር የሚፈጠር አመጽ ለማለት እንጂ ብዙ ሕዝብ ቁጥር የተሳተፈበትን ሕዝባዊ አመጽ/ተቃዉሞን(popular uprising) በመድን ሽፋኑ የሚሸፈን አይደለም የሚሉ መከራከሪያዎች እና የደረሰዉን ጉዳት ተጠሪ ካሳ እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት ድረስ ያሉትን ጉዳት በገለልተኛ ገማች ሳያስገምቱ ከአንድ ድርጅት ብቻ በመጠየቅ ያቀረቡት የተጋነነ ነዉ በሚል መከራከሩን ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ተረድተናል።

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኝ ክርክር በመ/ቁጥር 38532 ላይ በቀን 26/04/2010ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ግራ ቀኝ በቀን 05/04/2008 ዓ/ም የማርዘሚያ ዉል ያደረጉ ቢሆንም ከቀን 19/09/2007 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ እንዲሆን ስለተስማሙ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 659/1 ይህንነኑ ስለሚፈቅድ ከዚህ አኳያ የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለዉ፤የማራዘሚያ ዉል የተደረገዉ ዋናዉ ዉል ላይ በፕርፎርማዉ ላይ የተገለጸዉ በስህተት ሳይካተት በመቅረቱ በማካተት ለማሻሻል የተደረገ በመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ የመጀመሪያዉ ዉል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ሊሆን እንደሚገባ፤ ተጠሪ የዉል ማርዘሚያ የጠየቀዉ ቀድሞ በፕርፎርማ ላይ የተገለጸዉ በዋናዉ ዉል ላይ ሳይገለጽ በመቅረቱ ምክንያት ለማካተት ታሳቢ በመሆኑ ማራዘሚያ ተጠይቆ በተጠሪ በተሞላ ጥያቄ ላይ "ቀ" ተብሎ የጠሞላ ሆኖ በተራዘመዉ ሰነድ

ላይ በፊደል "ቸ" ላይ የተገለጸዉን ማግለያ በማሻሻል የተራዘመ ቢሆንም ይህም ከሀሳባቸዉ አንጻር ሲታይ የፊደል ስህተት ብቻ እንጂ መሠረታዊ ስህተት ካለመሆኑም በተጨማሪ በዚህ ስህተት ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስ ካለማድረጉም በተጨማሪ በዉሉ ላይ አመልካች ብቻዉን መፈረም የሚችልበት አሰራር ቢኖርም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1725/ለ፣1726 እና 1727(1 እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት የኢንሹራንስ ዉል በጽሁፍ ተደርጎ በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች መፈረም የሚገባዉ ዉል ሆኖ እያለ በአመልካች ብቻ መፈረሙ ስለተረጋገጠ በሕግ ፊት የሚጸና ዉል አይደለም በሚል በማስፊያ ዉሉ ላይ የተጠቀሱት ማግለያዎች የአሁኑን ተጠሪ(ከሳሽን) አያስገድዱም በሚል በአንድ በኩል ከወሰነ በኋላ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ይህንን የማስፊያ ዉል መሰረት በማድረግ ያቀረቡትን ክርክር በመቀበል የአሁን አመልካች በማስፊያ ዉሉ መሰረት በማሽኑ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የመለዋወጫ ዋጋ ከተለያዩ ድርጅቶች ማቅረብ አለመቻሉን ምክንያት በማድረግ ከደረሰዉ ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን ካሳ መወሰን አልተቻለም በማለት አመልካች ለተጠሪ ብር 400,000.00 ካሳ እንዲከፍል በርትእ መወሰኑን ከዉሳኔዉ ይዘት ተመልክተናል፡፡

ከላይ በተገለጸዉ መሠረት በተሰጠ የፍርድ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 214193 ላይ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በቀን 19/06/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዟል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ለተጠሪ የተሰጠዉ የመድን ሽፋን በአመጽ፣ በእርስ በእርስ ጦርነት፣ በአድማ፣በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ፣በወታደራዊ አመጽ የሚመጡትን ማንኛዉንም ፖለቲካዊ ይዘት ባላቸዉ ምክንያቶች የሚደርስ ጉዳት እንደማይሸፍን በዉሉ ማግለያ ፊደል "ቸ" እንደተመለከተ፤እንዲሁም በማስፊያ ዉሉ አንቀጽ 2/ለ ስር እንዲገለል የተደረገ ምክንያት መሆኑን፤ ከዚህ አንጻር የቀረበዉን ክርክር የስር ፍርድ ቤት ጭብጥ ይዞ ሳይመረምርና ዉሳኔ ሳይሰጥ ማለፉን፤ የስር ፍርድ ቤት በህዝባዊ አመጽ የሚደርስ አደጋ በፕርፎርማዉ ላይ ተካቶ እያለ በዋናዉ ዉል ላይ ሳይካተት በመቅረቱ ስህተቱን ለማረም የማስፊያ ዉሉ ስለተፈጸመ የማስፊያ ዉሉ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባዉ የመጀመሪያዉ ዉል ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነዉ ብሎ የወሰነዉ ፕርፎርማዉ የዉሉ አካል ባልሆነበትና ፕርፎርማ የሚሰጠዉ የመድን ሽፋን አይነትና የእያንዳንዱን ዋጋ ዝርዝር የሚገልጽ መግለጫ (offer) ብቻ መሆኑን ባለማገናዘብ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ፤ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ክርክር አንጻር የመድን ሽፋን ማስፊያዉ ዉል አመልካችና ተጠሪ መካከል የመጀመሪያዉ ዉል ሲቋቋም የተፈጠረዉን መሠረታዊ ስህተት ለማረም የተገባ ዉል ነዉ ብሎ ዉጤት እንዲኖረዉ ያደረገዉን ዉል በሌላ በኩል ከአመልካች ክርክር አንጻር ደግሞ የማስፊያ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1725/ለ፣ 1726 እና 1727(1 እና2) መሠረት ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ሊፈርሙበት ሲገባ በዉል ማስፊያዉ ላይ በዉል ማስፊያዉ ላይ ተጠሪ ስላልፈረሙበት በተጠሪ ላይ አስገዳጅነት የለዉም ሲል መወሰኑ አንድን የሕግ ነጥብ ለተጠሪ

ሲሆን የጸና የመድን ዉል ነዉ በማለት ለአመልካች ሲሆን ድግሞ የጸና አይደለም ሲል መወሰኑ ዉሉ በመድን ሰጪዉ ከተፈረመበት በቂ ነዉ ተብሎ በሰበር መ/ቁጥር 24703 እና 24704 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም ጭምር ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን፤ የመድን ዉሉ ማስፊያ ዉል ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ሲል የንግድ ሕጉን አንቀጽ 659/1ን ጠቅሶ መወሰኑ መሰረታዊ የአተረጓጎም ስህተት መሆኑን፤ አደጋ ከደረሰ በኋላ የደረሰዉን አደጋ ለመሸፈን የሚሰጥ የመድን ሽፋን ፖሊስ በሌለበት በተሠጠዉ ዉሳኔ እና ከካሳ አወሳሰን አኳያም በርትዕ መወሰኑ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 665 እና 677 ስር የተደነገገዉን የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ሰህተት ተፈጽሟል ተብሎ እንዲታረም በመጠየቅ አቤቱታዉን አቅርቧል።

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታ እና በስር ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ መርምሮ አመልካች በተጠሪ ንብረት ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ከዋናዉ የመደበኛ የመድን ሽፋን ዉልም ሆነ በማስፊያ ሽፋን ዉል ከታህሳስ 05 ቀን 2008ዓ/ም በተደረገዉ ዉል ሽፋን ላለመስጠት አግልየዋለሁ እያለ ኃላፊ ነህ የመባሉን አግባብነት ከግራ ቀኙ ዉልና ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 654 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል።

ተጠሪ በቀን 23/11/2011 ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ አመልካች በቀን 05/04/2008 ዓ/ም ፈርሞ ለተጠሪ በሰጠዉ ዉል በአመጽ ድርጊት ለሚመጣ ዉድመት የመድን ሽፋን በመስጠቱና የሽፋኑ ተፈጻሚነት የሚጀምረዉ በዋናዉ ዉል ሊካተት የሚገባዉ ጉዳይ የነበረ ከመሆኑ አንጻር ወደኋላ ተመልሶ የመድን ሽፋን ዉሉ ከተቋቋመበት ከቀን 01/09/2007 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ በግልጽ ተጽፎና ተፈርሞ የተሰጠዉ ዉል መሆኑን፤ የኢንሽራንስ ዉል ሽፋን ወደፊት ለሚደርስ አደጋ የሚገባ(የሚሰጥ) ሽፋን ቢሆንም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በንግድ ሕግ አንቀጽ 659/1 የተደነገገዉን በመጥቀስ ዉሉ ወደኋላ ተመልሶ ይሰራል ሲል መወሰኑ አግባብ እንደሆነና በዚህ መሰረት እንዳይተረጎም የሚከለክል ሕግ እንደሌለ፤ጉዳቱ የደረሰዉ ከቀን 04/04/2008ዓ/ም እስከ 06/04/2008ዓ/ም ድረስ በነበረዉ ሕዝባዊ አመጽ ምክንያት በመሆኑ ይህም በመድን ማስፊያ ዉሉ የተሸፈነ ምክንያት መሆኑን፤አመልካች በስህተት የተዋዋለዉ ዉል የለም እንጂ በስህተት የተዋዋለዉ ዉል ቢኖር እንኳን ዉሉን ያላስፈረሰ በመሆኑ ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ እንደሆነ፤ እንዲሁም የካሳ መጠኑን በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዉ ከብቸኛ ማሽን አቅራቢ የቀረበ ማስረጃ ሆኖ እያለ ይህንን ማስረጃ ማለፉና ከተጠየቀዉ ካሳ ቀንሶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ሊባል ከሚችል በስተቀር የመለዋወጫ ዋጋዉ የተጋነነ መሆኑን ለማስረዳት አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ማስረጃ የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ ተደርጎ እንዲወሰን በመጠየቅ ተከራክሯል።

አመልካችም በቀን 23/01/2012 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል።

የግራ ቀኝ ክርክር እና የክርክሩ አመጣጥ እንዲሁም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን እኛም የሚከተሉትን ጭብጦች፡-

1. የዋናዉ ኢንሹራንስ ዉል ሽፋን ማስፊያ (Extension) ዉል ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ተብሎ መወሰኑ አግባብ ነዉ ወይ ?

2. የዋናዉ ኢንሹራንስ ዉል ሽፋን ማስፊያ (Extension) ዉል ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል የሚባል ከሆነ በሽፋን ማስፊያ (Extension) ዉሉ በተመለከተዉ ማግለያ መሠረት ሲታይ የአሁን አመልካች ለደረሰዉ ጉዳት የመድን ካሳ ይክፈል መባሉ አግባብ ነዉ ወይስ አይደለም ? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

የመጀመሪያዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ ንብረትነታቸዉ የተጠሪ በሆኑ ሁለት የአለት መቆፈሪያ ማሽኖች(Rock Drilling Ring) ላይ በኢንሹራንስ ዉሉ ላይ በተገለጹ አደጋ ምክንያቶች ለሚደርስ ጉዳት የመድን ካሳ ለመክፈል አመልካች ከተጠሪ ጋር ዋናዉን የኢንሹራንስ ዉል ግራ ቀኝ የተዋዋሉት በቀን 22/11/2007 ዓ/ም በተጻፈ ዉል መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ያደረጉት ክርክር ያሳያል፡፡በዚህ በዋናዉ የኢንሹራንስ ዉል ላይ የተገለሉትን የአደጋ ምክንያቶች በማካተት የመድን ሽፋን ማስፊያ (Extension) ዉል በአመልካች ተፈርሞ የተሰጠዉ በቀን 05/04/2008 ዓ/ም መሆኑ በግራ ቀኝ የታመነና በዉሉ ማስረጃነትም በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉሉ ላይ አመልካች ብቻ መፈረማቸዉን በተመለከተ የተነሳዉን ክርክር አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ፍርድ ላይ በዉሉ ላይ አመልካች ብቻዉን መፈረም የሚችልበት አሰራር ቢኖርም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1725/ለ፣1726 እና 1727(1 እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት የኢንሹራንስ ዉል በጽሁፍ ተደርጎ በተዋዋይ ወገኖችና በሁለት ምስክሮች መፈረም የሚገባዉ ዉል ሆኖ እያለ በአመልካች ብቻ መፈረሙ ስለተረጋገጠ በሕግ ፊት የሚጸና ዉል አይደለም በሚል በማስፊያ ዉሉ ላይ የተጠቀሱት ማግለያዎች የአሁኑን ተጠሪ(ከሳሽን) አያስገድዱም ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር/መ/ቁጥር 23003 በቀን 16 ቀን 1999 ዓ.ም ከተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር እንደመረመርነዉ የኢንሹራንስ ውል የአጻጻፍ ፎርምን በሚመለከት ገዥው ሕግ የፍትሀብሔር ሕጉ አንቀጽ 1725 ቢሆንም በዚህ ህግ መሠረት የአጻጻፍ ፎርሙን መከተል የሚጠበቅባቸው ለብዙ ዘመን (for a long period of time) የሚቆይ የኢንሹራንስ ዉል ሲሆን ብቻ እንደሆነና ለአጭር ጊዜ የሚደረጉ የኢንሹራንስ ውሎች የህጉን አንቀጽ 1725 እና 1727ን በማጣቀስ በጽሁፍ አልተደረጉም፣ በተዋዋየች አልተፈረሙም ፣በሁለት ምስክርም አልተረጋገጡም በማለት ህጋዊ ውጤት እንዳይኖራቸው ማድረግ የሕጉን ዓላማ ግምት ውስጥ ያስገባ አተረጓጎም አይደለም በሚል ትርጉም የሰጠ በመሆኑ በተያዘዉም ጉዳይም ግራ ቀኝ የተዋዋሉት ዋናዉ የመድን ዉል የተፈጸመበትን ቀን መነሻ በማድረግ ስናይ የኢንሹራንስ ዉሉ ለአጭር ጊዜ የተደረገ ነዉ ሊባል የሚችል ከመሆኑ አኳያ ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰጠዉ ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አስገዳጅ ትርጉም በመሆኑ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ትርጉም ለዚሁ ተመሳሳይ ጉዳይ ተፈጻሚ ማድረግ ሲገባዉ የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉሉ በተጠሪ አለመፈረሙን ምክንያት በማድረግ የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉሉ በህግ ፊት የሚጸና አይደለም ሲል መደምደሙ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ይህ ምክንያት ዉሉ በሕግ ፊት እንዳይጸና አያደርግም ብለናል፡፡

ወደያዝነዉ ጭብጥ ስንመለስ የመድን ሽፋን ማስፊያ (Extension) ዉል በአመልካች ተፈርሞ የተሰጠዉ በቀን 05/04/2008 ዓ/ም መሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪ ወይም የስር ከሳሽ ኢንሹራንስ በተገባለት ማሽን ላይ ጉዳት ደርሶበታል ብሎ በክሱ የጠቀሰበት ቀን ታህሳስ 04 ቀን 2008 ዓ/ም መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ፍርድ ይዘት ያሳያል፡፡ ተጠሪ በማሽኑ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ ምክንያት(አደጋ) የኢንሹራንስ ካሳ የሚያስከፍል ምክንያት ነዉ ሲል ለክሱ መሠረት ያደረገዉ ዋናዉን የኢንሹራንስ ዉል ሳይሆን ዋናዉን የኢንሹራንስ ዉል በማሻሻል በቀን 05/04/2008 ዓ/ም ተፈርሞ የተሰጠዉን የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉል ነዉ፡፡በንግድ ሕጉ አንቀጽ 659/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተቃራኒ ዉሳኔ ከሌለ በቀር የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉ ከተፈረመበት ጊዜ አንስቶ የጸና እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉል ወይም በዋናዉ ዉል ማሻሻያ ላይ የመድን ሽፋኑ ተፈጻሚ የሚሆነዉ ዋናዉ ዉል ከተደረገበት ከቀን 22/11/2007 ዓ/ም ወይም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ ላይ ከተጠቀሰዉ ከግንቦት 19 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ነዉ ተብሎ በተዋዋይ ወገኖች በግልጽ የተደረገ ስምምነት የለም፡፡ በዚህ አግባብ የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉሉ ወደኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ተዋዋዮች በዉላቸዉ ላይ በግልጽ ባልወሰኑበት ሁኔታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመድን ሽፋን ማስፊያ ዉሉ የተደረገበት ዓላማ በዋናዉ ዉል ላይ በስህተት ሳይካተት የቀረዉን የአደጋ ምክንያት ለማካተት የተደረገ ማራዘሚያ(ማስፊያ) ዉል ስለሆነ ወደኋላ ተመልሶ ዋናዉ የኢንሹራንስ ዉል ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል ሲል የሰጠዉ ትርጉም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 659/1 ስር በግልጽ የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 654 ስር በተደነገገዉ ትርጓሜ መሰረት የኢንሹራንስ ዉል በዉሉ የተመለከተዉ አደጋ በደረሰ ጊዜ ኢንሹራንስ ሰጪዉ ኢንሹራንስ ለገባዉ ሰዉ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ዉል ነዉ፡፡ይህ ትርጉም እንደሚያሳየዉ የኢንሹራንስ ዉል የሚገባዉ ገና ያልደረሰ ወይም ወደፊት የሚደርስ በዉሉ ላይ የተመለከተዉ አደጋ የሚያደርሰዉን ጉዳት ኢንሹራንስ ሰጪዉ እንዲተካ (እንዲክስ) ለማድረግ ነዉ፡፡ ይህ ትርጓሜ የኢንሽራንስ ዉል ሽፋን ወደፊት ለሚደርስ አደጋ የሚሰጥ ሽፋን መሆኑን ስለሚያሳይ የኢንሹራንስ ዉልን ልዩ የሚያደርግ መሠረታዊ ባህሪይም ይሄዉ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ከዚህም አኳያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኢንሹራንስ ዉል መሰረታዊ ባህሪይ ያላገናዘበ አተረጓጎም በመከተል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

ሲጠቃለል የዋናዉን ኢንሹራንስ ዉል ሽፋን ለማስፋት በቀን 05/04/2008ዓ/ም የተፈረመዉ ማሻሻያ (ማስፊያ /Extension) ዉል ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ በተዋዋዮች ግልጽ ስምምነት ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የኢንሹራንስ ዉል ከመፈረሙ በፊት ለደረሰ ጉዳት ኢንሹራንስ ሰጪዉ ካሳ እንዲከፍል ተጠይቆ የሚቀርብ ክስ የኢንሹራንስ ዉል መሠረታዊ ባህሪይ ያላገናዘበ ሆኖ እያለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኢንሹራንስ ዉሉ ወደኋላ ተመልሶ ዉጤት እንዲኖረዉ አድርጎ በመተርጎም የአሁን አመልካች ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል መወሰኑና በዚህ መሰረት በተሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝቶ ያቀረበዉን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ ስህተቱን ማረም ሲገባዉ ይግባኙን በመሰረዝ ትእዛዝ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሁለተኛዉን ጭብጥ መመርመር ሳያስፈልግ የሚከተለዉን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38532 ላይ በቀን 26/04/2010 ዓ/ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 214193 ላይ በቀን 19/06/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ክስ የቀረበበትን ካሳ ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ፍርድ ቤት ደረጃ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

- የዚህ የፍርድ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
- የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ፤መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 171352

ጥር 25 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች ፦ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፦ የኢትዮጵያ አየር መንገድ

ተጠሪ፦ ብርሃን ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአየር በሚጓጓዝ እቃ(ካርጎ) ላይ በመጥፋት እና በመበላሸ ጉዳት ሲደርስ ካሳ ስለሚከፈልበት አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚህ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።ከክርክሩ እንደተረዳነዉ የአሁን ተጠሪ በመሰረተዉ ክስ በአሁን ተጠሪ የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠዉ ንብረትነቱ የገደብ ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር የሆኑ የጆንደር የእርሻ ትራክተር የተለያዩ መለዋወጫዎች 48 ፓሌት ከደቡብ አፍሪካ ወደ አዲስ አበባ አመልካች ተረክቦ ሲያጓጉዝ ቁጥራቸዉ 144 የሆኑ መለዋወጫዎች በዝናብና በፀሐይ በመበላሸታቸዉ እንዲሁም ብዛታቸዉ 18 የሆኑት ደግሞ በመጥፋታቸዉ ተጠሪ ጉዳቱን በባለሙያ በማስመርመር ለተበላሹትና ለጠፉት በድምሩ ብር 210,942.64 ለደንበኛዉ ካሳ መክፈሉን በመግለጽ አመልካች እቃዎቹን በተረከበበት አኳኋን በደህና ሁኔታ ባለማስረከቡ የደረሰ ጉዳት ነዉ በሚል ብር 210,942.64 አመልካች እንዲተካለት እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል።

የአሁን አመልካች የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ታግዷል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚመለከት መከራከሪያ እና ፍሬ ነገርን በተመለከትም ጉዳቱ የደረሰዉ በአስተሻሸግ ጉድለት በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም፤ ኃላፊነት አለብህ ከተባለም ተጠሪ ወይም ድንበኛዉ በእቃዉ ልዩ ጥቅም እንዳለዉ በመግለጽ ተጨማሪ የጭነት ዋጋ ባለመከፈሉ የጉዳት ካሳዉ መጠን ሊሰላ የሚገባዉ በኪሎ ግራም 17 ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት ማለትም በኪሎ ግራም 20 የአሜሪካን ዶላር ሂሳብ በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፈለዉ የሚገባዉ 1,809.00 የአሜሪካን ዶላር ወይም በኢትዮጵያ ብር 36,192.00 ብቻ በመሆኑ

ለተጠሪ ብር 36,192.00 እንድከፍልና ተጠሪ የእቃዎቹን ቅሪት እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት መከራከሩን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ያየዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 228970 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና የአመልካችን ምስክር ሰምቶ በቀን 27/11/2009 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ጉዳቱ በአስተሻሸግ ጉድለት መድረሱን አላስረዳም በሚል አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 እንደተሻሻለዉ አንቀጽ 18 መሰረት አመልካች አጓጉዞ ለተጠሪ እስከሚያስረክብ ድረስ በእቃዉ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡ የጉዳት ካሳ መጠን በተመለከተም በዋርሶዉ ስምምነት አንቀጽ 22(2/ሀ) ስር የካሳ መጠን የእቃዉ የግዥ ዋጋ መጠን ይሆናል በሚል በተደነገገዉ መሰረት 144 መለዋወጫዎች መጎዳታቸዉና ቁጥራቸዉ 18 የሆኑት መጥፋታቸዉን አመልካች ካለመካዱም በተጨማሪ ተጠሪ በማስረጃ አስረድቷል በሚል የ162 መለዋወጫዎች የግዥ ዋጋቸዉ በግዥ እና በባለሙያ ሰነድ ላይ በተመለከተዉ መሰረት በክፍያዉ እለት በነበረዉ ምንዛሬ ምጣኔ መሰረት በብር 19,942.64 ሂሳብ ስሌት መሰረት ብር 210,942.64 ይሆናል በማለት አመልካች ከ9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበዉ መከራከሪያ ዉድቅ መደረጉ እና ካሳ የተወሰነበትን አግባብና የካሳዉን መጠን በሚመለከት በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 205264 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 13/05/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 አንቀጽ 26 ስር የተደነገገዉ የይርጋ ድንጋጌ ባለመሆኑ የይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉም ሆነ የተወሰነዉ ካሳ በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 22(2/ሀ) እና በንግድ ሕጉ አንቀጽ 683/1 መሰረት ተገቢ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች በቀን 14/06/2011 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉም በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ተጠሪ በ14 ቀን ዉስጥ የደረሰበትን ጉዳት ለአመልካች በጽሁፍ ያላሳወቀ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 አንቀጽ 26.2 እና 26.4 ስር የተደነገገዉን ይርጋ ተጠቅሶ የቀረበዉ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 አንቀጽ 11 መሰረት የጉዞ ሰነድ (Air Way Bill) በተዋዋዮች መካከል ላለዉ ግንኙነት ዉል መኖሩን የሚያረጋግጥ ሰነድ እንደሆነ ስለተደነገገ ከዚህ ዉጭ የሚቀርብ ማንኛዉም ሰነድ ተቀባይነት ስለማይኖረዉ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ያቀረበዉን ሌላ ሰነድ መሰረት በማድረግ ካሳ መወሰናቸዉ፤ ተጠሪ በእቃዉ ላይ የተለየ ፍላጎት እንዳለዉ ያልገለጸና ተጨማሪ ክፍያ

ከፍሎ የልዩ እቃ ዋጋ መግለጫ ባለመፈጸሙ የአየር ጉዞ ሰነዱ ላይ ይሄዉ እንዳልተደረገ ለማመልከት የልዩ እቃ እና ዋጋ መግለጫ አልተደረገም (No Value Declared/NVD) ተብሎ እንደተጻፈበት ተጠሪ ከማመኑም በተጨማሪ ሰነዱም ይህንኑ የሚያሣይ ነዉ፡፡ በመሆኑም የተጓጓዙት እቃዎች ክብደታቸዉ 4343 ኪሎ ግራም ከሆኑት ዉስጥ 48 ጥቅል(ፓሌት) ዉስጥ 1 ጥቅል (ፓሌት) መለዋወጫ መበላሸቱ(መጥፋቱ) ስለተረጋገጠ 4343 ኪሎ ግራም ለ48 ጥቅል(ፓሌት) ሲካፈል የአንድ ጥቅል ክብደት 90.48 ኪሎ ግራም ስለሚሆን ይህም በወቅቱ በነበረዉ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ በብር 20.00 ሲባዛ ብር 36,192.00 ስለሆነ በዋርሶዉ ስምምነት አንቀጽ 22.2/ለ እና ከዚህ በፊት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 117673፣144915 እና 151083 ላይ በተመሳሳይ ጉዳይ በሰጠዉ ትርጉም መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ተሻሽሎ ይወሰንልኝ በማለት በመጠየቅ አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የሰበር አቤቱታዉን እና በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን መርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች አግባብነት ከዋርሶዉ ስምምነት አንጻር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በቀን 09/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ መልሱ ተጠሪ የጉዳቱን ልክ በበቂ የሰነድ ማስረጃ ማስረዳቱን፤የአየር ጭነት ማዘዣ ሰነድ (Air Way Bill) ላይ የእቃዉን መጠን እና ምንነት ተጠቅሶ በማስረጃነት ያቀረባቸዉን ሰነዶች የስር ፍርድ ቤቶች መርምረዉ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ከእቃዉ ዋጋ ጋር እኩል መሆኑን አረጋግጠዉ የሰጡት ዉሳኔዎች አግባብነት ያላቸዉ እንደሆነ፤ አመልካች እንዳለዉ የፕሮቶኮል ቁጥር 4 አንቀጽ 22(2/ለ) ተፈጻሚነት አለዉ ቢባል እንኳን አመልካች እየጠየቀ ባለዉ መሰረት የካሳ መጠኑ ኪሎ ግራምን መሰረት አድርጎ በቁርጥ ለማስላት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች በሙሉ አልተሟሉም፡፡ምክንያቱም አመልካች በዚሁ የማሻሻያ ፕሮቶኮል ለመጠቀም ያስችለዉ ዘንድ በዚሁ ዉል ላይ የተጠቀሰዉ የተጨማሪ ክፍያ(Supplementary Fee) ለጉዳዩ መነሻ ለሆነዉ ካርጎ ተፈጻሚነት ያለዉ መሆኑንና ይኸዉ ክፍያ አለመፈጸሙን አመልካች ማስረዳት እያለበት ከዚህ አኳያ ያለበትን የማስረዳት ግዴታዉን አልተወጣም፡፡ ስለሆነም አመልካች በፕሮቶኮል ቁጥር 4 አንቀጽ 22(2/ለ) ስር የሰፈረዉን የማስረዳት ሸክም ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በቀን 06/10/2011 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክሩን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም ለአከራካሪዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የትኛዉ የሕግ ማእቀፍ ነዉ? አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳዉ መከራከሪያ መታለፉ በአግባቡ ነዉ ወይ? መቃወሚያዉ መታለፉ አግባብ ነዉ የሚባል ከሆነና አመልካች ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊ ነዉ የሚባል ከሆነ ለተጠሪ ምን ያህል ካሳ በምን

አግባብ ተሰልቶ ሊከፈለዉ ይገባል? ከሚሉ ጭብጦች አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ እንደተረዳነዉ ተጠሪ የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠዉ ንብረትነቱ የገደብ ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የግ/ማኀበር የሆኑ የጆንደር የእርሻ ትራክተር የተለያዩ 48 ፓሌት መለዋወጫዎች በአመልካች አየር መንገድ አማካኝነት በእቃ ጭነት (Cargo) መልክ ተጭኖ ከደቡብ አፍሪካ ወደ አዲስ አበባ ሲጓጓዝ ቁጥራቸዉ 144 የሆኑ መለዋወጫዎች በዝናብና በፀሐይ በመበላሸታቸዉ እንዲሁም ብዛታቸዉ 18 የሆኑት ደግሞ በመጥፋታቸዉ ተጠሪ ለደንበኛዉ በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት የከፈለዉ ብር 210,942.64 በአሁን አመልካች እንዲተካለት እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁን አመልካች በበኩሉ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሳዉ ክርክር ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ የዋርሶዉ ስምምነት ለማሻሻል የወጣዉ ሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 ስለሆነ በዚህ ፕሮቶኮል አንቀጽ 26.2 እና 26.4 መሰረት ተጠሪ በ14 ቀን ዉስጥ የደረሰበትን ጉዳት ለአመልካች በጽሁፍ ያላሳወቀ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከማቅረቡም በተጨማሪ በፍሬ ነገር ረገድም አመልካች ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነ ተጠሪ በእቃዉ ላይ የተለየ ፍላጎት እንዳለዉ ያልገለጸና ተጨማሪ ክፍያ ከፍሎ የልዩ እቃ ዋጋ መግለጫ ባለመፈጸሙ የአየር ጉዞ ሰነዱ ላይ ይሄዉ እንዳልተደረገ ለማመልከት የልዩ እቃ እና ዋጋ መግለጫ አልተደረገም (No Value Declared/NVD) ተብሎ ስለተገለጸ መበላሸቱ(መጥፋቱ) የተረጋገጠዉ የእቃ ክብደት 90.48 ኪሎ ግራም ስለሚሆን ይህም በወቅቱ በነበረዉ የኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ በብር 20.00 ሲባዛ 36,192.00 ስለሆነ በዋርሶ ስምምነት አንቀጽ 22.2/ለ ለተጠሪ ሊከፈለዉ የሚገባዉ ብር 36,192.00 ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ከዚህ አኳያ የአሁን አመልካች ያቀረባቸዉን መከራከሪያዎች ባለመቀበል ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ መሰረት የዋርሶ ስምምነት እና የሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ በክሱ መሰረት አመልካች ለተጠሪ ካሳ እንዲከፍል ወስነዋል፡፡

በመጀመሪያም ለአከራካሪዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የትኛዉ የሕግ ማእቀፍ ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ ለክሱ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በአመልካች አየር መንገድ ከደቡብ አፍሪካ በእቃ ጭነት (Cargo) መልክ ተጭኖ ተጓጉዞ ወደ አዲስ አበባ በመጣ የተጠሪ ደንበኛ ንብረት በሆኑ እቃዎች ላይ የደረሰ ጉዳት ነዉ በሚል የተጠየቀ ካሳ መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡አመልካች ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ በ1955 የወጣዉ የዋርሶ ስምምነትና ይህንን ስምምነት ለማሻሻል የወጣዉ ሞንትሪያል ፕሮቶኮል ቁጥር 4 ነዉ በሚል ያሰማዉን ክርክር የስር ፍርድ ቤቶችም ተቀብለዉ እንዚህን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለዉሳኔዎቻቸዉ መሰረት አድርገዋል፡፡

ሆኖም ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ (INTERNATIONAL CARRIAGE BY AIR) የሚመለከተዉ እ.ኤ.አ. በ1929 የወጣዉ የመጀመሪያዉ የዋርሶዉ ቃል ኪዳን፣ በተከታታይ እ.ኤ.አ. በ1955 በወጣዉ የሄግ ፕሮቶኮል (the 1955 Hague Protocol)፣ እ.ኤ.አ በ1961 በወጣዉ የጓድአላጃራ ተጨማሪ ቃል ኪዳን (the Guadalajara Supplementary Convention of 1961) እ.ኤ.አ በ1971 በወጣዉ የጓትማላ ከተማ ፕሮቶኮል(1971 Guatemala City Protocol)፣ እ.ኤ.አ. በ1975 በወጡ ቁጥር 1፣2፣እና 3 የሞንትሪያል ፕሮቶኮሎች (Montreal Protocols 1, 2 and 3 of 1975) እና እ.ኤ.አ በ1975 በወጣዉ ሞንትሪያል ፖሮቶኮል ቁጥር 4 (1975 Montreal Protocol number 4) በተለያየ ሁኔታ እየተሻሻለና እየተለወጠ ከፕሮቶኮሎቹ ጋር ጎን ለጎን ተፈጻሚ ሲሆኑ የቆዩ ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ የሕግ ማእቀፎች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ የሕግ ማእቀፎች ወጥነት የሌላቸዉና ተበታትነዉ የሚገኙ በመሆናቸዉ የአጓጓዦችንና የተጠቃሚዎችን መብትና ጥቅም በሚዛናዊነት እና ፍትሐዊነት ሊያስከብር የሚችል በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆን የተዋሃደ ዘመናዊ ዓለም አቀፍ ሕግ ማዉጣት በማስፈለጉ ዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት የሚገዛባቸዉን ደንቦች ለማዋሃድ ሞንትሪያል ቃልኪዳን ተብሎ የሚታወቅ እ.ኤ.አ. ሜይ 28 ቀን 1999 (Montreal Convention of 1999) በሞንትሪያል ተፈርሞ እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 04 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አገራችንም በዚህ ቃል ኪዳን አንቀጽ 57(ሀ እና ለ) የተደነገገዉን ባለመቀበል ታቅቦ(Reserevation) በማስመዝገብ ቃልኪዳኑን በአዋጅ ቁጥር 820/2006 መሰረት አጽድቃ ከየካቲት 10 ቀን 2006ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ እንዲሆን አድርጋለች፡፡ ስለሆነም በተያዘዉ ጉዳይ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት በአመልካች አየር መንገድ አማካኝነት ተጭኖ ሲጓጓዝ በነበረ የተጠሪ ደንበኛ እቃ ላይ ጉዳት ደረሰ የተባለዉ ሞንትሪያል ቃልኪዳን 1999 በአገራችን ጸድቆ ተፈጻሚ እንዲሆን ከተደረገ በኋላ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የሕግ ማእቀፍ በስር ፍርድ ቤቶች የተጠቀሰዉ የሞንትሪያል ፖሮቶኮል ቁጥር 4 ሳይሆን የሞንትሪያል ቃልኪዳን 1999(ከዚህ በኋላ ቃልኪዳን ተብሎ የሚጠቀስ) በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ተፈጻሚነት የሌላቸዉን ተጠቃሾቹን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ለዉሳኔያቸዉ መሰረት ማድረጋቸዉ ስህተት መሆኑን ማረጋገጥ ችለናል፡፡

አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳዉ መከራከሪያ መታለፉ በአግባቡ ነዉ ወይ? በሚል የተያዘዉን ሁለተኛዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ባለዉ የሞንትሪያል ቃልኪዳን 1999 አንቀጽ 29 ስር በተደነገገዉ መሰረት በዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት ተጭኖ በሚጓጓዝ እቃ (cargo) ላይ ከደረሰ ጉዳት ጋር በተያያዘ ቃልኪዳኑን ወይም ዉልን ወይም ከዉል ዉጭ የመነጨ ኃላፊነትን መሰረት በማድረግ ክስ የሚያቀርብ ማንኛዉም ሰዉ በቃልኪዳኑ የተደነገጉ ሁኔታዎችን እና የኃላፊነት ወሰንን መሠረት በማድረግ ክሱን ማቅረብ አለበት፡፡ በቃል ኪዳኑ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መካከል አንዱ በአይሮፕላን ተጭኖ ሲጓጓዝ በነበረ እቃ (Cargo) ላይ የደረሰ ጉዳት ምክንያት በማድረግ

ካሳ ከመጠየቁ በፊት እቃዉን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 14 ቀን ዉስጥ ቅሬታ ወይም አቤቱታ(complaint) በጽሁፍ ለአጓጓዡ ማቅረብ እንዳለበትና በዚህ ጊዜ ቅሬታዉን ወይም አቤቱታዉን(complaint) ማቅረብ ካልቻለ ጊዜዉ ያለፈበት በመታለሉ ምክንያት መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር በአጓጓዡ ላይ ክስ መመስረት እንደማይችል በቃል ኪዳኑ አንቀጽ 31(2-4) ስር ተደንግጓል፡፡ አመልካች ከዚህ ጋር በማያያዝ የተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ይታገዳል በሚል መቃወሚያ በማቅረቡ የስር ፍርድ ቤቶች ይህ መከራከሪያ ይርጋን የሚመለከት ካለመሆኑም በተጨማሪ ክሱ 2 ዓመት ሳያልፍ የቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ አልታገደም በሚል የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ አድርገዋል፡፡ ሆኖም የስር ፍርድ ቤቶች መቃወሚያዉ በቀጥታ ከይርጋ ጋር የተያያዘ አይደለም በሚል መወሰናቸዉ ስህተት ባይሆንም በቃል ኪዳኑ አንቀጽ 31(2-4) ስር በተደነገገዉ አግባብ የተጠሪ ደንበኛ በእቃዉ ላይ የደረሰዉን ጉዳት በጽሁፍ በ14 ቀን ዉስጥ ለአጓጓዡ (ለአመልካች) ማሳወቅ አለማሳወቁን የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነም ፍሬ ነገሩን በማስረጃ በማረጋገጥ መወሰን ሲገባዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ ሲያይ በዚህ አግባብ ክርክሩ ተጣርቶ እንዲወሰን ማድረግ ሲገባዉ የሁኔታዉ መሟላት ክስ ለማቅረብ ብቁ የሚያደርግ ቅደመ ሁኔታ ሆኖ If no complaint is made within the times aforesaid no action shall lie against the carrier… በሚል በአስገዳጅነት ተደንግጎ እያለ መከራከሪያዉን ከይርጋ ጋር በማያያዝ የይርጋ ጊዜዉ አላለፈም ከሚል አቅጣጫ ብቻ በማየት ማለፋቸዉ ቃል ኪዳኑ የዘረጋዉን የክስ አቀራረብ ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳዉ መከራከሪያ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት ተጣርቶ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ በቃልኪዳኑ በቅድመ ሁኔታነት የተደነገገዉን ያሟላል ተብሎ መቃወሚያዉ ዉድቅ ተድርጎ በእቃዉ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት እና ለጠፋዉ እቃ አመልካች በቃል ኪዳኑ መሰረት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት መጠን እና ካሳ የሚሰላበት መንገድ በመርህ ደረጃ በቃልኪዳኑ አንቀጽ 22(3) ስር በተደነገጉት ሁኔታዎች መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ የእቃዉ ባለቤት ወይም የተጠሪ ደንበኛ ወይም በተያዘዉ ጉዳይ የእቃዉን ላኪ ወይም ባለቤት በመተካት የቀረበዉ የአሁን ተጠሪ እቃዉን በአየር መንገዱ ጭኖ እንዲያጓጉዝ ለአመልካች እቃዉን ሲያስረክብ በእቃዉ ላይ ያለዉን ልዩ ጥቅም በመግለጽ ተገቢዉን ተጨማሪ ዋጋ መክፈሉን ካላስረዳ በስተቀር አመልካች ካሳ ለመክፈል የሚገደደዉ በጠፋዉ ወይም ጉዳት ለደረሰበት እቃ በአንድ ኪሎ ግራም 17 ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት በመክፈል እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡በእቃዉ ላይ ልዩ ጥቅም መኖሩ ተገልጾ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈል መደረጉ ከተረጋገጠ የደረሰዉ ተጨባጭ ጉዳት(actual damage) የእቃዉ ዋጋ ነዉ ተብሎ ከተገለጸዉ አጠቃላይ ዋጋ የሚበልጥ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የሚከፈለዉ ካሳ የእቃዉ ዋጋ ነዉ ተብሎ ከተገለጸዉ

ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በቃል ኪዳኑ አንቀጽ 22(4-6) የተጠቀሱት ተጨማሪ ሁኔታዎች በተሟሉ ጊዜ በቃል ኪዳኑ አንቀጽ 22/3 ስር ከተደነገገዉ የካሳ ስሌትና መጠን በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ ካሳ ሊከፈል የሚችልበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የዋርሶዉ ስምምነት አንቀጽ 22(2/ሀ)ን በመጥቀስ እና ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረባቸዉን እቃዉ የተገዛባቸዉን ዋጋ የሚያሳዩ ሰነዶች መሰረት በማድረግ አመልካች ለተጠሪ የእቃዉን ዋጋ ብር 210,942.64 እንዲከፍል የወሰኑበት አግባብ ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ የዋርሶዉ ስምምነት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በሞንትሪያል ቃል ኪዳን 1999 የተተካ ከመሆኑም በተጨማሪ የዋርሶዉ ስምምነት አንቀጽ 22(2/ሀ) ካርጎን የሚመለከት ባለመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ካሳ የወሰኑበት አግባብ እና የወሰኑት የካሳ መጠን ከላይ ከተጠቀሱት የሞንትሪያል ቃልኪዳን 1999 ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ የተጠሪ ደንበኛ ለአመልካች እቃዉን ሲያስረክብ በእቃዉ ላይ ያለዉን ልዩ ጥቅም በመግለጽ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አለመክፈሉን በተመለከተ ግራ ቀኝ ክርክር አድርገዉ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ምንነት፣የእቃዉ ኪሎ ግራም ምን ያህል እንደሆነ ፣ በቃልኪዳኑ አንቀጽ 22/3 ስር በተደነገገዉ አግባብ በአንድ ኪሎ ግራም በ17 ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት ተሰልቶ ወደ አሜሪካን ዶላር እና ወደ ኢትዮጵያ ብር የተለወጠበት የምንዛሪ ምጣኔ በቃልኪዳኑ ላይ በተመለከተዉ አግባብ ስለመሆኑ በግልጽ በማሳየት የተሰጡ ዉሳኔዎች ባለመሆናቸዉ በቃልኪዳኑ በግልጽ ስለካሳ አወሳሰን እና መጠን በቅደምተከተል የተደነገጉትን ሁኔታዎችን ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

እንዲሁም የተጠሪ ደንበኛ ለአመልካች እቃዉን ሲያስረክብ በእቃዉ ላይ ያለዉን ልዩ ጥቅም መግለጽ አለመግለጹና ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አለመክፈሉ በጭብጥነት ተይዞ ክርክር ተደርጎበት በማስረጃ ሳይረጋገጥ በቃልኪዳኑ በአንድ ኪሎ ግራም 17 ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት ይከፈላል ተብሎ የተደነገገዉን በመተዉ የእቃዉ የግዥ ዋጋ መሰረት ተደርጎ አመልካች ካሳ እንዲከፍል ሲወስኑ የተከተሉበት የክርክር አመራር በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ከቁጥር 246-248 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተገቢዉን ጭብጥ ሳይዙና ከማስረጃ ወይም ከሕግ አንጻር ተገቢዉን ሳያረጋግጡ መወሰናቸዉን ስለሚያሳይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉ ሳ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 228970 ላይ በቀን 27/11/2009 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 205264 ላይ በቀን 13/05/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 228970 በማንቀሳቀስ፡-
    2.1. አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳዉን መከራከሪያ በተመለከተ በሞንትሪያል ቃልኪዳን አንቀጽ 31(2-4) ስር በተደነገገዉ አግባብ የተጠሪ ደንበኛ በእቃዉ ላይ የደረሰዉን ጉዳት በጽሁፍ በ14 ቀን ዉስጥ ለአጓጓዡ (ለአመልካች) ማሳወቅ አለማሳወቁን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክር ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 245/1 አንጻር በመስማትና በማስረጃ የሚረጋገጥ ነገር ሲኖር በማስረጃ እንዲረጋገጥ በማድረግ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩን መልስናል፡፡
    2.2. ከላይ በተራ ቁጥር 2.1. ስር በተወሰነዉ መሰረት ተጣርቶ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ በሚያስችለዉ ሁኔታ በቃልኪዳኑ በቅድመ ሁኔታነት የተደነገገዉን መስፈርት አሟልቷል ተብሎ አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሳዉ መከራከሪያ ዉድቅ የሚያደርግ ከሆነ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ከላይ በፍርዱ ሀተታ ከገጽ 6-7 በተመለከተዉ አግባብ የአመልካችን ኃላፊነት እና ካሳ መጠን በተመለከተ ቃልኪዳኑን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በ/ፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት በተደረገ ክርክር መነሻ ያወጡትን ወጪ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ወስነናል፡፡

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 179983

መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ኢትዮ ላይፍ ኤንድ ጄነራል ኢንሹራንስ አ.ማ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀሪያ ታደሰ ደስታ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ መድን ሰጪ ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉን ካሳ ከመድን ገቢዉ ለማስመለስ ዳኝነት ተጠይቆ በሚያቀርበዉ ክስ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረዉን ይርጋ እና አቆጣጠሩን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በመቀሌ መእከላዊ(ከፍተኛ) ፍርድ ቤት ሆኖ በዚህ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ በመሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ አመልካች ንብረትነቱ የተጠሪ ለሆነ በሰሌዳ ቁጥር 3-06609 ትግ ለሚታወቅ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰዉ ጉዳት ከቀን 16/07/2008ዓ/ም እስከ ቀን 15/07/2009ዓ/ም ድረስ ለሚቆይ ጊዜ በፖሊሲ ቁጥር ኤምኬ/ዲአይ/ ኤምቲ-ፒኤስ/0381/16 የሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን ሰጥቶ ባለበት ጊዜ ተሽከርካሪዉ በቀን 22/09/2008ዓ/ም መስመሩን ስቶ የሰሌዳ ቁጥር 3-18362አ.አ ተሽከርካሪ ገጭቶ በ4 ተሳፋሪዎች ላይ ሞት በ8 ተሳፋሪዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት በማድረሱ አመልካች ለሟች ቤተሰቦችና ጉዳት ለደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች ብር 103,030.45 የካሳ ክፍያ ፈጽሟል፡፡ ይህንን ተከትሎ አመልካች የተጠሪ ተሽከርካሪ የመጫን አቅሙ 11 ሰዉ ሆኖ እያለ አደጋዉ በደረሰበት ጊዜ በትራንስፖርት ባለስልጣን ከተፈቀደለት የመጫን አቅም በላይ 14 ተሳፋሪዎችን አሳፍሮ ሲጓዝ እንደነበር በፖሊስ ሪፖርት ስለተረጋገጠ የመድን ዉልን ጥሳለች በሚል ለሦስተኛ ወገን በከፈለዉ ካሳ ልክ ተመላሽ እንድታደርግለት በተጠሪ ላይ ክስ በመመስረት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበባት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ አደጋዉ የደረሰዉ በቀን 22/09/2008ዓ/ም ሆኖ ክሱን ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ በቀን 11/11/2010ዓ/ም ስላቀረበ የአመልካች ክስ በይርጋ ታግዷል በማለት ተቃዉማለች፡፡አመልካች በበኩሉ የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር ያለበት አመልካች ለተጎጂዎች ክፍያ ከፈጸመበት ከቀን 13/07/2009 ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ስለሚገባ ከዚህ ቀን ጀምሮ ክስ እስከተመሰረተበት ቀን ድረስ ያለዉ ጊዜ ሲቆጠር ሁለት አመት ባለማለፉ ክስ የማቅረብ መብቴ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ያየዉ የመቀሌ ከተማ መእከላዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29923 ላይ በቀን 29/04/2011 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ብይን አደጋዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 በግልጽ እንደተደነገገዉ በኢንሹራንስ ዉል ምክንያት የሚነሳ ክርክር ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ዉስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ስለተደነገገ ጉዳቱ በቀን 22/09/2008ዓ/ም ደርሶ ክሱ በቀን 11/11/2010 ዓ/ም ስለቀረበ ክሱ የቀረበዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነዉ በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 113679 ላይ በቀን 27/07/2011ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዟል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት በቀን 26/10/2011 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት አጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ጉዳት የደረሰዉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ በመሆኑ አመልካች በተጠሪ ላይ የመድን ዉሉን አላከበረም በሚል ክስ መስርቶ የከፈለዉን የጉዳት ካሳ ተመላሽ የመጠየቅ መብት የሚያገኘዉ ለሦስተኛ ወገኖች ካሳ ከከፈለ በኋላ በመሆኑ ክሱ የቀረበዉም በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡የይርጋ ጊዜዉ መታሰብ የሚገባዉ የካሳ ክፍያ በአመልካች ከተፈጸመበት ቀን ከመጋቢት 16 ቀን 2009ዓ/ም ጀምሮ ስለሆነ ክሱ በተመሰረተበት በቀን 11/11/2010 ዓ/ም ሁለት ዓመት አልሞላም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ከንግድ ሕጉ በኋላ የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 799/2005ን ባገናዘበ ሁኔታ የይርጋ ጊዜዉን ሳይመረምሩ ክሱ በይርጋ ታግዷል በማለት መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም በተጠሪ ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገን ላይ የሞትና የአካል ጉዳት የደረሰ በመሆኑ ድርጊቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 መሰረት በ5 ዓመት እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ ይህንን መነሻ ያደረገ የካሳ ክስ ሲቀርብ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ ለወንጀል ጉዳይ የተደነገገዉ ይርጋ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 መሰረት አደጋዉ ከደረሰበት ከግንቦት 22 ቀን 2008ዓ/ም ጀምሮ ሲሰላ 5 ዓመት ስላልሞላ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ሳይሆን በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ እንዲታረም በመጠየቅ አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የመድን ዉል ባላከበረ ደንበኛ ላይ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 መሰረት የሚቀርብ ክስ የይርጋ ጊዜዉ መታሰብ ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነዉ የሚለዉን ነጥብ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ብሎ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 12/02/2012 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርባለች፡፡

የአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 የመድን ፖሊሲ የዉል ሁኔታዎችን የሚመለከት እንጅ ስለ ይርጋ ጊዜ የሚመለከት ድንጋጌ ባለመሆኑ አመልካች ከዚህ ድንጋጌ ጋር በማያያዝ ያቀረበዉ ክርክር ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር የተደነገገዉ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት አመልካች ክሱን ጉዳቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባለዉ ሁለት አመት ጊዜ ዉስጥ ባለማቅረቡ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት በመወሰናቸዉ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ አቤቱታዉ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡

አመልካች በተጠሪ በቀረበ መልስ ላይ በቀን 29/03/2012 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረዉም አመልካች በፖሊሲ ቁጥር ኤምኬ/ዲአይ/ኤምቲ-ፒኤስ/0381/16 በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ አደጋ የመድን ሽፋን ሰጭ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የሰሌዳ ቁጥር 3-06609 ትግ የሆነ ተሽከርካሪያቸዉ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚያደርሰዉ አደጋ ከአመልካች የሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን የገዙ መድን ገቢ እንደሆነች ከክርክራቸዉ ተረድተናል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በቀን 11/11/2010 ዓ/ም የመሰረተዉ ክስ ይህ ለተጠሪ ተሽከርካሪ የተሰጠዉ የመድን ሽፋን ከቀን 16/07/2008ዓ/ም እስከ ቀን 15/07/2009ዓ/ም ድረስ ጸንቶ በቆየበት ጊዜ የተሽከርካሪዉ የተፈቀደለት የመጫን አቅም 11 ሰዉ ሆኖ እያለ አደጋዉ በደረሰበት ጊዜ በትራንስፖርት ባለስልጣን ከተፈቀደለት የመጫን አቅም በላይ 14 ተሳፋሪዎችን አሳፍሮ እንዲጓዝ በማድረጓ ተሽከርካሪዉ በቀን 22/09/2008ዓ/ም መስመሩን ስቶ የሰሌዳ ቁጥር 3-18362አ.አ ተሽከርካሪ ገጭቶ በ4 ተሳፋሪዎች ላይ ሞት በ8 ተሳፋሪዎች ላይ ደግሞ የአካል ጉዳት በማድረሱ አመልካች ለሟች ቤተሰቦችና ጉዳት ለደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች ብር 103,030.45 የካሳ ክፍያ ስለፈጸመ ይህ አደጋ ሊደርስ የቻለዉ ተጠሪ የመድን ዉሉንና የትራፊክ ደንብ በመጣሷ ምክንያት ነዉ በሚል ተጠሪ ለሦስተኛ ወገኖች የተከፈለዉን ገንዘብ እንድትተካልኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት የጠየቀበት ክስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ክሱ በይርጋ ታግዷል በሚል

ያቀረበችዉን መቃወሚያ በመቀበል የይርጋ ጊዜዉን አደጋዉ ከደረሰበት ከግንቦት 22 ቀን 2008ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ሐምሌ 11 ቀን 2010 ዓ/ም ድረስ ያለዉን ጊዜ በመቁጠር አመልካች ክሱን ያቀረበዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር የተደነገገዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ በማለት መዝገቡን ዘግተዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች በተጠሪ ላይ የመሰረተዉ ክስ አመልካች በሰጠዉ የሦስተኛ ወገን መድን ፖሊስ ሽፋን መሰረት በተጠሪ ተሽከርካሪ ምክንያት የሞትና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች የካሳ ክፍያ ከፈጸመ በኋላ ጉዳቱ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ሊደርስ የቻለዉ የመድን ዉሉንና የትራፊክ ደንብ በጣሰ አኳኋን የተጠሪ ተሽከርካሪ በትራንስፖርት ባለስልጣን ከተፈቀደለት የመጫን አቅም በላይ 14 ተሳፋሪዎችን አሳፍሮ እንዲጓዝ በመደረጉ ምክንያት ስለሆነ ተጠሪ የመድን ዉል ስለጣሰች ለሦስተኛ ወገኖች በከፈልኩት ካሳ ልክ ልትተካልኝ ይገባል በማለት ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ አደጋ የሚሰጥ የመድን ሽፋን የሚመነጨዉ በመድን ሰጭዉና በመድን ገቢዉ መካከል በሚደረግ የመድን ዉል ፖሊሲ መነሻ ቢሆንም በተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ አደጋ የመድን ሽፋን ለመስጠት በወጣ አዋጅ ቁጥር 799/2005 በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት በመድን ዉሉ ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ አደጋ የደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች በሽፋኑ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያደርግ ግንኙነት መፈጠሩን መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ ምንም እንኳን ግራ ቀኝ የመድን ዉሉ ተዋዋዮች ቢሆኑም ከዉሉ ተጠቃሚዎች ሦስተኛ ወገኖች ጭምር በመሆናቸዉ የመድን ዉል ፖሊሲዉ እና አዋጅ ቁጥር 799/2005 የሦስትዮሽ ግንኙነትን እንዳቋቋመ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ክሱን የመሰረተዉ የመድን ዉሉን እና በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ክሱ ስለሚያሳይ ግንኙነታቸዉም በመድን ዉል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት የሚኖረዉ የይርጋ ድንጋጌ ይህንን በዉል ላይ የተመሰረተዉን ግንኙነት መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ከዉል ዉጭ የሆነ ኃላፊነት መነሻ በማድረግ ካሳ ለማስከፈል ለሚቀርብ ክስ ተፈጻሚነት እንዲኖረዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር የተደነገገዉ የይርጋ ድንጋጌ የዉል ግንኙነትን መነሻ ባደረገ ክርክር ላይ ተፈጻሚነት ስለሌለዉ አመልካች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር የተደነገገዉ ነዉ በሚል ያቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በተጠሪ ላይ ክሱን የመሰረተዉ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ቢሆንም እንዲህ አይነት ክስ መቅረብ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 ስር አልተደነገገም፡፡ ከኢንሹራንስ ዉል ጋር የተያያዙ ክሶችን ይርጋ በተመለከተ በጠቅላላዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር በኢንሹራንስ ዉል ምክንያት የሚቀርብ

ማንኛዉም ክስ የሚታገደዉ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያላቸዉ ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ (በእንግሊዘኛዉ ቅጅ፡ …from the occurrence giving rise to the claim or from the day when the parties knew of the occurrence)ከሁለት ዓመት በኋላ ነዉ ሲል የይርጋ ጊዜና የይርጋ ጊዜዉ የሚቆጠርበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ይህ የይርጋ ጊዜ ከኢንሹራንስ ዉል የመነጨ ማንኛዉንም ክስ የሚመለከት መሆኑን የድንጋጌዉ ይዘት የሚያሳይ በመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ ልዩ ሕግ የሆነዉ አዋጅ ቁጥር 799/2005 የተሽከርካሪ አደጋ በሦስተኛ ወገን ከሚያደርሰዉ አደጋ ጋር በተያያዘ ለሦስተኛ ወገን መድን ሰጭዉ የከፈለዉን ካሳ መድን ገቢዉ እንዲተካለት የሚያቀርበዉን ክስ የሚመለከት የይርጋ ጊዜ ስላልደነገገ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ ይርጋ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር የተደነገገዉ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ከዚህ አኳያ የስር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ስር የተደነገገዉ ነዉ ማለታቸዉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

ሆኖም በፍትሐብሔር ሕጋችን ስለ ይርጋ በጠቅላለዉ በሚደነግገዉ ክፍል በአንቀጽ 1846 "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል ርእስ ሥር "የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታዉን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነዉ፤ወይም ዉሉ የሚሰጠዉ መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነዉ" በማለት ደንግጓል፡፡ የንግድ ሕጉን አንቀጽ 674/1 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌዎች ይዘት መንፈስና ዓላማ መሠረት በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለዉን ግንኙነትና የክሱን ምክንያት መሰረት አድርገን እንደመረመርነዉ በአዋጅ ቁጥር 799/2005 መሰረት አመልካች በተጠሪ ላይ ሊያነሳ የሚችለዉን ማንኛዉንም መከራከሪያ ጉዳት በደረሰባቸዉ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ማንሳትና ካሳ አልከፍልም ማለት ስለማይችል በዚህ አዋጅና በሦስተኛ ወገን የመድን ሽፋን ዉል መሰረት ለሦስተኛ ወገኖች የካሳ ክፍያ መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ለሦስተኛ ወገኖች ካሳ የከፈለዉ መጋቢት 16 ቀን 2009 ዓ/ም መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነዉ፡፡አመልካች በዉሉና በሕጉ መሰረት ተገዶ ካሳ በመክፈሉ ገንዘቡን ወጪ ያደረገዉ መጋቢት 16 ቀን 2009 ዓ/ም በመሆኑ ከዚህ ቀን በፊት ለሦስተኛ ወገን የከፈለዉ ካሳ ባለመኖሩ የመድን ዉል ፖለሲዉንም ሆነ አዋጅ ቁጥር 799/2005 አንቀጽ 6/2ን መሰረት በማድረግ ለሦስተኛ ወገኖች የከፍልኩትን ትተካልኝ በማለት በመድን ገቢዋ(በተጠሪ) ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችል የበሰለ መብት የለዉም፡፡ በእንዲህ አይነት ጉዳይ በመድን ገቢዉ ላይ ለክሱ ምክንያት የሆነ ጉዳት ደረሰበት ማለት የሚቻለዉ(the occurrence giving rise to the claim) እና በመብቱ ሊሰራ የሚችለዉ ለሦስተኛ ወገኖች የካሳ ክፍያ ከፈጸመበት ቀን ከመጋቢት 16 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ ባለዉ ሁለት ዓመት ጊዜ ዉስጥ እንጅ በሦስተኛ ወገኖች ላይ አደጋዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ አይደለም፡፡ ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በሦስተኛ ወገኖች ላይ አደጋ የደረሰበት ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር መነሻ ሊሆን የሚችለዉ መድን ሰጭዉን ካሳ ለማስከፈል ከሚቀርብ ክስ ጋር በተያያዘ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ከተጠሪ ጋር በፈጸመዉ የመድን ዉል መሰረት በተጠሪ ተሽከርካሪ አደጋ ደረሰባቸዉ ለተባሉት ሦስተኛ ወገኖችና ለተጎጂ ቤተሰቦች የካሳ ክፍያ የፈጸመበት ጊዜ በተጠሪ (በመድን ገቢዋ) ለመሰረተዉ ክስ ይርጋ አቆጣጠር መነሻ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ካሳ የከፈለዉ መጋቢት 16 ቀን 2009 ዓ/ም ሆኖ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 674/1 ሥር የተደነገገዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ሳያልፍ ሐምሌ 11 ቀን 2010 ዓ/ም በመሆኑ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ አልሆነም፡፡ ስለሆነም የመቀሌ ማእከላዊ ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉን አደጋዉ የደረሰበትን ቀን ለይርጋ አቆጣጠር መነሻ በማድረግ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ታግዷል በማለት መዝገቡን መዝጋቱና ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስህተቱን ሳያርም ማለፉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የመቀሌ ከተማ መእከላዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 29923 ላይ በቀን 29/04/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 113679 ላይ በቀን 27/07/2011ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የመቀሌ ከተማ መእከላዊ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 29923 በማንቀሳቀስ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮና እንደአስፈላግነቱ ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

- የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- ዉሳኔዉ ይታተም ዘንድ ለህግና ምርምር ክፍል ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 192580

ጥር 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- እንደራስ ናሽናል ኃላ/የ/የግ/ማኅበር

ተጠሪ፡- እንደራስ የንብረት አስተዳደር ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ምልክት እና የንግድ ስም ሸማቹን ወይም ተጠቃሚዉን ኅብረተሰብ አሳሳች ነዉ ሊባል የሚችልበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በመጀመሪያ በታየበት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተው ክስ አመልካች እንደራስ ናሽናል ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር በሚል የንግድ ስም በቀን 17/02/1998 ዓ/ም ተቋቁሞ ሪል እስቴትና ሌሎች ንብረቶችን በማስተዳደር፣የንግድ እንደራሴነት ሥራ፣የሪል እስቴት ልማት ሥራዎች፣የንብረት አቻ ግምት ሥራዎች እንደሚሠራ ገልጾ የሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ለመለየት እንደራስ ናሽናልስ እሴት ማኔጅመነት የሚል ቃል እና ምስል ያለበት የንግድ ምልክት በአለም አቀፍ ምድብ 36 እንዲመዘገብለት ለኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት አመልክቶ ተጠሪ የንግድ ምልክቱ እንዳይመዘገብ ተቃዉሞ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም የተጠሪን ተቃዉሞ ዉድቅ አድርጓል፡፡ ይህንን ተከትሎም ጽ/ቤቱ የንግድ ምልክቱን በምዝገባ ቁጥር LTM/3042/2009 መዝግቦ የንግድ ምልክት የምስክር ወረቀት ለአመልካች ሰጥቶታል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ከአመልካች ጋር አንድ አይነት የሆነ አሳሳች የንግድ ስም እና የንግድ ምልክት የሚጠቀም በመሆኑ በንግድ ስም ስያሜነት እና በንግድ ምልክትነት መጠቀሙን እንዲያቆም እንዲወሰንለት፣ የጉዳት ካሳ ብር 400,000.00 እና የሞራል ካሳ እንዲከፈለዉ እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲተካለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ የአመልካችን የንግድ ምልክትም ሆነ የንግድ ስም ተጠሪ አልተጠቀመም፡፡እንደራስ ከሚለዉ ቃል በስተቀር የግራ ቀኝ የንግድ ስም አይመሳሰልም፡፡ተጠሪ የሚሰጣቸዉ አገልግሎት አመልካች ከሚሰጣቸዉ አገልግሎቶች የተለዩ ናቸዉ፡፡የተጠሪ የንግድ ምልክት እንደራስ የንብረት አስተዳደር አገልግሎት ኃላ/የተ/የግ ማኅበር በሚለዉ የንግድ ስም እና የጣት አሻራ

ምስል በቅንጅት የተፈጠረ ነዉ፡፡የኢትዮጵያ አእምሮዊ ንብረት ጽ/ቤት ተጠሪ የአመልካች የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ ያቀረበዉን ተቃዉሞ ዉድቅ አድርጎ የአመልካችን የንግድ ምልክት መመዝገቡ የግራ ቀኙ የንግድ ምልክቶች ተመሳሳይ ናቸዉ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡አመልካች የደረሰበትን ጉዳት ያላስረዳ በመሆኑ እንዲከፈለዉ የጠየቀዉ ካሳ ከደረሰበት ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን የሚገባ መሆኑን እንዲሁም የሮያሊቲ ክፍያ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ነዉ በማለት መልሱን በመስጠት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የዳኘዉ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 171664 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር በመስማትና የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲሁም የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ስር ስለንግድ ምልክት እና ስለንግድ ስም ጥበቃና አሰጣጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመመርመርና በዋቢነት በመጥቀስ በቀን 26/06/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ውሳኔ የንግድ ስምንና የንግድ ምልክት ግጭት በተፈጠረ ጊዜ ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ጊዜ እንዴት እንደሚፈታ የሚገልጽ ሕግ ባይኖርም አመልካች የንግድ ስሙን ተጠሪ የተጠቀመ ስለመሆኑ በማስረጃ ያላረጋገጠ በመሆኑ፤ተጠሪ የሚጠቀመዉ የንግድ ምልክት ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይነት የሌለዉ በመሆኑ፤ ተጠሪ የሚጠቀመዉ የንግድ ምልክት አማካይ የሆነ ተጠቃሚን ሊያሳስት የሚችል ባለመሆኑ፤ግራ ቀኝ ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ተጠሪ የሚጠቅመዉ የንግድ ምልክት ህብረተሰቡን የማያሳክር በመሆኑ፤አመልካች የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበዉ ለንብረት ግምት አቻ ሥራዎች ስለሆነ በንግድ ምልክቱ ላይ ያለዉም የብቸኝነት መብት ከዚህ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በመሆኑ፤አመልካች እንደራስ የሚለዉን ቃል በብቸኝነት ሊጠቀም የሚችለዉ የንግድ ምልክቱን ካስመዘገበበት የንብረት ግምት አቻ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ብቻ በመሆኑ እንዲሁም አንደራስ የሚለዉን ቃል ሌሎች ሰዎች ሌሎች አገልግሎቶች መጠቀም እንዳይችሉ ለመከልከል የሚያስችል መብት በሕግ ስላልተጠበቀለት ተጠሪ በአመልካች የንግድ ስምም ሆነ የንግድ ምልክት ላይ ጥሰት አልፈጸመም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 239171 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 23/04/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡አመልካች ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት በቀን 09/07/2012 ዓ/ም ጽፎ ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የሚከተለው ነው፡፡

አመልካች የንግድ ምልክቱን ሲያስመዘግብ ተጠሪ አመልካች እንዲመዘገብለት የጠየቀዉ የንግድ ምልክት ከራሱ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ በመግለጽ/በማመን/ ተቃዉሞዉን ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት አቅርቦ ጽ/ቤቱ አመልካች የንግድ ምልክቱን አስቀድሞ ሲጠቀምበት የቆየ በመሆኑ

የቀደምትነት መብት እንዳለዉ በማረጋገጥ የተጠሪን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ በመወሰኑ ተጠሪ እንደራስ የንብረት አስተዳደር በሚለዉ ስም እና ምልክት ለመጠቀም መብት የለዉም፡፡ተጠሪ በቀዳሚነት መብት ቢኖረዉ ኖሮ አመልካች ሌላ የንግድ ምልክት እንዲቀይር ይገደድ ነበር፡፡ይህ የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ አልተሻረም፡፡የሥር ፍርድ ቤቶች የንግድ ስምንና የንግድ ምልክት ግጭት በተፈጠረ ጊዜ ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ጊዜ እንዴት እንደሚፈታ የሚገልጽ የሕግ ማእቀፍ የለም በሚል የደረሱበት ድምዳሜ በሰ.መ.ቁጥር 57179 ላይ የንግድ ምልክትና የንግድ ስም ህብረተሰቡን በሚያሳስት ደረጃ ተመሳሳይነት ሲኖራቸዉ ተያያዥነት ያላቸዉ የሕግ ማእቀፎች ተጣጥመዉ እንዲታዩ በማድረግ እንደቅድሚያ ምዝገባቸዉ አንዱ ሌላዉን ቀሪ እንዲያደርግ ተደርጎ ሊወሰን እንደሚገባ የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ለአመልካች የተመዘገበለት የንግድ ምልክት የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተጠሪን ተቃዉሞ ዉድቅ በማድረግ የመዘገበዉ ሆኖ እያለ የንግድ ምልክቱ ለአመልካች የተመዘገበዉ ምድብ 36 ላይ ለንብረት አቻ ግምት ብቻ ነዉ በማለት ተጠሪ መጠቀም ይችላል ብለዉ የሥር ፍርድ ቤቶች መወሰናቸዉ በአዋጅ ቁጥር 501/2006 አንቀጽ 13/1 እና በደንብ ቁጥር 273/2012 አንቀጽ 21፣26/1 እና 27/1 ላይ የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚከናወንበትንና ተቃዉሞ ዉድቅ የሚደረግበትን ሂደትና ዉጤቱን ያላገናዘበ ነዉ፡፡

እንዲሁም ለአመልካች የተመዘገበለት የንግድ ምልክት በአለም አቀፍ ምድብ 36 ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 2/7 እና በናይስ ዲፕሎማቲክ ኮንፈረንስ በወጣዉ ምድብ መሰረት ምድብ 36 ስር ያሉት የንግድ ምልክቶች የንብረት አስተዳደር፣የንብረት አቻ ግምት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ያቀፈ እንደመሆኑ አእምሯዊ ጸ/ቤት የአመልካችን እና የተጠሪን የመመስረቻ ጽሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ በመመልከት ከቀረበዉ ክርክር እና ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ተመልክቶ ምልክቱ ቢመዘገብ ተጠቃሚዉን ያሳስታል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ምክንያት ማን ነዉ ቀዳሚ የሚለዉን መለያ ነጥብ (ጭብጥ) በመያዝ አመልካች ቀዳሚ ነዉ በማለት ምልክቱ ለአመልካች መዝግቧል፡፡ በዚህ መሰረት ምልክቱ እንዲመዘገብ የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቶ ባለበት የሥር ፍርድ ቤቶች በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት መልስ የተሰጠባቸዉን ጉዳዮች በይግባኝ መልክ ጉዳዩ ሳይቀርብላቸዉ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን እንደገና በመመርመር መወሰናቸዉ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም በምድብ 36 የሚመዘገብ የንግድ ምልክት ሲታይ ግራ ቀኝ የምንሰጣቸዉን አገልግሎቶች ያቀፈ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 501/2006 አንቀጽ 2/7 የተደነገገዉን እና በናይስ ዲፕሎማቲክ ኮንፈረንስ የወጣዉን ምድብ ሕግ ያላገናዘበ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 15/02/2011 ዓ/ም ትእዛዝ የሰጠዉ የግራ ቀኝ የንግድ ምልክት እንድናቀርብ እንጂ ግራ ቀኝ የንግድ ስም ያስመዘገብንበትን ማስረጃ እንድናቀርብ ባልታዘዝንበት ከትእዛዙ ዉጭ ተጠሪ ያቀረበዉን የንግድ ስም ያስመዘገበበትን ማስረጃ የሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ

አቀራረብ ስርዓት ባልተከተለ ሁኔታ ተቀብሎና ይህንን ማስረጃ መሰረት አድርጎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የተጠሪ የንግድ ምልክትና የንግድ ስም ከአመልካች የንግድ ምልክትና ስም ጋር የሚመሳሰልና ተገልጋይ ህብረተሰቡን የሚያሣስት መሆን አለመሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 501/2006፣ ከአዋጅ ቁጥር 980/2008፣ከአዋጅ ቁጥር 813/2006 እና በሰ/መ/ቁጥር 57179 ላይ ከተሰጠዉ ትርጉም ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 13/02/2013 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለውን መልስ አቅርቧል፡፡

ለአመልካች የተሰጠዉ የንግድ ምልክት የተመዘገበዉና የሕግ ጥበቃ የተሰጠዉ በአለም አቀፍ ምደባ 36 ለንብረት አቻ ግምት ሥራዎች በመሆኑ አመልካች የንግድ ምልክቱን በመመስረቻ ጽሁፉ ለተዘረዘሩት ሌሎች የንግድ አላማዎች ሊጠቀምበት አይችልም፤ወይም በዚህ ረገድ የሕግ ጥበቃ አልተሰጠዉም፡፡ተጠሪ የሚሰጠዉ አገልግሎት የንብረት አስተዳደር አገልግሎት ነዉ፡፡ቀደም ሲል ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአመልካቹ የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ መቃወሚያ ያቀረበዉ ምልክቱን ለንብረት አስተዳደር አገልግሎት ይጠቀምበታል በሚል ግምት ነበር፡፡ነገር ግን የንግድ ምልክቱ የሚያገለግለዉ ለንብረት አቻ ግምት(Asset valuation Services) ሥራዎች መሆኑን ተጠሪ ስለተረዳ ያቀረበዉ መቃወሚያ ዉድቅ ሲሆን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ማሻር አላስፈለገዉም፡፡በመሆኑም የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ አልተሻረም በሚል ያቀረበዉ መከራከሪያ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም፡፡አመልካች እንደራስ ናሽናል የንብረት አስተዳደር የሚል ስም በንግድ ምልክትነት ወይም በንግድ ስምነት ሳያስመዘግብ የንግድ ምልክቱን የምጠቀምበት እንደራስ ናሽናል የንብረት አስተዳደር ለሚለዉ አገልግሎት ነዉ ማለቱ ሀሰት ነዉ፡፡የንግድ ስሙ እንደራስ ናሽናል ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር እንደሆነ የመመስረቻ ጽሁፉ ያሳያል፡፡ተጠሪ ለአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተቃዉሞዉን ያቀረበዉ ምልክቱን ለንብረት አቻ ግምት እየተጠቀምኩ ነዉ በሚል ሳይሆን አመልካቹ ምልክቱን ለንብረት አስተዳደር(Property Administration) ሊጠቀምበት ያለ መስሎት ስለነበር ሲሆን ይህ አለመሆኑን ሲረዳ በተቃዉሞዉ አለገፋበትም፡፡የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የአስተዳደር ፍርድ ቤት በመሆኑ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ዉሳኔ ስለማይገደዱ እና ጽ/ቤቱ ሁለቱንም ምልክቶች ያሳስታል አያሳስትም የሚለዉን ሳያነጻጽር የወሰነዉ ዉሳኔ በመሆኑ አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የጽ/ቤቱን ዉሳኔ እንደገና አይተዋል በሚል ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡

በተጨማሪም ተጠሪ የሚጠቀምበት የንግድ ምልክትና ስም አመልካች ከሚጠቀምበት የንግድ ስምና ምልክት ጋር በቅርጽም ሆነ በይዘት ስለማይመሳሰል እና ግንኙነት የሌላቸዉ እንደሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጦ የተወሰነ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ የንግድ ምልክቴን ህብረተሰቡን በሚያሳስት መልኩ

እየተጠቀመ ነዉ ያለዉ የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር መሰረት የለዉም፡፡አመልካቹ በተጠሪዉ የንግድ ስም የሚታየዉ የንግድ ምልክት ወይም ምስል ከእኔ የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት ስለሆነ ሕዝብ ያሳስታል የሚል ክርክር አቅርቦ ስለነበር ይህንን ለማጣራት ፍርድ ቤቱ የአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ የምስክር ወረቀትና የተጠሪ የንግድ ስም ምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲቀርብ የስር ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ትእዛዝ ሰጥቶ እንዲያቀርብ የተደረገ በመሆኑና ፍርድ ቤቱ በማንኛዉም ጊዜ ማስረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት የሚችል በመሆኑ ይህንን አመልካች እንደ ስህተት መቁጠሩ ተቀባይነት የለዉም ፡፡ ተጠሪ የንግድ ስም እንጂ የንግድ ምልክት የለዉም፡፡ እንዲሁም ተጠሪ በአመልካች የንግድ ምልክት ላይ የፈጸመዉ ጥሰትም ሆነ ያደረሰዉ ጉዳት ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ የፈጸሙት ስህተት የለም በማለት መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በቀን 16/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም “እንደራስ ናሽናልስ እሴት ማኔጅመነት” በእንግሊዝኛዉ “ENDERAS NATIONAL ASSET MANAGEMENT” የሚል ቃል እና ምስል ያለበት የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተመዝግቦ የሚገኘዉ በአመልካች ባለቤትነት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ለአመልካች ይህ የንግድ ምልክት በምዝገባ ቁጥር LTM/3042/2009 የተመዘገበላቸዉ በአለም አቀፍ ምድብ 36 ለንብረት አቻ ግመታ ሥራዎች እንደሆነም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንዲሁም ተጠሪ “እንደራስ የንብረት አስተዳደር አገልግሎት” በእንግሊዝኛ “ENDERAS PROPERTY ADMINISTRATION SERVICE” በሚል የሚታወቅ የንግድ ስም ያስመዘገበዉ በቀን 11/07/2004 ዓ/ም ሲሆን በንግድ ምልክትነት ግን እንዳላስመዘገበ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ እና ከግራ ቀኝ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ አመልካች ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ የንግድ ምልክቱን በአለም አቀፍ ምድብ 36 አስመዝግቤ እያለሁ ተጠሪ ከአመልካች ጋር አንድ አይነት የሆነና አሳሳች የንግድ ስም እና የንግድ ምልክት የሚጠቀም በመሆኑ በንግድ ስያሜነት እና በንግድ ምልክትነት መጠቀሙን እንዲያቆምና ብር 400,000.00 ካሳ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በሚል ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ እየተጠቀምኩ ያለሁት የንግድ ስም “እንደራስ የንብረት አስተዳደር አገልግሎት” በእንግሊዝኛ “ENDERAS PROPERTY ADMINISTRATION SERVICE” የሚል በመሆኑ ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር አይመሳሰልም፤አመልካች የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበዉና የሕግ ጥበቃ ያገኘዉ ለንብረት አቻ ግምት ሲሆን ተጠሪ ደግሞ የንግድ ስሙን እየተጠቀመ ያለዉ ከንብረት አስተዳደር አገልግሎት ጋር

በተያያዘ በመሆኑና "እንደራስ" ከሚለዉ ቃል በስተቀር ቃላቶቹ ስለማይመሳሰሉ ህበረተሰቡን አያሳስትም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንዲሁም አመልካች በክሱ ላይ እንደገለጸዉ የንግድ ምልክቱ በምዝገባ ሂደት ላይ እያለ የንግድ ምልክቱ ለአመልካች መመዝገቡን የሚቃወም ካለ ተቃዉሞዉን እንዲያቀርብ በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በማስታወቂያ በተደረገዉ ጥሪ መሰረት ተጠሪ ለአመልካች የንግድ ምልክቱ እንዳይመዘገብ ተቃዉሞ አቅርቦ የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት የተጠሪን ተቃዉሞ መርምሮ በቀን 09/10/2009ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተቃዉሞዉን ባለመቀበል የንግድ ምልክቱን ለአመልካች መመዝገቡን በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ዉስጥ የሚገኘዉ የጽ/ቤቱ ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡ አመልካች ይህንን የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዉሳኔ እና አመልካች ለጽ/ቤቱ ጽፎ የነበረዉን መቃወሚያ በማስረጃነት በማቅረብ ካስመዘገብኩት የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት የሆነ ሕብረተሰቡን በሚያሳስት መልኩ በንግድ ስምነት ወይም ምልክትነት ተጠሪ መጠቀሙን እንዲያቆም ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የንግድ ምልክቱ ለአመልካች እንዳይመዘገብ ተቃዉሞ እንደነበርና ተቃዉሞዉ ዉድቅ እንደተደረገ አምኖ በይግባኝና በሌላ አኳኋን በተቃዉሞዉ ያልገፋዉ ተቃዉሞዉን አቅርቦ የነበረዉ አመልካች ምልክቱን ለንብረት አስተዳደር አገልግሎት የሚያስመዘግብ መስሎት እንደሆነና በኋላ ለተጠሪ የንግድ ምልክቱ የተመዘገበዉ ለንብረት አቻ ግምት(Asset valuation Services) አገልግሎት መሆኑን በመረዳቱ እንደሆነ ገልጾ ተከራክሯል፡፡ በዚህ አግባብ የቀረበዉን የግራ ቀኙን ክርክር የሰሙት የሥር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃዎች መርምረዉ አመልካች የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበዉ አለም አቀፍ ምድብ 36 ለንብረት አቻ ግመታ መሆኑንና ምልክቱም ከተጠሪ የንግድ ሥም ጋር ስለማይመሳሰል ኅብረተሰቡን ስለማያሳክር ተጠሪ የንግድ ስሙን መጠቀም ይችላል በማለት የአመልካችን መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ ወስነዋል፡፡

በመሰረቱ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2/12 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 2/10 ላይ እንደተመለከተዉ የንግድ ምልክት የአንድን ነጋዴ ወይም ኩባንያ እቃ(ምርት) ወይም አገልግሎት ከሌላዉ ነጋዴ/ኩባንያ እቃ(ምርት) ወይም አገልግሎት ለመለየት የምልክቱ ባለቤት የሚጠቀምበት የአእምሮ ፈጠራ ዉጤት ሲሆን የንግድ ስም ደግሞ አንድ ነጋዴ/ኩባንያ በንግድ ሥራዉ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚታወቅበትና ኅብረተሰቡ ከሌላ ነጋዴ/ኩባንያ ለይቶ እንዲያዉቀዉ ለማድረግ የሚገለገልበት መጠሪያዉ ነዉ፡፡ እንዲሁም በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እንደተመለከተዉ የንግድ ምልክት የሚመዘገበዉ በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሲሆን የንግድ ስም የሚመዘገበዉ ደግሞ በንግድ ሚኒስቴር ነዉ፡፡በዚህ አግባብ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የመመዝገብ አሰራር በሌሎች አገሮችም የተለመደ ቢሆንም ይህ አሰራር ኅብረተሰቡን በሚያመሳክር ሁኔታ አንድ አይነት ወይም በጣም

የተቀራረበ የንግድ ምልክትና የንግድ ስም የተለያዩ ሰዎች እንዲያስመዘግቡ አሉታዊ አጋጣሚ የሚፈጥር አሰራር ሊሆን ይችላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 501/1998 ከአንቀጽ 26 እስከ 28 ድረስ በተደነገገዉ መሰረት የንግድ ምልክት በማስመዝገብ ባለቤት የሆነ ሰዉ የንግድ ምልክቱን ካስመዘገበበት እቃ ወይም አገልግሎት ጋር አያይዞ የመጠቀም ወይም ሌላ ሰዉ እንዲጠቀምበት የመፍቀድ እንዲሁም ሌላ ሰዉ ማንኛዉንም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ ምልክቱ ከተመዘገበባቸዉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ወይም ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳኋን ከሌሎች እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ እንዳይጠቀሙ የማገድ መብት አለዉ፡፡ እንዲሁም የንግድ ምልክቱን ወይም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ ያለበቂ ምክንያቶች ጥቅሙን ሊጎዳ በሚችል አኳኋን ሌላ ሰዉ እንዳይጠቀም እና መሰል ድርጊቶች እንዳይፈጸሙ ለማገድ/ለመከላከል የሚያስችል መብት አለዉ፡፡ይህም የንግድ ምልክቱን በባለቤትነት ያስመዘገበዉ ሰዉ ላስመዘገበበት የዓለም አቀፍ ምድብ የንግድ ምልክቱን በብቸኝነት የመጠቀም መብት(Exclusive Right) እንዳለዉ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

አንድን በንግድ ምልክትነት የተመዘገበ ማንኛዉንም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ ምልክቱ ከተመዘገበባቸዉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ወይም ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳኋን ከሌሎች እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ እንዲሁም የንግድ ምልክቱን ወይም የንግድ ምልክቱን የሚመስል መለያ በንግድ ምልክትነት ወይም በንግድ ስምነት ያለበቂ ምክንያቶች የንግድ ምልክቱን ባለቤት ጥቅም ሊጎዳ በሚችል አኳኋን እና በመሰል ድርጊቶች ሌላ ሰዉ ተጠቅሟልና ፍርድ ቤቱ ያስቁምልኝ የሚል ክርክር ሲቀርብ ፍርድ ቤቶች የተባሉት ድርጊቶች መፈጸም አለመፈጸማቸዉን በተከራካሪዎቹ ማስረጃዎች በማረጋገጥ እና አስፈላጊ ከሆነም የልዩ አዋቂ ሙያዊ ምስክርነት ቃል በመስማት የፍሬ ነገሩን መኖር አለመኖር አረጋግጠዉ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት መወሰን ይገባቸዋል፡፡እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ የንግድ ምልክቱ የተመዘገበበትን ምድብ እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ምንነት የሚመለከት ክርክር ቀርቦ ከሆነና የንግድ ምልክቱ የተመዘገበዉ የዓለም አቀፍ የንግድ ምልክት ምድብ ቁጥር ተጠቀሶ ከሆነ ጉዳዩ የንግድ ምልክት ምዝገባ የሚካሄድበትን ዓለም አቀፍ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ምድብ ለመወሰን በፈረንሳይቱ ናይስ ከተማ ከወጣዉ ናይስ ስምምነት እና በስምምነቱ ለምድቦቹ ከተሰጠዉ ማብራሪያ (Nice Agreement Concerning the International Classification of Goods and Services for the Purposes of the Registration of Marks)ጋር አገናዝቦ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም የንግድ ምልክትም ሆነ የንግድ ስም ተመዝግቦ የሕግ ጥበቃ የሚደረገዉ ለነጻ ገበያ ዉድድር እንቅፋት ባልሆነ አኳኋን የአእምሯዊ ንብረት መብት እንዲጠበቅ በማድረግ ሰዎች ለፈጠራ እንዲነሳሱ ለማድረግ እና ኢኮኖሚያዊ ቀልጣፋነትንና ማኅበራዊ ደህንነትን በማስፈን የንግድና

የኢንቨስትመንት አሰራር ለማቀላጠፍ ነዉ፡፡በንግድ ምልክትና በንግድ ስም መካከል መመሳሰል ኖሮ ሕዝቡን ያሳስታል እንዲሁም የአንዱ ባለቤት የሌላዉን ጥቅም በሚጎዳ አኳኋን መለያዉን ጥቅም ላይ አዉሏል የሚል ክርክር ከቀረበም በዚህ አግባብ ተፈጸመ የተባለዉ ድርጊት የተፈጸመዉ በንግድ ሥራ ሂደት ዉስጥ ማንኛዉንም ሀቀኛ ያልሆነ፣አሳሳች ወይም አታላይነት ያለበት እና የተወዳዳሪን የንግድ ጥቅም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ለመፈጸም በማሰብ ወይም የአንደኛዉን ተወዳዳሪነት ለመቀነስ በማለም እና በመሰል ተግባራትና ዓላማ የተፈጸመ ነገር መኖሩ ሲረጋገጥ የንግድ ምልክቱ ወይም የንግድ ስሙ ከተመዘገበበት ዓላማ ዉጭ ተገቢ ያልሆነ የንግድ ዉድድር በመፍጠር የንግዱን ማኅበረሰብና ሕዝቡን የሚጎዳ አሉታዊ ተጽእኖ ይፈጥራል፡፡ ስለሆነም እንዲህ አይነት ክርክር ሲነሳ በንግድ ምልክት እና በንግድ ስም መካከል መመሳሰል ኖሮ ሕዝቡን በሚያሳስት ሁኔታና አስመዝጋቢዉን በሚጎዳ መልኩ አገልግሎት ላይ ሲዉል አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችል የሕግ ማእቀፍ የለም ተብሎ የሚታለፍ ሳይሆን ከንግድ ዉድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ፣ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008፣በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና የእነዚሁ አዋጆች ማስፈጸሚያ ደንቦችን ጨምር መመርመርና ተገቢውን መወሰን ይገባል፡፡

ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር የያዝነዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ የንግድ ምልክቱ ሲመዘገብ ተጠሪ ተቃዉሞ አቅርቦ ተቃዉሞዉ በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ዉድቅ ተደርጎ ለአመልካች በንግድ ምልክትነት ከተመዘገበ በኋላ ተጠሪ ከንግድ ምልክቱ ጋር አንድ አይነት የሆነ አሳሳች የንግድ ስም እና የንግድ ምልክት እየተጠቀመ በመሆኑ በንግድ ስም ስያሜነት እና በንግድ ምልክትነት መጠቀሙን እንዲያቆም ይወሰንልን በሚል ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ ተቃዉሞ አቅርቤ የነበረዉ አመልካች የንግድ ምልክቱን ለንብረት አስተዳደር አገልግሎት ያስመዘግባል በሚል ስጋት ቢሆንም መቃወሚያ ካቀረብኩ በኋላ የንግድ ምልክቱ ለአመልካች እየተመዘገበ ያለዉ ለንብረት አቻ ግመታ መሆኑን ሳረጋግጥ በተቃዉሞዬ አልገፋሁም እንዲሁም “እንደራስ” ከሚለዉ ቃል በስተቀር የአመልካች የንግድ ምልክትና የተጠሪ የንግድ ስም ስለማይመሳሰል ሕዝቡን አያሳስትም በማለት ተከራክሯል፡፡የግራ ቀኙ ክርክር ይህንን የሚመስል ከሆነ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ተቃዉሞዉን ለአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ያቀረበዉ አመልካች በንግድ ምልክትነት እንዲመዘገብለት የጠየቀዉ መለያ ተጠሪ በንግድ ምልክትነትና በንግድ ስምነት ሲጠቀም ከነበረዉ ጋር አንድ አይነት ስለሆነ ወይም ስለሚመሳሰል ሕዝቡን ስለሚያሳስት ለአመልካች ሊመዘገብለት አይገባም በሚል ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ሊጣራና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ይህንን ፍሬ ነገር ለማጣራት ተጠሪ በቀን 05/12/2008 ዓ/ም በቁጥር እንአ/01/012/2008 ጽፎ ለአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ያቀረበዉ መቃወሚያ ነዉ ብሎ አመልካች በማስረጃነት ያቀረበዉ ሰነድ ይዘትና አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በጉዳዩ ላይ በቀን 09/10/2009ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እንደሆነ በመግለጽ በማስረጃነት ያቀረበዉ ማስረጃ ተገቢዉ ዋጋ ተሰጥቶት ከክርክሩ ጋር

ተገናዝቦ ሊመዘን ይገባል፡፡ሆኖም የሥር ፍርድ ቤቶች እነዚህ ማስረጃዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸዉ ሆነዉ እያሉ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት አለመመዘናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህ የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

እንዲሁም አመልካች የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበዉ ለንብረት አቓ ግመታ ዓለም አቀፍ ምድብ 36 መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ተጠሪ ማንኛዉንም የንግድ ምልክቱን በሚመስል አኳኋን በንግድ ስምነት ምልክቱ ከተመዘገበበት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ወይም ሕዝብን ሊያሳስት በሚችል አኳኋን ከሚሰጠዉ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የአመልካችን ጥቅም ሊጎድ በሚችል አኳኋን መጠቀም አለመጠቀሙን አመልካች በምስክርነት የቆጠራቸዉን ምስክሮች በመስማት ሊጣራና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡በተጨማሪም ምስክሮቹ በሚሰጡት ምስክርነት ቃል መነሻ ወይም ከክርክሩ ባህርይ በመነሳት ለክርክሩ ዉሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ መስሎ ከታየም የሥር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 136 መሰረት ልዩ አዋቂ(ኤክስፔርት) በማስረጃነት አስቀርቦ በመስማት ማረጋገጥ ሲገባዉ በዚህ አግባብ ሳያጣራ ተጠሪ በንግድ ስምነት የሚጠቀመዉ መለያ ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር አይመሳሰልም፤ተጠሪ የሚጠቀመዉ የንግድ ስም ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር ሲነጻጸር አማካይ የሆነ (Average)ተጠቃሚን አያሳክርም በማለት ችሎቱ በራሱ ግንዛቤ ድምዳሜ ላይ መድረሱ ፍርድ ቤቱ የገለልተኝነት መርህ ጠብቆ አንድን ፍሬ ነገር በመጀመሪያ ተከራካሪ ወገኖች አስቀድሞ የማስረዳት ሸክም ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ እንዲያስረዱ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ አንጻራዊ እዉነታ ለማረጋገጥ ካለበት ኃላፊነት አንጻር ተጨማሪ ማስረጃ ማስቀረብ ካለበትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 136 እና 264 መሰረት አግባብነት ያለዉን ማስረጃ አስቀርቦ አጣርቶ መወሰን እንደሚገባዉ የሚያስገነዝበዉን የክርክር አመራርና የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ያልተከተለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ግምት (presumption) በመዉሰድ መወሰን የሚችሉት ሕግ በግልጽ ሲፈቅድና ግምት የሚወሰድበት ነገር በገሀዱ አለም በአብዛኛዉ ሰዉ ዘንድ የሚታወቅ እና የተፈጥሮ እዉነታ ሲሆን እንጂ ሕግ ግምት በመዉሰድ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር ነዉ ብሎ በግልጽ ያልደነገገዉን የተጠቀሰዉን አይነት በልዩ አዋቂ ምስክርነት ጭምር በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባ ፍሬ ነገር ሁሉ በግምት ላይ ተመስርቶ እንዲወሰን በተግባር የዳበረዉ የዳኝነት አሰጣጥ ፍልስፍና (Judicial Jurisprudence) እና የማስረጃ ሕግን የሚመለከቱ መርሆዎች ስለማይፈቅዱ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

# ዉ ሳ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 171664 ላይ በቀን 26/06/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌደራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 239171 ላይ በቀን 23/04/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ፡-

   2.1 ተጠሪ ተቃዉሞዉን ለአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ያቀረበዉ አመልካች በንግድ ምልክትነት እንዲመዘገብለት የጠየቀዉ መለያ ተጠሪ በንግድ ምልክትነትና በንግድ ስምነት ሲጠቀም ከነበረዉ ጋር አንድ አይነት ስለሆነ ወይም ስለሚመሳሰል ሕዝቡን ስለሚያሳስት ለአመልካች ሊመዘገብለት አይገባም በሚል ነዉ ወይስ አይደለም፣ ተጠሪ ተቃዉሞዉን ያቀረበዉ አመልካች እንዲመዘገብለት የጠየቀዉ የንግድ ምልክት ከተጠሪ በንግድ ስምነትና ምልክትነት ከሚጠቀመዉ ጋር ስለሚመሳሰል ሕዝቡን ያሳክራል በሚል መሆኑን የቀረበዉ ማስረጃ የሚያሳይ ከሆነም ለማስረጃዉ ተገቢዉ ዋጋ ሰጥቶ መዝኖ ሊወሰን ይገባል ብለናል፡፡

   2.2 ተጠሪ በንግድ ስምነት የሚጠቀመዉ መለያ ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር የሚመሳሰል መሆን አለመሆኑን እና ተጠሪ የሚጠቀመዉ የንግድ ስም ከአመልካች የንግድ ምልክት ጋር ሲነጻጸር ምክንያታዊ በሆነ ሰዉ መመዘኛ ሲታይ ሕዝብን ያሳስታል ወይስ አያሳስትም፤ ያሳስታል ወደሚል ድምዳሜ ላይ ከተደረሰም አመልካች ባቀረበዉ ዳኝነት ጥያቄዎች ላይ ተመስርቶ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮና ምስክሮች በመስማት እንዲሁም እንደነገሩ ሁኔታ ተገቢዉን ተጨማሪ ማስረጃና ምስክሮች አስቀርቦ ሰምቶና መርምሮ ከላይ በፍርዱ ላይ ከተመለከቱት የሕግ ማእቀፎች ጋር አገናዝቦ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

# ት እ ዛ ዝ

1.የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ሲጠይቁ ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡

2. በትእዛዝ የመጣዉ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መ/ቁጥር 171664 የሆነዉ መዝገብ ለምድብ ችሎቱ ይመለስ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 197994

ሚያዚያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማኅበር

ተጠሪ፡- አቶ ዳዊት ገ/ሀና

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ ኢንሹራንስ ገቢ እንዲሸፍን የሚደረገዉ ክፍያ ወይም የራስ ኪሳራ ወይም በተለምዶ የአደጋ መነሻ ዋጋ (*Excess*) በሚል የሚገለጸዉን አፈጻጸምና ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ በደቡብ ክልል ሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ በግራ ቀኙ መካከል በውል ቁጥር MTC/1356/17H5 በተደረገ ስምምነት በአመልካች ስም በተመዘገበዉና የሰሌዳ ቁጥር 03-90046 ኢት በሆነው ሲኖትራክ ተሽከራከሪ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ብር 1,900,000.00(አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ካሳ ለመክፈል ተስማምቷል፡፡ተሽከርካሪዉ በቀን 29/09/2010 ዓ/ም በሆሳዕና ከተማ ባቴና ወንዝ ድልድይ ላይ ከሰሌዳ ቁጥር 3-92155 ኢት ከሆነ ሌላ ሲኖትራክ ተሽከርካሪ ጋር የተጋጨ ሲሆን በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ጥፋተኛዉ የሰሌዳ ቁጥር 3-92155ኢት መሆኑ በሌሞ ወረዳ ትራፊክ ፖሊስ ተረጋግጧል፡፡አመልካችም ይህንን በማረጋገጥ በቁጥር CL/MTC/0552/18/H5 ላይ በቀን 22/03/2011 ዓ/ም ከተሽከርካሪው የገበያ ዋጋ ላይ የአደጋ መነሻ ብር 360,000.00(ሦስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) ተቀናሽ በማድረግ ብር 1,440,000.00(አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) ለተጠሪ ከፍሏል፡፡ ሆኖም አመልካች በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው አደጋ በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት የመድን ሽፋን ብር 1,900,000.00 በውላችን መሰረት መክፈል ሲገባው የአደጋ መነሻ ዋጋ በሚል ብር 360,000.00 ከመቀነሱም በተጨማሪ መክፈል ከነበረበት ክፍያ ላይ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ ብር) ያለምክንያት ተቀናሽ አድርጓል፡፡ ስለሆነም አመልካች ያላግባብ ተቀናሽ ያደረገውን 360,000.00 እና ብር 100,000.00 በድምሩ ብር

460,000.00(አራት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በግራ ቀኙ መካከል እ.ኤ.አ ማርች 18 ቀን 2019ዓ/ም በተደረገ ስምምነት ተጠሪ ከተከፈላቸዉ ካሳ በተጨማሪ ምንም ዓይነት የጉዳት ካሳ ላለመጠየቅ ስለተስማሙ ይሕም ስምምነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731 መሰረት ለግራ ቀኙ ሕግ ሆኖ የሚያገለግልና ጸንቶ የሚገኝ በመሆኑ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ፡፡ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት የንግድ ሕጉ አንቀፅ 678 በሚፈቅደው መሰረት ተጠሪ መካስ ያለባቸው ተሽከርካሪው አደጋው በደረሰበት ወቅት በሚኖረው የገበያ ዋጋ በመሆኑ ይህንኑ ለማረጋገጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተጎዱ ንብረቶችን ለመገመት ፈቃድ በተሰጠዉ የንብረት ገለልተኛ ገማች ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ በሚገመትበት ወቅት የተሽከርካሪዉ የገበያ ዋጋ ተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ጨምሮ እስከ ብር 1,800,000.00(አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ብር) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚሁ ስሌት በውሉ መሰረት የአደጋ መነሻ ብር 360,000.00 ተቀናሽ በማድረግ ብር 1,440,000,00(አንድ ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሺህ ብር) ካሳ ክፍያ ለተጠሪ ተፈፅሟል፡፡ስለዚህ አመልካች ለተጠሪ ካሳ የከፈለዉ በሕጉ አግባብ በተሽከርካሪዉ ላይ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የነበረዉን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት የብር 100,000.00 ተጨማሪ ካሳ ጥያቄ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ በተጨማሪም በግራ ቀኝ መካከል በተደረገ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ የተጠሪ ጥፋት ባልሆነበት ሁኔታ የአደጋ መነሻ አይቀነስም የሚል ቅድመ ሁኔታ በማድረግ የተፈጸመ የውል ስምምነት ባለመኖሩ ከዚህ ጋር ተያይዞ ተጠሪ ጉዳቱ የደረሰዉ በሌላ ተሽከርካሪ ጥፋት ነዉ በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 21438 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 10/07/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች ተጠሪን ምንም አይነት ተጨማሪ የጉዳት ካሳ ጥያቄ ላለማቅረብ ተስማምቷል በማለት ቢከራከርም በዚህ መሰረት የተደረገ የዉል ስምምነት በማስረጃነት ለፍርድ ቤቱ ስላላቀረበ ከዚህ አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም ሲል ዉድቅ አድርጓል፡፡ የተሽከርካሪዉ የገበያ ዋጋ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተጎዱ ንብረቶችን ለመገመት ፈቃድ በተሰጠዉ ባለሙያ ኤልያስ ራጋሳ ተገምቶ ብር 1,800,000.00(አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ብር) መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው የመድን ዋስትና ውል(ፖሊሲ) ከጠቅላላ የመድን ሽፋን ገንዘብ አደጋ መነሻ ተቀንሶ እንደሚከፈል በመድን ዋስትና ውል ላይ በግልፅ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ አመልካች ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሳይኖር ተሽከርካሪ አደጋው በደረሰበት ወቅት ከነበረው የገበያ ዋጋና በባለሙያ ተገምቶ ከቀረበው ገንዘብ ብር 360,000.00 ቆርጦ አመልካች ማስቀረቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም አመልካች ተቀናሽ ያደረገውን ብር 360,000.00 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ሲል ወስኗል፡፡በሌላ በኩል ለንብረት የሚሰጥ የኢንሹራንስ ሽፋን አደጋው በደረሰበት ጊዜ ንብረቱ የነበረውን ዋጋ ለመካስና ንብረቱ በመጎዳቱ ምክንያት በባለንብረቱ ላይ የደረሰውን

ኪሳራ በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ከተመለከተው ገንዘብ ሳይበልጥ መከፈል እንዳለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 665(1 እና 2)፣678(1 እና 2) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 69966 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ብር 100,000.00 ተቀነሰብኝ ብለዉ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 15153 ላይ በቀን 28/12/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞበታል፡፡ አመልካች በቀን 07/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ለተጠሪ በተሽከርካሪዉ ላይ ጠቅላላ ዉድመት ስለደረሰበት ካሳ ከተከፈለ በኋላ ተጨማሪ ክፍያ አልጠይቅም ብለዉ የተስማሙበትን ስምምነት በመጥቀስ ክሱ ዉድቅ እንዲሆን አመልካች ያቀረበዉን መከራከሪያ የሥር ፍርድ ቤት በዝምታ ማለፉ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡በግራ ቀኙ መካከል በተደረገዉ የመድን ዋስትና ሽፋን ዉል ሰንጠረዥ እና ፖሊሲዉ መሰረት በተሽከራካሪዉ ላይ ለሚደርስ ጠቅላላ ዉድመት ከሚከፈለዉ የካሳ ክፍያ ላይ በዉሉ ላይ ኢንሹራንስ ገቢዉ የአደጋ መነሻ (Excess)10% የመተካት ኃላፊነት የተጠሪ ነዉ፡፡ ተጠሪ ለዚህ በሰጡት መልስ ያሰሙት ክርክር የዉሉን የአደጋ መነሻ ተጠሪ ለመክፈል የምገደደዉ አደጋዉ በእኔ ጥፋት የደረሰ ከሆነ ነዉ የሚል እንጂ በዉሉ ላይ የአደጋ መነሻ ለመክፈል አልተስማማሁም የሚል አይደለም፡፡የተጠሪ ክርክር ይህ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት የአደጋ መነሻ መቀነስ እንዳለበት የተደረገዉ የዉል ስምምነት ግልጽ አይደለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ከጭብጥ ዉጭ ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች ለተጠሪ ከከፈለዉ ካሳ ላይ ቀንሶ ያስቀረዉ ብር 360,000.00 በዉሉ በግልጽ የተመለከተና በተጠሪም ያልተካደ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት የሕግ መሰረት የለዉም ሲል ዉድቅ ማድረጉ መሰረታዊ ስህተት ነዉ፡፡በአመልካች የአደጋ መነሻ በዉሉ የተመለከተዉ 10% እጥፍ ተደርጎ መቀነሱ ከዉል ዉጭ ነዉ የሚል ክርክር በተጠሪ ተነስቶ ስለነበር አመልካች እጥፍ ተደርጎ የተቀነሰዉ በተሽከርካሪዉ ላይ አደጋዉ የደረሰዉ በምሽት ሲሽከረከር ወይም አዲስ መንጃ ፈቃድ በያዘ ግለሰብ ሲሽከረከር ከሆነ የአደጋ መነሻዉ ሊቀነስ የሚገባዉ በእጥፍ ይሆናል የሚል የዋናዉ የዉል አካል የሆነ ተጨማሪ ዉል(Endorsement) አመልካች በማስረጃነት ማቅረብ ባለመቻሉ እንደተጠሪ ክርክር በእጥፍ ብር 360,000.00 መቀነስ የለበትም ቢባል እንኳን የሥር ፍርድ ቤት መቀነስ ያለበት በዋናዉ ዉል መሰረት ከአጠቃላይ ካሳ ከብር 1,800,000.00 ላይ 10% ብር 180,000.00 ነዉ ብሎ ክስ ከቀረበበት ገንዘብ ላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 180,000.00 ብር ብቻ እንዲመልስ መወሰን ሲገባዉ አመልካች ለተጠሪ ብር 360,000.00 ይክፈል ብሎ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊሻሻል ይገባል በማለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉንና የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመመርመር ግራ ቀኙ በኢንሹራንስ ዉሉ ሰንጠረዥ ላይ የአደጋ መነሻ በተመለከተና መቀነስ ያለበት ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ ስምምነት ስለማድረጋቸዉ ተመልክቶ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን አልፎ የወሰነበትን አግባብነት ከኢንሹራንስ ዉሉ አኳያ ተጠሪ ባለበት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 24/05/2013 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች መክፈል የሚገባዉ ካሳ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 678 መሰረት እና በሰ/መ/ቁጥር 48698 መሰረት የተሽከርካሪዉን የወቅቱን ዋጋ ነዉ፡፡ሆኖም የተሽከርካሪዉ የወቅቱ ዋጋ ከብር 2,000,000 በላይ ሆኖ ሳለ የተጎዳዉን ተሽከርካሪ ግምት ብር 1,800,000.00 አድርጎ 10% ቀንሶ ብር 1,440,000.00 ብቻ መክፈሉ ሕግን መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡አመልካች እጥፍ የአደጋ መነሻ የሚያስቀነስ ተጨማሪ ዉል አለ ብሎ ቢከራከርም ዉሉን በማስረጃነት ባለማቅረቡ ከዚህ አንጻር በስር ፍርድ ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ከተጠሪ በኩል ምንም አይነት ጥፋት ከሌለ የአደጋ መነሻ በምንም ሁኔታ ከተጠሪ የማይቆረጥ መሆኑን በግልጽ በዉሉ ላይ ተጠቅሶ ተስማምተናል፡፡ ለደረሰዉ ጉዳት ተጠሪ ጥፋት እንደሌለበት ተረጋግጧል፡፡ስለዚህ ተጠሪ ለአደጋዉ መነሻ ሳልሆንና በእኔ ጥፋት የደረሰ ጉዳት ባልሆነበት በአመልካች የአደጋ መነሻ በሚል መቀነሱ ተገቢ ስላልሆነ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ቀንሶ ያስቀረዉን ብር 360,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍል በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካችም በቀን 08/06/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ከያዘዉ ማስቀረቢያ ነጥብ አንጻር በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ አመልካች በተጠሪ ስም በተመዘገበዉ የሰሌዳ ቁጥር 03-90046 ኢት በሆነው ሲኖትራክ ተሽከራከሪ ላይ ለሚደርስበት ጉዳት ለተጠሪ እስከ ብር 1,900,000.00(አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር) ካሳ ለመክፈል መስማማቱን ግራ ቀኙ ካለመካካዳቸዉም በተጨማሪ በስር ፍርድ ቤት በዉሉ ማስረጃነት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ እንዲሁም ይህ ኢንሹራንስ የተገባለት ተሽከርካሪ በቀን 29/09/2010 ዓ/ም ከሌላ የሰሌዳ ቁጥር 3-92155 ኢት ከሆነ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨቱ ጠቅላላ ጉዳት (total damage) የደረሰበት መሆኑም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ኢንሹራንስ የተገባለት ተጠቃሹ ተሽከርካሪ የገበያ ዋጋ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ባለዉ ገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ብር 1,800,000.00(አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ብር) እንደነበርም በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ ተጠሪ (ኢንሹራንስ ገቢዉ) እንዲሸፍን የሚደረገዉ ክፍያ/የራስ ኪሳራ (Excess) ወይም በተለምዶ

የአደጋ መነሻ ዋጋ በሚል የሚታወቀዉን ለተጠሪ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ አመልካች ቀንሶ የማስቀረቱ ሕጋዊነትና በዚህ አግባብ ሊቀነስ የሚገባዉ ገንዘብ መጠን በተመለከተ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የኢንሹራንስ ዓይነተኛ ባህሪይ ኪሳራን በሂደቱ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎች እንዲጋሩት ማድረግ (risk-distribution among a substantial number of members) ነዉ፡፡ይህም የሚሆነዉ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በኢንሹራንስ ዉሉ ሽፋን የተሰጠዉ ነገር ላይ አደጋ በደረሰ ጊዜ በዉል ወይም በሕግ የተመለከተዉን ካሳ እንዲከፍል በማድረግ እና በዚህ መልኩ በካሳ መልክ የሚከፍለዉን ገንዘብ የሚያገኘዉ ኢንሹራንስ ከገቡ በርካታ ሰዎች ከሚሰበስበዉ አርቦን (premium) ሲሆን ኢንሹራንስ ገቢዎችም አደጋዉ ከመድረሱ በፊት ለኢንሹራንስ ሰጪዉ አርቦን እየከፈሉ ኪሳራዉን እንዲጋሩት በማድረግ ነዉ፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነዉ በአንጻራዊነት ኢንሹራንስ ሰጪዎች ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያለዉን አርቦን ኢንሹራንስ ገቢዉን በማስከፈል ነዉ፡፡ በተጨማሪም ኢንሹራንስ በተገባለት ነገር ላይ ጉዳት ያደረሰዉ ሰዉ የደረሰዉን ጉዳት እንዲተካ በማድረግ ኪሳራዉ እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡በዚህ መልኩ የተገለጸዉ ኪሳራ የመጋራት አሠራር በኢንሹራንስ ንግድ ሥራ ዘርፍ በሰፊዉ የሚታወቅ ነዉ፡፡

ኢንሹራንስ ገቢዉ አርቦን በመክፈል ኪሳራ እንዲጋራ ከሚደረግበት አሠራር ባሻገር ኢንሹራንስ ገቢዉ ኪሳራ እንዲጋራ የሚደረግበት ሌላዉ አሠራር ኢንሹራንስ ገቢዉ በዉሉ ከኢንሹራንስ ሰጪዉ ጋር በሚያደርገዉ ስምምነት በሚወሰነዉ መጠን ልክ አደጋዉ ሲደርስ ኢንሹራንስ ሰጪዉ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ ጉዳቱን ለመካስ የሚያስችል ተጨማሪ ክፍያ ለመክፈል ወይም ካሳዉ ለኢንሹራንስ ገቢዉ የሚከፈል በሆነ ጊዜም ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በዉሉ በተመለከተዉ መጠን ልክ ቀንሶ እንዲያስቀር በፈቃደኝነት በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ የሚስማማበት ሲሆን ይህም በኢንሹራንስ ንግድ ሥራ ዘርፍ የራስ ኪሳራ(የአደጋ መነሻ) በእንግሊዝኛዉ *Excess/Own Damage* ተብሎ የሚታወቅ ነዉ፡፡ በዘርፉ ከተጻፉ ድርሳናት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በእንዲህ አይነት ስምምነት በስተጀርባ ያለዉ የፖሊሲ ምክንያትና ዓላማ ኢንሹራንስ ገቢዎች የኢንሹራንስ ሽፋን የገቡለትን ነገር በግድየለሽነት በመጠቀም ጉዳት እንዳያደርሱበት ለማድረግ ወይም ተገቢዉን ጥበቃ እንዲያደርጉለት ለማስቻል ወይም በጥቅሉ በተቻለ መጠን አደጋ ለመቀነስና ኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠዉ ነገር ለአደጋ እንዳይጋለጥ ለማድረግ የሚያስችል ኃላፊነት ኢንሹራንስ ገቢዎች እንዲወስዱ በማድረግ ካሳ የሚጠየቅበት አደጋ በደረሰ ጊዜ በስምምነቱ መሰረት በማስፈጸም ኪሳራ የማጋራቱን መሰረታዊ ዓላማ ከግብ ማድረስ ነዉ፡፡ይህም በአብዛኛዉ ተግባራዊ የሚሆነዉ በአንጻራዊነት አነስተኛ አርቦን በማስከፈል በምትኩ በዉሉ የተመለከተዉ አደጋ በደረሰ ጊዜ መጠኑ አስቀድሞ የተወሰነ ገንዘብ ኢንሹራንስ ገቢዉ እንዲከፍል ወይም ከካሳዉ ላይ ኢንሹራንስ ሰጪዉ ቀንሶ ሊያስቀር የሚችልበትን የራስ ኪሳራ(የአደጋ መነሻ/*Excess*) ስምምነት በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ በመዋዋል ነዉ፡፡በዚህ መልኩ የሚደረገዉ ስምምነት በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ወይም ሁኔታ የሌለዉ ሊሆን ይችላል፡፡ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የሚሆነዉ ኢንሹራንስ የተገባለት ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ለሚደርስ አደጋ ቢሆንና ኢንሹራንስ ገቢዉ ልምድ ለሌለዉ ወይም

አዲስ መንጃ ፈቃድ ሳወጣ አሽከርካሪ በመስጠት እንዲሽከረከር ቢያደርግ ወይም አደጋዉ የደረሰዉ ተሽከርካሪዉ በዉሉ በምሽት ማሽከርከር አይቻለም ተብሎ ተለይቶ በተገለጸበት የምሽት ሰዓት በሚሽከረከርበት ጊዜ ሲሆን የሚሉ ሁኔታዎችን በመጥቀስ አደጋዉ በደረሰ ጊዜ ከእነዚህ ሁኔታዎች አንዱ ተከስቶ ሲገኝ የኢንሹራንስ ገቢዉን ስህተት መሰረት ተደርጎ (Fault based) የአደጋ መነሻ/*Excess* ተግባራዊ የሚደረግበት አሰራር ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከትነዉን በኢንሹራንስ ሥራ ዘርፍ በተግባር ዳብሮ የሚሰራበትን አሠራር(ልማድ) በንግድ ሕጉ ስለ ኢንሹራንስ በአንቀጽ 654 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች ከተመለከተዉ አንጻር መርምረናል፡፡በዚህ ሕግ አንቀጽ 654/1 እና 658 ስር እንደተመለከተዉ በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ ከሚገለጹ ነገሮች መካከል ኢንሹራንስ ገቢዉ ስለሚከፈለዉ አርቦን ፣ኢንሹራንስ የተገባለት ንብረትና አደጋ አይነት፣የሚከፈለዉ ካሳ መጠን፣እና ከኢንሹራንስ ገቢዉ ኃላፊነት ጋር በተያያዘ የሚደረገዉ ስምምነት ወዘተ ይገኙበታል፡፡እንዲሁም በዚሁ ሕግ አንቀጽ 663/2 ስር እንደተደነገገዉ በኢንሹራንስ ሰጪዉና ገቢዉ መካከል በሚደረግ ተቃራኒ ስምምነት በኢንሹራንስ ገቢዉ ቸልተኝነት ለሚደርሰዉ አደጋ ኢንሹራንስ ሰጪዉ በሙሉም ሆነ በከፊል የጉዳት ካሳ ሊከፍል የማይችልበትን አግባብ መስማማት ይቻላል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ በኢንሹራንስ ሰጪዉና ኢንሹራንስ ገቢዉ መካከል በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ በሚደረግ ስምምነት በዉሉ የተመለከተዉ አደጋ በደረሰ ጊዜ መጠኑ አስቀድሞ የተወሰነ ገንዘብ ኢንሹራንስ ገቢዉ እንዲከፍል ወይም ከካሳዉ ላይ ኢንሹራንስ ሰጪዉ ቀንሶ ሊያስቀር የሚችለዉን የአደጋ መነሻ/*Excess* በሁኔታ ላይ በመመስረት ወይም ያለሁኔታ በኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ መዋዋል እንዲቻል ፈቃጅ ሕግ መኖሩን ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገዉ የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲ ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ኢንሹራንስ በተገባለት ተሽከርካሪ ላይ ለሚደርስ ጠቅላላ ጉዳት ከሚከፈለዉ ካሳ ወይም ጉዳቱን ለመጠገን ከሚወጣዉ ወጪ ላይ አመልካች 10% የራስ ኪሳራ(የአደጋ መነሻ) ወይም *Excess/Own Damage* ቀንሶ እንዲያስቀር ተጠሪ መስማማታቸዉን አረጋግጠናል፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731/1 ስር እንደተደነገገዉ በሕጉ አግባብ የተቋቋሙ ዉሎች ባቋቋሚቸዉ ሰዎች ላይ እንደሕግ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በተያዘዉም ጉዳይ ግራ ቀኝ ከላይ በተጠቀሰዉ መልኩ ያደረጉት ስምምነት በንግድ ሕጉ ስለ ኢንሹራንስ ሥራ በአንቀጽ 654 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች ከተደነገጉት ጠቅላላና ልዩ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣረስ ካለመሆኑም በተጨማሪ ሕጉ እንዲህ አይነት ስምምነት ማድረግን የሚፈቅድ እንጂ በግልጽ የሚከለክል ባለመሆኑ ግራ ቀኝ በዚህ አግባብ ያደረጉት ስምምነት ሊፈጸም የሚገባዉ ነዉ፡፡በመሆኑም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 678 ስር በተደነገገዉ መሰረት ኢንሹራንስ የተገባለትና ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ የነበረዉ የገበያ ዋጋ በባለሙያ ተገምቶ የተረጋገጠዉ ብር 1,800,000.00 በመሆኑ በዉሉ መሰረት የዚህ ገንዘብ 10% ብር 180,000(አንድ መቶ ሰማን ሺህ ብር) እንደ የራስ ኪሳራ (የአደጋ መነሻ/ *Excess*)ለተጠሪ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ አመልካች ቀንሶ የማስቀረት መብት አለዉ፡፡

ሆኖም አመልካች ከተጨማሪ ዉል ጋር በተያያዘ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ ክርክር በዝምታ እንደታለፈበት በመግለጽ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተሽከርካሪዉ በምሽት ሲሽከረከር ወይም አዲስ መንጃ ፈቃድ በያዘ ግለሰብ ሲሽከረከር በተሽከርካሪዉ ላይ አደጋ ከደረሰበት ለተጠሪ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ ተጨማሪ 10% የአደጋ መነሻ(*Excess)* አመልካች ቀንሶ ያስቀራል የሚል የዋናዉ የዉል አካል የሆነ ተጨማሪ ዉል (Endorsement) አመልካች ከተጠሪ ጋር መዋዋሉን የሚያሳይ ማስረጃ ለስር ፍርድ ቤት አቅርቦ አለማስረዳቱን ራሱ ለዚህ ችሎት ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ላይ ያመነ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር በማስረጃ አልተደገፈም በሚል የሚነቀፍ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለተጠሪ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ በዉሉ መሰረት ብር 180,000.00 ብቻ ቀንሶ ማስቀረት ሲገባዉ ብር 360,000.00 አለአግባብ ቀንሶ ማስቀረቱን ተገንዝበናል፡፡ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ በላይ በተመለከተዉ መሰረት መርምረዉ መወሰን ሲገባቸዉ በዋናዉ ኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉ ላይ በግልጽ የተመለከተዉን ወደ ጎን በመተዉ አመልካች በዉሉ መሰረት ቀንሶ ያስቀረዉን ጭምር ለተጠሪ እንዲመልስ መወሰናቸዉ ለግራ ቀኙ እንደሕግ የሚያገለግለዉን የኢንሹራንስ ዉል ፖሊሲዉን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ተከራካሪ ወገን ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ተገቢዉንና ሕጉ በተለየ ሁኔታ የሚጠይቀዉ ማስረጃ ካለም በሕግ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ የተባለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት (የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከቷል)፡፡ አመልካች ተጠሪ ብር 1,440,000.00 ሲከፈላቸዉ ተጨማሪ ካሳ አልጠይቅም በማለት ስለተስማሙ ተጨማሪ ካሳ እንዲከፈላቸዉ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ቢከራከሩም ይህንን ዉል ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት በማቅረብ ክርክሩን አላስረዳም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከዚህ አኳያ ያቀረበዉን መከራከሪያ ዉሉን በማስረጃነት አቅርቦ አላስረዳም በማለት ዉድቅ በማድረጉ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 21438 ላይ በቀን 10/07/2012 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 15153 ላይ በቀን 28/12/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. አመልካች ለተጠሪ ብር 360,000.00(ሦስት መቶ ስልሳ ሺ.ህ ብር) እንዲከፍል የተወሰነዉን በማሻሻል ብር 180,000.00(አንድ መቶ ሰማንያ ሺ.ህ ብር) ብቻ ይክፈል ብለናል፡፡ሌላዉ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ክፍል አልተነካም

3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ግልባጩ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 204199

ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት በላይ

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋዬ ሰኚ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የደላላነት ሥራ ክፍያ የሚመለከት ነዉ፡፡ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ የንግድ ፈቃድ አዉጥቼ የደላላነት ሥራ እየሰራሁ አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ክልል ዉስጥ ያላቸዉን የቤት ቁጥሩ 146 የሆነ ቤታቸዉን ተከራይ ፈልጌ እንዳከራይላቸዉ ጠይቀዉኛል፡፡የፓኪስታን ኤምባሲ የአምባሳደሩ ፀኃፊ ለኤምባሲዉ ለቢሮና ለመኖሪያ የሚሆን የሚከራይ ቤት ሲፈልጉ እንደነበር ባለኝ መረጃ ለአምባሳደሩና ለቤተሰባቸዉ ቤቱን ለሶስት ጊዜ በማስገብኘት ቤቱን ኤምባሲዉ በቀን 22/03/2009ዓ/ም በወር በ8000 ዶላር እንዲከራይ አድርጌያለሁ፡፡በዚህ መሰረት ኤምባሲዉ ለአመልካች የስድስት ወር ኪራይ ከፍሏቸዋል፡፡ኤምባሲዉ የሚጠበቅበትን ኮሚሽን 4800 ዶላር የከፈለኝ ቢሆንም አመልካችን ወክለዉ ስምምነት ያደረጉት የአመልካች ወኪል ኮሚሽንና ቦነስ እንደሚከፍሉኝ ቃል ገብተዉልኝ የነበረ ቢሆንም አመልካች ለመክፈል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡በመሆኑም አመልካች ለፈጸምኩት የደላልነት ሥራ 4800.00 ዶላር ወይም የዚህን ምንዛሬ ከቀን 22/03/2009ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እና ክሱ ካስከተለብኝ ወጪዎች ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ባነሱት መከራከሪያ ተጠሪ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 58 መሰረት የሙያ ተግባራቸዉ አድርገዉ ጥቅም ለማግኘት በንግድ ማኅበርነት ስላልተቋቋሙ ክሱን የማቅረብ መብት የላቸዉም፡፡አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረግሁት ስምምነት የለም እንጂ ከዛሬ ሶስት ዓመት በፊትም ሆነ የኪራይ ዉሉ በተፈጸመበት ጊዜ ተጠሪ የድለላ የንግድ ሥራ ፈቃድ አዉጥተዉ ይሰሩ እንደነበር ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡በማስረጃነት ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ የኪራይ ዉሉ ከተደረገ በኋላ የወጣ በመሆኑ ሕጋዊ ደላላ ስላልሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል

መብት ስለሌላቸዉ ክሱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/1 መሰረት ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ክስ የቀረበበት ክፍያ ከ2 ዓመት በኋላ የተጠየቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2024 መሰረት በይርጋ የታገደ ነዉ የሚሉ መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡እንዲሁም ፍሬ ነገሩን በሚመለከት በሚል ባቀረቡት መልስ - በንግድ ሕጉ መሰረት አበል የሚከፈለዉ የድለላ ሥራዉን እንዲሠራ የጠየቀዉ ወገን እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ተጠሪ ቤት እንዲያከራዩልኝ ባልጠየቅሁበት እና የድለላ ዉልም ባላደረግንበት ይህን ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡አመልካች ቤቱን እንዲያከራዩልኝ የጠየቅኳቸዉ አቶ ወንድወሰን አንጋሳ እና አብርሃም ስንታየሁ የተባሉ ሰዎችን ሲሆን ለእነዚህም ተገቢዉን የደላልነት ኮሚሽን ከፍያለሁ፡፡በመሆኑም ተጠሪ ቤቱን እንዲያከራዩልኝና የደላልነት ክፍያ እንደሚከፍላቸዉ ያደረግነዉ ስምምነት ስለሌለና የገንዘብ መጠኑም የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የሌለዉ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 175620 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ አስቀድሞ በቀን 19/06/2011ዓ/ም በሰጠዉ ብይን አንድ ሰዉ የድለላ ሥራ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 56 እና ተከታዮቹ መሰረት ሠርቷል የሚያሰኝ ዝርዝር ተግባር እስከፈጸመ ድረስ ይህን ሥራ በግለሰብ ደረጃ ወይም በማኅበር በመሆን መስራት ሥለሚችልና የንግድ ፈቃድ አለመኖሩ ብቻዉን ክስ እንዳያቀርብ የሚያደርግ ስላልሆነ ከዚህ አንጻር የቀረበዉ መቃወሚያ ተቀባይነት የለዉም፡፡እንዲሁም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2024 የተደነገገዉ የ2 ዓመት የሕግ ግምት የደላልነት ክፍያን የሚያጠቃልል አይደለም በማለት ከዚህ አኳያ የቀረበዉን መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ፍሬ ነገሩን በተመለከተ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 09/03/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለኤምባሲዉ ቤት በግላቸዉ ሲያፈላልጉ እንደነበር እና የአመልካችን ቤት ለኤምባሲዉ አሳይተዉ አምባሳደሩ ከእነ ቤተሰቡ እና የኤምባሲዉ ሠራተኞች ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲጎበኙ በማድረግ ምርጫቸዉ መሆኑን ሲወስኑ አብረዉ እንደነበሩ፤የአመልካች ወኪል የሆኑት አቶ ጫኔ በላይን ከአምባሳደሩ ጋር ያገናኘዉ አመልካች እንጂ አመልካች የገለጻቸዉ ሌሎች ደላሎች አለመሆናቸዉ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡ ኤምባሲዉ በጻፈዉ ደብዳቤ አምባሳደሩን ወስደዉ የሚከራየዉን ቤት ያስጎበኙት ተጠሪ እንደሆኑ መገለጹ ተደምሮ ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የድለላ ስምምነት ማድረጋቸዉን ያሳያል፡፡ተጠሪ ቀድሞ የቤቱን አድራሻ እና ይከራያል ስለመባሉ የማያዉቁትን ቤት ለማስጎብኘት አምባሳደሩን ይዘዉ ይሄዳሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከአመልካች ጋር ቤት ለማከራየት የድለላ ስምምነት እንደነበረዉ እና በዚያዉ መሰረት ቤቱን ለፓኪስታን ኤምባሲ ማከራየታቸዉ ተረጋግጧል፡፡ስለሆነም ምስክሮች በመሰከሩት ልማድ መሰረት ለደላልነት ሥራዉ መከፈል ያለበት የአንድ ወር ኪራይ ግማሽ በመሆኑ አመልካች 4000.00 ዶላር ወይም በቀን 22/03/2009 ዓ/ም በነበረዉ ምንዛሪ መሰረት ተለዉጦ እንዲሁም ክሱ ላስከተለዉ ወጪ ብር 24,830.00 ዉሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 247744 ላይ በቀን 08/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 08/07/2013ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ የደላልነት ሥራ ሙያ ተግባራቸዉ አድርገዉ ለመሥራት የንግድ ፈቃድ ያወጡት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ኪራይ ዉል ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በማስረጃነት ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ ማስረጃ ያሳያል፡፡በመሆኑም ተጠሪ የኪራይ ዉሉ ሲደረግ በደላላነት ሥራ ላይ ያልነበሩና የንግድ ፈቃድ ስለሌላቸዉ ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም ብሎ መወሰን ሲገባዉ አመልካች ያቀረብኩትን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡አመልካችና ተጠሪ መካከል የድለላ ሥራ ዉል መኖሩንና ቤቱን እንዲያከራዩልኝ አመልካች የጠየቅኳቸዉ ስለመሆኑ ተጠሪ በአግባቡ በማስረጃ ሳያስረዱና ማስረጃ በአግባቡ ሳይመዘን በአንጻሩ አመልካች ባቀረብኳቸዉ ምስክሮች ቤቱን እንዲያከራዩልኝ የጠየቅኳቸዉ ሌሎች ደላሎችን እንደሆነና አገልግሎቱን ለሰጡኝ ደላሎች ክፍያ እንደከፈልኩኝ አስረድቼቻለሁ፡፡ ከኤምባሲዉ የመጣዉ ማስረጃም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሆኖ ሳለ አለአግባብ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ ዉሳኔዉ የንግድ ሕጉን አንቀጽ 59ን ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም 4000.00 ዶላር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠዉም ዉሳኔ የሕግና የማስረጃ ድጋፍ የለዉም በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች ተጠሪ በደላላነት ቤቱን እንዲያከራዩላቸዉ ያቀረብኩት ጥያቄ የለም በሚል ያቀረቡት ክርክር ታልፎ በኤምባሲዉ በቀረበዉ ማስረጃ መነሻ ዉሳኔ የተሰጠበትን አግባብነት ከንግድ ሕጉ አንቀጽ 59 እና ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አኳያ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 22/10/2013ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበዋል፡፡የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- የተያዘዉ ጭብጥ የፍሬ ነገር ክርክርና የማስረጃ ምዘና ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑ በተያዘዉ ጭብጥ ላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሥልጣን የለዉም፡፡የስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ ተጠሪ ከአንዴም አራት ጊዜ የቤቱን ቁልፍ በመዉሰድ የኤንባሲዉን ፀሃፊ ፣አምባሳደሩን፣ፀሃፊዉንና ሹፌራቸዉን እንዲሁም አምባሳደሩንና ቤተሰባቸዉን እንዲሁም ሰራተኞቻቸዉን በመዉሰድ ማሳየቴንና በዚህም መነሻነት ቤቱ ለኤንባሲዉ መከራየቱን በምስክሮች እና ከኤምባሲዉ በመጣዉ ማስረጃ አስረድቼ በአግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ ነዉ፡፡እንዲሁም ቤቱ ለረጅም ጊዜ አልተከራየልኝምና አከራይልኝ ኮሚሽን እከፍላለሁ በማለት በወኪላቸዉ አማካኝነት ጠይቀዉኝ በቃል ባደረግነዉ ስምምነት መሰረት በንግድ ሕጉ አንቀጽ 59/2 መሰረት በደላልነት ቤቱን እንዳከራየሁ ባቀረብኩት ምስክሮች አስረድቼ የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ 4000 ዶላር እንዲከፈላቸዉ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ሲሉ ያቀረቡት ክርክር

በምስክሮች ቃል ተረጋግጦ የተወሰነ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍሬ ነገርንና ማስረጃ ምዘናን የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባ አይደለም በማለት የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲሆን በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ በማሻሻል ተጠሪ ለአመልካች የደላላነት ሥራ ሠራሁኝ ባሉበት ጊዜ የደላላነት ሥራ ንግድ ፈቃድ ባይኖራቸዉም ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ የመጠየቅ መብት አላቸዉ በሚል የአመልካች መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤት ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት በአመልካች ጠያቂነት ቤታቸዉን በደላልነት አከራይቸላቸዉ የአበል ክፍያ አልፈጸሙልኝም በማለት 4000 ዶላር እንዲከፈላቸዉ ወይም ይህ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ እንዲከፈላቸዉ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የኪራይ ዉሉ በተደረገበት ጊዜ የደላልነት ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ተጠሪ እንደሌላቸዉ በመግለጽ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት የላቸዉም በማለት ተቃዉመዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች የደላላነት ሥራ ሠራሁኝ ባሉበት ጊዜ የደላላነት ሥራ ንግድ ፈቃድ ባይኖራቸዉም ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲከፈላቸዉ የመጠየቅ መብት አላቸዉ ሲል በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ መወሰኑን መዝገቡን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡በዚህ መልኩ የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረጉ የተፈጸመ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደመረመርነዉም አንድ ሰዉ በሌላ ሰዉ ላይ ክስ በማቅረብ በዳኝነት አካል ማስወሰን የሚችለዉ ክሱ በቀረበበት ሰዉ የተጣሰበት/ የተነካበት በሕግ ወይም በዉል እዉቅና እና/ወይም ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረዉ ይገባል፡፡(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2 እና 3) ይመለከቷል፡፡) ይሕንንም ከሳሽ በፍሬ ነገር ደረጃ በክስ አቤቱታዉ ላይ ማሳየት(ማረጋገጥ) ይጠበቅበታል፡፡በዚህ መሰረት በፍሬ ነገር ደረጃ በክሱ ላይ የተገለጸዉን በተመለከተ ሌላኛዉ ወገን ክስ በተመሰረተበት ነገር ላይ ከሳሹ በሕግ እና/ወይም በዉል እዉቅና እና ጥበቃ ያገኘ መብት ወይም ጥቅም የለዉም እንዲሁም የሚያስከስሰኝን ተግባር አልፈጸምኩም ወይም በክሱ የተገለጸዉ ድርጊት የሚያስከስስ አይደለም በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ መቃወሚያ አቅርቦ እንዲቃወም ሳይጠብቅ ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በእራሱ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2 እና 3) እና 231(1/ሀ) መሰረት የክስ አቤቱታዉን መርምሮ ተገቢዉን የመወሰን ኃላፊነት አለበት፡፡እንዲሁም ተከሳሹ ይህንን መከራከሪያ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244/2 መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሥረ ነገሩን የሚመለከት ጭብጥ ከመመስረቱና በጭብጡ ላይ ማስረጃ ከመስማቱ እና ከመመርመሩ በፊት እንደነገሩ ሁኔታ

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 245/1 መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ ዉሳኔ ለመስጠት ተገቢ ነዉ ያለዉን ማስረጃ አስቀርቦና መርመሮ ዉሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረቱት የክስ አቤቱታ ላይ የደላልነት ሥራ የሰሩት ባላቸዉ የንግድ ፈቃድ እንደሆነ ከመግለጻቸዉም በተጨማሪ ይህንን ያስረዳልኛል ያሉትን ማስረጃ በማያያዝ አቅርበዋል፡፡አመልካች ደግሞ ይህ ለክርክሩ መነሻ የሆነ የደላላነት አበል የተጠየቀበት የኪራይ ዉል በተፈጸመበት ጊዜ የደላላነት ሥራ ለመስራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ ተጠሪ አልነበራቸዉም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር ፍርድ ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ዉድቅ ያደረገዉ በወቅቱ ተጠሪ የደላላነት ሥራ ለመስራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ እንዳልነበራቸዉ አረጋግጦ የንግድ ፈቃድ ባይኖራቸዉም ክስ የማቅረብ መብት አላቸዉ በሚል ነዉ፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ አስቀርበን እንደተመለከትነዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉና ተጠሪ የደላላነት ሥራ ሠራሁኝ ያሉት የአመልካች ቤት የተከራየበት ዉል በቀን 22/03/2009ዓ/ም እንደተደረገ እና ተጠሪ ያቀረቡት የንግድ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን 10/05/2009ዓ/ም እንደሆነና የታደሰበት ቀን ደግሞ በቀን 10/05/2009ዓ/ም እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በክስ አቤቱታቸዉ ላይ የንግድ ፈቃድ እንዳላቸዉ የገለጹ ቢሆንም የአመልካችን ቤት አከራየሁኝ ባሉበት ጊዜ ተጠሪ የደላልነት ሥራ ለመስራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ እንደሌላቸዉ ተረጋግጧል፡፡ የደላላነት ሥራ በቀድሞዉ የንግድ ሕግ አንቀጽ 5/19፣ 56 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎችም ሆነ በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 5/34 መሠረት የሙያ ሥራ ተደርጎ ጥቅም ለማግኘት የሚሰራ የንግድ ሥራ ነዉ፡፡ይህ ሥራም ሆነ ይህንን ሥራ የሚሠራዉ ሰዉ የሕግ ጥበቃ ሊያገኝ የሚችለዉ እንደማንኛዉም ሰዉ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት በነጋዴነት ተመዝግቦና የንግድ ፈቃድ አዉጥቶ መሥራት ሲችል ነዉ፡፡ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 119272 ላይ በቀን 25/01/2009ዓ/ም ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ የደላላነት ሥራ ለመስራት የሚያስችል የንግድ ፈቃድ አዉጥተዉ የአመልካች ቤት በደላላነት ማከራየታቸዉን ባላረጋገጡበት የደላላነት ሥራ ስለሠራሁ የአበል ክፍያ አመልካች ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በሕግ ጥበቃ የተደረገ መብት የላቸዉም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበዉን የአመልካችን መከራከሪያ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ አተገባበርና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት ተከታዩን ወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1.የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 175620 ላይ በቀን 19/06/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 247744 ላይ በቀን 08/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2.ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ/ 178414

ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሀኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ ገነት በላቸዉ

2. አቶ ጌታሁነኝ ገበየሁ

ተጠሪ፡- አቶ ዮሴፍ አከበረኝ

መዝገቡ ያደረዉ ለምርመራ ሲሆን መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ለዚህ መዝገብ መቅረብ ምክንያት የሆነዉ አመልካቾች በግንቦት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ፅፈዉ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሲሆን ለአቤቱታቸዉ ምክንያት የሆነዉ ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 219536 በቀን 2/7/2011 ዓ.ም የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 170021 በሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አመልካቾች (የስር ከሳሾች) በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጥር 16 ቀን 2010 ዓ.ም በአጭር ሥ/ሥርዓት ባቀረቡት የተሻሻለ የክስ ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር ያለንን ጉርብትናና መልካም ግንኙነት መሰረት በማድረግ መኪና እገዛላቸዋለሁ፣ መኪናዉን እስካስመጣ ድረስ ገንዘብ ስጡኝ ብሏቸዉ የተለያዩ ጥሬ ገንዘቦችን ባጠቃላይ ብር 215,000 (ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺህ) ከሰጡት በኋላ ለመተማመኛ በሚል ለ1ኛና 2ኛ አመልካቾች የዚህን ያህል ብር ዋጋ ያላቸውን በተለያየ ጊዜ የሚመነዘሩ ሦስት ቼኮችን ሰጥቷቸዉ በኋላ ላይ ግን በቃሉ ባለመገኘቱ ምክንያት ገንዘባቸዉን ለመዉሰድ ወደ ከፋዩ ባንክ በሚሄዱበት ጊዜ የተጠሪ ሂሳቦች እንደተዘጉ ከማረጋገጫ ጋር እንደተሰጣቸዉ ገልፀዉ ተጠሪ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ዋናዉን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል እንዲሁም ወጪና ኪሳራ እንዲተካላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በቀን 27/06/10 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበዉ መልስ የተባሉትን ቼኮች መስጠቱን አምኖ ነገር ግን የተሰጡበትን ምክንያት ክዶ ተከራክሯል፡፡ በተለይም የተሰማራበት ንግድ የመጠጥና ግሮሰሪ ሥራ እንጂ መኪና ማስመጣት እንዳልሆነ፤ መኪና ለማስመጣትም ምንም ፈቃድ እንደሌለዉና መኪና አስመጥቶም ሆነ ሸጦ እንደማያዉቅ ገልፆ 1ኛ አመልካች የቤት እመቤትና 2ኛ አመልካች ደግሞ የመንግስት ሠራተኛ ስለሆኑ ቼክ ለመቁረጥ የሚያበቃ የንግድ ግንኙነት እንደሌላቸዉ፤ መኪና ለመገበያየት በፅሁፍ የተደረገ ዉል ስለሚያስፈልግ ከአመልካቾች ጋር በዚህ መልኩ ያደረገዉ ዉል እንደሌለ ማስረጃም እንዳላቀረቡ ተከራክሯል፡፡ ቼኮቹ የሰጡት በተለያዩ ጊዜያት ስለሆኑ አመልካቾች ለመተማመኛ በአንድ ጊዜ ተሰጠን ካሉት ጋር የሚጣረስ እንደሆነና ሙሉ ገንዘቡን ባንዴ ወስዶ ቢሆን ኖሮ ለመተማመኛም የሚሰጠዉም አንዴ ወዲያዉ መሆን ይኖርበት ነበር ብሏል፡፡ ከአመልካቾች ጋር የነበረዉም ግንኙነት የአራጣ ብድር እንደሆነ፣ አመልካቾችና ተጠሪ በሚኖሩበት በጉለሌ ክ/ከ ቀጨኔ በሚባለዉ መኖሪያ ሥፍራ የአራጣ ብድር ግንኙነት የተለመደ ስለመሆኑ፣ ግንኙነቱም ህገ-ወጥ ስለሆነና ስለሚያስቀጣ በቃልም በፅሑፍም እንደማይደረግ፣ አራጣ አበዳሪዎች ላበደሩት ገንዘብ መመለሻ ዋስትና ቼክ፣ ሊብሬና ካርታ የመሳሰሉትን እንደሚይዙ ገልጿል፡፡ በዚሁ መሰረት በመጀመሪያ ብር 65,000 (ስላሳ አምስት ሺህ ብር) በሌላ ጊዜ ደግሞ ብር 20,000 (ሀያ ሺህ ብር) እና ብር 135,000 (አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ ብር) ተበድሮ እንደ ነበር፣ ዋናዉን ገንዘብም እስከሚመልስ ድረስም በወር 10 በመቶ ሲከፍል እንደ ነበርና እንደተበደረዉ ገንዘብ መጠን እና ጊዜ ለዋስትና ወደፊት በመፃፍ ቼኮችን እንደ ሰጠ፣ በየወሩም አራጣ ሲከፍል እንደቆየና ባጠቃላይ ወለድ ብቻ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺህ ብር) ከፍሎ እንደ ነበር ገልጿል፡፡ ይህ ስምምነታቸዉም በዉል ህጉ ከተደነገገዉ የ12 በመቶ ወለድ በላይ ስለሆነና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 712 የሚያስቀጣ ስለሆነ ሊፀና የሚችል የብድር ዉል እንዳልሆነ ተከራክሯል፡፡ የሰ/መ/ቁ. 20232፣ 24435 እና 55077 ጠቅሶ ቼክ ለመጻፉ መነሻ ከሆነዉ ዉል ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ስለሚገባ በመካከላቸዉ የተደረገዉ ዉል ደግሞ ሊፀና የሚችል ስላልሆነ ለዉሉ ዋስትና የተሰጡት ቼኮችም አስገዳጅ ዉጤት ስለሌላቸዉ በቼኮቹ የተመለከተዉን ገንዘብ ለመክፈል እንደማይገደድም ተከራክሯል፡፡

በቃል ክርክር ወቅት አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ምንም አይነት የዉል ግንኙነት እንደሌላቸዉ፣ ቼኮቹን የያዙት በቅን ልቦና እንደሆነ፣ አመልካቾችና ተጠሪ አብሮ አደግ እንደሆኑ፣ መኪና አስመጣለሁ ስላለ ባላቸዉ ጉርብትና ገንዘቡን እንደ ሰጡትና ቼኮቹን ለመተማመኛ ብሎ እንደሰጣቸዉ፣ ከ10 በመቶ በላይ ለማስከፍልም እንዳልተስማሙ፣ ግንኙነታቸዉ በቅን ልቦና የተደረገ ስምምነት ስለሆነ በህግ ፊት ተቀባይነት እንዳለዉ፤ ተጠሪ ግን አለ ስላሉት የአራጣ ዉልም ሆነ ከፍያለሁ ስላሉት ክፍያ ምንም ያቀረቡት ማስረጃ የለም፤ የቼኮቹን ቀናት አራርቆ የፃፈዉ ራሱ ተጠሪ ነዉ፤ ቼኮቹን እንዳታስመቱብኝ ብሎ ራሱን መደበቅ ጀመረ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ቼኮቹ ሦስት የተለያየ የብድር ግንኙነት እንደ ነበር የሚያስረዱ ናቸዉ በማለት አፅኖት ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካቾች እንዲፈፀምላቸዉ እየጠየቁት ስላለዉ ክፍያ ከመኪና ሽያጭ ዉል በመነጨ ግዴታ ቼኩን እንደተቀበሉ ማስረዳት ቢኖርባቸዉም የቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ቼክና የባንክ ማረጋገጫ ብቻ ስለሆነ እነዚህ ደግሞ ቼክ ስለመፃፉ መነሻ የሆነዉን ግንኙነት በተመለከተ ምንም ያስረዱት ነገር አለመኖሩን እና ያቀረቡትም የምስክሮች ቃልም እርስ በርስ የሚጣረሱ፣ ወጥነት የሌላቸዉ፣ ሊታመኑ የማይችሉ፣ በቦታዉ ነበርን ብሉም ቃላቸዉ የተለያየ ስለሆነ ፍፁም እዉነትነት የለሌዉ፣ የስጋና ጋብቻ ዝምድና ስላላቸዉ በመደጋገፍ የሰጡት ቃል መሆኑን ያሳያል በማለት ሳይቀበል አልፏል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የብድር ዉል ስለመኖሩና ብሩ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ 10 በመቶ ለመክፈል ስለመስማማታቸዉ በባርማንነት በተጠሪ ግሮሴሪ ዉስጥ ተቀጥሮ የሚሰራዉን ሠራተኛ እና ራሱ ተከሳሹ ወይም ተጠሪ የሰጡት ምስክርነት ግንኙነቱ ስለጀመረበት ቀንና ስለ ከፈሉት የገንዘብ መጠን በተመለከተ ልዩነት ባለዉ መልኩ ወይም በማይጣጣም መልኩ የመሰከሩ ቢሆንም ተጠሪ በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ለመክፈል ስምምነት ስለመፈጸማቸዉ የሰጡት የምስክርነት ቃል 1ኛ ምስክር 1ኛ አመልካች በተደጋጋሚ ተጠሪ ጋር ይመጡ ነበር በማለት ከሰጠዉ የምስክርነት ቃል ጋር ሲገናዘብ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉ የብድር ግንኙነት በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ለመክፈል ስምምነት የተደረገበት እንደሆነ የሚያስገነዝብ እንደሆነና የተጠሪ የምስክርነት ቃል በመሓላ ስር ሆኖ እስከመሰከረ ድረስ የተናገረዉ እዉነት ነዉ ተብሎ ግምት የሚወሰድበትና ግምቱንም የሚያፈርስ ማስረጃ በአመልካቾች በኩል አለመቅረቡን፤ ተጠሪ በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ለመክፈል ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት ከተረጋገጠ አመልካቾች የሚጠይቁት ዓመታዊ ወለድ መጠን ሲሰላ 120 በመቶ ስለሚሆን ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2479(1) ያስቀመጠዉን የ12 በመቶ ገደብ የሚጥስና የሰ/መ/ቁ. 80119 ላይ በወር የ10 በመቶ ወለድ መጠየቅ ከህግ ዉጪ ስለመሆኑ የሰጠዉን የህግ ትርጉም የሚቃረን እንደሆነና በወንጀል ህግ አንቀጽ 712 መሰረት የሚያስቀጣ በመሆኑ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገ ዉል ህግን የተከተለ ስላልሆነ ይህን መሰረት በማድረግ የተሰጡትም ቼኮች ተጠሪን ሊያስገድዱ ስለማይችሉ ተጠሪ በክሱ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ለአመልካቾች ሊከፍል አይገባም፤ ተጠሪ ለክርክሩ ያወጡትን የጠበቃ አበል ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በአመልካቾች ይተካለት በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የስር የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዉሳኔዉ ላይ የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ ተቀብሎ ካከራከረ በኋላ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኝ መካከል ያለዉ ግንኙነት የአራጣ ብድር ዉል ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ ቁ. 348(1) መሰረት አፅንቷል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታም እነዚህን ዉሳኔዎች ለማሳረም የቀረበ ነዉ፡፡ በዚሁ መሰረት አመልካቾች የስር ፍ/ቤቱ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት ያቀረቡት ምክንያቶችም ባጭሩ ከተጠሪ ጋር ባለን ጉርብትናና መቀራረብ ምክንያት እምነት በመጣል መኪና እገዛላችኋለሁ ስላለን ገንዘባችንን ከመስጠት ዉጪ ምንም የዉል ግንኙነት በመካከላችን እንደሌለ፣ ለዚህም መተማመኛ ይሆን ዘንድ ከተጠሪ ቼክ እንደተሰጠንና ይህንም ተጠሪ ራሱ አምኖ እያለ የስር ፍ/ቤቱ

ምንም ማስረጃ የላችሁም በማለት ማለፉና በመካከላችን ያለዉ የብድር ዉል እንደሆነ አድርጎ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም። ዉሳኔዉም በሰ/መ/ቁ. 123984 እና በን/ህ/ቁ. 827(ሀ) እና 854 መሰረት ቼክ እንደቀረበ የሚከፈልበት እንጂ ዉል መኖሩን የሚያሳይ ሰነድ አይደለም በማለት ከተሰጠዉ ዉሳኔ ጋር የሚቃረን ነዉ። ተጠሪ የ10 በመቶ ወለድ ለመክፈል ነዉ ቼኮቹን የፃፈዉ የሚለዉ እዉነት አይደለም፤ ከተባለዉም ገንዘብ በላይ ከፍያለሁ ስላለዉም ክፍያ ያቀረበዉ ማስረጃ የለም፤ ግንኙነቱ ህጋዊ ስላልሆነ ከቼኩ የሚመነጨዉ ግዴታ አስገዳጅነት የለዉም መባሉ ስህተት ነዉ፤ ተጠሪ የብር 215,000 (ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺህ ብር) ወለድ ብር 65,000 (ስልሳ አምስት ሺህ ብር) ከፍያለሁ ስላለዉም ያስረዱት ነገር ሳይኖርና በችሎትም ፊት የሰጡት የምስክርነት ቃል የተዛባ ሆኖ ሳለ ዉሉ ህገ-ወጥና የማይፀና ነዉ ብሎ መወሰኑ ተገቢነት የለዉም በማለት ተከራክረዉ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እንዲሻርላቸዉ ጠይቀዋል። የሰበር ማመልከቻዉና የተሰጠዉ ብይን ከፍ/ቤቱ መጥሪያ ጋር ለተጠሪ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ከቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ጋር ተልኮለት ችሎት ላይ ከቀረበ በኋላ መልሱን እንዲያቀርብ በተለያዩ የቀጠሮ ቀናት ቢጠበቅም (ከማረሚያ ቤት መቅረቡን ከግምት ዉስጥ በማስገባት) በታዘዘዉ መሰረት መልሱን ስላላቀረበ ችሎቱ የተጠሪን መልስ የማቅረብ መብት ህዳር 24 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ብይን ሰጥቶበት አልፎታል።

የጉዳዩ አመጣጥ፣ በስር ፍ/ቤቶች የተደረገዉ ክርክርና የተሰጡት ዉሳኔዎች እንዲሁም የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከቱት ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎትም በቀን 15/11/2011 በዋለዉ ችሎት “የስር ፍ/ቤቶች አመልካቾች ቼክን መሰረት አድርጎ እንዲከፈላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት ያደረጉት ዉል ህጉን የሚጥስ የወንጀል ተግባር ነዉ በማለት የን/ህ/ቁ. 717/1/ እና /3/ ጠቅሶ የዘጋበትን ከን/ህ/ቁ. 827 እና 854 እንዲሁም የሰበር ችሎት በመ/ቁ. 123984 ላይ ከሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ ጋር ለማጣራት ሰበር ያስቀርባል” በማለት ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩበት ብይን ሰጥቷል። ይህ ችሎትም የአመልካቾችን ክርክርና ጉዳዩ ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ አግባብነት ካለዉ ህግ እና የሰበር ዉሳኔዎች አንፃር መርምሮታል።

ከመዝገቡ ዉስጥ እንደሚታየዉ በግራ ቀኙ መካከል ገንዘብ መቀባበል እንደነበረና ስለገንዘቡም መጠን፣ አብሮ አደጎችና መልካም ግንኙነት የነበራቸዉ ጎሮቤታሞች እንደሆኑ ግራ ቀኙ በግልፅ ቋንቋ ተናግሯል። ግራ ቀኙ የተካከዱት ገንዘቡን ለመቀባበላቸዉ ምክንያት ስለሆነዉ ጉዳይ ነዉ። አመልካቾች ከጉርብትናዉና መልካም ግንኙነት የተነሳ መኪና እገዛላችዋለሁ (አስመጣላችዋለሁ) ስላለን ገንዘባችንን በእምነት ሰጠነዉ እንጂ ምንም የዉል ግንኙነት በመካከላችን የለም፤ ለመተማመኛ ብቻ በሚል ቼክ ተቀብለናል ሲሉ ተጠሪ ደግሞ ገንዘቡን የተቀበልኳቸዉ በአራጣ ብድር ሆኖ በወር 10 በመቶ እንድከፍላቸዉ ስለተስማማን ነዉ በማለት ተከራክረዋል (እዚህ ላይ አንዳንዴ ብር 10 ሺህ፣ አንዳዴ ደግሞ 10 በመቶ ተብሎ ስለተፃፈ ትክክለኛዉ የቱ እንደሆነ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ በትክክል መለየት አስቸግሯል፤ የብር 215 ሺህ 10 በመቶ ብር 10 ሺህ አለመሆኑን ግን ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል)። ከላይ እንደተገለጸዉ የስር የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ግንኙነት በህግ ፊት የማይጸና የአራጣ ስምምነት

ስለሆነ ተጠሪ ከአመልካቾች የተቀበለዉን ገንዘብ መልሶ ሊከፍል አይገባም የሚል ዉሳኔ እንደሰጠ እና በዚህ ዉሳኔ ላይ ሊደርስ የቻለበትም ምክንያት በተጠሪ በኩል ለቀረቡት ምስክሮች ከፍ ያለ ዋጋ (high probative value) በመስጠት መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የስር ፍ/ቤቶቹ የሰጡትን ዉሳኔ አግባብነት ለመመዘን እና ለቀረበዉ ክርክር እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ በሀገራችን ህጎች ዉስጥ ያለዉን የአራጣ ብድር ትርጉም ማየት ያስፈልጋል፡፡

በፍትሐ ብሔር ህጋችን ዉስጥ ስለ አራጣ ብድር የተሰጠ ትርጉም የለም፡፡ ስለዚህ አራጣን በተመለከተ ክርክር በሚነሳበት ጊዜ በወንጀል ህጋችን ዉስጥ በተሰጠዉ ድንጋጌና ትርጉም መመራት አማራጭ የሌለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በ1996ቱ የወንጀል ህጋችን የአራጣ ወንጀል ድርጊት በአንቀጽ 712 በሚከተለዉ መሰረት ተደንግጓል፡-

<u>አንቀጽ 712 አራጣ</u>

*1/ ማንም ሰዉ የተበዳዩን ችግረኛነት፣ የበታችነቱን፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን፣ ወይም መንፈሰ ደካማነቱን፣ ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለዉ መሆኑን መሠረት በማድረግ፡-*

*ሀ/ በህግ ከተፈቀደዉ ወለድ በላይ ገንዘብ ያበደረዉ እንደሆነ፤ ወይም*

*ለ/ ካበደረዉ ገንዘብ ጋራ በግልፅ ተመጣጣኝነት የሌለዉን ንብረት በምትኩ እንዲሰጠዉ ያደረገዉ ወይም ቃል ያስገባዉ እንደሆነ፤*

*በቀላል እሥራት፣ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል፡፡*

ስለዚህ በወንጀል ህጉ ድንጋጌ መሰረት አንድ የብድር ግንኙነት የአራጣ ብድር ነዉ ለማለት ከላይ በተጠቀሰዉ አንቀጽ ስር የተመለከቱት የህጉ ወሳኝ ፍሬ ነገሮች (basic elements) ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡ የፍሬ ነገሮቹ መኖር በማስረጃ ሲረጋገጥ ግን ይህ ጉዳይ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ስለሆነ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ጥቅም ላይ በሚዉለዉ ሚዛን በሚደፍ ማስረጃ የማስረዳት ሥርዓት (preponderance of evidence) መሰረት መረጋገጥ ይኖርበታል ፡፡

ከላይ ይዘቱ በተጠቀሰዉ አንቀጽ 712 ንዑስ አንቀጽ 1 የመግቢያ ዐረፍተ ነገር (chappeue) ላይ በግልፅ እንደተመለከተዉ አንድ አበዳሪ የአራጣ ድርጊት በመፈጸም አበድሯል ለማለት በድንጋጌዉ ከተጠቀሱት አማራጭ ሁኔታዎች መካከል ቢያንስ አንዱን ተጠቅሞ በንዑስ አንቀፅ (ሀ) ወይም (ለ) የተመለከተዉን ተግባር (ድርጊት) መፈፀሙ መረጋገጥ አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር በአንቀጹ መግቢያ ዐረፍተ ነገር የተገለጸዉ ሁኔታ ከሌለ በንዑስ አንቀፅ (ሀ) ወይም (ለ) ወስጥ የተቀመጠዉን ድርጊት ፈፅሞ መገኘቱ ብቻዉን አንድን ሰዉ አራጣ አበዳሪ ሊያሰኘዉ አይችልም ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም የአራጣ ብድር አለ ብሎ የሚከራከር ወገን ድርጊቱ መኖሩን በተለይ ከላይ በተጠቀሰዉ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የመግቢያ ዐረፍተ ነገር ላይ የተገለጸዉ ሁኔታ የገጠመዉ መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡

ከዚህ አንፃር በዚህ መዝገብ የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ግራ ቀኙ የነበራቸዉን ጉርብትናና መልካም ግንኙነት ለጊዜዉ ወደ ጎን ትተን ከተሰማሩበት የስራ መስክ አንፃር እንኳን ብንመለከት አመልካቾች (ባልና ሚስት የሆኑና 1ኛ አመልካች የቤት እመቤት፣ 2ኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ የሆኑ) የተጠሪን *"ችግረኛነት፣ የበታችነቱን፣ ወይም የገንዘብ ችግሩን፣ ወይም መንፈሰ ደካማነቱን፣ ወይም ልምድ ወይም ችሎታ የሌለዉ መሆኑን መሠረት"* አድርገዉ ገንዘብ ያበደሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ተጠሪም አመልካቾች ገንዘቡን ያበደሩት ችግረኛነቱን፣ የበታችነቱን ወይም የገንዘብ ችግሩን መሰረት አድርገዉ መሆኑን በመግለጽ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነዉ የስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል ያለዉ የአራጣ ብድር ግንኙነት ነዉ ብሎ ለመደምደም የቻለዉ ተጠሪ ራሱ በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ትከፍለኛለህ ብለዉኝ ለመክፈል ስምምነት አድርገናል በማለት የሰጠዉን የምስክርነት ቃል እና በተጠሪ ግሮሴሪ ዉስጥ በባርማንነት ተቀጥሮ ይሰራ የነበረዉ የተጠሪ 1ኛ ምስክር በሰጠዉ የምስክርነት ቃል ዉስጥ አመልካች "አልፎ አልፎ እየመጡ እንደሚጠይቁ" የሚለዉን መሠረት በማድረግ ነዉ፡፡ ነገር ግን የራሱ የተጠሪ ቃልም ሆነ የሌላኛዉ ምስክር ቃል የወንጀል ህጉ አንቀጽ 712 ንዑስ አንቀጽ 1 የመግቢያ ዐረፍተ ነገር እንዲኖሩ የሚጠይቃቸዉ ፍሬ ነገሮች (ሁኔታዎች) በተጠሪ ዘንድ ስለመኖራቸዉና አመልካቾችም ከእነዚህ አንዱን መሰረት አድርገዉ አራጣ ስለማበደራቸዉ አያመለክቱም፡፡ የአንድ ሰዉ ወይም አበዳሪ አልፎ አልፎ ወደ ተበዳሪዉ የስራ ቦታ መሄድ ህጉ ከሚደነግገዉ የአራጣ ግንኙነት ጋር በቀጥታ የሚያገናኘዉ ምንም ነገር የለም፡፡ እንዲሁም "አልፎ አልፎ እየመጡ እንደሚጠይቁ" የሚለዉ አገላለጽ በራሱ ምን እንደሚጠይቁ በግለፅ አላመለከቱም፡፡ በተጨማሪም የተጠሪ 1ኛ ምስክር በግራ ቀኙ መካከል የብድር ወይም የአራጣ ብድር ግንኙነት ስለመኖሩ እንደሚያዉቅ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል በመዝገቡ ዉስጥ ተፅፎ አይገኝም፡፡ ይልቁንም "ግንኙነቱን በተመለከተ ያስረዷቸዉ እንደሌለ" በግልፅ ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ከራሱ ከተጠሪ ቃል ዉጪ ከላይ የተጠቀሰዉ የወንጀል ህግ አንድን ድርጊት አራጣ ከሚያደርገዉ ሁኔታ አንፃር የአራጣ ብድር መኖሩን የሚያሳይ ምንም ማስረጃ በመዝገቡ ዉስጥ የለም፡፡ በማስረጃ ህግ መርህ አንፃር ደግሞ አንድ ተከራካሪ ስለራሱ የሚሰጠዉ የምስክርነት ቃል በሌሎች ማስረጃዎች ካልተደገፈ የተቀባይነቱ ደረጃ እጅጉን ደካማ እንደሚሆን የሚታወቅ ነዉ፡፡ የተጠሪ 1ኛ ምስክር በሰጠዉ የምስክርነት ዉስጥ የግራ ቀኙን "ግንኙነቱን በተመለከተ ያስረዷቸዉ እንደሌለ" ተናግሮ እያለና ሌሎችም ከተጠሪ ቃል ጋር በቀጥታ የሚጣረስ የምስክርነት ቃል ሰጥቶ ባለበት ሁኔታ (ራሱ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤቱ በግልፅ በፍርድ ሐተታ ክፍሉ ዉስጥ እንዳመለከተዉ ማለት ነዉ) ተጠሪ በመሓላ ሥር ሆኖ ስለመሰከረ ብቻ እዉነት ነዉ ብሎ መዉሰድ በየትኛዉም መልኩ ከህጉ ዓላማ ጋርም ሆነ ከማስረጃ ምዘና መርህ ጋር የሚሄድ አይደለም፡፡

በእርግጥ የፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2479(1) ላይ የብድር ወለድን በተመለከተ ተዋዋይ ወገኖች በዓመት ከ12 በመቶ በላይ የወለድ መጠን መስማማት እንደማይችሉ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ይህ አንቀጽ ከዚህ ከተቀመጠዉ ገደብ በላይ በሆነ የወለድ መጠን ተስማምቶ መገኘት የብድር ስምምነቱን

የአራጣ ብድር ያሰኘዋል የሚል ትርጉምም ሆነ ስምምነቱ ከዚህ የተነሳ ዉጤት የለዉም የሚል ድንጋጌ በፍፁም አልሰጠም፡፡ በተቃራኒዉ አንቀጽ 2479(3) ስር ተዋዋዮች (ባንኮችንና አበዳሪ ተቋማትን አይጨምርም) "በወለድ የሚከፈለዉ ገንዘብ በመቶ ከአስራ ሁለት በላይ በዓመት እንዲሆን በጽሑፍ የተደረገ ዉል ቢኖር እንኳ ተበዳሪዉ በመቶ ዘጠኝ ብቻ በዓመት ወለድ መክፈል አለበት" በማለት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ከስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ በተቃራኒ የፍ/ብ/ህጉ አንድ የብድር ዉል ከተደነገገዉ የወለድ መጠን በላይ ለመክፈል ስምምነት የተደረገበት ዉል ስላደረጉ ብቻ ዉሉ የአራጣ ብድር ዉል ነዉ ወይም ፈራሽ ነዉ (ዉጤት አይኖረዉም) የሚል አቋም የለዉም፡፡ ይልቁንም የህጉ አቋም የብድር ዉሉ ፀንቶ እንዲቀጥልና ተበዳሪዉ በአመት ዘጠኝ በመቶ ብቻ ወለድ እንዲከፍል በማድረግ ዉሉ ፍፃሜ እንዲያገኝ ማድረግ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል የአራጣ ብድር ግንኙነት ስለመኖሩ በተጠሪ በኩል በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ የተባሉትም ቼኮቹም ቢሆኑ ለአመልካቾች የሚከፈል ገንዘብ የመጠየቅ መብትን ከማመልከታቸዉ በስተቀር በመካከላቸዉ የአራጣ የብድር ግንኙነት ውል ስለመኖር የሚያስረዱ ሰነዶች (documentary evidence) አይደሉም፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎቱም እንዲጣራ በማለት በያዘዉ ጭብጥ ዉስጥ የጠቀሰዉ የሰ/መ/ቁ. 123984 ላይ የተመለከተዉ ትርጉምም የሚያረጋግጠዉ በን/ህ/ቁ. 827(ሀ) እና 854 ድንጋጌዎች መሰረት ቼክ የክፍያ ሰነድ ወይም ክፍያ የሚፈጸምበት ሰነድ እንጂ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የህግ መሰረት አለመኖሩን ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አመልካቾች የተባሉትን ቼኮች ለመተማመኛ ብቻ ብለን የተቀበል ነዉ ቢሉም በፍ/ብ/ህጉ እና በንግድ ህጉ ዉስጥ ስለ ዋስትና ወይም መያዣ ዉል የተደነገጉትን መስፈርቶች (ፎርሞች) ባገናዘበ መልኩ የተደረገ ዉል በመካከላቸዉ ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በተጨማሪም ተጠሪ በስር ፍ/ቤት የሰ/መ/ቁ. 20232፣24435 እና 55077 በመጥቀስ በመካከላቸዉ ያለዉ ግንኙነት ህገ-ወጥ ስለሆነ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን የብር መጠን ለመክፈል እንደማይገደድ ተከራክሮ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የሰ/መ/ቁ. 20232 የሚመለከተዉ በማስገደድ (እስራትን ጨምሮ) ስለተፈረመዉ የቼክ ሰነድ ስለሆነ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለዉም፡፡ ከዚህ የተነሳ የስር ፍ/ቤትም ይህን የሰበር ዉሳኔ መሰረት በማድረግ የሰጠዉ ትንታኔና የደረሰበት መደምደሚያ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሰ/መ/ቁ. 24435 እና 55077 ደግሞ በቼክ አዉጪና አምጪዉ መካከል ያለዉን የግል ግንኙነት ወይም ከቼኩ በስተጀርባ ያለዉን ስምምነት መሰረት በማድረግ የቼክ አዉጪዉ የሆነዉ ባለዕዳ በን/ህ/ቁ. 717 በሚፈቅደዉ መሰረት ሊያነሳቸዉ ስለሚችላቸዉ መቃወሚያዎች በተመለከተ የተሰጡ ዉሳኔዎች ናቸዉ፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተገለፁት ምክንያቶች የተነሳ በግራ ቀኙ መካከል በን/ህ/ቁ. 717 ድንጋጌና የተጠቀሱት የሰበር ዉሳኔዎች የሚጠይቁት አይነት የግል ግንኙነት (የአራጣ ብድር ግንኙነት) ስለመኖሩ የሚያመለክት ምንም ማስረጃ ስለሌለ እነዚህ ዉሳኔዎች ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የላቸዉም፡፡

ይልቁንም በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጉርብትና፣ አብሮ አደግነትና መልካም ግንኙነት በተወሰነ ደረጃ አንዱ በሌላዉ ላይ እምነት እንዲጥል እና ገንዘብ እንዲቀባበሉም ምክንያት ሆኗል ብሎ መገመት አያዳግትም። በእርግጥ እንዲህ አይነቱ ግንኙነትና መተማመን ለማህብረሰባችን እንግዳ ነገር አይደለም። አብሮ አደጎችና መልካም ግንኙነት ያላቸዉ ጎረቤታሞች ከዚህም ለበለጠ ነገር ሊተማመኑ ይችላሉ። በስር ፍ/ቤት ከቀረቡት ማስረጃዎች ማለትም ከግራ ቀኙ ከተማመኑት፣ በአመልካቾች በኩል ከቀረቡት የምስክሮች ቃል እና በቼኮቹ ከተረጋገጠዉ አንፃር ጎላ ብሎ በግልፅ የሚታየዉ እዉነት ተጠሪ ከአመልካቾች ላይ ብር 215,000 (ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺህ ብር) ስለ መቀበሉ ነዉ። ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ መሰረት ተጠሪ የተጠቀሰዉን ገንዘብ መኪና አስመጣላችዋለዉ ብሎ መቀበሉን በተወሰነ መልኩ (prima facie) ስለማስረዳታቸዉ እና ተጠሪ ግን ይህን በአግባቡ እንዳልተስተባበለ ነዉ። ከዚህም የተነሳ ተጠሪ መቀበሉን ያልካደዉን የገንዘብ መጠን ለአመልካቾች መልሶ ለመክፈል ይገደዳል ማለት ነዉ። ከመዝገቡ እንደተረዳነዉ ተጠሪ ከአመልካቾች ስለመቀበሉ ከተረጋገጠዉ ብር 215,000 (ሁለት መቶ አስራ አምስት ሺህ ብር) ዉስጥ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) በሆነ ቀን ከተጠሪ 1ኛ ምስክር እጅ 1ኛ አመልካች ተቀብብሏል (ለምን ምክንያት እንደሆነ ባይታወቅም) በማለት የመሰከረዉን ብንቀበል እንኳን ለአመልካቾች መክፈል ያለበት ብር 213,000 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ብር) በተጠሪ እንጅ እንዳለ ነዉ። ከዚህ ዉጪ ተጠሪ ለአመልካቾች ገንዘብ ስለመክፈሉ የሚያስረዳ ምንም አሳማኝ የሆነ ማስረጃ አልቀረበም። ስለዚህ ተጠሪ ተቀብያለዉ ብሎ በራሱ ቃል ያመነዉን ይህን የገንዘብ መጠን ለአመልካቾች እንዳይመልስ የሚያስችለዉ ምንም ህጋዊ ምክንያት የለም።

በአጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሳ የስር ፍ/ቤቶች በግራ ቀኙ መካከል በህግ ፊት የማይፀና የአራጣ ብድር ግንኙነት ነዉ በማለት እና ተጠሪ ከአመልካቾች ላይ የተቀበለዉን ጥሬ ገንዘብ ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመባቸዉ ናቸዉ ብለናል። ስለሆነም የሚከተለዉን ዉሳኔ ሰጥተናል።

## ዉሳኔ

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 219536 በቀን 2/7/2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ/ 170021 በሰኔ 25 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪ ከአመልካቾች እጅ የተቀበለዉን ቀሪ ገንዘብ ብር 213,000 (ሁለት መቶ አስራ ሶስት ሺህ ብር) ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ ከመቶ) ወለድ ጋር ለአመልካቾች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. ወጪና ክሳራ ግራና ቀኝ ራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

# አፈፃፀም

የሠ/መ/ቁጥር 193115

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡-አቶ ቶፊቅ መለሰ- ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ እንድሪስ ሳቢር } በሌሉበት

2. አቶ ቶፊቅ ሳሊህ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አክሲዮን በሐራጅ ለመሸጥ በወጣ ማስታወቂያ ላይ ያልተገለጸ የባለአክሲዮን ዕዳ የመክፈል ኃላፊነት የማን እንደሆነና በሐራጅ ሽያጩ ላይ የሚኖረዉን ሕጋዊ ዉጤት የሚመለከት ነዉ፡፡ ፍርዱን በሚያስፈጽመዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት፣ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለእዳ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት በተደረገ የአክሲዮን ሐራጅ ሽያጭ አክሲዮኑን የገዙ ናቸዉ፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነዉ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ያስፈረዱትን ገንዘብ ለማስከፈል 2ኛ ተጠሪ በሲነመር ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር ያላቸዉን አክሲዮን ተሸጦ የፍርድ እዳዉ እንዲከፈል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ትእዛዝ መነሻ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በቀን 12/03/2010 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲወጣ ባደረገዉ የሐራጅ ማስታወቂያ አመልካች በጨረታዉ ተሳትፈዉ ባቀረቡት ከፍተኛ ዋጋ በብር 490,000.00 የጨረታዉ አሸናፊ መሆናቸዉ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት አክሲዮኑ በስማቸዉ እንዲዞር(ለመረከብ) በሚጠይቁበት ጊዜ አክሲዮን ማኅበሩ የፍርድ ባለእዳዉ(ባለአክሲዮኑ) ያልከፈሉት የግንባታ መዋጮ ብር 532,272.72 እና የሥራ ማስኬጃና ቅጣት ብር 83,549.07 በድምሩ ብር 615,522.69 እዳ እንዳለባቸዉ በመግለጽ እዳዉ ካልተከፈለ አክሲዮኑን በስማቸዉ እንደማያዛዉር በመግለጽ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

ይህንን ተከትሎ አመልካች አቤቱታቸዉን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ማብራሪያ እንዲሰጥ አድርጎ በመ/ቁጥር 185895 ላይ በቀን 02/07/2011ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በዳይሬክቶሬቱ የተለመደ አሰራር አክሲዮን ሲሸጥ እዳ መኖሩ በማስታወቂያ ላይ

ለተጫራቾች እንደማይገልጽ ጠቅሶ አሰራሩ ይሕ ከሆነ ተጫራች በራሱ ጥረት አድርጎ ሊመጣበት የሚችለዉን ጉዳት መቀነስ እንደሚኖርበት መረዳቱን ገልጾ አመልካች በፈቃዳቸዉ ሳያጣሩ የገዙትን አክሲዮን ሊረከቡ ይገባል በማለት የአመልካችን ጥያቄ እንዳልተቀበለ በመግለጽ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች ከላይ ይዘቱ በተመለከተዉ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 175625 ላይ ተጠሪዎች ቀርበዉ እንዲከራከሩ ጥሪ አድርጎላቸዉ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸዉ የአመልካችን ይግባኝ ማመልከቻ መርምሮ በቀን 04/06/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የአክሲዮን ሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ አክሲዮኑ ያለበት እዳ ባለዉ አሰራር አይገለጽም ያለዉን መቀበሉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 423/2 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ካለ በኋላ ጸንቶ በሚገኘዉ ዉል የሚተላለፈዉ መብቱ ብቻ ሳይሆን ግዴታዉም ጭምር በመሆኑ ይግባኝ ባይ እዳዉ አይመለከተኝም በሚል ያቀረቡትን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤት ዉድቅ ማድረጉ ከዉጤት አንጻር የሕግ መሰረት ያለዉ ነዉ በማለት በማፅናት ወስኗል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት በቀን 03/09/2011 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በዚህ መሰረት በተሰጠው ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸው ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 423/2 ድንጋጌን አለመከተሉ አግባብ አይደለም በማለት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ነቅፎ ሳለ ተመልሶ መብትና ግዴታ አይነጣጠሉም በማለት የሰጠው ውሳኔ እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነዉ፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በመጨረሻ የሰጠው የፍርድ ሀተታ ሲታይ በሽያጭ ውል መብትና ግዴታ እኩል መታየት አለባቸው በሚለው አቅጣጫ ቢታይ እንኳ ሻጩ ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ባወጣው የሐራጅ ሽያጭ ላይ እዳ መኖሩን እስካልገለፀ ድረስ አመልካች በሚገዛው ንብረት ላይ እዳ መኖሩን ሳያውቅና ሳይገለፅለት ከገዛ እዳውንም አብሮ ተቀብሏል የሚያሰኝ የሕግ ድንጋጌም ሆነ የሕግ ግምት የለም፡፡በሽያጭ ውል መብትና ግዴታ በተመለከተ በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ክርክር አልተነሳም፡፡እንዲሁም ይህ ጉዳይ የንብረት ሽያጭ ጉዳይ ቢሆንም አፈፃፀሙ የሚመራው በሐራጅ ሽያጭ ስርዓት መሰረት እንጂ እንደ ውል ጉዳይ ተቆጥሮ የመብትና ግዴታ ነጥብ የሚነሳበት አይደለም፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በውጤት ደረጃ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፀንቷል ካለ በፍርዱ መግቢያ ላይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 423/2 መሰረት ያላደረገ ነው በማለት የያዘዉን ድምዳሜ መልሶ እንደመሰረዝ ስለሚሆን የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት መሰረታዊ ውሳኔ የትኛው ነው የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት አይነት ፍርድ መሰጠቱ በራሱ በአንድ ጉዳይ ሁለት አይነት ፍርድ እንደመስጠት ስለሚሆን በራሱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡የሕግ ስህተት በመፈጸም ጉዳዩ እንዳይፈጸም ያደረገዉ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በመሆኑ ይግባኙ እየተሰማ ባለበት ወቅት የፍርድ አፈፃፀም

ዳይሬክቶሬቱ ጣልቃ እንዲገባ ያቀረብኩትን አቤቱታው ፍርድ ቤቱ አለመቀበሉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ከአክሲዮን ሽያጭ ጋር በተያያዘ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 423 አኳያ ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር የሰጠዉን ትእዛዝ ተከትሎ ለተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸዉ በአቤቱታዉ ላይ መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ሆኖም ተጠሪዎች በአድራሻቸዉ ሊገኙ እንዳልቻሉ አመልካች በመሐላ ቃል በማረጋገጣቸዉ ተጠሪዎች አገራዊ ሽፋን ባለዉ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በሚወጣ ማስታወቂያ ጥሪ እንዲደረግላቸዉ ታዞ በቀን 11/03/2013 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ መጥሪያ ጥሪ እንደተደረገላቸዉ የሚገልጽ ጋዜጣ በማስረጃነት የቀረበ ቢሆንም ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የአመልካች አቤቱታና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የተባለዉ ትእዛዝና ዉሳኔ ይዘት ሲሆን እኛም በሐራጅ ማስታወቂያዉ ላይ ያልተመለከተዉን አክሲዮን ማኅበሩ የጠየቀዉን እዳ ጭምር አመልካች ሲከፍሉ ነዉ የአክሲዮኑ ስመ-ሀብት በስማቸዉ ዞሮ የሚመዘገበዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አማካኝነት በወጣዉ የሐራጅ ሽያጭ በመሳተፍ በጨረታዉ አሸናፊ በመሆን የገዙት በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ በሲነመር ትሬዲንግ አክሲዮን ማኅበር የሚገኝ አክሲዮን ነዉ፡፡ ዳይሬክቶሬቱ የአክሲዮን ሐራጅ ሽያጭ ለማከናወን ለሕዝብ ይፋ ባደረገዉ ማስታወቂያ ላይ ከአክሲዮኑ ጋር በተያያዘ ከባለአክሲዮኑ የሚፈለገዉን እዳ አለመግለጹ ተረጋግጧል፡፡ዳይሬክቶሬቱ በዚህ አግባብ እዳ መኖር አለመኖሩን በማስታወቂያዉ ላይ ሳይገልጽ ማስታወቂያ ያወጣበትን ምክንያት እንዲያብራር በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠይቆ በሰጠዉ አስተያየት አክሲዮን ለመሸጥ በሚወጣ ማስታወቂያ ላይ የእዳ መኖር አለመኖር መግለጽ የተለመደ አሰራር እንዳልሆነ ገልጿል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 423(2/ለ እና ሠ) ስር በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ንብረት ለመሸጥ ለሕዝብ ይፋ በሚደረግ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ ከሚሸጠው ንብረት ላይ የሚጠየቅ መብት ወይም ማንኛውንም ተጫራች ሊያውቀው የሚገባ ዝርዝር መገለጽ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡በሐራጅ ማስታወቂያዉ ላይ በዚህ መልኩ እንዲገለጽ ሕጉ የሚያስገድደዉ ተንቀሳቃሽ(ግዙፍነት ያለዉም ሆነ ግዙፍነት የሌለዉ) ንብረትም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ በሚወጣዉ ማስታወቂያ ላይ ሁሉ እንደሆነ የድንጋጌዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ዓላማ ገዥ ስለንበረቱ ባህርያትና ንብረቱን ከገዛ በኋላ ስለሚመጣበት ኃላፊነት እንዲሁም የሚያስከትልበትን ወጪ አዉቆና አመዛዝኖ

ለንብረቱ ተገቢ ነዉ ብሎ ያመነዉን ዋጋ በመወሰን መጫረት እንዲችል ነዉ፡፡ በፍርድ ባለእዳዉ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ አክሲዮን በሐራጅ ለመሸጥ ማስታወቂያዉ ያወጣዉ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አክሲዮን ለመሸጥ በሚወጣ ማስታወቂያ ላይ ከአክሲዮኑ የሚፈለግ እዳ ስለመኖሩ የሚገለጽበት የተለመደ አሰራር የለም ሲል የገለጸዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 423(2/ለ እና ሠ) ላይ በአስገዳጅነት የተደነገገዉን ያላገናዘበ ነዉ ፡፡የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳይሬክቶሬቱ የገለጸለትን እንዳለ በመቀበል እዳ መኖር አለመኖሩን ገዥ በራሱ አስቀድሞ ማረጋገጥ የሚገባዉ እንጂ በሐራጅ ማስታወቂያ ላይ ሊገለጽ የሚገባ ነገር እንዳልሆነ በመጥቀስ መወሰኑ ተጠቃሹን የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከዚህ አኳያ በስር ፍርድ ቤት የተፈጸመዉ ስህተት ታርሞ መወሰኑ ተገቢ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የሐራጅ ማስታወቂያ ሲወጣ ሽያጭ የተፈጸመበት አክሲዮን ሥመ-ሀብት ሲተላለፍ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚከፈል ዕዳ ስለመኖሩ ተገቢው ዝርዝር አለመግለጹ የሐራጅ ሽያጩ ጉልህ የሆነ የአሻሻጥ ጉድለት እንዳለበት በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሐራጅ ማስታወቂያ ሲወጣ ሽያጭ የተፈጸመበት አክሲዮን ሥመ-ሀብት ሲተላለፍ ለአክሲዮን ማኅበሩ የሚከፈል ዕዳ ስለመኖሩ ተገቢው ዝርዝር አለመገለጹ የሐራጅ ሽያጩ ጉልህ የሆነ የአሻሻጥ ጉድለት እንዳለበት የሚያሳይ መሆኑ በተረጋገጠበት የአክሲዮኑ ስመ-ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ የሚመዘገበዉ ወይም አመልካች ባለአክሲዮን እንደሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ የሚሰጣቸዉ በምን አግባብ ነዉ የሚለዉ ነጥብ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻ ነዉ፡፡ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈጸም ያዘዘዉ የሥር ፍርድ ቤት በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በኩል እንዲሸጥ ያደረገዉን አክሲዮን የፍርድ ባለዕዳው በአክሲዮኖ ላይ በነበራቸዉ መብትና ግዴታ ልክ ለአመልካች(ለገዥ) የማስተላለፍ ኃላፊነት ስላለበት የአመልካችን ሥመ-ሀብት ዝውውር ይፈጸምልኝ አቤቱታ ማስተናገድ አለበት፡፡

በሌላ በኩል በሐራጅ የተሸጠዉ ንብረት አክሲዮን ስለሆነ እንደሚታወቀዉ አክሲዮን ደግሞ ግዙፍነት የሌለዉ ተንቀሳቃሽ ንብረት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 435 ስር የሚንቀሳቀስ ንብረት እንዲሸጥ በሚወጣዉ ማስታወቂያ ላይ ጉድለት በመገኘቱ ወይም የሽያጩ ሥነ ሥርዓት በትክክል ባለመፈጸሙ ምክንያት ማናቸዉም የሚንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ እንደማይፈርስ፤ይልቁንም በሥርዓቱ መጓደል ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማናቸዉም ሰዉ ለጉዳቱ ኃላፊ በሆነዉ ሰዉ ላይ ክስ አቅርቦ ተገቢ ካሳዉን ሊጠይቅ እንደሚችል፤ለጉድለቱ ኃላፊ የሆነዉ ገዥዉ ራሱ የሆነ እንደሆነ ግን የገዛዉን እቃ እንዲመልስ ወይም ካሳ እንዲከፍል ሊወሰን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ይህ ድንጋጌ የሚያስገነዝበዉ የሚንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የተደረገ የሐራጅ ሽያጭ በገዥ ጉድለት ካልሆነ በስተቀር በሌላ ጉድለት ሊፈርስ እንደማይችልና የሚሸጠዉ አክሲዮን በሆነ ጊዜ በሐራጅ ማስታወቂያዉ ላይ በተፈጠረ ጉድለት ምክንያት ወይም የሽያጩ ሥነ ሥርዓት በትክክል አለመፈጸሙን መሰረት በማድረግ ሐራጁ ሊፈርስ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ ድንጋጌዉ አለማመላከቱን ነዉ፡፡

እንዲሁም ሽያጩን ከዉል ሕግ አንጻር የተመለከትን እንደሆነም የሐራጅ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይፋ ተደርጎ አመልካች በሀራጅ ማስታወቂያዉ መነሻ በሐራጁ ተሳትፈዉ አሸናፊ የሚያደርጋቸዉን ዋጋ ሲያቀርቡ ዉል የማቅረብ ተግባር (Offer) እንዳደረጉ ስለሚቆጠርና የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አመልካች ያቀረቡትን ከፍተኛ ዋጋ በመቀበል የጨረታዉ አሸናፊ እንደሆኑ ሲገልጽ ዉል የመቀበል ተግባር (Acceptance) እንደፈጸመ ስለሚያሳይ የአክሲዮን ሽያጭ ዉል ተቋቁሟል፡፡የአንድ ዉል ተዋዋይ ወገን እዉነቱን አዉቆ ቢሆን ኖሮ ዉሉን ሊዋዋል እንደማይችል ማስረዳት ከቻለ እንዲህ አይነት ስህተት የዉል ማፍረሻ ሊሆን የሚችል ዐይነተኛ ስህተት(fundamental mistake) ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1797 እና 1798 ስር እንደተደነገገዉ ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል፡፡ሆኖም አመልካች ከአክሲዮኑ ጋር በተያያዘ አክሲዮን ማኅበሩ የሚጠይቀዉ እዳ መጠን በሐራጅ ማስታወቂያ ላይ ተገልጾ ቢሆን ኖሮ በጨረታዉ በመሳተፍ አክሲዮኑን አልገዛም ነበር በማለት የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስ ባለመጠየቃቸዉ የዉል ሕጉን መሰረት በማድረግ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡

በተጨማሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በሐራጅ ማስታወቂያዉ ላይ የተፈጠረ ጉድለት የሚመለከት በመሆኑ ይህንን እንደ ጉድለት የሚቆጥረዉ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በመሆኑ የዚህ ጉድለት ሕጋዊ ዉጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉን ለመወሰን ተፈጻሚ ሊደረግ የሚገባዉም ከዉል ሕግ ይልቅ ይኸዉ የሥነ ሥርዓት ሕግ ሊሆን ይገባል፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ አመልካች የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ አለመጠየቃቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሐራጁ እንዲፈርስ ቢጠይቁ እንኳን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 435 ላይ የተደነገገዉ በጠባቡ መተርጎም ስላለበት በአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ የሚገባዉ ነገር ባለመገለጹ ምክንያት በተፈጠረ ጉድለት ምክንያት ሐራጁ ሊፈርስ አይችልም፡፡ ሕጉ በዚህ ድንጋጌ እንደ መፍትሔ ያስቀመጠዉ የሐራጅ ሽያጩን ማፍረስ ሳይሆን በተከሰተዉ ጉድለት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛዉም ሰዉ የሐራጅ ሽያጩ ሳይፈርስ ለጉዳቱ አላፊ በሆነዉ ሰዉ ላይ ክስ አቅርቦ ተገቢ ካሳ እንዲከፈለዉ ጠይቆ የሚካስበትን አግባብ ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ ይግባኝ እየተሰማ እያለ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ አመልክቼ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት አቤቱታዬን አለመቀበሉ ስህተት ነዉ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መርምረናል፡፡አመልካች ይግባኝ ያቀረቡት በአፈጻጸም መዝገብ ላይ የስር ፍርድ ቤት ሰጥቶ የነበረዉን ትእዛዝ በመቃወም ነዉ፡፡የፍርድ አፈጻጸም መዝገብ በዋናነት የሚከፈተዉ ፍርድ ለማስፈጸም በመሆኑ በዋናዉ ክርክር ጊዜ ያልነበረና ፍርዱ የማይመለከተዉ ሰዉ በክርክሩ እንዲሳተፍ በማድረግ እየተሰማ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት ያለበት ሰዉ ማነዉ ምን ያህል ካሳ መክፈል አለበት በሚለዉ ጭብጥ ላይ ክርክር ተሰምቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት አይደለም፡፡ለዚህም ነዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 435 ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰዉ ካሳ መጠየቅ የሚችለዉ ኃላፊነት ባለበት ሰዉ ላይ ክስ በማቅረብ ነዉ ተብሎ የተደነገገዉ፡፡ስለሆነም ይግባኝ

ሰሚዉ ችሎት አመልካች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በፍርድ አፈጻጸም መዝገብ ላይ ጣልቃ እንዲገቡ በመጠየቅ ያቀረቡትን አቤቱታ አለመቀበሉ የሥነ ሥርዓት ሕግ ድጋፍ ያለዉ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በሐራጅ ማስታወቂያዉ ጉድለት ምክንያት ከአክሲዮኑ ዋጋ በላይ ተጨማሪ እዳ እንዲከፍል ተጠይቀዉ እዳዉን በመክፈላቸዉ የሚደርስባቸዉን ኪሳራ (ጉዳት) አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት ኃላፊነት ባለበት ሰዉ ላይ ክስ በመመስረት እንዲተካላቸዉ ሊጠይቁ ከሚችሉ በስተቀር እዳዉ አይመለከተኝም በሚል ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡በመሆኑም የአክሲዮኑ ሥሙ-ሀብት ወደ አመልካች ስም ዞሮ ሊመዘገብና አመልካች ባለአክሲዮን መሆናቸዉን የሚገልጽ ማስረጃ ከአክሲዮን ማኅበሩ እንዲሰጣቸዉ ፍርዱን የሚያስፈጽመዉ ፍርድ ቤት ሊያዝ የሚችለዉ የፍርድ ባለዕዳው በአክሲዮኑ ላይ በነበራቸዉ መብትና ግዴታ ልክ በመሆኑ አመልካች እዳዉን መክፈል አለባቸዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 185895 ላይ በቀን 02/07/2011ዓ/ም የሰጠዉ ትዕዛዝ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 175625 ላይ በቀን 04/06/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## <u>ት እ ዛ ዝ</u>

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

# የወንጀል ህግ

የሰ.መ/ቁ. 185700

የካቲት 30/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- አቶ ቢዝነስ ለማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው የወንጀል ቅጣት ሊገደብ ስለሚቻልበት ሁኔታ በወንጀል ህጉ ውስጥ ስለ ወንጀል ቅጣት አገዳደብ ከተቀመጠው መመዘኛ እና በዚሁ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/17211 ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አኳያ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በሁለት ተከሳሾች ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የግራ ቀኙ ምስክሮች ተሰምተው ተጠሪ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በ1(አንድ) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖ የቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም በ2(ሁለት) ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ ታዟል፡፡ አመልካች የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ አይገባም በማለት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 08/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቀረበበትን ክስ ክዶ በተከራከረበት፤ ከተበዳይ ጋር ታርቆ ባልካሰበት እና የፍርድ ቤቱን ወጪ ለመክፈል ማረጋገጫ ባላቀረበበት የቅጣት ውሳኔው መገደቡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና 197 መመዘኛን ያላማከለ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከላይ በመግቢያው ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ግራ ቀኙ በተገኙበት ለማጣራት ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ጭብጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ እንግዲህ የወንጀል ቅጣት ዋና ዓላማው አጥፊውን ማስተማር ነው፡፡ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለማስተማር ደግሞ ሁሌም ወደ ማረሚያ ቤት መላክ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይልቁንም ለጥፋተኛው አንድ የፈተና ጊዜ ከፅኑ ማስጠንቀቂያ ጋር ሰጥቶ አመሉ ቢፈተሽ መልካም ይሆናል ተብሎ ሲታመን የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም ለጊዜው አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤት በአንድ የወንጀል ተከሣሽ ላይ የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ የተወሰነው የእሥራት ቅጣት ሳይፈፀም በገደብ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችልበት መሰረታዊ መርሆዎችም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 ስር ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሊገደብ የማይቻልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር ቅጣት እንዳይገደብ የተቀመጠው ክልከላ 1ኛ/ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የፅኑ እስራት ቅጣት ወይም ከ3(ሶስት) ዓመት በሚበልጥ ቀላል እስራት ቅጣት ተፈርዶበት ከሆነ እና አሁን ጥፋተኛ በተባለበት ወንጀልም ከእነዚሁ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት ከሆነ፣ 2ኛ/ ከዚህ በፊት ያልተቀጣ ሆኖ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት ዓመት የበለጠ ፅኑ እስራት የሚፈረድበት ከሆነ፣ 3ኛ/ የቅጣት አፈፃፀሙ ከመታገዱ በፊት ጥፋተኛው በተራ ቁጥር 1 እና 2 ስር ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ በአንዱ ሊያስቀጣው የሚችል ሌላ ወንጀል ስለመፈፀሙ የተደረሰበት ከሆነ፣ 4ኛ/ ወንጀለኛው ቅጣቱ ታግዶለት ለፈተና በተለቀቀበት ጊዜ ውስጥ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 200 ስር በተመለከተው አኳኋን አስቦ አንድን ወንጀል የፈፀመ ከሆነ ወይም 5ኛ/ የቅጣት አፈፃፀሙ በታገደለት ጉዳይ የተሰጠው የፈተና ጊዜ መልካም ፍሬ የሚያስገኝ አለመሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲረዳው የሚሉት ናቸው፡፡ እናም ፍርድ ቤት አንድን የወንጀል ቅጣት ከመገደቡ በፊት የቅጣት ውሳኔው እንዳይገደብ ከእነዚህ መመዘኛዎች ውስጥ በአንዱ ክልከላ ያልተደረገበት መሆኑን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ተገቢ ነው ያለውን የወንጀል ቅጣት ከወሰነ በኋላ የቅጣት ውሳኔን አፈፃፀም በፈተና ጊዜ እንዲቆይ አዟል፡፡ በተጠሪ ላይ የተወሰነው የቅጣት ውሳኔ እንዳይገደብ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር የተቀመጠ ክልከላ የለም፡፡ አመልካችም የቅጣት ውሳኔው ሊገደብ አይገባም የሚለው በወንጀል ህግ አንቀፅ 194 ክልከላ ተደርጎበታል በሚል ሳይሆን ተጠሪ ክሱን ክዶ ከመከራከሩም በላይ ከተበዳይ ጋር ታርቆ ለመካስ እና የፍርድ ቤቱን

ወጪ ለመሸፈን የሰጠው ማረጋገጫ የለም በሚል ነው፡፡ በመሰረቱ እነዚህ መመዘኛዎች በወንጀል ህጉ አንቀፅ 197 መሰረት ጥፋተኛው በተሰጠው የፈተና ጊዜ ውስጥ በመልካም ጠባይ እንዲመራ እና የፈተና ጊዜው ተገቢውን ፍሬ እንዲያፈራ በሚል ለመልካም ጠባይ አመራር ዋስትና የሚሰጡ ትዕዛዛት እንጂ ቅጣትን ለመገደብ ቅድመ ሁኔታዎች አይደሉም፡፡ በሰ/መ/ቁ/172111 ላይ የተሰጠው ውሳኔም በመዝገቡ ላይ በወንጀል ጥፋተኛ ከተባሉት ግለሰብ የግል ሁኔታ አንፃር የፈተና ጊዜ ቢሰጣቸው በመልካም ጠባይ የሚመሩ ለመሆኑ አሳይተዋል የሚያስብል ነገር አልተገኘም በሚል አቋም የተያዘበት ጉዳይ እንጂ ሁሌም ቢሆን የወንጀል ክስ ክዶ የተከራከረ ወይም ከተበዳዩ ጋር ታርቆ ተገቢውን ካሳ ላልከፈለ የወንጀል አጥፊ ቅጣት ሊገደብ አይገባም የሚል ግልፅ ትርጉም አይደለም፡፡ ከመነሻውም ቢሆን የወንጀል ክስን ክዶ መከራከር በራስ ላይ ማስረጃ ካለመሆን እና የወንጀል ጥፋተኝነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥ ድረስ ንፁህ ሆኖ ከመገመት ህገ መንግስታዊ መብት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የወንጀል ክስ ያላመነ ሰው የቅጣት ውሳኔ ሊገደብለት አይገባም በሚል ትርጉም ሊሰጥበት የሚቻል ጉዳይም አይደለም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የወንጀል ክስን ማመን፤ ከተበዳዩ ጋር ታርቆ በእውነት መፀፀትን ማሳየት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች የወንጀል ቅጣት ውሳኔን ለመገደብ በቅድመ ሁኔታነት የተቀመጡ መመዘኛዎች ሳይሆኑ የወንጀል አጥፊው በመልካም ጠባይ የሚመራ ለመሆኑ እንዲያቀርብ የሚጠየቅ የዋስትና ማረጋገጫ በመሆኑ በህግ በግልፅ ያልተቀመጠ ክልከላ መሰረት ተደርጎ ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላይ የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ ማገዱ እና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመቀበሉ የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ/ቁ/181393 ላይ ጥቅምት 26/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ያፀናበት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 186919

ታሕሳስ 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ ምላው

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 22/03/2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሽራሮ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07568 በቀን 24/10/2011 ዓ.ም አመልካችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ድንጋጌ ጥፋተኛ በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀን 02/11/2011 ዓ.ም አመልካች ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ተቀጥቶ ትምሕርት ስላላገኘ በአስራ ስምንት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሽራሮ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር 1ኛ ተከሳሽ እና በአሁን አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተከሳሾች የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 32/1/ሀ እና 670 ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በቀን 03/07/2011 ዓ.ም በግምት 5፡30 ሰዓት ሲሆን በሽራሮ ከተማ ቀበሌ ሙሴ ልዩ መጠሪያው ሰላም ፕላኔት ሆቴል አካባቢ የግል ተበዳይን 1ኛ ተከሳሽ ከኂላው በመምጣት በእጁ አንገቱን አንቆ ሲይዘው አመልካች ደግሞ ከፊት እጁን አንቆ በመያዝ ወደ ኮብል ስቶን በአፉ

በመድፋት እንዲወድቅ በማድረግ በሱሪው ኪስ ውስጥ የነበረውን ብር 400 ገንዘብ እና ብር 2200 የሚገመት ሞባይል ወስደዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽ ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተከሳሾች ክሱን እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽም ክሱን ለመከላከል ያስችለናል ያሉትን የመከላከያ ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ የቀረበባቸውን ክስ አልተከላከሉም በማለት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 31/1/ሀ እና 670 ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ቅጣቱንም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማስላት የስር 1ኛ ተከሳሽን በሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን አመልካችን በሚመለከት ደግሞ አመልካች ከዚህ በፊት በሶስት የተለያዩ መዝገቦች የተቀጣ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል፤ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188/1/2 ቅጣቱ የአዲሱ ወንጀል መጨረሻ ሊያርፍ እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ እና አመልካች በተደጋጋሚ ተቀጥቶ ትምሕርት ስላላገኘበት እና አሁን ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ አንቀጽ እስከ 15 ዓመት ሊደርስ በሚችል ቅጣት እንደሚቀጣ ስለሚደነግግ የዚህ እጥፍ 30 ዓመት ነው፤ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 የ 30 ዓመት እስራት ስለሌለ ወደ 25 ዓመት ወርዷል፤ ይህም እርከን 37 ላይ ያርፋል፤ ወንጀሉ በሕብረት የተፈጸመ በመሆኑ አንድ ማክበጃ ቢኖርም ከእርከን 37 በላይ የእስራት እርከን የለም፤ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ አለው በማለት ቅጣቱን አቅሎ በእርከን 36 ላይ በማሳረፍ በዚሁ እርከን ባለው ፍቅድ ስልጣን በ 18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካች ወንጀል እንደፈጸምኩ ባላስረዱበት ሁኔታ አመልካች ክሱን እንድከላከል ብይን መሠጠቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካች ባቀረብኳቸው መከላከያ ምስክሮች ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለበት ቦታ ላይ እንዳልነበርኩ አስረድቼ ሳለሁ መከላከያ ምስክሮቼ የሰጡት የምስክርነት ቃል በአግባቡ ሳይመዘን ጥፋተኛ መባሌ አግባብ አይደለም፤ አመልካች ከዚህ በፊት ተደጋጋሚ የወንጀል ሪርድ አለበት በማለት የቀረበው የቅጣት ማክበጃ የወንጀል ሕጉን ቁጥር 84 እና 188(1)(2) ድንጋጌን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ልማደኛ ደጋጋሚ ነው በማለት ቅጣቱን አክብደው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከቅጣት አንጻር አግባብነቱን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል በፊት በሶስት የተለያዩ ወንጀሎች ጥፋተኛ ተብሎ ተቀጥቷል፤ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188(2) እና (3) እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22/2 መሠረት ልማደኛ ደጋጋሚ በሚሆንበት ጊዜ በልዩ ሕግ ከተቀመጠው ቅጣት ከብዶ እጥፍ ተደርጎ ሊቀጣ እንደሚችል እና በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተቀመጠው ማለፍ እንደማይቻል ተደንግጓል፤ አመልካች ካንድም ሁለቴ ተቀጥቶ ከጥፋቱ ሊማር ስላልቻለ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ቅጣቱ ከብዶ መወሰኑ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መገንዘብ የቻልነው በአመልካች ላይ ቅጣቱ ከብዶ ሊወሰን የቻለው አመልካች ከዚህ በፊት በሶስት የተለያዩ መዝገቦች የተቀጣ ቢሆንም ከጥፋቱ መማር ስላልቻለ ቅጣቱ ሊሰላ የሚገባው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 188(1)እና(2) በሚደነግጉት አግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ሲያሰላ አመልካች በአዲሱ ወንጀል የሚቀጣበትን ጣሪያ ቅጣት በመውሰድ የዚሁን መጠን እጥፍ በመያዝ ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ነጥብ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው በማለት ቅጣቱን አክብዶ ለመወሰን አመልካች በአዲሱ ወንጀል ሊቀጣ የሚችልበትን ጣሪያ ቅጣት መያዙ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ሕጉ መሠረታዊ ዓላማ እና ግብ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የሕዝቦቹን፤ የነዋሪዎቹን፤ ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብት እና ጥቅም መጠበቅ እና ማረጋገጥ፤ ስለወንጀሎች እና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጽሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 1 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህንኑ ዓላማ በሚያሳካ ሁኔታም ቅጣት ስለሚሰላበት፤ ስለሚከብድበት እና ስለሚቀልበት ሁኔታ በዚሁ ሕግ ላይ ስለወንጀል ቅጣት እና አፈጻጸሙ በሚደነግገው ሁለተኛ መጽሐፍ ከአንቀጽ 87 ጀምሮ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 188/1 በዚሁ ሕግ አንቀጽ 67 /ስለደጋጋሚነት/ በተገለጹት ሁኔታዎች አንድ አዲስ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ፤ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ማክበድ ያለበት ሲሆን ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ መወሰን ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕጉ ልዩ ክፍል ለአዲሱ ወንጀል ወይም ከአዲሶቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ከባድ ስለሆነው ወንጀል የተደነገገውን ጣራ ቅጣት እጥፍ እስኪሆን ቅጣቱን ሊያከብድ ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ ንዑስ ቁጥር 2 በተደጋገሙት የወንጀሎች ዓይነት እና ብዛት እንዲሁም በወንጀለኛው ጥፋተኝነት እና በድርጊቱ አደገኛነት መጠን ፍርድ ቤቱ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ከፍተኛ ቅጣት ሳይከተል ለቅጣቱ ዓይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ሊያሳድግ ይችላል በማለት ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አንቀጽ 22/2 ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአዲሱ ወንጀል የመነሻ ቅጣቱ የሚያርፍበትን እርከን በመመሪያው መሠረት ከለየ በኋላ ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188 በተመለከተው መሠረት ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ ይችላል፤ በመቀጠልም ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፤ ነገር ግን በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ከድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው በተጠቀሰው አግባብ የአዲሱን ወንጀል የቅጣት ጣሪያ በመውሰድ ቅጣትን እጥፍ ድረስ ማክበድ የሚቻለው ወንጀሉ የተደጋገመ መሆኑን ብቻ በማየት ሳይሆን ጥፋተኛው የፈጸማቸው ወንጀሎች ዓይነት፤ ክብደት እና ብዛት እንዲሁም ጥፋተኛው ወንጀል ለመፈጸም የነበረው የአደገኝነት መጠን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ መሆኑን እና ይኸው ሲፈጸምም ፍርድ ቤቱ እንደ ሁኔታው ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ይህንኑ አንቀጽ መሠረት በማድረግ ቅጣትን ሲወስኑ እነኚህን ሁኔታዎች በጥንቃቄ ሊፈትሹ ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ከዚህ በፊት የመዝገብ ቁጥራቸው 4977፤ 05517 እና 05516 በሆኑ የተለያዩ ሶስት መዝገቦች በገደብ፤ በ4 ዓመት ጽኑ እሥራት እና በአንድ ዓመት ከ7 ወር እስራት ተቀጥቶ ሊታረም አልቻለም በማለት የአዲሱን ወንጀል ጣሪያ ቅጣት በመወሰድ እጥፉን ወስዶ ቅጣቱን ያሰላ ቢሆንም አመልካች ጥፋተኛ የተባለባቸው ወንጀሎች ዓይነት እና ክብደት እንዲሁም ጥፋተኛው ወንጀል ለመፈጸም የነበረው የአደገኝነት መጠን ምን እንደሚመስል በውሳኔው ላይ አላመላከተም፡፡ ስለሆነም ይህ ባልተሟላበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ደጋጋሚ ወንጀለኛ ነው በማለት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 188(1)እና(2) መሠረት በአዲሱ ወንጀል የሚቀጣበትን የቅጣት ጣሪያ እጥፉን በመውሰድ ቅጣቱን አስልቶ በ 18 ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት ቅጣቱን እንደሚከተለው አስልተናል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው፤ አመልካች ድርጊቱን ለመፈጸም የተጠቀመው መሳሪያ የሌለ እና የወሰደው ንብረት ግምት ብር 2400 በመሆኑ የወንጀል ደረጃው በደረጃ 2 የቅጣት መነሻ እርከን ደግሞ በእርከን 13 ላይ ያርፋል፤ አመልካች ደጋጋሚ ወንጀለኛ በመሆኑ በአምስት እርከን ቅጣቱ ሊከብድ የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፤ በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ስላሉ በድምሩ በሰባት እርከን ቅጣቱ ሲከብድ በእርከን 20 ላይ ያርፋል፤ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስላለው ቅጣቱ ሲቀል በእርከን 19 ላይ ያርፋል፤ በእርከን 19 ያለው ፍቅድ ስልጣን ከአራት ዓመት እስከ አራት ዓመት ከአስር ወር ነው፤ ስለሆነም በዚሁ ፍቅድ ስልጣን ስር አመልካችን ያርማል፤ ሌሎቹንም ያስጠነቅቃል ብለን ያመንበትን አመልካች በአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ በማለት ቅጣቱን አሻሽለን ወስነናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሽራሮ ከተማ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07568 በቀን 02/11/2011 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያስተላለፈው የቅጣት ውሳኔ፤ ይህንኑ የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 05844 በቀን 26/11/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 118545 በቀን 18/02/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት በአመልካች ላይ ተላልፎ የነበረውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል በአራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ በማለት ወስነናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁጥር 181206

መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ሐይሉ(አብይ) ሲሳይ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሀምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች የመግደል ሙከራ ሳልፈፅም እንደፈፀምኩ ተደርጎ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

አመልካች በስር የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስም ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀፅ 27(1) እና 540 በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስቦ በሰንዳፋ በኬ 02 ቀበሌ ውስጥ አለማየሁ ሙላቱ የተባለውን የግል ተበዳይ በሽጉጥ ተኩሶበት ሆዱ ላይ በመምታት ጉዳት አድርሶበት ህክምና በማግኘቱ ምክንያት ህይወቱ ሊተርፍ ችሏል በዚህም የመግደል ሙከራ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ከሷል፡፡

አመልካች ድርጊቱን አልፈፀምኩም በማለት ስለተከራከሩ የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው የተሰሙ ሲሆን 1ኛ ምስክር አመልካች ወደ ሱቃቸው መጥተው ሲጋራ እንዲሸጡላቸው አዘዋቸው ዞር ሲሉ ሽጉጥ ያልያዙ ቢሆንም ሲጋራውን ይዘው ዞር ሲሉ የተኩስ ድምፅ የሰሙ መሆኑን ሆዳቸውን በግራ በኩል ተመትተው ሲወድቁ አመልካች መታሁክ ብለው ጥለዋቸው የሄዱ መሆኑን ያስረዱ ሲሆን 2ኛ ምስክርም ድምጽ ሰምተው ጎሚስታ ቤታቸው ፊት ለፊት ስላለ የጎማ ድምፅ መስሏቸው

ሲወጡ አመልካች ሲሮጡ የተመለከቱ መሆኑን የግል ተበዳይ ውጪ ወጥተው የነበሩ ቢሆንም መሮጥ ያልቻሉ መሆኑን ምን ሆንክ ሲሉት አመልካች በሽጉጥ መታኝ ብለው የሆዳቸውን ግራ ጎን አሳይተዋቸው መቆም አቅቷቸው የወደቁ መሆኑን ስላስረዱ አመልካች እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቷል፡፡

አመልካች በሰጡት የተከሳሽነት ቃልም ከግል ተበዳይ ጋር ፀብ የሌላቸው መሆኑን በተለመደ ሁኔታ ወደ ሱቃቸው በመሄድ ሲጋራ፤ውሃ የመሳሰሉትን ገዝተው የሚያልፉና የግል ተበዳይም የሚሸጇቸው መሆኑን በእለቱም በተመሳሳይ ሊገዙ ሄደው ሽጉጣቸው በካቦርት የውጭ ኪሳቸው ስለነበረ አውጥተው ወደ ግራ ጎናቸው ሊያዛውሩ ሲሉ መሳርያው ባርቆባቸው የግል ተበዳይን የመታ መሆኑን ተመታህ ብለው ሆዱን ይዘውልት የነበሩ ቢሆንም ቤተሰቦቹ ስለነበሩ ይገሉኛል ብለው በመፍራት ሸሽተው የሄዱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የአመልካች ምሰክርም በእለቱ ውሃ ለመግዛት ሄደው ከአመልካች ጎን ቆመው የነበረ መሆኑን አመልካች ሽጉጡን ከካፖርቱ ቀኝ ኪስ ወደ ግራ ኪስ ለማዛወር ሲል መሳርያው ተተኩሶ ጥይቱ በኮንቴነር ውስጥ አልፎ የግል ተበዳይን የመታው መሆኑን በዚህ ጊዜ አመልካች" መታሁክ " ያሉ መሆኑን ነገር ግን ወደ ውስጥ ገብተው የግል ተበዳይን ያልያዙ መሆኑን አመልካች የግል ተበዳይን አስበውበት ያልመቱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔም አቃቤ ህግ በምስክሩ አመልካች የግል ተበዳይን በሽጉጥ ሆዳቸውን የመቱ መሆኑን ያስረዳ መሆኑን የህክምና ማስረጃውም የግል ተበዳይ በተተኮሰባቸው ጥይት በደረሰባቸው ጉዳት ትንሹ አንጀት የተለያየ ቦታ ተበሳስቶ ፤ትልቁ አንጀት የላይኛው ክፍል ትንሹን አንጀት ሸፍኖ የሚገኘው በሆዱና በጉበት ሽፋን ላይ ሰንበር መኖሩን የሚገልፅ ሆኖ ነገር ግን አመልካችና የመከላከያ ምስክራቸው ያስመዘገቡት ሽጉጡን ያዛወሩበትን ቦታ እና ከድርጊቱ በኋላ አመልካች የግል ተበዳይን መያዝ አለመያዛቸውን አስመልክቶ እርስ በእርሱ የሚጋጭ የምስክርነት ቃል ስለሰጡ አመልካች በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ ናቸው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶ በስድስት አመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው ይግባኙን የሰረዘው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ከግል ተበዳይ ጋር ከትውውቅ የዘለለ ፀብ ወይም ጥላቻ ሳይኖረኝ ምስክሮቹም በክሱ አግባብ ሳያስረዱ የግል ተበዳይን ልገድል የምሞክርበት ምክንያት ሳይኖር አቃቤ ህግ የወ/ህ/ቁ.540ን ጠቅሶ ከፈፀምኩት ድርጊት ጋር የማይመሳሰል ክስ ማቅረቡ አላግባብ ነው፤እንደ ድርጊቱ እና እንደ ማሰረጃው ቅርበት በእንዝላልነት ወይም በግዴለሽነት

ጥፋተኛ ተብዬ ልቀጣ ሲገባ በመግደል ሙከራ መቀጣቴ የወንጀል ህጉን አላማ የሳተ ነው፤የአመልካች ሽጉጥ ወንጀል የተፈፀመበት ስለሆነ ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ የታዘዘውም አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በእንዝላልነት ወይም በግዴለሽነት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ይሰጥልኝ እንዲሁም ሽጉጡ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተሠጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ሽጉጤ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፤

በአመልካች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከድርጊቱ አፈፃፀምና ከወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ በሰጠው መልስም የአቃቤ ህግ የሰውና የሰነድ ማስረጃ የግል ተበዳይ ሆዱ ላይ ተመትቶ ጉዳት የደረሰበት በአመልካች ሽጉጥ መሆኑን ያረጋገጡ በመሆናቸውና ይህ ፍሬ ነገር በአመልካች ያልተካደ በመሆኑ በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በዚሁ አግባብ የተሰጠ በመሆኑ ሊፀና ይገባል፤አመልካች ሽጉጡን አቀባበሎት ከቦታ ቦታ ሲዘዋወር እንደነበረ በአመልካች ያልተካደ ፍሬ ጉዳይ በመሆኑ የተቀባበለ ሽጉጥ ጉዳት ቢያደርስ ውጤቱን እቀበለዋለሁ በማለት ሲንቀሳቀስ ወንጀሉ በግል ተበዳይ ላይ ስለተፈፀመ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 58(2)(ለ) በዚህ አይነት የሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ሆነ ተብሎ እንደተፈፀመ የሚደነግግ በመሆኑ የመከላከያ ምስክሩም ወንጀሉ በእንዝላልነት መፈፀሙን በማስረዳት የአቃቤ ህግን ማስረጃ ያላስተባበሉ በመሆኑ ወንጀሉ የተፈፀመበት ሽጉጥ ይመለስልኝ ማለቱ አግባብነት የሌለው በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፤ከተገቢው ህግና፤ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡አንድ የወንጀል ድርጊት ተፈፀመ የሚባለው ህጋዊ ፤ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ መሆኑ በወ/ህ/አንቀፅ 23(2) የተመለከተ በመሆኑና አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው የወ/ህ/አ.540ን ተላልፈው የመግደል ሙከራ ወንጀል መፈፀማቸውን መሰረት በማድረግ በመሆኑ ከአመልካች በተተኮሰ ጥይት የግል ተበዳይ በግራ ጎን ሆዳቸው ላይ መመታታቸውን ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ በመሆኑ ይህም የህጉ መሰረታዊ ነጥብ ማለትም ግዙፋዊ ፍሬ ነገር የተሟላ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ በአመልካች ላይ በአንቀፅ 27(1) እና 540 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው አመልካች ድርጊቱን አስበው የፈፀሙ መሆናቸው በአቃቤ ህግ ማስረጃ ሲረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም አመልካች የወንጀል ሙከራ ድርጊቱን የፈፀሙት አስበው መሆኑን ያረጋገጠበትን የህግ

አግባብ በውሳኔው ላይ አላመለከተም፡፡ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው ምላሽ ሲሰጥ የተቀባበለ ሽጉጥ ይዘው መንቀሳቀሳቸው የተቀባበለው ሽጉጥ ጉዳት ቢያደርስ ውጤቱን ተቀብለው መንቀሳቀሳቸውን ስለሚያሳይ የሃሳብ ክፍሉ በወ/ህ/አ.58(2) አግባብ የተሟላ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ የወንጀል ድርጊት ቀጥተኛ ባልሆነ አውቆ አጥፊነት ተፈፀመ የሚባለው ድርጊቱ ህገ ወጥና የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነው ይሁን ብሎ ውጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ያከናወነ መሆኑ ሲረጋገጥ ለመሆኑ በወ/ህ/አ.58(1)(ለ) ተመልክቷል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ አቃቤ ህግ በመልሱ ላይ አመልካች ሽጉጡ መቀባበሉን የሚያውቁ መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም የአመልካች ሽጉጥ ተቀባብሎ የተቀመጠው አመልካች መቀባበሉን አውቀው ይሁን በእንዝላልነት አቀባብለው በመርሳታቸው መሆኑን ለይቶ ሊያስረዳ የሚገባ ቢሆንም ይህንን ስለማድረጉ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

ሽጉጡን ከአንድ ጎናቸው ወደ ሌላው ሲያዛውሩ ሽጉጡ የተቀባበለ መሆኑን ያውቁ የነበረ መሆኑንም አላስረዳም፡፡አመልካች ሽጉጡ መቀባበሉን እያወቁ እንዳይቀባበል በማድረግ ሊያዘዋውሩ ሲገባ ተቀባብሎ እያለ በጥንቃቄ ቢዘዋወር ጉዳት አያስከትልም ቢያስከትለም የመጣው ይምጣ በማለት ውጤቱን በመቀበል ሽጉጡን ሲያንቀሳቅሱ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱን ያደረሱ መሆኑን አቃቤ ህግ ባላስረዳበት ወይም ወደዚህ አይነት መደምደሚያ የሚወስድ የምስክርነት ቃል ባልተሰጠበት ከመነሻውም አመልካች ወደ ግል ተበዳይ ሱቅ ሲሄዱ የተቀባበለ ሽጉጥ የታጠቁ መሆኑን ያውቁ የነበረ መሆኑን ባላስረዳበት ድርጊቱን ቀጥተኛ ባልሆነ አውቆ አጥፊነት እንደተፈፀመ ተደርጎ በአመልካች ላይ በወ/ህ/አ.27(1) እና 540 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ የወንጀል ህግ አንቀፅ 23(2) እና 58(1)(ለ) ን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ከዚህ ይልቅ አመልካች ሽጉጡን ከአንድ ጎናቸው ወደ ሌላው ሲያዛውሩ መቀባበል አለመቀባበሉን በማረጋገጥ ሊያዘዋውሩ ሲገባ ይህንን ሳያደርጉ ሽጉጡን ሲያንቀሳቅሱ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳቱን ማድረሳቸው ጉዳት ያደረሰውን ድርጊት አስመልክቶ ምንም ጥንቃቄ ወይም በቂ ጥንቃቄ አለማድረጋቸው አመልካች ድርጊቱን በቸልተኝነት የፈፀሙ መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካች የግል ተበዳይን በሽጉጥ የመቱት በቸልተኝነት ከሆነ ደግሞ የአመልካች ድርጊት ሞትን ያላስከተለ በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ የግራ ቀኙ ክርክር ከወ/ህ/አንቀፅ 27(1) ሊታይና ሊመረመር ይገባል፡፡በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶች እንደ ሙከራ ሊቆጠሩ ይችላሉ የሚል አስተያየት ቢኖርም አንድን የወንጀል ድርጊት ሙከራ ነው ለማለት ድርጊቱ በእውቀትና በፍላጎት የተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑ በተለያዩ ሀገራት ህጎች ውስጥ መካተቱ

በቸልተኝነት የሚፈፀሙ ድርጊቶችን እንደ ሙከራ መቁጠሩ በአሁኑ ጊዜ ብዙም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያሳያል ፡፡

የወንጀል ህጋችንም በአንቀፅ 27(1) “ማንም ሰው አስቦ…” የሚለውን ሃረግ በማካተት መቀረፁ ድርጊቱ በአውቆ አጥፊነት የተጀመረ መሆኑ መረጋገጡ መሰረታዊ መስፈርት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች የተከሰሱበት ድርጊት በቸልተኝነት የተፈፀመ የሙከራ ድርጊት መሆኑ ከላይ በተመለከተው አግባብ የተረጋገጠ ሆኖ እያለ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሊያርሙ ሲገባ ሳያርሙ መቅረታቸው አግባብ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር አመልካች ከቀረበባቸው የመግደል ሙከራ የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አመልካች የወንጀል ሙከራ ድርጊቱን የፈፀሙበትን ሽጉጥ እንዲወረስ የወሰነበትን የህግ አግባብ በውሳኔው ላይ ያላመለከተ በመሆኑና ተጠሪም የወንጀል ሙከራ ድርጊቱ የተፈፀመበት መሳርያ የሚወረስበትን አሳማኝና ህጋዊ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1.በፊንፊኔ ዙርያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.18862 ግንቦት 06 እና 08 ቀን 2011 ዓም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.315181 በ04/10/2011 ዓም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.311856 በ28/10/2011 ዓም በተሰጠ ትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነትና የቅጣት እንዲሁም የሽጉጥ ውርስ ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.195 (2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2.አመልካች ከቀረበባቸው ክስ በነፃ የተሰናበቱ ስለሆነ ከእስር ሊለቀቁ ይገባል ብለናል፡፡ለማረሚያ ቤቱ የመፈቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡

3.መለያ ቁጥሩ EP1291212 የሆነው የቱርክ ሽጉጥ ለአመልካች እንዲመለስላቸው በአብላጫ ድምፅ ታዟል፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የሰ.መ.ቁ.209051

ጥር 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዳኜ ደጀኔ

ተጠሪ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሸካ ዞን ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 671(2) ድንጋጌን ጠቅሶ በአሁን አመልካች ላይ በቀድሞ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን የወንጀል ህጉን ድንጋጌ በመተላለፍ በሸካ ዞን በየኪ ወረዳና ቴፒ ከተማ ውስጥ ከነሐሴ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ በቡድን በመደራጀትና ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ በመያዝ በጫካ ውስጥ በመደበቅ በሰው ግድያ፣ በዘረፋና ጥይት በመተኮስ የዜጎችን ሰላም በማወክ ላይ ከተሰማሩት 1ኛ/አይሳነው ሲሳይ፣ 2ኛ/ ኡመር ሰይድ፣ 3ኛ/ አላዲ ኤሊያስ፣ 4ኛ/ ጮቤ/ሙክታር ከድር/፣ 5ኛ/ አቢቲ/ዳግም ታደሰ/ ከሚባሉት የወንበዴ ቡድኖች ጋር በመሆን በክሱ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት ሲፈፅም ከቆየ በኋላ ታህሳስ 21/2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ የመንግስት የፀጥታ ኃይል በሰላም በር ቀበሌ ልዩ ስፍራው ታችኛው አዋሽ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የአሰሳ ሥራ እያደረጉ ባሉበት የአሁን አመልካች እና ለጊዜው ያልተያዙት ከላይ በስም የተዘረዘሩት ሽፍቶች ተሰባስበው ጫት እየቃሙ ባሉበት የፀጥታ ኃይሎች በስፍራው ሲደርሱ በፀጥታ ኃይሎቹ ላይ ጥይት በመተኮስ ሁለት የፀጥታ ኃይሎች ላይ ጉዳት ካደረሱ በኋላ ሁለት ሞባይሎችን ጥለው ወደተለያየ አቅጣጫዎች ሩጠው ያመለጡ ሲሆን የአሁን አመልካች በዚያው አካባቢ በሚገኝ የግለሰብ ቤት ተደብቆ በነጋታው

በፀጥታ ኃይሎች በአካባቢው ላይ በተደረገ ፍተሻ የተያዘ በመሆኑ በፈፀመው የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካች ክሱን ሳይቃወም ወንጀሉን ፈፅምያለሁ፣ ጥፋተኛም ነኝ ብሏል፡፡ ዝርዝር ቃሉን ሲያስመዘግብም ከጥር ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስማቸው በክሱ ዝርዝር ውስጥ "የወንበዴ ቡድን" ተብሎ ከተጠቀሱት ግለሰቦች ጋር የቡድኑ አባል ሆኖ አብሮ መኖር የጀመረ መሆኑን፣ ግለሰቦቹ እሱን ወደ ከተማ የማያስወጡት መሆኑን፣ በራሳቸው ግን ተቦዳድነው ማታ ማታ ወደ ቴፒ ከተማ በመሄድ ጥይት ተኩሰው የሚመለሱ መሆኑን፣ በተጨማሪም ከሃብታሞች ገንዘብ በመጠየቅ የሚቀበሉ መሆኑን፣ መኪናም እያስቆሙ ከአንድ ኤፍ ኤስ አር ላይ ብር 1000፣ አይሱዙ ከሆነ ደግሞ ብር 500 ተመን አውጥተው የሚቀበሉ መሆኑን፣ ከዚያን በፊት ሎሌ/ሙክታር አባድር/ የተባለው የሚቀበለውን ገንዘብ በጋራ ሲጠቀም የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ እየተጠቀመ እንዳልሆነ፣ ታህሳስ 21/2013 ዓ.ም ከእነዚሁ ግሰለቦች ጋር ሆነው በክሱ ዝርዝር በተጠቀሰው ቦታ ከቀኑ 7፡00 ሰዓት አካባቢ ቡና ዛፍ ስር ተቀምጠው ጫት በመቃም ላይ እንዳሉ የፀጥታ ኃይሎች ሲመጡባቸው ኡመር ሰይድ እና አይሳነው ሲሳይ የተባሉት በፀጥታ ኃይሎቹ ላይ ተኩስ ከፍተዉባቸው ከእነክላሺንኮቭ መሳሪያቸው ሲያመልጡ እርሱም ሮጦ አምልጦ በነጋታው የተያዘ መሆኑን፣ የግለሰቦቹ ስራ ህገ ወጥ መሆኑን እያወቀ የሽፍታ አባል በመሆን ከእነርሱ ጋር ማበሩ ጥፋት መሆኑን መናገሩን ያሳያል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ሙሉ በሙሉ አምኗል በሚል በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134 መሰረት ክስ በቀረበበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ በማለት በ21 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 16/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም አመልካች በዝርዝር የእምነት ክህደት ቃሉ በክሱ የተገለፀውን ወንጀል ስለመፈፀሙ ሳይሆን ያልተያዙ ሌሎች ግለሰቦችን በመላላክና በመርዳት መሳተፉን እንጂ በውንብድና ወንጀል ስለመሳተፉ ቃሉን ያልሰጠ በመሆኑ ቃሉ በክህደት መመዝገብ ሲገባው ክሱን ሙሉ በሙሉ አምኗል በማለት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ሳይሰሙ ጥፋተኛ መባሉ አግባብ አለመሆኑን፣ በድርጊቱም ተበዳይ ነኝ የሚል አካል ቀርቦ ባልተሰማበት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ አግባብ አለመሆኑን ጠቅሶ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የውንብድና ወንጀል መፈፀሙን አምኗል በሚል የግራ ቀኝ ማስረጃ ሳይሰማ በወንጀል ህግ አንቀፅ 671(2) ስር ጥፋተኛ ተብሎ በ21 ዓመት ጽኑ

እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት አግባብ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 24 እና ከመሰረታዊ የክርክር አመራርና ማስረጃ ምዘና መርሆዎች አንጻር በዚህ ችሎት እንዲጣራ በመታዘዙ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ይህንን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ በግልፅ መገንዘብ እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው የአሁን አመልካችን የእምነት ቃል መሰረት አድርጎ ነው፡፡ በእርግጥ በወንጀል የተከሰሰ ሰው በክሱ ማመልከቻው ላይ የተዘረዘረውን ወንጀል ለመስራቱ በሙሉ ያመነ እንደሆነ ይኸው በመዝገብ ላይ ከተፃፈ በኋላ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134(1) ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ ውሳኔ ለመስጠት በቅድሚያ ተከሳሹ ቃሉን በዝርዝር ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን፣ በዝርዝር የተሰጠው ቃል ተከሳሹ ከተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር ጋር አንድ ሊሆን እንደሚገባ እና ዝርዝር ቃሉ ተከሳሹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ የማያጠራጥር እና ቃሉም ሙሉ እምነት የሚጣልበት ሊሆን እንደሚገባው ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተከሳሽ ቃል መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመስጠት እንዲህ አይነት ጥብቅ መመዘኛ ያስፈለገበት መሰረታው ዓላማ ማንኛውም ተከሳሽ በራሱ ላይ ማስረጃ ያለመሆን ህገ መንግስታዊ መብት ያለው በመሆኑና በወንጀል የተከሰሰን ሰው አጥፊነት በተገቢው የማስረዳት ደረጃ የማስረዳት ግዴታ የዐቃቤ ህግ በመሆኑ እንደሆነ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 20 ስር በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች ከተደረገው ጥበቃ፣ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134 እና 141 ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም አንዱ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ተከሳሹ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በዝርዝር ያመነ ቢሆንም እንኳን ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ዐቃቤ ህግ ለክሱ የሚደግፈውን ማስረጃ እንዲያቀርብ እና እንደ ነገሩ ሁኔታ ተከሳሹም የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊታዘዝ የሚችል ስለመሆኑ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 134(2) ስር መደንገጉ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች የተከሰሰው ከሌሎች የጦር መሳሪያ ይዘው ጫካ በመግባት በሰው ግድያ፣ ዘረፋ እና ጥይት በመተኮስ የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ በማወክ ላይ የተሰማሩት የሽፍታ ቡድን አባል በመሆን ከባድ የወንብድና ወንጀል ፈፅሟል በሚል ነው፡፡ አመልካች በሰጠው ዝርዝር የተከሳሽነት ቃል ሽፍታ ተብለው ከተጠቀሱት ግለሰቦች ጋር አባል መሆኑን ከመግለፁ ውጭ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተገለፀው አግባብ በሰው ግድያ፣ ዘረፋ እና ጥይት በመተኮስ በህብረተሰቡ ሰላም እና ፀጥታ ስለማደፍረሱ በግልፅ የሰጠው ቃል የለም፡፡ እንዲያውም ሌሎች የአመልካች አባሎች

ናቸው የተባሉት ማታ ማታ ወደከተማ እየወጡ ተሽከርካሪዎችን በማስቆም አስገድደው ገንዘብ ሲቀበሉ እና ሌሎች ድርጊቶችን ሲፈፅሙ ለእርሱ ግን ወደከተማ መውጣት የተከለከለ መሆኑን ገልፅጿል፡፡

እንግዲህ ውንብድና፣ ዘረፋ እና ሽፍታነት የሚሉት ቃላት በተለምዶ በህብረተሰቡ ዘንድ አንዱ ሌላውን ለመግለፅ ተፈራርቆ አግልግሎት ላይ የሚውል ቢሆንም ቴክኒካዊ ልዩነት በመካከላቸው ያለ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ውንብድና እና ዘረፋ በወንጀል ህጉም ቢሆን ከሞላ ጎደል ትርጉም የተሰጣቸው እና በራሳቸው በተናጠል የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትሉ ስለመሆኑ ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 670 እና 672 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የውንብድና ወንጀል ማለት ተገቢ ያልሆነ ብልፅግናን ለራስ አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ የሌላ ሰው የሆነውን ተንቀሳቃሽ ንብረት በኃይል ተግባር ወይም፣ ከባድ የሆነ ማንገላታት፣ ወይም ከባድ ዛቻን በመጠቀም ወይም ማናቸውንም ሌላ ዘዴን በመጠቀም ተበዳዩን እንዳይከላከል በማድረግ ንብረቱን በኃይል መውሰድ ማለት እንደሆነ የወንጀል ህግ አንቀፅ 670 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ የዘረፋ ወንጀል ማለት ደግሞ በተፈጥሮ፣ በሰው ሰራሽ አልያም በማናቸውም ምክንያት በተፈጠረ አለመረጋጋት ወይም አደጋ ውስጥ የሌላ ሰው የሆነን ንብረት መስረቅ ማለት እንደሆነ ከወንጀል ህግ አንቀፅ 672 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በወንጀል ህጉ ስለ ሽፍታነት በተወሰነ መልኩ የተገለፀው በአንቀፅ 240 ስር ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ሽፍታነት በዋናነት የጦር መሳሪያ በመያዝ በህግ በተቋቋመ መንግስት ላይ ታስቦ ከሚደረጉ አመፆች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የጦር መሳሪያ ይዞ ማመፅ በራሱ ወንበዴ ወይም ዘራፊ የሚያስብል አይደለም፡፡ ድርጊቱ ውንብድና ወይም ዘረፋ የሚሆነው በአመፁ ሂደት ውስጥ በኃይል ተግባር የሌላውን ሰው/አካል/ ንብረት መውሰድ ወይም መዝረፍ ሲረጋገጥ ነው፡፡ እናም የአንድ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊት "ውንብድና ነው" ወይም "ዘረፋ ነው" ወይም "ሽፍታነት ነው" ለማለት ከመነሻው አጠቃላይ የተፈፀመው ድርጊት እና የተከሳሹ ተሳትፎ በተገቢው መንገድ ተለይቶ ሊታወቅ እና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው የተከሳሽነት ቃል/የእምነት ክህደት ቃል/ "የሽፍታ ቡድን" ተብሎ በክሱ ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ከተገለፁት ሰዎች ጋር አባል በመሆን ጫካ ከመግባቱ ውጭ በቀረበው ክስ አግባብ በውንብድና ስራው ላይ የተሰማራ ስለመሆኑ የገለፀው ነገር የለም፡፡ የሽፍታ ቡድን የተባሉት ሰዎችም በቁጥር በርከት ያሉ ከመሆናቸው በዘለለ በእርግጥም "የወንበዴ ቡድን" በሚያሰኝ አኳኋን የቡድን አደረጃጀት የነበራቸው እና የውንብድና ስራ ላይ ተሰማርተው የነበረ ስለመሆኑም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በእርግጥ የተጠቀሱት ግለሰቦች በጦር መሳሪያ የታገዘ የውንብድና ስራ ላይ ተሰማርተው የነበረ ስለመሆኑ አመልካች በዝርዝር

የተከሳሽነት ቃሉ ውስጥ ገልጿል፡፡ ሆኖም በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚሰጠው ቃል ውጤት የሚኖረው የራሱን ጉዳይ በተመለከተ ብቻ በመሆኑ በአመልካች ቃል መነሻነት ብቻ በዚያ ደረጃ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የህግ አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የሰጠው ዝርዝር የተከሳሽነት ቃል ከተከሰሰበት ወንጀል ዝርዝር ጋር አንድ ባለመሆኑ አመልካቹ ወንጀሉን ለመፈፀሙ በማያጠራጥር እና ሙሉ እምነት በሚጣልበት አኳኋን ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን አምኗል የሚያሰኝ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካቹ የወንጀል አጥፊነት ሊረጋገጥ የሚገባው ተጠሪ በሚያቀርበው ማስረጃ እንጂ አመልካች በሰጠው ቃል ባለመሆኑ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ ሙሉ በሙሉ ታምኗል በሚል መነሻነት በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከህግ አግባብ ውጭ ነው፡፡ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ስህተት ማረም ሲገባቸው ውሳኔውን ማፅናታቸው በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/09143 ላይ መጋቢት 28/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/08986 ላይ የካቲት 25/2013 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/14782 ላይ የካቲት 02/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በቀረበው ክስ ላይ የዐቃቤ ህግ ማስረጃን በመስማት እና የግራ ቀኙን ክርክር በሥነ ሥርዓት ህጉ መሰረት በመመራት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. አመልካች ከዋስትና መብት አንፃር የሚያነሳው ጥያቄ ካለ ክርክሩን ለሚሰማው ፍርድ ቤት ያቅርብ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ.161448

ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- የሺመቤት ጥላሁን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የሚያዝበት በቂ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) ተጠቅሶ በተጠሪ ላይ ባቀረበው ስድስት የወንጀል ክስ ላይ የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ሌሎቹ የተሰጡት በተጠሪ እና ተበዳይ ተብለው በተጠቀሱት ግለሰቦች መካከል በነበረው የንግድ ግንኙነት መነሻነት ለካፒታል መዋጮ መተማመኛነት እንጂ ለምንዛሪ አለመሆኑን አረጋግጫለሁ በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 693(2) በመቀየር የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ማግኘቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ለማስለወጥ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ የወንጀል ህጉን አንቀፅ 693(1) ድንጋጌን ጠቅሶ የሚያዙበት በቂ ገንዘብ ሳይኖራቸው ለተለያዩ አራት ሰዎች የተለያየ የገንዘብ መጠን የተፃፈባቸውን በጠቅላላው ስድስት ቼኮችን ሰጥተዋል በሚል ስድስት የወንጀል ክስ አቅርቧል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ቀርበው ቼኮቹ ለተበዳዮች የተሰጡት ለሚያቋቁሙት የጠጠር ማምረቻ አክሲዮን ማህበር የአባላትን ድርሻ ለማረጋገጥ ለመተማመኛ

እንዲሆን እንጂ ለመመንዘር እንዳልሆነ በመግለፃቸው ፍርድ ቤቱ የተከሳሽነት ቃሉን በክህደት መዝግቦ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በመጨረሻም በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ ለካፒታል መዋጮ መተማመኛነት እንጂ ለምንዛሪ ያልተሰጡ መሆናቸውን በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ማረጋገጡን ጠቅሶ ከአራተኛ ክስ ውጭ ያሉትን አምስቱን ክሶች በተመለከተ ክስ የቀረበበት አንቀፅ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 113(2) መሰረት ወደ አንቀፅ 693(2) በመለወጥ አራተኛ ክስን በተመለከለተ ደግሞ ክስ በቀረበበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ በማለት ለአራተኛ ክስ የእስራት ቅጣትን፣ ለተቀሩት ደግሞ የገንዘብ መቀጮ ቅጣትን መርጦ በጠቅላላው በ1(አንድ) ዓመት ከ8(ስምንት) ወር ፅኑ እስራት እና ብር 3,500(ሶስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲቀጡ ከወሰነ በኋላ የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም በሁለት ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ አዟል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገው በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት አቤቱታው በአብላጫ ድምፅ ሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 18/2010 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ክስ የቀረበበት የወንጀል ህጉ አንቀፅ መሰረታዊ ዓላማ ቼክ አውጪው ቼክ ከማውጣቱ በፊት በባንክ ሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ መኖሩን እንዲያረጋግጥ በማድረግ ለገንዘብ እንቅስቃሴ ጥበቃ ማድረግ ሆኖ እያለ ከድንጋጌው ዓላማ ውጭ በዋስትና የተሰጠ ነው ተብሎ ድርጊቱ ወደ ቸልተኝነት መቀየሩ ከህግ አግባብ ውጭ ነው፣ የተወሰነው ቅጣትም ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጋር የማይመጣጠን ከመሆኑም በላይ ተጠሪ ከግል ተበዳዮች ጋር ታርቀው ገንዘቡንም ባልከፈሉበት የእስራት ቅጣት ውሳኔውን አፈፃፀም መገደቡ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ የግራ ቀኙ የንግድ ግንኙነት መሰረት ተደርጎ ክስ የቀረበበት አንቀፅ ወደ አንቀፅ 693(2) የተቀየረበት እና ቅጣቱም የተገደበበት የህግ አግባብ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በአጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ጥር 03/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ክስ ከቀረበባቸው ስድስት ቼኮች ውስጥ በአራተኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ የተሰጡት ከተበዳዮች ጋር በጋራ ላቋቋምነው ኩባንያ በተበዳዮቹ በኩል ለተደረገው የካፒታል መዋጮ ማረጋገጫነት እንጂ ለምንዛሪ አይደለም፣

ቼክን ጨምሮ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች በዋስትና ሊሰጡ የሚችሉ ስለመሆናቸው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2863 የሚደነግግ በመሆኑ ድርጊቱ ወንጀል አይደለም፤ ለንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ ተብሎ የሚዋጣው መዋጮ የውል ግዴታን ከማቋቋም አልፎ የወንጀልም ሆነ ከውል ውጭ ኃላፊነትን የማያስከትል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2037 ላይ ተመልክቷል፤ የስር ፍርድ ቤትም ቼኮቹ በንግድ ግንኙነት ውስጥ ለካፒታል መዋጮ እንጂ ለምንዛሪ አለመሰጠታቸውን አረጋግጦ የወሰነ በመሆኑ በውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፤ ቅጣቱም ቢሆን የወንጀል ህጉን እና የቅጣት መሰረታዊ ዓላማን ያገናዘበ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር ቅሬታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው የግራ ቀኙ ክርክር የሚያጠነጥነው ቼክ በዋስትና ሊሰጥ የሚችል መሆን አለመሆኑ እና ከወንጀል አኳያ በሚኖረው ውጤት ላይ ነው፡፡ ይህንን ነጥብ አስመልክቶ ይኸው ችሎት ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ ሰኔ 15/2003 ዓ.ም በዋለው ችሎት "የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት በሚል በወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) ውስጥ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ለማቋቋም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን/ያለመኖሩን/ ማረጋገጥ ብቻ በቂ ነው" የሚል የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ እናም ከወንጀል ተጠያቂነት አኳያ ቼክን ለዋስትና አልያም ከምንዛሪ ውጭ ለሆነ ሌላ ዓላማ ሰጥቻለሁ የሚለው የወንጀል ክስ መከላከያ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡

ሆኖም ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/166392 ላይ ሚያዝያ 26/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ቼክ እንደማንኛውም ሊተላለፍ እንደሚችል የንግድ ሰነድ በመያዥያነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን፤ ይህ ሲሆንም በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2864-2866 ላይ በተመለከቱት ጥብቅ መመዘኛዎች አግባብ መመራት እንዳለበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በእርግጥ ይህ የህግ ትርጉም የተሰጠው በፍትሓ ብሔር ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ቢሆንም ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የህግ ትርጉም በማናቸውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ላይ የአስገዳጅነት ባህሪ ያለው በመሆኑ በወንጀልም ሆነ በፍትሓ ብሄር ጉዳይ ላይ የሚሰጠው የህግ ትርጉም አንዱ ሌላውን እንዳያፋልስ እና ውጤትም እንዳያሳጣ ወጥነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ቀደም ሲል በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ የተሰጠው የህግ ትርጉም ባለበት በኋላ ላይ የተሰጠው ትርጉም በወንጀል ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ በውጤት ደረጃም ሲታይ አንድ ቼክ አውጪ በፍትሓ ብሔር

ክስ ቼኩን ለዋስትና አልያም ለመያዥያነት የሰጠ ስለመሆኑ አረጋግጦ ከክሱ ነፃ ቢባል እንኳን በወንጀል ጉዳይ በቼክ ማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ይቀጣል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከወንጀል እና ፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ተፈጥሮዓዊ ባህሪ እና ከሚያስከትሉት ውጤት አኳያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

እናም ቀደም ሲል የወንጀል ህጉ አንቀፅ 693(1) አተረጓጎምን አስመልክቶ በሰ/መ/ቁጥር 67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም ትርጉሙ የተሰጠበትን ድንጋጌ መሰረት አድርገው የሚቀርቡትን የወንጀል ክሶችን ተግባራዊ አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የድንጋጌው አተረጓጎም እና አተገባበር አጠቃላይ ከወንጀል ህግ መሰረተ ሀሳብ እንዲሁም በዚሁ ችሎት በሰ/መ/ቁ/166392 ላይ ከተሰጠው ትርጉም አኳያ ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ አግባብ ቀድሞ የተሰጠው የህግ ትርጉም "በወንጀል የተከሰሰ ቼክ አውጪ ቼኩን ለዋስትና ወይም ለመያዥያነት የሰጠ ለመሆኑ እና የዋስትና ወይም የመያዥያ ውሉም በንግድ ህግ ቁጥር 952 እና በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2864-2866 በተመለከተው አግባብ የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ አይገባም" በሚል በተሻሻለ ትርጉም ተተክቷል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይም ከዚሁ ከተሻሻለው የህግ ትርጉም አንፃር ተቃኝቷል፡፡ ተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩት ክስ ከቀረበባቸው ስድስት ቼኮች ውስጥ አምስቱ ለምንዛሪ ሳይሆን ለካፒታል መዋጮ የተሰጡ በመሆኑ በወንጀል ልጠየቅ አይገባም በሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ ቸልተኝነት አንቀፅ የለወጠው አምስቱ ቼኮች በተጠሪ እና የግል ተበዳዮች መካከል በነበረ የንግድ ግንኙነት ለካፒታል መዋጮ የተሰጡ ስለመሆናቸው አረጋግጫለሁ በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ ፍርድ ቤቱ በዚህ መልኩ ሲወስን ከላይ የተመለከተው የህግ ትርጉም ያልተሰጠ በመሆኑ ተፈፃሚነት ያለው በሰ/መ/ቁ/67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው ነው፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት ደግሞ ቼክን ለዋስትናም ሆነ ለሌላ ከምንዛሪ ውጭ ለሆነ ዓላማ ሰጥቻለሁ የሚለው ጉዳይ ለወንጀል ክስ መከላከያነት ሊውል የሚችል አይደለም፡፡ እናም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ምክንያት ጠቅሶ ድርጊቱን ወደ ቸልተኝነት አንቀፅ መቀሩ ከድንጋጌው አፈፃፀም እና አተረጓጎም አኳያ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ነው፡፡ ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ውሳኔ ደግሞ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4(ሸ)) የሚደነግግ በመሆኑ ውሳኔው በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው ነው፡፡

ሆኖም ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ ቀድሞ ከተሰጠው የህግ ትርጉም የተለየ ትርጉም የተሰጠ በመሆኑ የተጠሪ መከራከሪያ ተሻሽሎ ከተሰጠው የህግ ትርጉም አኳያ ስለሚኖረው ውጤት ማየቱ ተገቢ

ይሆናል፡፡ እንግዲህ ተሻሽሎ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ ሰጥቷል ተብሎ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ከወንጀል ኃላፊነት ነፃ ሊወጣ የሚችለው ቼኩ የተሰጠው በዋስትና ወይም በመያዥ ያነት መሆኑን እና የዋስትናው አልያም የመያዥያ ውሉም በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ ነው፡፡ አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ ቼኩን ለካፒታል መዋጮ ማረጋገጫነት ስለመስጠታቸው ያረጋገጡት በሰው ምስክር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በተሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት ቼኮቹ ስለመሰጠታቸው የተረጋገጠ ነገር ባለመኖሩ የተሻሻለው ትርጉም በተጠሪ የወንጀል ኃላፊነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/187459 ላይ ጥር 22/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሎ ተጠሪ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ክሶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) ስር ጥፋተኛ ናቸው ተብሏል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ የጥፋተኝነት ፍርድ ለተሰጠበት የወንጀል ህጉ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ እና እርከን የወጣለት ነው፡፡ ተጠሪ በአምስቱ ክሶች ውስጥ በቂ ስንቅ ሳይኖራቸው ሰጥተዋል በተባሉት ቼኮች ላይ ያለው የገንዘብ መጠን እንደ ቅደም ተከተላቸው ብር 5,000,000(አምስት ሚሊዮን ብር)፣ ብር 1,000,000(አንድ ሚሊዮን ብር)፣ ብር 240,000(ሁለት መቶ አርባ ሺህ ብር)፣ 100,000 ዩሮ(አንድ መቶ ሺህ ዩሮ) ወይም ብር 2,205,000(ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ አምስት ሺህ ብር) እና ብር 500,000(አምስት መቶ ሺህ ብር) ነው፡፡ በዚሁ አግባብ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት 1ኛ ክስ ደረጃ 10፣ የእስራት ቅጣት እርከን 23 እና መቀጮ እርከን 6፤ 2ኛ ክሰ ደረጃ 8 የእስራት ቅጣት እርከን 19 እና መቀጮ እርከን 6፤ 3ኛ ክስ ደረጃ 6 የእስራት ቅጣት እርከን 15 እና መቀጮ እርከን 4፤ 5ኛ ክስ ደረጃ 10 የእስራት ቅጣት እርከን 23 እና መቀጮ እርከን 6፤ 6ኛ ክስ ደረጃ 7 የእስራት ቅጣት እርከን 17 እና መቀጮ እርከን 5 ይሆናል፡፡

የእስራት ቅጣትን በተመለከተ በቅጣት እርከኖች ስር በተቀመጠው ፍቅደ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣታቸው ብቻ ተወስዶ ሲደመሩ 22 ዓመት ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡ የገንዘበ ቅጣትን በተመለከተ እርከን 4 እስከ ብር 5,000 (አምስት ሺህ ብር)፤ እርከን 5 እስከ ብር 7,000 (ሰባት ሺህ ብር) እና እርከን 6 እስከ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚደርስ ነው፡፡ በእነዚህ እርከኖች ስር አማካይ ቅጣት ተወስዶ ሁሉም ሲደመሩ በጠቅላላው እስከ ብር 35,500(ሰላሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይሆናል፡፡ የእስራት እና የገንዘብ አማካይ ቅጣቱ ተጠሪ በ4ኛ ክስ ስር ጥፋተኛ ከተባሉበት ጋር ሲደመር የእስራት ቅጣቱ 24 ዓመት ከ9 ወር ፅኑ እስራት እና እስከ

ብር 39,500(ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ብር) የገንዘብ ቅጣት ይሆናል፡፡ ይህም በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አባሪ አንድ በእስራት እርከን 37 እና መቀጮ እርከን 9 ስር የሚገኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት እና አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መኖራቸውን ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት ለመገንዘብ የተቻለ በመሆኑ እና በእነዚህ የቅጣት አስተያየቶች ላይ የቀረበ መከራከሪያ ባለመኖሩ ምክንያቶቹ በዚህ ችሎትም ተወስደዋል፡፡ በዚሁ አግባብ በሚደረግ ስሌት መጨረሻ ቅጣቱ የሚሰላው በእስራት እርከን 34 እና መቀጮ እርከን 6 ስር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህ እርከን የተቀመጠው ቅጣት ደግሞ ከ15(አስራ አምስት) ዓመት እስከ 18 (አስራ ስምንት) ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና እስከ ብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የሚደርስ መቀጮ ነው፡፡ እናም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በሚደረስ ስሌት ተጠሪ በትንሹ 15 ዓመት ፅኑ እስራት ይቀጣሉ ማለት ነው፡፡

ይሁንና ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት እንዲሁም ከድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ አኳያ የዚህ ቅጣት ተመጣጣኝነት እና አስተማሪነቱም መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንግዲህ የወንጀል ቅጣት ቀዳሚ ዓላማው ወንጀል ፈፃሚዎችን በማረም በቀሪ ህይወታቸው ከመሰል ድርጊት ታቅበው መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ የቅጣት ውሳኔ የወንጀል አጥፊዎችን ለማረም ደግሞ አጥፊው ከፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ አገላለፅ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ቀላል ወይም የአጥፊውን አደገኛነት የማያሳይ ሆኖ እያለ የተጋነነ ቅጣት የሚወሰንበት ከሆነ ወይም ድርጊቱ ከባድ ሆኖ አነስተኛ ቅጣት የሚወሰን ከሆነ አጥፊውንም ሆነ ሌላውን ማህበረሰብ የማያስተምር በመሆኑ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ ዓላማን የማያሳካ ነው ማለት ነው፡፡ ሥራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያም በመርህ ደረጃ የትኛውም የወንጀል ቅጣት ውሳኔ በመመሪያው መሰረት እንዲወሰን ካዘዘ በኋላ ከመመሪያው ውጭ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበትን ሁኔታ በአንቀፅ 27 ስር ያሰፈረውም በዚሁ መነሻነት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ የተከሰሱትም ሆነ በወንጀል ጥፋተኛ የተባሉት ስድስት የተለያየ የገንዘብ መጠን የተፃፈባቸውን ቼኮች ለአራት ግለሰቦች ሰጥተዋል በሚል ነው፡፡ በ4ኛ ክስ ውስጥ ከተጠቀሰው ቼክ ውጭ ቀሪዎቹ የተሰጡበት ሁኔታ የተጠሪን የወንጀል ኃላፊነት የሚያስቀር ባይሆንም በተጠሪ እና በቼክ ተቀባዮቹ መካከል በነበረው የጋራ የንግድ ስራ ውስጥ የተሰጡ ለመሆናቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ የዚህ ድርጊት አፈፃፀም ሁኔታ ሲታይ የተጠሪን ወንጀል የመፈፀም አደገኛነት የሚያሳይ አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በንግድ ግንኙነት ውስጥ በተሰጠ ቼክ መነሻነት ተጠሪ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተለየው የእስራት ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑ ከተፈፀመው ድርጊት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ቅጣቱ የወንጀል ህጉን አላማና ግብ

የማያሳካ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ቅጣቱ ከመመሪያው በመውጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 88(2) እና 179 መሰረት መወሰን እንደሚገባው ታምኗል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት የተፈፀመበት ከባቢያዊ ሁኔታ እና የተጠሪን አደገኛነት መጠን ከግንዛቤ በማስገባት ለሁሉም የወንጀል ድርጊቶች ተጠሪ ከዚህ በፊት በዚሁ ጉዳይ የታሰሩት ካለ ታስቦበት በ5(አምስት) ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 10,000(አስር ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል በወንጀል ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለማስተማር ሁሌም ወደ ማረሚያ ቤት መላክ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ይልቁንም ለጥፋተኛው አንድ የፈተና ጊዜ ከፅኑ ማስጠንቀቂያ ጋር ሰጥቶ አመሉ ቢፈተሽ መልካም ይሆናል ተብሎ ሲታመን የእስራት ቅጣቱን አፈፃፀም ለጊዜው አግዶ ማቆየት እንደሚቻል ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 192 እና ተከታዮቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የወንጀል ቅጣት ውሳኔ ሊገደብ የማይቻልባቸው ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 194 ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በእነዚህ መመዘኛዎች መሰረት የአሁን ተጠሪ ላይ በዚህ ችሎት የተላለፈው የእስራት ቅጣት ውሳኔ እንዳይገደብ የተቀመጠ ክልከላ ባለመኖሩ የቅጣቱ አፈፃፀም በፈተና ጊዜ እንዲቆይ ማድረጉ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. ከወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) አተረጓጎም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በዚሁ ችሎት በሰ/መ/ቁር67947 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የህግ ትርጉም በፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 26 መሰረት ተሻሽሏል፡፡ በዚሁ አግባብ "በወንጀል የተከሰሰ ቼክ አውጪ ቼኩን ለዋስትና ወይም ለመያዥያነት የሰጠ ለመሆኑ እና የዋስትና ወይም የመያዥያ ውሉም በንግድ ህጉ እና በፍትሐ ብሔር ህጉ በተመለከተው መመዘኛ መሰረት የተፈፀመ ስለመሆኑ ማስረዳት ከቻለ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሊቀጣ አይገባም" ተብሏል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ/187459 ላይ ጥር 22/2010 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና ይህንኑ ፍርድ በማፅናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/156522 ላይ ሚያዝያ 29/2010 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2)) መሰረት ተሻሽሎ ተጠሪ በ1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ክሶች በወንጀል ህግ አንቀፅ 693(1) ስር ጥፋተኛ ናቸው ተብሏል፡፡

3. በውሳኔ ተራ ቁጥር 2 ስር በተገለፀው አግባብ ተጠሪ ጥፋተኛ በተባሉበት ስድስቱም ክሶች በጠቅላለው በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 10,000(አስር ሺህ ብር) የመቀጮ እንዲቀጡ ተወስኖ የእስራት ቅጣት ውሳኔው አፈፃፀም በ4(አራት) ዓመት የፈተና ጊዜ እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

4. ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 197(2) መሰረት ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ብር 5,000(አምስት ሺህ) የአራት ዓመት ጊዜው እስኪጠናቀቅ ድረስ በዋስትና ያስይዙ፡፡

5. የቅጣት ውሳኔው ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ውጭ የተወሰነ መሆኑን እንዲያውቅ የዚህ ውሰኔ ግልባጭ ለፍርድ ቤቱ ለሚመለከተው የስራ ክፍል እንዲተላለፍ በመመሪያ አንቀፅ 27(3) መሰረት ታዟል፡፡

6. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ጎ

## የልዩነት ሃሣብ

እኛ ስማችን በተራ ቁጥር 4 እና 7 ስር የተሰየምነው የችሎቱ ዳኞች ከባልደረቦቻችን /አብላጫው ድምጽ ከያዙት/ የወንጅል ቅጣትን አስመልክቶ በሰጡት የውሣኔ ሃሣብ ላይ የተለየ ሀሳብ ስላለን ለልዩነት ያበቃንን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

የቀረበው ጉዳይ በቂ ስንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት የሚፈፀም ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን አስቀድሞ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በቼክ ማታለልን አስመልክቶ የጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ተሰጥቶ የነበረውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተወሰኑ መመዘኛዎች አንዲጨመሩበት በማድረግ እንዲሻሻል መደረጉ ተገቢና የምናምንበት ውሳኔ ነው፡፡

ሆኖም በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ የተወሰነውን ቅጣት አስመልክቶ አብላጫውን ድምጽ የያዙት የዚህ ችሎት ዳኞች ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከሚደነግገው መደበኛ የቅጣት አወሳሰን መርህ በመውጣት እንዲወሰን የሚወሰነው ቅጣት አፈፃፀም በፈተና ጊዜ ተገድቦ እንዲቆይ የተደረሰበት መደምደሚያ ላይ የምንስማማበት አይደለም፡፡

ምክንያቱም፡-

1ኛ. የቅጣት አላማው እና ግቡ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግሥት፣ የሕዝቦቿን፣ የነዋሪዎቹን፣ ሰላም፣ደህንነት፣ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም ማረጋገጥ እና ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል፣ ስለ ወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ እና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆን ወይም እንዲታረሙ ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በአንድ ሰው ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ ክርክር መርምረው ጥፋተኛ ሆነው ባገኙት ሰው ላይ ቅጣት ሲወስኑ ይህን አላማና ግብ ሊያሳካ የሚችልና በተጠቀሰው የወንጀል ህግ ተቀባይነት ያገኙትን የቅጣት አወሳሰን መርሆችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይገባል፡፡

የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 3 የቅጣት አወሳሰን መመሪያው የወጣበት ዋና ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመስረት ሲሆን፣ ግቡቹም ተቀራራቢና ተገማች የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን፣ እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኝነትም የቅጣትን ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በአጥፊዎች ላይ የሚወስኑትን ቅጣት በዚህ መመሪያ መሰረት ለመወሰን የማያስችል ነገር ካላገጠማቸው በስተቀር ቅጣቱ የሚወሰነው የቅጣት አወሳሰን መመሪያውንና አጥፊው ጥፋተኛ የተባለበትን ልዩ ድንጋጌ የሚያስቀምጠውን ቅጣት መሰረት በማድረግ መሆን ይገባዋል፡፡

ሆኖም የተለየ ነገር ሲያጋጥማቸው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 27/1 ስር በተደነገገው መሰረት ከመመሪያው ውጪ ወጥተው ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ እንደሚታወቀው በህግ አተረጓጎም የተለየ ነገር ሲባል በዋናው መርህ መሰረት ሊወሰን የማይችል በጠባቡ ሊተገበር የሚገባ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በወንጀል አጥፊዎች ላይ ቅጣት ሲወስኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ሲወጡ ከወዲሁ ከሌላው የተለየ በወንጀል አፈፃፀሙም ሆነ ባህሪው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኙው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ለማመን የሚያስችል ነገር ሲገጥማቸው ሊሆን ይገባል፡፡

በዚህ መርህ መሰረት አብላጫው ድምጽ ተጠሪ ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው ከቅጣት መመሪያው ተወጥቶ ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ አመልካች ላይ የቅጣት መነሻው ከብዶ እና በማቅለያ ምክንያት ቀልሎም ቢሆን 15 ዓመት ጽኑ እስራት ይሆናል፤ ይህ ደግሞ አስተማሪነቱ መፈተሽ አለበት በሚል እና በተጠሪ ላይ የሚጣለው ቅጣት አጥፊውን ሆነ ማህበረሰቡን አያስተምርም የሚል እሳቤን በመያዝ ነው፡፡

ነገር ግን ቼክን አስመልክቶ ህግ አውጭው ቅጣቱን ከፍ አድርጐ ያስቀመጠበት የማያወላዱ ምክንያቶች ያሉት ስለመሆኑ ልብ ሊባል የሚገባው ነው ብለን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም በቼክ የሚገበያዩ ሰዎች ስለ ቼክ በቂ እውቀት ያላቸው፣ በአገር ኢኮኖሚ እና በባንኮች ተአማኒነት ላይ የሚያመጣውንና የሚያደርሰውን ጉዳት ጠንቅቀው የሚረዱ መሆናቸውን እንዲሁም በቼክ አውጪና በቼክ ግብይት ፈፃሚዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን መተማመን ለማስጠበቅ ታስቦ እንደሆነ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ ይሄን በመድፈር በቂ ሰንቅ የሌለው ቼክ በማውጣት ወንጀል መፈፀማቸው የተረጋገጠባቸው ሰዎች የሚወሰንባቸው ቅጣት የተለየ ነገር ካላጋጠመ በስተቀር በመመሪያው መሰረት ሊሆን እንደሚገባ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ በያዝነው ጉዳይ አብላጫው ድምጽ ያየዙት የስራ ባልደረቦቻችን የአመልካች ቅጣት ከመመሪያው በመውጣት ቅጣቱን ለመወሰን ያበቃቸው ምክንያት ቅጣቱ ከብዷል በሚል ምክንያት እንጂ የአመልካች የወንጀል ድርጊት በቅጣት መመሪያው አንቀጽ 24/1 ስር የወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባህርይው በመመሪያው ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ያልተገኘ ወይም መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት ዓላማ እና ግብ የማያሳካ ስለመሆኑ የተቀመጡ መስፈርቶችን ያሟላ ሌላ የማይታለፍ ምክንያት ስላጋጠመ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው በመውጣት ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሳይኖር ቅጣት በዝቷል በሚል ምክንያት ብቻ በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ ከመመሪያው በመውጣት ቅጣት መወሰን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የፍርድ ቤቶችን ተገማችነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው ብለን እናምናለን፡፡

2ኛ. ስለተወሰነው ቅጣት አፈፃፀም መገደብን የሚመለከት ነው፡፡ በአንድ የወንጀል ጥፋተኛ ላይ የተወሰነው ቅጣት አፈፃፀሙን ለተወሰነ የፈተና ጊዜ ተገድቦ ስለሚቆይበት ሁኔታ ወይም መስፈርቶችን በሚመለከት፡-

- ጥፋተኛ የተባለው ሰው አስቀድሞ የተፈረደበት መሆን አለመሆኑን ግምት ውስጥ ሳይገባ፣
- ቅጣቱ ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ታግዶ ቢቆይ አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ የጥፋት ድርጊት ከመፈፀም የሚቆጠብ ወይም የሚታገድ ስለመሆኑ ሲታመንበት እና፣
- ስለአመሉ መሻሻል አንድ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት የወሰነው ቅጣት አፈፃፀም በገደብ ሆኖ እንዲቆይ ሊወሰን እንደሚችል የወንጀል ህግ አንቀጽ 192 ይደነግጋል፡፡
- ከዚህ በተጨማሪም በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይፈፀም በመልካም ጠባይ እንደሚመራ የተጣለበትን የገደብ ግዴታ የሚቀበል በተቻለው መጠን በጥፋቱ ምክንያት ያደረሰውን ጉዳት ሁሉ እንደሚክስ ወይም ለተበዳዩ እንደሚከፍል እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ወጪ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ሲሰጥ እንደሆነ የወንጀል ህግ አንቀጽ 197 ይደነግጋል፡፡

❖ እንዲሁም የቅጣት ገደብ ጥያቄ ጥፋተኛ በተባለው ሰው ስለተጠየቀ ብቻ የሚሰጥ መብት ሳይሆን የዳኞችን ፈቃድ መሰረት ያደረገ እና የሚከለክልም ሆነ የሚፈቅድ ሲሆን ክርክር የሚደረግበትና ማስረጃም የሚቀርብበት ስለመሆኑ ህጉ በግልጽ ደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከመጀመሪያውም ቢሆን በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት ከመመሪያው ሊወሰን አይገባም የሚል የፀና እምነት ያለን በመሆኑ ቅጣቱ ከ 5 አመት በላይ እንደሚያስቀጣ አያከራክርም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ቼክ አውጥቷል የተባለው 6 የተለያዩ ቼኮችን በመሆኑ ምንም እንኳን 5ቱን ያወጡት ከግል ተበዳዮች ጋር ባላቸው የንግድ ግንኙነት ነው ቢባል ቀጥለውም ሌላ ቼክ ፈርመው መስጠታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ ተደራራቢ ወንጀል የፈፀሙ መሆናቸው እንዲሁ ተረጋግጧል፡፡

ገደብ ለመከልከል የተቀመጡት መስፈርቶችን ስንመለከት ደግሞ ከ5 ዓመት በላይ የሚቀጣ ያልሆነ እንደሆነ እና ተጠሪ ጉዳዩ በክርክር ላይእያለ እልባት ሳያገኝ ከታሰሩበት መጥተው ጉዳዩን ወደ ችሎት መቅረብ ያቆሙ በመሆኑ የቅጣት ገደብ ከመስጠቱ በፊት በገደቡ ላይ የተጣሉባቸውን ግዴታዎች መቀበል አለመቀበላቸው ሳይረጋገጥ የተወሰነባቸውን የእስራት ቅጣት ከሚፈጽሙ ይልቅ በውጪ ሆነው አመላቸው ቢፈተን ሌላ ወንጀል ከመፈፀም ይገደባሉ የተጣለውንም ገደብ ያከብራሉ ተብሎ እምነት ለመያዝ የሚያስችሉ ምክንያቶች ባልተረጋገጠበት ስለአመላቸው መሻሻል ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ በችሎት ተገኝተው እንኳን የዳኛ ተግሳጽን ሊቀበሉ የማይችሉበት ሁኔታ የተወሰነባቸው የእስራት ቅጣት አፈፃፀም በገደብ እንዲሆን መወሰኑን የወንጀል ህግን አላማና ግብ የቅጣት መመሪያው መሰረት እና አስቀድሞ ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 171503 በሆነው ላይ ከተሰጠው የህግ ትርጉም ጋር የማይጣጣም ነው ብለን ስላላመን በሀሳብ ተለይተናል፡፡

## የማስማሚያ ሀሳብ

በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፣2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥ ያነት ወይም በዋስትና የሰጠ ቼክ አውጪ በወ/ህ/አ.693(1) የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት በሰ/መ/ቁ.67947 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ በመቀየር በተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ የምስማማበት ቢሆንም የስራ ባልደረቦች ወደዚህ መደምደሚያ የደረሱት ከመነሻውም የህጉ አቀራረፅ ግልፅ ያልሆነ በዚህ አግባብም ትርጉም የሚያስፈልገው መሆኑን መነሻ ሳያደርጉ ከዚህ ይልቅ የቀደመውን ውሳኔ ለመቀየር በቂ ተደርጎ የተቀመጠው በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሄር ጉዳይ ላይ የሚሰጠውን የህግ ትርጉም ወጥነት ከማረጋገጥ አንፃር ብቻ በመሆኑ በኔ እይታና ግንዛቤ የወ/ህ/አ.693 ለብቻው ሳይሆን በወንጀል ህጋችን ተካትቶ ከተቀመጠበት ምዕራፍ አንፃር በማየትና በመመርመር ትርጉም

ሊሠጠው ይገባል የሚል እምነት ስላለኝ በዚህ አግባብ በሰ/መ/ቁ.67947 የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመቀየር የሚከተለውን ምክንያት በተጨማሪነት ሊካተት ይገባል በማለት የማስማሚያ ሀሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የወ/ህ/አ.693 በወንጀል ህጋችን በስድስተኛ መፅሀፍ በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ስር በምዕራፍ ሶስት፣ ክፍል አንድ ማታለልን ካካተቱ ወንጀሎች ጋር የተቀመጠ መሆኑ ለክፍሉ ከተሰጠው አርዕስት ስንነሳ በወ/ህ/ቁ.693 የተመለከተው የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት የወንጀል ድርጊት የማታለል ድርጊትን የሚወክል ከማታለል የወንጀል ድርጊት ጋር የሚጠቃለል የወንጀል ተግባር መሆኑን ያሳያል፡፡በወ/ህ/አ.693 የተመለከተው ድርጊት በቼክ ማውጣት የሚፈፀምን የማታለል ድርጊትን የሚወክል ከሆነ ደግሞ በወ/ህ/አ.693 አንድን በሂሳቡ ውስጥ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ቼክ ፅፎና ፈርሞ የሰጠን ሰው ጥፋተኛ ለማለት ቼክ በሚወጣበት ወይም ቼኩ ለክፍያ ባንክ በቀረበበት ጊዜ በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ቼኩን የተቀበለውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም አታልሎ የቼክ ተቀባዩን ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት መፈፀሙ በተጨማሪነት ሊረጋገጥ የሚገባ መሆኑን ያሳያል፡፡

በኔ እምነት የቼክ ተቀባዩ ቼኩን በሚቀበልበት ወቅት መታለል ወይም አለመታለልን አስመልክቶ ለማረጋገጥ ሁሉንም የማስረጃ አይነቶች መቀበል ለክርክሮች መንዛዛት፣በዚህ አግባብም ፍርድ ቤቶችን ላልተፈለገ ጫና የሚዳርግ በመሆኑ በዚህ የሕግ ትርጉም ሊጠቀም የሚገባውም ምክንያታዊ እና ጥንቁቅ ቼክ አውጪ ብቻ ሊሆን ይገባል ብዬ ሰለማምን፣ በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፣2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥያነት ወይም በዋስትና የሰጠ ቼክ አውጪ ይህንኑ መስፈርት ያሟላ የመያዢያ የዋስትና ውል በማቅረብ ማስረዳት ከቻለ ፣ቼኩ የህጉን መስፈርት ያሟላ መያዥያ መሆኑን እያወቀ አምኖ የተቀበለው ቼክ ተቀባይ ተታልሏል፣ቼክ አውጪውም ቼኩን በመፃፍ ለቼክ ተቀባዩ ሲሰጥ ጀምሮ የቼክ ተቀባዩን የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት ተጠቅሟል በዚህ አግባብም አታልሎ የቼክ ተቀባዩን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ ድርጊት ፈፅሟል ሊባል ስለማይችል በንግድ ህጉ አንቀፅ 952 እና በፍታብሄር ህግ ቁጥር 2864፣2865 እና 2866 ላይ የተመለከቱትን ጥብቅ መመዘኛዎች ያሟላ ቼክ በመያዥያነት ወይም በዋስትና መስጠቱ የተረጋገጠ ቼክ አውጪ በወ/ህ/አ.693(1) የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በማውጣት ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል አይገባም በማለት ተጨማሪ የህግ ምክንያትን በማስቀመጥ የማስማሚያ ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

አ/ኃ

# አሠሪ እና ሰራተኛ

የሠ/መ/ቁጥር 219611

ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አስራኤል ሉሌ

ተጠሪ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከት የይርጋ ጊዜ አፈጻጸም የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በቀን 01/07/2012 ዓ/ም ጽፈዉ ባቀረቡት ክስ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከቀን 09/03/2006 ዓ/ም ጀምሮ ተቀጥረዉ እየሰሩ በቀን 12/01/2012ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሕግ አግባብ ዉጭ እንዳሰናበታቸዉ በመግለጽ ዉዝፍ ደመወዛቸዉን ከፍሎ ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመልሳቸዉ እንዲወሰን አሊያም የሕግ-ወጥ ስንብት ተከትሎ የሚከፈሉ ክፍያዎች ተጠሪ እንዲከፍላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠዉ መልስ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው ከቀን 20/01/2012 ዓ/ም ጀምሮ ነው፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡት ደግሞ በቀን 01/07/2012 ዓ/ም ማለትም የአመልካች የሥራ ውል ከተቋረጠ ከአምስት ወራት በኋላ ነው፡፡ አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ የሥራ ውሉ በተቋረጠ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ አመልካች ክስ ያቀረቡት በይርጋ ከታገደ በኋላ በመሆኑ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 77265 ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 08/01/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 163/2 መሰረት ሠራተኛው የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል በማለት ደንግጓል፡፡ የአመልካች የሥራ ውል በቀን 12/01/2012 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ከመስከረም 20 ቀን 2012 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ

መሆኑን ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ካቀረቡት ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡትና በሬጅስትራር በኩል ያስመሩት ደግሞ በቀን 01/07/2012 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች የሥራ ውሉ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ስለሆነ ወደ ሥራዬ ልመለስ ብለው ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ አምስት ወር ከ9 ቀን ካለፈው በኋላ ክሱ እንደቀረበ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የስራ ውሉ በተቋረጠ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ክሱን ሳያቀርቡ የቆዩት ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ እየታየ በመቆየቱ ምክንያት ነዉ በማለት ያቀረቡትም ክርክር ቢሆን በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 138 እና 145 መሰረት የዲስፕሊን ኮሚቴ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ባለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 165(1 እና 2) መሰረት የይርጋውን ጊዜ መቆጠር የሚያቋርጥ ምክንያት ባለመሆኑ አመልካች የሥራ ዉሌ ከሕግ ዉጭ ስለተቋረጠ ወደ ሥራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ በአዋጁ አንቀጽ 163/2 መሰረት በይርጋ የታገደ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ችሎቱ በመ/ቁጥር 250193 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 17/02/2014 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 16/05/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- የስር ፍርድ ቤቶች በሥራ ክርክር ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብት ያላቸው የመንግስት አካላት የሆኑት የሥራ ክርክር ችሎትና ቦርድ ብቻ ናቸው በማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2/5 ስር የተደነገገዉን የተከተለ አይደለም፡፡የህብረት ስምምነት በአዋጁ አንቀጽ 135/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሕግ ላይ ከተደነገገዉ የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ተፈጻሚነት አንዳለዉ የተደነገገ ሆኖ እያለ በሕብረት ስምምነት መሰረት የተቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የመወሰን ሥልጣን የለዉም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ይህንን ያገናዘበ አይደለም፡፡በተጠሪና በሠራተኞች መካከል በተቋቋመዉ በ12ኛዉ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 38 ተራ ቁጥር 7.2 እና 7.61 እና አንቀጽ 37 ስር ሠራተኛዉ በተወሰደበት የሥንብት ዉሳኔ ላይ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ይህ የዳኝነት ሥልጣን በመሆኑ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዉ በአዋጁ አንቀጽ 165/1 መሰረት የሥራ ክርክር የሚወስን አካል በመሆኑ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እየታየ የቆየበት ጊዜ የይርጋዉን ጊዜ የሚያቋርጥ ምክንያት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በተጠሪ ዘንድ በተቋቋመ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የአመልካች ቅሬታ ሲታይ ቆይቶ የተወሰነ መሆኑ ባልተካደበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮችን ለማስፈፀም የተቋቋመ አካል አይደለም በማለት ክሱን በይርጋ ውድቅ ያደረገበት አግባብ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 05/09/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-

በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 165(1 እና 2) የተመለከተው የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት የሥራ ክርክርን ለሚወስን ባለስልጣን ክስ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋልና ለማስፈፀም ኃላፊነት ለተሰጠው ባለስልጣን አቤቱታ ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ በፅሁፍ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ ነው፡፡አመልካች ቅሬታ ያቀረቡት ለድርጅቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንጂ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠዉ አካል አይደለም፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 165(1 እና 2) እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 16648 በቀን 20/04/1998 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የሥራ ክርክርን ለሚወስን ሥልጣን ያላቸዉ ባለስልጣን ፍርድ ቤቶችና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ናቸዉ ሲል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የድርጅቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንደ ዳኝነት አካል በሁለት ተከራካሪ ወገኖች መካከል በሚደረገው ክርክር ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል አካል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በሕጉ የተደነገገዉ ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ክሱን ማቅረባቸዉ ተረጋግጦ የአመልካች ክስ በይርጋ ታግዷል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በመሰጠቱ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም በቀን 19/09/2014 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ በቀን 12/01/2012 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ከሕግ አግባብ ዉጭ እንዳሰናበታቸዉ በመግለጽ ተጠሪ ወደ ሥራ ገበታቸዉ እንዲመልሳቸዉ፤ይህ የማይቻል ከሆነም ሕገ-ወጥ ስንብት ተከትለዉ የሚከፈሉ ክፍያዎችን ተጠሪ እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ተጠሪ ክሱ የቀረበዉ የ3 ወር የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ በመሆኑ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተቃዉሟል፡፡ተጠሪ አመልካችን ያሰናበተዉ ከቀን 20/01/2012 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ፣አመልካች በተጠሪ የተወሰደባቸዉን የስንብት እርምጃ በመቃወም በተጠሪ ባንክ ኅብረት ስምምነት መሰረት ለተቋቋመ ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታቸዉን ያቀረቡት በቀን 27/01/2012 ሆኖ ቅሬታ ሰሚዉ አካል በጉዳዩ ላይ

ዉሳኔ ሰጥቶ ዉሳኔዉን ለአመልካች ያሳወቀዉ ደግሞ በቀን 07/04/2012ዓ/ም ለአመልካች በጻፈዉ ደብዳቤ ነዉ፡፡ በመቀጠል አመልካች በተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት ደግሞ በቀን 01/07/2012 ዓ/ም መሆኑ በግራ ቀኙ የታመነና በስር ፍርድ ቤትም የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ክሱን ዉድቅ ያደረገዉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን ለመዳኘት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ባለመሆኑ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እየታየ በነበረበት የባከነዉ ጊዜ የይርጋ ማቋረጫ ሊሆን አይችልም በሚል ምክንያት ነዉ፡፡ የስር ፍርድ ቤት መሰረት ያደረገዉ ምክንያት ይህ ቢሆንም ተጠሪ በኅብረት ስምምነት የተቋቋመ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መኖሩንና ለዚሁ አካል አመልካች ቅሬታዉን አቅርቦ ሲታይ መቆየቱን አልካደም፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 163/2 መሰረት ሠራተኛዉ ከሕግ ዉጭ የሥራ ዉሉ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ሥራ ለመመለስ የሚያቀርበዉን ክስ ዉሉ በተቋረጠ በ3 ወር ጊዜ ዉስጥ ካላቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ደንግጓል፡፡በሌላ በኩል በዚሁ ሕግ አንቀጽ 163/4 ስር የሥራ ዉል በመቋረጡ ምክንያት በሠራተኛዉም ሆነ በአሠሪዉ የሚቀርብ ማንኛዉም የክፍያ ጥያቄ የሥራ ዉሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ዉስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ የሥራ ዉል መቋረጥን መነሻ በማድረግ ወደ ሥራ ለመመለስ በሚቀርብ ክስ እና በዚሁ ምክንያት ክፍያ ለማስከፈል ዳኝነት ተጠይቆ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉ የይርጋ ጊዜያት የተለያዩ በመሆናቸዉ የይርጋ መቃወሚያ ሲቀርብም ሆነ ዉሳኔ ሲሰጥ የቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ መሰረት ማድረግ ይገባል፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ የአመልካች ቀዳሚ የዳኝነት ጥያቄ ወደ ሥራ እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸዉ የጠየቁበት ቢሆንም በአማራጭ ደግሞ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የማይወሰንበት ምክንያት ካለ በሕገ-ወጥ መንገድ የሥራ ዉላቸዉ በመቋረጡ በሕጉ መሰረት ሊከፈላቸዉ የሚገባ ልዩ ልዩ ክፍያ እንዲከፈላቸዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉን የክሳቸዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 163/2 ስር የተደነገገዉን መሰረት በማድረግ ክሱ የቀረበዉ የ3 ወር የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ በሚል ሲወስን አመልካች በአማራጭ የጠየቁትን ዳኝነት ጥያቄ መሰረት በማድረግ ከአዋጁ አንቀጽ 163/4 አንጻር ክስ የማቅረብ መብታቸዉ በይርጋ ቀሪ መሆን አለመሆኑን ሳይመረምር ክሱን ሙሉ በሙሉ ዉድቅ በማድረግ መዝገቡ እንዲዘጋ የሠጠዉ ዉሳኔ እና ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ይህንን ሳያርም ያለፈበት አግባብ የክርክር አመራርና የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በተጨማሪም በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 29 ስር የኅብረት ስምምነት ማናቸዉንም የሥራ ግንኙነቶችንና የሥራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች እንደሚሸፍን ተደንግጓል፡፡እንዲሁም በዚሁ

አዋጅ አንቀጽ 130(3 እና 4) ላይ … ስለዲሲፕሊን አፈጻጸም፣ ስለሥራ ደንብና ስለቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት በኅብረት ስምምነት ላይ መሸፈን እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ የዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሠጣጥ፣ ቅሬታ በማን፣ ለማን እና መቼ ሊቀርብ እንደሚችልና ቅሬታ ስለሚሰማበት ሥነ ሥርዓት እና ስለዉሳኔ አሰጣጥ በኅብረት ስምምነት ላይ መወሰን እንደሚቻል ነዉ፡፡በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 135/2 ስር እንደተመለከተዉ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሕግ ከተደነገገዉ ይልቅ የኅብረት ስምምነቱ ለሠራተኞች የበለጠ ጥቅም የሚያስገኝ ሆኖ ሲገኝ ስምምነቱ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሰረት የሥራ ክርክር በስምምነት፣ በግልግል ዳኝነት አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች አሊያም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና በፍርድ ቤት በሚደረግ የሙግት ሥርዓት(litigation) ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ሊደረግ እንደሚችል በአንቀጽ 136፣142፣144 እና 145 ተደንግጓል፡፡ ሕጉ ያስቀመጠዉ አስገዳጅ የክርክር መፍቻ መንገድ ሳይጣስ በሕጉ ከተጠቀሱት በተሻለ ሁኔታ የጊዜ፣ የሰዉ እና የገንዘብ ሀብት የሚቆጥብ እና በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚከሰት አለመግባባት ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን የሚፈታበትን ዘዴ ወይም የሥራ ክርክር እልባት የሚያገኝበትን ሥርዓት በኅብረት ስምምነት መዘርጋትን ሕጉ አይከለክልም፡፡ በመሆኑም አሠሪም ሆነ ሠራተኛዉ በአዋጁ የተዘረጉትን የሥራ ክርክር የሚታይባቸዉን ዘዴዎች ከመጠቀማቸዉ በፊት በቅድሚያ በኅብረት ስምምነቱ በተቋቋመዉ የዲስፕሊን ወይም የቅሬታ ሰሚ አካል ጉዳያቸዉ እንዲታይ የማድረግ መብትም ሆነ ከኅብረት ስምምነቱ የመነጭ ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

በያዝነዉም ጉዳይ በተጠሪ ባንክ በኅብረት ስምምነት የተቋቋመ የቅሬታ ሰሚ አካል መኖሩ በተጠሪ የታመነ ጉዳይ ነዉ፡፡አመልካች ተጠሪ ከሕግ-ዉጭ የሥራ ዉላቸዉን አቋርጧል የሚለዉን የግል የሥራ ክርክር የሚመለከተዉን ክሳቸዉን ወደ ፍርድ ቤት ከማቅረባቸዉ በፊት በኅብረት ስምምነት በተቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል እንዲታይላቸዉ ቅሬታቸዉን ማቅረባቸዉ ኅብረት ስምምነቱን መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡በዚህ መልኩ በኅብረት ስምምነቱ ቅሬታ የሚሰማበት ሥርዓት የተዘረጋዉ በአዋጁ ከተዘረጉት አለመግባባትና ክርክር መፍቻ መንገዶች የተሻለ ጥቅም እንደሚያስገኝ በማሰብ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክሳቸዉን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችሉት በኅብረት ስምምነቱ ለተቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል ያቀረቡት ቅሬታ እልባት ከተሰጠ በኋላ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት በተጠሪ በቀን 20/01/2012ዓ/ም የስንብት ዉሳኔ ተላልፎባቸዉ አመልካች ለቅሬታ ሰሚዉ አካል አቤቱቻዉን በቀን 27/01/2012 ያቀረቡ ሲሆን ቅሬታ ሰሚዉ አካል ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት በቅሬታዉ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ለአመልካች ያሳወቀዉ ደግሞ በቀን 07/04/2012ዓ/ም ነዉ፡፡ በመቀጠል አመልካች በተጠሪ የተፈጸመባቸዉ የስንብት እርምጃ ሕገ-ወጥ ነዉ ተብሎ ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመልሳቸዉ አሊያም የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍላቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ክስ የመሰረቱት በቀን 01/07/2012 ዓ/ም ነዉ፡፡ የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር ያለበት ከቀን 08/04/2012 ዓ/ም *(ቅሬታ ሰሚዉ አካል ዉሳኔ ከሰጠበት ቀን ቀጥሎ ካለዉ ቀን ጀምሮ - የአዋጁ አንቀጽ 164/1 ይመለከቷል)* ጀምሮ

በመሆኑ ከዚህ ቀን ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ቀን 01/07/2012ዓ/ም ድረስ ያለዉ ጊዜ ሲቆጠር ገና ሦስት ወር አልሞላዉም፡፡በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 163/2 ስር የተደነገገዉ የ3 ወር የይርጋ ጊዜ ሳይደርስ የቀረበ ክስ በመሆኑ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ የሆነ አይደለም፡፡እንዲሁም ተጠሪ ለክርክሩ መሰረት ያደረገዉ በሰ/መ/ቁጥር 16648 ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 36730 ላይ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ የተለወጠ ከመሆኑም በተጨማሪ በእነኚህ መዛግብት ላይ የተሰጠዉ ትርጉም የይርጋ ጊዜ ማቋረጫ ምክንያት የሚመለከት ሲሆን የተያዘዉ ጉዳይ ደግሞ ከዚህ የተለየ በመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ የሕግ ትርጉም ባለመሆኑ አልተቀበልንም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በኅብረት ስምምነት በተዘረጋዉ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሰረት በመጀመሪያ መፍትሔ ለማግኘት ጥረት (exhausting internal remedy) ከማድረግ አኳያ ማየት ሲገባዉ ጉዳዩን ከይርጋ ማቋረጫ ምክንያት አንጻር በማየት የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ታግዷል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሠጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነዉ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራርና የሕግ አተገባበር ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 179409 ላይ በቀን 06/05//2014ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ አልታገደም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን በመስማት እንደነገሩ ሁኔታ ማስረጃዎቻቸዉን ሰምቶና መርምሮ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡
4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 222297

ግንቦት 02 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ተስፋልዑል ቱፋ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግል ሥራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ከቀን 15/07/2006 ዓ/ም ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የቅጥር ውል ፈፅመን በድርጅቱ ውስጥ በሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የሰው ሀብት ማሟላት ኬዝ ቲም ቡድን መሪ የሥራ መደብ በወር ጠቅላላ ደመወዝ ብር 16,628.00 እየተከፈላቸዉ ሲሰሩ ቆይተዉ አመልካች ድርጅት ከቀን 21/01/2013 ዓ/ም ጀምሮ የሥራ ውላቸዉን ከሕግ-ውጪ ማቋረጡን ገልጸዉ አመልካች ከሥራ ውል ማቋረጥ ጋር በተያያዘ ሊከፈል የሚገባውን ካሳ፣የሥራ ስንብት ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ ያልተወሰደ የአምስት ቀናት ደመወዝ፣ የ137 ቀን የዓመት እረፍት በገንዘብ ተቀይሮ፣ ክፍያ ለዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ እንዲከፍላቸዉ እና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካች በፈጸሙት ጥፋት በሕጋዊ መንገድ የተሰናበቱ ናቸዉ፡፡ አመልካች በድርጅቱ ያሉ ክፍት የሥራ መደቦችን በቅጥር ማስያዝ ሲያስፈልግ የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ያላቸዉን እጩ ተወዳዳሪዎች እንዲቀጠሩ እና ክፍት የሥራ መደቦች ሲፈጠሩ የዉስጥ ማስታወቂያ እያወጡ ብቁ ሠራተኞች ተወዳድረዉ በሥራ መደቡ ላይ እንዲያድጉ የማድረግ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ቢሆንም በቀረበባቸዉ ተደጋጋሚ ቅሬታ መሰረት በተጠሪ በተቋቋመው ገለልተኛ አጣሪ ኮሚቴ በሰውና በሰነድ ማስረጃ ተመርምሮ በተገኘው ግኝት በሥራቸዉ ላይ የማታለል ተግባር በመፈፀም የተጠሪን አገልግሎት በማቃወስ ለግል ጥቅማቸው በማሰብ የተዛባና የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የተለያዩ የሥራ ቅጥሮችና ዝውውሮች መፈጸማቸዉ ተረጋግጧል፡፡ስለዚህ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው ከተሰጣቸው ኃላፊነት ውጪ እና ተጠሪ ድርጅት የሚመራበትን የቅጥር፣ የዝውውርና የእድገት

መመሪያ በሚቃረን አኳኋን የተለያዩ ቅጥርና ዝውውር በመፈፀማቸው በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ አንቀጽ 27 እና በሕብረት ስምምነት አንቀጽ 47 በተደነገገዉ እና በሰ/መ/ቁጥር 25511 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በሕጋዊ መንገድ የተፈጸመ ስንብት ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 80465 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 11/09/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የሥራ ዉል ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር እንዲሁም ከቅጥር እና ከምደባ እድገት ጋር በተያያዘ አመልካች ፈጽመዋል የተባለዉ ግድፈቶችን ተጠሪ በጥናት እንደደረሰበት እና እርምጃ እንደወሰደ ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም እነዚህ ጥፋቶች ተፈጽመዋል ቢባል እንኳን ከሠራተኛ ቅጥር እና እድገት ጋር በተያያዘ የተፈጸሙ ጥፋቶች በቅጥር ኮሚቴ፣ ቀጥሎም ለመጽደቅ ወደ ኃላፊ ሲሄድ በዝርዝር እና በግልጽ ታይቶ ሊታረም ወይም ጥፋት አጥፍተዉ ከሆነም ሊቀጡበት የሚችል ባህሪ ያለዉ ነዉ፡፡በግራ ቀኙ የቀረቡት የሰው ምስክሮችም የሰጡት ቃል እንዲሁም ከህብረት ስምምነት አንቀፅ 14 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው እድገትም ሆነ ቅጥር በኮሚቴ እንደሚሰራ እና በተቋሙ የበላይ ኃላፊ የሚፀድቅ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም አመልካች በኮሚቴው በፀሀፊነት የሚሰሩና ድምፅ አልባ መሆናቸው ተመስክሯል፡፡ ከዚህ አኳያ ቅጥሮቹ እና እድገቶቹ ከተሰጡ ከአመታት በኋላ የሥራ ዉሉን ማቋረጥ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 መሰረት በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ እርምጃ ያልወሰደ ስለሆነ በይርጋ ስለሚታገድ እና ባልጸደቀ የሥራ መዘርዝር ምክንያት የአመልካችን የሥራ ዉል ማቋረጡ ከሕግ-ዉጭ ነዉ በማለት ተጠሪ ለአመልካች ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 250671 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 27/05/2014 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉን የይርጋ መቃወሚያ በግልጽ በማንሳት እልተከራከሩም፡፡ የስር ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያዉን በራሱ አነሳሽነት በማንሳት ባልቀረበ ክርክር ላይ ተመስርቶ የሰጠዉ ዉሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/2 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ሲል የወሰነውን የውሳኔ ክፍል በማሻሻል የአመልካች ምስክሮች ከሰጡት ቃል መረዳት እንደሚቻለው የተጠሪ ምስክሮች ቃል በሚያጠናክር መልኩ ቅጥርና ምልመላን በሚመለከት ለዳይሬክቶሬቱ የሚያቀርቡት አመልካች እንደሆኑ እንዲሁም ለጉባኤው ቃለ ጉባኤ እንደሚያቀርቡ የተወዳዳሪዎችን ፕሮፋይል ለኮሚቴው የሚያቀርቡትና ቅጥሩን የሚያሟሉ ሰዎችን አጣርተው ለኮሚቴ የሚያቀርቡት አመልካች መሆናቸውን፤ በቅጥር ኮሚቴ ላይ የተመዘገቡ ሠራተኞችን የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ከወጣው ማስታወቂያ ጋር አነፃፅሮ በተገቢው ሁኔታ አረጋግጠው የሚያቀርቡት አመልካች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡በመሆኑም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 13/2 ላይ የተመለከተውን ግዴታ ካለመወጣታቸዉም በተጨማሪ በአንቀፅ 27(1/ሐ) በተደነገገው

መሰረት በሥራቸው ላይ የማታለል ተግባር መፈፀማቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል የ137 ቀናት የአመት እረፍት ብቻ ወደ ገንዘብ ተለዉጦ ሊከፈላቸዉ ይገባል ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 28/06/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የይርጋ ክርክር ቀድሜ በክስ አቤቱታዬ ላይ ለማንሳት እድል አልነበረኝም ነበር፡፡ነገር ግን ተጠሪ መልስ ሲያቀርብ ስንብቱን የፈጸመዉ ከ4 ዓመት በላይ ባስቆጠረና የእኔ የሥራ ድርሻ ባልሆነ ድርጊት መሆኑን ምክንያት በማድረግ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3ን ጠቅሼ ተከራክሬያለሁ፡፡ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ ክርክር አቅርቤ እያለሁ የስር ፍርድ ቤት ባልተነሳ ክርክር ላይ ተመስርቶ እንደወሰነ በመቁጠር የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርቦ ሳይመለከት እና ሳይመዝን የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች በተጠሪ ድርጅት ዉስጥ በሚገኘዉ የቅጥር፣የምደባ እና የዝዉዉር ኮሚቴ ዉስጥ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ድምጽ ሳይኖረኝ በጸሃፊነት የማገለግል ነኝ፡፡ይህንንም ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃ አስረድቼ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ተፈጠረ ባለዉ ችግር አመልካች አንድም አስተዋጽኦ እንደሌለኝ አስረድቼ የስር ፍርድ ቤት ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ሆኖ እያለ በይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት መሻሩ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካችን በሕግ አግባብ አሰናብቷል ሲል የወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 27/3 አንጻር ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 22/07/2014 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን በማቅረብ፡-አመልካች በስር ፍርድ ቤት ለስንብት ምክንያት የሆኑት ጥፋቶች በይርጋ ቀሪ መሆናቸውን ጠቅሰዉ በፅሁፍም ሆነ በቃል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በፅሁፍ ያልተነሳ ክርክር በቃል ክርክር ወቅት ሊነሳ አይችልም፡፡ተጠሪ ዉሉን ሊያቋርጥ የሚችል ምክንያት መከሰቱን ባወቀ በ1 ወር ጊዜ ዉስጥ በመሆኑ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው የይርጋ ጊዜው ከማለፉ በፊት ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 82፣234(1/ሐ) እና 243/3 ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተፈጸመ ስህተት ስለሌለ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ ከእኔ ሥራ ጋር ባልተገናኘ ምክንያት ከሕግ-ዉጭ ከሥራ አሰናብቶኛል በማለት ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ ለክሱ በሰጠዉ መልስ የአመልካች የሥራ ዉል የተቋረጠዉ በድርጅቱ በሚገኙ ክፍት የሥራ መደቦች ሠራተኛ በቅጥር፣በዝዉዉር እና በምደባ ሲያሟሉ አመልካች ከድርጅቱ መመሪያ ዉጭ በሆነ አኳኋን ለግል ጥቅማቸው በማሰብ በሥራቸዉ ላይ የማታለል ተግባር በመፈፀም የተጠሪን አገልግሎት በሚያቃዉስ አኳኋን የተዛባና የተሳሳተ መረጃ በመስጠት የተለያዩ የሥራ ቅጥሮችና ዝውውሮች በመፈጸም በፈጠሩት ጥፋት ምክንያት ስለሆነ ስንብቱ "ሕጋዊ ነዉ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባሰሙት የቃል ክርክር ተጠሪ ለስንብቱ ምክንያት ያደረጋቸዉ ቅጥሮች ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት የተፈጸሙ በመሆኑ አሁን ላይ የሥራ ዉሉን ለማቋረጥ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም በማለት መከራከራቸዉን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካችን ክርክር መሰረት በማድረግ ተፈጸመ የተባለዉ ጥፋት በባህሪዉ ተደብቆ ሊቆይ የማይችል ሆኖ ሳለ ጥፋቱ ከታወቀ ወይም መታወቅ ካለበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ዉስጥ አመልካች ላይ እርምጃ ሳይወስድ ቆይቶ የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የአመልካችን የሥራ ቅጥር ዉል ማቋረጡ ስንብቱን ሕገ-ወጥ ያደርገዋል በማለት እንዲሁም ስንብቱ የተፈጸመዉ በቂና ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር ነዉ በማለት የወሰነ ሲሆን ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ደግሞ በስር ፍርድ ቤት በዚህ መልኩ የተወሰነዉ አመልካች በግልጽ የይርጋ መከራከሪያ ባላነሱበት ነዉ በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡

አንድ አሠሪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 መሰረት ሠራተኛዉ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ የሚያሰናብተዉን ድርጊት መፈጸሙን አዉቆ ይሄዉ ድርጊት መኖሩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ዉስጥ የሥራ ዉሉን ለማቋረጥ ባለዉ መብት ካልሰራበት መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡ በመሰረቱ ይርጋ(limitation) ከሚያስከትለዉ ዉጤት አንጻር ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ይኸዉም አንደኛዉ መብት የሚሰጥ(የሚያስገኝ) ይርጋ (acquisitive prescription) ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ መብት የሚያሳጣ (መብት ቀሪ የሚያደርግ) ይርጋ(extinctive prescription) በሚል የሚታወቁ ናቸዉ፡፡ የኋለኛዉ አይነት ይርጋ ባለመብቱ (ባለገንዘቡ) በሕግ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ መብቱን(ጥቅሙን ወይም ገንዘቡን) ሳይጠይቅ ቆይቶ ጊዜዉ ካለፈበት በመብቱ መስራት እንዳይችል የሚያደርግ (right killer limitation) ነዉ፡፡ መብት ለማስከበር የሚቀርብ ክስ በሕጉ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ባለመቅረቡ ክስ የማቅረብ መብትን ቀሪ የሚያደርግ ይርጋም (limitation of action) በዚህ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚታይ ነዉ፡፡ የዚህ ይርጋ ሌላዉ ገጽታዉ ከላይ በተጠቀሰዉ የአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር እንደተመለከተዉ የአሠሪዉን ዉል የማቋረጥ መብት የሚያሳጣ ነዉ፡፡

በዚህ ይርጋ መሰረት አሠሪዉ በሕጉ በተመለከተዉ ጊዜ የሠራተኛዉን ዉል የማቋረጥ እርምጃ ሳይወስድ ቆይቶ ጊዜዉ ካለፈ በኋላ ዉል ያቋረጠ እንደሆነ ሠራተኛዉ የጊዜ ገደቡ ባለፈበት ድርጊት

ተጠያቂ እንዳይሆን መብት ስለሚሰጠዉ ሠራተኛዉ የክስ ምክንያት በማድረግ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ እንዲባልለት መከራከር ይችላል፡፡ ሠራተኛዉ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ድንጋጌ ላይ ተመስርቶ በክስ አቤቱታዉ ላይ የክስ ምክንያት አድርጎ ለመግለጽ የሚገደደዉ የሥራ ዉል የማቋረጥ እርምጃ በአሠሪዉ የተወሰደዉ ድርጊቱ መፈጸሙን አሠሪዉ ከአወቀ ከ30 የሥራ ቀናት በኋላ መሆኑን ክሱን ሲያቀርብ እዉቀቱ ያለዉ እንደሆነ ነዉ፡፡ይህ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉ ይርጋ ክስ የማቅረብ መብትን ቀሪ የሚያደርግ ባለመሆኑ ሠራተኛዉ የተሰናበተበትን ምክንያት፣ ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን እና ምክንያቱ የተከሰተበትን ቀን አሠሪዉ መቼ እንዳወቀ በግልጽ በማሰናበቻ ጽሁፍ ላይ ሳይገለጽለት በመሰናበቱ ምክንያት ወይም በሌላ ምክንያት ለማወቅ ያልቻለ እንደሆነና እነዚህን ፍሬ ነገሮች ያወቀዉ አሠሪዉ ተከሶ በሰጠዉ መከላከያ መልስ ላይ ከተገለጸዉ ፍሬ ነገርና ከቀረበዉ ማስረጃ መነሻ የሆነ እንደሆነ ክሱን ማሻሻል የግድ ከሆነ ክሱን በማሻሻል የአዋጁን አንቀጽ 27/3 ይዘት ባገናዘበ መልኩ በማሻሻል አሊያም ክስ በሚሰማበት ጊዜ በቃል አንስቶ መከራከር ይችላል፡፡ በሁለቱም መንገድ በግልጽ የክርክር ነጥብ ሆኖ በሠራተኛዉ ሲነሳ አሠሪዉም በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ የበኩሉን ክርክር እንዲያሰማ ከተደረገ በኋላ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ የክርክር አይነት ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234(1/ሐ) እና 244(2/ሠ እና 3) ስር በተደነገገዉ መሰረት የከሳሽን ክስ የማቅረብ መብት የሚያስቀር የይርጋ መቃወሚያ በተከሳሹ በመከላከያ መልስ ላይ ተጽፎና በመጀመሪያ ክስ የሚሰማበት ሥነ ሥርዓት ከመከናወኑ በፊት መቅረብ አለበት፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ክስ የማቅረብ መብትን ቀሪ የሚያደርግ ይርጋን ጨምሮ ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ተከሳሹ ስለሚያቀርብበት ሥርዓት ለመደንገግ የተቀረጹ በመሆናቸዉ ሠራተኛ በከሳሽነት ዘንግ ሆኖ የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3ን ጠቅሶ ለሚያቀርበዉ መከራከሪያ ተፈጻሚነት የላቸዉም፡፡

በመሆኑም ከሳሽ አስቀድሞ እንዲህ አይነት መከራከሪያ በክሱ ላይ አልገለጸም በሚል ምክንያት መከራከሪያ አድርጎ እንዳያነሳ ሊከለከል አይገባም፡፡ዋናዉ ሊረጋገጥ የሚገባዉ ነገር እንዲህ አይነት ክርክር በተቻለ ፍጥነት ሠራተኛዉ ስለጉዳዩ እወቀት እንዳገኘ የመጀመሪያዉ የክስ አሰማም ሥነ ሥርዓት ከመጠናቀቁ በፊት መቅረብ መቻሉ ነዉ፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባዉ ሠራተኛዉ የአዋጁን አንቀጽ 27/3ን በመጥቀስ ባይከራከርም አሠሪዉ የሥራ ዉሉን የማቋረጥ እርምጃ የወሰደዉ ድርጊቱ መፈጸሙን ካወቀ ከ30 የሥራ ቀናት በኋላ መሆኑን ገልጾ ከተከራከረ ይህ አይነት ክርክር በአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር የተመለከተዉን ይርጋ የሚመለከት ነዉ ወይስ የፍሬ ነገር ክርክር የሚመለከት ነዉ? ለእንዲህ አይነት ክርክር ተፈጻሚነት ያለዉ ድንጋጌስ የትኛዉ ነዉ የሚለዉን የመለየት ኃላፊት ክርክሩን የሚሰማዉ ፍርድ ቤት ኃላፊነት መሆኑን ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱ በተሰማበት እለት ባሰሙት የቃል ክርክር ተጠሪ ለስንብቱ ምክንያት ያደረጋቸዉና አመልካች ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የገለጻቸዉ ቅጥሮች ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት የተፈጸሙ ስለሆኑ አሁን ላይ የሥራ ዉሌን ለማቋረጥ

ምክንያት ሊሆኑ ስለማይችሉ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ የሚል ይዘት ያለዉን ክርክር ማቅረባቸዉን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡አመልካች በዚህ መልኩ ክርክር ሲያቀርቡ በግልጽ የአዋጁን አንቀጽ 27/3ን ጠቅሰዉ ባይከራከሩም ፍርድ ቤቱ አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት ክርክር በአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉን ይርጋ የሚመለከት ነዉ በማለት ይህንን የአመልካችን ክርክር መሰረት በማድረግ ተፈጸመ የተባለዉ ጥፋት በባህሪዉ ተደብቆ ሊቆይ የማይችል ሆኖ ሳለ ተጠሪ ጥፋቱ ከታወቀ ወይም መታወቅ ካለበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ዉስጥ አመልካች ላይ እርምጃ ሳይወስድ ቆይቶ የጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የአመልካችን የሥራ ቅጥር ዉል ማቋረጡ ስንብቱን ሕገ-ወጥ ያደርገዋል የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በእኛም እምነት አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረቡት መከራከሪያ ለስንብቱ ምክንያት የሆነዉን ድርጊትና ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ የቀረበ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 ስር የተደነገገዉን ይርጋ የሚመለከት ነዉ መባሉ ተገቢ ነዉ፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ወደእዚህ ድምዳሜ ከመድረሱ በፊት በዚህ መልኩ አመልካች ያቀረቡት ክርክር ተጠሪ ዉሉን በማቋረጥ የወሰደዉን እርምጃ ሕገ-ወጥ የማድረግ አቅም ያለዉ መሰረታዊ መከራከሪያ ከመሆኑ እና አስቀድሞ በክሱ ላይ የክሱ ምክንያት ሆኖ ያልተገለጸ መከራከሪያ ከመሆኑ አንጻር አይቶ ሌላኛዉ ወገን(ተጠሪ) የበኩልን ክርክር እንዲያሰማ እድል መስጠቱን ዉሳኔዉ አያሳይም፡፡በዚህ መልኩ በአንደኛዉ ተከራካሪ የክርክር ነጥብ ሆኖ በተነሳና በክርክሩ ዉጤት ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽእኖ ባላቸዉ ክርክሮች ላይ የሌላዉ ተከራካሪ ወገን ክርክር ሳይሰማ የሚሰጥ ዉሳኔ የእኩልነትና የፍትሀዊነት መርሆዎችን የሚጥስ ስለሚሆን መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ በተገለጸዉ አግባብ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክር አመራር ላይ የታየዉን ጉድለት ማረም ሲገባዉ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 የተመለከተዉን ይርጋ የሚመለከት መከራከሪያ ከላይ በተመለከተዉ አግባብ በግልጽ አንስተዉ ተከራክረዉ እያለ አመልካች የአዋጁን አንቀጽ 27/3ን በመጥቀስ እና በክሳቸዉ ላይ የክስ ምክንያት አድርገዉ አለመግለጻቸዉን ምክንያት በማድረግ ወይም ደግሞ ክሱ ሲሰማ ከዚህ አኳያ ላቀረቡት ክርክር ተገቢዉን ትኩረት ባለመስጠትና ባለመቀበል አመልካች በመከራከሪያነት ያላነሱትን የስር ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ማንሳቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/2 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን ነዉ በማለት ሽሮ ጉዳዩን በስረ ነገሩ አይቶ ዉሳኔ የሰጠበት መንገድ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 80465 ላይ በቀን 11/09/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 250671 ላይ በቀን 27/05/2014ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ተጠሪ ለስንብቱ ምክንያት ያደረጋቸዉና አመልካች ጥፋት ፈጽመዋል በማለት የገለጻቸዉ ቅጥሮች ከሁለትና ሦስት ዓመት በፊት የተፈጸሙ ስለሆኑ አሁን ላይ የሥራ ዉሌን ለማቋረጥ ምክንያት ሊሆኑ ስለማይችሉ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ በማለት አመልካች ባቀረቡት ክርክር ላይ ተጠሪ የበኩሉን ክርክር እንዲያሰማ በማድረግ ተጠሪ የአመልካችን የሥራ ዉል ያቋረጠዉ ለስንብቱ ምክንያት ያደረገዉ ድርጊት መፈጸሙን ከአወቀ 30 የሥራ ቀናት ሳያልፍ ነዉ ወይስ አይደለም? 30 የሥራ ቀናት ካለፉ በኂላ የተወሰደ የስንብት እርምጃ ከሆነም ይህ ሊሆን የቻለበትንና ሕጋዊ ዉጤቱ እና እንደነገሩ ሁኔታ ሌሎች መከራከሪያዎችንም በተመለከተ ከተገቢዉ ሕግ አንጻር መርምሮ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሠ/መ/ቁጥር 194880

የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ተጠሪ፡- ፈይሰል አህመድ መህዲን

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ገቢዉ ምትክ ሆኖ በሚያቀርበዉ ክስ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረዉን ይርጋ ድንጋጌ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ በአሁን ተጠሪ(በስር 3ኛ ተከሳሽ) እና በሥር 1ኛ ተከሳሽ ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ፈቲ መሐመድ አህመድ ላይ በመሰረተዉ ክስ ንብረትነቱ የድሬዳዋ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት በሆነ በሰሌዳ ቁጥር 4-00325ድሬ ለሚታወቅ ተሽከርካሪ አጠቃላይ የመድን ዋስትና ሽፋን ሰጥቷል፡፡በስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሽከረከር የነበረ በተጠሪ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-03059ድሬ የሆነ ተሽከርካሪ በድሬዳዋ ከተማ እየተሽከረከረ ላለዉ ለደንበኛዉ ተሽከርካሪ ቅድሚያ ባለመስጠት የደንበኛዉን ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት አድርሷል፡፡ጥፋቱ የተጠሪ ተሽከርካሪ መሆኑ በትራፊክ ፖሊስ ተረጋግጧል፡፡በደንበኛዉ መኪና ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለማስጠገን በጨረታ በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበዉ ጋራዥ የአደጋ መነሻ እና የዕርጅና መዋጮ ቀንሶ ብር 140,038.90(አንድ መቶ አርባ ሺህ ሰላሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሳንቲም) መክፈሉን በመግለጽ ተጠሪና የስር ተከሳሾች ይህንን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ላይ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች በደንበኛዉ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት የደረሰዉ በቀን 10/09/2007ዓ/ም ሆኖ ክሱን ያቀረበዉ በቀን 08/05/2010ዓ/ም ከ2 ዓመት ከ7 ወር በኋላ በመሆኑ የተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 መሰረት በ2 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ እንዲያሰናብታቸዉ በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ባቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 68451 ላይ በቀን 12/02/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ብይን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 መሰረት ድርጊቱ በወንጀል የሚስቀጣ ከሆነ በወንጀል ሕጉ የተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆን በተደነገገዉ መሰረት በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ አሽከርካሪ የነበሩት የስር 2ኛ ተከሳሽ ራሳቸዉ አምነዉ በሰጡት መልስ በወንጀል ጥፋተኛ መባላቸዉ ስለተረጋገጠ ይርጋዉ በወንጀል ሕጉ መሰረት የሚታይ ነዉ፡፡የወንጀል ይርጋ ደግሞ ከሁለት ዓመት ጊዜ በላይ በመሆኑ የይርጋ አቆጣጠሩን በተመለከተ በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ በሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት ክሱን ይርጋ አያግደዉም በማለት መቃወሚያዉን ዉድቅ በማድረግ ብይን ሰጥቶ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲተኩለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ከፍ ሲል በተገለጸዉ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉ ላይ እና በፍሬ ነገሩ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 14998 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 29/08/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ጉዳት አደረሰ የተባለዉ አሽከርካሪ ፈቲ መሀመድ በድሬ ዳዋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00711 ላይ በወንጀል ሕግ ቁጥር 854 መሰረት ክስ ቀርቦባቸዉ ጥፋተኛ ተብለዉ ተወስኖባቸዋል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 736/2 ስር አንድ ሰዉ ሊቀጣ የሚችለዉ በደንብ መተላለፍ ወይም በወንጀል ሕግ መሰረት ብቻ እንጂ በሁለቱም ሊሆን እንደማይችል ተደንግጓል፡፡አሽከርካሪዉ በደንብ መተላለፍ የተቀጣ ሰዉ በወንጀል ሕጉ ሊቀጣ የሚችልበት ሌላ እድል ስለማይኖር ለደንብ መተላፍ የተቀመጠዉ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚነት ስለሚኖረዉ በደንብ መተላለፍ ከተከሰሰና ከተቀጣ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ በወንጀል ሕግ ቁጥር 773 ላይ ያለዉ አንድ ዓመት ይርጋ እንጂ በወንጀል ሕግ ቁጥር 214-219 ያሉት የይርጋ ደንቦች አይሆኑም፡፡በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ የተሰጠዉ ትርጉም አሽከርካሪዉ በደንብ መተላለፍ የተቀጡ ስለሆነ በድጋሚ በወንጀል ሕጉ ሊቀጡ የሚችሉበት ሁኔታ ስለማይኖር አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ስለሆነም ጉዳቱ ከደረሰበት ከቀን 10/09/2007ዓ/ም በኋላ ክስ በቀን 08/05/2010ዓ/ም የቀረበ በመሆኑ ሁለት ዓመት ጊዜዉ ስላለፈ ፍርድ ቤቱ ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበዉን የይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉና በፍሬ ነገሩ ላይ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም ሲል የሥር ፍርድ ቤትን ብይንና በፍሬ ነገሩ ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በመቀጠል አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም በመ/ቁጥር 181443 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/09/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡አመልካች በቀን 25/12/2012ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉም በፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በተሠጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

አንድ የጥፋት ድርጊት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆኑ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች ስር የሚያርፍበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡በዚህ ጉዳይም የአሽከርካሪዉ ድርጊት በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 572ም ሆነ በሕጉ በደንብ መተላለፍ ክፍል ሊያስቀጣ ይችላል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 736/2 የተደነገገዉ በአንደኛዉ ድንጋጌ ተከሶ የተቀጣ በሌላኛዉ ሊያስቀጣዉ በሚችል ድንጋጌ ሊቀጣ አይችልም የሚል አይደለም፡፡በአሽከርካሪዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 መሰረት ክስ ሊመሰረትባቸዉ የሚችልበት አግባብ ነበረ፡፡በመሆኑም ጥፋት አድራጊዉ በደንብ መተላለፍ ተከሶ ባይቀጣ ኖሮ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572 መሰረት በቸልተኝነት የትራፊክ ደንቦችን በመተላለፍ ንብረት አደጋ ላይ በመጣል እስከ 3 ዓመት ድረስ የሚያስቀጣዉ ድርጊት እንደነበር እርግጥ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ጥፋተኛዉ በወንጀል መቀጣት አለመቀጣቱ ወይም የተቀጣበት ምክንያት ግምት ዉስጥ እንደሚገባ አይደነግግም፡፡በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም ላይ ጥፋቱ እስካልተካደ ድረስ እና ድርጊቱ በመደበኛዉ የወንጀል ድንጋጌ ዉስጥ የተካተተ እስከሆነ ድረስ አልተከሰስኩበትም ወይንም አልተቀጣሁበትም የሚል ክርክር የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች የቀረበዉን የይርጋ መቃወሚያ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 መሰረት በማየት ዉድቅ አለማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልን በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጠሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የአመልካች የይርጋ ክርክር በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143 ትርጉምና ዓላማ አንጻር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 21/03/2013ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱ በአጭሩ፡-ጥፋት አድራጊዉ ሹፌር የተቀጡት በደንብ መተላለፍ ትራፊክ ጽ/ቤት ሳይሆን በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸዉ በመደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 መሰረት በሁለት ወር ቀላል እስራት ወይም በብር 1000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ መደረጉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አንድ ሰዉ በአንድ የወንጀል ድርጊት ሁለት ጊዜ እንደማይቀጣ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 6 እና 732 ላይ ተመልክቷል፡፡ስለሆነም አሽከርካሪዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 ስለተቀጡ አመልካች እንዳለዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 መሰረት ተጠያቂ የሚሆንበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ለወንጀል ሕግ አንቀጽ ተፈታሚነት ያለዉ የይርጋ ጊዜ አንድ አመት ነዉ፡፡ስለሆነም ይርጋዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ስር ያለዉ የ2 ዓመት ጊዜ እንጂ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 የተቀመጠዉ የ5 ዓመት ይርጋ ጊዜ አይደለም ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 13/04/2013ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎችን ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች ጠቅላላ የመድን ሽፋን የሰጠዉ ንብረትነቱ የድሬዳዋ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ለሆነዉ በሰሌዳ ቁጥር 4-00325 ድሬ ለሚታወቅ ተሽከርካሪ ነዉ፡፡ይህ በአመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠዉ ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የተጠሪ በሆነና በስር 2ኛ ተከሳሽ ሲሽከረከር በነበረ በሰሌዳ ቁጥር 3-03059 ድሬ በሆነ ተሽከርካሪ በቀን 10/09/2007ዓ/ም በመገጨቱ ጉዳት ስለደረሰበት አመልካች የደንበኛዉን ተሽከርካሪ ለማስጠገን ብር 140,038.90 ወጪ ማድረጉን ገልጾ በመድን ገቢዉ ምትክ ሆኖ ይህ ገንዘብ እንዲተካለት በተጠሪና በስር 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ በቀን 08/05/2010ዓ/ም ክስ አቅርቧል፡፡የአሁን ተጠሪ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1ን ጠቅሰዉ ክሱ በይርጋ ታግዷል በሚል ያቀረቡትን መቃወሚያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዉድቅ አድርጓል፡፡ ሆኖም ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት የፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳት አድራሹን ተሽከርካሪ ሲያሽከረክሩ የነበሩት የሥር 2ኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 መሰረት ጥፋተኛ ተብለዉ ስለተቀጡ የዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜ አንድ አመት በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ነዉ በማለት የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የአመልካች ክስ ዉድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስነዋል፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሹ ነጥቦች መድን ሰጪ መድን በተገባለት ንብረት ላይ የደረሰዉን ጉዳት በማስጠገን ያወጣዉን ወጪ (ለመድን ገቢዉ የከፈለዉን) በመድን ገቢዉ ምትክ ሆኖ ለማስመለስ በጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለቤትና አሽከርካሪዉ ላይ ለሚያቀርበዉ ክስ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የትኛዉ ነዉ የይርጋ ጊዜዉስ ከመቼ ጀምሮ ሊቆጠር ይገባል የሚሉ ጭብጦች ናቸዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ የሥር የፌዴራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ሳይሆን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ነዉ ብለዉ ሲወስኑ መሰረት ያደረጉት ምክንያት ድርጊቱ ጉዳት አድራሹን ተሽከርካሪ ሲያሽከረክሩ የነበሩት የሥር 2ኛ ተከሳሽ በወንጀል የተከሰሱትና ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡት በወንጀል ሕግ ስር ባለ የደንብ መተላለፍ ድንጋጌ አንቀጽ 856 ስለሆነና የዚህ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜ አንድ አመት ነዉ በሚል ነዉ፡፡አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ደግሞ አሽከርካሪዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 መሰረት ተከሰዉ ቢቀጡም ድርጊታቸዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572/1 ጭምር ሊያስቀጣቸዉ ስለሚችል፣የዚህ ድንጋጌ የይርጋ ጊዜ ደግሞ ከሁለት ዓመት በላይ በመሆኑ እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር *"…ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ"* የሚለዉ አገላለጽ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ መሆኑን የሚጠይቅ እንጂ የድርጊቱ ፈጻሚ ተከሶ መቀጣት እንዳለበት ከግምት ዉስጥ የሚያስገባ ባለመሆኑ ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባዉ የይርጋ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር የተደነገገዉ ነዉ በሚል ነዉ፡፡ተጠሪ ደግሞ አሽከርካሪዉ አንድ ጊዜ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 856 ስለተቀጡ በድጋሚ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572/1 መሰረት እንዲጠየቁ

የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 እና 736/2 ስለማይፈቅዱ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነዉ በአግባቡ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ድርጊቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 ስር ወንጀል ሆኖ የተደነገገ በመሆኑ አሽከርካሪዉ በዚህ ድንጋጌ ሊከሰሱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ በሚል የተከራከረ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ ወንጀል ተደርጎ የተደነገገዉና አጥፊዉ በድንጋጌዉ በተመለከተዉ ቅጣት የሚቀጣዉ የተፈጸመዉ ድርጊት *"ማንም አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብን በመጣስ የሌላዉን ሰዉ ሕይወት፣አካል፣ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ያጋለጠ እንደሆነ ነዉ"* ተብሎ የተደነገገዉን ድርጊቱን ወንጀል የሚያደርገዉን የድንጋጌዉን አነጋገር አሟልቶ ሲገኝ ነዉ፡፡

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 አነጋገር መሰረት አንድ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በፈጸመዉ ድርጊት ሌላዉ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ የሌላዉን ሰዉ ሕይወት፣አካል፣ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ሲያጋልጥ (ሲጎዳ) የመጀመሪያዉ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ የትራፊክ ደንብን በመጣስ ሌላዉን ሰዉ ለአደጋ በማጋለጡ የሚጠየቅበት ድንጋጌ እንጂ በተያዘዉ ጉዳይ የተከሰተዉን በአንደኛዉ አሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ በቸልተኛነት በመጣሱ ምክንያት በሁለት ተሽከርካሪዎች መካከል ግጭት በመፈጠሩ በሁለተኛዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ጉዳት አድራሹን አሽከርካሪ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡በመሆኑም በአመልካች ካሳ ለመጠየቅ መሰረት የተደረገዉ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 የሚገዛ ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር ታይቶ የይርጋ ጊዜዉ አለመወሰኑ ስህተት አይደለም፡፡

በወንጀል ሕጋችን በአንቀጽ 677(1/ለ እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት ማንም ሰዉ በመንግስት ወይም በሕዝብ ንብረት ላይ በቸልተኛነት በድንጋጌዎቹ በተገለጸዉ አነጋገር ጉዳት በማድረሱ ሊጠየቅ ከሚችል በስተቀር በንብረት መብቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ስድስተኛ መጽሐፍ ርእስ አንድ ስር በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት በመንግስት ወይም በሕዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ በቸልተኛነት ጉዳት ማድረስ እንደ መደበኛ ወንጀል ተቆጥሮ የሚያስጠይቅ አይደለም፡፡ እንዲሁም ምንም እንኳን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2 መሰረት በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በሰዉ አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተዉ በተለይም አንድ አሽከርካሪ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በሚሽከረከረዉ ተሽከርካሪ ራሱ ሌላ ተሽከርካሪ ወይም ንብረት በመግጨት በሌላ ተሽከርካሪ ወይም በሌላ ንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በወንጀል ሕጉ አልተደነገገም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 662 ስር በተደነገገዉ መርህ ላይ እንደተመለከተዉ በሌላ ሰዉ ንብረትና የኢኮኖሚ መብት ወይም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ መብቶች ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ከፍተኛነት ደረጃ ታይቶ በሕጉ ስድስተኛ መጽሐፍ ስር እንደወንጀል

ድርጊት ተቆጥሮ በግልጽ አስቀጪነታቸዉ ካልተደነገገ በስተቀር እንደአነስተኛ ድርጊት ተቆጥሮ አጥፊዎች በደንብ መተላለፍ እንዲቀጡ ማድረግ የሕግ አዉጭዉ ፍላጎት በመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ እንደታየዉ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ ጉዳት ያደረሰዉ አሽከርካሪ(የስር 2ኛ ተከሳሽ) የተከሰሱትና በፍርድ ቤት በተላለፈበት ዉሳኔ የተቀጡት በወንጀል ሕጉ ስለደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በስምንተኛ መጽሐፍ ስር በሚገኘዉ አንቀጽ 856 ላይ *የትራፊክ ደንብ በመጣስ ተሽከርካሪን በመጥፎ ሁኔታ በማሽከርከር ወይም በግዴለሽነት ወይም በቸልተኛነት በመጠቀም በሌላ ሰዉ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ የሚፈጸም ድርጊት …*በሚል በተደነገገዉና በዚሁ ድንጋጌ ላይ በተመለከተዉ ቅጣት መሰረት እንደሚቀጣ በተደነገገዉ መሰረት ነዉ፡፡ እንዲሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 773 ስር ማንኛዉም አይነት የደንብ መተላለፍ ድርጊት ቢሆን ክስ ሳይቀርብበት አንድ ዓመት ካለፈ፤የተፈረደዉም ቅጣት ተፈጻሚ ሳይሆን ሁለት ዓመት ካለፈ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 ስር *"…ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ…"* የሚለዉ አገላለጽ የተፈጸመዉ ድርጊት በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ የድርጊቱ ፈጻሚ በወንጀል ቢከሰስም ፤ባይከሰስም፤ቢቀጣም፤ ባይቀጣም የይርጋ ጊዜዉ የሚወሰነዉ ድርጊቱን የወንጀል ድርጊት ለሚያደርገዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ መሰረት ይሆናል ከሚል አላማ የተቀመጠ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ በቀን 22/06/2003 ዓ/ም (በቅጽ 11 ላይ እንደታተመዉ) የተመለከተዉ አስገዳጅ ትርጉም ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ድርጊቱን የፈጸመዉ አሽከርካሪ በወንጀል አልተከሰስኩም፤ አልተቀጣሁምም የሚል ክርክር አቅርበዉ ድርጊቱ በወንጀል ሕጉ እንደ ወንጀል ድርጊት የተደነገገ እስከሆነ ድረስ አሽከርካሪዉ በወንጀል ባይከሰሱም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/2 የተደነገገዉ የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል ተብሎ ትርጉም የተሰጠበት ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ጉዳቱን አደረሱ የተባሉት አሽከርከሪ(የስር 2ኛ ተከሳሽ) በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 856 መሰረት በዐቃቤ ሕግ ተከሰዉ በፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ጥፋተኛ ተብለዉ የተቀጡ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኖ የሚሰጥ አስገዳጅ ትርጉም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/4 (በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደተሻሻለዉ)መሰረት በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ዘንድ አስገዳጅነት ኖሯቸዉ ተፈጻሚ መሆን ያለባቸዉ ዉሳኔ ከሚፈልገዉና አከራካሪ በሆነዉ ተመሳሳይ ጉዳይ *(ratio decidendi - the point in a case that determines the judgement)* ላይ የተሰጠ የሕግ ትርጉም ሲሆን ነዉ፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 58920 የሕግ ትርጉም የተሰጠበት አከራካሪ ፍሬ ነገር እና በተያዘዉ ጉዳይ ዉሳኔ የሚፈልገዉ አከራካሪ ጉዳይ ተመሳሳይ (*ratio decidendi* ) ባለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 58920 ላይ የተሰጠዉ ትርጉም ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ አይደለም፡፡በመሆኑም ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት እና የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

እንዲሁም አመልካች አሽከርካሪዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 ሊከሰሱ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተዉ አሽከርካሪዉ የፈጸሙት ድርጊት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 572 የሚሸፈን ባለመሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 መሰረት ተከሰዉ ተቀጥተዋል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 60(ለ) ስር በተደነገገዉ መሰረት በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የሕግ ድንጋጌዎችን በመጣስ …ወንጀሎች ተፈጽመዉ ሲገኙ በሁለት የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ተደራራቢ ወንጀሎችን በመፈጸም ሊያስከስስ ይችላል፡፡ሆኖም በተያዘዉ ጉዳይ አሽከርካሪዉ የፈጸሙት ድርጊት በወንጀል ሕጉ በመደበኛ የወንጀል ድንጋጌዎች የሚያስቀጣ አለመሆኑ የተረጋገጠና ከላይ እንደተመለከተዉ በወንጀል ሕጉ በደንብ መተላለፍ ድንጋጌ በአንቀጽ 856 መሰረት ተከሰዉ የተቀጡ ስለሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 2/5 ስር በተደነገገዉ የሕጋዊነት መርህ መሰረት እና በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 736/2 መሰረት በወንጀል ሕጉ በመደበኛ የወንጀል ድንጋጌዎች የአሽከርካሪዉን ድርጊት የወንጀል ጥፋት የሚያደርግ ድንጋጌ የለም እንጂ ቢኖር እንኳን መጀመሪያ በተደራራቢነት እስካልተከሰሱ ድረስ በአንደኛዉ (በደንብ መተላለፍ)ከተቀጣ በኋላ በዚያዉ ድርጊት እንደገና የሚከሰስበትና የሚቀጣበት የወንጀል ሕግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበዉን ክርክር ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት እና የሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አለመቀበላቸዉ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ብለናል፡፡

በሌላ በኩል የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር ያለበት ከመቼ ጀምሮ ነዉ የሚለዉን ነጥብ መርምረናል፡፡ አመልካች ክሱን ያቀረበው በኢንሹራንስ ገቢው መብት በመዳረግ ወይም በምትክነት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ መሠረት ያደረገው የመድን ገቢው ጋር ያደረገው የዕቃዎች/ንብረት ኢንሹራንስ ሲሆን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 683 መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪው በከፈለው ካሣ መጠን ጉዳት እንዲደርስ ባደረጉ ሦስተኛ ወገኖች ላይ ክስ ለማቅረብ ኢንሹራንስ ለገባው ሰው በተከፈለው ገንዝብ መጠን፣ ባሉት መብቶችና ክሶች ኢንሹራንስ ሰጪው ምትክ ሆኖ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይሕም የመዳረግ መብቱ ከውል ሳይሆን ከሕግ የመነጨ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ የመዳረግ መብትን ተመስርቶ የሚቀርብ ክስ ይርጋ አቆጣጠርን ስንመለከት በአንድ በኩል የመዳረግ መብቱ ኢንሹራንስ ገቢው መብት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ መሆኑ እና በሌላ በኩል መዳረግ በሕግ የተፈቀደበት ሕግ አውጪው ሊያሳካው የፈለገው ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ መድን ገቢውና ተጠሪ ያላቸው ግንኙነት የተመሠረተው ከውል ውጭ በመሆኑ አመልካች በመድን ገቢው እግር ተተክቶ የሚያቀርበው ክስም ከውል ውጭ ማዕቀፍ የሚታይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 መሠረት ከውል ውጭ ክስ የሚቀርበው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም የይርጋ ጊዜውን የቆጠሩት ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡

አመልካች በሕግ የመዳረግ መብት ያገኘው ለመድን ገቢው ካሣውን ሲከፍል ነው፡፡ሕግ አውጪው የመዳረግ መብት ለኢንሹራንስ ሰጪው የደነገገበት በዋነኛነት ሁለት ዓላማዎችን ለማሳካት እንደሆነ

መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው ማሕበራዊ ምክንያት ነው።ይኸዉም መድን ገቢው ካሣውን ከኢንሹራንስ ሰጪው ከተቀበለ ጥፋት የፈጸመው ሠው ላይ ክስ ለማቅረብ ፍላጎት ስለማይኖረውና ክስ ቢያቀርብ እንኳን ለደረሰው ጉዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2090/1 እና 2091 መሠረት ከካሣ ተመዛዛኝነት መርሕ አኳያ ድጋሚ የሚካስበት ዕድል አይኖርም። ይሕም ጥፋቱን ያደረሰው ሰው ለጥፋቱ ተገቢው ተጠያቂነት ሳይከተልበት እንዲቀር ያደርጋል። ስለሆነም ኢንሹራንስ ሰጪው የመዳረግ መብት እንዲኖረው ማድረግ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ጥፋት ፈጻሚው ሰው ለጥፋቱ ኃላፊነት እንዲወሰድና በሂደትም ጥፋት መፈጸምን በመቀነስ ወይም በመተው በሕብረተሰቡ ዘንድ አዎንታዊ የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል ዓላማ ያደረገ ነው። ሁለተኛው ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ነው። የመዳረግ መብት መኖሩ ኢንሹራንስ ሰጪው ለመድን ገቢው የከፈለውን ገንዘብ እንዲተካለት ጉዳት አድራሹ ወይም የእሱ መድህን እንዲተካ በማድረግ የኢንሹራንስ ሥራ ትርፍ ማግኘት ከመሆኑ አኳያ ትርፋማ ድርጅት እንዲሆን ማድረግ ነዉ። ይሕም የአረቦን ክፍያ መጠን ላይ ቅናሽ እንዲደረግና ሕብረተሰቡ የኢንሹራንስ ኢንዱስትሪውን በተሻለ እንዲጠቀም ሊያበረታታ የሚችል ነው። ኢንሹራንስ ሰጪ ድርጅቶች ጤናማ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚኖራቸው ከሆነ በኢኮኖሚው ላይም አዎንታዊ ሚና የሚጫወት ይሆናል። ስለሆነም ሕጉ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በሕጉ ለማሳካት የተፈለገውን ዓላማ በማገናዘብ አመልካች በሕግ የተሰጠውን የመዳረግ መብቱን እንዲሰራበት በሚያስችል መልኩ ሊሆን ይገባል። ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች በሕግ የመዳረግ መብት ማግኘት የሚችለዉ ለመድን ገቢው ካሣውን ሲከፍል እንደመሆኑ ክስ ሊያቀርብ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን የመዳረግ መብቱን ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ይህም በካሣው አከፋፈል ሂደት በሕጉ የተመለከተው የሁለት ዓመት ጊዜ ሊያልፍ የሚችልበት ዕድል እንዳለ ያስገነዝባል።በመሆኑም የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 የተመለከተው የይርጋ ጊዜና አቆጣጠር በፍትሐብሔር ሕጋችን ስለ ይርጋ በጠቅላለዉ በሚደነግገዉ ክፍል በአንቀጽ 1846 "የይርጋው መነሻ ጊዜ" በሚል ርእስ ሥር "የይርጋው ቀን መቆጠር የሚጀምረው ግዴታዉን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነዉ ወይም ዉሉ የሚሰጠዉ መብት ከተሰራበት ቀን ጀምሮ ነዉ" በማለት ከተደነገገው ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር ይገባል።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143 እና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌዎች ስር የተደነገገዉን ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ መሠረት በማድረግ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለዉን ግንኙነትና የክሱን ምክንያት መሰረት አድርገን እንደመረመርነዉ አመልካች ለደንበኛዉ በሰጠዉ ጠቅላላ የመድን ሽፋን ዉል መሰረት ለደንበኛዉ የካሳ ክፍያ መክፈል ይጠበቅበታል። በዚህ መሰረት አመልካች ለደንበኛዉ ካሳ የከፈለዉ ወይም ጉዳት የደረሰበትን የደንበኛዉን ተሽከርካሪ በማስጠገን ለባለጋራዡ ክፍያ የፈጸመዉ መቼ እንደሆነ በስር ፍርድ ቤቶች አልተረጋገጠም። አመልካች በደንበኛዉ ምትክ በመሆን በተጠሪና በስር ተከሳሾች ላይ ክስ መመስረት የሚችለዉ የመድን ዉል ፖለሲዉንም መሰረት በማድረግ ለደንበኛዉ ካሳ ወይም የተሽከርካሪ ማስጠገኛ ክፍያ ሲፈጽም ነዉ። ይህንን ሳያደርግ ይተካልኝ በማለት በመድን ገቢዉ

ምትክ ሆኖ ክስ ለመመስረት የሚያስችል የበሰለ መብት አይኖረዉም፡፡ በእንዲህ አይነት ጉዳይ በመድን ሰጪዉ ላይ ለክሱ ምክንያት የሆነ ጉዳት ደረሰበት ማለት የሚቻለዉ (the occurrence giving rise to the claim) እና በመብቱ መሥራት የሚችለዉ ለደንበኛዉ የካሳ ክፍያ ከፈጸመበት ቀን ጀምሮ ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪን በመግጨት ጉዳት እንዲደርስበት ያደረጉት አሽከርካሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 856 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተከሰዉ የተቀጡ ስለሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 773 ስር የተደነገገዉ የ1 ዓመት የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ስር ከተደነገገዉ ከ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ያነሰ በመሆኑ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2143/1 ስር የተደነገገዉ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ነዉ፡፡ የይርጋ ጊዜዉም መቆጠር የሚጀምረዉ አመልካች ለደንበኛዉ ካሳ ወይም የተሽከርካሪ ማስጠገኛ ክፍያ ከፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለዉ ቀን ጀምሮ እንጂ በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ላይ አደጋዉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ለይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በተሽከርካሪዉ ላይ ጉዳት የደረሰበትን ቀን መነሻ በማድረግ መወሰናቸዉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካች ለደንበኛዉ ካሳ ወይም የተሽከርካሪ ማስጠገኛ ክፍያ የፈጸመበት ቀን የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 245/1 መሰረት ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉ ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68451 ላይ በቀን 12/02/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና በቀን 23/02/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14998 ላይ በቀን 29/08/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 181443 ላይ በቀን 26/09/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ አመልካች ለደንበኛዉ ካሳ ወይም የተሽከርካሪ ማስጠገኛ ክፍያ የፈጸመበትን ቀን የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 245/1 መሰረት አጣርቶ የይርጋ ጊዜ ለመቁጠር መነሻ የሚሆነዉን ቀን ለይቶ በተጠሪ በቀረበዉ የይርጋ መቃወሚያ ላይ ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

**<u>ት እ ዛ ዝ</u>**

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 204256

ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ተጠሪ፡- ሳምራዊት ጫኔ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከዉል ዉጭ የሆነ ኃላፊነት መነሻ ያደረገ ካሣ አወሳሰን የሚመለከት ነዉ፡፡የአሁን ተጠሪ በስር ተከሳሽ አቶ በላይ ባህሩ ላይ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ የአሁን አመልካች በተከሳሽ ጠያቂነት ጣልቃ ገብቶ የተከራከረ ሲሆን የክሱም አጭር ይዘት ንብረትነቱ የስር ተከሳሽ የሆነ ተሽከርካሪ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲጓዝ የነበረዉን የሰሌዳ ቁጥር 3-88863 የሆነዉን የተጠሪን አይሱዙ ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት ስላደረሰ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ለማስጠገን የወጣዉን ብር 495,000.00 ካሳ እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ተከሳሽ ጉዳቱ የደረሰዉ በእኔ ተሽከርካሪ ጥፋት ባለመሆኑ ለደረሰዉ ጉዳት ኃላፊነት እንደሌለባቸዉና የተጠየቀዉም ካሳ የተጋነነ እንደሆነ በመግለጽ ከመከራከራቸዉም በተጨማሪ የአሁን አመልካች ለተሽከርካሪያቸዉ የመድን ሽፋን እንደሰጠ በመግለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር እንዲወሰንላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡የአሁን አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ባቀረበዉ ክርክር ለደረሰዉ ጉዳት ደንበኛዉ ኃላፊነት እንደሌለባቸዉ፣ ኃላፊነት አለባቸዉ የሚባል ከሆነም በሁለት ተሽከርካሪዎች ግጭት ምክንያት የደረሰ ጉዳት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2084 መሰረት ተጠሪ የራሳቸዉን ይችላሉ እንጂ ደንበኛዉ ኃላፊነት እንደሌለባቸዉ፤ደንበኛቸዉ ኃላፊ እንደሆኑ የሚወሰን ከሆነ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ቅሪት ለጣልቃ ገብ ሊመለስ ይገባል፡፡የማይመለስበት ምክንያት ካለ የቅሪቱ ግምት ከካሳዉ ላይ ተቀናሽ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 22378 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ በቀን 18/07/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በተጠሪ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት የስር ተከሳሽ (የአመልካች

ደንበኛ) ኃላፊነት አለባቸዉ በማለት ተጠሪ ለተሽከርካሪያቸዉ ማስጠገኛ ያወጡትን ወጪ ብር 495,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡እንዲሁም ከዚህ ገንዘብ ላይ በመድን ዉሉ መሰረት አመልካች ብር 100,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 0108368 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 09/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ቅሪት አካሉ እንዲመለስለት ወይም ከጉዳት ገንዘቡ ላይ እንዲቀነስለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234(1/ረ እና ሠ) እና 215/2 መሰረት ዳኝነት በመክፈል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመመስረትና ዳኝነት በመክፈል ያቀረበዉ ክስ ባለመኖሩ የጠየቅሁት ዳኝነት በዝምታ ታልፎብኛል በማለት ያቀረበዉ ይግባኝ ተቀባይነት የለዉም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በቀን 08/07/2013ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090 እና 2091 እንደተደነገገዉ የሚከፈለዉ የጉዳት ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡ ከተጠየቀዉ የጉዳት ካሳ ላይ የቅሪቱ ተቀናሽ የማይደረግ ከሆነ የሚከፈለዉ ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት በላይ ይሆናል፡፡አመልካች ቅሪቱ ሊመለስ ወይም ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ ሊቀነስ ይገባል ብሎ ሲከራከር አዲስ ዳኝነት እየጠየቀ ሳይሆን ካሳዉ ተመጣጣኝ መሆን አለበት በማለት መከራከር በመሆኑ ዳኝነት ከፍሎ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እንዲያቀርብ ማቅረብ የሚገባዉ አይደለም፡፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት የቅሪት አካሉ ግምት ብር 95,000-100,000.00 ድረስ እንደሆነ በባለሙያ አስገምቶ ካረጋገጠ በኋላ ይህንን ሳይቀንስ ካሳ መወሰኑ ተጠሪ ከሚገባቸዉ በላይ ካሳ እንዲከፈላቸዉና ከደረሰዉ ጉዳት እንዲያተርፉ የሚያደርግ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም ለተጠሪ ከተወሰነላቸዉ ካሳ ላይ ብር 95,000.00 ተቀናሽ እንዲደረግ ይወሰንልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቅሪት አካሉ እንዲመለስ ወይም ግምቱ ከካሳዉ ላይ እንዲቀነስ ያቀረበዉን ክርክር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አላቀረበም በማለት ዉድቅ ማድረጉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ ተጠሪ ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ ቀርበዉ እንዲከራከሩ በቀን 01/11/2013ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በወጣ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎላቸዉ ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፎ በሌሉበት ተመርምሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ በስር ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኙ የቀረበዉን ክርክር፣ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች እና የሰበር አቤቱታ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም በአመልካች ክርክር መሰረት ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ቅሪት አካላት የሚመለሱት ወይም ተጠሪ ከጠየቁት ካሳ ላይ ግምቱ ተቀናሽ የሚሆነዉ አመልካች ዳኝነት ከፍሎ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቦ ሲከራከር ነዉ በሚል ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም ለክርክሩ መሰረት የሆነዉ ምክንያት የአመልካች ደንበኛ የሆኑት የስር ተከሳሽ ንብረት የሆነ ተሽከርካሪ የተጠሪን ተሽከርካሪ ገጭቶ ጉዳት አድርሷል የሚል በመሆኑ በተጠሪና በአመልካች ደንበኛ(በስር ተከሳሽ) መካከል የነበረዉ ግንኙነት ከዉል ዉጭ የሆነ ነዉ፡፡አመልካችም በክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 43 መሰረት ጣልቃ እንዲገባ የተደረገዉ በስር ተከሳሽ ተሽከርካሪ ለሚደርስ ጉዳት የመድን ሽፋን በመስጠተ ተጠሪ እንዲከፈላቸዉ ከጠየቁት ካሳ ላይ አመልካች በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት መክፈል የሚገባዉ ድርሻ አለ በሚል ምክንያት ነዉ፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት ክስ የስር ተከሳሽ ተሽከርካሪ ተሽከርካሪያቸዉን ገጭቶ ያደረሰዉን ጉዳት ለማስጠገን ባወጡት ወጪ መነሻ ብር 495,000.00 ጉዳት እንደደረሰባቸዉ በመግለጽ ብር 495,000.0 ካሳ እንዲከፈላቸዉ ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤትም የስር ተከሳሽንና የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪያቸዉን ለማስጠገን ላወጡት ወጪ የስር ተከሳሽ ብር 495,000.00 ካሳ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡በዚህ አጠቃላይ የካሳ መጠን ላይ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ የስር ተከሳሽ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ከተወሰነዉ ከተጠቀሰዉ የካሳ ገንዘብ ላይ አመልካች በኢንሹራንስ ዉሉ መሰረት ብር 100,000.00 እንዲከፍሉ በመወሰኑም ከመድን ሽፋኑ በላይ ባለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም፡፡ግራ ቀኙን ያከራከረዉ አመልካች ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ ቅሪት አካላት ተጠሪ ሊመልሱ ወይም ከሚከፈላቸዉ ካሳ ላይ ግምቱ ሊቀነስ ይገባል በማለት ያቀረበዉን ክርክር በተመለከተ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚመለከት ነዉ፡፡ከዚህ አንጻር የቀረበዉን ክርክር በተመለከተ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዝምታ ያለፈ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ አመልካች ዳኝነት በመክፈል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ባለማቅረቡ ከቅሪት አካል አንጻር አመልካች ያቀረበዉን ክርክር የስር ፍርድ ቤት በዝምታ ማለፉ ተገቢ ነዉ ሲል ይግባኙን ዉድቅ አድርጓል፡፡

እንደሚታወቀዉ የጉዳት ካሳ የሚከፈልበት ዓላማ ጉዳት የደረሰበትን ተበዳይ (ነገር) ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ስፍራ ለመመለስ እንጂ ተጎጂዉ ከጉዳቱ እንዲያተርፍ ለማድረግ አይደለም፡፡ ወደዚህ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ተቀባይነት ያለዉ የካሳ አከፋፈል መሠረታዊ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090/1 እና 2091 ላይ ተደንግጓል፡፡ይኸዉም በአንድ ጉዳት ምክንያት የሚከፈለዉ ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን መሆን እንዳለበት ወይም ደግሞ ለአንድ ጉዳት ኃላፊ የሆነዉ ሰዉ የሚከፍለዉ የጉዳት ካሳ ኃላፊነቱ ያመጣዉ ጉዳት በተበዳዩ ላይ ካደረሰዉ ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት የሚያስገድድ ነዉ፡፡ይህንን መርህ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ የጉዳት ካሳ ጠያቂዉ ከጉዳቱ አትራፊ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡ በዚህ መሠረት ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ አካላት በሌላ አካላት ተተክቶ የሚጠገን ከሆነ ጉዳት የደረሰባቸዉ ቅሪቶች ዋጋ ሊያወጡ የሚችሉ ስለሚሆኑ ሊገመቱና ግምታቸዉ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ ሊቀነስ ወይም ቅሪት አካላት በአይነት ለካሳ ከፋዩ ሊመለሱ ይገባል፡፡ ይሕ የማይሆን ከሆነና በንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰዉ ቅሪቱን የማይመልስ ወይም ግምቱ ከሚከፈለዉ ካሳ ላይ የማይቀነስ ከሆነ ለተጎጂዉ የሚከፈለዉ ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ

የሚመዛዘን መሆን አለበት የሚለዉ መርህ እንዲጣስና ተጎጂዉ መካስ ከሚገባዉ በላይ ካሳ በማግኘት ከጉዳቱ እንዲያተርፍ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 242 መሰረት የታመነ ፍሬ ነገር ነዉ በሚል ዉሳኔ ካልተሰጠ በስተቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ተካክደዉ የተከራከሩባቸዉ የፍሬ ነገር ወይም የሕግ ጭብጥ ሊለይ ይገባል፡፡እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 182/3 ስር እንደተደነገገዉ ከክርክሩ ላይ ከቀረቡት ብዙ ጭብጦች አንዱ ጭብጥ ብቻ ቢወሰን ሌሎችም ጭብጦች ላይ ተጠቃሎ ዉሳኔ እንደተሰጠ የሚያስቆጥር ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር አከራካሪ ሆነዉ የተያዙ ጭብጦችን ሁሉ በተናጠል በመመርመር በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባዉ በማስረጃ እንዲረጋገጥ ተደርጎ እንዲሁም የሕግ ጭብጥ ደግሞ በተገቢዉ ሕግ ላይ ተመስርቶ ተገቢዉ ምክንያት ተስጥቶባቸዉ ሊወሰኑ ይገባል፡፡ከዚህ አንጻር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች በግልጽ ክርክር በቀረበዉ ቅሪት አካሉን በሚመለከተዉ ጉዳይ ላይ ከተጠሪ በኩል የቀረበዉን ክርክር መሰረት በማድረግ ተገቢዉን ጭብጥ በመያዝ አጣርቶ ግልጽ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በዝምታ ማለፉ የክርክር አመራርና የፍርድ አሰጣጥ ጉድለት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡

እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የፈጸመዉን ስህተት ማረም ሲገባዉ እና የአመልካችን ክርክር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2090/1 እና 2091 አንጻር በማየት ተገቢዉን መወሰን ይገባዉ ነበር፡፡ሆኖም አመልካች በመከላከያ መልሱ ያቀረበዉ ክርክር ለተጠሪ የሚከፈለዉ ካሳ ከደረሰዉ ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ የሚመዛዘን መሆን አለበት በሚል የሕግ መሰረት ባለዉ መርህ ማዕቀፍ ዉስጥ ሆኖ በመከላከያ ክርክር መልክ የሚታይ ሆኖ እያለ፤ በአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ቀርቦ ተገቢዉ ዳኝነት ተከፍሎበት የተጠሪ ክርክርም ከዚህ አንጻር ተሰምቶ ዉሳኔ ማግኘት እንደሚገባዉ አዲስ እና ራሱን እንደቻለ ክርክርና የዳኝነት ጥያቄ አድርጎ በመቁጠር ዉድቅ በማድረግ የሠጠዉ ዉሳኔ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሊቀርብ የሚችልበትን አግባብ ያልተከተለና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 234(1/ረ) ስለተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተደነገገዉን ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22378 ላይ በቀን 18/07/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0108368 ላይ በቀን 09/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽለዋል፡፡

2. ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉ የካሳ ልክ የቅሪት አካሉን ግምት ጨምሮ ከብር 495,000.00 ሊበልጥ አይገባም ብለናል፡፡ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ከአጠቃላይ የካሳ መጠን ላይ ሊቀነስ የሚገባ የቅሪት አካላት ግምት መጠን ወይም ቅሪት አካላት በአይነት የሚመለሱ ከሆነም የሚመለሱ የቅሪት አካላት አይነት እና ብዛት ምንነት በተመለከተ እና ተያያዥ በሆኑ ነጥቦች ላይ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት ጉዳዩን መልስንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ

የሰ.መ.ቁ 200520

የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ - ዐ.ህግ አብይ መርዕድ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. እስክንድር ነጋ

2. ስንታየሁ ቸኮል

3. ቀለብ ስዩም

4. አስካለ ደምሴ

(ከ1-4 ጠበቃ ቤተማርያም አለማየሁ - ቀረቡ)

5. ጌትነት በቀለ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታሕሳስ 22 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 199376 ታሕሳስ 13 ቀን 2013 ዓ.ም የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ መሠረት ማስረጃ መቀበል ወይም አለመቀበል ላይ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የማይባልበት በመሆኑ እና ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የማስረጃ አሰማም ሂደት ላይ የተሰጠውን ብይን በመቃወም የቀረበ ቅሬታ በመሆኑ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 6/1/ለ መሠረት ጥበቃ የተደረገላቸው መሆኑን በመግለጽ አስራ ስድስቱ ምስክሮች በአዋጁ አንቀጽ 4/1/ቀ መሠረት ምስክርነታቸው በዝግ ችሎት እንዲሰማ፤ አምስቱ ምስክሮች ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 4/1/በ መሠረት በአካል ሳይታዩ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲመሰክሩ ይታዘዝለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት አስተያየት ኢትዮጲያ በፈረመቻቸው የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ሕጎችም ሆነ ሀይማኖትን መሠረት አድርገው አንድን ማሕበረሰብ በጅምላ በማጥቃት የሚፈጸሙ ወንጀሎች ወይም ዘር ማጥፋት ተፈጽሞባቸዋል በተባሉ የተለያዩ ዓለም አገራት ላይ እንኳን ዓቃቤ ሕግ በጠየቀው አግባብ በዝግ ችሎት ወይም ከመጋረጃ ጀርባ ምስክር እንዲሰማ አልተደረገም፤ የምስክሮች ጥበቃ አዋጅ ጥበቃ ተጠቃሚውን ብቻ ሳይሆን የተከሳሾችንም መብት ከግምት ያስገባ ነው፤ ከመጋረጃ ጀርባ ምስክር ቢሰማ የተጠሪዎችን የመከላከል መብት የሚያጣብብ በመሆኑ ሊፈቀድ አይገባም፤ ፍርድ ቤቱ የሙግት ሂደቱ ሙሉ ለሙሉ በግልጽ ችሎት እንዲታይ በማድረግ የማናቸውም ወገን ጥርጣሬ እና መላ ምት ተቀባይነት እንዳይኖረው የማድረግ ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲሰሙ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ በምስክሮች አሰማም ሂደት ላይ ያቀረቡትን ክርክር ከመረመረ በኋላ ዓቃቤ ሕግ ምስከሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ እንዲሰሙለት ያቀረበው ምክንያት ምስክሮች ከተከሳሾች ጋር የቅርብ ትውውቅ እንዳላቸው እና ከዚህ በፊትም ማስፈራሪያ ደርሶባቸው ነበር በማለት ነው፤ ይህ ደግሞ የምስክሮችን ማንነት ቀድሞ መታወቁን የሚያረጋግጥ ነው፤ የምስክሮች ማንነት ከታወቀ ደግሞ የጥበቃውን አስፈላጊነት ወይም የዓቃቤ ሕግን ጥያቄ ዋጋ ያሳጣዋል፤ በሌላ በኩል ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ከተከሳሾች ጋር የቅርብ ትውውቅ እንዳላቸው እና ከዚህ በፊትም ማስፈራሪያ ደርሶባቸው እንደነበር ከመግለጽ ውጪ በተጨባጭ ሊደርስባቸው የሚችል ከባድ አደጋ/ ስጋት እንዳለ በበቂ ሁኔታ አልተረጋገጠም፤ ስለሆነም የተጠሪዎችን ሕገ መንግስታዊ መብት በሚጥስ መልኩ ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ይሰሙልኝ በማለት የቀረበው አቤቱታ በሕግ አግባብነት የሌለው እና ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አደርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ መሠረት ማስረጃ መቀበል ወይም አለመቀበል ላይ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የማይባልበት በመሆኑ እና ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የማስረጃ አሰማም ሂደት ላይ የተሰጠውን ብይን በመቃወም የቀረበ ቅሬታ በመሆኑ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች ታሕሳስ 22 ቀን 2013 ዓ.ም ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፦ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ሊሰሙ ይገባል በማለት ባቀረብነው አቤቱታ ላይ የሰጠው ብይን የመጨረሻ ሊባል የሚችል እንጂ ጊዜያዊ ትዕዛዝ /interelocutory/ አይደለም፤ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት

የተሰጠው ውሳኔ የክርክሩን መቀጠል እና አለመቀጠል መወሰን በሚችል እና ተጠሪዎችን ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ነጻ ሊያስብል የሚችል በመሆኑ ስሕተት ነው፤ አመልካች ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ ይሰሙልኝ በማለት ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ በመደረጉ በምስክሮች አሰማም ቀጣይ ሂደት ላይ ይህን አቤቱታ በድጋሚ ለማቅረብ የሚችልበት እድል የለም፤ ክርክሩ ሲጠናቀቅም አጠቃሎ ሊያቀርበው የሚችለው ጉዳይ አይደለም፤ የምስክሮች ጥበቃ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ብይን ይግባኝ የተከለከለባቸው ጉዳዮች ስር አይሸፈንም፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 93234 ጊዜያዊ አገልግሎት ስላላቸው እና የመጨረሻ ውጤት ስላላቸው ጉዳዮች አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ ይህ ውሳኔ በክስ ላሻሽል ጥያቄ ላይ የተሰጠ ቢሆንም የሕግ ትርጉሙን ለመስጠት መነሻ የሆነው ምክንያት ግን የትዕዛዝ ይግባኝ የተከለከለ መሆኑን አስመልክቶ የተደነገገውን የስነ ስርዓት ሕጉ መርህ ሊተረጎም ስለሚገባበት አግባብ በመሆኑ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት አለው፤ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ይግባኝ የጠየቀበት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ መሠረት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የምስክሮች አሰማም ከመጋረጃ ጀርባ እንዲሆን እና በዝግ ችሎት እንዲታይ በዓቃቤ ሕግ የቀረበው ጥያቄ ውድቅ ተደርጎ የተሰጠው ትዕዛዝ ጊዜያዊ ስለሆነ ይግባኝ ሊባልበት አይገባም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 93234 ከሰጠው የሕግ ትርጉም እና ከአዋጅ ቁጥር 699/2003 እና ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በጠበቆቻቸው አማካኝነት የካቲት 04 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት የጽሑፍ መልስ ይዘት በአጭሩ፦ ሕገ መንግስቱ ካስቀመጠው ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች አንጻር እና ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 ከወጣበት ዓላማ አንጻር ሲታይ ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ እንዲሰሙለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፤ በምስክሮች አሰማም አቤቱታ ላይ የተሰጠው ብይን በመዝገቡ ላይ የመጨረሻ ሊባል የማይችል እና ጊዜያዊ ትዕዝዝ ነው፤ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፤ ዋናው ጉዳይ ሲጠናቀቅ ይግባኙን አጠቃሎ ለማቅረብ የሚያስችል ስርዓት በመኖሩ እንጭፍጫፊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይግባኝ ማቅረብ ክርክሮች እንዲጓተቱ እና መጠናቀቅ በሚገባቸው ጊዜ እንዳይጠናቀቁ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በዝግም ችሎት ሆነ ከመጋረጃ ጀርባ ባይሰሙ ማስረጃ ከመቅረቡ በፊት ተጠሪዎችን ነጻ ሊያስብል የሚችል ነው በማለት የሚከራከር ቢሆንም ማስረጃ ሳይቀርብ ቢቀር ወደፊት የማንቀሳቀስ መብት ተጠብቆ መዝገብ ይቋረጣል እንጂ ተጠሪዎችን ነጻ

የሚያስብል አይደለም፤ በሰ.መ.ቁ 93234 የተሰጠው ውሳኔ በክስ ላሻሽል አቤቱታ ላይ የተሰጠ በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የለውም የሚል ነው፡፡

5ኛ ተጠሪም በጠበቃው አማካኝነት የካቲት 09 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጠው መልስ አላስመሰክርም ማለት የዓቃቤ ሕግ መብት ነው፤ ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የማቅረብ ግዴታውን መወጣት አለመፈለጉ ይግባኝ በማይባልበት ነጥብ ላይ ይግባኝ ለማለት ዕድል ሊፈጥርለት አይገባም በማለት የተከራከረ ሲሆን በሌሎች ነጥቦች ላይ ደግሞ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ከሰጡት መልስ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልስ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከመዝገቡ ይዘት መገንዘብ የቻልነው አመልካች ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 6/1/ለ እና 4/1/ቀ ድንጋጌን መሰረት በማድረግ በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ከተቆጠሩት ምስክሮች ውስጥ ከፊሎቹ በዝግ ችሎት፤ ከፊሎቹ ደግሞ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲመሰክሩ ይታዘዝልኝ በማለት ላቀረበው አቤቱታ የሰጠው ምክንያት ተጠሪዎች የተከሰሱበት ክስ በባሕሪው በሕብረተሰቡ እና በአገር ሰላም እና ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል እና ከባድ ወንጀል ነው፤ የምስክሮች ጥበቃ አዋጅም የዚህ ዓይነት ወንጀሎች ላይ በምስክርነት የሚቀርቡ ሰዎች በልዩ ሁኔታ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ይደነግጋል፤ ምስክሮቹ ከተጠሪዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ለጥቃት ይጋለጡብኛል፤ እንዲሁም ጉዳዩን ለመለከታተል በሚመጡ ባልደረቦቻቸው፤ ጓደኞቻቸው እና ዘመድ ቤተሰቦቻቸው ታይተው ለአደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ ይኖራል፤ ቀዳሚ ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜም የግድያ ዛቻ የደረሰባቸው ምስክሮች አሉ በሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲሰሙ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ መሠረት በማድረግ አመልካች ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ የቀረበ አይደለም በማለት ተጠሪዎችን ሳያስቀርብ ከወዲሁ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ነጥብ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ሊሰሙልኝ ይገባል በማለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የሚባልበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ በ1954 ዓ.ም የወጣ ሲሆን የትዕዛዝ ይግባኝ ስላለመኖሩ አስመልክቶ የተደነገገው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 ድንጋጌ ፍርድ ቤቱ በቁጥር 94 መሠረት ቀጠሮ መስጠት ወይም አለመስጠትን፤ በቁጥር 131 መሠረት ስለሚቀርብ መቃወሚያ ወይም በቁጥር 146 መሠረት ማስረጃን ስለመቀበል ወይም ስላለመቀበል አስመልክቶ በሚሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የተከለከለ መሆኑን፤ ነገር ግን የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት፤ ለጊዜው በመልቀቅ ወይም ነጻ በመልቀቅ ፍርድ ተሰጥቶ ይግባኝ በተባለበት ጊዜ እነዚህ የተሰጡት ትዕዛዞች ይግባኝ ለማለት ምክንያቶች ለመሆን ይችላሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 በዋናው የስረ ነገር ክርክሩ ላይ ከሚሰጠው ፍርድ በፊት የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ የተጣለባቸውን ጉዳዮች የሚዘረዝር ሲሆን ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 699/2003 የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ ከወጣ አራት አሰርት ዓመታት ካለፉ በኋላ የወጣ እንደ መሆኑ መጠን በአዋጁ የተካተቱትን መብቶች አስመልክቶ ፍርድ ቤቶች በሚሰጧቸው ትዕዛዞች ላይ ስለሚኖረው የይግባኝ ስርዓት በመደበኛው የወንጀል ስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ተካተው አናገኛቸውም፡፡ ስለሆነም በዝግ ችሎት ወይም ከመጋረጃ ጀርባ ምስክር ሊሰማ አይገባም ተብሎ የተሰጠው ብይን በእርግጥም ይግባኝ የማይባልበት ጊዜያዊ ትዕዛዝ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመለየት የስነ ስርዓት ሕጉ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ከከለከለበት ምክንያት እና ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 ላይ የትዕዛዝ ይግባኝ የተከለከለበት ምክንያት የተሰጠው ትእዛዝ ከዋናው ጉዳይ ጋር ተጠቃሎ ሊቀርብ የሚችል እና አቤት ባዩም ወደፊት አጠቃሎ በሚያቀርበው ጉዳይ ላይ መፍትሄ ሊያገኝበት የሚችል ሲሆን እንደሆነ ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም የድንጋጌው ዓላማ ፍርድ ቤቶች በሚሰጧቸው ጊዜያዊ ትዕዛዞች በሙሉ ይግባኝ እየጠየቁ የፍትሕ ስርዓቱን እንዲጓተት ከማድረግ ይልቅ አቤት ባዩ ዋናውን ጉዳይ በሚመለከት ከሚያቀርበው ጉዳይ ጋር ተጠቃለው መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉ ጉዳዮች በዚያው ተጠቃለው እንዲቀርቡ በማድረግ የተቀላጠፈ የፍትህ ስርዐት እንዲኖር ማድረግ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ምስክሮች በዝግ ችሎት ወይም ከመጋረጃ ጀርባ እንዲሰሙ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን አመልካች ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፤ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል በማለት ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ጥያቄ ያቀረበባቸው ምስክሮች በግልጽ ችሎት እንዲሰሙ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ይግባኝ የሚጠየቅበት እና ለክርክር የሚቀርብ ጉዳይ አይለም፡፡ ስለሆነም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ምስክሮች በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ እንዲሰሙ ያቀረበውን

አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ መታየት ያለበት ትዕዛዝ ነው ከሚል መነሻ ብቻ ሳይሆን ከውጤቱም አኳያ ሊሆን ይገባል፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184/መ መሠረት ማስረጃ መቀበል ወይም አለመቀበል ላይ በሚሰጥ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የማይባልበት በመሆኑ እና ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የማስረጃ አሰማም ሂደት ላይ የተሰጠውን ብይን በመቃወም የቀረበ ቅሬታ በመሆኑ ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 199376 ታሕሳስ 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ጉዳይ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የቀረበ ሳይሆን የመጨረሻ ውጤት ባለው ብይን ላይ የቀረበ በመሆኑ ይግባኝ የሚባልበት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን በማለት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ መዝገብ ጥር 25 ቀን 2013 ዓ.ም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 260175 ምስክር ለመስማት የተጀመረው ሂደት እንዳይቀጥል በማለት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፤ ይጻፍ

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ 203051

የካቲት 22 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

| | |
|---|---|
| አመልካቾች፡- 1. አቶ ጀዋር ሲራጅ መሐመድ | ጠበቆች መሐመድ ጀማል |
| 2. አቶ በቀለ ገርባ ዳኮ | ምስጋኑ ሙለታ |
| 3. አቶ ሀምዛ አዳኔ ታዬ | ቱሊ ባይሳ |
| 4. አቶ ደጀኔ ጣፋ ገለታ | ገመቹ ጉተማ ቀረቡ |

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፡- ዐ/ሕግ ምኞት ደነቀው ቀረቡ

መዝገቡ በዛሬው ዕለት ሊቀርብ የቻለው የፍርድ ቤቱ ሬጅስትራር ተጠሪ በጉዳዩ ላይ መልስ ከሰጠ በኋላ አመልካቾች የመልስ መልስ መስጠት አያስፈልገንም በቀረበው መሠረት ታይቶ ይወሰንልን በማለታቸው መዝገቡ በችሎት ትዕዛዝ እንዲሰጥበት በማቅረቡ ነው፡፡ የአመልካቾች ጠበቆች በዛሬ ዕለት በችሎት ቀርበው ደንበኞቻቸው በጤና ችግር ምክንያት በሞት እና በሕይወት መካከል የሚገኙ መሆኑን ገልጸው በአስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩ ሕክምና ከማግኘት መብት ጋር የተገናኘ እና ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ አለመሆኑን ግንዛቤ በመውሰዱ በዛሬ ዕለት መዝገቡን መርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት የካቲት 18 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202289 በቀን 16/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በሕግ ጥላ ስር የሚገኙን እስረኛ ሕክምና ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካቾች በጠበቆቻቸው አማካኝነት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ

ቤት የካቲት ባቀረቡት አቤቱታ የግል ሐኪሞቻቸው በአስቸኳይ ሆስፒታል ሄደው መታከም እንዳለባቸው ያሳወቁ ቢሆንም ማረሚያ ቤቱ አመልካቾች የግል ሐኪም ቤት ሄደው እንዳይታከሙ በመከልከሉ ምክንያት ሕክምናቸው የተቋረጠ እና ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ መሆኑን በመግለጽ ማረሚያ ቤቱ አመልካቾች በመረጡት የግል የጤና ባለሙያ እና የሕክምና ተቋም የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ትዕዛዝ ይሰጥላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአመልካቾችን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ጠበቆቻቸውን በችሎት አስቀርቦ ከጠየቀ በኋላ ማረሚያ ቤቱ የካቲት 02 ቀን 2013 ዓ.ም ባመለከተው መሠረት አመልካቾች ለመታከም ፈቃደኛ ካልሆኑ እና የሚጠቅሱት ሆስፒታል ለሕዝብ እና ለደህንነት ስጋት የሚፈጥር ከሆነ ጦር ሀይሎች ሆስፒታል እንዲያሳክማቸው ያዘዘ ሲሆን በዛሬው እለት አመልካቾች የግል ሐኪም ቤት በመግለጽ ሕክምና እንዲደረግላቸው የጠየቁ እና የሕክምና ማዕከሉ የታወቀ በመሆኑ ማረሚያ ቤቱ አመልካቾችን አዲስ አበባ ከተማ ሜክሲኮ አካባቢ በሚገኘው ላንድ ማርክ ጀነራል ሆስፒታል በአጃቢ አስፈላጊውን ጥበቃ ተደርጎ ሕክምና እንዲደረግላቸው እንዲወስዳቸው ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ኢትዮጲያ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሕገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ትችት ከሰጠ በኋላ አዋጅ ቁጥር 1174/2012 እስረኞች ወደ ግል ሆስፒታል እንዳይሄዱ ገደብ ያልጣለ እና ገደቡ ከመንግስት አቅም እና የማሟላት ግዴታ አኳያ ብቻ እንጂ ከእስረኞች የግል አቅም አኳያ የማይገደብ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ አመልካቾች በግል ሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዳያገኙ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ በሌላ በኩል ተጠሪ ከጸጥታ ችግር አኳያ የሚያቀርበው ክርክር ዝቅተኛ ግምት ሊሰጠው አይገባም፤ አመልካቾች ከተከሰሱበት የእርስ በእርስ ግጭት ማስነሳት አኳያ እና ዓቃቤ ሕግ በይግባኙ ላይ ካቀረበው ለሕብረተሰብ እና ለአመልካቾች የደህንነት እና የጸጥታ ስጋት እንዲሁም ከነባራዊው ሁኔታ አኳያ ለአመልካቾች እና ለሕብረተሰቡ ደህንነት ሲባል በላንድ ማርክ ሆስፒታል የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የተሰጠው ትዕዛዝ አማራጭ የለውም፤ የሕክምና አገልግሎት በታካሚው ዘንድ ተቀባይነት ያለው እና የሚፈለገውን ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት፤ በመረጡት ሐኪም ሕክምና ማግኘት የታካሚው መብት ከመሆኑ አኳያ ያለፍላጎታቸው ይልቁንም ከፍተኛ ስጋት ያላቸው በመሆኑ በመንግስት የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተመራጭ አይደለም፤ ስለሆነም ከግራ ቀኙ ከተነሳው ክርክር አኳያ አመልካቾች የመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ፈቃደኝነት እና ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ የህክምና ሙያው በሚፈቅደው ደንብ መሠረት የሀኪሞች ቡድን በማደራጀት አመልካቾች ባሉበት በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ውስጥ ሙሉ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ዓቃቤ ሕግ ለስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የቀረበ በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 መሠረት ተቀባይነት የለውም፤ ተጠሪ የመጀመሪያው ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ በ15 ቀን ውስጥ ይግባኝ እንደሚል ያላሳወቀ በመሆኑ ያቀረበው ይግባኝ በጊዜ ገደብ የሚታገድ ነው፤ የስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደህንነት ችግር መኖሩን በማስረጃ ሳያረጋግጥ በላንድ ማርክ ሆስፒታል የህክምና አገልግሎት ቢሰጣቸው በአመልካቾች ላይ የጸጥታ ስጋት ይፈጠራል ማለቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች በመረጡት የግል ሐኪም የመታከም ሕገ-መንግስታዊ መብት አላቸው፤ የላንድ ማርክ ሆስፒታል ለንግድ የተቋቋመ እና በአንድ ቦታ የቆመ ድርጅት ሆኖ ሳለ ሆስፒታሉ ተነቅሎ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዲገባ የተሰጠው ትእዛዝ አግባብ አይደለም፤ አመልካቾች በሚገኙበት ማረሚያ ቤት ሕክምናውን እንዲያገኙ ቢደረግ የተለያዩ የሕክምና መሳሪያዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን እነዚህ መሳሪያዎች ደግሞ ለሕክምና በሚያመች መልኩ በሕክምና ተቋሙ ውስጥ የሚገኙ እንጂ እየተነቀሉ የሚሄዱ አይደሉም፤ ላንድ ማርክ ሆስፒታል ማረሚያ ቤት ድረስ በመሄድ ለአመልካቾች ሕክምና መስጠት እንደማይችል ያሳወቀ በመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ሊፈጸም የማይችል ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ሕክምና በተመለከተ የላንድ ማርክ ሆስፒታል የሀኪሞች ቡድን በማደራጀት ባሉበት ማረሚያ ቤት ውስጥ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሰት አንቀጽ 22/1 እና ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገር ክርክር የሚመለከት በመሆኑ ይህ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፤ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ የአመልካቾችን የሕክምና ጉዳይ በሚመለከት የመጨረሻ ትዕዛዝ በመሆኑ በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ በሚቀርብ ጊዜ ተጠቃሎ የሚቀርብ አይደለም፤ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 21/2 የታሰሩ ሰዎች ከሀኪሞቻቸው ጋር የመገናኘት መብት ያላቸው ቢሆንም በጥቅሉ የተቀመጠ ነው፤ በፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012 አንቀጽ 37 መሠረት ለእስረኞች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በማረሚያ ቤት ውስጥ የተዘጋጀ የጤና ተቋም ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 ላይ በማረሚያ ቤቱ የሚገኘው እስረኛ የጤና ሁኔታ በጤና ተቋሙ ከሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት አቅም በላይ የሆነ ሕክምና የሚጠይቅ ሲሆን በኮሚሽኑ በጤና ተቋሙ ባለሙያዎች በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት ወዲያውኑ ተገቢውን ጥበቃ በመመደብ እስረኛው ያስፈለገውን የሕክምና አገልግሎት ሊሰጥ ወደሚችል የመንግስት ሆስፒታል በመውሰድ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያደርጋል ይላል፤ አመልካቾች በመንግስት ሕክምና እምነት የለንም በማለታቸው የግል ሐኪማቸው እንዲያክሟቸው ሲደረግ የቆየ ሲሆን በሕገ

መንግስቱ የተሰጣቸው በግል ሐኪም የመጎብኘት መብት በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ሆነው በግል ሐኪማቸው የመታየት መብትን የሚሰጥ ነው ከሚባል በቀር ያለባቸው የጤና ችግር በተቋሙ ከሚሰጠው የሕክምና አቅም በላይ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በሌላ የሕክምና ተቋም እንዲታከሙ የሚያደርግ አይደለም፤ ሕክምናውን የሚሰጠው የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን ለመስጠት የተለያዩ መሳሪያዎችን ማጓጓዝ ይጠይቃል አላለም፤ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የአሁን ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በመረጡት ላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምና እንዲደረግላቸው በማለት የሰጠውን ትዕዝዝ በመቃወም ነው፡፡ በሌላ በኩል ግራ ቀኙ በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትም ሆነ በዚህ ችሎት ካደረጉት ክርክር ይዘት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በመረጥነው የግል ሐኪም ልንታከም ይገባል በማለት የሚከራከሩት በመንግስት የሕክምና ተቋም ብንታከም ከፍተኛ የሆነ ስጋት አለን በሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል /በግል የሕክምና ተቋም/ እንዲታከሙ ቢደረግ የጸጥታ ስጋት አለኝ የሚል መሆኑን ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው በቅድሚያ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ሲል የተሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ የሚባልበት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ዓቃቤ ሕግ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ሲል የሰጠውን ትዕዝዝ በዋነኝነት የሚቃወመው የጸጥታ ችግር ሊፈጠር ይችላል በሚል በመሆኑ እንደ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትዕዝዝ ቢፈጸም እና ምናልባትም ዓቃቤ ሕግ ሊፈጠር ይችላል ብሎ የሰጋው የጸጥታ ችግር ቢከሰት ይህንኑ የተፈጠረውን የጸጥታ ችግር ወደፊት በዋናው ጉዳይ ላይ ከሚያቀርበው ይግባኝ ጋር አጠቃሎ ሊያቀርበው የሚችል ባለመሆኑ ውጤቱ የሚቀለበስ አይደለም፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ የጠየቀበት ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 184 በተገለጸው አግባብ ይግባኝ የማይጠየቅበት ነው በማለት በአመልካቾች በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች በመረጡት ሐኪም ሕክምና ማግኘት የታካሚው መብት ከመሆኑ አኳያ ያለፍላጎታቸው ይልቁንም ከፍተኛ ስጋት ያላቸው በመሆኑ በመንግስት የሕክምና ተቋም አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ተመራጭ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በኋላ ተጠሪ ከጸጥታ ችግር አኳያ የሚያቀርበው ክርክር ዝቅተኛ ግምት ሊሰጠው አይገባም በማለት አመልካቾች የመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ፈቃደኝነት እና ፍላጎት

መሠረት ባደረገ መልኩ የህክምና ሙያው በሚፈቅደው ደንብ መሠረት የሀኪሞች ቡድን በማደራጀት አመልካቾች ባሉበት በቃሊት ማረሚያ ቤት ውስጥ ሙሉ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጣቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመልከት፡፡

የዓቃቤ ሕግ ዋነኛ ስጋት አመልካቾች በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል እንዲታከሙ ቢደረግ የጸጥታ ስጋት አለኝ የሚል መሆኑን በተለይም በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የዓቃቤ ሕግ ስጋት የመነጨው አንድም ዓቃቤ ሕግ ምናልባትም ሊፈጠር ይችላል በሚለው የጸጥታ ችግር ምክንያት ተጠሪጣሪዎቹ ቢያመልጡ ወይም በተጠርጣሪዎቹ ላይ አደጋ ቢደርስ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ከወዲሁ በመገመት መሆኑን ይህ ችሎትም ይገነዘባል፡፡

በመሠረቱ የመንግስት ዋነኛ ሚና የሕዝቦችን ሰላም እና ደህንነት ማረጋገጥ እና ማስጠበቅ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት መንግስት በፍትሕ ስርዓቱ ውስጥ የሚያልፉ ተጠርጣሪዎች ሰላም እና ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ይህ ግዴታም ተጠሪጣሪዎቹ በማረሚያ ቤት በሚገኙበት ጊዜ፣ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት እና ወደ ሕክምና ተቋማት በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ በጥብቅ ሊተገበር የሚገባው ነው፡፡ ይህን ካልን ዘንዳ በሕግ ጥላ ስር የሚገኝ ተጠርጣሪ ሕክምና ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ ሕክምና እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ሁሉ ማሟላት ያለበት መንግስት እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 1174/2012 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች በላንድ ማርክ ሆስፒታል ሊታከሙ ይገባል በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ዓቃቤ ሕግ ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ የለም፡፡ ይልቁንም ዓቃቤ ሕግ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የሚከራከረው የጸጥታ ችግር ስጋት ሊኖር ይችላል በሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ባስቀመጠው አማራጭ መሠረት ሕክምናውን እንዲያከናውን ትዕዛዝ የተላለፈለት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ማረሚያ ቤት ድረስ ሄጄ አመልካቾችን አላክምም ብሏል በማለት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን ክርክር በግልጽ በመካድ ከዓቃቤ ሕግ የተሰጠ ምላሽ የለም፡፡ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወሰደው አማራጭ ተፈጻሚ ሊሆን የማይችል መሆኑን ይህ ችሎት ግንዛቤ ወስዷል፡፡

በሌላ በኩል በአገራችን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽ ወደ ሕክምና ተቋሙ ሄዶ አገልግሎቱን የሚያገኝበት አሰራር እንጂ የሕክምና ተቋሙ ራሱ በማረሚያ ቤት የሚገኝ ተከሳሽ ባለበት ማረሚያ ቤት ሕክምናውን ለመስጠት የሚያስችሉ መሣሪያዎችን ይዞ በመሄድ ተንቀሳቃሽ ሕክምና ሊሰጥ የሚችልበት አሰራር የሌለ በመሆኑ እና በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን አካል በአማራጭ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሕክምና ቡድኑን በመያዝ ሕክምናውን በማረሚያ ቤቱ

ተቋም ሄዶ ባይሰጥ ሌላ አማራጭ ያልተቀመጠ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊፈጸም የማይችል እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም መንግስት ሊፈጠር ይችላል ያለውን የጸጥታ ስጋት ለማስወገድ ተገቢውን የጸጥታ እና ደሕንነት ማስጠበቅ ሃላፊነቱን በመወጣት አመልካቾች ቀድሞ በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን እንዲያገኙ እንዲያደርግ በማለት ወስነናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 202289 በቀን 16/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. መንግስት ሊፈጠር ይችላል ያለውን የጸጥታ ስጋት ለማስወገድ ተገቢውን የጸጥታ እና ደሕንነት ማስጠበቅ ሃላፊነቱን በመወጣት አመልካቾችን ቀድሞ በመረጡት የላንድ ማርክ ሆስፒታል ሕክምናውን እንዲያገኙ እንዲያደርግ በማለት ተወስኗል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.189472

ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አሸብር አውዴ

ተጠሪ፡- በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

የወላይታ ምድብ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 18 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 31815 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ያቀረበውን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31696 ታሕሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡- የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝናን የሚያጎድፍ እና ዛቻ መሰል አስተያየት እንደተጻፈ እና የእጅ ጽሑፉ ከአመልካች ጋር እንደሚመሳሰል በመግለጽ በቀን 06/11/2010 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ቢሮ ቀርቤ ምላሽ እንድሰጥ ትዕዛዝ ሰጥቶኛል፤ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ላይ በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ በዚህም ምክንያት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዳኞች እና ሠራተኞችም በማሰባሰብ በአስተያየት መስጫ መዝገቡ ላይ እኔ እንደጻፍኩ ገልጸዋል፤ ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሰው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለት ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሿን

ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው ምክንያት በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ፤ የመ.ቁ 32160፤ 33749 እና 30379 በሆኑት መዛግብት የተፈጸመብኝን በደል ይግባኝ ጠይቄ ፍትሕ አግኝቻለሁ፤ በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያዬን ውድቅ አድርጓል፤ አመልካች በቂም እና በጥላቻ በተደጋጋሚ የፍትሕ መዛባት የደረሰብኝ እና በተጠቀሱት ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ያለአድሎ የቀረበውን ክስ ሊሰማ የማይችል በመሆኑ ክሱ ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ተዛውሮ ይታይልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪ የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ፕሬዝደንቱ ጉዳዩን ለማጣራት አስተዳደራዊ ስራ ሰርቷል፤ ፕሬዝደንቱን በሚመለከት ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የደረሰ ክስ የለም፤ ሁለቱ ዳኞች የዲስፕሊን ክስ ቢቀርብባቸውም የመጨረሻ ውሳኔ አልተሰጠም፤ አንደኛው ዳኛ ከችሎት እንዲነሱ አቤቱታ ቀርቦ እንዲነሱ ተደርጓል፤ ሌላኛዋ ዳኛ ደግሞ የፍትሐብሔር ዳኛ በመሆን ዓመቱን ሙሉ የጨረሱ እና አሁንም እዚያው ያሉ ናቸው፤ ጉዳዮችን በይግባኝ ማሻር ለክስ ይዛወር ምክንያት አይሆንም፤ ፍርድ ቤቱ ከአስራ ሁለት በላይ ዳኞች ያሉበት እና በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩን እያዩ ያሉት ዳኞች ከተጠቀሱት ዳኞች ውጪ በመሆናቸው አመልካች ያቀረቡት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ፕሬዝደንቱ በሕግ በተሰጠው ስልጣን አስተዳደራዊ ተግባር መፈጸሙ ለክስ ይዛወርልኝ ምክንያትነት አይሆንም፤ ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤአለሁ በማለት ቀሪ ደብዳቤ መቅረቡ በእርግጥም አቤቱታው መድረሱን የሚያሳይ አይደለም፤ ደርሷል ቢባል እንኳን ክሱ ተቀባይነት አግኝቶ መልስ እንዲሰጡ የተደረገበት ሁኔታ የለም፤ በተቋሙ ባልደረቦችም በኩል በክፉ ዓይን እየታየሁ ነው በማለት የቀረበውም የራስ ጥርጣሬ ከሚሆን በቀር በምክንያትነት ሊወሰድ አይችልም፤ በዳኞቹ ላይ ለዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ስለማግኘቱ የቀረበ ማስረጃ የለም፤ አንደኛው ዳኛ ክስ የቀረበባቸው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን እንዳያዩ መደረጉ በችሎቱ ሂደት ተመዝግቦ እያለ ጉዳዩን በማያዩ ዳኛ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ መቅረቡ እንዲሁም በስም ተጠቃሿ ሌላኛዋ ዳኛም ጉዳዩን እያዩ ባለመሆኑ ጥያቄው ሕግን የተከተለ አይደለም፤ በይግባኝ ሥርዓት ጉዳዮች እንዲሻሩ፤ እንዲሻሻሉ ወይም እንዲጸኑ ማድረግ ሕጋዊ ሥርዓት ሲሆን ክርክሩ ደረጃውን ጠብቆ በይግባኝ ወይም በሰበር ስርዓት የሚቀጥል እና ተሻረ የተባለውም ጉዳይ የሕግ ትርጉም ተሰጥቶበት የሚሻርበት ወይም የሚሻሻልበት ሥርዓቶች በመሆናቸው ለክስ ይዛወርልኝ ምክንያት መሆን አይችሉም በማለት አመልካች ያቀረቡትን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ ይህም ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ከፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዛቻ እና ማስፈራራት እንደደረሰብኝ እና ከፍተኛ ጥላቻ እንዲያድርብኝ ማስደረጉን፤ ለክልሉ የሕዝብ ምክር ቤት እና ለዞኑ ምክር ቤት አቤቱታ ማቅረቤን እና በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ ማቅረቤን የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቤአለሁ፤ በተለያዩ መዝገቦች ከሙግት ስነ ስርዓት ውጪ ክርክር በመምራታቸው በአምስት የፍርድ ቤቱ ዳኞች ላይ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ በተከሰስኩበት የቼክ ወንጀል ፕሬዝደንቱ ሆን ብሎ የመሃል ዳኛ ሆኖ በመሰየም በዲስፕሊን ከከሰስኳቸው ዳኞች ጋር በመሆን መቃወሚያዬን ከሕግ ውጪ ውድቅ ማድረጉን፤ ክሱ የሚታይበት ፕሬዝደንት ዘመድ በሆነች ግለሰብ ላይ ያቀረብኩባትን የጉዳት ካሣና ኪሣራ ክስ አመልካች የጎፋ ብሔር ተወላጅ በመሆኔ ምክንያት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው፤ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቤ በሰ.መ.ቁ 164842 ጥቅምት 27 ቀ 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን እና የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔውን ያረመ መሆኑን፤ የክስ ይዛወርልኝ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የግል ተበዳይ የተባለው የዞኑ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መምሪያ ሃላፊ አጎቱ በመሆኑ እና በአካባቢው በሀብቱ እና በዘመዶቹ ብዛት ስሜን በማጥፋት መጠቀሚያ ያደረገኝ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች ባቀረብኩበት ሁኔታ አመልካች ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የስር ጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ባደረሰብኝ በደል በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩ በመሆኑ በገለልተኝነት ጉዳዩን ፍርድ ቤቱ ሊመለከት አይችልም በማለት ያቀረበውን የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ አቤቱታ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ያቀረበው የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጎበታል፤ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 106/2 መሠረት በግልጽ እንደተደነገገው እንዲዚህ ዓይነት ትዕዛዞች ይግባኝ የማይባልባቸው በመሆኑ አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ የወንጀል ሥነ ሥርዓቱን ያልተከተለ ነው፤ በጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ በተጻፈው የዛቻና የማስፈራሪያ ቃል አንጻር የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ይህን ጽሁፍ ጽፈዋል ተብለው ከተጠቆሙ ሰዎች ውስጥ አመልካችን ቢሮአቸው ጠርተው በማወያየታቸው እና የአስተዳደር ስራ በመስራታቸው ብቻ ለምን ተጠራሁ በሚል በሀሰት አቤቱታ ከማቅረባቸው በቀር አመልካች እንደሚሉት በፕሬዝደንቱ ላይ የቀረበ የዲስፕሊን ክስ የለም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ማዛወር /change of venue/ ትርጉም እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡፡

Change of venue is the removal of a suit began in one country or district to another country or district for trial, though the term is also sometimes applied to the removal of a suit from one court to another court of the same country or district.

በእኛም ሐገር ይህ ጽንስ ሐሳብ በአንድ ሥፍራ የተጀመረን ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ሄዶ እንዲታይ ማድረግ ወይም በአንድ ፍርድ ቤት የተጀመረን ክስ በዚያው ሥፍራ ላይ ወደሚገኝ ሌላ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ማድረግ ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶበታል፡፡

በወንጀል ጉዳይ የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ የሚቀርብበት ሥርዓት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 106 ላይ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓትን እና የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/1968 ተሻሽሏል፡፡ በዚሁ በተሻሻለው አዋጅ መሠረት በወንጀል ጉዳይ ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር መጠየቅ የሚቻለው ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ዓቃቤ ሕጉ ወይም ተከሳሹ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መሥማት የጀመረው የበታች ፍርድ ቤት በማመልከቻ የቀረበለትን ጉዳይ ያለአድሎ በትክክል ለመስማት የማይችል መሆኑን ወይም ጉዳዩ ዘወትር የማያጋጥም አስቸጋሪ የሕግ ክርክር የሚያስነሳ መስሎ መታየቱን ወይም በድንጋጌው አግባብ ትዕዛዝ ቢሰጥ ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለምስክሮች ምቹ መሆኑን ወይም ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ቢሰጥ በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ ለማስገኘት የሚያስችል ወይም ትዕዛዝ እንዲሰጥ የዚህ ሕግ ድንጋጌ የሚጠይቅ መሆኑን ሲያመለክት ነው፡፡

ከክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጽንስ ሐሳብ እና ከላይ ከተመለከተው ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ ወይም በዚያው ሥፍራ ላይ ወደሚገኝ ሌላ ፍርድ ቤት ሊዛወር የሚችለው ክሱ እየታየ ባለበት ሥፍራ ወይም ፍርድ ቤት ውስጥ ጉዳዩን ለማየት የሚችል ሥልጣን ያለው ሌላ ችሎት የሌለ በሆነ ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ሲጠይቁ ያቀረቧቸው ምክንያቶች በሙሉ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ ሊያይልኝ አይችልም በሚል የቀረቡ በመሆኑ የአመልካች ዋነኛ የክርክር አውድ የሚያጠነጥነው ከፍርድ ቤቱ ገለልተኝነት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በእርግጥም አመልካች ያቀረቧቸው ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ እንዳያይ የሚያደርጉ እና ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ

እንዲዛወር የሚያስችሉ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ ነጻ የዳኝነት አካል የተቋቋመ ስለመሆኑ፤ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል፤ ከማናቸውም ባለስልጣንም ሆነ ከማናቸውም ሌላ ተጽዕኖ ነጻ መሆኑን፤ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ሊያከናውኑ እንደሚገባ እና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሊመሩ እንደማይገባ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 እና 79 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም የዳኝነት ሥርዓቱ መሠረታዊ መርህ በመሆኑ ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች በላቀ ሥነ-ምግባር እና በጥብቅ ሊተገብሩት ይገባል፡፡ ይህን ተላልፈው በተገኙ ጊዜም አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በሕገ-መንግስቱ በተቋቋመው ነጻ የዳኝነት አካል ፊት በመቅረብ ፍትሕ የማግኘት መብታቸው የተረጋገጠላቸው ዜጎች ጉዳያቸው ውሳኔ ከማግኘቱ በፊትም ሆነ በኋላ ይህ መብታቸው በአግባቡ እንዲከበር ለማድረግ የሚያስችሉ መፍትሔዎች በተለያዩ ሕጎች ላይ ተቀምጠውላቸዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ገለልተኛ ያልሆነው ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ መጠየቅ፤ የክስ ወደ ሌላ ስፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄን ማቅረብ እና ዳኛው የሰጠው ፍርድ በይግባኝ እና በሰበር ስርዓት ማሳረም የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም በነጻነት እና ያለ አድሎ የመዳኘት ሕገ-መንግስታዊ ግዴታቸውን አክብረው ሥራቸውን ይከውናሉ ተብሎ ግምት የሚወሰድባቸው ዳኞች እና የፍርድ ቤት አመራሮች ይህን ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ አልተወጡም በማለት ተከራካሪ ወገኖች መብታቸውን ለማስከበር የሚያቀርቡት ማናቸውም አቤቱታ ሕጋዊ መሠረት ያለው እና በተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ላቀረቡት የክሥ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄ ያቀረቧቸው የመጀመሪያዎቹ ምክንያቶች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት በፍርድ ቤት አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝናን የሚያጎድፍ እና ዛቻ መሰል አስተያየት እንደተጻፈ እና የእጅ ጽሑፉ ከአመልካች ጋር እንደሚመሳሰል በመግለጽ ቢሮ ቀርቤ ምላሽ እንድሰጥ ትዕዛዝ በመስጠቱ የዲስፕሊን ክስ አቅርቤአለሁ፤ ይህንኑ ተከትሎ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ዳኞች እና ሠራተኞችም በማሰባሰብ በአስተያየት መስጫ መዝገቡ ላይ እኔ እንደጻፍኩ በመግለጽ በጥላቻ እንድታይ አድርገዋል፤ ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሱት ሁለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሿን ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ፤ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተለያዩ መዝገቦች ባደረግኩት ክርክር አላግባብ የተሰጠብኝን ውሳኔ በይግባኝ አሳርሜያለሁ፤ በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት

ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያዬን ውድቅ አድርጓል፤ ተጠቃሾቹ ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ያለአድሎ ሊያይ እንደማይችል ማሳያ ናቸው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ፍርድ ቤቱን በበላይነት የሚመራ በመሆኑ ራሱም ሆነ የፍርድ ቤቱ ዳኞች ከማናቸውም አካል ተጽእኖ ነጻ ሆነው ጉዳዮችን ያለአድሎ እንዲያዩ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ግዴታ ያለበት ሲሆን የፍርድ ቤቱንም ስም እና ክብር የመጠበቅ እና የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይህንኑ ሲያደርግም ሕግን እስካልተላለፈ ድረስ ተቋሙን በሚመለከት የሚቀርቡለትን ማናቸውንም መረጃዎች እና ማስረጃዎች እንደ አግባብነታቸው ሊጠቀምባቸው እና ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ያላቸውን አካላት ሊያነጋግር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት በፍርድ ቤቱ አስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝና የሚያጎድፍ ጽሑፍ በማየቱ ምክንያት አስተያየቱን ጽፏል ብሎ የገመተውን አመልካች ምላሽ እንዲሰጥበት ደብዳቤ መጻፉ ብቻውን አስተዳደራዊ ስራውን ሰርቷል ከሚያስብል በቀር የአመልካች ጉዳይ በነጻነት እና ያለአድሎ እንዳይታይ የማድረግ ውጤት አይኖረውም፡፡ ሆኖም የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ከዚህ አልፎ አመልካች የፍርድ ቤቱን ስም እና ዝና የሚያጎድፍ ጽሑፍ ጽፏል በሚል ምክንያት በፍርድ ቤቱ ዳኞች ላይ ተጽእኖ በመፍጠር የአመልካች ጉዳይ በገለልተኝነት እንዳይታይ የሚያደርግ ተግባር የፈጸመ ስለመሆኑ በተጨባጭ ማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ይዛወርልኝ ብሎ ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን እንደተመለከትነው አመልካች የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ፈጽሙት ያለውን ድርጊት ከማመላከት በቀር ፕሬዝደንቱ አቤቱታ ቀርቦባቸው መልስ ስለመስጠታቸውም ሆነ በቀረበው የዲስፕሊን ክስ መሠረት የተላለፈባቸው ውሳኔ ስለመኖሩ በመግለጽ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

አመልካች ስማቸው በአቤቱታው ላይ የተጠቀሱት የፍርድ ቤቱ ዳኞች ተከሳሽ በሆንኩበት የፍ.መ.ቁ 30379 በሆነው መዝገብ ተከሳሿን ለመጥቀም ከስነ-ስርዓት ውጪ ክርክሩን በመምራታቸው በዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ አቅርቤባቸዋለሁ በማለት የተከራከሩ ሲሆን በስም ተጠቃሾቹ ዳኞች ላይ ለዞኑ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ክስ የቀረበባቸው ቢሆንም ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ማግኘቱን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑን፤ አንደኛው ዳኛ ክስ የቀረበባቸው በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩን እንዳያዩ የተደረገ መሆኑ እና ሌላኛዋም ዳኛ ጉዳዩን የማያዩ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ይህ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ጉዳያቸውን በማየት ላይ የሌሉ ዳኞች ጉዳዬን በገለልተኝነት ሊያዩ አይችሉም በሚል ያቀረቡት የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

አመልካች በመ.ቁ 36642 ለቀረበብኝ የቼክ ወንጀል ክስ መቃወሚያ ያቀረብኩ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ ያቀረብኩበት የፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ተሰይሞ ሕግን ባልተከተለ ሁኔታ መቃወሚያዬን ውድቅ አድርጓል በማለት ያቀረቡት ምክንያትም ፕሬዝደንቱ አመልካችን ለመጉዳት ብለው ከሕግ ውጪ

መቃወሚያውን ውድቅ ስለማድረጋቸው በማስረጃ አለማረጋገጣቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመዝገቡ ላይ ተሰየሙ የተባሉት ፕሬዝደንት ገለልተኛ ሆነው ጉዳዩን አያዩም የሚሉ ከሆነ ፕሬዝደንቱ ከችሎት እንዲነሱ አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ከሚሆን በቀር ክስ ወደ ሌላ ስፍራ እንዲዛወር ለመጠየቅ የሚያስችል በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

ከላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወርላቸው ለመጠየቅ የሰጡት ሌላው ምክንያት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘመድ ላይ ያቀረብኩት ክስ አላግባብ ውድቅ ተደርጎ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች አቤቱታ አቅርቤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 164842 ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ በክርክር አመራር ረገድ የሕግ ስሕተት መፈጸሙን እና የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔውን አርሟል፤ ይህም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዬን በገለልተኝነት እንደማያይልኝ ማሳያ ነው የሚል ነው፡፡

ስለይግባኝ ሥርዓት በተመለከተው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስድስተኛ መጽሐፍ ቁጥር 320 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በተለይም ከቁጥር 337፤ 341፤ 343 እና 348 ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ የተጠየቀበት ፍርድ ሊጸና፤ ሊሻሻል፤ ሊለወጥ፤ ሊሻር ወይም ጭብጥ ተይዞ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲወሰን በማለት ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ሊመለስለት እንደሚችል ነው፡፡

አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 164842 አቤቱታ አቅርበው ጥቅምት 27 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው ውሳኔ ይዘት አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ዘመድ ናቸው የሚሏቸው የመዝገቡ 1ኛ ተጠሪ ሽንት ቤቱን ማፍረሳቸው ተረጋግጦ የፈረሰውን ለመገንባት የሚያስከትለውን ወጪ እንዲከፍሉ እና የተዘጋውን ሽንት ቤት እንዲያስከፍቱ ተወስኖ እያለና ውሳኔው ስለመሻሩ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሳይቀርብ አመልካች በዚህ ምክንያት የተቋረጠውን ገቢ ሲጠይቁ ሀላፊነትን የሚያሳይ የጸና ፍርድ ሕጋዊ ውጤት ምንድነው የሚለውን ሳይመለከቱ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ ሀላፊ አይደሉም ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች በክርክር አመራር ረገድ የፈጸሙት ስሕተት የአመልካች ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጋፋ ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና በመዝገቡ 1ኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር በመቀጠል ጭብጥ መስርቶ አከራክሮ እንዲወስን በሚል የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ይህም በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ላይ ስለ ይግባኝ ሥርዓት በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ክርክር ተደርጎ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ የተሻሻለ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ አመልካች እንደሚሉት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጉዳይ ገለልተኛ ሆኖ ባለማየቱ ምክንያት የተሰጠ ውሳኔ ስለመሆኑ ተገልጾ

ውሳኔው የተሻረ መሆኑን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ይህንኑ መሠረት በማድረግ ያቀረቡት የክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው መልስ ፍርድ ቤቱ ከአስራ ሁለት በላይ ዳኞች ያሉበት እና በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩን እያዩ ያሉት ዳኞች ከተጠቀሱት ዳኞች ውጪ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር በአመልካች በኩል ያልተካደ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ጉዳዬ በገለልተኝት ሊታይ አይችልም በማለት ያቀረቡት ምክንያት ተቀባይነት አለው ቢባል እንኳን ጉዳዩን የሚያዩት ዳኞች ከችሎት እንዲነሱ በሚቀርብ አቤቱታ መነሻነት ክሱ በዚያው ፍርድ ቤት ውስጥ በሚገኝ ሌላ ችሎት ላይ በሚያስችሉ ዳኞች እንዲታይ ከሚደረግ በቀር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውስጥ ያሉት ዳኞች በሙሉ የአመልካችን ጉዳይ በገለልተኝነት እንደማያዩ ተቆጥሮ ክሱ ወደ ሌላ ሥፍራ እንዲዛወር ማድረግ ፍርድ ቤቶች በሕገ-መንግስቱ የተጣለባቸውን ግዴታ አክብረው ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ጉዳዮችን ይዳኛሉ በሚል በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን አመኔታ በእጅጉ የሚሸረሽር በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክስ ወደ ሌላ ሥፍራ ይዛወርልኝ በማለት ላቀረቡት አቤቱታ የጠቀሷቸው ምክንያቶች ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው እና በተጨባጭ ማስረጃ ያልተረጋገጡ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 31815 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 31696 ታሕሳስ 01 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ጥር 21 ቀን 2012 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የሰ/መ/ቁጥር 211525

መጋቢት 08 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1ኛ መንሱር ጁሃር መሀመድ

2ኛ ፉአድ ጁሃር መሀመድ

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካቾች ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይኸው ይታረምልን በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

የነገሩ አመጣጥ የኮንትሮባንድ ወንጀል ጉዳይ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ የአሁን አመልካቾች የምግብና መድሀኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀጽ 46 እና የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በአዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንደተሻሻለው/አንቀጽ 168/2/ ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ የአሁን አመልካቾች ስልጣን ባለው አካል ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ወደ ሀገር እንዳይገባ ገደብ የተደረገበት ዕቃ መሆኑ እያወቁ ወይም ማወቅ ሲገባቸው በቀን 19/01/2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 10፡30 ሰዓት ላይ በሚሆንበት ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ልዩ ቦታው በግ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የቤት ቁጥር 668 በሆነ መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በተደረገው ፍተሻ

በአጠቃላይ ታክስና ቀረጥ መጠናቸው ብር 76,982.92 የሆነ ብዛቱ በቁጥር 80 ስቴክ ሻምላ የተባለ የስሪት ሀገሩ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ እና 79 ስቴክ ብሉስ የተባለ የስሪት ሀገሩ እንግሊዝ የሆነ ሲጋራዎችን በካርቶን አሰቀምጠው የተገኙ በመሆናቸው የኮንትሮባንድ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ከሷል፡፡

አመልካቾች ክሱ ደርሷቸው በችሎት ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የወንጀል ድርጊቱን አልፈጸምንም ጥፋተኛ አይደለንም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ ሁለት የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክርም በህብረተሰቡ ጥቆማ መሰረት በቀን 19/01/2013 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ሰዓት አካባቢ በብርበራ ትዕዛዝ እና ታዛቢዎች ባሉበት የአሁን አመልካቾች ቤት እንደተበረበረ እና የተለያዩ የውጭ ሀገር ብሮች እና ሲጋራዎች መገኘታቸውን፣ የተገኙት ሲጋራዎች የስሪት ሀገራቸው ኢንግላድ እና የአረብ ኤምሬትስ እንደነበር በሰዓቱ ደረሰኝ ተጠይቀው እንዳልነበራቸው፤ የአሁን 2ኛ አመልካች ዕቃው የእኛ ነው ብሎ እንዳላቸው ከዛም ዕቃዎቹን እና አመልካቾችን በመኪና ይዘናቸው ወደ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወስደናቸዋል በማለት መስክሯል::

2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በሰጡት የምስክርነት ቃልም በተሰጠን ጥቆማ መሰረት በቀን 19/01/2013 ዓ.ም ከቀኑ 10፡30 ሰዓት አካባቢ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 668 የሆነ አመልካቾች የሚያከራዩት አልጋ ቤት ውስጥ የብርበራ ትዕዛዝ ወጥቶ እንደተበረበረ እና በክሱ ላይ የተገለፁትን የውጭ ሲጋራዎች አግኝተናል የአሁን 2ኛ አመልካች ለ1ኛ አመልካች ደውሎለት መጣ፣ ደረሰኝ እናመጣለን ብለው የነበረ ቢሆንም አላመጡም በማለት መስክራለች፡፡ዐቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃዎችንም ከክሱ ጋር አያይዞ አቅርቧል፡፡

በዚሁ መሰረት ቀርበው የተሰሙት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች የአሁን አመልካቾች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውን ስላስረዱ የአሁን አመልካቾች ዐቃቤ ሕግ ክስ በመሰረተበት ድንጋጌዎች ስር በወ/መ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.142 መሰረት እንዲከለከሉ በማለት ብይን ሰጥቷል የአሁን አመልካቾች ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡1ኛ የመ/ምስክር የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለ ቀን 10፡00 ሰዓት አካባቢ እዝያው ቤት ውስጥ እንደነበሩ በዛን ሰዓት ሰፈሩ በፖሊሶች ተከቦ እየተፈተሸ እንደነበር እና የአሁን አመልካቾች አልጋ ቤት ዶላር ይመነዘራል ብለው እንደመጡ የአሁን አመልካቾች የሉም ይመጣሉ እንዳሏቸው፤ቤት ውስጥ ትንሽ ካዝና እንዳገኙ እና ቁልፍ ሲጠይቋቸው ቁልፍ የለም ሲሉ ሰብረው እንደከፈቱት እና ውስጡ ምንም እንዳልነበር፣ከዛም በመቀጠል የተከራዮችን ቤት እንደፈተሹ እና ከአንደኛው ቤት ውስጥ ሶስት ካርቶን ሲጋራ ይዘው እንደወጡ፣ ከዛም የአሁን 2ኛ አመልካች እንደመጣ እና ደረሰኝ አለህ ወይ ብለው ሲጠይቁት ቆይ ለወንድሜ ልደውል ብሎ ለአሁን 1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና እሱ እስኪመጣ ድረስ ብለው

ዕቃውን እና የአሁን 2ኛ አመልካችን ይዘው መሄዳቸውን፤ የተገኘው ሲጋራ ቤት ሰው የሙስሊም ኮፍያ እና ሽርጥ የለበሰ ሰውዬ እንደነበር እና ሰላም ብሎት እንደሄደ መስክሯል፡፡2ኛ መ/ምስክር መስከረም 19/2013 ዓ.ም ቁጭ ብዬ ጫት እየቃሙ እያለ ሰፈሩ ውስጥ የጦር መሳሪያ ፍተሻ እንደነበር እና ከዚያም ወደ አሁን አመልካቾች አልጋ ቤት እንደገቡ እና ፍተሻ እንደጀመሩ ከዛም የተቆለፈ ካዝና እንዳገኙ እና ቁልፍ ብለው ሲጠይቁ የለም ጠፍቷል ሲባሉ እንደተሰበረ ፣ የተከራዮች ቤት እየተፈተሸ እንደነበር እና አንደኛው ቤት ቁልፉ ተሰብሮ በሚፈተሽበት ወቅት ሁለት ካርቶን የተበታተነ ሲጋራ እንደተገኘ፣ ሲጋራው የተገኘው ቤት ሰውዬ ሰላም ብሏቸው እንደወጣ፣ የአሁን 2ኛ አመልካች እንደመጣ እና ለ1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና ሲመጣ ፖሊሶች ይዘዋቸው እንደሄዱ መስክሯል፡፡

3ኛ መ/ምስክር በበኩላቸው ወንጀሉ ተፈፀመ በተባለ ቀን ከአሁን 2ኛ አመልካች ጋር ማኪያቶ ጠጥተው እየተመለሱ እንደነበር እና ቤቱም እየተፈተሸ እንደነበር፣ አልጋ ቤቱ የእናታቸው እንደሆነ እና ፖሊሶቹ ካዝናውን እየሰበሩ እንደነበር እና ቤቶቹን እየፈተሹ እንደነበር፣ ከዛም ሲጋራው እንደተገኘ እና የአሁን 2ኛ አመልካች ለ1ኛ አመልካች እንደደወለለት እና የተከራየው ሰውዬ ደረሰኝ አለው ወይ ብሎ እንደጠየቀው እና አላየሁም እንዳለው፣ አልጋ የተከራየውንም ሰውዬ እየዞሩ እንደፈለጉት እና እንዳላገኙት እና አመልካቾችን ፖሊሶች ይዘዋቸው እንደሄዱ መስክሯል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ተከትሎ በሰጠው ውሳኔም በክሱ ላይ የተመለከተው የውጪ ሀገር ሲጋራ ከህብረተሰቡ በደረሳቸው ጥቆማ መሰረት ፍተሻ ተደርጎ እንደተገኘ 2ኛ አመልካችም እቃው የኛ ነው እንዳላቸው እና 1ኛ አመልካች ደረሰኝ አመጣለሁ ያለ ቢሆንም አለማምጣቱን አቃቤ ህግ በምስክሮቹ ማስረዳቱን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ቤቱን ሌላ ግለሰብ መከራየቱን በክርክራቸው አግባብ ያላስረዱ መሆኑን፤ቤቱን ሌላ ሰው ለመከራየቱ መታወቂያና ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን፤የመከላከያ ምስክሮቹ አመልካቾች እቃው የኛ ነው ብለው በገለፁበት ምስክሮቹ የሌላ ሰው ነው ማለታቸው የሚያሳምን አለመሆኑን በመጥቀስ አመልካቾችን በቀረበባቸው ክስ ጥፋተኛ በማለት አመልካቾችን ያርማል ሌላውንም ያስጠነቅቃል ባለው በአንድ ዓመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት እና ብር 15,000.00/አስራ አምስት ሺ.ህ/ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌ/ከ/ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 32 መግቢያ የብርበራ ስራ ስለሚከናወንበት ሂደት ይደነግጋል፡፡በዚሁ መሰረት ማንኛውም መርማሪ ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ በፍርድ ቤት በተሰጠ የብርበራ ማዘዣ መሰረት ካልሆነ በቀር ቤትን መበርበር እንደማይቻል በግልጽ ይደነግጋል፡፡ይህንን ተከትሎ አንቀጽ 32(2) በፍርድ ቤት የሚሰጥ የብርበራ ትዕዛዝ የሚበረበረውን ቦታና የሚያዘውን ዕቃ ማመልከት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ከዚህም ባለፈ

ብርበራው የሚያከናውነው የፖሊስ ባልደረባ በመያዣው ትዕዛዝ ከተመለከተው ዕቃ ውጭ መያዝ እንደማይችል በግልጽ ይደነግጋል፡፡ምንም እንኳን አመልካቾች የብርበራውን ትዕዛዝ ይዘት ብርበራው በተከናወነበት ወቅት በውል ባንረዳውም የተከበረው ፍ/ቤት ከመዝገቡ እንደሚረዳው በክሱም ሆነ በፍርዱ በግልጽ እንደተመለከተው ፖሊስ ከፍርድ ቤት ያወጣው የብርበራ ትዕዛዝ የቤት ቁጥር 668 ን የሚመለከት ነው፡፡በዚህም ቤት ውስጥ እንዲያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ዕቃ የጦር መሳሪያ እና የውጭ አገር ገንዘብ ነው፡፡

በብርበራ ትዕዛዙ የተጠቀሰው ቤትም ሆነ እንዲያዝ ትዕዛዝ የተሰጠበት ዕቃ ከአመልካቾች ምንም ግንኙነት ያለው አይደለም፤ በፍርድ ቤትም አልተረጋገጠም፤ይልቁንም በዐቃቤ ሕግ 2ኛ ምስክርና በአመልካቾች መ/ምስክር እንደተመሰከረው ዕቃዎቹ የተያዙት የተቆለፈ ክፍል ቤት በሩ ተሰብሮ ነው፡፡ይህ የተሰበረው ቤት ደግሞ እናታችን የሚያከራዪት ቤት ስለመሆኑ የተመሰከረ ሲሆን ይህ ቤት በዐቃቤ ሕግ ክስ እንደተመለከተው የአመልካቾች መኖሪያ ቤት አይደለም፡፡ይህ በብርበራ ትዕዛዝ የተመለከተው የቤት ቁጥር 668 ተበርብሮ እንዳበቃ እንዲሁ መደዳውን ያሉት ቤቶች ናቸው የተበረበሩት፡፡በዚህም ሂደት የእናታችን ቤት የቤት ቁጥር 664(ለ) ሲሆን ብርበራውም የተከናወነው መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ሲጋራዎቹም የተያዙት በቤት ቁጥር 668 ሳይሆን በዚህ ቤት ቁጥር 664(ለ) ውስጥ ሲሆን ብርበራው የተከናወነው በፍርድ ቤት ከተፈቀደው ቦታ ውጭ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ ፍርድ ቤት ሰጠ የተባለው የብርበራ ትዕዛዝ የውጭ ምንዛሪን እና የጦር መሳሪያ ፍለጋ ነው፡፡በብርበራው የተያዘው ግን በብርበራ ትዕዛዙ እንዲያዝ ፈቃድ ከተሰጠበት የጦር መሳሪያ እና የውጭ ምንዛሪ ውጭ ሲጋራ ነው፡፡ስለዚህ የተከበረው ፍርድ ቤት ፖሊስ በፍርድ ቤት ከተሰጠው ስልጣን በማለፍ ባልተፈቀደበት የቤት ቁጥር ቤቱን ሰብሮ በመግባት እንዲያዝ ከተፈቀደው ውጭ ያለን ዕቃ ነው የያዘው፡፡በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ የሚከናውን የባለስልጣን ተግባር ደግሞ እንዳልተከናወነ የሚቆጠር እና የሕግ ውጤት የማይሰጠው መሆኑ እየታወቀ አፈፃፀሙ የሕግ ስሕተት የለበትም መባሉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም ፖሊስ ብርበራ ያከናወነው በብርበራ ትዕዛዝ ከተጠቀሰው የቤት ቁጥር 668 ሌላ በቤት ቁጥር 664(ለ) በመሆኑ ያለስልጣኑ ነው የሰራው እንዲባልልን፤

አመልካቾች የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች ቃል በተገቢው ሁኔታ ያስተባበልን ሆኖ ሳለና የስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያለን የማስረጃ ምዘናን መርህ በመጣስ ሆኖ ሳለ በማስረጃ ምዘና ረገድ የተፈፀመ ስሕተት የለም መባሉ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፤ የአመልካቾች የእስራት ቅጣት ላለመገደብ በቂ ምክንያት ስለሌለው ሊገደብ የሚገባው ሆኖ እያለ አመልካቾች የእድሜያችን ለጋነት፤አዛውንትና በሽተኛ ወላጆቻችንን የምንረዳ እና የምንደግፍ መሆናችን

ከግምት ውስጥ ገብቶ ቅጣቱ ሊገደብ ሲገባ መታለፉ አግባብ አይደለም፤ ብርበራው የተደረገው የቤት ቁጥር 664(ለ) በሆነው የእናታችን ቤት ላይ መሆኑን ለማስረዳት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረብነውን የንግድ ፈቃድ እና የኪራይ ውል ይቀበለን ጥያቄ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ስለሆነም ክሱን በአግባቡ ተከላክለዋል ተብሎ ከክሱ በነፃ እንድንሰናበት ይወሰንልን፤ይህ የሚታለፍ ቢሆን የአመልካቾችን የእስራት ገደብ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባለመኖሩ የእስራት ቅጣቱ እንዲገደብልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የኮንትሮባንድ ዕቃ የተያዘው አመልካቾች ባከራዩት አልቤርጎ ክፍል ውስጥ ስለመሆኑ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባስረዱበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 እንደተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 168/2/ ስር ጥፋተኛ የተባሉበትን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2/ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ 25/02/2014 ዓ.ም በተፃፈ በሰጠው መልስ ሲጋራው የተገኘበት ቤት የአመልካቾች በመሆኑ እና ቤቱ ለሌላ ሰው የተከራየ ስለመሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቾች በቀረበባቸው ወንጀል ጥፋተኞች ናቸው በሚል እንዲቀጡ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነው ውሳኔ የሕግም ሆነ የማስረጃ ምዘና ስሕተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾችም የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አጣሪው በማሰቀረቢያነት ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ማንኛውም ሰው የግል ህይወቱ፣ግላዊነቱ የመከበር መብት ያለው መሆኑ፤ይህ መብቱም መኖሪያ ቤቱ፣ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን እንደሚያካትት በኢ.ፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 26(1) የተመለከተ ሲሆን ይህ መብት ያለ ገደብ የተሰጠ ሳይሆን በተወሰኑ በህጉ በተመለከቱት ሁኔታዎች ሊገደብ እንደሚችል በአንቀፅ 26(3) የተመለከተ ሲሆን በዚህ አግባብም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሄራዊ ደህንነትን፣የህዝብን ሰላም፣ወንጀልን በመከላከል፣ጤናንና የህዝብ የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር አላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ህጎች መሰረት የመብቱ አጠቃቀም ሊገደብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

በዚህ አግባብ ሊመረመርና ተገቢው የህግ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚገባው የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32 እና 33 ድንጋጌዎች አንድ መርማሪ ፖሊስ ወይም የፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ የወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል ብሎ ሲያምንና ከወንጀል ምርምራው ሂደት ጋር በተያያዘ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲረዳው ብርበራ በማድረግ ማስረጃዎቹን መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በመርህ ደረጃ

በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(1) የብርበራ ማዘዣ ከማንኛውም ፍርድ ቤት ሊያገኝ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን ለፍትህ አላማ እንዲረዳ ምርመራውን ለማገዝ እንዲችል ይህ ሲከወንም የተጠርጣሪውን ግለሰባዊ መብት ባከበረ መልኩ መፈፀሙ አስፈላጊ መሆኑ በፍርድ ቤቱ ታምኖበት የተሰጠው የብርበራ ማዘዣ የሚበረበረውንና የሚያዘውን እቃ በግልፅ ማመልከት ያለበት መሆኑን፤በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ ፖሊስ ሊይዝ የማይችል መሆኑን አንቀፅ 33(2) የሚደነግግ ሲሆን፤ብርበራው የሚደረግበትን ሰአት አስመልክቶም በተለየ ሁኔታ ካልታዘዘ በስተቀር ብርበራው የሚደረገው ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ እስከ ማታው አስራ ሁለት ሰአት ድረስ ብቻ መሆኑን በአንቀፅ 33(5) የተመለከተ መሆኑን መነሻ በማድረግ የተዘጋጀው በህጉ የተመለከተው ፎርም የብርበራው ቀንና ሰአት በግልፅ መመልከት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሁኔታዎች ብርብራ የሚደረግበትን የህግ ስርዓት በዝርዝር የሚያመለክቱ ቢሆኑም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32(2) የተመለከቱት ቀሪ ሁኔታዎች (Exceptions) በሌሉበት ብርበራ ያለ ብርበራ ትዕዛዝ ቢከናወን ወይም በብርበራ ትዕዛዙ ከተመለከተው ጊዜና ቦታ ውጪ ብርበራ ቢደረግ አልያም በብርበራ ትዕዛዙ ላይ ከተመለከተው እቃ ውጪ በብርበራ ቢያዝ በሂደቱ የተገኘው ማስረጃ አግባብነቱ ምን ሊሆን እንደሚገባ በህጉ በግልፅ አልተመለከተም፡፡በተለያዩ የህግ ስርዓቶች በብርበራ የተገኘ ማስረጃን አስመልክቶ ማስረጃው የተገኘበት አግባብ ህጋዊ አለመሆኑ ማስረጃውን ህገ ወጥ አያሰኘውም (Admissibility of evidence is not affected by the illegality of the means through which the party has been enabled to obtain the evidence) የሚለው በመጀመሪያ የነበረው መርህ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብትን (Right to privacy) ጥበቃ መስጠትን ግቡ በማድረግ በሂደት እየዳበረ ሄዶ የብርበራው ምክንያታዊ መሆን ከብርበራው ለተገኘው ማስረጃ ተቀባይነት የሚያስገኝለት ሆኖ ምክንያታዊ ካልሆነ በብርበራ የተገኘን ማስረጃ ዋጋ ማሳጣት እየተለመደ የመጣ ሲሆን የብርበራው ምክንያታዊ መሆንና አለመሆን የሚለካውም ብርበራው ሲካሄድ የነበሩትን አጠቃላይ (Total atmosphere of the case) ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን እንደሚገባ የተለያዩ የዘርፉ ፀሀፍት ያስረዳሉ፡፡

በዚህ አግባብም ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት በቂ እና ምክንያታዊ ጊዜ ነበርን? የሚለው የብርበራውን ህጋዊነት ለመመዘን ከግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባ መሰረታዊ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ከሶስት አመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ወንጀል ለማስረጃ የሚሆን ወንጀሉ የተፈፀመበት ነገር በአንድ ቦታ የተደበቀ ወይም የተቀመጠ መሆኑ ለመርማሪው ፖሊስ ወይም ለፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ የተነገረው ከሆነና መበርበሪያ ትዕዛዝ እስኪቀበል ድረስ ወንጀል የተሰራበት ነገር ካለበት ቦታ ይወሰዳል ተብሎ በበቂ ምክንያት የታመነ ከሆነ ብርበራው ያለብርበራ ማዘዣ ሊከናወን እንደሚችል በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.32(2)(ለ) መመልከቱ

ከላይ የተመለከተው ቀሪ ሁኔታ በስነ ስርዓት ህጋችንም ተገቢው አውቅና የተሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይም በብርበራ የተገኙት ሲጋራዎች ተቀባይነትና ማስረጃዊ ፋይዳ ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ከተሰጠው የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት አንፃር እየታየና እየተመዘነ የህግ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል ብለን እናምናለን፡፡አመልካቾች ብርበራው የተከናወነው ብርበራው እንዲከናወን ከተፈቀደለት ቤት ውጪ እናታቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እያከራዩ በሚጠቀሙበት የቤት ቁጥር 664(ለ) ውስጥ መሆኑን በብርበራ የተገኘው እቃም የብርበራ ፈቃድ ከተሠጠበት የጦር መሳሪያና የውጪ ምንዛሪ ውጪ ሲጋራ መሆኑን በመግለፅ በብርበራው የተገኘው በውጪ ሀገር የተመረተው ሲጋራ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብባቸው እንደማይገባ ገልጸው የተከራከሩ ቢሆንም በአመልካቾች ጭምር እንደታመነው ቤቱ እናታቸው አከራይተው የሚጠቀሙበት ሆኖ እያለ የመከላከያ ምስክሮቹ እንዳስረዱትም ቤቶቹ ለአልጋ ተከራዮች የሚከራዩ ሆኖ እያለ ይህም በቤቱ ላይ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት አላቸው ሊባሉ የሚችሉት በወቅቱ የተከራዩ ግለሰቦች የነበሩ መሆኑን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ያላስረዱ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመረጋገጡ አንፃር የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብቱ እጅግ ቢበዛ የእናታቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካቾች የቤቱ ባለቤት ባለመሆናቸው ብርበራው ከተከናወነበት ቤት ጋር በተያያዘ ሊከበር የሚገባ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት ያላቸው መሆኑን ከመነሻውም ባላሳዩበት ብርበራው ኢ-ምክንያታዊ ሆኖ የግል ህይወት የመከበርና የመጠበቅ መብታችንን ጥሷል በዚህ ምክንያትም ማስረጃው አግባብነት የለውም ብለው መከራከራቸው የሚያሳምን ሆኖ አልተገኘም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በብርበራው ወቅት የነበሩትን አጠቃላይ ሁኔታዎች ስንመዝንም ለመርማሪው ተጨማሪ የብርበራ ትዕዛዝ ለማግኘት የሚያስችሉ አለመሆናቸውን ምስክሮቹ ከሰጡት የምስክርነት ቃል የምንረዳው ነው፡፡ይህም አመልካቾች በብርበራ የተገኘው ሲጋራ ለፖሊስ ከተፈቀደለት ስልጣኑ ውጪ የተገኘ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችና መርህዎች መሰረት ያላደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

አመልካቾች ከማስረጃ ምርመራና ምዘና አንጻር ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በተመለከተ በመሰረቱ በኢ.ፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን

በተመለከተ በዋነኘነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው ውሳኔም በክሱ ላይ የተመለከተው የውጪ ሀገር ሲጋራ ከህብረተሰቡ በደረሳቸው ጥቆማ መሰረት ፍተሻ ተደርጎ እንደተገኘ 2ኛ አመልካችም እቃው የኛ ነው እንዳላቸው እና 1ኛ አመልካች ደረሰኝ አመጣለሁ ያለ ቢሆንም አለማምጣቱን አቃቤ ህግ በምስክሮቹ ማስረዳቱን አመልካቾች በምስክሮቻቸው ቤቱን ሌላ ግለሰብ መከራየቱን በክርክራቸው አግባብ ያላስረዱ መሆኑን፣ቤቱን ሌላ ሰው ለመከራየቱ መታወቂያና ሌላ አግባብነት ያለው ማስረጃ አለመቅረቡን፣የመከላከያ ምስክሮቹ አመልካቾች እቃው የኛ ነው ብለው በገለፁበት ምስክሮቹ የሌላ ሰው ነው ማለታቸው የሚያሳምን አለመሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣናቸውን ተጠቅመው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ያልተገኘ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መስጠታቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ገደብን አስመልክቶም ከእስር በገደብ መለቀቅ ማለት ፍርድ ቤት አንድ ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲፈታ የሚደረግበት የህግ ስርዓት መሆኑን ከወ/ህ/አ.190 የምንገነዘበው ነው፡፡የገደብ ውሳኔ በዘፈቀደ የሚሰጥ ወይም የሚከለከል ባለመሆኑ የገደብ አሰጣጥ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ ፍርድ ቤቶች በህግ የተመለከቱት ሁኔታዎች በዋነኘነትም በወ/ህ/አ.192፣194 እና 197 መሟላት አለመሟላታቸውን በጥንቃቄ ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡በዚህ አግባብ የገደብ ውሳኔ ካልተሰጠ የወንጀል ህጉን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት የማይቻል መሆኑ ይታመናል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የገደብ ጥያቄ አቅርበው የነበረ መሆኑን የግራ ቀኙን ክርክር ተከትሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚያሳይ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው በደፈናው ይገደብልን በማለት ያቀረቡትን ሀሳብ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም በማለት ነው፡፡የአመልካቾች የገደብ ጥያቄ ከወ/ህ/አ.192፣194 እና 197 መስፈርቶች አንፃር ተቀባይነት ያጣበትን ምክንያት በመዘርዘር በውሳኔው ላይ የገደብ ጥያቄውን ውድቅ ያደረገበትን ምክንያት በዝርዝር አላስፈረም፡፡ይህ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የገደብ ጥያቄን በደፈናው ውድቅ የማድረግ ሂደት

ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሊታረም ሲገባው ፍርድ ቤቱ ይህንን መሰረታዊ የህግ ስህተት ሳያርም መቅረቱ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በአመልካቾች የተጣለው የእስራት ቅጣት ከአምስት ፅኑ እስራት ያልበለጠ መሆኑ በወ/ህ/አ.194(1)(ለ) የተመለከተው መሰረታዊ መስፈርት መሟላቱን የሚያሳይ ሲሆን በአመልካቾች ላይ የተያዘ የቀደም ሪከርድ አለመኖሩና የእድሜያቸውን ሁኔታ እንዲሁም ማህበራዊ ተሳትፎአቸውና ለቤተሰባቸው የሚያደርጉት ድጋፍ ሲታይ አመልካቾች ከስህተታቸው እንዲማሩና በተመሳሳይ የወንጀል ድርጊት እንዳይሰማሩ አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ከዚህ በኋላ ባለው ህይወታቸው በመልካም ፀባይ እንዲመሩና ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲታቀቡ ይረዳል፤ያግዛል ብለን ስላመንን በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው የእስራት ቅጣት በሁለት አመት የፈተና ጊዜ ሊገደብ ይገባል በማለት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 289523 በቀን 15/10/2013 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነትና በ21/10 2013 ዓም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ (የገደብ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሳይጨምር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.272693 በቀን 14/11/2013 ዓ.ም ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላልተገኘ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 195 (2) (ለ) (2) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ገደብን አስመልክቶ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 289523 በ21/10/2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ክፍል እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ይህንን የውሳኔ ክፍል በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
3. በአመልካቾች ላይ የተጣለው የእስራት ቅጣት አፈፃፀሙ በሁለት አመት የፈተና ጊዜ የተገደበ ስለሆነ አመልካቾች በዚህ የፈተና ጊዜ ውስጥ በወንጀል ድርጊት ላለመሰማራት ግዴታ ገብተው ፈርመው ለገደቡ አፈፃፀም ዋስትና እየአንዳንዳቸው ብር 25,000.00(ሀያ አምስት ሺህ ብር) ሲያሲዙ ወይም ተመጣጣኙን ዋስትና ሲያቀርቡ ከእስር እንዲለቀቁና በዚህ ችሎት ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ታዟል፡፡

<u>መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡</u>

# የምርጫ ጉዳዮች

የሰ/መ/ቁ.207036

ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም.

ዳኞች-ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ - የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ - ተወካይ አቶ አውድሮ ታደሰ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡ - በሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ - ተወካይ አቶ ሰልሀዲን ተውፊቅ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ግንቦት 2 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 205809 በቀን 19/08/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው፡፡ ጉዳዩ የምርጫ ሂደትን መሰረት ያደረገ ሲሆን የአሁን ተጠሪን ጨምሮ በሀረሪ ክልል የሚገኙ የተለያዩ አካላት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ባቀረቡት አቤቱታ የተጀመረ ነው፡፡

1. ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የሀረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በቁጥር ሐጉ/183/4/13 በ27/7/2013፤ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ም/ቤት ጽ/ቤት በቁጥር ሐም/350/አጉ/2/13 በ27/07/13፤ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በቁጥር 1/9/15/2013 በ28/07/2013 እና የሐረሪ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት በቁጥር PP/14/H/111/2013 በ22/7/2013 በተፃፉ ደብዳቤዎች አቤቱታቸውን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አቅርበዋል፡፡
2. ባቀረቡት አቤቱታ ከክልሉ ውጭ የሚኖር የሐረሪ ሕዝብ የክልሉ ምክር ቤት አካል ለሆነው ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የመምረጥ መብት የሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሔደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ሰጥቷል፤ በዚህ መሰረትም አምስቱንም አገራዊ ምርጫዎች ከክልሉ ውጭ ያሉ የብሔረሰቡ አባላት መርጠዋል፤ በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በዚሁ መሰረት ሊፈጽም ይገባዋል በማለት ጥያቄያቸውን አቅርበዋል፡፡
3. የስራ አመራር ቦርዱ ጉዳዩንና የቀረቡትን ሰነዶች እንዲሁም ቀደም ሲል ተፈፀሙ የተባሉትን ምርጫዎች ከሕገ መንግስቱ አንፃር መርምሬያለሁ በማለት ሚያዚያ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ፡-

- በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት መሰረት በአንድ ክልል የመንግስት አወቃቀር ውስጥ የሚገኙ ም/ቤት አባላት መመረጥ የሚኖርባቸው በክልሉ ድምጽ መስጠት በሚችሉ ነዋሪዎች ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ሕገ መንግስቱ አንድ ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ ብሔረሰብ ለክልል ምክር ቤቶች አባላት ሲያስመርጥ ከክልሉ ውጭ ያሉ የብሔረሰቡ አባላት እንዲመርጡ የደነገገው፤ እንዲሁም ለዚህ ብሔረሰብ አባላት ለብቻው የተለየ አሰራር መተግበር የሚያስችል ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ የለም፡፡

- የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ከክልሉ ውጭ ነዋሪ በሆኑ የብሔረሰቡ አባላት ይመረጣል የሚለውን ውሳኔ የሚደግፍ የህገ መንግስት አንቀጽ ጠቅሶ መወሰኑም በውሳኔው ላይ እንደማይታይ ቦርዱ ተረድቷል፡፡
- በተጨማሪም ይህ መጋቢት 6/1987 የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰጠ የተባለው ውሳኔ አግባብ ያለመሆኑን ከሚያሳዩት ሁኔታዎች አንዱ በላዩ ላይ የም/ቤቱ ማህተም ያረፈበት አይደለም፡፡
- በሌላም በኩል በዚህ በመጋቢት 6/1987 የተወካዮች ም/ቤት ውሳኔ መሰረት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ አውጥቶ እንደ ውሳኔው ያለፉትን አምስት ምርጫዎች ሲያስፈጽም እንደነበር ያሳያል የተባለውም የቦርዱ መመሪያ ከቦርዱ ጽ/ቤት ማግኘት አልተቻለም፡፡
- ላለፉት 5 ምርጫዎች ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚመረጡ ተወካዮች ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰቡ አባላት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሲያስመርጥ ቆይቶ ቢሆንም፤ ቦርዱ ሲያከናውን በቆየው የምርጫ ማሻሻያ ወይም ሪፎርም እንደዚህ አይነት የሕገ መንግስትና የምርጫ ሕጉ መሰረት የሌላቸውን ልምዶችና አሰራሮች እንዳይቀጥሉ ማድረግን ዓላማው ያደረገ ነው፡፡
- ሕገ መንግስታዊ ድጋፍ ባይኖረውም ላለፉት 5 ምርጫዎች ይህ የሐረሪ ጉባኤ ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰቡ አባላት ሲመረጥ ቆይቷል የሚለውን (practice) ይዞ ለመቀጠል ቦርዱ ቢወስን፤ ሌሎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦች ከክልላቸው ውጭ ያሉት አባሎቻቸው በምርጫው እንዲሳተፉ ቢጠይቁ፤ ቦርዱ ልፈጽም አልችልም ቢል የቦርዱን በፍትሐዊነት እና በገለልተኝነት ምርጫን የማስተዳደሩ ጉዳይ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ያደርጋል፡፡
- በሕገ መንግስቱ ድጋፍ ያላቸውን አስቀድሞ ያሉ ልምዶችና አሰራሮች (practice) ብቻ ለመውሰድ ቦርዱ ይገደዳል፡፡
- በመሆኑም ከሕገ መንግስቱና ከሚተገብራቸው የምርጫ ህግና መመሪያዎች አንፃር ይህን ጥያቄ ተቀብሎ ለማስተናገድ አይቻልም በማለት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

4. በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ አመልካቹም መልስ እንዲሰጥ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አይኖረውም የሚል መቃወሚያን ጨምሮ በፍሬ ጉዳዩም የሰጠው ውሳኔ እንዲፀና ክርክሩን አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ፡- 1ኛ. የሐረሪ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የሕገ መንግስት ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ሥልጣን የለውም በሚል መልስ ሰጪው (የአሁን አመልካች) ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? 2ኛ. አይደለም ከተባለ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ የይግባኝ ባዩን (የአሁን ተጠሪ) ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. ቀዳሚውን ጭብጥ በተመለከተ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ይ/ባይ (የአሁን ተጠሪ) ቅሬታውን በቀጥታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሊያቀርብ የቻለው የስራ አመራር ቦርዱ የምርጫ ሂደትና ውጤትን በተመለከተ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ እና ለይግባኝ መነሻ የሆነው የቦርዱ ውሳኔም የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ነው በማለት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ይግባኙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረቡን በተመለከተ ያነሳው ተቃውሞ የሌለ ሲሆን ያነሳው የስልጣን መቃወሚያ የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ ከኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ጋር የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ ጉዳዩ ተስተናግዶ እልባት ሊያገኝ የሚገባው በፍርድ ቤት ሳይሆን በፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው በማለት ነው፡፡ ይሁንና የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ "የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ስልጣን አካል የፌዴራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ሕዝብ ነው፡፡ የክልል ከፍተኛ የስልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለወከለው ሕዝብ ነው፡፡" የሚል ሲሆን የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ደግሞ "የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ በሌላ በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል፡፡" የሚል ነው፡፡ ይህ የኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ አጠቃላይ መርህ ወይም መንፈስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በአገሪቱ ሕዝብ፣ የክልል ምክር ቤት ደግሞ በክልሉ ሕዝብ የሚመረጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ አጠቃላይ መርህ ልዩ ሁኔታዎች ሊኖሩት ይችላሉ ወይስ አይችልም የሚለው ሲታይ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ልዩ ሁኔታዎችን በአንቀጽ 17 ይደነግጋል፡፡ በተለይም አንቀጽ 17(3) በውጭ አገር የሚኖሩ

ኢትዮጵያውያን በአገሪቱ ውስጥ በሚደረግ ምርጫ ድምጽ መስጠትን የሚፈቅድ ነው፤ ይህም የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ ልዩ ሁኔታዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ መገንዘብ የሚያስችል ሲሆን የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌም በክልሉ ጉዳይ የዚህ አይነቱን ልዩ ሁኔታ የሚደነግግ ነው ከሚባል በቀር ይቃረናል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ቦርዱ ልዩ ሁኔታን የሚደነግገውን የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በአንቀጽ 17(3) ድንጋጌዎች አስመልክቶ የሕገ መንግስት ተቃርኖ ጥያቄ ያላነሳ ሆኖ ሳለ በተመሳሳይ አግባብ ልዩ ሁኔታን የሚደነግገውን የክልሉን ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ አስመልክቶ የሕገነመንግስት ተቃርኖ ጥያቄ ማንሳቱ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ድንጋጌ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ምክንያት ጉዳዩ የሕገ መንግስት ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም በሚል ቦርዱ ያቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

6. ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ በሰጠው ውሳኔም ለክርክሩ በአስረጅነት ከተጠቀሱት ሰነዶች አንዱ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት በ06/07/1987 ባደረገው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ያስተላለፈው ውሳኔ ሲሆን የዚህ ውሳኔ ተ.ቁ 2.1.2.2 ክርክሩን የሚደግፍ መሆኑን ቦርዱም ያመነበት ሲሆን ሰነዱን ቦርዱ ሳይቀበል የቀረው ምክር ቤቱ ውሳኔውን ሲያስተላልፍ በአስረጅነት የጠቀሰው የሕገ መንግስት ድንጋጌ የለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በእርግጥ ውሳኔው ተላለፈ የተባለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስቱ ከጸደቀ በኋላ ሲሆን በውሳኔው ላይ የተጠቀሰ የሕገ መንግስት ድንጋጌ የለም፡፡ ነገር ግን ክርክሩን የሚቃረን ግልጽ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ስለመኖሩ በቦርዱ በኩል የቀረበ አሳማኝ ምክንያት እስከሌለ በውሳኔው ላይ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ በአስረጅነት አለመጠቀሱ ብቻ ውሳኔውን ዋጋ የሚያሳጣው አይደለም፡፡ ሌላኛው የተጠቀሰው ሰነድ የክልሉ ሕገ መንግስት ሲሆን ድንጋጌዎቹ ተቀባይነት ያላገኙበት ምክንያት ስለመኖሩ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ያሰፈረው ትችት የለም፡፡ የክልሉ የቀድሞም ሆነ የተሻሻለው ሕገ መንግስት ስራ ላይ ከዋሉበት ጀምሮ በነበሩት ምርጫዎች ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላትን ሲመርጡ የነበረ መሆኑ በቦርዱ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ሲደረግ የነበረው ቦርዱ እንደሚከራከረው ካለምንም ህጋዊ መሰረት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት በ06/07/1987 ባደረገው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ባስተላለፈው ውሳኔ እና በዋነኛነት ደግሞ በክልሉ ሕገ መንግስት መሰረት ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ በሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔም ሆነ በክልሉ ሕገ መንግስት የሕገ መንግስት ተቃርኖ ጉዳይ ከየትኛውም አካል የተነሳ ተቃውሞም ሆነ የተላለፈ ተቃራኒ ውሳኔ የለም፡፡ ቦርዱ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እና የክልሉ ሕገ መንግስት እንዲሁም እነዚህን ሰነዶች መሰረት በማድረግ የሚከናወን የምርጫ

ሂደት ሕገ መንግስታዊ አይደለም የሚል ከሆነ ይህንን ማስለወጥ የሚገባው ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በሚያሰጠው ውሳኔ መሰረት ከሚሆን በቀር በራሱ በሚሰጠው ውሳኔ ሊሆን ስለማይገባ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ ጉድለት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው ብሏል፡፡ ይህን ተከትሎም ቦርዱ ያሳለፈውን ውሳኔ በመሻር የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት በ06/07/1987 ባደረገው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ባስተላለፈው ውሳኔ እና በክልሉ ሕገ መንግስት በተመለከተው መሰረት ቦርዱ ተገቢውን ሊፈጽም ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

7. የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘቱ ነው፡፡ አመልካች በቀን 02/09/2013 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም በሚል የአዋጁን አንቀጽ 17(1) ዝርዝር ድንጋጌዎች ባቀረብነው መልሳችን ላይ በማስረዳት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣኑ እንደማይመነጭለት ገልጸናል፤ ይህ ድንጋጌ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ ሲቪል ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በተለያየ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች እና በእስር ቤት የሚገኙ የመምረጥ መብታቸውን ያልታገዱ ዜጎች የሚሳተፉበት ልዩ ምርጫ ጣቢያ ቦርዱ እንዲያቋቁም ስልጣን የሚሰጥ ድንጋጌ እንጂ ከተጠሪ ጥያቄ ጋር ግንኙነት የለውም፤ ይህንንም በመልሳችን አስረድተን ሳለ አልተቃወመም በማለት ያለአግባብ ታልፎብናል፤ ሌላው የፍ/ቤቱን ስልጣን በተመለከተ ያቀረብነው ክርክር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ‹‹……የክልሉ ከፍተኛ የስልጣን አካል የክልሉ ም/ቤት ነው ተጠሪነቱም ለወከለው ህዝብ ነው›› የሚል በመሆኑና የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) የደነገገው ሙሉ ለሙሉ ይህን ድንጋጌ የሚቃረን ስለሆነ ይህ አይነት ጥሰት ሲፈጠር አይቶ የማረም ስልጣን የፌዴሬሽን ም/ቤት እንጂ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አይደለም የሚል ነው፤ ፍ/ቤቱም የሕገ መንግስት ትርጉም ውስጥ በመግባት አንቀጾቹን ለማስታረቅ በመሞከር ያለስልጣኑ የሕገ መንግስት ትርጉም በመስጠት ክርክራችንን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤ አንድ ክልል የሚያወጣው ሕገ መንግስት በምንም አይነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ላይ በግልጽ የተቀመጡትን የሚቃረን ሊሆን አይችልም፤ የሐረሪ ክልል ሁለቱም ም/ቤቶች በኢ/ፌ/ዲ/ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) መሰረት ሊመረጡ የሚገባው በክልሉ ነዋሪዎች እንጂ የክልሉ ሕገ መንግስት ከዚህ አንቀጽ ጋር የሚቃረን አንቀጽ በመደንገግ የአንዱ ም/ቤት በክልል ነዋሪዎች ሌላው ም/ቤት ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰብ አባላት ጭምር እንዲመረጡ መደንገጉና ይህንንም ፍ/ቤቱ ተቀብሎ ያለስልጣኑ በመተርጎም የህግ ጥሰት ፈጽሟል፡፡ በተጨማሪም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የክልሉ ም/ቤት በክልሉ ነዋሪዎች እንዲመረጥ የሚያደርግበት መርህን non territorial ሳይሆን territorial መርህን የተከተለ መሆኑን በዝርዝር አስረድተን ፍ/ቤቱ ያቀረብነውን ክርክር ምንም ሳይል አልፎታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 51(15) ምርጫን የሚመለከቱ ህጎች የማውጣት ስልጣን የፌደራል መንግስት ብቻ መሆኑን አንቀጽ 55(1) (መ) ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ምርጫን በተመለከተ ህግ የማውጣት ስልጣን መስጠቱን፣ ከክልል ም/ቤት በግልጽ ከምርጫ ጋር የተያያዘ ሕግ የማውጣት ስልጣን በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 13(2) ከአካባቢ ምርጫ ጋር በተያያዘ ስልጣን በመስጠቱ የክልሉ ሕገ መንግስት ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ወጥቶ በፌ/መ/ተወካዮች ም/ቤት ስልጣን ውስጥ በመግባት የደነገገው ድንጋጌ ከፍተኛ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም በሚል በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) አንፃር ያቀረብነውን ክርክር፤ እንዲሁም የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትን አንቀጽ 50(3) የሚቃረን በመሆኑ በክልሉ ሕ ገመንግስት ላይ ባሉ ድንጋጌዎች ለመፈፀም የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ መርምሮ በሚሰጠውና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚሰጠው ውሳኔ መሆኑን በማንሳት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የለውም በሚል ያቀረብነው የህግ ክርክር ውድቅ መደረጉ አላግባብ በመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት ያለበት ነው ተብሎ እንዲሻርልን፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሔረሰቦች የሚያደርገው ጥበቃ 'territorial' በሆነ መርህ እንጂ በ'non territorial' ያለመሆኑን በዝርዝር አስረድተን ፍ/ቤቱ ያቀረብነውን ክርክር ምንም ሳይል አልፎታል ስለሆነም የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን እንዲመረምርና ከዚህ አንፃር ውሳኔው እንዲሻርልን፡፡ እንዲሁም የምርጫ ሕግ የማውጣቱ ስልጣን የፌዴራል መንግስትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ሆኖ ሳለ የክልል ምክር ቤት የዞንና የወረዳ፣ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ የቀበሌ ም/ቤቶች ቁጥር (ወይም ወንበር) ከመወሰን ውጭ ሌላ ስልጣን እንደሌላቸው ያቀረብነውን ክርክር ሳይታይ መታለፉ አግባብ ባለመሆኑ ሰበር ችሎቱ ክርክራችንን ተቀብሎ የክልሉ መንግስት ያወጣው ሕገ መንግስት የሌላን የመንግስት አካል ስልጣን የሚጋፋ ያለስልጣኑ ሕግ ያወጣ መሆኑን በመገንዘብ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካች የሰጠው (ያሳለፈው) ውሳኔ ህጋዊና በህገ መንግስቱ ትክክለኛ ትርጉም ላይ የተመረኮዘ መሆኑን በመረዳት ከዚህ በተቃራኒ የበታች ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፍ/ቤቱ ውድቅ እንዲያደርግልን በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

8. ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ለአሁን አመልካች ቀርቦ የነበረው ጥያቄ ከምርጫ ድምጽ አሰጣጥ እና ውጤት ቆጠራ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከዚህ ውጭ በሆነ ጉዳይ ላይ ሆኖ እያለ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የቻለበት የህግ አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) አኳያ መመርመር ያለበት በመሆኑ፤ እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ከመታወጁ በፊት በሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ምክር ቤት ተሰጥቷል የተባለው ውሳኔ ህገ መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ተፈፃሚ የተደረገበት የህግ አግባብ እና ተያያዥ

የህጋዊነት ጉዳዮች ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 9 እና 50 ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

9. ተጠሪ በቀን 09/09/2013 ዓ.ም ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) ድንጋጌ ለስር ፍ/ቤት ስልጣን የሚሰጥ ድንጋጌ ከመሆኑም በላይ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ የዚሁ ድንጋጌውን መስፈርት ጭምር የሚያሟላ ነው፡፡ መራጮችን የመመዝገብና ካርድ የመስጠት ተግባራት የምርጫ ሂደቶች በመሆናቸው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ቦርዱ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎችን አስመልክቶ በይግባኝ ደረጃ ለማየት ስልጣን የተሰጠው አካል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት መሆኑን የአዋጁ ድንጋጌ በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ ጉዳዩ በስር ጠ/ፍ/ቤት ታይቶ መወሰኑ አግባብ ነው፡፡ አመልካች በክልሉ የሚያካሂደውን ምርጫ በገለልተኝነት ማስፈጸም ሲገባው ሌላ አዲስ ልዩ ምርጫ ጣቢያ እንዲያቋቁም የተጠየቀ በማስመሰል ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17 መሰረት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 17 ነው በማለት ለተለያየ አላማ የሚያገለግሉ አዋጆችን በማምታታትና በማዘባረቅ ያቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው ቦርዱ እንጂ ፍ/ቤት አይደለም ከሚል በቀር ጉዳዩ የምርጫ ሂደትን የማይመለከት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ያቀረበው ክርክር ባለመኖሩ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣንን አስመልክቶ ጉዳዩ የምርጫ ሂደትን የሚመለከት አይደለም ሲል ያቀረበው ክርክር የለም በሚል መተቸቱ አግባብነት ያለው ነው፡፡ አመልካች የስረ ነገር ስልጣን ክርክር ነጥብ አቅርቦ ቢሆን እንኳን በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) መሰረት በቦርዱ ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠበት የምርጫ ሂደት ላይ ጠ/ፍ/ቤቱ ከማየት የሚከለክለው ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪም አከራካሪው ጉዳይ ከክልሉ ውጭ የሚገኙ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት የፌደራል ተወካዮቻቸውን ጨምሮ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላትን በመራጭነት የመመዝገብና ካርድ የመውሰድ ተግባራት ከድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ በፊት የሚገኝ የምርጫ ሂደት እንጂ በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 155(4) ድንጋጌ የተመለከተውን የድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ የሚመለከት ክርክር ባለመሆኑ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም አከራካሪ የሆነው ጉዳይ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት መጋቢት 6/1987 በተወሰነው እና በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 እና 50(2) በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት በቦርዱ በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ በተቋቋሙ ምርጫ ጣቢያዎች አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ ከተሞች የሚገኙ ሐረሪዎች የፌደራል ተወካያቸውን ጨምሮ የሐረሪ ብሄራዊ ጉባኤ አባላትን በመራጭነት እንዲመርጡ የመመዝገብና የመራጭነት ካርድ መስጠት የምርጫ ሂደት እንጂ ይኸው ሀገራዊ ምርጫ በአሁን ደረጃ የሚገኝበት ሂደት ድምጽ አሰጣጥ ሂደት ገና ያልደረሰ በመሆኑ የድምጽ ቆጠራና ውጤት አግባብነት ያለው ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አግባብ ነው፡፡ በሌላም በኩል ግልጽ የህገ መንግስት ድንጋጌዎች ትርጉም የማያሻቸው እና እነዚሁኑ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ማድረግ ህገ መንግስታዊ ግዴታ እንጂ የህገ መንግስት ትርጉም መስጠት አይደለም፤ የሐረሪ

ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) ድንጋጌ የሚመለከተው የክልሉን ም/ቤት የሚያዋቅሩት ሁለት ጉባኤዎች መካከል አንደኛው ስለሆነው የሐረሪ ብሄራዊ ጉባኤ አባላት አመራረጥ ሲሆን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ደግሞ የሚያመለክተው የክልል ም/ቤቶች ተጠሪነትን ነው፡፡ ስለዚህ ድንጋጌዎቹ የሚያወሱት ሁለት ስለተለያዩ አካላት የሚመለከቱ እና የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚሸፍኑ በመሆናቸው ግንኙነት የሌላቸውና ግልጽ በመሆናቸው ሊቃረኑ የማይችሉ፣ ግልጽ፣ የማያሻሙና ትርጉም የማያሻቸው በመሆኑ የአመልካች ተቃውሞ ውድቅ መደረጉ አግባብ ነው፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እና የክልሉ ህገ መንግስት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገ ነው፤ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውሳኔ ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣምና የክልል ህገ መንግስት አካል ሆኖ መጽደቁ በፌደራሉም ሆነ በክልል ህገ መንግስት ድጋፍ ያለው ስለመሆኑ አስረጅዎች ናቸው፡፡ አመልካች መጋቢት 6/1987 በተካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ህገ መንግስቱ ኦፊሺያሊ ተፈጻሚ እንዲሆን ከታወጀበት ነሐሴ 15/1987 በፊት የሆነ በማስመሰል የውሳኔው ተፈጻሚነት አጠራጣሪ ለማድረግ የሚያቀርባቸው መከራከሪያዎች የህግ መሰረት የሌላቸው ናቸው ምክንያቱም ም/ቤቱ ውሳኔውን ካስተላለፈበት በፊት ህዳር 29/1987 ተመክሮና ተዘክሮ በህገ መንግስታዊ ጉባኤ ፀድቆ ስለነበር ም/ቤቱ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ ውሳኔ መስጠቱና በ1988 አዲስ ለሚመሰረተው ም/ቤት እስከሚያስረክብበት ጊዜ ድረስ ህገ መንግስቱም ፀድቆም ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜያት ጭምር በህገ መንግስቱ መሰረት ስራዎችን ሲያከናውን እንደነበር አስረጅ ነው፡፡ ከክልሉ ውጭ የሚገኙ የብሔሩ አባላት የፌደራል ተወካያቸውን ጨምሮ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ላይ የሚሰጡት ድምጽ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በተጨባጭ ለማስከበር ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ጋር በሚጣጣም መልኩ የተወሰነ አዎንታዊ እርምጃ ነው፡፡ የሐረሪን ክልል ም/ቤት አወቃቀር እና አወካከል የውስጥ ዲሞክራሲ አሰራር አስመልክቶ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አጥንቶ እንዲያቀርብ የተወከለው ኮሚቴ ተሞክሮ የተወሰደባቸው ሀገራት የአናሳ ቡድን እና ማህበረሰብ መብት መሰረት የሆኑ የአለም አቀፍ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ሰነዶች የሀገሪቱ ህግ አካል ከመሆናቸውም በላይ የአናሳ መብቶችን የሚደግፉ መሆናቸው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ውሳኔም የክልሉን ህገ መንግስት አንቀጽ 49 እና 50(2) ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ጋር በማጣጣም የተፈጸሙ ሆኖ ሳለ ቦርዱ ይህን ሳያገናዝብ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ድጋፍ እንደሌለው አድርጎ መውሰዱ መሰረታዊ ስህተት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 50(3) ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ቦርዱ የሚረዳው ‹‹የክልል ም/ቤት ሊመረጥ የሚችለው በክልል ውስጥ በሚኖሩ ህዝቦች ብቻ›› እንደሆነ ቦርዱ አመላክቷል፡፡ በቦርዱ የተጠቀሰው ይህ ድንጋጌ የማያሻማና ግልጽ ድንጋጌ በመሆኑ ትርጉም የማያሻው ሲሆን በትርጉም ሰበብ በድንጋጌው ባልተመለከተው አግባብ ስለ ክልል ም/ቤት ተጠሪነት የሚያወሳ ድንጋጌን የክልል ም/ቤት አመራረጥ ያወሳል ብሎ ህገ

መንግስታዊ ላልሆነው የቦርዱ የተሳሳተ አረዳድ ላይ የተመሰረተው አቋም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውና ተያያዥ ያልሆነ ድንጋጌ ጠቅሶ ያቀረበው ክርክር ከፍተኛ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ቦርዱ የክልል ም/ቤትን ተጠሪነትን የሚመለከተውን የህገ መንግስት ድንጋጌ የክልል ም/ቤት አመራረጥ እንደሆነ አድርጎ በመጥቀስ የኢትዮጵያ ምርጫ non territorial ሳይሆን territorial ነው የሚለው አተረጓጎም የተሳሳተ ነው፡፡ የክልል ም/ቤት አወቃቀርና አወካከል እንዲሁም የም/ቤት አባላት ቁጥር መወሰን የምርጫ ህግ ማውጣት ባለመሆኑ ቦርዱ በዚህ ረገድ ከሃላፊነት ተግባሩ በመሸሽ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ቦርዱ ከስልጣኑ በመተላለፍ የወሰነበት አግባብ ህግን ያልተከተለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነው፡፡ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቀን 06 መጋቢት 1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ የተሰጠው ውሳኔ ተመሳሳይ ስልጣን ባለው አካል ወይም ሌላ በህግ አግባብ ውሳኔው የተለወጠ ወይም የተሻረ አለመሆኑ እየታወቀ በበላይ አካል የተሰጠ ውሳኔ ለማረም ስልጣን ሳይኖረው ላለመፈጸም የያዘው አቋም የህግ የበላይነትን የሚጻረር ነው፡፡ የክልል መንግስትና የፌደራል መንግስታት መካከል መከባበር ግዴታ እንደመሆኑ የፌደራል አስፈጻሚ መስሪያ ቤት መካከል አንዱ የሆነው ቦርዱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ አንቀጽ 50(8) መሰረት ለክልሎች የተሰጠ ስልጣን በፌደራል መንግስት መከበር አለበት የሚለውን ድንጋጌ በሚጻረር መልኩ የምርጫ ሂደቱን በክልሉ ህገ መንግስት መሰረት ያለመምራቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስቱን አንቀጽ 50(8) የተላለፈ በመሆኑ እና የተጠሪ ጥያቄ የህግ መሰረት ያላቸው መሰረታዊ መብቶች እንጂ በስመ ሪፎርም የሚጨፈለቁ ህገ መንግስታዊ መሰረት የላቸውም በሚል ተራ ውሳኔ የሚገደቡ ባለመሆናቸው የቦርዱን ውሳኔ በመሻር የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ አግባብ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ተከታታይ አምስት አገራዊ ምርጫ ከክልሉ ውጭ የሚገኙ የሐረሪ ብሄረሰብ አባላት የፌደራል ወኪላቸውን ጨምሮ የሐረሪ ጉባኤ አባላትን መምረጣቸው የህግ ድጋፍ ሳይኖረው እንዲሁ ሲፈጸም የነበረ ተግባር ሳይሆን በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ ነው፤ ሆኖም ይህን ውሳኔ የሚቀይር ወይም የሚያስቀይር ተቃራኒ ውሳኔ ወይም ህግ ሳይኖር ምርጫ ቦርዱ ስልጣኑን በማለፍ በራሱ አተረጓጎም የማይቃረኑትን ይቃረናሉ ብሎ ትርጉም መስጠቱ በፌዴሬሽን ም/ቤት ስራ መግባት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ቦርዱ ግዴታውን እንዲወጣ የሰጠው ውሳኔ አግባብ እና ፍትሀዊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክሩን በማጠናከር ግንቦት 11/2013 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

10. የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት ክርክራቸውን በቃል ሰምቷል፡፡ የቃል ክርክራቸው ከመቅረፀ ድምፅ ተገልብጦ የመዝገቡ አካል እንዲሆንም አድርጓል፡፡ ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የተወካዮች

ምክር ቤት 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ከኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ በማድረግ፤ እንዲሁም የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ምርጫ አፈፃፀም መመሪያን በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡ አጠቃላይ ጉዳዩንም የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡

11. እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ቅሬታ እንዲሁም በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ ቀዳሚ ማጠንጠኛ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን የለውም በሚል የቀረበው ነው፡፡ ከዳኝነት ስልጣን ጋር ተያይዞ የቀረበው ይኸው ክርክር በሁለት መልክ የቀረበ ነው፡፡ አንደኛው የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም በሚል የአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) በዋቢነት ተጠቅሶ የቀረበው እና ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአጣሪ ችሎት የተጠቀሰው ለአሁን አመልካች ቀርቦ የነበረው ጥያቄ ከምርጫ ድምጽ አሰጣጥ እና ውጤት ቆጠራ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከዚህ ውጭ በሆነ ጉዳይ ላይ ስለሆነ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሊቀርብ የቻለበት የህግ አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 155(4) አኳያ ይመርመር መባሉ ነው፡፡ ሁለተኛው ከስልጣን ጋር የተያያዘ የክርክር ዘውግ የህገ መንግስት ትርጉም አሰጣጥን መሰረት ያደረገ ሲሆን የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 50(2) የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትን አንቀጽ 50(3) የሚቃረን በመሆኑ ጉዳዩ በሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ተመርምሮ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን በማንሳት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የለውም በሚል የቀረበ ክርክር ነው፡፡

12. ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ከዳኝነት ስልጣን ጋር የተያያዙ ክርክሮች ለመወሰን በምርጫ ነክ አዋጆች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤቶች ይግባኝ የሚቀርብበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች፤ ከህገ መንግስት ጋር በተያያዘ በሚነሱ ክርክሮች ላይ ፍርድ ቤቶች ስለሚኖራቸው ስልጣን፤ ስለ ህገ መንግስታዊነት ግምት፤ እንዲሁም በዳኝነት በተያዘ ጉዳይ ላይ የህገ መንግስት ትርጉም አስፈላጊነትን ስለመወሰን በሀገራችን የተዘረጋውን ስርዓትና የህጉን ማእቀፍ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

13. የምርጫ ቦርድ የመጨረሻ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ይግባኝ የሚሉበትና ውሳኔው እንዲሻር ማመልከቻ የሚቀርብበት ሂደት በህጉ ተመልክቷል፡፡ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17 ስለ ይግባኝ ስልጣን የሚደነግግ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 1 ስር እንደተመለከተው የስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጣቸው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የምርጫ ሂደትና ውጤትን በተመለከተ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በተመሳሳይ ቦርዱ በስነ ምግባር ጥሰቶች በሚሰጠው

አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ እንዲሁም በድምጽ ቆጠራና ውጤት በሚነሱ ክርክሮች ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርበው ይግባኝ በመለያየት ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 149 ስር እንደተመለከተው ቦርዱ የምርጫ ስነ ምግባር ጥሰቶችን ተከትሎ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአንቀጽ 155(4) ስር እንደተመለከተው ቦርዱ በድምፅ ቆጠራ እና ውጤት ላይ ለሚነሱ ክርክሮች በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ፍርድ ቤቶች ቦርዱ የተቋቋመበትን ዓላማ ማሳካቱና እና በህጉ አግባብ ጉዳዩን መወሰኑን እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በይዘታቸውም ምን አይነት ጉዳዮች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ምን አይነት ጉዳዮች ደግሞ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በተያዘው መዝገብ እያከራከረ ያለውና ቦርዱ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ከክልሉ ውጭ የሚገኙ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላትን ለመምረጥ እንዲችሉ ተገቢው ምርጫ ነክ ሥራ ምርጫን በሚያስተዳድረው ቦርድ እንዲፈፀም የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የምርጫ ስነ ምግባርን በመጣስ የሚተላለፍ አስተዳደራዊ ውሳኔ አይደለም፡፡ እንዲሁም በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 155(4) ድንጋጌ የተመለከተውን የድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ የሚመለከት ክርክር አይደለም፡፡ ይልቁንም በቦርዱ የምርጫ ሂደትን አስመልክቶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ (final decision with regard to electoral process) ሊባል የሚችልና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) ስር የሚያርፍ ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ደግሞ ይግባኙ ሊቀርብ የሚችለው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

14. በሌላ በኩል ከህገ መንግስት ነክ ክርክሮች አወሳሰንና የህገ መንግስት ትርጉም አስፈላጊነትን መወሰንን በተመለከተ የህጉን ማእቀፍ እንመልከት፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 ከጥር 12/2013 ዓ.ም ጀምሮ በፀናው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ተተክቷል፡፡ በሁለቱም አዋጆች እንደተመለከተው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሕገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡ (እንደ ቅደም ተከተላቸው የአዋጆቹን አንቀጽ 3(1) እና 3(1)(ሀ) ይመለከቷል፡፡) በተለይም አዲሱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 3(2) የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9(2) መሰረት የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የህገ መንግስት ትርጉምን በማይጠይቁ ህገ መንግስቱን መሰረት አድርገው የሚነሱ ክርክሮችን ተመልክተው ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሊሰጡ አይገባም የሚባልበት የህግ ምክንያት አይኖርም፡፡

15. በሌላም በኩል በፍርድ ቤት በተያዙ ጉዳዮች የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጥያቄው ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት አማካኝነት ለህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሊቀርብ

እንደሚችል የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁጥር 798/2005 አንቀጽ 3(2)(ሀ) እና አንቀጽ 4(1) ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የትርጉም ጥያቄ ለአጣሪ ጉባኤው የሚልከው ጉዳዩን ለመወሰን ሕገ መንግስቱን መተርጎም ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን ስለመሆኑ በአንቀጽ 4(2) ስር በግልጽ ተመልክቷል (….When *it believes* that the interpretation of the constitution is necessary to decide the case)፡፡ በመሆኑም ግልጽ የሆኑ የህገ መንግስት ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ በህገ መንግስት ክርክሮች ላይ ውሳኔ መስጠት እንዲሁም ትርጉም የማያሻቸው መሆኑን በፍርድ መወሰን የፍርድ ቤቶች ተግባር ሊሆን እንደሚገባ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ህጎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

16. ስለሆነም አመልካች የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የምርጫ አዋጆችን እንዲሁም የህገ መንግስት ትርጉም አስፈላጊነትን በማንሳት ያቀረበው ክርክር ከፍ ሲል በዝርዝር ያመለከትነውን የህጉን ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

17. ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ አመልካች በክርክሩ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ብሔረሰቦች የሚያደርገው ጥበቃ 'territorial' በሆነ መርህ እንጂ በ'non territorial' ያለመሆኑን፤ የምርጫ ሕግ የማውጣቱ ስልጣን የፌዴራል መንግስትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ መሆኑን፤ የክልሉ መንግስት ያወጣው ሕገ መንግስት የፌዴራሉን ህግ አውጪ የመንግስት አካል ስልጣን የሚጋፋና ያለስልጣኑ መሆኑ ታይቶ የይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ ተሽሮ ቦርዱ የሰጠው (ያሳለፈው) ውሳኔ እንዲፀና ተከራክሯል፡፡ ከዚህ ክርክሩ ሌላ ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ባሳለፈው ውሳኔም የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ከክልሉ ውጭ ነዋሪ በሆኑ የብሔረሰቡ አባላት ይመረጣል በማለት ያሳለፈው ውሳኔ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደማይገባ መወሰኑን፤ ላለፉት 5 ምርጫዎች ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚመረጡ ተወካዮች ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰቡ አባላት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ አውጥቶ ሲያስመርጥ ቆይቶ ቢሆንም ቦርዱ ሲያከናውን በቆየው የምርጫ ማሻሻያ ወይም ሪፎርም እንደዚህ አይነት ልምዶችና አሰራሮች እንዳይቀጥሉ ማድረግን ዓላማው ያደረገ መሆኑን መወሰኑን፤ እንዲሁም በምክር ቤቱ ውሳኔ እና በክልሉ ህገ መንግስት መሰረት ላለፉት 5 ምርጫዎች የሐረሪ ጉባኤ ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰቡ አባላት ሲመረጥ ቆይቷል የሚለውን (practice) ይዞ ለመቀጠል ቦርዱ ሊገደድ እንደማይገባ መወሰኑን የሚያሳይ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ የዚህን ክርክርና ውሳኔ ተገቢነት ግራ ቀኙ ከሚያቀርቡት ሙግት፤ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እና የክልል ህገ መንግስታት ሊኖራቸው ከሚገባው የህገመንግስታዊነት ግምት፤ እንዲሁም ህገ መንግስታዊ አይደሉምና ተግባራዊ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ ሊወሰን የሚችልበትን የህግ ስርዓት ጋር መመርመር ይገባል፡፡

18. እንደሚታወቀው የሐረሪ ክልል ከፍተኛ የህግ አውጪ አካል የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለወከለው ህዝብ መሆኑ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 46(1) ተመልክቷል፡፡ ይህ የክልሉ ምክር ቤት የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ እና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚባሉ ሁለት ጉባኤዎች እንደሚኖሩት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 49(1) ተመልክቷል፡፡ ይኸው አደረጃጀት የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ያሳለፈው ውሳኔ የክልሉ ህገ መንግስት አካል ተደርጎ የተፈጠረ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት ሐረሪዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ በክልሉ ነዋሪዎች የሚመረጡ ሲሆን የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በሐረሪዎች ብቻ የሚመረጡ መሆኑን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ያሳያል፡፡ በዚህ መልኩ የተዋቀረው የክልሉ ምክር ቤት 36 አባላት ያሉት ሲሆን 22ቱ የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት እንዲሁም 14ቱ ደግሞ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ የሕዝብ ተወካዮች ጉባኤን እና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር በሕገ መንግስቱ ተዘርዝሯል፡፡ የሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ምክር ቤት በ102ኛ ጉባኤው ካደረገው ውይይትና ከደረሰበት ውሳኔ እንዲሁም በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 59 ከተደነገገው መገንዘብ እንደሚቻለው የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ቀዳሚ ስልጣንና ተግባር የሐረሪዎችን እንደ ብሔረሰብ የመቀጠል ሁኔታ ማረጋገጥ የሚያስችሉ የቋንቋ፣ ባህል፣ ቅርስ እና የማንነት ጥበቃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ 14 አባላት ምርጫ ውስጥ ብቻ እንዲሳተፉ የመወሰኑ መሰረታዊ ምክንያትም ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎች ከክልላቸው እና ብሔራዊ ማንነታቸው ጋር ያላቸውን ቁርኝት ለማጥበቅና ለማረጋገጥ እንዲያስችላቸው እንዲሁም ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የተሰጠውን ህጋዊ ኃላፊነት ዳር ለማድረስ ስለመሆኑም መገንዘብ ይቻላል፡፡

19. ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ በሽግግር መንግስቱ የተወካዮች ምክር ቤት በ102ኛ ጉባኤው የተደረሰበት ውሳኔ ህገ መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለ በኋላም ተፈጻሚነት የሚኖረውና የህገ መንግስቱን መርሆች መሰረት በማድረግ መወሰኑን ምክር ቤቱ ከያዘው ቃለ ጉባኤ መገንዘብ ችለናል፡፡ ለዚህም ነው የፌዴራሉን ህገ መንግስት ተከትሎ በወጣው የክልሉ ህገ መንግስት ይኸው የተመለከተው፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአፅዳቂ ጉባኤው ህዳር 29/1987 ዓ.ም ተቀባይነት አግኝቶ ከፀደቀ በኋላ የተሰጠው ይኸው የተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔና በክልሉ ሕገ መንግስት ግልጽ ድንጋጌዎች የተካተቱት መርሆች የፌዴራሉ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርሆዎችን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የፌዴራሉ ህገመንግስት አንቀፅ 5(1)፣3፣39 (2)፣ 91(1) እና (2) ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ማንነታቸው ተጠብቆ መቀጠል የሚችሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ለሚያስችሉ የቋንቋ፣ ባህል፣ ቅርስ እና የማንነት ጥበቃ ያደርጋል፡፡ በተለይ በሕዝብ ቁጥር አነስተኛነት ምክንያት ማንነታቸው የሚገለፅበት የቋንቋ፣ ባህልና ቅርስ እንዳይጠፉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ሀገሪቱ

የተቀበለቻቸው አለማቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት እንዲሁም የማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ስምምነት ቀዳሚ(የመጀመሪያ) ድንጋጌዎች ይህን የሚቀበሉ ናቸው፡፡ በተለይ የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 1 እና 27 እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ በብሔር፣ በጎሳ፣ በሐይማኖት ወይም በቋንቋ አናሳ የሆኑ ቡድኖች አባላትን መብቶች አጠባበቅ አስመልክቶ በውሳኔ ቁጥር 47/135 ዲሴምበር 18/1992 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም በዴሞክራሲና ዕድገት የበለፀጉ ሃገራት ያላቸው የዳበረ ልምድ የሚያሳየው ለእነዚህ መብቶች ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ነው፡፡ የሐረሪ ብሔረሰብ የዚህ ጥበቃ ተጠቃሚ የሆነ ሲሆን ሌሎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ብሔረሰቦችም በተመሳሳይ የማንነታቸው መግለጫ የሆኑ የቋንቋ፣ ባህልና ቅርስ ጥበቃ እንዲኖራቸው ማድረግ ህገ መንግስታዊ ነው፡፡ የሐረሪ ክልል ምክር ቤት በህግ በልዩ ሁኔታ እንዲዋቀር መደረጉና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤን ማቋቋም እንዲሁም በልዩ ሁኔታ አባላቱ እንደሚመረጡ መደረጉ ሁሉ ይህን ጥበቃ ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

20. ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ከሰጠው ውሳኔ እና እስከዚህ ፍርድ ቤት ካቀረበው ክርክር የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት በ06/07/1987 ባደረገው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ያስተላለፈው ውሳኔ እና የክልሉ ህገመንግስት ድንጋጌዎች የተጠሪን ክርክር የሚደግፉ መሆኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ መገንዘቡን ተረድተናል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተገለፀው የምክር ቤቱ ውሳኔ ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይገባም፤ ላለፉት 5 ምርጫዎች ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ የሚመረጡ ተወካዮች ከክልሉ ውጭ ባሉ የብሔረሰቡ አባላት ሲያስመርጥ የቆየ ቢሆንም እንደዚህ አይነት ልምዶችና አሰራሮች እንዳይቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል፤ መሰል ልምዶችን (practice) ይዞ ለመቀጠል ቦርዱ አይገደድም በማለት ወስኗል፡፡ ይኸው ውሳኔ ከህገ መንግስት ትርጉም ስርዓት ጋር ተያይዞ እንደሚከተለው ሊመረመር የሚገባ ነው፡፡

21. ከህገ መንግስት ትርጉም ጋር በተያያዘም የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከር እና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 9 ስር በግልጽ እንደተመለከተው የአንድ ህግ ህገ መንግስታዊነት ተጣርቶ ግምቱን የሚያፈርስ ሌላ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ የወጣው ህግ ህገ መንግስታዊ ነው ተብሎ እንደሚገመት ይደነግጋል፡፡ የህጉን ህገ-መንግስታዊነት አጣርቶ ትርጉም ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ደግሞ ምክር ቤቱ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 4(1) እና በፌዴራሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 62(1) ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም በእኛችን ባለው ጉዳይ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ባካሄደው 102ኛ መደበኛ ስብሰባ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ከክልሉ ውጭ ነዋሪ በሆኑ የብሔረሰቡ አባላት ይመረጣል በሚል ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ህገ መንግስት ተያያዥ ድንጋጌዎች የፌዴራሉን ህገ መንግስት መሰረት ያደረጉ አይደለም፤ ህገ

መንግስታዊ ድጋፍም የላቸውም፤ እንዲህ አይነት አሰራር እንዳይቀጥል አደርጋለሁ በማለት በራሱ ውሳኔ ማሳለፉ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የህጉን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም። የምክር ቤቱ ውሳኔና የክልሉ ህገ መንግስት ድንጋጌ ህገ መንግስታዊ አለመሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ተጣርቶ ውሳኔ እስካልተሰጠበት ድረስ ህገ መንግስታዊ ነው ተብሎ ይገመታል።

22. ስለሆነም የአሁን አመልካች የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ እና የክልሉ ሕገ መንግስት እንዲሁም እነዚህን ሰነዶች መሰረት በማድረግ የሚከናወን የምርጫ ሂደት ሕገ መንግስታዊ አይደለም የሚል ከሆነ ይህንን ማስለወጥ የሚገባው ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በሚያሰጠው ውሳኔ መሰረት ከሚሆን በቀር በራሱ በሚሰጠው ውሳኔ ሊሆን ስለማይገባ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ ጉድለት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው። ውሳኔው ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘነውም።

23. በአጠቃላይ የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ 14 የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት እንደሚኖሩት እና አባላቱ በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጪ በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች እና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት የሚመረጡ ስለመሆኑ በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49(3) እና 50(2) የተደነገገ በመሆኑ፤ ይኸው አሰራር በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ የተደገፈ በመሆኑ፤ የክልሉ ህገ መንግስትም ሆነ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሳኔ ተግባራዊ መደረግና ሕገ መንግስታዊነት አስመልክቶ ህገ መንግስቱን ለመተርጎም ስልጣን ባለው አካል ፊት የቀረበ ተቃውሞ ባለመኖሩ፤ ከብሔሩ አባላት ቁጥር አናሳነት እና ሊደረግለት ከሚገባው ጥበቃ አንፃር ታይቶ ከክልሉ ውጪ የሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤን እንዲመርጡ መደረጉ ፀንቶ የኖረ ህጋዊ አሰራር በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረበለትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ አይደለም ብለናል። ይኸው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መታረሙም በአግባቡ ነው ብለናል። ተከታዩም ተወስኗል።

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 205809 በቀን 19/08/2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ የአመልካች የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት አጽንተናል።
2. ከሐረሪ ክልል ውጪ በሌሎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ ተወላጆች ከክልሉ ምክር ቤት ሁለት ጉባኤዎች መካከል አንዱ ለሆነው እና የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ለሚካተቱበት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላትን የመምረጥ መብት አስቀድሞ በህግ

በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ ከክልሉ የመንግስት አካላት የቀረበለትን ጥያቄ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርዱ ውድቅ በማድረግ ያሳለፈው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መሻሩ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. በክልሉ ሕገ መንግስት በተደነገገው እና የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 6/1987 ዓ.ም ባደረገው 102ኛ መደበኛ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ ሊፈጽም ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ በዚሁ መሰረት ቦርዱ ተገቢውን ይፈፅም፡፡
4. የሰበር አጣሪ ችሎቱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዳይፈፀም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ ግንቦት 4 ቀን 2013 ዓ.ም ያሳለፈው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ምርጫውን ለሚያስፈፅመው የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም ከስር ጀምሮ አቤቱታ ላቀረቡ አካላት ሁሉ ይተላለፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
7. ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የኢትዮጵያ ሽግግር መንግስት የተወካዮች ምክር ቤት 102ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በመጣበት መልኩ ለምክር ቤቱ ይመለስ፡፡
8. ውሳኔው ዛሬ ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 228650

ሀምሌ 6 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- የደ/ብ/ብ/ክ/መንግስት ብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና ፓርቲ)፡- ጠበቃ ካሌብ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1ኛ. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ፡- ተወካይ ወንጌል አባተ ቀረቡ

2ኛ. የቁጫ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቁህዴፓ)፡- ጠበቃ ጳውሎስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 06/10/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 282120 በ19/09/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቀ ነው፡፡ ጉዳዩ ከዳግም ምርጫ ጋር የተያያዘ ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁን አመልካች 1ኛ ተጠሪ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

1. ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) እና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መካከል በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተካሄደ ክርክር የቁጫ ምርጫ ክልል ምርጫ ውጤት ከድምጽ መስጫ ወረቀት ጋር በተያያዘ ግድፈት የተፈፀመበት ነው ተብሎ የምርጫ ውጤቱ ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ በመ/ቁ 211141 ነሐሴ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡
2. ቦርዱ እንደ ውሳኔው ለመፈፀም በእንቅስቃሴ ላይ እያለሁ አዲስ ሁኔታ ተከስቷል በማለት ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ውሳኔ አሳልፎ ውሳኔውን በቁጥር አ116211/434 ህዳር 1 ቀን 2014 ዓ.ም ለአሁን 2ኛ ተጠሪ አሳውቋል፡፡ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ የኢዜማ ፓርቲ ዕጩ የሆኑት ዶ/ር እንድሪያስ ሄባና እና ሻዛ ጋላላ ጋኔቦ ከምርጫ ውድድሩ ራሳቸውን በፈቃዳቸው ማግለላቸውን፤ እንዲሁም ሌላዋ ዕጩ ወ/ሮ ብርቱካን ጦቃ ሀብቴ ፓርቲውን ወክለው እንዳይወዳደሩ የፓርቲው ወረዳ ጽ/ቤት እንዳገዳቸው ተገልጾልኛል፡፡ ይህ አዲስ ሁኔታ እንደተከሰተ ቦርዱ ፓርቲውን ጠይቆ ፓርቲው ዕጩዎች ራሳቸውን ማግለል

እንደማይችሉ ከመግለጽ ውጪ ሌላ ምላሽ አልሰጠም። በዚህ ምክንያት ቦርዱ በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ለመፈፀም መቸገሩን በመግለጽ ስለፍርዱ አፈፃፀም መመሪያ እንዲሰጥ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ በተፈጠረው አዲስ ክስተት ምክንያት ውሳኔው የማይሻሻል (ማይለወጥ) መሆኑን በመግለጽ በመ/ቁ 211141 ጥቅምት 5/2014 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቷል። ይህን የፓርቲውን መልስ እና የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ ቦርዱ ጉዳዩን እንደገና መርምሮ ፓርቲው ዕጩዎችን ወዲያውኑ ከመተካት ውጪ ያለፈቃዳቸው ዕጩ ማድረግ የማይችል በመሆኑና በወቅቱም ላለመወዳደር የወሰኑትን ዕጩዎቹን የሚተኩ ዕጩዎች ባለማቅረቡ እንዲሁም አንደኛዋ ዕጩ በፓርቲው ከውድድሩ እንዲወጡ የተወሰነ በመሆኑ እንደፍርዱ ድጋሚ ምርጫ ለማድረግ መሰረት የሆነው የውሳኔ ሁኔታ የተቀየረ በመሆኑ ድጋሚ ምርጫ ለማድረግ የማይቻለው መሆኑን ቦርዱ ተገንዝቧል። በመሆኑም በቁጫ ምርጭ ክልል ድጋሚ ምርጫ ይደረግባቸው በማለት ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረት ዳግም ምርጫውን ማከናወን የማይቻለው መሆኑን ቦርዱ ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ምክንያት በምርጫ ክልሉ የሚገኘው ህዝብ ያለ ተወካይ እንዳይቀር ለክልል ምክር ቤት አሸናፊ ናቸው ተብለው አስቀድሞ በቦርዱ ማረጋገጫ የተሰጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች (የአሁን 2ኛ ተጠሪ ዕጮዎች) በምክር ቤቱ ተገኝተው የክልላቸው ህዝብ ህጋዊ ወኪል ሆነው እንዲያገለግሉ በማለት ወስኗል።

3. የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለከፍተኛው ፍ/ቤት በቀን 13/04/2014 ዓ.ም ባቀረበው ይግባኝ ቦርዱ የምርጫ አዋጁን እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብና መመሪያዎችን ሳይከተል በቁጫ ምርጫ ክልል የአንድ ዕጩ ፎቶ በምርጫ ወረቀት ላይ ባለማስቀመጡ የምርጫ ሥርዓት ግድፈት ፈጽሟል ተብሎ ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቀርቦ በመ/ቁ 211141 በቀን 21/12/2013 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ የምርጫ ክልሉ ውጤት እንዲሰረዝና ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ተወስኗል። በውሳኔው መሰረት 1ኛ ተጠሪ በቁጫ ምርጫ ክልል መስከረም 20/2014 ዓ.ም ድጋሚ ምርጫ ለማድረግ ቀጠሮ ይዞ ምርጫውን ለማስፈጸም ዝግጅት ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በሌሎች ምርጫ ክልሎች ምርጫ ተደርጎ በቁጫ ምርጫ ክልል ምርጫ ሳያደርግ ቀርቷል። 1ኛ ተጠሪ ጥቅምት 26/2014 ዓ.ም በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በቂ በሆኑ ህጋዊ ምክንያቶች ተሰርዟል ያለው ውሳኔ እያለ በተሰረዘው ውጤት ምርጫውን አሸንፈው የነበሩ የፓርቲ እጩዎች ህዝብን ወክለው ምክር ቤት ይግቡ በማለት የፍ/ቤቱን ውሳኔ የሚቃረን አስተዳደራዊ ውሳኔ ሰጥቷል። የ1ኛ ተጠሪ ውሳኔ የህግ የበላይነትና የፍ/ቤቶችን የዳኝነት ስልጣን ያላከበረ ነው። ማንኛውም ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በህግ አግባብ እስካልተለወጠ ድረስ የጸና ነው የሚለውን መርህ ያልተከተለ ከመሆኑ በተጨማሪ የህዝብ ሉአላዊነትን ያላከበረ ነው። ቦርዱ የፍ/ቤቱን ውሳኔ ለማስፈጸም አለመቻሉን የገለጸበት ምክንያት በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ረቺ የነበረው ኢዜማ ፓርቲ ሁለት እጩዎች ራሳቸውን ከምርጫ በማግለላቸው እና አንድ እጩ ፓርቲውን ወክለው እንዳይወዳደሩ የወረዳ ጽ/ቤት ያገዳቸው መሆኑን ተከትሎ

ነው፡፡ ምንም እንኳ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረበው ፓርቲ ኢዜማ ቢሆንም የተፈጠረው ስህተት በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በቀጥታ የሚመለከት በመሆኑ ኢዜማ ራሱን ከውድድሩ ማግለሉ ምርጫ ቦርድ በፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት ከመፈጸም አያግደውም፡፡ በመሆኑም ምርጫው ተሰርዞ ዳግም ምርጫ እንዲደረግ የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር 1ኛ ተጠሪ (ቦርዱ) የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቀሪ እንዲሆን ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

4. 1ኛ ተጠሪ በ20/04/2014 ዓ.ም በሰጠው መልስ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲ ተብሎ የተመዘገበው ብልጽግና ፓርቲ እንጂ የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ብልጽግና ፓርቲ ባለመሆኑ ክስ የማቅረብ መብት ያለው ዋናው ብልጽግና ፓርቲ ነው እንጂ ይግባኝ ባይ አይደለም፤ በዋናው ጉዳይ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ተከራካሪ የነበረው ኢዜማ እንጂ ይ/ባይ ባለመሆኑ የፍርዱ ተጠቃሚ ያልተደረገው ይ/ባይ ለሌላ አካል የተሰጠውን ውሳኔ መነሻ በማድረግ ተጠቃሚ የሚሆንበት አግባብ ባለመኖሩ ቅሬታ ለማስቀረብ የሚያስችል መብት የለውም፤ የቦርዱ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የምርጫ ውጤትን የሚመለከት ሲሆን የምርጫ ውጤትን በተመለከተ የሚቀርብን ክርክር አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ስልጣን ያለው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ነው እንጂ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን የለውም፤ የምርጫ ውጤትን በተመለከተ ቦርዱ በሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚቀርብ ይግባኝ ውሳኔ በተሰጠ 10 ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት በመሆኑ ይግባኝ ባይ ያቀረበው ይግባኝ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ተከራክረዋል፡፡

5. የአሁን 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ በ28/08/2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ድጋሚ ምርጫ ይደረግ ተብሎ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ ኢዜማ እና ምርጫ ቦርድ ተከራካሪ ሆነው ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ በድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም የሚል እና ሌሎች በ1ኛ ተጠሪ የቀረቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን እንዲሁም በፍሬ ነገሩ ዝርዝር መከራከሪያውን አቅርቧል፡፡

6. ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ውሳኔ መስጠት የሚችለው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መሰረት ቦርዱ የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ድጋሚ ምርጫ ይደረግ ወይም ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ አላደርግም ማለቱ ተገቢ ነው የሚለው ክርክር ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባው በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንጂ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፡፡ አስቀድሞም የምርጫ ክልሉን በተመለከተ ድጋሚ ምርጫ ይደረግ የሚል ውሳኔ የሰጠው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሆኖ እያለ በዛው ምርጫ ክልል ላይ የተነሳውን

ተመሳሳይ ጥያቄ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አይቶ ለመወሰን የሚያስችል ስልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ዳኝነት ስልጣን የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(2) እና 245(2) መሰረት በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

7. የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በ06/10/2014 ዓ/ም ባቀረበው ማመልከቻ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) መሰረት ቦርዱ በሚሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ እንደሚታይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚሁ ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መልኩ በፌዴራል የአስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ 1183/2012 አንቀጽ 49(1) መሰረት የአስተዳደር ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ የሚቀርበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ ፍ/ቤቱም የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጥ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረብነው ይግባኝ የቁጫ ምርጫ ክልልን አስመልክቶ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 211141 የሰጠውን ውሳኔ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአስተዳደራዊ ውሳኔ በመሻሩ ይኸው ውሳኔ እንዲከለስ የቀረበ ይግባኝ ነው፡፡ በመሆኑም በይግባኙ የተጠየቀው ዳኝነት 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በራሱ በመሻር የሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ይከለስ የሚል በመሆኑ ሊሰጥ የሚችለው ውሳኔ ከተጠየቀው ዳኝነት አንጻር ብቻ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በውሳኔው እንደገለጸው ምርጫው ዳግመኛ ይደረግ ወይም አይደረግ ብሎ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚያስችለው የህግ አግባብ የለም፡፡ አመልካች እንደ ስር ፍ/ቤት አገላለጽ የአፈጻጸም ወይም ያንን መሰል ዳኝነት ፈጽሞ አልተጠየቀም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት መደምደሚያ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ካቀረበው ጉዳይ አንፃር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 10 ተገቢነት የሌለው እና ይኸው ድንጋጌም ከአዋጁ አንቀጽ 155(1-4) እና አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) ጋር ተዳምሮ መተርጎም ያለበት ነው፡፡ የምርጫ ሂደትና ውጤትን አስመልክቶ የነበሩ ቅሬታዎች በጠቅላይ ፍ/ቤት ታይተው ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፤ለይግባኝ መንስኤ የሆነው የምርጫ ውጤት ተገልጾ በሂደቱ ላይ ቅሬታ ቀርቦ፣ ምርጫው በፍ/ቤት ከተሰረዘ በኋላ በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይሻርልን በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

8. ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ወስኖ እያለ 1ኛ ተጠሪ ይህን ውሳኔ ወደ ጎን በማድረግ ቀደም ሲል በፍ/ቤት በተሻረው ምርጫ ያሸነፉት እጩዎች ወደ ምክር ቤት እንዲገቡ አስተዳደራዊ በሆነ መልኩ ወስኗል የሚል ሆኖ እያለ አቤቱታው የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበት አግባብ ከምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133 አንቀጽ 17(1) እና ከፌደራል

ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 13(2) አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

9. 1ኛ ተጠሪ በቀን 17/10/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የኢዜማ አንድ እጩ ካለመውጣቷ ውጭ ነጻና ፍትሀዊ በነበረው ምርጫ ተሳትፈው በተወካዮቻቸው አማካኝነት በመንግስት አስተዳደር የመሳተፍ መብታቸውን ያረጋገጡ ዜጎችን መብት ለመጠበቅ ተገቢ ነው የሚለውን መፍትሔ ተጠሪ ሰጠ እንጂ የሻረው ምንም አይነት የፍ/ቤት ውሳኔ የለም፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረ አስተዳደራዊ ውሳኔ በ1ኛ ተጠሪ ባልተሰጠበት ሁኔታና የተሰጠ ውሳኔ ስለመኖሩም ማረጋገጫ ሳይቀርብ የፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረ አስተዳደራዊ ውሳኔ በ1ኛ ተጠሪ ተሰጥቷል በሚልና ሌሎችም ተያያዥ ምክንያቶች በማንሳት በአመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረበውን ክርክር ተመልክቶ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የምርጫ ሂደትና ውጤት ብሎም ድጋሚ ምርጫ ማድረግ አለማድረግን የሚመለከት እንደመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስልጣኑ የእኔ ሳይሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉ ምንም አይነት የህግ ስህተት የለውም፡፡ በመሆኑም ወደ ፍሬ ጉዳዩ ቢገባ የሚሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ የምርጫ ሂደትንና ውጤትን ብሎም ድጋሚ ምርጫ ማድረግን የሚመለከት እንደሆነ ፍርድ ቤቱ አረጋግጦ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በሚል በአመልካች ከህግ አግባብ ውጭ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ባለመኖሩ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ በቀን 17/10/2014 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጉድለት ስለሌለበት ውሳኔው እንዲጸና በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካችም አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

10. ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሳኔው የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ቅሬታ እንዲሁም በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ ማጠንጠኛ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ይህን ከዳኝነት ስልጣን ጋር የተያያዘ ክርክር ለመወሰን በምርጫ ነክ አዋጆች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤቶች ይግባኝ የሚቀርብበትን አግባብ በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በቅድሚያ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

11. የምርጫ ቦርድ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተከራካሪዎቹ ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰድ ይግባኝ የሚሉበትና ውሳኔው እንዲሻር ማመልከቻ የሚቀርብበት ሂደት በህጉ ተመልክቷል፡፡ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17 ስለ ይግባኝ ስልጣን የሚደነግግ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 1 ስር እንደተመለከተው የስራ አመራር ቦርዱ

የሚሰጣቸው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የምርጫ ሂደትና ውጤትን በተመለከተ የሚሰጣቸው የመጨረሻ ውሳኔዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

12. የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በተመሳሳይ ቦርዱ በስነ ምግባር ጥሰቶች በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ እንዲሁም በድምጽ ቆጠራና ውጤት በሚነሱ ክርክሮች ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ስለሚቀርበው ይግባኝ በመለያየት ይደነግጋል፡፡ በአንቀጽ 149 ስር እንደተመለከተው ቦርዱ የምርጫ ስነ ምግባር ጥሰቶችን ተከትሎ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን፤ በሌላ በኩል በአንቀጽ 155(4) ስር እንደተመለከተው ቦርዱ በድምፅ ቆጠራ እና ውጤት ላይ ለሚነሱ ክርክሮች በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

13. እነዚህ ከፍ ሲል የተመለከቱ ድንጋጌዎች ይዘታቸው ምን አይነት ጉዳዮች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ ምን አይነት ጉዳዮች ደግሞ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በተያዘው መዝገብ እያከራከረ ያለውና ቦርዱ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ የቁጫ ምርጫ ክልል ምርጫ ውጤት ከድምጽ መስጫ ወረቀት ጋር በተያያዘ ግድፈት የተፈፀመበት ነው ተብሎ የምርጫ ውጤቱ ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ በመ/ቁ 211141 ነሐሴ 21 ቀን 2013 ዓ.ም በፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ የሥራ አመራር ቦርዱ እንደ ውሳኔው ለመፈፀም በእንቅስቃሴ ላይ እያለሁ አዲስ ሁኔታ ተከስቷል በማለት ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ መሰረት ዳግም ምርጫውን ማከናወን የማይቻለው መሆኑንና በዚህ ምክንያት በምርጫ ክልሉ የሚገኘው ህዝብ ያለ ተወካይ እንዳይቀር አስቀድሞ አሸናፊ ናቸው ተብለው ማረጋገጫ የተሰጣቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ወደ ምክር ቤት እንዲገቡ የሰጠውን ውሳኔ የሚመለከት ነው፡፡ይህ የቦርዱ ውሳኔ ከምርጫ ሂደትና ውጤት ውጪ የሆነ ሌላ የአስተዳደራዊ ውሳኔ ተደርጎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ይግባኙ የቀረበው ከፍ ሲል በተጠቀሰው የቦርዱ ውሳኔ ላይ በመሆኑ በፍርድ ቤቱ በጭብጥነት ተይዞ ውሳኔ የሚሰጠው ቦርዱ በቁጫ ምርጭ ክልል ድጋሚ ምርጫ አላደርግም ማለቱ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ነው፡፡ መሰል ጉዳይ ደግሞ የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ነው፡፡

14. ስለሆነም ጉዳዩ በቦርዱ የምርጫ ሂደትን አስመልክቶ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ (final decision with regard to electoral process) ላይ የቀረበ እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) ስር የሚሸፈን ነው ብለናል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ደግሞ ይግባኙ ሊቀርብ የሚችለው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡

15. ሥረ ነገሩን ለመስማትና ለመዳኘት ሥልጣን የሌለው ፍርድ ቤት አቤቱታ የቀረበለት እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 9(1) እና 231 በተደነገገው መሰረት አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት

መመለስ የሚኖርበት ሲሆን ከዚህ አልፎ በተጠሪ በሚቀርብ የሥረ ነገር የዳኝነት ሥልጣን መቃወሚያ ላይ ክርክር ሰምቶ ሥልጣን የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጥ ውሳኔም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(1)(ሀ) እና 245 ድንጋጌን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

16. ስለሆነም አመልካች የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው በማለት ያቀረበው ክርክር ከፍ ሲል በዝርዝር ያመለከትነውን የመሰረታዊ እና የስነ ሥርዓት ህጉን ድንጋጌዎች ይዘት ያገናዘበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተከታዩም ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 282120 በቀን 19/09/2014 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ 208898

ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- የኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ-ተወካይ አውድሮ ታደስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሞቻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ -ተወካይ አለማየሁ ሻረው ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሠኔ 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ.መ.ቁ 206429 ግንቦት 11 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከካፋ ዞን ሳይለም ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች እና ከቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ እና ቴፒ ምርጫ ጣቢያዎች የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ ይወሰንለት ዘንድ ያቀረበውን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ከካፋ ዞን ሳይለም ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት የካፋ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ፤ ከቤንች ሸካ ዞን ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ቴፒ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከቴፒ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ ወደ ሚገኙበት የቤንች ሸካ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ከመዝገቡ ይዘት መረዳት እንደተቻለው የአሁን ተጠሪ ለአሁን አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ከካፋ ዞን ሳይለም ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ ምርጫ ክልል የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች፤ እንዲሁም በቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ቴፒ ምርጫ ክልል በሕገ ወጥ መንገድ የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች በመሆናቸው ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ እንዲደረግ ይወሰንልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪ ያቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በቀን 08/07/2013 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ያቀረባቸው ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸው መሆናቸው ቢታመንም አንዳንድ የምርጫ ክልሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች እያቀረቡ በመሆናቸው የሕዝብ እና የቤት ቆጠራ ሳይከናወን የምርጫ ክልል ማስተካከል ስለማይቻል ወጥ የሆነ አሠራር መከተል ስለሚኖርብን እንዲሁም በጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥ ከሸካ ብሔረሰብ ውጪ የሚኖሩ መራጮች ድምጽ የሚሰጡት በቴፒ የምርጫ ክልል በመሆኑ እና የሳይለም ምርጫ ጣቢያዎችም የ2013 ዓ.ም ምርጫ የሚካሄደው በ2007 ዓ.ም በተካሄደው የምርጫ ክልሎች እንዲሆን ተወስኗል የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ ወደ ሻካ ዞን እንዲጨመሩ የተደረጉ የምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ ለመስረቅ ሆን ተብለው የተፈጠሩ የምርጫ ጣቢያዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ ዕጩዎች ላይ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ደርሷል፤ በጉራፈርዳ እንኳንስ የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማድረግ ቀርቶ ዜጎች በጅምላ የሚገደሉበት እና ለሕይወት አስጊ ቦታዎች ናቸው፤ ለትራንስፖርትም ምቹ አይደሉም፤ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሸካ ዞን በተጨመሩ ወረዳና የምርጫ ጣቢያዎች በሚገኙበት አካባቢ የተጠሪ ዕጩዎች አለመኖራቸው ተጠሪን በነጻነት እኩል የፖለቲካ ምሕዳሩ ሰፍቶ ፕሮግራሙን ለመግለጽ የሚያስቸግረው እና ለመራጭ እና ለተመራጩ በሕገ መንግስት የተሰጣቸውን መብት የሚጋፋ ነው፤ ተጠሪ ለማይወክላቸው መራጮች ወደፊት ቢመረጥ የልማት ሥራዎችን እሠራለሁ ብሎ በምርጫ ቅስቀሳ ቃል ለመግባትም ሆነ ሲመረጥም ተግባራዊ ለማድረግ አይችልም፤ የተጠሪ ጥያቄ ከምርጫ ክልሎች አደረጃጀት ጋር መያያዙ አግባብ ካለመሆኑም በላይ በአዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች ለመለወጥ ከተሰጠው ሥልጣን ጋርም የሚጋጭ ነው፤ ስለሆነም ከከፋ ዞን ሳይለም ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች እና ከቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሸካ ዞን ቴፒ ወረዳ የተጨመሩት የምርጫ ጣቢያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ እንዲደረግ ይወሰንልን በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ የምርጫ ክልል የተካለለው በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 54/3 መሠረት ነው፤ ሕገ-መንግስቱ እስካልተቀየረ ድረስ ቀደም ሲል ምርጫ ሲካሄድባቸው የነበሩት የውክልና የምርጫ ክልሎች በተጠሪ ስልጣን ሊቀየሩ አይችሉም፤ የምርጫ ክልል ሊቀየር የሚችለው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ተደርጎ ሲሆን በውጤቱ መሠረት አመልካች ረቂቅ የውሳኔ ሀሳብ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቅርቦ ወሳኔ የሚሰጥበት በመሆኑ አመልካች በአሁን ወቅት የምርጫ ክልል ማካለል አይችልም፤ አመልካች የ2013 ዓ.ም ምርጫ በ2007 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለመላው የሐገሪቱ ሕዝብ አሳውቋል፤ የምርጫ ጣቢያ ሊጨመር ወይም ሊለወጥ የሚችለው በአዋጁ ቁጥር 15(6) መሠረት ቀድሞ የነበረው የምርጫ ጣቢያ ላይ የመራጩ ሕዝብ ቁጥር ከ 1500 በላይ ከሆነ እና በአርብቶ አደር አካባቢ የሕዝቡን የአኗኗር ሁኔታ መነሻ በማድረግ የሕዝብ መጨናነቅ ለመቀነስ ላይ የምርጫ ጣቢያ እንዲቋቋም ሲወሰን ነው፤ የምርጫ ጣቢያዎቹ አስቀድመው የነበሩ

በመሆኑ የአመልካች ክርክር አግባብነት የለውም፤ የጸጥታ ችግር ተነስቷል ቢባል እንኳን ችግሩ ሊቀረፍ የሚገባው በሕገ-መንግስት እና በምርጫ ሕጎች ነው፤ ይቀየሩ የተባሉት የምርጫ ጣቢያዎች በሌላ የምርጫ ክልል ውስጥ የሚገኙ በመሆኑ እነኚህን የምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሌላ የምርጫ ክልል መለወጥ ሕገ-መንግስትን መጣስ ይሆናል፤ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የተጠሪ ጥያቄ የምርጫ ክልልን የሚመለከት ነው? ወይስ የምርጫ ጣቢያን የሚመለከት? ተጠሪ በአመልካች ለይ ክስ ማቅረብ ይችላል? ወይስ አይችልም? የምርጫ ጣቢያን ለመቀነስ የግድ የሕዝብ እና ቤት ቆጠራ ሊደረግ ይገባል? ወይስ አይገባም? ከሳይለም እና ጉራፈርዳ ወረዳ ወደ ማሻና ቴፒ የምርጫ ክልሎች ውስጥ የተካተቱ የምርጫ ጣቢያዎች ሊነሱ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ያላግባብ የተጨመሩት የምርጫ ጣቢያዎቸ ይቀነሱልን የሚል እንጂ የምርጫ ክልል ይቀነስ ወይም ይጨመር የሚል አይደለም፤ ተጠሪ ሕጋዊ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ በመሆኑ እና ክሱም በምርጫ ክልሉ ውስጥ ያሉትን የምርጫ ጣቢያዎች የሚመለከት በመሆኑ በአመልካች ላይ ክስ የማቅረብ መብት አለው፤ ምርጫ ክልል የሚቋቋመው በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ያለውን ሕዝብ ብዛት መሠረት በማድረግ ነው፤ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ሊመርጥ የሚችለውን ሕዝብ ብዛት ለማወቅ በቅርቡ የተደረገ የህዝብ እና ቤት ቆጠራ የለም፤ የሕዝብ ቁጥር ባልታወቀበት ደረጃ ደግሞ ተገቢውን ቁጥር የያዘ መራጭ ሕዝብ እንዳለ ተቆጥሮ የምርጫ ጣቢያ ሊቀነስ አይችልም፤ በቂ ቁጥር ያለው መራጭ ሕብረተሰብ መኖሩ ሳይረጋገጥ በሸካ ዞን ማሻ እና ቴፒ ምርጫ ክልሎች የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲነሱ ቢደረግ የምርጫ ክልሉ በተገቢ ተደራጅቷል የሚያሰኝ አይሆንም፤ ስለሆነም በሁለቱም ወረዳዎች ያለው ሕዝብ ብዛት በተጨባጭ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የምርጫ ጣቢያዎች ይነሱልኝ ሲል ተጠሪ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ምርጫ ጣቢያዎች ከሚገኙበት የምርጫ ክልሎች ተቀንሰው በእነዚህ ጣቢያዎቸ የሚመረጡ መራጮች በሚኖሩበት ወረዳዎች አካባቢ ወደሚገኙ የምርጫ ክልሎች እንዳይጠቃለሉ የሚያደርግ ሕጋዊ ምክንያት አለ? ወይስ የለም? ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ምርጫ ጣቢያዎች ባሉበት ምርጫ ክልሎች እንዲቀጥሉ ቢደረግ በሸካ ዞን በሚገኝ ሕዝብ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ላይ የሚኖረው አሉታዊ ውጤት ምንድነው? በመራጩ ሕዝብ የመምረጥ መብት እና በተጠሪ የመመረጥ መብት ላይ ወይም በምርጫው ዲሞክራሲያዊነት እና ፍትሐዊነት ላይ የሚያስከትለው ውጤትስ ምንድነው? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት አላቸው ያላቸውን ዓለም ዓቀፋዊ እና አሕጉራዊ ስምምነቶቸ እንዲሁም ሐገራዊ ሕጎች ድንጋጌዎችን በዝርዝር ካስቀመጠ በኋላ ለክርከሩ መነሻ የሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች በሸካ ዞን አስተዳደር ክልል ውስጥ የማይገኙ መሆኑ

የታመነ ነው፤ እንዲሁም በሽግግር መንግስት ጊዜ በተቋቋሙ የምርጫ ክልሎች እና በኋላም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 54/3 ከተመለከተው 550 የምርጫ ክልሎች ውስጥ በሸካ ዞን አስተዳደር ውስጥ ለሚገኝ የሸካቸ ብሔረሰብ በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት መቀመጫ እንዳለው እና ለክልሉ ምክር ቤት ደግሞ በሁለቱ የምክር ቤት ክልሎች ስድስት የክልል ምክር ቤት አባላት መቀመጫ እንዳለው አመልካች ያመነው ጉዳይ ነው፤ የተጠሪ ክርክር ይህ የብሔረሰቡ ውክልና ሳይሸራረፍ ተግባራዊ እንዲደረግ የሚጠይቅ የምርጫ ጣቢያን የሚመለከት እንጂ ተጨማሪ የምርጫ ክልል ይደራጅልኝ የሚል አይደለም፤ የተጠሪ ጥያቄ በቀጥታ የምርጫ ክልል ይደራጅልኝ የሚል ቢሆን የምርጫ ክልል የሚደራጀው የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ በመሆኑ እና ላለፉት 10 ዓመታታ በላይ የሕዝብ ቆጠራ ያልተደረገ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም ነበር፤ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(13) እና በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 15(1) መሠረት የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር የመወሰን እና ለምርጫው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የተለያዩ ታሳቢዎች ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወሰነው ስፍራ የምርጫ ጣቢያ እንዲያቋቁም እና ቦታዎች እንዲለውጥ ሥልጣን የተሰጠው ሆኖ ሳለ ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ስለሚነሱ ባሉበት ይቀጥሉ ማለቱ አግባብ አይደለም፤ ምርጫ ጣቢያዎች የሚቀነሱበትም ሆነ የሚጨመሩበት የምርጫ ክልሎች በሽግግር መንግስት ጊዜ በነበረው የሕዝብ ቁጥር የተደራጁ ናቸው፤ የአገራችን የሕዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ ከዳኝነት አስተውሎት የምንገነዘበው በመሆኑ የሸካ ዞን የሕዝብ ቁጥር በዞኑ ለሚገኙ የምርጫ ክልሎች ከሚፈለገው ቁጥር ያንሳል የሚያስብል አሳማኝ ምክንያት የለም፤ በተመሳሳይ የምርጫ ጣቢያዎቹ የሚጨመሩበት የምርጫ ክልሎችም የሕዝብ ቁጥራቸው እንደጨመረ መገመት ይቻላል፤ ፍርድ ቤቱ ከዳኝነት አስተውሎት እንደሚገነዘበው በቀድሞም ሆነ በአሁኑ የምርጫ ሕግ የምርጫ ክልሎች የሚቋቋሙት የክልል መንግስታትን ድንበር በጠበቀ መልኩ የአገሪቱን የወረዳ አስተዳደርን መሠረት በማድረግ ነው፤ በደቡብ ክልል የዞኖች አደረጃጀት ልዩ ባሕርይ አንጻር አከራካሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች በሌሎች ዞኖችና ወረዳዎች አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኙ በመሆኑ በሸካ ዞን አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የምርጫ ክልሎች አካል ሆነው የሚደራጁበት የሕግ መሠረት የለም፤ ስለሆነም አከራካሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ሊደረጁ የሚገባው በእነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ መራጮች ድምጻቸውን ሊሰጡ የሚገባው ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት ዞን ወረዳ አስተዳደር አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ሊሆን በመሆኑ ከሚገኙበት ምርጫ ክልሎች ተቀንሰው መራጩ ሕዝብ በሚኖርበት ወረዳዎች አካባቢ ወደሚገኙ የምርጫ ክልሎች እንዲጠቃለሉ በተጠሪ የቀረበው ጥያቄ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው። በአስተዳደር ዞኖች በሸካ ዞን ውስጥ የማይኖሩ ሰዎች በአከራካሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግበው ድምጽ የመስጠት ዕድል ስለሚያገኙ የዞኑ ሕዝብ ራሱን በራሱ በማስተዳደር ጉዳይ ራሱን ችሎ የመወሰን መብቱ እንዲሸራረፍ የማያደርግ አሉታዊ ውጤት ያስከትላል።

ከደቡብ ክልል አደረጃጀት አንጻር የክልሉ ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች የብሔረሰብ ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች ሆነው የየራሳቸው ምክር ቤት ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካል ኖሯቸው የተደራጁ በመሆናቸው በክልል ደረጃ በወጣ ቀመር መሠረት የየራሳቸውን በጀት ይዘው ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ናቸው፤ ተጠሪ በዚሁ ዞን ውስጥ ላለ ሕዝብ ፖለቲካል እንቅስቃሴ ለማድረግ የተደራጀ በመሆኑ ዕጩዎችን የሚመለምለውም ሆነ የሚመርጠው በዚሁ ዞን አስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ በመሆኑ የአከራካሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች መጨመር ከክልሉ አደረጃጀት ጋር ይጣረሳል፡፡

አንድ ዞን ውስጥ ባለው ብሔረሰብ ስም የተደራጀ ፓርቲ በአደረጃጀት የማይወክለውን በሌላ ዞን ውስጥ ያለውን ብሔረሰብ እወክልሃለሁ ብሎ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርግበት ሁኔታ በተግባር አይኖርም፤ ተጠሪ በሌላ ዞን አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ አከራካሪዎቹ ምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ መራጮችን እንዲህ አደርግላችኋለሁ እና ምረጡኝ ብሎ ለመቀስቀስም ሆነ የሚመረጥ ቢሆን ደግሞ የተመረጠበትን የሸካ ዞን በጀት በመጠቀም በካፋ ዞን እና በቤንች ሸኮ ዞን ለሚገኙት አከራካሪ ምርጫ ጣቢያዎች በተዋቀሩበት አካባቢ ለሚኖሩ መራጮች ቃል የገባላቸውን ነገር መስራት አይችልም፤ ይህም መራጮች ከተጠሪ ይልቅ ከአንድ ዞን በላይ እነሱ ያሉበትን አካባቢ ጭምር ሊወክል የሚችል ሌላ ፓርቲ ወደ መምረጡ ስለሚያዘነብሉ የምርጫው ምሕዳር ፍትሐዊ እንዳይሆን የማድረግ ውጤት ይኖረዋል በማለት አመልካች እና የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ ከካፋ ዞን ሳይለም ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት የካፋ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ፤ከቤንች ሸካ ዞን ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ቴፒ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከቴፒ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ ወደሚገኙበት የቤንች ሸካ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ፤ የመራጮች ምዝገባ የተጠናቀቀ በመሆኑ በእነዚህ ምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡ መራጮች ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል የሚፎካከሩ ተወዳዳሪዎችን የሚመርጡበትን ሁኔታ አመልካች እንዲያመቻች ሲል በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 03/10/2013 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የምርጫ ክልል በጽንስ ሐሳብ ደረጃ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ እና ተመሳሳይ ፍላጎቶች የሚያንጸባርቁ ዜጎች ተወካዮቻቸውን እንዲመርጡ በአንድ አገር የተወሰነ የአገሪቱን የግዛት ክልል በመከፋፈል የሚደራጅ ነው፤ በሕግ መሠረት ለተለያዩ ምክር ቤቶች መቀመጫዎች የሚመረጡ ተወካዮች ቁጥር በሕግ የተቀመጠለት የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ይፋ ከመደረጉ አስቀድሞ በምርጫ አስፈጻሚ ሳይሆን ስልጣን ባለው የመንግስት አካል የምርጫ ክልል ወሰን ሲወስን የተለያዩ መስፈርቶች በማስቀመጥ ሊወሰን የሚችል ሲሆን የሕዝብ ቁጥር አሰፋፈርን መሠረት በማድረግ የሚሰጠው ውሳኔ አንዱ ነው፤ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ

13 እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(6) መሠረት የምርጫ ክልል የሕዝብ እና ቤት ቆጠራን መሠረት በማድረግ እና ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ቦርዱ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚያቀርበው የምርጫ ክልል ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤቱ ውሳኔ እንደሚሰጥበት በግልጽ ተመልክቷል፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ሳይሰጥ ለምርጫ ማስፈጸሚያ አላማ በምርጫ አካባቢ በተደራጀ የአገሪቱ ግዛት ላይ አመልካችን ጨምሮ ማንም አካል ለውጥ ማድረግ አይችልም፡፡

በሽግግር ጊዜ የተቋቋመው ምክር ቤት የብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ምርጫ ይካሄድ ዘንድ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር አዋጅ ቁጥር 9/1984 በማውጣት ተግባራዊ አድርጓል፤ በመቀጠልም የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚሽንን ያቋቋመው እና ስልጣን እና ተግባሩን የወሰነውን አዋጅ ቁጥር 11/1984 አውጥቶ ተግባራዊ አድርጓል፤ ይህ የምርጫ ኮሚሽን የሕገ-መንግስት አባላትን ለማስመረጥ ባወጣው የምርጫ አዋጅ መሠረት የአገሪቱን ወረዳዎች በሕዝብ ቁጥር ላይ ተመርኩዞ ፍትሐዊ የሆነ የምርጫ ክልል ለመመስረት ያስችል ዘንድ በ1976 ዓ.ም ተካሂዶ የነበረውን የሕዝብ ቤቶች ቆጠራ ውጤትን ወደ 1985 ዓ.ም በመተንበይ የነበረውን የሕዝብ ቁጥር ባለው የሕዝብ ተወካዮች መቀመጫ ልክ እንዲደለደል ያቀረበው ውሳኔ ሀሳብ በሽግግር መንግስቱ ተቀባይነት አግኝቷል፤ በዚህ መሠረት አንድ የምርጫ ክልል 100,000 ሕዝብ እንዲወክል ተደርጓል፤ በዚሁ መሠረት በ1985 ዓ.ም በክልል ውስጥ የሚኖር የሕዝብ ብዛትን መሠረት ብቻ በማድረግ የምርጫ ክልል ተካሏል፤ በ1985 ዓ.ም የምርጫ ክልል ድልድል ከተሰራ በኋላ እስካሁን ድረስ ቦርዱ በሚያቀርበው ጥናት መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ የምርጫ ክልል አልተካለለም፤ አመልካች ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ በውጤቱ ላይ ተመስርቶ የውሳኔ ሀሳብ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በማቅረብ የአከላለል ለውጥ ከሚያስወስን በቀር የምርጫ ክልሎችን ወሰን ለመለወጥ ስልጣን የለውም፤ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ተጠሪ እንደሚለው ከከፋ እና ቤንች ሸካ ዞን የምርጫ ክልሎች የተጨመሩ ሳይሆኑ ላለፉት 5 ጠቅላላ ምርጫዎች በማሻና ቴፒ ምርጫ ክልል ሥር ተከልለው ሲተገበር የቆየ ነው፤ የሸካቾ ብሔረሰብ በፌዴራልም ሆነ በክልል ምክር ቤቶች የሚወከልበት ሁለት የምርጫ ክልሎች ያሉት በመሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ወደ ሸካ ዞን መካለላቸው ራስን በራስ የማስተዳደር መብቱን የሚሸራርፍ አይደለም፤ በአሁኑ ጊዜ የምርጫ ሂደቱ የተጠናቀቀ እና ድምጽ የሚሰጥበት ቀን ብቻ የቀረ በመሆኑ፤ ለምርጫ ክልሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ ክልል ስም ታትመው ተሰራጭተው በተጠናቀቀበት ወቅት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሕጉን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር በሚመለከት የካፋ ዞን ሳይለም ወረዳ እና ከቀድሞ ቤንች ማጂ ዞን በአሁኑ ቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ወደ ሸካ ዞን ማሻና ቴፒ የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲቀነሱ ምክንያታቸውን በመጥቀስ ተጠሪ ለአመልካች ያቀረቡት ጥያቄ በኢትዮጲያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር

1162/2011 አንቀጽ 2(15) እና 2(16) መሠረት የምርጫ ክልል ነው? ወይም የምርጫ ጣቢያ ነው? በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ምርጫ ጣቢያ ነው ያለው በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ያገናዘበ ነው? ወይስ አይደለም? አመልካች በኢትዮጲያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 2(15) መሠረት የምርጫ ክልል አከላለል በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/6 መሠረት ጥናት ተደርጎ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሃሳብ ያቀረቡ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ በማድረግ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአብላጫ ድምጽ የመሻሩን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/6 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 10/10/2013 ዓ.ም በሰጠው መልስ የተጠሪ ጥያቄ ከምርጫ ክልል ማሻሻያ ጋር በፍጹም የሚገናኝ አይደለም፤ ከሸካ ዞን ውጪ ከሚገኙ የራሳቸው ማንነት እና አደረጃጀት ካላቸው ዞኖች ሥር የሚገኙ የወረዳ ሕዝብ ለማይወክሏቸው ለሸካ ዞን ተመራጭ ድምጽ እንዲሰጡ የምርጫ ጣቢያዎች ማደራጀቱ የምርጫ ሂደቱን ነጻ ተአማኒ እና ፍትሐዊ እንዳይሆን የሚደርግ ነው፤ በኢትዮጲያ ውስጥ ካሉ ክልሎች ከየዞኖች በሚወከሉ አባላት የብሔረሰቦች ምክር ቤት ያለው ብቸኛ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች በደቡብ የሚገኙ ሲሆኑ የየራሳቸውን በጀት ስለሚያስተዳድሩ ከሳይለም እና ከጉራፈርዳ ሕዝብ አንጻር የመልማት እና የመልካም አስተዳደር መብት ዙሪያ በቅስቀሳ ወቅት ብመረጥ አሟላለሁ ብሎ ቃል ቢገባ እንኳን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፤ ያላግባብ ሁለት የራሳቸው ማንነት ካላቸው ዞን ወረዳዎች የራሱ ማንነት ወዳለው ሸካ ዞን ስር የተጨመሩ ምርጫ ጣቢዎች ተቀንሰው ወደ ራሳቸው ዞን ሥር በሚገኙ የምርጫ ክልሎች ቢጨመሩ ባሉት ላይ እንዲጨመሩ እንጂ ሌላ የምርጫ ክልል ይፈጠራል ወይም የማሻ እና የቴፒ ምርጫ ክልሎች ይቀነሳል የሚል አይደለም፤ በተጠሪ የቀረበው ጥያቄ የምርጫ ክልሎችን የሚያፋልስ አይደለም፤ የአመልካች ክርክር ጥናት አድርገን አቅርበናል የሚል ሳይሆን ወደፊት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕዝብ እና ቤቶች ቆጠራ ተካሂዶ በሚወስነው ይሆናል የሚል ነው፤ ተጠሪ አዋጅ ቁጥር 9/1984፤ 11/1984 የጠቀሰ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 532/2000 ዓ.ም በሕግ የተቋቋመ የምርጫ ክልል አደረጃጀት የለም፤ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ቢሆን የምርጫ ክልሎች ወደፊት እንደሚቋቋሙ እና አደረጃጀቱ ምን መምሰል እንዳለበት የሚገልጽ እንጂ የምርጫ ክልል አላቋቋመም፤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪ ጥያቄ የምርጫ ክልል ይቀነስ ወይም ይጨመር የሚል አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል አመልካች በይግባኝ አላስለወጠም፤ አመልካች የመራጮች ምዝገባ እና የምርጫ ቁሳቁስ ማጓጓዝን አስመልክቶ ያቀረበው ክርክር አዲስ የክርክር ሐሳብ ነው፤ ስለሆነም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም በቀን 10/10/2013 ዓ.ም በሰጠው የመልስ መልስ የምርጫ ክልል መሠረታዊ ገጽታ ከሆኑት መካከል አንዱ እና ዋነኛው መልክአምድር ነው፤ ይህም በአንድ መልክአምድር ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦችን በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሚወከሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እና የተሳትፎ መብታቸውን እውን ለማድረግ የሚመሰረት ከመደበኛ የአስተዳደር ወሰን የተለየ የምርጫ አካባቢ ነው፤ ለአመልካች በሕግ የተሰጠው ስልጣን በሌላ አካል ሥልጣን መሠረት በተወሰነ አንድ የምርጫ ክልል ስር የተለያዩ ምርጫ ጣቢያዎችን መመስረት እና እነዚህኑ የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች በዚያ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች የመምረጥ መብት መረጋገጡን ተደራሽ ማድረግ ብቻ በማለት የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በዋነኝነት አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ ከካፋ ዞን ሳይለም ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች እና ከቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ እና ቴፒ ምርጫ ጣቢያዎች በሕገ ወጥ መንገድ የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ ይወሰንልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 13 እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(6) መሠረት የምርጫ ክልል የሕዝብ እና ቤት ቆጠራን መሠረት በማድረግ እና ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ቦርዱ ለፌደሬሽን ምክር ቤት በሚያቀርበው የምርጫ ክልል ረቂቅ መሠረት የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ውሳኔ እንደሚሰጥበት በግልጽ ተመልክቷል፤ የፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ሳይሰጥ ለምርጫ ማስፈጸሚያ ዓላማ በምርጫ አካባቢ በተደራጀ የአገሪቱ ግዛት ላይ አመልካችን ጨምሮ ማንም አካል ለውጥ ማድረግ አይችልም የሚል ነው፡፡ ስለሆነም ለጉዳዩ አወሳሰን መሠረታዊ የሆነው ጭብጥ የተጠሪ ጥያቄ የምርጫ ክልልን የሚመለከት ነው? ወይስ የምርጫ ጣቢያን የሚመለከት? የሚለው ነው፡፡

በኢትዮጲያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 2(15)እና(16) እና በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 2(6)እና(7) ላይ የምርጫ ክልል ማለት ለምርጫ አፈጻጸም እንዲያመች እና ሕዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በሕግ መሠረት የሐገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፤ የምርጫ ጣቢያ ማለት ደግሞ በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጭ ምዝገባ የሚካሄድበት፤ መራጮች ድምጽ የሚሰጡበት እና የድምጽ ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው በማለት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 15(6)እና(7) በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚስተናገደው የመራጮች ብዛት ከ1500 መብለጥ እንደሌለበት እና ለአንድ የምርጫ ጣቢያ በተከለለ አካባቢ ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም

እንደማይቻል ይደነግጋል። የመራጮች ብዛት በሕግ ተለይቶ በተቀመጠለት የምርጫ ጣቢያ ውስጥ በመራጮች የሚሰጠው ድምጽ ወደ ምርጫ ክልል የመራጮች ድምጽ መስጫ ቋት ውስጥ የሚገባ በመሆኑ የሕዝብ ብዛትን መሠረት በማድረግ የተከለለውን የምርጫ ክልል አደረጃጀት ላይ እና በምርጫ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ስለሆነም ተጠሪ ከካፋ ዞን ሳይለም ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች እና ከቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ እና ቴፒ ምርጫ ጣቢያዎች በሕገ ወጥ መንገድ የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የምርጫ ክልልን የሚመለከት እንጂ የምርጫ ጣቢያን የሚመለከት አይደለም። የተጠሪ ጥያቄ የምርጫ ክልልን የሚመለከት ነው ከተባለ የምርጫ ቦርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ቀጥለን እንመልከት።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 103(5) የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሄዳል። በውጤቱም መሠረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌደሬሽን ምክር ቤት ይወስናል በማለት ይደነግጋል። የኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/6 ለቦርዱ ከተሰጠው ስልጣን እና ተግባር ውስጥ አንዱ የምርጫ አከላለል በተመለከተ ጥናት አድርጎ ለፌደሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሐሳብ ማቅረብ ነው።

የኢትዮጲያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 13/1(ሀ) (ለ) ለምርጫ አፈጻጸም ዓላማ የክልል መንግሥታት ድንበር እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ የወረዳ አስተዳደርን መሠረት በማድረግ የሚከፋፈሉ በሕዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ማስተካከያ ሊደረግባቸው በሚችሉ ቋሚ የምርጫ ክልሎች ትከፋፈላለች፤ አገሪቱ እያንዳንዳቸው አንድ ተወካይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥባቸው ከ550 የማይበልጡ የምርጫ ክልሎች የሚኖሯት ሆኖ አከላለሉ የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው የሕዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሠቦች እና ሕዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ይወሰናል፤ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች የሚወከሉባቸው የምርጫ ክልሎች ሳይጨምር ምርጫ ክልሎቹ ተቀራራቢ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ሆነው በመካከላቸው ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ልዩነት ከ15 በመቶ መብለጥ የለበትም በማለት ይደነግጋል። ከእነዚህ ሁሉ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የምርጫ ክልሎች እና የምርጫ ጣቢያዎችን የማደራጀት እና የማካለል ሥራ አስተዳደራዊ ጉዳይ መሆኑን ነው።

እንደሚታወቀው ከ1987 ዓ.ም በኋላ በአገራችን አምስት ምርጫዎች የተከናወኑ ሲሆን እነዚህ ምርጫዎች የተከናወኑት የምርጫ ቦርድ ቀደም ሲል የነበረውን የሕዝብ ቆጠራ መነሻ በማድረግ የምርጫ ክልሎችን አከላለል በተመለከተ ባቀረበው ረቂቅ መነሻነት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ባሳለፈው

ውሳኔ መሠረት እንጂ አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ አዲስ የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልሎች አከላለልን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 103(5) እና በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/6 መሠረት ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሪቂቅ አቅርቦ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ ይህም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ባለው አካል የምርጫ ክልሎችን አከላለል በተመለከተ የተሰጠ ውሳኔ እንደሌለ የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ስልጣን ያለው አካል የምርጫ ክልሎችን አከላል በሚመለከት ያሳለፈው ውሳኔ ሳይኖር ተጠሪ ከካፋ ዞን ሳይለም ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች እና ከቤንች ሸካ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ እና ቴፒ ምርጫ ጣቢያዎች በሕገ ወጥ መንገድ የተጨመሩ የምርጫ ጣቢያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲነሱ እና በራሳቸው ዞን ድምጻቸውን እንዲሰጡ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ከመነሻውም ቢሆን የሕግ ድጋፍ የሌለው እና አላግባብ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡ ይህንኑ መሠረት በማድረግ የምርጫ ቦርድ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው አግባብ ሆኖ ሳለ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ ጥያቄ የብሔረሰቡ ውክልና ሳይሸራረፍ ተግባራዊ እንዲደረግ የሚጠይቅ የምርጫ ጣቢያን የሚመለከት እንጂ ተጨማሪ የምርጫ ክልል ይደራጅልኝ የሚል አይደለም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸውን ምክንያቶች እና በመጨረሻም የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪ የሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ተነስተው ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ ምርጫ ጣቢያ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለበት ዋነኛ ምክንያት የአገራችን የሕዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔ እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ ከዳኝነት አስተውሎት የምንገነዘበው ነው በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የዳኝነት አስተውሎት /judicial notice/ የሚወሰደው ተቀባይነት ያገኘ የታወቀ እውነት ሲኖር እና በሌላ ማስረጃ ማረጋገጥ የማያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ነው /Judicial notice of a fact means a court's declaration of the existence of a fact normally decided by the trier of fact, without requiring proof of that fact / ፤ ሆኖም የተያዘው ጉዳይ የምርጫ ክልል እና ምርጫ ጣቢያ አከላለል ሆኖ መነሻ የሚያደርገው የመራጭ የሕዝብ ቁጥር ስለመሆኑ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ይህም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 103 መሠረት የሕዝብ ቆጠራ ይህንኑ ለማድረግ ስልጣን በተሰጠው የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን የሚከወን እና በየአሥር ዓመቱ የሚካሄድ እና ውጤቱም ለሕዝብ የሚገለጽበት ነው፡፡ ምንም እንኳን የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድ የሚገመት ቢሆንም ለዳኝነት ሰጪ አካል በበቂ ማስረጃ ሳይረጋገጥ ውሳኔ ለመስጠት የሚቻልበት አይደለም፡፡ ስለሆነም በሌላ ስልጣን ባለው አካል ሊረጋገጥ የሚችለውን ውጤት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአገራችን የሕዝብ ቁጥር እድገት ምጣኔ

እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ እንዳልሆነ ከዳኝነት አስተውሎት የምንገነዘበው ነው ማለቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርደ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪ የሆኑት ምርጫ ጣቢያዎች ከሸካ ዞን ቴፒ እና ማሻ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ተነስተው ወደ ሚገኙበት ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ ምርጫ ጣቢያ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ ፍርድ ቤቶች ፍርድን ሲሰጡ ካላቸው ስልጣን እና ገደብ ጋር በማገናዘብ ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚው ሶስቱም የመንግስት አካላት ሲሆኑ በሕግ ተለይቶ የተሰጣቸው የየራሳቸው የሆነ ስልጣን እና ተግባር አላቸው፡፡ ፍርድ ቤቶች በሕግ አግባብ የተጠበቀ መብት በተነፈገ ጊዜ ይህንኑ አረጋግጠው ውሳኔ የመስጠት ያልተገደበ ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሆኖም በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ተጠሪ ያቀረበው አከራካሪ የሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ተነስተው ወደ ነበሩበት ይዛወሩልኝ የሚለው ጥያቄ ከምርጫ ክልል አከላለል ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም የምርጫ ጣቢያው ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር መወሰን የሚችለው በሕጉ ሥልጣን የተሰጠው አካል እንጂ ፍርድ ቤቶች አይደሉም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ያቀረበው የምርጫ ጣቢያዎች ይነሱልኝ ጥያቄም ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ተጠሪ ባቀረበው ጥያቄ መነሻነት ብቻ ሳይሆን የሐገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ የምርጫ ቦርድ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚያቀርበው የአከላለል ረቂቅ ምክር ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ምርጫን መሠረት በማድረግ ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌሎች ተከታታይ ጥያቄዎችን ሊያስነሳ የሚችል ውሳኔ መስጠቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከካፋ ዞን ሳይለም ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከማሻ አካባቢ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ በሚገኙበት የካፋ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ፣ ከቤንች ሸካ ዞን ቀበሌ ምርጫ ጣቢያዎች ወደ ሸካ ዞን ቴፒ ምርጫ ክልል የተጨመሩ ምርጫ ጣቢያዎች ከቴፒ ምርጫ ክልል ተቀንሰው ምርጫ ጣቢያዎቹ ወደ ሚገኙበት የቤንች ሸካ ዞን ወረዳ አካባቢ በሚገኝ የምርጫ ክልል ስር እንዲጠቃለሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ ስለምርጫ ክልሎች በሕገ መንግስቱ እና በምርጫ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 206429 ግንቦት 11 ቀን 2013 ዓ.ም በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 268971 ሚያዝያ 08 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁጥር 193480

ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ 1ኛ. ኢቢኤስ ቴሌቪዥን-ጠበቃ ጥላሁን ሰቦቃ

2ኛ. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን- ነ/ፈጅ ተስፋዬ አይናለም

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ አምሳሉ ሲሳይ ደምሴ

2ኛ. አቶ ቢራራ ካሳሁን

3ኛ. አቶ ሲሳይ አረጋ ስዩም

4ኛ. አቶ ቃለአብ ብርሃን መኮንን

5ኛ. አቶ ኑረዲን አብዱለጢፍ አብዱ

6ኛ. አቶ መርሃ አድሰው ታፈሰ

7ኛ. አቶ ሒርጳሳ ዳንጌ አንጌሳ

8ኛ. አቶ አድማው ጎበና ፈታ

9ኛ. ወ/ሮ ራሄል ዮሴፍ ሙላት

10ኛ. አቶ ቃሲም እርጋ አብዶ

11ኛ. አቶ ብርሀነ ታምራት ገ/ስላሴ

12ኛ. አቶ ዳንኤል ሀይሌ ወልደየስ

13ኛ. ዜድ ዋይ ኮንስትራክሽን

14ኛ. አቶ ዮናስ ያይንሸት ወ/ሩፋኤል

15ኛ. አቶ ቆጭቶ ሙቹሌ ማሞ

16ኛ. አቶ ተስፋዬ ሙንዬ ገረመው

17ኛ. አቶ ተወልደ ግደይ ገ/እግዜአብሔር

18ኛ. አቶ ጠና ተፈራ ምስክር

19ኛ. አቶ መገርሳ ጫላ ጉልማ

20ኛ. አቶ ብስራት ጉታ ዳባ

21ኛ. አቶ ግርማ ጉዲሳ ደበሌ

22ኛ. አቶ ሔኖክ ወርቁ

23ኛ. አቶ ተስፋዬ ብርሀኑ አምሳሉ

24ኛ. አቶ ግርማይ አሰፋ

25ኛ. አቶ ዮሐንስ መንገሻ ወጀቡ

26ኛ. አቶ ኢሳያስ ወለዱ ክፍሌ

27ኛ. አቶ ፍትዊ ፀሀዬ ገ/ሕይወት

28ኛ. አቶ ፔትሪኦት በረከት ስብስብ

29ኛ. አቶ አመኑ ለሚ ስዩም

30ኛ. አቶ ተቀባ ገ/ወልድ ሌልሾ

31ኛ. አቶ ያሲን ካሳ ፋሪስ

32ኛ. ወ/ሮ ታሪካ ወተንን አደሬ

33ኛ. አቶ ገብረህይወት ሙላው

34ኛ. አቶ አዲስ ጥላሁን ተፈራ

35ኛ. አቶ አክሊሉ ሰርጡ ጆማነህ

36ኛ. አቶ ዮሴፍ ደበበ

37ኛ. አቶ ተካበ ተሰማ ታንቶ

38ኛ. አቶ አበባ አስራት

39ኛ. ሁአብ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር

40ኛ. ዙና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር

41ኛ. አቤኔዘር ገበየው (አቤኔዘር ገበየው የማስታወቂያ ስራ ድርጅት)

42ኛ. አቶ ሰለሞን ክንፈ ገ/እግዚአብሔር

43ኛ. አቶ ፀጋው ወዳጅነው አብተው

44ኛ. አቶ በለጠ ንጉሴ ደስታ

45ኛ. አቶ አለማየው አበበ አንዳቦ

46ኛ. አቶ አብዱ መሐመድ አደም

47ኛ. አቶ ኢብራሂም ይማም ሰይድ

48ኛ. አቶ አበራ ለታ ዱላ

49ኛ. አቶ ጎሳዬ አለማየው ግርኬ

50ኛ. አቶ ከተማ መንግስቱ ጉርሙ

51ኛ. አቶ አበባየው ሙሳ ረቡ

52ኛ. ወ/ሪት ስምሃር ጁሀር ሙሀባ

53ኛ. አቶ ኑረዱን ዲታሞ አብደላ

54ኛ. አቶ ሳምሶን በላይ ዘውዴ

55ኛ. አቶ ኤርሚያስ ተሾመ ዘለሌ

56ኛ. አቶ ጌዲዮን አሰፋ ተስፋማርያም

57ኛ. መ/አ ፀጋዬ ብርሀኑ ገ/ሚካኤል

58ኛ. አቶ ወልደጊዮርጊስ ለሜሳ ተሊላ

59ኛ. ወ/ሮ የሺ አጥሌ ተክሌ

60ኛ. አቶ ጌቱ ኡርጋ ደበሌ

61ኛ. ወ/ሮ መሰረት ንብረት ገበየው

62ኛ. ዶ/ር ዘበናይ ቢተው ዘለቀ

63ኛ. አቶ በልዩ ጥላሁን ተፈራ

64ኛ. ወ/ሪት መሰረት ተክሌ ወርቁ

65ኛ. የገሱባ ኮ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር

66ኛ. አቶ ካላዩ መሐሪ ካህሳይ

67ኛ. አቶ የማነ ተስፋይ ረዳ

68ኛ. ዲሻ የህንፃ ስራ ተቋራጭ

69ኛ. አቶ ዳንኤል ገ/መድን ተስፋዬ እና ገ/የ/ሽ/ማ

70ኛ. አቶ ጥላሁን ታደሰ ሽንቁጥ

71ኛ. አቶ ጌታቸው ጀንበር

72ኛ. አቶ መስፍን ፈይሳ ወልቀባ

73ኛ. አቶ ከተማ ሙለታ ታደሰ

1ኛ አመልካች እና ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ 41 የተጠቀሱት ተጠሪዎች እንደየ ቅደም ተከተላቸው በሰ/መ/ቁጥር 193480 አመልካች እና ተጠሪዎች ሲሆኑ 2ኛ አመልካች እና ስማቸው በተራ ቁጥር 1-4፣ 42፣ 43፣ 5-7፣ 44፣ 45፣ 8፣ 46-50፣ 9፣ 51፣52፣ 11፣ 12፣ 53፣ 13፣ 54፣ 55፣ 14፣ 56፣ 15-17፣ 58-59፣ 18-20፣ 6፣ 21፣ 22፣ 61፣ 62፣ 23፣24፣ 63፣ 25፣ 64፣ 26፣ 27፣ 65፣ 28-31፣ 66-68፣ 32-35፣ 69፣ 36፣37፣ 70፣ 38፣ 71፣ 39፣ 73 ላይ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በዚህ ቅደም ተከተል በሰ/መ/ቁጥር 193482 አመልካች እና ተጠሪዎች ናቸው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመሳሳይ የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር የተደረገበት እና በስር ፍ/ቤት ጉዳያቸው በአንድ መዝገብ በታየ ተመሳሳይ ተከራካሪዎች መካከል የቀረበ ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት በሰ/መ/ቁጥር 193480 አጣምረን በመመርመር ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ ውልና ከውል ውጪ ግንኙነትን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎችን ጨምሮ 98 ሰዎች ከሳሾች፣ 40ኛ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ፤ 1ኛ አመልካች 3ኛ ተከሳሽ፣ 2ኛ አመልካች 2ኛ ተከሳሽ እንዲሁም 1ኛ አመልካች የአሁን 41ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባለት ባመለከተው መሰረት ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የስር ከሳሾች በከፍተኛ ፍ/ቤቱ በተለያዩ ሶስት መዝገቦች የስር ተከሳሾች ላይ ያቀረቡት ክስም በኮ/መ/ቁጥር 179107 ተጣምሮ እልባት አግኝቷል፡፡

ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ 40ኛ ተጠሪ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን፣ መለዋወጫዎችን እና መገልገያዎችን ከሌላ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት የሚያስችለው ቁጥሩ 14/673/212364/2007 የሆነን የንግድ ስራ ፈቃድ መስከረም 21 ቀን 2007 ዓ.ም ከንግድ ሚኒስቴር ማግኘቱን ተከትሎ ፈቃድ ያገኘበትን የንግድ ስራ መስክ የሚመለከት በቴሊቪዥን ጣቢያዎች የሚተላለፍ የኦዲዮቪዥዋል ማስታወቂያ 41ኛ ተጠሪ እንዲሰራለት ተዋውሎ ማስታወቂያው የተነገረላቸውን ተሽከርካሪዎች እና መሳሪያዎችን የሚያሳይ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን የያዘ ማስታወቂያ ተሰርቷል፡፡ ይህንንም ማስታወቂያ በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ ለማስተላለፍ 1ኛ አመልካች በወኪሊ ኢንኮም ትሬዲንግ አማካኝነት ማስታወቂያውን ካዘጋጀው እና የማስታወቂያ ወኪል ከሆነው 41ኛ ተጠሪ ጋር በመዋዋል ከጥቅምት 20 እስከ ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም እንዲሁም 2ኛ አመልካች ከ40ኛ ተጠሪ ጋር በተደረገ ውል ከነሐሴ 10 ቀን 2007 እስከ የካቲት 26 ቀን 2008 ዓ.ም ማስታወቂያው በቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ ተላልፏል፡፡ የስር ከሳሾችም በቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ የተነገረውን ማስታወቂያ በማመን ከ40ኛ ተጠሪ ጋር በተናጠል በተደረገ የውል ስምምነት 336 የፈረስ

ጉልበት ያላቸውን ሲኖ ትራክ ገልባጭ መኪና እና የተለያዩ ማሽነሪዎችን ውሉ በተደረገ ከ75 እስከ 90 ቀናት ባለው ግዜ ውስጥ ሊያስረክበን፣ ተጠሪዎች (የስር ከሳሾች) የጉምሩክ ፎርማሊቲዎችን ለማጠናቀቅ ይቻል ዘንድ በኢንቨስትመንት አዋጁ መሰረት የግብር ምህረት ወይም ሌሎች ማበረታቻ የሚያስገኙልንን ሰነዶች ውሉ ሲፈረም ለማስረከብ፤ ድርጅቱም 50% የሚሆነውን ብድር ከመንግስት ወይም ከግል ባንኮች የምናገኝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ተስማምቶ ከ25 እስከ 50% የሚደርስ ቅድሚያ ክፍያ የፈጸምን ቢሆንም ድርጅቱ (የስር 1ኛ ተከሳሽ) የውል ግዴታውን አልተወጣም፡፡ 40ኛ ተጠሪ ማስታወቂያውን ያስነገረው እንዲሁም ከስር ከሳሾች ጋር ውል በመፈረም ገንዘብ የሰበሰበው ተሽከርካሪዎቹን ወደ ሀገር ውስጥ ሳያስገባ እና የንግድ ፈቃዱ የተሰጠበት የበጀት አመት ካለፈ በኋላ ሳያሳድስ የማታለል ተግባር ለመፈፀም አስቦ ሲሆን ከሳሾችም ውሉን የተዋዋሉት በአመልካቾች ቴሌቪዥን የተነገረውን ማስታወቂያ በማመን ነው፡፡ አመልካቾች ማስታወቂያውን ከማሰራጨታቸው በፊት ድርጅቱ የታደሰ ንግድ ፍቃድና ለሚያስተዋውቃቸው ምርቶች የብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን፤ ማስታወቂያው የድርጅቱን ትክክለኛ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያሳይ፣ እውነተኛ፣ የማያሳስት፣ በማስታወቂያው የታዩት ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ፣ ቀረጥ የተከፈለባቸው መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታቸውን ባለመወጣት ከሳሾች እንዲሳሳቱ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም የከፈልነውን የቅድመ ክፍያ ውሉ ሊፈፀም ከሚገባው ቀን አንስቶ ከሚታሰብ ወለድ እንዲሁም ውሉ ቢፈፀም ተሽከርካሪዎቹን በማከራየት እናገኝ የነበረው የቀን ገቢ በቀን ብር 2,666.66 ታስቦ እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ ለማታለል በማሰብ የፈጸምኩት ተግባር የለም፤ እንደ ውሉ ያልፈጸምኩት በውጭ ምንዛሬ እጥረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው፤ ከሳሾች ግማሽ ክፍያ ብቻ የከፈሉ ስለሆነ የታጣ ገቢ ሊጠይቁ አይችሉም፤ ወለድም ልከፍል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

1ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ ከሳሾች ውሉን የተዋዋሉት መኪኖቹ በ40ኛ ተጠሪ እጅ እንደሌሉና ወደ ፊት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መሆናቸውን በግልፅ አውቀው እና ተረድተው ውሉ ከተፈረመበት ጊዜ አንስቶ ከ75 እስከ 90 ቀናት ውስጥ ለመረከብ ተስማምተው ነው፤ ውሉን በተዋዋሉበት ጊዜ ተሽከርካሪዎቹ በስር 1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኙ መሆኑን ማረጋገጥ ስለነበረባቸው ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ ማስታወቂያው አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት የለውም፤ በሀሰት የተነገረ ነው ከተባለም በ41ኛ ተጠሪ የተዘጋጀ በመሆኑ እና 1ኛ አመልካች በማስታወቂያው የተነገረውን ለመጠራጠር የሚያበቃው ተጨባጭ ሁኔታ ስለሌለ ኃላፊ ልሆን አይገባም፡፡ ማስታወቂያው በተነገረበት ጊዜም ተከሳሽ የፀና የንግድ ፍቃድ ነበረው፤ አብዛኞቹ ከሳሾች ተከሳሽ የፀና የንግድ ፍቃድ አልነበረውም በሚሉበት ጊዜ ውስጥ ውል ፈፅመዋል፤ የስር 1ኛ ተከሳሽ ለሚያስተዋውቃቸው ምርቶች የብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት የለብኝም፤ በውሉ መሰረት ከሳሾች ለስር 1ኛ ተከሳሽ የኢንቨስትመንት ፍቃዳቸውን የማቅረብ ግዴታን አልተወጡም፤ ወለድ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄም ተገቢ አይደለም፡፡ በከሳሾች

ላይ ለደረሰው ጉዳት 1ኛ አመልካች ኃላፊነት አለበት የሚባል ከሆነ በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀፅ 34(1)(ለ) መሰረት መረጃን የማረጋገጥ ግዴታን መተላለፍ የሚያስከትለው ቅጣት ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 በመሆኑ ከዚሁ ጋር ተገናዝቦ ሊወሰን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ማስታወቂያውን ያስተላለፍኩት 40ኛ ተጠሪ መስከረም 21 ቀን 2007 ዓ.ም ከንግድ ሚኒስቴር የተሰጠው ቁጥሩ 4/673/212364/2007 የሆነ የንግድ ፈቃድ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን፣መለዋወጫዎችንና መገልገያዎችን ከሌላ ሀገር አስመጥቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሸጥ የሚያስችለው መሆኑን አረጋግጬ ነው፤ ማስታወቂያው መተላለፍ በጀመረበት ነሐሴ 10 ቀን 2007 ዓ.ም የፀና ንግድ ፍቃድ ነበረው፤ ተሽከርካሪዎቹ ከቀረጥ ነፃ የገቡ እንዲሁም ለሚያስተዋውቀው እቃ የብቃት ማረጋገጫ ያለው መሆኑን የማረጋግጥ ግዴታ የለብኝም፤ ማስታወቂያውም የስር 1ኛ ተከሳሽ በፍ/ሕ/ቁጥር 1687 መሰረት የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን ከውጪ አስመጥቶ ለመሸጥ ያለውን ፍላጎት ያሳወቀበት በመሆኑ አስገዳጅ አይደለም፤ ከሳሾችም ውሉን ሊፈፅምላቸው የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ ነበረባቸው፤ ማስታወቂያው በአመልካች ቴሌቪዥን መተላለፍ ከመጀመሩ በፊት ድርጅቱ ጋር ውል የገቡ ከሳሾች አመልካች ላይ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

41ኛ ተጠሪ በበኩሉ የተነገረው ማስታወቂያ 40ኛ ተጠሪ በውሉ መሰረት ባለመፈጸሙ ከሳሾች ደርሶብናል ከሚሉት ጉዳት ጋር የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት የለውም፡፡ ማስታወቂያው የተዘጋጀው ማስታወቂያ የሚነገርላቸውን የኮንስትራክሽን መሳሪያዎች፤ መለዋወጫዎች፤ መገልገያዎች እና አቅርቦቶች ከሌላ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ አስመጥቶ ለመሸጥ የፀና ፍቃድ ባለው ጊዜ ሲሆን ማስታወቂያው በተነገረበት ጊዜም ፍቃዱ አልተሰረዘም፡፡ ከሳሾችም ውሉን ሲዋዋሉ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎቹ በ1ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነበረባቸው፡፡ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎቹን ያልተረከቧቸው ስለሆኑ ጉዳት ስለመድረሱ አልተረጋገጠም፡፡ የከፈሉትንም ገንዘብ ሊጠይቁ የሚችሉት ከከፈሉት ሰው ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም 40ኛ ተጠሪ ከሳሾች ለቅድመ ክፍያ የሰጡትን ገንዘብ እንዲመልስላቸው ያቀረቡትን ክስ ስላመነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 መሰረት ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከከሳሾች የተቀበለውን ቅድመ ክፍያ እንዲመልስ ከፊል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ በሌሎች ጉዳዮች ግራ ቀኙን አከራክሮ በ1ኛ አመልካች የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገ ሲሆን 40ኛ ተጠሪ ከከሳሾች ጋር በተናጠል ባደረገው ውል 336 የፈረስ ጉልበት ያላቸውን ሲኖ ትራክ ተሽከርካሪዎች ውሉ በተደረገ ከ75 እስከ 90 ቀናት ውስጥ ለማስረከብ ተስማምቶ ከ25 እስከ 50 በመቶ የሚሆን ክፍያ የተቀበለ ቢሆንም በዚህ አግባብ አልፈፀመም፡፡ ተጠሪዎች ማሽኖቹን ስራ ላይ አሰማርተው የሚያገኙትን የተጣራ ትርፍ ማወቅ የሚቻለው ማሽኖቹን በእጃቸው አስገብተው ገቢ በሚያስገኙላቸው ስራዎች ላይ ካሰማሩ በኋላ በመሆኑ እንደ ውሉ ባለመፈጸሙ አጥተነዋል የሚሉትን ገቢ 40ኛ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም፡፡ የውጭ ምንዛሬ

እጥረት በፍ/ሕ/ቁጥር 1792(1) መሰረት አስቀድሞ ሊታይ እና ሊገመት የማይችል አይነት ክስተት ስላልሆነ የውል ግዴታውን ላለመወጣቱ ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም፡፡ ከሳሾች ክፍያውን የፈፀሙት መኪኖቹን እና ማሽነሪዎቹን በስራ ላይ በማስማራት ገቢ ለማግኘት በመሆኑ እና ባንክ ቢያስቀምጡት ኖሮ ጥቅም ስለሚያገኙበት 40ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 ባመነው መሰረት ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ፍርድ ላይ ለከሳሾች እንዲከፍል በተወሰነው የገንዘብ መጠን ላይ ውሎቹ ሊፈፀሙ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ ወለድ ሊከፍል ይገባል፡፡

40ኛ ተጠሪ የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን፣ መለዋወጫዎችን፣ መገልገያዎችንና አቅርቦቶችን ከሌላ ሀገር አስገብቶ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሸጥ የሚያስችለው ቁጥሩ 14/673/21236/2007 የሆነ የንግድ ስራ ፈቃድ መስከረም 21 ቀን 2007 ዓ.ም በንግድ ሚኒስቴር ተሰጥቶታል፡፡ ንግድ ፍቃዱ በወቅቱ በስራ ላይ በነበረው የንግድ ስራ አዋጅ ቁጥር 686/2002(እንደተሸሻለ) አንቀፅ 2(10)(24) መሰረት እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ሊያገለገል ይችላል፡፡ ማስታወቂያውን በቴሌቪዥን ለማስተላለፍ ውል በተፈረመበትና በቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ የኦዲዮቪዥዋል ማስታወቂያ መተላለፍ በጀመረበት ጊዜ ንግድ ፍቃዱ የፀና በመሆኑ የንግድ ፍቃዱ መታደስ አለመታደሱ ማረጋገጥ ሳይጠበቅባቸው በውሉ ለተመላከተው ጊዜ ማስታወቂያውን የማስተላለፍ ግዴታ ስላለባቸው የንግድ ፍቃድን በሚመለከት የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 ድንጋጌን ጥሰዋል ለማለት አይቻልም፡፡ 40ኛ ተጠሪ ለሚያስተዋውቀው መኪና እና ማሽነሪዎች በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀፅ 9(1)(2) መሰረት የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ሊኖረው እንደሚገባ እንዲሁም በምን መንገድ ለውሉ አለመፈጸም ምክንያት እንደሆነም ከሳሾች አላስረዱም፡፡ በተጨማሪም አመልካቾች ተሽከርካሪዎቹና ማሽነሪዎቹ ቀረጥ የተከፈለባቸው መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በአዋጁ የተጣለባቸው ግዴታ የለም፡፡ ነገር ግን በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ የተላለፈው ማስታወቂያ የተነገረላቸው መኪኖችና ማሽነሪዎችን 40ኛ ተጠሪ ከውጪ ሀገር አስመጥቶ ሀገር ውስጥ የገቡ መሆኑን ጭምር መልእክት የሚያስተላልፉ እንደነበር ፍ/ቤቱ የተገነዘበ ቢሆንም ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ጊዜም ሆነ በተነገረበት ጊዜ በ40ኛ ተጠሪ እጅ ምንም አይነት መኪናም ሆነ ማሽነሪ አልነበረም፡፡ አመልካቾች ይህንንም አልካዱም፡፡ 41ኛ ተጠሪ ማስታወቂያውን ሲያዘጋጅ፣ አመልካቾችም ማስታወቂያውን ከማስተላለፋቸው በፊት መኪኖቹን እና ማሽነሪዎቹን 40ኛ ተጠሪ ከውጪ ሀገር አስመጥቶ ሀገር ውስጥ እንዳሉ አለማረጋገጣቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ማስታወቂያው መኪናዎቹ እና ማሽነሪዎቹ ሀገር ውስጥ ገብተው በድርጅቱ እጅ ይገኛሉ የሚል የተሳሳተ ግንዛቤን በተመልካቾች ዘንድ ሊያሳድር የሚችል አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማስታወቂያ ነው፡፡ አመልካቾችም የተነገረው ማስታወቂያ ይህን እምነት አይፈጥርም፤ ከሳሾችም ማስታወቂያው በቴሌቪዥን ሲተላለፍ አልተመለከቱም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ በመሆኑም በአዋጁ የተጣለባቸውን ማስታወቂያው አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም ትክክለኛ አቀራረብ ያለው አለመሆኑን እንዲሁም በማስታወቂያው የተነገረው ነገር ትክክል መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡

የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ለተሰራጨ ማስታወቂያ ማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያ ወኪሉ እና ማስታወቂያ አሰራጩ ሃለፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀፅ 30 ላይ የተገለፀ ሲሆን በህግ በትክክል የተገለፀ ድንጋጌን መተላለፍም ጥፋት መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2055(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ስለሆነም 41ኛ ተጠሪ እና አመልካቾች ማስታወቂያው ሊያሳድር በሚችለው የተሳሳተ እምነት ለደረሰ ጉዳት ከውል ውጪ 1ኛ አመልካች ከ1ኛ- 3ኛ ላሉት ተጠሪዎች ብቻ፤ 2ኛ አመልካች ተጠሪ ከ1ኛ- 39ኛ እና 42ኛ-73ኛ ላሉት ተጠሪዎች ከ40ኛ እና 41ኛ ተጠሪዎች ጋር በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀፅ 34(1)(ለ) ከብር 10,000 እስከ 100,000 በሚል የተገለፀው መቀጮ መረጃን የማረጋገጥ ግዴታን ያልተወጣ ማንኛውም ሰው ሊከተለው የሚገባን የቅጣት ወሰን የሚያመላክት እንጂ በማስታወቂያ የተነሳ ለደረሰ ጉዳት ከውል ውጪ የፍትሐብሔር ኃላፊነት ያለበት ሰው ለጉዳቱ ሊከፍል የሚገባውን የካሳ መጠን ለመወሰን የተደነገገ አይደለም፡፡ ነገር ግን ከሳሾቹ ማስታወቂያውን ከተመለከቱ በኋላ መልእክቱን ብቻ በማመን እንዳለ ተቀብሎ ከመዋዋል መኪኖቹ እና ማሽኖቹ ሀገር ውስጥ ገብተው በ40ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኙ መሆኑን በራሳቸው በኩል ለማጣራት ሙከራ ቢያደርጉ ውሉን ከመዋዋል በመቆጠብ የደረሰባቸውን ጉዳት የማስቀረት እድል የነበራቸው በመሆኑ ለደረሰው ጉዳት አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም በፍ/ሕ/ቁጥር 2098(2) መሰረት አመልካቾችና 41ኛ ተጠሪ 40ኛ ተጠሪ ከከሳሾች ላይ ከወሰደው ቅድመ ክፍያ ገንዘብ ውስጥ 1/4ኛውን ብቻ ውሎቹ ሊፈጸሙ ይገባ ከነበረበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ ወለድን ጨምሮ ከ40ኛ ተጠሪ ጋር የመክፈል የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ውሳኔውን በመቃወም በየግላቸው ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 27 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የ1ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ ባጭሩ ለክሱ መነሻ የሆነው ማስታወቂያ ይዘት እና አቀራረብ አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ሊባል የሚችል ስለመሆኑ በማስታወቂያና ሚድያ ልዩ ባለሙያዎች እንዲጣራ ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ባቀረብነው አቤቱታ መሰረት አለመጣራቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 327(3)፣ 345(1)(ለ)፣ 136 እና 182 ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ ተጠሪዎች ውሉን ከተዋዋሉ በኋላ የባንክ ሒደቶችን ተከታትለው ማሟላታቸው፣ ተሽከርካሪዎቹ ከ75 እስከ 90 ቀናት ውስጥ ከውጪ ሀገር ግዢ የሚፈጸምባቸው እና ውሉ በርካታ ቅድመ ሁኔታዎች ያሉት መሆኑ ተጠሪዎች ተሽከርካሪዎቹ ሀገር ውስጥ እንደሌሉ እያወቁ የተዋዋሉ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመሆኑ ማስታወቂያው በፍ/ሕ/ቁ 1697 እና 1698 በተገለፀው አግባብ ውሉን ለመቀበል የሚያደርስ ስህተትን የማያስከትል ስለመሆኑ ሊመረመር ይገባ

ነበር፡፡ በ1ኛ አመልካች የተሰራጨው ማስታወቂያ የማስታወቂያ አዋጁን ድንጋጌ በመተላለፍ የተሰራጨ ነው ቢባል እንኳ የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያው ወኪል እና የማስታወቂያው አሰራጭ ተሳትፎ ተለይቶ በአዋጅ ቁጥር 759/2005 አንቀፅ 30 በተገለፀው አግባብ በአንድነት ወይም በነጠላ ያለብን ኃላፊነት ሳይለይ በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይለም፡፡ ተጠሪዎች በ1ኛ አመልካች በተነገረው ማስታወቂያ ተሳስተን የሽያጭ ውሉን ተዋውለናል በማለት የሚያነሱትን መከራከሪያ የውሉን ይዘት መሰረት በማድረግ ከተሽከርካሪዎች ግብይት ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ ያለውን የንግድ ልምድ (Trade Custom) እና በንግዱ መስክ የዳበረውን የንግድ አፈፃፀም ስርዓት (Usage) ጋር በፍ/ሕ/ቁጥር 1713 እና 1732 መሰረት ተገናዝቦ ሳይመረመር የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ ከማስታወቂያው ቪዲዮ ዝግጅት ጋር በተያያዘ 1ኛ አመልካች ምንም አይነት አስተዋፅኦ እንደሌለው ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች አለመሰማታቸው፣ ማስታወቂያውንም ከ1ኛ አመልካች ቀድሞ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሬድዮ አስተላልፎት የነበረ መሆኑን ገልጾ ጣልቃ እንዲገባለት በጠየቀው መሰረት አለመታዘዙ፣ ማስታወቂያው በሚነገርበት ጊዜ 40ኛ ተጠሪ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዳስገባ ወይም በሂደት ላይ እንደነበር ከጉምሩክ እንዲጣራ ጠይቆ ሳይጣራ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የ2ኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት 1ኛ አመልካች ካቀረበው ቅሬታ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በተጨማሪም በፍ/ሕ/ቁጥር 2035(1) አንድ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚኖርበት ግልፅ ህግን የጣሰ ሲሆን ነው፡፡ አመልካች በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀፅ 8(1-17) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን ስለመፈፀሙ ሳይረጋገጥ የአዋጁን አንቀፅ 8(18) በመጥቀስ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፤ በአመልካች የተላለፈው ማስታወቂያ አሳሳች የሚያስብለው ሁኔታ የለም እንጂ አለ እንኳ ቢባል ቅጣቱ በአዋጁ አንቀፅ 30 እና 34(1)(ሐ) በተደነገገው አግባብ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ ተጠሪዎች(የስር ከሳሾች) ውል ከመዋዋላቸው በፊት ተገቢውን ማጣራት ቢያደርጉ ኑሮ የደረሰባቸውን ጉዳት ማስቀረት ይችሉ ነበር የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶ እያለ በፍ/ሕ/ቁጥር 2097(2) መሰረት 2ኛ አመልካችን ከኃላፊነት ነፃ ማድረግ ነበረበት፡፡ ማስታወቂያው በፍ/ሕ/ቁጥር 1687 መሰረት 40ኛ ተጠሪ ውል ለመዋዋል ያለውን ፍላጎት ከሚያመላክት በቀር ውል ለመዋዋል ጥያቄ እንዳቀረበ ስለማያስቆጥር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የያዟቸውን ጭብጦች በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት ተገቢውን ማጣራት አድርገው መወሰን አለመወሰናቸውን ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 241 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንፃር ለመመርምር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

40ኛ እና 41ኛ ተጠሪዎች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ሲሆን ከ1ኛ እስከ 39 እንዲሁም ከ42ኛ እስከ 73ኛ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪዎች በጠበቃቸው አማካይነት ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ የስር 1ኛ ተከሳሽ (40ኛ ተጠሪ) የማታለል ተግባሩን በከፍተኛ ሁኔታ ለማስፋፋት የተጠቀመው የቴሌቪዥን ማስታወቂያን በማሰራጨት ሲሆን አንድም መኪና ወደ ሀገር ውስጥ ያላስገባ ቢሆንም በርካታ አዳዲስ መኪኖች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እየተጓዙ በማሳየት፤ መኪኖቹን ማስመጣታችንን ስንገልፅ ደስታ ይሰማናል ልዩነታችን 50% የባንክ ብድር ማመቻቸታችን ነው በሚል የሌለውን ነገር እንዳለ በማስመሰል የተዘጋጀውን አሳሳች የሀሰት የቪዲዮ ምስሎች  አመልካቾች በሕግ የተጣለባቸውን የማስታወቂያውን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ ሳይወጡ በማሰራጨታቸው ተጠሪዎች በማስታወቂያው ምክንያት እምነት እንዲያድርብን እና ገንዘባችንን እንድንከፍል ሁነናል፡፡ ተከሳሹም ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ በማዋሉ ሊከፍለን ስላልቻለ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም

1ኛ. በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ የተላለፈው ማስታወቂያ አሳሳች ወይም ያልተገባ አቀራረብ ያለው መሆን? አለመሆኑ? በልዩ አዋቂ ባለሞያዎች ያለመጣራቱ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?

2ኛ. ማስታወቂያው አሳሳች ወይም ያልተገባ አቀራረብ አለው ከተባለ በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ መተላለፉ የማስታወቂያ አዋጁን ድንጋጌዎች ይቃረናል? ወይስ አይቃረንም? አመልካቾች ላይ የሚያስከትለው ኃላፊነትስ ምንድነው?

3ኛ. ተጠሪዎች ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ውሉን ሲዋዋሉ ተገቢ ማጣራት አለማድረጋቸው እንዲሁም የተዋዋሉት ውል ይዘት በተሸከርካሪዎች ግብይት ከዳበረው የንግድ ልምድ (Trade Custom) እና የንግድ አፈፃፀም ስርዓት (Trade Usage) አንፃር የሚኖረው ውጤት ምንድነው?

4ኛ. 1ኛ አመልካች ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሬድዮ ጣልቃ እንዲገባ፣ ከጉምሩክ ማስረጃ እንዲቀርብ እንዲሁም ምስክሮቹ እንዲሰሙለት ጠይቆ ከነበረ በዚህ አግባብ ያለመታዘዙን አግባብነት እንዲሁም

5ኛ. አመልካቾች ለተጠሪዎች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ ተጠሪዎች የከፈሉትን ቅድመ ክፍያ 1/4ኛ ወለድና ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤቶች ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

**<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በሚመለከት፡-</u>** ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት ወይም ለትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ መስሎ በታየው ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪዎቹ ወይም ከተከራካሪዎቹ በአንዱ አመልካችነት ጉዳዩ በልዩ አዋቂ እንዲመረመር ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136 ላይ ተመላክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ የተላለፈው ማስታወቂያ አሳሳች ወይም ያልተገባ አቀራረብ ነበረው? ወይስ አልነበረውም? የሚለው በልዩ አዋቂ መመርመር ነበረበት ወይ? የሚለውን ለመወሰን የማስታወቂያውን ይዘት ማስታወቂያ ተደራሽ እንዲሆን ከተፈለገው የማህበረሰብ ክፍል አንፃር መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኦዲዮ ቪዥዋል ማስታወቂያው 40ኛ ተጠሪ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ማሽኖችን፣ የቤት እና የመስክ መኪኖችን፣ ሲኖትራክ፣ ደረቅ ጭነት ገልባጭ መኪኖችን ስለማስመጣቱ እና ወደ ፊትም የሚያስመጣ እና 50% ብድር የሚያመቻች መሆኑን በመግለፅ ተሽከርካሪዎቹን በምስል በማሳየት የተላለፈ እንደነበር ነገር ግን ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ጊዜም ሆነ በተነገረበት ጊዜ በ40ኛ ተጠሪ እጅ ምንም አይነት መኪናም ሆነ ማሽነሪ እንዳልነበረ አረጋግጠዋል፡፡ ማስታወቂያው የሚነገርበት ዋና አላማም ተሽከርካሪዎቹን እና ማሽነሪዎቹን የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ከማስታወቂያ አስነጋሪው ጋር ግብይት ውስጥ እንዲገባ ማስቻል ነው፡፡ የማስታወቂያው ይዘትም ተሽከርካሪዎቹ እና ማሽነሪዎቹን በምስል የሚያሳይ፣ ሀገር ውስጥ እንደገቡ እና ወደ ፊት እንደሚገቡ የሚገልፅ እና ማንኛውንም ሰው ለግብይት የሚጋብዝ ነው ካልን የማስታወቂያው አሳሳች መሆን አለመሆን ወይም ያልተገባ አቀራረብ ያለው መሆኑ ልዩ አዋቂ የሚያስፈልገው ሳይሆን ይልቁንም አንድ ምክንያታዊ ሰው ማስታወቂያውን በመመልከት ከሚደርስበት መደምደሚያ (reasonable man standard) አንጻር የሚለካ ነው፡፡ ማስታወቂያውን የሚመለከት ማንኛውም ምክንያታዊ ሰውም በድምፅ የተነገረውን እና በምስል የታዩት ተሽከርካሪዎች በመመልከት ሀገር ውስጥ ገብተዋል ብሎ እንዲያምን የሚያደረግ ነው፡፡ ማስታወቂያው በተዘጋጀበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በኂላ መኪኖቹ እና ማሽነሪዎቹም ሀገር ውስጥ እንዳልገቡ በስር ፍ/ቤቶች ስለተረጋገጠ ማስታወቂያው አሳሳች ነው? ወይስ አይደለም? አቀራረቡስ ያልተገባ ነው? የሚለውን ለመለየት የተለየ የልዩ አዋቂ ማስረጃነት የሚጠይቅ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካቾች ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

**<u>ሁለተኛውን ነጥብ በሚመለከት</u>**፡- ማስታወቂያ ህብረተሰቡ በሚያከናውነው የምርት ግብይት ውስጥ ተፅእኖ የሚፈጥር፣ ገበያው ጤናማ በሆነ ውድድር እንዲመራ በማድረግ ጉልህ ሚና የሚጫወት፣ በስርዓት ካልተመራም የሕብረተሰቡን መብት እና ጥቅም እንዲሁም የሀገር ገጽታን የሚጎዳ መሆኑ፤ በዚህም ምክንያት የማስታወቂያ ወኪሎች፣ የማስታወቂያ አስነጋሪዎች እና የማስታወቂያ አሰራጮችን መብት እና ግዴታ በግልፅ ለመወሰን እንዲቻል የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 መውጣቱን ከአዋጁ መግቢያ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካት ማንኛውም ማስታወቂያ አሳሳች ወይም ተገቢ ካልሆነ አገላለጽ ነፃ መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣ በገበያ ውስጥ የሌለ ምርት ወይም አገልግሎት እንዳለ አስመስሎ

የሚያቀርብ ማስታወቂያ አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳለው ማስታወቂያ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ መሰል አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ በዚህ ምድብ ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 6(1)(ለ)፤ አንቀፅ 8(1)(10)፤ 8(18) ላይ ተመላክቷል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 27(1)(ሀ) ላይም ማንኛውም የማስታወቂያ ወኪል ወይም አሰራጭ በማስታወቂያ አስነጋሪው የቀረበለትን ማስታወቂያ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ ተደርጎ ምስላቸው እየታየ ማስታወቂያ የተነገራላቸው ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳልገቡ በስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህም ማስታወቂያውን የሚመለከቱ ሰዎች መኪኖቹ እና ማሽነሪዎቹ ሰዎች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል የሚል እምነት እንዲያድርባቸው የሚያደረግ በመሆኑ አሳሳች ወይም ያልተገባ አቀራረብ ያለው ነው፡፡ አመልካቾችም መኪኖቹ እና ማሽኖቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ በማጣራት የማስታወቂያውን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ኃላፊነታቸውን ስላልተወጡ የአዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የተፈፀመ ተግባር ነው፡፡ የአዋጁን ድንጋጌ በመተላለፍ የተሰራጨ ማስታወቂያ በማስታወቂያ አስነጋሪው፣ በማስታወቂያ ወኪሉ እና በማስታወቂያ አሰራጩ ፈቃድ እንደተሰራጨ ተቆጥሮ እንደሃላፊነታቸው መጠን በአንድነት ወይም በነጠላ ተጠያቂ እንደሚሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 30 ላይ የተገለፀ በመሆኑ ተጠሪዎች በማስታወቂያው ላይ እምነት በማሳደር ተዋውለው ለደረሰባቸው ጉዳት አመልካቾች ኃላፊነት አለባቸው መባሉ ተገቢ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ 2ኛ አመልካች ማስታወቂው በፍ/ሕ/ቁጥር 1687 መሰረት 40ኛ ተጠሪ ውል ለመዋዋል ያለውን ፍላጎት ከሚያመላክት በቀር ውል ለመዋዋል ጥያቄ እንዳቀረበ የሚወሰድ አይደለም በማለት የሚያቀርበውን መከራከሪያ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጠቀሰው ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ ለ ላይ አንድ የእቃ ዝርዝርን የሚያሳይ ፅኁፍ ለሌላ ሰው የላከ ወይም በአደባባይ በሚታይ ማስታወቂያ የገለፀ ወይም የንግድ እቃዎች ለሕዝብ ስለመሸጥ ያሳየ የውል ግዴታ እንደገባ የማያስቆጥረው መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ ነጋዴው ባስነገረው ማስታወቂያ መሰረት ውል እንዲገባ ሊገደድ የማይችል መሆኑን የሚያመላክት እንጂ በማስታወቂያ አዋጁ በልዩ ሁኔታ ማስታወቂያ አስነጋሪውም ሆነ ማስታወቂያ አሰራጩ አሳሳች ወይም ትክክለኛ ያልሆነ አቀራረብ ያለውን ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ከማድረግ እንዲቆጠቡ እንዲሁም የማስታወቂያ አስነጋሪው የማስታወቂያውን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታውን እንዲወጣ፤ ካልተወጡም በኃላፊነት የሚያስጠይቃቸው መሆኑን የሚገልፅ የአዋጁን ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚያስቀር ስላልሆነ 2ኛ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

ሌላው አመልካቾች በአዋጁ አንቀፅ 34(1) መሰረት ኃላፊነት አለባችሁ ቢባል እንኳ እንደየተሳትፏችን የአንድነት ወይም የነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብሎ መወሰን ሲገባው የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት አለባችሁ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሚያነሱት መከራከሪያ ነው፡፡ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የማስታወቂያ ወኪሉ፣ ማስታወቂያ አስነጋሪው ወይም ማስታወቂያ አሰራጩ እንደየሁኔታው ሁሉም ወይም አንዱ ኃላፊነት አለባችሁ ተብሎ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚያመላክት እንጂ ሁሉም

ኃላፊነት አለባቸው ከተባለ የኃላፊነት ሁኔታ በአንድነት እና በነጠላ እንዳይሆን ክልከላ የሚያደርግ ባለመሆኑ እና ሶስቱም የአዋጁን ድንጋጌ መተላለፋቸው ስለተረጋገጠ ቅሬታው ተገቢነት የለውም፡፡

<u>**ሶስተኛውን ነጥብ በሚመለከት፡-**</u> ማንኛውም ጠንቃቃ ገዢ ስለሚዋዋልበት ጉዳይ እና ስለሚዋዋልበት ነገር ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ተጠሪዎች ውሉን ከመዋዋላቸው እና ክፍያ ከመፈፀማቸው በፊት በእርግጥም መኪኖቹ እና ማሽነሪዎቹ በ40ኛ ተጠሪ እጅ ይገኙ እንደነበር በራሳቸው መንገድ ማጣራት ነበረባቸው፡፡ የውሉን ይዘት በሚመለከትም 40ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎቹን ከ75 እስከ 90 ባሉት ቀናት ውስጥ ሊያስረክባቸው፣ ተጠሪዎች የጉምሩክ ስርዓቱን ማስፈጸም የሚያስችሉ ሰነዶችን ለድርጅቱ ሊያቀርቡ፤ የክፍያውን 50 በመቶ ድርጅቱ ከባንኮች ጋር ብድር ሊያመቻች እና ተጠሪዎችም ከ25-50 በመቶ የሚሆነው ክፍያ የከፈሉ መሆኑን እንደሚገልፅ ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህ የውሉ ይዘት የሚኖረው ትርጉም በሀገራችን ከዳበረው የተሽከርካሪዎች ግብይት ልምድ (Trade Custom) ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የመኪና ሻጮች በእጃቸው ያሉ ተሽከርካሪዎችን ለመሸጥ በሚደርጉት ውል የተሽከርካሪው የሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ቁጥር፣ የምርት ዘመን፣ የተሽከርካሪው አይነት እና መሰል ጉዳዮች የሚጠቀሱበት ሲሆን ስም ተዛውሮ እስኪያልቅ ድረስ በገዢው እጅ እንዲቆይ ከሚደረገው መጠነኛ ገንዘብ ውጪ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ክፍያ ወዲያው ይከፈላል፡፡ በአንፃሩ ተሽከርካሪዎቹ በእጃቸው የሌሉ ከሆነ የተሽከርካሪውን አይነት ከመጥቀስ በዘለለ ዝርዝር ሁኔታዎች የማይገለፁበት ሲሆን በአብዛኛው ከግማሽ በላይ የሆነው ክፍያ ለሻጭ አይከፈልም፡፡ ይህን የዳበረ የንግድ ልውውጥ ልምድ በተጠሪዎች እና በዙና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል የተደረገውን የውል ይዘት ጋር ስናገናዝበው ተጠሪዎች ተሽከርካሪዎቹ በ40ኛ ተጠሪ እጅ እንዳልነበሩ አያውቁም የሚያስብል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ ከሆነ አመልካቾች ማስታወቂያ ማስነገራቸው ከ40ኛ እና 41ኛ ውጪ ባሉት ተጠሪዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገው አስተዋጽኦ ምንድነው? የሚለውን መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ያስተላለፉት ማስታወቂያ ይዘት 40ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎችን እና ማሽነሪዎችን አስመጥቶ የሚሸጥ እና ወደፊትም የሚያስመጣ መሆኑን የሚገልጽ መሆኑን የማስታወቂያውን ቪዲዮ በመመልከት ያረጋገጡ ሲሆን በአመልካቾችም በማስታወቂያው ይዘት ላይ መካካድ የለም፡፡ አመልካቾች በሰበር ቅሬታቸው ላይ የሽያጭ ውል የተደረገው 40ኛ ተጠሪ በእጁ የነበሩትን ተሽከርካሪዎች ለመሸጥ ሳይሆን ገና የሚያስመጣቸውን ለመሸጥ የተደረገ ውል ስለሆነ ሃላፊነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንደሚታወቀው የንግድ ግንኙነት የማይዳሰሱ(intangible) ጉዳዮች፣ የንግድ መልካም ስም (good wil)፣ መተማመን (trust) እና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በንግድ ግንኙነት ውሳኔ ላይ ተጽኖ ያላቸው በመሆኑ 40ኛ ተጠሪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸው ተሽከርካሪዎች ሳይኖሩ እንዳሉ ተደርጎ አመልካቾች ባስተላለፉት ማስታወቂያ መነገሩ 40ኛ ተጠሪ ውሉን ለመፈጸም መልካም ስም(good will) ያለውና ውሉን መፈጸም የሚችል ስለመሆኑ እምነት

እንዲጣልበት ያደርጋል፡፡ ይህም ማለት ተጠሪዎች ውል ከመፈጸማቸው በፊት ውል የተዋዋሉባቸው ተሽከርካሪዎች እና የተለያዩ ማሽነሪዎች በ40ኛ ተጠሪ እጅ እንደነበሩ እና እንዳልነበሩ የማጣራት ግዴታቸውን አልተወጡም እንኳን ቢባል በአመልካቾች የተነገረው ማስታወቂያ በውሳኔያቸው ላይ ተጽኖ በማሳደር ወይም በማሳሳት በውል መሰረት ይፈጸምልናል በሚል እምነት ውል እንዲዋዋሉ የማድረግ አቅም ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የማስታወቂያ አዋጁ ዋነኛ አላማም እንደዚህ አይነት አሳሳች ማስታወቂያዎችን በመከላከል የንግድ ግንኙነቱን ጤናማ ማድረግ ነው፡፡ በተቃራኒው አመልካቾች በአዋጁ የተጣለባቸውን ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ማስታወቂያ የማስተላለፍ ግዴታቸውን ባለመወጣት 40ኛ ተጠሪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባቸው ተሽከርካሪዎች ሳይኖሩ ተሽከርካሪ አስገብቶ የመሸጥ ልምድ ያለው መሆኑ የሚያሳይ ማስታወቂያ በማስነገር በተጠሪዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስ አስተዋጽኦ በማድረጋቸው ከ40ኛ እና 41ኛ ተጠሪዎችን ሳይጨምር በሌሎች ተጠሪዎች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለባቸው መባሉ የማስታወቂያ አዋጁን እና ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት በፍትህ ብሔር ህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**4ኛውን ነጥብ በሚመለከት፡-**</u> 1ኛ አመልካች በጉዳዩ ላይ እንዲሰሙ የቆጠርኳቸው ምስክሮቼ አልተሰሙም፤ ማስታወቂያውንም ከ1ኛ አመልካች ቀድሞ ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሬድዮ አስተላልፎት የነበረ መሆኑን ገልጬ ጣልቃ እንዲገባ በጠየኩት መሰረት ሊታዘዝ ይገባ ነበር፤ ማስታወቂያው በሚነገርበት ጊዜም 40ኛ ተጠሪ የተወሰኑ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዳስገባ ወይም በሂደት ላይ እንደነበር ከጉምሩክ እንዲጣራ በጠየኩት አግባብ አለመጣራቱ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍትሐ ብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው የክርክሩን ፍሬ ጉዳይ ለማጣራት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136-138፣ 145፣ 256፣ 257 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር ሊጣሩ የሚገባቸው ጉዳዮች በአመልካቾች የቴሌቪዥን ጣቢያ የተነገሩት ማስታወቂያዎች ይዘት አሳሳች መሆን አለመሆኑ፣ ተጠሪዎች በዚህ ማስታወቂያ መነሻነት እምነት አሳድረው አስነጋሪው ጋር መዋዋላቸው እና ክፍያ በመፈፀም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ እና ይህ ደግሞ ከሕግ አንጻር የሚኖረው ውጤት ነው፡፡ የተጠቀሱትን ፍሬ ነገሮች ደግሞ ፍ/ቤቱ በቀረቡለት ማስረጃዎች አጣርቶ ድምዳሜ ላይ የደረሰባቸው በመሆኑ እና ማስታወቂያው በተነገረበት ጊዜም ሆነ ከዚያ በኂላ ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳልገቡ ስለተረጋገጠ 1ኛ አመልካች ምስክሮቼ አልተሰሙም፤ ከጉምሩክ ተቋምም ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ጠይቄ ነበር በማለት ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከስር ፍ/ቤት መዝገብ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ጣልቃ እንዲገባ የጠየቀው የአሁን 41ኛ ተጠሪን ሲሆን በዚሁ አግባብ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሬድዮ ጣልቃ እንዲገባ ጠይቄ ነበር በማለት የሚያነሳው ቅሬታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>**5ኛውን ነጥብ በሚመለከት**</u>**፡-** አመልካቾች ኃላፊነት አለባችሁ ከተባልን ኃላፊነታችን በአዋጁ አንቀፅ 34(1)(ለ) በተገለፀው አግባብ ኃላፊነታችን ከብር 10,000 እስከ ብር 100,000 ባለው ወሰን ውስጥ ሊሆን

ይገባል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ድንጋጌው ይህ ገንዘብ መቀጮ መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን የአዋጁን ድንጋጌ በተላለፉ ላይ የሚጣል ቅጣትን የሚመለከት ነው፡፡ በአመልካቾች እና በተጠሪዎች መካከል የውል ግንኙነት ስለሌለ እንዲሁም አዋጁን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ በአንቀፅ 30 ላይ መገለፁን እና ግልጽ የሆነ ሕግን መተላለፍ ጥፋት መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2035 ላይ ስለተመለከተ ለተጠሪዎች ያለባቸው የኃላፊነት መጠን ከውል ውጪ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መሰላቱ ተገቢ ነው፡፡ በጉዳት ምክንያት የሚከፈል ካሳም ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ መሆን ያለበት(Compensation shall be equal to damage) ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 ላይ ተመላክቷል፡፡ በአንፃሩ የደረሰው ጉዳት የተጎጂው አስተዋፅኦ ያለበት እንደሆነ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን ኃላፊነቱ በከፊል እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁጥር 2098(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች እንደ አንድ ጠንቃቃ ገዢ ተገቢውን ማጣራት ያላደረጉ በመሆኑ የአመልካቾች ኃላፊነት በፍ/ሕ/ቁጥር 2098 መሰረት በከፊል ነው ተብሎ መወሰኑ እንዲሁም ተጠሪዎች ለ40ኛ ተጠሪ ክፍያ በመፈጸም ከደረሰባቸው ጉዳት አመልካቾች ሊክሱ የሚገባው 1/4ኛውን ብቻ ነው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁጥር 179107 ሚያዝያ 9 ቀን 2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 178548ና 178724 ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 235566 የተጀመረው አፈጻፀም ታግዶ እንዲቆይ በሰ/መ/ቁጥር 193482 እና 193480 ነሀሴ 6 ቀን 2012 የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

## የ ል ዩ ነ ት ሀ ሳ ብ

እኛ በተራ ቁጥር 2 እና 4 ላይ የተሰየምን ዳኞች በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ በተሰጠ ትርጉም ባለመስማማታችን በሚከተለዉ መሰረት የልዩነት ሀሳባችንን አስፍረናል፡፡

አመልካቾች ማስታወቂያውን ከማሰራጨታቸው በፊት ድርጅቱ (40ኛ ተጠሪ) የታደሰ ንግድ ፍቃድ እንዳለዉ፣ ማስታወቂያው የድርጅቱን ትክክለኛ የንግድ እንቅስቃሴ የሚያሳይ፣ እውነተኛ፣ የማያሳስት፣

በማስታወቂያው የታዩት ተሽከርካሪዎች ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸዉ አገር ዉስጥ መግባታቸዉን ወይም ከቀረጥ ነጻ መብት ሊተላለፉ በሚችሉበት ሁኔታ አገር ዉስጥ የገቡ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታቸውን ባለመወጣት የማስታወቂያ ተከታታዮችን በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ ከ40ኛ እና 41 ተራ ቁጥር ከተጠቀሱት ተጠሪዎች በስተቀር ያሉ ተጠሪዎችን (ገዥዎችን) ሊያሣስት የሚችል ማስታወቂያ አስተላልፈዋል የሚለዉ ፍሬ ነገር በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ነዉ ተብሎ በአብላጫ ድምጽ በተደረሰበት ድምዳሜ እንስማማለን፡፡ሆኖም ማስታወቂያዉ አገር ዉስጥ ያልገቡ ተሽከርካሪዎች አገር ዉስጥ እንደገቡ የሚገልጽ በመሆኑ ይህንን ማስታወቂያ የሰሙ ተጠሪዎች(ገዥዎች) ሊሳሳቱ የሚችሉት በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ በተመለከተዉ ልክ ሳይሆን ተሽከርካሪዎቹ አገር ዉስጥ እንደገቡ ቆጥረዉ ግዥ ለመፈጸም ሻጭ(40ኛ ተጠሪ) ዘንድ እንዲቀርቡ ባደረገዉ ልክ ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ ማስታወቂያዉ ተጠሪዎች(ገዥዎች) እንደማንኛዉም ሰዉ በማስታወቂያዉ ላይ የታዩ ተሽከርካሪዎችን ተመልክተዉ ዉል ከመዋዋል አንጻር የፈለጉትን መወሰን እንዲችሉ ተጠሪዎች(ገዥዎች) 40ኛ ተጠሪ ዘንድ እንዲቀርቡ ከማድረግ ባለፈ ከሻጭ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ ሊያደርጋቸዉ በሚችል ሁኔታ ሊያሳስታቸዉ የሚችል ነዉ ብለን አናምንም፡፡

በፍትሐ ብሔር ሕጋችን ከቁጥር 1681 እስከ 1695 ድረስ ባሉ ድንጋጌዎች ላይ የአገራችን የዉል ሕግ የዉል ሀሳብ በማቅረብ (Offer) እና የቀረበዉን ሀሳብ በመቀበል (Acceptance) ዉል ሊቋቋም የሚችልበትን እንዲሁም የዉል ማቅረብን (Offer) ወይም መቀበልን (Acceptance) ማስቀረት የሚቻልበትን (*Withdrawal of Offer)*አግባብ ደንግጓል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1687 ስር እንደተደነገገዉ አንድ ሰዉ ተጠቃሚዉን ሳይለይ (የዉሉ ተዋዋይ ሊሆን የሚችል ሰዉ ለይቶ ሳይገልጽ) አንድን ነገር ለመስጠት፣አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ፈቃደኛ መሆኑን የሚያሳይ ሀሳቡን መግለጹ፣ይህንኑ ሀሳቡን የሚያሳዉቅ ማስታወቂያ በአደባባይ መለጠፉ ወይም በብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች…ወዘተ ማስነገሩ ወይም ማሳየቱ ተራ የሆነ ሀሳብን መግለጽን *(Communication of the intention or mere declaration of the intention without addressing particular person)* ከሚያሳይ በስተቀር ተለይቶ ለሚታወቅ ተዋዋይ ወገን የዉል ማቅረብ (Offer) ተግባር ፈጽሟል የሚያስብል አይደለም፡፡ይህ ተግባር ዉል የማቅረብ ተግባር (Offer) ተደርጎ የሚወሰድ ቢሆንና በማስታወቂያ ለብዙሃን የተገለጸዉን ሃሳብ ወይም በአደባባይ የተለጠፈዉን ማስታወቂያ አይተዉ የመጡ ሰዎች በሙሉ ዉል የመቀበል ተግባር (Acceptance) ፈጽመዋል ወደሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ያደርሳል፡፡ እንዲሁም ሀሳቡን በማስታወቂያ የገለጸዉ ሰዉ ከብዙ ሰዎች ጋር ብዙ ዉል ፈጽሟል ወደሚል በተግባር ተጨባጭ ወደማይሆን የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል፡፡ በያዝነዉ ጉዳይ አመልካቾች ተዋዋይ ወገን አይደሉም፡፡40ኛ ተጠሪ ከዉጭ አገር ያስመጣቸዉና ለወደፊትም የሚያስመጣቸዉ ተሽከርካሪዎች እንዳሉት በአመልካቾች በኩል ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ያደረገዉ ለመላዉ ሕዝብ እንጂ ከ4ኛ እና 41ኛ ተጠሪዎች በስተቀር በተለየ ሁኔታ ለአሁን ተጠሪዎች አይደለም፡፡በመሆኑም ይህ የ40ኛ ተጠሪ አድራጎት ተራ የሆነ ሃሳብን የመግለጽ ድርጊት (*a mere declaration of the intention)* እንጂ ለተጠሪዎች(ለገዥዎች)

ዉል የማቅረብ ተግባር (Offer) ፈጽሟል የሚያስብል አይደለም፡፡በመሆኑም ከላይ በተመለከተዉ መሰረት 40ኛ ተጠሪ በአመልካቾች ሚዲያ እንዲተላለፍ ባስደረገዉ አሳሳች ማስታወቂያ መነሻ ተጠሪዎች(ገዥዎች) ወደ 40ኛ ተጠሪ ዘንድ የሚቀርቡት ዉል የመቀበል ተግባር (Acceptance) ለመፈጸም ሳይሆን በእርግጥም በማስታወቂያዉ ላይ የተነገረዉ እዉነት መሆኑን ወይም ተሽከርካሪዎቹ በ40ኛ ተጠሪ ይዞታ ስር እንደሚገኙ አረጋግጠዉ የግዥ ዉል መፈጸም የሚችሉበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩን በተግባር ለማረጋገጥ ነዉ፡፡ተጠሪዎች(ገዥዎች) ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል ከመዋዋላቸዉ በፊት ማስታወቂያዉን ከማየትና ከመስማት ባለፈ ገና ዉል ስላልተዋዋሉ በማስታወቂያዉ ላይ የታዩትን ተሽከርካሪዎች እንደገዙ ቆጥረዉ 40ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎችን እንዲያስረክባቸዉ መጠየቅ አይችሉም፡፡ይህንን ማድረግ የሚችሉት ለመግዛት የፈለጉት ተሽከርካሪ በእርግጥም በ40ኛ ተጠሪ ይዞታ ስር መኖሩን በማረጋገጥ አሊያም 40ኛ ተጠሪ ዘንድ በሄዱበት ጊዜ 40ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪዎቹ አገር ዉስጥ ገብተዉ በእጇ ይገኛሉ ብሎ የተሽከርካሪዎቹን ልዩ መገለጫ አሳይቶ የነገራቸዉን በማመን የሚገዙትን ተሽከርካሪ መርጠዉ ዋጋ በመስማማት የተሽከርካሪዉን ሻንሲ ቁጥር፣የሞተር ቁጥር፣የመጫን አቅሙን፣አይነቱን፣የተመረተበትን አመት እና መልኩን ጭምር የሚያሳይና ስለዋጋዉ አከፋፈል ጭምር ገልጸዉ ዉል ሲዋዋሉ ነዉ፡፡

ሆኖም በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ የተመለከተዉና የሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠዉ የዉሎቹ ይዘት እንደሚያሳየዉ ተጠሪዎች(ገዥዎች) ከ40ኛ ተጠሪ ጋር በተዋዋሉት ዉል ላይ የተሽከርካሪዎቹ ሻንሲ ቁጥር፣የሞተር ቁጥር፣የመጫን አቅማቸዉ፣ አይነታቸዉ፣ የተመረቱበት አመት እና መልካቸዉ አልተገለጸም፡፡ እነዚህ የተሽከርካሪዎችን ልዩ መገለጫዎች በዉሉ ላይ ሳይገለጹ ዉሉን መዋዋላቸዉ በግልጽ የሚያሳየዉ ተጠሪዎች(ገዥዎች) ማስታወቂያ ሰምተዉ ተጠሪ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ በማስታወቂያዉ ላይ እንደተነገረዉ እንዳልሆነ ወይም ደግሞ አገር ዉስጥ ገብተዋል የተባሉት ተሽከርካሪዎች አገር ዉስጥ እንዳልገቡ(አገር ዉስጥ ገብተዉ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ልዩ መገለጫዎች ስለሚታወቁ በዉሉ ላይ ይገለጽ ስለነበር) አዉቀዉ ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል መዋዋላቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአመልካቾች የተላለፈዉ አሳሳች ማስታወቂያ ተጠሪዎች 40ኛ ተጠሪ ዘንድ እንዲሄዱ ከማድረግ ባለፈ ተሽከርካሪዎቹ አገር ዉስጥ እንደገቡ አድርገዉ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዙና ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ አድርጓቸዋል ብሎ መደምደም ከላይ በተጠቀሱ ድንጋጌዎች ስለዉል አመሰራረት የተደነገገዉን የሚቃረን ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል፡፡

ስለሆነም የአመልካቾች ድርጊት ተጠሪዎች(ገዥዎች) ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ የማያደርግ ምክንያት ስለሆነ አመልካቾች መጠየቅ ያለባቸዉ 40ኛ ተጠሪ እንደዉሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት ተጠሪዎች(ገዥዎች) ላይ ለደረሰዉ ጉዳት በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀጽ 27/1 እና 30 መሰረት ሳይሆን ተጠሪዎች(ገዥዎች) አሳሳች ወይም እዉነተኛ ያልሆነ ማስታወቂያ ሰምተዉ 40ኛ ተጠሪ ዘንድ እንዲሄዱ በማድረግ ጥፋት በመፈጸማቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 27/1 እና 34(1/ለ) መሰረት በመቀጫ እንዲቀጡ በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካቾች ከዉል ዉጭ በሆነ አኳኋን ከ40ኛ እና 41ኛ ተጠሪዎች

ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ኃላፊ ይሆኑ የነበረዉ ያስተላለፉት አሳሳች ማስታወቂያ ተጠሪዎች ዉል እንዲዋዋሉ አድርጓቸዉ ቢሆን ኖሮ ነበር ፡፡

በተጨማሪም እንደሚታወቀዉ የንግድ ወይም የንግድ ድርጅት መልካም ስም(business goodwill) ከንግድ ስሙ እና/ወይም ከንግድ ምልክቱ ካገኘዉ እዉቅና፣ከደንበኞቹ ጋር ካለዉ መልካም ግንኙነት፣ካለዉ ሰፊ የደንበኞች መሰረት፣ ከሠራተኞቹ ጋር ካለዉ መልካም ግንኙነት እና ከሚጠቀመዉ ቴኪኖሎጂ ጋር በተያያዘ አንድ ንግድ (የንግድ ድርጅት) የሚያካብተዉ የማይዳሰስ ሀብት(incorporeal asset) ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ የንግድ መልካም ስም አንድ የንግድ ድርጅት እንደተቋቋመ እንዲሁ ተንስቶ በብዙሃን መገናኛ ስለተሰማራበት ንግድ ዘርፍ ወይም ስለሚሸጠዉ እቃ በሚዲያ ማስታወቂያ በማስነገር የሚያገኘዉ አይደለም፡፡ በመሆኑም 40ኛ ተጠሪ ወይም ሻጭ በአመልካቾች በኩል ተሽከርካሪዎችን፣ ማሽነሪዎችንና መሳሪያዎችን ከዉጭ አገር እንዳስመጣና አስመጥቶም እንደሚሸጥ ማስታወቂያ በማስነገሩ ብቻ 40ኛ ተጠሪ መልካም ስም እንዳለዉና የዉል ግዴታዉን በአግባቡ ይወጣል በማለት ተጠሪዎች(ገዥዎች) ግምት እንዲወስዱ እና ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ አድርጎ ማስታወቂያዉ እንዳሳሳታቸዉ ተደርጎ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ ላይ የተደረሰበትም ድምዳሜ የንግድ መልካም ስም ጽነሰ ሀሳብን ያልተከተለ ነዉ ብለን እናምናለን፡፡እንዲሁም ተጠሪዎች(ገዥዎች) እንደጠንቃቃ ገዥ 40ኛ ተጠሪ መልካም የንግድ ስም ከማጣራት እና በእርግጥም ለሽያጭ ዝግጁ የሆኑ ከዉጭ አገር ገብተዉ በ40ኛ ተጠሪ እጅ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች መኖር አለመኖራቸዉን አጣርተዉ ዉል ከመዋዋል አንጻር ያለባቸዉን ኃላፊነት ወደጎን በመተዉ የአመልካቾችን ኃላፊነት ከማስታወቂያ እና ከዉል አመሰራረት ሕግጋት አቋም ዉጭ በሆነ አኳኋን በማስፋት የሚያከብድና የሁለቱንም ኃላፊነቶች በሚዛኑ ያላየ ድምዳሜ ነዉ ብለን እናምናለን፡፡

ስለሆነም አመልካቾች አሳሳች ማስታወቂያ በማስተላለፋቸዉ በፈጸሙት ጥፋት ልክ በአዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀጽ 27/1 እና 34(1/ለ) መሰረት በመቀጫ ሊቀጡ ይገባል እንጂ ያስተላለፉት አሳሳች ማስታወቂያ ተጠሪዎች(ገዥዎች) ከ40ኛ ተጠሪ ጋር ዉል እንዲዋዋሉ ስላላደረጋቸዉ ለተጠሪዎች(ለገዥዎች) በዉሉ መሰረት ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰ ኪሳራ የጉዳት ካሳ ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተሻሽሎ መወሰን ነበረበት በማለት ከአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ በሀሳብ ተለይተናል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 191968

ቀን፡- ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ዋኬኔ ዲንቃ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኤብሳ እጅጉ

2. አቶ ታሪኩ ዱጋሳ

3. ወ/ሮ ደሜ ሞቲ

} ቀረቡ

4. አቶ ደበላ እጅጉ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ጥቅምት 01 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ በጉዱሩ ወረዳ ጉደኔ ጫላ ሲበሬ ቀበሌ የሚገኝ 15.5 ሄክታር መሬት ወላጅ እናቴ ንጉሴ ኦብሴ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ሕይወቷ ከማለፉ በፊት ስትጠቀምበት የነበረውን መሬት ስለያዙ እንዲለቁልኝ እና መሬቱን በማረስ የተጠቀሙበት የዓላባ ግምት በድምሩ ብር 3,607,212.00 እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ ይዞታውን ከ1971 ዓ/ም ጀምሮ የምንጠቀምበት ስለሆነ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16

መሠረት የገጠር መሬት ይዞታ ጋር የሚፈጠር አለመግባባት በሽምግልና ለመፍታት ጥረት መደረግ እንዳለበትና አለመግባባቱ ካልተፈታም ክሱ ለወረዳ ፍርድ ቤት እንደሚቀርብ የተመለከተ ስለሆነ አመልካች የገጠር መሬት ይዞታ ክርክሩን የሰብል ምርትና ዓላባን ምክንያት በማድረግ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ መመስረት የለበትም ብለናል፡፡ ክሱ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም እንጂ የሕግ ድጋፍ አለው ቢባል እንኳን ተጠሪዎች ይዞታውን ለ19 ዓመት የያዙት በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ ክሱ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክር ሳይሆን የውርስ ሀብት ጥያቄ በመሆኑ በሀብቱ ግምት መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ክስ የቀረበበትን ይዞታ ተጠሪዎች ለ18 ዓመት የያዙ ስለመሆኑ አመልካችም ያመኑ በመሆኑ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ነው ተብሎ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ካለ ክሱን ተቀብሎ ማስተናገድ አልነበረበትም፡፡ ክርክሩ የውርስ ሀብትን የሚመለከት በመሆኑና ይርጋው መቆጠር ያለበት አውራሼ ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ሊታገድ አይገባም፡፡ ተጠሪዎች ይዞታውን ለ19 ዓመት መያዛቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ የውርስ ክርክርም ቢሆን የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ክሱን ተቀብሎ በማስተናገድ ውሳኔ መስጠቱ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ከ1ኛ-3ኛ ያሉት ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ የእርሻ መሬት ላይ የሚገኝ ሰብል ግምቱ በብር 3,607,212.00 ገንዘብ ላይ የቀረበው ክስ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው፡፡ ይዞታውም ከ39 ዓመት በላይ በእጃችን የቆየ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡ 4ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ ለመመልከት የሥረ-ነገር ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው አመልካች ጥቅምት 01 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ በጉዱሩ ወረዳ ጉደኔ ጫላ ሲበሬ ቀበሌ የሚገኝ 15.5 ሄክታር መሬት ወላጅ እናቴ ንጉሴ ኦብሴ ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ/ም ሕይወቷ ከማለፉ በፊት ስትጠቀምበት የነበረውን መሬት ስለያዙ

እንዲለቁልኝ እና መሬቱን በማረስ የተጠቀሙበት የዓላባ ግምት በድምሩ ብር 3,607,212.00 እንዲከፍሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በዚህ ሂደት ከሚመረምራቸው ጉዳዮች መካከል ጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ዋነኛው ነው፡፡ የፍርድ ቤት ሥልጣን ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction)፣ የሥረ-ነገር ሥልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ወይም ከበባዊ ሥልጣን (local or territorial jurisdiction) በሚል የተከፋፈለ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ የሚመረመረው የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረነ-ገር ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ የሥረ-ነገር ሥልጣን በአንድ ሀገር ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች መካከል በዋነኛነት ታሳቢ የሚያደርገው የፍርድ ቤቱን አቅም ወይም ችሎታ (competence of the court)፣ ፍትሐዊነትን፣ ኢኮኖሚንና የሥራና ሀብት ክፍፍልን መሠረት አድርጎ በገንዘብ ግምት (pecuniary jurisdiction) ወይም በጉዳዩ ዓይነት (subject matter jurisdiction) ወይም ጉዳዩን በመጀመሪያ ሆነ በይግባኝ ደረጃ (original and appellate jurisdiction) የሚያዩት ሥለመሆኑ በፍርድ ቤቶች መካከል የሚመለከቱት ጉዳዩችን የሥልጣን ድልድል የሚደረግበት ነው፡፡

አመልካች ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ሁለት ዳኝነቶች በአንድ ላይ ተጣምረው የቀረቡበት ነው፡፡ የመጀመሪያ የገጠር መሬት ይዞታ እንዲለቀቅላቸው ሲሆን ይሕም በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16(1)(ረ) ላይ በወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ጉዳይ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሁለተኛው ዳኝነት የዓላባ ግምትና በይዞታው ላይ ያለ ንብረት ግምት በድምሩ ብር 3,607,212.00 እንዲከፈላቸው ያቀረቡት የገንዘብ ግምትን መሠረት ያደረገው ነው፡፡ ክሱ ጥቅምት 01 ቀን 2011 ዓ/ም ሲቀርብ የሥረ-ነገር ሥልጣን እንደገና ያደላደለው የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 ዓ/ም በክልሉ ምክር ቤት ጸድቆ ሥራ ላይ የዋለና ስድስት ወር የመሸጋገሪያ ጊዜ ያለው ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 30(3) ሆነ በቀድሞው አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(3) መሠረት ብር 3,607,212.00 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው፡፡

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 በዋነኛነት ስለገጠር መሬት ባለይዞታዎች ስላላቸው መብትና አስተዳደር ጋር የተያያዙ መሠረታዊ መብቶችን የሚመለከት ቢሆንም ስለፍርድ ቤት ሥልጣን የተመለከተው ድንጋጌ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ይዘት ያለው ነው፡፡ በአዋጁ ላይ የተመለከተው ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዘ ክርክር የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ስለመሆኑ ያመለከተው ክፍል ከሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሆነ ከፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ የተመለከቱ ጉዳዮች ቢኖሩም ከገጠር መሬት ጋር ለተያያዘ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 130/1999 ልዩ ሕግ ስለሆነ በሕግ አተረጓጎም መርሕ መሠረት ልዩ ሕጉ በቀዳሚነት መተግበር አለበት፡፡ ስለሆነም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ክርክር፤ ክርክሩ ይዞታ

መብትን ለማስከበርም ሆነ የውርስ መብትን ወይንም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ሌላ መብትን ለማስከበር፤ ክሱ መቅረብ ያለበት ለወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከገጠር መሬት ውርስ መብት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክስ በአዋጅ ቁጥር 130/1999 የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ተፈጻሚነት የለውም ማለቱ ሥህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

በሌላ በኩል የገጠር መሬት አዋጁ ሙሉ የሥነ-ሥርዓት ሕግን የሚሸፍን ድንጋጌዎች የሌሉት በመሆኑ ሌሎች የሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ሲኖሩ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ሆነ የኦሮሚያ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡ በገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 130/1999 ላይ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ ከሚቀርብ ክስ ጋር ተጣምረው በአንድ ላይ ሊቀርቡ ስለሚችሉ ጉዳዮች ሆነ በአንድ ላይ ተጣምረው የሚቀርቡ የተለያዩ ዳኝነቶች ሲኖሩ የፍርድ ቤቱ ሥልጣን እንዴት ይወሰናል በሚሉና በሌሎች ከክርክር አመራር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች የሚመለከት ዝርዝር ድንጋጌ የለውም፡፡ ሕጉ በዋነኛነት ስለገጠር መሬት ባለይዞታዎች መብትና መሬት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለመወሰን የወጣ በመሆኑ ዝርዝር የሥነ-ሥርዓት ሕጎችን እንዲሸፍንም አይጠበቅበትም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 120087 (በቅጽ 21 እንደታተመ) በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 218 እና 216 የተመለከተውን ከመሬት ሕጉ ጋር በማገናዘብ የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ እና ዓላባውን መሠረት ያደረገ ክስ ተነጣጥሎ በቀረበ ጊዜ ስለሚኖረው ወጤት ዋና ጭብጥ አድርጎ ክሶቹ ተነጣጥለው መቅረባቸው የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ያልተከተለ ነው ተብሎ ውድቅ ሊደረግ አይገባም በማለት ትርጉም የሠጠበት ቢሆንም ሁለቱም ዳኝነቶች አብረው ሲቀርቡ እና የፍርድ ቤት ሥልጣን አከራካሪ ሲሆን የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምን እንደሚሆን በጭብጥነት ይዞ ያልመረመረ በመሆኑ ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.17(2) ላይ በአንድ ክስ ውስጥ የተለያዩ ዳኝነቶች ተጣምረው ሲቀርቡ የፍርድ ቤቱ ሥልጣን የሚወሰነው ከፍተኛ ግምት ያለውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ሁለት ዳኝነቶች ያቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያ ግምት የሌለው የገጠር መሬትን ለመረከብ የቀረበ ሲሆን ይሕም ወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው፡፡ ሁለተኛው የዓላባ ጥቅም መሠረት ያደረገ ብር 3,607,212.00 ለማስከፈል የቀረበ ክስ ሲሆን ጉዳዩም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው፡፡ ከቀረቡት ሁለት ዳኝነቶች ከፍተኛ ግምት ያለው ሁለተኛው ዳኝነት በመሆኑ ክሱ ተጠቃሎ መቅረብ ያለበት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለሆነ የሥረ-ነገር ሥልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ክሱን ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረባቸው ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1)(ለ) መሠረት ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ወደ ክርክር ሂደት ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ የመመርመር ኃላፊነት አለበት፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክሱ እንደቀረበለት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን

ሳይመረምር ውሳኔ በሠጠ ጊዜ ክሱ የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ነው ማለቱ ተገቢነት የለውም፡፡ ሥልጣን የለኝም ካለም ክሱን ለመመልከት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት መመለስ ሲገባው በሥረ-ነገሩ ተመልክቶ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ የክርክር አመራር ግድፈት ያለበት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ሆኖ እያለ ሥልጣን የለኝም ማለቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡ ነገር ግን ክሱን ለመመልከት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ክሱን ተቀብሎ የይርጋ ክርክሩን መመርመሩ በውጤት ደረጃ ተቀብለነዋል፡፡

ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ አመልካች ላቀረቡት የውርስ ገጠር መሬት ይዞታና ገንዘብ ይከፈለኝ ክስ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ የይርጋ ክርክሩ የቀረበው አመልካች ክሱን ለማቅረብ የክስ የማቅረቢያ ጊዜው (limitation of action) አልፏል በሚል ነው፡፡ ይርጋ መብትን (extinctive prescription) እና/ወይም መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን ቀሪ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደ ክሱ መሠረት ዓይነት ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብና ሕግ የተለያየ ነው፡፡ የቀረበዉ ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶች መሰረት እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸዉ በከሳሽ ክስ ላይ የተመለከተዉን የክስ ምክንያት ነው፡፡ ሁሉም የገጠር የእርሻ መሬት ጋር የተያያዘ የክስ ዓይነት ላይ ተመሳሳይ የይርጋ ደንብ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ክሱ ይዞታ እንዲለቀቅ የሚቀርብ የይዞታ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስ ወይም የገጠር መሬት ውርስ ይገባናል በሚል የቀረበ ክስ ወይም ከገጠር መሬት ጋር የተያያዘ ውልን መሠረት ያደረገ ክስ መሆኑ እየታየ እንደ ክሱ የዳኝነት መሠረት ክሱ በይርጋ ቀሪ የሚሆንበት ጊዜና ለጉዳዩ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ወይም ድንጋጌ የተለያየ ነው፡፡ ስለሆነም የክሱን መሠረት መለየት የይርጋ ክርክሩንም ሆነ ቀጣይ ያሉ ሂደቶችን ለመመራት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የአመልካች የክስ መሠረት የሆነው የገጠር መሬት ውርስን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ያለዉ የይርጋ ድንጋጌ ስለመኖሩ የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 የተለየ ድንጋጌ የለዉም፡፡ ይህ ማለት ግን ከገጠር መሬት ውርስ መብት ጋር የተያያዘ በሚቀርብ ክስ ላይ የይርጋ ደንቦች ተፈፃሚ አይሆኑም ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ በሚቀርብ ክስ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ በፍ/ሕ/ቁ. 1677(1) እና 1845 የተመለከተው የ10 ዓመት ጊዜ ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተደረገ የቃል ክርክር መሬቱ በተጠሪዎች ከተያዘ ከ18 ዓመት በላይ መሆኑን አምነው የተከራከሩ ስለመሆኑ ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም ክስ የቀረበው ከ10 ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱን በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ መደረጉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

## ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 318367 ጥር 19 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 220530 ሰኔ 12 ቀን 2011 ዓ/ም፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 23958 ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

## የልዩነት ሃሳብ

እኛ ስማችን በ2ኛ እና 5ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተሰየምነዉ ዳኞች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ክስ ተቀብሎ የማየት ስልጣን የለዉም የሚል ሃሳብ ስላለን የልዩነት ሃሳባችንን እንደሚከተለዉ አስፍረናል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ የገጠር መሬትን የሚመለከት ነዉ፡፡ ከእርሻ መሬት ይዞታ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሳ ክርክር ጉዳዩ በሚመለከታቸዉ ተከራካሪዎች በዉይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር በተደነገገዉ መሠረት የሚወሰን ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት በወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12 ስር ተመላክቷል፡፡ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሳ የይዞታ ይገባኛል ክርክር እልባት የሚያገኝበትን አግባብ የኦሮሚያ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/99 ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት ክርክሮቹ በወረዳዉ ፍርድ ቤት ቀርበዉ ከመታየታቸዉ በፊት በግራ ቀኙ ስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና መታየት የሚገባቸዉ ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 16 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣዉ ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 18 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከገጠር መሬት ይዞታ መብት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በተቻለ መጠን በአካባቢዉ ሽማግሌ ካልሆነ ደግሞ ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ቀርበዉ በመጀመሪያ መታየት እንዳለባቸዉ ከላይ በተመለከቱት የፌዴራል እና የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር

እና አጠቃቀም አዋጆች የተደነገገበት መሠረታዊ ዓላማም በአርሶ አደሮች መካከል በእርሻ መሬት ይዞታ ምክንያት የሚነሱ አለመግባባት ጉዳዮች በቅርብ ታይተዉ በተቻለ መጠን ወደ ሙግት ሳይገባ እልባት እንዲሰጠዉ በማድረግ ወደ ሙግት የሚገባ ከሆነም ሙግቱ ቅርብ በሆነዉ በወረዳ ፍርድ ቤት እንዲታይ በማድረግ አርሶ አደሮች ከመሬት ይዞታ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ለምርት ስራ የሚያዉሉት ጊዜ እንዲሁም ገንዘብ ያላግባብ እንዳይባክን ጥበቃ ለማድረግ ነዉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ ከሚቀርብ ዳኝነት ጋር በተያያዘ የሚነሳን የስልጣን ጥያቄ በመወሰን ረገድም ይህንኑ የአዋጁን ዓላማ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ትርጓሜ መስጠት ያስፈልጋል የሚል እምነት አለን፡፡

አብላጫዉ ድምጽ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ በሚል ለደረሰበት ድምዳሜ የሰጠዉ መሠረታዊ ምክንያት የይዞታ ክርክር እና የአላባ ግምት አብረዉ በመቅረባቸዉ የተነሳ የፍርድ ቤት ስልጣን አከራካሪ የሆነ እንደሆነ የዳኝነት ስልጣን መወሰን የሚቻለዉ ከፍተኛ ግምት ያለዉን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 17(2) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ መሆኑን እና የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅም ይህን አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ የሌለዉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በእርግጥ ሁለት የተለያዩ ዳኝነቶች ተጣምረዉ በአንድ ላይ ሲቀርቡ የፍርድ ቤቱን ስልጣን ለመወሰን ከፍተኛ ግምት ያለዉን ዳኝነት መሠረት በማድረግ ነዉ የሚለዉን እኛም የምንስማማበት ነዉ፡፡ ይሁንና የሥ/ሥርዓት ህጉ በወጣበት ወቅት በነበረዉ የመንግስት አወቃቀር እና የፍርድ ቤቶች የስልጣን ድልድል መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረት (የማይንቀሳቀስ ንብረት መሬትን እንደሚያካትት በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 1130 ላይ ከተመለከተዉ መገንዘብ ይቻላል) እንደየአግባብነቱ ለወረዳ ፍርድ ቤት፣ ለአዉራጃ ፍርድ ቤት እና ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 13፣ 14 እና 15 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በየደረጃዉ ካሉት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለዉ የትኛዉ ፍርድ ቤት እንደሆነ የሚወሰነዉ የንብረቱን ግምት ወይም ከንብረት ማስመለስ ጥያቄዉ ጋር አብሮ ተያይዞ የሚቀርብ የገንዘብ ጥያቄ (ለምሳሌ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ከሚቀርብ ክስ ጋር ከንብረቱ የሚገኝ ጥቅም ወይም ዉዝፍ ኪራይ ወይም ከንብረቱ የሚገኘዉን ገቢ አጠቃሎ ማቅረብ እንደሚቻል ስለሚደነግገዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 218 /ሀ/ ማየት ይቻላል) መሠረት በማድረግ ነዉ፡፡ ከላይ የተመለከተዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 17 (2) ድንጋጌም ይህንኑ እዉነታ መሠረት በማድረግ የተቀረጸ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ፣ ከእርሻ መሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠር አለመግባባት ቢቻል ከሙግት ዉጪ በአማራጭ በአገር ሽማግሌዎች እንዲታይ ካልሆነም ለወረዳ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ መቅረብ እንዳለበት የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ አስገዳጅነት ባለዉ ኃይለ ቃል በግልጽ የሚደነግግ በመሆኑ ከዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ በጠቅላላዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖራቸዉም፡፡ ይህም ማለት የእርሻ

መሬትን የሚመለከት የዳኝነት ጥያቄ ከመሬቱ ከሚገኘዉ የአላባ ግምት ጭምር መቅረቡ እና የአላባዉ ግምት ከወረዳዉ ፍርድ ቤት ስልጣን በላይ ሆኖ መገኘቱ ዳኝነቱ በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ምክንያት ሊሆን አይገባም ማለት ነዉ፡፡ ከአላባ ግምት ጋር ተጣምሮ በመቅረቡ ምክንያት ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ክርክር ለዚህ ዓላማ በአዋጁ የተዘረጋዉን ሥርዓት ሳይከተል የቀረበዉን የገንዘብ ግምት ለማየት ስልጣን ላለዉ ለዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ማድረግ ከላይ የተመለከተዉን የአዋጁን ዓላማ የሚያፋልስ ዉጤት ይኖረዋል፡፡ በአዋጁ በተዘረጋዉ ስርዓት መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ ካለመፈለግ በአላባ እያሳበቡ ጉዳዩ በቀጥታ በተለይም ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ለሚፈልጉ ሰዎችም በር የሚከፍት ሲሆን ይህም አዋጁ በዚህ ረገድ የዘረጋዉ ስርዓት ወጥነት ባለዉ መልኩ ተግባራዊ እንዳይሆን ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ላይ ከስልጣን ጋር በተያያዘ የተመለከቱት መርሆዎች እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠር አለመግባባት ለማየት ስልጣን ያላቸዉን አካላት አስመልክቶ አዋጁ በልዩ ሁኔታ የደነገገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 17(2) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡

ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ሁሉ ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንዲሁም አጠቃላይ ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ የሚስተናገድበትን ሥርዓት አስመልክቶ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ አጠቃላይ ዓላማ አንፃር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ ያላግባብ የተያዘ ገጠር መሬት እንዲመለስለት ክስ የሚያቀርብ ወገን ከመሬቱ ከሚገኝ የአላባ ግምት ጋር አጣምሮ ማቅረብ እንደሌለበት እና ፍርድ ቤትም ሊቀበለዉ እንደማይገባ በሰ/መ/ቁጥር 120087 (ቅጽ 21 ላይ እንደታተመዉ) ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 108060 ላይም ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በአላባ ግምት ሰበብ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚቀርብ ክርክር ይህንኑ አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 16 ላይ ከተዘረጋዉ ሥርዓት ዉጪ ሊሆን የማይገባዉ መሆኑን ነዉ፡፡

በመሆኑም የአሁን አመልካች ለክርክሩ መነሻ ከሆነዉ መሬት ላይ መብት አለኝ የሚል ከሆነ በቅድሚያ ጥያቄዉን በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ መሠረት በየደረጃዉ ባሉት አካላት አቅርቦ መብቱን ካረጋገጠ በኋላ የአላባ ጥያቄዉን ማቅረብ ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ ዳኝነቱን ከአላባ ግምት ጋር በማጣመር ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረቡ ስህተት ሲሆን፣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህን የአመልካችን ክስ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ በአንድ በኩል ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለዉም እያለ በሌላ በኩል ስልጣን ሲኖረዉ ብቻ የሚመረምረዉን የይርጋ ጉዳይ መሠረት በማድረግ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ዉሳኔ መስጠቱ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶችም ይህን ማረም ሲገባቸዉ ያላግባብ (ስልጣን ለሌለዉ) ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን በመመርመር የሰጡት ዉሳኔ ከገጠር መሬት ዳኝነት ጋር በተያያዘ በክልሉ

የገጠር መሬት አዋጅ ላይ የተመለከተዉን አጠቃላይ ዓላማ የሚያፋልስ ከመሆኑም በላይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ በተመለከቱት መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በስር በየደረጃዉ ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ሙሉ በሙሉ ሊሻር ይገባዋል በሚል ሃሳብ ከአብላጫዉ ድምጽ በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.175719

ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ረዲ አህመድ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ መኪያ ሀሰን - ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.223910 በ10/8/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጋብቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ጋብቻችን በፍቺ እንዲፈርስ ወስኗል፡፡ ስለሆነም አመልካች እና ተጠሪ በጋራ ያፈራነዉ በሱሉልታ ከተማ ልዩ ስሙ ድሬ ጀርባ የሚገኘዉ የቤት ቁጥር 632 SUL 2.1 የሆነዉ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት እንድንካፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረቡት መልስ ይህን ቤት ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ ከተቋረጠ በኋላ ተጠሪ ከግለሰብ ገንዘብ ተበድሬ የተሰራ ስለሆነ የጋራ ንብረት ሳይሆን የግል ንብረቴ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር የሰዉ ምስክሮች በመስማትና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻቸዉ ባለመግባባት ያለ ስምምነት ከተቋረጠ በኋላ የአሁን ተጠሪ በግላቸዉ ያፈሩት የግል ንብረት እንጂ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት አይደለም፤ የብድር ገንዘብ በተመለከተ የአሁን አመልካችን አይመለከትም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ

ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ15/8/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡- አመልካች እና ተጠሪ በመካከላችን የነበረዉ ጋብቻ የፌ/መ/ደ/ሽሪዓ ፍ/ቤት በ8/5/2006 ዓ.ም በፍቺ ዉሳኔ ያፈረሰ ሲሆን ለክርክር ምክንያት የሆነዉ ቤት ጋብቻችን በፍቺ ዉሳኔ ከመፍረሱ በፊት በጋብቻዉ ዉስጥ እያለን የተገዛና የጋራ ንብረታችን ሆኖ ሳለ፣ አመልካች ባቀረበዉ ማስረጃም አረጋግጦ እያለ፣ የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱ የተጠሪ የግል ሀብት እንጂ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ዉድቅ ሆኖ እንዲታረምልኝ ፣ቤቱ የጋራ ንብረታችን መሆኑ ተረጋግጦ ግማሽ ድርሻዬ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል።

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት ሐምሌ 8 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ የሥር ፍ/ቤቶች የቀረበዉን የሰዉ ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃ መርምረዉ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ የመኖሪያ ቤት የተጠሪ የግል ሀብት እንጂ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለዉ በመሆኑ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ክርክራቸዉን አቅርበዋል። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር፣ ለዚህ ቅሬታ መነሻ የሆኑትን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፣የግራ ቀኙ ጋብቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በፍቺ ዉሳኔ ፈርሶ እያለ፣ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል። አመልካች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግልጽ ጽፎ ካቀረቡት ክስ፣ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ እንደሚቻለዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ ጋብቻ በመካከላቸዉ በተፈጠረዉ አለመግባባት፣ ጉዳዩ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ.ቁ.209/06 በ8/5/2006 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የግራ ቀኙን ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ ወስኗል። ከዚህ ዉሳኔ በኋላ የአሁን አመልካች የፍቺ ዉሳኔ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ክስ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን ፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔን በማጽናት መወሰኑን የሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል።

እንግዲህ እንደሚታወቀዉ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕግ መንግስት አንቀጽ 34 [5] ሥር እንደተመለከተዉ “ይህ ሕገ መንግስት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሀይማኖቶች ወይም በባህሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፤ ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን” ደንግጎ እናገኛለን።

እንዲሁም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 78 [5] ሥር በተደነገገዉ አግባብ የሀይማኖት እና የባህል ፍ/ቤቶች ሊቋቋሙ ወይም እዉቅና ሊሰጣቸዉ እንደሚችል ተመልክቷል። ይህን የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ ተከትሎ ከእስልምና ሀይማኖት አንጻር የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992 ወጥቶ እየተሰራበት ይገኛል። በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሰረት የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የወል የዳኝነት ስልጣን የሚኖራቸዉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩ ጉዳዮችን የሚመለከት ሆኖ፣ ፍ/ቤቶቹ ይህን የዳኝነት ስልጣን ሊኖራቸዉ የሚችለዉ ተከራካሪ ወገኖች በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ በፈቃዳቸዉ መርጠዉ የቀረቡ ከሆነ ብቻ መሆኑን ይደነግጋል። ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል በአዋጁ አንቀጽ 4 [1፣ ሀ] ሥር የተጠቀሱት ማናቸዉም የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የቀለብ አወሳሰን፣ አካለ መጠን ያላደረሱ ሕጻናት ሞግዚትነት እና በቤተሰብ ተዛምዶ ላይ የሚነሱ ጉዳዮች መሆናቸዉን ተመልክቷል። ተከራከሪ ወገኖች በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት ፈቃደኝነታቸዉን እና ተቃዉሟቸዉን የሚገልጹትና የሚያረጋግጡት በአዋጁ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከተዉ አግባብ ይሆናል። ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ በግልጽ ፈቃደኝነቱን እንደገለጸ እንደሚቆጠር ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። ጉዳዩ የቀረበለበት የሸሪዓ ፍ/ቤት ደግሞ ሌላ ተከራካሪ ወገን በፍ/ቤቱ ለመዳኘት ፈቃደኛ መሆን አለመሆኑን ከአዋጁ ጋር ተያይዞ በሚገኘዉ ቅጽ መሰረት ቀርቦ እንዲያረጋግጥ መጥሪያ እንደሚልክለት በአዋጁ አንቀጽ 5 [1] ሥር ተመልክቷል። ይህ ተከራካሪ ወገን ቀርቦ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ከአዋጁ ጋር በተያያዘ ቅጽ መሰረት ያረጋገጠ እንደሆነ በግልጽ ፈቃደኝነቱን መግለጹን ስለሚያረጋግጥ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የሸሪዓ ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቡትን ዳኝነት ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን ይኖረዋል ማለት ነዉ። ነገር ግን ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩ በቀረበለበት ሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ ስምምነት በሌለ ጊዜ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስለማይኖረዉ ፣ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸዉን በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲያስወስኑ ጉዳዩን ሥልጣን ላለዉ የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤት ማስተላለፍ እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 5 [3] ሥር ተደንግጓል። ተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ በሸሪዓ ፍ/ቤት በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን በማናቸዉም ምክንያት ወደ መደበኛዉ ፍ/ቤት፤ ወይም በመደበኛዉ ፍ/ቤት በመታየት ላይ የሚገኙ ጉዳዮችን ወደ ሸሪዓ ፍ/ቤት ተዘዋዉረዉ እንዲታዩ ማድረግ እንደማይችሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር ተመልክቷል። ከዚህ ድንጋጌ የምንገነዘበዉ ተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት ግልጽ በሆነ መንገድ ፈቃዳቸዉን ሰጥተዉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማየት ላይ እያለ ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ጉዳዩ ከሸሪዓ ፍ/ቤቶች ወደ የፌዴራል ፍ/ቤቶች እንዲተላለፍለት ጥያቄ ወይም አቤቱታ ማቅረብ እንደማይችሉ ነዉ። ተከራካሪ ወገኖች በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት በአዋጁ በተመለከተዉ አግባብ ግልጽ በሆነ መንገድ ፈቃደኝነታቸዉን ገለጸዉ ክርክር ከቀጠሉ ፣ይህን ጉዳይ ሰምቶ ሕጋዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያላቸዉ የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች እንጂ የፌዴራል መደበኛ ፍ/ቤቶች አለመሆናቸዉን ያስገነዝባል።

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉ ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ፣ የአሁን ተጠሪም ቀርበዉ በጉዳዩ ላይ ተገቢ ነዉ ያሉትን ክርክራቸዉን ማቅረባቸዉን ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና ከሸሪዓ ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ ግራ ቀኙ በሃይማኖታቸዉ በእስልምና ሀይማኖት ሥርዓት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃደኝነታቸዉን ግልጽ በሆነ መንገድ ስምምነት መኖሩን በሚያሳይ ሁኔታ ክርክራቸዉን ማቅረባቸዉን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን የጋብቻ ፍቺ ጉዳይ እና የፍቺ ዉሳኔ ዉጤት የሆኑትን ጉዳዮችን ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ማለት ግራ ቀኙ በፍቺ ጉዳይ በሸሪዓ ፍ/ቤት እየተከራከሩ እያሉ አንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ወይም ሁለቱም ይህ ክርክራቸዉ ወደ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተዘዋዉሮ የፍቺ ዉሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ለማቅረብም ሆነ የሸሪዓ ፍ/ቤቱ የፍቺ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል በሸሪዓ ፍ/ቤት ሳይሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለማቅረብ አይችሉም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ የወሰነ ስለሆነ፣ የፍቺ ዉጤቱንም ቢሆንም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አይደሉም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ጋብቻቸዉን በተመለከተ የፍቺ ዉሳኔና ውጤቱ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥላቸዉ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ፣ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ.ቁ.209/06 በ8/5/2006 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ የግራ ቀኙ ጋብቻ እንዲፈርስ የፍቺ ዉሳኔ ከሰጠ በኋላ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ይኼዉ ፍ/ቤት ሆኖ ሳለ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያፈራነዉን የጋራ ሀብታችን የሆነዉን የመኖሪያ ቤት እንድካፈል እንዲወሰንልኝ በማለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረበዉ አቤቱታ በዚህ ክርክር ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ለሌለዉ ፍ/ቤት ያቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ ዉሳኔ በመስጠቱ የፍቺ ዉጤት በተመለከተ ለማየት ስልጣን የለኝም ብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 [2]፣ የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀጽ 5 [4]፣ እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 [2፣ ሀ] እና 245 [2] መሰረት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ፣ የንብረት ክፍፍል በተመለከተ ግራ ቀኙን በማከራከር ዉሳኔ መስጠቱ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ማረም ሲገባዉ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ የህግ መሰረት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የፌዴራል ፍ/ቤቶች በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤት የፍቺ ዉሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ የፍቺ ዉጤት የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክረዉ ዉሳኔ ለመስጠት የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖራቸዉ መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.116454 በ16/2/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.223910 በ10/8/2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት ተሽሯል።
2. በግራ ቀኙ መካከል የነበረዉን ጋብቻ በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት በሰጠዉ የፍቺ ዉሳኔ ጋብቻቸዉን በማፍረስ የወሰነ ስለሆነ፣ የፍቺዉ ዉጤቱንም ሰምቶ ለመወሰን የሥረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ ይኼዉ የሸሪዓ ፍ/ቤት በመሆኑ፣ የፌዴራል ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የፍቺ ዉጤት የሆነዉን የንብረት ክፍፍል ለማየት የሥረነገር የዳኝነት ስልጣን የላቸዉም ብለናል።
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።
5. ይህ ችሎት በ7/9/2011 ዓ.ም የሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል። ለሱሉልታ ከተማ መሬት ልማትና ማናጅመንት ጽ/ቤት ይጻፍ።
6. የመ.ቁ.123631 የሆነዉ መዝገብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አረዳ ምድብ ችሎት ይመለስ፤ እንዲሁም የመ.ቁ.209/06 የሆነዉ መዝገብ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት ይመለስ ብለናል።
7. ይህ ዉሳኔዉ በ23/2/2013 ዓ.ም ተነቧል።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ.መ.ቁ 181359

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ዲክሳ ኪዳኔ

2. አቶ ቶማስ ኪዳኔ

3. ወ/ት ሀወኒ ኪዳኔ

ተጠሪ፡- የጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ቤቶች ልማት ጽ/ቤት

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሐምሌ 18 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 30165 ሠኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም በስሩ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች አከራካሪውን ቤት እንዲለቁ በአባታቸው ስም የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ወላጅ አባታቸው አቶ ኪዳኔ ዘውገ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ቤ.ቁ 680 የሆነው ቤት ሕጋዊ ተከራይ መሆናቸውን፤ አመልካቾች በዚሁ ቤት ውስጥ ተወልደው አድገው እስካሁን ድረስ በቤቱ በመኖር ላይ የሚገኙ መሆኑን፤ አባታቸው በከፍተኛ ሕመም ምክንያት እናታቸውን /ወ/ሮ ፍቅርተ ተረፈ/ ይዘው ከኢትዮጲያ ውጪ የወጡ መሆኑን፤ አባታቸው ባደረባቸው ከፍተኛ ሕመም ምክንያት ወደ ሐገር ቤት ተመልሰው የኪራይ ውሉን ለመዋዋል ያልቻሉ መሆኑን እና እናታቸው የቤቱን ኪራይ እየተመላለሱ የከፈሉ መሆኑን በመግለጽ በአባታቸው ስም የቤቱን ኪራይ

ተዋውለው ኪራይ በመክፈል በቤቱ መኖር እንዲቀጥሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- የቤቱ ተከራይ የሆኑት አባታቸው አቶ ኪዳኔ ዘውገ ለሕክምና እንግሊዝ አገር እንደሚገኙ እና እንደሚመለሱ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፤ አመልካቾች በወላጆቻቸው ስም ኪራይ ለመዋዋል የሚያስችላቸው ደንብም ሆነ መመሪያ የሌለ መሆኑን፤ የአመልካቾች ወላጆች ዜግነታቸው እንግሊዛዊ ስለሆነ እና ከአምስት ዓመት በላይ በቤቱ ስላልኖሩ በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 43/ሀ፤ 44/3 እና 44/13 እና 45/2 መሠረት ቤቱን እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢነት ያለው አሰራር መሆኑን በመግለጽ የአመልካቾች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የአመልካቾች አባት እንግሊዝ አገር የሚገኙት ለሕክምና ዓላማ ብቻ? ወይንስ ለዘለቄታው ለመኖር? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የአመልካቾች አባት እንግሊዘ አገር በሕክምና ላይ መሆናቸውን እና መቼ መመለስ እንደሚችሉ የሚያስረዳ ማስረጃ አመልካቾች እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል፤ በዚሁ መሠረት አመልካቾች አባታቸው በእንግሊዝ አገር በመደበኛ ታካሚነት እስከ 15/05/2010 በመታከም ላይ ያሉ እና ዋንድ የሕክምና ማዕከል የሚገኙ መሆናቸውን የሚያስረዳ ማስረጃ ቀርቧል፡፡ ተጠሪ በሰጠው አስተያየት የቀረበው ማስረጃ ለአባታቸው የታዘዘላቸውን መድሀኒት የሚያመለክት እንጂ በሕክምና ላይ መሆናቸውን እና በቀጣይ ወደ ኢትዮጲያ እንዲሚመጡ የሚያሳይ አይደለም፤ ይልቁንም በ1993 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር በስደተኝነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው በማለት አስተያየት የሰጠ መሆኑን ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመቀጠልም ጉዳዩን መርምሮ የቤቱ ተከራይ የሆኑት የአመልካቾች አባት ወደ እንግሊዝ አገር የሄዱት ለሕክምና መሆኑን እና የአመልካቾች ወላጅ እናት ባለቤታቸውን ለማስታመም አብረው መሄዳቸውን እና ወደ ኢትዮጲያ ተመልሰው የቤቱን ኪራይ ውል ለማደስ ተጠሪን ቢጠይቁም ፈቃደኛ አለመሆኑን እና አመልካቾችም በዚሁ ቤት ውስጥ ተወልደው ኪራዩን እየከፈሉ በመኖር ላይ ስለመሆናቸው በተጠሪ በኩል ማስተባበያ አልቀረበበትም፤ የተጠሪ ክርክር የአመልካቾች ወላጆች የእንግሊዝ አገር ዜግነት ያገኙ ስለሆነ በመመሪያው ቁጥር 43/ሀ መሠረት ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል የሚል ነው፤ የመመሪያው ቁጥር 45/2 ተከራይ ከሀገር ውጪ የወጣ እና እንደማይመጣ ሲረጋገጥ እና ሌሎች የውል ግዴታዎችን አለመወጣት ሲያጋጥም አከራይ የ30 ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ ይፈርሳል ቤቱን ይረከባል በማለት ይደነግጋል፤ የአመልካቾች አባት እና እናት ለሕክምና ከሄዱበት አገር እንደማይመጡ በተከሳሽ በኩል የቀረበ ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ የአመልካቾች ወላጅ እናት በ2010 ዓ.ም አጋማሽ ወር ላይ ወደ ኢትዮጲያ በመምጣት የኪራይ ውሉን ለማደስ ተጠሪን

ጠይቀው እንግሊዛዊ ስለሆንሽ አናዋውልም ማለቱ ተረጋግጧል፤ የአመልካቾች ወላጆች ሌሎች የውል ግዴታቸውን ያልተወጡ ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ከዚህም ሌላ የአመልካቾች ወላጅ አባት ለ1ኛው አመልካች ውክልና ሰጥተውት የሄዱ ስለሆነ የመመሪያው ቁጥር 45/3 አመልካቾችን የሚደግፍ ነው፤ ስለሆነም ከመመሪያው አንጻር ተጠሪ የቤቱ ተከራይ ልጆች ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡት በአባታቸው ስም ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ስለሆነ ሁከቱ ሊወገድ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታው ውድቅ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የቤቱ ሕጋዊ ተከራይ የሆኑት የአመልካቾች አባት አቶ ኪዳኔ ዘውገ ከሐገር መውጣታቸው እና ዜግነታቸው እንግሊዛዊ ስለመሆኑ አልተካደም፤ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔ መሠረት ያደረገው አቶ ኪዳኔ ዘውገ ወደ ሐገር እንደማይመለሱ ተጠሪ አላረጋገጠም በሚል ነው፤ በመንግሰት ቤቶች መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 44/13 የመንግስት መኖሪያ ቤት የሚከራየው በከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ኢትዮጲያዊ ዜግነት ያለው እና/ ወይም በከተማው ውስጥ ነዋሪ ሲሆን የጸና /የታደሰ የኢትዮጲያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ላለው የውጪ ዜጋ ብቻ መሆኑ ተደንግጓል፤ የአመልካቾች በቤቱ የመኖር መብት የሚመነጨው አባታቸው በተከራዩት ቤት ነው፤ ተጠሪ በመመሪያው መሠረት የቤቱ ተከራይ የሆኑት ግለሰቦች የውጪ ዜግነት ያላቸው እና በቤቱም የማይኖሩ መሆኑን አረጋግጦ የቤቱን የኪራይ ውል ማቋረጡ እና ቤቱን ለመረከብ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ አግባብ ሆኖ ሳለ ይህ ታልፎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ ተጠሪ ቤቱን እንዲለቁ የሰጠው ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር አይደለም ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች ወላጆቻችን እንግሊዝ አገር የሄዱት አባታችን በመታመሙ ምክንያት ሕይወቱን ለማትረፍ መሆኑን አስረድተናል፤ ተጠሪውም ለረጅም ዓመታት በውክልና ሲያዋውለን ቆይቷል፤ ወላጆቻችን ዜግነት የተሰጣቸው ለሕክምና ወጪ እንዲቀንስ እና እንዲረዱ ነው፤ ወላጆቻችን ተመልሰው ወደ ቤታቸው እንደሚመጡ አረጋግጠን ሳለ ተጠሪ ተወልደን ካደግንበት ቤት ለማስወጣት የጀመረው እንቅስቃሴ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፤ ስለሆነም አመልካቾች በቤቱ የመኖር መብት እንዳለን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 የሚደግፈን በመሆኑ በቤቱ የመኖር መብታችን ሊከበርልን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአመልካቾች ወላጆች ከሄዱበት ውጪ ሐገር ወደ ኢትዮጲያ እንደማይመለሱ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማረጋገጫ በሌለበት ሁኔታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ይግባኝ ሰሚ ሰበር ሰሚ ችሎት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሮ ሁከት የለም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የአመልካቾች ወላጅ አባት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ እንግሊዝ አገር በስደተኝነት ተመዝግበው እንደሚኖሩ እና ዜግነታቸውም እንግሊዛዊ በመሆናቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 44/13 በተቀመጠው መስፈርት ስለማይሸፈኑ ውል እንዲቋረጥ ተደርጓል፤ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄም ወላጆቻቸው የሌላቸውን መብት በውክልና ይዘን እንቀጥል የሚል ነው፤ ተከራይ በውክልና ቤቱን አስተላልፎ በውጪ ሐገር ሊኖር የሚችለው ከመነሻው ኢትዮጲያዊ ዜግነት ያለው ከሆነ እንጂ እንደ አመልካቾች ወላጆች ኢትዮጲያዊ ዜግነት የሌላቸውን ሰዎች የሚመለከት አይደለም፤ ክርክሩ የወላጆቻቸው ወደ ሐገር መመለስ እና አለመመለስ ሳይሆን የዜግነት ጉዳይ ነው፤ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ ከሐገር የወጡት በሕክምና ምክንያት መሆኑን አያስረዳም፤ ይልቁንም በስደት ከሐገር የወጡ ስለመሆኑ እና እንደማንኛውም ሰው የታከሙ መሆኑን የሚሳይ በመሆኑ የወላጆቻቸው ተመልሶ ወደ ሐገር የመምጣት ጉዳይ በተጠሪ በኩል የተወሰነውን ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም፤ ተጠሪ የአመልካቾች ወላጆች ወደ ሐገር አለመመለሳቸውን ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፤ ቢመለሱም ዜግነታቸው ኢትዮጲያዊ እስካልሆነ ድረስ ተጠሪ ሊያስተናግዳቸው የሚችልበት የሕግ አግባብ ስለሌለ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ በአባታቸው አቶ ኪዳኔ ዘውገ ስም የቤቱን ኪራይ ውል ተዋውለው ኪራዩን እየከፈሉ በቤቱ መኖር እንዲቀጥሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ሊጠይቁ የቻሉት ተጠሪ የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 43/ሀ፤ 44/3፤ 44/13 እና 45/2 ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የቤቱ ተከራይ የሆኑት የአመልካቾች አባት ለሕክምና እንግሊዝ አገር የሚገኙ እና እንደሚመለሱ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን፤ ዜግነታቸውም እንግሊዛዊ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ በቤቱ ያልኖሩ መሆኑን ጠቅሶ የኪራይ ውሉን አቋርጦ ቤቱን እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ በመስጠቱ ምክንያት እንደሆነ ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ካደረጉት ክርክር ይዘት መገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ በዚህ አግባብ የሚከራከር ከሆነ ይህንኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ በአንጻሩ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር መገንዘብ የተቻለው የአመልካቾች አባት አቶ ኪዳኔ ዘውገ የቤቱ ሕጋዊ ተከራይ መሆናቸውን እና ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ለ1ኛው አመልካች /ለልጃቸው/ ውክልና

ሰጥተው ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው በዚያው አገር በሚገኝ የሕክምና ማዕከል በመደበኛ ታካሚነት በመታከም ላይ የሚገኙ መሆኑን፤ የአመልካቾች ወላጅ እናትም ባለቤታቸውን ለማስታመም አብረው የሄዱ መሆኑን እና በመሆኑም ወደ ኢትዮጲያ ተመልሰው የቤቱን ኪራይ ውል ለማደስ ተጠሪን የጠየቁ ቢሆንም ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆኑን እና በቤቱ ውስጥ የሚኖሩት የቤቱ ሕጋዊ ተከራይ ልጆች የሆኑት አመልካቾች መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አኳያ በየደረጃው ያሉ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 45 የኪራይ ውል የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች የሚደነግግ ሲሆን የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ተከራይ ከሐገር ውጪ ከወጣ እና እንደማይመጣ ሲረጋገጥ እና ሌሎች የውል ግዴታዎችን አለመወጣት ሲያጋጥም አከራዩ የሰላሳ ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን እንደሚያፈርስ ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ ተከራይ ከባል፤ ከሚስት፤ ከልጅ፤ ከሞግዚት ውጪ ለሌላ ወገን በውክልና ስም አስተላልፎ አምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ውጭ አገር ከኖረ የቤት ኪራይ ውሉ ተቋርጦ መንግስት ቤቱን ይረከባል በማለት ይደነግጋል፡፡

ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የአመልካቾችን ጉዳይ ስንመለከተው የአመልካቾች አባት ከኢትዮጲያ የወጡ ቢሆንም ሌሎች የውል ግዴታዎችን አለመወጣታቸው እና ወደ ሐገር ተመልሰው እንደማይመጡ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማረጋገጫ የለም፡፡ የአመልካቾች አባት ወደ እንግሊዝ ሐገር የሔዱት ለሕክምና መሆኑ እና በዚያው ሐገር በሚገኝ የሕክምና ማዕከል ውስጥ መደበኛ ታካሚ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሕክምና በሚከታተሉበት ሐገር በስደተኝነት መመዝገባቸው ብቻውን ወደ ሐገራቸው እንደማይመጡ የሚያሳይ አረጋጋጭ ነው ተብሎ ድምዳሜ የሚወሰድበት አይደለም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአመልካቾች አባት ወደ ውጪ ሐገር ሲሄዱ ውክልና የሰጡት ልጃቸው ለሆነው 1ኛ አመልካች በመሆኑ ውክልናው በመመሪያው አንቀጽ 45/3 በተደነገገው አግባብ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳየን ነው፡፡ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩትም አስቀድሞ ከአባታቸው ጋር ይኖሩ የነበሩ የቤቱ ተከራይ ልጆች እንጂ ሌላ 3ኛ ወገን አይደለም፡፡ ስለሆነም ከመነሻውም ቢሆን ተጠሪ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ገልጾ ቤቱን ለመረከብ የሰጠው ማስጠንቀቂያ በመመሪያው አንቀጽ 45 ላይ በተመለከተው መሠረት ውል ለማቋረጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን ሳያረጋግጥ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ከመመሪያው አንጻር አመልካቾች ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡት ተጠሪ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ተገቢ አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ሰሚ ችሎት በስሩ ያሉት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለመሻር እንደ ምክንያት የወሰደው የቤቱ ተከራይ የውጪ ሐገር ዜግነት ያላቸው እና

በቤቱ የማይኖሩ በመሆኑ ተጠሪ የቤቱን የኪራይ ውል ማቋረጡ እና ቤቱን ለመረከብ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ አግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የቤቱ ሕጋዊ ተከራይ የሆኑት የአመልካቾች አባት ውሉን በተዋዋሉ ጊዜ ኢትዮጲያዊ የነበሩ እና ለሕክምና ወደ ውጪ ሐገር ከሄዱ በኂላ ዜግነታቸውን የለወጡ ከመሆኑ አኳያ የስር ሰበር ሰሚ ችሎት ዜግነታቸውን መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብ መሆን አለመሆኑን ቀጥለን እንመለከት፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 04/2009 አንቀጽ 44/13 የመንግስት መኖሪያ ቤት የሚከራየው በከተማ ውስጥ ነዋሪ ኢትዮጲያዊ ዜግነት ላለው እና/ ወይም በከተማው ውስጥ ነዋሪ ለሆነ የጸና /የታደሰ የኢትዮጲያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ላለው የውጭ ዜጋ ብቻ ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ በመሠረታዊነት የዚህ ድንጋጌ ተፈጻሚነት ከከተማው አስተዳደር ቤትን ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚከራዩ ሰዎች እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን አስቀድሞ የተፈጸመ የቤት ኪራይ ውል በሚታደስበት ጊዜም በድንጋጌው ላይ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል የሚባል ከሆነ ውል ለማደስ የሚጠይቀው ወገን ይህንኑ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የቤቱ ሕጋዊ ተከራይ የሆኑት የአመልካቾች አባት ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ለሕክምና ወደ ውጪ ሐገር የሄዱ እና በዚያው ሐገር በሚገኝ የሕክምና ማዕከል ውስጥ መደበኛ ታካሚ መሆናቸው የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባደረገው ክርክር የአመልካቾች አባት የእንግሊዝ ዜግነት ያላቸው በመሆኑ ውሉ ተቋርጦ አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቂያ መስጠታችን አግባብ ነው በማለት ከሚከራከር በቀር በእርግጥም የአመልካቾች አባት ወደ ኢትዮጲያ ተመልሰው በመምጣት በመመሪያው አንቀጽ 44/13 ላይ በተመለከተው መሠረት በከተማው ውስጥ ነዋሪ ሆነው የጸና/ የታደሰ የኢትዮጲያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለማግኘት በሚችሉበት የጤና ሁኔታ ላይ መሆናቸውንም ሆነ ከነጭራሹም ወደ ሐገራቸው የማይመለሱ መሆናቸውን በመግለጽ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ተጠሪ በዚህ አግባብ ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የአመልካቾች አባት የጤና ሁኔታቸው ሲስተካከል ወደ ሐገራቸው በመምጣት ኑሯቸውን ሊቀጥሉ እንደሚችሉ ግምት ይወሰዳል፡፡ የአመልካቾች አባት ጤናቸው ተስተካክሎ ወደ ሐገራቸው መጥተው መኖር የሚቀጥሉ ከሆነም አስቀድሞ በሕግ አግባብ በተከራዩት ቤት ውስጥ የመኖር መብት አላቸው፡፡ ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በዚህ አግባብ አይቶ መወሰን ሲገባው ተጠሪ የቤቱ ተከራይ የውጪ ዜግነት ያላቸው እና በቤቱም የማይኖሩ መሆኑን አረጋግጦ የቤቱን የኪራይ ውል ማቋረጡ እና ቤቱን ለመረከብ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ተገቢ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 30165 ሠኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 07038 ሕዳር 07 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የኢዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርደ ቤት በመ.ቁ 29631 ጥር 06 ቀን 2011 የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.181643

ህዳር 29/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ መዓዛ አሸናፊ

እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

አመልካች፡- ወ/ት እንኳአየሁሽ ነጋሽ

ተጠሪ፡- አቶ ካሳሁን ነጋሽ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የገጠር መሬትና መኖሪያ ቤት የውርስ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 89253 ላይ ሐምሌ 08/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በደቡብ አቼፈር ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር የተጠቀሰውን 13 ቃዳ የገጠር መሬት እና 42 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት የሟች እናታቸው ወ/ሮ ታገኝ አስማረ የውርስ ሀብት መሆኑን፣ የሟች ወራሾች ስድስት ልጆች ሲሆኑ አመልካች በመ/ቁ 75240 ላይ ግንቦት 25/2007 ዓ.ም ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የውርስ ሀብቱን በሽማግሌ ከተካፈሉ በኋላ ተጠሪ ድርሻቸውን ሊሰጧቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአሁን ተጠሪን መልስ ከሰማ በኋላ ክስ ከቀረበበት ይዞታ ውስጥ 10 ቃዳ መሬት ተጠሪ በውርስ ያገኙት በመሆኑ ሊያካፍሉ አይገባም በማለት ሶስት ቃዳ መሬቱን ብቻ

እንዲያካፍሉ የወሰነ መሆኑን፤ በዚሁ ውሳኔ ላይ በአሁን አመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በጉዳዩ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ለስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመለሰ መሆኑን፤ በዚሁ አግባብ ክርክሩ ቀጥሎ እያለ ሌሎች ወራሾች የጣልቃ ገብነት ጥያቄ አቅርበው የክርክር አካል ተደርገው ክስ ለመስማት በተቀጠረ ቀን የአሁን ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲሰማ ተደርጎ የአመልካች እና የጣልቃ ገቦች ማስረጃ የተሰማ መሆኑን፤ በኋላም የቀረቡት የሰው ምስክሮች የአሁን ተጠሪ ወደው እና ፈቅደው ክስ የቀረበበትን ይዞታ በስምምነት ማካፈላቸውም አላስረዱም፤ ተጠሪም ይዞታውን የያዙት ወራሽነታቸውን አረጋግጠው በመሆኑ ሊያካፍሉ አይገባም በማለት ይዞታውን በተመለከተ የቀረበውን ክስ እና የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ቤቱን በተመለከተ ብቻ ተጠሪ የአመልካችን ድርሻ ግምት እንዲያካፍላቸው በማለት ወስኖ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፀና መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ያሳያል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሀምሌ 25/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ክስ የቀረበበት ይዞታ የወላጅ እናታችን መሆኑን እና ከተጠሪ ውጭ ሌሎች ወራሾች መኖራቸው ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ከመሬት አስተዳዳር ጋር በመመሳጠር በወሰደው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መነሻነት የውርስ ሃብቱን ሊያካፍል አይገባም መባሉ አግባብ አይደለም፤ ይዞታውም በወራሾች መካከል በሽማግሌችዎ ተከፋፍሎ እያለ ፍርድ ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት አልተከፋፈለም ማለቱ አግባብ አይደለም፤ የወረዳው መሬት አስተዳደር ይዞታው በሟች እናታችን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ከገለፀ በኋላ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ስም ተመዝግቧል በሚል መግለጫ መስጠቱ እርስ በራሱ የሚጣረስ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን በተገቢ መንገድ ሳያጣሩ ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር የቀረበበት ይዞታ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ወራሽነቱን አረጋግጠ በስሙ በማስመዝገቡ ብቻ ሌሎች ወራሾች መውረስ እንደማይችሉ የተወሰነበት አግባብነት ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡ ሆኖም ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደረሷቸው ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ አጀማመር መገንዘብ እንደሚቻለው ጉዳዩ በወራሾች መካከል የተነሳ የገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ይገባኛል ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በመሰረቱ ጉዳዩ በሚመለከተው የክልል መሬት አስተዳደር ህግ አግባብ ከወራሾች መካከል የገጠር መሬት ይዞታን ለመውረስ የተለየ መስፈርት ወይም ልዩ ሁኔታ እስካልተደነገገ እና ይኸው ሁኔታ ስለመኖሩ እስካልተረጋገጠ ድረስ አንዱ ወራሽ ከሌላኛው ወራሽ የተለየ መብት የለውም፡፡ ወራሽነትን ቀድሞ አረጋግጦ የውርስ ሀብትን መያዝም ምናልባት ከይርጋ አኳያ የሚያጎናፅፈው መብት ካለ ተገቢ ክርክር ተደርጎበት ከሚወሰን በቀር ቀድሞ ወራሽነትን በማረጋገጥ ብቻ የሚገኝ ልዩ የመውረስ መብት አይኖርም፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ከገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ጋር በተያያዘ በአንቀፅ 17 እና ተከታዮቹ ወራሽ የሆነ/ች ሰው በግብርና ስራ የሚተዳደር አልያም ለመተዳደር ፍላጎት ያለው መሆን ያለበት ስለመሆኑ እና ሌሎች መሰል መመዘኛዎችን ከማስቀመጥ ባለፈ ወራሽነቱን ቀድሞ ያረጋገጠ ብቻውን የሚወርስ ስለመሆኑ የሚደነግገው ነገር የለም፡፡ የውርስ ጉዳይ በመርህ ደረጃ የሚገዛው በውርስ ህግ በመሆኑ በልዩ ህግ አጠቃላይ የውርስ ህግ መሰረተ ሀሳብን የሚቃረን ድንጋጌ ይወጣል ተብሎም አይጠበቅም፡፡ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ህግ መሰረት አመልካች ክስ የቀረበበትን ይዞታ ለመካፈል አይችሉም በሚል በአሁን ተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ እናም ተጠሪ ቀድሞ ወራሽነቱን በማረጋገጥ ይዞታውን በመያዙ ብቻ ሊያካፍል አይገባም በሚል የተሰጠው ውሳኔ ህግን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ክስ ያቀረቡት የውርስ ሃብትን ለመካፈል እስከሆነ ድረስ ይዞታውን በተመለከተ ተደርጓል የተባለው ክፍፍል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ መረጋገጡ በተጠየቀው ዳኝነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ እናም በስምምነት የተደረገ ክፍፍል ስለመኖሩ ከተካደ የውርስ ሀብት የተባለው ይዞታ አግባብ ባለው የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳር እና አጠቃቀም ህጋጋት መሰረት ወራሾች እንዲካፈሉ ከሚደረግ በቀር በፈቃደኝነት የተደረገ የክፍፍል ስምምነት የለም በሚል ክሱ ውድቅ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ህግን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ በእርግጥም የሚነቀፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ አቼፈር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/22683 ላይ መጋቢት 12/2011 ዓ.ም ተሰጥቶ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ተጠሪ ክስ ከቀረበበት የውርስ ይዞታ ውስጥ ሁለት ቃዳ መሬት ለአመልካች ሊያካፍሏቸው ይገባል፡፡

## ትዕዛዝ

4. አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጪ ዝርዝር ለወረዳው ፍርድ ቤት አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው ተጠብቋል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ.መ.ቁ.184533

መጋቢት 30 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አስገዳጅ ደብረ መዊ ቅዱስ ጊወርጊስ ቤ/ክርስቲያን

ተጠሪ፡ ቄስ ሞላ ሰማው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በስራ ምክንያት የተረከቡት ንብረት ባለመገኘቱ ምክንያት የንብረቱ ግምት እንዲከፈል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም አመልካች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የአሁን ተጠሪ የአመልካች ቤተክርስቲያን ግምጃ ቤት ኃላፊ በነበሩበት ወቅት በስራ ምክንያት የተረከቡትን የቤተክርስቲያኒቷ ቅርስ የሆነ በውስጡ ሜርኩሪ ያለውን እና በራሱ ኃይል የሚሰራ የዋጋ ግምቱ ብር 20,000,000(ሃያ ሚሊዮን) የሆነ ማሾ አጉድለው የተገኙ እና በዚህም ምክንያት በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ የቅርሱን ዋጋ ሊከፍሉ ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ የቀረበው መቃወሚያ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት ቅርስ አይደለም፤ ግምቱም ከብር 100/አንድ መቶ/ አይበልጥም የሚል ነው፡፡ የስረ ነገር ክርክሩ ይዘት ደግሞ የተጠቀሰው ማሾ ማዕድን ያለበት ቅርስ ሳይሆን እማሆይ አመተ ስላሴ የተባሉ ምዕመን ገዝተው ለቤተክርስቲያኒቷ የሰጡት በጋዝ የሚሰራ ነው፤ በወንጀል የተቀጣሁትም በተገለፀው አግባብ ሳይሆን የማሾው ብርጭቆ ጠፍቷል በሚል በብር 300(ሶስት መቶ) መቀጮ በመሆኑ የተጠቀሰውን ግምት ልጠየቅ አይገባም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የተጠቀሰው ማሾ ዋጋ በክልሉ ውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ቢሮ በኩል ተገምቶ እንዲቀርብ ያደረገ መሆኑን፣ የታዘዘው አካልም ክስ የቀረበበት ንብረት ብርጭቆ ቢኖረው ኖሮ ብር 50/ሃምሳ ብር/ ያወጣል በሚል የገለፀለት መሆኑን፣ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መነሻ

በማድረግ በቀረበው ግምት መሰረት ጉዳዩን ለማየት የስር ነገር ስልጣን የለኝም በሚል መዝገቡን የዘጋ መሆኑን፤ ይኸው ጉዳይ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ታይቶ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ስልጣን አለው ተብሎ አከራክሮ እንዲወስን የተመለሰለት መሆኑን፤ በዚሁ አግባብ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ ክስ የቀረበበት ንብረት ማዕድን ያለበት ቅርስ ሳይሆን እማሆይ አመተ ስላሴ የተባሉት በ1987 ዓ.ም ከመርካቶ በብር 150(አንድ መቶ ሃምሳ) ገዝተው ለቤተክርስቲያንዋ አገልግሎት እንዲውል በስጦታ ያበረከቱ መሆኑን፤ ማሾው ጠፋ በተባለበት ጊዜም ብርጭቆ የሌለው መሆኑን እና ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በብር 300(ሶስት መቶ) መቀጮ የተቀጡት የማሾውን ብርጭቆ ጠፍቷል በሚል እንደሆነ በማስረጃ ማረጋጡን ጠቅሶ የአሁን ተጠሪ የንብረቱ ዋጋ የተባለውን ብር 50(ሃምሳ ብር) ለአመልካች እንዲከፍሉ ወስኖ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መፅናቱን ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ ይዘት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች ወኪል ጥቅምት 08/2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክሩ ከቤተክርስቲያን ጋር በመሆኑ እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የንዘብ መጠን ሃያ ሚሊዮን ከመሆኑ አንጻር በክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆን አለመሆኑ ከህገ መንግሰቱ አንቀጽ 80(2) እንዲሁም ከፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(6) እና 11(1) ድንጋጌ አንጻር ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ የማስቀረቢያ ነጥቡ ከዳኝነት የስር ነገር ሥልጣን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መነሻውም አንዱ ተከራካሪ ወገን ቤተክርሲትያን በመሆንዋ እና ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ከክርክሩም መጠን አኳያ በክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዴት ሊታይ ቻለ የሚል ስለመሆኑ በማስቀረቢያ ነጥቡ ውስጥ ከተጠቀሱት ህግጋት አንፃር መረዳት ይቻላል፡፡

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት የስረ ነገር ስልጣን ምንጭ አንዱ በፌዴራል መንግስቱ በተመዘገቡ ህጋዊ ሰውነት በተሰጣቸው ድርጅቶች ላይ ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 5(6) ይደነግጋል፡፡ እናም የፌዴራል መንግስቱ

ተመዝጋቢ ድርጅቶች ተካፋይ የሆኑብት ክርክር የፌዴራል ጉዳይ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባልተቋቋመባቸው ክልሎች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች እንደክርክሩ መጠን ከክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጀምሮ የሚታይ ስለመሆኑ የህገ መንግስት አንቀፅ 78(2) እና 80((4) እና (5)) ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ የክርክሩ አንዱ አካል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ነች፡፡ የቤተክርስቲያንዋ ህጋዊ ሰውነት የሚመነጨው ከ1952ቱ የፍትሐ ብሔር ህግ አንቀፅ 398 እንጂ የፌዴራል መንግስቱ ተመዝጋቢ አካል አይደለችም፡፡ እናም ቤተክርስቲያንዋ ተካፋይ የሆነችበነት ክርክር የፌዴራል ጉዳይ የሚባል ሳይሆን እንደ ክርክሩ ዓይነት፣ መጠን እና ቦታ ጉዳዩ በቀረበበት ክልል የሚታይ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንፃር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ ለመወሰን የዳኝነት የስር ነገር ስልጣን ያለው በመሆኑ በየደረጃው ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ በመቀበላቸው የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/0326886 ላይ ሐምሌ 24/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ.መ/ቁ 181278

ጥቅምት 26/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ሀፍቱ ኪሮስ

ተጠሪ፡ የሀውልቲ ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው በከተማ መስፋፋት ምክንያት የገጠር ይዞታን ይዞ ወደ ከተማ የገባ ሰው በይዞታው ምትክ ሊሰጠው ከሚገባው ይዞታ መጠን በታች በመሰጠቱ ምክንያት የተሰጠውን ይዞታ ተቀብሎ ከቆየ በኋላ ተቀነሰብኝ በሚለው የይዞታ መጠን ላይ ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የለውም ተብሎ የተወሰነበትን ህጋዊ አግባብነት መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በትግራይ ብ/ራዊ ክልላዊ መንግስት በሐውልቲ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በከተማ መስፋፋት ምክንያት ቀደም ሲል ለጎጆ መውጫ ተብሎ በህጋዊ መንገድ የተሰጣቸውን 400 ካሬ ሜትር ይዞታ ይዘው ወደ ከተማ መካለላቸውን፤ ይህ ቦታ ለመሰረተ ልማት ይፈለጋል በሚል እንዲነሱ ተደርጎ በምትኩ 400 ካ.ሜ ሊሰጣቸው ሲገባ 140 ካ.ሜ ብቻ የተሰጣቸው መሆኑን በመግለፅ ያለአግባብ የተቀነሰባቸው 260 ካሬ ሜትር እንዲሰጣቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ አመልካች በምትክነት የተሰጣቸው 140 ካሬ ሜትር ይዞታ ተቀብለው አቶ ኪሮስ ገ/መስቀል ለተባሉት ግለሰብ የሸጡ በመሆኑ እና በተጠሪ ጽ/ቤትም ምንም ዓይነት ማህደር የሌላቸው በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በምትክነት የተሰጣቸውን ይዞታ ሸጠው ይዞታውን የሚመለከቱ ሰነዶችንም ለሌላ ሰው ካስተላለፉ

በኋላ ቀረኝ ባሉት ቦታ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2) መሰረት በብይን ዘግቷል፡፡

በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ዘግቷል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ በመ/ቁ/114270 ላይ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ሰምቶ ግንቦት 09/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በከተማ መስፋፋት ምክንያት አመልካች 400 ካሬ ሜትር ይዞታ ይዘው ወደ ከተማ መጠቃለላቸው በአሁን ተጠሪም ያልተካደ መሆኑን፣ ይህ ይዞታ በልማት ምክንያት ከአመልካች በመወሰዱ ምክንያት በ2005 ዓ.ም ለአመልካች 140 ካሬ ሜትር ምትክ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑን፣ ለአመልካች ምትክ ቦታ በተሰጠበት ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በ2003 ዓ.ም የወጣው መመሪያ መሆኑን፣ በዚህ መመሪያ መሰረት በልማት ምክንያት ይዞታው ለተወሰደበት ሰው ከከፍተኛው የከተማ ይዞታ መጠን እስካልበለጠ ድረስ በተወሰደው ይዞታ መጠን ምትክ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን፣ በእለቱ ለአመልካች 400 ካሬ ሜትር ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ሲገባ 140 ካሬ ሜትር ሲሰጣቸው አመልካች የተሰጣቸውን ተቀብለው ለሌላ ሰው አሳልፈው የሸጡ መሆኑን፣ አመልካች በዚህ መልኩ ተቀንሶ የተሰጣቸውን ይዞታ ተቀብለው ከ5 ዓመት በኋላ የተቀነሰብኝ ይዞታ ይሰጠኝ በሚል ያቀረቡት ክስ ቀድሞውኑ ቢሆን ቀረኝ ያሉት ይዞታ የማይገባቸው መሆኑን መቀበላቸውን የሚያሳይ በመሆኑ ከዚህ ያክል ቆይታ በኋላ ተቀነሰብኝ በሚለው ምትክ ቦታ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን እና ትዕዛዝ በምክንያት በማጠናከር አፅንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 15/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም አመልካች የነበራቸው ነባር ይዞታ 400 ካ.ሜ መሆኑን በምትክ የተሰጣቸው ደግሞ 140 ካሬ ሜትር ብቻ ስለመሆኑ በተጠሪም ጭምር ያልተካደ መሆኑን፣ ቀድሞ የተሰጣቸውን 140 ካ.ሜ ለሌላ ሰው በማስተላለፋቸው ምክንያት ቀሪውን ሊጠይቁ አይገባም መባሉ ንብረታቸውን መሸጥ ህገ-መንግስታዊ መብታቸውን የሚፃረር በመሆኑ አግባብ እንዳልሆነ፣ ክስ ያቀረቡትም ያላግባብ የቀረባቸውን 260 ካ.ሜ በሚመለከት እንጂ በሽያጭ ባስተላለፉት ንብረት ላይ ባለመሆኑ የተሸጠውን ንብረት የሚመለከተው ሰነድ ለሌላ ሰው በመተላለፉ ምክንያት ማህደር የላችውም ሊባል እንደማይገባ፣ ለአቶ ኪሮስ ገ/መስቀል ከተላለፈው ሰነድ ላይ አመልካች 400 ካ.ሜ እንደነበራቸው የሚያስረዳ መሆኑን በመግለፅ የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች አልፈው ክሳቸውን ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ከገጠር ወደ ከተማ ይዘው የገቡት የይዞታ መጠን 400 ካ.ሜ መሆኑና በዚሁ ይዞታ ምትክ ተለዋጭ 140 ካ.ሜ ይዞታ የተሰጣቸው በ2005 ዓ.ም መሆኑ ያልተካደ ሆኖ እያለ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መመሪያ ቁጥር 2003 ስለመሆኑ የክልሉ ሰበር ችሎት በተቀበለበት ሁኔታ እና መመሪያ ቁጥር 2003 ምትክ የሚሰጠው የነበረው ይዞታ መጠን የሚል ስለመሆኑ ተጠሪው በክልሉ ሰበር ችሎት ባቀረበው መልስ በገለፀበት ሁኔታ አመልካች የተሰጣቸውን 140 ካ.ሜ ይዞታ ለሌላ ወገን ስላስተላለፉ ቀሪ ይዞታ አለኝ በሚል ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን ታህሳስ 21/2012 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች ከገጠር ወደ ከተማ ሲገቡ ይዘውት የገቡት የመሬት ስፋት 400 ካ.ሜ መሆኑን፣ በዛን ወቅት በነበረው የልማት ተነሽነት መመሪያ ቁጥር 2002 በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 5.5 መሰረት ከቦታቸው የሚነሱ ሰዎች የሚሰጣቸው የይዞታ ስፋት 250 ካ.ሜ ያለ ካሳ፣ 140 ካ.ሜ ደግሞ ከካሳ ጋር እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ ለአመልካች 140 ካ.ሜ ከካሳ ጋር የተሰጣቸው መሆኑንና አመልካች በዚህ ጉዳይ በጊዜው ያቀረቡት ቅሬታ ያልነበር መሆኑን፣ በቦታው አምነውበት ካርታና ሳይት ፕላን ተሰጥቷቸው በ2006 ዓ.ም ለአቶ ኪሮስ ገ/መስቀል የሸጡላቸው መሆኑን፣ በዚህ ምክንያት በአንድ ይዞታ ሁለት ሰነድ እንደማይሰጥ ህጉ የደነገገ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ጥር 23/2012 ዓ.ም በሰጡት የመልስ መልስ በወቅቱ የነበረው መመሪያ ከገጠር ወደ ከተማ የገባ ቦታ እንደ ስፋቱ መጠን ከ140 እስከ 500 ካ.ሜ መስጠት እንደሚፈቅድ የደነገገ መሆኑን፣ 400 ካ.ሜ ይዞ ወደ ከተማ የገባ ሰው 400 ካ.ሜ እንዲሰጠው ህጉ የደነገገ መሆኑን፣ መመሪያ 2002 የሊዝ መመሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ከተማ ውስጥ ለቆየ ቦታ እንጂ ከገጠር ወደ ከተማ ለገባ ቦታ አለመሆኑን፣ የአመልካች ጉዳይ የሚዳኘው በመመሪያ 2003 መሰረት መሆኑን፣ ተጠሪ በመሰረተ ልማት ምክንያት የሚነሱ ከካሳ ጋር ከሆነ 140 ካ.ሜ ያለካሳ ከሆነ 250 ካ.ሜ ነው የሚሰጣቸው በማለት ያቀረበው መልስ ህግን መሰረት ያላደረገ መሆኑንና ህጉ በተወሰደው ቦታ መጠን አስፈላጊም ከሆነ ካሳ ተጨምሮለት ምትክ ቦታ እንዲሰጥ የሚደነገግ መሆኑን፣ የተሰጣቸው ካሳ ካለመኖሩም በላይ ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ መሆኑን፣ ይዞታውን ለ3ኛ ወገን ሸጠዋል ለሚለውም የተሰጣቸውን 140 ካ.ሜ ሸጠው ቀሪ 260 ካ.ሜ ለመጠየቅ የሚከለክላቸው ህግ አለመኖሩን በመግለፅ በቀረበው ቅሬታ መሰረት ሊወሰንልኝ ይገባል ሲሉ ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳይ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ይዘት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው አመልካች ክስ ያቀረቡት በልማት ምክንያት በተወሰደባቸው 400 ካሬ ሜትር ይዞታ ምትክ 400 ካሬ ሜትር ቦታ ሊሰጣቸው ሲገባ ከህግ አግባብ ውጭ ተቀንሶብኛል ባሉት 260 ካሬ ሜትር ላይ ነው፡፡ በእርግጥ ከምትክ ቦታ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ባለው መመሪያ ላይ በግራ ቀኙ መካከል ያለመግባባት እንዳለ ከሚያቀርቡት ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም የክልሉ ሰበር ችሎት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በ2003 ዓ.ም. የወጣው መመሪያ መሆኑን እና በመመሪያው መሰረት ከከፍተኛው የከተማ ይዞታ መጠን እስካላለፈ ድረስ ምትክ ቦታ የሚሰጠው በተወሰደው ይዞታ መጠን ስለመሆኑ ገልጿል፡፡ ይህ የሰበር ችሎቱ የህግ መረጣ እና አተረጓጎም አግባብ አይደለም በሚል በአሁን ተጠሪ በኩል ሥርዓቱን ጠብቆ የቀረበ የሰበር ቅሬታም ሆነ ግልፅ ክርክር የለም፡፡ ይህ በሌለበት አሁን ላይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሌላ የህግ ማዕቀፍ ነው በማለት ተጠሪ የሚያቀርበው መከራከሪያ ሥነ ሥርዓቱን የጠበቀ ባለመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ያለው በ2003 ዓ.ም የወጣው መመሪያ መሆኑን ከለየ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀናው በመመሪያው መሰረት 400 ካሬ ሜትር ምትክ ቦታ የሚገባህ ቢሆንም መጠኑ ተቀንሶ 140 ካሬ ሜትር ቦታ ብቻ ሲሰጥ ተቀብለህ ከ5 ዓመት ቆይታ በኋላ ቀረኝ ያልከውን ይዞታ ለመጠየቅ መብት የለህም በሚል ነው፡፡

እንግዲህ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 78 እና 79 መሰረት ለፍርድ ቤቶች የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን ህግን መሰረት ያደረገ የዳኝነት አገልግሎት መሰጠት ነው፡፡ ህግን መሰረት ያደረገ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት ማለት ፍርድ ቤት ለሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ፣ በተለይም ውሳኔው መብትን የሚያሳጣ በሆነ ጊዜ ግልፅ የህግ መሰረት ሊኖር ይገባል ማለት ነው፡፡ ለውሳኔው መሰረት የሆነ ህግ ሳይጠቀስ በደፈናው መብትን የሚያሳጣ ውሳኔ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ውድቅ ያደረገው ክሱ የክስ ምክንያት የለውም በሚል በመሆኑ በዚሁ ነጥብ ላይ አንድ ነገር ማለቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በእርግጥ የክስ ምክንያት የሌለው የክስ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 231(1(ሀ)) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ የክስ አቤቱታ የክስ ምክንያት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመለየት ፍርድ ቤቶች በክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ክሱን ያቀረበው ወገን የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ህግ የሚፈቅድለት መሆን አለመሆኑን በጥያቄነት ይዘው ሊመረምሩ እና “የክስ

ምክንያት አለው!" ለማለት ለተጠየቀው ጥያቄ አዎንታ መልስ ሊኖራቸው እንደሚገባ ይኸው ችሎት በሰ/መ/ቁ/45247 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት ክስም በዚሁ ስሌት መሰረት ሊቃኝ ይገባል፡፡

በዚሁ አግባብ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከህግ አግባብ ውጭ የተቀነሰብኝ 260 ካሬ ሜትር ምትክ ይዞታ ሊሰጠኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ ይኸው ፍሬ ነገር ቢረጋገጥ አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት እንዳያገኙ የተቀመጠ ግልፅ የህግ ክልከላ የለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ከሆነ ደግሞ ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ ለአመልካች የሚገባቸው መሆን አለመሆኑ በክርክር ሂደት በማስረጃ የሚነጥር ከሚሆን በቀር የክስ አቤቱታው የክስ ምክንያት የለውም ተብሎ በመጀመሪያው የክርክር ምዕራፍ ውድቅ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡ እናም የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ የክስ ምክንያት የለውም ማለቱ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ምክንያት ጨምሮ ይህንኑ ማፅናቱ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተገባበር ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሲጠቃለል ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/114270 ላይ ግንቦት 09/2011 የሰጠው ውሳኔ፣ የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/26177 ላይ የካቲት 05/2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የሐውልቲ ክ/ከተማ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/010931 ላይ ታህሳስ 05/2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የሐውልቲ ክ/ከተማ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ በክሱ ሥረ ነገር ክርክር ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና የተጠቀሰ ማስረጃም ካለ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 341(1) መሰረት ጉዳዩ ይመለስለት፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዮ/መ

የሰ/መ/ቁ. 187340

መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ዙፋን መንግስቱ

2. አቶ አየነው ቢሻው

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ በልስቲ አባተ

2. ወ/ሮ እመቤት አባተ

3. አቶ አንዷለም አባተ

4. ወ/ሮ የምስራች አባተ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የውርስ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ደንብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት አማራ ክልል ቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ደግሞ ከሌሎች አራት ግለሰቦች ጋር ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በቀን 08/07/2009 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ሟች አያታችን በ1989 ዓ.ም በድልድል ያገኙት፣ እኛም ከአባታችን ጋር እንደልጅና ቤተሰብ የተቆጥርንበትን 13 ገመድ የውርስ መሬት ተከሳሾች በተለያየ መጠን ተከፋፍለው በመያዝ እየተጠቀሙበት በመሆኑ ለቀው ያስረክቡን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው በሰጡት መልስ አባታችን (የአመልካቾች አያት) የሞተው በ1997 ዓ.ም ሲሆን አመልካቾች ደግሞ የወራሽነት ማረጋገጫ ያወጡት በ2009 ዓ.ም ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ደረጃም የአማራጭ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ የሰማው የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ውጭ ያሉት ተከሳሾች በሙሉ የያዟቸውን መሬቶች

በመልቀቅ ለአመልካቾች ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪዎች የይግባኝ አቤቱታ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም በአቤቱታው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች መሬቱን ከ2001 ዓ.ም ጀምረው እንደያዙት በማስረጃ ተረጋግጧል፤ አከራካሪውን መሬት በሚመለከት ግራ ቀኙ ወራሽ ሲሆኑ በወራሾች መካከል ለሚነሳ ክርክር ተፈፃሚነት ባለው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000(1) መሠረት ሶስት ዓመት ጊዜ ስለሆነና አመልካቾች ክሳቸውን ያቀረቡት ተጠሪዎች መሬቱን ከያዙ ከሶስት ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የወረዳው እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች በቀን 10/04/2012 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዎች ወራሽ ነን ሳይሉ፣ እንዲሁም የወራሽነት ማስረጃ ባላቀረቡበት ያልተነሳን የውርስ ይርጋ ክርክር እራሱ በማንሳት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) ላይ የተመለከተዉ የሦስት ዓመት የይርጋ ደንብ በእርሻ መሬት የዉርስ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚነት ያለዉ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ብሏል፡፡ ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጡ በሚል መጥሪያ የተላከላቸው ቢሆንም ባለመቅረባቸዉ መልስ የማቅረብ መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አዉራሽ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ1997 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የያዙት በ2001 ዓ.ም መሆኑ ስለመረጋገጡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይዘት የሚያሳይ ሲሆን፣ አመልካቾች ይህን ፍሬ ነገር በመካድ አይከራከሩም፡፡ ክርክሩ በወራሾች መካከል ስለመሆኑም የታመነ ነዉ፡፡ አመልካቾች ተጠሪዎች ይርጋ መቃወሚያ አላነሱም በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም፣ ተጠሪዎች ክሱ በይርጋ እንደሚታገድ የመጀመሪያ መቃወሚያ ያነሱ ስለመሆኑ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በቀን 22/06/2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ከሰጠዉ ብይን ይዘት ለመገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያን ዉድቅ ያደረገዉ ተጠሪዎች መሬቱን ከያዙት 10 ዓመት ያልሞላዉ መሆኑን ነዉ፡፡ በአንፃሩ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰዉ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉ ይርጋ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000(1) ላይ የተመለከተዉ

የሦስት ዓመት ጊዜ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡ በመሆኑም ከዉርስ ይርጋ ጋር በተያያዘ በፍትሐብሔር ህጉ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት አላቸዉ ወይ የሚለዉን ነጥብ በሰበር አጣሪ ችሎት ከተያዘዉ ጭብጥ አንፃር መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ አሁን በአገራችን በስራ ላይ ባለዉ የመሬት ስሪት መሠረት መሬት የህዝብ እና የመንግስት በመሆኑ እንዲሁም መሬት የእራሱ የሆነ የተለየ ባህርይ ያለዉ ቢሆንም፤ ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ መብቶች እና ግዴታዎች፣ ግንኙነቶች የሚመሩት በንብረት ህግ አጠቃላይ መርሆዎች በመሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀምን አስመልክቶ የሚወጡ ህጎች/አዋጆች በንብረት ህግ ማዕቀፍ ዉስጥ የሚመደቡ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከንብረት ጋር በተገናኘ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ህጎች እና መርሆዎች ከመሬት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክርክር እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የንብረት ህግ ማለት ለአንድ ንብረት ባለመብት ወይም ባለይዞታ የሆነ ሰዉ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት የሚገዛ ነዉ፡፡ የንብረት ህግ አንድ ሰዉ በአንድ ንብረት ላይ ባለቤትነት ወይም ባለይዞታ ሊሆን የሚቻልበትን መንገድ፤ የመብቱ ዓይነት፣ ስፋት እና ማዕቀፍ፤ መብቱ ከአንዱ ወደ ሌላ ሊተላለፍ የሚችልበትን ሥርዓት የሚደነግግ የህግ ክፍል ነዉ፡፡ ንብረትን የመከታተል መብት፣ በመብቱ ማዕቀፍ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የመጠቀም መብት እንዲሁም ክስ አቅርቦ መብትን የማስከበር መብት የንብረት ባለ ሀብት ወይም ባለይዞታ መሆን ከሚሰጣቸዉ መብቶች ዉስጥ ዋነኞቹ ናቸዉ፡፡

አንድ ሰዉ የአንድ ንብረት ባለመብት ወይም ባለይዞታ መሆኑ የሚታወቀዉ እና የንብረት ባለ ሀብት ወይም ባለይዞታ መሆን በሚሰጣቸዉ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለዉ ንብረቱን በህግ አግባብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑም ከአጠቃላይ የንብረት ህግ ጽንሰ ሃሳብ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ስለሆነም አንድን ንብረት አስመልክቶ የሚቀርበዉን ክስ ተከትሎ ንብረትን የሚመለከት የህግ ክፍል ተፈፃሚ የሚሆነዉ ከሳሽ ክሱን ያቀረበዉ ንብረቱን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በእጁ ካደረገ በኋላ በንብረቱ ላይ ያለዉ መብት እንዲከበርለት የቀረበ ክስ መሆኑ በክሱ የተረጋገጠ ሲሆን ነዉ፡፡ ይህም ማለት አንድ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ንብረትን የሚመለከት መሆኑ ብቻዉን ጉዳዩን የንብረት ክርክር አያደርገዉም ማለት ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ንብረትን የሚመለከት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ዳኝነት ሁለት ገጽታዎች ያሉት ሲሆን አንደኛዉ የንብረት ባለሀብትነት ወይም ባለይዞታነትን ወይም ከንብረቱ ጋር በተያያዘ ያለዉን ማንኛዉንም መብት ለማስከበር የሚቀርብ ዳኝነት ሲሆን፤ ሁለተኛዉ የንብረት ባለቤትነት ወይም ባለይዞታነት መብት በፍርድ ኃይል እንዲተላለፍለት በዚህም የንብረቱ ባለሀብት ወይም ባለይዞታ ለመሆን የሚቀርብ ዳኝነት ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ በንብረት ህግ ማዕቀፍ የሚመራ ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ዓይነት ለቀረበዉ የመብት ይተላለፍልኝ ጥያቄ መሠረት የሆነዉን ምክንያት መሠረት በማድረግ የሚወሰን ሲሆን እንደየጉዳዩ ባህርይ በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች መሠረት የሚዳኝ ነዉ፤ ይህም ማለት ለቀረበዉ የመብት ይተላለፍልኝ

ዳኝነት መሠረቱ ዉል ከሆነ የዉል ህግ ድንጋጌዎች፣ ዉርስ ከሆነ የዉርስ ህግ ድንጋጌዎች፣ ጋብቻ መፍረሱን ተከትሎ የቀረበ ከሆነ የቤተሰብ ህግን መሠረት በማድረግ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነዉ፡፡ ይህ፣ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት፣ ከመሬት ጋር የተያያዘ ለሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችም እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ይዞታችን ያላግባብ ተይዟል በሚል ሳይሆን ተጠሪዎች በዉርስ በእጃቸዉ ካስገቡት መሬት ዉስጥ የዉርስ ድርሻቸዉን እንዲለቁላቸዉ ነዉ፡፡ ይህም የአመልካቾች የባለይዞታነት መብት ይገባናል ጥያቄ ዉርስን መሠረት ያደረገ ሆኖ በፍርድ ኃይል በዉርስ በሚተላለፍላቸዉ ይዞታ ላይ ባለመብት ለመሆን ያቀረቡት ክስ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009ም ሆነ ከእርሱ በፊት የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/98 የገጠር መሬት በዉርስ የሚተላለፍባቸዉን ሁኔታዎች በተመለከተ የተለየ ድንጋጌ ቢኖራቸዉም፣ የገጠር መሬት በዉርስ እንዲተላለፍ ዳኝነት የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ የተለየ ድንጋጌ የላቸዉም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ደንብም ቢሆን ያላግባብ የተያዘን የገጠር መሬት ለማስለቀቅ ለሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄ እንጂ (ይህ የይርጋ ደንብ ይዞታዬ ያላግባብ ተይዟል በሚል ለሚቀርቡ ለሁሉም ጉዳዮች ተፈፃሚነት አለዉ ወይ? የሚለዉ ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ) የባለ ይዞታነት መብት ይተላለፍልኝ በሚል ዉርስን መሠረት በማድረግ ለሚቀርብ ክስ ተፈፃሚነት ያለዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ያቀረቡት የዉርስ ድርሻ ይገባኛል ጥያቄን በተመለከተ ተፈፃሚነት ያለዉ ህግ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1000 ላይ የተመለከተዉ የይርጋ ድንጋጌ እንጂ ከይዞታ ክርክር ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክስ የተመለከተዉ የአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ሊሆን አይገባም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፍትሐብሔር ህጉን አንቀጽ 1000(1) ላይ የተመለከተዉን ድንጋጌ በዋቢነት በመጥቀስ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነዉ በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-78188 በቀን 08/03/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 186431

ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ ወ/ሮ አዝመራ መኮንን ገ/መድን

ተጠሪዎች፡ 1ኛ አቶ ገ/ሂወት መኮንን ገ/መድን

2ኛ ወ/ሮ አኸዛ ሃ/ስላሴ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የይዞታ/የከተማ ቦታ/ ክርክር የተመለከተ ሲሆን አመልካች 1ኛ ተጠሪ ወንድሜ በቀን 21/05/1994 ዓ.ም ከነባር ይዞታው ውስጥ 200 ካ.ሜ ሸጦልኝ እየኖርኩ እያለ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ፍቺ በመፈፀማቸው ምክንያት የአመልካችም ቤትና ቦታ በፍ/ቤት የጋራ ሃብት ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የአመልካችን ቤትና ቦታ 10ሜ x 20ሜ = 200 ካ.ሜ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በዓዲ ሓቂ ወረደ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስም 1ኛ ተጠሪ ወንድሜ ሲሆን አዋሳኙ በክሱ የተገለፀውን 200 ካ.ሜ በቀን 21/05/1994 ዓ.ም በብር 2,500.00 በቤተዘመድ ሽማግሌዎች ፊት በጽሁፍ የሸጠልኝ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ወንድሜ በመሆኑ በእምነት እየኖርኩ እያለሁ ለኔ የሸጠልኝ ቤትና ቦታ ከራሱ ጋር ጨምሮ ጠቅላላ 20x20 = 400 ካ.ሜ በከተማ ማስፋፋት ምክንያት ወደ መቐለ ስለገባ በስሙ እንዲጠና ከተደረገ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ጋብቻ በመፈፀም አንድ ላይ እየኖሩ እያለ በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ፍቺ ፈጽመው የንብረት ክፍፍል እንዲያደርጉ ሲወሰን የ1ኛ ተጠሪ ቤትና ቦታ እንዲሁም የአመልካች ቤትና ቦታ ጨምሮ የጋራ ሃብት ተብሎ የተወሰነ መሆኑን በዚህ ሳምንት የሰማሁ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ የሸጠልኝ ቤትና ቦታ 10x20 ካ.ሜ እንዲያስረክበኝ

ወይም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ400 ካ.ሜ ውስጥ የ1ኛ ተጠሪ ድርሻ 10x20 = 200 ካ.ሜ ለአመልካች ይገባል ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪዎች በተናጠል በሰጡት መልስም 1ኛ ተጠሪ በክሱ አዋሳኝ እና ስፋቱ የተገለፀው ቤትና ቦታ የ1ኛ ተጠሪ እና የ2ኛ ተጠሪ የጋራ ሃብትና ንብረት ሆኖ እያለ ለብቻዬ ከባለቤቴ እውቅና ውጭ እና ያላመነችበትን ለአመልካች በብር 2,500.00 ብር ሽጬላት ነበር ነገር ግን ስሕተት መሆኑን በማመን ገንዘቡን ለአመልካች በቀን 07/10/2008 ዓ.ም ከወንድሜ አቶ ወ/ገብርኤል መኮንን ተቀብዬ በአምስት ምስክሮች ፊት መልሼላታለሁ፡፡ ቤትና ቦታውም በፍርድ ያለቀ እና ሸጠን የተካፈልነው ስለሆነ ልጠየቅበት አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስም 1ኛ ተጠሪ እና አመልካች ወንድምና እህት በመሆናቸው 2ኛ ተጠሪን ለማጉላላት እያደረጉ ያሉት ሴራ እንጂ ከጋራ ሃብታችን 400 ካ.ሜ ውስጥ አንድ ክፍል የያዘ ቤት እንደሸጠላቸው አላውቅም አልጠየቅበትም፡፡ ሆኖም ግን አመልካች የ1ኛ ተጠሪ እህት ሲሆኑ እኔ እና 1ኛ ተጠሪ ከማህበራዊ ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌደራል ሰበር ችሎት በዚህ የጋራ ሃብት ስንከራከር የእውነት ቢሆን ኖሮ በዋና ጉዳያችን ከውሳኔ በኋላ ይሁን ወይም በአፈፃፀም ወቅት በሕጉ ጣልቃ ገብተው በተከራከሩ ነበር ስለሆነም ክሱ አግባብነት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የዓዲ ሓቂ ወረደ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በሕግ የሚፀና የሽያጭ ውል ሳይኖር አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት ክስ በአግባቡ አይደለም፡፡ተጠሪዎች እንዲያስረክቧቸው የሚወሰን ቤትና ቦታ የለም በማለት እና 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ገንዘብ ተቀብለው የሸጡላቸው የነበረው ቦታ ውል አፍርሰው ቦታቸውን ስለወሰዱ ብር 2,500.00 ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የዓዲ ሓቂ ወረደ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ነጥብ አልተገኘም በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 337 መሰረት የይግባኝ ባይ ቅሬታውን በመሰረዝ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት አልተገኘበትም በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የወረዳ ፍ/ቤት ለውሳኔው መነሻ ያደረገው በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መሀል የተፈፀመ የቦታና ቤት ሽያጭ ውል፣ ውል ለማጽደቅ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ አልፀደቀም የሚል ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 እና 1815 መሰረት በማድረግ ውሉ በሕግ ፊት የፀና አይደለም በሚል ክሴን ውድቅ ማድረጉ ወረዳ ፍ/ቤት በፍርድ ሐተታው ላይ 1ኛ ተጠሪ

ከአመልካች ጋር ያደረገው የቦታ እና ቤት ሽያጭ ውል መኖሩን አልካደም አምኗል ሲል ሓተታው ላይ ካሰፈረው ጋር ሲታይ እርስ በርሱ የሚጋጭ ከመሆኑም በላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 13 በሰ/መ/ቁ 36887 በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያሽያጭ ውል መኖሩን በማመን ነገር ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 መሰረት ውል ለማፅደቅ ስልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ አልፀደቀም በሚል ክርክር የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ሊባል እንደማይገባው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723(1) ፤ 2878 በማያያዝ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከዚህ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ከመሆኑም በላይ 1ኛ ተጠሪ ያቀረበው ክርክር ከአመልካች ጋር የቦታና ቤት ሽያጭ ውል እንደነበራቸው አምኖ ነገር ግን ውሉ ፈርሶ ገንዘቡን መልሼላታለሁ ሲል የተከራከረው ውሉ ፈርሶ ገንዘቧን መመለሱን በማስረጃ ያልተረጋገጠ ሆኖ እያለ ወረዳ ፍ/ቤት ውሉ በሚመለከተው አካል አልፀደቀም በሚል ክሴን ውድቅ ማድረጉ እና ጉዳዩን በይግባኝ የቀረበላቸው ፍ/ቤቶችም ስሕተቱን ያለማረማቸው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔያቸው ተሽሮ ዳኝነት የጠየኩት 200 ካ.ሜ እንዲያስረክቡኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አከራካሪ የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በአመልካችና በተጠሪ መካከል መደረጉን ባልተካካዱበት ሁኔታ ውሉ በሚመለከተው አካል ዘንድ አልተመዘገበም በማለት ውሉ ይፍረስ ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተወሰነበት አግባብነት ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስም በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በ21/5/1994 ዓ.ም 200 ካ.ሜ በብር 2,500 ብር ቤትና ቦታ ለመሸጥ ቦታው ገና ወደ ከተማ ከመካለሉ በፊት በገጠር እያለ በመንደር ውል መስማማታችን የማይካድ ነው፡፡ ስለሆነም የሽያጭ ውሉ በሚፈፀምበት ጊዜ 1994 ቦታው በወቅቱ በገጠር ይተዳደር እንደነበረና 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች የሸጥኩላቸው ቤትና ቦታ ከመነሻውም መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የነበረበትና የገጠር ጥሻ ቦታ ተቆርጦ የተሸጠ በመሆኑ አካባቢው ወደ ከተማ ሲካለል አመልካች ከገጠር ወደ ከተማ ቦታው ርክክብ ሲደረግ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ከገጠር ወደ ከተማ ሊተላለፍ አልቻለም፡፡ ይህም በገጠር የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም እንዲሁም በሀገራችን ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 የአርሶ አደር ቤት መሸጥ መለወጥ እንደማይቻል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በተለያዩ ጊዜያትና መዛግብት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም የሽያጭ ውል መኖሩ ባይካድም ተፈፀመ የተባለው ውል ከሕግ ውጭና ቮይድ በሆነ ውል ስለነበረ 1ኛ ተጠሪ በዚህ ከሕግ ውጭ ተፈፀመ በተባለው የሽያጭ ውል የምገደድበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ቦታው በ1ኛ ተጠሪ ስም እኔ በማላውቀው ሁኔታ እንዲጠና አድርገዋል የሚሉት አመልካች ውሉ ትክክል ነበር ቢሉ ጥናቱ ተከታትለው ማስጠናት

የነበራባቸው ራሳቸው እንጂ 1ኛ ተጠሪ እንዲጠና አላደረገም የሚሉት አግባብነትና የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው 1ኛ ተጠሪ ምንም እንኳን 200 ካ.ሜ መሸጡን ባይገልጽም ቤትና ቦታው የጋራ ሃብት ነው ተብሎ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ እስከ ፌደራል ሰበር ድረስ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበረን ክርክር ባለቤቱ አይደለችም ቦታው ወደድኩሽ ወደድኩህ ከመባባላችን በፊት የተፈራ ሃብት ነው ብሎ ክርክር በማንሳቱ ምክንያት ተከራክረን ቤትና ቦታው የጋራ ሃብት መሆኑን በፌደራል ደረጃ የተወሰነ ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ እኔ በማላውቀውና በሽያጭ ውሉ ላይ ባልፈረምኩበትና ባልተስማማሁበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ በኃላፊነት የምጠየቅበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 መሰረት ውሉ በሕጋዊ አካል አለመመዝገቡ እኔን 2ኛ ተጠሪ በመንደር ውል ባላወኩትና ባላመንኩበት የምገደድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ደረጃም ለክርክር መነሻ የሆነው ቤትና ቦታው በሽያጭ ወደ ሶስተኛ ወገን በቀን 12/03/2011 ዓም ለአቶ ኃይላይ ገ/ዪሃንስ ለተባለው በሽያጭ ተላልፏል፡፡ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ውድቅ በማድረግ በነፃ እንዲያሰናብተኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ ከተገቢው ህግና፤ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡አመልካች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ ከ1ኛ ተጠሪ ገዛን የሚሉት ጥር 21 ቀን 1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ሲሆን ይህንን ይዞታ ሲገዙት በቦታው ላይ አንድ ክፍል ቤት የነበረው መሆኑን ገልፀው ከመከራከራቸው በተጨማሪ ይህንን ቦታ ሲገዙ ይዞታው ከተማ ክልል ያልገባ መሆኑን በሚያመለክት መልኩ …ይዞታው በከተማ መስፋፋት ምክንያት ወደ መቐለ ስለገባ…በማለት ገልፀው መከራከራቸው ክርክር የተነሳበት ይዞታ ሽያጭ ተፈፀመ በተባለበት ወቅት የገጠር መሬት መሆኑን ያሳያል፡፡

ክርክር ያስነሳው ይዞታ የገጠር መሬት ከሆነ ደግሞ ሽያጩ በተከናወነበት ጊዜ ተፈፃሚነት ያላቸውን የክልሉን የገጠር መሬት አጠቃቀም ለመወሰን የወጡትን አዋጆች ስንመረምራቸው አዋጅ ቁጥር 23/1989 በአንቀፅ 5 የገጠር መሬትን መሸጥ የተከለከለ መሆኑ መመልከቱ ፤ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 55/1994 አንቀፅ 21(1) ይህንን ተላላፎ ሽያጭ ማከናወን የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስከትል መሆኑ መመልከቱ፤ በአሁኑ ወቅት ተግባራዊነት ባለው አዋጅ ቁጥር 239/2006 ተመሳሳዩ ክልከላ መቀመጡ በገጠር እርሻ መሬት ላይ ቤት ይኑርበትም አይኑርበትም በሽያጭ ማስተላለፍ የተከለከለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ አንድ ክፍል ቤት ያረፈበትን በሽያጭ እንደገዙት በፍሬ ነገር የተረጋገጠ ጉዳይ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው የገጠር መሬትን በሽያጭ

ማስተላለፍ በህግ ክልከላ የተጣለበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን የይዞታ ልረከብ የዳኝነት ጥያቄ የሽያጭ ውሉ ከመጀመሪያውኑ ህጉን ያልተከተለ ህገ ወጥ ስለሆነ ይዞታውን ለመረከብ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ተገቢነት የለውም በማለት መወሰኑ እና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ውሳኔ ማፅናታቸው የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40(3) እና አግባብነት ያላቸውን የክልሉን ህጎች መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የዓዲ ሓቂ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 05101 በ07/08/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ የመቐለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 27544 በ28/10/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት ይህንን ፍርድ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 118107 በቀን 13/01/2012 ዓ.ም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**የግራ ቀኙ ክርክር ተገቢውን እልባት ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የሰ.መ.ቁ.185848

ሚያዚያ 28 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡........አቶ ጌታሰዉ አገሩ ለማ

ተጠሪዎች፡.........1. አቶ አስማማዉ ለማ

2. ወ/ሮ አባይ ለማ

3. ወ/ሮ እማምላክ ለማ

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍርድ

ይህ የእርሻ መሬት ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በሸበል በረንታ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪዎች የሥር 1ኛ፣ 3ኛና 5ኛ ከሳሾች፣ በዚህ ችሎት የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑት ሁለት ሰዎች ከሳሾች ሆነው ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-77218 ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የሥር ከሳሾች በሥር በወረዳ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የከሳሾች ሟች አባት አቶ ለማ አይችሉህም በቀን 3/9/2009 ዓ.ም በተደረገ የስጦታ ውል የመሬት ይዞታዉን ለተከሳሽ ያስተላለፈ ቢሆንም አባታችን እድሜዉ በመግፋቱ ተታሎ ያደረገዉ ዉል በመሆኑ፤ ተከሳሽም ሟችን ያልጦረ እና ከውርስም የነቀለን ዉል በመሆኑ እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የስር ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ በሰጠዉ መልስ የስጦታ ዉሉ የተደረገው ስጦታ ሰጪው ወዶና ፈቅዶ በህጉ መሰረት በመሆኑ ሊፈርስ አይገባዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት፣ በሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ የሚገባዉ የስጦታ ዉሉ ተደረገ በተባለበት ወቅት ስራ ላይ የነበረዉ የተሻሻለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 17 (1) በመሆኑ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት የመሬት ስጦታ ከመደረጉ ሶስት አመት በፊት የስጦታ ተቀባዩ የስጦታ ሰጪዉን የመጦር ግዴታ ያለበት ስለሆነ፣ ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ስጦታ ሰጪዉን ስጦታዉ ከመደረጉ በፊት ከ2 አመት ከ4 ወር ጀምሮ ሲጦረዉ የነበረዉ የተከሳሽ አባት እንጂ ተከሳሽ ባለመሆኑ የህጉን መስፈርት ስለማያሟላ የስጦታ ውሉ ፈርሷል በማለት ዉሳኔ አሳልፏል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ እና የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ቅሬታዉን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ እና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ9/3/2012 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአመልካች አያት የሆኑት አቶ ለማ አይችሉህም የመሬት ይዞታ ለአመልካች ስጦታ ያደረገዉ በህይወት እስካሉ ድረስ እንዲጦረዉ በመሆኑ፤ የመሬት ስጦታ ዉሉም በክፍሉ ወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የፀደቀ በመሆኑ፣ አመልካች ከዚህ ዉጭ ሌላ መሬት የሌለኝ ሲሆን ተጠሪዎች ግን የራሳቸዉ መሬት ያላቸዉ በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ፍትሐዊ ስላልሆነ እንዲሻርልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣አከራካሪው የስጦታ ውል ሊታይ የሚገባዉ የተሻሻለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 ነዉ ወይስ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ነዉ? የሚለዉን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት በ6/6/2012 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ አመልካች የሚች አባታችን አቶ ለማ አይችሉህም የልጅ ልጅ ስለሆነ ከአባታችን ጋር ለአንድ ቀንም አብሮት አልኖረም እርሱ የሚኖረዉም አዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ፣ የስጦታ ዉሉ በተደረገበት ቀን በሥራ ላይ የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/98 ነዉ፤ የስጦታ ዉሉ ከአዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 17 እና አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 16 ጋር የሚጋጭ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ አግባብ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ስላልሰጠ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራ ቀኙ ያደረጉት የጽሑፍ ክርክር ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር

አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አመልካች የሟች አቶ ለማ አይችሉህም የልጅ ልጅ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ የሟች ልጆች መሆናቸዉ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ሟች በሕይወት እያለ በ3/9/2009 ዓ.ም በተደረገዉ የመሬት ስጦታ ዉል ይዞታዉን ለአመልካች የሰጠ በመሆኑ፣ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር ሟች ይህን ስጦታ ያደረገዉ ተታሎ እና አመልካች ሟችን ያልጦረና ተጠሪዎችን ከዉርስ የነቀለ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል የሚል ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ስጦታዉ ሕጋዊ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ በዚህ መሰረት በሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አመልካች አያቱን ሟች አቶ ለማ አይችሉህምን እንዳልጦራቸዉ፣ ሟችን ለ2 ዓመትና 4 ወራት የጦራቸዉ የአመልካች አባት አቶ አገኑ ለማ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ሟች ለአመልካች ያደረጉት የመሬት ስጦታ ዉል ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ወይስ አይደለም? በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ የትኛዉ ነዉ? የሚለዉን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ሟች አቶ ለማ በሕይወት እያሉ የስጦታ ዉል ያደረጉት በመሬት ይዞታ ላይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደሚታወቀዉ ስጦታን በአጠቃላይ በሚመለከት በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 2427 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር የተጠቀሰ ሲሆን፣ በእነዚህ ድንጋጌዎች ሥር የስጦታ ትርጉም፣ ስጦታ ሊያሟላ የሚገባቸዉ መስፈርቶች፣ ስጦታ የሚያስከትለዉ ዉጤት እና ስጦታን ሊያስፈርሱ የሚችሉ ምክንያቶችም ተመልክተዉ እናገኛለን፡፡ የስጦታ ሰጪ ወራሾች አዉራሻቸዉ ያደረገዉ ስጦታ እንዲሻርላቸዉ ክስ አቅርበዉ ዳኝነት የሚጠይቁበት ምክንያቶች በዚህ ሕግ አንቀጽ 2449 ሥር ተዘርዝረዉ ይገኛሉ፡፡ የስጦታ ሰጪ ወራሾች በዚህ ድንጋጌ መሰረት ስጦታዉ እንዲሻርላቸዉ የሚያቀርቡት ክስ ስጦታ መኖሩን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ሟች ለአመልካች ስጦታ አድርጓል የተባለዉ የመሬት ይዞታ በመሆኑ ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 17 መሰረት የመሬት ባለይዞታ የይዞታና የመጠቀም መብትን በስጦታ ዉል ለማስተላለፍ የሚችልበትን አግባብ ይደነግጋል፡፡ አሁን በተያዘዉ ጉዳይ ሟች መሬቱን በስጦታ ዉል ለአመልካች አስተላልፏል በተባለ ጊዜ ሥራ ላይ የነበረዉ ሕግ አዋጅ ቁጥር 133/1998 መሆኑን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ሥር እንደተመለከተዉ የመሬት ስጦታ ዉል ተደርጓል ለማለት በድንጋጌዉ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዉ ሲገኙ ብቻ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች መካከል አንዱ በዚህ አንቀጽ 17 (1፣ ለ) ሥር የተደነገገዉ ሲሆን፣ ይዘቱም ስጦታ ተቀባዩ የባለይዞታዉን መሬት እያረሰ ወይም ሌላ ሥራ እየሰራ ስጦታዉ ከመከናወኑ በፊት ላሉት ሶስት ተከታታይ አመታት ሰጭዉን በነጻ ሲጦር መቆየቱ የታወቀ መሆን እንደሚገባዉ ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንጻር በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አመልካች ሟች በሕይወት እያለ ያልጠራቸዉ መሆኑ ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች ሟች በሕይወት እያለ አለመጠሩ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ የገጠር መሬት አዋጅ መሰረት የመሬት ስጦታ ዉል አለ ለማለት በአዋጁ የተመለከተዉ ቅድመ ሁኔታ ያልተሟላ መሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም ሟች ለአመልካች የመሬት ስጦታ ዉል አድርጓል፣ የመሬት ስጦታ ዉል አለ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ የሚመለከተዉ የመሬት ስጦታ ዉል በመሆኑ፣ በቅድሚያ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ የሚገባዉ የገጠር መሬት አዋጁ መሆኑ ብቻም ሳይሆን በመሬት አዋጁ መሰረት የመሬት የስጦታ ዉል አለ ለማለት በሕጉ የተገለጸዉ ቅድመ ሁኔታ ያልተሟላ ስለሆነ ከፍ ሲል የተጠቀሰዉ የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡ በሌላ በኩል ሟች በሕይወት እያሉ የስጦታ ዉል አድርጓልና በወቅቱ ስጦታዉ ተደርጓል የሚባለዉ በሥራ በነበረዉ አዋጅ መሰረት እንጂ ከዛ ወዲህ የክልሉ መንግስት የፖሊሲ ለዉጥ በማድረግ ያወጣዉን ሕግ መሰረት ተደርጎ መሆን የለበትም፡፡ በመሆኑም አዲሱ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረዉ አይገባዉም ብለናል፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት በዚህ ረገድ የያዘዉ ጭብጥ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

በዚህ አግባብ ሲታይ ሟች በ3/9/2009 ዓ.ም ለአመልካች አድርጓል የተባለዉ የመሬት ስጦታ ዉል በአዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 17 (1፣ ለ) መሰረት በድንጋጌዉ የተመለከተዉን ቅድመ ሁኔታ ያላሟላ በመሆኑ፣ ከመነሻዉ የመሬት ስጦታ ዉል አለ ለማለት ስለማይቻል፣ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጠው ዉሳኔ ተገቢ ነዉ፡፡ ይህ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ስለማያሳይ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ሟች በሕይወት እያለ ለአመልካች አድርጓል የተባለዉን የመሬት ስጦታ ዉል ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት ስለማይቻል የሚከተለዉ ተወስኗል፡፤

## ዉሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.03-77218 ጥቅምት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተደረገዉ ክርክር ምክንያት የደረሰዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁጥር 201181

ሚያዝያ 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ጳውሎስ አርሺሶ ኦሎንጀ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር ነ/ፈ ተወዳጅ መሀመድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች በጡረታ ከዳኝነት ስራቸው ሲነሱ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅሞች ለመወሰን በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት የሰሩበት የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ የሚደረግ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ስንመለከት አመልካች ለተጠሪ በመስከረም 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ሳገለግል ቆይቼ በጡረታ የተሰናበትኩ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1003/2009 መሰረት መብትና ጥቅሜ ይከበርልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም በቁጥር ገ/ኢ/1/33/39 በቀን 15/5/2013 ዓ.ም. በተጻፈ ምላሽ(ደብዳቤ) የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 መሰረት ከሀላፊነት የተነሱ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች በገንዘብ ተሰልተው ለባለመብቶች በአንድ ጊዜ የሚሰጡት መብቶች እና ጥቅሞች ለማግኘት ባለመብቱ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን ለአምስት አመት ማገልገል እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ አመልካች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት የሰጡት አገልግሎት ግን ከአንድ የምርጫ ዘመን ያነሰ በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ከሚያገኙ በስተቀር ሌሎች በገንዘብ ተሰልተው የሚገኙ መብቶች እና ጥቅሞችን ማግኘት አይችሉም፡፡ አመልካች በፌደራል ደረጃ በዳኝነት ከመሾማቸው በፊት በክልል መንግስት በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ የሰጡት አገልግሎት በአዋጁ አንቀጽ 53/3 መሰረት ሊያዝ አይችልም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በተጠሪ ጥያቄያቸው ውድቅ መደረጉን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በፌደራል ፍርድ ቤት በዳኝነት ሲያገለግል ቆይቶ በጡረታ የተሰናበተ ዳኛ በክልል መንግስት የተለያዩ የዳኝነት ደረጃዎች ላይ የሰጠው አገልግሎት እንዲታሰብ አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1003/2009 ስለማይፈቅድ አመልካች መብት እና ጥቅማ ጥቅም እንዲከበርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በተጠሪ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት የተጠሪን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት በተጠሪ እና በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ለማሳረም ሲሆን የቅሬታቸው ይዘት ሀምሌ ወር 2003 ዓ.ም. በወጣው የፌደራል ፍርድ ቤቶች እጩ ዳኞች ምልመላ ስርአት አፈጻጸም መመሪያ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ለመሾም ካስቀመጣቸው መስፈርቶች አንዱ የዳኝነት ሙያ አገልግሎት ዘመንን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካችም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኜ የተሾምኩት በከምባታ ጠንባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ስራ ለ19 አመት ከ5 ወር የሰጠሁት አገልግሎት ከትምህርት ደረጃዬ ጋር ታይቶ ነው፡፡ የዳኝነት ሙያ አገልግሎት በክልልም ይሁን በፌደራል አንድ አይነት ሙያ ነው፡፡ የዳኝነት ሙያ አገልግሎት አያያዝን አዋጁ በአንቀጽ 53/3 በዝምታ ያለፈው ዳኝነት የሙያ ተግባር ስለሆነ በክልል ፍርድ ቤት የተሰጠ የዳኝነት አገልግሎት ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት በሹመት ሲኬድ የክልል አገልግሎቱ የሚያዝ መሆኑን ታሳቢ በማረግ እንጂ የክልል አገልግሎት እንዳይያዝ ለመከልከል አይደለም፡፡ አዋጁ በዚህ መልኩ የማይተረጎም ከሆነ በመንግስት ከፍተኛ መሪዎች እና በዳኞች መካከል አድሎአዊ አሰራርን የሚፈጥር እና በህገ-መንግስቱ የተደነገገውን የእኩልነት መርህ የሚጥስ ነው፡፡ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ስራ ላይ በነበርኩበት ወቅት በፌደራል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት አገልግሎት የሰጠሁ ከመሆኑም በላይ በክልልም ሳገለግል የቆየሁት የአገራችንን ዜጎች እንጂ የሌላ አገር ዜጎችን አይደለም፡፡ አዋጁም ቢሆን መብትና ጥቅሞችን ለማግኘት ቢያንስ አምስት አመት ዳኛው ማገልገል እንዳለበት ከሚገልጽ ውጪ በፌደራል ፍርድ ቤት ብቻ ያገለገለ በሚል አያስቀምጥም፡፡ በመሆኑም በክልል የሰጠሁት አገልግሎት ሊያዝ አይገባም መባሉ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ታርሞ የማቋቋሚያ፤ የመኖሪያ ቤት፤ የተሽከርካሪ አበል እና የስንብት ክፍያ በመጨረሻ ላይ በወር ይከፈለኝ በነበረው የወር ደሞዝ ተሰልቶ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ አመልካች በክልል ፍርድ ቤቶች የሰጡት የዳኝነት አገልግሎት በአዋጅ ቁጥር 653/2001 የተመለከቱት ጥቅሞች እና መብቶች ለማግኘት ሊያዝላቸው አይገባም የመባሉን አግባብነት በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 78 እና 80 መሰረት በክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚሰጠው የፌደራል ዳኝነት አገልግሎት እና ከአዋጁ አንቀጽ 53/3 ድንጋጌ ጋር የተጣጣመ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በሰጠው መልስ በክልል የተሰጠ የአገልግሎት ዘመን በፌደራል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ለመሾም የሚያገለግል የስራ ልምድ ቢሆንም መብትና ጥቅሞችን ለማግኘት ታሳቢ የሚደረግ አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 የተቀመጡት መብትና ጥቅሞች ተፈጻሚ የሚሆኑት በፌደራል ደረጃ ቢያንስ ለአምስት አመት ለተሰጡ አገልግሎቶች ብቻ ነው፡፡ አመልካች መብትና ጥቅማቸውን መጠየቅ የሚችሉት አገልግሎት ከሰጡበት ክልል እንጂ ከፌደራል መንግስቱ አይደለም፡፡ አመልካች በፌደራል ደረጃ የሰጡት አገልግሎት ለ3 ዓመት ከ11 ወር ብቻ ስለሆነ በዚህ ጊዜ ታስቦ የስንብት ክፍያ ብቻ ከሚከፈላቸው በስተቀር ሌሎች መብትና ጥቅሞችን ማግኘት አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አመልካች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለ3 ዓመት ከ11 ወር በዳኝነት አገልግለው በጡረታ ሲሰናበቱ በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ሙያ የሰጡት የአገልግሎት ዘመን መብትና ጥቅማቸውን ለማግኘት በፌደራል መንግስት ታሳቢ ሊደረግ አይችልም የተባለበትን አግባብ ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ለ3 ዓመት ከ11 ወር ካገለገሉ በኋላ ከሐምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በጡረታ ተሰናብተዋል፡፡ አመልካች ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ከመሾማቸው በፊት በደቡብ ክልል ከምባታ ጠንባሮ ዞን ከፍተኛ እና በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በፕሬዝዳንትነት እና በዳኝነት ማገልገላቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ መካከል እያከራከረ ያለው አመልካች በጡረታ ሲሰናበቱ መብትና ጥቅማቸውን ለመወሰን በክልል ፍርድ ቤቶች ያገለገሉበት የአገልግሎት ዘመን ሊታሰብ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ክርክር ምላሽ ለማግኘት ከሀላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግስት መሪዎች፤ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶች እና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 635/2001 እና ማሻሻያውን አዋጅ ቁጥር 1003/2009 መመርመሩ ተገቢ ነው፡፡

በመጀመሪያም አዋጅ ቁጥር 653/2001ን መደንገግ ያስፈለገበትን መሰረታዊ አላማ ከአዋጁ መግቢያ (preamble) ላይ ስንመለከት የሀገር እና የመንግስት መሪዎች፤ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፤ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ለማስከበር ከፍተኛ የሀገር ሀላፊነትን በመሸከም የሚሰሩ በመሆናቸው ከሀላፊነት ሲነሱ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ችግር ሳይገጥማቸው የሀገርንና የራስን ክብር የሚያስጠብቅ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል፤ ከነበሩበት ኃላፊነት ቦታ አንጻር በሚሰጡት ውሳኔ ለጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥበቃና ከለላ ለመስጠት፤ በኃላፊነት በነበሩበት ወቅት ያካበቱትን እውቀት እና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም ለሀገር እድገት እና ልማት በቅንነት በታማኝነትና በትጋት እንዲሰሩ ለማበረታታት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት ከፍተኛ የመንግስት

ኃላፊዎች በጡረታ ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት ከሀላፊነት ሲነሱ የተለያዩ መብትና ጥቅሞች እንዲከበርላቸው ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ከሀላፊነት ከተነሱ በኋላ ስለሚገጥማቸው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ሳይጨነቁ ኃላፊነታቸውን በቅንነት፣በታማኝነት፣በገለልተኛነት እና በአጠቃላይ የስራውን ወይም የሙያውን ስነ-ምግባር በመጠበቅ የተጣለባቸውን ከፍተኛ የመንግስትና የህዝብ ሃላፊነት እንዲወጡ ለማስቻል ነው፡፡ እንደዚሁም በመንግስት ሃላፊነት ላይ በመቆየት ህዝብና ሀገርን ማገልገል እየቻሉ ሀላፊነታቸውን በመልቀቅ ወደሌላ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወደሚያስገኝ ስራ ለመሄድ በማሰብ ከሃላፊነታቸው እንዳይለቁ በማድረግ ያካበቱትን እውቀት እና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታ መፍጠር ሌላው አዋጁን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት ነው፡፡ የአዋጁ አላማ ይህ ከሆነ በአዋጅ ላይ የተመለከቱትን መብትና ጥቅሞች ለማግኘት ምን አይነት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው የሚለውን ቀጥሎ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

በተለይም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው አመልካች ከዳኝነት ኃላፊነታቸው በጡረታ ከተሰናበቱ በኋላ ያቀረቡት የመብት እና የጥቅማ ጥቅም የክፍያ ጥያቄ በመሆኑ ዳኞች ከዳኝነት ኃላፊነታቸው ከተሰናበቱ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና ማሻሻያ አዋጁ መሰረት የመብት እና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ማግኘት የሚችሉት መቼ ነው? የሚለውን ስንመለከት በአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 2/12-15 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት የመጀመሪያው መስፈርት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማለትም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ወይም የከፍተኛ ወይም ደግሞ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ማገልገል ነው፡፡ ይህም ማለት ዳኛው ከኃላፊነት በጡረታ ወይም በሌላ ህጋዊ ምክንያት በተነሳበት ወቅት በፌደራል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ሙያ ላይ ሲያገለግል የነበረ መሆን እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሌላው መስፈርት የአገልግሎት ዘመንን የሚመለከት ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 44/1፣46/1 እና 47/1 ድንጋጌዎች ማንኛውም ዳኛ ቢያንስ አምስት አመት አገልግሎ ወይም ከሁለት አመት ተኩል ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት እና በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል፣ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል እና የተሽከርካሪ አበል ክፍያ እንደሚያገኝ ያመለክታሉ፡፡ እነዚህን መብትና ጥቅሞች ለማግኘት ዳኛው ከሀላፊነት በሚነሳበት ወቅት የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ የነበረ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን አነስተኛ የአገልግሎት ዘመን ተብሎ በህጉ የተቀመጠው የአገልግሎት ጊዜ በፌደራል ፍርድ ቤት የተሰጠ የአገልግሎት ዘመን ብቻ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በግልጽ አያመለክቱም፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ በአዋጅ የተመለከቱትን መብት እና ጥቅሞች ለማግኘት ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት ከመምጣቱ በፊት በክልል ፍርድ ቤቶች የሰጠው የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ ይደረጋል ወይስ አይደረግም? ለሚለው አዋጁ በግልጽ ምላሽ አይሰጥም፡፡ አንድ ህግ ግልጽነት የሌለው ወይም አሻሚ ሲሆን ወይም ከሌላ ህግ ጋር ግጭት ሲኖረው ተቀባይነት ያገኙ የህግ አተረጓጎም መርሆዎችን በመከተል ህጉን ውጤታማ እና ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ የዳኝነት አካል ዋነኛ ተግባር መሆኑ እሙን ነው፡፡

በህግ አተረጓጎም ረገድ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የአተረጓጎም መርሆዎች ውስጥ አንዱ ወርቃማ የአተረጓጎም ዘዴ (Golden rule of interpretation) ሲሆን የዚህ አይነት አተረጓጎም መሰረተ ሀሳብ ህጉ በአጠቃላይ ወይም በህጉ በተወሰኑ ድንጋጌዎች ለማሳካት የታሰበውን አላማ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ትርጉም መስጠት ነው፡፡ ይህን የአተረጓጎም መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ህጉን ለማውጣት ያስፈለገበትን አጠቃላይ ምክንያት ከህጉ መግቢያ፣ ህግ አውጪው ህጉን ሲያወጣ የተወያየበትን ሰነድ (ሀተታ ዘምክንያት) እና መሰል ሰነዶችን እንዲሁም በህጉ በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከቱትን መሰረተ ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት አንዱን ከሌላው ጋር በማዛመድ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት አንደኛ ከአጠቃላይ የአዋጅ ቁጥር 653/2001 አላማና መንፈስ አንጻር ከፌደራል ፍርድ ቤቶች ውጪ በክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የዳኝነት የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ ሊደረግ ይገባል አይገባም የሚለውን መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በአዋጁ መግቢያ(preamble) ላይ አንዱ አዋጁን ማውጣት ያስፈለገበት አላማ ዳኞች እና ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች እንዲሁም የምክር ቤት አባላት ያካበቱትን እውቀት እና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ነው፡፡ የዳኝነት ሙያ በክልልም ሆነ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ለመሾም ዋነኛው መስፈርት የትምህርት ደረጃ እና የአገልግሎት ዘመን መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከትምህርት ደረጃ በተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን ለሹመት አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በሙያው የዳበረ ክህሎት እና ልምድ ሊገኝ የሚችለው ከህግ ትምህርት በተጨማሪ በሙያው ላይ ለረጅም አመት አገልግሎት በመስጠት መሆኑ ስለታመነበት ነው፡፡ በክልልም ሆነ በፌደራል ፍርድ ቤት በዳኝነት የተሰጠ አገልግሎት ዘመን በሹመት ወቅት ታሳቢ ተደርጎ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ግን በክልል በዳኝነት ሙያ የተሰጠበት የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ አይደረግም ማለት እርስ በርሱ የሚጋጭ ከመሆኑም በላይ በክልል የተሰጠ የዳኝነት የአገልግሎት ዘመን በአዋጁ መሰረት ተጠቃሚ ለመሆን ታሳቢ የማይደረግ ከሆነ በረጅም የአገልግሎት ዘመን የዳበረ የዳኝነት ሙያ ያላቸው ዳኞች ከክልል ወደ ፌደራል ፍርድ ቤት መጥተው በዳኝነት ሙያ ለማገልገል ፍቃደኛ እንዳይሆኑ በማድረግ የካበተ እውቀት እና ልምድ ለመጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር አዋጁ ታሳቢ ያደረገው አላማ እንዳይሳካ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ህጉን በዚህ አግባብ ተግባራዊ ማድረግ ህጉ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እንዳይሆን ስለሚያደርግ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛ የህጉን ይዘት ወይም አውድ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 53 የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርን በሚመለከት በንዑስ ቁጥር 3 ላይ የተደነገገውን ስንመለከት ከኃላፊነት የተነሳ ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል ከመሾሙ በፊት በክልል በድንጋጌው ላይ የተመለከቱት ኃላፊነቶች ላይ አገልግሎት ከሰጠ በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚያገኘው መብት እና ጥቅም በክልል ያገለገለበት ዘመን ታሳቢ እንደሚደረግለት ተደንግጓል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በክልል የተሰጠ አገልግሎትን ታሳቢ ማድረግ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት በአዋጁ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የአዋጁን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት ሲሆን ሌላው ከሃላፊነት የሚነሱ የክልል መንግስት መሪዎችን፣ ከፍተኛ

የመንግስት ሃላፊዎችን፣ የክልል ምክር ቤት አባላት የሚያገኟቸውን መብቶች እና ጥቅሞች እያንዳንዱ ክልል ባወጣው አዋጅ የተጠበቁ መብቶች ስለሆኑ እነዚህ ኃላፊዎች ወደ ፌደራል መንግስት ሲመጡም የፌደራል መንግስቱ ባወጣው አዋጅ የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ እንደዚሁም በህገ-መንግስቱ የተቀመጠውን የመንግስት አወቃቀር ተከትሎ የፌደራል መንግስት እና የክልል መንግስት በሚል የተዋቀረ ቢሆንም በክልል ይሁን በፌደራል መንግስት የተሰጠ አገልግሎት ለሀገር እና ለህዝቦቿ የተሰጠ አገልግሎት ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው፡፡

ነገር ግን የአዋጁ አንቀጽ 53/3 በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ስለተሰጠ የአገልግሎት ዘመን በፌደራል መንግስት ታሳቢ የሚደረግ ስለመሆን አለመሆኑ የሚለው ነገር የለም፡፡ ዳኝነትን በሚመለከት ድንጋጌው በክልል ስለተሰጠ የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ መደረግ አለመደረግ በዝምታ ማለፉ በዳኝነት ሙያ በክልል የተሰጠ አገልግሎት ዘመን በፌደራል ፍርድ ቤት እያገለገለ ቀይቶ ለተሰናበተ ዳኛ ታሳቢ እንዳይደረግ ለመከልከል ነው ሊባል አይችልም፡፡ ለዚህም አንደኛው ምክንያት በህግ አተረጓጎም መርህ በግልጽ ያልተከለከለ እንደተፈቀደ ስለሚቆጠር ነው፡፡ ይህም ማለት አዋጁ በክልል የተሰጠ የዳኝነት አገልግሎት ዘመን ታሳቢ እንዲደረግ የማይፈልግ ቢሆን ኖሮ በግልጽ ታሳቢ ሊደረግ እንደማይችል ያመለክት ነበር፡፡ በክልል ያገለገሉ ዳኞች የክልሉ መንግስት ባወጣው አዋጅ መብት እና ጥቅም እስከተጠበቀላቸው ድረስ ይሄው በክልል ያገኙት መብት በፌደራል አዋጁ ሊጠበቅላቸው ስለሚገባ አዋጁ በግልጽ በክልል የተሰጠ አገልግሎት ዘመን ታሳቢ እንዳይደረግ ለመከልከል በህግ አውጪው ታስቦ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የአዋጁ አንቀጽ 53/3 ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ ጋር በሚጣጣም መልኩ መተርጎም አለበት፡፡ የአዋጁ አንዱ አላማ የካበተ እውቀት እና ልምድ ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በመሆኑ በክልል መንግስት በዳኝነት ሙያ ላይ የተሰጠ አገልግሎትም አዋጁ ታሳቢ እንዲደረግ ያሰበ መሆኑን አመልካች ነው፡፡ ሶስተኛው ምክንያት እንደሚታወቀው የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 50/2 የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስት ሶስት አካላት እንደሚኖሩት እነርሱም ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈጻሚ እና ህግ ተርጓሚ ወይም የዳኝነት አካል መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 653/2001 መግቢያ የሚያሳየውም በአዋጁ የተጠቀሱ መብቶች እና ጥቅሞች የተጠበቁት በእነዚህ ሶስቱ የመንግስት አካላት ውስጥ ከፍተኛ መሪነት፣ ኃላፊነት፣ በምክር ቤት እና በዳኝነት ላገለገሉት ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 53/3 ድንጋጌ ከአገልግሎት አቆጣጠር አንጻር በክልል የተሰጠ አገልግሎት በፌደራል ደረጃ ለህግ አውጪው እና ለህግ አስፈጻሚው ታሳቢ እንደሚደረግ ለዳኝነት አካሉ ግን ታሳቢ እንደማይደረግ አድርጎ መተርጎም በሶስቱ የመንግስት አካላት መካከል አድሎአዊ አሰራርን የሚፈጥር ይሆናል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት የሚሾሙትን የሰው ኃይል የሚያገኙት በየደረጃዉ ካሉት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በህገ-መንግስቱ የተዘረጋውን በመተባበር ላይ የተመሰረተ የፌደራሊዝም ስርአት በመከተል ከክልል ፍርድ ቤቶች ጭምር በመሆኑ ይህንን ታሳቢ አለማድረግ የፌደራሊዝም መንግስት አወቃቀሩን እና የስልጣን ክፍፍል አላማ ያላገናዘበ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በነዚህ ከላይ በተጠቀሱ ሶስት ምክንያቶች የአዋጁ

አንቀጽ 53/3 በፌደራል መንግስት በዳኝነት አገልግሎ ለተሰናበተ ዳኛም በክልል በዳኝነት የሰጠው አገልግሎት ዘመን ሊታሰብለት እንደማይገባ ክልከላ የሚያደርግ ተደርጎ ሳይሆን በክልል የዳኝነት ሙያ የተሰጠበት የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ ማድረግን እንደማይከለክል ተደርጎ ሊተረጎም ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በደቡብ ክልል እና በከምባታ ጠንባሮ ዞን በፕሬዝዳንትነት እና በዳኝነት ሙያ ማገልገላቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት የተሾሙበት አንዱ መስፈርትም በክልሉ በዚህ መልኩ ያካበቱት እውቀት እና ልምድ ታሰቢ በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በክልል ፍርድ ቤቶች በዳኝነት እና በፕሬዝዳንትነት ማገልገላቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በክልል ያገለገሉበት ዘመን ከላይ በተገለጸው ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና በማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 1003/2009 ላይ የተመለከቱት በገንዘብ ተሰልተው የሚከፈሉ ክፍያዎችን ለማግኘት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያገለገሉበት ዘመን ሲቆጠር አመልካች በክልል በዳኝነት እና በፕሬዝዳንትነት የሰጡት አገልግሎት ታሳቢ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 653/2001 አንቀጽ 53/3 ድንጋጌን ከአዋጁ መሰረታዊ አላማ እና መንፈስ እንዲሁም ከኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ-መንግስት ጋር አገናዝቦ በማየት አመልካች በክልል በፕሬዝዳንትነት እና በዳኝነት አገልግሎት የሰጡበትን ጊዜ ታሳቢ አድርጎ መብትና ጥቅማቸውን አስልቶ ሊከፍል ሲገባ አመልካች በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያገለገሉበት ጊዜ የ3 ዓመት ከ11 ወር የስንብት ክፍያ ብቻ ነው የሚገባቸው ማለቱ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የተጠሪን ስህተት ማረም ሲገባው ማጽናቱ መሰረታዊ ህግ ስህተት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1ኛ. ተጠሪ ቁጥር ገ/ኢ/1/33/39 በቀን 15/03/2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 262417 በቀን 07/05/20113 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. ተጠሪ አመልካች በደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በከምባታ ጠምባሮ ዞን በፕሬዝዳንትነት እና በዳኝነት ያገለገሉበትን ጊዜ አጣርቶ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ካገለገሉበት ዘመን ጋር ታሳቢ በማድረግ መብትና ጥቅማቸውን ማለትም የመቋቋሚያ አበል፤ የመኖሪያ ቤት አበል እና የተሽከርካሪ አበል አስልቶ እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡፡ እንደዚሁም የስንብት ክፍያ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፈላቸው የወሰነው የ3ዓመት ከ11 ወር እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በክልል የሰጡትን የአገልግሎት ጊዜ ታሳቢ ሲያደርግ የሚቀረውን የስንብት ክፍያ አጣርቶ ለአመልካች እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡

3ኛ. አመልካች ስሌቱ መጨረሻ ላይ ሲያገኙ በነበረው ደመወዝ እንዲሰላ እንዲወሰንላቸው የጠየቁ ቢሆንም ተጠሪ የደመወዝ መጠን አሰላልን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ የሌለ በመሆኑ እና ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ከሚሰላው የደመወዝ መጠን ጋር በተያያዘ የሚነሳ ቅሬታ ካለ ተጠሪ ከሚሰጠው ውሳኔ በኋላ ሊታይ የሚገባ በመሆኑ ታልፏል፡፡

4ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/መ

የሰ/መ/ቁ. 180793

ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ያሬድ ተስፋይ /ያሬድ ተስፋይ ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንጂነሪንግ/

ተጠሪ፡- ዓዲግራት ዩንቨርስቲ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከመዝገብ ግልባጩ እንደተረዳነው ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ የታየ ሲሆን አመልካች በሥር የግልግል ጉባዔ ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም የማሕበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተከላ ለመፈጸም ውል አድርገናል፡፡ በውላቸው አለመግባባት ካለ ጉዳዩን ለመፍታት በግልግል ጉባዔ እንዲታይ ተስማምተዋል፡፡ በዚህ ሥምምነት መሠረት ግራ ቀኙ ተዋዋዮች የግልግል ዳኞችን መሰየም ባለመቻላቸው አመልካች የግልግል ዳኞች ይሾሙልኝ ጥያቄ ለትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በመዝገብ ቁጥር 22666 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ሦስት የግልግል ዳኞችን ፍርድ ቤቱ ሾሟል፡፡ አመልካች ለተሠየመው የግልግል ጉባዔ በውሉ መሠረት እንዲፈጸም እና ለደረሠባቸው ኪሣራ እንዲከፈላቸው ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የግልግል ዳኞች ምርጫና መቋቋም መብቴ ስላልተከበረልኝ የግልግል ጉባዔ ሊፈርስ ይገባል ሲል ተቃውሞ ያቀረበ ሲሆን ለክሱም ዝርዝር መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ የግልግል ጉባዔው ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ የግልግል ጉባዔው የተቋቋመው በፍርድ ቤት ውሳኔ ስለሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 እንደተመለከተው በይግባኝ እስካልተለወጠ ድረስ የጸና በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ በፍሬ

ጉዳዩም ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም በተደረገው ውል መሠረት ተጠሪ እንዲፈጽምና አመልካች ላይ የደረሠውን ኪሣራ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ያቀረበውን ይግባኝ መሠረት አድርጎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የማሕበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተቋም ተከላ ውል ለሕዝብ ጥቅም የተደረገና ለውሉ አፈጻጸም የተጠሪን የማያቋርጥ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.3132(ለ) መሠረት የአስተዳደር ውል ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(2) ላይ እንደተመለከተው የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎችን በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ ሕጉ በግልጽ ክልከላ አድርጓል፡፡ ፍርድ ቤት ሕግን በመጣስ ግልግል ጉባዔ ማቋቋም አይችልም፡፡ እንዲሁም የሥረ-ነገር ሥልጣን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9(2) እንደተደነገገው በማናቸውም ጊዜ የሚነሳ በመሆኑ ጉባዔውን ያቋቋመው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይሻር የጉባዔውን ሥልጣን መቃወም አይቻልም የሚለውን የአመልካችን ክርክርን አልተቀበልነውም በማለት የትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22666 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም እና የግልግል ጉባዔው ጥቅምት 03 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔን በመሻር ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የግልግል ጉባዔው በፍርድ ቤት ውሳኔ የተቋቋመ ነው፡፡ ውሳኔው እስካልተሻረ ድረስ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 እንደተደነገገው የጸና ነው፡፡ ውላችንም አለመግባባት በግልግል እንዲፈታ ይፈቅዳል፡፡ ሥለሆነም ጉባዔው በሕግ የተቋቋመና ሥልጣን ያለው ሆኖ እያለ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ውላቸው ጉዳዩን በግልግል ጉባዔ እንዲታይ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ እና የግልግል ዳኞች ሲመረጡ ተጠሪ ባልተቃወመበት ክርክሩ በግልግል ጉባዔ የሚታይ አይደለም መባሉ ሕጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የግልግል ዳኞች ምርጫ በፍርድ ቤት በተከናወነበት ወቅት ጊዜ እንዲሠጠን ጠይቀን እያለ ሳይቀበለን ቀርቷል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 3132 እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(2) መሠረት የአስተዳደር ውል በግልግል ጉባዔ የሚታይ አይደለም፡፡ ጉባዔው ሥልጣን እንደሌለው መቃወሚያ አቅርበናል፡፡ የሥልጣን ክርክርም በማናቸውም ጊዜ ሊነሳ የሚችል በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ የሚታይ አይደለም መባሉ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ እንደመረመርነው ሰዎች በመካከላቸዉ ከፈጠሩት ሕጋዊ ተግባራት በመነጨ ወይም ከዚህ ጋር በተያያዘ ለወደፊት በመካከላቸዉ የሚፈጠረዉን አለመግባባት ወይም ተፈጥሮ ያለዉን አለመግባባት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ዉጭ በግልግል ዳኝነት በኩል ለመፍታት የመዋዋል ነጻነታቸዉን

በመጠቀም መስማማት እንደሚችሉ የፍ/ሕ/ቁ. 3328 እና የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(1) ያስረዳሉ፡፡ የግልግል ዳኝነት ሥምምነት በጽሁፍ በተዋዋሉት በዋናዉ ዉላቸዉ በሚያደርጉት የግልግል ዳኝነት ስምምነት ቃል (Arbitration Clause) ወይም አስቀድሞ በመካከላቸዉ ተከስቶ ያለዉን አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ራሱን በቻለ የጽሁፍ የግልግል ዳኝነት ስምምነት (Arbitral Submission) ሊመለከት ይቻላል፡፡

አመልካች እና ተጠሪም ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ/ም ባደረጉት የማሕበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተከላ ውል አለመግባባት ቢከሰት በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የሚያዝ የሥምምነት ቃል (Arbitration Clause) ማድረጋቸውን ከክርክሩ ተረድተናል፡፡ በዚህ ሥምምነታቸው መሠረት አለመግባባት በመከሰቱ እና ተዋዋዮች የግልግል ዳኞችን መምረጥ ባለመቻላቸው አመልካች በፍርድ ቤት የግልግል ዳኞች እንዲመረጡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 316 መሠረት አቤቱታ አቅርበው የትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22666 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ሦስት የግልግል ዳኞችን ሾሟል፡፡ የግልግል ጉባዔው ከተቋቋመ በኋላ ግራ ቀኙን አከራክሮ በፍሬ ጉዳዩ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አለመግባባት ቢከሰት በግልግል ዳኝነት እንዲታይ የሚያዝ የሥምምነት ቃል (Arbitration Clause) መደረጉና የግልግል ጉባዔው አከራክሮ መወሰኑ ጉዳዩ የአስተዳደር ውል በመሆኑ እና የአስተዳደር ውል ጋር የተያያዘ አለመግባባት በግልግል ዳኝነት እንዳይታይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(2) መሠረት የተከለከለ በመሆኑ ጉባዔው ሥልጣን የለውም የሚለው ግልጽ ክርክር የቀረበው ጉዳዩ በይግባኝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረጃ በሚታይበት ጊዜ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱም አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የማሕበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተቋም ተከላ ውል ለሕዝብ ጥቅም የተደረገና ለውሉ አፈጻጸም የተጠሪን የማያቋርጥ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 3132(ለ) መሠረት የአስተዳደር ውል ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(2) ላይ እንደተመለከተው የአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎችን በግልግል ዳኝነት እንዲታዩ ሕጉ በግልጽ ክልከላ የተደረገበት በመሆኑ የግልግል ጉባዔውን ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ውል ሊመሠረት የሚገባው ችሎታ ባላቸው፣ በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ፣ የሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ በሕግ የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም ተከትሎ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ቁ. 1678 ላይ ተመልክቷል፡፡ የግልግል ስምምነት እንደማንኛዉም የዉል ስምምነት ልዩ ባህሪዉን ባገናዘበ ሁኔታ የተዋዋዮች የመዋዋል ችሎታ ማጣት፣ የፈቃድ ጉድለት፣ ዓላማዉ የግብረ ገብነት ጉድለት ያለበት መሆን፣ ዓላማዉ ከሕግ ዉጭ ወይም ሕገ-ወጥ መሆንን (immoral, illegal and unlawful object) ፣ በህግ የተቀመጠለትን የአጻጻፍ ስርዓት ያልተከተለ ከመሆን ጋር በሚያያዙ ምክንያቶች ፈራሽ ሊሆን ይችላል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330(1)(2) ስር ከግልግል ዳኝነት ስምምነት አተረጓጎም ጋር የተያያዘ ክርክር ቢነሳ አከራካሪዉ ነጥብ ላይ ዉሳኔ መስጠት እንዲችል በግልግል ስምምነቱ ላይ ለግልግል ዳኛዉ ስልጣን ሊሰጠዉ እንደሚችል እና በተለይ የራሱን ሥልጣን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች በራሱ እንዲወስን በግልግል ስምምነቱ ላይ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይህም በተምሳሌታዊ ሕግ (UNCITRAL Model Law እ.ኤ.አ በ1985 ወጥቶ በ2006 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 16 ስር ከተደነገገዉና በዘመናዊዉ የግልግል ዳኝነት የህግ ዘርፍ The Rule of Competence-Competence ተብሎ ከሚታወቀዉ መርህ ጋር ከሞላ ጎደል የሚመሳሰል ነዉ፡፡ ይህ መርህ የግልግል ዳኛዉ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ ያለዉ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የሚነሳ ክርክር ጭምር ሰምቶ መወሰን እንዲችል ስልጣን የሚሰጠዉ ቢሆንም ይህ መርህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 3330(3) ስር እንደተመለከተዉ በአገራችን በከፊል ተቀባይነት ባለማግኘቱ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአገራችን የግልግል ዳኛ የግልግል ዳኝነት ስምምነቱ ዋጋ የለዉም በሚል የሚነሳ ክርክር ሰምቶ በራሱ መወሰን እንዲችል ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡ ስለሆነም በአገራችን የግልግል ዳኝነት ስምምነት ዋጋ የለዉም በሚል የሚቀርብ ክርክር ሰምቶ የመወሰን ስልጣን ያለዉ ገላጋይ ዳኛዉ ወይም የግልግል ዳኝነት አካሉ ሳይሆን መደበኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡

የግልግል ስምምነቱ ፈራሽ ሊሆን ይገባል የሚሉት የተዋዋዮች የመዋዋል ችሎታ ማጣት ወይም የፈቃድ ጉድለት መሠረት በማድረግ ከሆነ የግልግል ጉባዔው ክርክሩን በማቆም ተዋዋዮች መብታቸውን በመደበኛ ፍርድ ቤት አስከብረው እንዲቀርቡ ማድረግ ይገባዋል፡፡ በሌላ በኩል የግልግል ስምምነቱ ተቀባይነት የለውም የሚሉት በሕጋዊነት ጉድለት ከሆነ እና ተጠሪ እንደሚከራከረው የግልግል ጉባዔውም ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የለውም የሚል ከሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 1809 እንደተመለከተው ውሉ ባይፈርስም ሕገ-ወጥ የሆነን ውል የመፈጸም ግዴታ ተዋዋዮች የሌለባቸው ስለመሆኑና ውሉ የማይረጋበትን ምክንያት በማንሳት ውሉ ከመፈጸም እንዲቆም መከራከርን ሕጉ የሚፈቅድ ስለሆነ እንዲሁም ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ እንዳይታይ ሕግ ክልከላ ያደረገበት ነው የሚለው የሥረ-ነገር ሥልጣን ክርክርንም የያዘ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9(2) እንደተመለከተው በማናቸውም ጊዜ ሊታይ የሚችል ጉዳይ በመሆኑ የግልግል ጉባዔው የግልግል ሥምምነቱ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት እንዲፈርስ መወሰኑን ሳይጠብቅ ጉዳዩን ተመልክቶ ሊወስነው የሚገባው ነው፡፡ የውሳኔው ውጤትም የግልግል ሥምምነቱን ፈራሽ የሚያደርግ ሳይሆን ሕገ-ወጥ ውልን መሠረት በማድረግ ለመፈጸም እምቢተኛ መሆንን የሚመለከት ነው፡፡

በግልግል ዳኝነት ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን (Arbitrability) በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 315(2) ስር እንደተደነገገዉ በግልግል ዳኝነት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸዉ ተብሎ በሕግ በግልጽ ከተደነገገዉ እና ከአስተዳደር ዉሎች ጋር ከተያያዘዉ ዉጭ የሆኑ ሕጋዊ ተግባራትን መነሻ ያደረጉ አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት ታይተዉ እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ ማናቸዉም ችሎታ ያላቸዉ ተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ነጻነታቸዉን በመጠቀም የግልግል ዳኝነት ስምምነት መዋዋል እንደሚችሉ በግልጽ

ተደንግጓል፡፡ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የማሕበረሰብ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ተቋም ተከላ ውል ለሕዝብ ጥቅም የተደረገና ለውሉ አፈጻጸም የተጠሪን የማያቋርጥ ተካፋይነት የሚጠይቅ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 3132(ለ) መሠረት የአስተዳደር ውል ነው፡፡ የአስተዳደር ውል ጋር የተያያዘ አለመግባባትን ለመዳኘት የግልግል ጉባዔ የማይችል ስለመሆኑ በሕግ ክልከላ የተደረገበት በመሆኑ ግራ ቀኙ ያደረጉት የግልግል ሥምምነት ቃል ሕጋዊ አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአስተዳደር ውልን መሠረት ያደረገ አለመግባባት በግልግል ዳኝነት ለመፍታት ያደረጉት የግልግል ሥምምነት ቃሉ ሕጋዊ ካልሆነ የግልግል ጉባዔው ጉዳዩን ለመዳኘት እንዳይችል ያደርገዋል፡፡ የሥር ግልግል ጉባዔ በሕግ እንዲመለከት ያልተፈቀደለትን ጉዳይ አከራክሮ በፍሬ ጉዳዩ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ይህን በማረም ከአስተዳደር ውል ጋር የተያያዘ አለመግባባት በግልግል ዳኝነት የሚታይ ባለመሆኑ ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን ያለው መደበኛ ፍርድ ቤት ነው ማለቱ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

አመልካች የግልግል ጉባዔው የተቋቋመው በትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ስለሆነ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በይግባኝ ሳይለወጥ ጉባዔው ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም ሊባል አይገባም በማለት ያቀረቡትን ክርክር እንደተመለከትነው የግልግል ዳኞች በተዋዋዮች ወይም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 316 መሠረት በፍርድ ቤት ሊሾሙ ይችላል፡፡ የግልግል ዳኞቹ በተዋዋዮች ሆነ በፍርድ ቤት መመረጣቸው ልዩነት ያለው ሂደት አይደለም፡፡ የግልግል ዳኞች መምረጥ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ጉባዔ እንዲታይ የማመቻቸት ሂደት አካል እንጂ በራሱ የመጨረሻ ውሳኔ አይደለም፡፡ የግልግል ዳኞች አመራረጥ ጉዳዩን የግልግል ጉባዔው ለመመልከት የሚችል መሆን አለመሆኑ ላይ ውጤት የለውም፡፡ የግልግል ዳኞቹ ከሁለቱ ሂደት በአንዱ ከተመረጡ በኋላ የግልግል ጉባዔው ሲሰየም ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ በሕግ የተፈቀደ መሆን አለመሆኑን የግልግል ጉባዔው ሆነ ፍርድ ቤቱ እንዳይመለከት የሚከለክል ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል የትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22666 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጠው የግልግል ዳኞችን የመምረጥ ትዕዛዝ፤ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መሻሩ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ግድፈት ያለበት ነው፡፡ ለይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በዳኞች አመራረጥ ላይ በተሠጠው ውሳኔ ላይ ሥርዓቱን የጠበቀ ይግባኝ ሳይቀርብለት እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 እንደተመለከተው ሥርዓቱን ጠብቆ በይግባኝ ያልተለወጠ ውሳኔ እንደጸና የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ የዳኞች አመራረጥ ጉዳዩ በግልግል ጉባዔ የሚታይ መሆን አለመሆኑ ላይ ውጤት የሌለው ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ዳኞችን ለመምረጥ የሠጠውን ትዕዛዝን መሻሩ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 166548 ሚያዚያ 21 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤት ነው ተብሎ የተሠጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

3. የትግራይ ክልል ምሥራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 22666 ጥቅምት 22 ቀን 2010 ዓ/ም የሠጠውን ትዕዛዝ በመሻር የሠጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

የሠ/መ/ቁጥር 188853

መጋቢት 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ሻረው ወርቅዬ

ተጠሪ፡- 1. ልክዬ ወርቅዬ

2. ወ/ሮ ጀምበሬ ወርቅዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ በስጦታ የሚተላለፍበት የሕግ አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ክልል መሀል ሳይንት ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በሞግዚታቸዉ አማካኝነት በመሰረቱት ክስ በዚሁ ወረዳ 041 ቀበሌ ጠጅ ዉሃ እየተባለ በሚጠራበት ቦታ አዋሳኞቹ በክሱ የተጠቀሰዉን የመሬት ይዞታ ከሟች አባታቸዉ ወርቅዬ መለስ ላይ ወርሰዉ በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አስመዝግበዉ የሚጠቀሙበትን መሬት አመልካች እንደያዘባቸዉ በመግለጽ እንዲለቁላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የያዝኩት ሟች አባቴ ወርቅዬ መለስ በ1991 ዓ/ም በህይወት እያለ በስጦታ አስተላልፎልኛል፡፡ አባቴ በ1995 ዓ/ም በሞት በመለየቱ ማንም ሰዉ ሰጥቶ የሞተዉን ሌላ ሰዉ ማፍረስ አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር እና ምስክሮች በመስማትና በመመዘን የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14467 ላይ በቀን 29/10/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክስ የተነሳበት መሬት የአሁን አመልካች በስጦታ ያገኙት ስለሆነ ለተጠሪዎች ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካቾች ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር ክስ የተነሳበት መሬት ለአመልካች በስጦታ ተላልፎ አድሯል ወይ?ደብተር ለተጠሪዎች ተሰርቶ

ለአመልካች ለምን አልተሰራም የሚሉትን ከወረዳዉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ማስረጃ በማስቀረብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ተጨማሪ ምስክሮችን በመስማት ካጣራ በኋላ መሬቱ ለማን ይገባል የሚለዉን የመሰለዉን እንዲወስን በማለት መልሶለታል፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከወረዳዉ ገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ማስረጃ በማስቀረብ፣አስቀድሞ የሰማቸዉ የግራ ቀኝ ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርመር በቀን 04/03/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ለአሁን አመልካች በስጦታ የተላለፈ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ስለሌለ ለአመልካች መሬቱ በስጦታ አለመተላለፉ ተረጋግጧል፡፡ምንም እንኳን የግራ ቀኙ ምስክሮች መሬቱ በአመልካች ስለማደሩ የመሰከሩ ቢሆንም በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት የመሬት ይዞታ በስጦታ ተላልፏል የሚለዉን የማያሚላ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሆኑ አንጻር ሊረጋገጥ የሚችለዉ በሰነድ ማስረጃ በመሆኑ በተሻለ ሁኔታ ግልጽ ማስረጃ በማቅረብ ተጠሪዎች መሬቱን በዉርስ እንዳገኙ ስላስረዱ አመልካች መሬቱን በስጦታ አላገኙም ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 38982 ላይ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን በቀን 11/04/2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን መሬት አመልካች ከ1991 ዓ/ም ጀምሮ ይዘዉ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡የአሁን ተጠሪዎች አከራካሪዉን መሬት ለ10 ሆነዉ በዉርስ መሬትነት በወረዳዉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በ2008ዓ/ም ያስመዘገቡ ቢሆንም አመልካች ደግሞ በለጠ ወርቅዬ ከተባለዉ ጋር በመሆን መሬቱን ከ1991 ዓ/ም ጀምሮ በመያዝ ይጠቀሙ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በ1991 ዓ/ም ላይ ደግሞ የመሬት ስጦታ ምዝገባ ያልነበረ እና በወቅቱ የነበረዉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 89/1989 ስለመሬት ስጦታ ምዝገባ ስለማይደነግግ የምዝገባ ስርዓት ባልነበረበት ወቅት የተቋቋመ መብት(የስጦታ ዉል) አልተመዘገበም በሚል በወረዳ ፍርድ ቤት ዉድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የተመዘገበ ስጦታ የለም አለ እንጂ ከጅምሩም ስጦታ የለም አላለም፡፡ በመሆኑም አመልካች የስጦታ ዉል ምዝገባ ባልነበረበት ወቅት በሰጦታ የያዙትን ይዞታ ወደ ዉርስ ይዞታ በመቀላቀል የሚያስረክቡበት ምክንያት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 0107704 ላይ አከራክሮ በቀን 03/02/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች የስጦታ ውል ከሟች የተደረገላቸዉ ለመሆኑ አላስረዱም፡፡ የስጦታ ውሉ አለመመዝገቡ ብቻ ሳይሆን በእርግጥ ሟች በስጦታ ስለማስተላለፋቸው አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች መሬቱን ከ1991 ዓ/ም

ጀምሮ ይጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ብቻውን በስጦታ አግኝተዉታል የሚያስብል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡እንዲሁም ተጠሪዎች በሞግዚት የሚተዳደሩና በጊዜዉ መብታቸዉን ሊጠይቁ የሚችሉ አለመሆናቸዉና ሥልጣን ያለዉ አካል መሬቱን ለአመልካች አለማጥናቱና ስለስጦታዉ የሚያዉቀዉ ነገር አለመኖሩ ተደምሮ ሲታይ አመልካች መሬቱን በስጦታ አግኝተዋል የሚያስብል ሆኖ አልተገኘም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር የመሀል ሳይንት ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎቱ በመ/ቁጥር 0327672 ላይ በቀን 04/05/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ሰርዞባቸዋል፡፡ አመልካች በቀን 07/05/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መልኩ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት አባቴ በ1991 ዓ/ም ላይ በስጦታ ሰጥቶኝ እስካሁን ድረስ ይዤ እየተጠቀምኩ የምገኝ ነዉ፡፡ ስጦታውም በጊዜው ስጦታ መዝጋቢ መስሪያ ቤት ባለመቋቋሙ የተነሳ በመስሪያ ቤት ያልተመዘገበ እና ስጦታው በቃል የተደረገ ስለመሆኑ በግራ ቀኝ ምስክሮች በስር ፍርድ ቤት ባስረዳም የሰነድ ማስረጃ አልቀረበም ሲል የወረዳዉ ፍርድ ቤት የሠጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፡፡በአንጻሩ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ስጦታውን በሰው ማስረጃ በአጥጋቢ ሁኔታ ማስረዳቴን አረጋግጦ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 122740 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡አከራካሪውን መሬት ወላጅ አባቴ በቃል በስጦታ ተሰጥቶኝ ከ1991 ዓ/ም አንስቶ መያዜ እስከተረጋገጠ ድረስ የፅሁፍ ውል አላቀረብክም በሚል ተጠሪዎች የሟች አባቴን ክስ ከቀረበበት መሬት ውጪ ያሉ አራት መሬቶችን ወርሰው ይዘዉ እያለ አመልካች ደግሞ ሟች አባቴ በህይወት እያለ የሰጠኝን ይህንን ክርክር የተነሳበትን መሬት ብቻ እንደያዝኩ እየታወቀ ፍትህንና ርትእን በሚቃረን መልኩ መሬቱን እንዲለቅ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መወሰኑ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናልኝ በማለት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ለአመልካች ከአባታቸዉ በ1991 ዓ/ም በስጦታ ተላልፎላቸዉ አባታቸው በ1995 ዓ/ም መሞታቸው ተረጋግጦ እያለ የስጦታ ዉሉ አልተመዘገበም በሚል የአመልካች ክርክር ውድቅ የተደረገበትን አግባብ የስጦታ ውሉ መመዝገብ አለበት የሚለዉ የክልሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 133 የወጣው 1998 ከመሆኑ አንጻር የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት እንዲመረመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 24/06/2012 ዓ/ም የተፃፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

አንድ የስጦታ ውል ሊደረግ የሚችለው በሕጉ አግባብ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2171 መሰረት መሆን ሲገባዉ አመልካች ምንም አይነት የስጦታ ውል አላቀረቡም፡፡ የስጦታ ውሉም በሕግ ፊት አልጸደቀም፡፡ የሟችን ንብረት በውርስ ያገኘነው ልጆች እያለን አመልካችም እንደ ልጅ ተቆጥረዉ ድርሻ መሬት ካገኙ በኋላ

የእኛን ድርሻ ለመካፈል የስጦታ ውል አለኝ አሉ እንጂ የሟች አባታችንን በውርስ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በ2008 ዓ/ም ወስደን ክፍፍል ስለተፈጸመ ድርሻችንን ሊወስዱ ስለማይችሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በቀን 07/07/2012 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደተመረመረውም ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የመሬት ይዞታ ከአባታቸዉ በዉርስ ተላልፎላቸዉ ከ2008ዓ/ም ጀምሮ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቷቸዉ በስማቸዉ የተመዘገበዉን አመልካች እንደያዙባቸዉ በመግለጽ አመልካች በፍርድ ኃይል ተገደዉ እንዲለቁ እንዲወሰንላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ደግሞ መሬቱን አባቴ በ1991 ዓ/ም በስጦታ ሰጥቶኝ እስካሁን ይገኙ እየተጠቀምኩ ስለምገኝ ልለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር የወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት አከራካሪዉ የመሬት ይዞታ በስጦታ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ የሚያሳይ በመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ጽ/ቤት የተመዘገበ ሰነድ በማስረጃነት ስላላቀረቡ መሬቱ በስጦታ የተላለፈላቸዉ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ለአመልካች አከራካሪዉ ይዞታ በ1991 ዓ/ም በስጦታ እንደተሰጣቸዉ ምስክሮች ስላስረዱ በወቅቱ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 89/1889 መሬት በስጦታ ሲተላለፍ የስጦታ ዉሉ መመዝገብ አለበት ብሎ ስለማይደነግግ የስር ፍርድ ቤት በወቅቱ ስራ ላይ ያልነበረዉን ሕግ መሰረት በማድረግ መሬቱ በስጦታ ስለመተላለፉ አመልካች የተመዘገበ ዉል በማስረጃነት አላቀረቡም ማለቱ ስህተት ስለሆነ አመልካች በስጦታ ተላልፎላቸዉ ይዘዉ ሲጠቀሙ የነበረዉ መሬት መሆኑን አስረድተዋል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡ በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች መሬቱን በስጦታ አግኝቻለሁ ይበሉ እንጂ የስጦታ ዉሉ አለመመዝገቡ ብቻ ሳይሆን በሟች አባታቸዉ ስጦታ የተደረገላቸዉ ስለመሆኑም ባለማስረዳታቸዉ አመልካች መሬቱን ከ1991 ዓ/ም ጀምሮ ይጠቀሙበት የነበረ መሆኑ ብቻውን በስጦታ አግኝተዉታል የሚያስብል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሽሯል፡፡

ለአመልካች አከራካሪዉ የመሬት ይዞታ በሕግ አግባብ በተደረገ የስጦታ ዉል ተላልፏል ወይስ አልተላለፈም የሚለዉ መመርመር ያለበት አመልካች መሬቱ በስጦታ ተላልፎልኛል ባሉበት በ1991ዓ/ም ተፈጻሚ ሲሆን በነበረው ሕግ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም ከሚለዉ አጠቃላይ መርህ (the principle of non-retroactivity of laws) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሕግ በዜጎች መካከል ያለዉን ግንኙነት ለመቆጣጠር ሲባል በሕግ አዉጪዉ አካል የሚወጣ ነዉ፡፡ ሕግ የሚወጣዉም ሕጉ በስራ ላይ ባለበት ወቅት በዜጎች መካከል ያለዉን ወይም ወደ ፊት የሚፈጠረዉን

ግንኙነት ለመቆጣጠር ወይም ለመዳኘት በመሆኑ ሕጉ ከመዉጣቱ በፊት ወይም ከተሻረ በኋላ በተፈጠረ/በሚፈጠር ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ ማድረግ አይቻልም፡፡ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉም መርህ ከዚሁ የመነጨ ሲሆን፣ መሠረተ ሃሳቡም ዜጎች በሚያዉቁት ሕግ መተዳደር አለባቸዉ የሚለዉን ታሳቢ ያደረገና ሕጉ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለተፈጠረ መብትና ግዴታ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ተፈጻሚ መሆን ስላለበት ነዉ፡፡ በሌላ አገላለጽ አንድ ሕግ ተፈፃሚ መሆን የሚጀምርበትን ጊዜ አስመልክቶ በሕግ አዉጪዉ ከተደነገገዉ ቀን በፊት ለተፈጠሩት ክስተቶች ወይም መብትና ግዴታዎች ተፈፃሚነት አይኖረዉም የሚል ሃሳብ ያለዉ ነዉ፡፡ ይህ መርህ ከሕግ የበላይነት መገለጫዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ ስለሆነም፣ አንድ መሠረታዊ ሕግ (substantive law) ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ሕግ አዉጪዉ እራሱ በልዩ ሁኔታ ካላመላከተ በስተቀር፣ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ለያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን መሠረታዊ ህግ ሲወስን መሠረት ሊያደርግ የሚገባዉ ወይም መሠረት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በተፈጠረበት ጊዜ በስራ ላይ የነበረዉን ሕግ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም ሕጋዊ ተግባሩ(Juridical act) ወይም መብትና ግዴታ በተፈጠረበት ጊዜ የነበረዉ ሕግ በሌላ ሕግ የተተካ ሆኖ ሲገኝ እና ክርክሩ ለፍርድ ቤት ወይም ለዳኝነት ሰጪ አካል የቀረበዉ አዲሱ ሕግ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት ያለበት በመብትና ግዴታው በተፈጠረበት ጊዜ ተፈጻሚ በነበረው ሕግ መሠረት ይሆናል፤ ክርክሩ አዲሱ ሕግ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ጉዳዩ በአዲሱ ሕግ መሠረት እንዲመራ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን ማድረግ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉን የሕግ መርህ የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የሕግ የበላይነት እንዳይረጋገጥ ወይም እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናል፡፡

ለያዝነዉ ጉዳይ ተገቢዉን እልባት መስጠት ይቻል ዘንድ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉን ሕግና የሕጉን ድንጋጌ በጥንቃቄ መለየት ያስፈልጋል፡፡ አመልካች አከራካሪዉ መሬት በስጦታ ተላልፎልኛል በሚል ይዘዉ መጠቀም የጀመሩት ከ1991 ዓ/ም ጀምሮ እንደሆነ በበታችኞቹ ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ በ1991 ዓ/ም በአማራ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት በስጦታ ሲተላለፍ በምን አግባብ መተላለፍ እንዳለበትና ስለዉሉ ፎርማሊቲ የሚደነግግ ሕግ እንዳልነበረ ተገንዝበናል፡፡ የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 89/1989 ከሰኔ 30 ቀን 1989 ዓ/ም ጀምሮ ከመጽናቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረዉ የገጠር መሬትን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 31/1967 ነዉ፡፡ ይህ አዋጅ ቁጥር 31/1967 የገጠር መሬት በስጦታ ስለሚተላለፍበት ሁኔታና ሲተላለፍም በምን የዉል ፎርማሊቲ መተላለፍ እንዳለበት የሚደነግግ አይደለም፡፡ይልቁንም ከዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 የምንገነዘበዉ የገጠር መሬት በስጦታ ጭምር እንዳይተላለፍ መደንገጉን ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ አዋጅ በ1989 በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 89/1989 ከመተካቱ በፊት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ/ም ጀምሮ ወጥቶ ሥራ ላይ በመዋሉ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3 ላይ መሬት የማይሸጥ

የማይለወጥ በኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ ባለቤትነት የሚታወቅ ንብረት እንደሆነ ቢደነግግም መሬት በሕግ በሚደነገገዉ ስርዓት መሰረት በዉርስ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ አይቻልም ሲል ሕገ መንግስቱ ያስቀመጠዉ ክልከላ የለም፡፡ሕገ መንግስቱን ተከትሎ በወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 89/1989 አንቀጽ 2/3 ላይ የይዞታ መብት ለቤተሰብ አባል በዉርስ ማስተላለፍን ጭምር የሚያካትት እንደሆነ መደንገጉ ሲታይ ከአዋጅ ቁጥር 31/1967 በኋላ የወጡ ሕጎች የገጠር መሬት በዉርስና በስጦታ እንዳይተላለፍ የሚያግዱ አይደሉም፡፡

ሆኖም ሕገ መንግስቱን ተከትሎ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 89/1989 የገጠር መሬት በስጦታ ሊተላለፍ አይችልም በሚል ያስቀመጠዉ ክልከላ ባይኖርም ይህ አዋጅ የገጠር መሬት አስተዳደርን በተመለከተ የክልል መንግስታት ሕግ ሲያወጡ መሰረት ሊያደርጉ የሚገባቸዉን ሁኔታዎች በመደንገግ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ የገጠር መሬት በስጦታ ሲተላለፍ የስጦታ ዉሉን ፎርማሊቲና ዉሉ ስለሚመዘገብበት አግባብ አልደነገገም፡፡ በዚህ ሕግ መነሻ በ1991 ዓ/ም ሆነ ከዚያ በፊት በተለይም የገጠር መሬት በስጦታ የሚተላለፍበትን አግባብ የሚደነግግ ሕግ በአማራ ክልል ወጥቶ ስራ ላይ አልዋለም፡፡ ምንም እንኳን የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተላለፍ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ልዩ ሕግ ሆነዉ ተፈጻሚ መሆን ያለባቸዉ ስለገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር የወጡ ሕጎች ቢሆኑም በእነዚህ ሕጎች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ እና እነዚህ ሕጎች ወጥተዉ ስራ ላይ ባልዋሉበት ጊዜ የተፈጸሙ ሕጋዊያን ተግባራት ላይ እንደነገሩ ሁኔታ በፍትሐ ብሔር ሕግ የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ስለሚተላለፍበት የተደነገገዉ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2443 ስር እንደተደነገገዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ ወይም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ መብት የሚሰጥ ስጦታ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አሰራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ አሰራር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ለግልጽ ኑዛዜ በተደነገገዉ ፎርማሊቲ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት በስጦታ ለመስጠት የሚደረገ ዉል በጽሁፍ ተደርጎ በአራት ምስክሮችና በስጦታ ሰጪዉ መፈረም አለበት፡፡የምስክሮቹ ቁጥር ሁለት ሊሆን የሚችለዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 882 ስር እንደተደነገገዉ የስጦታ ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበ ሲሆን ነዉ፡፡የስጦታ ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበ ከሆነ አዋዋዩ ኦፊሰር ምስክር እንደሆነ ተገልጾ በስጦታ ዉሉ ላይ ባይጻፍም የስጦታ ዉሉ ያለምንም ተጽእኖ በነጻነት እንዲደረግ ሂደቱን የመራ ሰዉ በመሆኑ እንደምስክር ሊቆጠር እንደሚገባ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37562 (ቅጽ 8 ላይ እንደታተመዉ)ትርጉም ሰጥቷል፡፡በዚሁ ሕግ ቁጥር 2447/1 ስር ስጦታ አለ የሚለዉ ሰዉ ስጦታ መኖሩን ማስረዳት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች አከራካሪዉ መሬት በሕጉ አግባብ በስጦታ ዉል የተላለፈላቸዉ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም አመልካች መሬቱን የያዝኩት በቃል በተደረገ የስጦታ ዉል ተላልፎልኝ ነዉ በሚል የተከራከሩ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 881 ወይም 882 አግባብ በጽሁፍ ተደርጎ በስጦታ ሰጪዉና በምስክሮች የተፈረመ የስጦታ ዉል በማስረጃነት በማቅረብ አላስረዱም፡፡ አመልካች በሕጉ ተቀባይነት ያለዉን ማስረጃ አቅርበዉ ካላረጋገጡ አከራካሪዉ መሬት ለአመልካች በስጦታ ተላልፎላቸዋል ብሎ መወሰን አይቻልም፡፡ እንዲሁም አመልካች በሕጉ አግባብ በተቋቋመ የስጦታ ዉል መሬቱን ከአባታቸዉ በስጦታ ስለማግኘታቸዉ ካላስረዱ መሬቱን ይዘዉ በመጠቀማቸዉ ብቻ መሬቱ በስጦታ ተላልፎላቸዋል ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ በሰ/መ/ቁጥር 122740 ላይ በቀን 30/08/2009ዓ/ም የተሰጠዉ ትርጉም ላይ የሥጦታ ዉሉ በጽሁፍ እንደተደረገ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሰረት ተደርጎ የተሰጠ የሕግ ትርጉም በመሆኑ በተያዘዉ ጉዳይ ላይ በጽሁፍ የተደረገ የስጦታ ዉል በማስረጃነት ስላልቀረበ በተጠቃሹ መዝገብ ላይ የተሰጠ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የመህል ሳይንት ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪዉን የገጠር መሬት በስጦታ ዉል ያገኙ ስለመሆኑ አላስረዱም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ባይሆንም የስጦታ ዉሉ ተደረገ በተባለበት በ1991ዓ/ም ተፈጻሚነት የሌለዉን በአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት የወጣዉን የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ወደኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ እንዲሆን በማድረግ የስጦታ ዉል የለም በማለት መወሰኑ ሕግ ወደኋላ ተመልሶ እንዳይፈጸም የሚከለክለዉን መርህ የሚጥስ በመሆኑ ከዚህ አኳያ የተፈጸመዉ ስህተት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታረሙ ተገቢ ነዉ ብለናል፡፡ ሆኖም የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሕግ አግባብ የተደረገ የስጦታ ዉል መኖር አለመኖሩን መርምሮ መወሰን ሲገባዉ ጉዳዩን የስጦታ ዉል ከማስመዝገብ አንጻር ብቻ በማየት የስጦታ ዉል እንዲመዘገብ የሚያስገድድ ሕግ ስለሌለ አከራካሪዉ መሬት ለአመልካች በስጦታ የተላለፈ ነዉ ወደሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለበት ስለሆነ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ ተገቢ ነዉ፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም እንኳን ከዚህ በላይ በተመለከተዉ አግባብ ተፈጻሚነት ያለዉን ሕግ በመለየትና ለአከራካሪዉ ፍሬ ነገር ተፈጻሚ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ አለመሆኑ ስህተት ቢሆንም ከዉጤት አንጻር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የገጠር መሬት አመልካች በስጦታ ተላልፎላቸዉ የያዙ ስለመሆኑ አላስረዱም በማለት የወረዳዉን ፍርድ ቤት በማጽናት በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በመሀል ሳይንት ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14467 ላይ በቀን 04/03/2012ዓ/ም ተወሰኖ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0107704 ላይ በቀን 13/02/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ እና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 0327672 ላይ በቀን 04/05/2012 ዓ/ም በተሰጠ ትእዛዝ መጽናቱ ተገቢ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ 160792

መጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ/ም

ዳኞች- መዓዛ አሸናፊ

ሰለሞን አረዳ

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጻውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ፈርተውኃል ኃ/ጊዮርጊስ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- ተስፋዬ መብራቴ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በመንግስት ሰራተኞች የጡረታ መብት አከባበር ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ለማህበራዊ ዋስትና ኤጄንሲ የዘላቂ ጡረታ መብት ይከበርልኝ ጥያቄ በማቅረባቸው ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ኤጄንሲውም የተጠሪ አገልግሎት ከሃያ አመት በታች ነው፣ የተሰናበትከውም በጡረታ ሳይሆን በሌላ ምክንያት ነው፣ በመሆኑም የሚወሰንልህ የዘለቄታ የጡረታ አበል የለም፣ ሊወሰንልህ የሚገባው ከጡረታ መዋጮ ተመላሽ ብቻ ነው በሚል ለተጠሪ በ26/07/2008 ዓ/ም ውሳኔውን ያሳወቃቸው ሲሆን ይህንኑ የኤጄንሲውን ውሳኔ ተከትሎ የአሁኑ ተጠሪ ይግባኛቸውን ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ባቀረቡት ይግባኝም የዘለቄታ ጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው አሰሪ መስሪያ ቤቱ ቢጠይቅላቸውም አገልግሎትህ ከሃያ ዓመት በታች፣ ከስራ የተሰናበቱትም በሌላ ምክንያት ስለሆነ የሚወሰን የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ተብሎ መወሰኑ በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ለ17 አመታት ከ11 ወራት አገልግለው በመስሪያ ቤቱ አደረጃጀት ለውጥ ምክንያት

በእጩነት በእውነት ከቀረቡት ውስጥ ሳይታቀፉ በመቅረታቸው የተሰናበቱ ከመሆኑም በላይ ስራውን በለቀቁበት ጊዜ ስራ ላይ በነበረው የአዋጅ ቁጥር 22/23 1955 መሰረት የጡረታ መብታቸው ሊከበርላቸው የሚገባ መሆኑንና ከዚህ በኋላ በወጣው ህግ ደግሞ ጉዳዩ ሊገዛ የማይችል መሆኑን ዘርዝረው የኤጀንሲው ውሳኔ ተሽሮ የዘለቄታ ጡረታ መብታቸው እንዲከበርላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በበኩሉ በሰጠው መልስ፡- ተጠሪ አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች በመሆኑ ከስራ የተሰናበቱት በጡረታ ሳይሆን በሌላ ምክንያት ስለሆነ ሊያገኙ የሚገባቸው የአንድ ጊዜ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤም የአሁኑ ተጠሪ አገልግሎታቸው ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በቀድሞው የጡረታ አዋጅ መሰረት የዘለቄታ ጡረታ መብት እንዲከበርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 22/23/1955 መሰረት ቢያንስ 10 ዓመት ካገለገለ እና እድሜው ለጡረታ የደረሰ ከሆነ የጡረታ መብት እንዲከበርለት ቢደነግግም አመልካች ከስራ በሚሰናበቱበት ወቅት እድሜያቸው ለጡረታ ያልደረሰ ስለሆነ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊስተናገዱ የሚችሉ አይደሉም፣ ጉዳያቸው መታየት የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 714/2003 መሰረት ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19/2/ ድንጋጌ ስር ደግሞ ቢያንስ 20 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ እድሜው መውጫ ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል በማለት ደንግጓል፣ አመልካች 17 አመት ከ11 ወር አገልግለው በሌላ ምክንያት የስራ ውላቸው የተቋረጠ በመሆኑ እና የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት በታች መሆኑ ተረጋግጧል የሚሉ ምክያቶችን በማስፈር ተጠሪ ሊኖራቸው የሚችለው መብት የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ማግኘት እንጂ ዘላቂ የጡረታ መብት ተጠቃሚነት አይደለም በማለት ደምድሞ የአሁኑ አመልካች የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወሰኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መስተናገድ የሚገባው በየትኛው ህግ ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ መሰተናገድ የሚገባው ጉዳዩ በቀረበበት ጊዜ በስራ ላይ ባለው ህግ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ ነው፣ ይህ አዋጅ ደግሞ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ ይህ ማሻሻያ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ መንገድ አገልግሎት ያቋረጠ የጡረታ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት የጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል በማለት ደንግጓል፣ የአሁኑ ተጠሪ በዳኞች ምርጫ አልታቀፉም ተብለው ከስራ የተሰናበቱት 17 ዓመት ከ11 ወር ካገለገሉ በኋላ ቢሆንም ስራውን የለቀቁት አዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/20007 እንደተሻሻለ) ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው ናቸው፣ የአሁኑ አመልካች መስሪያ ቤት ይህ አዋጅ ተፈፃሚ መሆን የሚገባው አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ከስራ በተሰናበቱ ሰራተኞች ላይ ነው

ብሎ ያቀረበው ክርክርም የተጠሪ ጉዳይ የቀረበው ይህ አዋጅ ፀንቶ ባለበት ወቅት ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ነው የሚሉ ምክንያቶችን አስፍሮ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁጡ/ይ/1/1/16/2008 ሐምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 56/4/ መሰረት መሻሩን ገልጾ የአሁኑ ተጠሪ ዘላቂ የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆን ይገባቸዋል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች መስሪያ ቤት ነገረ ፈጅ ሐምሌ 03 ቀን 2010 ዓ/ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም፡- ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የአዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ በአንቀፅ 19(2) ድንጋጌ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ ይህ ማሻሻያ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ መንገድ አገልግሎት ያቋረጠ የጡረታ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት የጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል በማለት በግልጽ በደነገገበትና ተጠሪ ስራውን በለቀቁበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው 205/55 በአዋጅ ቁጥር 5/1967 እንደተሻሻለ በአንቀፅ 4(1) ስር የዘለቄታ ጡረታ መብት ተጠቃሚ ለመሆን የሚቻለው ቢያንስ አስር አመት ያገለገለና በስራ ላይ እያለ የመጦሪያ እድሜው በመድረሱ ከስራ ሲሰናበት ስለመሆኑ ደንግጎ እያለ ተጠሪ ከስራቸው የተሰናበቱት እድሜአቸው ለጡረታ ደርሶ ሳይሆን ስራ ላይ ባለመመደባቸው ምክንያት ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የሕግ ማእቀፎች ከደነገጉት ውጪ ተጠሪ የዘላቂ ጡረታ መብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም ተጠሪ የመንግስት ሰራተኛ ሆነው 17 አመት ከ11 ወር አገልግለው ሰኔ 01 ቀን 1988 ዓ/ም ከስራ የተሰናበቱ ሲሆን የተጠሪ የጡረታ መብት ጉዳይ የቀረበው አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ ፀንቶ ባለበት ወቅት ስለሆነ ተጠሪ የዘላቂ ጡረታ መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 5(2) ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና በሰ/መ/ቁጥር 132861 ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከስራ በተሰናበቱበት ወቅት በስራ ላይ የነበረው አዋጅ ቁጥር 22/23/1955 መሰረት የዘላቂ ጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ መሆኑን ጠቅሰው

የሚከራከሩ መሆኑን፣ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ስራ በለቀቁበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው ተጠሪ የጠቀሱት ሳይሆን አዋጅ ቁጥር 209/55 በአዋጅ ቁጥር 5/67 እንደተሻሻለ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 5/67 አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ ስር ደግሞ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለና በስራ ላይ እያለ የመጦሪያ እድሜው በመድረሱ ከስራ የተሰናበት የመንግስት ሰራተኛ መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱበት እድሜያቸው ለጡረታ ደርሶ ሳይሆን ስራ ላይ ባለመመደባቸው ምክንያት በመሆኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ጥያቄአቸው የሚስተናገድበት አግባብ የሌለ መሆኑን፣ ጉዳዩ መታየት የሚገባው ተጠሪ ስራ በለቀቁበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው አዋጅ ቁጥር 209/55 በአዋጅ ቁጥር 5/67 እንደተሻሻለ አንቀጽ 9(2) ድንጋጌ መሰረት ሆኖ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም ተጠሪ አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች በመሆኑ መብታቸው የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ብቻ ስለመሆኑ፣ አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ አንቀጽ 19 (2) ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል ተብሎ የተደነገገ ቢሆንም በዚሁ አዋጅ ማሻሻያ መሰረት እድሜው ሲደርስ የዘለቄታ የጡረታ አበል ተጠቃሚ ለመሆን የሚቻለው ከ10 ዓመት አገልግሎት በኂላ ሰራተኛው ስራውን ያቋረጠው ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ከሐምሌ 03 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ ተጠሪ ግን አገልግሎታቸውን ያቋረጡት በ1988 ዓ.ም በመሆኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም በማለት የሚከራከር መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው ስለሚገባው ህግ ግራ ቀኙ ክርክር አቅርበው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ጭብጥ ይዞ የተጠሪ ጉዳይ መስተናገድ የሚገባው ጉዳዩ በቀረበበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው ህግ መሰረት ነው፣ ምክንያቱም በወቅቱ ስራ ላይ ያለው ህግ እያለ ስራ ላይ ያልነበረ ህግ ወደ ኂላ በመሄድ ተግባራዊ የሚደረግበት አግባብ ባለመኖሩ ነው፣ ጉዳዩ (ክርክሩ) የቀረበው ደግሞ በ2008 ዓ.ም ነው፣ በዚህ ጊዜ በስራ ላይ ያለው ህግ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ ነው ወደሚል ድምዳሜ የደረሰ መሆኑንና ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች መስሪያ ቤት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የአዋጅ ቁጥር 209/55 (በአዋጅ ቁጥር 5/67 እንደተሻሻለ) ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ ቅሬታ ማቅረቡ አመልካቹ መስሪያ ቤት ራሱ ቀድሞውኑ የአዋጅ ቁጥር 714/2003 ዓ/ም አንቀፅ 19 (2) ድንጋጌን መሰረት በማድረግ ጉዳዩን አይቶ ሰኔ 25 ቀን 2008 ዓ/ም አስተዳደራዊ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ተቀባይነት ስለሌለው ጉዳዩ ስራ ላይ ባለው ሕግ መታየቱ የሚነቀፍበት አግባብ የለም በማለት የሚከራከሩ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንጻር ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት ያለው ህግ ክርክሩ በሚታይበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 714/2003 በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ይህንኑ መሰረት በማድረግ የተጠሪን የዘላቂ ጡረታ አበል ተጠቃሚነት ጥያቄ የሕግ መሰረት ያለው መሆን ያለመሆኑን እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19 (2) ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚሁ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል አስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል የሚል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ መሰረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል እና በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ቅድመ ሁኔታዎቸ መሆናቸውን የድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የአዋጁ ድንጋጌ የአዋጁ ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 5 (2) የተተካ ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ይዘት ሲታይ ደግሞ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ የመንግስት ስራተኛ <u>**ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ**</u> በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ አንድ በተደነገገው መሰረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል የሚል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ይህ ማሻሻያ ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 19 (2) ስር ተጠቀሰው ከነበሩት መስፈርቶች የጨመረው **የሥራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ አዋጁ ከፀናበት ጊዜ አንስቶ** የሚለውን ሐረግ መሆኑን ከድንጋጌው ይዘት መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሥራ ውሉ የሚቋረጠው አዋጁ ከጸደቀበት ጊዜ ከሆነና ሌሎች በሕጉ የተመለከቱ ቅድመ ሁኔታዎች አንድ ላይ ተሟልተው ከተገኙ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ የመንግስት ሰራተኛ የመብቱ ተጠቃሚ እንደሚሆን ሕጉ የደነገገው ጉዳይ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀፅ 60 (2) ድንጋጌ መሰረት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 ያወጣ ሲሆን በዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ስር "**በራሱ** ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ከስራ ማቋረጥ ምክንያት ለሚቀርብ የጡረታ አበል ጥያቄ" የሚል አርዕስት ተሰጥቶ በአንቀፁ ፊደል (ሐ) ስር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 19 ንዑስ ቁጥር ሁለት መሰረት ማሻሻያ አዋጁ **ለ**ፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱ ከ10 አመት ያላነሰ 25 አመት ያልሞላ ከሆነ እድሜው በሕግ የተወሰነ የጡረታ መውጫ እድሜ ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የአገልግሎት የጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ እንደሚከፈለው መደንገጉ ሲታይም ከአስር አመት ያላነሰ 25 አመት ያልሞላው የመንግስት ሰራተኛ የዘላቂ ጡረታ አበል ተጠቃሚ የሚሆነው እድሜው የጡረታ መውጫ እድሜ የደረሰ ሆኖ በተጨማሪም ስራውን የለለቀው አዋጁ ከፀደቀበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ጀምሮ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑን ግልፅ ያደረገው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም የአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19(2) ማሻሻያ የሆነው የአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀፅ 5(2) ድንጋጌ የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል እና በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ቅድመ ሁኔታዎቹ ከመሆናቸውም በላይ የሥራ ውሉ መቋረጥ ያለበት ግን የአዋጅ ቁጥር 714/2003 ማሻሻያ የሆነው

አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ መሆን ያለበት መሆኑን ሕጉ አሰገዳጅነት ባለው ሁኔታ የደነገገ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ እና የመንግስት ሰራተኞችን በሚመለከት በወጣው አዋጅ ስር ያሉትን ድንጋጌዎችን ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ እንዲያወጣ በሕግ አውጪው የውክልና ስልጣን የተሰጠው አካል ያወጣው የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈፀሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀፅ 4 (ሐ) ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የአሁኑ ተጠሪ በዳኞች ምርጫ አልታቀፉም ተብለው ከስራ የተሰናበቱት 17 ዓመት ከ11 ወር ካገለገሉ በኂላ በ1988 ዓ/ም በመሆኑና በዚህ ጊዜ ደግሞ እድሜአቸው ለጡረታ ያልደረሰ የነበረ በመሆኑ፣ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) ተፈፃሚ መሆን የሚገባው አዋጁ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ከስራ በተሰናበቱ ሰራተኞች ላይ በመሆኑ በተጠሪ ጉዳይ አዋጁ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 132861 ሀምሌ 28 ቀን 2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከመፅናቱ በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት ከአስር አመት በላይ አገልግሎት በመስጠት ስራውን በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ለለቀቀ ሰራተኛ እድሜው ስልሳ አመት የሞላው እስከሆነ ድረስ የዘላቂ ጡረታ ተጠቃሚነት መብት አለው በማለት ለአዋጁ ማሻሻያ አንቀጽ 5 (2) የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የሕጉን ይዘትና መንፈስ ያልተከተለና ስህተት ሆኖ ስላገኘው ይህ ችሎቱ ራሱ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በሌላ ጊዜ መቀየር የሚችል መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) ድንጋጌ ያስቀመጠ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 132861 በዚህ ረገድ የተሰጠው የሕግ ትርጉም ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡ስለሆነም የአዋጅ ቁጥር 714/2003 ማሻሻያ የሆነው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከመፅናቱ በፊት በመንግስት መስሪያ ቤት ከአስር አመት በላይ አገልግሎት በመስጠት ስራውን በራሱ ፈቃድ ወይም በሌላ ምክንያት ለለቀቀ ሰራተኛ እድሜው ስልሳ አመት የሞላው እስከሆነ ድረስ የዘላቂ ጡረታ ተጠቃሚነት መብት በአዋጁ አንቀፅ 5(2) ድንጋጌ የተጠበቀ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተጠቀሱት ዝርዝር ሕጋዊ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5(2) የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት መሰረቱ ቢያንስ አስር አመት ማገልገል እና በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 18 መሰረት የጡረታ እድሜ መድረስ በመሆኑ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ እና በራሱ ፈቃድ ወይም በአዋጁ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ለዘለቄታው የማግኘት መብት አለው ተብሎ በሰ/መ/ቁጥር 132861 በ28/11/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 (1) መሰረት ተለውጧል፡፡

2. በፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 131833 በ22/09/2010 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁጡ/ይ/1/1/16/2008 ሐምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
4. በተሻሻለው የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 907/2007 አንቀጽ 5 (2) ድንጋጌ መሰረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር አመት ማገልገል እና በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 18 መሰረት የጡረታ እድሜ መድረስ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ቢያንስ አስር አመት ያገለገለ እና በራሱ ፈቃድ ወይም በአዋጁ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎቱን ያቋረጠው አዋጁ ከፀናበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡
5. በአዋጅ ቁጥር 714/2003 (በአዋጅ ቁጥር 907/2007 እንደተሻሻለ) አንቀፅ 19 (2) መሰረት ተጠሪ ዘላቂ የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆን አይችሉም ብለናል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**ሳ/ፀ**

የማይነበብ የሰባት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 187618

መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ የሽዋስ አስማረ

ተጠሪ፡- አቶ ያሲን አሊ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመሬት ይዞታ ለማስለቀቅ የቀረበ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በጉራፈርዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በጉራፈርዳ ወረዳ በበርጂ ቀበሌ መድሃኒአለም ቤተክርስቲያን ጀርባ 3ኛ ደረጃ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሚገኝ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን 50ሜትር በ600ሜትር የሆነ 3 ሄክታር የእርሻ መሬት የበርጂ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 10/06/1999ዓ/ም በተጻፈ ቃለ ጉባኤ (ቬርባል) ሰጥቶኛል፡፡እስከ 2004ዓ/ም ደረስ ግብር እየገበርኩ የተለያዩ ተክሎችን ተክዬ የምጠቀምበትን እንዲሁም ዓመታዊ ሰብል የማመርትበትን መሬት በ2004ዓ/ም በአካባቢዉ በተነሳዉ አለመረጋጋት ምክንያት ቤተሰቦቼን ይዤ ከተፈናቀልኩበት ስመለስ ተጠሪ ይህንን መሬቴን በመያዝ እየተጠቀሙ እንደሚገኝ በማወቅ እንዲለቁልኝ ስጠይቃቸዉ ፈቃደኛ ስላልሆኑ የመሬት ይዞታዬን እንዲለቁ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ የአመልካችን ይዞታ በኃይል ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ አልያዝኩም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ በ2004ዓ/ም ከዳንቅላ ቀበሌ ስፈናቀል በነበረኝ ይዞታ ምትክ በልዋጭ በወረዳዉ መንግስት ፈቃድ የተሰጠኝ ነዉ፡፡በቁጥር 150 የሚሆኑ የተለያዩ አትክልቶች ተክዬ ለፍሬ ካበቃሁ በኋላ አመልካች መጥተዉ የእኔ ነዉ አሉ እንጂ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ አልወሰድኩም፡፡የመንግስት የነበረ መሬት ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11475 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና ማስረጃ አስቀርቦ መርምሮ በቀን 18/10/2011ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክርክር ያስነሳዉ የመሬት ይዞታ አመልካች አስቀድሞ በሕጋዊ መንገድ ተመርተዉ የያዙት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ይዞታ ቃለ-ጉባኤ(ቭርባል) ተይዞ

ለአመልካች የተመራ መሆኑን አመልካች በእጃቸዉ በሚገኘዉ ሰነድ(ቬርባል) አስረድተዋል፡፡ በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ከጉራፈርዳ ወረዳ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የመጣዉ ማስረጃ ተጠሪ ይዞታዉን የተመሩበትን ሁኔታ የሚያሳይ ምንም ማስረጃ በጽ/ቤቱ ዘንድ እንደማይገኝ ገልጿል፡፡በ2004 ዓ/ም በአካባቢዉ በተፈጠረ አለመረጋጋት ምክንያት አመልካች ከአካባቢዉ ተፈናቅለዉ መሬቱን ለቀዉ ሲሄዱ ተጠሪ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 9 አግባብ ዉጭ በመያዝ አመልካች በ2009ዓ/ም ወደ አካባቢዉ ተመልሰዉ ሲጠይቁ ለመልቀቅ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በማስረጃ ማረጋገጡን ገልጾ ተጠሪ ሕጋዊ ባልሆነ ምሪት የያዙትን ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ለአመልካች ሊለቁ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 19556 ላይ በቀን 26/10/2011 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡በመቀጠል ተጠሪ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 07642 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 30/12/2011ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር የወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪዉን ይዞታ ተጠሪ በቀበሌ አመራር አማካኝነት ማግኘታቸዉን ተረጋግጧል፡፡ የአሁን አመልካች ይዞታዉን ያገኙት በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ ተብሎ በ2004ዓ/ም ሳይለካላቸዉ እንደቀረ በሰዉና በሠነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ ባለበት እንዲሁም አመልካች ሕገ ወጥ ይዞታ መሆኑን ተቀብለዉ የነበረዉን የቆርቆሮ ቤት አፍርሰዉ ሄደዉ የመብት ጥያቄ ሳያቀርቡ ቆይተዉ በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ መብት እንዳለዉ ሰዉ በመሆን ተጠሪ ከስድስት አመት በላይ ቋሚ ተክሎችን በመትከልና ቤት በመስራት ግብር እየገበሩበት ይዘዉ የቆዩትን ይዞታ ለቀዉ ለአመልካች እንዲያስረክቡ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡ስለሆነም አመልካች በአከራካሪዉ ይዞታ ላይ የተከሏቸዉ ቋሚ ተክሎች ካሉ በማስረጃ አረጋግጠዉ ግምት የመጠየቅ መብት ያላቸዉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ አከራካሪዉን ይዞታ ለአመልካች ሊለቁ አይገባም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 07877 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 25/03/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሠጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ አመልካች በቀን 14/04/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን 3 ሄክታር መሬት አመልካች በሕጋዊ መንገድ በቀን 10/06/1999ዓ/ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ ተሰጥቶኝ የተለያዩ አትክልቶችን በመትከል እየተጠቀምኩ እስከ 2004ዓ/ም ግብር እየገበርኩ ይዤ የቆየሁት ነዉ፡፡በ2004ዓ/ም አከራካሪዉን የመሬት ይዞታ ለቅቄ የወጣሁት በወቅቱ በአካባቢዉ የሚኖር የአማራ ተወላጅ ለቆ ይዉጣ በሚል በተፈጠረ አለመረጋጋት ከቤተሰቤ ጋር ጥቃት ይደርስብኛል

በሚል ነዉ፡፡አካባቢዉ ላይ መረጋጋት ሲፈጠር ከ3 ወር በኂላ ወደ አካባቢዉ ተመልሼ ይዞታዬን በመያዝ ንብረቴን እየተጠቀሙ የሚገኙት የአሁን ተጠሪ ይዞታዬን እንዲለቁ ለማስደረግ ለሚመለከታቸዉ የመንግስት አካላት አቤቱታ ሳቀርብ ቆይቼ አቅጣጫ ሲሰጥ ቢቆይም ተጠሪ ይዞታዬን እንዲለቁ ማድረግ ስላልቻሉ በፍርድ ኃይል ለማስለቀቅ ያቀረብኩት ክስ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመብት ጥያቄ ሳላቀርብ እንደቆየሁ አድርጎ የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ መሻሩ ስህተት ነዉ፡፡ ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት በምሪት ተሰጥቷቸዉ ስለመያዛቸዉ በምንም አይነት ማስረጃ አላስረዱም፡፡ተጠሪ በአመልካች የለማዉን መሬት ተሰጥቶኛል በማለት የሚያነሱት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡መሬቱ ለተጠሪ ተመርቷል ቢባል እንኳን አመልካች በተመራሁበት እና ባለማሁበት መሬት ላይ ለተጠሪ ደርቦ ለመምራት የሚያስችል የሕግ ስርዓት የለም፡፡ የጉራፈርዳ ወረዳ መንግስት አመልካች ከይዞታዬ እንዲፈናቀል የወሰነዉ ዉሳኔ የለም፡፡የወረዳዉ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት በጻፈዉ ደብዳቤ ላይ እንደተመለከተዉ የአመልካች ይዞታ በወቅቱ ያልተለካዉ ሕገ-ወጥ ስለሆነ ነዉ ያለበት ምክንያት አመልካች ከመጀመሪያዉም ይዞታዉን የያዝኩት በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ ለማለት ፈልጎ ሳይሆን በ2004ዓ/ም በጉራፈርዳ ወረዳ በነበረዉ የፖለቲካ አለመረጋጋት ከወረዳዉ የነበሩ አማራ አርሶአደሮች ከአካባቢዉ ይዉጡ ተብሎ ስለነበር አማራዎች የያዙት ይዞታ በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ቢሆንም ከክልላቸዉ ዉጭ መስፈራቸዉ ሕገ-ወጥ ነዉ የሚል የተሳሳተ ስያሜ ተሰጥቶት እንጂ ከመነሻዉም መሬቱ በሕገ-ወጥ መንገድ የተያዘ ነዉ ለማለት አይደለም፡፡ይህንን ባሉሙያ ጭምር በማስቀረብ ማጣራት እየተቻለ የተሳሳተ ግንዛቤ በመያዝና አመልካች ከተጠሪ የተሻለ ማስረጃ በማቅረብ በሕጋዊ መንገድ የያዝኩት ይዞታ መሆኑን አስረድቼ እያለሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/4 ላይ የኢትዮጵያ አርሶአደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለሕጋዊ ምክንያት ያለመፈናቀል መብት አላቸዉ የሚለዉን የሚቃረን ስለሆነ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የወረዳ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ወሳኔ ይጽናልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት በሕግ አግባብ ስላለመያዛቸዉ የሚመለከተዉ አካል እየገለጸ ባለበት አመልካች ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ ሲጠቀሙበት ቆይተዉ በ2004 ዓ/ም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መልቀቃቸዉ ተረጋግጦ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች አከራካሪዉ ይዞታ ለተጠሪ ይገባል በማለት የወሰኑበትን አግባብ ከመሰረታዊዉ የማስረጃ ምዘና መርህ አንጻር እንዲመረመር ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 16/11/2012 ዓ/ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ፡-

የጉራፈርዳ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ለፍርድ ቤቱ በጻፈዉ ደብዳቤ “ተጠሪ ይዞታዉን በወረዳዉ በስግሰጋ መልክ መዉሰዳቸዉን የሚያሳይ ምንም ገላጭ የሆነ መረጃ በጽ/ቤቱ ደረጃ እንደሌለ እንገልጻለን” በማለት የጻፈዉ ደብዳቤ መረጃ እንደሌለዉ የገለጸበት ነዉ እንጂ ተጠሪ ይዞታዉን በሕግ አግባብ አልያዙም ወይም አያያዙ ሕገ-ወጥ ነዉ በሚል የሠጠዉ ማረጋገጫ አይደለም፡፡የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ደብዳቤዉን የጻፈዉ ኃላፊ የአከራካሪዉ መሬት ሕጋዊ ባለይዞታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኔ አረጋግጧል፡፡ በቀን 02/12/2011ዓ/ም ለተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ተሰጥቶኛል፡፡ ሁሉም አቅርቤ ያሰማኋቸዉ ምስክሮቼ አከራከሪዉ መሬት የተሰጠኝ በዳንቅላ ቀበሌ በሕጋዊ መንገድ በሰፈራ የተመራሁት መሬት በአካባቢዉ በነበረ አለመረጋጋት ምክንያት ተወስዶብኝ ስለነበር የወረዳዉ መሬት አስተዳደር ከቀበሌ አስተዳደር ጋር በመሆን በልዋጭ መርቶኝ በቅጽ ተመዝግቦ ያገኘሁት መሆኑን አስረድተዋል፡፡መሬቱ በእጄ የሚገኝና ግብር የምገብርበት ነዉ፡፡አመልካች ይዞታዉን ከ1999ዓ/ም ጀምሮ በእጃቸዉ አድርገዉ በ2004ዓ/ም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የለቀቁ ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡አመልካች መሬቱን በምሪት ደብዳቤ(በቬርባል) አግኝቻለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ሰነዱን ለስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት አቅርበዉ አላስረዱም፡፡ አንዳችም የግብር ደረሰኝ በማስረጃነት አላቀረቡም፡፡አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ መንግስት ሳይመራቸዉ በሕግ አግባብ ዉጭ በመሬት ወረራ መያዛቸዉ በ2004ዓ/ም በተደረገ ማጣራት ተረጋግጦ እንደለቀቁ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ የተረጋገጠ ነዉ፡፡አመልካች ከሕግ ዉጭ እንድለቅ ተደርጌያለሁ የሚሉ ከሆነ ያፈናቀላቸዉን አካል ከሚጠይቁ በስተቀር የነበራቸዉን ቤት አፍርሰዉና ንብረት አንስተዉ አካባቢዉን ለቀዉ ከሄዱ በኋላ ተጠሪ መሬቱን በጉልበት እንዳልያዝኩ እያወቁ በመንግስት ምሪት በሕጋዊ መንገድ የያዝኩትን እንድለቅላቸዉ ሊጠይቁኝ አይችሉም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስረጃዎችን በአግባቡ መዝኖ ተጠሪ ይዞታዉን መልቀቅ እንደማይገባኝ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በቀን 18/02/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የመሬት ይዞታ አመልካች ከ1999ዓ.ም ጀምሮ በጉራፈርዳ ወረዳ በበርጂ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በቃሌ ጉባኤ መርቶኝ የተለያ ቋሚ ተክሎችን በመትከልና አመታዊ ሰብል በማምረት የየዝኩትን በ2004ዓ/ም በአካባቢዉ በተፈጠረ ግጭት ምክንያት ከጥቃት ለመዳን ቤተሰቦቼን ይዤ ከሄድኩበት ስመለስ ተጠሪ ያለማሁትን ይዞታዬን ይዘዉ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የመንግስት ይዞታ እንደሆነና በዚያዉ ወረዳ ዳንቅላ ቀበሌ በሚባልበት ከነበራቸዉ ይዞታ ሲፈናቀሉ

በልዋጭ በወረዳዉ መንግስት በ2004ዓ/ም ተመርተዉ በመያዝ የተለያዩ ተክሎችን ተክለዉ የያዙት የመንግስት መሬት እንደሆነ ገልጸዉ አመልካች ይዞታዉን ለማስለቀቅ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

በወረዳዉ ፍርድ ቤት አመልካች አቅርበዉ ያሰሙት አራት ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ቃል ነዉ ተብሎ በዉሳኔዉ የሰፈረዉ"…ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአመልካች ነዉ፡፡በ1999ዓ/ም የካቲት 7 ቀን ከቀበሌዉ ይዞታዉ የተሰጠዉ በቬርባል በመፈራረም ነዉ፡፡ከሳሽ ይዞታዉ ከተሰጠዉ በኋላ ይዞታዉን እያለማ 42 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ሰርቶበት ሲኖር ሳለ በ2004ዓ/ም ከአካባቢዉ አማራ ይዉጣ የሚል ብጥብጥ ተነስቶ ስለነበር ከሳሽ ሆነ ሌሎች አርሶ አደሮች አካባቢዉን ለቀዉ ሄደዉ ነበር፡፡የአካባቢዉ ሁኔታ መረጋጋቱን አዉቆ ከሳሽ ተመልሶ ሲመጣ ቤቱን አጥቷል፡፡በይዞታዉ ላይ የነበሩ አትክልቶች አሁንም አሉበት፡፡በ2009 ዓመት መጥቶ በይዞታ ጉዳይ አቤቱታ እያቀረበ ምንም ምላሽ አላገኘም፡፡በኋላ በዞኑ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት አመልክቶ በወረዳዉ አስተዳደር በኩል ይዞታዉ እንዲመለስለት ጽፎለት ነበር፡፡ሆኖም አልተፈጸመለትም፡፡ተከሳሹ በምን ሁኔታ የከሳሽን ይ+ዞታ ለመያዝ እንደቻለ አናዉቅም በማለት መስክረዋል፡፡"የሚል ነዉ፡፡እንዲሁም ከክሳቸዉ ጋር ከ1999ዓ/ም እስከ 2004ዓ/ም ግብር የገበሩበትን ሰነዶች እና ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴና ከሚመለከታቸዉ አካላት የተጻፉላቸዉን ሰነዶች አያይዘዉ እንዳቀረቡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ይዘት ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል በወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ አቅርበዉ ያሰሟቸዉ ሶስት ምስክሮች በሰጡት ምስክርነት ቃል፡-"…ክርክር የተነሳበት ይዞታ የለማና የተለያዩ አትክልቶች እያለበት በወቅቱ በነበረ የቀበሌ ተወካዮች እንደተሰጠዉ ገልጸዉ ከሳሽም ይዞታዉ የእኔ ነዉ ብሎ መከራከሩን እንደሚያዉቁ አስረድተዋል፡፡ይዞታዉ የለማዉ በከሳሽ ሲሆን አትክልቶቹን ተንከባክቦ ያሳደገዉ ተከሳሽ ነዉ ብለዋል፡፡ተከሳሽም ቀደም ብሎ በአቱዋ ቀበሌ በኬራንባ ጎጥ ዉስጥ እያለ ከሌሎች ጋር በመሆን ይዞታ እንዲሰጣቸዉ በጠየቁት መሰረት ይዞታዉ ለተከሳሽ እንደተሰጠዉ አስረድተዋል፡፡"በሚል መመስከራቸዉ ተመዝግቧል፡፡እንዲሁም ከመልሳቸዉ ጋር የ6 ዓመት የግብር ካርኒ በማስረጃነት አያይዘዉ እንዳቀረቡ በዉሳኔዉ ላይ ተመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማስረጃ ከጉራፈርዳ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ማስረጃ እንዲቀርብለት አዝዞ ጽ/ቤቱ በላከዉ ምላሽ "አሁን ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ከሳሽ ይዞ እያለማዉ ሲኖርበት ሳለ በቀበሌዉ መሬት አስተዳደር በሚለካበት ጊዜ ከሳሽ በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ የያዘዉ ተብሎ አልተለካለትም፡፡የከሳሽም ስም አሁን በጽ/ቤቱ ዉስጥ የሚገኝ ሲሆን ተከሳሽ ይዞታዉን ተመርቷል ይባላል እንጂ ግን ምንም መረጃ በጽ/ቤታቸዉ እንደሌለዉ በመግለጽ ጽፏል፡፡" የሚል ነዉ፡፡

በስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡ የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎች ከላይ በአጭሩ የተመለከተዉ ሲሆን ከእነዚህ ማስረጃዎች ዉጭ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ ስለመመርመሩ ዉሳኔዉ

አያሳይም፡፡በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ ተጠሪ ይዞታዉን በ2004ዓ/ም የተመሩበትን ማስረጃ እንዳላቀረቡ ገልጿል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/4 እና በተሻሻለዉ በደቡብ ብሔር በሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግስት ላይ በተመሳሳይ በተደነገገዉ መሰረት አርሶ አደሮች ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነዉ መሰረት መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸዉ ያለመፈናቀል መብት አላቸዉ፡፡በፌደራሉም ሆነ በክልል ሕገ መንግስታት አንቀጽ 40(7 እና 8) ስር እንደተደነገገዉ የመሬት ባለቤትነት የመንግስትና የሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ግለሰቦች ባለይዞታ በሆኑበት የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸዉ ሊቋረጥ የሚችለዉ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ በቅድሚያ ካሳ እና/ወይም ምትክ ቦታ ከተሰጣቸዉ ብቻ እንደሆነ፣ማንኛዉም በክልሉና ከክልሉ ዉጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገዉ ቋሚ ማሻሻል ሙሉ መብት እንዳለዉና ግለሰቦችም የመሬት ባለይዞታነት መብት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት አግባብ ባለዉ ሕግ በተደነገገዉ ስርዓት መሰረት ነዉ፡፡

እንዲሁም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 2/13 ስር በተመለከተዉ ትርጓሜ መሰረት የግል ይዞታ ማለት አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና ወይንም በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣዉ አካላት በግል ይዞታ ስር ያለ የገጠር መሬት ነዉ፡፡በአዋጁ አንቀጽ 5/1 የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም በተደነገገዉ ስር በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነጻ የማግኘትና የመጠቀም መብት እንደላቸዉ ተመልክቷል፡፡የአርሶ አደሮች፣ የከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ላልተወሰነ ጊዜ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት እንዳላቸዉ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 7/1 ላይ ተመልክቷል፡፡በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 13/14 ስር በተደነገገዉ መሰረትም ማንኛዉም ግለሰብ ወይም ድርጅት ያለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የገጠር መሬትን መጠቀም እንደማይችል ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል አንድ በክልሉ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ሰዉ የባለይዞታነት መብቱን ሊያጣ የሚችልበትም አግባብ በሕጉ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ይኸዉም በአዋጁ አንቀጽ 9/1 ስር ስለገጠር መሬት ሽግሽግ እንደተደነገገዉ ባለይዞታዎች በሕይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸዉ ወይም በሰፈራ ወይም በፍላጎታቸዉ ከተወሰነዉ ጊዜ በላይ አካባቢዉን ለቀዉ የቆዩ ከሆነ ይዞታቸዉ መሬት አልባ ለሆኑ ወይም መሬት ላነሳቸዉ አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በደንብ ላይ ተዘርዝሮ በሚደነገገዉ መሰረት በሽግሽግ ሊሰጥ ይችላል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 7/3 እና 13/11 በግል ባለይዞታነት የተያዘ የገጠር መሬትን ባለይዞታዉ በመሬቱ ላይ ላደረገዉ ማሻሻያና ላፈራዉ ንብረት አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ ተከፍሎትና በለቀቀዉ ምትክ ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ በማድረግ መሬቱን ለሕዝብ ጥቅም ለማዋል እንዲለቅ ማድረግ የሚቻል ሲሆን ከዚህ ዉጭ ባለይዞታዉ በመሬቱ

የመጠቀም መብቱን ሊያጣ የሚችለዉ በአንቀጽ 10/1 እና 13/12 ስር እንደተደነገገዉ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ በተወሰነዉ መሰረት ባለይዞታዉ መሬቱን በአግባቡ የመጠቀምና የመንከባከብ ግዴታዉን ባለመወጣቱ የተነሳ በመሬቱ ላይ ጉዳት(በቅጣት ብቻ ሊታለፍ የማይችል ጉዳት) ማድረሱ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ ባለይዞታዉ አግባብ ላለዉ አካል በግልጽ አሳዉቆ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን በፈቃዱ ካልተወ በስተቀር የገጠር መሬት ባለይዞታነት መብቱን ሊያጣ አይችልም(የአዋጁ አንቀጽ 10/4 ይመለከቷል)፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሕጎች የተደነገገዉንና በግራ ቀኝ ምስክሮችና ማስረጃዎች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ከግምት በማስገባት አከራካሪዉን ይዞታ ተጠሪ ለአመልካች ሊለቁ አይገባም ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ያቀረቡት ምስክሮች አመልካች አከራካሪዉን መሬት በ1999ዓ/ም ተመርተዉ እንደያዙ የመሰከሩላቸዉ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት ምስክሮች ደግሞ አመልካች አልምተዉ ይዘዉ የነበረዉን መሬት በቀበሌ አስተዳደር አማካኝነት ለተጠሪ ተሰጥቷቸዉ ስለመያዛቸዉ መስክረዉላቸዋል፡፡ሆኖም አመልካችም ሆኑ ተጠሪ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ በስር ፍርድ ቤቶች ካቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ጋር ወይም ሕጉ በሚፈቅደዉ የክርክር ደረጃ ላይ አከራካሪዉን መሬት አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ተመርተዉ(በድልድል) ስለማገኘታቸዉ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም በስማቸዉ ተመዝግቦ የተሰጣቸዉን የባለይዞታነት ማረጋገጫ ምስክር ደብተር በማቅረብ አላስረዱም፡፡አመልካች መሬቱን በቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት በቀን 10/06/1999ዓ/ም በተጻፈ ቃለጉባኤ(ቬርባል)ተሰጥቶኝ ነዉ የያዝኩት በሚል በክሳቸዉ ቢገልጹም ይህንን ማስረጃ በማስረጃነት ያቀረቡ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ግልባጭ ባያሳይም የስር ፍርድ ቤቶች ይህ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ አለማጣራታቸዉን ተገንዝበናል፡፡ተጠሪም በይዞታዉ ላይ በስሜ ተመዝግቦ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በቀን 02/12/2011ዓ/ም ተሰጥቶኛል ብለዉ ቢከራከሩም ይህንን ማስረጃ አግኝተዉ ከሆነም የወረዳ እና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ በመስጠት ይዞታዉን ለአመልካች እንዲያስረክቡ ከተወሰነና ጉዳዩ በይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ ተጠሪ ይዞታዉን ሊለቁ አይገባም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተሽሮ ከመወሰኑ በፊት በመሆኑ ለስር ፍርድ ቤቶች የቀረበ ማስረጃ ባለመሆኑ ተጠሪ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ እንዳቀረቡት ማስረጃ ተቆጥሮ ሊመዘን የሚችል አይደለም፡፡ እንዲሁም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከወረዳዉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ግራ ቀኝ ይዞታዉን በምን አግባብ እንደያዙ ለማጣራት ትእዛዝ ቢሰጥም አከራካሪዉን መሬት አስቀድመዉ የያዙትና ያለሙት አመልካች ቢሆኑም መሬቱ በቀበሌ መሬት አስተዳደር በሚለካበት ጊዜ አመልካች መሬቱን በሕገ-ወጥ መንገድ ነዉ የያዙት በሚል ምክንያት ሳይለካላቸዉ መታለፉንና በኋላም ተጠሪ መሬቱን ተመርተዋል ከሚባል በስተቀር ሁለቱም ወገኖች መሬቱን በምን አግባብ አግኝተዉ እንደያዙ ለጽ/ቤቱ መረጃ እንደሌለዉ በመግለጹ ሳይረጋገጥ ቀርቷል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ለስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡ ማስረጃዎች የሚያሳዩት ከ1999ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ አከራካሪዉን መሬት የያዙትና የተለያዩ ተክሎችን በመትከል እንዲሁም 2004ዓ/ም እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ ቤት ጭምር ሰርተዉ በይዞታዉ ሲጠቀሙ የቆዩት አመልካች መሆናቸዉ ቢረጋገጥም ይህንን ይዞታ አመልካች በምን አግባብና በማን ፈቃጅነት ይዘዉ ሲጠቀሙ እንደቆዩ ግን ተገቢዉን ማስረጃ በማስቀረብና የቀረቡትንም በመመዘን በሚገባ ባለመጣራቱ የፍሬ ነገሩ መኖር አለመኖር አለመረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ በወረዳዉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ለወረዳ ፍርድ ቤት በተላከ ማስረጃ ላይ ይዞታዉን አመልካች በሕገ-ወጥ መንገድ ይዘዋል በሚል በአመልካች ስም ሳይለካ ቀርቷል በሚል የገለጸዉ አገላለጽ መሬቱን አመልካች ከመነሻዉ በሕገ-ወጥ መንገድ በመያዛቸዉ ምክንያት ነዉ ወይስ በወቅቱ በአካባቢዉ በነበረ ግጭት ጋር በተያያዘ ለአመልካች መሬቱ አይገባቸዉም በሚል ነዉ የሚለዉን በግልጽ የማያሳይ በመሆኑ ተገቢዉ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ሊደረግና ትክክለኛዉ ምክንያት ማረጋገጥ ይገባዉ ነበር፡፡ እንዲሁም ይዞታዉ በአመልካች የተያዘበት መንገድ ካለመረጋገጡም በተጨማሪ አመልካች በአካባቢዉ በተፈጠረ አለመረጋጋት አማራ ናቸዉ በሚል ምክንያት ተፈናቅለዉ ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር ጥቃት እንዳይደርስባቸዉ ያለፍላጎታቸዉ ይዞታዉን ለቀዉ በ2004 ዓ/ም ወደ ሌላ አካበባቢ ሲሄዱ ደግሞ ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት በመያዝ ከ2004ዓ/ም ጀምሮ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ቢረጋገጥም ተጠሪም መሬቱን በምን አግባብና በማን ፈቃጅነት እንደያዙ ማስረጃዎችን ከሚመለከተዉ አካል በማስቀረብና የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን በአግባቡ እንዳልተጣራ ተረድተናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት አስቀድመዉ ይዘዉ ሲጠቀሙ የቆዩት አመልካች ሲሆኑ መሬቱ ለሕዝብ ጥቅም ያስፈልጋል በሚል ወይም መሬቱን ባለመንከባከብ ጉዳት እንዲደርስበት አድርገዋል በሚል እንዲለቁ ተደርገዋል የሚል ክርክር አልቀረበም፡፡እንዲሁም አመልካች በ2004 ዓ/ም መሬቱን የለቀቁት በአካባቢዉ በተፈጠረ ግጭት ምክንያት ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር ጥቃት ይደርስብኛል በሚል ተፈናቅለዉ እንጂ በሰፈራ ወይም በፍላጎታቸዉ በሕግ ከተወሰነዉ ጊዜ በላይ አካባቢዉን ለቀዉ በመቆየታቸዉ ምክንያት ባለመሆኑ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በዉሳኔዉ ላይ እንደገለጸዉ በክልሉ አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀጽ 9/1 መሰረት በመሬት ሽግሽግ ምክንያት አመልካች ከያዙት መሬት እንዲለቁ የሚደረግበት አግባብ ባለመኖሩ ተጠሪ መሬቱን በሽግሽግ ያገኙት ነዉ ብለዉ ያሰሙት ክርክር አመልካች የያዙትን መሬት እንዲለቁ የሚያደርግ ምክንያት አይደለም፡፡

እንዲሁም አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን የያዘዉ አግባብ ባላቸዉ የፌዴራልም ሆነ የክልሉ ሕግጋት ላይ ከተደነገገዉ አግባብ ዉጭ ቢሆን እንኳን ግለሰቡ በዚህ አግባብ የያዘዉን መሬት በሕግ በተደነገገዉ ስርዓት አግባብ ባለዉ የመንግስት አካል እንዲለቅ ይደረጋል እንጂ መሬቱን ከሕግ አግባብ ዉጭ ይዟል በሚል ባለይዞታዉን አስለቅቆ ሌላ ግለሰብ መሬቱን በመያዝ ባለይዞታ የመሆንበት አግባብ በሕግ የተፈቀደ ተግባር አይደለም፡፡በዚህ መሰረት ግለሰቦች አንዱ የሌላዉን መሬት በማስለቀቅ የሚይዙ

ከሆነ የሕግ የበላይነት መርህ ተጥሶ በምትኩ በጉልበት መመራትን ስለሚተካ በሕግ የሚደገፍ አይደለም፡፡በመሆኑም አመልካች አከራካሪዉን መሬት በሕግ አግባብ ባይዙ እንኳን በሕግ በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት አግባብ ያለዉ አካል እንዲያስለቅቃቸዉ ይደረጋል እንጂ አመልካች በጸጥታ ችግር ምክንያት ተፈናቅለዉ መሬቱን በለቀቁበት ጊዜ ዉስጥ ተጠሪ መሬቱን በቀጥታ ይዘዉ አልለቅም ለማለት የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት አለቅም በማለት መከራከር የሚችሉት በሕግ አግባብ በሚመለከተዉ የመንግስት አካል አመልካች መሬቱን እንዲለቁ ተደርጎ መሬቱ በድልድል(በምሪት) ሲሰጣቸዉ ብቻ ነዉ፡፡

ከመሠረታዊዉ አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ ከማስረዳት ሸክም መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ተከራካሪ ወገን ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ተገቢዉንና ሕጉ በተለየ ሁኔታ የሚጠይቀዉ ማስረጃ ካለም በሕግ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት (የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከቷል)፡፡እንዲሁም የምንከተለዉ የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት ፍርድ ቤቶች(ዳኞች) የገለልተኛነት መርህን በጠበቀ መልኩ ክርክሮችን በማስረጃ በማንጠር አንጻራዊ እዉነታን ከመፈለግ አንጻር ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ የሚጠይቅ በመሆኑ በራሳቸዉ አነሳሽነት ወደ እዉነታዉ የሚያደርስ ማስረጃ በትእዛዝ አስቀርበዉ እዉነታዉን ማጣራት ይጠበቅባቸዋል (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 136/1፣249፣264 እና 345/1 ይመለከቷል፡፡)

ሲጠቃለል አመልካች አከራካሪዉን መሬት ከ1999ዓ/ም ጀምሮ እስከ 2004 ዓ/ም ድረስ የተለያዩ ተክሎችን በመትከልና ቤት ሰርተዉ ሲጠቀሙ ቆይተዉ በአካባቢዉ በተፈጠረ ግጭት ምክንያት ተፈናቅለዉ ለቀዉ መሄዳቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡እንዲሁም ተጠሪ ከ2004ዓ/ም ጀምሮ ይህንን መሬት ይዘዉ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ተረጋግጧል፡፡ሆኖም አመልካች መሬቱን በሕግ አግባብ የሚመለከተዉን የመንግስት አካል አስፈቅደዉ መያዝ አለመያዛቸዉ እንዲሁም ተጠሪ አከራካሪዉን መሬት ይዘዉ እየተገለገሉ የሚገኙት አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ተፈቅዶላቸዉ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የወረዳዉ እና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ሊለቁ ይገባል ብለዉ መወሰናቸዉ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ሊለቁ አይገባም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የሰጠዉ ዉሳኔ በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ፍሬ ነገር እንዲረጋገጥ ሳያደርጉ የደረሱበትን ድምዳሜ እንደሆነ ስለሚያሳይ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሆነ የሕግ አተገባበርና የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የጉራፈርዳ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11475 ላይ በቀን 18/10/2011ዓ/ም የሰጠዉን ዉሳኔ፣ የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 19556 ላይ በቀን 26/10/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ፣ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 07642 ላይ በቀን 30/12/2011ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 07877 ላይ በቀን 25/03/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽርዋል፡፡

2. የጉራፈርዳ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ አመልካች አከራከሪዉን መሬት በቀበሌ አስተዳደር ተመርተዉ መያዝ አለመያዛቸዉን፣ መሬቱ በአመልካች ስም ሳይለካ የቀረበትን ምክንያት፣ይህንን አመልካች አልምተዉ ሲጠቀሙ የነበረዉን መሬት በአካባቢዉ ተፈጥሮ በነበረ የጸጥታ ችግር ምክንያት ራሳቸዉንና ቤተሰባቸዉን ከጥቃት ለመከላከል ለቀዉ ከሄዱበት ሲመለሱ መሬቱን ተጠሪ ሊያዙ የቻሉት በምን አግባብ እንደሆነና አመልካች መሬቱን በሕግ አግባብ እንዲለቁ ተደርጎ በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ለተጠሪ የተላለፈ መሆን አለመሆኑን ከቀበሌ አስተዳደርና ከሌላ ከሚመለከተዉ አካል ማስረጃ አስቀርቦ አጣርቶና የቀረቡለትን ማስረጃዎች መዝኖ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

## ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠ/መ/ቁጥር 187484

የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ በየነ ከበደ

ተጠሪዎች፡- 1. ገረመዉ አይናለም

2. አይናለም አበጀ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በኪራይ ዉል ተሰጠ የተባለ የገጠር እርሻ መሬት ይዞታ አስለቅቆ ለመረከብ የቀረበ ክስ በተመለከተ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በአማራ ክልል በጃዊ ወረዳ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ በወረዳዉ በዲር ማርያም ቀበሌ ክልል ዉስጥ የሚገኘዉን በክሱ አዋሳኞቹ የተጠቀሰዉን 6 ቃዳ የገጠር እርሻ መሬቴን ለ5 ዓመታት ለብር 500.00 ለ1ኛ ተጠሪ አከራይቻቸዉ የኪራይ ዘመኑ 2007ዓ/ም ቢያልቅም ተጠሪዎች መሬቴን በጉልበት በመያዝ ኪራይም ባለመክፈል ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች መሬቴን ለቀዉ እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለክሱ ባቀረቡት መልስ ለክሱ መነሻ የሆነዉን መሬት ለ10 ዓመት ይገፔ እየተጠቀምኩ ስለምገኝ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ፍሬ ነገሩን በተመለከተም መሬቱን የያዝኩት አመልካች የእኔና የባለቤቴ(የሚስቴ) የጡት አባት ስለሆኑ በ1990 ዓ/ም አካባቢዉን ለቀዉ ሲሄዱ መሬቱን ያዘዉ ብለዉ በስጦታ ሰጥተዉኛል፡፡በ1996ዓ/ም የመሬት ምዝገባ ሲደረግ ይህ መሬት በእኔ ስም እንዲመዘገብ በኮሚቴዎች ፊት ቀርበዉ ፈርመዋል፡፡አመልካች ክሱን ያቀረቡት የስጦታ ዉሉን በመጣስ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡2ኛ ተጠሪ በተናጠል በሰጡት መልስ መሬቱን የያዝኩት ከ1ኛ ተጠሪ በመከራየት በመሆኑ አመልካች ሊጠይቁኝ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 0875 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎች መርምሮ በቀን 07/10/2010 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 የገጠር መሬት ክርክር ጋር በተያያዘ የሚነሳ ይርጋ ቀሪ ስላደረገዉ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ አድርጓል።ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት የአመልካች ሕጋዊ ይዞታ መሆኑን 1ኛ ተጠሪ አልካዱም። መሬት ሊገኝ የሚችለዉ በአዋጁ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 11 መሰረት በሽግሽግ፣ በስጦታና በዉርስ እንደሆነ በተደነገገዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ መሬቱን በስጦታ አግኝቻለሁ በማለት የተከራከሩ ቢሆንም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በስጦታ የተሰጣቸዉ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 16/7 መሰረት በጽሁፍ የተደረገና በወረዳዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት የተመዘገበ የስጦታ ዉል በማስረጃነት አላቀረቡም።በተሰጣቸዉ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የአከራካሪዉ መሬት ባለይዞታ ተደርገዉ የሚቆጠሩት በሕግ አግባብ የወጣ ማስረጃ ሲሆን ነዉ። መሬቱ በ1989ዓ/ም በሽግሽግ ለአመልካች የተሰጠ መሆኑ በግራ ቀኙ ምስክሮችና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል።2ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከ1ኛ ተጠሪ በኪራይ መያዛቸዉን አምነዉ ተከራክረዋል።ስለሆነም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን 6 ቃዳ መሬት ለአመልካች ለቀዉ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል።

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 09-00202 ላይ በቀን 14/10/2010 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል።

በመቀጠል ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-79166 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 20/02/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ መሬት በወረራ ወይም በማንኛዉም ሕገ-ወጥ መንገድ ይዞ የሚገኝ ሰዉ የይርጋ ጊዜ ገደብን በይርጋ መቃወሚያነት ሊያነሳ የማይችል መሆኑ በተሻሻለዉ የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/209 አንቀጽ 55 ላይ ተደንግጓል።በተያዘዉ ጉዳይ የወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪዎችን የይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ ያደረገዉ አዋጁ የይርጋ መቃወሚያ ቀሪ አድርጓል በሚል ቢሆንም ድንጋጌዉ የሚያሳየዉ በሕገ-ወጥ መንገድ መሬት የያዘን ሰዉ እንጅ በሕጋዊ ግንኙነት መሬት የያዘን ሰዉ እንደማይመለከት በመሆኑ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የይርጋ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕጉን መንፈስ የተከተለ አይደለም።በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ መሬቱን ከ10 ዓመት በላይ ይዘዉ እየተጠቀሙበት መሆኑ ያልተካደና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ።አመልካች በክሳቸዉ መሬቱን ከ2007ዓ/ም ጀምሮ በኪራይ ከዚያ ወዲህ ደግሞ በሕገ-ወጥ መንገድ 1ኛ ተጠሪ ይዘዋል ቢሉም ባቀረቧቸዉ ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ በኪራይ ስለመያዛቸዉ አላስረዱም። በ1ኛ ተጠሪ በኩል የተደመጡት 2ኛ እና 3ኛ መከላከያ ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ መሬቱን የያዙት አመልካች ሰጥተዋቸዉ ስለመሆኑ ከመመስከራቸዉም በተጨማሪ የአመልካች 2ኛ ምስክርም በስጦታ መያዛቸዉን እንደሰሙ ከመገለጹ አኳያ ሲታይ የተሻለ ስላስረዱ የአመልካች ክስ

በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና በሰ/መ/ቁጥር 93013 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በቀን 08/04/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰዉ የአመልካች ክርክር በአግባቡ ሳይሰማና 1ኛ ተጠሪ መሬቱን የያዙት በኪራይ ነዉ ወይስ በስጦታ የሚለዉ ሳይጣራ ነዉ፡፡ይልቁንም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ሕጋዊ ባለይዞታ አመልካች እንደሆንኩ፣ 1ኛ ተጠሪ መሬቱን በስጦታ አለመያዛቸዉን እና 1ኛ ተጠሪ መሬቱን እስከ 2007ዓ/ም ድረስ በኪራይ እንደያዙና ዉሉም እስከ 2007ዓ/ም ድረስ እንዳልተቋረጠ አመልካች ባቀረብኩት ማስረጃዎችና በስር ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ በተደረጉ ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ነዉ የያዙት ክሱም በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተወሰነበትን አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪዎች በቀን 09/02/2009ዓ/ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የመልሳቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የአመልካች የነበረ ቢሆንም መሬቱን 1ኛ ተጠሪ የያዝኩት በኪራይ ሳይሆን አመልካች የጡት አባት በመሆን በ1991 ዓ/ም በአገራችን ወግና ባህል መሰረት በስጦታ ሰጥተዉኝ ነዉ፡፡ኪራይም ከፍዬ አላዉቅም፡፡ከዚህ በኋላም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በ1996ዓ/ም ተሰጥቶኛል፡፡የስጦታ ዉሉ ተመዘገበም አልተመዘገበ መሬቱ ለ21 ዓመታት በእጄ የሚገኝ ይዞታ መሆኑ ስለተረጋገጠ የአመልካች ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 16/02/2014ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጡ ዉሳኔዎች በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት የገጠር እርሻ መሬታቸዉን ለ1ኛ ተጠሪ በማከራየት የፈጸምኩት ኪራይ ዉል ዘመን በ2007 ዓ/ም ቢጠናቀቅም የኪራይ ገንዘብ ሳይከፍሉ ተጠሪዎች በጉልበት የእርሻ መሬቴን በመያዝ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቅ ነዉ፡፡ይህም የክሱ ስረ ነገር የኪራይ ዉል እንደሆነና የኪራይ ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ

ተጠሪዎች መሬቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አይደሉም በሚል በክሱ የተገለፀዉ ፍሬ ነገር ደግሞ የክሱ ምክንያት ሆኖ እንደቀረበ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ለዚህ ክስ 1ኛ ተጠሪ መሬቱን በስጦታ እንጂ በኪራይ አለመያዛቸዉን የሚገልጽ ክርክር ከማቅረባቸዉም በተጨማሪ መሬቱ ለረጅም ጊዜ በእጃቸዉ መቆየቱን ገልጸዉ የአመልካች ክስ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተቃዉመዋል፡፡

እንደሚታወቀዉ በልዩ ሕግ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር የሚመራዉ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2 እና 3) ፣80 እና 222(1/ረ እና ሸ) ላይ እንደተመለከተዉ በክስ አቤቱታ ላይ ለክሱ መሰረት የሆነዉ ነገር ፣ የክሱ ምክንያት ፣ተከሳሹ በክሱ ተጠሪ የሆነበት ምክንያት እና ለክሱ ምክንያት የሆኑ ነገሮች የተፈጠሩበት ጊዜ…እንዲገለጽ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ይጠይቃል፡፡የክስ አቤቱታ በዚህ አግባብ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ አስፈላጊ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ ተከሳሽ የሆነዉ ወገን ለክሱ መልሱን አዘጋጅቶ ሲያቀርብ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል የመቃወም ፍላጎት ካለዉ ተገቢዉን የይርጋ መቃወሚያ በማቅረብ መከራከር እንዲችል እና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማቅረብ ክሱን የመከላከል መብቱን በተሟላ መልኩ መጠቀም እንዲችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነዉ(የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 222(1/ረ እና ሸ) እና 234(1/ሐ) ጣምራ ንባብ ይመለከቷል)፡፡ከዚህም ሥነ ሥርዓት የምንረዳዉ የይርጋ መቃወሚያ የሚቀርበዉ ከሳሽ በክሱ ላይ የገለጸዉን ሥረ ነገርና የክስ ምክንያት መሰረት በማድረግ እንደሆነ ነዉ፡፡

በመሰረቱ ይርጋ ከሚያስከትለዉ ዉጤት አንጻር ሁለት ገጽታዎች አሉት፡፡ይኸዉም መብት የሚሰጥ(የሚያስገኝ) ይርጋ (acquisitive prescription) እና መብት የሚያሳጣ ይርጋ(extinctive prescription) በሚል የሚታወቁ ናቸዉ፡፡ ኋለኛዉ አይነት ይርጋ ባለመብቱ (ባለገንዘቡ) በሕግ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ መብቱን(ጥቅሙን ወይም ገንዘቡን) ሳይጠይቅ ቆይቶ ጊዜዉ ካለፈበት መብቱን መጠየቅ እንዳይችል የሚያደርግ (right killer limitation) ነዉ፡፡ይህ ኋለኛዉ አይነት ይርጋ መብት ለማስከበር የሚቀርብን ክስ ቀሪ የሚያደርግ(limitation of action)ጭምር ነዉ፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ክሱ በይርጋ ይታገዳል ብሎ መቃወሚያ ሲያቀርብ እየተቃወመ ያለዉ ይህንን የክስ ምክንያት መሰረት በማድረግ ክስ ለማቀርብ የሚቻልበት ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ ክሱ ስላልቀረበ በዚህ የክስ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብቱ ቀሪ ሆኗል በሚል ነዉ፡፡በመሆኑም የይርጋ መቃወሚያ የሚያቀርበዉ ተከራካሪ የክሱን ምክንያት መሰረት አድርጎ መቃወሚያ ማቅረብ አለበት እንዳልነዉ ሁሉ በክርክሩ ላይ ዉሳኔ የሚሰጠዉም ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይም አልሆነም የሚለዉን ጭብጥ ይዞ ሲወስን መሰረት ማድረግ ያለበት የክሱን ስረ ነገር እና ምክንያት ሊሆን ይገባል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የክሱ ሥረ ነገር የገጠር እርሻ መሬት ላይ ተደረገ የተባለ የኪራይ ዉል ሲሆን የክሱ ምክንያት ደግሞ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመሆን የኪራይ ዘመኑ በ2007ዓ/ም ካለቀ በኂላ መሬቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆኑም ተብሎ የተገለጸዉ ምክንያት ነዉ፡፡1ኛ ተጠሪ ደግሞ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ የሚል መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ከአመልካች ጋር የኪራይ ዉል ግንኙነት የለኝም በማለት ክደዋል፡፡እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ መሬቱን መልቀቅ የነበረብኝ በ2007ዓ/ም ሳይሆን ክሱ ከመቅረቡ ከ10 ዓመት በፊት ጀምሮ ነዉ በማለት በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡እንዲህ አይነት ክርክር ሲቀርብ ከላይ እንደገለጽነዉ የክሱን ምክንያት መሰረት በማድረግ ከ2007ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለዉን ጊዜ በመቁጠር እና ለክሱ ስረ ነገር አግባብነት ያለዉን የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በመለየት መወሰን ይገባል፡፡

የክርክሩ ስረ ነገር በገጠር የእርሻ መሬት ላይ ተደረገ የተባለ የኪራይ ዉል የሚመለከት በመሆኑ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት አለዉ፡፡የኪራይ ዉሉ ጊዜ ተጠናቀቀ በተባለበት በ2007ዓ/ም በክልሉ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 18 ላይ የገጠር መሬት በኪራይ ስለሚተላለፍበት አግባብ የተደነገገ ቢሆንም ከኪራይ ዉል ጋር የተያያዘ ክስ የሚቀርብበትን የይርጋ ጊዜ በተመለከተ በአዋጁ አልተደነገገም፡፡ክሱ በቀረበበት በቀን 10/08/2010 ዓ/ም ተፈጻሚ ሲሆን በነበረዉ በተሻሻለዉ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 በተመሳሳይ ከኪራይ ዉል ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ክስ ተፈጻሚ የሚደረገዉን የይርጋ ጊዜ በተመለከተ አልደነገገም፡፡ይልቁንም በዚህ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 54 ላይ አዋጁ ባልሸፈነባቸዉ ጉዳዮች ላይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚነት እንደሚኖረዉ ደንግጓል፡፡ በእነዚህ ሕግጋት የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ ስለሌለ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለዉ ግንኙነት ዉልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተፈጻሚነት የሚኖረዉ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር የተደነገገዉ የ10 ዓመት ጊዜ ነዉ፡፡አመልካች የኪራይ ዉሉ ጊዜ የተጠናቀቀዉ በ2007ዓ/ም ነዉ በማለት በክሳቸዉ ገልጸዉ ክሳቸዉን ያቀረቡት ደግሞ በቀን 10/08/2010ዓ/ም በመሆኑ ክሱ የቀረበዉ የ10 ዓመት ይርጋ ጊዜ ሳያልፍ ነዉ፡፡

ስለሆነም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ የኪራይ ዉልን መሠረት ያደረገ ሆኖ እያለ ከዚህ ዉጭ በሆነ ሥረ ነገርና የክስ ምክንያት ለሚቀርብ ክስ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 ስር የተደነገገዉን ይርጋ መሰረት በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ፡፡እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ እና ለ) ስር እንደተመለከተዉ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሕግ በዝርዝር በሚወሰነዉ አግባብ መርምረዉ እንዲያርሙ እንጂ ማስረጃ መርምረዉና መዝነዉ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር እንዲያረጋግጡ ሥልጣን አልተሰጣቸዉም፡፡ከዚህ አንጻር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ ስንመለከት ችሎቱ በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት የያዙት በኪራይ ነዉ ወይስ በስጦታ ? የሚል ጭብጥ ተይዞ ከዚህ አንጻር ማስረጃ

ተመርምሮና ተመዝኖ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር በሌለበት፤ በስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ምስክሮች ቀርበዉ የመሰከሩትን ቃል መርምሮና መዝኖ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት 1ኛ ተጠሪ ሊይዙ የቻሉት በኪራይ ሳይሆን በስጦታ መሆኑንና ከ10 ዓመት በላይ 1ኛ ተጠሪ ይዘዉ መቆየታቸዉን በተሻለ ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ አስረድተዋል የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የአመልካች ክስ የማቅረብ መብት በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 55 እና በሰ/መ/ቁጥር 93013 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት በ10 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በሚል ወስኗል፡፡በዚህ መልኩ የሰጠዉ ዉሳኔ በሕገ መንግስቱ ከተሰጠዉ ሥልጣን ዉጭ ማስረጃ መርምሮና መዝኖ መወሰኑን የሚያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪ ከላይ እንደተመለከተዉ የይርጋ መቃወሚያ ሊወሰን የሚገባዉ በክሱ ስረ ነገርና ምክንያት ላይ ተመስርቶ ነዉ በሚል የተመለከትነዉን የክርክር አመራር ሂደት የሚቃረንና ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ሕግና የሰበር ሰሚ ችሎት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ አልታገደም ብለናል፡፡

በተጨማሪም የሥነ ሥርዓት ሕጉም ዓላማ ክርክሮች ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ እና በዉስን የሰዉና የገንዘብ ሀብት ተገቢዉን እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ነዉ፡፡ ይህንን ዓለማ ማሳካት ይችል ዘንድ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት የክርክሩን ሥረ ነገርና የክስ ምክንያት እንዲሁም በተከራካሪዎች የቀረበዉን ክርክር መሰረት አድርጎ ግራ ቀኙ ተለያይተዉ የተከራከሩበትን የሕግ እና/ወይም የፍሬ ነገር ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን የመምራት፣በተጠየቀዉ ዳኝነት እና በአከራካሪዉ ጭብጥ ላይ ተገድቦ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡ከዚህ ዉጭ በሆነ አኳኋን ክርክሩን የሚመራ ከሆነ ክርክሩ ከጊዜ እና ከወጪ አንፃር ዉጤታማ እንዳይሆን በማድረግ ፍትህ የሚያጓድል ድምዳሜ ላይ ይደርሳል፡፡ይህም የሥነ ሥርዓት ሕጉ የቆመለት ዓላማ እንዳይሳካ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የስረ ነገር መብት(substantive right) ያሳጣል እንዲሁም ዜጎች በፍርድ ቤቶች ላይ የሚኖራቸዉን እምነት ይሸረሽራል፡፡ስለሆነም በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን የክርክር አመራር ሂደት ተከትሎ ለክርክሮች ተገቢዉን እልባት መስጠት ይገባል፡፡ከዚህ አንጻር በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ከሥረ ነገር አኳያ በስር ፍርድ ቤት ክርክሩ የተመራበትን አግባብ መርምረናል፡፡የወረዳዉ ፍርድ ቤት ከፍሬ ነገር አንጻር የመሰረተዉና ዉሳኔ የሰጠበት ጭብጥ *ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ሕጋዊ ይዞታነት የአመልካች ነዉ ወይስ የ1ኛ ተጠሪ?* የሚል ነዉ፡፡ነገር ግን ግራ ቀኙ ተካክደዉ የተከራከሩበትና ዉሳኔ የሚሹ ጭብጦች ደግሞ *1ኛ ተጠሪ መሬቱን የያዙት አመልካች አከራይተዋቸዉ ነዉ ወይስ በስጦታ ሰጥተዋቸዉ ነዉ?የያዙት በኪራይ ዉል ነዉ የሚባል ከሆነ መሬቱን ሊለቁ ይገባል ወይስ አይገባም?* የሚሉ ናቸዉ፡፡

ስለሆነም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ለአመልካች እንዲለቁ የወሰነዉ ተገቢዉን ጭብጥ ሳይመሰርት እና ከትክክለኛ ጭብጥ አኳያ ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን ባላረጋገጠበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የጃዊ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0875 ላይ በቀን 07/10/2010 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፣የአዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09-00202 ላይ በቀን 14/10/2010 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-79166 ላይ በቀን 20/02/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡
3. የጃዊ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ *1ኛ ተጠሪ መሬቱን የያዙት አመልካች አከራይተዋቸዉ ነዉ ወይስ በስጦታ ሰጥተዋቸዉ ነዉ?የያዙት በኪራይ ዉል ነዉ የሚባል ከሆነ መሬቱን ሊለቁ ይገባል ወይስ አይገባም?* የሚሉ ጭብጦች ላይ ዉሳኔ ለመስጠት አስቀድሞ የተሰማዉ ክርክርና ማስረጃ በቂ ካልሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ግራ ቀኙን በማከራከርና ምስክሮችን ሰምቶና አስፈላጊ የሚሆኑ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መርምሮና መዝኖ ሕግን መሰረት ያደረገ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልስንለታል፡፡
4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

## <u>ትዕዛዝ</u>

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ 210997

ነሐሴ 10 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

ተጠሪዎች፡- 1. እስክንድር ነጋ

2. ስንታየሁ ቸኮል

3. ቀለብ ስዩም

4. አስካለ ደምሴ

5. ጌትነት በቀለ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 199376 ግንቦት 04 ቀን 2013 ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ላይ ተጋረጡ የሚላቸውን ስጋቶች በምክንያት አስደግፎ እንዲያቀርብ በማድረግ መርምሮ እንዲወስን ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ጉዳዩ የተመለሰለት የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በመ.ቁ 260175 ሠኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ምስክሮች በግልጽ ችሎት እንዲሰሙ ሲል የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 210614 የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪዎች ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት የቆጠራቸው ምስክሮች ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 6/1/ለ መሠረት ጥበቃ የተደረገላቸው መሆኑን በመግለጽ አስራ ስድስቱ ምስክሮች በአዋጁ አንቀጽ 4/1/ቀ መሠረት ምስክርነታቸው በዝግ ችሎት እንዲሰማ፤ አምስቱ ምስክሮች ደግሞ በአዋጁ

አንቀጽ 4/1/በ መሠረት በአካል ሳይታዩ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲመሰክሩ ይታዘዝለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ የምስክሮች ማንነት ቀድሞ የታወቀ በመሆኑ የጥበቃውን አስፈላጊነት ዋጋ ያሳጣዋል፤ በሌላ በኩል ዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በተጨባጭ ሊደርስባቸው የሚችል ከባድ አደጋ/ስጋት እንዳለ በበቂ ሁኔታ ያላረጋገጠ በመሆኑ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አደርጎታል፡፡

አመልካች ይህን ብይን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአመልካች አቤቱታ በጊዜያዊ ትዕዛዝ ላይ የቀረበ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካች በመቀጠል ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ በጊዜያዊ ትዕዛዘ ላይ የቀረበ ሳይሆን የመጨረሻ ውጤት ባለው ብይን ላይ የቀረበ እና ይግባኝ የሚባልበት በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ሲል ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የምስክሮችን ጥበቃ በተመለከተ ስልጣኑ የዓቃቤ ሕግ ብቻ ነው፤ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን መርመረው መወሰን አይችሉም በማለት በዓቃቤ ሕግ የቀረበውን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ዓቃቤ ሕግ በዝግ ችሎት እና ከመጋረጃ ጀርባ ምስክሮች ሊሰሙ ይገባል የሚልበትንና ምስክሮች ላይ ተጋረጡ የሚላቸውን ስጋቶች በምክንያት አስደግፎ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ መርምሮ ተገቢውን እንዲወስን ሲል ጉዳዩን ለስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት አመልካች ምክንያቶቹን በዝርዝር እንዲያቀርብ በሰጠው ትዕዛዘ አመልካች በቀን 19/09/2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተቋም ምስክሮች ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ የወሰነው ስለምስክሮች እና ሊደርስባቸው ስለሚችል ጥቃት ዝርዝር የስጋት ትንተና ከሰራ በኋላ ነው፤ ከጥበቃ ስምምነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በሕግ በጥብቅ ሚስጥርነት ተፈርጀው በጥብቅ የሚጠበቁ ናቸው፤ ፍርድ ቤቱ በአዋጁ አንቀጽ 23 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተወሰኑ የጥበቃ ዓይነቶች በአግባቡ መደረጉን የማረጋገጥ ሃላፊነቱን ሲወጣ እያንዳንዱን የምስክር ጥበቃ ውሳኔ መነሻ የስጋት ትንታኔ ከዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤቱ አመራሮች እጅ እንዲቀርብ በማዘዝ አልያም ተከራካሪ ወገኖች

ባልተገኘንበት እና የሚቀርቡ ምስክሮች እነማን እንደሆኑ አንዳች ቦታ ሆኖ መከታተል በማይቻልበት ስፍራ አስቀርቦ በማድመጥ ለመረዳት ወይም ፍርድ ቤቱ ማናቸውንም አግባብነት ያላቸውን ከችሎት ውጭ ያሉ ማጣሪያዎችን እንዲያደርግ እንጠይቃለን፤ በምስክሮች ወይም በቤተሰቦቻቸው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጥቃት ስጋት የሚያመላክቱ ሁኔታዎችን በስጋት ትንተናው መሠረት ለችሎቱ በእያንዳንዱ ምስክር ደረጃ የሚቀርብ ቢሆን የምስክሮቹን ማንነት እንዲታወቅ የሚያደርግ ውጤት ይኖረዋል፤ ጥበቃ ተደርጎላቸው ቃላቸውን እንዲሰጡ የምንጠይቃቸው ምስክሮች በምንም ሁኔታ ፍርድ ቤት በግልጽ ችሎት ቀርበው ለመመስከር እንደማይችሉ ማረጋገጫ ሰጥተውናል፤ ምስክሮቹ በግልጽ ችሎት ቀርበው ለመሰማት ፍቃደኛ ያልሆኑት ማንነታቸው ቢታወቅ ከተጠሪዎች ደጋፊዎች የሚደርስባቸውን የበቀል እርምጃ በመፍራት ነው፤ ተጠሪዎች የፖለቲካ ርዕዮትን በሀይል ለማሳካት ሰዎችን ለመግደል እና ሰዎች ላይ ጥቃት ለማድረስ ደጋፊዎችን መልምለው ጥቃት ያደረሱ እና ጥቃት ለማድረስ ዝግጅት ላይ የነበሩ እንደሆኑ ምስክሮቻችን በቅርበት ከማወቃቸው በተጨማሪ ለመርማሪ ፖሊስ ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን በመስጠት የሕግ ምስክር ሆነዋል፤ ተጠሪዎች ለፖለቲካ ዓላማ መሳካት ባለስልጣኖችን ለመግደል ሰዎችን እንደሚያሰለጥኑ በክሳችን ተመልክቷል፤ ተጠሪዎች አዘጋጅተዋል ካልናቸው ምልምል እርምጃ ወሳጆች መሀከል የተወሰኑትን መቆጣጠር ቢቻልም ቀሪዎቹ በማሕበረሰብ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙ ናቸው፤ በጥበቃ ስር የሚንቀሳቀስ የመንግስት ባለስልጣንን ለመግደል የሚዘጋጅ ሀይል መንገዱ ላይ እንቅፋት የሚሆን ማናቸውንም ሰው በማሕበረሰብ ውስጥ በቀሩና ተጠሪዎች ባደራጅዋቸው ሰዎች ወይም ሌሎች ዓላማውን በሚደግፉ ሀይሎች ምስክሮች ላይ ጥቃት ሊያደርሱ ይችላሉ የሚል ግምት መውሰድ ተገቢ ነው፤ በዋነኝነት ሊታወቅ የሚገባው ምስክሮች ያለባቸውን ስጋት በሌላ በማንኛውም የጥበቃ ዓይነት ማስወገድ የሚቻል አለመሆኑ ነው፤ በዚሁ መሠረት፡-

ቁጠራቸው አምስት ለሆኑት ምስክሮች በአዋጁ አንቀጽ 4/1/በ መሠረት በአካል ሳይታዩ ከመጋረጃ ጀርባ በመሆን የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ የምንጠይቀው ምስክሮቻችን እና ቤተሰቦቻቸው ከታወቁ በቀላሉ በሕይወታቸው ላይ ጭምር አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ከባድ ስጋት ያደረባቸው በመሆኑ፤ ምስክርነት ቃላቸውን የሰጡባቸው ተጠሪዎች ብዛት ያላቸው ደጋፊዎች እና ተከታዮች ያሏቸው ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ቀን በተደረገላቸው ጥሪ እና ቅስቀሳ በመነሳሳት ቁጥራቸው 14 የሆኑ ሰዎች ሕልፈት እና በሚልዮኖች የሚደርስ ንብረት ውድመት እንዲደርስ ያደረጉ መሆናቸውን ጠቅሰው ቀጥታ በእነርሱ እና በደጋፊዎቻቸው ፊት ብንመሰክር ሕይወታችን አደጋ ላይ ይወድቃል የሚል ስጋት ያለባቸው በመሆኑ፤ ከቀጥታ አካላዊ ጥቃት እና ዛቻ በዘለለ የተጠሪዎች ደጋፊዎች የተለያዩ ሰዎችን ስም በማሕበራዊ ሚድያ በመዘርዘር በተጠሪዎች ላይ የመሰከሩ ናቸው በማለት በፌስቡክ የግለሰቦችን ስም ሲለጥፉ የነበረና በዚህ ጽሁፍ ስም ከመዘርዘሩ በተጨማሪ ስማቸው የተዘረዘረ ግለሰቦች የዓቃቤ ሕግ ምስክር ናቸው በሚል ማሕበረሰቡ እንዲያገላቸው እና ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሲዛት እና ቅስቀሳ ሲደረግ የነበረ መሆኑ፤ በሽብር ክስ ላይ ምስክር የሆነ ግለሰብ ያለምንም ጥፋት እንዲገደል

ሰው ተመድቦበት የነበረ በመሆኑ፣ እንዲህ ዓይነት ምደባ በርካታ ሰው ላይ የተደረገ በመሆኑ በተከሳሾች እና በደጋፊዎቻቸው ፊት ብንመሰክር ድጋሚ ለሞት መቅረብ ይሆናል በማለት ስጋታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡

ቁጥራቸው 16 የሆኑት የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በአዋጁ አንቀጽ 4/1/ቀ መሠረት በዝግ ችሎት እንዲሰሙልን የምንጠይቀው ከዚህ ቀደም በቀዳሚ ምርመራ ወቅት በተጠሪዎች ተከታዮች እና ደጋፊዎች አማካኝነት ምስክር ናቸው በሚል የጠረጠሯቸውን ግለሰቦች ላይ ማስፈራሪያ ዛቻ የተሰነዘረባቸው በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በአንድ ምስክር ላይ ሽጉጥ በመተኮስ የመግደል ሙከራ የተፈጸመበት በመሆኑ፣ ምስክሮቹ በግልጽ ችሎት መመስከር ለጥቃት የሚዳርጋቸው መሆኑን በተደጋጋሚ በመግለጻቸው ነው፣ ስለሆነም ቁጥራቸው 5 የሆኑት ምስክሮች በአካል ሳይታዩ ከመጋረጃ ጀርባ በመሆን የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ፣ ቁጥራቸው 16 የሆኑት ምስክሮች ደግሞ በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ትዕዛዝ እንዲሰጥልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት አስተያየት ዓቃቤ ሕግ ግን ሰራሁት ባለው የስጋት ትንተና ላይ በምስክሮች ላይ ብቻ ሊደርስ ይችላል የሚለውን አደጋ ከመተንተን በቀር በተጠሪዎች መብት ላይ የሚያስከትለውን የመብት ጥሰት ታሳቢ አላደረገም፣ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ እንዲመሰክሩ ቢደረግ ተጠሪዎች መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ የቀረበባቸውን ክስ የመከላከል መብታቸውን ያጣብባል፣ ከጥበቃ ተጠቃሚ ያልቀረበን ስጋት ዓቃቤ ሕግ ትንተና እንዲሰራበት አያደርግም፣ ዓቃቤ ሕግ በምስክሮች ላይ ደርሷል የሚለውን ስጋት በተጨባጭ ሁኔታ ያላረጋገጠ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ዓቃቤ ሕግ ምስክሮቼ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው ይሰሙልኝ ሲል ላቀረበው ጥያቄ በቂ ምክንያት ቀርቧል? ወይስ አልቀረበም? በዝግ ችሎት ይሰሙልኝ የሚላቸው 16 ምስክሮች በተመለከተ ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው ምክንያት ከዚህ ቀደም ማንነታቸው ታውቆ ዛቻና ማስፈራራት የደረሰባቸው ምስክሮች በዝግ ችሎት ቀርበው እንዲሰሙ ቢደረግ በዓቃቤ ህግ በኩል የሚነሳውን ስጋት ይቀርፋል? ወይስ አይቀርፍም? የሚሉትን ጭብጦችን በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 3/1 የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ወይም ያለጠቋሚው ምስክርነት ወይም ጥቆማው በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ ወይም ሊደረስበት የማይችል ሲሆን እና በምስክሩ፣ በጠቋሚው ወይም በቤተሰቡ ሕይወት፣ አካላዊ ደሕንነት፣ ነጻነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ሲታመን ነው በማለት ይደነግጋል፣ በዚህ አንቀጽ "ከባድ አደጋ" በሚል የተገለጸው ሀረግ በከፍተኛ ጥንቃቄና የተከሳሾችን መብቶች ባማከለ እና በማያጣብብ መልኩ መተርጎም አለበት፣ ዓቃቤ ሕግ ተጠሪዎች የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች በመሆናቸው እና ብዙ ደጋፊዎች ያላቸው በመሆኑ በምስክሮች እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ በማለት የሰጠው ምክንያት መላምትና ይህንኑ ምስክሮቹ ቀርበው ለፍርድ ቤት እንዲያስረዱ ከመጠየቁ በቀር የተጠሪዎችን እና የደጋፊዎቻቸውን የቀደመ

የሕይወት ታሪክና ባሕርይ የወንጀል አደገኝነት በተመሳሳይ ለመረዳት የሚያስችል አይደለም፤ ከዚሁ በተቃራኒ ተጠሪዎችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው ከዚህ ቀደም ባለው የፍርድ ቤት ውሎም ሆነ ጊዜያት ምንም ዓይነት የፍርድ ሂደቱን የሚያውክ ተግባር አለማሳየታቸው የወንጀል አደገኝነታቸውን የሚስረዳ አይደለም፤ ተጠሪዎች የፖለቲካ አመራር መሆናቸውና ደጋፊዎቻቸውም የነዚሁ ግለሰቦች ደጋፊ መሆናቸውም በአደገኝነት የሚያስፈርጅ አይደለም፤ በክሱ የተዘረዘረው የወንጀል ተግባር በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ክሱን ግምት ማድረግ የተጠሪዎችን ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ወደ ጎን የሚያደርግ ነው፤ በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ከተጠየቀው 16 ምስክሮች ውስጥ አንድ ምስክር በሽብር የመግደል ሙከራ የተደረገበት እና የተጠሪዎች ደጋፊዎች በማሕበራዊ ሚዲያ ምስክሮች ናቸው ያሉትን ሰዎች ስም ሲያጠፉ እንደነበር በዓቃቤ ሕግ መገለጹ ምስክሮች በተጠሪዎች ደጋፊዎች መለየታቸውን የሚያስረዳ በመሆኑ ምስክሮች በዝግ ችሎት የሚሰሙበትን ዓላማ ያሳጣዋል፤ ተጠሪዎች የፖለቲካ አመራር መሆናቸው እና ብዙ ደጋፊዎች አላቸው መባሉ ብቻውን ዓቃቤ ሕግ ለሚያቀርበው ስጋት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፤ ዓቃቤ ሕግ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር ከተዘረዘሩ የጥበቃ ዓይነቶች ውስጥ የጥበቃ ዓይነቱን ሲወስን የተጠሪዎችን ሕገ መንግስታዊ መብት ሊጎዳ በማይችል መልኩ መሆን እንዳለበት የሚደነግገውን የአዋጁን አንቀጽ 5/3 ከግምት ያላስገባ እና ከመጋረጃ ጀርባ እና ዝግ ችሎት ምስክር ይሰሙልኝ በማለት ያቀረበው ምክንያት በአዋጁ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 3/ ሀ ስር የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዮች ለስር ፍርድ ቤት እንዲመለሱ ከሚደረግበት ሥርዓት ውጪ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ አግባብ አይደለም፤ የምስክሮችን ጥበቃ በሚመለከት ዓቃቤ ሕግ በምክንያት አስደግፎ ፍርድ ቤት አቅርቦ ማጸደቅ የሚጠበቅበት አካለ መጠን ካላደረሰ ልጅ ጋር የተደረገ ልዩ የጥበቃ ስምምነት ብቻ ነው፤ ከምስክሮች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 7፤ 8 እና 23/1 መገንዘብ እንደሚቻለው ለፍርድ ቤት የተሰጠው ስልጣን በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ለምስክሮች የተደረገን ጥበቃ የመፍቀድ እና የመከልከል ሳይሆን ዓቃቤ ሕግ አምኖበት ጥበቃ ላደረገላቸው ምስክሮች ጥበቃው መፈጸሙን ማረጋገጥ ነው፤ ለፍርድ ቤት ማመልከቱም ያስፈለገበት ምክንያት በአዋጁ አንቀጽ 4/1 (ተ) እስከ (ሰ) እና (ዘ) ስር የተዘረዘሩት ጥበቃዎች በባሕርያቸው ከክርክር ሂደቱ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ነው፤ በዘርፉ የዳበረው ዓለም አቀፋዊ ልምድም የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ የሚወሰደው በአስፈጻሚው መሆኑን እና ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ በምስክሮች ላይ የተጋረጠውን ስጋት በዝርዝር ማቅረብ የምስክሩን ማንነት የመግለጽ ያህል ነው፤ አመልካች ተከራካሪ ወገኖች በሌሉበት ምስክሮችን ብቻ አስቀርቦ ፍርድ ቤቱ በራሱ መንገድ እንዲያረጋግጥ የጠየቀ ቢሆንም ጥያቄው ተቀባይነት አላገኘም፤ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው በሕብረተሰቡ

ላይ ስጋት በሚፈጥሩ ከባድ ወንጀሎች ላይ ነው፤ ተጠሪዎችም ሆነ ደጋፊዎቻቸው በችሎት የሚያሳዩት ባሕርይ መልካም ነው የሚለው ምክንያት ነገሩን ለመወሰን እንደ በቂ መነሻ ሆኖ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፤ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮችን በተመለከተ ያቀረበውን ስጋት ለሁሉም ምስክሮች እንደቀረበ ተደርጎ ያልታወቁትን ምስክሮች እንደታወቁ አድርጎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ምስክሮች በግልጽ ችሎት እንዲሰሙ ሲል የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 3፣ 4/1 (ቀ)፣ 5(1)(3)፣ 7፣ 8፣ 23(1)(2) እንዲሁም ከአዋጁ ዓላማ እና ፍርድ ቤቱ ካለው ሚና ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም አመልካች እና ከ1ኛ- 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በጽሑፍ እንዲከራከሩ የተደረገ ሲሆን 5ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ስላላቀረቡ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በምስክሮች ላይ የተጋረጡ አደጋዎች እና ስጋቶች ካሉ በቂ ምክንያት እና ማስረጃ አቅርቦ መከራከር የፍሬ ነገር ክርክር በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታይ አይደለም፤ ዓቃቤ ሕግ የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ከተደረገበት በኋላ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አስቀድሞም ቢሆን ጉዳዩን ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊመልሰው አይገባም ነበር በማለት የሚያቀርበው ክርክር ስነ ስርዓታዊ አይደለም፤ ለምስክሮች ጥበቃ ሊሰጥ የሚችለው የጥበቃ ተጠቃሚው ሊደርስበት ይችላል ተብሎ የሚገመተውን የአደጋ ሁኔታ ብቻ ከግንዛቤ በማስገባት ሊሆን እንደማይገባ በአዋጁ አንቀጽ 5/3 ላይ ተደንግጎአል፤ ዓቃቤ ሕግ የምስክሮች ጥበቃን በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሮአዊ የዳኝነት ስልጣን የሚጻረር ነው፤ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ በምስክሮች ላይ የተጋረጠ አደጋ መኖሩን ማረጋገጥ ባለመቻሉ ምስክሮች በግልጽ ችሎት እንዲመሰክሩ ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ያስቀርባል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ዓቃቤ ሕግ በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ከቆጠራቸው ምስክሮች ውስጥ አምስቱ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲመሰክሩ፤ አሥራ ስድስቱ ደግሞ በዝግ ችሎት እንዲመሰክሩ እንዲፈቀድለት የጠየቀ መሆኑን፤ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ዓቃቤ ሕግ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር

ከተዘረዘሩ የጥበቃ ዓይነቶች ውስጥ የጥበቃ ዓይነቱን ሲወስን የተጠሪዎችን ሕገ መንግስታዊ መብት ሊጎዳ በማይችል መልኩ መሆን እንዳለበት የሚደነግገውን የአዋጁን አንቀጽ 5/3 ከግምት ያላስገባ ሲሆን ከመጋረጃ ጀርባ እና ዝግ ችሎት ምስክር ይሰሙልኝ በማለት ያቀረበው ምክንያትም በአዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 3/ ሀ ስር የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ የሚያሟላ አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ያደረገው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል ዓቃቤ ሕግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት በዋነኝነት የሚከራከረው የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ የሚወሰደው በአስፈጻሚው በመሆኑ በምክንያት አስደግፌን ለፍርድ ቤቱ ማጸደቅ አይጠበቅብንም፤ ፍርድ ቤቶችም በዓቃቤ ሕግ የተወሰደውን የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ መርምሮ ለማጽደቅ ስልጣን የላቸውም፤ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮችን በተመለከተ ያቀረበውን ስጋት ለሁሉም ምስክሮች እንደቀረበ ተደርጎ ያልታወቁትን ምስክሮች እንደታወቁ ተደርጎ መወሰዱ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት ያለበት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ:-

1. ዓቃቤ ሕግ የወሰደውን የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ በምክንያት አስደግፎ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል? ወይስ አይኖርበትም?
2. ዓቃቤ ሕግ የወሰደውን የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ በምክንያት አስደግፎ ለፍርድ ቤቱ በማቅረብ ማጸደቅ ይኖርበታል ከተባለ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት የሚኖረው ሚና ምንድነው?
3. ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ በማለት በሁለት ዘርፍ በመክፈል ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

ዓቃቤ ሕግ ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ የምስክር ጥበቃ እርምጃ ተወስዷል በማለት የሚከራከረው በአዋጁ አንቀጽ 4/1 (ተ) እስከ (ሰ) እና (ዘ) ስር የተዘረዘሩት ጥበቃዎች በባሕርያቸው ከክርክር ሂደቱ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው እንጂ አቤቱታችንን በምክንያት አስደግፌን በፍርድ ቤት የማጸደቅ ግዴታ ስላለብን አይደለም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የዳኝነት ስልጣን በሕግ ተለይቶ ለሌላ አካል የተሰጠ ካልሆነ በቀር የፍርድ ቤቶች ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ይደነግጋል፡፡ ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች በተመለከተ የወጣው አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 7 እና 8 ሚንስቴሩ ዓቃቤ ሕግ በሚመለከተው አካል የቀረበለትን የጥበቃ ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ እንደሚሰጥ፤ የቀረበለትን የጥበቃ ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ በሰጠ ጊዜም ከጥበቃ ተጠቃሚው ጋር ስምምነት መፈራረም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ስለ ፍትሕ አካላት ሀላፊነት የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 23 (1) እና (2) ድንጋጌ ጉዳዩ የሚመለከተው ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 4/1 ከፊደል ተራ (ሰ) እስከ (ተ) የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደ አግባቡ

መወሰዳቸውን የማረጋገጥ ሀላፊነት፤ ጉዳዩ የሚመለከተው ዓቃቤ ሕግም በአዋጁ አንቀጽ 6/1(ለ) መሠረት ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ሰው መጠየቅ በማይችልበት ጊዜ እርሱን በመወከል ለጥበቃ ተጠቃሚነት የሚቀርብ ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ፤ በአዋጁ አንቀጽ 4/1 ከፊደል ተራ (ሰ) እስከ (ተ) እንዲሁም በፊደል ተራ (ዘ) የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለፍርድ ቤት ማመልከት የሚችል ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ እነኚህም ድንጋጌዎች መረጃ በሚሰጥበት የወንጀል ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊትም ሆነ በኋላ ተከሳሽ በጥበቃ ተጠቃሚው መኖሪያ ወይም የስራ ቦታ ወይም ትምህርት ቤት አካባቢ እንዳይደርስ ማገድ፤ የፍርድ ሂደት ተጀምሮ ምስክርነት እስኪሰጥ ድረስ የምስክር ማንነት እንዳይገለጽ ማድረግ፤ ምስክር በዝግ ችሎት እንዲሰጥ ማድረግ፤ ምስክርነት በአካል ሳይታይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ማንነትን በመሸፈን እንዲሰጥ ማድረግ፤ ማስረጃ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሌላ የተለየ ዘዴ እንዲቀርብ ማድረግ እና ለምስክሩ ወይም ለጠቋሚው የምክር አገልግሎት መስጠት ወይም እንዲያገኝ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ተወስዷል የሚለው የጥበቃ እርምጃ እነኚህን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የተወሰደ ስለመሆኑ ለስር ፍርድ ቤቱም ሆነ ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር የገለጸ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 23 (1)እና(2) ድንጋጌ መሠረት የጥበቃ እርምጃዎቹ እንዲወሰዱ ለፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ በምክንያት አስደግፎ ለፍርድ ቤት ለማቅረብ አልገደድም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

በአንደኛው ጭብጥ ላይ እንደተገለጸው ዓቃቤ ሕግ ተወስዷል የሚለውን የጥበቃ እርምጃ ለፍርድ ቤት ማመልከት አለበት ከተባለ በቀጣይነት ፍርድ ቤቱ የሚኖረው ሚና ምንድነው የሚለውን እንመልከት፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 23/1 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ጉዳዩ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት የተሰጠው ሀላፊነት በአዋጁ አንቀጽ 4/1 ከፊደል ተራ (ሰ) እስከ (ተ) የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች እንደአግባቡ መወሰዳቸውን የማረጋገጥ ሀላፊነት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህ ሀላፊነት እስከ ተሰጠው ጊዜ ድረስ ዓቃቤሕጉ ተወስዷል የሚላቸውን የጥበቃ እርምጃዎች በአግባቡ የተወሰዱ መሆናቸውን ባረጋገጠ ጊዜ ማጽደቅ እንደሚችል፤ የጥበቃ እርምጃዎቹ በአግባቡ ያልተወሰዱ መሆናቸውን ባረጋገጠ ጊዜ ደግሞ የጥበቃ እርምጃዎቹን ውድቅ ማድረግ እንደሚችል ድንጋጌው ራሱ አመላካች ሲሆን ፍርድ ቤቶች በፊታቸው የቀረቡላቸውን ጉዳዮች ዓይተው ለመወሰን የሚያስችላቸውን ተፈጥሮአዊ ስልጣን መሠረት በማድረግ በመፍቀድ ወይም በመንፈግ ውሳኔ ሊሰጡበት የሚችል ጉዳይ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ የምስክሮች ጥበቃ እርምጃ የሚወሰደው በአስፈጻሚው እንጂ ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የላቸውም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20 የተከሰሱ ሰዎች የተከራካሪዎችን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን ሞራል ሁኔታ እና የሐገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት እንዲሰማ ካልተወሰነ በቀር ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት እንዳላቸው፣ የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

ስለ ወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች በተመለከተ የወጣው አዋጅ ቁጥር 699/2003 አንቀጽ 3/1 በአዋጁ መሠረት የምስክሮች ጥበቃ ተግባራዊ የሚሆነው በሕግ የተመለከተው የጽኑ እሥራት መነሻ ከግምት ሳይገባ አሥር ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ በሚችል የወንጀል ድርጊት ተጠርጣሪ ላይ የሚሰጥ ምስክርነትን ወይም ጥቆማን ወይም የሚካሄድ ምርመራን የሚመለከት ሆኖ የወንጀል ድርጊቱ ያለምስክሩ ወይም ያለጠቋሚው ምስክርነት ወይም ጥቆማ በሌላ ማናቸውም መንገድ ሊረጋገጥ ወይም ሊደረስበት የማይችል ሲሆን እና በምስክሩ፣ በጠቋሚው ቤተሰብ፣ ሕይወት፣ አካላዊ ደንነት፣ ነጻነት ወይም ንብረት ላይ ከባድ አደጋ ይደርሳል ተብሎ ሲታመን ነው በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5/3 ሊሰጥ የታሰበው ጥበቃ በሌላ ሰው መብት እና ሕጋዊ ጥቅም ላይ የሚስከትለው ጉዳት ግምት ውስጥ መግባት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህም የተከሰሱ ሰዎች በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠላቸው መብት ታልፎ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ ወይም በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ሊፈቀድ የሚችለው ምስክሩ ባደረበት ስጋት ምክንያት ብቻ ሳይመሰክር ቀርቶ በምስክሩ ብቻ ሊረጋገጥ የሚችለውን ወንጀል ተዳፍኖ እንዳይቀር ለማድረግ ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ምክንያት በቂ፣ አሳማኝ እና በአዋጁ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ የተፈቀደበትን ዓላማ የሚያሳካ ሊሆን ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤ ሕግ አምስቱ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው እንዲሰሙ በማለት ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል የሚረጋገጠው በእነዚህ ምስክሮች ብቻ ስለመሆኑ በመግለጽ ያቀረበው ክርክር ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት አያመለክትም፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤ ሕግ ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው ሊሰሙ ይገባል የሚላቸው ምስክሮች አለ የሚለው ስጋት ተጠሪዎች የፖለቲካ ርዕዮትን በሀይል ለማሳካት ሰዎችን ለመግደል እና ሰዎች ላይ ጥቃት ለማድረስ ደጋፊዎችን መልምለው ጥቃት ያደረሱ እና ጥቃት ለማድረስ ዝግጅት ላይ የነበሩ እንደሆኑ ምስክሮቻችን በቅርበት ከማወቃቸው በተጨማሪ ለመርማሪ ፖሊስ ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን በመስጠት የሕግ ምስክር ሆነዋል፣ ምስክርነት ቃላቸውን የሰጡባቸው ተጠሪዎች ብዙ ደጋፊዎች እና ተከታዮች ያሏቸው ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ቀን በተደረገላቸው ጥሪ እና ቅስቀሳ በመነሳሳት ቁጥራቸው 14 የሆኑ ሰዎች ሕልፈት እና በሚልዮኖች የሚደርስ ንብረት ውድመት እንዲደርስ ያደረጉ መሆኑን ጠቅሰው በእነርሱ እና

በደጋፊዎቻቸው ፊት ብንመሰክር ሕይወታችን አደጋ ላይ ይወድቃል የሚል ስጋት አለባቸው፤ ከቀጥታ አካላዊ ጥቃት እና ዛቻ በዘለለ የተጠሪዎች ደጋፊዎች የተለያዩ ሰዎችን ስም በማሕበራዊ ሚድያ በመዘርዘር በተጠሪዎች ላይ የመሰከሩ ናቸው በማለት በፌስቡክ የግለሰቦችን ስም ሲለጥፉ የነበረና በዚህ ጽሁፍ ስም ከመዘርዘሩ በተጨማሪ ስማቸው የተዘረዘረ ግለሰቦች የዓቃቤ ሕግ ምስክር ናቸው በሚል ማሕበረሰቡ እንዲያገላቸው እና ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሲዛት እና ቅስቀሳ ሲደረግ ነበር፤ በሽብር ክስ ላይ ምስክር የሆነ ግለሰብ ያለምንም ጥፋት እንዲገደል ሰው ተመድቦበት የነበረ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ምደባ በርካታ ሰው ላይ ተደርጓል በሚል ነው፡፡

ሆኖም ዓቃቤ ሕግ ተጠሪዎች የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች በመሆናቸው እና ብዙ ደጋፊዎች ያላቸው በመሆኑ በምስክሮች እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ በማለት የሚከራከር ቢሆንም የሰጠው ምክንያት መላምት መሆኑ እና ተጠሪዎችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው ከዚህ ቀደም በነበረው የፍርድ ቤት ውሎም ሆነ ጊዜያት ምንም ዓይነት የፍርድ ሂደቱን የሚያውክ ተግባር ያላሳዩ መሆኑን በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤ ሕግ ስጋቱን በምክንያት አስደግፎ እንዲያቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባቀረበው አቤቱታ ከቀጥታ አካላዊ ጥቃት እና ዛቻ በዘለለ የተጠሪዎች ደጋፊዎች የተለያዩ ሰዎችን ስም በማሕበራዊ ሚድያ በመዘርዘር በተጠሪዎች ላይ የመሰከሩ ናቸው በማለት በፌስቡክ የግለሰቦችን ስም ሲለጥፉ የነበረና በዚህ ጽሁፍ ስም ከመዘርዘሩ በተጨማሪ ስማቸው የተዘረዘረ ግለሰቦች የዓቃቤ ሕግ ምስክር ናቸው በሚል ማሕበረሰቡ እንዲያገላቸው እና ማንኛውም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሲዛት እና ቅስቀሳ ሲደረግ የነበረ መሆኑ፤ በሽብር ክስ ላይ ምስክር የሆነ ግለሰብ ያለምንም ጥፋት እንዲገደል ሰው ተመድቦበት የነበረ በመሆኑ፤ እንዲህ ዓይነት ምደባ በርካታ ሰው ላይ ተደርጓል በማለት በግልጽ አመልክቷል፡፡ ይህም የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ጉዳት ያደርሱባቸዋል በተባሉት አካላት የታወቁ መሆኑን የሚሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል በዝግ ችሎት እንዲሰሙ አቤቱታ የቀረበባቸው ምስክሮችም በቀዳሚ ምርመራ ወቅት በተጠሪዎች ተከታዮች እና ደጋፊዎች አማካኝነት ምስክር ናቸው በሚል የጠረጠሯቸው ግለሰቦች ላይ ማስፈራሪያ ዛቻ የተሰነዘረባቸው መሆኑ፤ በአንድ ምስክር ላይ ሽጉጥ በመተኮስ የመግደል ሙከራ የተፈጸመበት መሆኑ በአቃቤ ሕግ አቤቱታ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም ዓቃቤ ሕግ በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ጥያቄ ያቀረበባቸው ምስክሮች የተለዩ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በአዋጁ መሠረት ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው ወይም በዝግ ችሎት እንዲሰሙ ጥበቃ የሚደረግላቸው ተፈጽሟል የተባለው ወንጀል በሌላ ሁኔታ ሊረጋገጥ የማይችል በሆነ ጊዜ እና ምስክሩ ባደረበት ስጋት ምክንያት ብቻ ሳይመሰክር ቀርቶ በምስክሩ ብቻ ሊረጋገጥ የሚችለውን ወንጀል ተዳፍኖ እንዳይቀር ለማድረግ ዓቃቤ ሕግ የሚቀርበው ምክንያት በቂ፤ አሳማኝ እና በአዋጁ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ የተፈቀደበትን ዓላማ የሚያሳካ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ በተጠሪዎች ተፈጽሟል የተባለው ወንጀል በሌላ ሁኔታ ሊረጋገጥ የማይችል መሆኑን በመግለጽ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ ክርክር የሌለ ከመሆኑ በላይ ዓቃቤ ሕግ ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት እንዲሰሙ አቤቱታ ያቀረበባቸው ምስክሮች አስቀድመው የተለዩ መሆኑን ዓቃቤ ሕግ ራሱ ካቀረበው ምክንያት የተረጋገጠ በመሆኑ የዓቃቤ ሕግ ጥያቄ በአዋጁ ምስክሮች ከመጋረጃ ጀርባ እና በዝግ ችሎት ሆነው እንዲሰሙ ከተፈቀደበትን ዓላማ ውጪ የቀረበ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖም በክሱ የተዘረዘረው የወንጀል ተግባር በማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ክሱን ግምት ማድረግ በዓቃቤ ሕግ በኩል በምስክሮች ላይ ይደርሳል ተብሎ የተጠቀሰው ስጋት የተጠሪዎችን ነጻ ሆኖ የመገመት መብት የሚጋፋ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ምስክሮች በግልጽ ችሎት እንደሰሙ ሲል የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 260175 ሠኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 210614 ሐምሌ 07 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ  ጸንቷል፡፡
2. ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
    - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

### የልዩነት ሃሳብ

-ስማችን በሶስተኛ እና አራተኛ መስመር ላይ የተጠቀሰው ዳኞች ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የተባሉትን ምስክሮች አስመልክቶ አብላጫው ድምፅ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ በተጠቀሰው ምክንያት እና በደረሰበት ድምዳሜ ያልተስማማን በመሆኑ ለልዩነት ያበቃንን ሀሳብ በሚከተለው መልኩ አስፍረናል፡፡

-በመሰረቱ ለህዝብ ግልፅ በሆነ ችሎት መዳኘት ህገ መንግስታዊ መብት መሆኑ የኢ/ፌ/ድ/ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 20/1/ ይደነግጋል፡፡ አንድን በፍርድ ቤት የቀረበን ጉዳይ በዝግ ችሎት /ከግልፅ ችሎት ውጭ/ ማየት ልዩ ሁኔታ ወይም በስተቀር /Exception/ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ በዝግ ችሎት ሊሰማ የሚችለው የተከራካሪዎችን የግል ህይወት የህዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ስለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰው የህገ መንግስቱ አንቀፅ ይደነግጋል፡፡ በህገ መንግስቱ የተገለፁትን ውስን ምክንያቶች በልዩ ሁኔታነት ከማስቀመጥ ባለፈ ለምስክሮች ደህንነት ሲባል ክርክር በዝግ ችሎት ሊከናወን ስለሚችልበት አግባብ አልያም ዝርዝር ሁኔታው በህግ የሚወሰን ስለመሆኑ የተጠቀሰው ነገር የለም፡፡

- ሆኖም ስለወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ጥበቃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 699/2003 ለጥበቃ ተጠቃሚ የወንጀል ምስክሮች እና ጠቋሚዎች ሊደረግላቸው ስለሚችል የጥበቃ እርምጃዎች በአዋጁ አንቀፅ 4 ስር የዘረዘረ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ምስክርነት በአካል ሳይታይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ወይም ማንነትን በመሸፈን እንዲሰጥ ማድረግ አልያም ምስክርነትን በዝግ ችሎት እንዲሰጥ ማድረግ ስለመሆኑ በንዑስ አንቀፅ 1/ቀ እና በ/ስር ተመልክቷል፡፡

- በዚህ መልኩ ምስክርነትን መስማት ለተከሳሹ በግልፅ ችሎት የመዳኘት ህገ መንግስታዊ መብት ልዩ ሁኔታ ወይም በስተቀር በመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 4/1/ቀ እና በ/ ስር የተጠቀሰው ፈቃጅ ሁኔታ በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን መርህ በማይሸረሸርበት አኳኋን እና የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማ ባገናዘበ መልኩ ብቻ በጠባቡ ሊተረጎም እና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ ይታመናል፡፡

- የተጠቀሰው አዋጅ መሰረታዊ ዓላማ በዋናነት ሁለት ናቸው፡፡ አንዱ በህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ ስጋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ወንጀል ፈፃሚዎችን በማጋለጥ ወንጀልን መከላከል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ወንጀለኞችን በማጋለጥ ሂደት ውስጥ በጠቋሚነት እና ምስክርነት የሚሳተ□ትን ሰዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚደርስባቸው አደጋ እና ጥቃት መከላከልና ደህነታቸውን መጠበቅ ስለመሆኑ አዋጁ መግቢያ ላይ ከሰፈረው መሰረት ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

- ይህንን የአዋጁን መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካት ይረዳሉ ተብለው በአዋጁ አንቀፅ 4 ስር የተዘረዘሩት የጥበቃ እርምጃዎች በጥቅሉ በሁለት ዘንግ የሚመደቡ ናቸው፡፡ አንደኛው የወንጀል ጠቋሚውን ወይም የምስክሩን ማንነት በመደበቅ የሚወሰድ የጥበቃ እርምጃ ሲሆን ሌላኛው ማንነትን መደበቅ ሳያስፈልግ በሌላ አኳኋን ሊወሰድ የሚችልን የጥበቃ እርምጃን የሚመለከት ነው፡፡ ጥበቃው በምስክሩ አልያም በጠቋሚው ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊደርስ ከሚችል ጥቃት እና አደጋ መካላከል በመሆኑ ማንነትን የመደበቅ ተግባሩ አንድም ከተከሳሾች ከራሳቸው እንዲሁም ከተከሳሾች ቤተሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መልኩ ሊወሰዱ ከሚችሉ የጥበቃ እርምጃዎች የምስክሩን ማንነት መቀየር ፣ የፍርድ ሂደቱ ተጀምሮ ምስክርነት እስኪሰጥ ድረስ የምስክሩን ማንነት ያለመግለፅ፣ ምስክሩ በአካል ሳይታይ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ወይም ማንነትን በመሸፈን ምስክርነቱን እንዲሰጥ ማድረግ ተብለው የተገለፁትን መጥቀስ ይቻላል፤ ከዚህ ውጭ የሚወስዱት የጥበቃ እርምጃዎች ማንነትን መደበቅ የግድ የሚሉ አይደሉም፡፡ ለአብነት ያክልም ምስክርነት በዝግ ችሎት እንዲሰጥ በማድረግ የሚወሰደው እርምጃ የምስክሩ ማንነት ችሎቱን በሚታደሙ የተከሳሾች ቤተሰቦች እና ሌሎች ታዳሚዎች እንዳይታወቅ ከሚያደርግ በቀር ምስክሩን በተከሳሾች እንዳይታወቅ የሚያደርገው አይደለም፡፡

- በሌላ በኩል የምስክሩ ማንነት የሚደበቀው ከተከሳሽም ይሁን ከችሎት ታዳሚዎች ማንነቱ በማናቸውም መልኩ ቀድሞ ከታወቀ ማንነትን በመደበቅ የሚወሰደውን የጥበቃ እርምጃ አስፈላጊነት ትርጉም የሚያሳጣው በመሆኑ ሌሎች የጥበቃ አማራጮች እንደ አግባብነታቸው ተግባራዊ ከሚደረጉ በቀር የምስክሩን ማንነት ልደብቅ ማለት መፍትሔ ሊሆን እንደማይችል እኛም የምንቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት ማንነትን በመደበቅ ጥበቃ እንዲደረግላቸው

የተፈለጉት ምስክሮች በተከሳሾችም ሆነ በቤተሰቦቻቸው አልያም በደጋፊዎቻቸው ተለይተው የሚታወቁ በመሆኑ ጉዳዩ ላይ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡

- አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ለምስክሮቹ ጥበቃ እንዲደረግላት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ የመጀመሪያው ጥበቃ እንዲደረግላቸው የተጠየቀላቸው ምስክሮች ቀድሞ የሚታወቁ በመሆኑ እርምጃውን መውሰዱ ትርጉም የለውም የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በምስክሮቹ ላይ ተጨባጭ የደህንነት አደጋ የተጋረጠ ለመሆኑ አመልካች አላስረዳም የሚል ነው፡፡ አብላጫው ድምፅ ቢሆን ምስክሮቹ የሚታወቁ ስለመሆኑ አመልካች በራሱ ያቀረበው አቤቱታ ያረጋግጣል በሚል ይህንኑ ምክንያት ቃል በቃል ተቀብሏል፡፡ እንግዲህ አመልካች የጥበቃ እርምጃውን ያቀረበው በሁለት መንገድ ነው፡፡ ለአምስቱ ምስክሮች ማንነታቸው ሳይታወቅ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው ቃላቸውን እንዲሰጡ የሚል ሲሆን የተቀሩት አሥራ ስድስቱ ምስክሮች ደግሞ በዝግ ችሎት ይሰሙኝ በሚል ነው፡፡

- ከዚህ ጋር በተያያዘ በዝግ ችሎት ምስክርነታቸው እንዲሰማ የተጠየቁት በቀዳሚ ምርመራ ወቅት ፍርድ ቤት ቀርበው መመስከራቸው ከመገለፁ ውጭ ከመጋረጃ በሰተጀርባ ሆነው ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የተፈለጉት አምስቱ ምስክሮች የሚታወቁ ስለመሆኑ አመልካች የገለፀው ነገር የለም፡፡ በፅሁፍ ያቀረበው አቤቱታም ቢሆን በዚህ መልኩ ለመረዳት በሚያስችል ሁኔታ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ እርግጥ ነው አመልካች የጥበቃ እርምጃውን አስፈላጊነት በሚያስረዳው የአቤቱታው ሀተታ ውስጥ በአሁን ተጠሪዎች ላይ ምስክር የሆኑት ናቸው በሚል በተለያዩ ሰዎች ማንነታቸው በማህበራዊ ድህረ ገፅ ላይ በተለቀቁ ግለሰቦች ላይ ጥቃት እና ዛቻ የተፈፀመ ስለመሆኑ ገልጿል፡፡ ከዚህ ባለፈ አመልካች ስማቸው በማህበራዊ ድህረገጽ ላይ የተለቀቀው እና ለጥቃት የተዳረጉት ግለሰቦች ምስክሮቼ ናቸው በሚል የገለፀው ነገር የለም፡፡

- እንዲያውም አመልካች የምስክሮቼ ማንነት አይታወቅም፤ ፍርድ ቤቱ ይታወቃሉ የሚለውን የተሳሳተ ግንዛቤ የወሰደው የጥበቃውን አስፈላጊነት ለማስረዳት በተከሳሾች ላይ ምስከር የሆኑት ናቸው በሚል በተለያዩ ሰዎች ማንነታቸው በማህበራዊ ድህረ ገፅ በተለቀቁ ሰዎች ላይ ጥቃት ተፈጽሟል በማለት ከገለጽኩት ሀሳብ ነው በማለት እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ አጥብቆ እየተከራከረ ይገኛል፡፡ ጉዳዩ ይህ በሆነበት ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው ምስክርነታቸው እንዲሰማ የተባሉት የአመልካች ምስክሮች ማንነት ቀድሞ ታውቋል በሚል በደፈናው የአመልካች አቤቱታ መታለፉ የግራ ቀኙን ክርክር ይዘት ያገናዘበ ሳይሆን በአመልካች ያልተገለፀ/ያልተነገረ/ ፍሬ ነገርን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ሊነቀፍ የሚገባ መሰረታዊ የክርክር ጭብጥ አረዳድ ስህተት ነው፡፡ በምስክሮቹ ላይ ተጋርጧል የተባለው የደህንነት አደጋ ተጨባጭነትን በተመለከተ ተጨባጭ ስጋት ስለመኖሩ አመልካች ገልጿል፡፡የጥበቃ እርምጃው እንዲወሰድ ጥያቄው ለፍርድ ቤት የቀረበውም ተገቢው የአደጋ ስጋት ትንተና ተደርጎ በመታመኑ ምክንያት ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ችሎቱ ስለዚሁ ጉዳይ የበለጠ ማጣሪት እና እርግጠኛ መሆን የሚያስፈልገው ከሆነም ከአመልካች መስሪያ ቤት አመራሮች በመጠየቅ አልያም ግራ ቀኙ ተከራካሪ

ወገኖች ባልተገኙበት ምስክሮቹን አስቀረቦ በመስማት ወይም ባመነበት በማናቸውም መንገድ እንዲያጣራ በአሁን አመልካች በኩል ጥያቄ ስለመቅረቡ የስር ፍርድ በት የመዝገብ ግልባጭ የሚያሳይ ቢሆንም ችሎቱ ጥያቄውን በዝምታ አልፎታል፡፡ እናም አመልካች ያቀረበው ጥያቄ ተገቢ ካልሆነም በግልፅ ተተችቶ ውድቅ ባልተደረገበት አልያም በተጠየቀው አግባብ የተጣራ ነገር በሌለበት በምስክሮቹ ላይ ተጨባጭ የደህንነት ስጋት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም በሚል መታለፉ በእርግጥም ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የጉዳይ አመራር ግድፈት ነው፡፡

- በመሆኑም ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆነው ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ የተጠየቀባቸውን የአመልካች ምስክሮችን አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ አመልካች በጠየቀው መሰረት አምስቱ ምስክሮቹ ከመጋረጃ በስትጀርባ ሆነው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሊወሰን ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረቦቻችን የተለየ አቋም ይዘናል፡፡

የሰ.መ.ቁ.205727

ጥቅምት 29/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡- ባህሩ ታዬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ ህግ ወጥ የጦር መሣሪያ ማዘዋወር ወንጀል ክስን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/99038 ላይ ጥር 24/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል በነፃ በማሰናበት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የጦር መሣሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4(2) ድንጋጌን ጠቅሶ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጠዳ ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ተጠሪ በተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ የተመለከተውን ክልከላ በመተላለፍ የንምራ ቁጥሩ C21 mm 16-08-04-167 የሆነ የቱርክ ሽጉጥ፤ ሶስት የአብራራው ጥይት እና አንድ የክላሽ ጥይት በህገ ወጥ መንገድ ይዞ ከጎንደር ወደ ማክሰኚት አቅጣጫ በመኪና በመጓዝ ላይ እያለ ሐምሌ 11 ቀን 2012 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 4፡00 ሰዓት አካባቢ ጠዳ ከተማ ዩኒቨርሲቲው አካባቢ ኬላ ላይ በተደረገ ፍተሻ የተያዘ በመሆኑ ህገ ወጥ የጦር መሣሪያ ማዘዋወር ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ የተጠቀሰውን ሽጉጥ ለራሱ መጠበቂያነት በሚል ገዝቶ ይዞ የተገኘ መሆኑን፤ የተጠቀሱትን ጥይቶች ግን የፈተሸው ፖሊስ ኪሱ ውስጥ ከትቶ ከኪሱ አገኘሁ ያለ እንጂ የእርሱ አለመሆናቸውን ጠቅሶ ክዷል፡፡ በዚሁ ምክንያት የአመልካች ምስክሮች ቀርበው

እንዲሰሙ ተደርጓል፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም በተባለው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት ተጠሪ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የጦር መሳሪያዎች ይዞ ሲጓዝ ኬላ ላይ በተደረገ ፍተሻ መያዙን በመግለፃቸው ተጠሪ ክሱን እንዲከላከል ተነግሮታል፡፡ ሆኖም ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ እንደሌለው በማሳወቁ የመከላከል መብቱ ታልፎ ክስ በቀረበበት አንቀፅ ስር ጥፋተኛ ተብሎ በ2 ዓመት ከ3 ወር እስራት እና በብር 1,000(አንድ ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪን ይግባኝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በነበሩት ህጎች እና አሰራሮች ሳይመዘገብ ወይም ፈቃድ ሳይሰጣቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተቆጣጣሪ ተቋሙ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ቀርበው ማስመዝገብ እንደሚችሉ የሚደነግግ መሆኑን፣ ሆኖም በወቅቱ ተቆጣጣሪ ተቋሙ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ ወደ ተግባር ያልገባ በመሆኑ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘቱ ብቻውን ወንጀል አለመሆኑን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 23/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነውን የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር አይደለም በሚል በነፃ የተሰናበተበት አግባብ ከጦር መሣሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 4(2)፣ 6 እና 23(2) አንፃር በዚህ ችሎት እንዲመረምር በመደረጉ ተጠሪ የፅሑፍ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡ ሆኖም ተጠሪ በተደረገለት የጋዜጣ ጥሪ መሰረት ቀርቦ መልስ ባለመስጠቱ ክርክሩ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ታዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከአመልካች የሰበር ቅሬታ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪን ከቀረበበት ክስ በነፃ ያሰናበተው ክስ የቀረበበትን አዋጅ ለማስፈፀም የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው አካል አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ የሌለውን የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች መሳሪያውን አስመዝግበው ፈቃድ ለመውሰድ የሚችሉበትን የጊዜ ሰሌዳ ወስኖ ወደ ስራ ያልገባ በመሆኑ ተጠሪ በዚሁ ጊዜ ውስጥ መሳሪያውን

ይዞ መገኘቱ ወንጀል አይደለም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በመሰረቱ ክስ የቀረበበት አዋጅ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በፍቃድም ሆነ ያለፈቃድ የተያዙ መሳሪያዎች በአዋጁ መሰረት ሊመዘገቡ የሚገባበትን ሁኔታ ከማስቀመጥ ባለፈ በተቀመጠው የጊዜ ወሰን ውስጥ መሳሪያውን ይዞ መገኘት አያስጠይቅም በሚል የተቀመጠ የእፎይታ ጊዜ የለም፡፡ ከመነሻውም ቢሆን ህጋዊ ፈቃድ የሌለውን የጦር መሳሪያን ይዞ መገኘት ወንጀል ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 808 ስር ተደንግጓል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንዱ መሰረታዊ ዓላማም ለብዙሃን ጥቅም ሲባል በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ያለ ፈቃድ በግለሰቦች እጅ የገቡ የጦር መሳሪያዎች ላይ ተገቢውን ህጋዊ ቁጥጥር በማድረግ ወደ ሥርዓት ማስገባት የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር ስለመሆኑ በአዋጁ መግቢያ ላይ ከሰፈረው መሰረተ ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይህንን ለማድረግ ይቻል ዘንድም አዋጁ ከመፅናቱ በፊት ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖራቸው የጦር መሳሪያ የያዙ ሰዎች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ተቆጣጣሪው ተቋም በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በአካል ቀርበው ፈቃድ መጠየቅ እና በአዋጅ መሰረት የተመለከቱ መስፈርቶችን አሟልተው በተቆጣጣሪ ተቋሙ ፈቃድ መውሰድ ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀፅ 23(2) ስር ተመልክቷል፡፡ ከአዋጁ መሰረታዊ ዓላማ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የዚህ ድንጋጌ ዋናው ዓላማ ፈቃድ የሌላቸው ሰዎች ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ መሳሪያውን ይዘው ሲንቀሳቀሱ ሊያጋጥማቸው ከሚችለው የህጋዊነት ጥያቄ ለመጠበቅ እንጂ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለማንም ጠያቂ የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመፍቀድ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በእጁ ተይዘዋል ከተባሉት የጦር መሳሪያዎች ውስጥ ጥይቶቹን በተመለከተ ከመካድ ባለፈ ያመነውን የጦር መሳሪያን አስመልክቶ ህጋዊ ፈቃድ ያለው ለመሆኑ አልያም ፈቃድ በማውጣት ሂደት ላይ እያለ የተያዘ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ እንዲያውም የአመልካች ማስረጃ የተሰሙት በተካደው ፍሬ ነገር ላይ መሆኑን እና በተጠሪ እጅ ተገኝቷል የተባለውን ሽጉጥ አስመልክቶ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠው ተጠሪ በችሎት በሰጠው የእምነት ቃል መነሻነት ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ በመሳሪያው ላይ ፈቃድ ያላወጣው ተቆጣጣሪ ተቋሙ ወደ ስራ ባለመግባቱ ምክንያት ነው በሚል ያቀረበው ክርክርም ሆነ ከዚህ አንፃር የተረጋጠ ነገር የለም፡፡ ይህ በሌለበት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የአዋጁን ድንጋጌ ባልተገባ መንገድ ተርጉሞ ተጠሪን ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ ማድረጉ በእርግጥም ሊነቀፍ የሚገባው መሰረታዊ የህግ አረዳድ እና አተረጓጎም ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ ፈፅሟል የተባለው የወንጀል ድርጊት ህገ ወጥ የጦር መሳሪያን ይዞ ሲጓዝ ተገኝቷል በሚል ነው፡፡ ይህ ድርጊት የወንጀል ተግባር ተደርጎ የተደነገገው በአዋጁ አንቀፅ 4(1) ስር ሲሆን ክሱ የቀረበው አንቀፅ 4(2) ተጠቅሶ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ይህ

የወንጀል ድርጊት ስለሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነት የተመለከተው በአዋጁ አንቀፅ 22(2) ስር ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን ሲያሰላ አንቀፅ 22(1) ብሎ ጠቅሷል፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው ቅጣት በአንቀፅ 22(2) ስር የተመለከተውን ቅጣት ቢሆንም በድንጋጌው አፃፃፍ ላይ የአርታዒ ግድፈት ያለ ለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚሁ ጥቃቅን ስህተቶች ታርመው የወረዳው እና የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/99038 ላይ ጥር 24/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በማዕከላዊ ጎንደር ዞን የጠዳ ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/020407 ላይ ሐምሌ 17/2012 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/02-34525 ላይ ነሓሴ 22/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪን አፈላልጎ በተገኘበት በመያዝ ለክልሉ ማረሚያ ቤት አስተዳደር እንዲያስረክብ፤ የክፍሉ ማረሚያ ቤት ተጠሪ ተይዞ ሲቀርብለት ቀድሞ በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ቀሪ የእስራት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ይፃፍ፡፡

2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ.209763

ጥር 25/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ እምራን ታጁ

ተጠሪ፡- የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በህገ ወጥ መንገድ ቡና ማጓጓዝ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበውም አመልካች ጥፋተኛ ተብሎ በተቀጣበት በህገ ወጥ መንገድ ቡናን የማጓጓዝ ወንጀል አግባብነት ያለው ህግ በፌዴራል መንግስቱ የወጣው አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ነው? ወይስ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የወጣው አዋጅ ቁጥር 160/2002 ነው? የሚለውን እና ተያያዥ ነጥቦችን መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ሐምሌ 15/2012 ዓ.ም ፅፎ በአሁን አመልካች እና በሌላ አንድ ግለሰብ ላይ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቡና ጥራትን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 160/2002 አንቀፅ 23(4) እና 23(7) ድንጋጌን ጠቅሶ በቡኖ በደሌ ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የቀረበውም ክስ ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው አመልካች እና ሌላኛው ግለሰብ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና ክስ የቀረበበትን አዋጅ አንቀፅ 23(4) ድንጋጌን በመተላለፍ በህገ ወጥ መንገድ ቡናን ለማጓጓዝ አስበው ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም መጀመሪያ ከሌሊቱ 9፡50 ሰዓት ላይ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተጠቀሰው የስልክ ቁጥር የኬላ ጥበቃ ሰራተኛ ወደሆኑት ም/ሳጅን አሊ አባሚልኪ ወደተባሉት የፖሊስ ባልደረባ የእጅ ስልክ ላይ “ትንሽ እቃ ነው! 1,500 ብር!” የሚል እና “እሺ 2000 ብር!” የሚል የስልክ የፅሁፍ መልዕክት ከላኩ በኋላ የንግድ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና የይለፍ ወረቀት

ሳይኖራቸው ጠቅላላ የዋጋ ግምቱ ብር 442,000(አራት መቶ አርባ ሁለት ሺህ ብር) የሆነ 65 ኩንታል ቀሽር ቡና የሰሌዳ ቁጥሩ በክሱ ዝርዝር በተጠቀሰው አይሱዙ የጭነት ተሽከርካሪ በህገ ወጥ መንገድ ጭነው ከጮራ ከተማ ወደ በደሌ ከተማ በመጓዝ ላይ እንዳሉ ኬላ ላይ በተደረገ ፍተሻ እጅ ከፈንጅ የተያዙ በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ቡና የማጓጓዝ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ክስ ደግሞ ተከሳሾቹ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ)) እና ክስ የቀረበበትን አዋጅ አንቀፅ 23(7) ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ የተገለፀውን ድርጊት ሲፈፅሙ የተጠቀሰውን ቡና የቡናውን ጥራት በሚጎዳ እና ባልተፈቀደ ማዳበሪያ ጨምረው ያጓጓዙ በመሆኑ በጥራት አሰራር እና ቡና ገበያ ላይ ህገወጥ ተግባር ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካችም ሆኑ ሌላኛው ተከሳሽ የቀረበባቸውን ክስ ክደው በመከራከራቸው የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተሰምቷል፡፡ በመጨረሻም የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎች በክሱ መሰረት አስረድተው እያለ አመልካች እና ሌላኛው ግለሰብ ባቀረቧቸው የሰው ምስክሮች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃውን አላስተባበሉም በሚል በተከሰሱባቸው ሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ ተብለው እያንዳንዳቸው በ6 ዓመት ከ6 ወር ጽኑ እስራት እና በብር 5,000(አምስት ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ይግባኝ ባይነት ይህንኑ ውሳኔን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ ከአመልካች ጋር ተከስሶ የነበረውን ግለሰብ በነፃ አሰናብቷል፡፡ አመልካችን በተመለከተ ደግሞ በ1ኛ ክስ ብቻ ጥፋተኛ በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔን በማሻሻል አመልካች በ4 ዓመት ከ2 ወር እስራት እና በብር 4,500(አራት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(1) መሰረት ሰርዟል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ "በጉዳዩ ላይ ተፈፃሚነት ያለው በፌዴራል መንግስት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ነው? ወይስ የክልሉ አዋጅ ቁጥር 160/2002 ነው?" የሚል ነጥብ ይዞ ጉዳዩን በማስቀረብ ካራከረ በኋላ "ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ አዋጅ መሆን አለበት!" በማለት በአብላጫ ድምፅ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡ ከአብላጫው ድምፅ የተለየ አቋም የያዙት ሁለት ዳኞች ደግሞ ለጉዳዩ ተፈፃሚ ሊሆንም የሚገባውም ሆነ ለአመልካች የሚጠቅመው በፌዴራል መንግስቱ የወጣው አዋጅ በመሆኑ ይኸው አዋጅ ተፈፃሚ ሊደረግ ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይተዋል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 22/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ

ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመታዘዙ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን ከግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር፣ ከማስቀረቢያ ነጥቡ እና ከስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት ያለው ህግ በፌዴራል መንግስቱ የወጣው አዋጅ ነው? ወይስ በክልል መንግስቱ የወጣው አዋጅ ነው? የሚለውን ነጥብ ከማየታችን በፊት ስለ የፌዴራል መንግስት እና የክልል መንግስታት የስልጣን ምንጭ፤ ስላላቸው ስልጣን ምንነት እና ተግባራዊ ውጤቱ በትንሹ ማየት ያስፈልጋል፡፡ እንግዲህ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 1/1987 ከታወጀ በኋላ በሀገሪቱ የስልጣን አወቃቀር በፌዴራል እና በክልሎች የተዋቀረ መሆኑን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 50(1) ተመልክቷል፡፡ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት የስልጣን ምንጭም ህገ መግስቱ ስለመሆኑ በዚሁ የህገ መንግስቱ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 ስር ተደንግጓል፡፡ ለሁለቱም መንግስታት የተሰጠው ስልጣንም የህግ አውጪነት፣ የህግ አስፈፃሚነት እና የዳኝነት ስልጣን ስለመሆኑ በአንቀፅ 50(2) ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጠው ስልጣን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 51 ስር የተዘረዘረ ሲሆን ለክልሎች የተሰጠው ስልጣን ደግሞ በአንቀፅ 52 ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በህገ መንግስቱ ለሁለቱም መንግስታት የተሰጠውን ስልጣን በጥቅሉ በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ለፌዴራል መንግስቱ ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ስልጣን(Exclusive Federal Jurisdiction) ነው፡፡ ሁለተኛው ለክልል መንግስታት ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ስልጣን(Exclusive Regional Jurisdiction) ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ለሁለቱም መንግስታት በጋራ የተሰጣቸው ስልጣን(Concurrent Jurisdiction) ነው፡፡ በህገ መንግስቱ ለክልል መንግስታት ከተሰጠው ስልጣን ውስጥ አንዱ በግልፅ ተለይቶ ለፌዴራል መንግስቱ ብቻ ወይም ለፌዴራል መንግስት እና ለክልል መንግስታት በጋራ ባልተሰጠ ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 52(1) ይደነግጋል፡፡ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት በዚህ መልኩ የተሰጣቸው መንግስታዊ ስልጣን ተግባራዊ ሲያደርጉ አንዳቸው የሌላኛቸውን ስልጣን ማክበር እንዳለባቸው የህገ መንግስቱ አንቀፅ 50(8) ያዝዛል፡፡

በቀረበው ጉዳይ የቡና ጥራት ቁጥጥርን አስመልክቶ የህግ አውጪነት ስልጣኑ የፌዴራል መንግስቱ አልያም የክልል መንግስታት ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ በግልፅ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በተጨባጭ ደግሞ የፌዴራል መንግስቱ አዋጅ ቁጥር 1051/2009፤ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደግሞ አዋጅ ቁጥር 160/2002 አውጥተው ሁለቱም ህግጋት በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ

አንፃር በአጠቃላይ በሁለቱ ህግጋት መካከል መጣረስ ቢኖር አልያም በተለያየ ምክንያት የህግ መረጣ ውስጥ የሚገባበት አስገዳጅ ሁኔታ ቢፈጠር "የትኛው ህግ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል?" የሚለው ጉዳይ በዚህ ችሎት ትርጉም የሚሰጥበት አይደለም፡፡ ሆኖም የቀረበው ጉዳይ ወንጀልን የሚመለከት በመሆኑ ይህንኑ ነጥብ አስመልክቶ በሁለቱ ህግጋት የተመለከተውን የወንጀል ኃላፊነት እና የቅጣት ድንጋጌዎችን ብቻ በመመርመር ከወንጀል ህግ ጠቅላላ መርህ እና ከህገ መንግስቱ አንፃር እልባት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በፌዴራል መንግስቱም ሆነ በክልሉ መንግስት የወጡት ህግጋት በህገ ወጥ የቡና አጓጓዦች ላይ የወንጀል ኃላፊነትን የሚጥሉ ቢሆንም በወንጀሉ ጥፋተኛ በተባሉት አጥፊዎች ላይ ሊጣል ስለሚገባው የወንጀል ቅጣት አስመልክቶ በመካከላቸው ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ፡፡ በፌዴራል መንግስቱ የወጣው አዋጅ በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በተገኙት ላይ ከ1 ዓመት የማያንስ እና ከ3 ዓመት የማይበልጥ እስራት እና ከብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) እስከ 40,000(አርባ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ሊወሰን እንደሚችል በአዋጁ አንቀፅ 19(10) ደንግጓል፡፡ በአንፃሩ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የወጣው አዋጅ ደግሞ ለተመሳሳይ የወንጀል ጥፋት በአጥፊው ላይ በወንጀል ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከ3 ዓመት የማያንስ እና ከ5 ዓመት የማይበልጥ እስራት እና በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት ሊወሰን እንደሚችል በአዋጁ አንቀፅ 23(4) ስር ደንግጓል፡፡

እንግዲህ እነዚህ ሁለቱም ህግጋት በወንጀል ረገድ ቅጣትን የሚደነግጉ ልዩ ህጎች ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነት ልዩ ህጎች በተለየ አኳኋን ካልደነገጉ በቀር በመደበኛው የወንጀል ህግ በተመለከቱት መርሆዎች የሚመሩ ለመሆኑ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ህጉ ከተመለከቱት ጠቅላላ የወንጀል ህግ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ስለ ወንጀል እና አፈፃፀሙ የሚደነግገው በአንቀፅ 23 ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚሁ መሰረት አንድ ድርጊት ወንጀል ነው ተብሎ የሚያስቀጣው ህገ ወጥነቱ እና አስቀጪነቱ በህግ በተደነገገ ጊዜ መሆኑን፤ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ለመሆኑ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መልኩ ስለ ወንጀሎች እና አፈፃፀማቸው እንዲሁም ስለሚያስከትሉት ቅጣት አጠቃላይ መርህን እና ዝርዝር ድንጋጌዎችን የያዘውን የወንጀል ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስቱ የህገ አውጪ አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 55(5) ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ጉዳይን በተመለከተም ክልሎች ያላቸው ብቸኛ ስልጣን በፌዴራል ህግ አውጪው አካል ስለ ወንጀል በተደነገገው ህግ በግልፅ ባልተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ህግ ማውጣት ስለመሆኑ በዚሁ አንቀፅ ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ውጭ ክልሎች የወንጀል

ጉዳይን አስመልክቶ በፌዴራል መንግስቱ ህግ በግልፅ በተደነገገባቸው ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስቱን ህግ በሚቃረን መልኩ የራሳቸውን ህግ የሚያውጁበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ አብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከታወጀ በኋላ የቡና ንግድ እና ጥራት ቁጥጥርን አስምልክቶ የታወጀው የመጀመሪያው ህግ በፌዴራል መንግስቱ የወጣው የቡና ጥራት ቁጥጥርና ግብይት አዋጅ ቁጥር 602/2000 ነው፡፡ ይህ አዋጅ በህገ ወጥ እና አግባብ ባልሆነ መንገድ ቡናን ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውሩ ሰዎችን በወንጀል ተጠያቂ በማድረግ በሌላ ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር ከ3 ዓመት በማያንስ እና ከ5 ዓመት በማይበልት እስራት እና በብር 50,000(ሃምሳ ሺህ ብር) የሚቀጡ መሆኑን በአንቀፅ 15(4) ስር ደንግጓል፡፡ የክልል መንግስታትም አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጋቸውን ህግ ማውጣት እንደሚችሉ በአዋጁ አንቀፅ 19(3) ስር ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህግ አውጪ አካል ለሆነው ጨፌ በክልሉ ህገ መንግስት የተሰጠው የህግ አውጪነት ስልጣን ከፌዴራል ህገ መንግስቱ እና የፌዴራል መንግስቱ ሌሎች ህጎችን የማይፃረሩ ልዩ ልዩ ህጎችን ማውጣት ስለመሆኑ የተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀፅ 49(3(ሀ)) ይደነግጋል፡፡ አሁን ለክርክር ምክንያት የሆነው የክልሉ ጨፌ ያወጣው አዋጅም ከዚህ አዋጅ በኋላ በ2002 ዓ.ም የወጣ ሲሆን የወንጀል ኃላፊነቱን እና ቅጣቱን አስመልክቶ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ከዚሁ አዋጅ የተቀዳ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በግልፅ መረዳት የሚቻለው የክልሉ ጨፌ ከቡና ንግድ እና ጥራት ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ቢያንስ ከወንጀል ኃላፊነት እና ቅጣት አንፃር በፌዴራል መንግስቱ አዋጅ የተደነገገውን ህግ መቀበሉን እና ያከበረ መሆኑን ነው፡፡ አሁን ላይ ችግሩ የተፈጠረው ለክልሉ ህግ መውጣት መሰረት የነበረው የፌዴራሉ መንግስት አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 1051/2009 ተሻሽሎ በቀደመው አዋጅ ከፍ ተደርጎ የተቀመጠው የወንጀል ቅጣት በአዲሱ አዋጅ ሲቀንስ የክልሉ አዋጅ ባለበት መቆየቱ ነው፡፡

መነሻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን የወንጀል ጉዳይን አስመልክቶ ክልሎች በፌዴራል መንግስቱ የወጣውን የወንጀል ይዘት ያለው ህግ በሚቃረን መልኩ ህግ ሊያወጡ አይችሉም፡፡ ወጥቶ እንኳን ቢገኝ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በፌዴራል መንግስት የወጣው ህግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት በህገ ወጥ መንገድ ቡናን የማጓጓዝ ወንጀል በፌዴራል መንግስቱ አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀፅ 19(10) እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አዋጅ ቁጥር 160/2002 አንቀፅ 23(4) መካከል በወንጀል ቅጣት ረገድ አለመጣጣም ያለ በመሆኑ ከላይ በፍርድ ሀተታው ውስጥ በተጠቀሰው ምክንያት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው እና ተፈፃሚም ሊደረግ የሚገባው የፌዴራል መንግስቱ አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ነው፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ

ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ አዋጅ ነው በሚል ትርጉም የስር ፍርድ ቤቶችን ስህተት ሳያርም ማለፉ የጉዳዩን ልዩ ባህሪ እና በህገ መንግስቱ ለፌዴራል መንግስት እና ለክልል መንግስታት የተሰጠውን ስልጣን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ አግባብ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ በተሰጠው የጥፋተኝነት ፍርድ መሰረት የወንጀል ቅጣቱ በፌዴራል መንግስቱ የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀፅ 19(10) መሰረት ተሰልቷል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር የተቀመጠው ቅጣት ከ1 ዓመት የማያንስ እና ከ3 ዓመት የማይበልጥ እስራት እና ከብር 20,000(ሃያ ሺህ ብር) እስከ ብር 40,000(አርባ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ነው፡፡ ለዚህ የወንጀል ድርጊት ስራ ላይ ባለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ደረጃ እና እርከን ያልወጣለት በመሆኑ በከፍተኛው ፍርድ ቤት በተገለፀው አግባብ የወንጀሉ ደረጃ ከባድ በሚል ተወስዷል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 19 መሰረት በሚደረግ ስሌትም "ከባድ የወንጀል ደረጃ" ለሚለው ያለው ቅጣት ከ2 ዓመት እስከ 2 ዓመት ከ6 ወር እስራት እና እስከ ብር 26,666.67(ሃያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ከ67/100) የሚደርስ ነው፡፡ በተጨማሪም በስር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኙት አንድ የቅጣት ማክበጃ እና አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በዚህም ችሎት ተወስደዋል፡፡

ይኸው ታሳቢ ተደርጎ በአጠቃላይ አመልካች ጥፋተኛ በተባለበት የወንጀል ድርጊት በ2(ሁለት) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር እስራት እና በብር 4,500(አራት ሺህ አምስት መቶ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/337085 ላይ ግንቦት 11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት በክልሉ የበታች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት መሰረት የክልል መንግስታት የወንጀል ጉዳይን አስመልክቶ በፌዴራል መንግስቱ ከወጣው ህግ ጋር የሚቃረን ወይም የማይጣጣም ህግ የማውጣት ስልጣን ያልተሰጣቸው በመሆኑ በህገ ወጥ መንገድ ቡናን ከማጓጓዝ ወንጀል ጋር በተያያዘ ተፈፃሚነት ያለው በፌዴራል መንግስቱ የወጣው አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ነው፡፡

3. በውሳኔ ተራ ቁጥር 2 ስር በተገለፀው አግባብ በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነት ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሻሽሎ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀፅ 19(10) ስር በ2(ሁለት) ዓመት ከ6(ስድስት) ወር እስራት እና በብር 4,500(አራት ሺህ አምስት መቶ ብር) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡

## ትዕዛዝ

1. ተሻሽሎ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የሰ.መ.ቁ.210238

ህዳር 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡-ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- አቶ ጌታቸው ታደሰ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ጭብጥም ለፍርድ አፈፃፀም በወጣ የፍርድ ቤት የተሽከርካሪ ሽያጭ የሃራጅ ጨረታ ላይ ተወዳድረው የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-18474 አ/አ የሆነ ተሽከርካሪ ገዝተው የተሽከርካሪው ስመ ሀብት ወደ ስማቸው የዞረላቸው መሆኑን፤ ይህንኑ ተሽከርካሪ በማሽከርከር ላይ እያሉ የአሁን አመልካች መስከረም 07/2012 ዓ.ም ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ በአዲስ አበባ ከተማ ለገሃር ተብሎ በሚጠራ አካባቢ ጉልበቱ እና ሥልጣኑ ተጠቅሞ የነጠቃቸው መሆኑን በመግለፅ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ በተሽከርካሪው ውስጥ የነበሩትን ንብረቶች ግምት እና ተሽከርካሪው በመቆሙ ምክንያት የተቋረጠባቸውን ገቢ በጠቅላላው ብር 347,800(ሶስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ብር) ከፍሎ ንብረቱን እንዲለቅላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን አመልካች ቀርቦ ለክሱ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪ ለመንገድ ሥራ ፕሮጀክት በሚል ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር የገባ ነው፤ የመንገድ ስራው እንደተጠናቀቀ ተሽከርካሪው ተመልሶ ከሀገር ሊወጣ አልያም ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ሊከፈልበት የሚገባው ነው፤ ተሽከርካሪውን ወደ ሀገር ያስገባው ድርጅት ሀገር ጥሎ በመጥፋቱ ምክንያት ከድርጅቱ ላይ የሚፈለገው ቀረጥ እና ታክስ ሂሳብ ተሰርቶ በጠቅላላው ወደ ብር

98,474,585.17(ዘጠና ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ከ17/100 ብር) የሚፈለግበት መሆኑ ተረጋግጦ ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ በአመልካች በኩል የእግድ ትዕዛዝ ተላልፏል፣ ተሸከርካሪው ለፍርድ አፈፃፀም በሚል በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተሸጠውም ይኸው በአመልካች የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ፀንቶ ባለበት ነው፣ አመልካች መስሪያ ቤት ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለባቸውን ንብረቶች ተከታትሎ የመያዝ እና የሚፈለግበትን እዳ የማስከፈል በህግ የተሰጠው ሥልጣን አለው፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ተሽከርካሪም በዚሁ ምክንያት በቁጥጥር ስር የዋለ በመሆኑ ድርጊቱ ህገ ወጥ የሁከት ተግባር የሚባል አይደለም፣ ተሽከርካሪው ውስጥ አሉ የተባሉትን ንብረቶች ያልተረከብኩ እና ተቋረጠ የተባለውን ገቢም ልጠየቅ የማይገባ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት ተሽከርካሪ ለፍርድ አፈፃፀም በሚል በፍርድ ቤት በወጣ ጨረታ ተገዝቶ የተያዘ በመሆኑ አመልካች መብቱን መጠየቅ ያለበት ህጋዊ ሂደቶችን ተከትሎ መክፈል ሲኖርበት ያልከፈለው ድርጅት መሆን ሲገባው በፍርድ ቤት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ንብረቱን ተረክቦ እና ሰመ ሀብቱን በራሱ አዙሮ ከያዘው ሰው ላይ መቀበሉ የሁከቱ ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ንብረቱ ለተጠሪ ሊመለስ ይግባል፣ በተሽከርካሪው ውስጥ አሉ የተባሉትን ንብረቶች እና ታጣ የተባለው ገቢ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

በዚሁ ጉዳይ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ የቀደምትነት መብት አለኝ ካለ መብቱን ሊያስከብር የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 418 ስር በተመለከተው አግባብ ሊሆን ይገባል፣ በዚህ መልኩ የቀረበ ጥያቄ ሳይኖር በአፈፃፀም የተሸጠን ንብረት በጉልበት መያዙ የሁከት ተግባር ነው በሚል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በምክንያት በማጠናከር አጽንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 29/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈጽሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ተጥቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም የስር ፍ/ቤት አመልካች በተሸከርካሪው ላይ አለኝ ያለውን ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ መጠየቅ ያለበት ተሸከርካሪውን ወደ ሀገር ካስገባው ድርጅት እንጂ ከአሁን ተጠሪ ላይ አይደለም በማለት የሰጡት ፍርድ አግባብ አለመሆኑን፣ ክስ የቀረበበትን ተሸከርካሪ ጨምሮ ዩቲኤ ኤልሳሜክስ ኢትዮጵያ በተሰኘ የመንገድ ስራ ተቋራጭ ድርጅት ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል የመንገድ ስራው እንደተጠናቀቀ ተመልሰው ከሀገር ሊወጡ ወይም ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው በሀገር ውስጥ እንዲቆዩ በአዋጁ አንቀጽ 71፣ እና 130 መሰረት ወደ ሀገር የገባ መሆኑን፣ ተቋራጩ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቱን በመቋረጥ ከሀገር

በመውጣቱ የአመልካች ኦዲት ለመንግስት ሊከፈል ከነበረው የኦዲት ጉድለት የተገኘ መሆኑን፣ በአዋጁ አንቀጽ 130 መሰረት ክርክር ያስነሳው ተሽከርካሪ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ የሚችለው ቀረጥና ታክስ ከተከፈለበት ወይም የሚተላለፍለት ሰው ተመሳሳይ የቀረጥ ነጻ መብት ያለው ሲሆን ብቻ መሆኑን፣ አመልካች ተሽከርካሪውን በመያዝ ከተሽከርካሪው ላይ የሚፈለገውን ቀረጥና ታክስ ለመሰብሰብ ሥልጣን ያለው አካል መሆኑንና የቀደምትነት መብት ያለው መሆኑን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ/49889 ላይ አመልካች የጉሙሩክ ህግን በማስከበር ረገድ በሚወስደው እርምጃ ወጭና ኪሳራ እንደማይጠየቅ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የወጪ ኪሳራ ዝርዝር እንዲያቀርብ መብት መጠበቃቸው አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ የሰር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ተሽከርካሪ በተጠሪ እጅ አግኝቶ ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል አመልካች ተሽከርካሪውን መያዙ የሁከት ተግባር ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከጉሙሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 130 አንጻር ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ተጠሪ መስከረም 27/2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የስር ፍ/ቤት አመልካች ቀረጥና ታክስ መጠየቅ ያለበት ተሽከርካሪውን ወደ ሀገር ካስገባው ድርጅት እንጅ በህጋዊ መንገድ ተሽከርካሪውን ገዝቶ ስመ-ንብረቱን ጭምር አዙሮ ከያዘው ተጠሪ አይደለም ማለታቸው በአግባቡ ነው፤ አመልካች በስር ፍ/ቤት ክርክርም ሆነ አፈጻጸም ጣልቃ ገብቶ የቀደምትነት መብቱን በህግ አግባብ ማስከበር ሲገባው በፍ/ቤት ትዕዛዝ የተረከቡትን ተሽከርካሪ መያዝ ሁከት መሆኑን በመግለጽ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካችችም መከራከሪያውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በመስጠት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገበዋል በማለት ሞግቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በፍርድ አፈፃፀም በጨረታ በመግዛት በህግ አግባብ የባለቤትነት መብት ባቋቋምኩበት ተሽከርካሪ ላይ አመልካች ሁከት ፈጥሮ በጉልበት የወሰደብኝ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ንብረቱን ሊመልስልኝ ይገባል በሚል ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ክስ የቀረበበትን ንብረት የያዘው ከቀድሞ የንብረቱ ባለቤት ከሆነው ድርጅ ላይ መሰብሰብ የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ በመኖሩ፤ እንዲሁም ተሽከርካሪው ከቀረጥ ነፃ ወደ ሀገር የገባ

ሲሆን በተሽከርካሪው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈል የቀረጥ እና ታክስ ነፃ መብት ላልተሰጠው ሰው የተላለፈ በመሆኑ ለማስከፈል በሚል እንደሆነ ገልፆ ድርጊቱ የሁከት ተግባር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ተሽከርካሪ በህግ አግባብ በጨረታ ገዝቻለሁ ከማለት ባለፈ ከንብረቱ ላይ የሚፈለግ ቀረጥ እና ታክስ የለም በሚል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡

በመሰረቱ አመልካች መስሪያ ቤት ከቀረጥ እና ታክስ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ቁጥጥር የማድረግ ስልጣን በህግ የተሰጠው አካል ነው፡፡ ይህም ስልጣን የጉምሩክ ህጉ መከበሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ማናቸውንም እርምጃ መውሰድን የሚያጠቃልል ሆኖ ከዚህ ውስጥ አንዱ ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለባቸውን ወይም አስፈላጊው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያለተፈፀመባቸውን ንብረቶች እና እቃዎች ተከታትሎ በመያዝ የሚፈለገውን እዳ ማስከፈል ስለመሆኑ ከጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 141፣ 2(22)፣ 2(38)፣ 143 እና 147 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በጉምሩክ ህጉ መሰረት ቀረጥ እና ታክስ ሊከፈልባቸው ከሚገባቸው ንብረቶች ውስጥ አንዱ ከቀረጥ ነፃ መብትን በመጠቀም ወደ ሀገር የገባ እቃ ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው/አካል በሚተላለፍበት ጊዜ ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀፅ 130(1 እና 2)ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንግዲህ በአዋጁ መሰረት ቀረጥ የሚከፈለው በገቢ እና ወጭ ንብረት ላይ በመሆኑ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ እዳ ካለ ከንብረቱ ተለይቶ የማይታይ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት ለአመልካች መስሪያ ቤት የተሰጠው መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ የቀረጥ እዳን ተከታትሎ የማስከፈል ሥልጣን በዋናነት የንብረቱን ባለቤት ሳይሆን ንብረቱን እራሱን የሚከተል ይሆናል፡፡ እናም አመልካች ከአንድ ንብረት ላይ የሚፈለግ ቀረጥ እና ታክስ ስለመኖሩ እስካረጋገጠ ድረስ ንብረቱ በማናቸውም መንገድ በተላለፈላቸው ሶስተኛ ወገኖች እጅ ጭምር በመያዝ መከፈል ያለበትን የመንግስት እዳ የማስከፈል በህግ የተረጋገጠ መብት አለው ማለት ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተከሰሰው በፍርድ አፈፃፀም በሀራጅ ተሽጦ ተጠሪ እጅ የገባን ንብረት በቁጥጥር ስር በማዋል የሁከት ተግባር ፈፅሟል በሚል ነው፡፡ የሁከት ክስ የቀረበበት አካል ደግሞ የሥራውን አደራረግ የሚፈቅድ ለእርሱ የሚናገርለት መብት መኖሩን በፍጥነት እና በማይታበል ዓይነት ማስረዳት ከቻለ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1149(3) ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ለክሱ መሰረት የሆነው ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነፃ በሆነ መብት ወደ ሀገር የገባ ሆኖ ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፈልበት በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት በሀራጅ ተሽጦ ለአሁን ተጠሪ የተላለፈላቸው ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ከንብረቱ ላይ የሚፈለግ እዳ መኖሩ ከተረጋጠ ደግሞ ንብረቱ በፍርድ ቤት የአፈፃፀም ሃራጅ ለተጠሪ መተላለፉ በአመልካች የመቆጣጠር ህጋዊ ስልጣን ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖርም፡፡ እናም አመልካች ክስ የቀረበበትን ተሽከርካሪ በቁጥጥር ስር

እንዲውል ማድረጉ በህግ የተሰጠውን የመቆጣጣር ኃላፊነት ተግባራዊ አድርጓል ከሚባል በቀር ድርጊቱ ህገ ወጥ የሁከት ተግባር ነው የሚያስብል አይደለም፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካች እርምጃ የሁከት ተግባር ነው ማለታቸው የጉዳዩን ባህሪ እና በአዋጁ መሰረት ለአመልካች የተሰጠውን የጉምሩክ ቁጥጥር ስልጣን ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/90002 ላይ ታህሳስ 26/2013 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/267595 ላይ ግንቦት 23/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለበት ንብረት በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት በሀራጅ በሌላ ሰው እጅ የገባ ቢሆንም እንኳን አመልካች ከንብረቱ ላይ የሚፈለገውን ቀረጥ እና ታክስ ለማስከፈል ንብረቱን ተከታትሎ የመያዝ ከህግ የመነጨ ስልጣን ያለው በመሆኑ ድርጊቱ የሁከት ተግባር ነው የሚባል አይደለም፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡